

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት ውሳኔዎች ቅፅ - 24

# የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
# ሰበር ውሳኔዎች



ቅፅ- 24

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክረሲያዊ ሪፐብሊክ
ፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

# የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት

# ሰበር ሰሚ ችሎት ውሣኔዎች

## ቅጽ-24


የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

ጠቅላይ ፍ/ቤት

የጥናትና ህግ ድጋፍ ዳይሬክቶሬት

ታህሣሥ 2013 ዓ.ም.

አዲስ አበባ



ድህረ-ገፅ፡-www.fsc.gov.et
ስልክ፡-+251-111-55-34-00/+251111733031
ፋክስ፡-+251-111-56-55-33
የመ.ሣ.ቁ. 6166
ነፃ የስልክ መስመር፡- 992



# የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት መልዕክት

በአዋጅ ቁ. 454/1997 አንቀጽ 2 ሥር የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ከአምስት ያላነሱ ዳኞች በተሰየሙበት የሰበር ችሎት የሚሰጠው የህግ ትርጉም በሁሉም ደረጃ ባሉት የፌደራል እና ክልል ፍርድ ቤቶች ላይ አስገዳጅነት እንዳለው በግልጽ ተደንግጓል፡፡ የዚህ ድንጋጌ መሰረታዊ ዓላማዎችም በሀገሪቱ ውስጥ የሚወጡ ህግጋት ወጥነት ባለው መንገድ እየተተረጎሙ ሥራ ላይ እንዲውሉ እንዲሁም ተመሳሳይ የፍሬ ነገር እና የህግ ክርክር ያለባቸው ጉዳዮች ተመሳሳይ የፍርድ ውሳኔ እንዲሰጥባቸው ለማስቻል ነው፡፡ እንደዚህ ዓይነቱ አካሄድ ብዙ ጠቀሜታዎች ያሉት ሲሆን በዋናነት ፍርድ ቤቶች የሚሰጡት የፍርድ ውሳኔዎች ጥራት፣ ተገማችነትና ተዓማኒነት እንዲጨምር ይረዳል፤ የፍርድ ቤቶችና የባለጉዳዮች ጊዜ፣ ጉልበት እና ገንዘብ አላስፈላጊ ላልሆኑ ወጪዎችና ብክነት እንዳይዳረጉ ያግዛል ፤ የህግና ፍትህ ስርዓቱም ከጊዜ ወደ ጊዜ በተናበበ መልኩ እየዳበረ እንዲሄድ የበኩሉን አስተዋጽዖ ያደርጋል፡፡ እነዚህ ዓላማዎች ለማሳካት ይቻል ዘንድ አዋጁ በአንቀጽ 2 ሥር በሰበር ችሎቱ አስገዳጅ የህግ ትርጉም የተሰጠባቸውን ውሳኔዎች አሳትሞ ለሁሉም ፍርድ ቤቶች የማሰራጨት ኃላፊነት ለፌደራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ተሰጥቷል፡፡ በዚህ መሰረት የሰበር ችሎቱ አስገዳጅ ውሳኔዎች በጥራዝ መልክ እየታተሙ ያሉ ሲሆን እነሆ አሁን 24ኛ ቅጽ ላይ ደርሷል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም ውሳኔዎቹ ለሁሉም አካላት በሁሉም ቦታ ተደራሽ እንዲሆኑ ለማድረግ በፍርድ ቤቱ ድህረ ገጽ ላይ እንዲለቀቁ ይደረጋል፡፡

ፍርድ ቤቶች የሚሰጡት የዳኝነት አገልግሎት እያደገና እየዳበረ እንዲሄድ አስገዳጅ የሆኑ የሰበር ውሳኔዎች ለሁሉም አካላት ተደራሽ እንዲሆኑ ማድረግ ወሳኝ ቢሆንም ብቻውን ግን በቂ አይደለም፡፡ ከሁሉም በላይ ፍርድ ቤቶች በሚያሳልፏቸው የፍርድ ውሳኔዎች ላይም ሆነ አጠቃላይ በዳኝነት ሥርዓቱ ላይ ምርምር፣ ምሁራዊ ክርክሮችና ትችቶችን ማድረግ አስፈላጊ ነው፡፡ ስለሆነም በዚህ ረገድ ፍርድ ቤታችን ከሁሉም ባለድርሻ አካላት እና የህግ ባለሙያዎች የሚቀርቡትን ገንቢ አስተያየቶችና ትችቶች ለማስተናገድ ዝግጁ መሆኑን ከወዲሁ ለመግለጽ እወዳለሁ፤ አመሰግናለሁ፡፡

**ወ/ሮ መዓዛ አሸናፊ መንግስቱ**
**የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት**

# የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት የጥናትና ህግ ድጋፍ ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር መልዕክት

ክቡራን የሰበር ውሳኔዎች ቅጾች አንባብያንና ተጠቃሚዎች!

በቅድሚያ የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የሚሰጣቸው አስገዳጅ የህግ ትርጉም የያዙ ውሳኔዎች መታተም ከጀመሩበት ከ1997 ዓ.ም አንስቶ እስከ አሁን ድረስ ገንቢ አስተያቶችንና ትችቶችን በመስጠት አብራችሁን በመዝለቃችሁ በፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ስም ልባዊ ምስጋናችንን ማቅረብ እንፈልጋለን።

አስገዳጅ የህግ ትርጉም የተሰጠባቸው የሰበር ሰሚ ውሳኔዎች ለተመሳሳይ ጉዳዮች ውሳኔ ለመስጠት ጥቅም ላይ ከመዋላቸው በተጨማሪ ለህግ ትምህርት ቤት ተማሪዎች መማሪያነት፣ ለተለያዩ ህግ እና ህግ ነክ ለሆኑ ጥናትና ምርምር ስራዎች እንዲሁም ለሌሎች ህግን ማወቅ ለሚፈልጉ አካላት የሚሰጡት ጥቅም ሊለካ የሚችል አይደለም። ነገር ግን የውሳኔዎቹ መታተም ከላይ በተጠቀሰው መልኩ ለህብረተሰቡ ከሚሰጡት ጥቅም በተጨማሪ የህትመቱና የውሳኔዎቹ ባለቤት የሆኑት ፍ/ቤቶችም በውሳኔዎቹ ላይ በሚቀርቡ አስተያየቶችና ውሳኔዎቹን መሰረት አድርገው በሚሰሩ የጥናትና ምርምር ስራዎች ተጠቃሚ መሆናቸው የማይካድ ሃቅ ነው። ይህም ለፍትህ ስርዓቱ መሻሻል እንደዚሁም ለዚሁ ለሰበር ስርዓት መዘመን ጉልህ አስተዋጽኦ ያደርጋል ብለን እናምናለን።

በዚህም የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት የጥናትና ህግ ዳጋፍ ዳይሬክቶሬት እነዚህንና ሌሎች ህትመቶችን አሳትሞ በማሰራጨት ረገድ ከመቸውም ጊዜ በበለጠ ጥረት የሚያደርግ ሲሆን አንባብያንና ተጠቃሚዎችም እንደከዚህ ቀደሙ አስተያየቶችን በመስጠት ተሳትፏችሁ እንዳይለየን በታላቅ አክብሮት እንጠይቃለን።

**አመሰግናለሁ!**

**አሮን ደሳለኝ ሃብቱ**

**የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት የጥናትና ህግ ድጋፍ ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር**

# የፌ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የህግ ትርጉም የሰጠባቸው ውሣኔዎች ማውጫ /ቅፅ 24/

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| | **ፍትሐብሔር ሥነ-ሥርዓት** | | | | 1 |
| 1. | ፍ/ቤቶች የፍ/ቤቱን የስራ ቋንቋ የማይችሉ ተከሳሾች በቀረቡላቸው ጊዜ አስተርጓሚ በመመደብ ክሱ በሚገባቸው ቋንቋ በዝርዝር የመንገር እና በጠበቃ ታግዘው የመከራከር መብት እንዳላቸው፤ ጠበቃ ለማቆም የሚያስችል ዓቅም ከሌላቸው በመንግሥት ወጪ ጠበቃ የማግኘት መብት እንዳላቸው የመንገር ሀላፊነት ያለባቸው ስለመሆኑ<br>የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገመንግሥት አንቀጽ አንቀጽ 9/4 እና 13(1)(2)፣20፣የሲቪል እና የፖለቲካ መብት አንቀጽ 14 | 160916 | አቶ ቦጃ በየነ<br>እና<br>የኦሮሚያ ጠቅላይ ዓቃቤ ሕግ | ታሕሣሥ 30 ቀን 2011 ዓ.ም | 2 |
| 2. | ተከራካሪ ወገኖች ጉዳያቸው በሽማግሌዎች እንዲታይ ወደውና ፈቅደው ከተስማሙ በኂላ ሽማግሌዎች የሰጡት ውሳኔ ባለበት ሁኔታ በሕጉ በተዘረጋው ሥርዓት ይግባኝ በመጠየቅ እንዲታረም ከማድረግ በስተቀር አዲስ ክስ ማቅረብ ተገቢ ስላለመሆኑ<br>በፍ/ብ/ሕ/ቁ 3325፣የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ 244/2/ረ/ | 161062 | አቶ መህዲ ሽረፋ<br>እና<br>አቶ ሻፊ ሽረፋ | 26/04/2011 ዓ/ም | 7 |
| 3. | ከሳሽ ወገን ክስ በሚሰማበት ወቅት ያላቀረበው ማስረጃ መኖሩን በበቂ ምክንያት በማስደገፍ ያቀረበው አቤቱታ ተቀባይነት ባገኘበት ሁኔታ ተከሳሽ የመከላከያ መልሱን እንዲያሻሽል የሚያቀርበውን ጥያቄ ውድቅ በማድረግ | 160314 | የኦሮሚያ ውሃ ስራዎች ኮንስትራክሽን ድርጅት<br>እና | 30/09/2011 | 10 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| | በተሟላ መልስ ባልተከራከረበት ሁኔታ ተከሳሽ ከሳሽ ባቀረበው ሰነድ ላይ አስተያየቱን በጽሁፍ ብቻ ያቅርብ ብሎ የመደመጥ መብቱ ሊታለፍ የማይገባው ስለመሆኑ<br>የፌዴራል ህገ መንግስት አንቀጽ 37 ፤ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ91፤137(1)፤223፤256 | | ቢ.ጋና ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር | | |
| 4. | አንድ የግልግል ጉባኤ ከቤቶች የባለህብትነት መብት ጋር የተያያዘ የመፋለም ክርክርን ተቀብሎ ዉሳኔ ለመስጠት የዳኝነት ስልጣን የሌለው ስለመሆኑ<br>በኢ.ፌ.ዲ.ሪ.ሕገ መንግስት አንቀጽ 37 እና 78፤የፍ/ብ/ሕ/ቁ.1731 ፤3325 ፤3329 | 137302 | ወ/ሮ ዳንሴ ጉርሙ<br>እና<br>አቶ ተመስገን ደምሴ | ታህሳስ 26 ቀን 2010 ዓ.ም | 15 |
| 5. | በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ዉስጥ የተቋቋሙ የኅብረት ሥራ ማኅበራት ከሳሽ በመሆን የሚያቀርቧቸዉን ክሶች በተመለከተ የመዳኘት የሥረ ነገር ሥልጣን የከተማ አስተዳደሩ ፍርድ ቤቶች ሥልጣን ሳይሆን የፌዴራል ፍርድ ቤቶች ስለመሆኑ<br>በፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 11(1/ለ) እና 14(2)፤የአዲስ አበባ ከተማ ቻርተር አዋጅ ቁጥር 361/1995 አንቀጽ 41(1/ረ)፤በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ደንብ ቁጥር 46/2004<br>**/የፌ/ፍ/ቤቶችን አዋጅ እንደገና ለማሻሻል በወጣው አዋጅ ቁጥር 454/1997 መሰረት በፌ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ቀደም ሲል በሰ/መ/ቁጥር 90421 ተሰጥቶ የነበረው የህግ ትርጉም ውሳኔ ተለውጧል።/** | 165289 | ወ/ሮ ወሰኔ ገብረዮሐንስ<br>እና<br>የካ ክፍለ ከተማ ወረዳ 07 ቀበሌ 11/12/08 የሸማቾች ኃላ/የተ/የኅብረት ሥራ ማኅበር | መጋቢት 29 ቀን 2012 ዓ/ም | 22 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| 6. | • የወራሽነት የምስክር ወረቀትን በተመለከተ የሚቀርብ የተቃውሞ አቤቱታ የማስረጃውን ትክክለኛነት እና ህጋዊነት ከማረጋገጥ ያለፈ አንድምታ የሌለው መሆኑ ከተረጋገጠ ማስረጃውን የሰጠው ፍርድ ቤት የማስረጃው ይሰረዝልኝ ጥያቄን ማስተናገድ የሚገባው ስለመሆኑ<br>• በሐሰት ለተገኘ የወራሽነት ማስረጃ ይሰረዝልኝ ጥያቄ ተፈጻሚነት ያለው የይርጋ ጊዜ የአስር አመት የይርጋ ጊዜ ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1000፣1677፣1845 እና 1846<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 358 እና 359 | 161650 | አቶ ኃይለገብርኤል አየለ<br>እና<br>ወ/ሮ ፀሐይ አየለ | ሚያዚያ 29 ቀን 2011 ዓ/ም | 33 |
| 7. | አንድ ተከራካሪ ወገን በፍ/ቤት ፈቃድ ክሱን የተወ እና አዲስ ክስ ባቀረበ ጊዜ በቀረበው አዲስ ክስ ላይ በግራቀኙ ተከራካሪ ወገኖች የቀረቡት እና በፍ/ቤቱ ትዕዛዝ መሠረት የቀረቡ ማስረጃዎች ተመርምረው እና ተመዝነው ውሳኔ የሚሰጥበት እንጂ አስቀድሞ በፍ/ቤት ፈቃድ በተዘጋው መዝገብ ላይ ቀርበው በነበሩ ማስረጃዎች መሠረት ውሳኔ የሚሰጥበት አግባብ ስላለመኖሩ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 278 | 161301 | እነ አቶ አዲስ አልታሰብ<br>እና<br>የፋርጣ ወረዳ ቋልህ ቀበሌ አስ/ጽ/ቤት | ሚያዝያ 30 ቀን 2011 ዓ.ም | 38 |
| 8. | አንድን ክርክር በመጀመሪያ ደረጃ ሲሰማ በነበረበት ፍርድ ቤት በከሳሽነትም ሆነ ተከሳሽነት ቁጥራቸው ከአንድ በላይ የሆኑ ተከራካሪዎች በቀረቡበት | 165616 | አቶ ፈለቀ ታደሰ<br>እና | ህዳር 26 ቀን 2012 ዓ/ም | 43 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| | መዝገብ ላይ በሚሰጥ ውሳኔ ላይ እያንዳንዱ ተከራካሪ ወገን በተናጠል ይግባኝ ያቀረበ እንደሆነ በአንድ በይግባኝም ሆነ በሰበር ችሎት በቀረበ ጉዳይ ላይ በመዝገቡ ላይ ያልቀረቡት ቀድሞ የክርክሩ አካል የነበሩት አካላት በሌላ መዝገብ ላይ ቀርበው ከሆነ ተገቢ ማጣራት እና ክትትል ተደርጎ መዝገቦቹ ተጣምረው እንዲታዩ ማድረግ የሚገባ ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁጥር 331 | | እነ አቶ ሣሙኤል ሱሊቶ | | |
| 9. | ተከራካሪ ወገኖች የሚያቀርቡትን ክርክር በቅን ልቦና እና እውነተኘነት ባለው ማስረጃ የማይከራከሩ በሆነ ጊዜ ፍ/ቤቶች የቀረበላቸው ነገር እውነት መሆኑን ባልተረዱ እና ፍፁም ድብቅ በሆነባቸው ጊዜ እውነት ላይ ለመድረስ በሀሰተኛ ማስረጃ እና በሃሰተኛ ተከራካሪዎች ቅን ልቦና መጉደል ምክንያት እውነትን የያዙ ሰዎች ላይ ያልተገባ ፍርድ እንዳይሠጥ ተገቢውን ማጣራት በማድረግ ትክክለኛ ነው ያሉትን ውሣኔ መስጠት ያለባቸው ስለመሆኑ | 168094 | አቶ ምስጋናው አሰጌ<br>እና<br>እነ አቶ አይናዲስ አሰጌ | ታህሳስ 22 ቀን 2012 ዓ.ም. | 47 |
| 10. | የአፈፃፀም ችሎት በፍርድ ባለመብትና በፍርድ ባለዕዳ መካከል አንድን ቤት በዓይነት ለመካፈል ስምምነት እንደሌለ በማረጋገጥ በሐራጅ እንዲሸጥ ትዕዛዝ የሰጠ እና ግራቀኙም በቀረቡት ተጫራቾች ሐራጁ እንዲቀጥል በፊርማቸው አረጋግጠው ቤቱ የተሸጠ ከሆነ የሐራጁ የሽያጭ ሥርዓት ተገቢ ባልሆነ መንገድ ወይም በማጭበርበር ተፈጽሟል ለማለት የሚያስችል ስላለመሆኑ | 165775 | የአቶ ተሾመ ጎርፌ ወራሽ መቅደስ ተሾመ<br>እና<br>ወ/ሮ ፈሰሰች ወንድማገኝ | የካቲት 29 ቀን 2011ዓ.ም | 53 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| | በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 445 | | | | |
| 11. | አንድን ክስ በመጀመሪያ መቃወሚያ ዉድቅ በማድረግ የተሰጠን ዉሳኔ ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት ከሻረው በኋላ የስር ፍርድ ቤት በፍሬ ጉዳዩ ላይ ተገቢዉን እንዲወስን መመለስ ሲገባው ያን ሳያደርግ ፍሬ ጉዳዩን በተመለከተ ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ራሱ የሚሰጠዉ ዉሳኔ ማስረጃን መዝኖ ፍሬ ነገርን ከማረጋገጥ ጋር በተያያዘ ሊፈጠር የሚችለዉን ስህተት ለማሳረም ይግባኝ የማቅረብ መብትን ከማስፋት አንፃር ታይቶ ተፈፃሚነት ሊኖረዉ የሚገባውን የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ አንቀፅ 341 ድንጋጌን ትክክለኛ አፈፃፀም ያልተከተለ ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ አንቀፅ 341 | 163166 | አቶ ሙስጠፋ መሐመድ<br>እና<br>አቶ ናስር ኢሳ | ግንቦት 30 ቀን 2011 ዓ.ም | 58 |
| 12. | ለአንድ ክስ መሻሻል ወይም ለክርክሩ መለወጥ ቀደም ሲል የቀረበን የክስ ምክንያት በሌላ የክስ ምክንያት በመቀየር ለመሟገት ማቅረብ ነገሩን ይበልጥ የሚያብራራ ወይም ትክክለኛ ፍትህ ለመስጠት የሚረዳ ነው በሚል ክስ እንዲሻሻል የሚፈቀድበት የህግ ምክንያት ስላለመኖሩ<br>/በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 91/1/2/ | 161736 | አቶ ተጫኔ ካሳ<br>እና<br>እነ አቶ ባህረ ሀፍቱ | ግንቦት 29ቀን 2011 ዓ.ም | 61 |
| 13. | • ፍ/ቤቶች ተከራካሪ ወገኖች በሚያቀርቡት ክስ ላይ ያቀረቡትን መቃወሚያ እና በክሱ መነሻነት የቀረበ የተከሳሽ ከሳሽነት ክስ ካለ ራሱን ችሎ መፍትሔ ማግኘት ያለበት ክርክር ስለሆነ የተከሳሽ | 173416 | እነ አቶ ዮሐንስ ዘውዴ አበራ<br>እና | ጥር 26 ቀን 2012 ዓ.ም | 68 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| | ከሳሽነት ክሱ ላይ ተገቢውን ሀተታ በማስፈር አግባብነት ያለውን ትዕዛዝ ወይም ብይን መስጠት የሚገባቸው ስለመሆኑ<br>• በተከራካሪዎች ለዳኝነት በቀረበ ጉዳይ ላይ ፍ/ቤቶች በራሳቸው አነሳሽነት ወይም በተከራካሪዎቹ በሚቀርብ መቃወሚያ መነሻነት የስረ ነገር ስልጣን የሌላቸው መሆኑን ካረጋገጡ መዝገቡን የስረ ነገር ስልጣን ላለው ፍ/ቤት ሊያስተላልፉ የሚገባ ስለመሆኑ<br>የፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 17(3) እና 91(5)፤ 182(3) | | ወ/ሮ ተናኜ ማንያህልሀል ላቀው | | |
| 14. | • ከመደበኛ ፍ/ቤት ውጭ አንድን ጉዳይ የማየት የዳኝነት ስልጣን የተሰጠው አካል ጉዳዩን ማየት እንደማይቻል ገልጾ ከመለሰው ጉዳዩን የማየት ስልጣን ለሌላ አካል ተሰጥቷል የሚል ክርክር እስካልቀረበበት ድረስ መደበኛ ፍ/ቤቱ ይህን ጉዳይ ማየት አልችልም በሚል መመለስ የማይቻል ስለመሆኑ<br>• የፕራይቬታይዜሽን ኤጀንሲ በኤጀንሲው የሚታይ ጉዳይ አይደለም በሚል አረጋግጦ የመለሰው ጉዳይ በስልጣኑ ላይ ሌላ ክርክር እስካልቀረበበት ድረሰ ፍ/ቤቶች ተቀብለው ማስተናገድ ያለባቸው ስለመሆኑ<br>የኢ.ፌ.ዴ.ሪ. ህገ መንግስት አንቀፅ 37፣78(2) እና 79(1) | 169716 | እነ ወ/ሪት ሰላማዊት ይልማ እና<br>እነ የኢ/ያ ቀይ መስቀል ማህበር ቢ.ታጅራ ቅርንጫፍ | ጥቅምት 24 ቀን 2012 ዓ.ም | 72 |
| 15. | አንድ የእርቅ ስምምነት በፍርድ ቤት ተረጋግጦ ከተመዘገበ በኋላ የእርቅ | 162106 | ወ/ሮ ሙሉ ወንድሙ | ጥር 30/ 2011 ዓ.ም | 79 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| | ስምምነቱ የፀደቀበት መዝገብ ባለበት ሁኔታ የእርቅ ስምምነቱን ለማስረዝ በሌላ መዝገብ አዲስ ክስ ማቅረብ የሚቻልበት የህግ አግባብ የሌለ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 274፣277 | | እና<br>እነ ወ/ሮ ዘመኗ ድንቁ | | |
| 16. | በፍርድ ቤት ከቀረበ ክርክር ጋር በተያያዘ ከአስተዳደር ክፍል የሚሰጥ መግለጫ እንደየአግባብነቱ ለፍርድ ቤቱ ከቀረቡት ሌሎች የሰው እና የሰነድ ማስረጃዎች ይዘት ጋር ተገናዝቦ የሚወሰድ እንጂ በራሱ የመጨረሻ ማስረጃ ስላለመሆኑ | 169522 | አቶ ሲራጅ አባፎጊ<br>እና<br>እነ አቶ አባቦር አባጨብሳ | 29/3/2011ዓ/ም | 85 |
| 17. | በይግባኝ ደረጃ ግራ ቀኝ ወገኖች ለክርክር በተቀጠረበት ቀን ባለመቅረባቸው ተዘግቶ የነበረ መዝገብ በይግባኝ ባዩ አመልካችነት ሲከፈት መልስ ሰጪው እንዲያውቀው ሳይደረግ በሌለበት ውሳኔ መስጠት እና መልስ ሰጪው በሌለበት የተሰጠው ውሳኔ እንዲነሳለት የሚያቀርበውን አቤቱታ በቂ ባልሆነ ምክንያት ውድቅ ማድረግ አግባብነት የሌለው ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህግ አንቀጽ 233 | 169407 | በኬሚካል ኢንዳስትሪ ኮርፖሬሽን ሙገር ሲሚንቶ ፋብሪካ<br>እና<br>አቶ ይትባረክ ተካ | 29/9/2011 ዓ/ም | 92 |
| 18. | በሐሰት ማስረጃ የተሰጠ ፍርድ እንዲነሳ የሚቀርብ ጥያቄ በዳግም ዳኝነት ጥያቄ ቀርቦ ከሚስተናገድ በቀር መደበኛ(አዲስ) ክስ በማቅረብ ውሳኔው እንዲሻር የሚጠየቅበት የህግ አግባብ የሌለ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ/ 6 | 166205 | ገ/ኢየሱስ ሙሉነህ<br>እና<br>እነ አቶ ወልዴ አቡቴ | 29/09/2011ዓ/ም | 95 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| 19. | አንድ ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት በህግ በተሰጠው ስልጣን መሰረት የሥር ፍ/ቤት ውሳኔን በመሻር ጉዳዩ በድጋሚ እንዲታይ ነጥብ ለይቶ እስከመለስ ድረስ የሥር ፍ/ቤቱ በበላይ ፍ/ቤቱ ትዕዛዝ ወይም መመሪያ መሰረት ግራ ቀኝ ተካራካሪ ወገኖችን በማከራከር ፣ በመስማት፣ ተገቢውን ጭብጥ በመመስረት እና በማስረጃ በማጣራት ዉሳኔ የመስጠት ኃላፊነት ያለበት ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.246-249፣341(1) | 166617 | አቶ ገ/መድህን መልካ ጻድቅ<br>እና<br>እነ አቶ ቀነኒ ዲባባ | ግንቦት 30 ቀን 2011 ዓ.ም | 98 |
| 20. | አንድ የውርስ ንብረት ክፍፍል ጥያቄ ድርሻን መሰረት በማድረግ የቀረበ ሲሆን አመልካቹ በድርሻው ተመስርቶ ዳኝነት እስከጠየቀ ድረስ ከድርሻው ውጪ ያለውን ግምት መሰረት አድርጎ ዳኝነት እንዲከፍል የሚደረግበት የህግ አግባብ ስላለመኖሩ እና የውርስ ንብረቱ ጠቅላላ ግምት የፍርድ ቤቱን የስረ ነገር ስልጣን ለመወሰን የግድ የሚባልበት የሕግ መሰረት የሌለ ስለመሆኑና<br>በአዋጅ ቁጥር 25/88 አንቀጽ 14 ፣ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 17 እና 225 | 167589 | ወ/ሮ ጽጌ ታደሰ<br>እና<br>እነ ወ/ሮ አልማዝ ሳህሌ | ግንቦት 16 ቀን 2011 ዓ.ም | 102 |
| 21. | ግራቀኝ ተከራካሪ ወገኖች በሚያደርጉት ስምምነት መሰረት አለመግባባታቸውን በኢትዮጵያ መሰረታዊ ህግ (Substantive Law) እንዲሁም በውጪ ሃገር የሥነ-ሥርዓት ህግ መሰረት በሚቋቋም የግልግል ዳኝነት አካል በውጭ ሃገር ለመቋጨት በተስማሙት መሰረት የተቋቋመው | 155880 | አግሪኮም ኢንተርናሽናል ኩባንያ<br>እና<br>የኢትዮጵያ ንግድ ስራዎች | ሰኔ 28 ቀን 2011 ዓ.ም | 105 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| | የግልግል ጉባኤ የሰጠው ውሳኔ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት ታይቶ እንዲታረም የሚቀርብ የሰበር ማመልከቻ ተቀባይነት የሌለው ስለመሆኑ<br>የኢፌዴሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 80(3)(ሀ) እና በፌዴራል ፍርድ ቤቶች ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 10 (በአዋጅ ቁጥር 454/97 አንቀጽ 2 እንደተሻሻለ)፤ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 458(ሀ) እና 461(1)(ሀ) | | ኮርፖሬሽን | | |
| 22. | አንድ በዉጭ አገር የተሰጠ ፍርድ በኢትዮጵያ ፍርድ ቤቶች ለማስፈጸም በኢትዮጵያ እና ፍርዱን በሰጠዉ ፍርድ ቤት አገር መካከል ይህን አስመልክቶ የተደረገ ስምምነት (bilateral agreement) ባይኖርም በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 458 ስር የተመለከቱት ቅድመ ሁኔታዎች መሟላታቸዉ ከተረጋገጠ የኢትዮጵያ ፍርድ ቤቶች ፍርዱን ተቀብለዉ ማስፈጸም የሚችሉ ስለመሆኑ<br>ፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 456፣458 | 161597 | ወ/ሮ ፍሬህይወት ገበየሁ<br>እና<br>አቶ ዘሪሁን ተፈራ | ግንቦት 27 ቀን 2012 ዓ.ም | 118 |
| **ቤተሰብ** | | | | | **122** |
| 23. | በፍርድ ቤት የጸደቀ የጉዲፈቻ ውል ስምምነት በወሳኝ ኩነት ምዝገባ ፅ/ቤት ተመዝግቦ የጉዲፈቻ ሰርተፍኬት ስለሚሰጥበት አግባብ<br>አዋጅ ቁጥር 760/2004 አንቀፅ 70(2)፣ መመሪያ ቁጥር 7/2010 አንቀፅ | 173628 | እነ አቶ ወ/ጨርቆስ በጋሻው<br>እና<br>በየካ ክ/ከተማ አስተዳደር | ግንቦት 28 ቀን 2011 ዓ.ም | 123 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| | 43(3) | | የወረዳ 13 የወሳኝ ኩነት ምዝገባ ፅ/ቤት | | |
| 24. | በልጅ ቀለብ አወሳሰን ጊዜ የከፋዩን የተጣራ የገቢ መጠን በማጣራት ተገቢ ነው የሚባለው የቀለብ ገንዘብ መጠን መወሰን የሚገባው ስለመሆኑ<br>የኢ.ፌ.ዲ.ሪ. ህገ መንግስት በአንቀጽ 36(2)፣አዋጅ ቁጥር 213/1992 የተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ አንቀጽ 113 | 172784 | አቶ አቡበከር አህመድ መሐመድ<br>እና<br>ወ/ሮ ሳራ ሱፍያን አብዱረህማን | ሰኔ 24 ቀን 2011 ዓ.ም. | 127 |
| 25. | የኮንደምኒየም ቤት እጣ ከጋብቻ በፊት ወጥቶ የኮንዶሚኒየም ቤቱ የሽያጭ ውል የተፈረመው ወይም የተደረገው በጋብቻ ውስጥ በሆነበት ሁኔታ ለቤቱ የተከፈለው ገንዘብ ምንጭ የሆነው ወገን የግሉ መሆኑን ካላስረዳ በስተቀር ቤቱ የአንደኛው ተጋቢ የግል ንብረት ነው ሊባል የሚችልበት ህጋዊ ምክንያት የሌለ ስለመሆኑ<br>የፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ህግ ቁጥር 255 | 153405 | ወ/ሮ ፅጌ በንቲ<br>እና<br>አቶ ተስፋዬ ታደሰ | ግንቦት13 ቀን 2011 ዓ.ም | 131 |
| 26. | የኢትዮጵያ ተወላጅ የሆኑ የዉጭ ዜጎች የሀገሪቷን ባህል፣ቋንቋ፣እሴት እንደማያዉቁ የዉጭ ሀገር ጉዲፈቻ አድራጊዎች በጉዲፈቻ የሚወስዱትን ኢትዮጵያዊ ሕፃን የሀገሩን ባህል፣ወግ ፣ልማድና በማህበረሰቡ እሴት ታንፆ እንዳያድግ ተፅዕኖ በማድረግ፣ፍቅር በመንፈግ ለስነ-ልቦናዊና ማሕበራዊ ችግር ያጋልጧቸዋል ብሎ በማሰብ የኢትዮጵያዊያን ዳያስፖራዎች በሀገር እድገት እና ብልጽግና እንዲሁም ለወገኖቻቸዉ ኑሮ መሻሻል ያላቸዉን ሚና | 189201 | እነ አቶ ወንድወሰን ታደሰ ይስማ<br>እና<br>የለም | መጋቢት 02 ቀን 2012 ዓ/ም | 136 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| | ባለመገንዘብ ኢትዮጵያውያንን በጉዲፈቻ እንዳይወስዱ መከልከል አግባብነት የሌለው ስለመሆኑ<br>የሕፃናት መብት ኮንቬንሺን አንቀጽ 20 ፤የአፍሪካ ሕፃናት መብቶችና ደህነት ቻርተር አንቀጽ 24(ለ)፣24(ረ) ፤ የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 36(5)፤ አዋጅ ቁጥር 1070/2010 መቅድም (preamble)፤ ከተሻሻለዉ የቤተሰብ ሕግ አዋጅ ቁጥር 213/1992 አንቀጽ 193፣ 194(3)(መ) ፤ የዉጭ ዜጎችን በትዉልድ ሀገራቸዉ ተጠቃሚ ለማድረግ የወጣዉ አዋጅ ቁጥር 270/1994 አንቀፅ 5 እና 6 | | | | |
| 27. | ከወራሾቹ አንዱ ለውርስ የሚከፍለው እዳ ያለበት እንደሆነ የውርስ ንብረት ክፍፍል ከመደረጉ በፊት የውርስ እዳ ሊቀነስ የሚገባ ስለመሆኑ<br>በፍትሓብሔር ህግ ቁጥር 1014፤1090 | 144585 | እነ ወ/ሮ ሀና ካሳዬ<br>እና<br>ወ/ሮ ዘነበች ከሳዬ | ግንቦት 13 ቀን 2010 ዓ/ም | 142 |
| **አሰሪና ሰራተኛ** | | | | | **149** |
| 28. | አንድ የመንግስት ሰራተኛ በተከሰሰበት የዲሲፕሊን ጥፋት ምክንያት ከስራ እንዲሰናበት ካልተወሰነበት በስተቀር ከሥራ በታገደበት ወቅት ሳይከፈለው የቀረው ደመወዝ የሚከፈለው ስለመሆኑ<br>በፌዴራል መንግስት ሰራተኞች አዋጅ ቁጥር 1064/2010 አንቀጽ 72 (4) | 161880 | አቶ አብርሃም ዱአ<br>እና<br>ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት | ታህሳስ 23 ቀን 2011 ዓ.ም. | 150 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| 29. | የሲቪል ሰርቪስና የሰው ሀብት ልማት ሚ/ር አጥንቶ ስራ ላይ ባዋለው በነጥብ የስራ ምዘናና ደረጃ አወሳሰን ዘዴ/JEG/ የመንግስት ሰራተኞች ድልድል አፈጻጸም መመሪያ መሰረት ለአንድ የሥራ መደብ የሚያስፈልገው የትምህርት ዝግጅት በግልጽ ተቀምጦ እያለ ተጨማሪ የትምሕርት ዓይነትን አካቶ ሰራተኞችን ማወዳደር የድልድል መመሪያውን የሚጥስ ስለመሆኑ | 173887 | የኢትዮጵያ ጤና መድህን ኤጀንሲ<br>እና<br>አቶ ዋቅጋሪ ጥላሁን | 24/10/2011 ዓ/ም | 153 |
| 30. | አንድ የመንግስት መስሪያ ቤት ባወጣው የቅጥር ማስታወቂያ መሰረት ተወዳድሮ አሸናፊነቱ ተረጋግጦ ቅጥር የፈፀመ ሰራተኛ ቅጥሩ የቅጥር ስርዓት ለመግዛት የወጣው ህግን ባልተከተለ መንገድ የተፈፀመ መሆኑ ከተረጋገጠ ስህተቱ የቀጣሪው መንግስት መስሪያ ቤት ቢሆን እንኳን ቅጥሩ ፀንቶ የሚቆይበት አግባብ የሌለ ስለመሆኑ<br>የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመንግሥት ሠራተኞች አዋጅ 56/2010 አንቀፅ 94 | 165886 | አቶ አምባቸው ተፈራ<br>እና<br>ልደታ ክ/ከተማ ወረዳ 9 ፐብሊክ ሰርቪስና የሠው ሃብት ልማት | የካቲት 11 ቀን 2011 ዓ/ም | 157 |
| **ንብረት** | | | | | **160** |
| 31. | አንድ የመንግስት የንግድ ቤት ኪራይ መብት ከልጅነት ጀምሮ በአውራሼ ዘንድ አድጌያለሁ እንዲሁም የኑዛዜ ወራሽ ነኝ በማለት በዉርስ ሊተላለፍና የንግድ ቤት የኪራይ መብት ተጠቃሚ ሊያደርግ የማይችል ስለመሆኑ<br>በአ/አ/ከ/አስ/የቤቶች ልማትና አስተዳደር ቢሮ የመንግስት ቤቶች አስተዳደር | 164326 | አቶ አበበ ዘገየ<br>እና<br>ከተማ ክ/ከተማ ወ/07 ኮ/የቤቶች ልማት ጽ/ቤት | 28/05/2011 | 161 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| | *መመሪያ ቁጥር 4/2009 አንቀጽ 24* | | | | |
| 32. | አንድ የገጠር መሬት ባለይዞታ የሆነ አርሶ አደር በሕግ አግባብ ካሳ ተከፍሎት ወይም ምትክ መሬት ተሰጥቶት እንዲለቅ ከሚደረገው በቀር በመንግስት ወይም በአስተዳደር አካላት ፍላጐት ብቻ ከመሬቱ ሊነቀል የማይችል ሲሆን መሬቱ ለሌላ አርሶ አደር ከመስጠቱ በፊት አስቀድሞ ባለይዞታ የነበረን ሰው ከመሬቱ መነቀልን እንዳያስከትልበት በተገቢው ጥንቃቄ ተደርጐ መጣራት ያለበት ስለመሆኑ<br>የኢፌዲሪ ሕገ-መንግስት አንቀጽ 40/4/ | 162083 | ወ/ሮ አበቡ ተመስገን<br>እና<br>እነ አቶ በሬ አባተ /አምስት ሰዎች/ | ሚያዚያ 28 ቀን 2011 ዓ.ም | 164 |
| 33. | በአንድ የገጠር መሬት ሕግ ላይ የስነ አእምሮ ችግር ያለባቸው ሰዎች የመሬት ተጠቃሚነት መብት እንዲቀጥል ለማድረግ በሕጉ የተቀመጡትን መስፈርቶች የስነ አእምሮ ችግር ያለባቸውን ሰዎች ጥቅም ለመጠበቅ ሲባል በፍትሐብሔር ሕግ ላይ ስለፍርድ ክልከላ ከተደነገጉት ድንጋጌዎች ጋር አጣጥሞ በማየት በፍ/ቤት የተሰጠ የፍርድ ክልከላ ውሳኔ ተቀባይነት ያለው ስለመሆኑ<br>*የገጠር መሬት አስተዳደር እና አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር 239/2006 አንቀጽ 11/1/፣አንቀጽ 11/5 ንዑስ አንቀጽ (ሰ) እና (በ)፣አዋጁን ለማስፈጸም የወጠው ደንብ ቁጥር 85/2006 አንቀጽ 13/8* | 178664 | የአቶ ጸጋይ ገ/ሕይወት ሞግዚት አቶ ኪዳነማሪያም ሐይሉ<br>እና<br>ወ/ሮ አሚት አጽብሃ | ግንቦት 28 ቀን 2012 ዓ.ም | 169 |
| 34. | አንድ ቤት በዓዋጅ 47/67 መሰረት ከተወረሰ በኂላ የተወረሱ ቤቶችን | 165314 | የድሬደዋ ከተማ አስ/ቀበሌ | 30/09/2011 | 175 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| | ለመመለስ በወቅቱ ስልጣን የነበረዉ የከተማ ልማትና ቤት ሚኒስቴር ቤቱ እንዲመለስ የወሰነው ዉሳኔ መኖሩን የሚያሳይ ማስረጃ ባልቀረበበት ሁኔታ ምትክ ቤት እንዲሰጥ መወሰኑ ብቻ የተወረሰ ቤት ይመለስ ማለት ስላለመሆኑ | | 03<br>እና<br>ወ/ሮ ስንዱ ሳልቫቶር | | |
| 35. | ከመሬት ይዞታ ጋር በተያያዘ ግጭትና አለመግባባት ሲኖር ጉዳዩ አስቀድሞ በቀበሌ አስተዳደር አማካይነት ወይም በተከራካሪ ወገኖች ምርጫ በስምምነት በሽማግሌዎች ታይቶ እንዲፈታ ማድረግ ለተከራካሪ ወገኖች የተፈቀደ አማራጭ እንጂ አስገዳጅ ስላለመሆኑ<br><br>የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር 456/97 አንቀጽ 12፤በኦሮሚያ ክልል መንግስት የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም አዋጅ ቁ/ 130/99 አንቀጽ 16፣17 | 169648 | አቶ ተሻለ ዋቆ<br>እና<br>አቶ ንጉሴ ቦንቱ | ሰኔ 21 ቀን 2011 ዓ/ም | 179 |
| 36. | በባለመሬቱ ወይም በባለይዞታዉ ፈቃድ አትክልቶችን በሌላ ሰው ይዞታ ላይ የተከለ ሰዉ ከባለይዞታው ጋር ባለው ስምምነት መሠረት የመሬቱ አላባ ተጠቃሚ እንደሆነና ከስምምነቱ ዉጪ አትክልቶቹ እንዲነሱ ሲደረግ ካሳ የሚገባው ስለመሆኑ<br>የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገመንግስት አንቀጽ 40(3 እና 4)፣የፍ/ብ/ሕ/ቁ 1175፣1176 | 164489 | አቶ አባዝናብ አባድማ<br>እና<br>አቶአባተማም ሼህ ሽኩር | ግንቦት 28 ቀን 2011 ዓ.ም | 183 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| 37. | የሊዝ ዉል እንዲቋረጥ የተሰጠ አስተዳደራዊ ዉሳኔ ባልተሻረበት ሁኔታ በሊዝ ዉል የተያዘ መሬት ለማስለቀቅ የመሬት አስተዳደር አካል መሬቱን ለመረከብ እንዲቻለው የሚሰጠው ማስጠንቀቂያ የሁከት ተግባር ነዉ ሊባል የማይቻል ስለመሆኑ<br>በፍ/ብ/ህግ አንቀጽ 1149/3/፤የከተማ ቦታን በሊዝ ስለመያዝ አዋጅ ቁ/721/04 አንቀጽ 25 | 158527 | ወ/ሮ ዘይነባ ሀሰን<br>እና<br>እነ የቢሾፍቱ ከተማ የመሬት ልማትና ማኔጅመንት ኤጀንሲ | ጥር 27 ቀን 2011 ዓ.ም. | 187 |
| 38. | የገጠር መሬት ባለይዞታዎች መካከል የሚደረግ ማንኛዉም የልዉዉጥ ዉል አግባብ ባለዉ የወረዳ የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ጽ/ቤት ቀርቦ በሀሰተኛ መረጃ ላይ መሰረት በማድረግ አስተዳደሩን በማሳሳት የተገኘ የይዞታ ደብተርና የተደረገው ምዝገባ ህጋዊ ዉጤት የማይኖረው እና በህግ ፊት በማይጸና ዉል የያዘ ወገን መሬቱን እንዲለቅ የሚደረግ ስለመሆኑ<br>በአማራ ብ/ክ/መንግስት የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም አዋጅ ቁ/252/09 አንቀጽ 20/3/ | 161676 | አቶ መልካሙ አበራ<br>እና<br>ቄስ ዳምጤ በየነ | የካቲት 25 ቀን 2011ዓ.ም | 191 |
| 39. | የኢ.ፌ.ዴ.ሪ. ህገ መንግስት ከታወጀ በኂላ ባለው የመሬት ስሪት መሰረት የፍ/ብ/ህ/ቁ/1065 መሬትን በሚመለከት ተፈፃሚ የሚሆነው ቀድሞ በስጦታ የተወሰደን ይዞታ በዓይነት ወደ ውርስ ይዞታ እንዲመለስ በማድረግ ሳይሆን የይዞታውን መጠን በልኬት በመለየት መጠኑ ከአጠቃላይ የውርስ ይዞታው ውስጥ ለስጦታ ተቀባዩ ከሚደርሰው ድርሻ ላይ እንዲቀነስ በማድረግ | 169030 | እነ አቶ አሰፋ ሰቦቃ<br>እና<br>እነ አቶ ከበደ ሰቦቃ | ህዳር 30/2012ዓ.ም | 194 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| | ስለመሆኑ<br>የኢ.ፌ.ዴ.ሪ. ህገ መንግስት አንቀፅ 40፣ የፍ/ብ/ህ/ቁ/ 1065፣ገጠር መሬት አስተዳደር እና አጠቃቀም አዋጁ ቁጥር 130/1999 አንቀፅ 9(2) እና ደንብ ቁጥር 151/2005 አንቀፅ 10(10 | | | | |
| 40. | ለሕዝብ ጥቅም ሲባል የእርሻ መሬቱ የተወሰደበት ሰው ካሳም ሆነ ትክ መሬት ባለማግኘቱ በአስተዳደር አካል መፍትሄ ሳይሰጠው ለፍርድ ቤት አቤቱታውን ሲያቀርብ ፍርድ ቤት ጉዳዩን አከራክሮ ዳኝነት ሊሰጥበት የሚገባዉ ስለመሆኑ<br>በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገመንግሥት አንቀጽ 37፣ከአዋጅ ቁ/455/97 አንቀጽ 3/1/ | 168556 | አቶ ተሾመ ድለንሴ<br>እና<br>እነ የቀርሳ ማሊማ ወረዳ<br>ገጠር መ/ባለስልጣን ጽ/ቤት | ሰኔ 14 ቀን 2011 ዓ.ም | 201 |
| 41. | አንድ ባለይዞታ አንድን ይዞታ በስጦታ አግኝቶ ለረጅም ዓመታት ይዞ በሚመለከታቸዉ የመንግስት አካላት ዕዉቅና ሲጠቀምበት የነበረ መሆኑ ከተረጋገጠ በክልል ከተሞች ዉስጥ የተሟላ ሰነድ የሌላቸዉና ሰነድ አልባ ይዞታዎችን በማጣራት የይዞታ ማረጋገጫ ሰነድ/ካርታ ለመስጠት ተሻሽሎ በወጣ መመሪያ ቁጥር 8/2007 መሠረት የመስተናገድ መብት ያለው ስለመሆኑ<br>የይዞታ ማረጋገጫ ሰነድ/ካርታ ለመስጠት ተሻሽሎ የወጣ መመሪያ ቁጥር 8/2007 አንቀጽ 4(5) | 169864 | ወ/ሮ ብርሃን ማለዳ<br>እና<br>የባህር ዳር ከተማ ጣና<br>ክ/ከተማ | 28/09/2011 | 204 |
| 42. | አንድ ሰው የገጠር መሬት በሕጋዊ መንገድ የያዘ ስለመሆኑ እስካልተረጋገጠ | 179827 | ካሱ ምስጋናው | ታሕሳስ 20 ቀን 2012 ዓ.ም | 209 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| | ጊዜ ድረስ መሬቱን የያዘው በሕገወጥ መንገድ መሆኑ ግምት የሚወሰድበት በመሆኑ የይርጋ መቃወሚያን በስነ-ስርዓት መቃወሚያነት ሊያነሳ የማይችል ስለመሆኑ<br>የአማራ ክልል የገጠር መሬት አስተዳደር እና አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር 252/2009 አንቀጽ 55 እና 2/39 | | እና<br>ጥላዬ አስረስ | | |
| **ንግድና ኢንሹራንስ** | | | | | **214** |
| 43. | አንድ የመድን ገቢ ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት ካልሆነ በስተቀር መድን የተገባለት ተሽከርካሪ ላይ አደጋ መድረሱን በተገባለት የመድን ዉልም ሆነ በሕግ የተመለከተዉን ለመድን ሰጭዉ አደጋን የማሳወቅ ቅድመ ሁኔታ በአግባቡ አሟልቶ እያለ መድን ሰጪው ለ3ኛ ወገን የከፈለውን ካሳ መድን ገቢው መልሶ ለመድን ሰጪው የሚከፍልበት አግባብ የሌለ ስለመሆኑ | 161598 | አቶ ሰለሞን በቀለ<br>እና<br>ኢትዮ ላይፍ ኤንድ ጄኔራል ኢንሹራንስ አ.ማ | የካቲት 13ቀን 2011 ዓ.ም | 215 |
| 44. | የኢንሹራንስ ፖለሲ የኢንሹራንስ ዉል አካል በመሆኑ በኢንሹራንስ ፖሊሲዉ ላይ የተመለከተዉ ቃል የኢንሹራንስ ዉል ቃል ተደርጎ ሊወሰድ የሚገባ ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 1733፣የንግድ ሕግ ቁጥር 657(1 እና 2) | 160602 | አቶ ነጋ ባንቲሁን<br>እና<br>የኢትዮጵያ መድን ድርጅት | ኅዳር 30 ቀን 2012 ዓ/ም | 222 |
| 45. | የመድን ድለላ አገልግሎት የኮሚሽን ክፍያ ስለሚከፈልበት አግባብ<br>የንግድ ህግ አንቀጽ 56(1)፣ የመድን ሥራ አዋጅ ቁጥር 746/2004 አንቀጽ | 158262 | ናይል ኢንሹራንስ ኩባንያ አ.ማ | ሀምሌ 30 ቀን 2011 ዓ.ም. | 232 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| | 2(19) | | እና<br>ጀነራል ኢንሹራንስ ብሮከርስ | | |
| 46. | • የአክሲዮን መተላለፍ ገዥና ሻጭን ለማስገደድ በጽሁፍ መደረግ ያለበት ሲሆን ማህበሩን ለማስገደድና የተላለፈለት ሰዉ በባለአክሲዮንነት ሙሉ መብት ለመጠቀም ስለአክሲዮን መተላለፉ ማህበርተኞች የተስማሙበት ዉሳኔ በአክሲዮኖች መዝገብ ሊመዘገብ የሚገባው ስለመሆኑ<br>• የአክሲዮኖች መተላለፍ በ3ኛ ወገን ላይ መቃወሚያ ሊሆን የሚችለዉ ስለአክሲዮኖች መተላለፍ ዉል ሲኖር ወይም ማህበርተኞቹ የአክሲዮኖችን መተላለፍ ተቀብለዉ የተስማሙበት ሰነድ በሰነዶች ማረጋገጫና ምዝገባ ጽ/ቤት ተረጋግጦ መመዝገቡ ሳይሆን የአክሲዮኖቹ መተላለፍ በንግድ ሚኒስቴር የአክሲዮኖች መዝገብ ላይ ሲመዘገብ ስለመሆኑ<br>የንግድ ሕግ አንቀጽ 522 እና 523 /3/ | 103472 | የኢት/ንግድ ባንክ ነ/ፈጅ ኢትዮጵያ ታመነ<br>እና<br>እነ አቶ ጌታነህ ምናለ | 27/01/2008 ዓ.ም | 238 |
| 47. | በአንድ የአፈፃፀም መዝገብ የፍርድ ባለዕዳ የነበሩ ኃ/የተ/የግ/ማህበር አክሲዮኖች በፍ/ቤት በተሰጠ ዕግድ ትዕዛዝ ለ3ኛ ወገን እንዳይተላለፉ ከመታገዳቸው በፊት አክሲዮኖቹ ለሌላ ወገን በሽያጭ ስለመተላለፋቸዉ ፤በንግድ ሚኒስቴር የአክሲዮን መዝገብ ላይ ስለመመዝገባቸው ካልተረጋገጠ | 154564 | እነ አብዱሰላም ሰይዱ አብዱ<br>እና<br>የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ | ግንቦት 28ቀን 2011 ዓ.ም | 244 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| | አክሲዮኖች በሀራጅ ተሸጠዉ ለፍርድ ባለመብት እንዲከፈል የተሰጠ የአፈጻጸም ትዕዛዝ እንዲነሳ የሚቀርብ መቃወሚያ ተቀባይነት የሌለው ስለመሆኑ<br>የንግድ ሕግ ቁጥር 522፣523(3) | | | | |
| 48. | አንድ ባንክ ለደንበኛው ክፍያ የፈጸመዉ በዋናነት ተከፋዩ ሰዉ ብቻ ያዉቀዋል ተብሎ የሚገመተዉን ፍሬነገር ማለትም ገንዘቡን የላከዉ ሰዉ ማንነት፤የተላከዉ ገንዘብ መጠን፤የሚስጥር ቁጥር እና የተላከለት ሰዉ ስም እና ተከፋዩ ሰዉ የሰጠዉ መረጃ ተዛማጅና ትክክል መሆናቸዉ በተለመደዉ አሰራር መሰረት በማረጋገጥ እስከሆነ ድረስ ክፍያዉን የተቀበለዉ ሰው ሀሰተኛ የቀበሌ መታወቂያ ይዞ የቀረበ ለማይገባው ሰዉ ነዉ በሚል ምክንያት ባንኩ በድጋሚ ገንዘቡን እንዲከፍል የሚገደድበት የህግ ምክንያት የሌለ ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁጥር 592/2000 አንቀጽ 2/2/መ/፣ 53 | 188419 | አባይ ባንክ አ.ማ<br>እና<br>አቶ ማርቆስ ጋትሮ | መስከረም 25 ቀን 2012ዓ.ም | 252 |
| | **ውል** | | | | **257** |
| 49. | አንድ ውል ለተፈለገው ዓላማ ሳይውል ከቀረ ለውል መሠረዝ ምክንያት የሚሆን ሲሆን ውሉ ከተሰረዘ በኋላ ተዋዋይ ወገኖች ከውል በፊት ወደ ነበሩበት ሁኔታ እንዲመለሱ የማድረግ ውጤት የሚያስከትልና ውሉ | 161153 | ወጋገን ባንክ አ.ማ.<br>እና<br>የኢትዮጵያ የንግድ እና | ሚያዝያ 28 ቀን 2011 ዓ.ም | 258 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| | በመሠረዙ ምክንያት የደረሰ ጉዳት ካለ ለደረሰ ጉዳት በካሣ መልክ አንዱ ለሌላው የመክፈል ግዴታ ያለበት ስለመሆኑ<br>ፍ/ብ/ሕጉ አንቀጽ 1771/2/፣1788፣1790፣1791፣1799፣1815 | | የዘርፍ ማህበራት ም/ቤት | | |
| 50. | • አንድ ውል እንደ ውሉ ባለመፈፀሙ ለደረሰ ጉዳት ኪሳራ የመክፈል ኃላፊነት ያለበት ተዋዋይ ወገን ሊከፍል የሚገባውን የኪሳራ መጠን ለመወሰን በግራ ቀኙ መካከል የተደረገው የውል ዓይነት፣የነበራቸውን ግንኙነት እንዲሁም ቀድሞ የሚታወቁ ሁኔታዎች ሁሉ ግምት ውስጥ ሊገቡ የሚገባቸው ስለመሆኑ<br>• አንድ የኪራይ ውል እንደ ውሉ ባለመፈፀሙ ምክንያት የደረሰ ኪሳራ የሚቆረጠው በኪራይ ውል ስሌት ተመን መሰረት ሲሆን የኪራዩን ገንዘብ ልክ ለመወሰን አግባብነት የሚኖረው ማስረጃ የማዘጋጃ ቤት ባለስልጣናት የሚወስኑት ታሪፍ በመሆኑ ለተመሳሳይ ቤት የሚታወቅ ታሪፍ ቢኖር በመጠየቅ እንዲሁም ታሪፍ ከሌለ የቦታዎቹን ልማድ በመከተል ሊወሰን የሚገባ ስለመሆኑ | 169077 | መይ ሪል ስቴት ዴቨሎፐመንት ኃ/የተ/የግ/ማህበር<br>እና<br>አቶ ያየህ ይራድ ፍቅሬ | ሰኔ 28ቀን 2011 ዓ.ም. | 268 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| | በፍ/ብ/ህ/ቁ 1771፣1799፣1801፣2950(2) | | | | |
| 51. | የቤት ኪራይ እንዲከፈል መጠየቅ ካለበት ጊዜ ጀምሮ እስከ ሁለት ዓመት ድረስ ካልተጠየቀ የቤት ኪራይ ክፍያ እንደተከፈለ ይቆጠራል የሚለዉ የሕግ ግምት፣ ሁለት ዓመቱ ሳይደርስ ባለገንዘቡ ገንዘቡ እንዲከፈለዉ ባለዕዳዉ ላይ ክስ አቅርቦ እንደሆነ እዳዉ እንደተከፈለ ይቆጠራል የሚለው የህግ ግምት ቀሪ ስለሚያደርገው ክሱ በሁለት ዓመት ይርጋ የማይታገድ ስለመሆኑ<br><br>በፍ/ብ/ሕ/ቁ.2024(መ)፣2025 (ለ) | 168198 | አፍሪካ ክንፋ መረዳጃ እድር<br>እና<br>እነ አቶ ዮሴፍ ደበበ | ሠኔ 24 ቀን<br>2011ዓ.ም | 273 |
| | **ከውል ውጪ ኃላፊነት** | | | | **277** |
| 52. | የአንድ ሕንጻ ባለሀብት ወይም ባለይዞታ ሕንጻው ሊያደርስ ይችላል ተብሎ ያልታሰበ ድንገተኛ ነገር ቢያደርስ ሕንጻው ለሚያደርሰው ጉዳት ከውል ወጪ ኃላፊነት ያለበት ሲሆን ጉዳት የደረሰበት ባለንብረትም የኢንሹራንስ ውል ያለው ከሆነ ኢንሹራንስ ድርጅቱ ለደረሰው ጉዳት ተገቢውን ክፍያ ከከፈለ በኂላ ጉዳት በደረሰበት ሰው ተተክቶ የህንፃውን ባለሀብት ለመጠየቅ መብት ያለው ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2088 ፣2077፣ የንግድ ህግ 683 | 161417 | ፀሀይ ኢንሹራንስ አ/ማ<br>እና<br>የኢትዮጵያ መድን ድርጅት | ግንቦት 12 ቀን<br>2011 ዓ.ም | 278 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| 53. | • የአንድ ባለሙያ ማስረጃ በቀረበ ጊዜ በዋናነት የሚመረመረው የባለሙያው ገለልተኛነት እና ሙያዊ ብቃት ሲሆን ሁለቱን መስፈርቶች ካሟላ ማስረጃው የፍሬ ነገሩን መኖር ወይም አለመኖር ለማረጋገጥ ከፍተኛ ግምት የሚሠጠው (high probative value) ማስረጃ በመሆኑ ለባለሙያ ማስረጃ ውጤት ሳይሰጥ ውጤቱን አለመቀበል የማስረጃ ምዘና መርህ ስህተት ስለመሆኑ<br>• በአንድ በተዘረጋ የኤሌክትሪክ መስመር ምክንያት ለደረሰ ጉዳት ኃላፊነቱን የሚወስደው የኤሌክትሪክ መስመሩን የዘረጋው አካል እንጂ ሌላ ሰው በቤቱ በዘረጋውና ባለቤት ላልሆነበት የኤሌክትሪክ መስመር አጥፊ ሳይሆኑ ኃላፊ ስለመሆን በተደነገገው የውል ውጭ ኃላፊነት ክፍል ኃላፊ ሊሆን የማይገባው ስለመሆኑ<br><br>የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2066 — 2086 | 175142 | የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት ሠሜን ሪጅን ሑመራ ዲስትሪክት<br>እና<br>አቶ ወሉ ገ/ሔር | ግንቦት 24 ቀን 2012 ዓ/ም | 282 |
| | **ግብር** | | | **286** | |
| 54. | የግብር አስገቢ ባለስልጣን አንድ ግብር ከፋይ ገቢውን በየጊዜው እያሳወቀ ግብሩን እየከፈለ መሆኑ ብቻ በቂ አይደለም ብሎ ካመነ በግብር ከፋዩ የቀረቡ ማንኛውንም መግለጫዎች ሰነዶች እና የሂሳብ መዝገቦች በማናቸውም ጊዜ | 153016 | ወ/ሮ ከበደች ዘሚካኤል<br>እና<br>የአራዳ ክፍለ ከተማ | ጥር 30 ቀን 2011 ዓ.ም. | 287 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| | በመመርመርና በማረጋገጥ በግብር ከፋዩ የተገኙትን የግብይት ማስታወሻዎች በባለሙያዎች በማስመርመር ተጨማሪ ግብር መወሰኑ ስላመቻሉ<br>የገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 286/94 አንቀጽ 38/2፣66 | | አነስተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት | | |
| 55. | • በንግድ የግብር ዘመን የደረሰ ኪሳራ ሊሸጋገር የሚችለው ከሚቀጥሉት ሶስት የግብረ ዘመናት ውስጥ የሚገኝ ግብር የሚከፈልበት ገቢ ላይ መጀመሪያ ያጋጠመው ኪሳራ በኂላ ካጋጠመው አስቀድሞ በማካካስ ሊሸጋገር የሚችል እና ይህም በማናቸውም ሁኔታ ከሁለት ሶስት ዓመታት ከሚቆጠሩ ስድስት ዓመታት በላይ ሊሸጋገርና ሊቀናነስ የማይችል ስለመሆኑ<br>• የአንድ ግብር ከፋይ ኪሳራ ሊሸጋገር የሚችለው በግብር ባለሥልጣን ኦዲት ተደርጐ ተቀባይነት ሲያገኝ ወይም በውጭ ኦዲተር የተመረመረ የሂሳብ መግለጫ ሲቀርብ ስለመሆኑ<br><br>አዋጅ ቁጥር 286/94 አንቀጽ 28/1/ እና /3/፤በደንብ ቁጥር 78/1994 እንደተሻሻለው አንቀጽ | 161867 | የኢትዮጵያ ገቢዎች ጉምሩክ ባለሥልጣን<br>እና<br>ሱፐር ማክስ ኦብቲካል ሚዲያ ኃላ/የተ/የግ/ማህበር | ሚያዚያ 25 ቀን 2011 ዓ.ም. | 293 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| **የወንጀል ሕግ** | | | | | |
| 56. | አንድ ጉዳት የደረሰበት ሰው ጉዳት አድራሹ በህግ ቁጥጥር ሥር ውሎ በዋስ በመፈታቱ ላይ ቅሬታ ቢኖረው በህግ በተቀመጠው ሥነሥርዓት መጠየቅ እንጂ ለምን በዋስ ተፈታ፣እንደገና ጉዳት ያደርስብኛል በሚል ትንበያ፣እንዲሁም ፍትህ ተደክሟል በሚል በራሱ ፍትህን ለማስፈጸም ግድያ በፈፀመበት ሁኔታ የደረሰበት ጉዳት ወንጀል ለመፈጸም ቀስቃሽ ሆኗል በሚል ቅጣትን አቅልሎ መወሰን ተከሳሹን የማያስተምር እና ፍትህን በራሱ መፈጸሙ ምክንያታዊ እንደሆነ እንዲሰማው የሚያደርግ ፣ሌላውን ማኅበረሰብ ፍትህን በራሱ እንዲያስፈጽም የሚገፋፋ ወይም መጥፎ አርአያ የሚሆን፣ዋነኛው የወንጀል ህግ ዓላማ የሆነውን የህዝብን ሠላምና ደኅንነት የማስጠበቅ ዓላማ እንዳይሳካ የሚያደርግ ስለመሆኑ | 171943 | የፌዴራል ጠቅላይ ዐቃቤ ህግ<br>እና<br>ኪዳኔ ቶላ | ህዳር 26 ቀን 2012 ዓ/ም | 298 |
| 57. | በአንድ የወንጀል ጉዳይ ተከሳሽ የሆነ ሰው የቀድሞ የጥፋተኝነት ሪኮርድ ያልቀረበበት፣ ጥፋቱን አምኖ የተፀፀተና የቤተሰብ አስተዳዳሪ መሆኑ ሲታይ ቅጣትን በገደብ ለማቆም የተመለከቱትን ቅድመ ሁኔታዎች በአብዛኛው ያሟላ ቢሆንም የስር ፍ/ቤት የቅጣቱ መገደብ ላይ ባለማመኑ የቀረበለትን የገደብ ጥያቄ ውድቅ ሲያደርግ ቅጣቱ እንዳይገደብ የሚያደርጉ ምክንያቶችን ባለመግለፁ ብቻ ጉዳዩ ወደ ስር ፍ/ቤት መመለስ አስፈላጊ ስላለመሆኑ | 169726 | አቶ ፍቅሩ ደሌሳ<br>እና<br>የፌዴራል ጠቅላይ ዐ/ሕግ | ግንቦት 14 ቀን 2011 ዓ.ም | 305 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| 58. | አንድ ተከሳሽ ማንኛውም የንግድ ዕቃን ከመደበኛው የግብይት አሰራር ውጭ በማናቸውም ማጓጓዣ ከተፈቀደ የስርጭት መስመር ውጭ ሲያጓጉዝ የተያዘ ስለመሆኑ ሳይረጋገጥበት፤ዕቃውም የተፈቀደ የስርጭት መስመር ያለው መሆን አለመሆኑና ከመስመር ውጪ ሲጓጓዝ የነበረ መሆኑ ባልተረጋገጠበት ሁኔታ በወንጀል ጥፋተኛ ሊባል የማይገባው ስለመሆኑ<br>የነጋዴዎች እና የሸማቾች ጥበቃ አዋጅ ቁጥር 813/2006 አንቀጽ 24/3/ እና 43/4/ | 168067 | ሰይድ አሊ አበጋዝ<br>እና<br>የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የንግድ እና ሸማቾች ዓቃቤ ሕግ | 29/09 / 2011 ዓ.ም. | 313 |
| 59. | አንድን ዕቃ ከውጪ የሚያስመጣ ሰው ለጉምሩክ ሥርዓት አፈጻጸም ሲባል ስለሚያስመጣው ዕቃ አስፈላጊ የሆኑ መግለጫዎችን በመስጠት በዲክላራሲዮን ላይ በማስመዝገብ ወደ ሐገር ውስጥ የሚገቡ ዕቃዎች በላኪው እና በአስመጪው መካከል በሚደረግ ስምምነት ወደ ሐገር ውስጥ የሚገቡ ከመሆናቸው አኳያ ወደ ሐገር ውስጥ እንዲገባ የተደረገው ዕቃ አስመጪው በዲክላራሲዮን ካስመዘገበው ዕቃ የበለጠ ዋጋ ያለው ሆኖ በተገኘ ጊዜ አስመጪው የተላከውን ዕቃ ሊያውቅ የሚችልበት ሁኔታ የለም ተብሎ ከወንጀል ተጠያቂነት ነፃ ሊደረግ የማይገባ ስለመሆኑ<br>የጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 859/06 አንቀጽ 13/4/፣169/2/ | 163069 | የፌዴራል ጠቅላይ ዓቃቤሕግ<br>እና<br>እነ ክኤሳድ ጠቅላላ የንግድ ሥራ ኃ/የተ/የግ/ማሕበር | ሕዳር 26 ቀን 2012 ዓ.ም | 318 |
| 60. | ከተገኘ ገቢ የሚከፈል ግብርንና የተሰበሰበን ተጨማሪ እሴት ታክስ ክፍያ ደረሰኞች ሐሰተኛ መሆናቸው ብቻ አንድን ተከሳሽ ጥፋተኛ ሊያስብለው | 181958 | አቶ ገበያው ሽቴ<br>እና | ታሕሳስ 20 ቀን 2012 ዓም | 324 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| | የማይችልና ሐሰተኛ ደረሰኝ ናቸው የተባሉት ደረሰኞች አፈጣጠርና ለገቢ ሰብሣቢው መስሪያቤት አቀራረብ ሂደት ላይ የተከሳሹን ድርሻና በሕግ የተጣለበት ግዴታ ከወንጀል ህግ መሰረታዊ መርህና የወንጀል ማስረጃ ምዘና መርህን በተከተለ መንገድ ሊመረመር የሚገባው ስለመሆኑ<br>ከወንጀል ሕግ አንቀፅ 23(1) ፣የተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ ቁጥር 285/94 አንቀፅ 22፣49፣50 (1) | | የሰሜን ሸዋ ዞን ገቢዎች ዐ/ህግ | | |
| 61. | በወንጀል ሕግ አንቀጽ 539/1/ሀ መሰረት በሰው መግደል ወንጀል በተመሰረተ ክስ ላይ የግል ተበዳይ ህይወት በጠፋበት እና ወንጀሉ የአካል ጉዳት ማድረስ ስለመሆኑ በማስረጃ ባልተረጋገጠበት ሁኔታ የተከሳሾች የሀሳብ ክፍል ከባድ የአካል ጉዳት ለማድረስ ነው በሚል የክሱን የህግ ድንጋጌ ወደ አንቀጽ 556/2/ሀ ዝቅ በማድረግ የሚሰጥ የቅጣት ውሳኔ ተቀባይነት የሌለው ስለመሆኑ | 164030 | የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ፍትሕ ቢሮ ዓቃቤ ሕግ<br>እና<br>እነ ሀብታሙ በለጠ<br>(3 ሰዎች) | ሕዳር 30 ቀን 2012 ዓ/ም | 332 |
| 62. | አንድ ሰው ለብዝበዛ ዓላማ ሲባል በሕገ-ወጥ መንገድ ሰዎችን የማዘዋወር ወንጀል ፈፅመኻል ሊባል ስለሚችልበት አግባብ<br>ሕገ-ወጥ የሰዎች ዝውውር እና ስደተኞችን በሕገ-ወጥ መንገድ ድንበር ማሻገር ወንጀልን ለመከላከልና ለመቆጣጠር የወጣ አዋጅ ቁጥር 909/07 አንቀጽ 3/2/ሀ/ | 167965 | አህመድ ኢብራሂም<br>እና<br>የኦሮሚያ ክልል ዐ/ህግ | ህዳር 26 ቀን 2012 ዓ.ም | 343 |
| 63. | የአራጣ ወንጀል የተፈጥሮ ሰው ላይ ብቻ ሳይሆን በህግ የሰውነት መብት | 167805 | የትግራይ ክልል ፍትህ ቢሮ | ጥቅምት 26 ቀን | 351 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| | በተሰጠው ድርጅት/ማህበር/ ላይም ተፈጻሚ ሊሆን የሚችል ስለመሆኑ<br>የወንጀል ህግ አንቀጽ 712/1/ሀ/ | | እና<br>እነ አቶ ታደሰ ኪዳነማርያም | 2012 ዓ.ም | |
| 64. | አንድ ተከሳሽ አስቀድሞ በፈጸመዉ ወንጀል ጥፋተኛ ተብሎ በአመክሮ ከተፈታ አምስት ዓመት ያለፈዉ ቢሆንም ለፍ/ቤት የመሰየም ጥያቄ አቅርቦ ባልተሰየመበትና ቅጣቱም ከፍርድ መዝገብ ተሰርዞ እንዳልተሰጠ ባልተቆጠረበት ሁኔታ የጥፋተኝነቱ ሪከርዱን በቅጣት ማክበጃነት መያዝ ተገቢ ስለመሆኑ<br>በወ/ሕ/አንቀጽ 82(1/ሀ) ፣84(1/ሐ)፣ 232፣ 233 | 161791 | ታምሬ አበራ ረጋሳ<br>እና<br>የፌዴራል ጠቅላይ ዐ/ሕግ | የካቲት 25 ቀን 2011 ዓ.ም | 356 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| 65. | ከአንድ የወንጀል ድርጊት ጋር በተያያዘ ንብረት የሚወረሰዉ ወይም ለመንግስት ገቢ የሚደረገዉ በወንጀል ህጉ እና በወንጀል ስ/ስ/ህጉ መሠረት በቅጣት መልክ በመሆኑ ንብረቱ የሚወረስ መሆን አለመሆኑ ዉሳኔ ማግኘት ያለበት በወንጀል መዝገብ እንጂ በወንጀል መዝገብ ላይ የተሰጠን ውሳኔ ብቻ መነሻ በማድረግ በአዲስ መልክ በሚቀርብ የፍትሐብሔር ክርክር ስላለመሆኑ የወንጀል ህግ አንቀጽ 98፣100(1) እና 140 | 137908 | የጋሞ አካባቢ ከፍተኛ ዐቃቤ ሕግ<br>እና<br>ወ/ሮ ፀሐይ አሰፋ | 21/05/2010 | 360 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| 66. | አንድ ከባድ የአካል ጉዳት ማድረስ ወንጀል ፈፅመሃል ተብሎ የተከሰሰ ተከሳሽ ድርጊቱን ለመፈጸም የተጠቀመበት መሳሪያ የሌለ መሆኑ በማስረጃዎች በተረጋገጠበት ሁኔታ በከባድ የአካል ጉዳት ማድረስ ወንጀል ጥፋተኛ ሊባል የማይገባ ስለመሆኑ<br>የወንጀል ህግ አንቀፅ 555 ፣556(1) | 168166 | አቶ ይገዙ ቡርዜ<br>እና<br>የደቡብ/ ብ/ብ/ሕ/ክ/መ/ ፍትህ ቢሮ ዓቃቤ ህግ | ግንቦት 28 ቀን 2011 ዓ.ም. | 367 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| 67. | ቅጣት ሊገደብ የሚችለው ጥፋተኛ የተባለን ሰው ለጥፋቱ መነሻ የሆኑትን ምክንያቶችን በጠቅላላው በመመልከት፤ የወንጀሉ ከባድነት/ the gravity of the crime/ በማየት፤ በጥፋተኛው ላይ የተወሰነውን ቅጣት ለጊዜው በገደብ እንዲታገድ በማድረግ የወንጀለኛውን ጠባይ ለማረምና ለማሻሻል እንዲሁም ወደ መደበኛ ማህበራዊ ኑሮው ለመመለስ ጠቃሚ መሆኑ ሲታመን እና በአጠቃላይ ቅጣት ስለሚገደብባቸው ሁኔታዎች በወንጀል ሕጉ የተቀመጡት መስፈርቶች መሟላታቸው ሲረጋገጥ ስለመሆኑ<br>የወንጀል ሕግ አንቀጽ 192፣194፣196/2/ እና 197 | 171403 | መላኩ ያዕቆብ<br>እና<br>የፌዴራል ጠቅላይ ዓቃቤ ሕግ | ሕዳር 22 2012 ዓ.ም | 372 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| 68. | አንድ ሰው በፈጸመው ወንጀል ምክንያት በማረሚያ ቤት በመሆኑ በሕፃናት ልጆቹ ላይ የሚደርሰውን ቁሳዊም ሆነ ኅሊናዊ ጫና ለማስቀረት ሲባል እንዲሁም ሕጻናቱ የወላጆቻቸውን እንክብካቤ እና ድጋፍ አግኝተው እንዲያድጉ ለማድረግ ሲባል፤ ፍ/ቤቶችም የሕጻናት ደኅንነት በቅድሚያ የማረጋገጥ ሕገመንግስታዊ ግዴታ ያለባቸው በመሆኑ በወንጀለኛው ላይ የተወሰነውን ቅጣት በመገደብ ህፃናቱ ተገቢውን የወላጅ እንክብካቤ እንዲያገኙ ለማድረግ ያስችል ዘንድ በወንጀል ህጉ ቅጣት ለማገድ የተቀመጡትን ሁኔታዎች በማረጋገጥ የተወሰነውን ቅጣት እንዳይፈጸም ማገድ የሚገባ ስለመሆኑ<br>የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገመንግሥት አንቀጽ 36/2፤የወንጀል ህግ አንቀጽ 192፣194፤የዓለም አቀፉ የህፃናት መብቶ፤ች ስምምነት የጠቅላላ ጉባኤ ውሳኔ ቁጥር 44/25 እንደ ኤሮፓውያን አቆጣጠር 1989 የወጣው አንቀጽ 7 (1)፤ የህፃናት መብቶች ኮንቬንሽን አንቀጽ 18 | 177216 | አቶ ገብርኤል ፓራቶሪ አንቶንዮ<br>እና<br>የፌዴራል ጠቅላይ ዐቃቤ ህግ | ሕዳር 30 ቀን 2012 ዓ/ም | 378 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| 69. | ዓቃቤ ሕግ የሚያቀርበው የክስ አቤቱታ በወንጀል ሥነ-ሥርዓት ሕግ መሠረት ያልቀረበ ሆኖ ሲገኝ ክሱ የቀረበለት ፍ/ቤት በራሱ አነሳሽነት ክሱ በህጉ አግባብ ተሻሽሎ እንዲቀርብ ማድረግ ያለበት ስለመሆኑ እና ዓቃቤ ሕግ ክሱን አሻሽሎ እንዲቀርብ ሳይደረግ በሕጉ አግባብ ተዘጋጅቶ ያልቀረበው ክስ የተከሳሹን የመከላከል መብት የሚያጣብብ በመሆኑ ተከሳሹ በሕግ አግባብ ተዘጋጅቶ ባልቀረበው ክስ ጥፋተኛ ሊባል የማይገባ ስለመሆኑ<br>በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ ቁጥር 118 እና 119/1/ | 165440 | አየለ ሀፌቦ<br>እና<br>የደቡብ ክልል ፍትሕ ቢሮ ዓቃቤሕግ | ጥር 27 ቀን 2012 ዓ.ም | 387 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| 70. | የወንጀል ሕግ አንቀጽ 23/2 ድንጋጌ እና የሙስና ወንጀሎች አዋጅ ቁጥር 881/2007 መሰረት ዓቃቤ ሕግ መደበኛውን የወንጀል ሕግ ወይም ወንጀል መፈጸሙን ለማስረዳት ልዩ መስፈርትን የማያስቀምጡ ልዩ ሕጎችን መሠረት በማድረግ ክስ ሲያቀርብ በወንጀል ሕግ አንቀጽ 23/2 መሠረት የአንድ ተከሳሽን የሀሳብ ክፍል እንዲያረጋግጥ የተጣለበት የማስረዳት ሸክም ለሙስና ወንጀሎች በተመሳሳይ ተፈጻሚ የማይሆን ስለመሆኑ እና በሙስና ወንጀሎች አዋጅ በተደነገገው መሠረት ግዙፋዊ ፍሬነገር መፈጸሙ በተረጋገጠ ጊዜ ተከሳሹ በድንጋጌው የተመለከተውን ግዙፋዊ ፍሬነገር ለመፈጸም የነበረውን የሀሳብ ክፍል ተቃራኒ ማስረጃ በማቅረብ እንዲያስተባብል የማስረዳት ሸክሙ ወደ ተከሳሹ የሚዛወር ስለመሆኑ<br>የወንጀል ህግ አንቀጽ 23/2/፣የሙስና ወንጀሎች አዋጅ ቁጥር 881/2007አንቀጽ 3 ፣አንቀጽ 13/3 እና 13/1/ሐ | 162738 | እነ አቶ መሐመድ ያዕቆብ ከድር አልይዘአ<br>እና<br>የኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጸረ ሙስና ኮሚሽን ዓቃቤሕግ | መጋቢት 30 ቀን 2012 ዓ.ም | 393 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| 71. | አንድ ተከሳሽ በጋዜጣ ጥሪ ተደርጎለት ክስ የቀረበበት ስለመሆኑ አውቋል የሚል ግምት ሊወሰድ የሚገባው ሐገር አቀፍ ስርጭት ባለው ጋዜጣ ጥሪ የተደረገለት መሆኑ በተረጋገጠ ጊዜ እንጂ በአንድ ክልል ብቻ ተደራሽ በሆነ ጋዜጣ ብቻ ጥሪ መደረጉን መጥሪያ እንደደረሰው ማረጋገጫ አድርጎ በመውሰድ እና መጥሪያ ደርሶታል የሚል ግምት በመውሰድ ጉዳዩን ተከሳሹ በሌለበት አይቶ ውሳኔ መስጠት በሕገ-መንግስቱ ለተከሰሱ ሰዎች የተጠበቁላቸውን መሠረታዊ መብት የሚነካ ስለመሆኑ<br>የወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ 161፣199(ሀ) | 173967 | አቶ አማኑኤል ገ/ጊዮርግስ<br>እና<br>የትግራይ ክልል ፍትሕ ቢሮ ዓቃቤሕግ | መጋቢት 28 ቀን 2012 ዓ.ም | 413 |
| **የወንጀል ሥነ-ሥርዓት ሕግ** | | | | | |
| 72. | የወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ አንቀፅ 63 እና 67 በተከሳሾች ላይ ስላላቸው ተፈጻሚነት | 182266 | የደቡብ ብሔሮች ብሔረሠቦች እና ሕዝቦች ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ዓ/ሕግ እና<br>አሸብር ዳጌታ ሄሎ | ጥቅምት 19 ቀን 2012 ዓ.ም | 420 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| 73. | አንድ ድርጊት ከመፈፀሙ በፊት፣ ሲፈፀም ወይም ድርጊቱ ከተፈፀመ በኃላ ዐቃቤ ህግ ስላቀረበው ክስ ማስረጃ ይሆነኛል በማለት በሕጉ አግባብ ያቀረበውን ማስረጃ በማስረጃነት ሊቀርብ የማይችልና ተቀባይነት የሌለው (Inadmissible evidence) ነው የሚል ግልፅ ክልከላ የሚያደርግ የሕግ ድንጋጌ በሌለበት የማስረጃው አስረጂነት ዋጋ ሳይታይና ሳይመዘን በደፈናው ማስረጃው ከተከሳሾች ጋር አብሮ ተከሳሽ የነበረ ነው፤ የተከሳሾችን የመከላከል መብት ይጎዳል በሚል ምክንያት ተቀባይነት የሌለው ነው በማለት ውድቅ ማድረግ የማስረጃ ተቀባይነት፤አግባብነትና ምዘና መርህን፤ የክርክር አመራርና የዳኝነት አሰጣጥ ስርዓትን ያልተከተለ ስለመሆኑ ወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ 108-122፣የሙስና ወንጀሎች አዋጅ ቁጥር 881/2007 አንቀጽ 8 እና የተሻሻለው የጸረ ሙስና ልዩ የሥነ ሥርዓትና የማስረጃ ሕግ አዋጅ ቁጥር 434/1997 እንደተሻሻለው አዋጅ ቁጥር 882/2007 አንቀጽ 41፣43 | 163947 | የፌዴራል ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ<br>እና<br>እነ አቶ ጌታቸው ዋለልኝ | ሐምሌ 15 ቀን 2011 ዓ.ም. | 430 |
| 74. | • በሙስና ወንጀሎች አዋጅ መሰረት በተመሰረተ ክስ ተከሳሹ እንዲከላከል ብይን ተሰጥቶ ይህ ብይን የተሰጠበት ድንጋጌ አማራጭ ቅጣትን ያስቀመጠ ሆኖ በተሻሻለው የፀረ-ሙስና ልዩ የስነ ስርአትና የማስረጃ ህግ (ማሻሻያ) አዋጅ ቁጥር 882/2007 አንቀጽ 3/1 ሁለተኛ ሀሳብ ላይ ከአራት አመት በላይ በሚል የተደነገገውን ቅጣት | 182050 | የፌዴራል ጠቅላይ ዐ/ህግ<br>እና<br>ብርጋዴር ጀነራል ሐድጉ ገ/ጊዮርጊስ | ታሕሳስ 24 ቀን 2012 ዓ.ም | 437 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| | እንደ መነሻ ቅጣት በመውሰድ የቅጣት መነሻቸው አራት ዓመት የሆነ በጽኑ እሥራት የሚያስቀጡ ወንጀሎችን የሚመለከት እንደሆነ አድርጎ በመውሰድ ዋስትናን መፍቀድ ተቀባይነት የሌለው ስለመሆኑ የተሻሻለው የጸረ-ሙስና ልዩ የሥነ-ሥርዓት እና የማስረጃ ሕግ አዋጅ ቁጥር 434/97 አንቀጽ 4/1/<br>• ተከሳሹ በፈፀመው የወንጀል ድርጊት ምክንያት የደረሰው የጉዳት መጠንን በተመለከተ አቃቤ ህግ ክስ በመሰረተበት የህግ አንቀጽ በተከሳሹ የወንጀል ድርጊት ምክንያት የደረሰውን የጉዳት መጠን አለመግለጹ ተከሳሽ በዋስትና ቢለቀቅ ዋስትናውን አክብሮ ሊቀርብ አይችልም የሚል ግምት በመውሰድ የዋስትና መብትን የማያስከለክል ስለመሆኑ<br>የወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 67 | | | | |
| 75. | አንድ ተከሳሽ ጥፋተኛ ቢባል በቀላል እሥራት፤ ከ12 ዓመት በታች በሆነ ጽኑ እሥራት ወይም ከአሥራ ሁለት ዓመት በላይ በሆነ ጽኑ እሥራት ሊቀጣ የሚችል በመሆኑ ተመራጭ የሚሆነው የፍርድ ሂደት ተከሳሹ በተከሰሰበት ድንጋጌ የተቀመጠው ከፍተኛ ቅጣት ሊቀጣ ይችላል ብሎ ከወዲሁ በማሰብ ጉዳዩን በሌለበት እንዲታይ ማድረግ ሳይሆን የተከሳሽ በችሎት ተገኝቶ የመከራከር መብት ከሚጣስ ይልቅ ተከሳሽ እስኪገኝ ድረስ | 179416 | ሀለቃ ንጉሴ አብርሃ<br>እና<br>የትግራይ ክልል ፍትሕ ቢሮ | ሰኔ 23 ቀን 2012 ዓ.ም | 454 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| | የፍርድ ሂደቱ እንዳይካሄድ በማድረግ ስለመሆኑ<br>የኢፌዲሪ ሕገመንግስት አንቀጽ 20/4፣ ዓለም ዓቀፍ የሲቪል እና የፖለቲካ መብቶች ስምምነት አንቀጽ 14፣የወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ 162(2) | | | | |
| 76. | አንድ ወንጀል ክስ እንዲሻሻል ትእዛዝ የሚሰጠዉ በክስ ማመልከቻ ፎርም ወይም በክሱ ማመልከቻ ላይ ስለወንጀሉ አስፈላጊ ዝርዝር ዉስጥ ስህተት ሲገኝ ወይም ሳይጠቀስ ሲቀርና ይህም መሰረታዊ ነገር ሆኖ ሲገኝ ስለመሆኑ<br>በወንጀለኛ መቅጫ ስነ ስርዓት ህግ አንቀጽ 111፣112፣118 እና 119/1/ | 171521 | የፌዴራል ጠቅላይ ዓቃቤ ህግ<br>እና<br>ወ/ሮ ትርሃስ መስፍን ገ/እግዚአብሔር | ታኅሳስ 23 ቀን 2012 ዓ/ም | 459 |
| **ልዩ ልዩ** | | | | | |
| 77. | የእርሻ የኢንቨስትመንት መሬት በሚመለከተው አካል እውቅና በሕግ አግባብ መብት ከሚተላለፍበት ስርአት ውጭ በኪራይ ለኢንቨስትመንት ሥራ የተገኘ መሬት በሽያጭ ለ3ኛ ወገን ማስተላለፍ የማይቻል ስለመሆኑ<br>የተሻሻለው ትግራይ ክልል የኢንቨስትመንት የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር 239/2006 አንቀጽ 2፣22/5/፤24፣26/4/ | 159062 | አቶ መረሳ ወ/ማርያም<br>እና<br>ቄስ ወ/ጊዮርጊስ ኪዳኔ | ጥር 30ቀን 2011 ዓ.ም | 466 |
| 78. | በጉምሩክ አዋጅ እና መመሪያ መሰረት በመጋዘን ገብተው ሊወጡ ያሉ ዕቃዎች ዉስጥ የኮንትሮባንድ ዕቃ መኖሩን ጠቁሞ በማስያዝ ምክንያት | 169729 | የገቢዎች ሚኒስቴር<br>እና | ግንቦት 30 ቀን 2011 ዓ.ም. | 471 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| | ለጠቃሚ ስለሚከፈለው የወሮታ ክፍያ አግባብነት<br>የጉሙሩክ አዋጅ ቁጥር 859/2006 አንቀጽ 56 እና 132 ፤የህገ ወጥ ዕቃዎች መረጃ አሰጣጥ፣ አያያዝ እና ወሮታ ክፍያን ለመወሰን ተሻሽሎ የወጣውን መመሪያ ቁጥር 78/2004 አንቀጽ 2(7)፣19(ለ) | | አቶ አስራት አሰግድ | | |
| 79. | በውጭ ሀገር ሥራና ሰራተኛ አገናኝነት ሥራ ዋስትና የሚሆን ገንዘብ በማስያዝ ከኢፌዴሪ ሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ፈቃድ አውጥቶ የሚሰራ ኤጀንሲ የዋስትና ገንዘቡ ተመላሽ እንዲደረግለት ለማድረግ ኤጀንሲው ፈቃዱን መመለስ አለመመለሱ፤ አስቀድሞ የተሰጠው ፈቃድ ካልተመለሰ ፈቃድ ሳይመለስ የዋስትና ገንዘብ ሊመለስ የሚገባ ስለመሆን አለመሆኑ፤ እንዲሁም ኤጀንሲው ለሥራ ወደ ውጪ አገር ለላካቸው ዜጎች መብትና ደህንነት ማስከበሪያ በባንክ ያስያዘው የዋስትና ገንዘብ እንዲለቀቅለት ሊያሟላ የሚገባቸው ሁኔታዎች የተሟሉ መሆን አለመሆኑን ከክርክርና ማስረጃ አንጻር ታይቶና በአግባቡ ተገናዝቦ መወሰን ያለበት ስለመሆኑ<br>የውጪ ሀገር ስራ ስምሪት አዋጅ ቁጥር 923/2008 አንቀጽ 60(5)፣ አንቀጽ 78 | 171530 | የኢፌዴሪ ሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር<br>እና<br>አቶ ሱልጣን ጃቢር መሀመድ | ግንቦት 29 ቀን 2011 ዓ.ም. | 478 |
| 80. | በፍርድ ክልከላ የተደረገበት ሰው ክልከላው እንዲወሰን ያደረጉት ምክንያቶች በቀሩ ጊዜና የተከለከለው ሰው ንብረቱን ለመምራትና ለማስተዳደር የሚችል የሆነ እንደሆነ በተደረገው ክልከላ ምክንያት ሌላ አዲስ ክስ ማቅረብ | 167560 | አቶ ቢቂላ አያኖ<br>እና | 30/09/2011 | 482 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| | የማይችል ቢሆንም የተደረገው ክልከላ እንዲነሳለት አቤቱታ ማቅረብ የሚችል ስለመሆኑ<br>በፍ/ህግ ቁጥር 351(1) ፣377፣378 | | አቶ አሊቢ ቂላ | | |

# ፍትሐብሔር ሥነ-ሥርዓት

የሰ.መ.ቁ 160916

ታሕሣሥ 30 ቀን 2011 ዓ.ም

**ዳኞች:-** ብርሃኑ አመነዉ

በዕዉቀት በላይ

እንዳሻዉ አዳነ

ሃይሉ ነጋሽ

እትመት አሠፋ

**አመልካች:-** አቶ ቦጃ በየነ

**ተጠሪ:-** የኦሮሚያ ጠቅላይ ዓቃቤ ሕግ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍ ር ድ**

ለሰበር አቤቱታው መነሻ የሆነው ጉዳይ ወንጀልን የሚመለከት ነው፡፡ የአሁን ተጠሪ በአሁን አመልካች ላይ በስር ፍ/ቤት ያቀረበው ክስ ይዘት አመልካች የኦሮሚያ ክልል የቡና ጥራትና ንግድ ቁጥጥር ለመወሰን የወጣውን አዋጅ ቁጥር 160/2002 አንቀጽ 13/2፤19(1)(2)(5)(6) እና 23(6) ድንጋጌን በመተላለፍ ሆን ብሎ አስቦበት በቀን 26/05/2010 ዓ.ም ከምሽቱ በግምት 3:00 ሰዓት በምዕራብ ጉጂ ዞን ገላና ወረዳ ፖሬ ከተማ ልዩ ቦታው ኬላ በተባለው ሕገ-ወጥ ቡና ንብረትነቱ የአመልካችበሆነ የሰሌዳ ቁጥሩ 3-38518 ኢ.አ በሆነ የጭነት መኪና ግምቱ ብር 6፣3520 የሆነ 14 ኩንታል ታጥቦ የተቀሸረ ቡና በመጫን ለጊዜው እጁ ካልተያዘ ሹፌር ጋር በመሆን ያለምንም ፈቃድ ከቡናው ላይ ሌላ ዕቃ በመጫን በማጓጓዝ ላይ እያለ ተይዟል የሚል ነው፡፡

አመልካች ቀርቦ ማንነቱ ከተረጋገጠ በኋላ ክሱ የደረሰው መሆኑን ለችሎቱ የገለጸ መሆኑን፤ ችሎቱም በሚገባው ቋንቋ የዓቃቤሕግን ክስ አንብቦለት ገብቶኛል በማለት ከገለጸ በኋላ መቃወሚያ የሌለው መሆኑን በመግለጽ የእምነት ክህደት ቃሉን ሲጠየቅ ድርጊቱን እንዳልፈጸመ እና ከመኪናው ረዳት እና ሹፌር ጋር ወደ ዲላ ከተማ በመጓዝ ላይ እንዳለ ህገወጥ ቡና ጭነሃል በማለት የተያዘ መሆኑን እና መኪናው ምን እንደጫነ የማያውቅ መሆኑን በመግለጽ ክሱን ክዶ የተከራከረ መሆኑን፤ ፍ/ቤቱም የዓቃቤሕግን ምስክሮች ሰምቶ አመልካች የቀረበበትን ክስ እንዲከላከል በማለት ብይን የሰጠ መሆኑን፤ አመልካች የመከላከያ ምስክር እንዲያቀርብ እድል ቢሰጠውም የመከላከያ ምስክር የለኝም በማለት ቅጽ ሞልቶ ያቀረበ መሆኑን እና ፍ/ቤቱም መከላከያ ምስክር ማቅረብ መብት እንጂ ግዴታ

አይደለም በማለት የአመልካችን ምስክር የማቅረብ መብት አልፎ አመልካችን ጥፋተኛ በማለት በሶስት ዓመት ጽኑ እሥራት እና በብር 25,000 መቀጮ እንዲቀጣ የወሰነ መሆኑን መዝገቡ ያሳያል፡፡ አመልካች ይህን ውሳኔ በመቃወም በየደረጃው ላሉ የክልሉ ፍ/ቤቶች አቤቱታ ያቀረበ ቢሆንም አቤቱታው ተቀባይነት አላገኘም፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው ይህን ውሳኔ በመቃወም ነው፡፡

የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሠረታዊ ይዘትም፡- የስር ፍ/ቤት አመልካች በጠበቃ እንድከራከር በራሱ ተነሳሽነት ሊያመቻችልኝ ሲገባ በዝምታ አልፎታል፤ አመልካች መንግስት ጠበቃ እንዲያቆምልኝ ያቀረብኩትን ጥያቄ በማለፍ የግል ጠበቃ እንዳቆም ጊዜ ሳይሰጠኝ በማልሰማው እና መናገር በማልችለው ቋንቋ ያለአስተርጓሚ የተከሰስኩበትን ነገር ሳላውቅ የተሰጠው ውሳኔ አመልካች በሕገ-መንግስቱ የተሰጠኝን መብት የሚነፍግ ነው፤ አመልካች የተከሰስኩበት ሕግ ከተጠረጠርኩበት ወንጀል ጋር አግባብነት የለውም፤ አመልካች መኪናውን አላሽከረከርኩም የጫነውንም ነገር አላወቅኩም፤ ሹፌሩ መኪናውን ትቶ በመሸሹ በመኪናው አጠገብ ስለተገኘሁ ብቻ ጥፋተኛ ልባል የማይገባ በመሆኑ የስር ፍ/ቤቶች እነኚህን ሁኔታዎች ሳያገናዝቡ የሰጡት ውሳኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ሥሕተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል የሚል ነው፡፡

የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ አመልካች የመኪናው ባለቤት ቢሆንም ለሾፌር ሰጥቶ ሲያሽከረክር ከነበረበት ሾፌሩ ማምለጡ ተረጋግጦ ባለበት፤ አመልካች የቡና ነጋዴ ወይም አምራች መሆኑ ባልተረጋገጠበት፤ በሌላ በኩል አመልካች የቡናውን መጫን ያውቅ የነበረ መሆኑ ባልተረጋገጠበት እና በሚገባው ቋንቋ በአግባቡ ስለመተርጎሙ እና የመከላከል መብቱን ስለማወቁ ጥርጣሬ በፈጠረ ሁኔታ የመከላከል መብቱ ታልፎ የመኪናው ባለቤት በመሆኑ ብቻ ጥፋተኛ የመባሉን አግባብነት ከወንጀል ሕግ አንቀጽ 23 እና ከተጠቀሰው አዋጅ ጋር በማገናዘብ ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ በዚህ ችሎት እንዲታይ ተደርጓል፡፡ ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎም ግራቀኙ በጽሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

የተጠሪ መልስ ይዘት በአጭሩ፡- አመልካች የመኪናው ባለቤት ሆኖ ፈቃድ ሳይኖረው በክሱ የተጠቀሰውን ቡና በሌላ ዕቃ ስር ጭኖ ሲሄድ መያዙ ተረጋግጦበታል፤ ቡናው የተጫነው ከአመልካች ዕውቅና ውጪ ነው የሚለው ክርክር አሳማኝ አይደለም፤ ቡናው በሌሊት የተጫነ እና ከሌላ ዕቃ ስር የተጫነ በመሆኑ አመልካች የወንጀል ሀሳብ እንዳለው የሚያሳይ ነው፤ አመልካች በአዋጁ መሠረት ሀላፊነት ስላለበት የመኪናው ባለቤት ስለሆንኩ ተጠያቂ ልሆን አይገባም በማለት የሚያቀርበው ክርክር አግባብነት የለውም፤ ፍ/ቤቱ ለአመልካች ክሱን ካነበበለት በኋላ በሚገባው መልኩ በድጋሚ የተነበበለት መሆኑ ተገልጿል፤ የክልሉን ፍ/ቤቶች እንደገና ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር 141/200 አንቀጽ 17/2 ፍ/ቤቱ ተከላካይ ጠበቃ ለማቆም የሚገደደው የተከሰሰበት ወንጀል ከአምስት ዓመት ጽኑ እሥራት በማያንስ የሚያስቀጣ ከሆነ እና በራሱ ጠበቃ ለማቆም የማይችል ከሆነ ነው፤የተሰጠው የቅጣት ውሳኔ አመልካችን የሚጠቅም በመሆኑ የስር ፍ/ቤቶች የሰጡት ውሳኔ ሊጸና ይገባል የሚል ነው፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ  በአጭሩ ከላይ የተገለጸው ነው፡፡ እኛም በስር ፍ/ቤት የተሰጠው ውሳኔ የአመልካች የመሰማት መብት ተጠብቆ የተሰጠ ውሳኔ ነው ወይስ አይደለም የሚለውን ጭብጥ በመያዝ ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸው ሕጎች ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው መርምረነዋል፡፡

በመሠረቱ የተከሰሱ ሰዎች በሕግ የመሰማት መብት / the right to fair trial / ያላቸው ሲሆን ክስ ከቀረበባቸው በኋላ ተገቢ በሆነ አጭር ጊዜ ውስጥ በመደበኛ ፍ/ቤት በመቅረብ ጉዳዩ በዝግ ችሎት እንዲታይ የሚያስችል ሕጋዊ ምክንያት ከሌለ በቀር ለሕዝብ ግልጽ በሆነ ችሎት የመሰማት መብት ያላቸው መሆኑን የሕገመንግሥቱ አንቀጽ 20/1 ድንጋጌ ያስገነዝበናል፡፡ ኢትዮጲያ የተቀበለችው የሲቪል እና የፖለቲካ መብቶች ዓለምዓቀፍ የቃልኪዳን ሰነድ አንቀጽ 14 ድንጋጌም  ........everyone shall be entitled to a fair and public hearing by a competent, independent and impartial tribunal established by law....... በማለት ይደነግጋል፡፡ ይህ መብት በሕገ-መንግስቱም ሆነ ኢትዮጲያ በተቀበለችው ዓለምዓቀፍ ስምምነት እውቅና የተሰጠው መሠረታዊ መብት እንደሆነ እና በየደረጃው ያሉ ፍ/ቤቶችም ይህን መሠረታዊ የሆነ መብት የማክበር እና የማስከበር ሀላፊነት እንዳለባቸው ከሕገመንግስቱ አንቀጽ 9/4 እና 13(1)(2) ድንጋጌዎች መገንዘብ ይቻላል፡፡

የተከሰሱ ሰዎች ክሱ በቂ በሆነ ዝርዝር እንዲነገራቸው እና በጽሑፍ የማግኘት መብት ያላቸው መሆኑን፤ በፍርድ ሂደት ባሉበት ወቅት በተከሰሱበት ወንጀል እንደ ጥፋተኛ ያለመቆጠር እና በምስክርነት እንዲቀርቡ ያለመገደድ፤ የቀረበባቸውን ማንኛውንም ማስረጃ የመመልከት፤ምስክሮችን የመጠየቅ፤ ለመከላከል የሚያስችላቸውን ማስረጃ የማቅረብ፤ ምስክሮቻቸው ቀርበው እንዲሰሙላቸው የመጠየቅ፤በመረጡት የሕግ ጠበቃ የመወከል፤ ጠበቃ ለማቆም አቅም በማጣታቸው ፍትሕ ሊጓደል የሚችልበት ሁኔታ ሲያጋጥም ከመንግስት ጠበቃ የማግኘት መብት፤ ይግባኝ የመጠየቅ እና የፍርዱ ሒደት በማይገባቸው ቋንቋ በሚካሄድበት ሁኔታ በመንግስት ወጪ ክርክሩ እንዲካሄድላቸው የመጠየቅ መብት ያላቸው ስለመሆኑ የሕገ-መንግሥቱ አንቀጽ 20 በዝርዝር የተደነገገ ሲሆን የሀገሪቱ ሕግ አካል በሆነው የሲቪል እና የፖለቲካ መብት አንቀጽ 14 ድንጋጌም ላይ በዝርዝር ተመልክቷል፡፡

የተከሰሱ ሰዎች የቀረበባቸውን ክስ በአግባቡ ተረድተው ክሱን መከላከል የሚችሉትም ክሱ በሚገባቸው ቋንቋ በዝርዝር ሲነገራቸው እና በጠበቃ ሲታገዙ እንደሆነ ግልጽ ነው፡፡ በመሆኑም ፍ/ቤቶች የፍ/ቤቱን የስራ ቋንቋ የማይችሉ ተከሳሾች በቀረቡላቸው ጊዜ አስተርጓሚ በመመደብ ክሱ በሚገባቸው ቋንቋ በዝርዝር የመንገር እና በጠበቃ ታግዘው የመከራከር መብት እንዳላቸው፤ ጠበቃ ለማቆም የሚያስችል ዓቅም ከሌላቸው በመንግሥት ወጪ ጠበቃ የማግኘት መበት እንዳላቸው የመንገር ሀላፊነት አለባቸው፡፡

የአመልካች ዋነኛ ክርክር የስር ፍ/ቤት አመልካች በጠበቃ በመታገዝ እንድከራከር አላደረገም፤ አመልካች የፍ/ቤቱን የስራ ቋንቋ የማልችል ሲሆን ያለአስተርጓሚ የተከሰስኩበትን ነገር ሳላውቅ

የተሰጠው ውሳኔ ሕገ-መንግስታዊ መብቱን የሚጻረር ነው የሚል ሲሆን ተጠሪ በዚህ ፍ/ቤት ባደረገው ክርክር ፍ/ቤቱ ለአመልካች ክሱን ካነበበለት በኋላ በሚገባው መልኩ በድጋሚ የተነበበለት መሆኑ ተገልጿል፤ የክልሉን ፍ/ቤቶች እንደገና ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር 141/200 አንቀጽ 17/2 ፍ/ቤቱ ተከላካይ ጠበቃ ለማቆም የሚገደደው የተከሰሰበት ወንጀል ከአምስት ዓመት ጽኑ እሥራት በማያንስ የሚያስቀጣ ከሆነ እና በራሱ ጠበቃ ለማቆም የማይችል ከሆነ ነው በማለት ከሚከራከር እና በስር ፍ/ቤት ውሳኔም ላይ አመልካች በሚገባው ቋንቋ ክሱ በድጋሚ ተነቦለታል በሚል ከመገለጹ በቀር አመልካች የፍ/ቤቱን የስራ ቋንቋ የማይችል ከመሆኑ አኳያ የተከሰሱ ሰዎች በሕገመንግሥቱ በተጠበቀላቸው መብት መሠረት አስተርጓሚ ተመድቦለት ክሱ የተነበበለት እና እንዲረዳው የተደረገ መሆኑን፤በጠበቃ የመወከል መብት እንዳለው እና በግሉ ጠበቃ ማቆም የማይችል ከሆነ በመንግስት ወጪ ጠበቃ የማግኘት መብት እንዳለው የተነገረው መሆኑን የስር ፍ/ቤት ውሳኔ ይዘት አያመላክትም፡፡ አመልካች አስተርጓሚ ተመድቦለት ክሱን እንዲረዳው እስካልተደረገ እና በጠበቃ እስካልታገዘ ድረስ የቀረበበትን ክስ በአግባቡ ተረድቶ ክሱን ለመከላከል ይችላል ተብሎ አይገመትም፡፡ በመሆኑም ጉዳዩ የቀረበለት ፍ/ቤት አመልካች የቀረበበትን ክስ በአግባቡ ተረድቶ መከላከል ይችል ዘንድ ለአመልካች አስተርጓሚ እንዲመደብ በማድረግ፤ አመልካች ጠበቃ የማቆም መብት እንዳለው እና ጠበቃ ለማቆም የሚያስችል አቅም ከሌለው በመንግስት ወጪ ጠበቃ የማግኘት መብት እንዳለው በመንገር ጉዳዩ እንዲታይ ማድረግ ሲገባው ይህን ሳያደርግ የሰጠው ውሳኔ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገመግስቱ እና ኢትዮጲያ በተቀበለቻቸው ዓለምዓቀፍ ስምምነቶች ለከተሰሱ ሰዎች የተጠበቁትን መሠረታዊ መብቶች ያላገናዘበ እና መሠረታዊ የሆነ የሕግ ሥሕተት የተፈጸመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. በኦሮሚያ ብሔራው ክልላዊ መንግሥት የገላና ወረዳ ፍ/ቤት በመ.ቁ 03750 በቀን 13/06/2010 ዓ.ም የሰጠው የጥፋተኝነት እና የቅጣት ውሳኔ የምዕራብ ጉጂ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 00832 በቀን 30/06/2010 ዓ.ም የሰጠው ትእዛዝ፤ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 260947 መጋቢት 13 ቀን 2010 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ፤የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 284002 ግንቦት 21 ቀን 2010 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 195/2/ለ/2 መሠረት ተሽሯል ፡፡
2. በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገመንግሥት አንቀጽ 20 ላይ ለተከሰሱ ሰዎች የተጠበቁላቸው መሠረታዊ መብቶች ሳይከበሩ የሚሰጥ ውሳኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ሥሕተት የተፈጸመበት ነው ብለናል፡፡
3. የገላና ወረዳ ፍ/ቤት በአመልካች ላይ ያስተላለፈው የጥፋተኝነት እና የቅጣት ውሳኔ የተሻረ መሆኑን አውቆ ለአመልካች አስተርጓሚ እንዲመደብለት በማድረግ፤ አመልካች በግሉ ጠበቃ

ማቆም የሚችል ከሆነ በግሉ ጠበቃ እንዲያቆም በማድረግ፤ አመልካች በግሉ ጠበቃ ማቆም የማይችል ከሆነ በመንግሥት ወጪ ጠበቃ እንዲመደብለት በማድረግ አመልካች የቀረበበትን ክስ እዲረዳው ካደረገ በኂላ ጉዳዩን አይቶ ተገቢውን እንዲወስን በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 195/2/ለ/2 መሠረት ጉዳዩ ተመልሶለታል፡፡

<u>**ት ዕ ዛ ዝ**</u>

-በአመልካች ላይ የተላለፈው የጥፋተኛነት እና የቅጣት ውሳኔ የተሻረ እና ጉዳዩ በድጋሚ እንዲታይ የተወሰነ በመሆኑ ተጠሪ ይህ ውሳኔ ከደረሰው ቀን ጀምሮ በአሥራ አምሥት ቀን ጊዜ ውስጥ መዝገቡን እንዲያንቀሳቅስ ታዟል፡፡

-የገላና ወረዳ ፍ/ቤት የአመልካችን አቆያየት በተመለከተ አግባብነት ያላቸውን ሕጎች መሠረት በማድረግ ተገቢውን ትዕዛዝ እንዲሰጥበት ታዟል፡፡

መዝገቡ ውሳኔ ስላገኘ ተዘግቷል፡፡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

**ፅ/ወ**

የሰ/መ/ቁ. 161062

ቀን 26/04/2011 ዓ.ም

ዳኞች፡- ተኽሊት ይመሰል

ተፈሪ ገብሩ /ዶ/ር/

ቀነዓ ቂጣታ

ተሾመ ሽፈራው

ፀሐይ መንክር

አመልካች፡- አቶ መህዲ ሽረፋ ጠበቃ መስፍን አለማየሁ ቀረቡ::

ተጠሪ፡- አቶ ሻፊ ሽረፋ - የቀረበ የለም::

መዝገቡን መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍርድ

1. በዚህ መዝገብ አከራካሪ የሆነው ነጥብ በዘመድ ሽማግሌ ውሳኔ መቋጫ ያገኘው ጉዳይ የውሳኔው ተገቢነት የሚመረምርበት ሥርዓት መኖር አለመኖሩን ነው፡፡ የጉዳዩ አመጣጥ ሲታይ በስር አመልካች ከሳሽ ተጠሪ ተከሳሽ በመሆን ተከራክሯል፡፡ አመልካች በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በኮ/መ/ቁ 104286 ህዳር 08 ቀን 2008 ዓ.ም ያቀረቡት ክስ ባጭሩ በቦሌ ክፍለ ከተማ ወረዳ 11 የቤት ቁጥር አዲስ ካርታ ቁጥር 1648-11/9/4/7 የሆነውን ቤት ለተጠሪ እንዲያስተዳድሩለት በአደራ የሰጡዋቸው ቢሆንም ተጠሪ እንዲያስተዳድሩ የተሰጣቸው ቤት በስማቸው ካርታ ያሰሩ በመሆኑ ቤቱን ለቀው እንዲያስረክቡ ይወሰን ዘንድ ዳኝነት ጠይቋል፡፡
2. የአሁን ተጠሪ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ እንዲሁም በፍሬ ነገሩ ዝርዝር መልስ ያቀረቡ ሲሆን ተጠሪ ያቀረቡት የመጀመሪያ ደረጃ ይዘት ሲታይም ጉዳዩ በዘመድ ሽማግሌዎች ተመርምሮ ውሳኔ የተሰጠበት በመሆኑ በፍርድ ቤት ድጋሚ ክስ ሊቀርብ አይገባም በማለት መከራከራቸውን የሚያመለክት ነው፡፡
3. በዚሕ አግባብ ክርክሩ የቀረበለት የስር ፍርድ ቤትም የግራቀኙ ክርክር ከመረመረ በኂላ አመልካች እና ተጠሪ የሚከራከሩበት ጉዳይ ጥቅምት 20 ቀን 2008 ዓ.ም በዘመድ ሽማግሌዎች ውሳኔ ማግኘቱን፤የውሳኔው ይዘትም ንብረቱ የጋራ ስለሆነ ከተስማሙ በስምምነት እንዲጠቀሙበት፤የማይስማሙ ከሆነ ግን ቤቱን ሽጠው እንዲከፋፈሉ መወሰናቸውን፤አመልካች

ሽማግሌዎች መምረጣቸውን ሳይክዱ ሽማግሌዎች በሰጡት ውሳኔ ላይ አልፈረምኩም በማለት የሚያቀርቡት ክርክር ተገቢ አለመሆኑን በመግለጽ የአመልካች ክስ በብይን ውድቅ አድርጎታል። አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የይግባኝ ቅሬታ ያቀረቡ ሲሆን ፍርድ ቤቱም ግራቀኙን ከአከራከረ በኋላ የስር ፍ/ቤት ብይን አጽንቷል።የአሁን የሰበር አቤቱታ የቀረበውም የስር ፍ/ቤቶች ውሳኔና ብይን በመቃወም ለማሳረም ነው።

4. አመልካች ሀምሌ 6 ቀን 2010 ዓ.ም የተፃፈ የሰበር አቤቱታ ያቀረቡ ሲሆን መሰረታዊ ይዘቱ እንደተመለከትነው ሽማግሌዎች ጭብጥ በመለየት የግራቀኙ ማስረጃ በመስማት ውሳኔ ያልሰጡ ስለመሆኑና፤በሽማግሌዎች ጉዳዩ እንዲታይ ወላጅ አባታቸው ጫና ያሳደሩ በመሆኑ ብይኑ ተሽሮ በፍርድ ቤት ታይቶ እንዲወሰን የሚጠይቅ ነው።የአመልካች አቤቱታ የመረመረው አጣሪ ችሎትም በ18/12/2010ዓ.ም በሰጠው ትዕዛዝ ጉዳዩ በዘመድ ሽማግሌ ታይቷል የመባሉ አግባብነት ተጠሪ ባሉበት ማጣራት ይቻል ዘንድ ለዚህ ችሎት ያስቀርባል የተባለ ሲሆን ተጠሪም በሕጉ አግባብ ጥሪ ተደርጎላቸው ጥቅምት 20 ቀን 2011 ዓ.ም የተፃፈ መልስ አቅርበው ጉዳዩ በሽማግሌዎች ተመርምሮ ከተወሰነ በኋላ አመልካች ይግባኝ እንዳልጠየቁ ፤ጉዳዩም በሚገባ ተጣርቶ የተወሰነ በመሆኑ የስር ፍርድ ቤቶች ብይንና ፍርድ ሊጸና ይገባል በማለት ተከራክሯል።አመልካች ህዳር 13 ቀን 2011 ዓ.ም የተፃፈ መልስ አቅርቧል።ፍርድ ቤቱም ለትክክለኛ ፍትህ አሰጣጥ ይረዳ ዘንድ የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የካ ምድብ ችሎት የኮ/መ/ቁ 104286 በማስቀረብ ተመልክቷል።

5. ከስር የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን እኛም የስር ፍርድ ቤቶች የሰጡት ብይን እና ፍርድ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት መሆን አለመሆኑን ክርክሩን እንደሚከተለው መርምረናል።

6. መዝገቡ እንደመረመርነው አመልካች አጥብቀው የሚከራከሩት ከተጠሪ ጋር ባደረጉት ስምምነት ጉዳዩ በዘመድ ሽማግሌዎች ውሳኔ እንዲያገኝ ፈቃድ የሰጡ ቢሆንም ሽማግሌዎች ግራቀኙ ሳያነጋግሩ በውሳኔውም ሳይፈርሙ የተሰጠ ውሳኔ በመሆኑ ተገቢ አይደለም በሚል ነው።ተጠሪ በበኩላቸው የዘመድ ሽማግሌዎች ጉዳዩን አጣርተው የሰጡት ውሳኔ በመሆኑ ሊነቀፍ አይገባም በማለት ተከራክሯል።ከመዝገቡ እንደሚታየው አመልካች እና ተጠሪ ጥቅምት 20 ቀን 2008 ዓ.ም ለዘመድ ሽማግሌዎች የዕርቅ ስልጣን መስጠታቸውን ያከራከረ ጉዳይ አይደለም።በግራቀኙ የተመረጡ ሽማግሌዎች ጥቅምት 20 ቀን 2008 ዓ.ም በሰጡት ውሳኔ ለክርክር መነሻ የሆነው ቤት የጋራ ንብረት በመሆኑ እንደ መጀመሪያው ተስማምተው እንዲኖሩ ካልተስማሙ ግን ንብረቱ የታላቅና የታናሽ የጋራ ንብረት ስለሆነ ሽጠው በጋራ በእኩል እንዲካፈሉ በሙሉ ድምጽ መወሰናቸውን የሚያሳይ ነው።አመልካች ይህ ውሳኔ መኖሩን ሳይክዱ ውሳኔ በተሰጠበት ሂደት ተሳትፎ ያልነበራቸው በተለይም ማስረጃ ሳያቀርቡ መወሰኑ ተገቢ አይደለም የሚል ክርክር ማቅረባቸውን ተመልክተናል።

7. በመሰረቱ ተከራካሪ ወገኖች ጉዳያቸው በዘመድ ዳኛ ለመጨረስ መስማማት እንደሚችሉ በፍ/ብ/ሕ/ቁ 3325 እና ተከታይ ድንጋጌዎች ተመልክቷል፡፡አመልካች ጉዳያቸው በሽማግሌዎች እንዲታይ ወደውና ፈቅደው ከተስማሙ በኂላ ሽማግሌዎች የሰጡት ውሳኔ ባለበት ሁኔታ አዲስ ክስ ማቅረባቸው በሕጉ አግባብ ነው ለማለት አልተቻለም፡፡ አመልካች ሽማግሌዎች የሰጡት ውሳኔ የሚነቅፍ ነገር ካለው በሕጉ በተዘረጋው ሥርዓት ይግባኝ በመጠየቅ ከሚያሳርሙ በስተቀር አዲስ ክስ ማቅረብ ተገቢ አለመሆኑን፣ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ያቀረበለት ፍርድ ቤትም በዚህ ጉዳይ ብይን መስጠቱ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ 244/2/ ረ/ ያገናዘበ ነው ከሚል በቀር መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው ለማለት አልተቻለም፡፡ አመልካች ለክርክሩ መነሻ የሆነውን ቤት በተመለከተ የቤተ ዘመድ ሽምግልና ዳኞች የሰጡት ውሳኔ ተገቢ አይደለም በማለት የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 350 እና ተከታይ ድንጋጌዎች በሚፈቅደው አግባብ ይግባኝ ጠይቀው ውሳኔውን ስለማሻራቸው ያቀርቡት ክርክር የለም እንዲህ ከሆነ ደግሞ የፀና የቤተዘመድ ሽምግልና ዳኞች ውሳኔ ባለበት ሁኔታ በሕጉ ያልተመለከቱ መስፈርቶች በመጥቀስ ውሳኔውን መቃወም ተገቢነት የለውም ብለናል፡፡ በመሆኑም አመልካች የሽምግልና ዳኝነት ውሳኔ ከሚያሳርሙ በስተቀር በውሳኔው አልፈረምኩም በሚል ምክንያት በድጋሚ ክስ ማቅረብ የህግ ድጋፍ ያለው ሆኖ አልተገኘም፡፡ በዚህ ሁሉ ምክንያት የስር ፍርድ ቤቶች አመልካች ያቀረቡት ክስ በድጋሚ የቀረበ ነው በማለት የሰጡት ብይን እና ውሳኔ በሕጉ አግባብ ነው ከሚል በስተቀር መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው ለማለት አልተቻለም፡፡ በዚሕም ተከታዩን ወስነናል፡፡

**<u>ው ሳ ኔ</u>**

1. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በኮ/መ/ቁ 104286 በ03/05/2009 ዓ.ም የሰጠው ብይን፣የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በኮ/መ/ቁ 182345 በ13/10/2010 ዓ.ም የሰጠው ፍርድ ጸንቷል፡፡
2. የዚህ ፍ/ቤት ክርክር ያስከተለው ወጪና ኪሳራ ግራቀኙ የየራሳቸው ይቻሉ ብለናል ዕግድ ካለ ተነስቷል፡፡ይፃፍ፡፡ የስር ፍ/ቤት መዝገብ በመጣበት አኳኃን ይመለስ ብለናል፡፡

መዝገቡ ውሳኔ ያገኘ በመሆኑ ወደ መ/ቤት ተመለሰ ውሳኔ በ02/05/2011 ዓ/ም ተነበበ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ፋ/ዘ

የሰ/መ/ቁ160314

ቀን 30/09/2011

ዳኞች፡ ተኽሊት ይመሰል

ተፈሪ ገብሩ (ዶ/ር)

ቀነዓ ቂጣታ

ተሾመ ሽፈራው

ፀሐይ መንክር

አመልካች፡ የኦሮሚያ ውሃ ስራዎች ኮንስትራክሽን ድርጅት-ነ/ፈጅ አሸናፊ ፊጣ

ተጠሪ፡ ቢጋና ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር- አልቀረቡም ፡፡

መዝገቡን መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

1. በዚህ መዝገብ የተያዘው ጉዳይ የኮንስትራክሽን መስሪያዎች ኪራይ ውል የተመለከተ ሲሆን የጀመረው በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ተጠሪ በአመልካች ላይ በኮ/መ/ቁ138392 ባቀረበው ክስ መነሻ ነው፡፡ የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ እና ትእዛዝ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ነው በማለት አመልካች ያቀረቡት አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን የቀረበ ጉዳይ ነው፡፡ የአሁኑ ተጠሪ ያቀረቡት ክስ ይዘት ባጭሩ፡- ከአመልካች ጋር ሰኔ እና ሐምሌ 2002 ዓ.ም በተደረገው ውል ዲኤስቢ3-ዲዜድ 0279 ባለ 305 የፈረስ ጉልበት ዲ 8ቢ0342ባለ 305የፈረስ ጉልበት በሰዓት ብር 1437.50 ለመክፈል በመስማማት የተከራየ ቢሆንም ክፍያው አጠቃልሎ ባለመክፈሉ ብር 875,158.63 የ3 ዓመት ወለድ ታስቦ ብር 1,111,451.46 እንዲሁም ክስ ከተመሰረተበት ቀን ጀምሮ የሚታሰብ ወለድ እንዲከፈለው እንዲወሰን ዳኝነት ጠይቋል፡፡
2. አመልካች ባቀረበው መልስ፡- ክፍያ ለመጠየቅ የተጠሪ ተወካይ እና የአመልካች ኦፕሬተር የፈረሙት ሰነድ መቅረብ እንደሚገባ አዲስ አበባ ለተሰሩ ስራዎች ተገቢ ክፍያ መፈፀሙ አመልካች የሚያውቀው ሌላ ክፍያ የሌለ መሆኑን፣ ተጠሪ ክሱን ለማስረዳት ያዘጋጀው የጊዜ መቆጣጠሪያ ማጠቃልያ ራሱ ያዘጋጀው በመሆኑ በፍ/ብ/ህ/ቁ2016 መሰረት ተቀባይነት እንደሌለው፣ ከውሉ በስተቀር ሌላ ማስረጃ ያላቀረበ በመሆኑ ውሉ ስራ መሰራቱን አያሳይም በማለት ክሱ ውድቅ እንዲሆን አመልክቷል፡፡

3. በዚሁ መልኩ ክርክሩ የቀረበለትን ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙ ክርክር እና ማስረጃ እንዲሁም በፍርድ ቤት ትእዛዝ የቀረበው ማስረጃ ከመረመረ በኂላ አመልካች ለተጠሪ ያልከፈለው ገንዘብ መኖሩ ባቀረበው ማስረጃ አስረድቷል፡፡ክሱ በተሰማበት ቀን ከሳሽ አለኝ የሚለውን የሰዓት መቆጣጠሪያ ቅጾች ከመግለጫ ጋር እንዲያቀርብ በ03/8/2006 ዓ.ም ታዞ ግንቦት 30 ቀን 2008 ዓ.ም አቅርቧል፡፡አመልካች የቀረበው ማስረጃ በዋና መስሪያ ቤት የሌለ በመሆኑ በሀሰት የተዘጋጀ ሊሆን ስለሚችል እንዲመረመር ባቀረበው ጥያቄ መሰረት በፎረሲክ ተመርምሮ ውጤቱ የቀረበ ሲሆን በሰነዱ ያለው ፊርማ ከአንድ በስተቀር በአመልካች ሰራተኞች መፈረሙን ተረጋግጧል፡፡ አመልካች ማስረጃው በመጀመርያ ክርክር አልቀረበም የሚል መቃወሚያ ያቀረበ ቢሆንም በፍርድ ቤት ትእዛዝ የቀረበ በመሆኑ ክርክሩ ተገቢነት የለውም፡፡ አመልካች ያልከፈለው ዋና ገንዘብ ወለድ በድምር ብር 1,105,507.12 እንዲከፍል የነዳጅ በተመለከተ እንዲከፈለው ክሱ በሚሰማበት ጊዜ አልጠየቀም፡፡ በህጉ አግባብ የመከላከያ መልስ ለማሻሻል ጥያቄ ከሚቀርብ በስተቀር አዲስ ክርክር ማቅረብ አይቻልም በማለት ፍርድ ሰጥቷል፡፡ አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ያቀረበው ይግባኝ ቅሬታ ተቀባይነት ያላገኘ በመሆኑ ውሳኔው እና ትእዛዙ በመቃወም ለማሳረም ይህ የሰበር አቤቱታ አቅርበዋል፡፡

4. አመልካች በ21/10/2010 ዓ.ም የተፃፈ 7 ገጽ የሰበር አቤቱታ ያቀረበ ሲሆን መሰረታዊ ይዘቱ ሲታይም የስር ፍርድ ቤት ውሉ ካለው ስታንዳርድ /ኖርም/ አንጻር  መተርጎም እንደነበረበት ተጠሪ ያቀረበው ማስረጃ ክስ ሲያቀርብ በእጁ የነበረ ከመሆኑ አንፃር በሂደት  ያቀረበው ጥያቄ ተቀባይነት ማግኘቱ በህጉ አግባብ አለመሆኑን፣ የመከላከያ መልስ ለማሻሻል ያቀረበው ጥያቄ ውድቅ መደረጉ የቀረበበት ክስ የመከላከል መብት የሚያጣብብ መሆኑን፣ የነዳጅ ክፍያ በተመለከተ ያቀረበው ክርክር ውድቅ መደረጉ የግራ ቀኙ ስምምነት መሰረት ያላደረገ መሆኑን የክፍያ ስርዓቱ ውጤታማ የስራ ሰዓት ግምገማ መሰረት በማድረግ ስሌቱ ቢሰራ ሊከፈል ይገባ የነበረ ብር 217,274.71 ብቻ እንደሆነ በመግለጽ የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ እና ትእዛዝ እንዲሻር መጠየቁን የሚያሳይ ነው፡፡ የአመልካች አቤቱታ የመረመረው የሰበር አጣሪ ችሎትም አመልካች ተጨማሪ ማስረጃ በመቃወም አቤቱታው ለማሻሻል ያቀረበው ጥያቄ ተቀባይነት ያለማግኘቱን አግባብነት እንዲሁም ክፍያው መሰራት ያለበት የስራ ዓይነትና ዋጋ መሰረት በማድረግ ነው ወይስ ተሰራ የተባለው ሰዓት በማሰላት ብቻ ነው? የሚል አከራካሪ ጭብጥ ከውሉ አንቀጽ 8.1 እና 8.2 አንፃር አግባብነቱ ተጠሪ ባለበት መመርመር ይቻል ዘንድ ጉዳዩ ለዚህ ችሎት ያስቀርባል ተብሏል፡፡ ተጠሪም ጥቅምት 20 ቀን 2011 ዓ.ም ባቀረበው መልስ አመልካች መልሱ ለማሻሻል ያቀረበው ጥያቄ ውድቅ መደረጉ በአግባቡ መሆኑ፣ በቀረበው ሰነድ አስተያየት መስጠቱን ክፍያውም ተደምሮ አማካይ በመውሰድ የሚሰራ እንጂ በውጤታማነት የስራ ሰዓት ብቻ ተመርኩዞ የሚወሰን አለመሆኑን የተሰራውን ስራ መጠን የሚያሳይ ሰነድ ቀርቦ የተወሰነ በመሆኑ የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ እና ትእዛዝ ሊነቀፍ አይገባም በማለት

ተከራክሯል፡፡ አመልካች ባቀረበው የመልስ መልስ አቤቱታው አቤቱታውን አጠናክሯል፡፡ ችሎቱም ለትክክለኛ ፍትህ አሰጣጥ እንዲመች የከፍተኛ ፍርድ ቤት መ/ቁ 138392 በ14/09/2011 ዓ.ም በሰጠው ትእዛዝ በማስቀረብ ተመልክቷል፡፡

5. የጉዳዩ አመጣጥ ባጭሩ ከላይ የተገለፀው ይዘት ያለው ሲሆን እኛም ግራ ቀኙ በጽሁፍ ያደረጉት ክርክር ለሰበር አቤቱታ መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ የስር ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሳኔና ትእዛዝ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት መሆን አለመሆኑን ክርክሩን እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

6. ከክርክሩ ሂደት መረዳት የተቻለው አመልካች እና ተጠሪ የኮንስትራክሽን መሳሪያዎች ኪራይ ውል ማድረጋቸውን ያላከራከረ ቢሆንም ተጠሪ እንዲከፈለው ዳኝነት የጠየቀበት የገንዘብ መጠን በተመለከተ ግን ክርክር መነሳቱን መዝገቡ ያሳያል፡፡ አመልካች አጥብቆ የሚከራከረው ለውሳኔ መሰረት የሆነውን የሰነድ ማስረጃ ተጠሪ ክሱ ሲመሰርት አያይዞ ያላቀረበው ከመሆኑ አንፃር በክርክር ሂደት እንዲያቀርብ መፈቀዱ ስነ ስርዓታዊ አይደለም በሚል ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ አመልካች ቀሪ ክፍያ አለ የሚባል ቢሆን ስሌቱ መሰራት ያለበት ባቀረበው ሰዓት ድምር ሳይሆን ውጤታማ የስራ ሰዓት ግምገማ መሠረት በማድረግ ነው የሚል ክርክር ማቅረቡን መዝገቡ ያመለክታል፡፡ ተጠሪ በበኩሉ አመልካች ከክሱ በኋላ የቀረበው የሰነድ ማስረጃ ላይ አስተያየቱን የሰጠ በመሆኑ የመከላከያ መልሱ ለማሻሻል ያቀረበው ጥያቄ ተቀባይነት ማጣቱ በአግባቡ ስለመሆኑ ቀሪ ክፍያ በተመለከተም በተደረገው ማጣራት ያልተከፈለ ገንዘብ መኖሩን ተረጋግጦ የተሰጠው ውሳኔ ሊነቀፍ አይገባም ብሏል፡፡

7. በመሰረቱ መብት ለማስከበር ክስ የሚመሰርት ሰው ክሱን ለማስረዳት ይጠቅማል ያለውን ማስረጃ ዓይነት እና ዝርዝር ሁሉ መጀመርያ ከሚያቀርበው ክስ ጋር አያይዞ ማቅረብ ያለበት ሲሆን በእጁ የሌሉ ማስረጃዎች ካሉ በፍርድ ቤት ትእዛዝ ማቅረብ እንዲቻል የሚገኙበት መስርያ ቤት (ስፍራ) ጭምር በመግልጽ ማቅረብ ያለበት ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ137(1) እና 223 ድንጋጌዎች መሰረታዊ ይዘት እና መንፈስ ያስገነዝቡናል፡፡ የከሳሽ ወገን መጀመሪያ ያላቀረበው ማስረጃ ካለ በልዩ ሁኔታ በቂ ምክንያት መኖሩን በማስረዳት በፍርድ ቤት ፈቃድ ሊቀርብ እንደሚችል የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ137(2) እና 256 ጥምር ንባብ ያመለክታል፡፡ በሌላ በኩል ፍርድ ቤት ማስረጃ በማስቀረብ የሚመረምርበት ስርአት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ቁ145 እና 256 ተደንግጓል፡፡ በተያዘው ጉዳይ ተጠሪ ክስ በሚሰማበት ወቅት ያልቀረበ ሰነድ መኖሩን በመግለጽ ያቀረበው አቤቱታ ተቀባይነት ማግኘቱን መዝገቡ ያሳያል፡፡ ተጠሪ ማስረጃ እንዲያቀርብ ከተፈቀደለት በኋላ አመልካች የመከላከያ መልስ ለማሻሻል ያቀረበው ጥያቄ ውድቅ መደረጉን መዝገቡ ያሳያል፡፡ ተጠሪ ክሱን ለማስረዳት ይጠቅመኛል ያለውን የሰው እና የሰነድ ማስረጃ ክስ በመሰረተበት ቀን ያላቀረበበት በቂና ህጋዊ ምክንያት ምን እንደሆነ የስር ፍርድ ቤት በ3/8/2006 በሰጠው ትእዛዝ ግልጽ አላደረገም፡፡ ተጠሪ ክሱን ለማስረዳት በመጀመሪያ ቀጥሮ ያላቀረበው

ማስረጃ በሂደት እንዲያቀርብ ከተፈቀደ አመልካችም የቀረበውን ማስረጃ አግባብነት እና ተአማኒነት ለመቃወም እንዲችል የመከላከያ መልሱ እንዲያሻሽል ሊፈቀድ ይገባ ነበር፡፡ ምክንያቱም መጀመሪያ ያልቀረበው ማስረጃ ለውሳኔው መሰረት ከተደረገ አመልካችም ይህ ማስረጃ ተገቢ አለመሆኑን ለማሳየት ወይም ለመከላከል እኩል የመደመጥ መብት ሊነፈግ አይገባም፡፡ የስር ከፍተኛ ፍርድ ቤት ክርክሩን የመራበት አግባብ በህጉ የተዘረጋውን ጥብቅ የክርክር አመራር ስርዓት የተከተለ ባይሆንም የተጠሪ ማስረጃ እንዲቀረብ በፈቀደበት ሁኔታ አመልካችም የበኩሉን ማስተባበያ ለማቅረብ ይችል ዘንድ የመልስ ማሻሻል ጥያቄ ተቀባይነት ሊያገኝ ይገባል፡፡ አመልካች በተሟላ መልስ ባልተከራከረበት ሁኔታ ተጠሪ ባቀረበው ሰነድ ላይ አስተያየቱን በጽሁፍ ብቻ ያቅርብ ተብሎ የመደመጥ መብቱ ሊታለፍ አይገባም፡፡ ምክንያቱም ተጠሪ ያቀረበው አዲስ ማስረጃ የክርክሩ ይዘት እና ጭብጥ ሊለውጥ የሚችል በመሆኑ ነው፡፡ የስር ፍርድ ቤት አመልካች በ23/10/2006 ዓ.ም ያቀረበው የመከላከያ መልስ የማሻሻል መሰረታዊ ጥያቄ ውድቅ ማድረጉ የፌዴራል ህገ መንግስት አንቀጽ 37 እና የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ91 ያላገናዘበ ነው ብለናል በመሆኑም አመልካች የተሟላ ክርክር ለማቅረብ እንዲችል የመከላከያ መልሱ እንዲያሻሽል ሊፈቀድለት ይገባል ብለናል፡፡

8. አመልካች በስር ፍርድ ቤት ተፈፀመ ያለው ሌላ መሰረታዊ ስህተት ክፍያው የተሰራበት ስሌት ተገቢነት ነው፡፡ አመልካች ካቀረበው ክርክር መገንዘብ የተቻለው ቀሪ ክፍያ የተሰራበት ስሌት ውሉን መሰረት አላደረገም በሚል ነው፡፡ አመልካች በሰበር አቤቱታው በዝርዝር እንደገለጸው ክፍያው የአከፋፈል ስታንዳርድ እና ኖርም የተከተለ አይደለም በሚል ነው፡፡ተጠሪ በበኩሉ ክፍያው በአግባቡ ተሰልቶ የቀረበ በመሆኑ የአመልካች ክርክር ውድቅ እንዲደረግ አመልክቷል፡፡ የስር ፍርድ ቤትም ውሳኔ እንደተመለከተነው የክፍያው ስሌት የተሰራው አጠቃላይ የተሰራው ሰዓት በመደመር መሆኑን ከሚያሳይ ውጭ በአመልካች አቤቱታ እንደተገለጸው ውጤታማ የስራ ሰዓት ግምገማ መሰረት ያደረገ መሆን አለመሆኑን ተጣርቶ የተወሰነ ስለመሆኑ መዝገቡ አያሳይም፡፡ በመሆኑም ቀሪ ክፍያ መኖሩን ከተረጋገጠ በውሉ መሰረት ክፍያ ሊፈፀም የሚገባው አመልካች እንደሚለው ውጤታማ የስራ ሰዓት ግምገማ መሰረት በማድረግ ነው ወይስ ተጠሪ እንደሚከራከረው የስራ ሰዓት ተደምሮ አማካይ በመውሰድ ነው? የሚል መሰረታዊ ጭብጥ በግራ ቀኙ ክርክርና ማስረጃ እንዲሁም ውሉ መሰረት በማድረግ በሚቀርብ የባለሞያ ማብራሪያ መሰረት ተጣርቶ የሚወሰን እንጂ ከወዲሁ የአመልካች የዳኝነት ጥያቄ ውድቅ የሚደረግበት ሁኔታ አይኖርም፡፡ በመሆኑም የክፍያ ስርዓቱ በውሉ መሰረት መከፈል አለመከፈሉን በድጋሚ ሊጣራ የሚገባው ነጥብ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በዚህ ሁሉ ምክንያት መጀመሪያ ጉዳዩን የተመለከተው የከፍተኛ ፍርድ ቤት ተጠሪ ያቀረበው ተጨማሪ የሰነድ ማስረጃ ተቀብሎ አመልካች ያቀረበው የመከላከያ መልስ ማሻሻያ ጥያቄ ውድቅ ማድረጉ እንዲሁም ክፍያ የተጠየቀው በውሉ መሰረት መሆን አለመሆኑን በአግባቡ ሳያጣራ መወሰኑ

እየታወቀ ይኸው ውሳኔ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በትእዛዝ መጽናቱ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት ተከታዩን ወሰነናል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ138392 በ26/06/2010 ዓ.ም የሰጠው ፍርድ፣ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በይ/ብ/ይ/መ/ቁ156988 በ30/09/2010ዓ.ም የሰጠው ትእዛዝ ሽረናል፡፡
2. አመልካች ያቀረበው የመከላከያ መልስ የማሻሻያ ጥያቄ ውድቅ መደረጉ በህጉ አግባብ አይደለም ብለናል፡፡
3. አመልካች በተሟላ ሁኔታ ለመከራከር እንዲያስችለው መልሱን እንዲያሻሽል አዘናል፡፡
4. የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የተዘጋው የመ/ቁ138392 በማንቀሳቀስ አመልካች መልሱን ካሻሻለ በኋላ በፍርድ ይዘቱ እና መንፈስ እንዲጣሩ የተለዩ ነጥቦች መሰረት በማድረግ ክፍያ የተጠየቀው በውሉ መሰረት ነው ወይስ አይደለም? የሚል መሰረታዊ ጭብጥ እና ተያያዥ ነጥቦች በግራ ቀኙ ክርክርና ማስረጃ በማጣራት እንዲሁም አግባብነት ካለው ተቋም ተገቢ ነው ያለውን ማስረሰጃ በማሰባሰብ ወይም ባለሞያ በመመደብ በማጣራት ተገቢ ውሳኔ ይሰጥ ዘንድ ጉዳዩ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ343(1) በሚያዘው መሰረት መልሰንለታል፡፡
5. የዚህ ፍርድ ቤት ክርክር ያስከተለው ወጪ እና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸው ይቻሉ ብለናል፡፡
6. የውሳኔው ትክክል ግልባጭ ለስር ፍ/ቤቶች ይተላለፍ፡፡
7. መዝገቡ ሲሰራ ቆይቶ በ06/10/2011 ዓ.ም ተነበበ፡፡

መዝገቡ ተዘጋ ወደ መዝገብ ቤት ተመለሰ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

መ/አ

የሰ.መ.ቁ.137302

ታህሳስ 26 ቀን 2010 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዳኜ መላኩ

ተኽሊት ይመሰል

ቀነዓ ቂጣታ

ተሾመ ሽፈራዉ

ፀሐይ መንክር

አመልካች፡- ወ/ሮ ዳንሴ ጉርሙ - ጠበቃ አቶ ዳኛቸው ቱሉ ቀርበዋል፡፡

ተጠሪ፡- አቶ ተመስገን ደምሴ - ጠበቃ አቶ ብርሃኑ ታዬ ጋር ቀርበዋል፡፡

ይህ መዝገብ የተቀጠረዉ ለምርመራ ሲሆን ተመርምሮ የሚከተለዉ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ይህ የሰበር ጉዳይ የቤት ክርክርን የሚመለከት ሲሆን ለችሎቱ ሊቀርብ የቻለዉ የአሁን አመልካች የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁ.132562 ጥር 25 ቀን 2009 ዓ.ም የሰጠዉ ዉሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ እንዲታረምልኝ በማለት ያቀረቡትን አቤቱታ መርምሮ ለመወሰን ነዉ፡፡

የጉዳዩ መነሻ ሲታይ በግልግል ጉባኤ ዳኞች ዘንድ የአሁን አመልካች የመቃወም አመልካች፣የአሁን ተጠሪ ደግሞ የመወቃወም ተጠሪ ሆኖ ሲከራከሩ ነበር፡፡ ይህ ችሎት የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት የመ.ቁ.110552 አስቀርቦ እንደተመለከተዉ፤ ይህ ጉዳይ የተጀመረዉ የአሁን ተጠሪ በሥር ተከሳሽ ዶ/ር አብነት ግርማይ ላይ ባቀረቡት ክስ መነሻነት ሲሆን፣ የክሱም ይዘት በአጭሩ፡- በከሳሽ እና ተከሳሽ መካከል ሰኔ 23 ቀን 1997 ዓ.ም / June 30/2005 GC/ በተደረገዉ የኪራይ ዉል ተከሳሽ በአዲስ አበባ ከተማ በቦሌ ክ/ከተማ በቀድሞ ወረዳ 17 ቀበሌ 15 /በአሁኑ በቦሌ ክ/ከተማ ወረዳ 4 አስተዳደር/ ክልል ዉስጥ የሚገኘዉን የቤት ቁጥር 414 የሆነዉን ሕንጻ ተከራይተዉ ሲጠቀሙበት ቆይተዉ የኪራይ ዉሉ የተቋረጠ በመሆኑ ለቤቱ እድሳት ከሳሽ ያወጣዉን ወጪ እንዲከፍሉኝ፣ ያልተከፈለዉን ዉዝፍ የኪራይ ክፍያ እንዲከፍሉኝ፣ የመማር ማስተማሩ ሂደት በቤት ጥበት ምክንያት ተጎዳብኝ በማለቱ 5 ክፍል በከሳሽ ተሰርቶ ሲገለገልበት ከቆዩ በኂላ ነባሩን በር በብሎኬት ዘግቶና አጥሩን አፍርሶ ሌላ መዉጫ በር በመስራት የሚገለገልበት ያላስረከበዉን 5 ክፍል ቤት እንዲያስረክብ፣ በእነዚህ ክፍሎች ላይ የኪራይ ክፍያ በገበያ ዋጋ እንዲከፍለኝ በማለት ከሷል፡፡ ተከሳሽ በበኩሉ ባቀረበዉ መልስ አምስት ክፍል ቤቶችን በተመለከተ ከሳሽ የባለሀብትነት ማረጋገጫ ማስረጃ ያላቀረበ በመሆኑ መብትና ጥቅም የለዉም፣ ተከሳሽ ቤቱን የሚመለከተዉ አካል በማስፈቀድ የሰራ ነዉ በማለት እና በሌሎች ነጥቦች ላይ መከላከያ ክርክራቸዉን አቅርቧል፡፡

ከዚህ በኋላ የግልግል ጉባኤዉ ግራ ቀኛቸዉን በማከራከር በሰጠዉ ዉሳኔ የሕንጻ ኪራይ ዉሉን መሰረት በማድረግ የዉዝፍ ኪራይ ክፍያ፣ ለሕንጻዉ እድሳት እንዲሁም ወጪና ኪሳራ በተመለከተ ሊከፈል ይገባል ያለዉን ገንዘብ በመወሰን፣ ተከሳሽ በኪራይ ዉሉ መሰረት ከተከራየዉ ዋናዉ ቤት ይዞታ ዉጭ ባለዉ ቦታ የተሰሩትን 5 ክፍሎች በከሳሽ የተሰሩ መሆናቸዉን የሰዉ ምስክሮች ያረጋገጡ ስለሆነ ተከሰሽ በዉል የያዛቸዉንና በርክክብ ወቅት ያላስረከባቸዉን አምስት ክፍል ቤቶችን ከነአጥር ግቢዉ ለከሳሽ እንዲያስረክብ እና በሌሎች ጉዳዮች ላይ ተገቢ ነዉ ያለዉን ዉሳኔ ሰጥቷል፡፡

ከዚህ ዉሳኔ በኋላ የመቃወም አመልካች ወ/ሮ ዳንሴ ጉርሙ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.358 መሰረት የፍርድ መቃወሚያ ማመልከቻ አቅርቧል፡፡ የመቃወሚያ አቤቱታቸዉ ይዘት በአጭሩ፡ በቦሌ ክ/ከተማ ወረዳ 4 ክልል ዉስጥ የሚገኝ በ950 ካ.ሜ ቦታ ስፋት ላይ ያረፈዉ ቤት በእነ ወ/ሮ አየለች ወርቁ ስም ተመዝግቦ ካርታ የተሰጠበትን የመቃወም አመልካች በሽያጭ ዉል ገዝተዉ የተላለፈላቸዉ እና የሊዝ ዉል ከቦሌ ክ/ከተማ መሬት አስተዳደር ጽ/ቤት የፈጸሙበትን፣ እንዲሁም የቤቱን ስመ ሀብት ወደ አመልካች ለማዛወር በሂደት ላይ እያለሁ፣ ይህ ቤት እንደፍርድ ባለዕዳ ንብረት ተቆጥሮ የአፈጻጸም ትዕዛዞች የተሰጠበት ስለሆነ እነዚህ አምስት ክፍል ቤቶች የመቃወም አመልካች ንብረት ስለሆኑ የተሰጠዉ ዉሳኔ እንዲሻርልኝ በማለት አመልክቷል፡፡

በዚህ የመቃወሚያ ማመልከቻ ላይ ከሳሽ አቶ ተመስገን ደምሴ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ እና አማራጭ መልስ ያቀረቡ ሲሆን፣ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወምያ በአጭሩ፡ የመቃወም አመልካች ወደ ክርክሩ ለመግባት መብትና ጥቅም የላቸዉም፣ ይህ ጉዳይ የግልግል ጉባኤ የሰጠዉ ዉሳኔ በይግባኝ የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ.ቁ.110552 በ10/3/2008 ዓ.ም በሰጠዉ ፍርድ ጸንቷል፤ አመልካች በአፈጻጸም ላይ ጣልቃ ገብተዉ መብታቸዉን ማስከበር ነበረባቸዉ፣ የመቃወም አመልካች የዚህ ንብረት ባለሀብት ስለመሆናቸዉ ካርታ አላቀረቡም፣ አመልካች በዉል ገዝቻለሁ ያሉት ቤት የቤት ቁጥር የለዉም፤ የመቃወም አመልካች አቤቱታ ዉሳኔ ከተሰጠበት ጉዳይ ጋር የሚገናኝ አይደለም ጉባኤዉ የመቃወም አቤቱታዉን አይቶ የመወሰን ስልጣን የለዉም፣ እንዲሁም በአማራጭ መልስ እንዳቀረቡ ተመልክቷል፡፡ ተከሳሽ ዶ/ር አብነት ግርማይ በወረዳዉ አስተዳደር በኩል መጥሪያና አቤቱታዉ በድርጅቱ ቤት ላይ ቢለጠፍም ባለመቅረባቸዉ ሳይከራከሩ ቀርተዋል፡፡

በመቀጠል የግልግል ጉባኤዉ፣ ግራ ቀኛቸዉን በማከራከር፣ የቀረበዉን የሰነድ ማስረጃ በመመዘን፣ አስቀድመዉ የተሰሙትን የሰዉ ምስክሮች ቃል በመመርመር፣ በሰጠዉ ብይን ከሳሽ እነዚህን ቤቶች መስራታቸዉን በምስክሮች ቃል ያስረዱ ሲሆን የመቃወም አመልካች ይህን የሚያስተባብል ማስረጃ ያላቀረቡ በመሆኑ የመቃወም አመልካች ክስ ባቀረቡት አምስት ክፍል ቤቶች ላይ በዉል ወይም በሕግ የተረጋገጠ መብትና ጥቅም የላቸዉም በማለት ከሳሽ ያቀረበዉን የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ በመቀበል አቤቱታቸዉን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.33 /2/ /3/ እና 244/2፣ መ/ መሰረት ዉድቅ በማድረግ ወስኗል፡፡ የሥር የመቃወም አመልካች ይህን ዉሳኔ በመቃወም ይግባኝ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ያቀረቡ ሲሆን፣ ፍ/ቤቱም ግራ ቀኛቸዉን በማከራከር በሰጠዉ

ዉሳኔ ምክንያቱን በማስቀመጥ የግልግል ጉባኤዉን ዉሳኔ በማጽናት ወስኗል፡፡ የአሁን የሰበር አቤቱታዉ የቀረበዉ በዚህ ዉሳኔ ቅር በመሰኘት ለማስለወጥ ነዉ፡፡

የአሁን አመልካች በ29/5/2009 ዓ.ም የተጻፈ አራት ገጽ አቤቱታ አቅርቧል፡፡ የአቤቱታዉ ይዘት በአጭሩ፡ ለክርክር ምክንያት የሆኑት በ950 ካ.ሜ ቦታ ላይ ያረፉት 5 ክፍል ቤቶች በእነ ወ/ሮ አየለች ወርቁ ስም የተመዘገበ እና በሽያጭ ለአመልካች የተላለፈ እንዲሁም አመልካች ከቦሌ ክ/ከተማ መሬት አስተዳደር ጋር የሊዝ ዉል ፈጽመዋል፡፡ አመልካች ይህን ንብረት በእጃቸዉ አድርገዉ የሚቆጣጠሩ እና የሚያስተዳደሩ ሆኖ ሳለ የግልግል ጉባኤዉ እና የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ንብረቱ የአሁን ተጠሪ ነዉ በማለት የሰጡት ዉሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመባቸዉ ስለሆኑ እንዲታረምልን፣ የጠበቃ አበል ከወጪ ጋር እንዲወሰንልን በማለት አመልክቷል፡፡

የሰበር አጣሪ ችሎት ጉዳዩን በማየት በዚህ ጉዳይ የሚጣራ ነጥብ አለ በማለት ተጠሪ መልስ እንዲሰጡ ባዘዘዉ መሰረት መጋቢት 4 ቀን 2009 ዓ.ም የተጻፈ አራት ገጽ መልስ አቅርቧል፡፡ የመልሱም ይዘት በአጭሩ፡ በዚህ ጉዳይ የግልግል ጉባኤዉ የሰጠዉ ብይን እና የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት የሰጠዉ ፍርድ ጉዳዩን በሕግ አግባብ አጣርተዉ የሰጡት ዉሳኔ እና የህግ ስህተት የሌለባቸዉ ስለሆኑ አመልካች ያቀረቡት የሰበር አቤቱታ ዉድቅ ተደርጎ የሥር ዉሳኔ እንዲጸናልኝ በማለት በዝርዝር ተከራክሯል፡፡ የአሁን አመልካች የሰበር አቤቱታቸዉን በማጠናከር የመልስ መልስ አቅርቧል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ከላይ የተመለከተዉ ሲሆን ይህ ችሎት የግራ ቀኛቸዉን ክርክር አግባብነት ካላቸዉ የህግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ እንዲሁም ‹‹የግልግል ጉባኤዉ ይህን ጉዳይ ተቀብሎ ግራ ቀኛቸዉን አከራክሮ የመወሰን ስልጣን አለዉ ወይስ የለዉም?›› የሚለዉን ነጥብ እንደጭብጥ በመያዝ እንደሚከተለዉ መርምሮታል፡፡ ይህ ችሎት የሰበር አጣሪ ችሎት በጉዳዩ ፍሬ ነገር ከያዘዉ ጭብጥ አስቀድሞ የስልጣን ጥያቄ ምላሽ ማግኘት ያለበት ጉዳይ ሆኖ በመገኘቱ የስልጣን ጥያቄን እንደጭብጥ ለመያዝ ችሏል፡፡ ተከራካሪ ወገኖች ባያነሱትም የዳኝነት ጥያቄን የሚያይ ፍ/ቤት በመጀመሪያ ደረጃ ጉዳዩን ለማየት የስረ ነገር ስልጣን ያለዉ መሆኑን በራሱ አነሳሽነትም ቢሆን ማረጋገጥ እንደሚገባዉ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ.9 /2/ ሥር ተመልክቷል፡፡ ተከራካሪ ወገኖች ባያነሱትም ፍ/ቤት የስልጣን ጥያቄ በማንሳት ጉዳዩን ለማየት ስልጣን የሌለዉ እንደሆነ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.244 /2፣ ሀ/ እና 245 /2/ መሰረት ክሱ ተቀባይነት የለዉም ብሎ መወሰን እንደሚገባዉ ተደንግጓል፡፡ ይህ ደግሞ ለግልግል ጉባኤዉም የሚሰራ በመሆኑ የስልጣን ጉዳይ ምላሽ የሚያስፈልገዉ ጉዳይ ነዉ፡፡

በዚህ አግባብ እንደመረመርነዉ የግልግል ጉባኤዉ በከሳሽ አቶ ተመስገን ደምሴ እና በተከሳሽ ዶ/ር አብነት ግርማይ መካከል ያለዉን ክርክር ተቀብሎ ለመወሰን ስልጣን ያገኘዉ ሁለቱ ግለሰቦች ሰኔ 23 ቀን 1997 ዓ.ም / June 30/2005 GC/ ባደረጉት የሕንጻ ኪራይ ዉል መነሻነት መሆኑን ከሥር ዉሳኔዎች ግልባጭ መገንዘብ ይቻላል፡፡ የዚህ ዉል አንቀጽ 11 በአከራዩ እና ተከራዩ መካከል ከዉሉ ጋር ተያይዞ የሚነሱትን ግጭቶች በስምምነት ለመፍታት፣ ይህ ካልተቻለ ጉዳዩ ግራ ቀኛቸዉ

በሚመርጡት ገላጋይ ሽማግሌዎች ታይቶ ዉሳኔ እንደሚሰጥበት መስማመታቸዉን ያመለክታል፡፡ የሕንጻ ኪራይ ዉሉ የተፈጻሚነት አድማስ ደግሞ በዉሉ አንቀጽ 1 የተመለከተ እና የቤት ቁጥር 414 ሕንጻ ከነግቢ እና በጊዜያዊነት የተሰሩትን ተገጣጣሚ ግንባታዎችን እንደሚመለከት እና ይህን የሚያመክት አባሪም የዉሉ አካል እንደሆነ ያሳያል፡፡ በዚህ ዉል የአከራይ እና የተከራይ መብትና ግዴታ በዝርዝር ተመልክቷል፡፡ በመሆኑም የግልግል ጉባኤዉ በዚህ ጉዳይ ስልጣን ሊኖረዉ የሚችለዉ በዉሉ የተፈጻሚነት ወሰን ድረስ እንደሆነ የሚያከራክር አይደለም፡፡

እንደሚታወቁ ተዋዋይ ወገኖች የፍ/ብ/ሕ/ቁ.1678 ሥር የተመለከቱትን ሁኔታዎችን በማሟላት ዉል የተደረጉ እንደሆነ፣ በሕግ የተቋቋመዉ ዉል ዉሉን ባቋቋሙት ተዋዋይ ወገኖች መካከል ሕግ እንደሆነ የፍ/ብ/ሕ/ቁ.1731 /1/ ሥር ተደንግጎ እናገኛለን፡፡ አንድ ዉል አስገዳጅነት የሚኖራዉ ዉሉን ፈቅደዉና ተስማምተዉ በተዋዋሉ ተዋዋይ ወገኖች ላይ እንጂ የዉሉ አካል ባልሆኑት ሶስተኛ ወገኖች ላይ አስገዳጅነትም ሆነ ተፈጻሚነት እንደሌለዉ መገንዘብ ያስፈልጋል፡፡

ይህ ከሆነ ደግሞ የአሁን ተጠሪ እና የሥር ተከሳሽ ዶ/ር አብነት ግርማይ መካከል የተደረገዉ የኪራይ ዉል ተፈጻሚነት ዉሉን ባደረጉት ተዋዋይ ወገኖች ብቻ ላይ ነዉ፤ በዚህ ዉል መነሻነት የሚነሳዉም አለመግባባት በግልግል ጉባኤዉ ታይቶ ዉሳኔ ሊሰጥ የሚችለዉ በእነዚህ ሰዎች መካከል ብቻ ነዉ፡፡ በዚህ የኪራይ ዉል መሰረት የኪራይ ክፍያ፣ የቤቱ እድሳትና የጥገና ጉዳይ፣ ተከራይ በዉሉ በግልጽ ተገልጾ የተረከበዉን ሕንጻ፣ ክፍሎች እና ዕቃዎች ከማስረከብ ጋር የተያያዙትን ጉዳዮች የሚያጠቃልል እንደሆነ ማየት ይቻላል፡፡ እነዚህን ጉዳዮች በተመለከተ በአከራይ እና ተከራይ መካከል አለመግባባት የተነሳ እንደሆነ በዚህ ዉል አግባብ ሊፈታ እንደሚገባ ግልጽ ነዉ፡፡ እነዚህ ተዋዋይ ወገኖች በኪራይ ዉል ምክንያት በመካከላቸዉ የሚነሳዉን አለመግባበት በገላጋይ ሽማግሌዎች እንዲታይላቸዉ መስማማታቸዉ ደግሞ በፍ/ብ/ሕ/ቁ.3325 እና ተከታይ ድንጋጌዎች መሰረት ተቀባይነት ያለዉ ጉዳይ ነዉ፡፡ በመሆኑም ተዋዋይ ወገኖች በመካከላቸዉ የሚነሳዉን አለመግባባት በሽምግልና ዳኝነት ለመጨረስ መስማማታቸዉ የሕጉን ዓላማ የተከተለ እንደሆነ የሚያከራክር አይደለም፡፡ ይሁን እንጂ የሽምግልና ዳኝነት ስልጣን በጠባቡ መተርጎም እንዳለበት የፍ/ብ/ሕ/ቁ.3329 ሥር ተደንግጎ እናገኛለን፡፡ ከእነዚህ የሕግ ድንጋጌዎች መገንዘብ እንደሚቻለዉ ተዋዋይ ወገኖች በምን አግባብ የገላጋይ ዳኞችን መምረጥ እንደሚችሉም በዝርዝር ተመልክቷል፡፡ ስለሆነም በዚህ አግባብ የተቋቋመዉ የግልግል ጉባኤ ስልጣን ሊኖረዉ የሚችለዉ በዚህ አግባብ ተስማምተዉ ገላጋይ ዳኞችን መርጠዉ ስልጣን በሰጡት ወገኖች ብቻ ላይ እና በዚህ አግባብ እንዲታይላቸዉ በተስማሙበት ጉዳይ ወሰን ድረስ ብቻ እንደሆነ መገንዘብ ያስፈልጋል፡፡

ከዚህ አንጻር አሁን ወደ ተያዘዉ ጉዳይ ስንመለስ የአሁን አመልካች ባቀረቡት መቃወሚያ በከሳሽ እና በተከሳሽ በተደረገዉ ክርክር መነሻነት የተሰጠዉ ዉሳኔ መብቴን ይነካል፣ እነዚህ ለክርክር ምክንያት የሆኑት አምስት ክፍል ቤቶች የፍርድ ባለዕዳ የዶ/ር አብነት ግርማይ ንብረት ሳይሆኑ አመልካች በሽያጭ ዉል ከሌሎች ግለሰቦች ገዝተዉ የተላለፉላቸዉ እና የሊዝ ዉል የፈጸሙበት የግል

ሀብታቸዉ እንደሆነ በመግለጽ ነዉ፡፡ የአሁን ተጠሪ በበኩላቸዉ ባቀረበዉ ክርክር እነዚህ ቤቶች የራሱ ንብረት መሆናቸዉንና ባለሀብት ተጠሪ እንደሆኑ ምስክሮች አረጋገጠዋል፣ አመልካች መብት እንደሌላቸዉ በመግለጽ ነዉ፡፡ ከዚህ ክርክር መገንዘብ እንደሚቻለዉ ግራ ቀኞቸዉ የፍ/ብ/ሕ/ቁ.1204-1206 ባሉት ድንጋጌዎች አግባብ የባለሀብትነት መብት በተመለከተ የመፋለም ክርክር ማቅረባቸዉን የሚያመለክት እንደሆነ ነዉ፡፡ እንዲሁም ከጅምሩም በከሳሽ እና በተከሳሽ መካከል እነዚህን አምስት ክፍል ቤቶች በተመለከተ ሲካሄድ የነበረዉ የመፋለም ክርክር እንደነበር የቀደመዉ የግራ ቀኞቸዉ ክርክር፣ መቃወሚያ ያቀረበበት የግልግል ጉባኤዉ ዉሳኔ እና የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ዉሳኔ የሚያስገነዝብ ጉዳይ ነዉ፡፡ ከፍ ሲል እንደተጠቀሰዉ በአመልካች እና በተጠሪ መካከል በተደረገዉ ክርክር የግልግል ጉባኤዉም ሆነ የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ላይ ዉሳኔ እንደሰጡ ቢገለጽም የዉሳኔያቸዉ ይዘት ሲታይ ግን ለክርክር ምክንያት የሆኑት አምስት ክፍል ቤቶች ማን እንደሰራቸዉ፣ ቤቶች የማን ንብረት እንደሆኑ የቀረቡትን የሰነድ ማስረጃዎች በመመዘን እንዲሁም አስቀድሞ የተሰሙትን የተጠሪን የሰዉ ምስክሮች በመመርመር የባለሀብትነት መብት ላይ ዉሳኔ እንደሰጡ የዉሳኔዎቹ ግልባጭ ያመለክታል፡፡

ይህ ከሆነ ደግሞ ምላሽ የማግኘት ያለበት ጉዳይ የግልግል ጉባኤዉ በአመልካች እና በተጠሪ መካከል የተነሳዉን የአምስት ክፍል ቤቶችን የባለሀብትነት መብት ጋር የተያያዘ የመፋለም ክርክር ተቀብሎ ግራ ቀኞቸዉን አከራክሮ ዉሳኔ ለመስጠት የዉልም ሆነ የሕግ ስልጣን አለዉ ወይስ የለዉም? የሚለዉ ነጥብ ነዉ፡፡ ከፍ ሲል እንደተመለከተዉ የአሁን ተጠሪ ባቀረበዉ ክስ ለክርክር ምክንያት የሆኑት አምስት ክፍል ቤቶችን በተመለከተ በኪራይ ዉሉ እንደተሸፈኑ ሳይሆን የሥር ተከሳሽ እነዚህን ቤቶች አጥር ሰርተዉ ሌላ በር ከፍተዉ በሕገ ወጥ መንገድ ሲገለገሉበት እንደነበር እና የኪራይ ዋጋም ቢሆን በኪራይ ዉሉ ላይ የተመለከተዉ ሳይሆን በገበያ ዋጋ በወር በብር 25 ሺህ ብር ታስቦ እንዲከፈላቸዉ መጠየቃቸዉን ያሳያል፡፡ የዚህ የዳኝነት ጥያቄ እንደሚያመለክተዉ እነዚህ ቤቶች በኪራይ ዉሉ የተካተቱ ነበር ወይ? የሚለዉን ጥያቄ የሚያነሳ ነዉ፡፡ ከዚህም በላይ እነዚህን ቤቶች በተመለከተ በከሳሽ እና ተከሳሽ መካከል የመፋለም ክርክር መነሳቱን የዉሳኔዉ ግልባጭ ያመለክታል፡፡ ይህ በእንዲህ እንዳለ በአሁን ተጠሪ እና በሥር ተከሳሽ ዶ/ር አብነት ግርማይ መካከል የተደረገዉ የሕንጻ ኪራይ ዉል ተፈጻሚነት ያለዉ በእነዚሁ ተዋዋይ ወገኖች ላይ እንጂ የአሁን አመልካች ላይ እንዳልሆነ ግልጽ ነዉ፡፡ ይህ ዉል የሚፈጥረዉ መብትና ግዴታ አመልካችን የማይመለከት እና ዉሉን መነሻ ያደረገ አለመግባባት ቢከሰትም በገላጋይ ዳኞች እንዲፈታ ለማድረግ የሚገደዱበት አግባብ አይኖርም፡፡ እንዲሁም የአሁን አመልካች እነዚህን የግልግል ዳኞች መርጠዉ ጉዳያቸዉ እንዲታይላቸዉ ስልጣን የሰጡት ነገር ባለመኖሩ የግልግል ጉባኤዉ የአመልካችን የዳኝነት ጥያቄ ለመዳኘት የህግ ስልጣን የለዉም፡፡ ይህ ሲባል ግን የግልግል ጉባኤዉ የአመልካችን መቃወሚያ ከጅምሩ ስልጣን የለኝ በሚል ምክንያት ዉድቅ እንዲያደርግ ሳይሆን አመልካች ያቀረቡትን የፍርድ መቃወሚያ ማመልከቻ መሰረት በማድረግ አስቀድሞ እነዚህ አምስት ክፍል ቤቶችን በተመለከተ የባለሀብትነት መብት ላይ የሰጠዉን ዉሳኔ

የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.360 /2/ መሰረት ተገቢዉን በመወሰን ነዉ፡፡ ይህ ማለት የግልግል ጉባኤዉ በኪራይ ዉል የተመለከቱትን ቤቶች የባለሀብትነትን መብት በተመለከተ የመፋለም ክርክርን ሰምቶ ዉሳኔ ለመስጠት ስልጣን እንደሌለዉ በመገንዘብ በእነዚህ አምስት ክፍል ቤቶች ላይ አስቀድሞ የሰጠዉን ዉሳኔ ማንሳት ይገባዉ ነበር፡፡

የአሁን አመልካች በበኩላቸዉ የራሴ ንብረት ናቸዉ የሚሏቸዉን እነዚህን ቤቶች በተመለከተ በገላጋይ ዳኞች እንዲታይላቸዉ የተስማሙት ነገር የለም፣ የመረጡትም የገላጋይ ዳኛ አለመኖሩን የሥር ዉሳኔ ግልባጭ ያመለክታል፡፡ ይህ ከሆነ ደግሞ የአሁን አመልካች በኢ.ፌ.ዲ.ሪ.ሕገ መንግስት አንቀጽ 37 እና 78 መሰረት ነጻና ገለልተኛ በሆነ መደበኛ ፍ/ቤት ጉዳያቸዉ ታይቶ ዉሳኔ እንዲሰጥበት ሕገ መንግስታዊ መብት አላቸዉ፡፡ ምክንያቱም በዚህ ጉዳይ ዉሳኔ የሰጠዉ የግልግል ጉባአዉ ለአመልካች ነጻና ገለልተኛ የዳኝነት አካል ነዉ ለማለት ስለማይቻል ነዉ፡፡ አመልካች በሕገ መንግስቱ የተጠበቀላቸዉ በሕግ በተቋቋመ ነጻና ገለልተኛ የዳኝነት አካል በሆነዉ የመደበኛ ፍ/ቤት የመዳኘት መብት የሚነፈጉበት አግባብ የለም፡፡

በመሆኑም የግልግል ጉባኤዉ ለክርክር ምክንያት የሆኑትን አምስት ቤቶችን በተመለከተ የባለሀብትነትን የመፋለም ክርክር ሰምተዉ መወሰን ስልጣን እንደሌለዉ በመገንዘብ አስቀድሞ በእነዚህ ቤቶች ላይ የሰጠዉን የዉሳኔ ክፍል በመሻር ግራ ቀኛቸዉ በዚህ ጉዳይ ከፈለጉ ክርክራቸዉን ስልጣን ላለዉ ፍ/ቤት ማቅረብ እንደሚችሉ በመጠቆም መወሰን ሲገባዉ፣ ባልተሰጠዉ ስልጣን እነዚህን አምስት ቤቶች በተመለከተ ማስረጃ በመመዘን ተጠሪ ባለሀብት ናቸዉ በማለት ዉሳኔ መስጠቱ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ሲሆን የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎትም በበኩሉ ከስልጣን አንጻር ጉዳዩን በመመርመር የግልግል ጉባኤዉን ብይን ማረም ሲገባዉ ከዚህ ይልቅ የራሱን ዝርዝር ምክንያቶችን በማከል የሥር ብይን በማጽናት የሰጠዉ ዉሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ፡፡

ሲጠቃለል የግልግል ጉባኤዉ የማይንቀሳቀስ ንብረት የባለሀብትነት የመፋለም ዳኝነት ጥያቄን ተቀብሎ ግራ ቀኛቸዉን አከራክሮ የመወሰን ስልጣን ሳይኖረዉ ለክርክር ምክንያት የሆኑት አምስት ክፍል ቤቶች የአሁን ተጠሪ ንብረት ናቸዉ፣ አመልካች ግን መብትና ጥቅም የላቸዉም በማለት የሰጡት ዉሳኔ እና የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይህን ዉሳኔ በማጽናት የሰጠዉ ዉሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመባቸዉ ስለሆኑ የሚከተለዉ ተወስኗል፡፡

## ዉ ሳ ኔ

1. የግልግል ጉባኤዉ እነዚህን አምስት ክፍል ቤቶች በተመለከተ ጥር 25 ቀን 2007 የሰጠዉ የዉሳኔ ክፍል እና መስከረም 4 ቀን 2009 ዓ.ም የሰጠዉ ብይን እና ይህን ብይን በማጽናት የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁ.132562 ጥር 25 ቀን 2009 ዓ.ም

የሰጠዉ ዉሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመባቸዉ ስለሆኑ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.348 /1/ መሰረት ተሽሯል፡፡

2. የግልግል ጉባኤዉ ለክርክር ምክንያት የሆኑትን አምስት ክፍል ቤቶችን በተመለከተ የባለሀብትነት የመፋለም ክርክር ሰምቶ ለመወሰን ስልጣን የለዉም ብለናል፡፡
3. የአሁን ተጠሪም ሆነ የአሁን አመልካች አሁን ለክርክር ምክንያት የሆኑትን እነዚህን አምስት ክፍል ቤቶች በተመለከተ ስልጣን ባለዉ ፍ/ቤት ክስ አቅርበዉ መብታቸዉን ከመጠየቅ ይህ ዉሳኔ የሚያግዳቸዉ አይሆንም ብለናል፡፡
4. የግልግል ጉባአዉ ጥር 25 ቀን 2007 ዓ.ም የሰጠዉ ዉሳኔ ከፍ ሲል ከተጠቀሱት አምስት ክፍል ቤቶች ዉጭ በሌሎች ጉዳዮች ላይ የሰጠዉ የዉሳኔ ክፍል ጸንቷል፡፡
5. የዚህ ዉሳኔ ግልባጭ ለግልግል ጉባኤዉ እና ለሥር ፍ/ቤት ይድረስ ብለናል፡፡
6. ግራ ቀኛቸዉ በዚህ ችሎት የደረሰባቸዉን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸዉን ይቻሉ፡፡
7. በ30/5/2009 ዓ.ም የተሰጠዉ የእግድ ትዕዛዝ በዚህ ዉሳኔ ተነስቷል፡፡ ይጻፍ፡፡

**መዝገቡ ተዘግቷል፡፡**

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ሠ/አ

የሠ/መ/ቁጥር 165289

መጋቢት 29 ቀን 2012 ዓ/ም

ዳኞች ፡- ሰለሞን አረዳ

ብርሃኑ አመነዉ

ተሾመ ሽፈራዉ

ደረጀ አያና

ሀብታሙ እርቅይሁን

ብርሃኑ መንግሥቱ

ነጻነት ተገኝ

አመልካች ፡-ወ/ሮ ወሰኔ ገብረ ዮሐንስ

ተጠሪ፡- የካ ክፍለ ከተማ ወረዳ 07 ቀበሌ 11/12/08 የሽማቾች ኃላ/የተ/የኅብረት ሥራ ማኅበር

መዝገቡ ተመርምሮ ከዚህ የሚከተለዉ የፍርድ ዉሳኔ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የሥረ ነገር ዳኝነት ሥልጣን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረዉ በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ሆኖ በዚህ ፍርድ ቤት የአሁን ተጠሪ ከሳሽ አመልካች ደግሞ ተከሳሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡ተጠሪ በአሁን አመልካች ላይ በመሰረተዉ ክስ አመልካች በየካ ክፍለ ከተማ ወረዳ 16 ቀበሌ 08 ክልል ዉስጥ የሚገኝ የቤት ቁጥር 915/ለ የሆነ ቤት በወር 15 ብር ኪራይ ተከራይታ ከ1998ዓ/ም ጀምሮ የቤት ኪራይ መክፈል አቋርጣለች፡፡ቤቱን ሰርቶ የሚያከራየዉና የሚያስተዳድረዉ የሕዝብ ሱቅ መዝናኛ ክበብ ሲሆን በኂላ የቀበሌዉ ባለአደራ ቦርድ ሲያስተዳድረዉ የነበረዉን በደንብ ቁጥር 46/2004 የወረዳዉ ሸማቾች ኅብረት ሥራ ማኅበር ተረክቦ እንዲያስተዳድር የተደረገ ሲሆን ተከራይ በቤት ኪራይ ዉሉ መሰረት የቤት ኪራይ ገቢ ባለመክፈል የያዙትን ቤት እንዲያስረክቡና ያለባቸዉን ዉዝፍ ኪራይ ብር 1320.00፣ የዉሉን መቀጮ ብር 5000.00 እና ቤቱን እስኪያስረክቡ ድረስ በቀጣይ የሚኖረዉን ኪራይ እንድትከፍል ይወሰንልኝ በማለት ዳኝነት ጠይቋል፡፡

አመልካች ለክሱ ባሰማችዉ ክርክር ለክርክሩ መነሻ የሆነዉን ቤት ላገኝ የቻልኩት በ1982 ዓ/ም በወቅቱ የነበሩት የቀድሞ ከፍተኛ 16 የቀበሌ 08 አመራሮች የነበረዉን የመኖሪያ ቤት ችግር ለመፍታት በማሰብ

ባዶ ቦታዎችን በመምረጥና በሂደት ባለቤቶች የምንመልሰዉን ብር 29,000.00 ከቀድሞ ከፍተኛ 16 ቀበሌ 08 ሕብረት ሱቅ ወጭ ሆኖ ለሌሎች ሰዎች ጭምር እንዲሰጠን አድርገዉ በግምት 5 በ6 በሆነ ቦታ ላይ የነበረዉን ቤት ሙሉ ለሙሉ አፍርሰን የወሰድነዉን ብር በኪራይ መልክ ከፍለን ጨርሰናል፡፡ ለዚህ ቤት ካርታ ሊሰራልኝ በመጨረሻ ሂደት ላይ ይገኛል፡፡ ተጠሪ ያቀረባቸዉ ማስረጃዎች ይህንን ቤት መረከቡን  አያሳዩም፡፡ በመሀከላችን ምንም አይነት የቤት ኪራይ ዉል ሳይኖር ተጠሪ ለክሱ ምክንያት የሆነዉን መኖሪያ ቤት በባለቤትነት የሚያስተዳድር መሆኑን ማስረጃ ሳያቀርብ በደፈናዉ በአሁን ሰዓት በሥራ ላይ የሌለና ለ6 ወራት ብቻ በሥራ ላይ የነበረ ደንብ ቁጥር 46/2004 በመጥቀስ ያልተገባ ጥቅም ለማግኘት በማሰብ ያቀረበዉ ክስ የሕግና ማስረጃ ድጋፍ የለዉም ተብሎ ዉድቅ እንዲደረግ በመጠየቅ ተከራክራለች፡፡

የሥር የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 40079 ላይ ግራ ቀኙን አከራክሮና ማስረጃዎችን መርምሮ በቀን 20/01/2010ዓ/ም በዋለዉ ችሎት በሰጠዉ ዉሳኔ ለክርክሩ መነሻ የሆነዉን ቤት የቀድሞ ሕብረት ሱቅ ሲያስተዳድረዉ የነበረና የአሁን ተጠሪ የማስተዳደር ሥልጣን ያገኘዉ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ደንብ ቁጥር 46/2004 መሰረት ሆኖ በቀን 28/01/2005ዓ/ም በተዘጋጀ መረካከቢያ ሰነድ በመረከብ እንደሆነ ተጠሪ በማስረጃ ያስረዳዉን ተጠሪ ታቃራኒ ማስረጃ በማቅረብ አለማስተባበሏን፣ አመልካች በዚህ ቤት ላይ በቀን 24/05/2003ዓ/ም ከየካ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 11/12/08 የህ/ሱ/መ/ተ/ጽ/ቤት ጋር የኪራይ ዉል ማድረጓን ከማስረጃዎቹና ከቤቱ ማኅደር ማረጋገጡን እንዲሁም አመልካች ከተጠሪ ጋር የኪራይ ዉሉን አለማደሷ የቀድሞዉን የኪራይ ዉል ቀሪ የሚያደርገዉ ሳይሆን በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 2968/1 መሰረት የቀድሞዉን የኪራይ ዉል ላልተወሰነ ጊዜ እንዲራዘም የሚያደርግ እንደሆነ፤ አመልካች የኪራይ ዉሉን ሳያስፈረሱ የቤቱ ባለይዞታ ነኝ በማለት ያቀረበችዉ ክርክር በሰ/መ/ቁጥር 46947 ላይ በተሰጠዉ ትርጉም መሰረት ተቀባይነት እንደሌለዉ፤ በአንጻሩ ተጠሪ ያቀረባቸዉ ማስረጃዎች የተጠሪ ቤቱን የማከራየት መብት ከሕግ የመነጨ እንደሆነና አመልካች ዉሉን አለማደሷ ተከራይታ የነበረዉን ቤት እንስትወስድና ኪራይ ሳትከፍል እንድትገለገል የሚፈቅድ የሕግ ድጋፍ የለም፤አመልካች ቤቱ የራሷ መሆኑን ከተጠሪ የተሻለ ማስረጃ በማቅረብ አላረጋገጠችም በማለት አመልካች አከራካሪዉን በየካ ክፍለ ከተማ ወረዳ 16 ቀበሌ 08 ክልል ዉስጥ የሚገኘዉን የቤት ቁጥር 915/ለ የሆነ ቤት ለተጠሪ እንድታስረክብ ወስኖ ተጠሪ ዉዝፍ ኪራይ እንዲከፈለዉ የጠየቀዉን ዳኝነት በይርጋ ታግዷል በማለት ዉድቅ በማድረግ ወስኗል፡፡

እንዲሁም አመልካች በዚህ ዉሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ያቀረበች ቢሆንም ፍርድ ቤቱ በመ/ቁጥር 205269 ላይ ግራ ቀኙን አከራክሮ በቀን 16/02/2011 ዓ/ም በሰጠዉ ዉሳኔ ክሱ ከቤት ኪራይ ዉል ጋር የተያያዘና አልተከፈለም የተባለዉን ኪራይ ለማስከፈልና ቤቱን ለማስለቀቅ የቀረበ በመሆኑ የስር ፍርድ ቤት ጉዳዩን የመዳኘት ስልጣን አለዉ በሚል ከዚህ አኳያ የቀረበዉን ይግባኝ ዉድቅ በማድረግ ፍሬ ነገሩን የሚመለከተዉን የይግባኝ ቅሬታ መርምሮ አመልካች የቤት ባለቤትነትን የመፋለም ክስ ማቅረብ እንደምትችል በመግለጽ አመልካች ቤቱን እንድታስረክብ

በሥር ፍርድ ቤት የተወሰነዉን በማጽናት ወስኗል፡፡በዚህ መሰረት በተሰጡ ዉሳኔዎች መሰረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል በሚል አመልካች በቀን 04/03/2011 ዓ/ም ጽፋ ያቀረበችው የሠበር አቤቱታ ይዘት በአጭሩ የሚከተለዉ ነዉ፡፡

የሥር የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በሌሎች መዝገቦች ላይ የቀረቡትን ተመሳሳይ ጉዳዮችን በተመለከተ ጉዳዩን የመዳኘት ስልጣን የለኝም በማለት ክሱን ዉድቅ ቢያደርግም ይህንን ጉዳይ በተመለከተም የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁጥር 90421 በሰጠዉ አስገዳጅ ትርጉም መሰረት ጉዳዩን የመዳኘት ሥልጣን እደሌለዉ በማወቅ ሥልጣን የለኝም በማለት ዉድቅ ማድረግ ሲገባዉ ሥልጣን አለዉ ቢባል እንኳን ያለዉ ስልጣን የኪራይ ጉዳይን በተመለከተ ብቻ በመሆኑ ይህም ቢሆን የተጠሪ ኪራይ የመጠየቅ መብት በይርጋ ቀሪ ሆኗል ሲል በወሰነበት ከክሱ ጋር ግንኙነት የሌለዉን ነጥብ በማንሳት የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ጉዳዩን ተመልክቶ አመልካች ቤቱን ለተጠሪ ታስረክብ ብሎ ዉሳኔ መስጠቱና ጉዳዩን በይግባኝ አይቶ እንዲያርም ይግባኝ የቀረበለት የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ስህተቱን ሳያርም ዉሳኔዉን ማጽናቱ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ነዉ፡፡ ፍሬ ነገርን በተመለከተ በሰጠዉ ዉሳኔ በሥራ ላይ የሌለዉን ደንብ ቁጥር 47/2004 በመጥቀስ ዉሳኔ መስጠቱ፤ ተጠሪ ከንግድና ኢንዱስትሪ በቀን 28/01/2005ዓ/ም በተጻፈ መረካከቢያ ቅጽ 17 ክፍሎችን ተረክቤያለሁ ከሚል በስተቀር የትኞቹን ቤቶች እንደሆኑ የቤት ቁጥሮች ባልተጠቀሰበት፣ማን አስረካቢና ተረካቢ እንደሆነ በአግባቡ ሳይገለጽ፤ አመልካች ከተጠሪ ጋር ምንም አይነት የቤት ኪራይ ዉል ስምምነት ባላፈጸምኩበትና ተጠሪም በቀን 06/10/2006ዓ/ም ይህንኑ ባረጋገጠበት ማስረጃ በአግባቡ ሳይመረመርና ከሚመለከተዉ አካል ማስረጃ እንዲጣራልኝ በጠየኩት መሰረት ሳይፈጸም ምስክሮቼን ሳይሰማ የሰጠዉ ዉሳኔ በመሆኑ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ነዉ ተብሎ እንዲታረምልኝና ለክሱ መነሻ የሆነዉ ቤት የአመልካች የግል ቤት ነዉ ተብሎ እንዲወሰን እንዲሁም አመልካች ቤቱን ለተጠሪ እንድታስረክብና ኪራይም እንድትከፍል የተሰጠዉ ዉሳኔ እንዲሻርላት በመጠየቅ አቤቱታዋን አቅርባለች፡፡

የሰበር አጣሪ ችሎት አቤቱታውን መርምሮ ተጠሪ ያቀረበዉን ክስ የፌዴራል ፍርድ ቤቶች አይተዉ የወሰኑበትን አግባብ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በየወረዳዉ የሚገኙ የሕዝብ ሱቆችና ሌሎች ገቢ ማስገኛ ተቋማትን ወደ ሸማቾች የህብረት ሥራ ማኀበር ለማስተላለፍ ካወጣዉ ደንብ ቁጥር 46/2004 ድንጋጌዎች እና የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁጥር 190421 ከሰጠዉ አስገዳጅ የህግ ትርጉም ጋር በማገናዘብ መጣራት ያለበት በመሆኑ ጉዳዩ ለሰበር ሰሚ ችሎት ያስቀርባል ብሎ ትዕዛዝ በመስጠቱ ተጠሪ በቀን 17/04/2011 ዓ/ም የተፃፈ በአጭሩ የሚከተለዉን መልስ አቅርቧል፡፡

አመልካች የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ጉዳዩን የመዳኘት ሥልጣን የለዉም በሚል በሥር ፍርድ ቤት በመቃወሚያነት ያላነሳችዉን ክርክር በሰበር ደረጃ እንድታነሳ የፍ/ብ/ስ/ስ/ሕግ ቁጥር 182/2 እና 329 አይፈቅድላትም፡፡ክሱ የቤት ኪራይ ለማስከፈልና ቤቱን ለማስለቀቅ የቀረበ በመሆኑ

በአዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 5 መሰረት ጉዳዩን የመዳኘት ስልጣን ያላቸዉ የፌዴራል ፍርድ ቤቶች ናቸዉ፡፡በመሆኑም ክሱ በስር የፌዴራል ፍርድ ቤቶች ታይቶ በመወሰኑ የተፈጸመ ስህተት የለም፡፡ የፍሬ ነገር ክርክር በተመለከተ አመልካች ለክሱ መነሻ የሆነዉ ቤት ባለቤት መሆኗን የሚያስረዳ ምንም አይነት ማስረጃ አላቀረበችም፡፡ አመልካች በማስረጃነት ያቀረበችዉ ሰነዶች አመልካች ለክሱ መነሻ በሆነዉ ቤት ላይ የባለቤትነት መብት እንዳላት የሚያስረዱ አይደሉም፡፡በአንጻሩ ተጠሪ ለክሱ መነሻ የሆነዉን ቤት ከቀበሌ የሕዝብ ሱቅና መዝናኛ ተቋም ጋር ስለመከራየቷ የሚያስረዳ ማስረጃ በማቅረቡና በአንጻሩ አመልካች የቤቱ ባለቤት መሆኗን የሚያሳይ ማስረጃ በማቅረብ ባለማስረዳቷ ክርክሯ የሕግ መሰረት የለዉም ተብሎ በስር ፍርድ ቤቶች በማስረጃ ምዘና ነጥሮ የተረጋገጠ ፍሬ ነገር ነዉ፡፡ ስለሆነም ከቀረበዉ የክስ ምክንያት አንጻር አመልካች ቤቱን እንድትለቅ በመወሰኑ በስር ፍርድ ቤቶች የተፈጸመ ስህተት የለም ተብሎ አመልካች ያቀረበችዉ የሰበር አቤቱታ ዉድቅ ይደረግልኝ በማለት ተከራክሯል፡፡ አመልካች በተጠሪ በቀረበ መልስ ላይ በቀን 17/05/2011 ዓ/ም የተጻፈ የመልስ መልስ በማቅረብ ተከራክራለች፡፡

ከዚህ በላይ የተመዘገበዉ የግራ ቀኝ ክርክርና በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጡ ዉሳኔዎች ይዘት ሲሆን እኛም የሰበር አጣሪ ችሎት ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ያስቀርባል ሲል ከያዘዉ ጭብጥ አንጻር እና አመልካች በኪራይ የያዘችዉን አከራካሪዉን ቤቱ ለተጠሪ ታስረክብ ተብሎ በስር ፍርድ ቤቶች በመወሰኑ የተፈጸመ መሰረታዊ የሕግ ስህተት መኖር አለመኖሩን አግባብነት ካለዉ ሕግ ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለዉ መርምረናል፡፡

በመጀመሪያም ጉዳዩን የመዳኘት የሥረ ነገር ስልጣን የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፍርድ ቤቶች ነዉ ወይስ የፌዴራል ፍርድ ቤቶች ነዉ? የሚለዉን ጭብጥ መርምረናል፡፡ ተጠሪ ክሱን ያቀረበዉ አመልካች ተከራይታ የያዘችዉን በየካ ክፍለ ከተማ ወረዳ 16 ቀበሌ 08 ክልል ዉስጥ የሚገኝ የቤት ቁጥር 915/ለ የሆነ በመዝናኛ ክበብነት የሚያገለግል ቤት ኪራይ ለመክፈል ፈቃደኛ ባለመሆኗ ዉዝፍ ኪራይ ከፍላ ቤቱን እንድታስረክበኝ ይወሰንልኝ በማለት ዳኝነት በመጠየቅ ነዉ፡፡ እንዲሁም ቤቱን የማስተዳደር ስልጣን ያገኘዉ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ባወጣዉ ደንብ ቁጥር 46/2004 መሰረት ቀደም ሲል በባለአደራ ቦርድ ሲተዳደሩ የነበሩ መሰል ቤቶችን ተረክቦ እንዲያስተዳድር በተሰጠዉ መብት መሰረት እንደሆነ በመግለጽ ደንቡን ጠቅሶ መከራከሩን የስር ፍርድ ቤቶች ዉሳኔዎች ይዘት ያሳያል፡፡ በፍ/ብ/ስ/ስ/ሕግ ቁጥር 9/1 እና 231(1/ለ) ስር በተደነገገዉ መሰረት የክስ አቤቱታ የቀረበለት ፍርድ ቤት ጉዳዩን የመዳኘት የሥረ ነገር ዳኝነት ስልጣን ያለዉ መሆን አለመሆኑን የክስ አቤቱታዉን በመመርመር የሥረ ነገር ዳኝነት ሥልጣን የሌለዉ መሆኑን ሲያረጋግጥ ተከሳሹን ሳይጠራ የክስ አቤቱታዉ ተቀባይነት የለዉም በማለት መመለስ ይጠበቅበታል፡፡የሥረ ነገር ሥልጣን ያለዉ መስሎት ተከሳሹ መልስ እንዲሰጥ አድርጎ ተከሳሹ ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን ለመዳኘት የሚያስችል የዳኝነት ሥልጣን የለዉም የሚል መቃወሚያ በፍ/ብ/ስ/ስ/ሕግ ቁጥር 244(2/ሀ) ሲያቀርብ ወይም በዚህ አግባብ በተከሳሹ መቃወሚያ ባይቀርብም እንኳ ፍርድ ቤቱ በራሱ አነሳሽነት ጉዳዩን የመዳኘት ስልጣን እንደሌለዉ

በተረዳበት ጊዜ ሥልጣን የለኝም በማለት መወሰን እንዳለበት በፍ/ብ/ስ/ስ/ሕግ ቁጥር 9/2 ስር በግልጽ ተደንግጓል፡፡ በዚህ አግባብ በአስገዳጅነት የተደነገገበት ምክንያት የሥረ ነገር ዳኝነት ስልጣን የሌለዉ ፍርድ ቤት ትክክለኛ ፍትህ ለመስጠት የሚያስችል ብቃት የለዉም የሚል አጠቃላይ ግንዛቤ ሕግ አዉጭዉ በመያዙ ምክንያት እንደሆነ ይታመናል፡፡

በተያዘዉ ጉዳይ አመልካች የስር የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ጉዳዩን የመዳኘት ስልጣን የለዉም የሚል መቃወሚያ ካለማቅረቧም በተጨማሪ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ ዳኝነት ሥልጣን ያየዉ የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትም ጉዳዩን የመዳኘት የስረ ነገር ሥልጣን እንዳለዉ በመቁጠር ተጠሪ ያቀረበዉን ክስ ተቀብሎ ዉሳኔ መስጠቱን ከክርክሩ ተረድተናል፡፡ አመልካች ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ባቀረበችዉ ይግባኝ የስር ፍርድ ቤት በጉዳዩ ላይ ዉሳኔ የሰጠዉ ሥልጣን ሳይኖረዉ ነዉ የሚል ቅሬታ ያቀረበች ቢሆንም ፍርድ ቤቱ ከዚህ አንጻር የተነሳዉን ቅሬታ መርምሮ የስር ፍርድ ቤት ከኪራይ ዉል ጋር በተያያዘ ኪራይ ለማስከፈልና ቤት ለማስለቀቅ የቀረበዉን ክስ የመዳኘት ስልጣን አለዉ በማለት የአመልካችን ቅሬታ ዉድቅ በማድረግ መወሰኑን ከዉሳኔዉ ተመልክተናል፡፡ አመልካች ከዚህ አኳያ ለሰበር ሰሚ ችሎት ያቀረበችዉን ቅሬታ በስር ፍርድ ቤቶች ያልተነሳ አዲስ ክርክር በመሆኑ በፍ/ብ/ስ/ስ/ሕግ ቁጥር 182/2 እና ቁጥር 329 ስር በተደነገገዉ አግባብ በሰበር ደረጃ ሊነሳ የሚገባ ክርክር አይደለም በማለት ተጠሪ የተከራከረ ቢሆንም አመልካች ከዚህ አኳያ ያነሳችዉ ክርክር የስረ ነገር ዳኝነት ሥልጣንን የሚመለከት እንጂ ፍሬ ነገርን የሚመለከት አዲስ ክርክር ባለመሆኑ ከላይ እንደተገለጸዉ የፍ/ብ/ስ/ስ/ሕግ ቁጥር 9/2ን መንፈስና ዓላማ ከግምት በማስገባት እንዲህ አይነት መከራከሪያ በሰበር ደረጃም ሊነሳ የሚችል ነዉ በማለት በዚህ ረገድ ተጠሪ ያቀረበዉን ክርክር ባለመቀበል የስር የፌዴራል ፍርድ ቤቶች ጉዳዩን የመዳኘት ስልጣን ያላቸዉ መሆን አለመሆኑን ከዚህ ቀደም የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁጥር 53551፣ በሰ/መ/ቁጥር 65706 እና በሰ/መ/ቁጥር 90421 ላይ ከሰጠዉ አስገዳጅ ትርጉም አንጻር መርምረናል፡፡

የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁጥር 53551 እና በሰ/መ/ቁ. 65706 ላይ በሰጠዉ ትርጉም በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ሥር ባሉት ቀበሌያት የተደራጀ ባለአደራ ቦርድ ሕጋዊ ሰዉነት ያለዉ ሆኖ የቀበሌ የሕዝብ ሱቆች ተብለዉ የሚታወቁ ቤቶችን እንዲያስተዳድር በከተማ አስተዳደሩ የተቋቋመ በመሆኑ ከከተማዉ የቀበሌ አስተዳደር አንደ አንዱ አስፈጻሚ አካል የሚቆጠር በመሆኑ በአዲስ አበባ ከተማ ቻርተር አዋጅ ቁጥር 361/1995 አንቀጽ 41(1/ረ) መሰረት የከተማ አስተዳደሩ ከሚያስተዳድራቸዉ የመንግስት ቤቶች ጋር የተያያዙ ክርክሮችን የመዳኘት ስልጣን የተሰጠዉ ለከተማ ፍርድ ቤቶች በመሆኑ የሕዝብ ሱቅ የከተማ አስተዳደሩ የሚያስተዳድረዉ እንደመሆኑ ከሕዝብ ሱቁ ጋር በተያያዘ የሚነሳ ክርክር የመዳኘት ስልጣን ያለዉ የከተማ አስተዳደሩ ፍርድ ቤቶች ናቸዉ በማለት ወስኖ እንደነበር ከዉሳኔዉ ተመልክተናል፡፡

እንዲሁም በሰ/መ/ቁጥር 90421 በተሰጠዉ ትርጉም በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በየወረዳዉ የሚገኙ የሕዝብ ሱቆችና ሌሎች ገቢ ማስገኛ ተቋማትን ወደ ሸማቾች የሕብረት ሥራ ማኅበራት ለማስተላለፍ

በከተማ አስተዳደሩ ሐምሌ 05 ቀን 2004 የወጣዉ ደንብ ቁጥር 46/2004 ሥራ ላይ ከመዋሉ በፊት የሕዝብ ሱቅ የሚተዳደረዉ በቀበሌ የሕዝብ መዝናኛ ማእከላት ባለአደራ ቦርድ በመሆኑ ባለአደራ ቦርዱ የሕዝብ ሱቆችንና ሌሎች መዝናኛ ማእከሎችን በተመለከተ የሚያቀርበዉን ክስ ተቀብለዉ የማየት ሥልጣን ያላቸዉ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደሩ ፍርድ ቤቶች ነዉ ተብሎ በሰ/መ/ቁጥር 65706 ላይ ትርጉም መሰጠቱን በመጥቀስ የከተማ አስተዳደሩ በየወረዳዉ የሚገኙ የሕዝብ ሱቆችንና ሌሎች ገቢ ማስገኛ ተቋማትን ባወጣዉ ደንብ ቁጥር 46/2004 ወደ ሸማቾች ህብረት ሥራ ማኅበራት አስተላልፏል፡፡በዚህ ደንብ አንቀጽ 5 መሰረት ለሸማቾች ህብረት ሥራ ማኅበራት የተላለፉትን ንብረቶችና ገንዘብ ማኅበራቱ ለሕዝብ በሚጠቅም መንገድ የሚያስተዳድሩ መሆኑን የመቆጣጠርና የእርምት እርምጃ የመዉሰድ ሥልጣን ለአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ንግድና ኢንዱስትሪ ቢሮ ሰጥቷል፡፡ እንዲሁም በደንብ ቁጥር 46/2004 ድንጋጌዎች መሠረታዊ ባህሪያትም ሆነ በአሰራሩ የሸማቾች ህብረት ሥራ ማኅበራት በባለአደራ ቦርድ ሲተዳደሩ የነበሩትን የሕዝብ ሱቆችንና ሌሎች ገቢ ማስገኛ ተቋማት፣ንብረት፣ የሠራተኞችንና መብትና ግዴታ በመረከብ በሚጠቅም መንገድ የማስተዳደር ኃላፊነት ስላለበት በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ቁጥጥርና ክትትል የሚደረግበት የሕዝብ አገልግሎት ሰጭ ተቋም በመሆኑ በሰ/መ/ቁጥር 65706 ላይ በተሰጠዉ አስገዳጅ ትርጉም መሰረት ባለአደራ ቦርዱ በከተማ አስተዳደሩ ፍርድ ቤቶች ክስ ለማቅረብ ይችላል የተባሉ ጉዳዮችን በተመለከተ የሸማቾች ህብረት ሥራ ማኅበር ክስ የማቅረብ መብት አለዉ፡፡ የከተማ አስተዳደሩ ፍርድ ቤቶችም በዚህ አግባብ የሸማቾች ህብረት ሥራ ማኅበር የወረዳዉን የሕዝብ ሱቆችና ሌሎች የገቢ ማስገኛ ተቋማት የኪራይ ዉል አፈጻጸም በተመለከተ የሚቀርብ ክስ መርምሮ የመወሰን የዳኝነት ሥልጣን አለዉ በማለት መወሰኑን የዉሳኔዉ ይዘት ያሳያል፡፡

ከላይ ከተጠቀሱት የሰበር ሰሚ ችሎት ዉሳኔዎች እና በተያዘዉ ጉዳይ ተጠሪ ካቀረበዉ ክስ ላይ በግልጽ እንደተመለከተዉ ቀደም ሲል በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደሩ የቀበሌ የሕዝብ መዝናኛ ማእከላት ባለአደራ ቦርድ ሲተዳደሩ የነበሩት የሕዝብ ሱቆች፣ ሌሎች የመዝናኛ ማእከሎች እና ንብረቶች በከተማ አስተዳደሩ ሐምሌ 05 ቀን 2004 ዓ/ም የወጣዉን ደንብ ቁጥር 46/2004ን ተከትሎ በየወረዳዉ ለተቋቋሙት ለሸማቾች ሕብረት ሥራ ማኅበራት መተላለፋቸዉን ነዉ፡፡ በደንቡ አንቀጽ 11 ስር የባለአደራ ቦርድ መብትና ግዴታዎች ለሸማቾች ሕብረት ሥራ ማኅበራት እንደተላለፉ መደንገጉም የሚያሳየዉ ይህንኑ ነዉ፡፡ እንዲሁም በዚሁ ደንብ አንቀጽ 12 ስር እንደተደነገገዉ ከባለአደራ ቦርድ ጋር የተደረጉ ዉሎች ደንቡ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በሁለት ወር ዉስጥ ከሸማቾች ሕብረት ሥራ ማኅበር ጋር መታደስ እንዳለበት በግልጽ ተመልክቷል፡፡

ከላይ እንደተመለከተዉ በሰ/መ/ቁጥር 53551 እና በሰ/መ/ቁ. 65706 ላይ በተሰጠዉ አስገዳጅ ትርጉም መሰረት በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ሥር ባሉት ቀበሌያት ተደራጅቶ የነበረዉ የቀበሌ የሕዝብ መዝናኛ ማእከላት ባለአደራ ቦርድ እንደ ከተማዉ የአስፈጻሚ አካል ሊቆጠር የሚችል መሆኑ አከራካሪ አይደለም፡፡ አከራካሪዉ ጉዳይ የቀበሌ የሕዝብ መዝናኛ ማእከላት ባለአደራ ቦርድ መብትና

ግዴታ በደንብ ቁጥር 46/2004 የተላለፈላቸዉ የሸማቾች የኅብረት ሥራ ማኅበራት እንደ ከተማዉ አስተዳደር አስፈጻሚ አካል ሊቆጠሩ የሚችሉ መሆን አለመሆኑ ነዉ፡፡

እንደሚታወቀዉ የኅብረት ሥራ ማኅበራት በአዋጅ ቁጥር 147/1991(ይህ አዋጅ በአዋጅ ቁጥር 985/2009 ተተክቷል) በተደነገገዉ መሰረት በነጻ ገበያ የኢኮኖሚ ሥርዓት ዉስጥ ተመሳሳይ ፍላጎት ባላቸዉ ሰዎች መካከል በፈቃደኝነት ላይ የተመሰረተ ሕብረት በመፍጠር ገንዘብን፣ዕዉቀትን፣ንብረትንና ጉልበትን በማስተባበር ኢኮኖሚያዊ፣ ማኅበራዊ፣ ባህላዊና ሌሎች ፍላጎቶቻቸዉን እርስ በእርስ በመደጋገፍ ለማሟላትና ሌሎች በአዋጁ የተዘረዘሩትን ዓላማዎች ከግብ ለማድረስ በፌዴራል ደረጃ ወይም በክልል ደረጃ ኃላፊነቱ የተወሰነ ሆነዉ የመሥራቾች ስብሰባ ቃለ ጉባኤ፣ መተዳደሪያ ደንብ፣የአባላት ስም ዝርዝርና ፊርማቸዉን፣ የማኅበሩን ሥራ አመራር ኮሚቴ አባላት ስምና ፊርማቸዉን፣ የማኅበሩን ዕቅድ፣የመነሻ ካፒታሉን...ወዘተ የሚሉ በአዋጁ የተዘረዘሩትን ሌሎች ሰነዶችን በማቅረብ በመመዝገብ የሚቋቋሙ ሕጋዊ ሰዉነት ያላቸዉ ድርጅቶች እንደሆኑ በአዋጅ ቁጥር 147/1991 በአንቀጽ 9 እና 10 ወይም በአዋጅ ቁጥር 985/2009 አንቀጽ 10 እና 11 የተደነገገዉ ያሳያል፡፡ ከዚህም መረዳት የሚቻለዉ ምንም እንኳን የኅብረት ሥራ ማኅበራት የተቋቋሙበት ዓላማ የንግድ ሥራ በመስራት ለአባላቱ ጥቅም ከማስገኘት ባሻገር ለሕብረተሰቡ የሚጠቅሙ ሌሎች ተግባራትን በመፈጸም ማኅበራዊ ችግሮችን መፍታት ጭምር ቢሆንም የተቋቋሙት ግን እንደአስተዳደር አካል በመሆን ሳይሆን ኃላፊነቱ የተወሰነ ሕጋዊ ሰዉነት ያላቸዉ ድርጅቶች ወይም የኅበረት ሥራ ማኅበራት ሆነዉ እንደሆነ ነዉ፡፡

እንዲሁም በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ዉስጥ የተቋቋሙ የሸማቾች ኅብረት ሥራ ማኅበራት የከተማዉን ነዋሪዎች ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ችግሮች ከመቀነስ አንጻር ያላቸዉን ፋይዳ ከግምት በማስገባት የከተማ አስተዳደሩ ደንብ ቁጥር 46/2004ን በማዉጣት ቀደም ሲል በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደሩ የቀበሌ የሕዝብ መዝናኛ ማእከላት ባለአደራ ቦርድ ሲተዳደሩ የነበሩትን የሕዝብ ሱቆች፣ ሌሎች የመዝናኛ ማእከሎች እና ንብረቶች ከሐምሌ 05 ቀን 2004 ዓ/ም ጀምሮ በየወረዳዉ ለተቋቋሙት ለሸማቾች ኅብረት ሥራ ማኅበራት አስተላልፏል፡፡ በሌላ አነጋገር እነዚህ ማኅበራት በዚህ ደንብ የቀበሌ አስፈጻሚ አካል ሆኖ ተቋቁሞ በነበረዉ ባለአደራ ቦርድ ሲተዳደሩ የነበሩ ንብረቶችን የማስተዳደር መብት (በቦርዱ ሲተዳደሩ የነበሩ ቤቶችን የማከራየትና የማስተዳደር መብት ጨምሮ) መዉረሳቸዉ(በሕግ ማግኘታቸዉ) ከላይ እንደተመለከተዉ ሕጋዊ ሰዉነት ኖሯቸዉ ኃላፊነቱ የተወሰነ የኅብረት ሥራ ማኅበራት ሆነዉ የተቋቋሙበትን ህልዉናዊ ማንነታቸዉን (identity of legal personality) የሚቀይር አይደለም፡፡ እንዲሁም ከዚህ ጉዳይ ጋር በተያያዘ የከተማ አስተዳደሩ ያወጣዉ ደንብ ቁጥር 46/2004 ዓላማም ባለአደራ ቦርዱ የነበረዉ መብትና ግዴታ በከተማ አስተዳደሩ ለሚገኙ የሸማቾች ኅብረት ሥራ ማኅበራት የሚተላለፍበትንና በቀጣይ ማኅበራቱ ከባለአደራ ቦርዱ የተረከቡትን ገንዘብና ንብረት የከተማ አስተዳደሩን ነዋሪዎች በሚጠቅሙ ተግባራት ላይ የሚያዉሉበትን ሁኔታ መደንገግ እንጅ በከተማ አስተዳደሩ የሚገኙትን የሸማቾች ኅብረት ሥራ ማኅበራትን የከተማ አስተዳደር አስፈጻሚ አካል

የማድረግ ወይም የማኅበራቱን የባለቤትነት መብት ለከተማ አስተዳደሩ በማስተላለፍ ማኅበራቱን በከተማ አስተዳደር ባለቤትነት የሚተዳደሩ የልማት ድርጅቶች (enterprises) የማድረግ ዓላማ ደንቡ የለዉም፡፡

በተጨማሪም በደንብ ቁጥር 46/2004 አንቀጽ 5 ሥር የሽማቾች ኅብረት ሥራ ማኅበራት በደንቡ መሰረት የተረከቡትን ገንዘብና ንብረቶች ለሕዝብ በሚጠቅም መልኩ እያስተዳደሩ የሚገኙ መሆን አለመሆኑን የመቆጣጠርና የእርምት እርምጃ የመዉሰድ ሥልጣን ለከተማ አስተዳደሩ ንግድና ኢንዱስትሪ ቢሮ ተሰጥቷል፡፡የዚህ ድንጋጌ ዓላማም የሚያመላክተዉ የሸማቾች ኅብረት ሥራ ማኅበራት የሚያስተዳድሩትን ንብረትና ገንዘብ ለሕዝብ ጥቅም ማዋላቸዉን ማን ቁጥጥር እንደሚያደርግባቸዉና ማን የማስተካከያ እርምጃ እንደሚወስድባቸዉ ለአንድ ተለይቶ ለሚታወቅ አስተዳደር አካል ኃላፊነትና ተግባር መስጠት እንጂ የሸማቾች ኅብረት ሥራ ማኅበራት የሚያስተዳድሩትን ቤቶች በተመለከተ ከተፈጸሙ ዉሎች ጋር በተያያዘ ኪራይ ለማስከፈልና ቤቶችን በሕግ አግባብ ክስ መስርቶ ለማስለቀቅ በቢሮዉ በኩል ካልሆነ በራሳቸዉ ምንም መፈጸም እንዳይችሉና ማኅበራቱን የቢሮዉ ተቀጽላ ተቋም የማድረግ ዓላማ ያለዉ ድንጋጌ እንዳልሆነ ተገንዝበናል፡፡ እንዲሁም በዚህ ድንጋጌ መሰረት በቢሮዉ ቁጥጥርና ክትትል እንዲደረግባቸዉ መደረጉ በቀጥታ የሸማቾች ኅብረት ሥራ ኃላፊነታቸዉ የተወሰነ የኅብረት ሥራ ማኅበራት ሆነዉ የተደራጁትን ማኅበራት በሕግ ያሳካሉ ተብሎ የታቀደዉንና የተቋቋሙበትን ዝርዝር ዓላማዎች በማስቀረት እንደ ሕዝብ አገልግሎት ሰጭ አስተዳደር አካል የሚያስቆጥራቸዉ አይደለም፡፡

ከዚህ በላይ በደረስነዉ ድምዳሜ መሰረት በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ዉስጥ የሚገኙት የሸማቾች ኅብረት ሥራ ማኅበራት እንደ ከተማ አስተዳደሩ አስፈጻሚ አካል ወይም በከተማ አስተዳደር ባለቤትነት የሚተዳደር የልማት ድርጅቶች (enterprises) የሚቆጠሩ አይደሉም፡፡ ባለአደራ ቦርዱ ሲያስተዳድር የነበረዉን ንብረትና ገንዘብ የማስተዳደር ሥልጣን የተላላፈላቸዉ የሸማቾች ኅብረት ሥራ ማኅበራት በተለይም የሕዝብ ሱቆች፣ ሌሎች የመዝናኛ ማእከሎች እና ንብረቶች በተመለከተ በተፈጸሙ የኪራይ ዉሎች የሚመነጩ መብቶችን ከመጠየቅ እና ቤቶችን ከተከራዮቹ አስለቅቆ ተረክቦ ከማስተዳደር ጋር በተያያዘ ዳኝነት በመጠየቅ የሚያቀርቧቸዉን ክሶች በተመለከተ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፍርድ ቤቶች የመዳኘት ሥልጣን ይኖራቸዋል ተብሎ በተጠቃሹ ደንብ ቁጥር 46/2004 ላይ በግልጽ አልተደነገገም፡፡ እንዲሁም በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ዉስጥ የተቋቋሙ የኅብረት ሥራ ማኅበራት የሚያስተዳድሩትን ቤቶች እና እነዚህን ቤቶች በማከራየት ከሚፈጽሙት ዉሎች ጋር በተያያዘ ወይም በጠቅላላዉ በከተማ አስተዳደሩ ዉስጥ የተቋቋሙ የኅብረት ሥራ ማኅበራት ከሳሽ በመሆን የሚያቀርቧቸዉን ክሶች በተመለከተ የመዳኘት ሥልጣን የከተማ አስተዳደሩ ፍርድ ቤቶች ሥልጣን ነዉ ተብሎ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ቻርተር አዋጅ ቁጥር 361/1995(በማሻሻያ አዋጅ ቁጥር 408/1996) ስር በግልጽ አልተደነገገም፡፡

በሌላ በኩል በፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 11(1/ለ) እና 14(2) ስር እንደተደነገገዉ  በሌላ ሕግ ለሌሎች አካላት የተሰጠዉ የዳኝነት ሥልጣን እንደተጠበቀ ሆኖ በዚህ አዋጅ

አንቀጽ 3 እና 5 ሥር በፌዴራል ፍርድ ቤቶች የሚዳኙ ጉዳዮች ናቸዉ ተብለዉ ከተዘረዘሩት ጉዳዮችና ከተዘረዘሩት ሕጎች ከሚመነጩ ጉዳዮች ዉጭ ሆነዉ በአዲስ አበባ ከተማ እና በድሬዳዋ ከተሞች ዉስጥ የሚነሱ ሌሎች የፍትሐብሔር ጎዳዮችን የመዳኘት ሥልጣን ግምታቸዉ እስከ ብር 500,000.00 ድረስ የሆኑት በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ግምታቸዉ ከዚህ በላይ የሆኑት ደግሞ በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት እንደሚዳኙ ተገልጾ የፌዴራል ፍርድ ቤቶች የሥረ ነገር ሥልጣን ሆኖ በግልጽ ተለይቶ ተደንግጓል፡፡

በተያዘዉ ጉዳይ ከሳሽ የሆነዉ የየካ ክፍለ ከተማ ወረዳ 07 ቀበሌ 11/12/08 የሸማቾች ኃላፊነቱ የተወሰነ የኅብረት ሥራ ማኅበር (የአሁን ተጠሪ) ምንም እንኳን ለክሱ መነሻ የሆነዉን ቤት የማስተዳደር ሥልጣን ያገኘዉ የከተማዉ አስፈጻሚ አካል ከነበረዉ የቀበሌ ባለአደራ ቦርድ ቢሆንም ይህ ማኅበር የከተማ አስተዳደሩ አስፈጻሚ(አስተዳደር) አካል ካለመሆኑም በተጨማሪ ይህ ማኅበር የሚያስተዳድረዉን የቀድሞ የሕዝብ ሱቆች፣ ሌሎች የመዝናኛ ማእከሎች እና ንብረቶች ኪራይ ዉል ጋር በተያያዘ ኪራይ ለማስከፈልና በኪራይ ዉል ተይዘዋል ያላቸዉን ቤቶች ለማስለቀቅ የሚቀርበዉን ክስ የመዳኘት ስልጣን ለአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፍርድ ቤቶች አልተሰጣቸዉም፡፡በአዋጅ ቁጥር 361/1995 አንቀጽ 41(1/ረ) ስር የአዲስ አበባ ከተማ ፍርድ ቤቶች የዳኝነት ሥልጣን ሆኖ የተደነገገዉ በከተማ አስተዳደሩ መዋቅር ሥር በሚገኙ አስተዳደር አካላት የሚተዳደሩ የመንግስት ቤቶች ጋር በተያያዘ የሚነሱ ጉዳዮችን የሚመለከት እንጂ ንብረትነታቸዉ የመንግስት የሆኑ ቤቶች ሆነዉ በሕግ የማስተዳደር ሥልጣን ለሸማቾች ኅብረት ሥራ ማኅበራት የተሰጡትን ቤቶች ጋር በተያያዘ በማኅበራትና በግለሰቦች መካከል የሚነሱ ክርክሮችን የሚመለከት ድንጋጌ አይደለም፡፡

ከዚህ በመቀጠል የተመለከትነዉ በሰበር/መ/ቁጥር 90421 ላይ በተሰጠዉ ዉሳኔ ለድንጋጌዉ የተሰጠዉ ትርጉም አሁን በያዝነዉ መዝገብ ከተሰጠዉ ትርጉም እንዴት ይጣጣማል? የሚለዉን ነዉ፡፡ ከላይ በሰፊዉ እንደተገለጸዉ የሸማቾች ኃላፊነቱ የተወሰነ የኅብረት ሥራ ማኅበራት የአሁኑን ተጠሪ ጨምሮ የአስተዳደር አካል አለመሆናቸዉ፣ ከባለአደራ ቦርዱ የተላለፉለትን የቀድሞ የሕዝብ ሱቆች፣ ሌሎች የመዝናኛ ማእከሎች እና ንብረቶች ኪራይ ዉል ጋር በተያያዘ እና በኪራይ ዉል የተያዙ ቤቶችን ለማስለቀቅ የሚቀርቡ ክሶች በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፍርድ ቤቶች ይዳኛሉ በሚል በከተማ አስተዳደሩ ደንብ ቁጥር 46/2004 ላይ በግልጽ አልተደነገገም፡፡ እንዲሁም በጠቅላላዉ በከተማ አስተዳደሩ ዉስጥ የተቋቋሙ የኅበረት ሥራ ማኅበራት ከሳሽ በመሆን የሚያቀርቧቸዉን ክሶች በተመለከተ የመዳኘት ሥልጣን የከተማ አስተዳደሩ ፍርድ ቤቶች ሥልጣን ነዉ ተብሎ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ቻርተር አዋጅ ቁጥር 361/1995(በማሻሻያ አዋጅ ቁጥር 408/1996) ላይ በግልጽ አልተደነገገም፡፡ ይልቁንም በፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 11(1/ለ) እና 14(2) መሰረት የተያዘዉን አይነት ጉዳይ (የአከራካሪዉ ንብረት ግምት መጠን እየታየ) የመዳኘት የሥረ ነገር ስልጣን ያላቸዉ የፌዴራል ከፍተኛ እና መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤቶች እንደሆኑ በግልጽ ተደንግጓል፡፡

ስለሆነም አሁን ባለን ሥርዓት በተለይም የአዲስ አበባ ከተማ የፍርድ ቤቶች ሥልጣን ከሕግ የሚመነጭ በመሆኑ የተያዘዉን አይነት ጉዳይ የመዳኘት ስልጣን በሕግ ለአዲስ አበባ ከተማ ፍርድ ቤቶች አልተሰጠም፡፡ይልቁንም ጉዳዩን የመዳኘት ሥልጣን የፌዴራል ፍርድ ቤቶች በመሆኑ በፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 25/1988 (በአዋጅ ቁጥር 454/1997 እንደገና እንደተሻሻለዉ) አንቀጽ 10/4 ስር በተደነገገዉ መሰረት ቀደም ሲል በሰበር/መ/ቁጥር 90421 ላይ እንዲህ አይነት ጉዳይ የመዳኘት ሥልጣን የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፍርድ ቤቶች ነዉ ተብሎ ተሰጥቶ የነበረዉን ትርጉም ለዉጠን በዚህ በያዝነዉ መዝገብ ላይ የተሰጠዉ ትርጉም ገዥ ይሆናል ብለናል፡፡በዚህ መሰረት አመልካች በሰበር/መ/ቁጥር 90421 ላይ የተሰጠዉን ትርጉም መሰረት በማድረግ ጉዳዩን የመዳኘት ሥልጣን የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ነዉ ይባልልኝ በማለት ያቀረበችዉን ክርክር አልተቀበልንም፡፡ ክርክሩ በስር የፌዴራል ፍርድ ቤቶች በመዳኘቱ የተፈጸመ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የለም ብለናል፡፡

በመቀጠልም አመልካች ለክርክሩ መነሻ የሆነዉን ቤት ዉዝፍ ኪራይ ከፍላ ታስረክብ ተብሎ መወሰኑ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ነዉ ተብሎ ይታረምልኝ በማለት አመልካች ያቀረበችዉን ቅሬታ በተመለከተ እንደመረመርነዉ የአንድን ፍሬ ነገር መኖርና አለመኖር በተመለከተ የቀረቡትን ማስረጃዎች በመመርምርና በመመዘን በሕግ የተሰጣቸዉን ሥልጣን ተጠቅመዉ የማረጋገጥ ኃላፊነት የተጣለባቸዉ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ እና በይግባኝ ባዩት የሥር ፍርድ ቤቶች ላይ ነዉ፡፡ ለክርክሩ መነሻ የሆነዉ ቤት በአመልካች ባለቤትነት የሚታወቅ ሳይሆን አመልካች በኪራይ ዉል መነሻ ይዛ የኪራይ ዉሉ ጊዜ ተጠናቆ ዉሉ ላልተወሰነ ጊዜ ቢራዘምም የኪራይ ክፍያ ለመክፈል ፈቃደኛ ባለመሆን ይዛ የቆየችዉ ቤት እንደሆነ የስር ፍርድ ቤቶች አረጋግጠዋል፡፡ እንዲሁም ቤቱን የማስተዳደርና በቀጣይ የኪራይ ዉሉን የመዋዋል መብት ለተጠሪ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በወጣዉ ደንብ ቁጥር 46/2004 እንደተሰጠዉ ከግራ ቀኝ ክርክርና ማስረጃዎች በማረጋገጥ ላልተወሰነ ጊዜ ተራዝሞ የነበረዉ የኪራይ ዉል ቀሪ ሆኖ አመልካች ዉዝፍ ኪራይ ከፍላ ቤቱን ለተጠሪ እንድታስረክብ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ እና በይግባኝ ያዩት የሥር ፍርድ ቤቶች ማስረጃዎችን መዝነዉ ዉሳኔ ሰጥተዋል፡፡ እንዲሁም አመልካች አከራካሪዉን ቤት በኪራይ ዉል ሳይሆን የቤቱ ባለቤት በመሆን እንደያዘች የሚያሳይ ከተጠሪ የተሻለ ማስረጃ በማቅረብ ካለማስረዳቷም በተጨማሪ የፍ/ብ/ስ/ስ/ሕግ ቁጥር 223(1/ሀ) እና 145 ስር በተደነገገዉ አግባብ የቤቱ ባለቤት መሆኑን የሚያሳይ አግባብነት ያለዉ ማስረጃ ምን እንደሆነና ማስረጃዉ የሚገኝበትን ቦታ በማመላከትና በመዘርዘር ከመልሷ ጋር ባቀረበችዉ የማስረጃ መግለጫዋ ላይ ገልጻ ተከራክራ እያለች የታለፈበት መሆኑን በበታች ፍርድ ቤት ያሰማችዉና በዚኅ ችሎት ያቀረበችዉ ክርክር አያሳይም፡፡ በተጨማሪም የተጠሪ ዳኝነት ጥያቄ የኪራይ ዉሉን መሰረት ያደረገ በመሆኑና የኪራይ ዉሉ መኖሩ በተረጋገጠበት በሕጉ አግባብ የተቋቋመዉ የኪራይ ዉል በሕጉ አግባብ እስካልፈረሰ ድረስ በተዋዋይ ወገኖች መካከል አስገዳጅነት ያለዉ በመሆኑ አመልካች የኪራይ ዉሉን ሳታስፈርስ ተጠሪ የኪራይ ዉሉን መሰረት በማድረግ ባስከፈተዉ መዝገብ ላይ የቤት ባለቤትነትን የመፋለም ክርክር ማቅረቧ ተገቢ አይደለም ተብሎ በሥር ፍርድ ቤቶች የተያዘዉ አቋምም የሚነቀፍ አይደለም፡፡

ስለሆነም አመልካች የአከራካሪዉ ቤት ባለቤት ነኝ በማለት ያቀረበችዉ ክርክርም ሆነ ማስረጃዎችን በሚመለከት ያቀረበዉ የሰበር አቤቱታ የፍሬ ነገርና የማስረጃ ምዘናን የሚመለከት በመሆኑ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ. ሕገ መንግስት አንቀጽ 80(3/ሀ) እና በአዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 10 መሰረት ይህ ችሎት የፍሬ ነገርና የማስረጃ ምዘና ክርክር የመዳኘት ስልጣን ስላልተሰጠዉ ከዚህ አኳያ ያቀረበዉን ክርክር አልተቀበልነዉም፡፡በመሆኑም ተከታዩን ዉሳኔ ሰጥተናል፡፡

## ዉ ሳ ኔ

1. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 40079 ላይ በቀን 20/01/2010ዓ/ም የሰጠዉ ዉሳኔ እና የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 205269 ላይ በቀን 16/02/2011 ዓ/ም የሰጠዉ ዉሳኔ በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 348/1/ መሰረት ፀንተዋል፡፡
2. ጉዳዩን የመዳኘት የሥረ ነገር ሥልጣን የፌዴራል ፍርድ ቤቶች ነዉ ብለናል፡፡
3. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡

## ት ዕ ዛ ዝ

- የዚህ ዉሳኔ ግልባጭ ለሥር ፍርድ ቤቶች ይተላለፍ፡፡
- ዉሳኔዉ ይታተም ዘንድ ለሕግና ጥናት ክፍል ግልባጩ ይተላለፍ፡፡
- መዝገቡ ተዘግቷል፤ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የሰባት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ም/ቶ

የሠ/መ/ቁ. 161650

ሚያዚያ 29 ቀን 2011 ዓ/ም

**ዳኞች፡-** አልማው ወሌ

ሙስጠፋ አህመድ

አብርሃ መሰለ

ፊይሳ ወርቁ

ጳውሎስ ኦርሺሶ

**አመልካች፡-** አቶ ኃይለገብርኤል አየለ - ጠበቃ ትዕግስት ላዕከ ቀረቡ፡፡

**ተጠሪ፡-** ወ/ሮ ፀሐይ አየለ - ጠበቃ ወይንሸት መንግስቱ ቀረቡ፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍ ር ድ**

ይህ ጉዳይ የወራሽነት ማስረጃ ይሰረዝልኝ ጥያቄን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረውም የአሁኗ ተጠሪ ባሁኑ አመልካች ላይ ባቀረቡት የመቃወሚያ አቤቱታ ነው፡፡ ተጠሪ በአመልካች ላይ በአዲስ አበባ ከተማ መጀመሪያ ደረጃ ጳጉሜ 01 ቀን 2009 ዓ/ም ባቀረቡት ማመልከቻ፡- አመልካች ከሟች አቶ አየለ ግዛው ያለመወለዳቸውንና ምንም አይነት የደም ግንኙነት የሌላቸው መሆኑን ገልፀው አመልካች የሟቹ ወራሽ ነኝ በማለት በሐሰት ያገኙት ማስረጃ እንዲሰረዝላቸው ይወሰን ዘንድ ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡ የአሁኑ አመልካች ለተጠሪ መቃወሚያ በሰጡት መልስም ጉዳዩን ለማየት ፍርድ ቤቱ ስልጣን እንደሌለው እና ወራሽነታቸውን በ1997 ዓ/ም አረጋግጠው ከ2002 ዓ/ም ጀምሮ ከተጠሪ ጋር በፍርድ ቤት ክርክር ላይ የነበሩ ሁኖ እያለ መቃወሚያው መቅረቡ በይርጋ በታገደ ጉዳይ መሆኑን የሚያሳዩ ነጥቦችን በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያነት ያነሱ ሲሆን በፍሬ ነገሩ ላይም ተገቢ ነው ያሉትን ክርክር አቅርበዋል፡፡

ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው ፍርድ ቤትም ለአመልካች በመ/ቁጥር 1463/97 ሐምሌ 14 ቀን 1997 ዓ/ም የሰጠውን የወራሽነት ማስረጃ ይሰረዝልኝ ጥያቄ የማስተናገድ ስልጣን እንዳለው ገልጾ በዚህ ረገድ የቀረበውን የአመልካችን መቃወሚያ ያለፈው ሲሆን ይርጋውን በሚመለከት ግን አግባብነት ያላቸው ድንጋጌዎች በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1000 (1) እና 1000 (2) ድንጋጌዎች መሆናቸውን ከለየ በኂላ በእነዚህ ድንጋጌዎች መሰረት ጥያቄው በጊዜ ገደቡ ውስጥ ያልቀረበ ነው ወደሚለው ድምዳሜ የተጠሪን መቃወሚያ በይርጋ የታገደ ነው በማለት መዝገቡን ዘግቶታል፡፡ ከዚህም በኃላ የአሁኗ ተጠሪ ይግባኛቸውን ለከተማው ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት አቅርበው ፍርድ ቤቱም ግራ ቀኙን ከአከራከረ በኂላ ጉዳዩን መርምሮ የስር ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሳኔ ሙሉ በሙሉ አፅንቶታል፡፡ ተጠሪ የሰበር አቤቱታቸውን ለከተማው ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት አቅርበው ግራ ቀኙ እንዲከራከሩ ከተደረገ በኂላ ችሎቱ ጉዳዩን መርምሮ የአሁኗ ተጠሪ የሟች ንብረት ስለመያዛቸው

ገልፀው በተከራከሩበትና የአሁኑ አመልካችም ይህንኑ የተጠሪ ክርክር ባላስተባበሉበት ሁኔታ በአመልካች የተነሳው የይርጋ ክርክር በተጠሪ ላይ ሊታሰብባቸው አይገባም ወደሚለው ድምዳሜ ደርሶ ተጠሪ በአመልካች የወራሽነት ማስረጃ ላይ መቃወሚያ ለማቅረብ ይርጋ አያግዳቸውም በማለት ወስኖ ፍሬ ነገሩን የስር ፍርድ ቤት አጣርቶ እንዲወሰን ጉዳዩን መልሶለታል፡፡ የአሁኑ ሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ አመልካች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም፡- ከተጠሪ ጋር በተለያየ እርከን በሚገኙ ፍርድ ቤቶች ሲከራከሩ የቆዩና ተጠሪም በአመልካች የወራሽነት ማስረጃ ውሳኔ ላይ መቃወሚያ ሳያቀርቡ ለረዥም አመታት በቆዩበት ሁኔታና ተጠሪ የሟችን የውርስ ንብረት ስለመያዛቸው በማስረጃ ሳይረጋገጥ ለጉዳዩ አግባብነት የሌለው ድንጋጌ ተጠቅሶ መቃወሚያው በይርጋ የሚታገድ አይደለም ተብሎ መወሰኑ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት መከራከራቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ አቤቱታቸው ተመርምሮም በዚህ ችሎት እንዲታይ የተደረገ ሲሆን ተጠሪ ቀርበውም ግራ ቀኙ በጽሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን ይህ ችሎትም ለሰበር አቤቱታው መነሻ የሆነውን ውሳኔ አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩን እንደሚከተለው መርምሮታል፡፡ እንደመረመረውም የችሎቱን ምላሽ የሚያስፈልጋቸው አበይት ነጥቦች ተጠሪ ያቀረቡት የወራሽነት ማስረጃ ይሰረዝልኝ ጥያቄ በይርጋ ሊታገድ ይችላል ወይስ አይችልም? ከተባለስ ለጉዳዩ አግባብነት ያለው የይርጋ ጊዜ ምን ይህል ነው? የሚሉት ሁነው ተገኝተዋል፡፡

ከክርክሩ መገንዘብ የተቻለው ለመቃወሚያው አቤቱታ መነሻ የሆነው የአሁኑ አመልካች የሟች አቶ አየለ ግዛው ወራሽ ነኝ በማለት በመ/ቁጥር 1463/97 በ14/11/1997 ዓ/ም ያገኙት የወራሽነት ማስረጃ ሲሆን ተጠሪ ይህ ማስረጃ ከሕግ ውጪ የተገኘ ነው በማለት ማስረጃው እንዲሰረዝላቸው የመቃወሚያ አቤቱታ ያቀረቡት ጳጉሜ 01 ቀን 2009 ዓ/ም መሆኑን፣ ከዚህ በፊት ደግሞ አመልካችና ተጠሪ ከ2002 ዓ/ም ጀምሮ እስከ 2007 ዓ/ም ድረስ በተለያዩ ፍርድ ቤቶች በክርክር ላይ የነበሩ መሆኑን፣ አመልካች የሟች አቶ አየለ ግዛው ልጅ ነኝ የሚል አቋም ያላቸው ቢሆንም ተጠሪ ደግሞ ይህንኑ በመቃወም አመልካች የሟቹ ልጅ አይደሉም በማለት የሚከራከሩ በመሆኑ ግራ ቀኙ የአቶ አየለ ግዛው ተወላጆች ናቸው በማለት ከወዲሁ መደምደም የማይቻል መሆኑን፣ የከተማው ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት የተጠሪ መቃወሚያ በይርጋ ሊታገድ የሚችል አይደለም ወደሚለው ድምዳሜ የደረሰው ተጠሪ የሟቹን ንብረት መያዛቸውን አመልካች አላስተባበሉም በሚል አቢይ ምክንያትና የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1000 (1) ደንጋጌን በዋቢነት በመጥቀስ መሆኑን ነው፡፡

በመሰረቱ በተያዘው ጉዳይ ለጉዳዩ ቀጥተኛ ተፈጻሚነት ያለው አንዱ የሕግ ማዕቀፍ በአዋጅ ቁጥር 361/95 እና ይህንኑ አዋጅ ባሻሻለው አዋጅ ቁጥር 408/96 የተዘረጋው ስርዓት ሲሆን በአዋጁ አንቀፅ 41 ድንጋጌ አግባብ የወራሽነት ማስረጃ፣ የሞግዚትነት ምስክር ወረቀት ማስረጃ የመስጠት የስረ ነገር ስልጣን ለአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፍርድ ቤቶች የተሠጠ መሆኑን በግልጽ ያሳያሉ፡፡ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፍርድ ቤቶች በወራሽነት ምስክር ወረቀትና በሞግዚትነት ስልጣን ላይ የማስረጃ

ወረቀት ውሳኔ መስጠት የሚችሉ መሆኑ በሕጉ ተመልክቷል፡፡ ከዚህም በላይ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 358 መሰረት የተቃውሞ አቤቱታ የሚቀርበው በፍትሓ ብሔር ሥነ ሥርዓት ሕጉ በተሰጠው የውሳኔ ትርጉም (አንቀፅ 3 ይመልክቷል) መሰረት ሊፈፀም የሚችል ውሳኔ ከተሰጠ እና ውሳኔው የክርክሩ ተካፋይ ያልሆነ ወገን መብትና ጥቅም የሚነካ መሆኑ ሲረጋገጥና አቤቱታው ውሳኔው ከመፈፀሙ በፊት ከቀረበ ነው፡፡ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 358 አይነተኛ አላማ ማስረጃው ትክክለኛነቱና ሕጋዊነቱ ተረጋግጦ በማስረጃነቱ (Declaratory Judgement) በሚሰጠው ውሳኔ ላይ ሳይሆን ከላይ እንደተገለፀው ሊፈፀም በሚችል ውሳኔ የክርክሩ ተካፋይ ያልሆነ ወገን መብትና ጥቅምን ማስከበር ነው፡፡

ከላይ እንደተገለጸው አዋጅ ቁጥር 361/1995 አንቀፅ 41/1//ሸ/ በአዋጅ ቁጥር 408/1996 አንቀፅ 2/1/ እንደተሻሻለው የወራሽነት የምስክር ወረቀት ለማግኘት በሚቀርብ አቤቱታ ላይ የአዲስ አበባ ከተማ ፍርድ ቤቶች የዳኝነት ስልጣን እንዳላቸው የተደገገ ሲሆን ተቃውሞ የቀረበበት ውሳኔ የተሰጠውም በሕጉ በተደለደለው የዳኝነት ስልጣን መሰረት ነው፡፡ በሌላም በኩል የተቃውሞ አቤቱታው ያስከተለው የሕግ እና የፍሬ ነገር ክርክር ይዘት ሲታይ ከወራሽነት የምስክር ወረቀቱ የዘለለ እንድምታ የሌለው መሆኑ ከተረጋገጠ ማስረጃውን የሰጠው ፍርድ ቤት የማስረጃው ይሰረዝልን ጥያቄ ማስተናገድ ያለበት መሆኑን በመግለጽ ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁጥር 105211 በቀረበው ጉዳይ ላይ በአዋጅ ቁጥር 454/97 አንቀፅ 2(1) ድንጋጌ መሰረት በየትኛውም እርከን የሚገኝ ፍርድ ቤትን የሚያስገድድ የሕግ ትርጉም ሰጥቷል፡፡ በዚህ አስገዳጅ የሕግ ትርጉም የስረ ነገር ስልጣን ጥያቄን ለመወሰን መርህ የሆነው የክሱን ምክንያት ይዘት መመልከት አስፈላጊ መሆኑንና በዚህም መሰረት ከይዘቱ ውጭ የሆኑ ሌሎች የማያመሳስሉ ሁኔታዎች መኖር ጉዳዮች በተመሳሳይ የስረ ነገር ስልጣን ስር ያርፋሉ የሚል መደምደሚያ ላይ የሚያደርስ መሆኑ ከተረጋገጠ ማስረጃውን የሰጠው ፍርድ ቤት የማስረጃው ይሰረዝልኝ ጥያቄን ማስተናገድ የሚገባው መሆኑን፣ ሆኖም የማስረጃው ይሰረዝልኝ ጥያቄ ከማስረጃው መሰረዝ ባለፈ በሌሎች ህጋዊ መብቶች ውጤት ላይ ሁሉ አንድምታ ያለው፣ ማስረጃውን ለሰጠው ፍርድ ቤት ያልተሰጠውን ጉዳይ የሚመለከትና ሌሎች ሕጎች የሚነካ የፍሬ ነገር እና የሕግ ክርክር የሚመለከት መሆኑ ከተረጋገጠ ግን ማስረጃውን የሰጠው ፍርድ ቤት ማስረጃው ይሰረዝልኝ በሚል መነሻ ስልጣኑ ስር የማያወድቀውን ጉዳይ ሊመለከተው የማይገባ መሆኑን ችሎቱ መወሰኑን ከውሳኔው ይዘትና መንፈስ የምንረዳው ጉዳይ ነው፡፡ ስለሆነም የወራሽነት የምስክር ወረቀትን በተመለከተ የሚቀርብ የተቃውሞ አቤቱታ የማስረጃውን ትክክለኛነት እና ህጋዊነት ከማረጋገጥ ያለፈ አንድምታ የሌለው መሆኑ ከተረጋገጠ ብቻ ማስረጃውን በሰጠው ፍርድ ቤት የሚስተናገድ ይሆናል፡፡ የወራሽነት ማስረጃ ይሰረዝልኝ ጥያቄ ማስረጃውን በሰጠው ፍርድ ቤት የሚስተናገድ ነው ከተባለ እና መቃወሚያው የሚቀርበውም ከላይ በተገለጸው አግባብ ከሆነ ክርክሩ የሚመራው በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 359 ስር በተደነገገው አግባብ በመደበኛው የክርክር አመራር ስርዓት ነው፡፡ከዚህ አንጻር ሲታይ መደበኛ ክርክር ላይ በሕጉ አግባብ የተነሳ የይርጋ መቃወሚያ ሲኖር ፍርድ ቤቱ ለጉዳዩ አግባብነት ያለውን ድንጋጌን

በመለየት በመቃወሚያው ላይ ተገቢው ብይን መስጠት ያለበት መሆኑን የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 244 እና 245 ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ ያስገነዝባሉ፡፡

የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1000 ድንጋጌ ተፈፃሚነት የሚኖረው አንድ እውነተኛ የሆነ ወራሽ ትክክለኛው ወራሽ መሆኑ ታውቆለት ዋጋ ያለው የወራሽነት ማስረጃ ሳይኖረው የውርሱን ንብረት በእጁ ያደረገው ሰው የውርሱን ንብረት እንዲለቅ ክስ በሚያቀርብበት ጊዜ ስለመሆኑ የድንጋጌው ይዘት በግልጽ ያሳያል፡፡ ነገር ግን በተያዘው ጉዳይ የተጠሪ ክስ የሟች አቶ አየለ ግዛው የውርስ ንብረት በአሁኑ አመልካች ስለተያዘ ይለቀቅልኝ የሚል ይዘት የሌለው ሲሆን በአመልካች ላይ የፍርድ መቃወሚያ አቤቱታ የቀረበው አመልካች ከሟች አቶ አየለ ግዛው ጋር ምንም ዓይነት የተወላጅነት ግንኙነት ሳይኖራቸው አመልካች የሚቹ ልጅ ነኝ በማለት የወሰዱት የወራሽነት ማስረጃ ይሰረዝልኝ የሚል መሆኑን የክርክሩ ሂደት በግልጽ ያሳያል፡፡ በመሆኑም የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1000 ድንጋጌ ለዚህ ጉዳይ ተፈፃሚ ሊደረግ የሚችልበት የሕግ አግባብ የለውም፡፡

ተጠሪ በዚህ መልኩ ያቀረቡት አቤቱታ በምን ያሕል ጊዜ መቅረብ እንዳለበት በውርስ ሕጉ ድንጋጌዎች በግልጽ አልተመለከተም፡፡ የውርስ ሕጉ በዚህ ረገድ ክፍተት ካለበት ወደ ጠቅላላ ሕግ በመሄድ ለጉዳዩ እልባት መስጠት በሕግ አተረጓጎም መርህ /principles of legal interpretation/ የተፈቀደ ነው፡፡ በዚሁ መሠረትም ጉዳዩን በፍትሐብሔር ሕጉ ጠቅላላ ስለውሎች ከተደነገገው አንፃር መመልከት የግድ ይላል፡፡ በዚህ ክፍልም ግዴታዎች ከውል የተገኙ ባይሆንም በውል ሕግ ላይ የተመለከቱት ድንጋጌዎች ተፈፃሚነት እንዳላቸው በቁጥር 1677/1/ ላይ ተመልክቷል፡፡ በውል ሕግ ደግሞ ዋናው የይርጋ ድንጋጌ በቁጥር 1845 ላይ የተመለከተው የ10 ዓመት የይርጋ ጊዜ ነው፡፡ የይርጋ አቆጣጣር ጊዜ መነሻ ሊሆን የሚችለው ጊዜም በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1846 ድንጋጌ አግባብ ሊታይ የሚችል ነው፡፡

በተያዘው ጉዳይ ተጠሪ አመልካች ከሕግ ውጪ የወራሽነት ማስረጃ አግኝተዋል በማለት ማስረጃውን ለሰጠው ፍርድ ቤት ለአመልካች የሰጠውን የወራሽነት ማስረጃ እንዲሰረዝ የመቃወሚያ አቤቱታ ያቀረቡት ጳጉሜ 01 ቀን 2009 ዓ.ም. ሲሆን አመልካች ይህንን ማስረጃ ያገኙ መሆኑን ያወቁት ደግሞ ከ2002 ዓ/ም ጀምሮ መሆኑን የክርክሩ ሂደት በግልፅ ያሳያል፡፡ አመልካች ያያዙት የወራሽነት ማስረጃ በፍርድ ቤት የተረጋገጠ በመሆኑ ሕጋዊ ውጤት የሚኖረው እንደመሆኑ መጠን ተጠሪ ይህ ማስረጃ ከሕግ ውጪ ለአመልካች መሰጠቱን ከአወቁበት ጊዜ ጀምሮ በ10 ዓመት ጊዜ ውስጥ ተጠሪ አቤቱታውን የማቅረብ ግዴታ አለባቸው፡፡ ከዚህ አንጻር ሲታይ ተጠሪ ከ2002 ዓ/ም ጀምሮ ጉዳዩን የሚያውቁ በመሆኑ ከዚህ ጊዜ ጀምሮ በአስር አመት ጊዜ ውስጥ መቃወሚያውን ማቅረብ የሚችሉ በመሆኑና የአስር አመት ጊዜ ሳያልፍ በ2009 ዓ/ም መቃወሚያቸውን ያቀረቡ በመሆኑ ክሱ በይርጋ የሚታገድበት አግባብ የለም፡፡

ስለሆነም የከተማው ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ለጉዳዩ አግባብነት የሌለውን የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1000 ድንጋጌ ለውሳኔው ዋቢ ማድረጉ ተገቢ ባሆንም ክሱ በይርጋ የታገደ አይደለም

በማለት የደረሰው ድምዳሜ ግን ከውጤት አንጻር የሚነቀፍ ባለመሆኑ ውሳኔው መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ነው ለማለት አልተቻለም፡፡

**ው ሣ ኔ**

1. የአዲስ አበባ ከተማ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 28169 ሰኔ 05 ቀን 2010 ዓ/ም የሰጠው ውሳኔ ከውጤት አንጻር በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 348/1/ መሠረት ጸንቷል፡፡
2. በሐሰት ለተገኘ የወራሽነት ማስረጃ ይሰረዝልኝ ጥያቄ ተፈጻሚነት ያለው የይርጋ ጊዜ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1677 እና 1845 ድንጋጌዎች መሰረት የአስር አመት የይርጋ ጊዜ ነው ብለናል፡፡
3. ተጠሪ ያቀረቡት የወራሽነት ማስረጃ ይሰረዝልኝ መቃወሚያ በይርጋ ቀሪ አልሆነም ተብሎ ተወስኗል፡፡
4. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ ወጭና ኪሣራ ይቻቻሉ፡፡ መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መ/ቤት ይመለስ ብለናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ብ/ግ

የሰ.መ.ቁ 161301

ሚያዝያ 30 ቀን 2011 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ብርሃኑ አመነዉ

በዕዉቀት በላይ

እንዳሻዉ አዳነ

ሃይሉ ነጋሽ

እትመት አሠፋ

አመልካቾች:- 1. አቶ አዲስ አልታሰብ

2. ወ/ሮ አለም ታደሰ

ተጠሪ፡- የፋርጣ ወረዳ ቋልህ ቀበሌ አስ/ጽ/ቤት

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍርድ**

ለሰበር አቤቱታው መነሻ የሆነው ጉዳይ የመሬት ይዞታን የሚመለከት ነው፡፡ በሥር ፍ/ቤት በተደረገው ክርክር የአሁን አመልካቾች ተከሳሾች፤ የአሁን ተጠሪ ደግሞ ከሣሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡ የአሁን ተጠሪ በስር ፍ/ቤት ያቀረበው ክስ ይዘት በአጭሩ፡-አመልካቾች አዋሳኙ በክሱ ተ.ቁ 1 ላይ የተገለጸውን 2.5 ቃዳ መሬት ወረው የያዙ እና የሚጠቀሙበት መሆኑን፤ አዋሳኙ በክሱ ተ.ቁ 2 ላይ የተጠቀሰውን 10 ቃዳ መሬት ደግሞ 1.5 ቃዳ ገፍተው የሚጠቀሙበት መሆኑን በመግለጽ ይዞታውን እንዲያስረክቡ እና የምርት ዘመን አላባ ግምት እንዲከፍሉ ይወሰንለት ዘንድ ዳኝነት መጠየቁን የሚያሳይ ነው፡፡

የአሁን አመልካቾች በሰጡት መልስ ከአሁን በፊት በጉዳዩ ላይ የተከራከሩ እና ድጋሚ ክስ ሊቀርብ የማይገባ መሆኑን፤ ጉዳዩ በመሬት አመቻች ያልታየ እና በእርቅ ያለቀ መሆኑን፤ ከሁለት ዓመት በላይ የሰብል ግምት ሊጠየቁ የማይገባ መሆኑን በመግለጽ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ያቀረቡ ሲሆን በፍሬነገሩ ላይ በሰጡት መልስ በተጠቀሰው የምርት ዘመን በመሬቱ ላይ የተመረተ ምርት የሌለ መሆኑን፤ ከሳሽ የሕዝብ ግጦሽ ያዙ በሚል ክስ ካቀረበ በኋላ የእርሻ መሬት አስመስሎ ክስ ማቅረቡ እርስ በእርሱ የሚጋጭ መሆኑን፤ ክስ የቀረበበት መሬት የተከሳሽ ወላጅ አባት መሆኑን እና መሬቱ

የግጦሽ መሬት ነው በሚል ጭቅጭቅ ተነስቶ የተወሰነላቸው መሆኑን በመግለጽ የተጠሪ ክስ ውድቅ ሊደረግ ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡

ጉዳዩ የቀረበለት በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የፋርጣ ወረዳ ፍ/ቤት ተጠሪ ምስክር እንዲያሰማ ታዞ ማቅረብ ባለመቻሉ መብቱን በማለፍ የአመልካቾችን ምስክሮች የሰማ መሆኑን፤ ከዚህ በኋላ የመሬቱን መጠን በሚመለከት ክሱ ተሻሽሎ እንዲቀርብ የታዘዘ እና ክሱ ተሻሽሎ የቀረበ መሆኑን፤ ፍ/ቤቱ በመቀጠል የግራቀኙ ምስክሮች እንዲሰሙ ትዕዛዝ የሰጠ መሆኑን፤ በዚሁ መሠረት ተጠሪ ምስክሮችን አቅርቦ ያሰማ መሆኑን እና አመልካቾችም አስቀድሞ አቅርበውት ከነበረው መልስ እና ምስክሮች ውጪ ሌላ መልስ እና ምስክር እንደሌላቸው የገለጹ መሆኑን መዝገቡ ያመለክታል፡፡

ጉዳዩ የቀረበለት ፍ/ቤት የግራቀኙን ማስረጃ ከመረመረ በኋላ የአመልካቾች ምስክሮች የጠቀሱት መሬት ተመሳሳይ አይደለም፤ አመልካቾች መሬቱ የእነርሱ ስለመሆኑ የሚገልጽ የይዞታ ማስረጃ አላቀረቡም፤ የሚመለከተው የአስተዳደር አካል 1ኛው መሬት የወል መሬት መሆኑን፤ ሁለተኛውን መሬት ከራሳቸው ይዞታ በመነሳት በስተምዕራብ በግምት 1.5 ቃዳ የገፉ መሆኑን በመግለጽ ምላሽ የላከ በመሆኑ አመልካቾች የአከራካሪው መሬት ባለይዞታ ነን በማለት ያቀረቡት ክርክር በክልሉ የገጠር መሬት ሕግ መሠረት ተቀባይነት ስለሌለው መሬቱን እንዲለቁ እና የአዝመራ ግምት እንዲከፍሉ ሲል ወስኗል፡፡

አመልካች ይህን ውሳኔ በመቃወም ለደቡብ ጎንደር መስተዳድር ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት የይግባኝ አቤቱታ ያቀረቡ ቢሆንም አቤቱታቸው በትዕዛዝ ውድቅ ተደርጓል፡፡ አመልካቾች በመቀጠል ለክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አቤቱታ አቅርበዋል፡፡ የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ግራቀኙን ካከራከረ በኋላ ክሱ የተስተካከለው የመሬቱን መጠን አስመልክቶ እስከሆነ ድረስ አጠቃላይ የተደረገውን ክርክር እና ስነ ስርዓት ሊለውጠው የሚችል ባለመሆኑ የተጠሪ ምስክሮች እንዲሰሙ መደረጉ ተገቢ አልነበረም፤ ሆኖም አስቀድሞ በነበረው ማስረጃ መሠረት ጉዳዩ ሲታይ መሬቶቹ የወል ናቸው መባሉ ተገቢ ነው፤ ከሳሽ ክስ በማሻሻል ሒደት ምስክር ማሰማቱ ስነስርዓታዊ አይደለም ስለተባለ የሰብል ግምት ሊከፍል አይገባም በማለት የስር ፍ/ቤቶች የሰጡትን ውሳኔ በማሻሻል ወስኗል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው ይህን ውሳኔ በመቃወም ነው፡፡

የአመልካቾች የሰበር አቤቱታ መሠረታዊ ይዘትም፡- ተጠሪ መሬቱን በበላይነት የሚያስተዳድረው አካል አቅርቦት የነበረውን እና የተወውን ክስ የቀበሌው አስተዳደር ውክልና ሰጥቶኛል በሚል ክስ መመስረቱ አግባብ አይደለም፤ ተጠሪ በምን አግባብ ክስ እንዳቀረበ ሳይመረመር በደፈናው አመልካቾች ያቀረብነው መቃወሚያ ውድቅ መደረጉ አግባብ አይደለም፤ አስቀድሞ የተዘጋው ክስ በድጋሚ ከሚንቀሳቀስ በቀር ፍሬጉዳዩ እና ጭብጡ አንድ በሆነ ጉዳይ በድጋሚ የቀረበው ክስ አግባብ አይደለም፤ ጉዳዩ አስቀድሞ በመሬት አመቻች ኮሚቴ ሳይታይ ክስ መቅረቡ ተገቢ አይደለም፤ አመልካቾች ጉዳዩ አግባብነት ባላቸው አካላት እንዲጣራ ጠይቀን ተቀባይነት አላገኘንም፤ የተወሰነ ነዋሪ መሬቱ የሕዝብ

ግጦሽ መሬት ነው በማለት ለፍትሕ ጽ/ቤት አመልክቶ ጉዳዩ እንዲጣራ በተሰጠው ትዕዛዝ መነሻነት ክስ የተነሳበት መሬት የአመልካቾች መሆኑ ተረጋግጧል፤ ዐቃቤሕግ ጉዳዩ ውሳኔ ሊሰጥበት ሲል ክሱን እንዳዘጋ በገለጽንበት ሁኔታ የስር ፍ/ቤት አስቀድሞ የተዘጋውን መዝገብ እና የተጣራበትን ሪፖርት በትዕዛዝ አስቀርቦ ማየት ሲገባው ይህ ሳይደረግ ውሳኔ መሰጡቱ አግባብ አይደለም የሚል ነው፡፡

የአመልካቾች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ ቀደም ሲል በስር ፍ/ቤት በመ.ቁ 17143 በአሁን አመልካች ላይ የቀረበው ክስ በከሳሽ ጥያቄ ከተዘጋ በኋላ በድጋሚ በመ.ቁ 17497 ክስ ቀርቦ ፍ/ቤቱ በቀን 14/02/09 በዋለው ችሎት ተጣርቶ እንዲቀርብለት በሰጠው ትዕዛዝ የመሬት አስተዳደር በ18/02/09 የተጻፈ ሪፖርት ባቀረበበት ሁኔታ የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት መመዘን ያለበት ማስረጃ በተዘጋው መዝገብ የቀረበውን ነው በማለት ተጣርቶ የቀረበው ሪፖርት ሳይመዘን የወሰነበትን አግባብነት ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ በዚህ ችሎት እንዲታይ ተደርጓል፡፡ ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎም ግራቀኙ በጽሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

የተጠሪ መልስ ይዘት በአጭሩ፡- በቅድሚያ በወረዳው መሬት አስተዳደር እና አጠቃቀም ጽ/ቤት ክስ ቀርቦ መሬቱ የማነው የሚለው ሊረጋገጥ የሚገባው መሬትን ለማስተዳደር በሕግ ስልጣን ባለው የመሬት አስተዳደር መስሪያ ቤት ባለሙያ ሊሆን ይገባው ነበር፤ ይህ ታልፎ ጉዳዩ በምትክ ዳኛ እንዲጣራ መደረጉ በአግባቡ ካለመሆኑም ባሻገር ምትክ ዳኛው በመሬቱ ተጠቃሚ የሆነውን ማህበረሰብ በትቸታው ባላካተተ መልኩ አጣርቶ ያቀረበው ማስረጃ የተሳሳተ መሆኑ በፍትሕ ማሻሻያ ኮሚቴ መረጋገጡ እና ክሱ ሲመሰረትም የአዋሳኝ ችግር የነበረበት መሆኑ ግምት በማስገባት ጉዳዩን እንደገና አጣርተን ክስ ማቅረብ ያግዝ ዘንድ ክስ እንድናነሳ ይፈቀድልን በማለት ዓቃቤሕግ ያቀረበውን ጥያቄ ፍ/ቤቱ ተቀብሎ መዝገቡን የዘጋ መሆኑን ተከትሎ አከራካሪው መሬት የወል መሬት መሆኑን ስልጣን ባለው አካል በሚገባ አጣርቶ ማስረጃ እንዲሰጥ ተደርጓል፤ ተጠሪ ማስረጃውን መሠረት በማድረግ የወል መሬት ተጠቃሚዎችን ወክሎ ክስ ማቅረብ ያለበት የቀበሌው አስተዳደር መሆኑን በመረዳት በአዲስ መልክ ቀበሌው ጽ/ቤቱን ከሳሽ በማድረግ ክሱ መቅረቡ አግባብ ነው፤ የተጠሪ ምስክር መሰማት በተመለከተ በክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ምላሽ የተሰጠው በመሆኑ በድጋሚ መቅረቡ አግባብ አይደለም፤ አመልካቾች አከራካሪውን መሬት በውርስ ስለማግኘታቸው ምንም ዓይነት ማስረጃ አላቀረቡም፤መሬቱ የወል ስለመሆኑ በአግባቡ ተረጋግጧል፤ጉዳዩ በቅድሚያ በገላጋይ ሽንጎ እንዲታይ በክልሉ ሕግ በአስገዳጅነት ያልተቀመጠ በመሆኑ የስር ፍ/ቤት የሰጠው ውሳኔ ሊጸና ይገባል የሚል ነው፡፡ አመልካችም የሰበር አቤቱታቸውን በማጠናከር የመልስ መልስ ሰጥተዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ በአጭሩ ከላይ የተገለጸው ነው፡፡ እኛም እንዲጣራ የተያዘውን ነጥብ ከግራቀኙ ክርክር፤ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸው ሕጎች ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው መርምረነዋል፡፡

አከራካሪውን መሬት በተመለከተ ቀደም ሲል ቀርቦ የነበረው ክስ ከሳሽ የነበረው ወገን ባቀረበው ጥያቄ በፍ/ቤት ፈቃድ የተቋረጠ መሆኑን፤ በመቀጠልም የአሁን ተጠሪ አዲስ ክስ ያቀረበ መሆኑን፤ ጉዳዩ የቀረበለት ፍ/ቤት የግራቀኙን ማስረጃ ከመረመረ በኋላ አመልካቾች ይዞታው የእነርሱ መሆኑን የሚያሳይ ማስረጃ አለማቅረባቸውን እና ምስክሮቻቸውም የጠቀሱት መሬት ክስ ከቀረበበት መሬት ጋር ተመሳሳይ አለመሆኑን እና የሚመለከተው የአስተዳደር አካል 1ኛው መሬት የወል መሬት መሆኑን፤ ሁለተኛውን መሬት ከራሳቸው ይዞታ በመነሳት በስተምዕራብ በግምት 1.5 ቃዳ የገፉ መሆኑን በመግለጽ ምላሽ የላከ መሆኑን በመግለጽ አመልካቾች መሬቱን እንዲለቁ እና የአዝመራ ግምት እንዲከፍሉ በማለት የወሰነ መሆኑን፤  የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎትም ክሱ የተስተካከለው የመሬቱን መጠን በሚመለከት ብቻ በመሆኑ አጠቃላይ የተደረገውን ክርክር እና ስነ ስርዓት ሊለውጠው የሚችል ባለመሆኑ የተጠሪ ምስክሮች እንዲሰሙ መደረጉ ተገቢ አለመሆኑን፤ ሆኖም አስቀድሞ ቀርቦ በነበረው ማስረጃ መሠረት ጉዳዩ ሲታይ መሬቶቹ የወል ናቸው መባሉ ተገቢ መሆኑን በመግለጽ ከሳሽ ክስ በማሻሻል ሒደት ምስክር ማሰማቱ ስነስርዓታዊ አይደለም ስለተባለ የሰብል ግምት ሊከፍል አይገባም በማለት የስር ፍ/ቤቶች የሰጡትን ውሳኔ በማሻሻል የወሰነ መሆኑን ከክርክሩ ሒደት መገንዘብ ችለናል፡፡

በመሠረቱ ክስ ከቀረበ በኋላ በማናቸውም ጊዜ ከሳሹ ያቀረበውን ክስ በማንሳት ከተከሳሾቹ አንዱ ወይም ከአንድ በላይ የሆኑትን ከክሱ ውጪ ለማድረግ ወይም ያቀረበውን ክስ በሙሉ ወይም በከፊል ለመተው እንደሚችል ፍ/ቤቱም ተከሳሹ ባቀረበው ነገር በከፊል ወይም በሙሉ አዲስ ክስ ለማቅረብ ሊያስፈቅድለት የሚችል በቂ ምክንያት ያለው ሲሆን ስለጉዳዩ ተገቢ መስሎ የታየውን ትዕዛዝ በመስጠት ከሳሹ በሙሉ ወይም በከፊል በተወው ነገር አዲስ ክስ ለማቅረብ የሚችልበትን መብቱን በመጠበቅ ያቀረበውን ክስ በሙሉ ወይም በከፊል እንዲተው ሊፈቅድለት የሚችል መሆኑን፤ በዚሁ መሠረት በፍርድ ቤቱ ፈቃድ እንደገና ለሚቀርቡ ክሶች ሁሉ የመጀመሪያው ክስ እንዳልቀረበ ተቆጥሮ የይርጋው ዘመን የሚታሰበው በአዲሱ ክስ መሠረት መሆኑን የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 278 ድንጋጌ ያስገነዝበናል፡፡ ከድንጋጌው ይዘት መገንዘብ የሚቻለው አንድ ተከራካሪ ወገን በፍ/ቤት ፍቃድ ክሱን የተወ እና አዲስ ክስ ያቀረበ በሆነ ጊዜ በቀረበው አዲስ ክስ ላይ በግራቀኙ ተከራካሪ ወገኖች የቀረቡት እና በፍ/ቤቱ ትዕዛዝ መሠረት የቀረቡ ማስረጃዎች ተመርምረው እና ተመዝነው ውሳኔ የሚሰጥበት እንጂ አስቀድሞ በፍ/ቤት ፍቃድ በተዘጋው መዝገብ ላይ ቀርበው በነበሩ ማስረጃዎች  መሠረት ውሳኔ የሚሰጥበት አይደለም፡፡

አመልካቾች ለዚህ ችሎት ባቀረቡት ክርክር አስቀድሞ ቀርቦ በነበረው እና ውሳኔ ሊሰጥበት ሲል ዓቃቤሕግ ባዘጋው የክስ መዝገብ ክስ የቀረበበት መሬት የአመልካቾች መሆኑ ተረጋግጧል፤ የስር ፍ/ቤት አስቀድሞ የተዘጋውን መዝገብ እና የተጣራበትን ሪፖርት በትዕዛዝ አስቀርቦ ማየት ሲገባው ይህ ሳይደረግ ውሳኔ መሰጠቱ አግባብ አይደለም በማለት የሚከራከሩ ቢሆንም አስቀድሞ ቀርቦ የነበረው ክስ በፍ/ቤት ፍቃድ የተተወ በመሆኑ እና ተጠሪ ባቀረበው አዲስ ክስ መነሻነት በግራቀኝ ተከራካሪ ወገኖች

እና በፍ/ቤቱ ትዕዛዝ መሠረት የቀረቡ ማስረጃዎች ተመርምረው እና ተመዝነው ውሳኔ የሚሰጥበት ከመሆኑ አኳያ አመልካቾች በዚህ አግባብ ያቀረቡት ክርክር ተቀባይነት ያለው አይደለም፡፡

በሌላ በኩል የሰበር አጣሪው ችሎት ሊጣራ ይገባዋል በማለት የያዘው ነጥብ አስቀድሞ ቀርቦ የነበረው ክስ በከሳሽ ጥያቄ ከተዘጋ በኋላ በድጋሚ በቀረበው ክስ ጉዳዩ ተጣርቶ እንዲቀርብ በተሰጠው ትዕዛዝ የመሬት አስተዳደር በ18/02/09 የላከው ሪፖርት ሳይመዘን የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ሊመዘን የሚገባው ማስረጃ በተዘጋው መዝገብ የቀረበው ነው በማለት ተጣርቶ የቀረበውን ሪፖርት ሳይመዘን የማለፉን አግባብነት ለማጣራት በሚል ቢሆንም የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ውሳኔ የሰጠው በፍ/ቤት ፍቃድ በተተወው መዝገብ ላይ ቀርቦ የነበረውን ማስረጃ መሠረት በማድረግ ሳይሆን የመሬት መጠኑን አስመልክቶ ክሱ ተሻሽሎ ከመቅረቡ በፊት ቀርቦ የነበረውን ማስረጃ መሠረት በማድረግ በመሆኑ ውሳኔው በአግባቡ የተሰጠ ነው ከሚባል በቀር የተፈጸመ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስሕተት አላገኘንበትም፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

## ውሳኔ

1. በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 63639 ሰኔ 29 ቀን 2010 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 348/1 መሠረተ ጸንቷል፡፡
2. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪ ግራቀኙ የየራሣቸውን ይቻሉ፡፡
3. ነሐሴ 03 ቀን 2010 ዓ.ም በመዝገቡ የተሰጠው የዕግድ ትዕዛዝ ተነስቷል፡፡ ይጻፍ

- መዝገቡ ውሳኔ ስላገኘ ተዘግቷል፡፡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ብ/ም

የመ/ቁ 165616

ህዳር 26 ቀን 2012 ዓ/ም

ዳኞች፡- እትመት አሰፋ

ጳውሎስ ኦርሺሶ

ፀሐይ መንክር

መላኩ ካሳዬ

እስቲበል አንዱዓለም

አመልካች፡- አቶ ፈለቀ ታደሰ ቀርበዋል፡፡

ተጠሪዎች፡- 1. አቶ ሣሙኤል ሱሊቶ በሌሉበት፡፡

2. ወ/ሮ አየለች አቤቦ ወኪል አቶ ተካልኝ ጴጥሮስ ቀርበዋል፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ ላይ የቀረበው ጉዳይ የከተማ የመኖሪያ ቤት መስሪያ የምሪት ቦታ ይገባኛል ክርክርን የሚመለከት ነው፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው የደቡብ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት በፍ/ር/ ሰበር መ/ቁ/10579 ላይ ነሐሴ 17/2010 ዓ.ም በዋለው ችሎት የስር ፍርድ ቤቶችን ውሳኔ በማፅናት የሰጠው የመጨረሻ ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ነው በማለት ለማስለወጥ ነው፡፡

ክርክሩ የተጀመረው የአሁን አንደኛ ተጠሪ በሆሳዕና ከተማ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ህዳር 06/2009 ዓም የአሁን አመልካችን 1ኛ ተከሳሽ፤ ሆሳዕና ከተማ ማዘጋጃ ቤትን እና የሻቾ ዱና ክፍለ ከተማ ማዘጋጃ ቤትን እንደቅደም ተከተላቸው 2ኛ እና 3ኛ ተከሳሾች በማድረግ አሻሽለው ባቀረቡት የክስ አቤቱታ ነው፡፡ የክሱ ይዘት በአጭሩ በሆሳዕና ከተማ ከ1997-1999 በተደረገ የመኖሪያ ቤት መስሪያ ቦታ ሽንሽና በሻቾ ዱና ክፍለ ከተማ በሻቾ ዱና ቀበሌ ባለወልድ ሳይት ዕጣ ቁጥር 57 የሆነ እና አዋሳኙ በክሱ ዝርዝር የተጠቀሰው ቦታ የደረሳቸው መሆኑን፤ በዚሁ ይዞታ ላይ 2ኛ እና 3ኛ ተከሳሽ የሆኑት

አስተዳደር ክፍሎች ለአሁን አመልካች በመወገን ቦታውን ደርበው የሰጧቸው መሆኑን በመግለፅ ይዞታው የ1ኛ ተጠሪ/ከሳሽ/ ነው ተብሎ በቦታው ላይ ካርታ እንዲሰጣቸው ዳኝነት የሚጠይቅ ነው፡፡

ጉዳዩ በክርክር ላይ እያለ የአሁን 2ኛ ተጠሪ በጣልቃ ገብነት ቀርበው ግራ ቀኙ የሚከራከሩበት ይዞታ በህጋዊ መንገድ አግኝተው ቤት ሰርተውበት ይዘው የሚገኙ መሆኑን ገልፀው ተከራክረዋል፡፡ ጉዳዩ የቀረበለት ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክር እና ማስረጃ ከሰማ በኋላ ግራ ቀኙ የሚከራከሩበት ይዞታ ከሳሽ ለነበሩት የአሁን 1ኛ ተጠሪ በህጋዊ መንገድ የተሸነሸነ ስለመሆኑ ማረጋገጡን በምክንያትነት ጠቅሶ የአሁን 2ኛ ተጠሪ በይዞታው ላይ የሰሩትን ቤት አፍርሰው ይዞታውን ለ1ኛ ተጠሪ እንዲያስረክቡ እና አስተዳደር ክፍሉም በቦታው ላይ የይዞታ ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ሰርቶ እንዲሰጣቸው ሲል ወስኗል፡፡

በዚሁ ውሳኔ ላይ የአሁን አመልካች እና 2ኛ ተጠሪ በተናጠል ለሀዲያ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በተለያየ መዝገብ ላይ ይግባኝ አቅርበዋል፡፡ አመልካች ለዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ያቀረቡት ይግባኝ በመ/ቁ/17602 ላይ የካቲት 21/2010 ዓ.ም የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ ፀንቶ ከዚያ በኋላ በየደረጃው ባሉት ፍርድ ቤቶች ቅሬታቸው ተቀባይነት ባለማግኘቱ በዚህ መዝገብ ላይ ለሰበር ቀርቧል፡፡ በሌላ በኩል የአሁን 2ኛ ተጠሪ ለዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ያቀረቡት ይግባኝ በመ/ቁ/17696 ላይ ተስተናግዶ የካቲት 09/2010 ዓ.ም በዋለው ችሎት የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ ተሽሮ ክርክር በተነሳበት ይዞታ ላይ የተሻለ መብት ያላቸው የአሁን 2ኛ ተጠሪ ናቸው በማለት ተወስኗል፡፡ በዚህ ውሳኔ ላይ የአሁን 1ኛ ተጠሪ እስከዚህ ሰበር ችሎት ድረስ አቤቱታ አቅርበው በሰ/መ/ቁ/165588 ላይ ህዳር 27/2011 ዓ.ም በዋለው ችሎት ቅሬታው ለሰበር ክርክር አያበቃም ተብሎ ውድቅ የተደረገ መሆኑን ለመገንዘብ ተችሏል፡፡ የአሁን አመልካች በዚህ መዝገብ ላይ ህዳር 12/2011 ዓ.ም ፅፈው ባቀረቡት የሰበር ቅሬታ በስር ፍርድ ቤቶች ተፈፅሟል ያሉትን መሰረታዊ የህግ ስህተት ጠቅሰው በዚህ ችሎት እንዲታረምላቸው ጠይቀዋል፡፡

የቀረበው አቤቱታ ተመርምሮ ክርክር ባስነሳው ይዞታ ላይ ለአሁን አመልካች ካርኒ በቅድሚያ የተቆረጠ ለመሆኑ ተረጋግጦ እያለ ይዞታውን እንዲያስረክቡ የተወሰነበት አግባብ ከመሰረታዊ የማስረጃ ምዘና መርሆ አኳያ በዚህ ሰበር ችሎት ሊመረመር የሚገባ መሆኑ በመታመኑ ተጠሪዎች መልስ እንዲሰጡበት ታዟል ግራ ቀኙ የፅሁፍ ክርክር እንዲለዋወጡ ተደርጓል፡፡ በዚሁ መሰረት አንደኛ ተጠሪ የፍርድ ቤቱ መጥሪያ ደርሷቸው መልስ ባለማቅረባቸው መብታቸው የታለፈ ሲሆን 2ኛ ተጠሪ ጥር 03/2011 ዓ.ም የተፃፈ መልስ እንዲሁም አመልካች ጥር 24/2011 ዓ.ም የተፃፈ የመልስ መልስ በማቅረብ ተከራክረዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ ይዘት ጠቅለል ባለ መልኩ ከላይ የተመለከተውን ሲመስል ችሎቱም ጉዳዩን መርምሯል፡፡ በዚሁ መሰረት በስር ፍርድ ቤቶች የነበረውን የክርክር አመራር እና ውጤቱ

ክርክር በተነሳበት ይዞታ ላይ በዚሁ ሰበር ችሎት በሰ/መ/ቁ/165588 ላይ በተሰጠው ውሳኔ ላይ የሚያመጣው ለውጥ በቅድሚያ ሊፈተሽ የሚገባው መሆኑ ታምኗል፡፡

ከጉዳዩ አመጣጥ መረዳት እንደሚቻለው የሆሳዕና ከተማ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በሰጠው ውሳኔ ላይ የአሁን አመልካች እና 2ኛ ተጠሪ በተናጠል ይግባኝ ለሀዲያ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርበው ፍርድ ቤቱ በሁለት የተለያዩ መዝገቦች ላይ አከራክሮ ወስኗል፡፡ የአሁን አመልካች ይግባኝ ባቀረበበት መዝገብ ላይ በመልስ ሰጪነት የተቆጠሩት የአሁን ተጠሪዎች ሲሆኑ የአሁን 2ኛ ተጠሪ ይግባኝ ባሉበት መዝገብ ላይ ደግሞ መልስ ሰጪ የነበሩት የአሁን 1ኛ ተጠሪ ናቸው፡፡

አንድን ክርክር በመጀመሪያ ደረጃ ሲሰማ በነበረ ፍርድ ቤት በከሳሽነትም ሆነ በተከሳሽነት ቁጥራቸው ከአንድ በላይ የሆኑ ተከራካሪዎች በቀረቡበት መዝገብ ላይ በሚሰጥ ውሳኔ ላይ አንዱ ተከራካሪ በጠቅላላው ውሳኔ ላይ ይግባኝ ማለት የሚችል መሆኑን እና በዚህ ዓይነት ሁኔታ በይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት የሚሰጠው ውሳኔ ይግባኝ ባላቀረቡት ተከራካሪዎች ላይም የሚፀናባቸው ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁጥር 331 ድንጋጌ ያስገነዝባል፡፡ ችግሩ እያንዳንዱ ተከራካሪ ወገን በተናጠል ይግባኝ ያቀረበ እንደሆነ ነው፡፡

እንደዚህ ዓይነት ሁኔታ ሲያጋጥም በአንድ ጉዳይ ላይ የተለያየ ውሳኔ ሊሰጥ የሚችልበት እድል እንዳይፈጠር ፍርድ ቤቶች ከፍተኛ ጥንቃቄ ሊያደርጉ እንደሚገባ ይታመናል፡፡ ከዚህ ጋር ተያይዞ በአንድ በይግባኝም ሆነ በሰበር ችሎት በቀረበ ጉዳይ ላይ በስር ፍርድቤቶች በርካታ ተከራካሪዎች የነበሩ መሆኑ መዝገቡ የሚያሳይ ከሆነ ሌሎች በመዝገቡ ላይ ያልቀረቡት ቀድሞ የክርክሩ አካል የነበሩት አካላት በሌላ መዝገብ ላይ ቀርበው ከሆነ ተገቢ ማጣራት እና ክትትል ተደርጎ መዝገቦቹ ተጣምረው እንዲታዩ ማድረግ በዚህ ሰበር ችሎትም ጭምር በአሰራር የዳበረ የሙግት አመራር ልምድ በመሆኑ በየደረጃው ያሉ ፍርድ ቤቶች መሰል አሰራር ሊከተሉ ይገባል፡፡

አሁን በቀረበው ጉዳይ የሀዲያ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በይግባኝ በቀረበለት ጉዳይ በስር ፍርድ ቤት ተከራካሪ የነበሩት ሁለት አካላት ተቀራራቢ በሆነ የመዝገብ ቁጥር ላይ በተናጠል ይግባኝ አቅርበው እያለ ፍርድ ቤቱ ሁለቱን መዝገቦች አጣምሮ መወሰን ሲገባው በቀናት ልዩነት በአንደኛው መዝገብ ላይ የስር ፍርድ ቤትን ውሳኔ በመሻር በሌላኛው ላይ ደግሞ በማፅናት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ ይህ ከላይ ከተጠቀሰው የዳኝነት ሙግት አመራር ሥርዓት አንፃር አግባብ ያልሆነ እና የሚነቀፍ ተግባር ነው፡፡

ያም ሆኖ ግድፈቱ ቀጥሎ በነበረው ክርክር በተሰጠው ውሳኔ ላይ የሚኖረው ተፅዕኖ ስለመኖሩ ለመለየት በሰር ፍርድ ቤት ክርክር ወቅት በፍሬ ነገር ደረጃ የተረጋገጠውን እና ያንን መሰረት በማድረግ የተሰጡትን ውሳኔዎች ይዘት በጥንቃቄ መፈተሹ ተገቢ ይሆናል፡፡

በዚሁ መሰረት ይግባኝ ሰሚው የሀዲያ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት የስር ፍርድ ቤት ውሳኔን በሻረበት የመ/ቁ/17602 ላይ ክርክር የተነሳበትን ይዞታ የአሁን 2ኛ ተጠሪ ከ2005 ዓ.ም ጀምሮ ይዘው ሁለት ክፍል ቤት ሰርተውበት እየኖሩበት ለመሆኑ በስር ፍርድ ቤት ክርክር ወቅት በፍሬ ነገር ደረጃ የተረጋገጠ መሆኑን፤ በአንፃሩ ሌላው ተከራካሪ ወገን ከይዞታው ጋር በተያያዘ የምሪት ካርኒ እና እጣ የደረሳቸው ለመሆኑ አስረጂ የሚሆኑትን ሰነዶች አቅርበው የሚከራከሩ መሆኑን፤ ከዚህ አኳያ በኢ.ፌ.ዴ.ሪ. ህገ መንግስት መሰረት መሬት የመንግስት እና የህዝብ ንብረት በመሆኑ በመሬት ላይ የይዞታ መብት አለን ከሚለው ይልቅ ይዞታውን በእጁ አድርጎ ንብረት ያፈራበት ሰው የተሻለ መብት ያለው ስለመሆኑ በዚህ ሰበር ችሎት በሰ/መ/ቁ/105125 ላይ የተሰጠውን አስገዳጅ የህግ ትርጉም በዋቢነት ጠቅሶ ይዞታው ለአሁን 2ኛ ተጠሪ ይገባል ማለቱን እና ይኸው ውሳኔ እዚህ ሰበር ችሎት ደርሶ በሰ/መ/ቁ/165588 ላይ የፀና መሆኑን ለመገንዘብ ተችሏል፡፡

ክርክር የተነሳበትን ይዞታ በተመለከተ በዚህ መዝገብ ላይ ተከራካሪ የሆኑት ሶስቱም አካላት የይገባኛል ክርክር ባቀረቡበት ሁኔታ በፍሬ ነገር ደረጃ ይዞታውን በተጨባጭ በእጃቸው አድርገው ንብረት አፍርተዉበት ያሉት 2ኛ ተጠሪ መሆናቸው ከተረጋገጠ ይኸው ሰበር ችሎት በሰ/መ/ቁ/105125 ላይ ከሰጠው አስገዳጅ የህግ ትርጉም አኳያ በውጤት ደረጃ የስር ፍርድ ቤት ውሳኔን የሚያስለውጥ አይደለም፡፡ በመሆኑም ምንም እንኳን የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ጉዳዩን የመራበት ሁኔታ ከሙግት አመራር ሥነ ሥርዓት አኳያ የሚነቀፍ ቢሆንም የሥነ ሥርዓት ግድፈቱ በውሳኔው ይዘት እና ውጤት ላይ የሚያመጣው ለውጥ አለመኖሩ የተረጋገጠ በመሆኑ እና ግድፈቱ አመልካችን ያሳጣው መሰረታዊ መብት ባለመኖሩ መሰረታዊ የሚባል ስህተት ሆኖ አልተገኘም፡፡ በመሆኑም ተከታዩ ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

## ው ሳ ኔ

የደቡብ ብሔሮች ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት በፍ/ር/ ሰበር መ/ቁ/10579 ላይ ነሐሴ 17/2010 ዓ.ም በዋለው ችሎት የስር ፍርድ ቤቶችን ውሳኔ በማፅናት የሰጠው የመጨረሻ ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህግ ቁጥር 348(1) መሰረት ፀንቷል፡፡

## ት ዕ ዛ ዝ

1. የዚህን ሰበር ችሎት ክርክር ወጪ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡
2. መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ሰ/ጥ

የሰ/መ/ቁ. 168094

ታህሳስ22 ቀን 2012 ዓ.ም

ዳኞች፡- እትመት አሠፋ

ጳውሎስ ኦርሺሶ

ፀሐይ መንክር

መላኩ ካሣዬ

እስቲበል አንዱዓለም

አመልካች፡- አቶ ምስጋናው አሰጌ

ተጠሪ፡- 1ኛ አቶ አይናዲስ አሰጌ

2ኛ አቶ በልስቲ አይናዲስ አሰጌ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍ ር ድ**

ይህ የሰበር መዝገብ ተከፍቶ ሊቀርብ የቻለው የአሁን አመልካች በተጠሪዎች ላይ በአማራ ክልል የደጋ ዳሞት ወረዳ ፍ/ቤት ተጠሪዎች በውርስ ያገኘሁት መሬቴን ቀምተው ቤት የሰሩበት በመሆኑ ቤቱን አፍርሰው መሬቴን እንደያስረክቡ ይወሰንልኝ ብለው ባቀረቡት ክስ በወረዳ ፍ/ቤት የተሰጠው ውሣኔ በይግባኝ ከፀና በኋላ በክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ተሽሮ በይርጋ አይታገድም የተባለውንም መሬት አስመልክቶ በ10 ዓመት ይርጋ ይታገዳል በማለት የተሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት በመሆኑ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ ሲሉ አመልካች አቤቱታ በማቅረባቸው ነው፡፡

በወረዳ ፍ/ቤቱ ቀርቦ የነበረው ክስ በአጭሩ በዳሞት ጽዩን ቀበሌ ውስጥ 1ኛ/ በምስራቅ ዋሌ በሰሜን መዋጮ በደቡብ አለሙ ወልዲያ ጉጥ አማጋው 1 ጥማድ መሬት፣ 2ኛ በምዕራብ ዋሌ በሰሜን ዋሌ በደቡብ ዋሌ በወልዲያ ጉጥ ዋሌ 1 ጥማድ መሬት፣3ኛ በምዕራብ ሞላ በሰሜን አለሙ በደቡብ አይናዲስ በወልዲያ ጉድ ጉርድ 2 ጥማድ መሬት በሚች አባቴ አቶ አሰጌ መንግሥቱ አጥብቸ አስታምሜ ጡሬ የቀበርኩት ሥለሆነ እኔም በዚሁ ፍ/ቤት ህጋዊ የውርስ ማረጋገጫ ወራሽነቴን አረጋግጨ የያዝኩትን ተከሣሾች የቀሙኝ እና ቤት የሠሩብኝ በመሆኑ ቤቱን አፍርሰው እንዲያስረክቡኝ ይወሰንልኝ ሲሉ ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡

ተከሣሾች በበኩላቸው የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ያቀረቡ ሲሆን፣ ሟች በስሙ የተቆጠረለት መሬት ሲሆን እኛም የወረስነው ነገር የሌለ በመሆኑ ልንጠየቅ አይገባም፣ መሬቱን በ1996 ዓ.ም የመሬት ማረጋገጫ ደብተር በኋላም አረንጋዴ ደብተር አስመዝግቤ የያዝኩት እንጂ የሟችን መሬት በውርስ የያዝነው ነገር የለም፣ መሬቱን ከያዝነውም 15 ዓመት በላይ ነው በመሆኑም በ10 ዓመት ይርጋ ቀሪ ሊሆን ይገባል፣ መቃወሚያው ከታለፈም ክስ የቀረበበት የውርስ መሬት የሟች አቶ አሰጌ መንግሥቱ መሬት ሳይሆን የኛ ይዞታ ስለሆነ እና ከያዝነውም ከ15 ዓመት በላይ በመሆኑ ከሳሽ ያወጣው ውርስ እንዲታይልን እና የውርስ መሬት ለመጠየቅ ስለማይችል መዝገቡ ይዘጋልን ሲሉ መልሳቸውን አቅርበዋል፡፡

ፍ/ቤቱም የሚያከራክረው መሬት የማን ነው? ከመቼ ጀምሮ ተከሣሾች ያዙት ክሱ በይርጋ ቀሪ ሊሆን ይገባል አይገባም ?ተከሣሾች መሬቱን ሊለቁ ይገባል ወይስ አይገባም? የሚሉ ሰፊ ጭብጦችን ከመሰረተ በኋላ የግራ ቀኙን ምስክሮች ሰምቷል፡፡

የአካባቢ ገ/መ/አስ/ግንባታ/አጠ//ጽ/ቤትን ክርክር ስላስነሳው ይዞታ ጠይቆ ምላሽ ያገኘ እና የሰው ምስክሮችን ቃል በማገናዘብ መርምሮ ክርክር ያስነሳው ይዞታ ቀደም ሲል የአ/ይ አሰጌ መንግሥቱ እና እ/ይ እቴነሽ አለምነህ ሆኖ የተደለደለው በ1989ዓ.ም.መሆኑን፣ አ/ይ አሰጌ መንግሥቱ በ1994 ዓ.ም. መሞታቸውን፣ ከሣሽ እና 1ኛ ተከሣሽ የሟችን መሬት ተካፍለው ይዘውት የነበረ እና የያዙትም በክሱ ተራ ቁጥር 3 የተጠቀሰውን 1ኛ ተከሣሽ መያዙን 2ኛ እና 3ኛ ተራ ቁጥር ላይ የተጠቀሱትን ሁለት መሬቶች ከሣሽ የያዘና በ2008 ዓ.ም. ከጥር ወር ወዲህ የቀሙት መሆኑን፣ 2ኛ ተከሣሽ የቤተሰብ አባል ያልነበረ ከወላጅ አባቱ ከ1ኛ ተከሣሽ ጋር ያደገ መሆኑን ተከሣሽ የያዘውን መሬት ከ1994 ዓ.ም. ጀምሮ ይዞት ቤት ሰርቶበት እስከዛሬ ድረስ ይዞት የሚገኝ መሆኑን ሌሎችን ግን ተከሣሾች ይዘውት የማያውቁ እና የከሣሽ ድርሻ ሆኖ እያለ በ2008 ከጥር ወዲህ የቀሙት መሆኑ በምስክሮች የተረጋገጠ በመሆኑ ብይን ሰጥቶ በክሱ ተራ ቁጥር 3 ስር የተጠቀሰውን መሬት በተመለከተ 1ኛ ተከሣሽ ከ10 ዓመት በላይ ይዞት ስለሚገኝ በ3 ዓመት ይርጋ ይታገዳል፣ በተ.ቁ. 1ኛ እና 2ኛ ላይ የተመለከቱትን ይዞታዎች ግን ተከሣሾች በጉልበት ከከሣሽ የቀሙት መሆኑ ስለተረጋገጠ ለቅቀው እንዲያስረክቡ ሲል ወስኗል፡፡

የስር 1ኛ ተከሣሽ የወረዳ ፍ/ቤቱን ውሣኔ በመቃወም ይግባኝ ለምዕራብ ጐጃም ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ቢያቀርቡም ይግባኛቸው ተቀባይነት አላገኘም፡፡

ለአማራ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የአሁን ተጠሪ የሰበር አቤቱታ ያቀረቡ ሲሆን ሰበር ሰሚ ችሎቱ ግራ ቀኙን አስቀርቦ እና ጉዳዩን መርምሮ የወረዳ ፍ/ቤቱ በይርጋ አይታገድም በማለት የስር ተከሣሾች ለቅቀው እንዲያስረክቡ ሲል የሰጠውን የውሣኔ ክፍል እና ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤትም የሰጠውን የማጽናት ውሣኔ በመሻር በአዋሣኝ የተጠቀሱት ሁለት መሬቶችም ጭምር በ10 ዓመት ይርጋ ይታገዳል ሲል ወስኗል፡፡

አመልካች ከላይ በተጠቀሰው የሰበር ውሣኔ ላይ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት በመሆኑ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ ሲሉ ታህሳስ 2 ቀን 2011 ዓ.ም የተፃፈ 5 ገጽ የሰበር አቤቱታ አቅርበዋል፡፡ ይዘቱም በአጭሩ፡- በስር ፍ/ቤት ተጠሪዎች ምንም አይነት ማስረጃ ያላቀረቡ እና ምስክሮችም ያላሰሙ፣ ምስክር የተሰማውም የእኔ ሆኖ እያለ እና በፍርዱም ላይ በገለፀበት ሁኔታ ተጠሪዎች በስር ወረዳ ፍ/ቤት ሁለት የመከላከያ ምስክር እንዳሰሙ አድርገው አቤቱታ ስላቀረቡ በሀሰት ተዘጋጅቶ የቀረበ ውሣኔን ተመልክቶ የሰጠው ፍርድ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ነው፣

የወረዳ ፍ/ቤቱን ውሣኔ የእጅ ጽሁፍ ኮፒ ሆኖ የሚታይ ባለመሆኑ መዝገቡን አስቀርቦ መርምሮ መወሰን ሲገባው ወይም በእጁ የሚገኘውን አስቀርቦ መመርምር ሲገባው ይህን ሳያደርግ መወሰኑ ተገቢ አለመሆኑን እና በሁለቱ ውሣኔዎች መካከል ያለው ልዩነት ናቸው ያሏቸውን 9 ነጥቦችን ለይተው በአቤቱታው ላይ በማሳየት የስር ሰበር ሰሚ ችሎት ውሣኔ በሃሰተኛ ውሣኔ ላይ መሠረት ተደርጐ የተሰጠ በመሆኑ ሊሻር ይገባዋል ሲሉ በጥብቅ ጠይቀዋል፡፡

አቤቱታው በአጣሪው ተመርምሮ ተጠሪን ያስቀርባል ተብሎ ጭብጥ በመያዙ መነሻነት መዝገቡ ለችሎቱ ሊቀርብ ችሏል፡፡

ተጠሪዎችም አቤቱታው ከማስቀረቢያ ነጥቡ ጋር እንዲደርሳቸው ተደርጐ መጋቢት 24 ቀን 2011 ዓ.ም. በአንድነት የተፃፈ መልስ አቅርበዋል፡፡ አመልካችም የመልስ መልስ አቅርቦ ከመዝገቡ ጋር ተያይዞ የግራ ቀኙ የጽሁፍ ልውውጥ በዚሁ ተጠናቋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ከላይ የተመለከተውን ሲመስል እኛም የቀረበውን አቤቱታ ከስር ፍ/ቤቶች ውሣኔዎች እና ከመልስ እና የመልስ መልሱ እንዲሁም ከጉዳዩ ጋር አግባብነት ካላቸው የህጉ ድንጋጌዎች ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡

እንደመረመርነውም አመልካች በወረዳ ፍ/ቤቱ አቅርበውት የነበረው ክስ ከላይ እንደተመለከትነው በተለያዩ ቦታዎች አዋሳኙን ጠቅሶ የተለያየ መጠን ያላቸው መሬቶችን ተጠሪዎች ቀምተውኛል፣ በመሆኑም የሰሩትን ቤት አፍርሰው መሬቴን ይልቀቁልኝ የሚል ክስ ያቀረቡ ሲሆን፣ ተጠሪዎችም ክርክሩ በይርጋ ይታገዳል በማለት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ያነሱና በፍሬ ጉዳዩም ላይ ሙሉ መልሳቸውን አቅርበዋል፡፡ ፍ/ቤቱም ከውሣኔው መረዳት እንደተቻለው በአመልካች በኩል የቀረቡ ምስክሮችን የሰማ እና በተጠሪዎች በኩል ግን በመልሳቸው ላይ የማስረጃ ዝርዝር ያላቀረቡ በመሆኑ ምስክር ያለመስማቱን አትቷል፡፡

ወረዳ ፍ/ቤቱም ጉዳዩን መርምሮ መሬቱን እንዲለቁ አዋሳኞችን ጠቅሶ የወሰነ ሲሆን ይህ ውሣኔ በይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት በይግባኝ ያልተለወጠ ቢሆንም ተጠሪዎች ለክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት የሰበር

አቤቱታ በማቅረባቸው መነሻነት ውሣኔው ተሸሮ የቀረበው ጉዳይ በይርጋ የሚታገድ በመሆኑ ሊለቁና ሊያስረክቡ አይገባም ተብሎ ተወስኗል፡፡

አመልካች አጥብቀው የሚከራከሩት ለክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ከአቤቱታው ጋር የቀረበለት የወረዳ ፍ/ቤት ውሣኔ የተለወጠ እና ሃሰተኛ ውሣኔ በመሆኑ መዝገቡን አስቀርቦ እና መርምሮ ሊወስን ሲገባው ይህን ሳያደርግ በመወሰኑ ስህተት ፈጽሟል በሚል ነው፡፡

የአመልካች አቤቱታ የስር ፍ/ቤቶች መዛግብት ሳይቀርብ እና ሳይመረመር ሊወሰን የማይችል መሆኑን ችሎቱ ስለተረዳው የደጋዳሞት ወረዳ ፍ/ቤት እና የይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት መዛግብትን ከሚገኙበት እንዲቀርቡ ትዕዛዝ ተሰጥቶ መዛግብቱ ቀርበው ከጉዳዩ ጋር አብሮ ተመርምሯል፡፡

በዚህ መሠረት በፍሬ ጉዳዩ ላይ ተመርምሮ ውሣኔ ከመሰጠቱ በፊት የወረዳ ፍ/ቤት የሰጠው ውሣኔ ትክክል ግልባጭ ለክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ቀርቦለት የውሣኔውን ትክክለኛነት አረጋግጦ ስለመወሰን አለመወሰኑ መመልከት ተገቢ ሆኖ አግኝተነው በጭብጥነት በመያዝ መርምረናል፡፡

በመሆኑም የስር የደጋ ዳሞት ወረዳ ፍ/ቤት መ/ቁ/ 12826/09 በ7/9/2009 ዓ.ም.በዋለው ችሎት የሰጠው ውሣኔ በችሎቱ ዳኛ የእጅ ጽሁፍ የተፃፈ እና 5 ገጽ ያለው ሲሆን፣ በዚሁ መዝገብ ውስጥ በአሁን ተጠሪዎች በ12/04/2009 ዓ.ም. በእጅ የተፃፈ 2 ገጽ መልስ ተያይዟል፡፡ ከዚህ መልስ ጋር የተያያዘ የማስረጃ ዝርዝር መግለጫ የሌለ መሆኑንም ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

የወረዳ ፍ/ቤቱ የፍርድ ሃተታውን ሲጽፍ በአሁን አመልካች በኩል የቀረቡ ምስክሮችን የሰማ እና ከተጠሪዎች መልስ ጋር የተያያዘ የማስረጃ ዝርዝር የሌለ በመሆኑ ምስክር ያለመስማቱን ገልጿል፡፡

ይህ በእንዲህ እንዳለ የክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ/ 68465 ታህሳስ 3 ቀን 2011 ዓ.ም. በዋለው ችሎት በሰጠው ፍርድ ገጽ 2 10ኛ መስመስር ላይ " የግራ ቀኙን ምስክሮች ሰምቶ-----" የሚል ሃረግ ያለ መሆኑን ከውሣኔው መረዳት ተችሏል፡፡

እንዲሁም በገጽ 3 ላይ 8ኛ መስመር "------ የአመልካች ሁለቱ እንዲሁም የተጠሪው 1ኛ እና 3ኛ ምስክሮች ------" በማለት አትቷል፡፡

የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት በስር ፍ/ቤት ተከሣሾች በነበሩት ግለሰቦች ማስረጃ ዝርዝር ያልቀረበ እና ምስክርም ያልተሰማ መሆኑ በውሣኔው ላይ ተገልጾ እያለ እንዴት የክልሉ ሰበር ተጠሪዎች እንዴት ምስክር ሳያሰሙ ምስክር እንዳሰሙ ተደርጐ ውሣኔ ተሰጠላቸው? የሚለውን ለማጣራት የሰበሩ ክርክር ሲከናወን ለአሁን አመልካች በስር ፍ/ቤት ተወስኗል ሲሉ የስር ሰበር አመልካቾች አቅርበውት የነበረው ውሣኔ ኮፒን መመልከት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ ቀርቦልን ስንመለከተው የወረዳ ፍ/ቤቱ ዳኛ ጽሁፍ ያለመሆኑን፣ የገፁም ብዛት የሚለያይ፣ ከውሣኔው ውስጥ ከላይ ለመግለጽ እንደተሞከረው ምስክር

አቅርበው አሰምተው የተወሰነ መሆኑን የሚያሳዩ ሃረጐች የገቡበት እና የተለያዩ ልዩነቶች ያሉበት መሆኑን ተመልክተናል፡፡

ችሎቱ ይህን ተመልክቶ ብቻ ያበቃ ሳይሆን የአሁን 2ኛ ተጠሪ የአመልካች ተወካይ በተገኙበት በችሎት በዳኞች ለቀረበለት ጥያቄ ሲመልስ በስር ወረዳ ፍ/ቤት ራሱ ከ1ኛ ተጠሪ አባቱ ጋር እየቀረበ እንደተከራከረ፣ የውሣኔ ግልባጭም በኮፒ ከችሎቱ እንደወሰደ የፍ/ቤቱም ማህተም ያረፈበት መሆኑን፣ ባቀረቡት መልስ ላይ የማስረጃ ዝርዝር እንዳቀረቡ እና በዚሁ መሠረት 3 ምስክሮችን አቅርበው ማሰማታቸውን ፣ የምስክሮችን ስም ጭምር ጠቅሶ እንደገለፀ ለችሎቱ ያስረዳ ሲሆን፣ በችሎቱ በስር ፍ/ቤት መዝገብ ላይ ቀርቦ የነበረውን መልሳቸውን እንዲያይና እንዲያረጋግጥ ሲጠየቅም ይህን ያቀረብን አይመስለኝም በማለት ለችሎቱ ተናግሯል፡፡

አንድ ሙግት በተከራካሪ ወገኖች መካከል መከናወን ያለበት በቅን ልቦና እና ማስረጃን በማቅረብ መሆን ያለበት ሲሆን፣ ይግባኝ የሚባልበት በሆነ ጊዜም በስር ፍ/ቤት የተከናወነው ክርክር እውነትነቱን ይዞ መቀጠል ያለበት መሆኑ የክርክር አመራር ስነ ስርአት መሆኑ ይታወቃል፡፡

ተከራካሪ ወገኖች የሚያቀርቡትን ክርክር በቅን ልቦና እና እውነትነት ባለው ማስረጃ የማይከራከሩ በሆነ ጊዜ ፍ/ቤቶች የቀረበላቸው ነገር እውነት መሆኑን ባልተረዱ እና ፍፁም ድብቅ በሆነባቸው ጊዜ እውነት ላይ ለመድረስ የሚያደርጉት ጥረት እንደተጠበቀ ሆኖ በቀረበላቸው ማስረጃም እውነተኛውን ውሣኔ እንዳይሰጡ የሚገድባቸው ከመሆኑም በላይ እውነትን የያዙ ሰዎች በሀሰተኛ ማስረጃ እና በሃሰተኛ ተከራካሪዎች ቅን ልቦና መጉደል ምክንያት እውነትን የያዙ ሰዎች ላይ ያልተገባ ፍርድ እንዲሰጡ የሚያደርግ በመሆኑ ፍትህ እንዲዛባ፣ ማህበረሰቡም በፍ/ቤቶች ላይ እምነት እንዳይኖረው የሚያደረግ አደገኛ አካሄድን የሚፈጥር መሆኑ እሙን ነው፡፡

ወደ ቀረበው ጉዳይ ስንመለስ የስር ወረዳ ፍ/ቤት የሰጠው ውሣኔ እንዲለወጥ እና በክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ውሣኔው እንዲሻር መነሻ የሆነው ለሰበር ሰሚ ችሎቱ ከአቤቱታው ጋር የቀረበለት በተጠሪዎች የተቀየረው እና ምስክር ሳያሰሙ ምስክር እንዳሰሙ ተደርጐ የተለወጠው ውሣኔ በመሆኑ የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት እውነተኛውን ክርክር እንዳይመለከት እና ተገቢውን ውሣኔ እንዳይሰጥ ወይም በሌላ አነጋገር የተዛባ ውሣኔ እንዲሰጥ የተደረገ መሆኑን ለመመልከት ችለናል፡፡

የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት በስር ፍ/ቤት ተሰጥቶ የነበረው ትክክለኛ ውሣኔ ሳይበረዝ ሳይከለስ ቀርቦለት ቢሆን ኑሮ አሁን የደረሰበት መደምደሚያ ላይ ላይደርስ ይችል ይሆናል የሚል ግምት ያስነሳል፡፡ የአመልካችም ክርክር ከዚህ የራቀ አይደለም፡፡

አመልካች የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ላይ መልስ ሲያቀርቡ አሁን ያነሱትን መከራከሪያ ሊያነሱ ያልቻሉት ደግሞ ይህን ያወቁት የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ውሣኔ ተገልብጦ ከተሰጣቸው በኋላ

በመሆኑ ተጠሪዎች በፈፀሙት የተንኮል አሰራር አመልካችን ብቻ ሳይሆን ፍ/ቤቱንም እንዳጭበረበሩና ተገቢ ያልሆነ ፍትህ ለማግኘት ሲሉ የወረዳ ፍ/ቤቱን ውሣኔ ሃረጐች ለእነሱ በሚያመች መልኩ እንደቀየሩ ባደረግነው ማጣራት ተረጋግጧል፡፡

በመሆኑም የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ውሣኔ የሰጠው የወረዳ ፍ/ቤቱ ትክክለኛ ውሣኔ ሳይደርሰው እና የተለወጠ ውሣኔ ደርሶት መሆኑን ያረጋገጥን በመሆኑ በዚህ የተለወጠ ውሣኔ ምክንያት የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት የሰጠው ውሣኔ እውነተኛ ፍርድን መሠረት በማድረግ የተሰጠ እና እውነት ላይ ለመድረስ በሚያዳግት ውሣኔ ላይ ተመስርቶ በመሆኑ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ስላገኘነው ሊሻር የሚገባው ነው ብለን ተከታዩን ወስነናል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. የአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግሥት ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ/ 68465 ታህሳስ 3 ቀን 2011 ዓ.ም. በዋለው ችሎት የሰጠው ውሣኔ በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ /ቁ/ 348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡
2. የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት በውሣኔ የዘጋውን መዝገብ እንደገና በማንቀሳቀስ የደጋ ዳሞት ወረዳ ፍ/ቤት መ/ቁ/ 12826 የሆነውን መዝገብ በማስቀረብ እና በዚህ መዝገብ ላይ የተሰጠውን እውነተኛ የዳኛ ውሣኔ በመመልከት ከቀረበለት አቤቱታ ጋር በማገናዘብ እና የአሁን አመልካችን በተገቢው ውሣኔ ላይ መልስ በማሰጠት ትክክለኛ ነው ያለውን ውሣኔ እንዲሰጥበት በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ/ 341/1/ መሠረት ጉዳዩን መልሰን ልከንለታል፡፡
3. በዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት በግራ ቀኙ የወጣ ወጪ ካለ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

## ትዕዛዝ

1. የአሁን ተጠሪዎች በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በደጋዳሞት ወረዳ ፍ/ቤት በመ.ቁ 12826/2009 በቀን 07/09/09 ዓ.ም የተሰጠ ነው ተብሎ የቀረበው ውሳኔ በፍ/ቤቱ ያልተሰጠ ለመሆኑ ይህ ችሎት የስር ፍ/ቤት መዝገብን አስቀርቦ ያረጋገጠ በመሆኑ የክልሉ ፖሊስ በተጠሪዎች እንዲሁም ከጉዳዩ ጋር ተያያዥነት ባላቸው አካላት ላይ ተገቢውን የወንጀል ምርምራ እንዲያከናውን ታዟል፤ ይጻፍ፡፡
2. የአራዳ ፖሊስ 2ኛ ተጠሪን ለክልሉ ፖሊሰ እንዲያስረክብ ታዟል፤ ይጻፍ
3. በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የምዕራብ ጎጃም ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት የመ.ቁ 69774 የሆነው መዝገብ እና የደጋ ዳሞት ወረዳ ፍ/ቤት የመ.ቁ 01012826/2009 የሆነው መዝገብ በመጡበት አኳኋን ወደ መጡበት ይመለሱ፡፡

- መዝገቡ ተዘግቷል፤ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

የሰ.መ.ቁ 165775

የካቲት 29 ቀን 2011ዓ.ም

**ዳኞች፡-**ሰለሞን አረዳ

ብርሃኑ አመነዉ

በዕዉቀት በላይ

ሃይሉ ነጋሽ

እትመት አሠፋ

**አመልካች:-** የአቶ ተሾመ ጎርፌ ወራሽ መቅደስ ተሾመ

**ተጠሪ፡-** ወ/ሮ ፈሰሰች ወንድማገኝ ወራሽ ጣሰው ተሾመ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል።

## ፍርድ

ለሰበር አቤቱታው መነሻ የሆነው ጉዳይ አፈጻጸምን የሚመለከት ነው። በሥር ፍ/ቤት በተደረገው ክርክር የአሁን ተጠሪ የፍርድ ባለመብት የአሁን አመልካች ደግሞ የፍርድ ባለዕዳ በመሆን ተከራክረዋል። የአሁን አመልካች ለስር አፈጻጸም ችሎቱ ባቀረቡት አቤቱታ የፍርድ አፈጻጸም ዳይሬክቶሬት በመጀመሪያው አማራጭ በዓይነት የማካፈል ስራ ሳይሰራ ንብረቱን በሐራጅ እንዲሸጥ ማድረጉ አግባብ ስላልሆነ የሀራጅ ሽያጩ ታግዶ በዓይነት እንድንካፈል ትዕዛዝ ይሰጥላቸው ዘንድ ዳኝነት ጠይቀዋል። አፈጻጸሙን የመራው ፍርድ ቤት አመልካች ያቀረቡትን አቤቱታ መርምሮ ፍ/ቤቱ ከሰጠው ውሳኔ እና ትዕዛዝ ውጪ እየተደረገ ያለ የአፈጻጸም ሂደት ስለመኖሩ የቀረበ ማስረጃ የሌለ በመሆኑ ሐራጁ የሚታገድበት የሕግ አግባብ የለም በማለት የአመልካችን አቤቱታ ውድቅ አድርጎታል። አመልካች ይህን ትዕዛዘ በመቃወም ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አቤቱታ ያቀረቡ ቢሆንም በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 337 መሠረት አቤቱታቸውውድቅ ተደርጓል። የሰበር አቤቱታው የቀረበው ይህንትዕዛዝ በመቃወም ነው።

የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሠረታዊ ይዘትም፡- አመልካች እና ተጠሪ የውርስ ሐብት በሆነው ንብረት ላይ እኩል ድርሻና መብት አለን፤ ክፍፍሉን በተመለከተ ወደ ሌሎች አማራጭ መሔድ የሚቻለው ፍርድ ያረፈበት ቤት መካፈል የማይችል ከሆነ ነው፤ ቤቱንማካፈል እየቻለ በሐራጅ ቢሸጥ የአመልካችን መብት ይጎዳል፤ የክፍለከተማው የይዞታ አስተዳደር የሽግግር ጊዜ አገልግሎት ፕሮጀክት ጽ/ቤት በቀን

12/01/10 ዓ.ም ጽፎ በላከው ማስረጃ በመመሪያ ቁጥር 12/2006 መሠረት መካፈል የሚችል መሆኑን ገልጾ ሳለ በዚሁ አግባብ ክፍፍሉ መፈጸም ሲገባው የመጨረሻውን አማራጭ በመጠቀም በሐራጅ እንዲሸጥ መደረጉ ተገቢ አይደለም፤ ቤቱ በሐራጅ ቢሸጥ ዋጋው በጣም አነስተኛ ስለሚሆን እና በቤቱ እንዳልገለገል የሚያደርገኝ በመሆኑ ቤቱ በሐራጅ መሸጡ ቀርቶ በዓይነት እንድካፈል ይወሰንልኝ የሚል ነው፡፡

የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ ቤቱ መካፈል መቻል አለመቻሉን በተመለከተ ከአፈጻጸም ዳይሬክቶሬቱ ለቀረበው ጥያቄ በመመሪያ ቁጥር 12/2006 መሠረት መካፈል ይችላል የሚለው ምላሽ ውጤቱ ባልታወቀበት ተጠቃሹ ቤት በጨረታ እንዲሸጥ መወሰኑ ዋናውን ውሳኔ ያገናዘበ መሆን አለመሆኑን ለማጣራት ሲባል ጉዳዩ በዚህ ችሎት እንዲታይ ተደርጓል፡፡ ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎም ግራቀኙ በጽሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

የተጠሪ መልስ ይዘት በአጭሩ፡- ቤቱን በዓይነት ለማካፈል የማይቻል መሆኑን የክፍለከተማው የሰነድ አልባ ይዞታዎች ዴስክ ቦታው ድረስ መሐንዲስ በመላክ አረጋግጧል፤ ቤቱን በዓይነት እኩል መካፈል የማይቻለው በአንድ በኩል ያለው ቤት በብረት እና በብሎኬት በጥራት የተሰራ ትልቅ ቪላ ቤት ሲሆን በሌላ አቅጣጫ ያሉት ቤቶቸ ደግሞ በእንጨት እና በጭቃ የተሰሩ ያረጁና እየፈራረሱ ያሉ ቤቶች በመሆናቸው ነው፤ ይህንኑ ለመግለጽም የሰነድ አልባ ይዞታዎች የተጠቀመው አገላለጽ ቤቶቹ የተሰሩበት ቁስ ወይም ማቴሪያል የሚል ነው፤ ቤቱ በዓይነት መካፈል የማይችል እና ግራቀኞችን በስምምነት መካፈል ያልቻልን በመሆኑ በሐራጅ እንዲሸጥ ታዟል፤ መመሪያ ቁጥር 12/2006 የይዞታ አሰጣጥ መመሪያ እንጂ የውርስ ሀብት የሆነ የቤት ክፍፍል መመሪያ አይደለም፤ ቤቱ በሐራጅ ከተሸጠበት ከነሐሴ 28 ቀን 2010 ዓ.ም ጀምሮ በውሳኔው ለአመልካች እንዲከፈላቸው የተወሰነው 9 በመቶ ወለድ በተጠሪ ላይ እየቆጠረብኝ በመሆኑ አመልካች አላግባብ ያቀረቡት አቤቱታ ውድቅ ሊደረግ ይገባል የሚል ነው፡፡ አመልካችም የሰበር አቤቱታቸውን በማጠናከር የመልስ መልስ ሰጥተዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ  በአጭሩ ከላይ የተገለጸው ነው፡፡ እኛም እንዲጣራ የተያዘውን አከራካሪውን ጭብጥ ከግራቀኙ ክርክር፤ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸው ሕጎች  ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው መርምረነዋል፡፡

አከራካሪ የሆነው ቤት ግማሽ ድርሻ የአቶ ተሾመ ጎርፌ መሆኑ እና ግማሹ ድርሻ ደግሞ የሟች ወ/ሮ ተናኜ ተሾመ በመሆኑ የሟች ወ/ሮ ተናኜ ተሾመ ግማሽ ድርሻ ወራሻቸው ለሆኑት የወ/ሮ ፈሰሰች ወንድማገኝሁ ድርሻ ነው በማለት የተወሰነ መሆኑን፤ በመዝገቡ ተከራካሪ የሆኑት አቶ ተሾመ ጎርፌ እና ወ/ሮ ፈሰሰች ወንድማገኝሁ ከዚህ ዓለም በሞት በመለየታቸው በአመልካች በኩል መቅደስ ተሾመ በተጠሪ በኩል ደግሞ ጣሰው ተሾመ ተተኪ ወራሽ በመሆን ክርክሩ የቀጠለ መሆኑን የሥር መዝገብ የሚያሳይ ሲሆን የአሁን አመልካች አፈጻጸሙን ለመራው ፍ/ቤት አቤቱታ ያቀረቡት በመጀመሪያው

አማራጭ መሠረት በዓይነት የማካፈል ስራ ሳይሰራ ቤቱ በሐራጅ እንዲሸጥ መደረጉ አግባብ ስላልሆነ የሐራጅ ሽያጩ ታግዶ በዓይነት እንድንካፈል ይደረግልኝ በሚል ነው፡፡

አመልካች በዚህ አግባብ አቤቱታ ያቀረቡ ቢሆንም የፍርድ አፈጻጸም ዳይሬክቶሬት ቤቱ በዓይነት መካፈል የሚችል መሆን አለመሆኑን ተጣርቶ እንዲቀርብለት ለክፍለከተማው የይዞታ አስተዳደር የሽግግር ጊዜ አገልግሎት ፕሮጀክት ጽ/ቤት በሰጠው ትዕዛዝ መሠረት ተጠቃሹ አካል በቀን 12/01/10 ዓ.ም በጻፈው ምላሽ ካርታው ወጪ ያልሆነ ሰነድ ስለሆነ በሰነድ አልባ ዴስክ እንጂ በኛ በኩል ለማካፈል የማንችል መሆኑን እየገለጽን ነገርግን በመመሪያ ቁጥር 12/2006 መሠረት መካፈል የሚችል መሆኑን እንገልጻለን የሚል ምላሽ የሰጠ መሆኑን፣ ይህንኑ ምላሽ መነሻ በማድረግ የአፈጻጸም ዳይሬክቶሬቱ ክፍለከተማው የይዞታ አስተዳደር የሽግግር ጊዜ አገልግሎት ፕሮጀክት ጽ/ቤት የሰነድ አልባ ፕሮጀክት ዴስክ ቤቱን በዓይነት እንዲያካፍል በማለት ትዕዛዝ የሰጠ መሆኑን፣ ትዕዛዙ የተላለፈለት የክፍለከተማው ሰነድ አልባ ዴስክም በቀን 21/06/2010 ለዳይሬክቶሬቱ በሰጠው ምላሽ ቦታው ድረስ በመገኘት ለመካፈል በተደረገው ጥረት መሠረት ቤቱን በዓይነት ለማካፈል የተሰራበት ቁስ / ማቴርያል / ስለሚለያይ ለማካፈል ተቸግረናል በማለት ምላሽ የሰጠ መሆኑን፣ የአፈጻጸም ዳይሬክቶሬም በግራቀኙ መካከል ስምምነት የሌለ መሆኑን በመግለጽ ቤቱ በብር 32,1,279.13 የጨረታ መነሻ ዋጋ በሐራጅ እንዲሸጥ በማለት ትዕዛዝ የሰጠ መሆኑን፣ በዚሁ መሠረት አከራካሪው ቤት ለጨረታ የቀርበ እና አመልካች እና ተጠሪ በቀረቡት ተጫራቾች ጨረታው እንዲቀጥል በማለት በፊርማቸው አረጋግጠው ወ/ት ራሔል ሞገስ የተባሉ ግለሰብ በብር 6,850,000 /ስድስት ሚልዬን ስምንት መቶ ሀምሳ ሺህ ብር / ጨረታውን ያሸነፉ እና ገንዘቡን ገቢ ያደረጉ መሆኑን የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የአፈጻጸም መዝገብ እና የፍርድ አፈጻጸም ዳይሬክቶሬት የአፈጻጸም መዝገብ አስቀርበን በማየት መገንዘብ ችለናል፡፡

በመሠረቱ የውርስ ሐብት ክፍያን በሚመለከት በተቻለ መጠን በዓይነት የሚከፋፈል ስለመሆኑ፣ በዓይነት መካፈል የማይችል ከሆነ እና በባለመብቶቹ መካከል ስምምነት ከታጣ ንብረቱ በሐራጅ ተሸጦ ክፍፍሉ የሚፈጸም ስለመሆኑ የውርስ ክፍፍለን አስመልክቶ ከተደነገጉት የፍትሐብሔር ሕጉ ድንጋጌዎች መገንዘብ ይቻላል፡፡ በሌላ በኩል የሽያጭ ሥርዓት ተገቢ ባልሆነ መንገድ ወይም በማጭበርበር ተፈጽሟል በማለት እንዲፈርስ ወይም እንዲታገድ ማመልከቻ ማቅረብየሚቻል መሆኑን የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 445 ድንጋጌ ያስገነዝባል፡፡

በያዝነው ጉዳይ አመልካች እና ተጠሪ የየራሳቸውን መስመር በመከተል የንብረቱ ባለቤቶች የነበሩት ተተኪ ወራሾች ሲሆኑ የክፍለከተማው የይዞታ አስተዳደር የሽግግር ጊዜ አገልግሎት ፕሮጀክት ጽ/ቤት ካርታው ወጪ ያልሆነ ሰነድ ስለሆነ በሰነድ አልባ ዴስክ እንጂ በኛ በኩል ለማካፈል የማንችል መሆኑን እየገለጽን ነገርግን በመመሪያ ቁጥር 12/2006 መሠረት መካፈል የሚችል መሆኑን እንገልጻለን የሚል ምላሽ በመስጠቱ የአፈጻጸም ዳይሬክቶሬቱ ክፍለከተማው የይዞታ አስተዳደር የሽግግር ጊዜ አገልግሎት

ፕሮጀክት ጽ/ቤት የሰነድ አልባ ፕሮጀክት ዴስክ ቤቱን በዓይነት እንዲያካፍል በማለት ትዕዛዝ በሰጠው ትዕዛዝ መሠረት ተጠቃሹ አካል ቦታው ድረስ በመገኘት ለማካፈል በተደረገው ጥረት መሠረት ቤቱን በዓይነት ለማካፈል የተሰራበት ቁስ / ማቴርያል / ስለሚለያይ ለማካፈል የተቸገረ መሆኑን በመግለጽ ምላሽ ሰጥቷል፡፡ ይህንኑ ተከትሎ ቤቱን በዓይነት ለመካፈል በግራቀኙ መካከል ስምምነት የሌለ በመሆኑ ቤቱ በሐራጅ እንዲሸጥ ትዕዛዝ ተሰጥቶ አመልካች እና ተጠሪ በቀረቡት ተጫራቾች ጨረታው እንዲቀጥል በማለት በፊርማቸው አረጋግጠው ወ/ት ራሔል ሞገስ የተባሉ ግለሰብ በብር 6,850,000 /ስድስት ሚልዬን ስምንት መቶ ሀምሳ ሺህ ብር / ጨረታውን አሸንፈው ገንዘቡን ገቢ አድርገዋል፡፡

አመልካች ለዚህ ችሎት ባቀረቡት ክርክር ክፍፍሉን በተመለከተ ወደ ሌሎች አማራጭ መሔድ የሚቻለው ፍርድ ያረፈበት ቤት መካፈል የማይችል ከሆነ ነው፤ ቤቱ መካፈል እየቻለ በሐራጅ ቢሸጥ መብቴን ይጎዳል በማለት የሚከራከሩ ቢሆንም የክፍለከተማው የይዞታ አስተዳደር የሽግግር ጊዜ አገልግሎት ፕሮጀክት ጽ/ቤት ካርታው ወጪ ያልሆነ ሰነድ ስለሆነ በሰነድ አልባ ዴስክ እንጂ በኛ በኩል ለማካፈል የማንችል መሆኑን እየገለጽን ነገርግን በመመሪያ ቁጥር 12/2006 መሠረት መካፈል የሚችል መሆኑን እንገልጻለን የሚል ምላሽ የሰጠ ከመሆኑ አኳያ፤ ይህንኑ ምላሽ መነሻ በማድረግ የአፈጻጸም ዳይሬክቶሬቱ ክፍለከተማው የይዞታ አስተዳደር የሽግግር ጊዜ አገልግሎት ፕሮጀክት ጽ/ቤት የሰነድ አልባ ፕሮጀክት ዴስክ ቤቱን በዓይነት እንዲያካፍል በማለት ትዕዛዝ የሰጠ ከመሆኑ አኳያ፤ ትዕዛዙ የተላለፈለት የክፍለ ከተማው ሰነድ አልባ ዴስክም ቦታው ድረስ በመገኘት ለመካፈል በተደረገው ጥረት መሠረት ቤቱን በዓይነት ለማካፈል የተሰራበት ቁስ / ማቴርያል / ስለሚለያይ ለማካፈል የተቸገረ መሆኑን በመግለጽ ምላሽ የሰጠ ከመሆኑ አኳያ እና የአፈጻጸም ዳይሬክቶሬቱም በግራቀኙ መካከል ስምምነት እንደሌለ በማረጋገጥ ቤቱ በሐራጅ እንዲሸጥ ትዕዛዝ የሰጠ እና አመልካች እና ተጠሪ በቀረቡት ተጫራቾች ሐራጁ እንዲቀጥል በፊርማቸው አረጋግጠው ቤቱ በብር 6,850,000 /ስድስት ሚልዬን ስምንት መቶ ሀምሳ ሺህ ብር / የተሸጠ ከመሆኑ እና በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 445 በተገለጸው አግባብ የሐራጁ የሽያጭ ሥርዓት ተገቢ ባልሆነ መንገድ ወይም በማጭበርበር ተፈጽሟል ለማለት የሚያስችል ሁኔታ ያልተገኘ ከመሆኑ አኳያ የስር ፍርድ ቤቶች የአመልካችን አቤቱታ ውድቅ በማድረግ በሰጡት ውሳኔ ላይ የተፈጸመ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ሥሕተት አላገኘንበትም፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

**ውሳኔ**

1. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ.ቁ 250862 ሐምሌ 24 ቀን 2010 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ እና ይህንን ትዕዛዝ በማጽናት የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 219963 ሕዳር 10 ቀን 2011 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥሕ/ቁ 348/1 መሠረት ጸንቷል፡፡

2. ሕዳር 20 ቀን 2011 ዓ.ም በመዝገቡ የተሰጠው የዕግድ ትዕዛዝ ተነስቷል፡፡ ይጻፍ

3. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪ ግራቀኙ የየራሣቸውን ይቻሉ፡፡

**ትዕዛዝ**

-የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት መ.ቁ 250862 የሆነው መዝገብ እና የፌዴራል ፍርድ አፈጻጸም ዳይሬክቶሬት መ.ቁ 29549 የሆነው መዝገብ ወደ መጣበት ይመለስ

-መዝገቡ ውሳኔ ስላገኘ ተዘግቷል፡፡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

ሳ/ፀ የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት ፡፡

**የሰ/መ/ቁ** - 163166

**ቀን** - 30/09/2011

**ዳኞች**፡- ተኽሊት ይመሰል

ተፈሪ ገብሩ (ዶ/ር)

ቀነዓ ቂጣታ

ተሾመ ሽፈራዉ

ፀሐይ መንክር

**አመልካች**፡- አቶ ሙስጠፋ መሐመድ

**ተጠሪ**፡- አቶ ናስር ኢሳ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍ ር ድ**

ለዚህ ፍርድ መነሻ የሆነዉ ጉዳይ የተጀመረዉ በሆሮ ወረዳ ዞን ፍርድ ቤት ሲሆን፣ አመልካች ከሳሽ ተጠሪ ደግሞ ተከሳሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡ የአመልካች ክስ ይዘትም በአጭሩ፡- አባቴ አቶ መሐመድ አባያሲን በሻምቡ ከተማ 01 እና 02 ቀበሌ ዉስጥ ያለዉን ንብረቶቹን እንዲጠብቁ እና እንዲያከራዩ ለተከሳሽ ዉክልና ሰጥተዉ በ2004 ዓ.ም ከሞት የተለዩ ሲሆን፣ ከአባታችን ሞት በኋላም የአባቴ ወራሾች ለተከሳሽ ተመሳሳይ ዉክልና ሰጥተናል፤ ይሁንና ተከሳሽ የከተማዉን አስተዳደር በማሳሳት በሻምቡ ከተማ ቀበሌ 02 ዉስጥ የሚገኘዉ እና አዋሳኞቹ በክሱ የተመለከተዉን እና በዉርስ የሚተላለፍልኝን ሁለት ክፍል የንግድ ቤት በስሙ በማድረግ እየተጠቀመበት የሚገኝ በመሆኑ ቤቱን እንዲያስረክበኝ ይወሰንልኝ የሚል ነዉ፡፡

ተጠሪ ለክሱ በሰጠዉ መልስ፡- ከሳሽ አባቱ ከሞተ ከ 9 ዓመት በኋላ የወራሽነት መብት አለኝ በሚል ያቀረበዉ ክስ በፍትሐብሔር ህጉ አንቀጽ 1000(1) መሰረት በይርጋ ይታገዳል የሚል የመጀመሪያ መቃወሚያ በማስቀደም ፍሬነገሩን በተመለከተም የከሳሽ አባት በህይወት እያሉ ቤቱን ለባንክ አስይዘዉ የተበደሩትን ገንዘብ ባለመመለሳቸዉ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ቤቱን ለመሸጥ ያወጣዉን ጨረታ ተወዳድሬ ከባንክ የገዛሁት የግሌ ነዉ በማለት ተከራክሯል፡፡

ጉዳዩ በመጀመሪያ የቀረበለት የወረዳዉ ፍርድ ቤት ከግራ ቀኝ በዚህ መልኩ የቀረበዉን ክርክር እና ማስረጃ ከሰማ በኋላ የአመልካች አባት ከዚህ ዓለም በሞት ከተለዩበት ከ 8 ዓመት በኋላ አመልካች ያቀረበዉ ክስ በፍትሐብሔር ህጉ አንቀጽ 1000(1) መሰረት በይርጋ ቀሪ ነዉ በማለት ክሱን ዉድቅ በማድረግ ወስኗል። አመልካች ይህን ዉሳኔ ባለመቀበል ለሆሮ ጉዱሩ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ያቀረበ ሲሆን፣ ይግባኝ ሰሚዉ ችሎት መዝገቡን አስቀርቦ ከመረመረ በኋላ ክሱ በይርጋ የማይታገድ መሆኑን ጠቅሶ የወረዳዉ ፍርድ ቤት በዚህ ረገድ የሰጠዉን ዉሳኔ የተቸ ሲሆን፣ በሌላ በኩል ተጠሪ ለክርክሩ መነሻ የሆነዉን ቤት ከባንክ ገዝቶ የያዘ ስለመሆኑ ተረጋግጧል በሚል የወረዳዉን ፍርድ ቤት ዉሳኔ በዉጤት ደረጃ በማጽናት ወስኗል። አመልካች ይህን ዉሳኔ ባለመቀበል ለኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ያቀረበዉ አቤቱታም ተቀባይነት አላገኘም።

አመልካች በቀን 23/12/2010 ዓ.ም ተዘጋጅቶ በቀረበ አራት ገጽ የሰበር አቤቱታ በሆሮ ወረዳ ፍርድ ቤት እንዲሁም በሆሮ ጉዱሩ ወለጋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ተሰጥቶ በኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በትዕዛዝ የፀናዉ ዉሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ የሚልባቸዉን ምክንያቶች በመዘርዘር ታርሞ ይወሰንለት ዘንድ ዳኝነት ጠይቋል። አቤቱታዉ ተመርምሮ ያስቀርባል በመባሉም ተጠሪ በተደረገለት ጥሪ መሠረት ቀርቦ ግራ ቀኝ ክርክራቸዉን በጽሑፍ ተለዋዉጠዋል።

ከስር ጀምሮ የክርክሩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለ መልኩ ሲታይ ከላይ የተመለከተዉን ሲመስል፣ ይህ ችሎትም ለሰበር አቤቱታዉ ምክንያት የሆነዉን ዉሳኔ ከግራ ቀኝ ክርክር እና ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸዉ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መዝገቡን እንደሚከተለዉ መርምሮታል። መዝገቡን መርምረን የወረዳዉ ፍርድ ቤት የአመልካችን ክስ ዉድቅ በማድረግ ለሰጠዉ ዉሳኔ መሠረት ያደረገዉ ክሱ በፍትሐብሔር ህጉ አንቀጽ 1000(1) መሰረት በሦስት ዓመት ይርጋ የሚታገድ መሆኑን ነዉ። ከላይ እንደተገለጸዉ ከፍተኛዉ ፍርድ ቤት ክሱ በይርጋ የማይታገድ መሆኑን ጠቅሶ ግን የስር ፍርድ ቤት የአመልካችን ክስ ዉድቅ በማድረግ የሰጠዉን ዉሳኔ በዉጤት ደረጃ ሊያፀና የቻለዉ የወረዳዉ ፍርድ ቤት ቤቱ የማን እንደሆነ የከተማዉን አስተዳደር ጠይቆ ያረጋገጠ በመሆኑ ጉዳዩን ወደ ስር ፍርድ መመለስ ላላስፈላጊ ወጪ እና ድካም ከሚዳርግ ዉጪ ሌላ ፋይዳ የሌለዉ መሆኑን ነዉ። በእኛ በኩል እንደተመለከትነዉ የወረዳዉ ፍርድ ቤት ከፍሬ ነገር ክርክር ጋር በተያያዘ በግራ ቀኝ የቀረቡትን ክርክሮች እና ማስረጃዎች ይዘት በዉሳኔዉ ያሰፈረ ቢሆንም የቀረቡትን የሰዉ ማስረጃዎች ከግራ ቀኝ ክርክር አንፃር በመመዘን እና በመመርመር የሰጠዉ ዉሳኔ የለም። የፍ/ብ/ሥ/ሥርዓት ህጉ አንቀጽ 341 ክስን በመጀመሪያ መቃወሚያ ዉድቅ በማድረግ የተሰጠን ዉሳኔ ይግባኝ ሰሚዉ ሽሮ የስር ፍርድ ቤት በፍሬ ጉዳዩ ላይ ተገቢዉን እንዲወስን ሊመልስ እንደሚገባ ይደነግጋል። የክርክሩን ፍሬ ነገር በተመለከተ ዉሳኔ መስጠት ማለት ደግሞ ማስረጃዎችን ማሰባሰብ ብቻ እንዳልሆነ እና የቀረቡትን ማስረጃዎች ከግራ ቀኝ ክርክር አንፃር በማገናዘብ፣ መርምሮ እና መዝኖ በፍሬ ነገር ረገድ ድምዳሜ ላይ

መድረስን እንደሚያካትት ግልጽ ነዉ፡፡ የህጉ አንቀጽ 341 ድንጋጌ አፈፃፀም ማስረጃን መዝኖ ፍሬ ነገርን ከማረጋገጥ ጋር በተያያዘ ሊፈጠር የሚችለዉን ስህተት ለማሳረም ይግባኝ የማቅረብ መብትን ከማስፋት አንፃር ታይቶ ተፈፃሚነት ሊኖረዉ ይገባል፡፡

ከዚህ አንፃር ሲታይ የሆሮ ጉዱሩ ወለጋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት የወረዳዉ ፍርድ ቤት ክሱን በይርጋ ዉድቅ በማድረግ የሰጠዉን ዉሳኔ ማረሙ ተገቢ ሆኖ ግን ፍሬ ጉዳዩን በተመለከተ የግራ ቀኝን ክርክር ከቀረቡት የተለያዩ ማስረጃዎች እንዲሁም እንዳስፈላጊነቱ ተጨማሪ ማስረጃም ካለ እንዲቀርብ በማድረግ መርምሮ እና መዝኖ ተገቢዉን ዉሳኔ እንዲሰጥ በፍ/ብ/ሥ/ሥርዓት ህጉ አንቀጽ 341(1) መሰረት መመለስ ሲገባዉ ይህን ባለማድረግ ፍሬ ጉዳዩን በተመለከተ የሰጠዉ ዉሳኔ የዚህን ድንጋጌ ትክክለኛ አፈፃፀም መሰረት ያደረገ ባለመሆኑ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ ብለናል፡፡ በመሆኑም ተከታዩ ተወስኗል፡፡

## ዉ ሳ ኔ

1. የሆሮ ወረዳ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 19041 በቀን 01/10/09 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት የሰጠዉ ዉሳኔ፣ የሆሮ ጉዱሩ ወለጋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 21964 በቀን 14/05/2010 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት የሰጠዉ ዉሳኔ፣ እንዲሁም የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 283705 በቀን 28/09/2010 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት የሰጠዉ ዉሳኔ ተሽረዋል፡፡
2. የሆሮ ወረዳ ፍርድ ቤት የተዘጋዉን መዝገብ በማንቀሳቀስ ለክርክሩ መነሻ የሆነዉን ቤት ተጠሪ የያዘዉ ከአመልካች አባት እንዲሁም ከአመልካች በአደራ ነዉ ወይስ ከባንክ ገዝቶ ነዉ የሚለዉን ጭብጥ ከግራ ቀኝ ክርክር እና ማስረጃ እንዲሁም እንዳስፈላጊነቱ ተጨማሪ ማስረጃም ጭምር በማስቀረብ ከመረመረ በኋላ ተገቢዉን ዉሳኔ እንዲሰጥበት መዝገቡ በፍ/ብ/ሥ/ሥርዓት ህጉ አንቀጽ 341(1) መሠረት ተመልሶለታል፡፡
3. በዚህ ችሎት የተደረገዉ ክርክር ያስከተለዉን ወጪ እና ኪሳራ ግራ ቀኝ የየራሳቸዉን ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

መ/አ

የሰ/መ/ቁ.161736

ግንቦት29 ቀን 2011 ዓ.ም.

**ዳኞች-**፡ተኽሊት ይመስል

ተፈሪ ገብሩ (ዶ/ር)

ቀነአ ቂጣታ

ተሾመ ሽፈራው

ፀሐይ መንክር

**አመልካች** - አቶ ተጫነ ካሳ

**ተጠሪዎች** - 1ኛ. አቶ ባህረ ሀፍቱ

2ኛ. አቶ ሀጎስ ሀፍቱ

3ኛ. አቶ ወርቁ አዲሱ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

በዚህ መዝገብ የተያዘው ጉዳይ አቤቱታ ማሻሻልን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የጀመረው የአሁን አመልካች በ1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች ላይ በትግራይ ክልል ምዕራባዊ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሑመራ ምድብ ችሎት ባቀረቡት ክስ ነው፡፡

የሥር ፍርድ ቤቶች መዝገብ ግልባጭ እንደሚያሳየው የአሁን አመልካች 3ኛ ተጠሪ ለሆኑት አቶ ወርቁ አዲሱ ከሌሎች ተጠሪዎች ጋር በአንድ የውል ሰነድ ገንዘብ ስለሰጠኗቸው በ3ኛ ተከሳሽነት አካትቼ ክሱን አሻሽዬ ላቅርብ በማለት አቤቱታ አቅርበው ፍርድ ቤቱም ክሱ እንዲሻሻል ፈቅዷል፡፡ ነገር ግን አመልካች በ28/03/2010 ዓ.ም የተሻሻለ ክስ ሲያቀርቡ በአጭር ስርዓት እንዲታይ ቀርቦ የነበረውን የብድር ክስ ምክንያት በመቀየር ያላግባብ የመበልፀግ ክስ አድርገው አቅርበዋል፡፡ ፍርድ ቤቱ አመልካች አሻሽለው ያቀረቡትን ክስ ባለመቀበል በቀደመው የክስ ምክንያት 3ኛ ተከሳሽን ጨምረው የተሻሻለውን ክስ እንዲያቀርቡ በ18/05/2010 ዓ.ም በዋለው ችሎት ትዕዛዝ ሰጥቶ ቀጠሮ ለውጧል፡፡ ነገር ግን አመልካች ክሱን በማሻሻል አቅርቤያለሁ ከዚህ ውጪ ማሻሻል አልችልም፤ በቀደመው ክስ ክርክርም አልቀጥልም በማለታቸው ይህን ተከትሎ ፍርድ ቤቱ በአመልካች ጉድለት ለቀጠሮው ምክንያት የሆነው ጉዳይ አልተፈፀመም በማለት በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ 199(2) መሰረት መዝገቡ እንዲዘጋ ብይን ሰጥቷል፡፡

አመልካች ይህን በመቃወም ቅሬታቸውን ለትግራይ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ እና ሰበር ችሎቶች ቢያቀርቡም ተቀባይነት አላገኙም፡፡ የሰበር አቤቱታው ለዚህ ፍርድ ቤት የቀረበው በዚህ ነው፡፡

አመልካች ያቀረቡት የሰበር አቤቱታ በአጣሪ ችሎቱ ተመርምሮ አመልካች ክሳቸውን አሻሽለው እንዲያቀርቡ በምክንያትነት የጠቀሱት ተከራካሪ ወገንን ጨምሮ ለማቅረብ መሆኑንና በዚህም መነሻ ከተፈቀደ በኋላ አመልካች በከሰሱበት ጉዳይ ከህግ የመነጨ መብት ያላቸው መሆኑን ለማሳየት ይረዳ ዘንድ በክስ ምክንያታቸው ላይ ለውጥ አድርገው ማቅረባቸው ሲታወቅ በሃገራችን የሙግት አመራር ስርዓት ፍርድ ቤቶች በእራሳቸው አነሳሽነት ከሚጫወቱት ሚና እና ፍትህ ከማግኘት ህገ መንግስታዊ መብት አንጻር ታይቶ ጉዳዩ ሊስተናገድ ይገባል? ወይስ አስቀድሞ በተያዘው አቅጣጫ መሰረት አመልካች ፈጽመው ሊቀርቡ አልቻሉም በሚል በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 199(2) መሰረት ጉዳዩ በጅምሩ ሊቋጭ ይገባል? የሚለውን ለይቶ ለመወሰን እንዲቻል ጉዳዩ ለሰበር ሰሚ ችሎት እንዲቀርብና ተጠሪዎች መልስ እንዲሰጡበት ተደርጓል፡፡ በዚህ መሰረት ግራቀኙ ክርክራቸውን በጽሁፍ ተለዋውጠዋል፡፡

ከፍሲል ባጭሩ የገለጽነው የጉዳዩን አመጣጥ ነው፡፡ ለሰበር ችሎቱ የተያዘውን ጭብጥ ቅሬታ ከቀረበበት ብይን እና ተገቢነት ካላቸው የህጉ ድንጋጌዎች ጋር በማያያዝ እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

ከላይ እንደተገለፀው የሥር ፍርድ ቤት በአመልካች ጉድለት ለቀጠሮው ምክንያት የሆነው ጉዳይ አልተፈፀመም በማለት መዝገቡ እንዲዘጋ ብይን የሰጠው አስቀድሞ የቀረበው የብድር ክስ ምክንያት ሳይለወጥ 3ኛ ተከሳሽን ጨምረው የተሻሻለውን ክስ እንዲያቀርቡ ትዕዛዝ ሰጥቶ አመልካች በራሴ አሻሽዬ ካቀረብኩት ውጪ ክሱን ማሻሻል አልችልም በቀደመው ክስም ክርክሩን አልቀጥልም በማለታቸው ነው፡፡ የዚህን ፍርድ ቤት ውሳኔ የሚሻውም የሥር ፍርድ ቤት የተሻሻለውን ክስ ውድቅ ለማድረግ የሕግ መሠረት ነበረው? መዝገቡ መዘጋቱስ በአግባቡ ነው? አይደለም? የሚሉት ናቸው፡፡

ክሱ እንዲሻሻል በስር ፍርድ ቤት የተፈቀደበት ምክንያት 3ኛ ተጠሪ የሆኑት አቶ ወርቁ አዲሱ ከሌሎች ተጠሪዎች ጋር በአንድ የውል ሰነድ ገንዘብ ስለሰጡኋቸው በ3ኛ ተከሳሽነት አካትቼ ላቅርብ በማለት አመልካች አቤቱታ አቅርበው ፍርድ ቤቱም ስለተቀበለው መሆኑ በብይኑ ላይ ተመልክቷል፡፡ ይህን ተከትሎ አመልካች ባቀረቡት የተሻሻለ አቤቱታ ግን የብድሩን ክስ ወደ ያላግባብ የመበልፀግ ክስ ቀይረው አቅርበዋል፡፡ ፍርድ ቤቱ በቀደመው የክስ ምክንያት ተከሳሽ ጨምረው የተሻሻለውን ክስ እንዲያቀርቡ ቢያዝም ከዚህ ውጪ ማሻሻል እንደማይችሉ ገልፀዋል፡፡ ስለሆነም የክስ አቤቱታ ሲሻሻል ዳኝነት የተጠየቀበት የክሱ ምክንያት መለወጥ የሚቻል መሆን አለመሆኑን መመልከቱ ተገቢ ይሆናል፡፡ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 91(1) እንደተደነገገው ፍርድ ከመስጠቱ በፊት በማናቸውም ጊዜ ወይም ፍ/ቤቱ ተገቢ ሆኖ ካገኘው ተከራካሪዎቹ ወገኖች ክሳቸውን እንዲያሻሽሉና ክርክራቸውን እንዲለውጡ ሊፈቅድላቸው ይችላል፡፡ ስለሆነም የዚህ አይነት መብት ለተከራካሪዎቹ ወገኖች የሚሰጠው የክሱ መሻሻል ወይም የክርክሩ መለወጥ ነገሩን ይበልጥ የሚያብራራው ወይም ትክክለኛ ፍትህ ለመስጠት የሚረዳ ሆኖ በተገመተ ጊዜ ብቻ ነው፡፡

የእንግሊዘኛው ቅጅ፡-

"The court may at any time before judgment allow either party to alter or amend his pleading …………. and all such amendments shall be made as may be necessary for the purpose of determining the real questions in dispute" በማለት ይደነግጋል፡፡

ከድንጋጌው መገንዘብ እንደሚቻለው ተከራካሪው ክሱን ለማሻሻል ወይም ክርክሩን ለመለወጥ የሚችለው የክሱ መሻሻል ወይም የክርክሩ መለወጥ ክስ የቀረበበትን ጉዳይ ይበልጥ ግልጽ የሚያደርገው እንዲሁም ትክክለኛ ፍትህ ለመስጠት አስፈላጊ መሆኑ በፍርድ ቤቱ ሲታመንበት ብቻ ነው፡፡ ስለሆነም የክሱ መሻሻል ወይም የክርክሩ መለወጥ የሚፈቀድበት መሰረታዊ ማጠንጠኛ በግራ ቀኙ መካከል ያለውን ክርክር ለመወሰን አስፈላጊ የሚሆን (for the purpose of determining the real questions in dispute) መሆኑ ነው፡፡

በተያዘው ጉዳይ አመልካች በቀደመው ክሳቸው ዳኝነት የጠየቁት የብድር ገንዘብ እንዲመለስላቸው ሲሆን ክሱን ለማሻሻል በምክንያትነት የጠቀሱትም 3ኛ ተጠሪ የሆኑት አቶ ወርቁ አዲሱ ከሌሎች ተጠሪዎች ጋር በአንድ የውል ሰነድ ገንዘብ ስለወሰዱ በ3ኛ ተከሳሽነት ተካተው እንዲቀርቡ ለማድረግ ነው፡፡ ብድሩ ከተካደ በግራ ቀኙ መካከል አከራካሪ የሚሆነው ጉዳይ (the real questions in dispute) ብድር አለ? ወይስ የለም? የሚለው ነው፡፡ ስለሆነም የክሱ መሻሻል ወይም የክርክሩ መለወጥ ይህን (የብድሩን ጉዳይ) ይበልጥ የሚያብራራው ወይም ትክክለኛ ፍትህ ለመስጠት የሚረዳ ሊሆን ይገባል፡፡ ነገር ግን አመልካች አሻሽለው ባቀረቡት ክስ የብድር ክስ ምክንያቱን በመቀየር ያላግባብ የመበልፀግ ክስ አድርገው አቅርበዋል፡፡ ይህ ደግሞ ነገሩን ይበልጥ የሚያብራራው ወይም ትክክለኛ ፍትህ ለመስጠት የሚረዳ ነው የሚባልበት የህግ ምክንያት የለም፡፡

በመሆኑም በሃገራችን የሙግት አመራር ስርዓት አቤቱታ የሚሻሻለው ጉዳዩን ይበልጥ ለማብራራት ወይም ትክክለኛ ፍትህ ለመስጠት አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ብቻ ሲሆን አመልካች የብድሩን የክስ ምክንያት ቀይረው ያላግባብ በመበልፀግ ክስ ለመሟገት መቅረባቸው በሥነ ስርዓት ህጉ የተዘረጋውን የማሻሻያ ሥርዓት የተከተለ ባለመሆኑ የሥር ፍርድ ቤት የተሻሻለውን ክስ አለመቀበሉ የሚነቀፍ ሆኖ አላገኘነውም፡፡

በሌላ በኩል ክሱን እንዲያሻሽል የተፈቀደለት ወገን ይህንኑ ካላቀረበ ክሱን የማሻሻል ወይም ሙግቱን የመለወጥ መብቱ እንደሚቀርና የዚህም ውጤት በቀደመው ክስ ክርክሩን መቀጠል መሆኑን ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 91(2) ይዘት መገንዘብ ይቻላል፡፡ በተያዘው ጉዳይ አመልካች ክሱን በህጉ አግባብ ብቻ እንዲያሻሽሉ ተጠይቀው አሻሽለው ካቀረቡት ውጪ ማሻሻል እንደማይችሉና አስቀድመው ባቀረቡት ክስ ክርክሩን ለመቀጠል እንደማይፈልጉ መግለፃቸውን ተከትሎ ፍርድ ቤቱ በአመልካች ጉድለት መዝገቡን

መዝጋቱ በሥነ ሥርዓቱ አግባብ ጉዳዩን መምራቱን ከሚያሳይ በቀር የህግ ስህተት ፈጽሟል የሚያሰኘው አይደለም፡፡

የሰበር አጣሪ ችሎቱ የጠቀሰው ሌላው ምክንያት ፍርድ ቤቶች በራሳቸው አነሳሽነት የሚጫወቱት ሚና እና ፍትህ የማግኘት ህገ መንግስታዊ መብት ነው፡፡ ፍርድ ቤቶች በራሳቸው አነሳሽነት የሚጫወቱት ሚና ሊተገበር የሚችለው በሥነ ሥርዓት ህጉ አግባብ ሲሆን በህጉ በግልጽ ያልተደነገገ ሲሆን ተፈጥሯዊ የሆኑትን መርሆች (Principles of Natural Justice) መከተልም ተገቢ ነው፡፡ የዳኞች ክርክር የመምራት ሚና በሥነ ሥርዓት ህጉና ተፈጥሯዊ የሆኑ መርሆችን በመከተል የተወሰነ በመሆኑ ጉዳዩን በዚህ ስርዓት መምራት ፍትህ የማግኘት መብትን የሚያረጋግጥ ነው ከሚባል በቀር መብቱን የሚጥስ ነው የሚባልበት ምክንያት የለም፡፡

በአጠቃላይ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ጉዳዩን በህጉ አግባብ በመምራት ብይን የሰጠ በመሆኑና የበላይ ፍርድ ቤቶችም ይህን መቀበላቸው የሚነቀፍ ባለመሆኑ ተከታዩን ወስነናል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. በትግራይ ክልል የምዕራብ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሑመራ ምድብ ችሎት በመ/ቁ 14280 በ22/05/2010 ዓ.ም የሰጠው ብይን እንዲሁም የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁ 104354 በ17/08/2010 ዓ.ም እና የክልሉ ሰበር ችሎት በመ/ቁ 107559 በ25/10/2010 ዓ.ም የሰጡት ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 348(1) መሰረት ፀንቷል፡፡
2. ግራቀኙ ወገኖች በዚህ ፍ/ቤት ለተካሄደው ክርክር ወጪና ኪሣራ ይቻቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ወደመዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የሶስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

## የልዩነት ሀሳብ

እኛ ስማችን በተራ ቁጥር ሶስት እና አምስት ላይ የተጠቀስን ዳኞች በዚህ ጉዳይ የአብላጫ ድምጽ ከሰጠዉ ዉሳኔ በሚከተለዉ ምክንያት ተለይተን የልዩነት ሀሳብ አስቀምጠናል፡፡

ከሥር ፍ/ቤት ዉሳኔ ግልባጭ መገንዘብ እንደሚቻለዉ የአሁን አመልካች (የሥር ከሳሽ) መጀመሪያ ባቀረበዉ ክስ የብድር ዉል መሰረት በማድረግ የአሁን 1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች (የሥር 1ኛ እና 2ኛ ተከሳሾች) ገንዘብ እንዲከፍሉት ዳኝነት መጠየቃቸዉን ነዉ፡፡ ነገር ግን የአሁን አመልካች ክስ ለማሻሻል ባቀረበዉ ጥያቄ የአሁን 3ኛ ተጠሪ (የሥር 3ኛ ተከሳሽ) ይህን ገንዘብ ከሌሎች ተጠሪዎች ጋር የመክፈል ኃላፊነት እንዳለበት በመግለጽ እሱን አካትቶ ክሳቸዉን አሻሽለዉ ለማቅረብ ጠይቋል፡፡ የሥር ፍ/ቤትም የአሁን አመልካች ክሳቸዉን ለማሻሻል ያቀረቡትን ጥያቄ በመቀበል የተሻሻለዉን ክስ እንዲያቀርቡ

በ18/5/2010 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት በሰጠዉ ትዕዛዝ ፈቅዶለት ነበር፡፡ ነገር ግን ፍ/ቤቱ የአሁን አመልካች የተሻሻለዉን ክስ ባቀረበ ጊዜ የተሻሻለዉ ክስ ከቀደመዉ ክስ ጋር አንድ ስላልሆነ ተቀባይነት የለዉም በማለት አመልካች ከፈለገ በቀደመዉ ክስ እንዲቀጥል ትዕዛዝ ሲሰጥ፣ አመልካቹ በቀደመዉ ክስ መቀጠል እንደማይፈልግ በመግለጹ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.199 (1) መሰረት መዝገቡን መዝጋቱን የዉሳኔዉ ግልባጭ ያሳያል፡፡ ይህ ችሎት የአብላጫ ድምጽ በበኩሉ አመልካች አሻሽሎ ያቀረበዉ ክስ ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.91 (1) መሰረት ተቀባይነት የለዉም በማለት የሥር ፍ/ቤት ዉሳኔ በማጽናት ወስኗል፡፡

እኛ ይህን ጉዳይ እንደመረመርነዉ የሥር የከፍተኛ ፍ/ቤት የአሁን አመልካች የብድር ዉል መሰረት በማድረግ ገንዘብ እንዲከፈለዉ የአሁን 1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች ላይ ያቀረበዉን ክስ አሻሽለዉ የአሁን 3ኛ ተጠሪን አካትተዉ ገንዘቡን ተጠሪዎች እንዲከፍሉት ለመጠየቅ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.91 (1) መሰረት ያቀረበዉን ጥያቄ ተቀብሎ አመልካች የተሻሻለዉን ክስ እንዲያቀርብ ፈቅዶለታል፡፡ የሥር የከፍተኛ ፍ/ቤት በሰጠዉ ትዕዛዝ አመልካች ክሱን አሻሽሎ 3ኛ ተጠሪን አካትተዉ ገንዘብ እንዲከፈለዉ መጠየቅ እንደሚችል ከፈቀደ በኋላ ተሻሽሎ የቀረበዉ ክስ የክስ ምክንያት ከቀደመዉ ክስ ጋር አንድ ስላልሆነ ተቀባይነት የለዉም የሚልበት እና አንድ ጊዜ የፈቀደዉን መልሶ ትዕዛዙን በማንሳት የሚከለክልበት የህግ አግባብ የለም፡፡ የሥር የከፍተኛ ፍ/ቤት አመልካች የተሻሻለዉን ክስ ማቅረብ እንደሚችል ከፈቀደለበት በኋላ በራሱ ተነሳሽነት ይህን ትዕዛዝ በማንሳት የተሻሻለዉን ክስ አልቀበልም በማለት የራሱን ትዕዛዝ ከሕግ ዉጭ መልሶ የሚሽርበት የሕግ አግባብ ሊኖር አይችልም፡፡ ስለዚህ የሥር ፍ/ቤት የአሁን አመልካች ክሱን ለማሻሻል ያቀረበዉን ምክንያት ተቀብሎ መጀመሪያ ያቀረበዉን ክስ እንዲተዉ እና የተሻሻለ ክስ እንዲቀርብ ትዕዛዝ ከሰጠ በኋላ ተሻሽሎ የቀረበዉን ክስ ባለመቀበል አመልካች ከፈለገ በመጀመሪያዉ ክስ እንዲቀጥል የሚያደርግበት የሕግ አግባብ የለም፡፡

እንደሚታወቀዉ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.91 (1) እንደሚደነግገዉ ‹‹ፍርድ ከመሰጠቱ በፊት በማናቸዉም ጊዜ ወይም ፍርድ ቤቱ ተገቢ ሆኖ ካገኘዉ ተከራካሪዎቹ ወገኖች ክሳቸዉን እንዲያሻሽሉና ክርክራቸዉን እንዲለዉጡ ሊፈቀድላቸዉ ይችላል፡፡ ስለሆነም የዚህ ዓይነት መብት ለተከራካሪዎቹ ወገኖች የሚሰጠዉ የክሱ መሻሻል ወይም የክርክሩ መለወጥ ነገሩን ይበልጥ የሚያብራራ ወይም ትክክለኛ ፍትሕን ለመስጠት የሚረዳ ሆኖ በተገመተ ጊዜ ብቻ ነዉ፡፡ ይህንንም በሚፈቅድበት ፍርድ ቤቱ ተገቢ መስሎ የታየዉን ኪሳራ ለመወሰን ይችላል››፡፡ በማለት ይደነግጋል፡፡ አንድ ተከራካሪ ወገን ክስ ከቀረበ በኋላ ወሳኝ የዳኝነት ጥያቄ የቀረበት መሆኑን በሂደት የተገነዘበ እንደሆነ ክስ አሻሽሎ መብቱን መጠየቅ እንዲችል እድል የሚሰጥ ነዉ፡፡ በዚህ ድንጋጌ መሰረት የክስ ማሻሻል የማይፈቀድበት ሁኔታ አንዱ የክስ ማሻሻል ጥያቄዉ የክርክሩን ጭብጥ ለመወሰን ምንም የማይጠቅም እንደሆነ ብቻ ነዉ፡፡ የዚህ ድንጋጌ እንግሊዘኛዉ ቅጅ “The amendment of pleading shall not be allowed when the amendment is not necessary for the purpose of determining the real questions in dispute” የሚል ነዉ፡፡ ይህ ማለት ፍ/ቤት ለትክክለኛ ፍትህ አሰጣጥ ይረዳል ብሎ የሚገምት እንደሆነ ወይም የክርክሩን

መሰረታዊ ጭብጥ ወይም ጥያቄ ለመወሰን የሚያስችል እንደሆነ አቤቱታ ማሻሻል መፍቀድ እንዳለበት የሚያመለክት ነዉ፡፡ እንዲሁም ይህ ድንጋጌ በክስ ማመልከቻ ላይ በሚፈጠረዉ ስህተት የተከራካሪ ወገኖች መሰረታዊ መብቶች እንዳይጎዳ ሕጉ ሰፊ ማዕቀፍ እንደዘረጋ የሚያሳይ ነዉ፡፡ ፍ/ቤት ደግሞ በዚህ አግባብ ክስ እንዲሻሻል ሲያደርግ የሌላኛዉ ወገን መብት እንዳይጎዳ በቂ ነዉ ያለዉን ኪሳራ መወሰን እና ተሻሽሎ በቀረበዉ ክስ ላይ ተገቢ ክርክር እንዲያቀርብ እድል መስጠት አለበት፡፡ ከዚህ ዉጪ ግን አንድ ተከራካሪ ወገን ክሱን ለማሻሻል በቂ ምክንያት ያለዉ መሆኑን እየገለጸ፣ ሕጉም ደግሞ ፍርድ ከመሰጠቱ በፊት ክስ ማሻሻል እንደሚቻል በግልጽ እያመለከተ፣ ይህን ድንጋጌ ከመጠን በላይ አጥብቦ በመተርጎም ክስ እንዳይሻሻል እና ተሻሽሎ የቀረበዉን ክስ ዉድቅ በማድረግ የተከራካሪ ወገን ፍትህ የማግኘት ሕገ መንግስታዊ መብት እና መሰረታዊ መብቱን ማሳጣት የሚቻልበት አግባብ የለም፡፡ በዚህ መሰረት አሁን ወደ ተያዘዉ ጉዳይ ስንመለስ የአሁን አመልካች በዚህ ጉዳይ 3ኛ ተጠሪን ጨምሮ ተጠሪዎች ገንዘቡን እንዲከፍሉት ለመጠየቅ ክሱን ለማሻሻል ያቀረበዉ ጥያቄ ተቀባይነት አግኝቶ ከተፈቀደለት በኋላ የቀደመዉ ክስ አመልካች ገንዘብ እንዲከፈለዉ የጠየቀዉ የብድር ዉል መሰረት በማድረግ ሲሆን በተሻሻለዉ ክሰ ደግሞ ያለ አግባብ መበለጸግ መሰረት በማድረግ ስለጠየቀ፣ የተሻሻለዉ ክስ ከቀደመዉ ክስ ስለሚለይ ተቀባይነት የለዉም በማለት አመልካች ከፈለገ በቀደመዉ ክስ ክርክሩን እንዲቀጥል ሲጠየቅ፣ በመጀመሪያ ክስ ክርክሩን መቀጠል እንደማይፈልግ በመግለጹ ክሱን ዉድቅ ማድረጉን መገንዘብ ተችሏል፡፡ በዚህ ጉዳይ የክርክሩ መሰረታዊ ጭብጥ የአሁን አመልካች ከተጠሪዎች አለኝ የሚለዉን ገንዘብ የሚያስመልስበት አግባብ ነዉ፡፡ አመልካች መጀመሪያ 1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች ላይ ክስ ሲያቀርብ የብድር ዉል እንደሆነ የጠቀሰ ቢሆንም 3ኛ ተጠሪን ወደ ክሱ በሚጨምርበት ጊዜ ደግሞ ያለ አግባብ መበልጸግ መሰረት በማድረግ እንደሆነ ተገልጿል፡፡ ስለዚህ አመልካች ከተጠሪዎች ሊከፍሉኝ ይገባል የሚለዉን ገንዘብ መኖሩን አግባብነት ባለዉ ማስረጃ የማረጋገጥ ኃላፊነት የእሱ ቢሆንም ይህን መብቱን ለመጠየቅ ግን መጀመሪያ ባቀረበዉ ክስ ላይ የተፈጠረዉን ስህተት በማረም በተሻሻለዉ ክስ ‹‹ያለ አግባብ መበልጸግ›› መሰረት በማድረግ መጠየቁ እና ተጠሪዎች ደግሞ በዚህ በተሻሻለዉ ክስ ተገቢዉን ክርክር የማቅረብ እና ክርክሩ ለዘገየበት ተገቢ የሆነ ኪሳራ የሚከፈላቸዉ ከተደረገ መብታቸዉ የሚጎዳበት አግባብ አይኖርም ማለት ነዉ፡፡ የአሁን አመልካች ለክርክር ምክንያት የሆነዉን ገንዘብ ተጠሪዎች እንዲከፍሉት ለመጠየቅ በሚያስችለዉ አግባብ ክሱን አሻሽሎ እንዲያቀርብ ማድረግ ማለት ትክክለኛ ፍትህ ለመስጠት የሚረዳ ወይም የክርክሩን ወሳኝ ጥያቄ ወይም ጭብጥ ለመወሰን የሚያስችል ጉዳይ ነዉ፡፡ ይህ ደግሞ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.91 (1) ሥር የተመለከተዉን መስፈርት የሚያሟላ ሆኖ እናገኘዋለን፡፡ በመሆኑም የሥር ፍ/ቤቶች የአሁን አመልካች ያቀረበዉን የተሻሻለዉን ክስ ተቀብሎ ተጠሪዎች ተገቢ ክርክራቸዉን እንዲያቀርቡና ተገቢ ኪሳራ እንዲከፈላቸዉ በማድረግ ግራ ቀኛቸዉን በሕጉ አግባብ የማከራከርና የመሰማት መብታቸዉን በማረጋገጥ አጣርቶ ተገቢ ነዉ ያለዉን ዉሳኔ መስጠት ይገባቸዉ ነበር፡፡ ነገር ግን የሥር ፍ/ቤቶች ይህን ጉዳይ በዚህ አግባብ በማየት አመልካች ያቀረበዉን የተሻሻለዉን ክስ ተቀብሎ ግራ ቀኛቸዉን አከራክሮ ጉዳዩን አጣርቶ

መወሰን ሲገባቸዉ ዉድቅ በማድረግ መዝገቡን መዝጋታቸዉ፣ አመልካች በኢ.ፌ.ዴ.ሪ.ሕገ መንግስት አንቀጽ 37 መሰረት ፍትሕ የማግኘት መብቱን እና መሰረታዊ መብቱን የሚነፍግ እንዲሁም ከፍ ሲል የተጠቀሰዉን የፍትሐ ብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕግ ድንጋጌን የሚጥስ ነዉ፡፡

በመሆኑም የሥር ፍ/ቤቶች በዚህ ጉዳይ የሰጡት ዉሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.348 (1) መሰረት ተሽሮ የአሁን አመልካች ያቀረበዉ የተሻሻለዉ ክስ በመቀበል ለተጠሪዎች ተገቢ ኪሳራ ተቆርጦላቸዉና ክርክራቸዉን እንዲያቀርቡ በማድረግ ጉዳዩ ተጣርቶ ዉሳኔ እንዲሰጥበት ለሥር ፍ/ቤት መመለስ ነበረበት ብለን የአብላጫ ድምጽ ከሰጠዉ ዉሳኔ በመለየት የልዩነት ሀሳባችን አስቀምጠናል፡፡

**መዝገቡ ተዘግቷል፡፡**

የማይነበብ የሁለት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ሳ/ፀ

የሰ/መ/ቁ. 173416

ጥር 26 ቀን 2012 ዓ.ም

ዳኞች ፡- ብርሀኑ አመነው

ተሾመ ሽፈራው

ሀብታሙ እርቅይሁን

ብርሀኑ መንግስቱ

ነፃነት ተገኝ

| | | |
|---|---|---|
| አመልካቾች ፡ 1ኛ አቶ ዮሐንስ ዘውዴ አበራ | | |
| 2ኛ ወ/ሮ አህላም መሐመድ አብዱልአዚዝ | | ጠ. ገ/እግዚአብሄር ኪዳኔ-ቀረቡ፡፡ |
| 3ኛ አቶ አራዶም መብራቱ ወልዱ | | |
| 4ኛ አሕላም ትሬዲንግ ኃ/የተ/የግ/ማህበር | | |

ተጠሪ ፡ ወ/ሮ ተናኜ ማንያህልሀል ላቀው - አልቀረቡም፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ በተከሳሽ ከሳሽነት የቀረበ ክርክርን ይመለከታል፡፡ ክርክሩ በተጀመረበት የፌ/የመ/ደረጃ ፍ/ቤት ተጠሪ ከሳሽ አመልካቾች ተከሳሾች ነበሩ፡፡ ተጠሪ ሰኔ 30 ቀን 2008 ዓ.ም ፅፈው ባቀረቡት የተሻሻለ ክስ ከሐምሌ 1 ቀን 2008 እስከ ሰኔ 30 ቀን 2009 ያልተከፈለ ውዝፍ የቤት ኪራይ ብር 480,000.00 (አራት መቶ ሰማንያ ሺ) ከ9% ወለድ ፣ ቤቱን እስኪያስረክቡ ድረስ የሚታሰብ ኪራይ እና መቀጮ ብር 10,000.00 (አስር ሺ) እንዲከፍሉ እንዲወሰንላቸው ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡ አመልካቾች ባቀረቡት የመከላከያ መልስ ክሱ እስከቀረበበት ቀን ድረስ ወለድን ጨምሮ ዳኝነት የተጠየቀበት ጠቅላላ የገንዘብ መጠን ብር 512,400.00 (አምስት መቶ አስራ ሁለት ሺ አራት መቶ) ስለሆነ ፍ/ቤቱ ጉዳዩን የማየት የስረ ነገር ስልጣን የለውም በማለት መቃወሚያቸውን አቅርበዋል፡፡

ፍርድ ቤቱም የ1 ዓመት ወለድ በባለሞያ ተሰልቶ ውጤቱ እንዲቀርብ ትዕዛዝ የሰጠ ሲሆን ወለዱ ብር 43,200.00 (አርባ ሶስት ሺ ሁለት መቶ) መሆኑን በማረጋገጥ መቀጮ እና ዋናውን ገንዘብ ጨምሮ ጠቅላላ ዳኝነቱ ብር 533,900.00( አምስት መቶ ሰላሳ ሶስት ሺ ዘጠኝ መቶ) ስለሆነ ጉዳዩን አይቶ

ለመወሰን የስረ ነገር ስልጣን የለኝም በማለት መዝገቡን ዘግቶታል፡፡ አመልካቾች በጉዳዩ ለፌ/ከ/ፍ/ቤት ይግባኝ ያቀረቡ ቢሆንም በፍ/ሥ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 337 መሰረት በመሰረዙ በዚሕ ችሎት የሰበር አቤቱታቸውን አቅርበዋል፡፡

የአመልካቾች የሰበር አቤቱታ ይዘት ተጠሪ በስር ፍ/ቤት ብር 632,000.00 (ስድስት መቶ ሰላሳ ሁለት ሺ) እንዲከፈላቸው በመሰረቱት ክስ መነሻነት አመልካቾች በተከሳሽ ከሳሽነት ብር 162,194.16 (አንድ መቶ ስልሳ ሁለት ሺ አንድ መቶ ዘጠና አራት ብር ከ16/100) እንዲወሰንልን ዳኝነት የጠየቅን ሲሆን ፍ/ቤቱ አመልካቾች ያነሳነውን መቃወሚያ በመቀበል ጉዳዩን የማየት የስረ ነገር ስልጣን የለኝም በሚል ብይን ሲሰጥ ያቀረብነው የተከሳሽ ከሳሽነት ክስ በዝምታ በመታለፉ ለችሎቱ አቤቱታ ያቀረብን ቢሆንም የከፍተኛ ፍ/ቤቱ ይመልከተው በማለት በሰጠው ትዕዛዝ የተፈፀመውን የሕግ ስህተት በማረም የተከሳሽ ከሳሽነት ክሱ ላይ አከራክሮ እንዲወስን ይወሰንልን በማለት ጠይቀዋል፡፡

ጉዳዩ በሰበር አጣሪ ችሎት ተመርምሮ የስር ፍ/ቤት የተከሳሽ ከሳሽነት ክሱን በዝምታ የማለፉን አግባብነት ከፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 182(3) አንፃር ለመመርመር ለሰበር ሰሚ ችሎት ያስቀርባል በመባሉ ተጠሪ መልሳቸውን እንዲያቀርቡ ታዟል፡፡ ተጠሪም በመልሳቸው የአመልካቾች ዳኝነት በዝምታ የታለፈ እንጂ በድጋሜ የቀረበ ክስ ነው ተብሎ ውድቅ ባለመደረጉ የስር ፍ/ቤት ብይን ተገቢ ነው በማለት ተከራክረዋል፡፡ አመልካቾች በመልስ መልሳቸው የሰበር አቤቱታቸውን በማጠናከር ተከራክረዋል፡፡

የክርክሩ አመጣጥ ባጭሩ ከላይ የተመለከትነው ሲሆን ጉዳዩ በሰበር አጣሪ ችሎቱ ተመርምሮ ያስቀርባል ከተባለበት ነጥብ አንፃር መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት መሆን አለመሆኑን በስር ፍርድ ቤት በግራ ቀኙ ከቀረቡ ክርክሮች፣ በማስረጃ ከተረጋገጡ ፍሬ ጉዳዮች እና ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸው ሕጎች አንፃር እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

ጉዳዩን እንደመረመርነው ተጠሪ በፌ/የመ/ደ/ፍ/ቤት ባቀረቡት ክስ ዳኝነት የጠየቁበት የገንዘብ መጠን ከፍ/ቤቱ የስረ ነገር ስልጣን በላይ በመሆኑ አመልካቾች ባቀረቡት መቃወሚያ መሰረት ፍ/ቤቱ መዝገቡን በብይን ዘግቶታል፡፡ እንዲሁም በስር በነበረው ክርክር አመልካቾች የተከሳሽ ከሳሽነት ክስ አቅርበው የነበረ መሆኑም ግራ ቀኙን አላከራከረም፡፡ የአመልካች ቅሬታ የስር ፍ/ቤት ያቀረቡትን መቃወሚያ ተቀብሎ የተጠሪን ክስ ቢሰርዘውም ያቀረብነውን የተከሳሽ ከሳሽነት ክስ በዝምታ ማለፉ እና አከራክሮ አለመወሰኑ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ነው የሚል ነው፡፡ በመሰረቱ ፍ/ቤቶች በተከራካሪዎች የሚነሱ የክርክር ነጥቦች በአንድ ጭብጥ ተካተው ሊወሰኑ ከሚችሉት በቀር ክርክሮቹን በአግባቡ መርምሮ የቀረቡትን ጭብጦች በየራሳቸው መወሰን እና ተገቢውን ሀተታ በማስፈር የብይን ወይም የፍርዱ አካል ሊያደርጓቸው የሚገባ ስለመሆኑ ከፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 182(3) ድንጋጌ መገንዘብ ይቻላል፡፡ አመልካቾች በተጠሪ ክስ ላይ ያቀረቡት መቃወሚያ እና በክሱ መነሻነት ያቀረቡት የተከሳሽ ከሳሽነት ክስ እራሱን ችሎ መፍትሔ ማግኘት ያለበት ክርክር ነው፡፡ በመሆኑም የስር ፍ/ቤት አመልካቾች ያቀረቡት የተከሳሽ ከሳሽነት

ክስ ላይ አግባብነት ያለውን ትዕዛዝ ወይም ብይን አለመስጠቱ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ አግኝንተነዋል፡፡

ሌላው በጉዳዩ መፍትሔ ማግኘት ያለበት ነጥብ አመልካቾች በቀረበው የተከሳሽ ከሳሽነት ክስ ላይ የስር ፍ/ቤት አከራክሮ ሊወስን ይገባ ነበር በማለት የሚያነሱት መከራከሪያ ነው፡፡ በተከራካሪዎች ለዳኝነት በቀረበ ጉዳይ ላይ ፍ/ቤቱ በራሱ አነሳሽነት ወይም በተከራካሪዎቹ በሚቀርብ መቃወሚያ መነሻነት የስረ ነገር ስልጣን የሌለው መሆኑን ካረጋገጠ መዝገቡን የስረ ነገር ስልጣን ላለው ፍ/ቤት ሊያስተላልፍ የሚገባ መሆኑ ከፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 17(3) እና 91(5) መገንዘብ ይቻላል፡፡ መዝገቡ ስልጣን ወዳለው ፍ/ቤት መተላለፍ አለበት ከተባለ የተላለፈለት ፍ/ቤት ጉዳዩን ከየት ጀምሮ መቀጠል አለበት የሚለውን መመልከቱ ተገቢ ነው፡፡ ስልጣን ወዳለው ፍ/ቤት በሚተላለፍ መዝገብ ውስጥ የግራ ቀኙ የጽሁፍ ክርክር ብቻ ተጠናቆ የክስ መሰማት ሂደቱ ካልተጀመረ መዝገብ የተላለፈለት ፍ/ቤት ጉዳዩን ከቆመበት መቀጠሉ ችግር አይኖረውም፡፡ ነገር ግን ጉዳዩን ሲመለከተው የነበረው ፍ/ቤት የስረ ነገር ስልጣን የለኝም ያለው የጽሁፍ ክርክር ካበቃ በኃላ ከክስ መስማት ጀምሮ ያሉ የክርክር ሂደቶችን ካደረገ በኃላ ከሆነ ከክስ መስማት ጀምሮ የተደረጉት ሂደቶች ስልጣን በሌለው ፍ/ቤት የተደረጉ በመሆኑ ሂደቶቹ በተላለፈው መዝገብ ውስጥ ቢኖሩም መዝገቡ የተላለፈለት ፍ/ቤት ከክስ መስማት ጀምሮ ያሉትን የክርክር ሂደቶች እንዳልተደረጉ በመቁጠር እንደገና ሂደቱን ከክስ መስማት ጀምሮ መቀጠል አለበት፡፡

በዚህ መሰረት የፌደራል መ/ደ/ፍ ቤት ተጠሪዎች ክስ ሲያሻሽሉ ጉዳዩን የማየት የስረ ነገር ስልጣን የሌለው መሆኑን ሲያረጋግጥ እንዳለ መዝገቡን ስልጣን ወዳለው ፍ/ቤት እንዲተላለፍ ማድረግ ሲገባው ስልጣን የለኝም ካለ በኃላ መዝገቡን መዝጋቱ መሰረታዊ የስነ ስርዓት ሕግ ግድፈት የተፈፀመበት ነው፡፡ የፌደራል መ/ደ/ፍ/ቤት የስነ ስረዓት ህጉን ተከትሎ መዝገቡን እንዳለ ስልጣን ወዳለው ከፍተኛ ፍ/ቤት ቢያስተላልፍ ኖሮ የአመልካቾች የተከሳሽ ከሳሽነት ክስ አብሮ የሚተላለፍ በመሆኑ ለቅሬታ ምክንያት የሆነውም ጉዳይ በዚያው እልባት ማግኘት ይችል ነበር፡፡

አመልካቾች አጥብቀው የሚከራከሩት ያቀረብነው የተከሳሽ ከሳሽነት ክስ ላይ ፍ/ቤቱ አከራክሮ ውሳኔ ሊሰጥ ይገባዋል የሚል ነው፡፡ ይሁን እንጂ ፍ/ቤቱ በቀረበው ክስ ላይ የስረ ነገር ስልጣን ስለሌለው ከስነ ስርዓት ሕጉ ዋና አላማዎች መካከል አንዱ ክርክሮች በአነስተኛ ወጪ በአጭር ጊዜ እና በተፋጠነ ሁኔታ ተጠቃለው መፍትሔ እንዲያገኙ ማስቻል ሲሆን፤ ይህም ትክክለኛ ፍትህ ላይ ለመድረስ አስፈላጊ ስለሆነ በስረ ነገር ስልጣኑ ስር ያሉትን መርጦ የማየትና ከስረ ነገር ስልጣኑ በላይ የሆኑት ጉዳዮች ስልጣን ላለው ፍ/ቤት ይቅረብ በማለት ትዕዛዝ መስጠት አይችልም፡፡ ምክንያቱም የተከሳሽ ከሳሽነት ክስ የቀረበ እንደሆነ የፍ/ቤቱ የስረ ነገር ስልጣን የሚወሰነው ከተከራካሪዎቹ አንደኛው ወገን ያቀረበው ከፍተኛ የገንዘብ መጠን መሰረት በማድረግ መሆኑ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 17(3) ተመላክቷል፡፡ በመሆኑም

የአመልካቾች የተከሳሽ ከሳሽነት ክስ በከፍተኛ ፍ/ቤቱ ተጠሪ ካቀረቡት ክስ ጋር ተጠቃሎ ታይቶ ውሳኔ ሊያገኝ የሚገባው በመሆኑ ተከታዩን ወስነናል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. የፌ/የመ/ደ/ፍ/ቤት በመ/ቁጥር 43175 በቀን 27/09/2010 በዋለው ችሎት የሰጠው እና በፌ/ከ/ፍ/ቤት በመ/ቁጥር 223476 በቀን 21/05/2011 በትዕዛዝ የፀናው ውሳኔ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ተሻሽሏል፡፡ ተጠሪ ያቀረቡትን ክስ አከራክሮ ለመወሰን የስረ ነገር ስልጣን የለኝም በማለት የሰጠው ብይን ፀንቷል፡፡
2. የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት የተጠሪ ክስ እና አመልካቾች ያቀረቡት የተከሳሽ ከሳሽነት ክስ ተጠቃሎ ውሳኔ እንዲያገኝ የመዝገብ ቁጥሩ 43175 የሆነውን መዝገብ ስልጣን ላለው የፌ/ከ/ፍ/ቤት ያስተላልፍ ብለናል፡፡ ከፍተኛ ፍ/ቤቱም የቀረበውን ክስ እንዲሁም የተከሳሽ ከሳሽነት ክስ መርምሮ ተገቢ የመሰለውን ይወስን፡፡
3. በዚህ ችሎት የተደረገው ክርክር ያስከተለውን ወጪ እና ኪሳራ ግራ ቀኙ ይቻቻሉ፡፡

## ት እ ዛ ዝ

ውሳኔው እንዲታተም ለጥናትና ህግ ስራ ክፍል ይተላለፍ፡፡

የውሳኔ ግልባጭ ለስር ፍ/ቤቶች ይተላለፍ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ዕ/ወ

የሰ/መ/ቁ169716

ጥቅምት 24/2012 ዓም

ዳኞች፡- እትመት አሰፋ

ኃይሉ ነጋሽ

ፀሐይ መንክር

መላኩ ካሳዬ

እስቲበል አንዱዓለም

አመልካቾች፡-1. ወ/ሪት ሰላማዊት ይልማ (9 ሰዎች)

ተጠሪዎች፡-1. የኢትዮጵያ ቀይመስቀል ማህበር ቡታጅራ ቅርንጫፍ ነ/ፈጅ አቶ ሳሙኤል ቀረቡ፡፡

2. የቡታጅራ ከተማ አስተዳደር ጽ/ቤት ዐ/ህግ ቀረቡ፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍርድ

በዚህ መዝገብ ላይ የቀረበው ጉዳይ የዳኝነት የስረ ነገር ስልጣንን የሚመለከት ነው፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው የቡታጅራ አካባቢ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በአሁን አመልካቾች የቀረበለትን ክስ በተመለከተ የተጠሪዎችን መልስ ከሰማ በኂላ በመ/ቁ/10273 ላይ ታህሳስ 26/2010 በዋለው ችሎት "ጉዳዩን የማየት የስረ ነገር ስልጣን የለኝም" በማለት የሰጠው ብይን በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት መደበኛ ይግባኝ ችሎት በፍ/ይ/መ/ቁጥር 09874 ላይ የካቲት 07/2010 ዓ.ም በመፅናቱ እና የክልሉ ሰበር ችሎትም በሰ/መ/ቁ/10581 ላይ ሚያዝያ 26/2010 በዋለው ችሎት "በጉዳይ ላይ የሰበር ስልጣን የለኝም" በማለት የሰጠውን ትዕዛዝ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ እንዲህ ነው፡፡ የአሁን አመልካቾች ለቡታጅራ አካባቢ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በአሁን 1ኛ ተጠሪ ላይ ባቀረቡት ክስ አውራሻቸው አቶ ይልማ ሳህሌ በህይወት እያሉ በቡታጂራ ከተማ ቀበሌ 04 ውስጥ በ1,275 ካሬ ሜትር ላይ ያረፈ የንግድ ድርጅት ቤት የነበራቸው መሆኑን፤ በወቅቱ ድርጅቱን ባጋጠመው መጠነኛ የስራ መቀዛቀዝ ድርጅቱ ታድሶ በአዲስ መልክ ስራ እስኪጀምር ድርስ በመዘጋቱ በጊዜው የነበሩት የቀበሌ ተመራጮች ያለአንዳች መመሪያ እና ትዕዛዝ እንዲሁም አዋጅ ከሚፈቅደው ውጭ ቤቱን ሰብረው ለወዛደሮች ቡና ቤት እንዲሰሩበት እንዳደረጉ፤ በዚሁ ምክንያት

አውራሻቸው ቤቱ ያለአግባብ የተወሰደባቸው መሆኑን ገልፀው እንዲመለስላቸው ለተለያዩ አካላት አቤቱታ ሲያቀርቡ የቆዩ መሆኑን፤ ንብረቱ የአውራሻቸው ስለመሆኑ እና ያለአግባብ የተወሰደባቸው መሆኑንም በሚመለከተው አካል ተጣርቶ የተረጋገጠ ቢሆንም የያዙ አካላት ቤቱን ለቀው ንብረቱን ለባለሃብቱ ማስረከብ ሲገባቸው የአሁን 1ኛ ተጠሪ በምን አግባብ እንደያዘ ባልታወቀበት ሁኔታ ቤቱን ይዞ ያለአግባብ እየተገለገለበት ያለ መሆኑን፤ ይህንኑ ገልፀው ቤቱን እንዲያስረክባቸው ቢጠይቁም ፈቃደኛ አለመሆኑን በመግለፅ በፍርድ ኃይል ተገዶ ቤቱን እንዲያስረክባቸው እና ከ2000 ዓ.ም ጀምሮ በመያዙ የቀረባቸው ገቢ በወር በብር 1,000(አንድ ሺህ) ታስቦ ከህጋዊ ወለድ ጋር እንዲከፍላቸው ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡

የአሁን 1ኛ ተጠሪ ለክሱ በሰጠው መልስ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ እና ተገቢ ነው ያለውን የፍሬ ነገር ክርክር በማቅረብ ቤቱን የተረከበው ከአሁን 2ኛ ተጠሪ መሆኑን ገልፆ በጣልቃ ገብነት ወደ ክርክሩ እንዲገባለት ጠይቋል፡፡

ጉዳዩ የቀረበለት ፍርድ ቤት 2ኛ ተጠሪን በጣልቃገብነት የክርክሩ አካል አድርጎ መልስ ካሰጠ በኋላ ክርክር የተነሳበት ቤት በመንግስት እጅ ቆይቶ በአሁን 2ኛ ተጠሪ ለ1ኛ ተጠሪ ሐምሌ 12/1999 ዓ.ም የተላለፈ መሆኑን፤ ከዚህ ጊዜ በፊትም ሆነ በኋላ ቤቱ በመንግስት ቁጥጥር ስር ሆኖ ለ1ኛ ተጠሪ የተሰጠውም በጊዜያዊነት ለመሆኑ እንዳረጋገጠ፤ በመንግስት እጅ ባለ ቤት ወይም ይዞታ ላይ በመንግስት እና በግለሰቦች መካከል የሚነሳን ክርክር የማየት የስረ ነገር ስልጣን ያለው በአዋጅ ቁጥር 110/1987 እና 572/2000 መሰረት የፕራይቬታይዜሽን ኤጀንሲ እንጂ መደበኛ ፍርድ ቤት አለመሆኑን ጠቅሶ ጉዳዩን የማየት የስረ ነገር ሥልጣን የለኝም በማለት መዝገቡን ዘግቷል፡፡

በዚሁ ብይን ላይ ይግባኝ የቀረበለት የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት አቤቱታውን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ቁጥር 337 መሰረት ሰርዟል፡፡ አመልካቾች ለክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት የሰበር አቤቱታ ያቀረቡ ሲሆን ችሎቱ ከተከራካሪ ወገኖች ውስጥ የአሁን 1ኛ ተጠሪ በፌዴራል መንግስት የተመዘገበ ተቋም በመሆኑ ጉዳዩ የፌዴራል ጉዳይ መሆኑን እና የክልሉ ሰበር ችሎት የሰበር ስልጣን ያለው በክልል ጉዳይ ላይ ብቻ መሆኑን በምክንያትነት በመጥቀስ የሰበር ስልጣን የለኝም ሲል መልሷል፡፡

የአሁን የሰበር አቤቱታ የቀረበው ይህንኑ በመቃወም ነው፡፡ አመልካቾች ጥር 22/2011 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ በዚህ ሰበር ችሎት ሊታረም ይገባል ያሉትን ነጥቦች ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ የአቤቱታው ፍሬ ቃልም ክርክር የተነሳበት ቤት የመንግስት ስለመሆኑ የቀረበ ማስረጃ በሌለበት፤ በአዋጅ፣ በመመሪያ በቀላጤ አልያም በትዕዛዝ ስለመወረሱም የቀረቡት ማስረጃዎች በአግባቡ ሳይመረመሩ የከፍተኛው ፍርድ ቤት ክርክሩ ከመንግስት ጋር በመሆኑ የዳኝነት የስረ ነገር ስልጣን የለኝም ማለቱ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት በሰ/መ/ቁ/37281 ላይ ከሰጠው አስገዳጅ ትርጉም አኳያ አግባብ አይደለም፤ የክልሉ ሰበር ችሎትም ከአሁን 1ኛ ተጠሪ የቀረበለት ክርክር ሳይኖር 1ኛ ተጠሪ በፌዴራል መንግስት

የተመዘገበ ተቋም በመሆኑ ጉዳዩ የፌዴራል ጉዳይ ነው በሚል የሰበር ስልጣን የለኝም ማለቱ አግባብ አይደለም የሚል ነው፡፡

በአመልካቾች የተጠየቀው ዳኝነት ያለአግባብ የተያዘብን ቤት ይለቀቅልን የሚል ሆኖ እያለ የስር ፍርድ ቤቶች የስረ ነገር ስልጣን የለንም ያሉበት አግባብ ለዚህ ሰበር ችሎት ቀርቦ እንዲታይ በሰበር አጣሪ ችሎት በመታዘዙ ተጠሪዎች መልስ እንዲሰጡበት ተደርጎ እንደቀደም ተከተላቸው ሰኔ 22 እና 21 ቀን 2011 ዓ.ም የተፃፈ አንድ አይነት ይዘት ያለው የተናጠል መልስ አቅርበዋል፡፡

ፍሬ ቃሉም አመልካቾች በዚሁ ፍርድ ቤት በሰ/መ/ቁ/159230 ላይ የሰበር አቤቱታ አቅርበው ጊዜ ያለፈበት አቤቱታ ነው ተብሎ ውድቅ የተደረገባቸው በመሆኑ ድጋሚ አቤቱታ ሊያቀርቡ አይገባም፤ ክርክር የተነሳበት ቤት ከ1967 ዓ.ም ጀምሮ በመንግስት እጅ(በአሁን 2ኛ ተጠሪ) የሚገኝ በመሆኑ እና እንደዚህ አይነት ክርክርን የማየት ስልጣን በአዋጅ ቁጥር 110/1987 መሰረት ለኢትዮጵያ ፕራይቬታይዜሽን ኤጀንሲ የተሰጠ በመሆኑ እና ይኸው ሰበር ችሎትም በሰ/መ/ቁ/23608 እና 31682 ላይ ተመሳሳይ ትርጉም የሰጠ በመሆኑ የስር መደበኛ ፍርድ ቤቶች ሥልጣን የለም ማለታቸው ተገቢ ነው፤ የክልሉ ሰበር ችሎትም የስረ ነገር ስልጣንን በተመለከተ ከተከራካሪዎች የሚነሳን ጥያቄ ሳይጠብቅ አይቶ ስልጣን የለኝ ማለቱ የሚነቀፍ አይደለም የሚል ነው፡፡

አመልካቾች ሐምሌ 19/2011 ዓ.ም በሰጡት የመልስ መልስ ቀደም ሲል ያቀረቡት የሰበር አቤቱታ ጊዜው ያለፈበት ነው ተብሎ ውድቅ ቢደረግም በውሳኔው ላይ ጊዜ ያለፈበት አቤቱታ ቀርቦ እንዲታይ መጠየቅ የሚቻል ስለመሆኑ በመገለፁ ይኸው መነሻ ተደርጎ ጊዜ ያለፈበት አቤቱታ ቀርቦ እንዲታይ ማስፈቀጃ ቀርቦ በሰ/መ/ቁ/168197 ላይ በተፈቀደው መሰረት ይህ መዝገብ ሊከፈት የቻለ መሆኑን በመግለፅ በተቀረው ቀደም ሲል የቀረበው የሰበር አቤቱታ በማጠናከር ተከራክረዋል፡፡

በግራ ቀኙ የቀረበው ክርክር አጠር ባለ መልኩ ከላይ የተመለከተውን ሲመስል ችሎቱም ጉዳዩን አግባብነት ካለው ህግ ጋር በማገናዘብ መርምሯል፡፡

በመጀመሪያ አሁን የቀረበው የሰበር አቤቱታ ቀደም ሲል ቀርቦ ጊዜ ያለፈበት ነው ተብሎ ውድቅ ተደርጓል በሚል የቀረበውን መቃወሚያን አስመልክቶ በግራ ቀኙ የተጠቀሱትን መዛግብት ችሎቱ አስቀርቦ ተመልክቷል፡፡ በዚሁ መሰረት በእርግጥም አመልካቾች በዚህ መዝገብ ላይ ያቀረቡትን አቤቱታ ቀደም ሲል በሰ/መ/ቁ/159230 ላይ አቅርበው አቤቱታው ጊዜ ያለፈበት መሆኑ ተረጋግጦ በህጉ አግባብ ጊዜ ያለፈበት የሰበር አቤቱታ ቀርቦ እንዲታይ ከሚጠየቅ በቀር በቀረበው አግባብ ሊታይ አይገባም ተብሎ ውድቅ መደረጉን፤ በዚሁ ምክንያት አመልካቾች በሰ/መ/ቁ/168197 ላይ የማስፈቀጃ አቤቱታ አቅርበው ጥር 14/2011 ዓ.ም የተፈቀደ መሆኑን ለመገንዘብ ተችሏል፡፡ በመሆኑም በዚህ መዝገብ ላይ

የቀረበው አቤቱታ የህግ ሥረዓቱን ጠብቆ የቀረበ በመሆኑ ከዚህ አኳያ በተጠሪዎች የቀረበውም መከራከሪያ ችሎቱ አልተቀበለውም፡፡

ዋናውን ጉዳይ በተመለከተ በመሰረቱ በፌዴራልም ሆነ በክልል የዳኝነት ስልጣን የመደበኛ ፍርድ ቤቶች ስለመሆኑ የኢ.ፌ.ዴ.ሪ. ህገ መንግስት አንቀፅ 79(1) ይደነግጋል፡፡ የዳኝነት ስልጣን በመርህ ደረጃ የመደበኛ ፍርድ ቤቶች ቢሆንም ተለይተው በታወቁ ጉዳዮች ላይ በልዩ ህግ የዳኝነት ሥልጣን ለሌላ አካል ሊሰጥ የሚችል ለመሆኑ ከህገ መንግስቱ አንቀፅ 37 ድንጋጌ መገንዘብ ይቻላል፡፡ እናም ዳኝነትን በተመለከተ መሰረታዊ ስልጣኑ የመደበኛ ፍርድ ቤት በመሆኑ መደበኛ ፍርድ ቤቶች ዳኝነት በተጠየቁበት ጉዳይ ላይ የስረ ነገር ስልጣን የለኝም ከማለታቸው በፊት ዳኝነት የተጠየቀበት ጉዳይ በልዩ ህግ ለሌላ አካል የተሰጠ ለመሆኑ በተገቢው መንገድ አጣርተው ሊያረጋግጡ ይገባል፡፡ በዚህ መልኩ ሳይጣራ ስልጣን የለኝምበሚል የሚወሰድ እርምጃ በህገ መንግስቱ አንቀፅ 37 የተረጋገጠውን ፍትህን የማግኘት መሰረታዊ መብትን የሚጥስ በመሆኑ ተቀባይነት አይኖረውም፡፡

አሁን በቀረበው ጉዳይ የአመልካቾች ጥያቄ ክርክር የተነሳበት ቤት ከአዋጅ ውጭ በወቅቱ በነበሩ የቀበሌ ሹማምንት ትዕዛዝ ለወዛደሮች ተሰጥቶ የነበረ በመሆኑ እንዲመለስ በቀረበ አቤቱታ መነሻነት የቤቱ አያያዝ ህገ ወጥነት ቢረጋገጥም ሊመለስልን ሲገባ ለአሁን 1ኛ ተጠሪ የተላለፈ በመሆኑ 1ኛ ተጠሪ ሊያስረክበን ይገባል የሚል ነው፡፡

ጉዳዩ የቀረበለት ፍርድ ቤት በአሁን ተጠሪዎች በቀረበለት መቃወሚያ መሰረት ክርክር የተነሳበት ቤት በመንግስት እጅ የነበረ እና ለአሁን 1ኛ ተጠሪ በጊዜያዊነት በመንግስት ተላልፎ የተሰጠ በመሆኑ ጉዳዩ የማየት የስረ ነገረ ስልጣን ያለው የፕራይቬታይዜሽን ኤጀንሲ ነው ብሏል፡፡ በእርግጥ ከአዋጅ ቁጥር 47/1967 ውጭ በመመሪያ፣ በቀላጤ ወይም በትዕዛት የተወሰዱ ንብረቶችን በሚመለከት የሚነሳ ክርክርን አይቶ የመወሰን የስረ ነገር ስልጣን የተሰጠው ለኢትዮጵያ ፕራይቬታይዜሽን ኤጄንሲ ስለመሆኑ የአዋጅ ቁጥር 110/1987 አንቀፅ 4(1) ድንጋጌ ያስገነዝባል፡፡

ሆኖም ፍርድ ቤት ጉዳዩን የማየት ስልጣን የለኝም ከማለቱ በፊት ክርክር የተነሳበት ቤት/ንብረት/ በተመለከተ የተነሳው ጥያቄ በትክክል በኤጀንሲ ሥልጣን ስር የሚወድቅ ስለመሆኑ፤ ከሆነም በዚያ ረገድ የተደረገ ክርክር እና የተወሰደም አቋም ካለም ከግራ ቀኙ በሚቀርቡለት ክርክር እና ማስረጃ በተገቢው ሁኔታ ሊያጣራ ይገባል፡፡

ይህ ችሎም ይህንኑ መሰረት በማድረግ የክርክሩን አመጣጥ ከስረ መሰረቱ ፈትሿል፡፡ በዚሁ መሰረት ክርክር የተነሳበትን ቤት በተመለከተ የአሁን አመልካቾ ወላጅ አባት የሆኑት አቶ ይልማ ሳህሌ ቤቱ እንዲመለስላቸው በደርግ ዘመነ መንግስት ለሸዋ ክፍለ ሀገር ከተማ ልማትና ቤት ሚኒስቴር አቤቱታ ያቀረቡ መሆኑን፤ ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱም ጉዳዩን አጣርቶ እንዲያቀርብለት ለቡታጅራ ልዩ ከፍተኛ

ከነማ ጽ/ቤት ጥቅምት 14/1981 ዓ.ም ትዕዛዝ መስጠቱን፣ ጽ/ቤቱ ጉዳዩ በቀበሌ ፍርድ ሸንጎ እንዲጣራ ካደረገ በኋላ ሰኔ 24/1981 ዓ.ም ትዕዛዙ ለሰጠው ሚኒስቴር መስሪያ ቤት በሰጠው ምላሽ ክርክር የተነሳበት ቤት የአመልካቾ አባት ዘግተው በመሄዳቸው ምንክያት ከ1968 ዓ.ም ጀምሮ በቀበሌ የተያዘ ስለመሆኑ ማረጋገጡን ገልፆ መመሪያ እንዲሰጥበት መጠየቁ እና ከዚህ በኋላ የተሰጠ ውሳኔ አለመኖሩ ለመረዳት ተችሏል፡፡

በሌላ በኩል ይኸው ቤት እንዲመለስላቸው የአመልካቾች አባት ሐምሌ 29/1988 ዓ.ም የተፃፈ አቤቱታ ለፕራይቬታይዜሽንና የመንግስት ልማት ድርጅቶች ተቆጣጣሪ ኤጀንሲ ጥያቄ አቅርበው ኤጀንሲ መስከረም 12/1999 ዓ.ም በሰጠው ውሳኔ ቤቱ ከአዋጅ ውጭ በመመሪያ፣ በቀላጤ ለመወሰዱ ወይም በአዋጅ ቁጥር 47/1967 አስፈፃሚ አካል ስለመፈቀዱ የቀረበ ማስረጃ ባለመኖሩ ኤጀንሲው ጉዳዩን የማየት ስልጣን የለውም በሚል ምክንያት መዝገቡን መዝጋቱን እና ይኸው ውሳኔ በይግባኝ በኤጀንሲ ስር ከአዋጅ ውጭ የተወሰዱ ንብረቶች ማስፈፀሚያ ፕሮጀክት ጽ/ቤት ኃላፊ ቀርቦ መስከረም 22/1999 ዓ.ም በምክንያት ተጠናክሮ የፀደቀ መሆኑን ከመዝገቡ ውስጥ ለመረዳት ተችሏል፡፡

ከጉዳዩ አመጣጥ በግልፅ መረዳት እንደሚቻለው ክርክር የተነሳበት ቤት ከ1968 ዓ.ም ጀምሮ በመንግስት እጅ የነበረ ሲሆን በአዋጅ ቁጥር 47/1967 መሰረት ለመወረሱ የቀረበ ክርክርም ሆነ የቀረበ ማስረጃ የለም፡፡ እናም በአዋጅ ቁጥር 110/1987 መሰረት በዚህ መልኩ ከአዋጅ ውጭ በመመሪያ፣ በቃላጤ አልያም በቃል ትዕዛዝ የተወሰዱ እና በመንግስት ቁጥጥር ስር ያሉትን ንብረቶች በተመለከተ የሚነሳን ክርክር ተቀብሎ የማየት የስረ ነገር ስልጣኑ የኢትዮጵያ ፕራይቬታይዜሽን አጀንሲ ነው፡፡ ጉዳዩ ይህ ሆኖ እያለ ኤጀንሲው የዳኝነት ስልጣን የለኝም ብሎ የመለሰበት አግባብ ግልፅ አይደለም፡፡

ከዚሁ ጋር ተያይዞ “በልዩ ህግ የዳኝነት ስልጣን የተሰጠው አካል የቀረበለትን የዳኝነት ጥያቄን አስመልክቶ ጉዳዩን የማየት የስረ ነገር ስልጣን የለኝም በማለት ቢመለስ እና ተመሳሳይ የዳኝነት ጥያቄ ለመደበኛ ፍርድ ቤት ቢቀርብ ውጤቱ ምን ይሆናል?” የሚለውን ማየቱ ተገቢ ይሆናል፡፡

ከላይ ለመጥቀስ እንደተሞከረው በኢ.ፌ.ዴ.ሪ. ህገ መንግስት የዳኝነት ስልጣን የተሰጠው ለመደበኛ ፍርድ ቤቶች ብቻ ነው፡፡ መርሆው ይህ ቢሆንም ይህንኑ ስልጣን ለፍርድ ቤቶች የሰጠው ህገ መንግስት በልዩ ሁኔታ በህግ የዳኝነት ስልጣን ለሌላ አካል ሊሰጥ የሚችል ስለመሆኑ እውቅና የሰጠ በመሆኑ ይኸው የህገ መንግስቱ ድንጋጌ በፍርድ ቤቶች በአግባቡ ሊከበር ይገባል፡፡ ሆኖም ከመደበኛ ፍርድ ቤት ውጭ አንድን ጉዳይ የማየት በህግ የዳኝነት ስልጣን የተሰጠው አካል በአንድም ይሁን በሌላ ምክንያት ጉዳዩን አላይም ብሎ ከመለሰ የዳኝነት ተፈጥሮኣዊ ስልጣን የፍርድ ቤት በመሆኑ እና ፍትህ የማግኘት መብት በህገ መንግስቱ የተረጋገጠ በመሆኑ ጉዳዩን የማየት ስልጣን ለሌላ የዳኝነት አካል ተሰጥቷል የሚል ክርክር እስካልቀረበ ድረስ መደበኛ ፍርድ ቤት በተመሳሳይ መልኩ ጉዳዩን ሊመልስ አይገባም፡፡

ከዚሁ ጋር በተያያዘ ይኸው ሰበር ችሎት በሰ/መ/ቁ/ 37964 ላይ ጥር 27/2003 ዓ.ም በዋለው ችሎት የፕራይቬታይዜሽን ኤጀንሲ ስልጣን ሥር የሚወድቅ አይደለም በሚል በኤጀንሲው የተረጋገጠ ጉዳይን በተመለከተ ጉዳዩን የማየት ስልጣን ለሌላ የዳኝነት አካል የተሰጠነው በሚል ክርክር እስካልቀረበ ድረስ ፍርድ ቤቶች ተቀብለው ማስተናገድ የሚችሉ ስለመሆኑ ትርጉም ተሰጥቷል፡፡

በመሆኑም ጉዳዩ የማየት የስር ነገር የዳኝነት ስልጣን በልዩ ህግ የተሰጠው የፕራይቬታይዜሽን ኤጀንሲ ጉዳዩ ከቀረበለት ከ10 ዓመት በኋላ በኤጀንሲ ሥልጣን ስር አይወድቅም ብሎ የመለሰ ለመሆኑ ማስረጃ ቀርቦ መዝገብ ውስጥ እያለ እና ስልጣኑ ለሌላ የዳኝነት አካል ተሰጥቷል በሚል በተከራካሪ ወገኖች የቀረበ ክርክር በሌለበት ጉዳዩ በመጀመሪያ ደረጃ የቀረበለት የቡታጅራ አካባቢ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የስረ ነገር ስልጣን ያለው የፕራይቬታይዜሽን ኤጀንሲ ነው ማለቱ የቀረበውን ማስረጃ እና የፍርድ ቤቶችን ተፈጥሮኣዊ ባህሪን ያላገናዘበ ነው፡፡ በዚሁ ጉዳይ ላይ ይግባኝ የቀረበለት የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤትም ስህተቱን ከዚህ አኳያ አይቶ ማረም ሲገባው አቤቱታውን መሰረዙ የአመልካቾን ፍትህ የማግኘት ህገ መንግስታዊ መብት የገፈፈ መሰረታዊ ስህተት ሆኖ ተገኝቷል፡፡

በመጨረሻም የክልሉ ሰበር ችሎት በቀረበው ጉዳይ ላይ የሰበር ስልጣን የለኝም ያለውን በተመለከተ በአመልካቾም እንደ አንድ የሰበር ቅሬታ የተነሳ በመሆኑ አንድ ነገር ማለቱ ተገቢ ይሆናል፡፡ በኢ.ፌ.ዴ.ሪ. ህገ መንግስት የዳኝነትት ስልጣን በፌዴራል እና በክልል የተከፈለ ሲሆን የክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤቶች የሰበር ስልጣን የተሰጣቸው በክልል ጉዳይ ላይ ብቻ ስለመሆኑ የህገ መንግስቱ አንቀፅ 80(3(ለ)) ድንጋጌ ያስገነዝባል፡፡ የፌዴራል ፍርድ ቤቶች የዳኝነት ስልጣን በፌዴራል ጉዳዮች ላይ ስለመሆኑ እና ከዚህ ውስጥ አንዱ በፌደራል መንግስት የተመዘገቡ ተቋማት የክርክር ተካፋይ በሚሆኑባቸው ጉዳዮች ስለመሆኑን የፌዴራል ፍርድ ቤቶች ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀፅ 5(6) ይደነግጋል፡፡

በሌላ በኩል የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ እና ከፍተኛ ፍርድ ቤት በህግ በክልሎች እስከሚቋቋሙ ድረስ የዳኝነት ስልጣናቸው እንደቅደም ተከተላቸው ለክልል ከፍተኛ እና ጠቅላይ ፍርድ ቤት የተሰጠ መሆኑን የህገ መንግስቱ አንቀፅ 78(2) እና 80(4 እና 5) ድንጋጌ ያስገነዝባል፡፡ የክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በፌዴራል ጉዳይ ላይ በይግባኝ አይቶ የሰጠው የመጨረሻ ውሳኔ ላይ የሰበር አቤቱታ የሚቀርበው ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት ስለመሆኑ የፌዴራል ፍርድ ቤቶች መቋቋሚያ አዋጅ ቁር 25/1988 አንቀፅ 10(3) ይደነግጋል፡፡

አሁን በቀረበው ጉዳይ 1ኛ ተጠሪ በፌዴራል መንግስት የተቋቋመ ድርጅት በመሆኑ ተቋሙ ተካፋይ የሚሆንበት የፍርድ ቤት ክርክር የፌዴራል ጉዳይ ይሆናል፡፡ በፌደራል ጉዳይ ላይ የደቡብ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በይግባኝ አይቶ የስር ፍርድ ቤት ውሳኔን በማፅናት የሰጠው ውሳኔ የመጨረሻ በመሆኑ ከላይ በተጠቀሰው የህግ መንግስቱ እና የፌዴራል ፍርድ ቤቶች ማቋቋሚያ አዋጅ መሰረት

የሰበር ስልጣን ያለው ይህ ችሎት ነው፡፡ የዳኝነት የስረ ነገር ስልጣንን በተመለከተ ስልጣን ያለው መሆን ስላለመሆኑ የማረጋገጥ ቀዳሚ ኃላፊነት የፍርድ ቤቶች በመሆኑ የተከራካሪ ወገኖችን መቃወሚያ ወይም መከራከሪያ የሚጠብቅ አይደለም፡፡

በመሆኑም የክልሉ ሰበር ችሎት በጉዳዩ ላይ የሰበር ስልጣን የለኝም ማለቱ ህጉን በአግባቡ በመተርጎም ተግባራዊ ያደረገ ነው ከሚባል በቀር የሚነቀፍበት ምክንያት ባለመኖሩ ከዚህ አንፃር የቀረበውን የአመልካቾችን መከራከሪያ ችሎቱ አልተቀበለውም፡፡

ሲጠቃለል ይህንን ጉዳይ በተመለከተ ተከታዩ ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

## ውሳኔ

1. በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልላዊ መንግስት የቡታጂራ አካባቢ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ/10273 ላይ ታህሳስ 26/2010 ዓ.ም በዋለው ችሎት ተሰጥቶ በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ችሎት በፍ/ይ/መ/ቁ/09874 ላይ የካቲት 07/2010 ዓ.ም በዋለው ችሎት የፀደቀው ብይን በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁጥር 348(1) መሰረት ተሽሯል፡፡

2. አመልካቾች ክስ ያቀረቡበትን ጉዳይ በተመለከተ የዳኝነት ስልጣን የተሰጠው ለኢትዮጵያ ፕራይቬታይዜሽን ኤጀንሲ ቢሆንም ኤጀንሲው በስልጣኔ ስር አይወድቅም በማለት የመለሰ በመሆኑ እና የዳኝነት ተፈጥሯአዊ ስልጣን የመደበኛ ፍርድ ቤቶች ስለመሆኑ በኢ.ፌ.ዴ.ሪ. ህገ መንግስትም የተረጋገጠ በመሆኑ የቡታጅራ አካባቢ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ጉዳዩ የማየት የስረ ነገር ስልጣን አለው፡፡

3. የቡታጅራ አካባቢ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በአመልካቾች በቀረበለት ክስ ላይ የግራ ቀኙን ክርክር እና ማስረጃ በመስማት የመሰለውን እንዲወስን በፍ/ሥ/ሥ/ህግ ቁጥር 341(1) መሰረት ተወስኗል፡፡

## ትዕዛዝ

1.የዚህ ፍርድ ትክክለኛ ግልባጭ ለስር ፍርድ ቤት ይተላለፍ፡፡

2.የዚህን ሰበር ችሎት ክርክር ወጪ ግራ ቀኙ የራሳቸውን ይቻሉ፡፡

3.መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

አ/ኃ

የሰ/መ/ቁ.162106

ጥር 30 ቀን 2011 ዓ.ም

ዳኞች ፡- ተኽሊት ይመስል

ተፈሪ ገብሩ /ዶ/ር/

ቀነዓ ቂጣታ

ተሾመ ሽፈራው

ፀሐይ መንክር

አመልካች፡- ወ/ሮ ሙሉ ወንድሙ ተወካይ ዘላለም አበበ

1ኛወ/ሮ ዘመኗ ድንቁ

2ኛ አቶ እንግዳሰው ክብረት

3ኛ አቶ ክብረት ባልቻ

የሁሉም ተወካይ 2ኛ ተጠሪ ቀረቡ፡፡

መዝገቡን መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍርድ

1. በዚህ መዝገብ የተያዘው ጉዳይ የእርቅ ውል ስለማስፈረስ የቀረበ ክስ የሚመለከት ክርክር ሲሆን የጀመረው በኦሮሚያ ክልል አሰላ ከተማ ወረዳ ፍርድ ቤት የአሁን 1ኛ ተጠሪ በአመልካች እና ከ2ኛ-3ኛ በተጠቀሱ ተጠሪዎች በመዝገብ ቁጥር 01410 በ19/7/2010 ዓ.ም ባቀረቡት ክስ መነሻ ነው ፡፡ የአሁኗ 1ኛ ተጠሪ ያቀረቡት ክስ ባጭሩ በሥር ፍርድ ቤት 1ኛ ተከሣሽ የነበረ በዚህ መዝገብ 2ኛ ተጠሪ ሆኖ የተመዘገበው ባለቤታቸው መሆኑን ገልጸው፤ ባለቤታቸው ከወላጅ አባቱ በ500 ካሬ ሜትር ላይ ያረፈ ቤትና ይዞታ በ26/9/1999 ዓ.ም በተደረገ የስጦታ ውል ያገኙት የጋራ ንብረት ያላቸው ሲሆን ፤ይኸው ቤት በማስያዝ ከባንክ ገንዘብ የተበደሩ መሆኑን ጠቅሰው 2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች ውል ሰጪ አመልካች ደግሞ ውልተቀባይ በመሆን በ3/6/2008 ዓ.ም ያደረጉት የእርቅ ውል የባልና ሚስት በሆነው ንብረት የተደረገ በመሆኑ የእርቅ ውል በሌላቸው መብት የተደረገ በመሆኑ እንዲፈርስ ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡

2. የሥር ተከሳሾች ያቀረቡት የመከላከያ መልስ እንደተመለከተው 2ኛ ተጠሪ የእርቅ ውል በጋራ ንብረት የተደረገ በመሆኑ ውሉ ቢፈርስ እንደማይቃወም ሲገልጽ 3ኛ ተጠሪም የእርቅ ውል ሌላ ሰው ንብረት የተደረገ እኔም ደካማ ሽማግሌ በመሆኔ ውል ስለመደረጉ አላውቅም ብሏል። የአሁኑ አመልካች በበኩላቸው የአሁን 1ኛ ተጠሪ የእርቅ ስምምነት እንዲፈርስ ያቀረቡት ክስ ውድቅ መደረጉን፤ የስጦታ ውሉ እንደሚያውቁት፤ የሶጦታ ውል መደረጉን ካወቁ በኃላ ክስ አቅርበው በአመልካች፤2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች በ3/6/2008 ዓ.ም በተደረገው የእርቅ ስምምነት 2ኛ ተጠሪ 100 ካሬ ሜትር ብቻ ወስዶ ሌላው መሬት እንዲለቅ መስማማታቸውን ገልጸው የእርቅ ውሉ የሚፈርስበት ምክንያት የለም በማለት መከራከራቸውን መዝገቡ ያሳያል።
3. በዚህ አግባብ ክርክሩ የቀረበለትን የአሰላ ወረዳ ፍርድ ቤትም የግራቀኙን ክርክርና ማስረጃ ከመረመረ በኃላ የእርቅ ስምምነቱ የ1ኛ ተጠሪ መብትና ጥቅም የሚጎዳ በጋብቻ ንብረት ላይ የተደረገ ነው በማለት ስምምነቱን በመሻር ወስኗል። የአሁኑ አመልካች ለአርሲ ዞን ከፍተኛ ፍርደ ቤት ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት ይግባኝ አቤቱታ አቅርበው ተቀባይነት አላገኘም ። በመቀጠልም አመልካች ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሠበር ሰሚ ችሎት የሰበር አቤቱታ አቅርበው ፍርድ ቤቱ የአመልካችን አቤቱታ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት አይደለም በማለት በትዕዛዝ መዝገቡን ዘግቷል። የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህ ውሳኔ በመቃወም ለማሳረም ነው። አመልካች ሐምሌ 30/2010 ዓ.ም የተፃፈ አቤቱታ አቅርበው የእርቅ ውሉ የሚፈርስበት አንዳችም ሕጋዊ ምክንያት በሌለበት ሁኔታ እንዲፈርስ መወሰኑ ተገቢ አለመሆኑን ተደረገ የተባለው የስጦታ ውልም የጋራ ንብረት ባለተለየበት የተሰጠ በመሆኑ ሊሻር ይገባል በማለት ተከራክሯል። የአመልካችአቤቱታ የመረመረው አጣሪ ችሎትም የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሠበር ሠሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 253020 የተሰጠው ውሳኔ በፀናበት ሁኔታ በተመሳሳይ ጭብጥ ነገር ግን በሌላ መ/ቁ 289813 ውሳኔ የሰጠበት አግባብ ተጠሪዎች ባሉበት ጉዳዩን ማጣራት ይቻል ዘንድ ለዚህ ችሎት ያስቀርባል ተብሏል። ተጠሪዎችም ቀርበው በ14/02/2011 ዓ.ም የተፃፈ መልስ አቅርበው የሥር ፍ/ቤቶች ውሳኔ እንዲፃፍ አመልክቷል። የመልስ መልስም ቀርቧል።
4. ከሥር የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን እኛም የሥር ፍርድ ቤቶች የሰጡት ፍርድና ትዕዛዝ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት መሆን አለመሆኑን ክርክሩን እንደሚከተለው መርምረናል።
5. እንደመረመርነውም አመልካች አጥብቀው የሚከራከሩት ከ2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች ጋር ያደረጉት የእርቅ ስምምነት በሕግ አግባብ የተደረገ በመሆኑ ሊፈርስ አይገባም በሚል ነው። ከዚህ በተያያዘም የአሁኗ 1ኛ ተጠሪ አመልካች ባቀረቡት የአፈፃፀም መዝገብ ጣልቃ ገብተው በየደረጃው ክርክር ሲደረግ ቆይቶ በመ/ቁ253020 በ20/10/2010 ዓ.ም የመጨረሻ ውሳኔ ያገኘ በመሆኑ 1ኛ ተጠሪ አዲስ ክስ ሊያቀርቡ አይገባም የሚል ክርክርም ቀርቧል። ከሥር ፍርድ ቤት መዝገቡ መረዳት የተቻለው አመልካች፤ 2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች በ03/06/2008 ዓ.ም የእርቅ ስምምነት

አድርጓል ለዚህ እርቅ ውል መነሻ የሆነው ጉዳይ የአሁኑን 3ኛ ተጠሪ የጋራ ንብረት የሆነውን ለክርክሩ መነሻ የሆነውን ቤትና ይዞታ ለ1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች ከአመልካች እውቅና ውጭ ሰጥቷል በማለት ስጦታው ለማስፈረስ በወረዳ ፍርድ ቤት ክስ በማቅረባቸው ነው፡፡አመልካች፤ 2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች ጉዳያቸው በእርቅ የቋጩ በመሆኑ የእርቅ ስምምነቱ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 277/1/ መሠረት ተመዝግቦ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ አመልካች በ03/06/2008 ዓ.ም በተደረገው የእርቅ ስምምነት መሠረት እንዲፈጸምላቸው የአፈፃፀም መዝገብ ከፍቷል፡፡ የአሁኗ 1ኛ ተጠሪ አመልካች ያቀረቡት አፈፃፀም መብትና ጥቅሜ የሚነካ ነው በማለት የክርክሩ ተከፋይ ሆናለች፡፡ ጉዳዩ መጀመሪያ የተመለከተው የወረዳው ፍርድ ቤት የእርቅ ስምምነቱ ፍርድ/ውሳኔ/ ስላልሆነ የአመልካች መቃወሚያ ተገቢነት የለውም በማለት ስምምነቱን በመሻር ቤቱ የ1ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች ነው በማለት የወሰነ ሲሆን አመልካች ይግባኝ ቢጠይቁም ተቀባይነት አላገኙም፡፡

6. አመልካች የሥር ፍ/ቤቶች ውሳኔ በመቃወም ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሠበር ሰሚ ችሎት የሰበር አቤቱታ አቅርበው ፍርድ ቤቱም ግራቀኙ ከአከራከረ በኋላ በመዝገብ ቁጥር 3770 በሆነው ላይ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 277/1/ የተመዘገበ የእርቅ ውል የአፈጻጸም ክስ ምክንያት መሆኑ እየታወቀ የአሁኗ 1ኛ ተጠሪ የተዘጋው መዝገብ የእርሷን መብት የሚጎዳ ከሆነ በዛ መዝገብ የእርቅ ውል እንዲሻር ከመጠየቅ በቀር በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 358 ያቀረበችው መቃወሚያ ማስተናገድ የክርክር አመራር ሥርዓት ያልተከተለ የአመልካች መብት የሚያሳጣ ነው በማለት ውሳኔውን ሽሮ 1ኛ ተጠሪ አለኝ የምትለውን ህጋዊ መብት ካለ ልትጠይቅ እንደምትችል በትዕዛዝ ክፍሉ አመላክቷል፡፡

7. በክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው አመልካች ከ2ኛ እና 3ኛ ተጠሪ ያደረጉት የእርቅ ውል በፍርድ ቤት የተመዘገበ መሆኑ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሠበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ 253020 በ20/01/2010 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ ግልባጭ አረጋጋጭ ነው፡፡ የአሁኗ 1ኛ ተጠሪ የእርቅ ስምምነቱ ለማሰረዝ አዲስ ክስ ማቅረቧን መዝገቡ ያመላክታል፡፡ የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት በአፈፃፀም መዝገብ ጣልቃ መግባት ተገቢ አለመሆኑን በመግለጽ የሥር ፍ/ቤቶች ውሳኔ ሽሯል ፡፡ የአሁኗ 1ኛ ተጠሪ በእርቅ ስምምነት የተዘጋው መዝገብ በመቃወም ያቀረቡት አቤቱታ ስለመኖሩ መዝገቡ አያሳይም፡፡ አመልካች፣ 2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች ባደረጉት የእርቅ ስምምነት 2ኛ ተጠሪ 100 ካሬ ሜትር ብቻ ወስዶ ቀሪው 400 ካሬ ሜትር እንዲመልስ የተዋዋሉ መሆኑን ከቀረበው ክርክር ተገንዝበናል በመሠረቱ ተከራካሪ ወገኖች ጉዳያቸው በእርቅ መቋጨት እንደሚችሉ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 274 እና ተከታይ ድንጋጌዎች ያስገነዝባሉ፡፡ የእርቅ ስምምነቱ በፍርድ ቤት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 277/1/ መሠረት ተረጋግጣ ከተመዘገበ በእርቁ መሠረት እንዲፈጽም ፍ/ቤት ትዕዛዝ ሊሰጥ እንደሚችል ላይ የተገለጸው ህግ 277/2/ በግልጽ ያመለክታል፡፡ ከዚህ የምንረዳው የእርቅ ስምምነት የአፈፃፀም ክስ ሊቀርብበት የሚችል ህጋዊ ውጤት ያለው ተግባር መሆኑን ነው፡፡ በተያዘው ጉዳይ 1ኛ ተጠሪ አመልካች ፣2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች ያደረጉት ስምምነት መነሻ

በማድረግ የተዘጋው መዝገብ ከሚያንቀሳቅሱ በቀር አዲስ ክስ ማቅረባቸውን በሕጉ የተዘረጋው የሙግት አመራር ሥርዓት የተከተለ ሆኖ አልተገኘም፡፡ በመሆኑም አመልካች የእርቅ ስምምነት የፀደቀበት መዝገብ ላይ መቃወሚያ አቅርበው የስጦታ ውል ያለ መሆን አለመሆኑን አለ ከተባለም የጋራ ነው የተባለውን ንብረት 3ኛ ተጠሪ ብቻቸውን ሊሰጡ የሚችሉበት ህጋዊ ምክንያት መኖር አለመኖሩን ተመርምሮ ከሚወሰን በቀር የአሁና 1ኛ ተጠሪ ክስ አቅርበው በየደረጃው ያሉ ፍርድ ቤቶችም የክርክሩ ይዘትና ባሕሪ በአግባቡ ሳይገናዘቡ የእርቅ ስምምነቱ እንዲሻር መወሰናቸው በሕጉ የተዘረጋው የሙግት አመራር ሥርዓት ያልተከተለ መሠረታዊ የህግ ስሕተት ያለበት ነው ብለናል፡፡ የአሁኗ 1ኛ ተጠሪ አመልካች፤ 2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች በ3/6/2008 ዓ.ም ያደረጉት የእርቅ ስምምነት የፀደቀበት መዝገብ ከሚያንቀሳቅሱ በስተቀር አዲስ ክስ ማቅረብ የሚችሉበት የህግ አግባብ የለም ብለናል፡፡ በዚህም ተከታዩን ወስነናል፡፡

**<u>ውሳኔ</u>**

1. በኦሮሚያ ክልል የአሰላ ከተማ ወረዳ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 01410 በ14/06/2010 ዓ.ም፤ የአርሲ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 79705 በ29/08/2010 ዓ.ም ፤ የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ስሚ ችሎት በመ/ቁ289813 በ03/11/2010 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጡት ውሳኔ እና ትዕዛዝ በድምፅ ብልጫ ተሽሯል፡፡
2. የአሁኗ 1ኛ ተጠሪ የእርቅ ስምምነት የፀደቀበት መዝገብ ባለበት ሁኔታ በሌላ መዝገብ አዲስ ክስ ሊያቀርቡ አይገባም በማለት ወስኗል፡፡
3. 1ኛ ተጠሪ የእርቅ ስምምነት የፀደቀበት መዝገብ የማንቀሳቀስ መብታቸው ይህ ውሳኔ አያግዳቸውም ብለናል፡፡
4. የዚህ ፍ/ቤት ክርክር ያስከተለው ወጪና ኪሣራ ግራቀኙ የየራሳቸው ይቻሉ ብለናል፡፡
5. የውሳኔ ግልባጭ ተረጋግጦ ለሥር ፍ/ቤቶች ይተላለፍ ብለናል፡፡
6. ውሳኔው በ26/06/2011 ዓ.ም ተነበበ፡፡

መዝገቡ ዘግተን ወደ ፍ/ቤት መልሰናል፡፡

የማይነበብ የአራት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

*ሠ/ኃ*

## የልዩነት ሃሳብ

እኔ ስሜ በአራተኛ ተራ ቁጥር የተጠቀሰዉ ዳኛ 1ኛ ተጠሪ የእርቅ ስምምነት በጸደቀበት መዝገብ ላይ የመቃወም አቤቱታ ማቅረብ ከሚትችል በቀር አዲስ ክስ ማቅረብ አትችልም በሚለዉ በአብላጫዉ ድምጻሜ ስለማልስማማ በሃሳብ ተለይቻለሁ፡፡

1ኛ ተጠሪ ከሳሽ በመሆን በስር ፍርድ ቤት የጠየቁት ዳኝነት የአሁን 2ኛ ተጠሪ የባልና ሚስት የጋራ ንብረታቸዉ የሆነውን የቤት መስሪያ ቦታ ለአመልካች እና ለ3ኛ ተጠሪ በመስጠት ያደረጉት የእርቅ ስምምነት በፍርድ ኃይል እንዲፈርስ ነዉ፡፡ በዚህ መልኩ ዳኝነት የተጠየቀበት ስምምነት በባህሪው በፍትሐብሔር ህጉ አንቀጽ 3307 ስር በተመለከተዉ ድንጋጌ ስር የሚወቅድ ሲሆን፣ ይህ ድንጋጌም ተዋዋይ ወገኖች አንዱ ላንዱ አንድን ነገር ትቶ ወይም ሰጥቶ የተጀመረዉን ክርክር የሚያቆሙበት ወይም የሚፈጠረውን ክርክር አስቀድመው የሚያስቀሩት አንድ ውል ስለመሆኑ ያስገነዝባል፡፡ በህግ ተለይቶ ከተመለከቱት ሁኔታዎች በቀር ውሎች ተፈፃሚነታቸዉ ውሉን ባደረጉት ሰዎች ላይ ብቻ የተገደቡ ስለመሆናቸው በፍትሐብሔር ህጉ አንቀጽ 1711፣ 1731 እና 1952(1) ስር ከተመለከቱት ድንጋጌዎች ይዘት እና መንፈስ መገንዘብ ይቻላል፡፡ ይህም የተፈጠረዉን ወይም ሊፈጠር የሚችለውን ክርክር ለመጨረስ ግራ ቀኝ የሚያደርጓቸዉ ስምምነቶች የስምምነቱ አካል ያልሆነውን 3ኛ ወገን ሊያስገድድ የማይችል መሆኑን ያሳያል፡፡ የሦስተኛ ወገንን መብትና ጥቅም በሚነካ መልኩ የሚደረግ የእርቅ ስምምነትም ህገ ወጥ ነዉ፡፡ በመሆኑም በአመልካች፣ በ2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች መካከል ተደርጎ በፍርድ ቤት የፀደቀው እና 1ኛ ተጠሪ ላቀረቡት የዳኝነት ጥያቄ መሠረት ያደረጉት ስምምነቱን ካደረጉት ሰዎች አልፎ 1ኛ ተጠሪን ሊያስገድድ የሚችልበት የህግ ምክንያት የለም፡፡

አብላጫው ድምጽ 1ኛ ተጠሪ ስምምነቱ በጸደቀበት መዝገብ ላይ በፍ/ብ/ሥ/ሥርዓት ህጉ አንቀጽ 358 መሠረት የመቃወም አቤቱታ ማቅረብ እንጂ አዲስ ክስ ሊያቀርቡ አይችሉም በሚል ድምዳሜ ላይ የደረሰው በፍርድ ቤት የጸደቀ ስምምነት እንደ ፍርድ ተቆጥሮ ሊፈጸም የሚችል መሆኑን ነዉ፡፡ በርግጥም ግልግል በተዋዋይ ወገኖች ይግባኝ ሳይኖረዉ መጨረሻ ሆኖ እንደተፈረደ ፍርድ እንደሚቆጠር በፍትሐብሔር ህጉ አንቀጽ 3312 ስር የተመለከተ ሲሆን፤ በፍርድ ቤት የፀደቀ የእርቅ ስምምነት እንደ ፍርድ እንደሚቆጠር በፍ/ብ/ሥ/ሥርዓት ህጉ አንቀጽ 277(2) ስርም ተመልክቷል፡፡ ይሁንና እንደ ፍርድ ሆኖ አስገዳጅ የሚሆነው በተዋዋይ ወገኖች ላይ ብቻ ስለመሆኑ ከየድንጋጌዎቹ መረዳት ይቻላል፡፡ በግራ ቀኝ ስምምነት ተደርጎበት በፍርድ ቤት በጸደቀ የእርቅ ስምምነት ላይ የተመለከተ ዉሳኔ ግራ ቀኝ ወደው እና ፈቅደዉ ያደረጉትን ስምምነት መነሻ ያደረገ ውሳኔ እንጂ መደበኛ የሙግት ሂደትን ተከትሎ የህግ እና የፍሬ ነገር ክርክር ተደርጎበት በፍርድ ቤት ተለይቶ የተሰጠ ፍርድ/ውሳኔ ባለመሆኑ እንደ መደበኛ ፍርድ/ውሳኔ ሊታይ የሚገባውም አይደለም፡፡ በመሆኑም እንደ ፍርድ/ውሳኔ እንደሚቆጠር ከፍ ሲል በተመለከቱት ድንጋጌዎች የተመለከተው የእርቅ ስምምነቱን ያደረጉ ሰዎች ሊገደዱበት እንደሚገባ

እና በተመሳሳይ ጉዳይ ላይ በድጋሜ ለፍርድ ቤት የሚቀርብ ክርክር ተቀባይነት እንደሌለዉ ለማስገንዘብ ያህል እንጂ መደበኛውን የፍርድ ሂደት ተከትሎ በፍርድ ቤቱ በእራሱ እንደተሰጠ ፍርድ እንዲወሰድ ታስቦ ነው ለማለትም አይቻልም፡፡

በሌላ በኩል የፍ/ብ/ሥ/ሥርዓት ህጉ አንቀጽ 358 መሠረታዊ ዓላማ እና አስፈላጊነት አንድ ክርክር በሂደት ላይ በነበረበት ወቅት በፍ/ብ/ሥ/ሥርዓት ህጉ አንቀጽ 40፣ 41 እና 43 መሠረት ጣልቃ ለመግባት መብት ያለዉ ወገን በተለያየ ምክንያት በክርክሩ ጣልቃ ገብቶ መብቱን ለማስከበር ያልቻለ ወገን ውሳኔው ከተሰጠ በኂላም ቢሆን ወደ ክርክሩ ገብቶ መብቱን እንዲያስከብር ለማስቻል ነዉ፡፡ በዚህ መልኩ የቀረበ የመቃወም አቤቱታ ተቀባይነት ያገኘ እንደሆነ ክርክሩ የሚሰማው የመጀመሪያ ክርክር በተሰማበት ሥነ ሥርዓት መሠረት ስለመሆኑም የህጉ አንቀጽ 360 ድንጋጌ ያስገነዝባል፡፡ ከላይ እንደተገለጸው የእርቅ ስምምነትን በማጽደቅ የሚሰጥ ውሳኔ ተዋዋይ ወገኖች በስምምነታቸው የደረሱበትን ውሳኔ እንጂ ፍርድ ቤት በክርክር ሂደት አረጋግጦ የሚሰጥ ውሳኔ ባለመሆኑ መብት ያለዉ ወገን በክርክሩ ወቅት ከፍ ሲል በተመለከቱት የፍ/ብ/ሥ/ሥርዓት ህጉ ድንጋጌዎች መሠረት ጣልቃ ሊገባ ይችላል ተብሎ አይጠበቅም፡፡ በዚህ መልኩ ጣልቃ እንዲገባ የማይጠበቅበት ሰው ደግሞ በፍ/ብ/ሥ/ሥርዓት ህጉ አንቀጽ 358 መሠረት የመቃወም አቤቱታ ሊያቀርብ አይችልም፡፡

ከዚህ ሁሉ የምንረዳው በፍ/ብ/ሥ/ሥርዓት ህጉ አንቀጽ 358 እና ተከታዮቹ ስር ከመቃወም አቤቱታ አቀራረብ ጋር በተያያዘ የተደነገገው ድንጋጌ መደበኛ የክርክር ሂደትን ተከትሎ በፍርድ ቤት የተሰጠን ውሳኔ ታሳቢ በማድረግ የተቀረጸ መሆኑን ነዉ፡፡ ከዚህ አንፃር ሲታይ 1ኛ ተጠሪ በአመልካች፣ በ2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች መካከል የተደረገ የእርቅ ስምምነት መብቴን ይነካል የሚሉ ከሆነ፣ የእርቅ ስምምነት በጸደቀበት መዝገብ ላይ የመቃወም አቤቱታ ማቅረብ ሳያስፈልግ፣ አዲስ ክስ አቅርበዉ ስምምነቱ እንዲፈርስ ከመጠየቅ ሊከለከሉ የሚችሉበት የህግ ምክንያት የለም፡፡ በመሆኑም የስር ፍርድ ቤቶች የ1ኛ ተጠሪን ክስ ተቀብለዉ ለክርክሩ መነሻ የሆነው የእርቅ ስምምነት ሊፈርስ ይገባል በማለት የሰጡት በአግባቡ ነው ከሚባል በስተቀር መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነው ለማለት የሚያስችል የህግ ምክንያት የሌለ በመሆኑ ሊጸና ይገባል የሚል እምነት ስላለኝ ከሌሎች ባልደረቦቼ በሃሳብ ተለይቻለሁ፡፡

የማይነበብ የአንድ ዳኛ ፊርማ አለበት፡፡

ሠ/ኃ

የሰ/መ/ቁ. 169522

ህዳር 29 ቀን 2012 ዓ.ም

ዳኞች፡ እትመት አሰፋ

ጳውሎስ ኦርሺሶ

ፀሐይ መንክር

መላኩ ካሳዬ

እስቲበል አንዱዓለም

አመልካች፡ አቶ ሲራጅ አባፎጊ ቀርበዋል፡፡

ተጠሪዎች፡ 1. አቶ አባቦር አባጨብሳ

2. አቶ ነዚፍ አባጨብሳ

3. ወ/ሮ ሙራዴ አባጨብሳ

4. አቶ ኑሩ አባጨብሳ

5. አቶ መጫ አባጨብሳ

(2–5) የቀረበ የለውም፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍርድ

በዚህ መዝገብ ላይ የቀረበው ጉዳይ የገጠር መሬት ይዞታ ክርክርን የሚመለከት ነው፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው የኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት በመ/ቁ/300663 ላይ ታህሳስ 15/2011 ዓ.ም በዋለው ችሎት የጅማ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰቃ ወረዳ ፍርድ ቤትን ውሳኔ በማፅናት በሰጠው ትዕዛዝ ላይ በአሁን አመልካች የቀረበለትን የሰበር አቤቱታ ለሰበር ችሎት ክርክር አያስቀርብም በማለት የሰጠው የመጨረሻ ትዕዛዝ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ነው በማለት ለማስለወጥ ነው፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ እንዲህ ነው፡፡ የአሁን አመልካች ታህሳስ 03/2009 ዓ.ም ፅፈው በአሁን 1ኛ ተጠሪ ላይ በሰቃ ወረዳ ፍርድ ቤት ባቀረቡት ክስ መገኛ ቦታ እና አዋሳኙ በክሱ ውስጥ

የተጠቀሰውን የገጠር መሬት ይዞታ ወላጅ እናታቸው ከ1977 ዓ.ም ጀምሮ እስከ 1994 ዓ.ም ድረስ ተጠቅመውበት ሲሞቱ ተላልፎላቸው እስከ 2009 ዓ.ም ድረስ ግብር እየከፈሉበት እና የተለያዩ አትክልቶችን ተክለው አልምተው በመጠቀም ላይ እያሉ የአሁን 1ኛ ተጠሪ መስከረም 2009 ዓ.ም ወደ ይዞታው ገብተው በኃይል በመያዝ ቤት መስራት ሲጀምሩ ለቀበሌ አመልክተው የጀመሩትን ግንባታ እንዲያቆሙ ቢነገራቸውም ፈቃደኛ አለመሆናቸውን በመግለፅ በፍርድ ኃይል ተገደው የጀመሩትን ግንባታ አፍርሰው ይዞታውን እንዲያስረክቧቸው ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡

በዚሁ ክስ ላይ መልስ እንዲሰጥ በታዘዘው መሰረት የአሁን 1ኛ ተጠሪ ታህሳስ 12/2009 ዓ.ም በተፃፈ መልስ ክርክር የተነሳበትን ይዞታ ለአሁን አመልካች እናት በኪራይ የሰጧቸው ከመሆኑ ውጭ ይዞታው የራሳቸው ለመሆኑ የይዞታ ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ያላቸው መሆኑን በመግለፅ ልለቅ አይገባም በማለት ተከራክረዋል፡፡

ጉዳዩ የቀረበለት ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክር እና ማስረጃ ከሰማ በኋላ የካቲት 17/2009 ዓ.ም በዋለው ችሎት የአሁን 1ኛ ተጠሪ ክርክር በተነሳበት ይዞታ ላይ የጀመሩትን ግንባታ አፍርሰው መሬቱን ለአመልካች እንዲያስረክቡ ወስኗል፡፡ በዚሁ ውሳኔ ላይ በአሁን 1ኛ ተጠሪ ይግባኝ የቀረበለት የጅማ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን የይግባኝ ክርክር ከሰማ በኋላ ጉዳዩ እንደገና ተጣርቶ እንዲወሰን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁጥር 343(1) መሰረት በነጥብ መልሷል፡፡ በዚሁ መነሻነት የወረዳው ፍርድ ቤት በታዘዘው መሰረት ጉዳዩን አጣርቶ ህዳር 28/2010 ዓ.ም በዋለው ችሎት በቀደመው ውሳኔ መሰረት ወስኗል፡፡ ከዚህ በኋላ ስላለው የክርክር ሂደት መዝገቡ የሚገልፀው ነገር ባይኖርም አመልካች በሰበር አቤቱታቸው ጉዳዩ እስከዚህ ሰበር ችሎት ደርሶ የፀና መሆኑን ገልፀዋል፡፡

በዚሁ መሰረት አመልካች የአፈፃፀም መዝገብ ከፍተው ጉዳዩ በሂደት ላይ እንዳለ የአሁን ከ2ኛ እስከ 5ኛ ተጠሪዎች በመቃወም አመልካችነት ይቀርባሉ፡፡ የወረዳው ፍርድ ቤትም በመቃወም አቤቱታው ላይ ግራ ቀኙን ካከራከረ በኋላ ጥቅምት 28/2011 ዓ.ም በዋለው ችሎት ክርክር የተነሳበት ይዞታ በአቶ አባጨብሳ አባጎሹ ስም ግብር ሲገበርበት የነበረ ለመሆኑ እና በክልሉ ገጠር መሬት አስተዳደር እና አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር 130/1999 አንቀፅ 5(5) መሰረት ለአሁን 1ኛ ተጠሪ እና ስር ፍርድ ቤት የመቃወም አመልካቾች የተላለፈ መሆኑን አረጋግጫለሁ በማለት ቀድሞ የሰጠውን ውሳኔ በመሻር ለአሁን ተጠሪዎች ወስኗል፡፡ ይህ ውሳኔ እስከ ክልሉ ሰበር ችሎት ድረስ የፀና ለመሆኑ ከመዝገቡ ይዘት እንዲሁም የሰበር አጣሪ ችሎቱ አስቀርቦ ከመዝገብ ጋር ካያያዛቸው የስር ፍርድ ቤት ውሳኔዎች ይዘት ለመገንዘብ ተችሏል፡፡

የአሁን የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ነው፡፡ አመልካች ጥር 20/2011 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ በስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔና ትዕዛዝ ላይ ተፈፅሟል

ያሉትን መሰረታዊ የህግ ስህተት ጠቅሰው በዚህ ችሎት እንዲታረምላቸው ጠይቀዋል፡፡ ፍሬ ቃሉም የአሁን ከ2ኛ እስከ 5ኛ ያሉት ተጠሪዎች በመቃወም አመልካችነት ባቀረቡት አቤቱታ ላይ መጋቢት 17/2010 ዓ.ም በሰጡት የፅሁፍ መልስ ያቀረቧቸውን አምስት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያዎችን በመዘርዘር የወረዳው ፍርድ ቤት በመቃወሚያዎቹ ላይ ብይን ሳይሰጥ ያለፈ መሆኑን፣ ክርክር የተነሳበት ይዞታን በተመለከት በአስተዳደር ክፍል ተጣርቶ እንዲቀርብ የተሰጠው ትዕዛዝ እሳቸው በሌሉበት የአሁን ተጠሪዎች እና ሽማግሌዎች በተገኙበት ብቻ በአንድ ወገን በቀረበ ማስረጃ ላይ ተንተርሶ የቀረበ ከመሆኑም በላይ በዚሁ ማስረጃ ላይ ተገቢውን ክርክር ለማቅረብ እድል ያልተሰጣቸው መሆኑን፣ ማስረጃውም ስለዚሁ ክርክር ስለተነሳበት ይዞታ ቀደም ሲል ከአንዴም ሶስት ጊዜ ተጣርቶ ከቀረበው የአስተዳደር ክፍል ሪፖርት ጋር የሚቃረን መሆኑን፣ የወረዳው ፍርድ ቤት እነዚህን ሁኔታዎች አልፎ ውሳኔ መስጠቱ እና ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤትም ሆነ የክልሉ ሰበር ችሎት ያለማረማቸው መሰረታዊ የህግ ስህተት በመሆኑ ሊታረም ይገባል የሚል ነው፡፡

የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ አመልካች ክርክር በተነሳበት ይዞታ ላይ ቤት ሰርተው ሲጠቀሙበት የነበረ ለመሆኑ ከወረዳው መሬት አስተዳዳር የቀረበው ማስረጃ እየገለፀ የስር ፍርድ ቤት ይህንን ማስረጃ አልፎ መሬቱ አይገባቸውም በማለት የወሰነበት አግባብ ለዚህ ሰበር ችሎት ቀርቦ እንዲታይ በመታዘዙ ግራ ቀኙ የፅሑፍ ክርክር እንዲለዋወጡ ተደርጓል፡፡

ተጠሪዎች ወኪላቸው በሆኑት 2ኛ ተጠሪ በኩል መጋቢት 24/2011 ዓ.ም ፅፈው ባቀረቡት መልስ አመልካች በስር ፍርድ ቤት አቅርቤ ብይን ሳይሰጥበት ታልፏል ብለው በዘረዘሯቸው መቃወሚያዎች ላይ ዝርዝር መልስ በመስጠት ክርክር የተነሳበት ይዞታ የቤተሰቦቻቸው በመሆኑ የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ የሚነቀፍ አይደለም በማለት ተከራክረዋል፡፡

አመልካች በበኩላቸው ሚያዝያ 25/2011 ዓ.ም በሰጡት የመልስ መልስ ተጠሪዎች በሰበር ማስቀረቢያ ነጥቡ ላይ የሰጡት መልስ ባለመኖሩ እንዳመኑ ተቆጥሮ በአቤቱታው መሰረት ሊወሰን ይገባል የሚል እና ቀድሞ ያቀረቡትን መከራከሪያ የሚያጠናክር ምክንያት በማከል ሞግተዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ ይዘት ጠቅለል ባለ መልኩ ከላይ የተመለከተውን ሲመስል ችሎቱም በማስቀረቢያ ነጥቡ ሳይወሰን ከሰበር ቅሬታው አኳያ በስር ፍርድ ቤቶች የነበረውን የክርክር አመራር ፈትሿል፡፡

በዚሁ መሰረት የአሁን አመልካች በአሁን ከ2ኛ እስከ 5ኛ ባሉት ተጠሪዎች በቀረበ የመቃወም አቤቱታ ላይ መጋቢት 17/2010 ዓ.ም በሰጡት መልስ በዝርዝር አምስት፣ በይዘት

ደረጃ ደግሞ አራት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ማቅረባቸውን፤ እነዚህም 1ኛ/ የመቃወም አመልካቾቹ ከአሁን 1ኛ ተጠሪ ጋር በተለያየ ደረጃ ክርክር ሲደረግ ያውቁ የነበረ በመሆኑ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት በሰ/መ/ቁ/56795 ላይ በሰጠው አስገዳጅ የህግ ትርጉም መሰረት ቀድመው የሚያውቁን ክርክር ውጤት ጠብቀው በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁጥር 358 መሰረት መቃወሚያ ሊያቀርቡ አይችሉም፤ 2ኛ/ የመቃወም አመልካቾቹ ከአቤቱታቸው ጋር ያቀረቧቸው የግብር ካርኒዎች የእነርሱን ስም የማይጠራ በመሆኑ እና ወራሽ ለመሆናቸውም ያቀረቡት ማስረጃ ባለመኖሩ መቃወሚያ ባቀረቡበት ጉዳይ ላይ መብት ወይም ጥቅም የላቸውም፤ 3ኛ/ የመቃወም አመልካቾቹ በጉዳዩ ላይ መብት ወይም ጥቅም አላቸው ቢባል እንኳን ክርክር የተነሳበትን ይዞታ ከ12 ዓመት በፊት ከእናቴ ተላልፎልኝ ይዤ እየተገለገልኩበት ያለሁ በመሆኑ በክልሉ መሬት አስተዳደር እና አጠቃቀም ደንብ ቁጥር 151/2005 አንቀፅ 32 መሰረት ጥያቄያቸው በይርጋ ይታገዳል፤ 4ኛ/ አመልካቾች ይዞታው በውርስ ተላልፎልናል የሚሉ ከሆነ ማንን እንደወረሱ እና አውራሻቸው መቼ እንደሞቱ በአቤቱታቸው ውስጥ አልጠቀሱም፤ ይህ መሆኑም አቤቱታው በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁጥር 216 መሰረት ተሟልቶ ያልቀረበ እና አመልካች ከፍ/ብ/ህ/ቁጥር 1000 አኳያ ማቅረብ የሚችለውን መከራከሪያ ያጣበበብኝ በመሆኑ ውድቅ ሊደረግ ይገባል የሚል መሆኑን የሰበር አጣሪ ችሎቱ አስቀርቦ ከመዝገብ ካያያዘው ሰነድ ለመረዳት ተችሏል፡፡

የቀረበው መቃወሚያ ይህ ሲሆን ጉዳዩን የተመለከተው የወረዳ ፍርድ ቤት የመቃወም አመልካቾች ዋናው ክርክር ሲካሄድ ያውቁ ነበር በማለት በቀረበው መቃወሚያ ላይ ብቻ ትዕዛዝ ሰጥቶ ስለ ሌሎቹ ምንም ሳይል ማለፉን ከስር ፍርድ ቤት የመዝገብ ግልባጭ ለመገንዘብ ተችሏል፡፡

አንድን ክርክር የሚሰማ ፍርድ ቤት በተከራካሪ ወገን በተለያየ የክርክር ደረጃ የሚቀርብለትን መከራከሪያ በተመለከተ ስለመቀበሉም ሆነ ስላለመቀበሉ ምክንያትን መሰረት ያደረገ ግልፅ ምላሽ ሊሰጥ ይገባል፡፡ በተለይ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ በባህሪው ወደ ዋናው ክርክር መግባት ሳያስፈልግ የተጀመረውን ክርክር በመጀመሪያው የክርክር ምዕራፍ ላይ የማቋረጥ ውጤት ያለው በመሆኑ ጉዳዩን የሚያየው የዳኝነት አካል የቀረበውን መቃወሚያ ያልተቀበለበትን ግልፅ ምክንያት ሳያሰፍር ወደ ፍሬ ነገር ክርክር ሊሸጋገር እንደማይገባ ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ/244 እና 245 ደንጋጌዎች ይዘት እና መንፈስ መረዳት ይቻላል፡፡ ይህ ሳይፈፀም በዝምታ ታልፎ በፍሬ ነገር ላይ አከራክሮ መወሰን ተከራካሪዎችን አስፈላጊ ላልሆነ እንግልት እና ወጪ የሚዳርግ ጉልህ የሆነ የጉዳይ አመራር እና የሥነ ሥርዓት ግድፈት በመሆኑ ተቀባይነት አይኖረውም፡፡

አሁን በቀረበው ጉዳይ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ ያየው የወረዳው ፍርድ ቤት በአመልካች ከቀረበለት በርካታ መቃወሚያዎች ውስጥ በአንዱ ላይ ብቻ ትዕዛዝ ሰጥቶ ሌሎቹን በዝምታ አልፎ በፍሬ ነገር ላይ ውሳኔ መስጠቱ እንዲሁም በየደረጃው ያሉት ፍርድ ቤቶችም ይህንን ስህተት ሳያርሙ ማለፋቸው መሰረታዊ የፍትሐብሔር ጉዳይ የሙግት አመራር ሥነ ሥርዓት ስህተት ሆኖ ተገኝቷል፡፡

በሌላ በኩል ክርክር የተነሳበት ይዞታ በተመለከተ ተጣርቶ እንዲቀርብ በወረዳው ፍርድ ቤት በተለያየ ጊዜ በተሰጠ ትዕዛዝ መነሻነት የሰቃ ጮቆርሳ ወረዳ የገጠር መሬት አጠቃቀም ጽ/ቤት በቁጥር BUB/244/2010 ህዳር 19/2010 ዓ.ም በሰጠው መግለጫ የአሁን አመልካች እናት ከ30 ዓመት በፊት ይዘው ቤት ሰርተውበት ሲጠቀሙበት ቆይተው እሳቸው ሲሞቱ ወደ አመልካች የተላለፈ መሆኑን፤ አመልካችም አትክልት ተክሎበት የመንግስት ግብር እየገበረ ያለ እና ይዞታው በመንገድ ግንባታ ምክንያት በተነካ ጊዜም አመልካቹ ካሳ የተከፈለው መሆኑን የገለፀ ሲሆን ሰኔ 13/2010 ዓ.ም በሰጠው መልስ ደግሞ በይዞታው ላይ ላለፉ ሃምሳ ዓመታት ግብር ሲከፈል የነበረው በአቶ አባጨብሳ አባጎሹ ስም መሆኑን እና ክርክር በሚደረግበት ወቅትም ይዞታው በመቃወም አመልካቾች እጅ የነበረ ስለመሆኑ አጣርቶ ሪፖርት ማቅረቡን ለመረዳት ተችሏል፡፡

እነዚህ በወራት ልዩነት ከአንድ አስተዳደር መስሪያ ቤት የተሰጡ ማረጋገጫዎች በይዘት ፍፁም ተቃራኒ ሲሆኑ ጉዳዩን በያዘው ፍርድ ቤት በምን መልኩ እንዲህ ዓይነት ማረጋገጫ ሊሰጥ እንደቻለ እንኳን ለማጣራት የተወሰደ እርምጃ ስለመኖሩ መዝገቡ የሚገልፀው ነገር የለም፡፡

በመሰረቱ በፍርድ ቤት ከቀረበ ክርክር ጋር በተያያዘ ከአስተዳደር ክፍል የሚሰጥ መግለጫ እንደየአግባብነቱ ለፍርድ ቤቱ ከቀረቡት ሌሎች የሰው እና የሰነድ ማስረጃዎች ይዘት ጋር ተገናዝቦ የሚወሰድ እንጂ በራሱ የመጨረሻ ማስረጃ አይደለም፡፡ ከአስተዳደር ክፍል የሚሰጥ መግለጫ በራሱ የመጨረሻ ነው የሚባል ከሆነ በፍርድ ቤት ዳኝነት በተጠየቀበት ጉዳይ ላይ ወሳኙ ጉዳዩን የያዘው ፍርድ ቤት ሳይሆን አስተዳደር ክፍሉ ይሆናል ማለት ነው፡፡ ይህ መሆኑ ደግሞ በህገ መንግስት በዳኝነት ሊያልቁ በሚችሉ ጉዳዮች ላይ ለመደበኛ ፍርድ ቤት የተሰጠውን የዳኝነት ስልጣን ለሌላ አካል አሳልፎ የመስጠት ውጤትን የሚያስከትል በመሆኑ ፍርድ ቤቶች ከአስተዳደር ክፍል በሚቀርቡላቸው መግለጫዎች አቀባበል እና ምዘና ላይ ጥብቅ ጥንቃቄ ሊወስዱ ይገባል፡፡

አሁን በቀረበው ጉዳይ የተስተዋለው ይኸው ከላይ የተጠቀሰው ስጋት ነው፡፡ መጀመሪያ ክርክር የተነሳበት ይዞታ የአሁን አመልካች ስለመሆኑ በምስክሮች አረጋግጫለሁ የሚል መግለጫ ሲቀረብ ለአመልካች ተወሰነ፡፡ በኋላ ላይ ደግሞ ይዞታው የመቃወም አመልካቾች አባት ለመሆኑ

አጣርቻለሁ ሲባል ለተጠሪዎች ተወሰነ፡፡ እናም ጉዳዩን በትክክል ለመግለፅ ፍርድ ቤቱ በአስተዳደር ክፍል የተወሰነውን ውሳኔ ተቀብሎ መዘገበ ከሚባል በቀር በጉዳዩ ላይ የዳኝነት ውሳኔ ሰጥቷል ማለት አይቻልም፡፡

በፍርድ ቤት ዳኝነት በተጠየቀበት ጉዳይ ላይ የአስተዳደር ክፍል እገዛ ካስፈለገም ተጣርቶ እንዲቀርብ የሚሰጠው ትዕዛዝ ከሞላ ጎደል አስተዳዳር ክፍሉ ክርክር ከተነሳበት ጉዳይ ጋር በተያያዘ በእጁ የሚገኙ ሰነዶች ላይ ብቻ ያተኮረ ሊሆን ይገባል፡፡ ከዚህ ባለፈ አስተዳደር ክፍል በፍርድ ቤት በቀረበ ጉዳይ ላይ ምስክር ሰምቶ አልያም በቃለጉባኤ እያጣራ እንዲያቀርብ የሚሰጥ የውክልና ትዕዛዝ አግባብነት የለውም፡፡ አከራካሪው ነጥብ በምስክር የሚጣራ ከሆነ ምስክሮችን አስቀርቦ በሥ/ሥርዓት ህጉ መሰረት ምስክሮቹን ጠይቆና መርምሮ ማጥራት ያለበት ፍርድ ቤት እራሱ እንጂ ሌላ አካል አይደለም፡፡

እናም የስር የወረዳው ፍርድ ቤት አንድም በአስተዳደር ክፍሉ በምስክር እና ቃለ ጉባኤ ተጣርቶ የቀረበለትን መግለጫ ሙሉ በሙሉ ከመቀበሉም በላይ በተለያየ ጊዜ የቀረቡት መግለጫዎች ፍፁም ተቃራኒ በሆኑበት ሁኔታ ልዩነቱ እንዴት ሊፈጠር እንደቻለ በአግባቡ ሳያጣራ እና የቀረበለትን ሪፖርት ይዘት ከቀረቡት ሌሎች ማስረጃዎች ይዘት ጋር በተገቢው ሁኔታ ሳያገናዝብ አልፎ ከአስተዳደር ክፍል መግለጫ ጋር የሚለዋወጥ ውሳኔ መስጠቱ ህግን ያልተከተለ ብቻ ሳይሆን ፍትሕንም በእጅጉ የጎዳ መሰረታዊ የህግ ስህተት ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በመሆኑም ተከታዩ ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

## <u>ውሳኔ</u>

1. የኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት በመ/ቁ/300663 ላይ ታህሳስ 15/2011 ዓ.ም በዋለው ችሎት የጅማ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰቃ ወረዳ ፍርድ ቤትን ውሳኔ ያፀናበትን ትዕዛዝ በማፅናት የሰጠው ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁጥር 348(1) መሰረት ተሽሯል፡፡

2. የሰቃ ጮቆርሳ ወረዳ ፍርድ ቤት በውሳኔ የዘጋውን መዝገብ በማንቀሳቀስ በአሁን አመልካች በአሁን ከ2ኛ እስከ 5ኛ ባሉት ተጠሪዎች የመቃወም አቤቱታ ላይ መጋቢት 17/2010 ዓም ባቀረቡት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያዎች ላይ ተገቢውን ብይን እንዲሰጥ ተወስኗል፡፡

3. በውሳኔ ተራ ቁጥር ሁለት መሰረት በሚሰጥ ብይን የአሁን አመልካች የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ የሚታለፍ ቢሆን፡-

3.1 የወረዳው የገጠር መሬት አስተዳዳር ጽ/ቤት ክርክር ከተነሳበት ይዞታ ጋር በተያያዘ ቀደም ሲል ህዳር 19/2010 እና ሰኔ 13/2010 በሰጠው መግለጫ እርስ በራሱ የሚጋጭ መግለጫ የሰጠበትን ምክንያት በማጣራት፤

3.2 የወረዳው የገጠር መሬት አስተዳደር ክርክር የተነሳበትን ይዞታ በተመለከተ የተደራጀ ማህደር በእጁ ካለ ከማህደሩ በመመርመር ነባር ይዞታነቱ የማን እንደሆነ፣ በይዞታው ላይ አግባብነት ያለው የይዞታ ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ማን ከመቼ ጀምሮ እንዳለው፤ ይህ ከሌለ በይዞታው ላይ ግብር በማን ስምና ከመቼ ጀምሮ እየተከፈለ እንዳለ በአግባቡ ተጣርቶ እንዲቀርብለት በማዘዝ፤ እና

3.3. ከላይ በተመለከተው ሁኔታ ተጣርቶ የሚቀርብለትን ሪፖርት ቀድሞ በግራ ቀኙ ከተሰሙት ምስክሮች ቃል ጋር በማገናዘብ እንዲሁም ለትክክለኛ ፍትህ አሰጣጥ አስፈላጊ መስሎ የታየውን ተጨማሪ ምስክር በመስማት ወይም ማስረጃ በማስቀረብ ማስረጃዎቹን ሁለንተናዊ በሆነ መልኩ መርምሮ እና መዝኖ የመሰለውን እንዲወስን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁጥር 343(1) መሰረት መዝገቡ ይመለስለት፡፡

**<u>ትዕዛዝ</u>**

የዚህን ሰበር ችሎት ክርክር ወጪ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ብ/ም

የሰ/መ/ቁጥር 169407

ቀን 29/9/2011 ዓ/ም

**ዳኞች ፡-** አልማው ወሌ

ሙስጠፋ አህመድ

አብርሃ መሰለ

ፈይሳ ወርቁ

ጻውሎስ ኦርሺሶ

አመልካች - በኬሚካል ኢንዳስትሪ ኮርፖሬሽን ሙገር ሲሚንቶ ፋብሪካ ነገረ ፈጅ ወዳጄ ማሞ ቀረቡ፡፡

ተጠሪ - አቶ ይትባረክ ተካ፡- ቀረቡ፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍርድ**

ለዚህ ሰበር መዝገብ ክርክር መነሻ የሆነው ጉዳይ የቀረበው አመልካች ጥር 15 ቀን 2011 ዓ.ም በተፃፈ አቤቱታ የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁጥር 185419 ህዳር 25 ቀን 2011 ዓ/ም በዋለው ችሎት የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት ቅሬታውን በማቅረቡ ነው፡፡ ቅሬታውም አቤት የተባለበትን ውሣኔ፣ አመልካች የሚቃወምባቸውን ምክንያቶች የሚዘረዝርና በሰበር ሰሚው ችሎት በኩል ሊታይልኝ ይገባል የሚለውን ዳኝነት የሚጠይቅ ሲሆን፣ የስር ፍ/ቤት በአመልካችና ተጠሪ መካከል የነበረው የስራ ክርክር በ5/6/2010 ዓ/ም በቃል ክርክር በተያዘው ቀጠሮ ቀን ግራ ቀኙ ባለመቅረባችን መዝገቡ ተዘግቶ እያለና መዝገቡ ተከፍቶ ክርክር የቀጠለ መሆኑ ሳይነገረኝ በሌለሁበት የተሰጠ ውሳኔ በመሆኑ ውሳኔው ተነስቶ ክርክር እንዳደርግ መወሰን ሲገባ አቤቱታዬን ውድቅ ማድረጉ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ይታረምልኝ የሚል ነው፡፡

በስር ፍ/ቤት የነበረው ክርክር የጀመረው ከአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርድ ሲሆን ከሳሽ የአሁን ተጠሪ ሲሆን ተከሳሽ የአሁን አመልካች ነው፡፡ የአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርድ በሰጠው ውሳኔ ላይ የአሁን ተጠሪ ለፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት የይግባኝ ቅሬታ አቅርቦ የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት የአሁን አመልካች በሌለበት የሰጠውን ውሳኔ የአሁን አመልካች በሌለሁበት የተሰጠው ውሳኔ ይነሳልኝ ሲል በማመልከቱ ነው፡፡ መልስ ሰጪ የአሁን አመልካች ለፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ያቀረበው አቤቱታ በ5/6/2010 ዓ/ም ለቃል ክርክር ለያዘው

ቀጠሮ ግራ ቀኞችን ባለመቅረባችን መዝገቡ የተዘጋ ሲሆን ሳይነገረኝ በሌለሁበት የሰጠው ውሳኔ መብቴን የሚጎዳ በመሆኑ በሌለሁበት የተሰጠው ውሳኔ ይነሳልኝ ሲል ጠይቋል፡፡ ይግባኝ ባይ የአሁን ተጠሪም ለቃል ክርክር እንዲቀርብ የተላከለት መጥሪያ የደረሰው መሆኑን አልካደም፡፡ የአፈጻጸም ክስ ቀርቦበት ከፈጸመልኝ በኃላ በሌለሁበት የተሰጠብኝ ውሳኔ ይነሳልኝ ሲል ያቀረበው አቤቱታ ተቀባይነት የሌለው በመሆኑ ውድቅ ይሁንልኝ በሚል መልስ ሰጥተዋል፡፡ የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁጥር 185419 ህዳር 25 ቀን 2011 ዓ/ም በዋለው ችሎት የሰጠው ውሳኔ ለመ/ሰጪ ለቃል ክርክር እንዲቀርብ መጥሪያ ደርሶት በቃል ክርክር ጊዜ ሁለቱም ባለመቅረባቸው መዝገቡ የተዘጋ ሲሆን ይግባኝ ባይ መዝገቡ እንዲከፈትለት ምክንያቱን ገልጾ መዝገቡ ተከፍቶለት ክርክሩ እንዲቀጥል ያስፈቀደ ሲሆን መ/ሰጪም ይህንኑ መፈጸም ነበረበት፡፡ መ/ሰጪ በተሰጠው ውሳኔ መሰረት እንዲፈጽም ክስ ቀርቦበት ለይግባኝ ባይ ከፈጸመ በኃላ በሌለሁበት የተሰጠው ውሳኔ ይነሳልኝ በማለት ያቀረበው አቤቱታ ተቀባይነት የሌውም ሲል አቤቱታ ውድቅ አድርጓል፡፡

የአሁን አመልካችም ይህን ውሳኔ በመቃወም ቀርቧል፡፡ መዝገቡም ተመርምሮ ለክርክር ምክንያት የሆነውን ጉዳይ በይግባኝ የተመለከተው የስር ፍ/ቤት የአሁን አመልካች መጥሪያ ተልኮለት ሳይቀርብ የቀረ ቢሆንም የስር ፍ/ቤትን ውሳኔ ከይግባኝ ባይ ክርክር ጋር በመመርመር የወሰነ መሆን አለመሆኑን ከመሰረታዊ የክርክር አመራር ስነ ሥርዓት ጋር በማገናዘብ ለመመርመር ሲባል ቀርቧል፡፡ መልስና የመልስ መልስም ተሰጥቶበታል፡፡ ተጠሪ መጋቢት 19 ቀን 2011 ዓ/ም በተጻፈ መልስ የስር ፍ/ቤት የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት እንዳልተፈጸመበት በማንሳት ይጽናልኝ ሲል ተከራክሯል፡፡ አመልካችም ሚያዝያ 1 ቀን 2011 ዓ/ም በተጻፈ የመልስ መልስ አቤቱታቸውን በማጠናከር ተከራክረዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ከላይ የተመለከተውን ሲሆን፣ እኛም የቀረበውን አቤቱታ፣ መልስ እና የመልስ መልሱን እንዲሁም የስር ፍርድ ቤት ውሣኔዎችን እና ከጉዳዩ ጋር አግባብነት ያላቸውን የሕግ ድንጋጌዎችን መሠረት በማድረግ በጉዳዩ ላይ የተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት መኖር አለመኖሩን መርምረናል፡፡ እንደመረመርነውም በስር ፍ/ቤት በተደረገው ክርክር የአሁን ተጠሪ የአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርድ በሰጠው ውሳኔ መብቴ ተጎድቷል ሊታረምልኝ ይገባል ሲል ለፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት የይግባኝ ቅሬታ አቅርቧል፡፡ የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ለግራ ቀኙ ክርክር እንዲያቀረቡ በተቀጠረበት ቀን ሁለቱም ባለመቅረባቸው መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ የይግባኝ ቅሬታ የሚያቀርበው ሰው፣ የተወሰነበት ወገን ወይም ይግባኝ የሚባልበት ውሳኔ መብቴን ጎድቶታል የሚለው ወገን ሲሆን፣ በውሳኔው ተጠቃሚ የሆነው ወገን እንዲጸናለት የሚከራከር እንጂ ይግባኝ የሚጠይቅበት ሁኔታ አይኖርም፡፡ እንደዚሁም የይግባኝ መዝገብ የተዘጋ እንደሆነም መዝገቡ እንዲከፈትለት የሚጠይቀው ሰው፣ የስር ፍ/ቤት ውሳኔ መብቴን ጎድቶታልና መዝገቡ ተንቀሳቅሶ የስር ፍ/ቤት ውሳኔ ይታረምልኝ የሚለው ወገን እንጂ በውሳኔ ተጠቃሚ የሆነው ወገን የተዘጋው መዝገብ እንዲከፈት የሚገደድበት አግባብ የለም፡፡ የተዘጋው መዝገብ ከተከፈተ በኂላ ሌላው ወገን መዝገቡ መንቀሳቀሱን አውቆ ቀርቦ እንዲከራከሩ ሊደረግ እንደሚገባ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህግ አንቀጽ 233 ድንጋጌ በተመሳሳይ ለይግባኝ ክርክር ጊዜም እንደነገሩ አግባብ መፈጸም አለበት፡፡ ይግባኝ የተባለበትን ውሳኔ የፈጸመ ተከራካሪ ወገን ለይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ይግባኝ ቅሬታ

ለማቅረብም ሆነ አቤቱታ ለማቅረብ የሚከለክለው የህግ ድንጋጌ የሌለና የትኛውንም ወገን የሚጎዳም አይደለም። ይህ ሆኖ እያለ የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት የህግ መሰረት በሌለው ምክንያት ግራ ቀኙ ለክርክር በተቀጠረው ቀን ባለመቅረባቸው ተዘግቶ የነበረው መዝገብ በይግባኝ ባዩ አመልካችነት ሲከፈት መ/ሲጪ እንዲያውቀው ሳይደረግ በሌለበት ውሳኔ መስጠቱ እና አመልካች በሌለበት የተሰጠው ውሳኔ እንዲነሳለት ያቀረበውን አቤቱታ በቂ ባልሆነ ምክንያት ውድቅ ማድረጉ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም የሚገባው ነው ብለናል።

## <u>ውሳኔ</u>

1. የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁጥር 185419 ሚያዝያ 25 ቀን 2010 ዓ/ም በዋለው ችሎት የሰጠው ውሳኔ እና ህዳር 25 ቀን 2011 ዓ/ም በዋለው ችሎት የአሁን አመልካችን አቤቱታ ውድቅ በማድረግ የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህግ ቁጥር 348(1) መሰረት ተሽሯል።
2. የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት የአሁን ተጠሪ ባቀረበው የይግባኝ ቅሬታ ያስቀርባል በተባለው ጭብጥ የአሁን አመልካች ክርክሩን እንዲያቀርብ በማድረግ ካከራከረ በኋላ ውሳኔ እንዲሰጥበት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህግ ቁጥር 341(1) መሰረት መልሰናል።
3. በዚህ መዝገብ ክርክር ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሣቸውን ይቻሉ።
4. የዚህ ውሳኔ ትክክለኛ ግልባጭ ለስር ፍ/ቤት ይድረሳቸው ብለናል።
5. መዝገቡ ተዘግቶ ወደ መ/ቤት ተመልሷል።

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት።

ሠ/ኃ

የሰ/መ/ቁ166205

ቀን 29/09/2011ዓ/ም

**ዳኞች**፡- ተኽሊት ይመሰል

ተፈሪ ገብሩ(ዶ/ር)

ቀነዓ ቂጣታ

ተሾመ ሽፈራው

ፀሐይ መንክር

**አመልካች** ፡- አቶ ገ/ኢየሱስ ሙሉነህ - ቀረቡ፡፡

**ተጠሪ** ፡- 1ኛ አቶ ወልዴ አቡቴ - አልቀረቡም፡፡

2ኛ ወ/ሮ አዳነች ዱላ - ቀረቡ፡፡

መዝገቡ መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል።

**ፍርድ**

1. በዚህ መዝገብ የተያዘው ጉዳይ የቤት ክርክር የሚመለከት ሲሆን የጀመረው በደ/ብ/ብ/ሕ/ክ የሆሳዕና ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ነው፡፡ በስር አመልካች ከሳሽ 1ኛ ተጠሪ ተከሳሽ 2ኛ ተጠሪ ደግሞ ጣልቃ ገብ በመሆን ተከራክረዋል፡፡አመልካች በስር ፍርድ ቤት ያቀረቡት ክስ ይዘት ባጭሩ፦ አንደኛ ተጠሪ የሀሰት ማስረጃ አቅርበው በ21/08/2006 ዓ/ም በተሠጠው ውሳኔ ከነበራቸው ይዞታ 48 ካ.ሜ ወስደዋል፡፡ ይሁንና 1ኛ ተጠሪ ያቀረቡት እና ለውሳኔ መሰረት የሆነው ማስረጃ የሐሰት መሆኑን በፍርድ ቤት ተረጋግጦ በወንጀል ተከሰው 4 ዓመት ከ5 ወር የተቀጡ በመሆኑ ፍርዱ ተሽሮ የሰሩትን ቤት አፍርሰው ይዞታውን እንዲያስረክቧቸው እንዲሁም ካሣ ለመጠየቅም የመክሰስ መብት እንዲጠበቅላቸው ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡
2. 1ኛ ተጠሪ ክሱ ፍርድ ባገኘው ጉዳይ በድጋሚ የቀረበ መሆኑን፣ በወንጀል ጉዳይ የተሰጠው ፍርድ ከፍ/ህግ ግንኙነት የሌለው በመሆኑ ውድቅ እንዲደረግ ሲያመለክቱ፤2ኛ ተጠሪ በበኩላቸው ለክርክሩ መሰረት የሆነው ይዞታ ጨምሮ 500 ካ.ሜ ከ1ኛ ተጠሪ የገዙ በመሆኑ

ጣልቃ ገብተው እንዲከራከሩ ጠይቀው ፍርድ ቤቱም አቤቱታው ተቀብሎ የክርክሩ ተካፋይ እንዲሆኑ አዟል፡፡

3. በዚህ መልኩ ክርክሩ የቀረበለት ፍርድ ቤትም ለክርክሩ መነሻ የሆነውን ይዞታ 2ኛ ተጠሪ ከ1ኛ ተጠሪ የገዙት በመሆኑ የአመልካች ክስ ተቀባይነት የለውም በማለት ወስኗል፡፡ አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ለዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት እንዲሁም ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ያቀረቡት ይግባኝ ቅሬታ እና ሰበር አቤቱታ ተቀባይነት አላገኘም፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ  የቀረበውም የስር ፍ/ቤቶች ውሳኔ እና ትዕዛዝ በመቃወም ለማሳረም ነው፡፡

4. አመልካች በ23/03/2011 ዓ/ም የተፃፈ የሰበር አቤቱታ አቅርበው የስር ፍ/ቤቶች ውሳኔ እና ትዕዛዝ እንዲሻር አመልክቷል፡፡ የአመልካች አቤቱታ የመረመረው የሰበር አጣሪ ችሎትም ጉዳዩ በዚህ ችሎት እንዲታይ ያቀረበው ሲሆን ተጠሪዎች የበኩላቸውን መልስ  በማቅረብ ውሳኔው እንዲጸና ጠይቀዋል፡፡ የመልስ መልስም ቀርቧል፡፡

5.  ከስር የጉዳዩ አመጣጥ ባጭሩ ከላይ የተገለፀው ይዘት ያለው ሲሆን እኛም  በየደረጃው ጉዳዩን የተመለከቱት የስር ፍ/ቤቶች የሰጡት ፍርድ እና ትዕዛዝ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት መሆን አለመሆኑን ክርክሩን በሚከተለው መልኩ መርምረናል፡፡

6. እንደመረመርውም፦ ከመዝገቡ እንደተረዳነው የአመልካች መሰረታዊ የዳኝነት ጥያቄ በሐሰት ማስረጃ የተሰጠው ፍርድ እንዲነሳ የሚጠይቅ ነው፡፡ የስር ፍርድ ቤት የተጠየቀው ዳኝነት ባሕሪ እና ይዘት ሳያገናዝብ ይዞታው 2ኛ ተጠሪ ከ1ኛተጠሪ በግዢ ያገኙት በመሆኑ ሊለቁ አይገባም በማለት መወሰኑን ያሳያል፡፡ አመልካች በስር ፍርድ ቤት ካቀረቡት ክስ መገንዘብ የተቻለው 2ኛ ተጠሪ ከአመልካች ጋር ተከራክረው ለተሰጠው ፍርድ መሰረት የሆነው ማስረጃ ሀሰተኛ ሰነድ ላይ የተመሰረተ ነው የሚል ነው፡፡ የስር ፍርድ ቤት ዳኝነት እንደገና እንዲታይ የቀረበ አቤቱታ መሆኑን ተገንዝቦ በዚሁ አግባብ ስላልቀረበ መዝገቡን መዝጋት ሲገባው በመደበኛ (አዲስ) ክስ በማስተናገድ ውሳኔ መስጠቱ ተገቢ ሆኖ አልተገኘም፡፡ የ2ኛ ተጠሪ የመብት ጥያቄም በውሳኔ ተዘጋ በተባለው መዝገብ ህጋዊ ውጤት ከሚታይ በስተቀር በዚህ መዝገብ ጣልቃ ገብ በመሆን የሚከራከሩበት ሕጋዊ ምክንያት አይኖርም፡፡ በመሆኑም አመልካች የዳግም ዳኝነት ጥያቄው በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ6 መሰረት አቅርበው ከሚስተናገዱ በስተቀር አዲስ ክስ በማቅረብ ውሳኔው እንዲሻር የሚጠይቁበት የሕግ አግባብ አይኖርም፡፡ የስር ፍርድ ቤትም ክሱ ውድቅ ማድረግ ሲገባው የአመልካች ክስ ተቀብሎ እንደ አዲስ  ክስ ማስተናገዱ፤ ይኸው  ውሳኔ በየደረጃው ባሉ ፍ/ቤቶች መጽናቱ መሰረታዊ የሕግ ስሕተት መፈጸሙን የሚያሳይ በመሆኑ ሊሻር የሚገባው ነው፡፡ በዚህ ሁሉ ምክንያት ተከታዩን ወስነናል፡፡

## ውሳኔ

1. በደ/ብ/ብ/ሕ/ክ የሆሳዕና ከተማ የመጀመርያ ደረጃ በመ/ቁ 23099 በ20/04/2010 ዓ/ም፣ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ17695 በ18/5/2010 ዓ/ም፣ እንዲሁም የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ በመ/ቁ10056 በ09/1/2011 ዓ/ም በዋለው ችሎት የሰጡት ፍርድ እና ትዕዛዝ ተሸሯል፡፡
2. የአመልካች መሰረታዊ የዳኘነት ጥያቄ በዳግም ዳኝነት እንዲታይ የቀረበ ሁኖ ሳለ በአዲስ ክስ መስተናገዱ በሕጉ አግባብ አይደለም በማለት ወስነናል፡፡
3. አመልካች ይሁን 2ኛ ተጠሪ በሌላ አግባብ መብታቸው ለማስከበር የሚያቀርቡት ክርክር ይህ ውሳኔ አያግዳቸውም ብለናል፡፡
4. የዚህ ፍርድ ቤት ክርክር ያስከተለው ወጪ እና ኪሳራ ግራቀኙ የየራሳቸው ይቻሉ ብለናል፡፡
5. የውሳኔው ግልባጭ ለስር ፍ/ቤት ይተላለፍ፡፡

መዝገቡ ተዘጋ ወደ መዝገብ ቤት ተመለሰ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ዮ/መ

የሰ/መ/ቁ.166617

ግንቦት 30 ቀን 2011 ዓ.ም

ዳኞች፡…. ተኽሊት ይመሰል

ተፈሪ ገብሩ (ዶ/ር)

ቀነዓ ቂጣታ

ተሾመ ሽፈራዉ

ፀሐይ መንክር

አመልካች፡…… . . አቶ ገ/መድህን መልከጻድቅ ፡- ጠበቃ አየለ ቦጋለ ቀርበዋል፡፡

ተጠሪዎች፡………. . . 1. አቶ ቀነኒ ዲባባ ፡- የቀረበ የለም፡፡

2. አቶ ዘሪሁን ሳምሶን ጌታቸዉ

ይህ መዝገብ ተመርምሮ የሚከተለዉ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ይህ ክርክር የተጀመረዉ በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ሲሆን፣የአሁን አመልካች ተከሳሽ፣የአሁን ተጠሪዎች ደግሞ ከሳሽ ሆኖ ሲከራከሩ ነበር፡፡ ጉዳዩ ለዚህ ችሎት ሊቀርብ የቻለዉ የአሁን አመልካች የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ.212821 ህዳር 11 ቀን 2011 ዓ.ም የሰጠዉ ትዕዛዝ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ እንዲታረምልኝ በማለት በማመልከቱ ነዉ፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ሲታይ ከሳሽ (የአሁን ተጠሪዎች) ባቀረቡት ክስ በከሳሾች እና በተከሳሽ መካከል ጥቅምት 3 ቀን 1980 ዓ.ም በተደረገ የወለድ አገድ ዉል በልደታ ክ/ከተማ ወረዳ 4 ክልል ዉስጥ የሚገኘዉን የቤት ቁጥር 752 የሆነዉን የከሳሾችን ቤት ከተከሳሾች ብር 20,000 (ሀያ ሺህ) ተቀብለን ቤቱን አስረክበን የተበደርን ሲሆን የብድሩ ጥቅምት 3 ቀን 1990 ዓ.ም ልንከፍል ተስማምተን ብሩን ተቀብለን ቤቱን ያስረከብን ሲሆን፣ ተከሳሽ ገንዘቡን ወስዶ ቤቱን እንዲያስረክበን ብንጠይቀዉም ፈቃደኛ ስላልሆነ ገንዘቡን ተቀብለዉ፣ ቤቱን እንዲስረክበን፣ ቤቱን አከራይተን የሚናገኘዉን ጥቅም ብር 10,000 እንዲከፍለን በማለት ከሷል፡፡

በዚህ ክስ ላይ ተከሳሽ ባቀረበዉ መልስ ከሳሽ ጥቅምት 3 ቀን 1990 ዓ.ም ጀምሮ ከ17 ዓመት በኂላ ስለሆነ ክሱ በይርጋ የሚታገድ ነዉ፤ በዉሉ ላይ በተመለከተዉ መሰረት ከሳሾች ገንዘቡን በጊዜ ካልመለሱ ተከሳሽ ቤቱን ሸጠዉ ገንዘቡን መዉሰድ እንደሚችል ስለተስማማን በዚህ መሰረት ታህሳስ 5 ቀን 2007 ዓ.ም ለአቶ መላኩ ዮሐንስ የሸጥኩኝ ስለሆነ ክሱ ተቀባይነት የለዉም፡፡ ነገር ግን ፍ/ቤቱ ቤቱ ለከሳሾች ሊመለስ ይገባል የሚል ከሆነ ከሳሾች የወሰዱትን የብድር ገንዘብ ብር 20,000 (ሀያ ሺህ) ከጥቅምት 3 ቀን 1980 ዓ.ም ጀምሮ ከሚታሰብ ወለድ ጋር እንዲከፍሉኝ በማለት ተከራክሯል፡፡

ከዚህ በኂላ የሥር የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ በመመርመር በሰጠዉ ዉሳኔ ከሳሾች ያቀረቡት ክስ በይርጋ የሚታገድ ነዉ በማለት ዉድቅ በማድረግ ወስኗል፡፡ የሥር ከሳሾች በዚህ ዉሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት አቅርቦ ፍ/ቤቱ ግራ ቀኛቸዉን በማከራከር በመ.ቁ.177014 በ18/8/2009 ዓ.ም በሰጠዉ ዉሳኔ የሥር ፍ/ቤት ከሳሾች ያቀረቡት ክስ በይርጋ ቀሪ ሆኗል ያለበት አግባብ ሕግን መሰረት ያላደረገ በመሆኑ የሥር ዉሳኔ ዉሳኔ ተሽሯል በማለት በዋና ጉዳይ አከራክሮ እንዲወሰን በማለት ለሥር ፍ/ቤት መልሶታል፡፡

ከዚህ በኂላ የሥር የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ጉዳዩን ድጋሚ በማየት በሰጠዉ ዉሳኔ በከሳሾች እና በተከሳሾች መካከል ጥቅምት 3 ቀን 1980 ዓ.ም የተደረገዉ የወለድ አገድ ዉል ሕጋዊ ዉጤት የሌለዉ በመሆኑ ከሳሾች የተበደሩትን ብር 20,000 (ሀያ ሺህ) ለተከሳሽ በመክፈል ተከሳሽ ደግሞ የቤት ቁጥር 752 የሚታወቀዉን ለከሳሾች እንዲያስረክቡ በማለት ወስኗል፡፡ የሥር ተከሳሽ በዚህ ዉሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ያቀረበ ቢሆንም ፍ/ቤቱ የቀረበዉን ይግባኝ ዉድቅ በማድረግ የሥር ዉሳኔ በማጽናት ወስኗል፡፡ የአሁን የሰበር አቤቱታ በዚህ ትዕዛዝ በመቃወም ለማስለወጥ ነዉ፡፡

የአሁን አመልካች ታህሳስ 1 ቀን 2011 ዓ.ም በተጻፈ የሰበር አቤቱታ፡ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በዚህ ጉዳይ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት የሥር ዉሳኔ በመሻር ግራ ቀኛቸዉን በዋኛዉ ጉዳይ አከራክሮ እንዲወሰን በመለሰለት መሰረት ፍ/ቤቱ ግራ ቀኞችንን በጉዳዩ ላይ አከራክሮ መወሰን ሲገባዉ ግራ ቀኞችንን ሳያከራክርና የቀረበዉን ማስረጃ ሳይመረምር የሰጠዉ ዉሳኔ የሥር የከፍተኛ ፍ/ቤት ትዕዛዝ (መመሪያ) እና የፍትሐብሔር ሥነሥርዓት ሕጉን ድንጋጌዎች የጣሰ ስለሆነ የህግ ስህተት ተፈጽሟል፡፡ ስለሆነም የሥር ፍ/ቤቶች የሰጡት ዉሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ እንዲሻርልኝ በማለት በዝርዝር ቅሬታዉን አቅርቧል፡፡

የሰበር አጣሪ ችሎት ጉዳዩን በማየት ፤የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በዚህ ጉዳይ የሰጠዉ ዉሳኔ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በሰጠዉ ፍርድ መሰረት ነዉ ወይስ አይደለም? የሚለዉን ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.341 ድንጋጌ አፈጻጸም ከመሰማት መሰረታዊ መብት አንጻር ለመመርመር ሲባል የሰበር አቤቱታዉ ያስቀርባል በማለት ተጠሪዎች መልስ እንዲሰጡ ባዘዘዉ መጋቢት 16 ቀን 2011 ዓ.ም የተጻፈ መልስ አቅርቧል፡፡ የመልሱም ይዘት በአጭሩ፡ የሥር ፍ/ቤቶች በዚህ ጉዳይ የሰጡት ዉሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያልተፈጸመበት ስለሆነ ዉሳኔዉ እንዲጸናልን ወጪና ኪሳራ የመጠየቅ መብታችን እንዲጠበቅልን በማለት በዝርዝር ተከራክሯል፡፡ የአሁን አመልካች የሰበር አቤቱታዉን በማጠናከር መልስ አቅርቧል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ከፍ ሲል የተመለከተዉ ሲሆን ይህ ችሎት የግራ ቀኛቸዉን ክርክር አግባብነት ካላቸዉ የህግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ እንዲሁም የሰበር አቤቱታዉ ያስቀርባል ሲባል ከተያዘዉ ጭብጥ አንጻር እንደሚከተለዉ መርምሮታል፡፡ እንደመረመርነዉ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የአሁን ተጠሪዎች ያቀረቡትን ክስ በተመለከተ የአሁን አመልካች ያቀረበዉን የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ

በመቀበል ተጠሪዎች ያቀረቡት ክስ በይርጋ የሚታገድ ነዉ በማለት መወሰኑን መዝገቡ ያሳያል፡፡ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ደግሞ የቀረበለትን ይግባኝ በመመርመር የሥር ፍ/ቤት የተጠሪዎችን ክስ በይርጋ ዉድቅ ማድረጉ ተገቢ አይደለም በማለት በመሻር የሥር ፍ/ቤት በዋናዉ ጉዳይ ግራ ቀኛቸዉን አከራክሮ ዉሳኔ እንዲሰጥ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.341 (1) መሰረት የመለሰለት መሆኑን የሥር ዉሳኔ ግልባጭ ያመለክታል፡፡ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በዚህ አግባብ የተመለሰለትን ጉዳይ በመ.ቁ.228538 በ2/5/2010 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በሰጠዉ ዉሳኔ መሰረት ተጠሪዎች መዝገብ እንዲከፈትላቸዉ መጠየቃቸዉን በመግለጽ፣ ተጠሪዎች ለአመልካች መጥሪያ እንዲያደርሱ፣ መዝገቡን መርምሮ ለመስራት ለየካቲት 16 ቀን 2010 ዓ.ም ቀጠሮ ሰጥቷል፡፡ በዚህ መሰረት የሥር የከፍተኛ ፍ/ቤት የካቲት 16 ቀን 2010 ዓ.ም ዉሳኔ መስጠቱን የሥር ዉሳኔ ግልባጭ ያሳያል፡፡ ይህ ማለት የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የበላይ ፍ/ቤት በሰጠዉ ትዕዛዝ መሰረት ግራ ቀኛቸዉን ሳያከራክር ዉሳኔ መስጠቱን ያመለክታል፡፡

እንደሚታወቀዉ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.341 (1) እንደሚያመለክተዉ ‹‹ይግባኝ የተባለበትን ፍርድ ወይም ዉሳኔ የሰጠዉ ፍርድ ቤት ነገሩን የወሰነዉ ክርክር ዉስጥ ሳይገባ በመጀመሪያ ደረጃ የቀረበለትን መቃወሚያ ብቻ መሰረት በማድረግ ሲሆንና ይህ ፍርድ ወይም ዉሳኔ በይግባኝ ሰሚዉ ፍርድ ቤት የተለወጠ እንደሆነ ክርክሩ ወደ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት እንዲመለስ በማድረግ መታየት የሚገባቸዉን ነጥቦች ለይቶ እንደገና እንዲታይ ለማዘዝ ይችላል›› በማለት ይደነግጋል፡፡ በዚህ አግባብ አሁን ወደ ተያዘዉ ጉዳይ ስንመለስ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ተጠሪዎች ያቀረቡትን ክስ በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ በይርጋ ዉድቅ ያደረገ ቢሆንም የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ጉዳዩን በማየት የሥር ዉሳኔ በመሻር ግራ ቀኛቸዉን በዋናዉ ጉዳይ አከራክሮ ዉሳኔ እንዲሰጥበት የመለሰ መሆኑን መገንዘብ ተችሏል፡፡ ይህ ከሆነ ደግሞ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በዚህ የህግ ድንጋጌ መሰረት ዉሳኔ የሰጠ መሆኑን እና ዉሳኔዉም ሕግን የተከተለ መሆኑን ያስገነዝባል፡፡ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.341 (1) መሰረት ዉሳኔ ለመስጠት በሕግ ስልጣን እስከተሰጠዉ እና በዚህ አግባብ የሥር ዉሳኔ በመሻር የሥር የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ጉዳዩን ድጋሚ እንዲያይ ነጥብ ለይቶ እስከመለሰ ድረስ፣ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በዚህ ዉሳኔ መሰረት የመፈጸም ኃላፊነት እንዳለበት የሚያከራክር አይሆንም፡፡ ይህ ማለት የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የበላይ ፍ/ቤት በሰጠዉ ትዕዛዝ ወይም መመሪያ መሰረት ግራ ቀኛቸዉን አከራክሮ ዉሳኔ የመስጠት ኃላፊነት አለበት፡፡ ከዚህ መረዳት እንደሚቻለዉ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የበላይ ፍ/ቤት በሰጠዉ ዉሳኔ መሰረት ግራ ቀኛቸዉን ማከራከር እንዳለበት ነዉ፣ ይህም ግራ ቀኛቸዉ ክርክራቸዉን እንዲያሰሙ እና ዋና የክርክር የመስማት ሂደት መከናወን እንዳለበት ያስገነዝባል፡፡ ፍ/ቤቱ በዋናዉ የክርክር መስማት ሂደት ደግሞ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.246-249 ድንጋጌዎች መሰረት ጭብጦችን መመስረት፣ ግራ ቀኛቸዉ ክሳቸዉን እና መልሳቸዉን ሲያቀርቡ የጠቀሱትን ማስረጃ እንዲያቀርቡ ማድረግና መመርመር፣ ፍርድ እና ዉሳኔ የመስጠት ተግባራትን ይፈጽማል ማለት ነዉ፡፡ ከዚህ አንጻር አሁን ወደ ተያዘዉ ጉዳይ

ስንመለስ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት የሰጠዉን ዉሳኔ መነሻ በማድረግ መዝገቡ የተንቀሳቀሰ መሆኑን ለተከራካሪ ወገኖች በማሳወቅ ዉሳኔ መስጠቱን እንጂ በዚህ አግባብ ግራ ቀኛቸዉ ክርክራቸዉን እንዲያሰሙ እና ዋናዉን የክርክር መስማት ሂደት ያካሄደበት ሁኔታ የለም፡፡ ፍ/ቤቱ በዚህ አግባብ አለመፈጸሙ ደግሞ ከፍ ሲል በተጠቀሱት የህግ ድንጋጌዎች መሰረት በማድረግ የበላይ ፍ/ቤት ከሰጠዉ ዉሳኔ የሚቃረን ስለሆነ የሕግ ድጋፍ የለዉም ብለናል፡፡

ሲጠቃለል የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የበላይ ፍ/ቤት ማለትም የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በሰጠዉ ዉሳኔ መሰረት ግራ ቀኛቸዉን ሳያከራክር፣ ሳይሰማቸዉ፣ ጭብጥ ሳይመሰርት እና በማስረጃ ሳያጣራ ዉሳኔ መስጠቱ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ የሚከተለዉ ተወስኗል፡፡

## ዉ ሳ ኔ

1. የፌዴራል የመጀረመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ.ቁ.228538 በ16/6/2010 ዓ.ም የሰጠዉ ዉሳኔ እና የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ.212821 ህዳር 11 ቀን 2011 ዓ.ም የሰጠዉ ትዕዛዝ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348 (1) መሰረት ተሽሯል፡፡
2. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የተዘጋዉን መዝገብ በማንቀሳቀስ በፍርድ ሐተታዉ በተመለከተዉ መሰረት የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በሰጠዉ ዉሳኔ መሰረት ግራ ቀኛቸዉን በማከራከር፣ ጭብጥ በመያዝ፣ ጉዳዩን በማስረጃ በማጣራት ተገቢ ነዉ ያለዉን ዉሳኔ እንዲሰጥበት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.343 (1) መሰረት ተመልሶለታል፡፡
3. የዚህ ዉሳኔ ግልባጭ ለሥር ፍ/ቤቶች ይድረስ፡፡
4. ግራ ቀኛቸዉ በዚህ ችሎት የደረሰባቸዉን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸዉን ይቻሉ፡፡
5. የመ.ቁ.228538 ለፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ይመለስ፡፡

**መዝገቡ ተዘግቷል፡፡**

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ሠ/ኃ

የሰ/መ/ቁ. 167589

ግንቦት 16 ቀን 2011 ዓ.ም

**ዳኞች**፡- አልማው ወሌ

ሙስጠፋ አህመድ

አብርሃ መሰለ

ፈይሳ ወርቁ

ጻውሎስ ኦርሺሶ

አመልካች፡- ወ/ሮ ጽጌ ታደሰ - ጠበቃ ውቤ ጓዴ ቀረቡ፡፡

ተጠሪ፡-

1. ወ/ሮ አልማዝ ሳህሌ ወኪል ግርማ ታደሰ ቀረቡ፡፡
2. አቶ ሰይፉ ታደሰ
3. አቶ ግርማ ታደሰ - ቀረቡ፡፡
4. አቶ ደረጀ ታደሰ - ወኪል ግርማ ታደሰ ቀረቡ፡፡
5. አቶ ወንድወሰን ታደሰ
6. ወ/ሮ ዘውድነሽ ታደሰ
7. አቶ አሳምነው ታደሰ
8. አቶ ብሩክ ታደሰ - ወኪል ግርማ ታደሰ ቀረቡ፡፡

(5–7) አልቀረቡም፡፡

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ ከውርስ ድርሻ ክፍፍል ጥያቄ የተነሳውን የስረ ነገር ስልጣን ጉዳይ የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ አመልካች ባሁኑ ተጠሪዎች ላይ በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመሰረቱት ክስ ነው፡፡

የአሁኑ አመልካች ጥቅምት 20 ቀን 2010 ዓ/ም ጽፈው ባቀረቡት ማመልከቻ ከውርስ በጠቅላላ የተገመተ ሃብት ሊተላለፍላቸው የሚገባውን ድርሻቸው ብር 274,333.00 (ሁለት መቶ ሰባ አራት ሺህ ሶስት መቶ ሰላሳ ሶስት ብር) መሆኑን በመለየት ተጠሪዎች እንዲያካፍሏቸው ይወሰንልን በማለት ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡ የዳኝነት ገንዘቡንም በዚሁ ገንዘብ መጠን በታሪፉ መሰረት ብር 5,593.33 ከፍለው ፋይሉን ከአስከፈቱ እና ለችሎቱ ከቀረበ በኋላ ችሎቱ ክሳቸውን መርምሮ ከሳሽ ባቀረቡት የንብረት ክፍፍል ጥያቄ ላይ ክፍያ የሚፈፀመው በውርሱ ቤት ወይም አክሲዮን ተገምቶ እና ተሸጦ በመሆኑ ፍርድ ቤቱ የክፍያ ውሳኔ የሚሰጠው በቴክኒካዊ መንገድ ለቤቱና ለአክሲዮኑ ስለሆነ ሊከፈል የሚገባው ዳኝነትም ሆነ ጉዳዩ ሊቀርብበት የሚገባው ፍርድ ቤት የሚወስነው በንብረቱ ጠቅላላ ግምት በመመሰረት እና ሁሉንም ንብረት ለማካፈል ስልጣን ባለው ፍርድ ቤት እንጂ ለፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ

ቤት ሊሆን እንደማይገባው ደምድሞ ፍርድ ቤቱ መዝገቡን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 231(ለ) መሰረት ዘግቶታል፡፡ በዚህ ብይን የአሁኑ አመልካች ቅር በመሰኘት ይግባኛቸውን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርበው ግራ ቀኙ እንዲከራከሩ ከተደረገ በኋላ ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን መርምሮ የስር ፍርድ ቤት የሰጠውን ብይን ሙሉ በሙሉ አፅንቶታል፡፡ የአሁኑ የሠበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ዳኝነት በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ የአመልካች የሠበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም፡- ውርስ ተጣርቶ የወራሾች ድርሻ በተለየበት ሁኔታ አመልካች ድርሻቸውን ተጠሪዎች እንዲያካፍሉ ያቀረቡት ክስ የውርስ ንብረቱን ጠቅላላ ግምት መሰረት በማድረግ የፍርድ ቤቱ የስረ ነገር ስልጣን የሚታይ ነው ተብሎ መወሰኑ ከዳኝነት አከፋፈል እና በዳኝነት ከሚጠየቅ መብት አንፃር ተገቢነት የሌለው ነው የሚል ሲሆን አቤቱታቸው ተመርምሮም በዚህ ችሎት እንዲታይ የተደረገ ሲሆን ተጠሪዎች ቀርበውም ግራ ቀኙ በጽሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም፡-የፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ጉዳዩን የማየት የሥረ ነገር ስልጣን የለኝም በማለት የአመልካቾችን ክስ መዝጋቱ በአግባቡ ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ በመያዝ ጉዳዩን እንደሚከተለው ተመልክቷል፡፡

አመልካች በስር ፍርድ ቤት ክስ ሲመሰርቱ ከውርስ ጠቅላላ የተገመተ ሃብት ድርሻቸውን ከሌሎች ወራሾች ይደርሰኛል ያሉትን መጠኑን በግልጽ በመለየትና በመጥቀስ ሲሆን ዳኝነት የጠየቁትም ድርሻቸውን ተከሳሾች እንዲያካፍሏቸው ይወሰን ዘንድ የውርስ ቤትና አክሲዮን ግምት ከብር 4,000,000.00 (አራት ሚሊዮን ብር) በላይ መሆኑን ተጠሪዎች ገልፀው የሚከራከሩ መሆኑን ተገንዝበናል፡፡

አመልካች የጠየቁት የውርስ ንብረት አይነቱንና ግምቱን ለይተው ድርሻቸው የሆነውንና ከብር 500,000.00 (አምስት መቶ ሺህ ብር ) በታች የሆነውን ብር 274,333.00 (ሁለት መቶ ሰባ አራት ሺህ ሶስት መቶ ሰለሳ ሶስት ብር) እንዲከፈላቸው ይወሰን ዘንድ ነው፡፡ የተያዘውን ጉዳይ መሰረት ያደረገው የገንዘብ መጠን ሲታይ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ ስልጣኑ የማየት የስረ ነገር ስልጣን ያለው የፌደራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ስለመሆኑ ከአዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 14(1(ሀ)) ድንጋጌ መረዳት የምንችለው ሲሆን አመልካች ከድርሻቸው ውጪ ያለውን ግምት መሰረት አድርገው ዳኝነት የሚጠይቁበት የሕግ አግባብም የለም፡፡ የሥረ ነገር የዳኝነት ስልጣን መሰረት የሚያደርገው የጉዳዮችን ክብደትና ቅለት መሆኑ የሚታመን ቢሆንም ከሳሹ ከሚጠይቀው ዳኝነት ውጪ ያለው እና ከሳሹ ከሚጠይቀው ንብረት ጋር ተያያዥነት ያለው ንብረት ግምት ሁሉ መሰረት ተደርጎ የፍርድ ቤት የስረ ነገር ስልጣን እንዲታይ የሚስገድድ የስነ ስርዓት ሕግ ድንጋጌ የለም፡፡ አመልካች ድርሻቸውን ለይተው በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 225 መሰረት ተገቢውን ዳኝነት ከፍለው በድርሻቸው ላይ ክርክር ከሚያቀርቡ በስተቀር ፍርድ ቤቱ ውርሱ ሲጣራ የውርስ ንብረት ስለመሆኑ በተረጋገጠው ንብረት ላይ ሌላ ክርክር የሚመራበት ሁኔታም የሌለ ሲሆን ተጠሪዎቹም ቢሆኑ ክርክር የቀረበባቸው ንብረቶች የውርስ ሃብት

አይደሉም የሚል ክርክር ያቀረቡ ስለመሆኑ የክርክሩ ሂደት አያሳይም፡፡ ከተጠሪዎች ውጪ ያለወገን መብት ቢኖር እንኳን አመልካች በድርሻቸው ተመስርተው ዳኝነት እስከጠየቁ ድረስ በሕጉ አግባብ የሚጠየቁበት ከሚኖር በስተቀር የንብረቱ ጠቅላላ ግምት የፍርድ ቤቱን የስረ ነገር ስልጣን ለመወሰን የግድ የሚልበት የሕግ መሰረት የለም፡፡

ሲጠቃለልም አመልካች የውርስ ንብረት ክፍፍል ጥያቄውን ያቀረቡት ድርሻቸውን መሰረት በማድረግ በመሆኑና የተጠሪ ድርሻ ደግሞ ከብር 500,000.00 (አምስት መቶ ሺህ ብር) በታች በመሆኑ በአዋጅ ቁጥር 25/88 አንቀጽ 14፣ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 17 እና 225 እና ሌሎች የውርስ ህግ ድንጋጌዎች መሰረት ክሱን የማየት የስረ ነገር ስልጣን ያለው የፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ሆኖ እያለ የሥር ፍርድ ቤት የህግ መሰረት የሌለውን መስፈርት በመጥቀስ ጉዳዩን የማየት የሥረ ነገር ስልጣን የለኝም በማለት መዝገቡን መዝጋቱም ሆነ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤትም ይህንኑ የስር ፍርድ ቤትን የሕግ መሰረት የሌለውን ብይን መቀበሉ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ሆኖ አግኝተናል፡፡ በዚህም መሰረት ተከታዩን ወስነናል፡፡

<u>**ው ሳ ኔ**</u>

1. በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 68766 በ21/02/2010 ዓ/ም ተሰጥቶ በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 205383 በ07/3/2011 ዓ/ም የጸናው ብይን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡
2. ጉዳዩን የማየት የሥረ ነገር ስልጣን የፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ነው ብለናል፡፡
3. የፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 68766 ክርክሩን ቀጥሎ በጉዳዩ ላይ ተገቢውን ዳኝነት እንዲሰጥበት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 341(1) መሠረት መልሰን ልከንለታል፡፡ ይጻፍ፡፡
4. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር ወጪና ኪሣራን በተመለከተ ግራ ቀኙ ወገኖች የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ብ/ግ

የሰ/መ/ቁ.155880

ሰኔ 28 ቀን 2011 ዓ.ም.

ዳኞች - መዓዛ አሽናፊ

ተፈሪ ገብሩ (ዶ/ር)

ቀነአ ቂጣታ

ተሾመ ሽፈራው

ፀሐይ መንክር

አመልካች - አግሪኮም ኢንተርናሽናል ኩባንያ -ጠበቃ አለሙ ደነቀው ቀረቡ::

ተጠሪ- የኢትዮጵያ ንግድ ስራዎች ኮርፖሬሽን-ጠበቆች ሜሮን ሰለሞን እና ዶ/ር ዘውድነህ በየነ ቀረቡ::

መዝገቡን መርምረን ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የስንዴ ግዢ ውልን መሰረት ያደረገ ሲሆን ክርክሩ የተደረገው ግራ ቀኙ እ.ኤ.አ ኖቨንበር 25/2011 ባደረጉት ስምምነት መሰረት አለመግባባታቸውን በኢትዮጵያ መሰረታዊ ህግ (Substantive Law) እንዲሁም በ Grain and Feeds Trading association (GAFTA) የሥነ ሥርዓት ህግ ቁጥር 125 (GAFTA Rules NO. 125) መሰረት በሚቋቋም የግልግል ዳኝነት አካል በእንግሊዝ ሃገር ለመቋጨት በተስማሙት መሰረት ነው፡፡

1. የአሁን ተጠሪ ለግልግል ጉባኤው ባቀረበው ክስ 200,000 ሜትሪክ ቶን ስንዴ ለማቅረብ አመልካች የውል ግዴታ ገብቶ ማቅረብ ባለመቻሉ ጥቅምት 9/2005 ዓ.ም ማስጠንቀቂያ ሰጥቼ ውሉን በማቋረጥ ሌላ ግዢ ፈጽሜያለሁ፤ ስለሆነም በፈፀምኩት አዲስ ግዢ ምክንያት ለ 11,549,000.00 (አስራ አንድ ሚሊዮን አምስት መቶ አርባ ዘጠኝ ሺህ) የአሜሪካ ዶላር ተጨማሪ ወጪ ተዳርጌያለሁ፤ ይህንኑ ገንዘብ እንዲከፍል ይወሰንልኝ በማለት ዳኝነት መጠየቁን የሚያሳይ ነው፡፡
2. አመልካች ለቀረበበት ክስ በሰጠው መልስ ስንዴውን ለማቅረብ ያልቻልኩት ስንዴውን ለማቅረብ የሚያስፈልገውን የባንክ የመተማመኛ ሰነድ (L/C) ተጠሪ አስተካክሎ በወቅቱ ለማቅረብ ባለመቻሉ በራሱ ጥፋት ነው፤ የራሱን ግዴታ ባልተወጣበት ሁኔታ ውሉን ለማቋረጥም ሆነ ኪሳራ ለመጠየቅ አይችልም፤ ከዚህም ሌላ ውሉ በሚተዳደርበት በኢትዮጵያ ህግ መሰረት ተገቢው ማስጠንቀቂያ ሳይሰጥ ተጠሪ ውሉን ሊያቋርጥ አይችልም፤ ስለሆነም ካሳ እንድከፍል ሊጠይቀኝ አይችልም፤ ይህ የሚታለፍ ቢሆንና የደረሰ ጉዳት አለ ከተባለ ተጠሪ ሊጠይቅ የሚችለው ለ200,000 ሜትሪክ ቶን የዋጋ መጠን በተሰጠው የመልካም ሥራ አፈፃፀም ሰነድ (Performance Bond) ማለትም 5,855,000.00 (አምስት ሚሊዮን ስምንት መቶ ሃምሳ አምስት ሺህ) የአሜሪካን ዶላር ብቻ ነው በማለት ተከራክሯል፡፡

3. ጉዳዩ በዚህ መልኩ የቀረበለት የግልግል ጉባኤ ክርክርና ማስረጃውን መርምሮ ተጠሪ ውሉን ያቋረጠው በአግባቡ ነው፤ ውሉን ለማቋረጥ የተሰጠው ማስጠንቀቂያም የኢትዮጵያ ህግ የሚጠይቀውን የሚያሟላ ነው፤ እንዲሁም ተጠሪ የጠየቀውን የካሳ መጠን የማይከፍልበት ምክንያት የለም በማለት አመልካች ለተጠሪ 11,549,000.00 (አስራ አንድ ሚሊዮን አምስት መቶ አርባ ዘጠኝ ሺህ) የአሜሪካ ዶላር እንዲከፍል የካቲት 20/2010 ዓ.ም ባሳለፈው ፍርድ ወስኗል፡፡
4. የሰበር አቤቱታው የቀረበው ይህን ውሳኔ በመቃወም ነው፡፡ አመልካች መጋቢት 18/2010 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር ማመልከቻ ውሳኔው የተሰጠው በኢትዮጵያ ህግ ላይ ተመስርቶ መሆኑንና ውሳኔውም የመጨረሻና በሁለቱ ወገኖች ላይ ተፈፃሚነት ያለው መሆኑ መደንገጉን፤ እንዲሁም የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰበር መዝገብ ቁጥር 42239 ከሰጠው ውሳኔ አንጻር ጉዳዩን ተቀብሎ ለመዳኘት እንደሚችልና ህገመንግስታዊ ሥልጣን ያለው መሆኑን ጠቅሶ ማመልከቻውን አቅርቧል፡፡
5. አመልካች በሰበር ማመልከቻው በ09/02/2005 ዓ.ም ተሰጠ የተባለው ማስጠንቀቂያ በ16/02/2005 ዓ.ም ከተጠሪ በተላከ መልዕክት የተነሳና የተሰረዘ በመሆኑ፤ ይህም ባይሆን ማስጠንቀቂያው የተሰጠው ተጠሪ የራሱን ግዴታ ሳይወጣና በቂ ጊዜም ሳይሰጥ የፍትሐብሔር ህጉንና የሰበር ውሳኔዎች ያስቀመጣቸውን መስፈርቶች ሳያሟላ ስለሆነ በአግባቡ ባልተቋረጠ ውል ላይ ተመስርቶ አመልካች 11,5490,00.00 (አስራ አንድ ሺህ አምስት መቶ አርባ ዘጠኝ) የአሜሪካ ዶላር እንዲከፍል የተሰጠው የግልግል ጉባኤ ውድቅ እንዲደረግ ጠይቋል፡፡ ይህ የሚታለፍ ከሆነም ለደረሰው ጉዳት መከፈል ያለበት ለ 200,000 ሜትሪክ ቶን ስንዴ ግራቀኙ ካደረጓቸው ውሎች ተለይቶ በተሰጠው የፐርፎርማንስ ቦንድ ገንዘብ መጠን ማለትም 5,855,000.00 (አምስት ሚሊዮን ስምንት መቶ ሃምሳ አምስት ሺህ) የአሜሪካን ዶላር ብቻ ነው ተብሎ እንዲወሰን አመልክቷል፡፡
6. የሰበር ማመልከቻው በአጣሪ ችሎቱ ተመርምሮ የግልግል ጉባኤው የሰጠው ውሳኔ ተዋዋይ ወገኖች ውሉን በተናጠል ለመሰረዝ (Unilateral Cancillation of Contract) ስለሚችሉበት አግባብ በሰበር መዝገብ ቁጥር 57280 ከተሰጠው አስገዳጅ የህግ ትርጉም አኳያ ተገቢነቱን መርምሮ ለመወሰን በሚል ጉዳዩ ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ እና ተጠሪ መልስ እንዲሰጥበት ተደርጓል፡፡
7. ተጠሪ መስከረም 22/2011 ዓ.ም በተፃፈ መልስ የኢፌዴሪ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የቀረበውን ጉዳይ ለማየት ስልጣን የለውም የሚል የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ እና በፍሬነገሩም መልስ ሰጥቷል፡፡
8. ተጠሪ ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን ለማየት ሥልጣን የሌለው ስለመሆኑ ባቀረበው የመቃወሚያ ክርክር የግልግል ዳኝነቱ መቀመጫ ኢትዮጵያ ውስጥ ባልሆነ የግልግል ዳኝነት የተሰጠ ውሳኔ በመሆኑ

ለኢትዮጵያ ፍርድ ቤት ጉዳዩ እንዲታይ የሚቀርብበት የህግ መሰረትም ልምድም የለም፤ የግልግል ዳኝነቱ ውሳኔ እንደ ኢትዮጵያ ፍርድ ቤቶች የመጨረሻ ውሳኔ ሆኖ እንዲቆጠር በተዋዋዮች መካከል የተደረገ ስምምነት ስለሌለ ውሳኔውን በኢትዮጵያ ግዛት ውስጥ እንደተሰጠ ውሳኔ ቆጥሮ በመሰረታዊ የህግ ስህተት ስም ለሰበር ሰሚ ችሎት እንዲቀርብ የሚደረግበት የህግ መሰረት የለም፤ ጉዳዩ በሰበር እንዲታይ የሚቀርብበት የህግ አግባብ የለም እንጂ አለ እንኳ ቢባል ሊቀርብ ይገባ የነበረው የግልግል ዳኝነቱ ህጋዊ መቀመጫ ሆኖ በተመረጠውና በተዋዋይ ወገኖች ተቀባይነትን ባገኘው እ.ኤ.አ በ1996 በፀደቀው የዩናይትድ ኪንግደም የአርቢትሬሽን ህግ መሰረት ለለንደን የከፍተኛው ፍርድ ቤት የንግድ ችሎት ብቻ ነበር፤ አመልካች የግልግል ዳኝነት አካሉ የመጀመሪያ ጉባኤ (First Tier Tribunal) በሰጣቸው ውሳኔዎች ቅር በመሰኘት ከአንዴም ሁለት ጊዜ የይግባኝ አቤቱታውን ለለንደን የከፍተኛው ፍርድ ቤት ንግድ ችሎት አቅርቦ ውድቅ ተደርጎበታል፤ አመልካች እ.ኤ.አ. በፌብሪዋሪ 27 ቀን 2018 በአምስት ዳኞች የተላለፈውን የ GAFTA የግልግል ዳኝነት የይግባኝ ጉባኤ የመጨረሻ ውሳኔ ቀሪ እንዲደረግ፣ እንዲሻር ወይም እንዳይፈፀም ለማድረግ አቤቱታውን ማቅረብ የነበረበት የግልግል ጉባኤው መቀመጫ ሀገር ህግ በሚፈቅደው መሰረት ሥልጣን ላለው ለለንደኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ንግድ ችሎት ነበር፤ ስለሆነም ይህ የሰበር አቤቱታ ስልጣን ለሌለው ፍ/ቤት የቀረበ በመሆኑ ውድቅ ሊደረግ ይገባል፡፡ አመልካች በሰ/መ/ቁ 42239 የተሰጠውን ውሳኔ በመጥቀስ አቤቱታውን ያቀረበ ቢሆንም በሁለቱ መዛግብት ክርክር ያስነሳው ጉዳይ፣ የውሉ ሁኔታዎች እና የግልግል ጉባኤው መቀመጫ ፈጽሞ የተለያየ በመሆኑ በሰ/መ/ቁ 42239 የተሰጠው ገዢ ትርጉም በዚህ መዝገብ ላይ ተፈጻሚ ሊሆን አይገባም፤ ሰበር ችሎቱ የመጨረሻና ይግባኝ የማይባልባቸው ናቸው የተባሉ የግልግል ዳኝነት ውሳኔዎችን ተቀብሎ ማየት የሚችለው የመጨረሻውን የግልግል ዳኝነት ወሳኔ ያስተላለፈው የግልግል ዳኝነት አካል ህጋዊ መቀመጫ (Juridical or Legal Seat) በኢትዮጵያ ከሆነ ብቻ ነው፤ ከዚህም ሌላ ተዋዋይ ወገኖች ውሳኔያቸውን የሚገዛው መሰረታዊ (የሥረ ነገር) ህግ (Substantive Law) የኢትዮጵያ ህግ በመሆኑና የኢትዮጵያ ህግ ሲተረጎም ደግሞ መሰረታዊ ስህተት ከተፈጸመበት ሊያቃና የሚችለው የኢትዮጵያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት ነው ከሚል ግንዛቤ የቀረበው ክርክር ተቀባይነት የለውም፤ በግራቀኙ የተመረጠው መሰረታዊ ህግ የኢትዮጵያ ህግ ቢሆንም ክርክር ሂደቱን የሚገዛው የሥነ ሥርዓት ህግ ደግሞ የግልግል ዳኝነት አካሉ (የ GAFTA የአርቢትሬሽን የሥነ ሥርዓት ህግ) ህጋዊ መቀመጫ ሀገር ህግ በመሆኑ ይህ ሰበር ችሎት "መሰረታዊ የህግ ስህተት ተፈጽሞበታል" የተባለውን የግልግል ዳኝነት ጉባኤ ውሳኔ የማየት ሥልጣን የለውም፡፡ በተዋዋይ ወገኖች የአርብትሬሽን የሥነ ሥርዓት ህጎች የሚወሰኑትም ከፍርድ ቤቶች ጣልቃ ገብነት ለመራቅ ሲባል ነው፡፡ በሌላም በኩል አመልካች በአቤቱታው የገለፀው ጥቅምት 9/2005 ዓ.ም የተሰጠው ማስጠንቀቂያ ጥቅምት 16/2005 ዓ.ም በተፃፈ ደብዳቤ ተነስቷል? ወይስ አልተነሳም? የሚለው ክርክር ማስረጃን የሚመለከት በመሆኑና

ውሳኔም የተሰጠው ማስረጃዎቹ ታይተው በመሆኑ በዚህ ረገድ የቀረበው ክርክር የህግ ክርክር አይደለም ለሰበር ችሎቱ በህግ በተሰጠው ስልጣን መሰረት ሊታይ የሚችል አይደለም ተብሎ ውድቅ ይደረግልን በማለት መቃወሚያውን አቅርቧል፡፡

9. ተጠሪ ከዚህም ሌላ በፍሬ ጉዳዩ ላይ ዝርዝር መልስ ሰጥቷል፡፡ የመልሱ ይዘት ባጭሩ ሲታይ በተጠሪ የተሰጠው ማስጠንቀቂያ አልተነሳም፤ በግራ ቀኙ መካከል በተገባው ውልና የውል ማራዘሚያ መሰረት አመልካች ሥንዴውን ማቅረብና ማጠናቀቅ የነበረበት ጊዜ ባለማቅረቡ ተጠሪ ጥቅምት 13/2005 ዓ.ም ማስጠንቀቂያ ሰጥቷል፤ ከዚህ በኋላ በአመልካች በቀረበ ጥያቄ መሰረት ተጠሪ ጥቅምት 16/2005 ዓ.ም የጻፈው ደብዳቤም ማስጠንቀቂያውን ያለቅድመ ሁኔታ አንስቻለሁ የሚል ሳይሆን ቅድመ ሁኔታዎችን በግልጽ አስቀምጦ ሁኔታዎች ከተሟሉ ብቻ ማስጠንቀቂያው ሊቀር እንደሚችል ገልጾ ነው፤ አመልካች ሁኔታዎችን ያላሟላ መሆኑንና ጥቅምት 13/2005 ዓ.ም የተሰጠው ማስጠንቀቂያ የፀና ስለመሆኑ የግልግል ዳኝነት ጉባኤው አጣርቶ ውሳኔ ሰጥቶበታል፤ ስለሆነም ማስጠንቀቂያው ተነስቷል ወይም ተሰርዟል በማለት ያቀረበው ክርክር የውልም ሆነ የህግ መሰረት የሌለው ነው፡፡ የተሰጠው ማስጠንቀቂያም በፍትሐብሔር ህጉ የተመለከቱትን ድንጋጌዎች እንዲሁም በሰ/መ/ቁ 57280 የተሰጠውን የህግ ትርጉም ባሟላ መልኩ የተደረገ ነው፡፡ በአጠቃላይ ተጠሪ ማስጠንቀቂያ የመስጠት ህጋዊ ግዴታ ባይኖርበትም ተጠሪ በአግባቡ ህጉን የተከተለ ማስጠንቀቂያ የሰጠ በመሆኑና የግልግል ዳኝነት ጉባኤው ማስረጃዎችን መርምሮ የተሰጠው ማስጠንቀቂያ ያልተነሳ መሆኑን በማረጋገጥ እንዲሁም ተጠሪ የሚጠበቅበትን የውል ግዴታ ቢወጣም አመልካች ግን ግዴታውን ያልተወጣ መሆኑን በማስረጃ አረጋግጦ የወሰነ በመሆኑ ቅሬታው ውድቅ ይደረግ፡፡ የመልካም ሥራ አፈጻፀም ዋስትና (ቦንዱ) በተመለከተም በአመልካች አቤቱታ የተጠቀሰው መጠን ስህተት ነው፤ በውሉ አንቀጽ 13 እንደተቀመጠው የመልካም ሥራ አፈጻፀም ዋስትናው የሚገባው የውሉን ዋጋ 10% መሆኑን ስለሚደነግግ ይህ ሲሰላ 14,637,500.00 የአሜሪካ ዶላር ይሆናል፤ አመልካች የ200,000 ሜትሪክ ቶን ስንዴ ዋጋን መሰረት በማድረግ ያስቀመጠው የዋስትና ገንዘብ መጠን የተሳሳተ እና የውል መሰረት የሌለው ነው፤ ውሉ የመልካም ሥራ አፈጻፀም ዋስትና (ቦንድ) መጠኑን ሲያስቀምጥ የዋሱን ኃላፊነት መጠን ለመገደብ እንጂ የጉዳቱን መጠን ለመገደብ እንደሆነ ያስቀመጠው ነገር የለም፤ ከቦንዱ በላይ ጉዳት ቢደርስ ተጨማሪ ካሳ መጠየቅ አይቻልም የሚል መደምደሚያ ላይ የሚያደርስ ነገርም የለም፤ በተጨማሪም በውሉ አንቀጽ 17 ላይ liquidated damage የተቀመጠ ሲሆን ይህም በአንቀጽ 13 ላይ የተቀመጠው የጉዳት ካሳ የመልካም ሥራ አፈጻፀም ዋስትና ሰነድ የጉዳት መጠኑን በአጠቃላይ ለመገደብ የተቀመጠ እንዳልሆነ የሚያሳይ ነው፡፡ በአጠቃላይ የአመልካች የሰበር አቤቱታ ውድቅ ተደርጎ የግልግል ጉባኤው ውሳኔ እንዲፀና በማለት ተከራክሯል፡፡

10. አመልካች ጥቅምት 23/2011 ዓ.ም በተጻፈ የመልስ መልስ በመቃወሚያው ላይ የበኩሉን ክርክር አቅርቧል፡፡ በዚህም መሰረት የጋፍታ የግልግል ጉባኤ (ቦርድ) የሰጠው ውሳኔ ጉዳዩ የሚዳኝበትን የኢትዮጵያ ህግ የጣሰ ነው በማለት የቀረበን ቅሬታ በኢትዮጵያ ህገ መንግስት አንቀጽ 80 እና በአዋጅ ቁጥር 454/97 መሰረት ለማየት ሥልጣን ያለው ሰበር ሰሚው ችሎት ነው፤ ሁለቱ ወገኖች ጉዳያቸውን በኢትዮጵያ መሰረታዊ ህግ (substantive law) መሰረት ለመገዛት ፈቃደኛነታቸውን በውል ከገለፁ የኢትዮጵያን ህግ አስመልክቶ ክርክር ቢነሳ ጉዳዩ ከሰበር ሰሚው ስልጣን ውጪ የሚሆንበት የህግ መሰረት የለም፤ ይህ ያልተገደበ የሰበር ስልጣን ፍርዱ በየትም ቦታ ቢሰጥ ወይም ውሳኔ የሰጠው አካል የተከተለው ሥርዓት (Procedure) ምንም ይሁን የተሰጠው ውሳኔ የኢትዮጵያ የህግ መስፈርቶችን አያሟላም የሚል ጥያቄ ከተነሳ ውሳኔ የሚሰጠው በህግ ስልጣን የተሰጠው ሰበር ሰሚ ችሎት ብቻ ነው፤ ተዋዋዮች በአንድ የግልግል ተቋም አማካኝነት በተወሰነ ሃገር ለመዳኘት ፈቃድ መስጠታቸው የግልግል ተቋሙ የሚመራበትን ሥርዓት (procedure) መቀበላቸውን ከሚያረጋግጥ በቀር መሰረታዊውን ህግ በተመለከተ ያላቸውን መብት ተነፍገዋል ማለት አይደለም፡፡ አመልካች በተለያዩ ጊዜያት ይግባኝ ሲያቀርብ የነበረው ለለንደኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ነው አሁንም በዚያው መሰረት ሊያቀርብ ይገባል ተብሎ በተጠሪ በኩል የቀረበውን ክርክር በተመለከተም ፍሬ ነገርን ወይም መሰረታዊ (የስረ ነገር) የህግ ስህተትን አስመልክቶ ለለንደን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ያቀረብነው አንዳችም ይግባኝ የለም፤ በርግጥ ጉዳዩ በግልግል ጉባኤ በመታየት ላይ እያለ ሁለት የሥነ ሥርዓት ጥያቄዎች ላይ በመመስረት አቤቱታ ለለንደን ፍርድ ቤት አቅርበናል፡- ይኸውም በመጀመሪያ ጉዳዩ ለግልግል ጉባኤ በቀረበበት ወቅት የአቤቱታ ማቅረቢያው ጊዜ አልፏል በማለት፣ ሁለተኛ ደግሞ ክርክሩ አልቆ ውሳኔውን ከመስማታችን በፊት ተዋዋይና ከሳሽ ወገን የነበረው የኢትዮጵያ እህል ንግድ ድርጅት አስቀድሞ ፈርሶ እያለ በፈረሰው ድርጅት ሥም ሲካሄድ የነበረው ክርክር እንደተካሄደ ሊቆጠር አይገባም በማለት የቀረበ የሥነ ሥርዓት ተቃውሞ ነው፤ የዚህ አይነት የሥነ ሥርዓት ተቃውሞ ደግሞ ክርክሩ የሚካሄድበትን ሥርዓት መሰረት በማድረግ በይግባኝ ለከፍተኛው ፍርድ ቤት መቅረቡ በአግባቡ ነው፡፡ ስለሆነም ተጠሪ ያቀረበው የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ውድቅ ሊደረግ ይገባል ብሏል፡፡ ፍሬ ጉዳዩን በተመለከተም አመልካች የቀደመ ክርክሩን በማጠናከር ውሉ የተቋረጠው ያላግባብ ስለሆነ የግልግል ጉባኤው ውሳኔ ውድቅ እንዲደረግ፤ ይህ የሚታለፍ ከሆነም የካሳው መጠን በመልካም ሥራ አፈጻፀም ቦንዱ ላይ የተቀመጠው የገንዘብ መጠን 5,855,000.00 (አምስት ሚሊዮን ስምንት መቶ ሃምሳ አምስት ሽህ) የአሜሪካን ዶላር ነው ተብሎ እንዲወሰን ጠይቋል፡፡

11. የጉዳዩ አመጣጥና የግራቀኙ የጽሁፍ ክርክር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተመለከተው ሲሆን ይህ ችሎትም በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያው ላይ ክርክራቸውን በቃል ሰምቷል፡፡ ጉዳዩንም የሠበር

አቤቱታ ከቀረበበት ውሣኔ እና አግባብነት ካላቸው የህግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምረናል፡፡

12. እንደመረመርነው በሰበር አጣሪ ችሎቱ እንዲታይ የተያዘው ጭብጥ ፍሬ ጉዳዩን የተመለከተ ቢሆንም ከዚህ በፊት የችሎቱን ምላሽ የሚጠይቀው ነጥብ የአሁን ተጠሪ ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት ጉዳዩን ተቀብሎ ለመወሰን ስልጣን የለውም በማለት ያቀረበው ክርክር ነው፡፡ ይህን ጭብጥ ለመመለስ ግራቀኙ በገቡት ስምምነት መሰረት ጉዳዩ በግልግል ጉባኤ ውሳኔ ያገኘበትን አግባብ እና የተሰጠውን ውሳኔ ተፈጥሮ፤ መሰል የአማራጭ ሙግት መፍቻ ዘዴዎችን በመጠቀም በሚሰጡ ውሳኔዎች ላይ ለመደበኛ ፍርድ ቤቶች አቤቱታ የሚቀርብበትን ሁኔታ፤ እንዲሁም በሀገራችን የተዘረጋው የሰበር ስርዓት አላማና የህጉን ማእቀፍ መመልከቱ ተገቢ ነው፡፡

13. በሀገር ውስጥ የግልግል ጉባኤ የመጨረሻ ውሳኔ ከሰጠ በኋላ ተከራካሪዎቹ ጉዳያቸውን ወደ ፍርድ ቤት በመውሰድ ይግባኝ የሚሉበትና ውሳኔው እንዲሻር ማመልከቻ የሚቀርብበት ሂደት በሥነ ሥርዓት ህጉ ተመልክቷል፡፡ ከፍትሐብሄር ሥነ ሥርዓት ህጉ ግልጽ ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ መረዳት እንደሚቻለው የግልግል ውሳኔው እንዲሻር የሚቀርበውን ማመልከቻ በመቀበል እንዲሁም የአፈፃፀም ክርክሩን በመወሰን ፍርድ ቤቶች የግልግል ዳኝነት ሂደትን ይቆጣጠራሉ፡፡ ፍርድ ቤቶች የግልግል ዳኛ በመሾም፣ በመሻር፣ ጉዳይን ወደ ግልግል በመምራት እንዲሁም ውሳኔ ከተላለፈ በኋላ ፍርዱን ሊመረምሩ የሚችሉበት ሁኔታ በህጉ ተደንግጓል፡፡ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህጉ ከአንቀጽ 350 እስከ 354 ስለ ይግባኝ፤ ከአንቀጽ 355 እስከ 356 ብይኑ ስለሚሻርበት እና ማመልከቻው ስለሚቀርብበት ሁኔታ የተደነገጉት ድንጋጌዎች ፍርድ ቤቶች የግልግል ዳኝነቱ የተቋቋመበትን ዓላማ ማሳካቱና እና በህጉ አግባብ ጉዳዩን መርቶ መወሰኑን እንዲያረጋግጡ የሚያስችሉ ናቸው፡፡ በአንፃሩ እነዚህ ድንጋጌዎች በውጪ ሀገራት የተሰጡ የግልግል ዳኝነቶችን በቀጥታ ይመለከታሉ ባይባልም የሥነ ሥርዓት ህጉ ከአንቀጽ 456 እስከ 461 ድረስ ከውጪ አገር ስለሚመጡ የግልግል ውሳኔዎች አፈፃፀም ሂደትን የሚመለከቱ ድንጋጌዎችን ይዟል፡፡

14. በሌላ በኩሉ በዓለም አቀፍ የግልግል ዳኝነት ያለው ልምድ እና የዳበረ የግልግል ዳኝነት ህግጋት ያላቸው የበርካታ ሀገራት ህጎች እንዲሁም አለምአቀፍ ስምምነቶች እንደሚያረጋግጡት የግልግል ዳኝነት ውሳኔዎች እንደመደበኛ ፍርድ ቤት ውሳኔ ተቆጥረው የግልግል ውሳኔዎችን በፍርድ ውሳኔ ለማስቀረት (setting aside) ወይም ለማሰረዝ (annulment) አቤቱታ ሊቀርብ የሚችለው በተዋዋይ ወገኖች መካከል ይኸው በስምምነት ሲደገፍ፣ ተዋዋይ ወገኖች በመረጡት የግልግል ዳኝነት የሥነ ሥርዓት ህግ (Institutional Arbitration Rule) ይኸው ሲደገፍ፣ እንዲሁም የግልግል ዳኝነቱ ህጋዊ መቀመጫ ሀገር (Juridical or Legal Seat) ህግ ይህንኑ የሚደግፍ ሲሆን ነው፡፡ በተያዘው ጉዳይ የግልግል ዳኝነቱ መቀመጫ በእንግሊዝ ሀገር መሆኑ

እንዲሁም ግራቀኙ ባደረጉት ስምምነት ውስጥ የግልግል ዳኝነቱ ውሳኔ እንደ ኢትዮጵያ ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ሆኖ እንዲቆጠር የተደረገ ስምምነት አለመኖሩ አላከራከረም፡፡ የተመረጠው የግልግል ዳኝነት መቀመጫ ሀገር ህግም ቢሆን በግልግል ጉባኤው የመጨረሻ ውሳኔ ላይ በዚያው ሀገር ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቤቱታ እንዲቀርብ የሚፈቅድ ነው፡፡ ስለሆነም የግልግል ጉባኤው ውሳኔ እንዲሻር/እንዲሻሻል አቤቱታው ለዚህ ፍርድ ቤት በቀጥታ የቀረበው ይህን የሚፈቅድ ህግ እንዲሁም የተዋዋይ ወገኖች ሥምምነት በሌለበት ነው፡፡

15. ከዚህ ጋር በተያያዘ አመልካች የግልግል ዳኝነት አካሉ የመጀመሪያ ጉባኤ (First Tier Tribunal) በሰጣቸው ውሳኔዎች ቅር በመሰኘት ከአንዴም ሁለት ጊዜ የይግባኝ አቤቱታውን ለለንደን የከፍተኛው ፍርድ ቤት ንግድ ችሎት አቅርቦ ውድቅ ተደርጎበታል፤ በመጨረሻው ውሳኔ ላይም ቅሬታው ሊቀርብ የሚገባ በዚሁ አግባብ ነው በማለት ተጠሪ የተከራከረ ሲሆን አመልካች በሰጠው መልስ ሁለት ጊዜ የይግባኝ አቤቱታ ለለንደን የከፍተኛው ፍርድ ቤት አቅርቦ እንደነበር ሳይክድ ያቀረበው ይግባኝ የስነ ሥርዓት ጉዳዮችን በተመለከተ ብቻ እንደነበርና ፍሬ ነገርን ወይም መሰረታዊ (የስረ ነገር) የህግ ስህተትን አስመልክቶ ለለንደን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ያቀረበው ይግባኝ እንደሌለ ተከራክሯል፡፡ እንደሚታወቀው በአንድ በተሰጠ ውሳኔ ላይ ይግባኝ የማለት መብት መሰረታዊ መብት ሆኖ የሚቆጠር ሲሆን የይግባኝ መብቱ ዝርዝር አፈፃፀም ግን የሚወሰነው በሥነ ሥርዓት ህጎች ነው፡፡ ስህተቱ የሥነ ሥርዓትም ሆነ የፍሬ ነገር ቢሆን ሊሰማና ሊታረም የሚችለው ለጉዳዩ ተፈፃሚነት ባለው የሥነ ሥርዓት ደንብ እየተመራ ነው፡፡ ስለሆነም የግልግል ዳኝነቱ አካል የሚመራበት ሥነ ሥርዓት ላይ ግራ ቀኙ ስምምነት አድርገው በዚሁ አግባብ ሁለት ጊዜ የይግባኝ አቤቱታ ለለንደኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት መቅረቡ ባላከራከረበት ሁኔታ አመልካች ፍሬ ነገርን ወይም መሰረታዊ የህግ ስህተትን አስመልክቶ ለመደበኛው ፍርድ ቤት ያቀረብኩት ቅሬታ የለም በማለት ያቀረበው ክርክር የሥምምነታቸውን ይዘት እና ጉዳዩ የሚገዛበትን ህግና ልምድ የተከተለ ባለመሆኑ ተቀባይነት የለውም፡፡

16. በሌላ በኩል አመልካች አጥብቆ የሚከራከረው ሁለቱ ወገኖች ጉዳያቸውን በኢትዮጵያ መሰረታዊ ህግ (substantive law) መሰረት ለመገዛት ፈቃደኛነታቸውን በውል ከገለፁ የኢትዮጵያን ህግ አስመልክቶ ክርክር ቢነሳ ጉዳዩ ከሰበር ሰሚው ስልጣን ውጪ የሚሆንበት የህግ መሰረት የለም፤ ይህ የሰበር ስልጣን ፍርዱ በየትም ቦታ ቢሰጥ ወይም ውሳኔ የሰጠው አካል የተከተለው ሥርዓት (Procedure) ምንም ይሁን የተሰጠው ውሳኔ የኢትዮጵያ የህግ መስፈርቶችን አያሟላም የሚል ጥያቄ ከተነሳ ውሳኔ የሚሰጠው ሰበር ሰሚ ችሎቱ ብቻ ነው በሚል ነው፡፡ ለዚህ ክርክራቸው መሰረት የሚያደርጉትም በሰ/መ/ቁ 42239 የተሰጠውን አስገዳጅ ትርጉም እና የህገ መንግስቱን አንቀጽ 80 እንዲሁም የአዋጅ ቁጥር 454/97 ድንጋጌን ነው፡፡ በእርግጥ በኢትዮጵያ ሁኔታ በግልግል ጉባኤ የሚሰጥ የመጨረሻ ውሳኔ አስገዳጅና ይግባኝ የማይባልበት ስለመሆኑ በተከራካሪዎች ስምምነት የተደረገበት ቢሆን ጉዳዩ በሰበር ችሎት ሊታይ ይገባል

ወይስ አይገባም? የሚለው ነጥብ አከራካሪ ሆኖ ይታያል፡፡ የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት በጉዳዩ ላይ አስቀድሞ ሰጥቶት የነበረውን አስገዳጅ ትርጉም በፓናል ችሎት በመለወጥ ትርጉም ሰጥቷል፡፡ በሰ/መ/ቁ 42239 *ብሔራዊ ማዕድን ኮርፖሬሽን ኃ/የተ/የግል ኩባንያ* እና *ዳኒ ድሪሊንግ ኃ/የተ/የግል ኩባንያ* መካከል በተደረገው ክርክር ሰበር ችሎቱ የግልግል ውሳኔን የመጨረሻነት እንዲሁም በግልግል ዳኝነት አካላት የተሰጡ ውሳኔዎችን በተመለከተ ፍርድ ቤቶች ሊኖራቸው የሚገባውን ሚና አስመልክቶ አስገዳጅ ትርጉም ሰጥቶ ወስኗል፡፡ በዚህም መሰረት "...... *አማራጭ የሙግት መፍቻ ዘዴዎች በኢትዮጵያ የህግ ስርዓት ውስጥ ተካተው የሚገኙ ሲሆን እነዚህን የሙግት መፍቻ ዘዴዎች ፍርድ ቤቶች የሚያበረታቱበት አጋጣሚ እንዳለ ሁሉ የሚቆጣጠሩበት ሁኔታ መኖሩን............፣ ከዚህ አኳያ አንድ ጉዳይ ለሰበር የመቅረቡ ሁኔታ በህገ መንግስቱ ለፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የተሰጠ ሥልጣን በመሆኑ የሰበር ስርዓቱ ሊጫወተው ከተፈለገው ዐቢይ ዓላማ አንፃር ሲታይ ጉዳያቸው በግልግል ዳኝነት እንዲታይላቸው የተስማሙ ወገኖች የግልግል ዳኝነቱ የሚሰጠው ውሳኔ የመጨረሻ ነው በማለት ስለተስማሙ ብቻ ጉዳዩ በሰበር ሥርዓቱ እንዳይታይ ፍላጎት አሳይተዋል ተብሎ መሰረታዊውን የህግ ስህተት ላለማሳረም ምክንያት ሊሆን የሚችል አይደለም...."* በማለት የኢፌዴሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 80(3)(ሀ)፣ አዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 10፣ እና አዋጅ ቁጥር 454/1997 አንቀጽ 2(1) መሰረት በማድረግ ወስኗል፡፡ ነገር ግን ሊታይ የሚገባው ይህ ውሳኔ ለተያዘው ጉዳይ ያለው ተገቢነትና አስገዳጅነት ነው፡፡ ከውሳኔው መገንዘብ እንደሚቻለው በጉዳዩ ላይ በሰበር ችሎቱ ውሳኔ የተሰጠው የግልግል ችሎቱ መቀመጫ እዚሁ ኢትዮጵያ ውስጥ መሆኑን ተከትሎ በመሆኑ አሁን በእጃችን ካለው ጉዳይ ጋር የተገናኘ አይደለም፡፡ በተያዘው ጉዳይ ግራቀኙ ባደረጉት የግዥ እና ሽያጭ ውል የግልግል ዳኝነት መቀመጫውን በእንግሊዝ ሀገር ለንደን ከተማ ያደረገ የግልግል ተቋም የመረጡ ሲሆን በ Grain and Feeds Trading association (GAFTA) የሥነ ሥርዓት ህግ ቁጥር 125 (GAFTA Rules NO. 125) መሰረት ለመዳኘትም ተስማምተዋል፡፡ በሰ/መ/ቁ 42239 የተሰጠው ውሳኔ ደግሞ ይህን መሰረት አድርጎ የተሰጠ ባለመሆኑ ከተያዘው ጉዳይ ጋር የሚገናኝ አይደለም፡፡ ተመሳሳይ የፍሬ ነገር ወይም የህግ ክርክሮች በሌሉበት ሁኔታ አስቀድሞ የተሰጠ የሰበር ውሳኔ በጉዳዩ ላይ ተፈፃሚ እንዲሆን የሚደረግበት የህግ አግባብ እንደሌለም ከአዋጅ ቁጥር 454/97 አንቀጽ 2(4) ግልጽ ድንጋጌ መገንዘብ ይቻላል፡፡

17. በሌላ በኩል የሰበር አቤቱታ የቀረበበት የግልግል ጉባኤ ውሳኔ (APPEAL AWARD NO: 4496 & 4515) መግቢያ ላይ በተራ ቁጥር 1.4 ሥር የሚከተለው ተመልክቷል፡-

> "As the seat of the arbitration is in England and an Award subject to English procedural and Ethiopian substantive law, it therefore follows that it is an English Award for the purpose of recognition and enforcement

under the terms of the 1958 New York Convention on the Recognition and Enforcement of Foreign Arbitral Awards"

የዚህ የአማርኛ ትርጉምም እንደሚከተለው ይነበባል፡-

> "የግልግል ዳኝነቱ መቀመጫ ቦታ እንግሊዝ ሀገር በመሆኑና የዳኝነቱ ሂደት የሚመራው በእንግሊዝ የሥነ ስርዓት ህግ፣ የውሉን ይዘት በተመለከተ ግን ተፈፃሚው የኢትዮጵያ ህግ በመሆኑ፤ የግልግል ውሳኔው እንደ እንግሊዝ አገር ውሳኔ ተቆጥሮ ውሳኔው ዕውቅና የሚያገኘውና ተፈፃሚም የሚሆነው ከአንድ አገር ውጪ የተሰጠን ውሳኔ አፈፃፀም በተመለከተ በ1958 የወጣው የኒዮርክ ዓለም አቀፍ ኮንቬንሽን ነው"

18. ከዚህ የግልግል ጉባኤ ውሳኔ ይዘት መገንዘብ እንደሚቻለው የግልግል ውሳኔው ከአንድ አገር ውጪ የተሰጠ ውሳኔ (በእንግሊዝ) ተደርጎ የሚወሰድና ውሳኔው ዕውቅና የሚያገኘውና ተፈፃሚም የሚሆነው በ1958 የወጣው የኒዮርክ ዓለም አቀፍ ኮንቬንሽን መሰረት ስለመሆኑ ነው፡፡ ስለሆነም ለሰበር ክርክሩ አወሳሰን ሲባል ይህ የግልግል ጉባኤው ውሳኔ ተፈጥሮና በ1958 የወጣው የኒዮርክ ዓለም አቀፍ ኮንቬንሽን በሀገራችን የህግ ሥርዓት ያለውን ቦታ በአግባቡ መመርመር ይጠይቃል፡፡

19. ከሀገር ውጪ የሚሰጡ የግልግል ውሳኔዎችን በሃገራት ውስጥ በማስፈፀም ረገድ እ.ኤ.አ በ1958 የወጣው ለግልግል ዳኝነት ውሳኔዎች ዕውቅና መስጠትና ማስፈፀምን የሚመለከት የኒውዮርክ ኮንቬንሽን (The New York Convention on the Recognition and Enforcement of Arbitral Awards) እንደ ትልቅ ስኬትና እመርታ ይወሰዳል፡፡ በርካታ የዘርፉ ተመራማሪዎች እንደሚመሰክሩለትም ከሁሉም ሃገራት ፍላጎት ጋር በሚስማማ መልኩ የግልግል ውሳኔዎች በቀላሉ የሚፈፀሙበትን መንገድ ዘርግቷል ተብሎ ይታመናል፡፡ በሃገራችንም ከኢኮኖሚው እድገት ጋር ተያይዞ ድንበር ተሻጋሪ የንግድ ልውውጦች እየተጠናከሩ በመሆኑና ግዙፍ ኩባንያዎች የገበያ አድማሳቸውን በማስፋት ወደ ሃገራችን በማቅናት መዋዕለ ንዋያቸውን እያፈሰሱ በመሆኑ ይህን ዘላቂ ለማድረግ፤ በተለይም ኢትዮጵያ የዓለምአቀፉ የንግድ ማህበር (World Trade Organization) አባል ለመሆን በምታደርገው ጥረት አንዱ መመዘኛ ተደርጎ የሚወሰድ በመሆኑ፤ እንዲሁም አለመግባባቶች በግልግል መቋጨታቸው ከሚኖረው ዘርፈ ብዙ ጠቀሜታ አንፃር ሃገራችን የኒውዮርኩን ኮንቬንሽን ለማጽደቅ በሂደት ላይ መሆኗ ይታወቃል፡፡

20. የኒዮርኩ ኮንቬንሽን እስካሁን በሃገራችን አልፀደቀም ማለት ግን በህግ ሥርዓታችን ውስጥ ምንም ቦታ አልተሰጠውም ማለት እንዳልሆነ ተገቢነት ያላቸውን ድንጋጌዎች በማየት መገንዘብ ይቻላል፡፡ በሀገራችን ውስጥ በግልግል ጉባኤዎች የሚሰጡ ውሳኔዎች የሚፈፀሙት የፍርድ ውሳኔዎች በሚፈፀሙበት መንገድ ስለመሆኑ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 319 በግልጽ ተደንግጓል፡፡

በሌላ በኩል ከውጪ ሀገር የሚመጡ የግልግል ውሳኔዎች የሚፈፀሙበት ራሱን የቻለ ሥርዓት በፍትሐ ብሔር ሥነ ሥርዓት ህጉ ከአንቀጽ 456 እስከ 461 ተደንግጎ ይገኛል፡፡

21. ከኒዮርኩ ስምምነት ይዘትና ከሃገራችን ህጎች መገንዘብ እንደሚቻለው በውጭ ሃገራት የሚሰጡ የግልግል ውሳኔዎችን በማስፈፀም ረገድ የኢትዮጵያ ህግ ከኒዮርክ ስምምነት ጋር ተመሳሳይነት አለው፡፡ መመሳሰሉን ለማሳየት የሚከተሉትን ነጥቦች በማነፃፀር ማንሳት ይቻላል፡-
    - የስምምነቱ አንቀጽ 1(3) ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 458(ሀ) እና 461(1)(ሀ)
    - የስምምነቱ አንቀጽ 3 ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 461(1) ይዘት ጋር
    - ከኒውዮርኩ ስምምነት በዋናነት የሚጠቀሱት በአንቀጽ 5 ሥር የተጠቀመጡት ሁኔታዎች ሲሆኑ እነዚህ ሁኔታዎች ከኢትዮጵያ ህግ ጋር በእጅጉ የሚመሳሰሉ መሆኑን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 461(1)(ለ)-(ሠ) ከተዘረዘሩት ጋር በማነፃፀር መረዳት ይቻላል፡፡

22. በዚህ መልኩ በኒውዮርክ ስምምነት እና በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 461 መካከል የቃል በቃል መመሳሰል እንዴት ሊፈጠር ቻለ የሚለውን በአግባቡ ማየትም ያስፈልጋል፡፡ በኒውዮርክ ስምምነት እና በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህጉ መካከል ላለው መመሳሰል በምክንያትነት የሚጠቀሰው የሥነሥርዓት ህጉ የወጣው የኒውዮርኩ ስምምነት በወጣ በጥቂት አመታት ውስጥ መሆኑ ነው፡፡ የሥነ ሥርዓት ህጉ እ.ኤ.አ በ08/10/1965 የወጣ ሲሆን የኒዮርክ ስምምነት ለፊርማ ክፍት የሆነው እ.ኤ.አ በ31/12/1958 ነው፡፡ ከዚህ በመነሳት ህግ አውጭው በውጪ ሃገራት የተሰጡ የግልግል ውሳኔዎችን ለማስፈፀም እንዲሁም አፈፃፀሙን ለመቃወም ሊጠቀሱ የሚችሉ ምክንያቶችን ከኒዮርክ ስምምነት ሊወስድ መቻሉ ይታመናል፡፡

23. ስለሆነም በተያዘው ጉዳይ ግራቀኙ ያደረጉትን ስምምነት ተከትሎ የግልግል ጉባኤው የሰጠው ውሳኔ እንደ እንግሊዝ አገር ውሳኔ የተቆጠረ በመሆኑ መሰረታዊ የህግ ስህተት ለማሳረም በሚል ለዚህ ፍርድ ቤት መቅረቡ ተገቢ ባይሆንም ውሳኔው ዕውቅና የሚያገኘውና ተፈፃሚም የሚሆነው ከአንድ አገር ውጪ የተሰጠን ውሳኔ አፈፃፀም በተመለከተ በ1958 በወጣው የኒዮርክ ዓለም አቀፍ ኮንቬንሽን መሰረት በመሆኑ በዚህ አግባብ አቤቱታ ሊቀርብና ሊስተናገድ አይገባም ማለት ግን አይሆንም፡፡

24. በአጠቃላይ ግራቀኙ ወገኖች በ Grain and Feeds Trading association (GAFTA) የሥነ ሥርዓት ህግ ቁጥር 125 (GAFTA Rules NO. 125) መሰረት በሚቋቋም የግልግል ዳኝነት አካል በእንግሊዝ ሃገር ክርክራቸውን ለመቋጨት የተስማሙ በመሆኑና የግልግል ዳኝነቱ ውሳኔ የተሰጠውም ይህን ስርዓት ተከትሎ በመሆኑ፤ አመልካቹም በግልግል ጉባኤው ውሳኔ ላይ የይግባኝ ቅሬታውን በውል ስምምነታቸው እና በህግ በተዘረጋው ስርዓት መሰረት ለንደን ለሚገኘው ከፍተኛ ፍርድ ቤት ቅሬታውን በየጊዜው ያቀርብ እንደነበር የተረጋገጠ በመሆኑ፤ አመልካች አቤቱታውን ለዚህ ሰበር ችሎት ለማቅረብ በዋቢነት በጠቀሰው የሰ/መ/ቁ 42239

የተሰጠው የህግ ትርጉም የግልግል ጉባኤው መቀመጫ በተዋዋዮች በስምምነት ወይም ከህግ በተሰጠ ስልጣን በውጪ ሀገር እንዲሆን ተደርጎ በውጪ ሀገር የተሰጠ ፍርድን የሚመለከት ባለመሆኑ፤ እንዲሁም ለፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት በኢፌዴሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 80(3)(ሀ) እና በፌዴራል ፍርድ ቤቶች ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 10 (በአዋጅ ቁጥር 454/97 አንቀጽ 2 እንደተሻሻለ) የተሰጠው መሰረታዊ የህግ ስህተትን የማረም ስልጣን የተያዘውን ጉዳይ የሚመለከት ባለመሆኑ አመልካች ያቀረበው የሰበር አቤቱታ ተቀባይነት የለውም ብለናል፡፡ ተከታዩንም ወስነናል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. አመልካችና ተጠሪ እ.ኤ.አ ኖቬንበር 25/2011 ባደረጉት ስምምነት መሰረት አለመግባባታቸውን በ Grain and Feeds Trading association (GAFTA) የሥነ ሥርዓት ህግ 125 (GAFTA Rules NO. 125) መሰረት በሚቋቋም የግልግል ዳኝነት አካል በእንግሊዝ ሃገር ለመቋጨት በተስማሙት መሰረት የተቋቋመው ጉባኤ የሰጠው ውሳኔ (APPEAL AWARD NO: 4496 & 4515) በኢፌዴሪ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት ታይቶ እንዲታረም የቀረበው የሰበር ማመልከቻ በግራቀኙ የተደረገውን ስምምነት እና ህጉን መሰረት ያደረገ ባለመሆኑ ተቀባይነት የለውም በማለት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 244(2)(ሀ) እና 245(2) መሰረት ወስነናል፡፡
2. አመልካች ለዳኝነት ከከፈለው ብር 1,605,760.10 (አንድ ሚሊዮን ስድስት መቶ ሰምስት ሺህ ሰባት መቶ ስድሳ ብር ከአስር ሳንቲም) ላይ በደንቡ መሰረት የሚቀነሰው ሂሳብ ከተቀነሰ በኋላ ቀሪው ገንዘብ ለአመልካች እንዲመለስ ብለናል፡፡ የፍርድ ቤቱ ሬጅስትራር ይህን ተከታትሎ ያስፈጽም፡፡
3. ውሳኔው ሀምሌ 5/2011 ዓ.ም በችሎት ተነቧል፡፡
4. በዚህ ችሎት ስለተደረገው ክርክር ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአራት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

## <u>የልዩነት ሀሳብ</u>

ውል የተዋዋይ ወገኖችን ነፃነት የሚያሳይ መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ ነገር ግን ተዋዋይ ወገኖች ውል በሚያደርጉበት ጊዜ ውሉ ህግን እና ሞራልን የሚቃረን መሆን ሊቃረን አይገባም፡፡

አመልካችና ተጠሪ ጉዳያቸውን በግልግል ለማሳየት መስማማታቸው የዳኝነቱ አገር እና የስነ ስርአት ህግ መምረጣቸው ጤናማ የውል ስምምነት ሲሆን ነገር ግን ከተዋዋዮች አንዱ የኢትዮጵያ መንግስት

መ/ቤት ሆኖ የተዋዋሉበት ነገር ለኢትዮጵያ ሆኖ የተዋዋሉበት ነገር ለኢትዮጵያ እና ህዝቦቿ ጥቅም እንዲሰጥ መሆኑ ተረጋግጦ አለ እንዲሁም የሚፈፀመውም በኢትዮጵያ ሆኖ አመልካችን እንደ አንድ ተዋዋይ ግለሰብ በማሰብ የኢትዮጵያ ፍ/ቤት በማንኛውም ደረጃ ጉዳዩ ቢቀርብለት የማየት ስልጣን እንደሌለው አድርጎ መዋዋል ህግን እና ሞራልን የሚጋፋ እንዲሁም ብሄራዊ ጥቅምን የሚጎዳ ከመሆኑም በላይ በውጭ አገር የተሰጠው ፍርድ የኢትዮጵያ መሰረታዊ ህግ ግድፈት በተፈፀመበት ጊዜ በኢትዮጵያ ፍ/ቤት አይታይም አይልም እንጂ የግልግል ዳኝነቱ መቀመጫም ሆነ የሚመራበት ስነ ስርአት ህግ በኢትዮጵያ ባለመሆኑ እና የሚሰጠው ፍርድም የለንደን ፍርድ እንደሆነ መቆጠሩ በኢትዮጵያ ፍ/ቤት ፍርዱ ላይ መሰረታዊ የህግ ጥሰት ተፈጽሟል የሚል ወገን አቤቱታ ሲያቀርብ ፍ/ቤቱ የማየት ስልጣን የለውም የሚባል ከሆነ ኢትዮጵያን በራሷ ጥቅም ላይ ጉዳይዋን እንዳታይ ያገለለ ከመሆኑ አንፃር ውሉ በራሱ ለህግና ለሞራል ተቃራኒ የሆነ ውል በመሆኑ ከመነሻው ተቀባይነት ማግኘት ያልነበረበት ውል ነው ባይ ነኝ፡፡

በአመልካች እና በተጠሪ መካከል ጉዳዩ በግልግል እንዲታይ፣ መስማማታቸው በስምምነታቸው መሰረትም የግልግል ዳኝነቱ ህጋዊ መቀመጫ አገር ለንደን መሆኑን እና ግልግሉ የሚመራበትን የስነ ስርአት ህግ የመረጡ መሆኑ እና ውሳኔው በኢትዮጵያ እንደተሰጠ ፍርድ እንደማይቆጠር በመስማማታቸው ላይ ልዩነት እንደሌላቸው ተረድቻለሁ፡፡

ነገር ግን በዚህ መልኩ ተዋዋይ ወገኖች የተዋዋሉ መሆኑ እና በተለይ መንግስት በሚያስተዳድረው መ/ቤት የተወከሉ የስራ ኃላፊዎች ጉዳዩ በውጭ አገር እንዲታይ እና በውጭ አገር ህግም እንዲመራ የተስማሙበትን ልዩ ምክንያት ሳያስቀምጡ በአገር ጥቅም ላይ ስምምነት በማድረጋቸው ብቻ የኢትዮጵያ ፍ/ቤቶች በተለይም የሰበር ሰሚ ችሎቱ ስልጣን የለውም ለማለት የሚቻልበት አግባብ ተገቢነት ያለው አይደለም፡፡

ግራ ቀኙ  የስነ ስርአት ግድፈት ሲፈጽም ለለንደን ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ ማለት የሚችሉ መሆኑ የተዋዋሉ በመሆኑ አመልካች በለንደን በስነ ስርአት ጉዳይ ላይ ይግባኝ ማለቱን አልካደም፣ ተጠሪም በስነ ስርአት ጉድለት ብቻ ሳይሆን በፍሬ ነገር ላይም ይግባኝ ብሏል ቢልም በምን አይነት ፍሬ ነገር ላይ ይግባኝ እንዳለ ባልገለፀበት እና በአብላጫው ድምጽ እንደተገለጸው ሁለት ጊዜ ለለንደን ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ የተባለው በስነ ስርአት ግድፈት ላይ መሆኑ የሚያስረዳ ሆኖ እያለ በፍሬ ጉዳይ ላይ ይግባኝ እንዳለ በመቁጠር በስምምነቱ መሰረት ጉዳዩ የሚታየው በለንደን አገር እና በለንደን ፍ/ቤት ብቻ ነው መባሉ ሌላው ጉዳይ ነው፡፡

እንዲሁም ክርክር ያስነሳው ጉዳይ ሰንዴን ወደ ኢትዮጵያ ለማስመጣት ሆኖ ስንዴውን የሚጠቀሙት ኢትዮጵያውያን ሆነው እያለ እንዲሁም የግልግል ጉባኤው የመጨረሻ ውሳኔ ላይ ለዛው አገር ከፍተኛ ፍ/ቤት አቤቱታ የሚቀርብ መሆኑን ይግለጽ እንጂ በኢትዮጵያ ፍ/ቤት የሰበር ስልጣንን በሚያስቀር

መልኩ ስለመዋዋላቸው የሚያሳይ ነገር ሳይኖር አመልካች ቀደም ሲል በስነ ስርአት ግድፈት ምክንያት ለከፍተኛ ፍ/ቤቱ ይግባኝ ያቀረበ ሲሆን ለዛው ይግባኙን ላየው ፍ/ቤት ደግሞ አቤቱታ እንዲያቀርብ ስምምነቱን ማድረጉ በራሱ ኢትዮጵያ ምንም አይነት ተሳትፎ እንዳይኖራት ተደርጎ ውል የተደረገ መሆኑን ከማሳየቱም በላይ አመልካች በኢትዮጵያ የሚገኝ የመንግስት ተቋም እንደመሆኑ መጠን በኢትዮጵያ መሰረታዊ የሆኑ ህጎች የመዳኘት መብት ያለው መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ እና አመልካች ውል ውስጥ ሲገባ ማንኛውንም መብት የተወ መሆኑን ባልገለጸበት ሁኔታ የአመልካቾች ጥያቄም የኢትዮጵያ መሰረታዊ ህግ ተጥሶብናል በሚል አቤቱታ አቅረበው ባለበት፣ በስምምነታቸውም የስነ ስርኣት ግድፈት ሲኖር ይግባኝ ማለት እንደሚችሉ እንጂ መሰረታዊ ህግ ሲጣስ ለለንደን ፍ/ቤት ይግባኝ ይላሉ ተብሎ ውል ባልተገባበት ሁኔታ በተለይ ተዋዋይ ወገኖች መንግስታዊ አካላት ከሆኑ የሚዋዋሉትን ውሎች የመንግስትን እና የአገሪቱን ጥቅም በሚያስጠብቅ ሁኔታ መዋዋል ያለባቸው መሆኑ ስለታመነበት የፌዴራል ጠቅላይ ዐቃቤ ህግን ለማቋቋም እና ስልጣኑን ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 943/2008 አንቀጽ 6/4/ለ/ መሰረት የፌዴራል ጠ/ዐቃቤ ህግ ውሎችን እንዲመረምር መደረጉ ከብሄራዊ ጥቅም አንፃር በራሱ በዚህ መልኩ የሚፈፀሙ ውሎች በአገር ጥቅም ላይ ጉዳት ሊያድርሱ የሚችሉ ከመሆኑ አኳያም ሲታሰብ የአገሪቱ የመጨረሻ የሆነው ፍ/ቤት በውጭ አገር የተሰጠን ፍርድ የግልግል ዳኝነቱ አገር በመመረጡ እና የስነ ስርአት ህጉ በመመረጡ እንዲሁም ፍርዱ በኢትዮጵያ እንደተሰጠ ፍርድ ይቆጠራል በሚል በውሉ ባለመገለፁ መሰረታዊ የህግ ጥሰት እንዲታረም የቀረበን አቤቱታ ባለመቀበል ፍ/ቤቱ ስልጣን የለውም ተብሎ በአብላጫው የተሰጠው ፍርድ ተገቢ አይደለም በማለት ፍ/ቤቱ ጉዳዩን ለማየት ስልጣን አለው ተብሎ ብይን ተሰጥቶ ወደ ዋናው ጉዳይ ተገብቶ ሊመረመር ይገባ ነበር በማለት ስሜ በተራ ቁጥር 5 ስር የተሰየምኩት የችሎት ዳኛ በአብላጫው ድምጽ በሃሳብ ተለይቻለሁ፡፡

የማይነበብ የአንድ ዳኛ ፊርማ አለበት፡፡

ፋ/ዘ

የሰ/መ/ቁ. 161597

ግንቦት 27 ቀን 2012 ዓ.ም

ዳኞች ፡- ብርሀኑ አመነው

ተሾመ ሽፈራው

ሀብታሙ እርቅይሁን

ብርሀኑ መንግስቱ

ነፃነት ተገኝ

አመልካች፡- ወ/ሮ ፍሬህይወት ገበየሁ

ተጠሪ፡- አቶ ዘሪሁን ተፈራ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ በውጪ ሀገር የተሰጠ ፍርድ የሚፈፀምበትን አግባብ የሚመለከት ነው፡፡ አመልካች ለፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በቀን 19/07/2009 ዓ.ም ፅፈው ባቀረቡት የአፈፃፀም አቤቱታ የአሜሪካን የዲስትሪክት ፍ/ቤት በአመልካችና በተጠሪ መካከል የነበረውን የባልና ሚስት ፍቺና ንብረት ክፍፍል ክርክር መርምሮ እንደ አውሮፓውያን አቆጣጠር በቀን 1/02/2013 ዓ.ም በሰጠው ውሳኔ መሠረት ተጠሪ እንዲፈፅሙ ይወሰንልኝ በማለት ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡

ፍርድ ቤቱም የአመልካችን አቤቱታ መርምሮ በውጪ ሀገር የተሰጠ ፍርድ በኢትዮጵያ ውስጥ እንዲፈፀም ሊሟሉ ከሚገባቸው ቅድመ ሁኔታዎች አንዱ እንዲፈፀም የተጠየቀውን ፍርድ የሰጠው ፍርድ ቤት የሚገኝበት ሀገር በኢትዮጵያ የተሰጠውን ፍርድ የሚፈፅም መሆኑ ሲረጋገጥ በመሆኑ ይህንኑ መሠረት በማድረግ የኢትዮጵያ ፍ/ቤቶች የሚሰጡት ውሳኔ በአሜሪካን ፍርድ ቤቶች የሚፈፀሙ ስለመሆን አለመሆኑ እንዲሁም ይህንኑ በተመለከተ የሁለቱ ሀገራት የሁለትዮሽ ስምምነት ስለመኖር አለመኖሩ ለፍ/ቤቱ እንዲገለፅ ለኢ.ፌ.ዲ.ሪ የውጪ ጉዳይ ሚኒስቴር በቀን 01/03/2010 ዓ.ም ትዕዛዝ ሰጥቶ በቀን 10/04/2010 ዓ.ም በተፃፈ ምላሽ በሁለቱ ሀገራት መካከል ፍርድን ለማስፈፀም የሚያስችል ስምምነት አለመኖሩ የተገለፀ በመሆኑና የኢትዮጵያ ፍርዶችም በአሜሪካን ሀገር የማይፈፀሙ ስለመሆኑ በቀን 27/04/2010 ዓ.ም በተፃፈ ደብዳቤ ከኢ.ፌ.ዲ.ሪ የውጪ ጉዳይ ሚኒስቴር ስለተገለፀ አመልካች ያቀረቡት የፍርድ ይፈፀምልኝ አቤቱታን አልተቀበልኩትም በማለት መዝገቡን ዘግቶታል፡፡ በዚህ ውሳኔ ቅር የተሰኙት

አመልካች ይግባኛቸውን ለፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ይግባኝ ቢያቀርቡም የይግባኝ አቤቱታቸው ተቀባይነት ሳያገኝ ቀርቷል፡፡

ለዚህ ፍርድ መነሻ የሆነው የሰበር አቤቱታ የቀረበውም እነዚህ በስር ፍርድ ቤት የተሰጡትን ውሳኔዎች ለማስለወጥ ነው፡፡ አመልካች በጠበቃቸው አማካኝነት ሐምሌ 18 ቀን 2010 ዓ.ም በተፃፈ 03 ገፅ የሰበር አቤቱታ በስር ፍርድ ቤቶች ተፈፅመዋል ያሏቸውን ስህተቶች ዘርዝረው በማቅረብ እንዲታረሙላቸው ጠይቀዋል፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ ይዘት በአጭሩ የስር ከፍተኛ ፍ/ቤት በሁለቱ ሀገሮች መካከል የአንዱን ሀገር ፍርድ እንዴት እንደሚፈፀም የጋራ ስምምነት የለም ተብሎ ተረጋግጦ እያለ በተዘረጋለት ስርዓት ጉዳያችንን ሊያስተናግድ ሲገባ "የተለየ ስምምነት ከሌለ..." የሚለውን ሀረግ በስህተት በመተርጎም ፍርዱ ሊፈፀም አይገባም በማለት መወሰኑ ተገቢነት የሌለው በመሆኑ ሊታረም ይገባዋል የሚል ነው፡፡

ጉዳዩም በሰበር አጣሪው ተመርምሮ አመልካች በአሜሪካን ሀገር ፍ/ቤት የተሰጠዉን ዉሳኔ መሠረት አድርገው በኢትዮጵያ ፍ/ቤት ያቀረቡት የአፈፃፀም ክስ በሁለቱ ሀገራት መካከል ፍርድን ለማስፈፀም የሁለትዮሽ ስምምነት የለም ተብሎ ውድቅ የመደረጉን አግባብ ከፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ. 256 እና ተከታዮቹ አንፃር ለማጣራት መዝገቡ ለሠበር ችሎት ቀርቧል፡፡ በጉዳዩ ላይ አመልካች መልስ እንዲሰጥበት በጋዜጣም ጭምር ጥሪ ቢደረግለትም ሊቀርብ ባለመቻሉ መልስ የማቅረብ መብታቸው ታልፎ ክርክሩ በሌለበት እንዲቀጥል ትዕዛዝ ተሰጥቷል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ ይዘት አጠር ባለ መልኩ ከላይ የተገለፀውን ሲመስል ይህ ችሎትም የአመልካችን የሠበር አቤቱታ በሰበር አጣሪ ችሎት ከተያዘው ጭብጥና ከተገቢው የህጉ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ ከፍ ሲል እንደተገለጸዉ ይህ ጉዳይ በዉጭ አገር የተሰጠ ፍርድ የሚፈጸምበትን ሁኔታ የሚመለከት ነዉ፡፡ በፍ/ብ/ሥ/ሥርዓት ህጉ የተመለከተው የፍርድ አፈጻጸም ጉዳይ በሁለት ዓብይት ምዕራፎች የተመለከተ ሲሆን፣ በምዕራፍ 1 ላይ የተመለከተው በኢትዮጵያ ግዛት ውስጥ የተሰጠን ፍርድ በማስፈፀም ረገድ ተፈጻሚነት ያላቸው ድንጋጌዎች ሲሆን፣ በምዕራፍ 2 (ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 456 እስከ 461 የተጠቀሱት ድንጋጌዎች) ደግሞ በውጭ ሀገር የተሰጠ ፍርድ ወይም ብይን የሚፈፀምበትን ሁኔታ የሚመለከቱ ናቸው፡፡ በዉጭ አገር የተሰጠን ፍርድ በኢትዮጵያ ፍርድ ቤቶች ከማስፈጸም ጋር በተያያዘ መሠረቱ (principle) በህጉ አንቀጽ 456 ላይ የተመለከተ ሲሆን፣ በዚህ አንቀጽ ንዑስ ቁጥር 1 ላይ የተመለከተዉ ድንጋጌ “በኢንተርናሲዮናል ስምምነት በተለየ እንዲፈጸም የሚደረግ ልዩ ህግ ከሌለ በቀር ከኢትዮጵያ ዉጪ የተሰጠ የፍርድ ዉሳኔ ወይም ብይን የሚፈጸመዉ በዚህ ህግ በተመለከተዉ ድንጋጌ መሠረት ነዉ” በማለት የሚያስቀምጥ ሲሆን፣ የድንጋጌዉ የእንግሊዝኛ ትርጉምም “Unless otherwise expressly provided by international law conventions, foreign judgments may not be executed in Ethiopia except in accordance with the provisions of this chapter” በማለት ያስቀምጣል፡፡ የዉጭ አገር ፍርድ በኢትዮጵያ ፍርድ ቤቶች ሊፈጸሙ የሚችሉባቸዉ ሁኔታዎችም

በህጉ አንቀጽ 458 ላይ ተመልክተዋል፡፡ እነዚህም ሁኔታዎች እንዲፈጸም የተጠየቀዉን ፍርድ የወሰነዉ ፍርድ ቤት የሚገኝበት አገር በኢትዮጵያ የተሰጠዉን ፍርድም የሚያስፈጽም መሆኑ ሲረጋገጥ፤ ፍርዱ የተሰጠዉ በህግ በተቋቋመ ፍርድ ቤት መሆኑ ሲታወቅ፤ የፍርድ ባለዕዳዉ ቀርቦ መቃወሚያዉን ለማሰማት መብት የተሰጠዉ መሆኑ ሲረጋገጥ፤ ፍርዱ የመጨረሻና ተፈፃሚነት ያለዉ መሆኑ ሲታወቅ እና የፍርዱ መፈጸም ለህዝብ ሞራልና ጸጥታ ተቃራኒ ያለመሆኑ ሲታወቅ ስለመሆኑ በድንጋጌዉ ላይ ከተቀመጡት ድንጋጌዎች መረዳት ይቻላል፡፡

ከእነዚህ ሁሉ መገንዘብ የሚቻለዉ፣ በዉጭ አገር የተሰጠ ፍርድ በኢትዮጵያ ፍርድ ቤቶች ሊፈጸም የሚችለዉ በመርህ ደረጃ በኢትዮጵያ እና ፍርዱን በሰጠዉ ፍርድ ቤት አገር መካከል ይህን አስመልክቶ የተደረገ ስምምነት (bilateral agreement) መኖሩ ሲረጋገጥ ሲሆን፣ በልዩ ሁኔታ በህጉ አንቀጽ 458 ስር የተመለከቱት ቅድመ ሁኔታዎች ተሟልተዉ ሲገኙ ነዉ፡፡ በመሆኑም በህጉ አንቀጽ 458 የተመለከቱት ቅድመ ሁኔታዎች መሟላታቸዉ ከተረጋገጠ ምንም እንኳ የዉጭ አገር ፍርድ የሚፈጸምበትን ሁኔታ በተመለከተ የተደረገ የሁለትዮሽ ስምምነት ባይኖርም፣ የኢትዮጵያ ፍርድ ቤቶች ፍርዱን ተቀብለዉ ማስፈጸም የሚችሉ መሆኑን ነዉ፡፡  ስለሆነም በዉጭ አገር የተሰጠን ፍርድ እንዲያስፈጽም ዳኝነት የቀረበለት የኢትዮጵያ ፍርድ ቤት በቅድሚያ እንዲያጣራ የሚጠበቅበት ለአፈፃፀም የቀረበዉን ፍርድ በሰጠዉ ፍርድ ቤት አገር እና በኢትዮጵያ መካከል የፍርድ አፈፃፀምን አስመልክቶ የተደረገ የሁለትዮሽ ስምምነት መኖር አለመኖሩን፣ ስምምነት የሌለ መሆኑ ከተረጋገጠ በህጉ አንቀጽ 458 ላይ የተመለከቱት ቅድመ ሁኔታዎች የተሟሉ መሆን አለመሆኑን ነዉ፡፡

ወደ ተያዘዉ ጉዳይ ስንመለስ፣ ከፍ ሲል እንደተገለጸዉ፣ የስር ከፍተኛ ፍርድ ቤት በአመልካች የቀረበዉን የአፈፃፀም ጥያቄ ዉድቅ ያደረገዉ፣ ከፍርድ አፈፃፀም ጋር በተያያዘ በኢትዮጵያ እና በአሜሪካን ሀገር መካከል የተደረገ የሁለትዮሽ ስምምነት አለመኖሩንና በኢትዮጵያ የተሰጡ ፍርዶች በአሜሪካ የማይፈጸሙ ስለመሆኑ የኢፌዲሪ የዉጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ከጻፈለት ደብዳቤ ማረጋገጡን ነዉ፡፡ ይሁንና ከላይ እንደተገለጸዉ የሁለትዮሽ ስምምነት መኖር ብቸኛዉ ቅድመ ሁኔታ አይደለም፡፡ በመሆኑም የአሜሪካን አገር ፍርድ ቤቶች በኢትዮጵያ የተሰጡትን ፍርዶች የሚፈጽሙ መሆን ያለመሆኑን ጨምሮ ሌሎች በህጉ አንቀጽ 458 ላይ የተጠቀሱት ቅድመ ሁኔታዎች በተጨባጭ ማስረጃ ሊረጋገጡ የሚገባቸዉ ናቸዉ፡፡ የአሜሪካን አገር ፍርድ ቤቶች በኢትዮጵያ የሚሰጡትን ፍርድ የሚፈጽሙ መሆን ያለመሆኑና ሌሎች በህጉ የተመለከቱት ሁኔታዎች ፍርድ ቤቱ የአፈፃፀም አቤቱታዉን ተቀብሎ ለማስተናገድ ስልጣን ያለዉ መሆን ያለመሆኑን በመወሰን ረገድ ሊረጋገጡ የሚገቡ መሠረታዊ የፍሬ ነገር ጭብጦች በመሆናቸዉ እና ፍሬ ነገሩን ለማስረዳት ሊቀርብ የሚገባዉ የማስረጃ ዓይነት በህግ ተለይቶ የተወሰነ እስካልሆነ ድረስ፣ ፍርድ ቤቱ ማናቸዉንም ማስረጃ በማስቀረብ እና በመመርመር እነዚህን ፍሬ ነገሮች የማረጋገጥ ኃላፊነት ይኖርበታል፡፡ ይህ በመሆኑም የስር ከፍተኛ ፍርድ ቤት እነዚህን ፍሬ ነገሮች በዚህ መልኩ አጣርቶ መወሰን ሲገባዉ፣ ከኢፌዲሪ የዉጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የቀረበዉን ደብዳቤ ብቻ መሠረት

በማድረግ የሰጠዉ ትዕዛዝ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ስለሆነም ተከታዩ ዉሳኔ ተሰጥቷል፡፡

ዉ ሳ ኔ

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 193868 በቀን 14/06/2010 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት እንዲሁም የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 156444 በቀን 30/08/2010 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት የሰጡት ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥርዓት ህጉ አንቀጽ 348(1) መሠረት ተሽረዋል፡፡

2. የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ተዘግቶ የነበረዉን መዝገብ በማንቀሳቀስ፣ የአሜሪካን አገር ፍርድ ቤቶች በኢትዮጵያ የተሰጠዉን ፍርድ የማስፈጸም ልምድ ያላቸዉ መሆን ያለመሆኑን ሌሎች በህጉ አንቀጽ 458 ላይ የተመለከቱትን ሁኔታዎች አመልካች በሚያቀርቡትና ስለጉዳዩ ማስረዳት የሚችል ማንኛዉንም ማስረጃ በማስቀረብ እና በመመርመር ተገቢ ነዉ የሚለዉን ዉሳኔ እንዲሰጥ መዝገቡ በፍ/ብ/ሥ/ሥርዓት ህጉ አንቀጽ 343(1) መሠረት ተመልሶለታል፡፡

3. በዚህ ችሎት የተደረገዉ ክርክር ያስከተለዉን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኝ የየራሳቸዉን ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ብ/ግ

# ቤተሰብ

የሰ/መ/ቁ. 173628

ግንቦት 28 ቀን 2011 ዓ.ም

ዳኞች፡- ሰለሞን አረዳ

አልማው ወሌ

ሙስጠፋ አህመድ

አብርሃ መሰለ

ፈይሳ ወርቁ

**አመልካች፡-** 1. አቶ ወ/ጨርቆስ በጋሻው ቀረቡ፡፡

2. ወ/ሮ ቅድስት በለጠ

3. ወ/ሮ ዘውዲቱ በቀለ - ወኪል አያሌው ዋልቴ ቀረቡ፡፡

**ተጠሪ፡-** በየካ ክ/ከተማ አስተዳደር የወረዳ 13 የወሳኝ ኩነት ምዝገባ ፅ/ቤት - ታልፏል፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ በፍርድ ቤት በፀደቀው የጉዲፈቻ ውል መሰረት የጉዲፈቻ ልጆች ወላጆች ስም ሳይቀር ውሉ ተመዝግቦ ሰርቲፊኬት ይሰጠኝ ጥያቄ ጋር ተያይዞ የተነሳውን ክርክር የሚመለከት ጉዳይ ነው፡፡

ክርክሩ የተጀመረው በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ሲሆን በዚሁ ፍርድ ቤት ክርክሩ የጀመረውም የአሁኑ አመልካቾች ሲሆኑ በአሁኑ ተጠሪ ላይ በ11/12/2010 ዓ/ም በመሰረቱት ክስ የአሁኑ አመልካቾች በ12/12/2009 ዓ/ም ባደረጉት የጉዲፈቻ ውል ስምምነት የአሁኑ 1ኛ እና 2ኛ አመልካቾች ከአብራካቸው ያፈሯቸውን ተማሪ ብሌን ወ/ጨርቆስ፣ ተማሪ ቢታንያ ወ/ጨርቆስ፣ ተማሪ ማህሌት ወ/ጨርቆስ እና ተማሪ ኑህሚን ወ/ጨርቆስ የተባሉ ልጆቻቸውን ለአሁኗ 3ኛ አመልካች እንደ ልጆቻቸው አድርገው እንዲያሳድጉ በተወካያቸው በአቶ አያሌው ዋልቴ አማካኝነት በጉዲፈቻ መስጠታቸውንና ይህ ውል በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 206723 በ30/09/2010 ዓ/ም በተሰጠ ውሳኔ መጽደቁን፣ ይህንኑ መሰረት በማድረግም ጉዲፈቻ የተደረጉት ልጆች የወላጅ አባታቸውና እናታቸው ስም ሳይለወጥ የጉዲፈቻ ውሉን መዝግቦ የጉዲፈቻ የምስክር ወረቀት እንዲሰጥ የአሁኑን አመልካች ሲጠይቁ የጉዲፈቻ ተቀባይ በወካያቸው አማካኝነት የጉዲፈቻ ሰርቲፊኬት ሊቀበሉ እንደማይችሉ፣ የጉዲፈቻ ተደራጊዎች የአባት ስም ሳይቀር የጉዲፈቻ ሰርቲፊኬት እንደማይሰጥ በቁጥር የካ/ክ/ክ/1013/ወ/ኩ/260/10 በ12/11/2010 በተፃፈ ደብዳቤ የገለፃላቸውና ይህ የተጠሪ አድራጉትት ምንም የህግ መሰረት የሌለው መሆኑን ዘርዝረው የተጠሪ ክልከላ የሕግ መሰረት የሌለው መሆኑ ተረጋግጦ ያለምንም ቅድመ ሁኔታ የጉዲፈቻ ተደራጊ ልጆቹን የአባትና የእናት ስም ሳይቀይሩ የጉዲፈቻ ውሉን በመመዝገብ ሰርተፍኬቱን እንዲሰጡና ሰርተፍኬቱ ላይ የዘገዬ የሚል ሳይፃፍ እንዲሰጥ ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ ክሱ የቀረበለት ፍርድ ቤትም የአሁኑን ተጠሪ ከመጥራቱ በፊት ውሉ በፍርድ ቤት የፀደቀ መሆኑ መረጋገጡን ጠቅሶና

ከጉዲፈቻ ጋር የተያያዙ ጉዳዮች ራሱን በቻለ ልዩ ችሎት የሚታዩ በመሆኑ ለዚሁ ችሎት ማቅረብ ወይም በውሳኔው መሰረት ይፈፀም የሚባል ከሆነም ውሳኔውን ለሰጠው ችሎት ወይም ለአፈፃጸም ችሎት ከሚቀርብ በስተቀር በዚህ ችሎት የሚታይ አይደለም በማለት የአመልካቾችን ክስ ውድቅ አድርጎታል፡፡ በዚህ ትዕዛዝ የአሁኑ አመልካቾች ቅር በመሰኘት ይግባኛቸውን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርበውም ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በኋላ ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን መርምሮ የአሁኑ ተጠሪ በጉዲፈቻ አድራጊ ተወካይ በኩል የቀረበውን የሰርተፊኬት ይሰጠኝ ጥያቄ አልፈፅምም ማለቱ በጉዳዩ ላይ ቀድሞ ፍርድ በተሰጠበት ጊዜ በወኪል በኩል የተደረገ የጉዲፈቻ ውል መሆኑንና በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2199 ስር የተመለከተውን እንዲሁም በወሳኝ ኩነቶች አዋጅ በዚህ ረገድ ክልከላ ያለመደረጉን መሰረት ያላገናዘበ ነው በሚል ምክንያት ተገቢነት እንደሌለው ገልጾ በዚህ በኩል የቀረበውን የተጠሪን ክርክር ውድቅ ያደረገው ቢሆንም የጉዲፈቻ ተደራጊ ህፃናት የአባትና አያት ስም ግን በጉዲፈቻ አድራጊ የአባት እና አያት ስም ሳይቀየር ሰርተፍኬቱ አይሰጥም መባሉ በአዋጅ ቁጥር 760/2004( በአዋጅ ቁጥር 1049/2009 እንደተሻሻለ) በአንቀፅ 70(2) መሰረት በወጣው መመሪያ ቁጥር 7/2010 አንቀጽ 30 ክፍል 4 ንዑስ ክፍል 3 አንቀፅ 43 ድንጋጌ ተገቢ ነው በማለት ወስኗል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ የአመልካቾች የሰበር አቤቱታ  መሰረታዊ ይዘትም፡- ተጠሪ የጉዲፈቻ ተደራጊ ህጻናት አባትና አያት ስም በጉዲፈቻ አድራጊዋ አባትና አያት ስም ሳይቀየር የጉዲፈቻ ሰርተፊኬት አልሰጥም በማለት የፈጸመው ክልከላ በሕጉ መሰረት ነው ተብሎ መወሰኑ ጉዳዩ ቀድሞ በፍርድ ቤት የፀደቀ መሆኑን፣ መመሪያው ሌሎች ሕጎችን መሻር የማይገባው መሆኑን ጭምር ያላገናዘበ ነው በማለት መከራከራቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ አቤቱታቸው ተመርምሮም በዚህ ችሎት እንዲታይ የተደረገ ሲሆን ተጠሪ መጥሪያ ደርሶት ባለመቅረቡ በፅሑፍ መልስ የመስጠት መብቱ ታልፏል፡፡ እንዲሁም የስር ፍርድ ቤት ቁጥሩ 139051 የሆነ መዝገብ፣ የፌዴራል  ከፍተኛ ፍርድ ቤት ደግሞ ቁጥሩ 217446 የሆነ መዝገብ እንዲመጣ ተደርጓል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የአመልካቾችን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩን ለዚህ ችሎት ሲቀርብ ከተያዘው መሰረታዊ ጭብጥ አንጻር እንዲሚከተለው ተመልክተናል፡፡ ጉዳዩ ለዚህ ችሎት ሲቀርብ የተያዘው ጭብጥ አመልካቾች የጉዲፈቻ ውሉን አስመልክቶ ፍርድ ቤት በሰጠው ውሳኔ መሰረት ተጠሪ ሰርቲፊኬት እንዲሰጣቸው ያቀረቡት ጥያቄ በተጠሪ ተቀባይነት በማጣቱ ይግባኝ የቀረበለት ፍርድ ቤት አፈጻጸሙ በአዋጅ ቁጥር 760/2004 መሰረት በወጣው መመሪያ ቁጥር 7/2010 አንጻር ነው ማለቱ ቀድም ብሎ ፍርድ ቤቱ በመ/ቁጥር 206723 በሰጠው ውሳኔ ላይ ተፅእኖ አለው? ወይስ የለውም? የሚል ነው፡፡

በመሰረቱ አዋጅ ቁጥር 760/2004 የወጣበትን መሰረታዊ አላማ በአዋጁ መግቢያ ላይ የተጠቀሰ ሲሆን ይኼው አዋጅ በአዋጅ ቁጥር 1049/2009 ተሻሽሎ ይገኛል፡፡ በማሻሻያ አዋጁ በአንቀፅ 70(2) ስር አግባብ ያለው የፌዴራል አካል አዋጁንና በአዋጁ መሰረት የወጣውን ደንብ ለማስፈፀም የሚያስፈልጉ መመሪያዎችን ሊያወጣ እንደሚችል ደንግጓል፡፡ በአዋጁ አንቀፅ 2(7) ስር ደግሞ አግባብ ያለው አካል

ማለት ደግሞ በአዋጁ አንቀፅ መሰረት የተቋቋመ ወይም የተሰየመ የክልል አካል መሆኑ፣ በአንቀፅ 5 ስር ደግሞ የወሳኝ ኩነት ምዝገባን ተግባራትን በክልል ደረጃ የሚመራ፣ የሚያስተዳድርና የሚደግፍ እንዲሁም የምዝገባ መረጃዎችን አግባብ ባለው የፌደራል አካል የሚያስተላልፍ አካል መሆኑን በእያንዳንዱ ክልል የሚቋቋም ወይም የሚሰየም መሆኑን የሚገልጽ ሲሆን በአዋጁ አንቀፅ 2(11) ክልል ማለት የአዲስ አበባን አስተዳደር እንደሚጨምር ተደንግጓል፡፡

በዚህም መሰረት የአሁኑ ተጠሪ በአዲስ አበባ አስተዳደር ስር የወሳኝ ኩነት ምዝገባን ተግባራትን ለመምራት፣ ለማስተዳደርና ለመደገፍ እንዲሁም የምዝገባ መረጃዎችን አግባብ ባለው የፌደራል አካል ለማስተላለፍ የተሰየመ አካል መሆኑ ግልፅ ሲሆን ይህ አካል አዋጅ ቁጥር 760/2004 በአዋጅ ቁጥር 1049/2009 እንደተሻሻለ ለማስፈጸም ወይም አዋጁን ተከትሎ የወጣውን ደንብ ለማስፈፀም የሚያስችል መመሪያ ማውጣት የሚችል መሆኑን ሕግ አውጪው ስልጣን ሰጥቷል፡፡ በዚህ መሰረት ከወጡት መመሪያዎቸ መካከል ደግሞ መመሪያ ቁጥር 7/2010 አንዱ ሲሆን ይህ መመሪያ በክፍል 4 ንዑስ ክፍል አንቀፅ 43 ንዑስ ቁጥር 3 ስር የጉዲፈቻ አድራጊዋ ሴት ከሆነች የጉዲፈቻ ልጅ ስም ከጉዲፈቻ ውል ላይ የተፃፈው ስም፣ የአባት ስም የጉዲፈቻ አድራጊዋ አባት ስም እና የጉዲፈቻ አድራጊዋ አያት ስም እንደሚመዘገብ ደንግጓል፡፡ በፍርድ ቤት የፀደቀውን የጉዲፈቻ ውል በሚመለከት ደግሞ በንዑስ ክፍል አራት አንቀጾ 50፣51፣ 52፣53 እና 54 ስር የዘረዘረ ሲሆን በእነዚህ ድንጋጌዎች የጉዲፈቻ ተደራጊ ልጆች የአባት ስምና የአያት ስም በፍርድ ቤት ከጸደቀው የጉዲፈቻ ስምምነት ግልባጭ ታይቶ የሚመዘገብ መሆኑን የሚያሳይ ግልጽ ድንጋጌ የለም፡፡ በመሆኑም በፍርድ ቤት የጸደቀ የጉዲፈቻ ውል ስምምነት በተጠሪ ተመዝግቦ የጉዲፈቻ ሰርቲፊኬት ሊሰጥ የሚገባው በአዋጅ ቁጥር 760/2004 አንቀፅ 70(2) ድንጋጌ አግባብ በተጠሪ በወጣው መመሪያ ቁጥር 7/2010 ክፍል አራት ንዑስ ክፍል ሶስት አንቀፅ 43(3) ድንጋጌ መሰረት እንጂ የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 206723 የጉዲፈቻ ውሉ ስምምነት ሲያጸድቅ በውሉ ላይ ስለሕጻናቱ አባትና አያት ስም በሰፈረው አግባብ ሊሆን የሚችልበት ምክንያት የለም፡፡ ተጠሪ መመሪያውን ጠቅሶ የአመልካቾችን ጥያቄ ለማስተናገድ የማይችል መሆኑን ማሳወቁም በፍርድ ቤት የተሰጠን ውሳኔ ካለመፈፀም ጋር የሚያገናኘው ምክንያት የሌለ መሆኑን ተገንዝበናል፡፡ ምክንያቱም ፍርድ ቤቱ በአመልካቾች መካከል የተደረገው የጉዲፈቻ ውል ሕጋዊ መሆን ያለመሆኑን በመመርመር የስምምነት ሰነዱን ከማረጋገጥ(AUTHENTICATE) ውጪ በአዋጅ ቁጥር 760/2004 ድንጋጌዎች እና በመመሪያ ቁጥር 7/2010 አግባብ ስለጉዲፈቻ ውል ሰርቲፊኬት አሰጣጥ በጭብጥነት ይዞ የሰጠው ዳኝነት የለም፡፡ በመሆኑም የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 206723 የሠጠው ውሳኔ የጉዲፈቻ ውል ስምምነት መኖሩን የሚያሳይ በመሆኑና ይህ ሰነድ ደግሞ ውሉ መኖሩን የሚያሳይ ማስረጃ እንደመሆኑ መጠን በዚሁ ውል መሰረት ስልጣን ያለው አካል የጉዲፈቻ ውል ሰርቲፊኬት ሲሰጥ በመመሪያው መሰረተ መሟላት ያለባቸው ቅድመ ሁኔታዎች እንዲሟሉ ማድረጉ በሕጉ የተሰጠውን ኃላፊነትና ተግባር መወጣቱን ከሚያሳይ በቀር ለሕግና ለፍርድ ቤት ውሳኔ ተቃራኒ የሆነ ተግባር ፈፅሟል ሊባል የሚችልበት አግባብ የለም፡፡ መመሪያው ከ1952ቱ የፍትሃ ብሔር ሕጋችን በኃላ በወጣው በአዋጅ ቁጥር 760/2004 አንቀፅ 70(2) መሰረት የወጣ

ከመሆኑም በላይ በፍትሃብሔር ሕጉ 41 ስር የተመለከተውን ድንጋጌን ሊቃረን የሚችል ነው ተብሎ የሚደመደምበትን አግባብ ስላለገኘን አመልካቾች ከሕግ ደረጃና አፈጻጸም አንጻር ያነሱትን ክርክርም ለመቀበል የሚቻል ሁኖ አልተገኘም፡፡

አመልካቾች ጉዲፈቻ ተደራጊ ህፃናት የሚወሰዱት ወደ አሜሪካን አገር መሆኑን ጠቅሰው ከህፃናቱ መብትና ጥቅም አንጻር ያቀረቡት ክርክር ሲታይም በመሰረቱ ጉዲፈቻ ውል እንዲደረግና የሕግ ጥበቃ እንዲደረግለት ያስፈልገው በዋናነት የሕፃኑን ጥቅም ለመጠበቅ ሲባል እንደሆነ፣ የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገ-መንግስትም ሆነ ኢትዮጵያ ያፀደቀቻቸው አለም ዓቀፍ ስምምነቶች ህፃናትን የሚመለከቱ ጉዳዮች ለሕፃናት ጥቅም ደህንነት (best interest of the child) ቅድሚያ መስጠት አስፈላጊ መሆኑ በመርህ ደረጃ ማስቀመጣቸውን፣ በሕገ-መንግስቱ አንቀጽ 36/5/ ስር መንግስት ለእጓለማውታን ልዩ ጥበቃ እንደሚያደርግላቸው፣በጉዲፈቻ የሚያድጉበትን ስርአት የሚያመቻቹና የሚያስፋፉ እንዲሁም ደህንነታቸውንና ትምህርታቸውን የሚያራምዱ ተቋማት እንዲመሰረቱ እንደሚያበረታታ መደንገጉን፣ከፍ ሲል የተመለከቱት ድንጋጌዎች ሁሉ የጉዲፈቻ ጉዳይ በጥንቃቄ መታየት ያለበት መሆኑንና በድንጋጌ አተረጓጐም ላይ ጥንቃቄ እንደሚያስፈልግ፣ በዚህም መሰረት የጉዲፈቻ ስምምነት ላይ የሚሰጠው ውሳኔ በልጁ አኗኗርና አያያዝ እንዲሁም ወደፊት ሕይወቱ ላይ በተጨባጭ ጉዳት እንዳይኖር ብቻ ሳይሆን ወደፊት ሊደርስ የሚችል ጉዳት እንደሌለም ማረጋገጥ ሲቻል እንደሆነ ይህ ችሎት በሰ/መ/ቁጥር 44101 ከሰጠው አስገዳጅ የሕግ ትርጉም ይዘት የምንረዳው ጉዳይ ነው፡፡ ተጠሪ ያወጣው መመሪያ ቁጥር 7/2010 ክፍል አራት ንዑስ ክፍል ሶስት አንቀፅ 43(3) ድንጋጌም ጉዲፈቻ ተደራጊ ህፃናት በሚሄዱበት አገር በተገቢው መንገድ ተገቢውን አገልግሎት እንዲያገኙ ያደረጋል ተብሎ ከሚታሰብ በስተቀር በሕጻናቱ አኗኗርና አያያዝ እንዲሁም ወደፊት ሕይወቱ ላይ በተጨባጭ ጉዳት የሚያስከትል፤ ወደፊትም ጉዳት ሊያደርስ የሚችል ነው ሊያሰኝ የሚችል ሁኔታ መኖሩን ለመገንዘብ የሚያስችል ምክንያት አላገኘንም፡፡ በመሆኑም በዚህ ረገድ የቀረበውን የአመልካቾችን ክርክርም አልተቀበልነውም፡፡

ሲጠቃለልም ከላይ በተዘረዘሩት ምክንያቶች ተከታዩን ወስነናል፡፡

## <u>ው ሳ ኔ</u>

1. የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 217446 በ26/06/2011 ዓ/ም የተሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ህ/ቁጥር 348 (1) መሰረት ፀንቷል፡፡
2. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡
   መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

አ/ኃ

የሰበር መዝገብ ቁጥር 172784

ሰኔ 24 ቀን 2011 ዓ.ም.

**ዳኞች፡-** አልማው ወሌ

ሙስጠፋ አህመድ

አብርሃ መሰለ

ፈይሳ ወርቁ

ጻውሎስ ኦርሺሶ

**አመልካች፡-**አቶ አቡበከር አህመድ መሐመድ - ተወካይ ወ/ሮ ሰዓዳ አብደላ - ቀረቡ፡፡

**ተጠሪ፡-**ወ/ሮ ሳራ ሱፍያን አብዱረህማን - ጠበቃ ሀኒፍ ይህደጎ - ቀረቡ፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ ከልጅ ቀለብ ጋር ተያይዞ የተነሳ ክርክርን የሚመለከት ሲሆን አመልካች የሰበር አቤቱታቸውን ለዚህ ችሎት ያቀረቡት ለአንድ ልጅ ቀለብ ከግንቦት ወር 2010 ዓ.ም. ጀምሮ በየወሩ ብር 10,000 /አስር ሺህ/ እንዲከፍሉ በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 85022 በ24/08/2010 ዓ.ም. ተሰጥቶ በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 219131 በ05/06/2011ዓ.ም. በፍርድ የጸናው ውሳኔ በከፊል መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት ነው፡፡

ተጠሪዋ በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በ14/05/2010 ዓ.ም. ባቀረቡት ክስ ፍቺ እንዲወሰን እና አመልካቹ በሶስት የንግድ ፈቃዶች በመሥራት በወር በአማካይ ብር 100,000/ አንድ መቶ ሺህ/ ገቢ የሚያገኙ መሆኑን ገልጸው በጋብቻው ለተወለደው የሶስት ወር ዕድሜ ላለው ልጃቸው በየወሩ ብር 20,000 /ሃያ ሺህ/ ቀለብ እንዲከፍሉ እንዲወሰን የጠየቁ ሲሆን አመልካቹ በበኩላቸው በ20/06/2010 ዓ.ም. በሰጡት መልስ የፍቺ ጥያቄውን የማይቃወሙ መሆኑን እና የወር ገቢያቸው ግን ተጠሪዋ እንደሚሉት ሳይሆን በወር ከብር 5,000 /አምስት ሺህ/ የማይበልጥ መሆኑን ገልጸው በተጠሪዋ የቀረበው የተጋነነ የልጅ ቀለብ ጥያቄ ውድቅ እንዲደረግ ተከራክረዋል፡፡ክሱ

የቀረበለት ፍርድ ቤትም በጊዜያዊነት የብር 4,000 /አራት ሺህ/ የልጅ ቀለብ ትዕዛዝ ከሰጠ በኋላ የአመልካቹ ገቢ ተጣርቶ እንዲቀርብ አድርጎ በሚመለከተው አካል የተገለጸውን የአመልካች ገቢ መጠን በአስረጂነት በመጥቀስ የፍቺ ውሳኔ በሰጠበት ቀን አመልካቹ ለአንድ ልጅ ቀለብ ከግንቦት ወር 2010 ዓ.ም. ጀምሮ በየወሩ ብር 10,000 /አስር ሺህ/ እንዲከፍሉ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡በይግባኝ ሰሚው ፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በፍርድ የጸናው ይኸው ውሳኔ ሲሆን አመልካቹ ለዚህ ችሎት ያቀረቡት የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ የስር ፍርድ ቤት ለቀለብ አወሳሰኑ መሠረት ያደረገው ከገቢዎች አስተዳደር ጽ/ቤት የተላከው ማስረጃ የአመልካቹን ጠቅላላ ገቢ እንጂ ልዩ ልዩ ተቀናሽ ወጪዎችን ያላገናዘበ ከመሆኑ አንጻር የቀለብ አወሳሰኑን አግባብነት ተጠሪዋ ባሉበት ለማጣራት ይቻል ዘንድ ጉዳዩ ለሰበር ክርክር እንዲቀርብ በመደረጉ ግራ ቀኙ የጽሁፍ ክርክር ተለዋውጠዋል፡፡የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም ክርክሩ የተስተናገደበትን የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት መዝገብ በማስቀረብ ጭምር አቤቱታ የቀረበበት ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት መሆን አለመሆኑን ለጉዳዩ ከተያዘው ነጥብ አንጻር መርምረናል፡፡

በዚህም መሰረት የልጅ ቀለብ አወሳሰን ጥንቃቄ የሚያስፈልገውና የሕፃናትን ደህንነትና ጥቅም የሚያረጋግጥ መሆን እንደሚገባው የሚታወቅ ሲሆን የሕፃናትን ጉዳይ በሚመለከት የሚወሰዱ እርምጃዎች እና የሚሰጡ ውሣኔዎች በሙሉ የሕፃናትን ጥቅም ተቀዳሚ ያደረጉ መሆን ያለባቸው ስለመሆኑ የኢ.ፌ.ዲ.ሪ. ህገ መንግስት በአንቀጽ 36(2) ስር ይደነግጋል፡፡በሕጻናት መብት አጠባበቅ እና አወሳሰን ረገድ አገሪቱ ያፀደቀቻቸው የአገሪቱ የሕግ አካል የሆኑ ዓለም አቀፍ ስምምነቶችም ከግምት መግባት እንደሚገባቸው የሚያጠያይቅ አይደለም፡፡ፍርድ ቤት ጋብቻ እንዲፈርስ ሲወስን ውሳኔ ሊያሳርፍባቸው ከሚገቡ ቀዳሚ ጉዳዮች መካከል አንዱ የልጆች አስተዳደግ፣የትምህርት፣የጤና፣የቀለብ እና የአጠቃላይ አኗኗራቸው ጉዳይ ስለመሆኑ በአዋጅ ቁጥር 213/1992 በተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ በአንቀጽ 113 (1) ስር የተመለከተ ሲሆን በቀለብ አወሳሰን ረገድም ውሳኔው በሚሰጥበት ጊዜ የነበረው የወላጆች የገቢ፣የዕድሜ፣የጤና እና የአኗኗር ሁኔታ፣እንዲሁም የልጆቹ ዕድሜ፣ጥቅማቸው እና ፍላጎታቸው ከግምት መግባት የሚገባቸው ስለመሆኑ በዚሁ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ (2) ስር ተመልክቷል፡፡ከዚህም በተጨማሪ ፍርድ ቤቱ በዚህ አንቀጽ መሰረት ስለልጆች አያያዝ እና አጠባበቅ የሚሰጠው ውሳኔ የሁኔታዎች መለዋወጥን ምክንያት በማድረግ በሚቀርብ ጥያቄ ሊሻሻል ወይም ሊለወጥ የሚችል ስለመሆኑም በዚሁ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ (3) ስር ተደንግጎ ይገኛል፡፡

በተያዘው ጉዳይ የአመልካቹን ወርኃዊ የገቢ መጠን በተመለከተ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ክርክር ያቀረቡ ሲሆን ጉዳዩ የቀረበለት የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትም በቀለብ አወሳሰኑ ረገድ ተገቢውን ውሳኔ መስጠት ያስችለው ዘንድ በደቡብ ወሎ ዞን የደሴ ከተማ ገቢዎች ጽ/ቤት የአመልካቹን የ2009 ዓ.ም. ዓመታዊ ገቢ አጣርቶ እንዲገልጽ በ14/07/2010 ዓ.ም. በሰጠው ትዕዛዝ

መሠረት አመልካቹ የሂሳብ መዝገብ ያቀረቡ መሆኑን እና ዓመታዊ ገቢያቸው ብር 1,817,379.04 /አንድ ሚሊዮን ስምንት መቶ አስራ ሰባት ሺህ ሶስት መቶ ሰባ ዘጠኝ ከዜሮ አራት ሳንቲም/ መሆኑን ገልጾ ጽ/ቤቱ በቁጥር አወ/አሰ/ክት/7213/2010 በ02/08/2010 ዓ.ም. በተጻፈ ደብዳቤ ምላሽ ሰጥቷል፡፡ፍርድ ቤቱ ከገቢዎች ጽ/ቤት በቀረበው ምላሽ ላይ የግራ ቀኙን የጽሁፍ አስተያየት ከተቀበለ በኋላ የቀለብ ውሳኔ የሰጠው በጽ/ቤቱ የተገለጸውን ዓመታዊ ገቢ ወደ ወርኃዊ ገቢ በመለወጥ አመልካቹ ብር 151,448 /አንድ መቶ ሃምሳ አንድ ሺህ አራት መቶ አርባ ስምንት/ ወርኃዊ ገቢ አላቸው በማለት መሆኑን ከዋናው መዝገብ ተመልክተናል፡፡ይሁን እንጂ በደቡብ ወሎ ዞን የደሴ ከተማ ገቢዎች ጽ/ቤት የአመልካቹን ዓመታዊ ገቢ ከመግለጹ በቀር ይህ ዓመታዊ ገቢ ተገቢ ተቀናሾች ሁሉ ታሳቢ ተደርገው ከግብር በኋላ የተገኘ የተጣራ ገቢ ስለመሆኑ ለይቶ ያልገለጸ መሆኑን ከስር መዝገብ ጋር ተያይዞ ከሚገኘው የደብዳቤው ይዘት እና ግራ ቀኙ በደብዳቤው ላይ በጽሁፍ ካቀረቡት አስተያየት ተገንዝበናል፡፡የተጣራ መሆኑ ያልተረጋገጠን የገቢ መጠን መሠረት በማድረግ የሚሰጥ የቀለብ ውሳኔ ደግሞ የከፋዩን ትክክለኛ የመክፈል አቅም ያገናዘበ ነው ለማለት የሚቻል አይደለም፡፡በመሆኑም የቀለብ መጠኑ እንደገና ተጣርቶ እንዲወሰን ጉዳዩ ለፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ሊመለስ የሚገባው መሆኑን ተገንዝበናል፡፡

በሌላ በኩል  የተጣራ ዓመታዊ ገቢያቸው ብር 154,235.43 /አንድ መቶ ሃምሳ አራት ሺህ ሁለት መቶ ሰላሳ አምስት ከአርባ ሶስት ሳምቲም/ መሆኑን እና  የተጣራ ወርኃዊ ገቢያቸው ደግሞ ብር 12,860.45 /አስራ ሁለት ሺህ ስምንት መቶ ስድሳ ከአርባ አምስት ሳምቲም/ መሆኑን አመልካች ለዚህ ችሎት ባቀረቡት የሰበር አቤቱታ ላይ የገለጹ መሆኑን መሠረት በማድረግ ይህ ውሳኔ እስከተሰጠበት ጊዜ ድረስ የሚከፍሉት በስር ፍርድ ቤት በተወሰነባቸው መጠን መሠረት መሆኑ እንደተጠቀበ ሆኖ  ትክክለኛው የቀለብ መጠን በስር ፍርድ ቤት ተጣርቶ እስኪወሰን ድረስ አመልካቹ ከሐምሌ ወር 2011 ዓ.ም. ጀምሮ የተጣራ ወርኃዊ ገቢዬ ነው በማለት የገለጹትን ገቢ አጋማሽ ብር 6,430.22 /ስድስት ሺህ አራት መቶ ሰላሳ ከሃያ ሁለት ሳንቲም/የልጅ ቀለብ እየከፈሉ እንዲቆዩ ማድረጉ ተገቢ መሆኑን ተገንዝበናል፡፡ ሲጠቃለል አቤቱታ የቀረበበት ውሳኔ በከፊል መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት እና ሊሻሻል የሚገባው ሆኖ በመገኘቱ የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. አመልካቹ ለአንድ ልጅ ቀለብ ከግንቦት ወር 2010 ዓ.ም. ጀምሮ በየወሩ ብር 10,000 /አስር ሺህ/ እንዲከፍሉ በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 85022 በ24/08/2010 ዓ.ም. ተሰጥቶ በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 219131

በ05/06/2011ዓ.ም. በፍርድ የጸናው ውሳኔ በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 348 (1) መሠረት ተሻሽሏል፡፡

2. አመልካች የሚከፍሉት ወርኃዊ የልጅ ቀለብ የገንዘብ መጠን ብር 10,000 /አስር ሺህ/ ነው በሚል የተሰጠው የውሳኔ ክፍል ተሽሯል፡፡
3. የአመልካቹን የተጣራ የገቢ መጠን አጣርቶ ተገቢ ነው የሚለውን የቀለብ ገንዘብ እንዲወስን ጉዳዩ በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 343 (1) መሠረት በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት እንዲመለስ ወስነናል፡፡
4. ይህ ውሳኔ እስከተሰጠበት ጊዜ ድረስ የሚከፍሉት በስር ፍርድ ቤት በተወሰነባቸው መጠን መሠረት መሆኑ እንደተጠቀበ ሆኖ ትክክለኛው የቀለብ መጠን በስር ፍርድ ቤት ተጣርቶ እስኪወሰን ድረስ አመልካቹ ከሐምሌ ወር 2011 ዓ.ም. ጀምሮ የተጣራ ወርኃዊ ገቢዬ ነው በማለት የገለጹትን ገቢ አጋማሽ ብር 6,430.22 /ስድስት ሺህ አራት መቶ ሰላሳ ከሃያ ሁለት ሳንቲም/ የልጅ ቀለብ እየከፈሉ እንዲቆዩ ወስነናል፡፡
5. በቀሪ ጉዳዮች ረገድ የተሰጠው የውሳኔ ክፍል አልተነካም፡፡
6. የውሳኔው ቅጂ ተገቢውን መፈጸም ያስችለው ዘንድ ለፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት፣እንዲያውቀው ደግሞ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይላክ፡፡
7. የሰበር ክርክሩ ያስከተለውን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡
8. ውሳኔ ያገኘ ስለሆነ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ፅ/ወ

የሰ/መ/ቁ.153405

ግንቦት 13 ቀን 2011 ዓ/ም

ዳኞች ፡- አልማው ወሌ

ሙስጠፋ አህመድ

አብርሃ መሰለ

ፈይሳ ወርቁ

ጳውሎስ ኦርሺሶ

አመልካች ፡- ወ/ሮ ፅጌ በንቲ - የቀረበ የለም፡፡

ተጠሪ ፡- አቶ ተስፋዬ ታደሰ - ጠበቃ አቶ ይልማ በየነ ቀረቡ ፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ ቀጥሎ ያለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

የነገሩ አመጣጥ የፍቺ ውጤትን የሚመለከት ነው ፡፡ ጉዳዩ የጀመረው በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት አራዳ ምድብ ችሎት ነው ፡፡ የአሁን አመልካች ታህሳስ 5 ቀን 2005 ዓ/ም ያቀረቡት የክስ አቤቱታ ከተጠሪ ጋር የነበራቸው ጋብቻ ህዳር 19 ቀን 2005 ዓ/ም በተሰጠ ውሳኔ መፍረሱን ፣ ከተጠሪ ጋር በጋብቻ በነበሩ ጊዜ ያፈሩት የጋራ ንብረት የሆነው በየካ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 13/14 ብሩህ ተስፋ ቁጥር 1 በሚባለው ሳይት ላይ የህንፃ ቁጥር B6/10 የኮንደሚኒየም ቤት ከየካ ክፍል ከተማ የቤቶች ማስተላለፍ ጽ/ቤት ጋር ህዳር 20 ቀን 2000 ዓ/ም በተደረገው የሽያጭ ውል መግዛታቸውን፣የቤቱ ካርታ በተጠሪ ስም የተሰጠውም በየካቲት 10 ቀን 2002 ዓ/ም መሆኑን ገልጸው በተጠሪ ስም የተመዘገበ ቢሆንም በጋብቻ ውስጥ የተፈራ በመሆኑ የጋራ ንብረት ነው ተብሎ እንዲወሰንልኝ በማለት ዳኝነት ጠይቋል የአሁን ተጠሪም መጋቢት 23 ቀን 2005 ዓ/ም ጽፈው ባቀረቡት መልስ የኮንደሚኒየሙን ቤት የተመዘገቡት ፣ እጣው የወጣው አጠቃላይ ክፍያውን አጠናቀው የከፈሉት አመልካችና ተጠሪ ጋብቻቸውን ከመፈጸማቸው በፊት መሆኑን አመልካችና ተጠሪ ጋብቻ የፈጸሙት በህዳር 19 ቀን 2000 ዓ/ም ከቀኑ 8፡15 ሰዓት እንደሆነ ፣ ለኮንደሚኒየም ክፍያ የተከፈለው ግን ጠዋት መሆኑን ፣ ለዚህም አመልካች በቤቱ ባለቤትነት ሳይሆን በምስክርነት የፈረሙ መሆኑን ገልጸው የአመልካች ጥያቄ ውድቅ ይደረግ በማለት ተከራክሯል ፡፡

ጉዳዩን የተመለከተው የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት አራዳ ምድብ ችሎት የግራ ቀኙን ክርክርና የቀረቡትን የሰነድ ማስረጃዎችን ከመረመረ በኃላ የቤቱ እጣ የወጣው ጋብቻ ከመፈጸሙ በፊት ሲሆን የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰበር መዝገብ ቁጥር 51893 ፣ 46606 እና 75562 በሰጣቸው ውሳኔዎች መሰረት ለኮንደሚኒየም ባለቤትነት ዋናው ጉዳይ እጣ መውጣቱ ነው ። ስለዚህ ቤቱ የአሁን ተጠሪ የግል ሀብት ነው ሲል ወስኗል ። አመልካች ይህን ውሳኔ በመቃወም ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ አቅርቧል ። ይግባኙ የቀረበለት የከፍተኛ ፍርድ ቤቱም ይግባኙን ተቀብሎ የግራ ቀኙን ክርክር ካዳመጠ በኂላ የስር ፍርድ ቤትን ውሳኔ አጽንቶታል ።

ይህ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ውሳኔውን ለማስቀየር ሲሆን አመልካች በጠበቃቸው በኩል ጥር 30 ቀን 2010 ዓ/ም የተጻፈ ቅሬታ ያቀረቡ ሲሆን ይዘቱም በአጭሩ በአመልካችና  በተጠሪ መካከል ጋብቻ የተፈጸመው ህዳር 19 ቀን 2000  ዓ/ም ሲሆን የኮንደሚኒየም ቤቱን አስመልክቶ ተጠሪ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የየካ ክፍለ ከተማ የቤቶች ማስተላለፍ ጽ/ቤት ጋር የሽያጭ ውል የተፈራረመው ህዳር 20 ቀን 2000 ዓ/ም በጋብቻ ውስጥ ነው ። የቤቱ ሽያጭ ዋጋ ብር  29,087.10 /ሀያ ዘጠኝ ሺህ ሰማኒያ ሰባት ብር ከአስር ሳንቲም/ የተከፈለው በጋብቻ ውስጥ ነው ። ይህ ገንዘብ የተከፈለውም አመልካች በተበዳሪነት በፈረሙት የብድር ውል መሰረት ህዳር 19 ቀን 2000 ዓ/ም አመልካች እና ተጠሪ ሆነን ከወ/ሮ ትዕግስት ሐዋዝ በብድር ካገኘነው ብር 200,000 /ሁለት መቶ ሺህ ብር/ ላይ ወጪ ተደርጎ ነው። የስር ፍርድ ቤቶች ቤቱ የጋራ አይደለም በማለት የወሰኑት የቤቱ ቅድመ ክፍያ የተፈጸመውና የሽያጭ ውሉ የተደረገው በጋብቻ ውስጥ ቢሆንም የኮንዶሚኒየም እጣው ለተጠሪ የደረሰው ከጋብቻ በፊት ነው በሚል ምክንያት ነው። እጣ መውጣት ለብቻው የቤት ባለቤት አያደርግም የቤት ባለቤትነት የሚገኘው በነፃ ሳይሆን በግዢ በመሆኑ እጣው የደረሰው ሰው ከሚመለከተው መንግስት አካል ጋር የሽያጭ ውል ተዋውሎ የሽያጩን ገንዘብ ካልከፈለ እድሉ ከሚያመልጠው በቀር እጣው ብቻ ባለሀብት ሊያደርገው አይችልም ። በመሆኑም የቤቱ ባለቤት ለመሆኑም የቤቱ ባለቤት ለመሆን ዋናው ጉዳይ የሽያጭ ውሉን ማድረግና ክፍያውን መፈጸም ነው። አሁን በተያዘው ጉዳይም የሽያጭ ውሉ የተፈረመውና ክፍያ የተፈጸመው በጋብቻ ውስጥ በመሆኑ ቤቱ የጋራ ንብረት ነው። በመሆኑም የስር ፍርድ ቤቶች ቤቱ የጋራ አይደለም ብለው መወሰናቸው ስህተት ነው። የኮንዶሚኒየም ቤቱን ከመንግስት ከተረከብን በኂላ በጋብቻው ውስጥ የልስን ስራ ተሰርቷል ፣ ቻክ ተደርጎ ቀለም ተቀብቷል ለመኝታ ቤት እና ለሻዎ ቤት ሁለት በሮች ተገጥመዋል ፣ ሻዎ ቤት እና ሽንት ቤት ሙሉ እቃ ተሟልቶበት በሴራሚክ ተሰርቷል ፣ ለማዕድ ቤቱ ኪችን ካቢኔት ተስርቷል ፣ ሌሎች የማጠናቀቂያ ስራዎች ተሰርተዋል። ይህን የማጠናቀቂያ ስራ ለመስራትም ብር 80,200 /ሰማኒያ ሺህ ሁለት መቶ ብር/ ወጪ ተደርጓል። ይህን ስራ ለመስራት ከባለሙያ ጋር የተደረገው ውል በማስረጃነት ለስር ፍርድ ቀርቧል። የቤቱ ወጪ የተሸፈነው አመልካችና ተጠሪ በጋራ በተበደርነው ብር 200,000 /ሁለት መቶ ሺህ ብር/ መሆኑን ክርክር እንዲሁም የጽሁፍ ማስረጃ አቅርቤ ምስክሮችን ዘርዝሬ እያለሁ የስር ፍርድ

ቤቶች ግን በተለይም የከፍተኛው ፍርድ ቤት አመልካች ለቤቱ መገኘት ያደረጉት አስተዋጽኦ የለም በማለት ቤቱ የጋራ አይደለም ማለታቸው መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነው የሚል ነው፡፡

የሰበር አቤቱታውን አጣሪው መርምሮ በዚህ ጉዳይ አመልካች የአካራካሪው የኮንደሚኒየም ውል የተፈረመው ፣ የቤት ሽያጭ ዋጋ የተከፈለውም በጋብቻ ውስጥ በጋራ በተፈረመ ብድር ነው በማለት ያቀረበችው ክርክር በስር ፍርድ ቤቶች የቤቱ እጣ የወጣው ከጋብቻ በፊት ነው በሚል ብቻ የሰበር መዝገብ ቁጥር 43988 ተጠቅሶ የመወሰኑን አግባብነት መጣራት ያለበት መሆኑ ስለታመነበት ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ይቅረብ ሲል ትዕዛዝ ሰጥቷል ፡፡

ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎላቸው በጠበቃቸው በኩል የካቲት 29 ቀን 2011 ዓ/ም የቀረበው የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ አቤቱታው ጊዜ ካለፈ በኋላ የቀረበ ነው የሚል ሲሆን አማራጭ መልስ ይዘትም በአጭሩ የኮንደሚኒየም እጣ ቅድመ ክፍያ እና የማጠቃለያ ክፍያ በሙሉ የተፈጸመው ከጋብቻ በፊት ከግል ገንዘቤ ሲሆን አመልካች በኮንደሚኒየም የቤት ሽያጭ ዋጋ የተከፈለው በጋራ በተፈረመ የብድር ውል በተገኘ ገንዘብ ነው በማለት ያቀረቡት ክርክር ከእውነታው ውጪ ከመሆኑም በላይ በሀሰት የቀረበ ክርክር ነው ፡፡ አመልካች የኮንደሚኒየም ቤት ሙሉ ክፍያ ከግል ገንዘቤ ከከፈልኩ በኋላ ያውም በማላዉቀዉ እና ባልፈረምኩት የብድር ዉል በተገኘ ገንዘብ ቤት ክፍያ እንደተፈጸመ ተደርጎ የቀረበዉ ክርክር ተቀባይነት የለዉም፡፡ የሰበር መዝገብ ቁጥር 43988 ዉሳኔ ከተያዘዉ ጉዳይ ጋር አግባብነት የለዉም፡፡ አመልካች በሽያጭ ዉል ላይ የፈረሙት የምስክርነት ነዉ የቤት እድሳትም የተከናወነዉ አመልካች እንደሚሉት በብድር ገንዘብ ሳይሆን ተጠሪ አሜሪካ ሀገር ከሄድኩ በኋላ በላኩት ገንዘብ ሲሆን የቤቱ ጠቅላላ ዋጋ ብር 29,087.10 /ሃያ ዘጠኝ ሺህ ሰማኒያ ሰባር ብር ከአስር ሳንቲም /ስለሆነ ብር/ 200,000 /ሁለት መቶ ሺህ ብር/ የምትበደርበት ምክንያት የሌለ ከመሆኑም በላይ እድሳቱም ቢሆን ለቤቱ ከተከፈለዉ ብር 29,087.10 በላይ ብር 80,000 ከቤቱ ዋጋ ከሶስት  እጥፍ በላይ ወጭ አድርጌበታለሁ በማለት ያቀረቡት አቤቱታ በሀሰት የቀረበ ከመሆኑም በላይ ሊታመን የማይችል በመሆኑ በዚህ በኩል የቀረበዉ አቤቱታ የህግ ክርክር ሳይሆን የፍሬ ነገር እና የማስረጃ በመሆኑ ለዚህ ሰበር ሊቀርብ አይገባም፡፡ ሲጠቃለልም የስር ፍ/ቤቶች ዉሳኔ በአግባቡ ስለሆነ ሊጸና ይገባል የሚል ነዉ፡፡ የአመልካች ጠበቃም ሚያዚያ 02 ቀን 2011 ዓ/ም የተጻፈ የመልስ መልስ አቅርቧል፡፡

የነገሩ አመጣጥ የክርክሩ ሂደት በአጭር ከላይ እንደተገለጸዉ ሲሆን ለክርክሩ ምክንያት የሆነዉ የኮንድሚንየም ቤት የተጠሪ የግል ንብረት ነዉ ተብሎ በተሰጠዉ ዉሳኔ ላይ መሰረታዊ ህግ ስህተት ተፈጽሞበታል ወይስ አልተፈጸመበትም የሚል ጭብጥ ተይዞ ጉዳዩ እንደሚከተለዉ ተመርምሯል፡፡ በቅድሚያ ግን በተጠሪ ጠበቃ ከሰበር አቤቱታ ጊዜ ማለፍ ጋር አያይዘዉ ያነሱትን መቃወሚያ በተመለከተ የአመልካች ጠበቃ በሰጡት የመልስ መልስ ጉዳዩ በሌላ መዝገብ በስር ክርክር ካለዉ ጉዳይ ጋር የተያያዘ በመሆኑ አመልካች በቀረቡ ጊዜ የማንቀሳቀስ መብት ተጠብቆ ተዘግቷል፡፡

በመሆኑም አመልካች በሌላ መዝገብ ያለዉ ክርክር ማለትም የፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የካ ምድብ ችሎት በኮ/መ/ቁ. 79982 የነበረዉ ክርክር ተጠናቆ በቀን 25/04/2011 ዓ/ም ዉሳኔ የተሰጠበት በመሆኑ ከዚህ መዝገብ ጋር ተያይዞ ቀድሞ በተሰጠዉ ትእዛዝ መሰረት ጉዳዩ ከቆመበት እንዲቀጥል ጥር 10 ቀን 2011 ዓ/ም አቤቱታ በመቅረቡ ነዉ በማለት ተከራክሯል፡፡ ከዚህ ጋር የተነሳዉ ክርክር ይህ ችሎትም እንደተመለከተዉ ለቤቱ ግዢ እና ተጠሪን ወደ አሜሪካን አገር ለመሸኘት ተወስዷል ተብሎ አመልካች ተጠሪ እንዲከፍሉ ተብሎ የቀረበ የብድር ገንዘብ ክስ ምክንያት ያደረገ ክርክር ቀደም ሲል እስከዚህ ሰበር ችሎት ድረስ ደርሶ በሰበር መዝገብ ቁጥር 117975 ሚያዚያ 25 ቀን 2009 ዓ/ም በሰጠዉ ዉሳኔ የሚጣሩ ነጥቦች ተለይተዉ በስር ፍ/ቤት ቤት ተመልሷል፡፡ ጉዳዩ የተመለሰለት የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የካ ምድብ ችሎት ጉዳዩን አጣርቶ በኮ/መ/ቁ. 79982 በቀን 25/04/2011 ዓ/ም ዉሳኔ መስጠቱን ከተደረገዉ ክርክር ይዘት እንዲሁም ከዉሳኔዉ የተመለከትን በመሆኑም በዚህ ምክንያት ለዚህ ሰበር መነሻ የሆነዉ አቤቱታ ተዘግቶ መቆየቱን ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡ ስለዚህ ተጠሪ ከዚህ ጋር አያይዘዉ ያነሱትን ቅሬታ አግባብነት ያለዉ ሆኖ አላገኘነዉም፡፡

በሌላ በኩል ዋናዉን ጉዳይ በተመለከተ ከላይ በዝርዝር እንደተመለከተዉ በግራ ቀኙ መካከል ጋብቻ የተፈጸመዉና ለክርክሩ ምክንያት ለሆነዉ ቤት ክፍያ የተከፈለዉ ህዳር 19 ቀን 2000 ዓ/ም ነዉ፡፡

ተጠሪ ይህንን ሳይክዱ የሚከራከሩትን የኮንድሚንየም ቤት ገንዘብ ጠዋት ከተከፈለ በኃላ ጋብቻ ከሰአት በኃላ ተፈጽሟል የሚል ነዉ፡፡ በአንድ ቀን ዉስጥ በተለያየ ጊዜ የተለያየ ህጋዊ ድርጊት እንደተፈጸመና ይህም ልዩነት ልያመጣ እንደሚችል ተጠሪ ቢከራከሩም በስር ፍ/ቤቶች ዉሳኔ ላይ የተረጋገጠ ፍሬ ነገር የኮንደምንየም ቤቱ ክፍያ እና የቤቱ ሽያጭ ዉል የተፈጸመዉ ጋብቻ ዉስጥ መሆኑ ነዉ፡፡የስር ፍ/ቤቶችም ዉሳኔያቸዉ ይህንን አምነዉ ተቀብለዋል፡፡የፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የኮንደምንያም ቤቱ የተጠሪ የግል ንብረት ነዉ በማለት ሊደመድም የቻለዉ እጣዉ ከጋብቻ በፊት የደረሰ በመሆኑ ነው የሚል ነው፡፡ የኮንደምኒየም ቤት እጣው ብቻ ከጋብቻ በፊት መድረስ ክፍያ ባልተፈጸመ ሁኔታ ተጠሪን ለክርክሩ ምክንያት የሆነዉ ቤት ብቸኛ ባለመብት ሊያደርግ ይችላልን? የሚለዉን ምላሽ ሊያገኝ የሚገባዉ ነዉ፡፡ በዚህ ረገድ አመልካች ለዚህ ሰበር ችሎት አቅርቦ የተከራከሩት ክርክር ይሁንታ የሚሰጠው ነዉ የሚል ነዉ፡፡ ምክንያቱም እጣ መዉጣት ለብቻዉ የቤት ባለቤት አያደርግም፡፡ የኮንድምንየም ቤት ባለቤትነት የሚገኘዉ በነጻ ወይም እጣዉ በመዉጣቱ ብቻ ሳይሆን በግዢ በመሆኑ ገንዘቡ ሲከፈል ነው ፡፡ በተያዘው ጉዳይ ከላይ እንደተገለጸው ገንዘብ የተከፈለው በጋብቻ ውስጥ ነው፡፡ ይህ የተከፈለው ገንዘብም በብድር የተገኘ መሆኑንና የብድር ውሉንም አያይዘው ማቅረባቸው አመልካች አጥብቀው ተከራክረዋል ፡፡ ተጠሪ ለዚህ ችሎት ባቀረቡት ክርክር ለኮንደሚኒየም ቤቱ የተከፈለው ገንዘብ የግላቸው ስለመሆኑ የተከራከሩ ቢሆንም ይህንን በስር ፍርድ ቤት በማስረጃ አላረጋገጡም ፡፡ በአንድ ክርክር ላይ መብትና ጥቅም አለኝ የሚል ተከራካሪ ወገን ይህንን የማስረዳት ሽክም የእራሱ ስለመሆኑ ከማስረጃ ህግ መርህ የምንገነዘበው ነው የፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ህግ ቁጥር 255 እና ተከታዮቹ

ድንጋጌዎችም ይህንን መርህ የሚያጠናክሩ ናቸው ፡፡ በፍትሐብሔር ክርክር አንድ መብት ወይም ግዴታ አለ ብሎ የሚከራከር ወገን መብቱ ወይም ግዴታው ስለመኖሩ የማስረዳት ሸክም ያለበት ስለመሆኑ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በሰበር መዝገብ ቁጥር 44634 አስገዳጅ ትርጉም ሰጥቶበታል ፡፡ በመሆኑም ለክርክሩ ምክንያት ለሆነው ቤት የተከፈለው ገንዘብ ምንጭ የተጠሪ የግል መሆኑን ካላስረዱ በስተቀር ቤቱ የተጠሪ የግል ነው ሊባል የሚችልበት ህጋዊ ምክንያት አይኖርም ፡፡ከዚህ በተጨማሪ የአካራካሪው ኮንደሚኒየም ቤት የሽያጭ ውል የተፈረመው ወይም የተደረገው በጋብቻው ውስጥ ነው፡፡ የቤት ባለቤትነት ወይም የቤቱ ካርታ በተጠሪ ስም የተሰጠውም የካቲት 10 ቀን 2002 ዓ/ም ሲሆን ይህም አመልካችና ተጠሪ በጋብቻ ውስጥ አብረዉ እያሉ ነው፡፡ እነዚህ ሁሉ ተዳምረው ለክርክሩ ምክንያት የሆነው ቤት የጋራ ንብርት እንደሆነ አረጋጋጭ ናቸው፡፡

በመጨረሻም የስር ፍርድ ቤቶች የተረጋገጡ ፍሬ ነገሮችን በአግባቡ ሳያጤኑ ለክርክሩ ምክንያት የሆነው ኮንደሚኒየም ቤት የተጠሪ የግል ንብረት ነው ሲሉ የደረሱበት ድምዳሜ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነው ፡፡ በመሆኑም ቀጥሎ ያለው ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

<u>ው ሳ ኔ</u>

1. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በፍ/መ/ቁ.103524 በቀን 28/02/07 ዓ/ም እንዲሁም የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ.163552 በቀን 20/4/2010 ዓ/ም የሰጡት ውሳኔ በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ህግ ቁጥር 348/1/ መሰረት ተሽሯል፡፡
2. ለክርክሩ ምክንያት የሆነው ኮንደሚኒየም ቤት የአመልካችና የተጠሪ የጋራ ንብረት ነው ተብሎ ተወስኗል ፡፡
3. የዚህን ችሎት ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡
4. የውሳኔው ግልባጭ ለስር ፍርድ ቤቶች ይድረሳቸው፡፡
5. ጉዳዩ ስለተወሰነ መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ሰ/ጥ

የሰበር መዝገብ ቁጥር 189201

መጋቢት 02 ቀን 2012 ዓ.ም

ዳኞች ፡-ተፈሪ ገብሩ (ዶ/ር)

ቀነዓ ቂጣታ

ደጀኔ አያንሳ

ኑረዲን ከድር

ብርቅነሽ እሱባለው

አመልካቾች፡- ---1. አቶ ወድወሰን ታደሰ ይስማ

2. ወ/ሮ ወይንሸት ደስታ አጠረዉ } የሌሎችም ወኪል 2ኛ አመልካች ቀርበዋል

3. ወ/ሪት ጥሩነሽ በቀለ ስዩ

ተጠሪ ፡- የለም

መዝገቡ ለዛሬ የተቀጠረው ለምርመራ ሆኖ ተመርምሮ ቀጣዩ ፍርድ ተሰጥቷል ፡፡

ፍ ር ድ

ኢትዮጵያዊ እናት እና አባት የሆኑት 1ኛ እና 2ኛ አመልካቾች በትዉልድ ኢትዮጵያዊ በዜግነት አሜሪካዊ የሆኑት የ2ኛ አመልካች እህት 3ኛ አመልካች የ1ኛ እና 2ኛ አመልካቾች ልጅ የሆነችዉን ተማሪ ኤፍራታ ወንደሰን ቤተሰብ ለልጅ የሚያደርገዉን ሁሉ ከልጅነቷ ጀምሮ ካለችበት ሀገር ሆና ስትንከባከባት የነበረች እና በምትኖርበት ሀገርም ልጇ መሆኗን የተለያዩ ፍርሞችን መሙላቷን አንስተዉ በአመልካቾች መካከል የተደረገዉ የተማሪ ኤፍራታ ወንደሰን የጉዲፈቻ ስምምነት እንዲፀድቅላቸዉ ለፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት አቤቱታ አቅርበዉ ፍርድ ቤቱ በመዝገብ ቁጥር 103957 በ2/11/2011 በዋለዉ ችሎት የዉጭ ሀገር ጉዲፈቻ በአዋጅ ቁጥር 1070/2010 የተከለከለ ነዉ በማለት አቤቱታዉን ባለመቀበል ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡ ይህን ትዕዛዝ በመቃወም ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ባቀረቡት የይግባኝ ነባሩ የዉጭ ጉዲፈቻን በአዋጅ ቁጥር 1070/2010 መተካት ያስፈለገዉ ሕጉን ከብሔራዊ የሕፃናት ፖሊሲ ጋር ለማጣጣም ሆኖ ለሕጉ መሻሻል መሠረት የሆነዉ ፖሊሲ ይዘትም ኢትዮጵያዊያን ህፃናት የትዉልድ አከባቢያቸዉን ባህል፣ልማድ፣ወግ እና ማህበራዊ እሴቶችን ጠብቀዉ እንዲያድጉ የተቀረፀ ሲሆን ትዉልደ ኢትዮጵያዊያን የዉጭ ሀገር ዜጎች እንደ ሀገሪቱ ዜጋ በኢኮኖሚያዊ፣ማህበራዊ፣አስተዳደርዊ ጉዳዮች እንዲሳተፉ ህግ ወቶ በመንቀሳቀስ ላይ እያሉ የዉጭ ሀገር ጉዲፈቻን የሚከለክል የህግ ማሻሻያ መደረጉ እና ይህ ክልከላ ትዉልደ ኢትዮጵያዊያን የዉጭ ሀገር ዜጎችን እንደማይመለከት በግልጽ አለመደንገጉ ዕገዳዉ እነሱንም የሚጨምር መሆኑን ያመላክታል በማለት የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በፍ/ሥ/ሥ/ ሕግ ቁጥር 337 መሠረት በመዝገብ

ቁጥር 237661 ላይ ታህሳስ 16 ቀን 2012 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት የተሰጠዉ ብይን መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነዉ በማለት በሰበር እንዲታረምላቸዉ አመልካቾች ጥር 14 ቀን 2012 ዓ.ም ጠይቀዋል፡፡

አመልካቾች ያቀረቡት አቤቱታ ይዘት በአጭሩ፥-ተጠቃሹ አዋጅ የከለከለዉ በአመልካቾች መካከል የተደረገዉ የጉዲፈቻ ዉል ሳይሆን ኢትዮጵያዊ ዜጋ ለሌላ ሀገር ዜጋ በጉዲፈቻ ሲሰጥ ሆኖ እያለ የጉዲፈቻ ዉል ሰጪዎች ኢትዮጵያዊያን ሲሆኑ 2ኛ የጉዲፈቻ ዉል ሰጪ የጉዲፈቻ ዉል ተቀባይ ታላቅ እህት ሆኖ ባለዉ የመረዳዳት ባሕህል በጉዲፈቻ ልትወስዳት የፈለገችዉን ተማሪ ኤፍራታ ወንደሰን በእናት እና አባት ለልጅ መደረግ የሚገባዉን ሁሉ እያደረገች አሁን እስካለችበት እድሜ የምትንከባከባት እና በምትኖርበት ሀገርም ልጄ በማለት ፎርማሊትዎችን አሟልታ የጉዲፈቻ ዉሉን መፅደቅ ብቻ የምትጠባበቅ መሆኑን ገልፀዉ ያቀረቡት የጉዲፈቻ ዉል እንዲፀድቃላቸዉ ጠይቀዋል፡፡የሰበር አጣሪ ችሎቱም የጉድፈቻ ጥያቄ ትዉልደ ኢትዮጵያዊያን የሆኑትን የዉጭ ሀገር ዜጎችን ያካትታል ወይስ አያካትትም የሚለዉን ከአዋጅ ቁጥር 1070/2010 እና ቤተሰብ ህጉ አላማ እና አተረጓገም አንፃር ለማጣራት መዝገቡ ለሰበር ችሎቱ እንዲቀርብ ትዕዛዝ ሰቷል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ እና በዚህ ችሎት የተደረገዉ ክርክር ከላይ የተጠቀሰዉን የሚመስል ሲሆን ችሎቱም መዝገቡን 3ኛ አመልካች የጉዲፈቻ ዉሉን ለመቀበል አይችሉም ተብሎ የተሰጠዉ ዉሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት መሆን /አለመሆኑን አግባብነት ካለዉ ሕግ ጋር እንደሚከተለዉ መርምሯል፡፡ጉዲፈቻ ከሥጋ መወለድ ዉጭ ወይንም የደም ትስስር ሳይኖር በህግ ልጅነት ወይንም የልጅ ቤተሰብ ግንኙነት የሚፈጠርበት ህጋዊ ተግባር (juridical act) ነዉ፡፡ይህ ተግባር ጥንታዊ ሆኖ የተስፋፋዉ እና ብዙ ሀገሮች የህግ ሥርዓታቸዉ አካል ማድረግ የጀመሩት ከ2ኛ ዓለም ጦርነት ወዲህ ነዉ፡፡በኢትዮጲያም የጉዲፈቻ ባህል በተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች ተግባራዊ ሲደረግ ቆይቷል፡፡በጥንቱ ዘመን ጉዲፈቻ ይደረግ የነበረዉ ጉዲፈቻ አድራጊዉን በእርጅና ጊዜ ለመርዳት፣ወራሽ እንዲያገኝ ፣ዘሩ እንዲቀጥል፣ሴት ወይንም ወንድ ልጅ ለሌላቸዉ ለመስጠት ወዘተ ሆኖ በአጠቃላይ ለጉዲፈቻ አዲራጊዉ ጥቅም ተብሎ የሚደረግ ነበር፡፡በተፈጥሮ እና ሠዉ ሰራሽ ክስተቶች ምክንያት መፈናቀል እየበዛ ሲመጣ ወላጅ አልባ ለሆኑት እና ተጥሎ የተገኙ ህፃናትን ለመታደግ ጉዲፈቻ እዉነተኛ የቤተሰብ ተቋም እየሆነ መቷል፡፡በዘመናዊዉ ሕግ የጉዲፈቻ ዓላማ የሕፃናት ደህንነትን (best interst of the child) በማስጠበቅ ሕፃናት በሥጋ ከወለዷቸዉ ቤተሰብ ዉጭ ተተኪ ቤተሰብ እንዲያገኙ ለማስቻል ነዉ፡፡

በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ጠቅላላ ጉባኤ እ. ኤ. አ ታህሳስ 20 ቀን 1989 ዓ.ም ፀድቆ መስከረም 2 ቀን 1990 ዓ.ም በሥራ ላይ የዋለዉ ኢትዮጵያም ተቀብላ ያፀደቀችዉ የሕፃናት መብት ኮንቬንሺን አንቀጽ 20 ላይ እንደተገለጸዉ ተዋዋይ ሀገሮች ከቤተሰባቸዉ ለተለዩ ሕፃናት አማራጭ እንክብካቤ የሚያገኙበት መንግስት ማዘጋጀት ያለበት መሆኑንና ከዚህ ዉስጥ ጉዲፈቻ አንዱ መሆኑን

አንቀጽ 20 የሚደነግግ ሲሆን በአንቀጽ 21(ለ) መሠረት የዉጭ ሀገር ጉዲፈቻ የሚፈቀደዉ ሕፃናት በሀገር ዉስጥ አማራጭ እንክብካቤ የሚያገኙበት ማዕከል የሌለ እንደሆነ መሆኑን ያስረዳል፡፡በሀገር ዉስጥ እና በዉጭ ሀገር የሚደረግ ጉዲፈቻ እኩል ጥበቃ የሚደረግላቸዉ መሆኑን፣ጉዲፈቻ ዉስጥ ተሳትፎ ያላቸዉ አካላት የማይገባ ጥቅም እንዳያገኙ እርምጃ የሚወሰድ መሆኑና የሕጉን ዓላማ ለማራመድ በሀገሮች መካከል የሁለትዮሽ እና ሌሎች ስምምነቶች እንደሚደረጉ አንቀጽ 21(ሐ)፣(መ) እና (ሠ) ይደነግጋል፡፡የአፍርካ ሕፃናት መብቶችና ደህንነት ቻርተር አንቀጽ 24(ለ) የሕፃናት መብቶች ስምምነቶች በተቀበሉ ወይንም ባፀደቁ ሀገራት መካከል የዉጪ ሀገር ጉዲፈቻ እንደመጨረሻ አማራጭ የሚደረግ መሆኑና አንቀጽ 24(ረ) ሥር ጉዲፈቻ የተደረገዉ የሕፃናት ደህንነት ለማረጋገጥ የሚያስችሉ ሥርዓቶችን መዘርጋት ግዴታ መሆኑን ያስረዳል፡፡እነዚህ ኢትዮጵያ ያፀደቀቻቸዉ ዓለም አቀፍ ስምምነቶች የሀገሪቱ የሕግ አካል መሆናቸዉን የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 9(4) ይደነግጋል፡፡ የሕጻናት መንት ኮንቬንሽን በአዋጅ ቁጥር 11/1984 የጸደቀ ሲሆን የአፍሪካ ሕጻናት መብቶችና ደህንነት ቻርተር ደግሞ በአዋጅ ቁጥር 283/1994 ጸድቋል፡፡ በአጠቃላይ ከላይ የተጠቀሱት ስምምነቶች የዉጭ ሀገር ጉዲፈቻ በሀገር ዉስጥ አማራጭ ሕፃናት ከወላጆቻቸዉ ዉጭ እንክብካቤ የሚያገኙበት መንገድ በማይኖርበት ወቅት የሚደረግ ሆኖ ሕፃናቱ ለተለያየ የሰበአዊ መብት ጥሰት እንዳይጋለጡ ከፍተኛ ጥንቃቄ መደረግ ያለበት መሆኑን ያስረዳሉ፡፡

መንግስት እጓለ ሙታን በጉዲፈቻ የሚያድጉበትን ሥርዓት እንደሚያመቻች ሕገ መንግስቱ አንቀጽ 36(5) ይደነግጋል፡፡የቤተሰብ ሕጉን ለማሻሻል ካስፈለጉት ምክንያቶች ዉስጥ አንዱ ለሕፃናት ደህንነት ቅድሚያ ለመስጠት መሆኑ ከተሻሻለዉ የቤተሰብ ሕግ አዋጅ ቁጥር 213/1992 መግቢያ መገንዘብ ይቻላል፡፡በዚህ አዋጅ አንቀጽ 194(3)(መ) መሠረት ጉዲፈቻ አድራጊዉ የዉጭ ሀገር ዜጋ ሊሆን የሚችለዉ ሕፃኑ በኢትዮጵያ ዉስጥ የሚያድግበት ሁኔታ አለመኖሩ ሲረጋገጥ ሆኖ አፈፃፀሙም በአንቀጽ 193 ሥር ተመላክቷል፡፡የተሻሻለዉ የቤተሰብ ሕግ ለ17 ዓመታት በሥራ ላይ ከዋለ በኋላ ሚያዚያ 2009 ዓ/ም የወጣዉ የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት የህፃናት ፖሊሲ በአስቸጋሪ ሁኔታ ዉስጥ የሚገኙት ህፃናት *በኢትዮጵያ ባህል፣በአከባቢያቸዉ ወግ ፣ልማድና በማህብረሰባዊ እሴት ታንፀዉ እንዲያድጉ* ለማድረግ በአገር ዉስጥ ባሉ አማራጭ የድጋፍ እና እንክብካቤ አገልግሎቶች ማለትም በማህብረሰብ አቀፍ ድጋፍ እና እንክብካቤ፣በሀገር ዉስጥ ጉዲፈቻ፣በአደራ ቤተሰብ እና በመልሶ ማቀላቀል እና ማዋሀድ ፕሮግራሞች *ብቻ* እንዲደረግ ማድረግ ከዝርዝር ዓላማዎቹ ዉስጥ አንዱ ነዉ፡፡ፖሊሲዉ ዉስጥ እንደ ዋና ዋና ጉዳዮች ከተጠቀሱት መካከል በአስቸጋር ሁኔታ ዉስጥ ያሉት ሕፃናት የሚደገፉበትን የሚመለከት ሲሆን በተለያዩ ምክንያቶች ወላጆቻቸዉን ያጡ ተንከባካቢ የሌላቸዉ ሕፃናት የቤተሰብ ፍቅር ፣ እንክብካቤ እና ጥበቃ አግኝተዉ መሰረታዊ ፍላጎቶቻቸዉ ተሟልተዉ እንዲያድጉ ለማድረግ የሚያስችሉ እንክብካቤ የሀገር ዉስጥ ጉዲፈቻ፣የአደራ ቤተሰብ እና በማህብረሰብ አቀፍ ድጋፍ እና እንክብካቤ ፕሮግራሞችን በማስፋፋት

ለሕይወታቸዉ ጠቃሚ የሆኑ የምክር አግልግሎት ሰጪ ተቋማት እንዲስፋፉ እና ተደራሽ በማድረግ የኢኮኖሚያዊ እና ማሕበራዊ አገልግሎቶችን በጥራት፣ በስፋት በወቅቱ እንዲደርሳቸዉ በማድረግ እንደየ ችግራቸዉ ዓይነት በማህበረሰቡ ያሉ እሴቶችን በመቀመርና በማስፋፋት በሀገር ዉስጥ ባሉ አመራጭ የድጋፍ እና እንክብካቤዎች ዚዴዎች ብቻ እንደሚደገፉ ተመላክቷል።ሀገር ዉስጥ ምርጫ ሲጠፋ ተፈቅዶ የነበረዉ የዉጪ ሀገር ጉዲፈቻ ሙሉ ለሙሉ  በማስቀረት ለችግሩ ሀገራዊ መፍትሔ ብቻ በመስጠት የፖሊሲ ምርጫ የተወሰደበት ዋናዉ ምክንያት የዉጭ ሀገር ጉዲፈቻ የተፈጥሮ ቤተሰብ ፍቅር እና እንክብካቤን የማይተካ ከመሆኑም በላይ የዚህ አማራጭ ተጠቃሚ የሆኑት ሕፃናት በማያዉቁት ቋንቋ፣ባህል እንዲያድጉ በመደረጋቸዉ ለማንነት ቀዉስ ፣ለስነ-ልቦናዊና ማህበራዊ ችግሮች ሲጋለጡ በመታየታቸዉ የዉጭ ሀገር ጉዲፈቻ ተመራጭ የድጋፍ እና እንክብካቤ ዜዴ እንዳልሆነ ፖሊሲዉ ያመለክታል።ፖሊሲውን ተግባራዊ ለማድረግ በተሻሻለዉ የቤተሰብ ህግ ላይ ማሻሻያ እንደሚደረግ ተገጿል።የዉጭ ሀገር ጉዲፈቻን በሚመለከት የተሻሻለዉን የቤተሰብ ሕግ አንቀጾችን ማሻሻል ያስፈለገዉ በፖሊሲዉ እና በሕጉ መካከል የሚቃረኑ ሀሳቦች በመኖራቸዉ ሁለቱን ሰነዶች ለማጣጣም መሆኑ ህጉ ሲወጣ ከተያዘዉ ቃለጉባኤ እና የተሻሻለዉን የቤተሰብ ህግ አንቀጽ 193 እና 194(3)(መ)ን የሻረዉ አዋጅ ቁጥር 1070/2010 መቅድም (preamble) መረዳት ተችሏል።

የዉጭ ሀገር ዜግነት ያላቸዉ ትዉልደ ኢትዮጵያዊን በሚመለከት በተቀረፀዉ የዲያስፖራ ፖሊሲ በንግድ፣ቱሪዝም፣በዕዉቀት እና ቴክኖሎጂ ሽግግር፣የዉጭ ምንዛሪን በማስገኘት ብሎም በሀገር ገጽታ ግንባታ ረገድ ዲያስፖራዉ ትልቅ ሀገራዊ ኃላፊነት ተጥሎበታል።የፖሊሲዉ ዓላማ በዉጭ ሀገር የሚኖሩት ኢትዮጵያዊ እና ትዉልደ ኢትዮጵያዊ ከትዉልድ ሀገሩ ጋር ያለዉን ትስስር በማጠናከር በልማት፣ሰላምና ዲሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ ጠንካራ ተሳታፊ ሆኖ ራሱን ጠቅሞ ትዉልድ ሀሩን በመጥቀም በጋራ ለማደግ ምቹ ሁኔታ ለመፍጠር ነዉ።ፖሊሲዉን ለማስፈፀም ከወጡት ሕጎች ዉስጥም የኢትዮጵያ ተወላጅ የሆኑ የዉጭ ዜጎችን በትዉልድ ሀገራቸዉ ተጠቃሚ ለማድረግ የወጣዉ አዋጅ ቁጥር 270/1994 አንዱ ሲሆን የሕጉ ዓላማ ተብሎ በአዋጁ መቅድም(preamble) እንዲሁም በቁጥር 3 ከተገለፀዉ መረዳት እንደሚቻለዉ ትዉልደ ኢትዮጵያዊያን ከትዉልድ ሀገራቸዉ ጋር ያላቸዉ ግንኙነት እንዲጠነክር የሚፈልጉ በመሆኑ በዉጭ ዜጎች ላይ የተጣሉት የመብት ገደቦች ለማላላት የተለያዩ መብቶች እና ጥቅማ ጥቅሞች ባለቤቶች በማድረግ ለትዉልድ ሀገራቸዉ እድገት እና ለወገኖቻቸዉ ኑሮ መሻሻል አስተዋጽኦ እንድያደርጉ ለማስቻል መሆኑ ተገልጿል።በዚሁ አዋጅ በቁጥር 5 ሥር የተጠቀሱት መብቶችም ወደ ኢትዮጵያ ለመግባት፣ ሀገር ዉስጥ ለመቆየት እና ለመኖር የመግቢያ ቪዛ እና የመኖሪያ ፈቃድ የማይጠየቁ መሆኑ፣ያለ ሥራ ፈቃድ ኢትዮጵያ ዉስጥ ተቀጥሮ መስራት፣የማይንቀሳቀስ ንብረት ባለቤት መሆን፣የዉጭ ሀገር ዜጎች ተጠቃሚ እንዳይሆኑ የሚገድቡ ህጎች፣አሠራር፣ልምድ ልዩነት ሳይደረግባቸዉ የኢኮኖሚ፣የማህበራዊ እና አስተዳዳራዊ ጥቅሞችን ማግኘት እንዲችሉ እና እንደ ሀገር ዉስጥ ባለሀብት መቆጠር ከፈለጉ ለሀገር ዉስጥ ባለሀብት በተፈቀዱ የኢንቬስትመንት መስኮች መሳተፍ

እንደሚችሉ ያስረዳል።በቁጥር 6 ሥር በመንግስት ደረጃ በሚደረግ ምርጫ መምረጥም ሆነ መመረጥ፣በሀገር መከላከያ፣የሀገር ደህንነት በዉጭ ጉዳይና መሰል የፖለትካ መሥሪያ ቤቶች በመደበኛነት ተቀጥሮ መሥራት እንደማይችሉ ገደብ ተጥሏል።የባንክ ሥራ አዋጅን ለማሻሻል የወጣዉ አዋጅ ቁጥር 1159/2012 ህጉን ለማሻሻል ያስፈለገዉ የዉጭ ሀገር ዜግነት ያላቸዉ ትዉልደ ኢትዮጵያዊያን በባንኩ ዘርፍ እንዲሳተፉ እና የባለቤትነት ድርሻ እንዲኖራቸዉ ለማድረግ መሆኑን የአዋጁ መቅድም (preamble) ያስረዳል።የዲያስፖራ ፖሊሲን ለማስፈፀም እና የኢትዮጵያዊያን ዲያስፖራዎችን መብት እና ጥቅም ማስከበር ዓላማዉ ያደረገ የኢትዮጵያ ዲያስፖራ ኤጀንሲ በሚል ስያሜ የህግ ሰዉነት ያለዉ የፌዴራል መንግስት መሥሪያ ቤት በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 432/2011 ተቋቁሟል።

ሕግ አዉጭዉ የህፃናቱን ደህንነት አስጠብቅበታለሁ ብሎ የያዘዉ አቋም ሕዝብ በተወካዮቹ በኩል ያደረገዉ የፖሊሲ ምርጫ ከዲሞክራሲ መርህ አንፃርም ሆነ ከኢ/ፌ/ዲ/ሪ ሕገ መንግስት አዋጅ ቁጥር 1/1987 አንቀጽ 50(3) ድንጋጌ መሠረት በፌዴራል መንግስቱ ከፍተኛ የሥልጣን አካል የወጣ ሕግ በመሆኑ እንዲሁም ከሥልጣን ክፍፍል መርህ (principle of separation of power) አንፃርም የፍርድ ቤት ሥራ ህግ ማዉጣት ስላልሆነ ሥልጣን በተሰጠዉ አካል የወጣዉ ሕግ መከበር ያለበት ሆኖ ህግ ሲወጣ ሁሉንም ጉዳዮች እንዲገዛ አጠቃላይ(general) ባህርይ ስላለዉ ህጉ ሳይቀየር ለህጉ አዲስ ትርጉም በመስጠት በህጉ እና ተጨባጭ በሕብረተሰቡ ኑሮ መካከል ያለዉን ክፍተት በትርጉም በመሙላት ለቀረቡላቸዉ ጉዳዮች እልባት በመስጠት ህግ አዉጭዉን ማገዝ የፍርድ ቤቶች የሥራ ግዴታ ነዉ።በሌላ በኩል ሕፃናትን አስመልክቶ የሚወሰዱ ማንኛዉም እርምጃዎች የሕፃናት ደህንነት በቀደምትነት መታሰብ እንዳለበት የኢ/ፌ/ዲ/ሪ ሕገ መንግስት አዋጅ ቁጥር 1/1987 አንቀጽ 36(2) የሚያስረዳ ሲሆን ይህ ችሎትም አግባብነት ያላቸዉን ሕጎች በመመርመር የሕፃናት መብት እና ጥቅም ለማስከበር በቀደምትነት መርህ የሕፃናት ጥቅምና ደህነት (best interest of the child) ስለመሆኑ በመዝገብ ቁጥር 23632,35710 እና በሌሎች በርካታ መዛግብት አስገዳጅ ዉሳኔ ሰቷል።

ወደተያዘዉ ጉዳይ ስንመለስ የኢትዮጵያዊያን ዲያስፖራዎች ለሀገር እድገት እና ብልጽግና በሀገር ዉስጥም ሆነ በዉጭ ሀገር ትልቅ ኃላፊነት የተጣለባቸዉ በሆነ ምክንያት ኢትዮጵያዊ ዜግነታቸዉን ቢያጡም ትዉልድ ሀገራቸዉ ኢትዮጵያ ስለሆነች እና ዜጎቿም ወገኖቻቸዉ ስለሆኑ ነዉ።በትዉልድ ሀገራቸዉም እንደ ዉጭ ዜጋ እንዳይታዩ ልዩ መብት እና ጥቅማ ጥቅሞች ተክብሮላቸዋል።ሕጉ መብቶቻቸዉን ዘርዝሮ በመቀጠል ገድብ ማስቀመጡ ዝርዝሩ ሙሉ አለመሆኑን ማሳያ ነዉ።የኢትዮጵያ ተወላጅ የሆኑ የዉጭ ዜጎች ከኢትዮጵያዊያን ዜጎች መብቶች ዉስጥ ጥቂቶቹ ስለተቀነሱባቸዉ ሙሉ በሙሉ እንደ ሌላ የዉጭ ሀገር ዜጋ ማየት ተገቢ አይሆንም።በሌላ በኩል ኢትዮጵያዊ ማንነት ያላቸዉን የዉጭ ዜጎች ትልቅ ሀገራዊ ኃላፍነት የተጣለባቸዉ የሀገርቷን ባህል፣ቋንቋ፣እሴት እንደማያዉቁ

የዉጭ ሀገር ጉዲፈቻ አድራጊዎች በጉዲፈቻ የሚወስዱትን ኢትዮጵያዊ ሕፃን የሀገሩን ባህል፣ወግ ፣ልማድና በማህብረሰቡ እሴት ታንፀዉ እንዳያድግ ተፅኖ በማድረግ፣ፍቅር በመንፈግ ለስነ-ልቦናዊና ማሕበራዊ ችግር ያግልጣቸዋል ብሎ በማሰብ የሥጋ ዘመዶቻተዉን በጉዲፈቻ እንዳይወስዱ መከልከል የተጣላባቸዉን ኃላፊነት ካለመረዳት የሚመነጭ ነዉ፡፡ትዉልደ ኢትዩጵያዊያኑ እና በጉዲፈቻ የሚወሰዱት ኢትዩጵያዊያን ሕፃናት የጋራ ባህል እና ማንነት ያላቸዉ ሆኖ በዜግነት ብቻ የሚለያዩ ስለሆኑ የህፃናቱ የቀደመ ማንነት በሌላ አዲስ ማንነት ለመቀየር ፍላጎት ይኖራቸዋል ተብሎ አይታሰብም፡፡ በተያዘዉ ጉዳይ 3ኛ አመልካች በጉዲፈቻ ለመቀበል ለምትፈለገዉ ልጅ አክስት ስትሆን ምንም የህግ ግዴታ ሳይኖርባት በማህብረሰቡ ዉስጥ ባለዉ የመረዳዳት ባህል እናት እና አባት ለልጅ የሚያደርጉትን ሁሉ እያደረገች እና እንደ ልጇ በምትኖርበት ሀገር ያስመዘገበች መሆኑን ከመዝገቡ መረዳት ተችሏል፡፡3ኛ አመልካች እና በተማሪ ኤፍራታ ወንደሰን መካከል የደም ግንኙነት መኖሩ፣ሕጋዊ ግዴታ ሳይኖርባት ስትረዳት መቆየቷ በራሱ ለቆየዉ የመረዳዳት እሴታችን ያላትን ቦታ ማሳያ መሆኑ፣የሚጋሩት የጋራ ባሕል ያላቸዉ መሆኑ ለጉዲፈቻ ተደራጊዋ ከቤተሰዋ ጋር ከትዉልድ ሀገሯ የመዉጣት ያክል ሆኖ እያለ እና 3ኛ አመልካች የምትኖረዉ አሜርካ ሀገር ብዙ ትዉልደ ኢትዩጵያዊያን ያሉበት መሆኑ ታዳጊዋን ኢትዩጵያዊ ማንነቷን ይዛ በመልካም ስብዕና ለማደግ የሚያስችል ምቹ ሁኔታ መኖሩ መልካም አጋጣሚ ሆኖ እያለ የኢትዮጵያዊያን ዲያስፖራዎች በሀገር እድገት እና ብልጽግና እንዲሁም ለወገኖቻቸዉ ኑሮ መሻሻል ያላቸዉን ሚና ባለመገንዘብ የህጻኗን የደህነት ቀደምትነት መብት በመንፈግ በሥር ፍርድ ቤቶች የተሰጠዉ ዉሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ቀጣዩ ተወስኗል፡፡

## ዉሳኔ

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 237661 በ16/04/2012 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት የሠጠዉ ብይን እና የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 103957 በ02/11/2012 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት የሠጠዉ ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሔ/ሥ/ሥ ህግ ቁጥር 348(1) መሠረት ተሽሯል፡፡
2. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የተዘጋዉን መዝገብ ቁጥር 103957 በማንቀሳቀስ 3ኛ አመልካች ተማሪ ኤፍራታ ወንደሰን በጉዲፈቻ ለማሳደግ የሚያስችላቸዉን መስፈርት ማሟላት አለማሟላታቸዉን በማጣራት ተገቢ ነዉ የሚለዉን ዉሳኔ ይሰጥ ዘንድ መዝገቡ በፍ/ብ/ሔ/ሥ/ሥ ህግ ቁጥር 341(1) መሠረት መልሰንለታል፡፡
3. የመዝገቡ ትክክለኛ ግልባጭ ለሥር ፍርድ ቤቶች ይድረስ፡፡

መዝገቡ ዉሳኔ ስላገኘ ተዘግቷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፍርማ አለበት፡፡

ፋ/ዘ

የሰ/መ/ቁ.144585

ግንቦት 13 ቀን 2010 ዓ/ም

ዳኞች፡- ፀጋዬ አስማማው

አልማው ወሌ

ሙስጠፋ አህመድ

አብርሃ መሰለ

ጳውሎስ ኦርሺሶ

አመልካቾች፡- 1. ወ/ሮ ሀና ካሳዬ
2. ወ/ሮ ገነት ካሳዬ - ጠበቃ አካል ዶይሰማ ቀረቡ፡፡

ተጠሪ፡-ወ/ሮ ዘነበች ከሳዬ - ቀረቡ፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

የነገሩ አመጣጥ የውርስ ንብረት ክርክርን የሚመለከት ነው፡፡ጉዳዩ የተጀመረው በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ሲሆን የአሁን ተጠሪ ከሳሽ ሲሆኑ የአሁን አመልካቾች ደግሞ ተከሳሾች ነበሩ፡፡ የሥር ከሳሽ /የአሁን ተጠሪ/ መጋቢት 6 ቀን 2008 ዓ/ም ጽፈው ባቀረቡት የክስ አቤቱታ ከሳሽ የሟች እናታቸው የወ/ሮ እልፍነሽ ሄይ ብቸኛ ወራሽ መሆናቸውን፣ የሟች አናታቸው የውርስ ሀብት በመ/ቁ. 97412 ተጣርቶ ግንቦት 26 ቀን 2007 ዓ/ም መጽደቁን፣ ሟች እናታቸው ከሟች አቶ ካሳዬ ደሳለኝ ጋር በትዳር አብረው የቆዩ በመሆናቸው የሟች አቶ ከሳዬ ድርሻ በወራሾቻቸው በኩል በመ/ቁ. 62253 ተጣርቶ የቀረበ መሆኑን፣ የሟቾቹን የውርስ ንብረት የውርስ አጣሪ ተሹሞ ያጣራ መሆኑንና በፍርድ ቤት መጽደቁን፣ ተከሳሾች ከጥቅምት 22 ቀን 2002 ዓ/ም እስከ ሀምሌ 19 ቀን 2003 ዓ/ም ድረስ እንዲሁም ከግንቦት 1 ቀን 2005 እስከ ሚያዝያ 30 ቀን 2006 ዓ/ም ድረስ ከመኖሪያ ቤትና ወፍጮ በወር ብር 20,513 /ሃያ ሺህ አምስት መቶ አስራ ሶስት/ ለ31 ወር ሲሰበስቡ መቆየታቸውን፣ በአጠቃላይ ብር 20,513 X 31 ወር = 635,903 /ስድስት መቶ ሰላሳ አምስት ሺህ ዘጠኝ መቶ ሶስት/ ብር መሰብሰቡን ገልጸው የከሳሽ ድርሻ ብር 211,967 /ሁለት መቶ አስራ አንድ ሺህ ዘጠኝ መቶ ስልሳ ሰባት ብር/ ከእነ ወለዱ ተከሳሾች እንዲከፍሉ እንዲሁም ለክርክሩ የወጣውን ወጪ እንዲተኩ በማለት ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡

ተከሳሾች ሚያዝያ 26 ቀን 2008 ዓ/ም በተጻፈ መልስ የወፍጮ ቤት ገቢን በተመለከተ ሟች ከሞቱበት ከ2002 ዓ/ም ጀምሮ ወፍጮ ቤት እስከተከራየበት መስከረም 29 ቀን 2005 ዓ/ም ድረስ ያለው ብር ሲሰባሰብ ቢቆይም ከቤት ኪራይና የወፍጮ ቤት ኪራይ ከሚገኘው ገቢ ውስጥ ለመንግሥት የሚከፈል እዳ፣ የከሳሽ ወላጅ እናት በህይወት እያሉ የወሰዱትን ለቀለብና ለህክምና የወጣ በፍርድ ቤት የተወሰነውን ተቀንሶ ድርሻቸውን ብር 2,865.15 /ሁለት ሺህ ስምንት መቶ ስልሳ አምስት ብር ከአስራ አምስት ሳንቲም/ ስለሚደርሳቸው መውሰድ ይችላሉ በማለት ተከራክረዋል፡፡

ጉዳዩን የተመለከተው ፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ጉዳዩን መርምሮ የቤት ኪራይ በተመለከተ በመዝገብ ቁጥር 62253 ላይ ግራ ቀኙ በተገኙበት የተጣራው ንብረት ውስጥ የቤት ኪራይ በአጠቃላይ ብር 435,430 /አራት መቶ ሰላሳ አምስት ሺህ አራት መቶ ሰላሳ/ ሲሆን ከዚህ ውስጥ በንብረት አስተዳዳሪዎች እጅ አለ የተባለው ብር 176,840 /አንድ መቶ ሰባ ስድስት ሺህ ስምንት መቶ አርባ/ ሲሆን በተከሳሾች እጅ የሚገኘው ብር 258,590 /ሁለት መቶ ሃምሳ ስምንት ሺህ አምስት መቶ ዘጠና ብር/ መሆኑ ነው፡፡ የወፍጮ ቤት ገቢን በተመለከተ ከውርስ አጣሪ ሪፖርት ለመረዳት የተቻለው ጣልቃ ገብ የነበሩ የአሁን ከሳሽ እናት ያቀረቡት ገቢ ብር 618,750 /ስድስት መቶ አስራ ስምንት ሺህ ሰባት መቶ ሃምሳ ብር/ ሲሆን በወቅቱ በውርስ አጣሪ መዝገብ ቁጥር 62253 ላይ ተጠሪዎች የነበሩ የአሁን ተከሳሾች በኩል የታመነ ነው የተባለው ብር 432,960.16 /አራት መቶ ሰላሳ ሁለት ሺህ ዘጠኝ መቶ ስልሳ ብር ከአስራ ስድስት ሳንቲም/ ነው፡፡ ከዚህ ገንዘብ ውስጥ በንብረት አስተዳዳሪዎች እጅ የነበረው ብር 133,860 /አንድ መቶ ሰላሳ ሶስት ሺህ ስምንት መቶ ስልሳ ብር/ ስለሆነ ተከሳሾች በውርስ አጣሪ ሪፖርት ላይ ያመኑት ገቢ ቢወሰድ እንኳን በውርስ አስተዳዳሪዎች እጅ የነበረው ሲቀነስ ብር 299,100 /ሁለት መቶ ዘጠና ዘጠኝ ሺህ አንድ መቶ ብር / ይሆናል፡፡ ስለዚህ ከቤት ኪራይ 258,590 /ሁለት መቶ ሃምሳ ስምንት ሺህ አምስት መቶ ዘጠና ብር/ እና ከወፍጮ ብር 299,100 /ሁለት መቶ ዘጠና ዘጠኝ ሺህ አንድ መቶ ብር / ሲደመር ብር 557,690 /አምስት መቶ ሃምሳ ሰባት ሺህ ስድስት መቶ ዘጠና ብር/ ይሆናል፡፡ በውርስ አጣሪ ሪፖርት በወጪነት የተያዘው በጋራ ብር 7,051 /ሰባት ሺህ አምሳ አንድ ብር/ ሲሆን ይህ እዳ ለሶስት ሲካፈል ብር 2,350 /ሁለት ሺህ ሶስት መቶ ሃምሳ ብር/ ይሆናል፡፡ ለከሳሽ አውራሽ ቀለብ ተብሎ የታሰበው ብር 7,890 /ሰባት ሺህ ስምንት መቶ ዘጠና ብር/ ስለሆነ የከሳሽ ድርሻ ወጪ ብር 10,240 /አስር ሺህ ሁለት መቶ አርባ ብር/ ይሆናል፡፡ ይህ ወጪ ከከሳሽ ወጪ የሚተካ ይሆናል፡፡ ስለሆነም አጠቃላይ ገቢ ብር 557,690 /አምስት መቶ ሃምሳ ሰባት ሺህ ስድስት መቶ ዘጠና ብር/ ለ3 ሲካፈል ብር 185,896.66 /አንድ መቶ ሰማኒያ አምስት ሺህ ስምንት መቶ ዘጠና ስድስት ብር ከስልሳ ስድስት ሳንቲም/ ሲሆን ከዚህ ውስጥ የከሳሽ ብር 10,240 /አስር ሺህ ሁለት መቶ አርባ ብር/ ሲቀነስ ብር 175,656.66 /አንድ መቶ ሰባ አምስት ሺህ ስድስት መቶ ሃምሳ ስድስት ብር ከስልሳ ስድስት ሳንቲም/ መሆኑን ፍርድ ቤቱ ከውርስ አጣሪ ሪፖርት ተረድቷል፡፡ ስለዚህ ተከሳሾች ለከሳሽ በፍርድ ቤት ቀርቦ በፀደቀው የውርስ አጣሪ ሪፖርት መሠረት ብር 175,656.66

/አንድ መቶ ሰባ አምስት ሺህ ስድስት መቶ ሃምሳ ስድስት ብር/ ውሳኔ ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ ከሚታሰብ 9% ወለድ ጋር ሊከፍሉ ይገባል በማለት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

የአሁን አመልካቾች ይህን ውሳኔ ቅር ተሰኝተው ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ያቀረቡ ሲሆን የይግባኝ ሰሚው ከፍተኛ ፍርድ ቤትም ይግባኛቸውን ሰርዞባቸዋል፡፡

ይህ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ውሳኔውን ለማስለወጥ ሲሆን የአመልካቾች አቤቱታ ይዘትም በአጭሩ፡- የውርስ አጣሪ ሪፖርቱ ላይ በወጪነት /በእዳነት/ የተመዘገበውን ብር 185,455.25 /አንድ መቶ ሰማኒያ አምስት ሺህ አራት መቶ ሃምሳ አምስት ብር ከሃያ አምስት ሳንቲም/ ፍርድ ቤቱ በኮ/መ/ቁ. 62253 ሰኔ 16 ቀን 2006 ዓ/ም ያለማንም ነቀፋ እና ተቃውሞ አጽድቆት እያለ የሥር ፍርድ ቤት በወጪነት ሳይዝ ዝም ብሎ ማለፉ አግባብነት የሌለው በመሆኑ ሊታረም የሚገባው ነው፡፡ ስለሆነም አመልካቾች የተጠሪ ድርሻ የሆነን ወጪ (እዳ) የምንወስድበት የህግ አግባብ የለም፡፡በመሆኑም ለተጠሪ ሊከፈል የሚገባው የገንዘብ መጠን በፀደቀው የውርስ አጣሪ ሪፖርት መሠረት ከሚደርሳቸው የውርስ ድርሻ ብር 185,896.66 /አንድ መቶ ሰማኒያ አምስት ሺህ ስምንት መቶ ዘጠና ስድስት ብር ከስልሳ ስድስት ሳንቲም/ ላይ ወጪዎችን /እዳዎችን/ ተቀናሽ በማድረግ ነው፡፡ ስለሆነም ለተጠሪ ሊከፈላቸው የሚገባው የገንዘብ መጠን ብር 185,896.66 - ብር 61,818.21 - ብር 10,240 = 113,838.21 /አንድ መቶ አስራ ሶስት ሺህ ስምንት መቶ ሰላሳ ስምንት ብር ከሃያ አንድ ሳንቲም/ ሆኖ እያለ ብር 175,656.66 ይከፈል መባሉ አግባብነት የሌለው ውሳኔ በመሆኑ እና ይህንን ለማድረግ የሚያስችል ሥልጣን የሌለው በመሆኑ ሊሻር የሚገባው ነው የሚል ነው፡፡

የሰበር አቤቱታውን አጣሪው መርምሮ የጉዳዩ አከራካሪ የሆነውን የውርስ ንብረት ለማቆየት አመልካቾች በውርስ አጣሪ በተራ ቁጥር 7 ላይ የተጠቀሰውን ወጪ ሳይቀንስ ወይም ሳይተቸው በማለፍ ይክፈሉ ያለበት አግባብነት መጣራት ያለበት መሆኑ ስለታመነበት ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ይቅረብ ሲል ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡

ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎላቸው በጠበቃቸው በኩል ጥቅምት 16 ቀን 2010 ዓ/ም ባቀረቡት መልስ የአመልካቾች ክርክር ስሌትን፣ ፍሬ ነገርን እና ማስረጃን የተመለከተ እንጂ የህግ ትርጉም ጥያቄ የሚያስነሳ ስላልሆነ ለሰበር ችሎት ቀርቦ የሚታይበት የህግ አግባብ የለም፡፡ በውርስ አጣሪ ሪፖርቱ ተራ ቁጥር 7 ላይ ተጠቅሶ በፍርድ ቤትም የፀደቀውን እዳ ብር 185,455.25 በተመለከተ ዘጠኙ ባለጉዳዮች የደረሱበት እና ፍርድ ቤቱም ያፀደቀው ስምምነት በውርስ አጣሪው ሪፖርት ላይ በግልጽ እንደተቀመጠው የውርስ እዳውን እኩል ለመከፋፈል ነው፡፡ በዚሁ መሠረት ብር 185,455.25 እዳ ለዘጠኝ እኩል ሲካፈል ተጠሪ የሚደርስባቸው ብር 20,6006.00 /ሃያ ሺህ ስድስት መቶ ስድስት ብር/ እንጂ ብር 61,818.25 /ስልሳ አንድ ሺህ ስምንት መቶ ስምንት ብር ከሃያ አምስት ሳንቲም/ አይደለም፡፡ በሥር ፍርድ ቤት በነበረው ክርክር የአሁን ተጠሪ ሊከፈለኝ ይገባል ሲሉ ያቀረቡት የውርስ ሀብት ገቢ

ድርሻ መጠን በግልጽ የተቀመጠ ቢሆንም ከውርስ ሀብቱ እዳ ላይ በውርስ አጣሪው ሪፖርት መሠረት ሊከፍሉት የሚገባ ያልከፈሉት ወይም ቀድመው ያላቻቻሉት የእዳ ድርሻ መኖሩን አመልካቾች ያቀረቡት ምንም ክርክርም ሆነ ማስረጃ የለም፡፡ በፍትሓብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ ቁጥር 329 በመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ያልተነሳ አዲስ ክርክር ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ሊቀበል እንደማይችል ተቀምጧል፡፡ ከብር 185,455.25 የውርስ እዳ ላይ ያልተከፈለ ወይም ያልተቻቻለ የተጠሪ የእዳ ድርሻ አለ የሚለው የአመልካቾች ክርክር ሥር መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ያልተነሳ አዲስ ክርክር ነው፡፡ በመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ያልተነሳ ክርክር በመሆኑ ደግሞ በይግባኝ ላይም ሆነ በሰበር ችሎት ሊቀርብ የሚችል አይደለም በማለት ተከራክረዋል፡፡

የነገሩ አመጣጥና የክርክሩ ሂደት በአጭሩ ከላይ የተመለከተውን የሚመስል ሲሆን በውርስ አጣሪ የተረጋገጠውና በፍርድ ቤት የፀደቀው የውርስ እዳ ከውርስ ንብረት ገቢ ላይ ሳይቀነስ ለአሁን ተጠሪ ድርሻቸው እንዲከፈል የተወሰነበት በአግባቡ ነው ወይስ አይደለም? የሚለው እንደሚከተለው ተመርምሯል፡፡ የአሁን አመልካቾች አባት፣ የተጠሪ እናት እንዲሁም ሌላኛዋ የአመልካቾች አባት ሚስት ንብረት እንዲጣራ ተደርጎ በኮ/መ/ቁ. 62253 ግንቦት 28 ቀን 2006 ዓ/ም በተጻፈ ሪፖርት ለፌዴራል የመጀመሪያ ፍርድ ቤት መቅረቡን፣ ፍርድ ቤቱም የቀረበውን ሪፖርት በኮ/መ/ቁ. 62253 ሰኔ 16 ቀን 2006 ዓ/ም ማጽደቁን ተመልክተናል፡፡ የውርስ አጣሪው ባቀረበው ሪፖርት ተራ ቁጥር 7 ላይ ከጥቅምት 22/2002 እስከ ግንቦት 28/2006 ዓ/ም ድረስ ያለው ጠቅላላ ወጪ ብር 185,455.25 /አንድ መቶ ሰማኒያ አምስት ሺህ አራት መቶ አምሳ አምስት ብር ከሃያ አምስት ሳንቲም/ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ በወቅቱ በህይወት የነበሩት የአሁን ተጠሪ አውራሽ ይህን ወጪ እንደማይቃወሙ በመግለጽ መስማማታቸውን የውርስ አጣሪው ሪፖርት ያስረዳል፡፡ ይህም የውርስ እዳ በፍርድ ቤት መጽደቁ ግራ ቀኙን አላከራከረም፡፡ የአሁን ተጠሪ በዚህ ችሎት ባቀረቡት ክርክር አራት ነጥቦችን ያነሱ ሲሆን የመጀመሪያው የአመልካቾች አቤቱታ የስሌት ጉዳይ ስለሆነ ለሰበር ክርክር ብቁ አይደለም የሚል ነው፡፡ ይህንን ክርክር ስንመለከት የስሌት ስህተትን መሠረት ያደረገ ክርክር አይደለም፡፡ ምክንያቱም የአመልካቾች ክርክር የታወቀና የተረጋገጠ የውርስ እዳ እያለ እዳው በድርሻ ልክ ሳይቀነስ ተጠሪ ከውርስ ንብረት የሚገኘውን ገቢ ብቻ ሊካፈሉ አይችሉም በማለት የሚከራከሩ በመሆናቸው ነው፡፡ ተጠሪ ለዚህ ችሎት ያቀረቡት ሌላኛው መከራከሪያ ነጥብ አመልካቾች ለሰበር ያቀረቡት አቤቱታ ፍሬ ነገርን የሚመለከት ስለሆነ ችሎቱ ሊያየው አይገባም የሚል ነው፡፡ የአመልካቾች ክርክር ደግሞ የተረጋገጠና በፍርድ ቤት የፀደቀ የውርስ እዳ እያለ ተጠሪን የሚመለከተው የውርስ እዳው ድርሻ ሳይቀነስ ከውርስ ንብረት የተገኘውን ገቢ ድርሻ እንዲወስዱ መወሰኑ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነው የሚል ነው፡፡ የውርስ እዳዎች አከፋፈል ቅድም ተከተል በፍትሓብሔር ህግ ቁጥር 1014 እና ተከታዮቹ ድንጋጌዎች ውስጥ በዝርዝር ተቀምጠዋል፡፡ እንዲሁም ከወራሾቹ አንዱ ለውርስ የሚከፍለው እዳ ያለበት እንደሆነ እዳው በድርሻው ውስጥ ይታሰባል በማለት የፍትሕብሔር ህግ ቁጥር 1090 በግልጽ

ይደነግጋል፡፡ ከእነዚህ ድንጋጌዎች የምንመለከተው የውርስ እዳ ካለ የውርስ ንብረት ክፍፍል ከመደረጉ በፊት የውርስ እዳ ሊቀነስ የሚገባ መሆኑን ነው፡፡ በተያዘው ጉዳይ አመልካቾች የውርስ እዳ ስላለ ከውርስ ንብረት ገቢ ላይ የሚደርሳቸው ድርሻ ላይ ተቀንሶ ለተጠሪ የሚገባቸው እንዲከፈል መደረግ ሲገባው አልተደረገም በማለት ያቀረቡት ቅሬታ ነጥብ እንደ ተጠሪ አባባል ፍሬ ነገርን የሚመለከት ክርክር ሳይሆን ከላይ እንደተገለጸው የህግ መሠረት ያለው ወይም የህግ ነጥብን የሚመለከት ክርክር ነው፡፡ ተጠሪ ለዚህ ሰበር ያቀረቡት ሶስተኛው የመከራከሪያ ነጥብ በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የካ ምድብ ችሎት በኮ/መ/ቁ. 62253 ላይም ሆነ በውርስ አጣሪው ሪፖርት ላይ ተከራካሪ ወገን ሆነው የቀረቡት ግለሰቦች ብዛት በዚህ የሰበር ክርክር ላይ አመልካቾች እና ተጠሪ ሆነው የቀረቡትን ጨምሮ አንድ አመልካች፣ ሶስት ተጠሪዎች እና አምስት ጣልቃ ገቦች በአጠቃላይ ዘጠኝ ባለጉዳዮች ናቸው፡፡ በውርስ አጣሪ ሪፖርቱ ተራ ቁጥር 7 ላይ ተጠቅሶ በፍርድ ቤትም የፀደቀውን ብር 185,455.25 /አንድ መቶ ሰማኒያ አምስት ሺህ አራት መቶ አምሳ አምስት ብር ከሃያ አምስት ሳንቲም/ በተመለከተ ዘጠኝ ባለጉዳዮች የደረሱበት እና ፍርድ ቤቱም ያፀደቀው ስምምነት በውርስ አጣሪው ሪፖርት ላይ በግልጽ እንደተቀመጠው የውርስ እዳውን እኩል ለመክፋፈል ነው፡፡ በዚሁ መሠረት ብር 185,455.25 እዳ ለዘጠኝ እኩል ሲካፈል ለተጠሪ የሚደርሳቸው ድርሻ ብር 20,606.45 እንጂ ብር 61,818.45 አይደለም የሚል ነው፡፡ ይህንን መከራከሪያ ነጥብ ከውርስ አጣሪው ሪፖርት እና ሪፖርቱ ከፀደቀው ውሳኔ ላይ ተመለክተናል፡፡ የውርስ አጣሪው ንብረትን ሲያጣራ በአመልካችነት፣ በተጠሪነት እና በጣልቃ ገብነት የተመዘገቡት የሟች አቶ ካሳ ደሳለኝ ልጆች ሰባት ሲሆኑ ወ/ሮ እልፍነሽ ሄይ ማለትም የአሁን ተጠሪ አውራሽ እናት እና ወ/ሮ ገላዬ በጋሻው የሟች አቶ ካሳዬ ደሳለኝ ሚስቶች ነበሩ፡፡ ይህን መሠረት በማድረግ የውርስ አጣሪው የውርስ ንብረቱ በአመልካቾች አባት እና በሁለቱ ሚስቶች አስተዋፅኦ የተፈራ በመሆኑ እኩል ሶስት ቦታ እንዲካፈል በሪፖርቱ ተራ ቁጥር 8 ላይ አስተያየቱን የገለጸ መሆኑንና ይህም ፍርድ ቤት ቀርቦ ማጽደቁን ተመልክተናል፡፡ ለክርክሩ ምክንያት የሆነው ንብረት ለሶስት እኩል የሚካፈል ከሆነ የውርስ እዳም ሶስት ቦታ እኩል ከሚካፈል ወጪ ለዘጠኝ የሚካፈልበት ህጋዊ መሠረት የለም፡፡ የአሁን ተጠሪ እንደሚሉትም እዳው ለዘጠኝ እኩል እንዲካፈል ስለመስማማታቸው የውርስ አጣሪው ሪፖርት በፍጹም አያሳይም፡፡ ይልቁንም በውርስ አጣሪው ሪፖርት ላይ እያንዳንዱ ወጪዎች በሙሉ የሟች የውርስ ሀብት ጠብቆ ለማቆየት የተደረገ ስለመሆኑ የመደምደሚያ ሀሳብ ስለተደረሰ ተጠሪዎች የአሁን አመልካቾች/ ወጪ በማለት ያቀረቡት በሙሉ ቢመዘገብ የሥር አመልካችም፣ 1ኛ ጣልቃ ገብ /የአሁን ተጠሪ እናትም/ እንደማይቃወሙ በመግለጽ መስማማታቸውን ነው፡፡ ስለሆነም የአሁን ተጠሪ የውርስ እዳው የሚካፈል ቢሆን እንኳን ለዘጠኝ ሰው ሊካፈል ይገባል በማለት ያቀረቡት ክርክር ተቀባይነት ያለው ሆኖ አላገኘነውም፡፡

የተጠሪ የመጨረሻ መከራከሪያ ነጥብ የውርስ እዳ ስለመኖሩ አመልካቾች በሥር ፍርድ ቤት አንስተው አልተከራከሩም የሚል ነው፡፡ ከሥር ፍርድ ቤት የውሳኔ ግልባጭ እንደተመለከትነው የአሁን

አመልካቾች በመልሳቸው ላይ የወፍጮ ቤት ገቢን በተመለከተ ሟች ከሞቱበት ከ2002 ዓ/ም ጀምሮ ወፍጮ ቤት እስከተከራየበት መስከረም 29 ቀን 2005 ዓ/ም ድረስ ያለው ብር ሲሰባሰብ ቢቆይም ከቤት ኪራይና የወፍጮ ቤት ኪራይ ከሚገኘው ገቢ ውስጥ ለመንግሥት የሚከፈል እዳ፣ የከሳሽ ወላጅ እናት በህይወት እያሉ የወሰዱትን ለቀለብና ለህክምና የወጣ በፍርድ ቤት የተወሰነውን ተቀንሶ ድርሻቸውን ብር 2,865.15 /ሁለት ሺህ ስምንት መቶ ስልሳ አምስት ብር ከአስራ አምስት ሳንቲም/ ስለሚደርሳቸው መውሰድ ይችላሉ በማለት መከራከራቸውን ያሳያል፡፡ በዚህ ክርክር ላይ በግልጽ እንደተገለጸው የውርስ እዳ መኖሩን ነው፡፡ በመሆኑም አመልካቾች የውርስ እዳ እንደነበረ አንስተው አልተከራከሩም፣በዚህ ችሎት አንስተው የተከራከሩት ክርክር ነው በማለት ተጠሪ ያቀረቡት ክርክር በሥር ፍርድ ቤት የውሳኔ ግልባጭ ላይ የተመዘገበውን የአመልካቾችን ክርክር ይዘት ያገናዘበ ሆኖ አላገኘነውም፡፡

ሲጠቃለልም የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የካ ምድብ ችሎት ተጠሪ የጠየቁትን የውርስ ንብረት ገቢን በተመለከተ የውርስ አጣሪውን ሪፖርት መሠረት በማድረግ የወሰነ ሲሆን ለዚህ የሰበር አቤቱታ ምክንያት የሆነውን በውርስ አጣሪው ተጣርቶ ከቀረበ በኋላ በፍርድ ቤቱም የፀደቀውን የውርስ እዳ ሳይቀንስ ከውርስ ንብረት ላይ ከሚገኘው ገቢ ላይ ለተጠሪ ድርሻቸው እንዲከፈል የሰጠው ውሳኔ እንዲሁም ይህ ውሳኔ በይግባኝ የቀረበለት ከፍተኛ ፍርድ ቤትም ስህተቱን ሳያርም ይግባኙን መሠረዙ ሲታይ መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በመሆኑም ቀጥሎ ያለው ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በኮ/መ/ቁ. 111280 በቀን 03/04/09 ዓ/ም የሰጠው ውሳኔ እንዲሁም የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በኮ/መ/ቁ. 182802 በቀን 25/08/2009 ዓ/ም የሰጠው ትዕዛዝ በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ ቁጥር 348 1/ መሠረት ተሻሽሏል፡፡
2. የከሳሽ አውራሽ ወጪ ብር 10,240 /አስር ሺህ ሁለት መቶ አርባ ብር/ ከተጠሪ ድርሻ ላይ እንዲቀነስ ተብሎ የተሰጠው የውሳኔ ክፍል ፀንቷል፡፡
3. በውርስ አጣሪ ሪፖርት በተራ ቁጥር 7 ላይ የተገለጸው የውርስ እዳ ብር 185,455.25 በኮ/መ/ቁ. 62253 ሰኔ 16 ቀን 2006 ዓም የፀደቀው የውርስ ንብረት ክፍፍል ለሶስት እኩል እንዲካፈል በተወሰነው መሠረት እዳውም ለሶስት እኩል ተካፍሎ በሚደርሰው ድርሻ ልክ የአሁን ተጠሪ ብር 61,818.45 /ስልሳ አንድ ሺህ ስምንት መቶ አስራ ስምንት ብር ከአርባ አምስት ሳንቲም/ እዳቸው ነው ተብሎ ተወስኗል፡፡
4. ለተጠሪ ሊከፈላቸው ይገባል ተብሎ ከተወሰነው ብር 175,656.66 /አንድ መቶ ሰባ አምስት ሺህ ስድስት መቶ ሃምሳ ስድስት ብር ከስልሳ ስድስት ሳንቲም/ ላይ ብር 61,818.45 /ስልሳ አንድ ሺህ ስምንት መቶ አስራ ስምንት ብር ከአርባ አምስት ሳንቲም/ ተቀንሶ ብር 113,838.21

/አንድ መቶ አስራ ሶስት ሺህ ስምንት መቶ ሰላሳ ስምንት ብር ከሃያ አንድ ሳንቲም/ በመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ውሳኔ ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ ከሚታሰብ 9% ወለድ ጋር አመልካቾች ለተጠሪ ሊከፍሉ ይገባል ተብሎ ተወስኗል፡፡

5. የዚህን ችሎት ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡
6. የውሳኔው ግልባጭ ለሥር ፍርድ ቤቶች ይድረሳቸው፡፡

መዝገቡ ውሳኔ ስላገኘ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቅ/ሀ

# አሠሪ እና ሠራተኛ

የሰ/መ/ቁ.161880

ታህሳስ 23 ቀን 2011 ዓ.ም

ዳኞች፡-አልማው ወሌ

ሙስጠፋ አህመድ

አብርሃ መሰለ

ፈይሳ ወርቁ

ጳውሎስ ኦርሺሶ

አመልካች፡-አቶ አብርሃም ዴአ ቀረቡ፡፡

ተጠሪ፡-ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ነ/ፈጅ አባተ ደጀኔ ቀረቡ፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ ከስራ የማሰናበት የዲሲፕሊን ውሳኔን በመቃወም የተነሳ የመንግስት አስተዳደር ሰራተኛ ክርክርን የሚመለከት ሲሆን አመልካች የሰበር አቤቱታቸውን ለዚህ ችሎት ያቀረቡት በመስሪያ ቤቱ ዲሲፕሊን ኮሚቴ የቀረበላቸውን የውሰኔ ሀሳብ በመቀበል የተቋሙ የበላይ ኃላፊ በአመልካቹ ላይ ያስተላለፉትን የጥፋተኛነት እና ከስራ የማሰናበት የዲሲፕሊን ውሳኔ በማጽናት የኢ.ፌ.ዲ.ሪ. የፐብሊክ ሠርቪስ እና የሰው ኃብት ልማት ሚኒስቴር አስተዳደር ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 073/2010 በ16/08/2010 ዓ.ም የሰጠው እና በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 157439 በ19/11/2010 ዓ.ም በትዕዘዝ የጸናው ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት ነው፡፡

አመልካቹ በተጠሪው ተቋም የዲሲፕሊን ኮሚቴ ዘንድ ክስ የተመሰረተባቸው በመስሪያ ቤቱ በሙሉ ሰዓት ሰራተኛነት ተቀጥረው በማገልገል ላይ እያሉ ከተጠሪ ተቋም የተሰጣቸው ፈቃድ ሳይኖር በቀን ክፍለ ጊዜ ለአንድ ዓመት ተኩል አካባቢ ያህል ግማሽ ቀን በትምህርት ላይ የነበሩ መሆኑ በመረጋገጡ በፌዴራል መንግስት ሰራተኞች አዋጅ ቁጥር 515/1999 አንቀጽ 68 (1) ስር የተደረነገገውን ተላልፈው ሆን ብለው የአሠራር ሥነ ሥርዓት ወይም የመንግስት ፖሊሲ ባለመከተል በስራ ላይ በደል የማድረስ ጥፋት ፈጽመዋል ተብለው ሲሆን የዲሲፕሊን ኮሚቴው የአመልካቹን መልስ ከተቀበለ እና ጉዳዩን በማስረጃ ካጣራ በኃላ አመልካች ድርጊቱን መፈጸማቸው በማስረጃ የተረጋገጠባቸው መሆኑን ገልጾ

በአዋጁ አንቀጽ 67(1)(ረ) በተመለከተው መሰረት ከስራ እንዲሰናበቱ በማለት የውሳኔ ሀሳብ አቅርቧል፡፡የውሳኔ ሀሳቡ በተቋሙ የበላይ ኃላፊ ተቀባይነት በማግኘቱ አመልካቹ ከስራ እንዲሰናበቱ የተወሰነ ሲሆን አመልካች የሰበር አቤቱታቸውን ለዚህ ችሎት ያቀረቡት የተጠሪ ተቋም ውሳኔ በአስተዳደር ፍርድ ቤት በፍርድ እና በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ደግሞ በትዕዛዝ በመጽናቱ ነው፡፡

አመልካች ለዚህ ችሎት ያቀረቡት በየሰበር አቤቱታ ተመርምሮ ተጠሪው መስሪያ ቤት የአሁኑ አመልካች መስሪያ ቤታችንን ሳያሳውቁ በቀን ክፍለ ጊዜ ትምህርት ተከታትለዋል በሚል ከስራ ኦንዲሰናበቱ የወሰነበትን አግባብነት ከፌዴራል መንግስት ሰራተኞች አዋጅ ቁጥር 515/1999 አንቀጽ 67(1) ስር ከተዘረዘሩት የቅጣት ዓይነቶች አንጻር ተጠሪው ባለበት ለማጣራት ይቻል ዘንድ ጉዳዩ ለሰበር ክርክር እንዲቀርብ በመደረጉ ግራ ቀኙ የጽሁፍ ክርክር ተለዋውጠዋል፡፡የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም ጉዳዩ እልባት ማግኘት የሚገባቸው፡-

1. በአመልካቹ ላይ የተወሰደው የዲሲፕሊን የጥፋተኛነት እና የስንብት ውሳኔ ሊሻር ይገባል ወይስ አይገባም?
2. ለአመልካቹ ውዝፍ ደመወዝ ሊከፈል ይገባል ወይስ አይገባም?

የሚሉ መሆናቸውን በመገንዘብ ጉዳዩን ከእነዚሁ ነጥቦች አንጻር መርምረናል፡፡

የመጀመሪያውን ነጥብ በተመለከተ ተጠሪ ተቋም በዲሲፕሊን ኮሚቴ ተጣርቶ በቀረበለት የውሳኔ ሀሳብ መሰረት በአመልካቹ የዲሲፕሊን የጥፋተኛነት እና ከስራ የማሰናበት ውሳኔ ያስተላለፈው እና በአስተዳደር ፍርድ ቤትም ይኸው ውሳኔ እንደጸና ሲከራከር የነበረው አመልካቹ በተጠሪ መስሪያ ቤት በሙሉ ሰዓት ሰራተኛነት ተቀጥረው በማገልገል ላይ እያሉ ከተጠሪ ተቋም የተሰጣቸው ፈቃድ ሳይኖር በቀን ክፍለ ጊዜ ለአንድ ዓመት ተኩል አካባቢ ያህል ግማሽ ቀን በትምህርት ላይ የነበሩ መሆኑ በመረጋገጡ በፌዴራል መንግስት ሰራተኞች አዋጅ ቁጥር 515/1999 አንቀጽ 68(1) ስር የተደነገገውን ተላልፈው ሆን ብለው የአሠራር ሥነ ሥርዓት ወይም የመንግስት ፖሊሲ ባለመከተል በስራ ላይ በደል የማድረስ ጥፋት መፈጸማቸው በማስረጃ ተረጋግጧል በማለት ነው፡፡ሁለቱ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤቶች የተጠሪ ተቋም የተላለፈውን ውሳኔ ያጸኑትም ይህንኑ ክርክር በመቀበል ነው፡፡ጉዳዩ ለሰበር ክርክር እንዲቀርብ በአጣሪው ችሎት ጭብጥ የተያዘው የቅጣቱን ተመጣጣኝነት እና አግባብነት ለማጣራት በሚል ቢሆንም ተጠሪ ተቋም በሰጠው መልስ ላይ በየደረጃው ያሉ ፍርድ ቤቶች በጉዳዩ ላይ ውሳኔ ያሳረፉ ቢሆንም አመልካች ከስራ እንዲሰናበቱ ከመወሰኑ በፊት የነበራቸውን አፈጻጸም፣ከጥፋታቸው የታረሙ መሆኑን ከግምት በማስገባት እና የቤተሰብ አስተዳዳሪ በመሆናቸው ምክንያት የደረሰባቸውን ችግር ከግምት በማስገባት ወደ ቀድሞ ምድብ ስራቸው ቢመለሱ የማይቃወም መሆኑን ገልጿል፡፡በመሆኑም በአመልካቹ ላይ የተላለፈውን የጥፋተኛነት እና ከስራ የማሰናበት ውሳኔ አግባብነት

በተመለከተ ተጨማሪ ምርመራ ማድረግ ሳያስፈልግ የዲሲፕሊን ጥፋተኛነት ውሳኔውም ሆነ የማሰናበት ውሳኔው ተሽሮ አመልካቹ ወደ ቀድሞ ምድብ ስራቸው እንዲመለሱ ሊወሰን የሚገባው መሆኑን ተገንዝበናል፡፡

ሁለተኛውን ነጥብ በተመለከተ የተጠሪውን መልስ ከተመለከቱ በኃላ ያልተከፈላቸው ደመወዝ እና ጥቅማ ጥቅም ተጠብቆ ወደ ስራቸው እንዲመለሱ እንዲወሰንላቸው አመልካቹ በመልስ መልሳቸው ጠይቀዋል፡፡የመንግስት ሰራተኛው በተከሰሰበት የዲሲፕሊን ጥፋት ምክንያት ከስራ እንዲሰናበት ካልተወሰነበት በስተቀር በእግዱ ወቅት ሳይከፈለው የቀረው ደመወዝ ያለወለድ የሚከፈለው ስለመሆኑ በፌዴራል መንግስት ሰራተኞች አዋጅ ቁጥር 515/1999 አንቀጽ 70 (4)ስር ተመልክቶአል፡፡ጉዳዩ በክርክር ላይ እያለ የመንግስት ሰራተኞች አዋጅ ቁጥር 515/1999 ከ06/04/2010 ዓ.ም. ጀምሮ የተሻረ እና በአዋጅ ቁጥር 1064/2010 የተተካ መሆኑ የሚታወቅ ሲሆን ይህ አዲሱ አዋጅም በዚህ ረገድ የያዘው ድንጋጌ ተመሳሳይ መሆኑን የአዋጁ አንቀጽ 72(4) ድንጋጌ ያመለክታል፡፡ከላይ በመጀመሪያው ጭብጥ ላይ እንደተመለከተው በአመልካቹ ላይ ተላልፎ የነበረው የዲሲፕሊን ጥፋተኛነት እና ከስራ የማሰናበት ውሳኔ የተሻረ እስከሆነ ድረስ በአዋጁ አንቀጽ 70(4) ስር በተመለከተው መሰረት ከስራ እንዲሰናበቱ ከተወሰነበት ጥቅምት 21 ቀን 2010 ዓ.ም ጀምሮ ይህ ውሳኔ እስከተሰጠበት /ወደ ስራ እስከሚመለሱበት/ ቀን ድረስ ያለው ውዝፍ ደመወዝ ያለወለድ ታስቦ ሊከፈላቸው የሚገባ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በመሆኑም የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. በመስሪያ ቤቱ የዲሲፕሊን ኮሚቴ የቀረበላቸውን የውሰኔ ሀሳብ በመቀበል የተቋሙ የበላይ ኃላፊ በአመልካቹ ላይ ያስተላለፉት የጥፋተኛነት እና ከስራ የማሰናበት የዲሲፕሊን ውሳኔ፣ይህንኑ ውሳኔ በማጽናት የኢ.ፌ.ዲ.ሪ. የፐብሊክ ሠርቪስ እና የሰው ኃብት ልማት ሚኒስቴር አስተዳደር ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 073/2010 በ16/08/2010 ዓ.ም የሰጠው እና በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 157439 በ19/11/2010 ዓ.ም በትዕዘዝ የጸናው ውሳኔ በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 348 (1) መሰረት ተሽሯል፡፡
2. አመልካች ወደ ቀድሞ ስራቸው እንዲመለሱ እና ከስራ እንዲሰናበቱ ከተወሰነበት ጥቅምት 21 ቀን 2010 ዓ.ም. ጀምሮ ወደ ስራ እስከሚመለሱበት ቀን ድረስ ያለው ውዝፍ ደመወዝ ያለወለድ ታስቦ እንዲከፈላቸው ወስነናል፡፡
3. የሰበር ክርክሩ ያስከተለውን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡
4. ውሳኔ ያገኘ ስለሆነ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ፍ

የሰ/መ/ቁጥር 173887

ቀን 24/10/2011 ዓ/ም

**ዳኞች ፡-** አልማው ወሌ

ሙስጠፋ አህመድ

አብርሃ መሰለ

ፊይሳ ወርቁ

ጻውሎስ ኦርሺሶ

**አመልካች** ፡- የኢትዮጵያ ጤና መድህን ኤጀንሲ ነ/ፈ ደነቀ ጉታ - ቀረቡ፡፡

**ተጠሪ** ፡- አቶ ዋቅጋሪ ጥላሁን - ቀረቡ፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ለዚህ ሰበር መዝገብ ክርክር መነሻ የሆነው ጉዳይ የቀረበው አመልካች መጋቢት 17 ቀን 2011 ዓ.ም በተፃፈ አቤቱታ የፌደራል ሲቪል ሰርቪስና ሰው ሀብት ልማት ሚኒስቴር አስተዳደር ፍ/ቤት በመ/ቁጥር 039/2011 ታህሳስ 25 ቀን 2011 ዓ/ም በዋለው ችሎት የሰጠው ውሳኔ እና የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 169597 መጋቢት 5 ቀን 2011 ዓ/ም በዋለው ችሎት የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት ቅሬታውን በማቅረቡ ነው፡፡ ቅሬታውም አቤት የተባለበትን ውሣኔ፣ አመልካች የሚቃወምባቸውን ምክንያቶች የሚዘረዝርና በሰበር ሰሚው ችሎት በኩል ሊታይልኝ ይገባል የሚለውን ዳኝነት የሚጠይቅ ሲሆን፣ የስር ፍ/ቤቶች የሲቪል ሰርቪስና ሰው ሀብት ልማት ሚኒስቴር ባጠናው የስራ ምዘናና ደረጃ አወሳሰን ዘዴ የመንግስት ሰራተኞች ድልድል አፈጻጸም መመሪያ መሰረት የአሁን ተጠሪ ባከራከረው የስራ መደብ ተፈላጊውን የትምህርት ዝግጁነት የማያሟላ መሆኑ ታውቆ እያለ የአመልካችን መ/ቤት ሥራና መብት በሚጥስ ሁኔታ ተጠሪ ተወዳድሮ ምደባ እንዲደረግ የሰጡት ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ይታረምልኝ የሚል ነው፡፡

በስር ፍ/ቤት የነበረው ክርክር የጀመረው ከፌደራል ሲቪል ሰርቪስና ሰው ሀብት ልማት ሚኒስቴር አስተዳደር ፍ/ቤት ሲሆን ይግባኝ ባይ የአሁን ተጠሪ ባቀረበው ቅሬታ መልስ ሰጪ የአሁን አመልካች በድልድል (JEG) አፈጻጸም መመሪያ መሰረት ካለአግባብ የተሰጠኝ የስራ ምደባ ተገቢ ባለመሆኑ ጅማ ቅርንጫፍ በሚገኘው አቤቱታና ቅሬታ ማስተናገጃ ቡድን መሪ ደረጃ XIV ስራ መደብ ላይ ተወዳድሬ ምደባ ላገኝ ሲገባ እንዳልወዳደር መደረጉ ካለአግባብ በመሆኑ ይታረምልኝ በማለት ቅሬታውን አቅርቧል፡፡ መ/ሰጪም ይግባኝ ባይ ለጠየቀው

የስራ መደብ የተቀመጠውን የትምህርት ዝግጁነት የማያሟላ በመሆኑ በስራ መደብ ላይ ለውድድር አልቀረበም፡፡ በመሆኑም ቅሬታው ውድቅ ይሁንልኝ በሚል መልስ ሰጥተዋል፡፡ የፌደራል ሲቪል ሰርቪስና ሰው ሀብት ልማት ሚኒስቴር አስተዳደር ፍ/ቤት በመ/ቁጥር 039/2011 ታህሳስ 25 ቀን 2011 ዓ/ም በዋለው ችሎት የሰጠው ውሳኔ ላከራከረው የስራ መደብ አቤቱታና ቅሬታ ማስተናገጃ ቡድን መሪ ደረጃ XIV ስራ መደብ በተዘጋጀው ፎርም 14 የስራ መዘርዝር ላይ በመ/ሰጪ መ/ቤት የድልድል አፈጻጸም (JEG) መመሪያ መሰረት በማድረግ ለስራ መደቡ የተጠየቀው የትምህርት ዝግጁነት፣ በማናጅመንት በህዝብ አስተዳደር፣ በሰው ሀብት ሥራ አመራር እና በሳይኮሎጅ የመጀመሪያ ዲግሪ እና 8 ዓመት የስራ ልምድ ያለው ነው፡፡ ይግባኝ ባይ ያለው የትምህርት  ዝግጅት በኢኮኖሚክስ የመጀመሪያ ዲግሪ ያለው መሆኑ ታውቋል፣ ላከራከረው የስራ መደብ በኢኮኖሚክስ የመጀመሪያ ዲግሪ ያለው ሰው ብቁ መሆን አለመሆኑን አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ሙያዊ አስተያየት እንዲሰጥ ተጠይቆ በስራ መደቡ የተሰጠውን ተግባር ለማከናወን እና ኣላማውን ለማስፈጸም የሚከለክል አለመሆኑን አንዲሁም ከሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን አደረጃጀት ስራ ምዘናና ክፍያ ጥናት ክፍል የተሰጠው ማብራሪያ ላከራከረው የስራ መደብ በተዘጋጀው ፎርም 14 የስራ መዘርዝር ላይ ተጨማሪ የትምህርት ዓይነት የሚያስፈልግ ከሆነም በተቋሙ ጠያቂነት መተካት የሚቻል መሆኑን ገልጾ አቅርቧል፡፡ በመሆኑም በተጠቀሰው የትምህርት ዝግጁነት በኢኮኖሚክስ የመጀመሪያ ዲግሪ ባለመገለጹ በኢኮኖሚክስ የመጀመሪያ ዲግሪ ያለው ሰው ባከራከረው የስራ መደብ ላይ እንዳይወዳደር መደረጉ ለጉዳዩ አግባብ ያለውን ነጥብና የስራ ምዘና ደረጃ አወሳሰን የመንግስት ሰራተኞች የስራ ድልድል መመሪያ መሰረታዊ መርህና ዓላማን ያላገናዘበና የሜሪቱን ስርዓት ያልተከተለ በመሆኑ አልተቀበልነውም፣ የመ/ሰጪ ውሳኔ ተሽሯል፡፡ ባከራከረው የስራ መደብ ላይ እንደገና ይ/ባይንም በማወዳደር ምደባ እንዲደረግ ሲል ወስኗል፡፡ መ/ሰጪ የአሁን አመልካች ለፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የይግባኝ ቅሬታ በመ/ቁጥር 169597 መጋቢት 5 ቀን 2011 ዓ/ም በዋለው ችሎት በሰጠው ትእዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህግ ቁጥር 337 መሰረት አያስቀርብም ሲል ይግባኙን ሰርዞታል፡፡

የአሁን አመልካችም ይህን ውሳኔ በመቃወም ቀርቧል፡፡ መዝገቡም ተመርምሮ በስር ፍ/ቤት የተጠሪ የትምህርት አይነት ኢኮኖሚክስ የመጀመሪያ ደረጃ ዲግሪ ለክርክር ምክንያት በሆነው የስራ መደብ ዝርዝር ውስጥ ባልተካተተበት እና ሲቪል ሰርቪስ ተጠይቆ ተጨማሪ የትምህርት ዓይነት የሚያስፈልግ ከሆነ በተቋሙ ጠያቂነት ማካተት እንደሚቻል ምላሽ በሰጠበት ሁኔታ እና በዚህ አግባብ እንዲካተት ባልተደረገበት የስር ፍ/ቤት የተጠሪ የትምህርት ዝግጅት ለአከራካሪው የስራ መደብ የሚጋብዘው መሆኑን አመልካችን አሳውቆ በ15 ቀን ውስጥ “በጄኢጂ” አፈጻጸም መመሪያ መሰረት በስራ መደቡ ላይ እንዲመደብ የወሰነበትን አግባብ ከፐብሊክ ሰርቪስ እና የሰው ሀብት ልማት ሚ/ር በነጥብ የስራ ምዘናና ደረጃ አወሳሰን ዘዴ የመ/ሠ/ድ/አ/መ/ ግንቦት 2008 ዓ/ም ጋር በማገናዘብ ለመመርመር ሲባል ቀርቧል፡፡ መልስና የመልስ መልስም ተሰጥቶበታል፡፡ ተጠሪ ሚያዝያ 25 ቀን 2011 ዓ/ም በተጻፈ መልስ የስር ፍ/ቤት የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት እንዳልተፈጸመበት በማንሳት ይጽናልኝ ሲል ተከራክሯል፡፡ አመልካችም ግንቦት 14 ቀን 2011 ዓ/ም በተጻፈ የመልስ መልስ አቤቱታቸውን በማጠናከር ተከራክረዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ከላይ የተመለከተውን ሲሆን፣ እኛም የቀረበውን አቤቱታ፣ መልስ እና የመልስ መልሱን እንዲሁም የስር ፍርድ ቤት ውሣኔዎችን እና ከጉዳዩ ጋር አግባብነት ያላቸውን የሕግ ድንጋጌዎችን መሠረት በማድረግ በጉዳዩ ላይ የተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት መኖር አለመኖሩን ከተያዘው ጭብጥ አንጻር መርምረናል፡፡ እንደመረመርነውም በስር ፍ/ቤት በተደረገው ክርክር ባከራከረው የስራ መደብ አቤቱታና ቅሬታ ማስተናገጃ ቡድን መሪ ደረጃ XIV ላይ ተወዳድሮ ለመመደብ የሲቪል ሰርቪስና የሰው ሀብት ልማት ሚኒስቴር አጥንቶ ስራ ላይ ባዋለው፣ በነጥብ የስራ ምዘናና ደረጃ አወሳሰን ዘዴ የመንግስት ሰራተኞች ድልድል አፈጻጸም መመሪያ መሰረት የሚያስፈልገው የትምህርት ዝግጁነት በማናጅመንት በህዝብ አስተዳደር፣ በሰው ሀብት ሥራ አመራር እና በሳይኮሎጅ የመጀመሪያ ዲግሪ ያለው መሆኑ አላከራከረም፡፡ ባከራከረው የስራ መደብ በመመሪያው መሰረት ተወዳድሮ ለመመደብ በተዘጋጀው ፎርም 14 የስራ መዘርዘር ተፈላጊው የትምህርት ዝግጁነት በማናጅመንት በህዝብ አስተዳደር፣ በሰው ሀብት ሥራ አመራር እና በሳይኮሎጅ የትምህርት ዓይነት ብቻ ተጠቅሶ የተቀመጠ ሲሆን ዝርዝሩ ተመሳሳይ ሌላ የትምህርት ዓይነትን በሚጋብዝ መልኩ የተቀመጠ አይደለም፡፡ እነዚህ የተጠቀሱት የትምህርት ዓይነቶች ላከራከረው የስራ መደብ ተፈላጊው የትምህርት ዓይነቶች ሲሆኑ ጥናት ተደርጎ ለቦታው ትክክለኛው የትምህርት ዓይነቶች መሆናቸው ተለይቶ የተወሰዱ ናቸው፡፡ ከሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን አደረጃጀት ስራ ምዘናና ክፍያ ጥናት ክፍልም በፍ/ቤት ጥያቄ የተሰጠው ማብራርያም መ/ቤቱ የአሁን አመልካች የሚጠይቅ ከሆነ በተጨማሪነት ለቦታው የሚያስፈልግ የትምህርት ዓይነት ካለ በጥናት የሚካተት መሆኑን የሚገልጽ ሲሆን የኢኮኖሚክስ የትምህርት ዓይነት ለቦታው በጥናት በወጣው መመሪያ መዘርዝሩ መሰረት ተፈላጊ የትምህርት ዓይነት ነው የሚል መልዕክት የለውም፡፡ ሌላው በፍ/ቤት ጠያቂነት ከአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የቀረበውም ሙያዊ አስተያየት ሲሆን ላከራከረው የስራ መደብ ኢኮኖሚክስ የትምህርት ዓይነት ሊሰራ እንደሚችል ሙያዊ አስተያየት መስጠቱ፣ ጥናት ተደርጎበት ላከራከረው የስራ መደብ ተፈላጊ የትምህርት ዓይነቶች ተብለው ተዘርዝረው የተቀመጠውን መመሪያ በመጣስ ተጨማሪ የትምህርት ዓይነት በፍ/ቤት እንዲጨመርበት ለመወሰን የሚያበቃ ምክንያት አይደለም፡፡ ይህ ሆኖ የአመልካች መ/ቤት የሲቪል ሰርቪስና የሰው ሀብት ልማት ሚኒስቴር ተጠንቶ ስራ ላይ ከዋለው መመሪያ በግልጽ አስቀምጦ ካለው ውጪ ላከራከረው የስራ መደብ ተወዳድሮ ለመመደብ አስፈላጊ የሆነው የትምህርት ዝግጁነት በግልጽ ተዘርዝረው እያሉና ትርጉም ባላስፈለገበትና ባላከራከሩበት ሁኔታ የአሁን አመልካች መ/ቤት ሌላ ተጨማሪ የትምህርት ዓይነት እንደሚያስፈልገው ባልጠየቀበት በግልጽ በመመሪያው ከተዘረዘሩት ውጪ የትምህርት ዓይነት ኢኮኖሚክስ ተካቶ እንዲወዳደር መወሰኑ የፐብሊክ ሰርቪስ እና የሰው ሀብት ሚኒስቴር በነጥብ የስራ ምዘናና ደረጃ አወሳሰን ዘዴ የመንግስት ሰራተኞች ድልድል አፈጻጸም መመሪያ የሚጥስ በመሆኑ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነው ብለናል፡፡

## <u>ው ሳ ኔ</u>

1. የፌደራል ሲቪል ሰርቪስና ሰው ሀብት ልማት ሚኒስቴር አስተዳደር ፍ/ቤት በመ/ቁጥር 039/2011 ታህሳስ 25 ቀን 2011 ዓ/ም በዋለው ችሎት የሰጠው ውሳኔ እና የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ

ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 169597 መጋቢት 5 ቀን 2011 ዓ/ም በዋለው ችሎት የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህግ ቁጥር 348(1) መሰረት ተሽሯል፡፡

2. የአሁን ተጠሪ ላከራከረው የስራ መደብ አቤቱታና ቅሬታ ማስተናገጃ ቡድን መሪ ደረጃ XIV ላይ የአመልካች መ/ቤት ጂማ ቅርንጫፍ ተወዳድሮ ለመመደብ በኢኮኖሚክስ የትምህርት ዓይነት የሲቪል ሰርቪስና የሰው ሀብት ልማት ሚኒስቴር አጥንቶ ስራ ላይ ባዋለው፣ በነጥብ የስራ ምዘናና ደረጃ አወሳሰን ዘዴ የመንግስት ሰራተኞች ድልድል አፈጻጸም መመሪያ መሰረት የትምህትር ዝግጁነት ስለማያሟላ በአመልካች መ/ቤት መከልከሉ ተገቢ ነው ብለናል፡፡

3. በዚህ መዝገብ ክርክር ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሣቸውን ይቻሉ፡፡

4. በዚህ ችሎት 273313 ላይ የተሰጠው የአፈጻጸም እግድ ተነስቷል፡፡ ይጻፍ፡፡

5. የዚህ ውሳኔ ትክክለኛ ግልባጭ ለስር ፍ/ቤት ይድረሳቸው ብለናል፡፡

6. መዝገቡ ተዘግቶ ወደ መ/ቤት ተመልሷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት ፡፡

ፅ/ወ

የሰበር መዝገብ ቁጥር 165886

የካቲት 11 ቀን 2011 ዓ/ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ሙስጠፋ አህመድ

አብርሃ መሰለ

ፈይሳ ወርቁ

ጳውሎስ ኦርሺሶ

አመልካች፡- አቶ አምባቸው ተፈራ - ቀረቡ::

ተጠሪ፡- ልደታ ክ/ከተማ ወረዳ 9 ፐብሊክ ሰርቪስና የሠው ሃብት ልማት - የቀረበ የለም::

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ ከመንግስት ሰራተኛ ቅጥር መሰረዝ ጋር ተያይዞ የተነሳውን ክርክር የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ አመልካች ለአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሃብት ልማት ቢሮ አስተዳደር ፍርድ ቤት ሐምሌ 25 ቀን 2010 ዓ/ም ፅፈው ባቀረቡት አቤቱታ መነሻ ነው፡፡ የአመልካች አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም፡- ከተጠሪ ጋር ለስራ መደቡ በወጣው ማስታወቂያ አግባብ ተወዳድረው ተቀጥረው ከጥር 09 ቀን 2010 ዓ/ም ጀምሮ በመስራት ላይ እያሉ ተጠሪ በቁጥር ል/ክ/ከ/ወ/09/ፐ/ሡ/የሰ/ሃ/ል/148/10 እና በቁጥር ል/ክ/ከ/ወ-9/ፐ/ሰ/የሰ/ሃ/ል/145/10 በቀን 16/11/2010 ዓ/ም በተፃፉ ደብዳቤዎች እና ል/ክ/ከ/ወ-9/ፐ/ሰ/የሰ/ሃ/ል/160/10፣ ል/ክ/ከ/ወ-9/ፐ/ሰ/የሰ/ሃ/ል/159/10 በቀን 25/11/2010 በተጻፈ ደብዳቤ መደቡ ላይ ቅጥሩ የተፈፀመው መስፈርቶችን ሳታሟሉ ነው በሚል ምክንያት ቅጥሩን የሰረዘባቸው መሆኑን ዘርዝረው የስራ ውሉ የተቋረጠው ከሕግ ውጪ ነው ተብሎ እንዲወሰንላቸው ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ የአሁኑ ተጠሪ ለክሱ በሰጠው መልስም ቅጥሩ የተሰረዘው የሚመለከተው አካል ኢንስፔክሽን ስርቶ ቅጥሩ የተፈመፀው ከመመሪያው ውጪ መሆኑን በማረጋገጡ ነው በማለት ተከራክሯል፡፡ ጉዳዩን የተመለከተው የአስተዳደር ፍርድ ቤቱም የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማና ተገቢ ነው ባለው መንገድ ከአጣራ በኂላ አመልካች የተቀጠሩበት መንገድ በሚመለከተው አካል የወጣውን መመሪያ ያልተከተለ መሆኑ በኢንስፔክሽን በመረጋገጡና የሚመለከተው አካል ቅጥሩ እንዲሰረዝ አስተዳደራዊ ውሳኔ በአስተላለፈው አግባብ ተጠሪ ቅጥሩን መሰረዙ ለጉዳዩ ቀጥተኛ

ተፈፃሚነት ካለው ከአዋጅ ቁጥር 56/2010 አንቀፅ 94 ድንጋጌ አንጻር የሚነቀፍበት የሕግ አግባብ የለም በማለት የአመልካችን አቤቱታ ውድቅ አድርጎታል፡፡ በዚህ ውሳኔ የአሁኑ አመልካች ቅር በመሰኘት ይግባኛቸውን ለከተማው አስተዳደር ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ቢያቀርቡም ተቀባይነት አላገኙም፡፡፡ እንዲሁም የሰበር አቤቱታቸውን ለከተማው ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አቅርበውም ተሰርዞባቸዋል፡፡ የአሁኑ የሠበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንን ውሳኔ በመቃወም ነው፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም አመልካች ቀድመው ይሰሩበት የነበረውን ስራ ለቀው ተጠሪ መስሪያ ቤት በአወጣው ማስታወቂያ ተወዳድረው አሸናፊነታቸው ተረጋግጦ ቅጥሩ ከተፈጸመና ከስድስት ወራት በላይ በስራ ላይ ቆይተው የአፈፃጸም ችግር ባላሳዩበት ሁኔታ ቅጥሩ መመሪያውን ያልተከተለና የስራ መደቡ የሚጠይቀውን መመዘኛ አመልካች ሳያሟሉ የተፈፀመ ነው ተብሎ መሰረዙ ያላግባብ ነው የሚል ነው፡፡ የሰበር አቤቱታቸው ተመርምሮም በዚህ ችሎት እንዲታይ የተደረገ ሲሆን ተጠሪ ቀርቦም ግራ ቀኙ በፅሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጎአል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀ ሲሆን ይህ ችሎትም በጉዳዩ ላይ በተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት መፈፀም ያለመፈፀሙን በጭብጥነት ይዞ ጉዳዩን እንደሚከተለው መርምሮታል፡፡ እንደመረመረውም አመልካች ከተጠሪ ጋር ቅጥር የፈፀሙት ተጠሪ በአወጣው ማስታወቂያ መሰረት ተወዳድረው አሸናፊነታቸው በመረጋገጡ ቢሆንም ይህ ሂደት ግን የቅጥር ስርዓት ለመግዛት የወጣው መመሪያን ያልተከተለ መሆኑን በኢንስፔክሽን የተረጋገጠ መሆኑን ተገንዝበናል፡፡ እንዲህ በሆነ ጊዜ ደግሞ ቅጥሩ በማናቸውም ጊዜ የሚሰረዝ መሆኑን በከተማው አስተዳደር ምክር ቤት በወጣውና የመንግስት ሰራተኞችን ጉዳይ በሚገዛው አዋጅ ቁጥር 56/2010 አንቀፅ 94 ስር በግልጽ ተቀምጧል፡፡ አዋጁ የቅጥር ስርዓቱን ባልከተለ መንገድ የተፈፀመ ቅጥር ስህተቱ የቀጣሪው መንግስት መስሪያ ቤት ቢሆን እንኳን ቅጥሩ ፀንቶ የሚቆይበት አግባብ መኖሩን የሚያስገነዝብ አይደለም፡፡ በዚህ መልኩ ያለመደንገጉ ደግሞ ስራንና ሰራተኛን ከማገናኘት በተጨማሪ ከሕግ ውጪ በተለያዩ ምክንያቶች የሚፈጸሙ የመንግስት ሰራተኞች የቅጥር ውሎች ፀንተው እንዳይቆዩ ለማድረግ የታሰበ ነው ተብሎ ይታመናል፡፡ በመሆኑም አመልካች መጀመሪያውን የተቀጠሩት ከህግ ውጪ በወጣው የውድድር መስፈርት መሆኑን እያመኑ ስህተቱ እርሳቸውን እንደማይመለከት በማድረግና ይኼው ተግባር ቀድሞ በነበራቸው የስራ እድል ላይ የፈጠረውን ችግር በማንሳት ለጉዳዩ አዋጅ ቁጥር 56/2010 አንቀፅ 94 ድንጋጌ ተፈፃሚነት ሊኖረው እንደማይገባ አድርገው የሚያቀርቡት ክርክር በሕግ ፊት ተቀባይነት ሊያገኝ የሚችልበት አግባብ ስለሌለ የበታች ፍርድ ቤቶች በጉዳዩ ላይ የሰጡት ውሳኔ በክርክሩ ሂደት የተረጋገጡትን ፍሬ ነገሮችንና ለጉዳዩ አግባብነት ያለውን ህግ መሰረት ያደረገ ነው ከሚባል በስተቀር መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ሁኖ አልተገኘም፡፡ በዚህም መሰረት ተከታዩን ወስነናል፡፡

<u>**ውሳኔ**</u>

1. **በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የፐብሊክ እና የሰው ሃብት ልማት ቢሮ አስተዳደር ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር** 985/2010 **በ**09/01/2011 **ዓ/ም ተሰጥቶ በከተማው ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር** 29035 **በ**28/02/2011 **ዓ/ም፣ በከተማው ይግበኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ አጣሪ ችሎት በመ/ቁጥር** 29323 **በ**13/03/2011 **ዓ/ም የፀናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር** 348(1) **መሰረት ፀንቷል፡፡**
2. **ለክርክሩ የወጣውን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡**

**መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡**

**የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡**

**ሰ/ጥ**

# ንብረት

**የሰ/መ/ቁ** - 164326

**ቀን** - 28/05/2011

**ዳኞች**፡- ተኽሊት ይመሰል

ተፈሪ ገብሩ (ዶ/ር)

ቀነዓ ቂጣታ

ተሾመ ሽፈራዉ

ፀሐይ መንክር

**አመልካች**፡- አቶ አበበ ዘገየ - ቀርበዋል፡፡

**ተጠሪ**፡- አዲስ ከተማ ክ/ከተማ ወ/07 ኮ/የቤቶች ልማት ጽ/ቤት - በሌለበት፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ የመንግስት ቤት ኪራይ መብት በዉርስ ሊተላለፍልኝ ይገባል በሚል የቀረበዉን ክርክር መሠረት በማድረግ የተሰጠ ዉሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ በማለት የቀረበን አቤቱታ የሚመለከት ነዉ፡፡ ክርክሩ የተጀመረዉ በአዲስ አበባ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ሲሆን፣ አመልካች ታህሳስ 20 ቀን 2009 ዓ.ም ባቀረቡት ክስ በአ/ከ/ክ/ከተማ ወረዳ 7 ክልል ዉስጥ የሚገኘዉን የቤ/ቁጥር 634 ተከራይተዉ የነበሩት እናታቸዉ በሞት መለየታቸዉን ተከትሎ ወራሽነት ያረጋገጡ ቢሆንም የሚች ልጅ አይደለህም በሚል ምክንያት ተጠሪ የኪራይ መብቱን በስማቸዉ ለማድረግ ፈቃደኛ አለመሆኑን ጠቅሰዉ ይህኑን ተገዶ እንዲፈጸምለት ይወሰንለት ዘንድ የጠየቀዉን ዳኝነት መሠረት ያደረገ ነዉ፡፡

ተጠሪ ጥሪ ተደርጎለት ባለመቅረቡ ጉዳዩ በሌለበት የታየ ሲሆን፣ ጉዳዩን በመጀመሪያ የተመለከተዉ ፍርድ ቤትም የአመልካችን አቤቱታ ስለጉዳዩ ከሚመለከተዉ መመሪያ እና ከቀረቡት ማስረጃዎች ጋር በማገናዘብ ከመረመረ በኋላ ለክርክሩ መነሻ የሆነዉ ከፊሉ የመኖሪያ ቤት ሲሆን ከፊሉ የንግድ ቤት መሆኑ መረጋገጡን እና ከንግድ ቤቱ ከኋላ በኩል የሚገኙትን ሁለት ክፍል የመኖሪያ ቤቶች የመከራየት መብት እንዲተላለፍላቸዉ፤ በሌላ በኩል አመልካች የሚች የእህት ልጅ በመሆን ከሚች ዘንድ አደጉ እንጂ ከሚች ያልተወለዱ በመሆኑ በመመሪያ ቁጥር 4/2009 አንቀጽ 24 መሠረት የንግድ ቤቱን የመከራየት መብት የሌላቸዉ መሆኑን ገልፆ የንግድ ቤቱን በተመለከተ የቀረበዉን ዳኝነት

ዉድቅ በማድረግ ወስኗል፡፡ አመልካች በዚህ ዉሳኔ ባለመስማማት ለከተማዉ ይግባኝ ሰሚ እና ሰበር ሰሚ ችሎት በቅደም ተከተል ያቀረበዉ አቤቱታም ተቀባይነት አላገኘም፡፡

ይህ የሰበር አቤቱታ የቀረበዉም ይህን ዉሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ሲሆን፣ አመልካች በቀን 06/02/2011 ዓ.ም ተዘጋጅቶ በቀረበ አራት ገጽ የሰበር አቤቱታ አመልካች ከሟች ጋር ለክርክሩ መነሻ በሆነዉ ቤት ዉስጥ ረዘም ላለ ጊዜ መኖራቸዉ ተረጋግጦ እያለ እና በዚህም መሠረት በመመሪያ ቁጥር 4/2009 አንቀጽ 15(1)(ሐ) እና አንቀጽ 24 መሠረት የኪራይ መብቱ ሊተላለፍልኝ እየተገባ የስር ፍርድ ቤት ይህን ጥያቄዬን ዉድቅ በማድረግ የሰጡት ዉሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ታርሞ ይወሰንልኝ በማለት ጠይቀዋል፡፡

አቤቱታዉ ተመርምሮም አመልካች የኑዛዜ ወራሽነትን አረጋግጠዉ ባቀረቡበትና ኑዛዜዉ ባልተሸረበት ሁኔታ የኪራይ መብቱ ሊተላለፍላቸዉ አይገባም በሚል የተሰጠዉን ዉሳኔ አግባብነት ለማጣራት ያስቀርባል በመባሉ፣ ተጠሪ እንዲቀርብ ጥሪ የተደረገለት ቢሆንም ቀርቦ መልስ ባለመስጠቱ መልስ የመስጠት መልስ ታልፏል፡፡

ከስር ጀምሮ የክርክሩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለ መልኩ ሲታይ ከፍ ሲል የተመለከተዉን ሲመስል፣ ይህ ችሎትም አቤቱታዉ ለማስቀረብ የተያዘዉን ጭብጥ ከአመልካች ክርክር እና ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸዉ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መዝገቡን እንደሚከተለዉ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረዉም አመልካች በሟች ዘንድ ያደጉ እና የሟች የኑዛዜ ወራሽ መሆኑ እንዲሁም ለክርክሩ መነሻ የሆነዉ ቤት ከፊሉ የንግድ ቤት መሆኑ በስር ፍርድ ቤት ተረጋግጧል፡፡ አመልካች አጥብቀዉ የሚከራከሩት ከልጅነታቸዉ ጀምሮ በሟች ዘንድ አድገዉ እና የሟች የኑዛዜ ወራሽ በመሆናቸዉ የንግድ ቤቱም እንደሚገባቸዉ በመግለጽ ነዉ፡፡

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የቤቶች ልማትና አስተዳደር ቢሮ የመንግስት ቤቶች አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 4/2009 አንቀጽ 24 የቀበሌ ንግድ ቤትን ለሦስተኛ ወገን ማስተላለፍ ስለሚቻልበት ሁኔታ ይደነግጋል፡፡ በዚህ ድንጋጌ መሠረት ተከራይ በመሞቱ ምክንያት የንግድ ቤቱ ለ3ኛ ወገን ሊተላለፍ የሚችለዉ ለሟች ህጋዊ ባል ወይም ሚስት እንዲሁም ለሟች ህጋዊ ወራሽ ስለመሆኑ በንዑስ አንቀጽ "ሀ" እና "ለ" ስር ተመልክቷል፡፡ አመልካች በሟች ዘንድ ያደጉ ቢሆንም ከሟች የተወለዱ ባለመሆናቸዉ የሟች ህጋዊ ወራሽ ሊሆኑ አይችሉም፡፡ በመሆኑም አመልካች በሟች ዘንድ ማደጋቸዉ እና የሟች የኑዛዜ ወራሽ መሆናቸዉ ለክርክሩ መነሻ በሆነዉ የንግድ ቤት የኪራይ መብት ተጠቃሚ ሊያደርጋቸዉ የሚችል አይደለም፡፡ አመልካች በአቤቱታቸዉ የሚጠቅሱት የመመሪያዉ አንቀጽ 39 ድንጋጌም የቀበሌ የመኖሪያ ቤት ከፊሉን ወደ ንግድ ቤት መቀየር ስለሚቻልበት ሁኔታ የሚደነግግ እንጂ ከፊሉ የንግድ ቤት በሆነዉ ቤት ዉስጥ ከሟች ዘንድ ያደገ ሰዉ በቀጥታ የንግድ ቤቱ የኪራይ

መብት ሊተላለፍለት እንደሚችል ስለማይደነግግ አመልካች በዚህ ረገድ ያቀረቡት አቤቱታም ተቀባይነት ያለዉ አይደለም፡፡

በአጠቃላይ በስር በየደረጃዉ ባሉት ፍርድ ቤቶች የተሰጠዉ ዉሳኔ ይህኑን መመሪያ ገናዘበ ነዉ ከሚባል በስተቀር መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ ስላልተገኘ ተከታዩ ተወስኗል፡፡

## ዉ ሳ ኔ

1. የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 27955 በቀን 26/07/2010 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት፣ የከተማዉ የመጀመሪያ ደረጃ እና ይግባኝ ሰሚ ችሎት በቅደም ተከተል የሰጡትን ዉሳኔ እና ትዕዛዝ፣ በማጽናት የሰጠዉ ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥርዓት ህጉ አንቀጽ 348(1) መሠረት ፀንቷል፡፡
2. በዚህ ችሎት የተደረገዉ ክርክር ያስከተለዉን ወጪ እና ኪሳራ ግራ ቀኝ የየራሳቸዉን ይቻሉ፡፡

   መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ሰ/ጥ

የሰ/መ/ቁጥር 162083

ሚያዚያ 28 ቀን 2011 ዓ.ም

ዳኞች፡- ብርሃኑ አመነው

በዕውቀት በላይ

እንደሻው አዳነ

ሃይሉ ነጋሽ

እትመት አሠፋ

አመልካች ፡- ወ/ሮ አበቡ ተመስገን - ወኪል መኩርያው አዱኛ ቀርበዋል፡፡

ተጠሪዎች፡- 1. አቶ በሬ አባተ

2. አቶ አስችሏል አለም

3. መ/ሬ ማረጌ ፍቃዱ

4. አቶ ማስሬ አለማየሁ

5. አቶ ሰማኝ ባህሩ

(ተጠሪዎች 1–4) ወኪል አስቻለው አልቀረቡም፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍርድ**

ለዚህ ሰበር መነሻ የሆነው የገጠር መሬት ጉዳይ ሲሆን የተጀመረው በአማራ ክልል በዋድላ ወረዳ ፍርድ ቤት ነው፡፡ በዚህ ፍርድ ቤት ተጠሪዎች በአመልካች ላይ ያቀረቡት ክስ ይዘት፡- ከወል ይዞታ ላይ በአዋሳኝ ተለይቶ የይዞታ ማረጋገጫ ተሰጥቶን የያዝነውን ይዞታችንን አመልካች በሀምሌ ወር 2009ዓ.ም አርሳ ሁከት ስለተፈጠረችብን ሁከት ይወገድልን የሚል ነው፡፡

አመልካች በበኩላቸው በሰጡት መልስ ክስ የቀረበብኝ መሬት በ1983 ዓ.ም የተሰጠሁት የይዞታ መሬት ክሱ በይርጋ ይታገዳል፡፡ በይዞታ ማረጋገጫ ደብተሬ ላይ ያስመዘገብኩት ይዞታዬ ስለሆነ የራሴን መሬት ማረሴ ሁከት ሊባል ስለማይችል ክሱ ውድቅ ይደረግልኝ በማለት ተከራክረዋል፡፡

ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው የዋድላ ወረዳ ፍ/ቤት የግራ ቀኙን ምስክሮች ከሰማ እና የወረዳው የመሬት አስተዳደር ጽ/ቤት በባለሙያ አጣርቶ ባቀረበው ሪፖርት ደልዳይ ኮሚቴ አባላት ይዞታው በ1983ዓ.ም ለአመልካች ባለቤት የተደለደለ ይዞታ ነው ሲሉ አብዛኛው የህብረተሰብ ክፍል ደግሞ የወል ይዞታ መሬት የነበረ መሆኑንና ለተጠሪዎች በ2009 ዓ.ም ተሰጥቶ የይዞታ ማረጋገጫ የተሰራላቸው መሆኑን መግለፁን ተከትሎ ማስረጃውን መዝኖ አመልካች  የተጠሪዎችን ይዞታ በማረስ የፈጠሩት ሁከት ይወገድ በማለት ወስኗል፡፡ በዚህ ውሣኔ አመልካች ቅር ተሰኝተው ባቀረቡት ይግባኝ መነሻነት ጉዳዩን የተመለከተው የሰሜን ወሎ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ግራ ቀኙን ካከራከረ በኋላ የስር ፍ/ቤትን ውሣኔ በማጽናት ወስኗል፡፡ በመቀጠል አመልካች ባቀረቡት የሰበር አቤቱታ መነሻነት ጉዳዩን የተመለከተው የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ግራ ቀኙን ካከራከረ በኋላ መርምሮ የስር ፍ/ቤቶችን ውሣኔ በማፅናት ወስኗል፡፡ ይህ የሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚሁ ውሣኔ አመልካች ቅር በመሰኘታቸው ነው፡፡

አመልካች ያቀረቡት የሰበር አቤቱታ ይዘት፡- ተጠሪዎች በተሰጠን የጋራ መሬት ላይ ሁከት ተነሳብን ብለው የሀሰት ማስረጃ ከማቅረብ ውጪ ለብዙ ዓመታት ይዘው ለመቆየታቸው ያቀረቡት ማስረጃ የለም፡፡ አመልካች ከ1983 ዓ.ም ጀምሮ ለ26 ዓመታት በእጄ የቆየውንና የመንግስት ግብር ስገብርበት የነበረ መሆኑን፤የተሰጠኝ የይዞታ ማረጋገጫ ይህንኑ መሬት በውስጡ አቅፎ እንደሚይዝ እየገለፅኩ በስር ፍ/ቤት ለማስረጃዬ ልዩ ትርጉም ተሰጥቶ  ውድቅ መደረጉ ተገቢ አይደለም፡፡ የተጠሪዎች ክስ አቀራረብ መሬቱ በጥቅምት ወር 2009 ዓ.ም በእጃቸው የገባ የጋራ መሬት መሆኑን ይግለጹ እንጂ በእጃቸው ስለመግባቱ ያቀረቡት አስረጂ የለም፡፡ የአመልካች ምስክሮቼ ይዞታው አስቀድሞ ለሟች ባለቤቴ ተደልድሎ እንደነበርና ሲሞት እኔ መጠቀም እንደቀጠልኩ በሚገባ አረጋግጠዋል፡፡ ስለሆነም የስር ፍ/ቤቶች ሁከት ይወገድ ሲሉ የሰጡት ውሣኔ ስህተት በመሆኑ ይሻርልኝ የሚል ነው፡፡

የአመልካች አቤቱታ ተመርምሮ የስር ፍ/ቤት የመሬት አስተዳደር በ19/03/2010 ዓ.ም በተፃፈ ሪፖርት በ1983 ዓ.ም ደልዳይ ኮሚቴ ለተከሳሽ ተሰጠ እንዳሉ የአካባቢው ህብረተሰብ ደግሞ የወል መሬት ነው ብለን ከማለት ያለፈ መሬቱን በትክክል የማን እንደሆነ አጣርቶ ባልገለፀበት ሁኔታ የአመልካች ክርክር ውድቅ የተደረገበት አግባብ ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ ለሰበር ያስቀርባል የተባለ ሲሆን ግራ ቀኙ መልስና የመልስ መልስ በጽሁፍ በማቅረብ ተከራክረዋል፡፡

ተጠሪዎች ያቀረቡት መልስ ይዘት የስር ፍ/ቤት ለቀበሌው አስተዳደር በሰጠው ትእዛዝ መሠረት አስተዳደሩ ለክቶና አጣርቶ በሰጠው መልስ ይዞታው ተጣርቶ የተሰጠን መሆኑን አረጋግጧል፡፡ የወል መሬቱ ጥቅምት 16 ቀን 2009 ዓ.ም መሬቱ ተለክቶ የተሰጠን የወረዳው የመሬት ዴክስ ኃላፊና የቀበሌ መሬት አጠቃቀም የቀበሌው የመሬት መሀንዲስ ዋና ኃላፊ ባሉበት የአካባቢውም ህዝብ እና አመልካች ባሉበት የተሰጠን የልማት መሬት እንጂ ተጠሪዎች ባልነው ብቻ የተሰጠን አይደለም፡፡ በወቅቱ አመልካች አልተቃወመችም፡፡ ስለሆነም የአመልካች አቤቱታ ውድቅ ተደርጐ የስር ፍ/ቤቶች ውሣኔ

ይጽናልኝ የሚል ነው፡፡ አመልካች ባቀረቡት የመልስ መልስ የሰበር አቤቱታቸውን በሚያጠናክር መልኩ ተከራክረዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ከላይ የተመለከተውን የሚመስል ሲሆን ከስር ፍ/ቤት ውሣኔ እና ጉዳዩ ለሰበር ያስቀርባል ተብሎ ከተያዘው ጭብጥ ጋር በማገናዘብ መርምረናል፡፡

መርምረን እንደተረዳነው ግራ ቀኙን ያከራከረው ክርክር ያስነሳው ይዞታ ለተጠሪዎች በ2009 ዓ.ም ከመሰጠቱ በፊት ይዞታው የአመልካች ነው ወይስ የወል ይዞታ የነበረ ነው የሚለው ነው፡፡ የወረዳው ፍ/ቤት ክርክር ያስነሳው ይዞታ ከ2009 ዓ.ም በፊት የወል መሬት ነበር የሚል መደምደሚያ ላይ የደረሰው የወረዳው የመሬት አስተዳደር ጽ/ቤት አጣርቶ በላከው ሪፖርት ላይ በ1983 ዓ.ም መሬቱ ለአመልካች ባለቤት የተደለደለ መሆኑን ቢገልፁም የአካባቢው አብዛኛው ሕብረተሰብ መሬቱ የወል ይዞታ መሆኑን መግለፃቸውንና አመልካች ይዞታውን ተደለደልን የሚሉት በ1983 ዓ.ም ቢሆንም የይዞታ ማረጋገጫ ያወጡት ግንቦት 20 ቀን 2009 ዓ.ም መሆኑ አስቀድሞ የተደለደሉት መሬት መሆኑን አያሳይም በሚል ነው፡፡ አመልካች አጥብቀው የሚከራከሩትም ሆነ ጉዳዩ ለሰበር ያስቀርባል ሲባል የተያዘው ጭብጥ ክርክር ያስነሳው ይዞታ በ1983 ዓ.ም ለአመልካች ባለቤት የተደለደለ መሆኑን የመሬት ደልዳይ ኮሚቴዎች በገለፁበት እና የአካባቢው ሕብረተሰብ የወል መሬት ነው ባሉበት ሁኔታ በአግባቡ ሳይጣራ አመልካች መሬቱን ማረሳቸው የሁከት ተግባር ነው ተብሎ መወሰኑ በአግባቡ ነው ወይስ አይደለም የሚለው ነው፡፡

በመሠረቱ የፌዴራሉ ሕገ-መንግስት አንቀጽ 40/4/ የኢትዮጵያ አረሶ አደሮች መሬት በነፃ የማግኘትና ከመሬታቸው ያለመነቀል መብታቸው የተከበረ መሆኑ በግልጽ ተደንግጐ ይገኛል፡፡ ከዚህ ድንጋጌ ይዘት መገንዘብ የሚቻለው አንድ የገጠር መሬት ባለይዞታ የሆነ አርሶ አደር በሕግ አግባብ ካሳ ተከፍሎት ወይም ምትክ መሬት ተሰጥቶት እንዲለቅ ከሚደረገው በቀር በመንግስት ወይም በአስተዳደር አካላት ፍላጐት ብቻ ከመሬቱ ሊነቀል አይችልም፡፡ መሬቱ ለሌላ አርሶ አደር ከመስጠቱ በፊት አስቀድሞ ባለይዞታ የነበረን ሰው ከመሬቱ መነቀልን እንዳያስከትልበት በተገቢው ጥንቃቄ ተደርጐ መጣራት አለበት፡፡

በተያዘው ጉዳይ በ1983 ዓ.ም የመሬት ደልዳይ ኮሚቴ የነበሩ ሰዎች ክርክር ያስነሳው መሬት ለአመልካች ባለቤት ተደልድሎ ይዘው ሲገለገሉበት የቆዩ መሆናቸውን በማጣራት ሂደት ከመገለፃቸውም በላይ ዘግይቶም ቢሆን ለአመልካች በግንቦት 20 ቀን 2009 ዓ.ም የተዘጋጀ የይዞታ ማረጋገጫ ተሰጥቷቸዋል፡፡ በሌላ በኩል የአካባቢው ሕብረተሰብ ይዞታው ለተጠሪዎች ከመሰጠቱ በፊት ጽ/ቤት የአመልካች ይዞታ ሳይሆን የወል ይዞታ መሆኑ በማጣራት ሂደት ለወረዳው መሬት አስተዳደር ጽ/ቤት ገልፀዋል፡፡ የወረዳው ፍ/ቤት ይህን አከራካሪ የሆነ ጉዳይ ለመለየት ተገቢው ማጣራት ማድረግ ሲገባው ለአመልካች ዘግይቶ የይዞታ ማረጋገጫ መሰጠቱ ላይ በመመስረት ይዞታው የውል ይዞታ ነበር የሚል

ድምዳሜ ላይ ደርሷል፡፡ የይዞታ ማረጋገጫ ዘግይቶ ለአመልካች መሰጠቱ በምንም መልኩ ይዞታው የአመልካች ያልነበረ መሆኑን አያረጋግጥም፡፡ ምክንያቱም አመልካች ይዞታው የተሰጣቸው በ2009 ዓ.ም ነው የሚል ክርክር የላቸውም ይልቁንም ክርክር ያስነሳው ይዞታ ክርክር ያላስነሳውና አሁንም በአመልካች እጅ የሚገኝ ሕጋዊ ይዞታቸው አካል መሆኑን እና የይዞታ ማረጋገጫ ዘግይቶ ቢሰጣቸውም በ1983 ዓ.ም ጀምሮ ይዞታውን ተደልድለው እያረሱ ሲጠቀሙበት ቆይተው በ2009 ዓ.ም ላይ የይዞታ ማረጋገጫ የተሰጣቸው መሆኑን ነው፡፡ ስለዚህ አመልካች ክርክር ያስነሳውን ይዞታ ከ1983 ዓ.ም ጀምሮ ተደልድለው ሲጠቀሙበት የቆዩ ከሆነ ከይዞታቸው ያለመነቀል መብታቸውን ለማስከበር በቅድሚያ ከ2009 ዓ.ም በፊት ክርክር ያስነሳው ይዞታ ለምን አገልግሎት ይውል እንደነበር የይዞታው አዋሳኝ መሬት ወይም ይዞታ ያላቸውን ሰዎች በማጣሪያ ምስክርነት በማስቀረብ ለግራ ቀኙ መስቀለኛ ጥያቄ የመጠየቅ እድል በሚፈጥር መልኩ ማጣራቱ ተገቢ ነበር፡፡

ሲጠቃለል የስር ፍ/ቤቶች ክርክር ያስነሳው ይዞታ በ2009 ዓ.ም ለተጠሪዎች ከመሰጠቱ በፊት ለምን አገልግሎት ይውል እንደነበር ማን ሲገለገልበት እንደነበርና ከመቼ ጀምሮ የሚለውን ክርክር ያስነሳው ይዞታ አዋሳኝ መሬቶችን ባለይዞታዎችን በማጣሪያ ምስክርነት በማስቀረብና በማጣራት ተገቢውን ውሣኔ መስጠት ሲገባው ለአመልካች የይዞታ ማረጋገጫ ደብተር ግንቦት 20 ቀን 2009 ዓ.ም ዘግይቶ መሰጠቱ ላይ በመመስረት ይዞታው የወል ይዞታ ነበር በሚል ድምዳሜ ላይ መድረሱ አመክኗዊ ካለመሆኑም በላይ በአግባቡ ሳይጣራ ውሣኔ መሰጠቱ በፌዴራሉ ሕገ መንግስት አንቀጽ 40/4/ የተመለከተውን የአርሶ አደር ከመሬት ያለመነቀል መብት ሊጥስ የሚችል በመሆኑ በአግባቡ ሳይጣራ የተሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት በመሆኑ ተሽሮ እንደገና ተጣርቶ ሊወሰን የሚገባው ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በመሆኑም የሚከተለው ውሣኔ ሰጥተናል፡፡

**<u>ውሣኔ</u>**

1ኛ. በዋድላ ወረዳ ፍ/ቤት በመ/ቁ 14292 ታህሳስ 24 ቀን 2010 ዓ.ም ተሰጥቶ፤ በሰሜን ወሎ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ. 23130 መጋቢት 14 ቀን 2010 ዓ.ም በተሰጠ ውሣኔ እና በአማራ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁ.03-21728 ሐምሌ 28 ቀን 2010 ዓ.ም በተሰጠ ውሣኔ የፀናው ውሣኔ በፍ/ስ/ስ/ህ/ቁ.348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡

2ኛ. ከላይ በፍርድ ሀተታው በተገለጸው አግባብ ክርክር ያስነሳው ይዞታ በ2009 ዓ.ም ለተጠሪዎች ከመሰጠቱ በፊት የአመልካች የእርሻ መሬት ይዞታ ነው ወይስ የወል ይዞታ ነበር የሚለውን የይዞታውን አዋሳኝ መሬት በባለይዞታዎችን በማጣሪያ ምስክርነት በማስቀረብ እና በማጣራት ወይም በሌላ ተገቢ ነው ባለው መንገድ በማጣራት ተገቢውን ይወስን ዘንድ በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 343/1/ መሰረት ጉዳዩን ለዋድላ ወረዳ ፍ/ቤት መልሰንለታል፡፡ ይፃፍ፡፡

3ኛ. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡ መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መ/ቤት ተመላሽ ብለናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ብ/ግ

የሰ.መ.ቁ 178664

ግንቦት 28 ቀን 2012 ዓ.ም

ዳኞች፡- እትመት አሠፋ

ጳውሎስ ኦርሺሶ

ፀሐይ መንክር

መላኩ ካሣዬ

እስቲበል አንዱዓለም

አመልካች፡- የአቶ ጸጋይ ገ/ሕይወት ሞግዚት አቶ ኪዳነማሪያም ሐይሉ

ተጠሪዎች፡- ወ/ሮ አሚት አጽብሃ

መዝገቡ ለምርመራ የተቀጠረ ነው፡፡ በመሆኑም መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

የሰበር አቤቱታው ሊቀርብ የቻለው አመልካች ሰኔ 05 ቀን 2011 ዓ.ም ጽፈው ባቀረቡት የሰበር አቤቱታ በትግራይ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 107657 መጋቢት 25 ቀን 2011 ዓ.ም ሞግዚት የሆኑለት አቶ ጸጋይ ገ/ሕይወት መሬቱ ከሚገኝበት አካባቢ ውጪ በአማራ ክልል የሚኖር እና የስነ-አእምሮ ችግር እንዳለው መሬቱ ባለበት ማሕበረሰብ ያልተረጋገጠ በመሆኑ ከደንብ ቁጥር 85/2006 አንቀጽ 13/8 ውጭ የስነ አእምሮ ችግር እንዳለው ማስረጃ ቀርቧል በሚል ምክንያት በይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት የተሰጠው ውሳኔ ተገቢ አይደለም በማለት የሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት አቤቱታ በማቅረባቸው ነው፡፡

ጉዳዩ የእርሻ መሬት ክርክርን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው በትግራይ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት በሐድነት ቀበሌ መሬት ዳኝነት ነው፡፡ በመሬት ዳኝነቱ በተደረገው ክርክር የአሁን አመልካች ከሳሽ፤ በዚህ የሰበር ክርክር የሌሉ 4 ግለሰቦች ከ1ኛ እስከ 4ኛ ተከሳሾች፤ የአሁን ተጠሪ ደግሞ 5ኛ ተከሳሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡ የአሁን አመልካች በመሬት ዳኝነቱ ያቀረቡት ክስ ይዘት በአጭሩ፡- ሞግዚት የሆኑላቸው አቶ ጸጋይ ገ/ሕይወት በሐድነት ቀበሌ አዋሳኙ በክሱ የተገለጸውን በእንፎ ጎጥ ውስጥ የሚገኘውን የእርሻ መሬት እና በማይ ዝሕልቶ የሚገኘውን የመስኖ መሬት ቀደም ሲል በወላጅ አባታቸው በሰማዕት ታጋይ ገ/ሕይወት ሀይሉ ስም የነበረ መሆኑን፤ ይህንኑ መሬት ሕጋዊ ወራሽ በመሆን የያዙት መሆኑን፤ ከባድ የስነ አእምሮ ችግር ያለባቸው እና በሞግዚት የሚተዳደሩ መሆኑን፤ ከ1ኛ እስከ 4ኛ ያሉት ተከሳሾች አዋጅ ቁጥር 239/2006 አንቀጽ 11/5(ለ)(ሐ) ድንጋጌን በመጣስ

መሬቱን ለተጠሪ ያደሉባቸው መሆኑን በመግለጽ መሬቱን እንዲያስረክቧቸው ይወሰንላቸው ዘንድ ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡

የስር ከ1ኛ እስከ 4ኛ ያሉት ተከሳሾች በሰጡት መልስ፡- አከራካሪውን መሬት በ1983 ዓ.ም ታጋይ ገ/ሕይወት ሀይሉ የታደሉት መሆኑን እና በሕይወት እስከነበሩበት ጊዜ ድረስ ሲጠቀሙበት የነበረ መሆኑን፤ ከዚህ ዓለም በሞት ከተለዩ በኂላም ለሌላ ሰው ተሸጋሽጎ የነበረ መሆኑን፤ አመልካች በውርስ ይገባኛል ብሎ ተቃውሞ በ2001 ዓ.ም በውርስ ያገኘው መሆኑን፤ መሬቱን እንደወረሰው ወደ ምዕራብ ጎጃም የሄደ መሆኑን፤ በአዋጁ እና በደንቡ መሠረት ተጠንቶ መሬቱ የተሸጋሸገ መሆኑን፤ የአእምሮ ችግር አለኝ የሚለው ሆነ ብሎ በተንኮል መሆኑን፤ ሕመምተኛ መሆኑን የሚያረጋግጥ የሕክምና ማስረጃ ያላቀረበ መሆኑን፤ አመልካች የውክልና መብታቸው ሲዘጋባቸው እንደገና የአእምሮ ችግር አለበት በማለት ክስ የመሰረቱ መሆኑን፤ መሬቱን ሕግ እና መመሪያ ተከትለው ያሸጋሸጉት መሆኑን በመግለጽ የአመልካች ክስ ውድቅ ሊደረግ ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡

የአሁን ተጠሪ በሰጡት መልስ መሬቱ የሰማዕት ታጋይ የነበረ በመሆኑ በሕይወት እስከነበሩበት ጊዜ ድረስ የመጠቀም መብት የነበራቸው መሆኑን፤ አባታቸው በሞት ከተለዩ በኂላ ለሌላ ሰው ሊተላለፍ የማይችል መሆኑን፤ አመልካች በክሱ የገለጸው የሰማእት ታጋይ ተጠቃሚ መሆኑን የሚያሳይ ሳይሆን ወራሽ መሆኑን የሚያሳይ መሆኑን፤ ከ2001 ዓ.ም ጀምሮ ቀበሌውን ለቆ ወደ ሌላ አገር ስለሄደ በቀበሌው እና በጎጥ መሬቱ ተጠንቶ ለ7 ዓመት የጠበቁት መሆኑን ፤ አመልካች ከሁለት ዓመት በላይ አካባቢን ስለለቀቅ በመሬቱ የመጠቀም መብት የሌለው መሆኑን፤ ግለሰቡ ከቀበሌአቸው ለቃቂ መሆናቸው እና በስነ አእምሮ ሕመም ምክንያት እንደተለዩ ተጠንቶ መሬቱ በሽግሽግ እንዲሰጥ የተወሰነ መሆኑን እና ተጠሪ መሬት ስላልነበራቸው የተሰጣቸው መሆኑን፤ አመልካች ከዚህ በፊት በውክልና ክስ አቅርበው ውክልናው ተቀባይነት የለውም ተብሎ ውድቅ ከተደረገባቸው በኂላ የስነ አእምሮ ችግር አለበት በማለት ከሌለ አካባቢ የፍ/ቤት ማስረጃ በማቅርብ ያቀረቡት ክስ ተገቢ ስላልሆነ ወድቅ ሊደረግ ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡

ጉዳዩ የቀረበለት የመሬት ዳኝነት የግራቀኙ ምስክሮች እንዲሰሙ በሰጠው ትዕዛዝ መሠረት የአመልካች ምስክሮቸ አከራከሪው መሬት አመልካች ሞግዚት የሆኑለት አባት የታጋይ ገ/ሕይወት ሀይሉ የነበረ እና ለተጠሪ የተሸጋሸገ መሆኑን በመግለጽ የመሰከሩ ሲሆን የተጠሪ እና የስር ተከሳሾች ምስክሮች ደግሞ አከራካሪው መሬት የታጋይ ገ/ሕይወት ሀይሉ የነበረ መሆኑን እና ልጁ በ2001 ዓ.ም የወረሰው መሆንኑ፤ አመልካች ለሰባት አመታት ወደ አማራ ክልል ስለሄደ በጎጥ ተጠንቶ መሬቱ ለተጠሪ የተሸጋሸገ መሆኑን በመግለጽ መስክረዋል፡፡ የመሬት ዳኝነቱም ምስክሮች የሰጡትን የምስክርነት ቃል መዝኖ ሽግሽጉ ሕጋዊ ስለሆነ አከራካሪው መሬት ለተጠሪ ሊጸናላት ይገባል በማለት ወስኗል፡፡

አመልካች ይህን ውሳኔ በመቃወም ለምስራቅ ዞን ጋንታ አፈሹም ወረዳ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የይግባኝ አቤቱታ አቅርበዋል፡፡ ይግባኙ የቀረበለት ፍ/ቤት ግራቀኙን ካከራከረ በኋላ አመልካች ሞግዚት የሆኑለት አቶ ጸጋይ ገ/ሕይወት የሰማዕት ታጋይ አባቱን መሬት ወርሷል፤ ግለሰቡ የአእምሮ ችግር ያለበት በመሆኑ በሞግዚት ሊተዳደር እንደሚገባ እና የሕግ ክልከላ እንደተደረገበት የሚያሳይ የፍ/ቤት ውሳኔ እንዳቀረበ መዝገቡ ያሳያል፤ የገጠር መሬት ተጠቃሚነት ሊቋረጥ የሚችለው በአዋጅ ቁጥር 239/2006 አንቀጽ 11/1 መሰረት ሆኖ በአዋጁ አንቀጽ 11/2-9 ላይ ካሉት ምክንያቶች ውጪ እንደሆነ በግልጽ ተደንግጓል፤ የአመልካች ክስ በማስረጃ ተደግፎ ቀርቦለት እያለ ሽግሽጉ ሕጋዊ ነው በማለት የተሰጠው ውሳኔ አግባብ አይደለም በማለት የመሬት ዳኝነቱ የሰጠውን ውሳኔ ሽሮ አከራከሪው መሬት ለአቶ ጸጋይ ገ/ሕይወት ሊሆን ይገባል ሲል ወስኗል፡፡

ተጠሪ በበኩላቸው ይህን ውሳኔ በመቃወም ለምስራቅ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አቤቱታ ያቀረቡ ቢሆንም አቤቱታቸው ተቀባይነት አላገኘም፡፡ ተጠሪ በመቀጠል ለክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የሰበር አቤቱታ አቅርበዋል፡፡ የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ግራቀኙን ካከራከረ በኋላ ተጠሪ አከራካሪውን መሬት ወርሶ መሬቱ ባለበት ቦታ ሆኖ በመሬቱ ካልተጠቀመበት እና አካባቢውን ከለቀቀ በደንብ ቁጥር 85/2006 አንቀጽ 15/2 መሠረት መሬቱ ሊሸጋሸግ እንደሚችል ተደንግጓል፡፡ አመልካች መሬቱ ከሚገኝበት አካባቢ ውጪ በአማራ ክልል የሚኖር እና የስነ-አእምሮ ችግር እንዳለው መሬቱ ባለበት ማሕበረሰብ ያልተረጋገጠ በመሆኑ ከደንብ ቁጥር 85/2006 አንቀጽ 13/8 ውጭ የስነ አእምሮ ችግር እንዳለው ማስረጃ ቀርቧል በሚል ምክንያት በይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤቶች የተሰጠው ውሳኔ ተገቢ አይደለም በማለት ሽሮ የመሬት ዳኝነቱ የሰጠውን ውሳኔ አጽንቷል፡፡

የሰበር አቤቱታው የቀረበው ይህን ውሳኔ በመቃወም መሠረታዊ የሕግ ስሕተት ተፈጽሞበታል በሚል ሲሆን ይዘቱም፦ አመልካች ሞግዚት የሆንኩለት አቶ ጸጋይ ገ/ሕይወት የሟች ሰማእት ገ/ሂወት ልጅ እና ሕጋዊ ወራሽ ነው፤ የሰማእት ልጅ በመሆኑም በአዋጅ ቁጥር 239/2006 አንቀጽ 11/5/ሐ መሠረት በሕይወት እስካለ ድረስ የተጠቃሚነት መብት አለው፤ በአዋጁ አንቀጽ 11/5/ሰ ከባድ የአእምሮ ችግር ያለው ከሚኖርበት ቀበሌ ለቆ ሌላ ቀበሌ ወይም ከተማ የሔደ ሰማዕት ታጋይ እና ሚሊሻ መሬት የመጠቀም መብት አለው፤ የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት የአእምሮ ችግር እንዳለበት ለማስረዳት የቀረበውን ከአማራ ክልል ወረዳ ፍ/ቤት የተሠጠውን ማስረጃ በደንብ ቁጥር 85/2006 አንቀጽ 13/8 መሠረት ተቀባይነት የለውም ማለቱ አግባብ አይደለም፤ ደንብ ቁጥር 85/2006 የፍ/ቤት ማስረጃ እንዳይቀርብ ግልጽ ክልከላ ባላስቀመጠበት ሁኔታ የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ማስረጃው ተቀባይነት የለውም ሲል የሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል የሚል ነው፡፡

የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ የአሁን አመልካች የአእምሮ ሕመምተኛ መሆኑ ባለበት አካባቢ ታውቆ በሞግዚት የሚተዳደር ሆኖ ሳለ ክርክር የተነሳበት መሬት ባለበት አካባቢ ባለው

ማሕበረሰብ ስላልተረጋገጠ መሬቱ ለአመልካች አይገባም ተብሎ የመወሰኑን አግባብነት ከክልሉ አዋጅ ቁጥር 239/2006 አንቀጽ 11/5(ሐ) እና ከደንብ ቁጥር 85/2006 ጋር በማገናዘብ ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ በዚህ ችሎት እንዲታይ ተደርጓል፡፡ ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎም ግራቀኙ በጽሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

የተጠሪ መልስ ይዘት በአጭሩ፡- አመልካች አስቀድመው በውክልና ክስ አቅርበው መዝገቡ ከተዘጋባቸው በኋላ የስነ አእምሮ ችግር አለበት በሚል ምክንያት ሞግዚት ነኝ ብለው መቅረባቸው አግባብ አይደለም፤ በክልሉ የገጠር መሬት አስተዳደር እና አጠቃቀም ሕግ መሠረት መሬቱ ከሚገኝበት ማህበረሰብ ወይም በሕክምና ቦርድ ያልተሰጠ ማስረጃ ተቀባይነት የለውም፤ የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ይህንኑ መሠረት በማድረግ የሰጠው ውሳኔ ተገቢ ስለሆነ ሊጸና ይገባል የሚል ነው፡፡ አመልካቾችም የሰበር አቤቱታቸውን በማጠናከር የመልስ መልስ ሰጥተዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ  በአጭሩ ከላይ የተገለጸው ነው፡፡ ይህ ችሎትም በሰበር አጣሪው ችሎት ሊጣራ ይገባዋል ተብሎ የተያዘውን ነጥብ ከግራቀኙ ክርክር፤ ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸው ሕጎች ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው መርምሮታል፡፡

ከክርክሩ ሒደት መገንዘብ የቻልነው አመልካች ሞግዚት የሆኑለት አቶ ጸጋይ ገ/ሕይወት የሚች ታጋይ አባቱ የነበረውን መሬት የወረሰ መሆኑን፤ ግለሰቡ አካባቢውን ከለቀቀ ከሰባት ዓመት በላይ መሆኑን፤ ይህንኑ መሠረት በማድረግ በሚመለከታቸው የአስተዳደር አከላት መሬቱ ተጠንቶ ለተጠሪ የተሸጋሸገ መሆኑን፤ አቶ ጸጋይ ገ/ሕይወት ባለበት የስነ አእምሮ ሕመም ምክንያት የሕግ ክልከላ እና አሳዳሪነትና ሞግዚትነት መስጠት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ ስለራሱ ደህንነት እና ስለንብረቱ አጠባበቅ በፍ/ብ/ሕ/ቁ 359/1 መሠረት አመልካች አሳዳሪ እና ሞግዚት ሆነው የተሾሙለት መሆኑን ነው፡፡
ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተው የወረዳው ፍ/ቤት አመልካች በማስረጃነት ያቀረቡትን የፍ/ቤት ውሳኔ ተቀብሎ አቶ ጸጋይ ገ/ሕይወት የስነ አእምሮ ሕመም ያለበት በመሆኑ አካባቢውን የለቀቀ ቢሆንም የመሬት ተጠቃሚነቱ ሊቋረጥ አይገባም በማለት የወሰነ ሲሆን የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ደግሞ አመልካች መሬቱ ከሚገኝበት አካባቢ ውጪ በአማራ ክልል የሚኖር እና የስነ-አእምሮ ችግር እንዳለው መሬቱ ባለበት ማሕበረሰብ ያልተረጋገጠ በመሆኑ ከደንብ ቁጥር 85/2006 አንቀጽ 13/8 ውጭ የስነ አእምሮ ችግር እንዳለው ማስረጃ ቀርቧል በሚል ምክንያት የመሬቱ ተጠቃሚ ሊሆን አይገባም በማለት ወስኗል፡፡ በመሆኑም በዚህ ችሎት ምላሽ ሊሰጠው የሚገባ የክርክሩ መሠረታዊ ጭብጥ አቶ ጸጋይ ገ/ሕይወት ባለበት የስነ አእምሮ ሕመም ምክንያት የሕግ ክልከላ እና አሳዳሪነትና ሞግዚትነት መስጠት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ ስለራሱ ደህንነት እና ስለንብረቱ አጠባበቅ በፍ/ብ/ሕ/ቁ 359/1 መሠረት አመልካች አሳዳሪ እና ሞግዚት ሆነው ተሹመውለታል በማለት ከአማራ ክልል ዱርቤቴ ወረዳ ፍ/ቤት የተሰጠው የፍ/ቤት ውሳኔ ግለሰቡ የመሬት ተጠቃሚነት መብቱ እንዳይቋረጥ ለማድረግ

የሚያስችል ተቀባይነት ያለው ማስረጃ ነው? ወይስ አይደለም? የሚለው ነው፡፡ በመሆኑም ለዚሁ መሠረታዊ ጭብጥ ምላሽ መስጠት ያስችለን ዘንድ ከክልሉ የገጠር መሬት አስተዳደር እና አጠቃቀም ሕጎች እና አግባብነት ካላቸው የፍትሐብሔር ሕጉ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው መርምረነዋል፡፡

በመሠረቱ መከልከሉ ለጤናው እና ለጥቅሙ የሚያስፈልግ ሆኖ ሲገኝ እንዲሁም ስለዕብዱ ሰው ወራሾች ጥቅም ዕብድ ሰው እንዲከለከል / እንዲጠበቅ / ዳኞች ፍርድ ለመስጠት የሚችሉ መሆኑን፤ ዳኞች የአንዱን ሰው መከልከል ከመፍረዳቸው በፊት ክልከላውን ለማድረግ የግድ አስፈላጊ መሆኑን መረዳት ተረድተው አሳዳሪ እና ሞግዚት የሚሾሙለት መሆኑን እና ይህንኑ ውሳኔ የሚሰጠውም የስነ-አእምሮ ችግር አለበት የተባለው ሰው በሚገኝበት አካባቢ ያለ ፍርድ ቤት ስለመሆኑ ስለ ፍርድ ክልከላ የሚደነግጉት የፍትሐብሔር ሕጉ ቁጥር 351 እና ተከታይ ድንጋጌዎች ይዘት ያስገነዝቡናል፡፡ እነዚህ ድንጋጌዎች የስነ አእምሮ ችግር ያለበትን ሰው እና ወራሾች ጥቅም ለመጠበቅ ሲባል በልዩ ሁኔታ የተደነገጉ ድንጋጌዎች ሲሆኑ ተፈጻሚነታቸውም የፍርድ ክልከላ የተደረገበት ሰው ለጤናው እና ለጥቅሙ አስፈላጊ ሆኖ በተገኘበት ማናቸውም ጉዳይ ላይ ስለመሆኑ ከድንጋጌዎቹ ይዘት መገንዘብ ይቻላል፡፡

በሌላ በኩል የክልሉ የገጠር መሬት አስተዳደር እና አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር 239/2006 አንቀጽ 11/1 በአዋጁ ከተፈቀዱት ምክንያቶች ውጪ ከሚኖርበት ቀበሌ ከሁለት ዓመት በላይ ወደ ሌላ ቀበሌ ወይም ከተማ የለቀቀ የገጠር መሬት ባለይዞታ መሬቱ ተነስቶ የሚተዳደር መሆኑ ይደነግጋል፤ የዚሁ አዋጅ አንቀጽ 11/5 ንዑስ አንቀጽ (ሰ) እና (በ) ከባድ የሥነአእምሮ ችግር፤ የአካል ጉዳት ያለባቸው እና ራሣቸው ለማረስ የማይችሉ ጧሪ እና ተንከባካቢ አጥተው ቀበሌአቸውን የለቀቁ እና በቀበሌው ሥራ አስፈጻሚ የሚታመንባቸው በነበራቸው የገጠር የመሬት ይዞታ ያላቸው የተጠቃሚነት መብት የተጠበቀ እንደሆነ ይደነግጋል፡፡ አዋጁን ለማስፈጸም የወጠው ደንብ ቁጥር 85/2006 አንቀጽ 13/8 ድንጋጌም እነዚህ ግለሰቦች ያላቸው በገጠር መሬት የመጠቀም መብት የሚጠበቅላቸው መሬታቸው በሚገኝበት ቦታ ባለው ሕብረተሰብ የሚታመንበት ከሆነ ወይም እንደአስፈላጊነቱ በሕክምና ቦርድ የተፈረመ ማስረጃ ሲቀርብ ነው በማለት ይደነግጋል፡፡

በክልሉ የገጠር መሬት አስተዳደር እና አጠቃቀም አዋጅም ሆነ አዋጁን ለማስፈጸም በወጣው ደንብ ላይ ከላይ በተገለጸው አግበብ የተደነገገ ቢሆንም የስነ አእምሮ ችግር ያለበት ሰው ለጤናው እና ለጥቅሙ አስፈላጊ ሆኖ በተገኘበት ማናቸውም ጉዳይ ላይ ተፈጻሚ እንዲሆን በማለት በፍትሐብሔር ሕጉ ላይ ስለፍርድ ክልከላ የተደነገጉትን ድንጋጌዎች መሠረት በማድረግ በፍ/ቤት የተሰጠ የፍርድ ክልከላ ውሳኔ ተቀባይነት አይኖረውም ወደሚል ድምዳሜ የሚወስደን አይደለም፡፡ ይልቁንም በክልሉ የገጠር መሬት ሕግ ላይ የስነ አእምሮ ችግር ያለባቸው ሰዎች የመሬት ተጠቃሚነት መብት እንዲቀጥል ለማድረግ የተቀመጡትን መስፈርቶች የስነ አእምሮ ችግር ያለባቸውን ሰዎች ጥቅም ለመጠበቅ ሲባል

በፍትሐብሔር ሕጉ ላይ ስለፍርድ ክልከላ ከተደነገጉት ድንጋጌዎች ጋር ተጣጥምው ሲታዩ አመልካች ሞግዚት እና አስተዳዳሪ የሆኑለት አቶ ጸጋይ ገ/ሕይወት በሚኖርበት አካባቢ ካለው ዱርቤቴ ወረዳ ፍ/ቤት የተሰጠው የፍርድ ክልከላ ውሳኔ የመሬት ተጠቃሚነቱ እንዲቀጥል ለማድረግ የሚያስችል ሕጋዊ እና ተቀባይነት ያለው ማስረጃ መሆኑን የሚያሳይ ነው፡፡

በመሆኑም የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ጉዳዩን በዚህ አግባብ በማየት መወሰን ሲገባው አመልካች ሞግዚት እና አስተዳዳሪ የሆኑለት አቶ ጸጋይ ገ/ሕይወት መሬቱ ከሚገኝበት አካባቢ ውጪ በአማራ ክልል የሚኖር እና የስነ-አእምሮ ችግር እንዳለው መሬቱ ባለበት ማሕበረሰብ ያልተረጋገጠ በመሆኑ ከደንብ ቁጥር 85/2006 አንቀጽ 13/8 ውጭ የስነ አእምሮ ችግር እንዳለው ማስረጃ ቀርቧል በሚል ምክንያት የመሬቱ ተጠቃሚ ሊሆን አይገባም በማለት የሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ ስለሆነም ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

## ውሳኔ

1. በትግራይ ብሔራው ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 107657 መጋቢት 25 ቀን 2011 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 348/1 መሠረት ተሽሯል፡፡
2. የምስራቅ ዞን የጋንታ አፈሹም ወረዳ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 16243 ግንቦት 22 ቀን 2010 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ፣ ይህንኑ ውሳኔ በማጽናት የምስራቅ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 23813 ሠኔ 11 ቀን 2010 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ ጸንቷል፡፡
3. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪ ግራቀኙ የየራሣቸውን ይቻሉ፡፡

- መዝገቡ ውሳኔ ስላገኘ ተዘግቷል፡፡ ይመለስ፡፡

**የሰ/መ/ቁ** - 165314

**ቀን** - 30/09/2011

**ዳኞች**፡- ተኽሊት ይመስል

ተፈሪ ገብሩ (ዶ/ር)

ቀነዓ ቂጣታ

ተሾመ ሽፈራዉ

ፀሐይ መንክር

**አመልካች**፡- የድሬዳዋ አስ/ቀበሌ 03 ጽ/ቤት - አልቀረቡም፡፡

**ተጠሪ**፡- ወ/ሮ ስንዱ ሳልቫቶር - ቀርበዋል፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍርድ**

ለዚህ ፍርድ መነሻ የሆነዉ ጉዳይ የተጀመረዉ በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ሲሆን፤ ተጠሪ ከሳሽ፣ አመልካች ደግሞ ተከሳሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡

የተጠሪ ክስ ይዘትም በአጭሩ፡- በድሬዳዋ ከተማ ቀበሌ 03 ቁጥሩ 315 ሆኖ ንብረትነቱ የሟች እናቴ የወ/ሮ ለምለም ሞገስ የነበረዉ ቤት በአዋጅ ቁጥር 47/67 መሠረት በመንግስት የተወረሰ ሲሆን ቤቱ እንዲመለስላቸዉ ወላጅ እናቴ ከ1977 ዓ.ም ጀምሮ በየደረጃዉ ላሉ ጉዳዩ ለሚመለከታቸዉ አካላት ባመለከቱት መሰረት ተገቢዉ ማጣራት ተደርጎ ተፈቅዶላቸዋል፤ አዋጁን የማስፈጸም ስልጣን ያለዉ የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን መምሪያ በዉሳኔዉ መሠረት ቤቱን ለሟች እንዲያስረክቡ በተዋረድ ለሚገኙት አካላት ትዕዛዝ የሰጠ ቢሆንም ተከሳሽ ቤቱን የያዙትን ሰዎች አስለቅቆ አላስረከበም፣ ይልቁንም ቤቱን አከራይቶ ኪራይ እየሰበሰበ ይገኛል፤ በመሆኑም ተከሳሽ የኪራይ ዉሉን አቋርጦ ቤቱን የያዙትን ሰዎች አስለቅቀዉ እንዲያስረክበኝ ይወሰንልኝ የሚል ነዉ፡፡

አመልካች ለክሱ በሰጠዉ መልስ፡- ቤቱ በአዋጅ ተወርሶ መንግስት የሚያስተዳድረዉ መሆኑን እና የተወረሰዉ ቤት እንዲመለስ ጥያቄ አቅርቦ ቤቱ እንዲመለስለት ስልጣን ባለዉ አካል የተወሰነለት መሆኑን የሚያረጋግጥ ማስረጃ አቅርቦ ባለመብት መሆኑን ሳያረጋግጥ ከሳሽ ያቀረቡት ክስ ተቀባይነት የለዉም በማለት ተከራክሯል፡፡

ጉዳዩን በመጀመሪያ የተመለከተዉ ፍርድ ቤትም ከግራ ቀኝ በዚህ መልኩ የቀረበዉን ክርክር እና የቤቱን ማህደር ጨምሮ ሌሎች የተለያዩ ማስረጃዎችን አስቀርቦ ከመረመረ በኋላ የተጠሪ አዉራሽ ወ/ሮ ለምለም ሞገስ አከራካሪዉ ቤት በአዋጅ ከተወረሰባቸዉ በኋላ በወቅቱ ስልጣን ባለዉ አካል ሌላ ቤት የሌላቸዉ መሆኑ ተረጋግጦ ቤቱ የተመለሰላቸዉ መሆኑ መረጋገጡን ጠቅሶ አመልካች ተከራዮችን አስለቅቆ ቤቱን ለተጠሪ እንዲያስረክብ በማለት ወስኗል፡፡ በአመልካች አቤቱታ መነሻነት ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተዉ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤትም ግራ ቀኝን አስቀርቦ ካከራከረ በኋላ በስር ፍርድ ቤት የተሰጠዉን ዉሳኔ በማጽናት ወስኗል፡፡

ይህ የሰበር አቤቱታ የቀረበዉም ይህኑን ዉሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ሲሆን፣ አመልካች በቀን 05/03/2011 ዓ.ም በተፃፈ አቤቱታ የተወረሱ ቤቶችን የማስመለስ ስልጣን ያለዉ የከተማና ቤቶች ልማት ሚኒስቴር ብቻ እንጂ በስሩ የሚዋቀሩ የአስተዳደር እርከኖች ጭምር አለመሆኑን ሰበር ሰሚ ችሎት ትርጉም የሰጠበት ከመሆኑም በላይ ስልጣን አላቸዉ እንኳ ቢባል የከተማ ልማትና ቤት ሚኒስቴር የሐረርጌ ክ/ሀገር ቅርንጫፍ መስሪያ ቤት የወሰነዉ በተወረሰዉ ቤት ምትክ ተለዋጭ ቤት እንዲሰጥ የሚል ሆኖ እያለ የስር ፍርድ ቤቶች የተወረሰ ቤት ለተጠሪ አዉራሽ እንዲመለስ እንደተወሰነ በማድረግ ተጠሪ ቤቱን እንዲረከቡ የሰጠ ዉሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት መሆኑን ጠቅሶ ታርሞ ይወሰንለት ዘንድ ዳኝነት ጠይቋል፡፡ አቤቱታዉ ተመርምሮም ቤቱ ለተጠሪ አዉራሽ እንዲመለስ ሳይታዘዝ እና ይልቁም የተወሰነዉ ምትክ ቦታ እንዲሰጣቸዉ በሚል በሚመለከተዉ አካል የተሰጠዉን ዉሳኔ የስር ፍርድ ቤቶች የተረጎሙበትን አግባብ ግራ ቀኝ በተገኙበት አከራክሮ ለመወሰን ሲባል ያስቀርባል በመባሉ ተጠሪ በተደረገለት ጥሪ መሠረት በቀን 22/04/2011 ዓ.ም በተፃፈ መልስ በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጠ ዉሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት አይደለም የሚልባቸዉን ምክንያቶች በመዘርዘር ፀንቶ እንዲወሰንለት ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡ አመልካች በቀን 17/05/2011 ዓ.ም የተፃፈ የመልስ መልስ አቅርቧል፡፡

ከስር ጀምሮ የጉዳዩ አመጣጥ እና የግራ ቀኝ ክርክር ይዘት አጠር አጠር ባለ መልኩ ሲታይ ከፍ ሲል የተመለከተዉ ሲሆን፣ ይህ ችሎትም መዝገቡን ለማስቀረብ በአጣሪ ችሎት የተያዘዉን ጭብጥ ከግራ ቀኝ ክርክር እና ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸዉ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መዝገቡን እንደሚከተለዉ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረዉም ለክርክሩ መነሻ የሆነዉ ቤት በአዋጅ ቁጥር 47/67 መሰረት የተወረሰ መሆኑ አላከራከረም፡፡ ተጠሪ በስር ፍርድ ቤት ባቀረቡት ክስ አመልካች ቤቱን እንዲያስረክቧቸዉ ለጠየቁት ዳኝነት መሠረት ያደረጉት ሟች እናታቸዉ ቤቱ እንዲመለስላቸዉ ከ1977 ዓ.ም ጀምሮ ለሚመለከተዉ አካል ባቀረቡት ጥያቄ መሠረት ቤቱ እንዲመለስላቸዉ በስራና ቤቶች ሚኒስቴር የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን መምሪያ እንዲመለስላቸዉ የወሰነ መሆኑን ግን በየደረጃዉ ያሉ የከተማዉ መስተዳደር አካላት ቤቱን ሊያስረክቧቸዉ ፍቃደኛ አለመሆናቸዉን ሲሆን፤ አመልካች በበኩሉ ቤቱ በመንግስት የተወረሰ እና ለሟች እንዲመለስ ስልጣን ባለዉ አካል የተሰጠ ዉሳኔ አለመኖሩን ገልፆ

ይከራከራል፡፡ የስር የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትም ቤቱ ከተወረሰ በኂላ ለተጠሪ አዉራሽ የተወሰነ መሆን አለመሆኑን በጭብጥነት ይዞ ግራ ቀኝ ካቀረቧቸዉ ማስረጃዎች በተጨማሪ ከድሬዳዋ አስተዳደር መሬት ልማት ቢሮ ቤቱን የሚመለከት ማህደር አስቀርቦ የመረመረ መሆኑን ተመልክተናል፡፡ ሚያዝያ 18/1977 ዓ.ም በድሬዳዋ ከተማ አጠቃላይ የከተማ ነዋሪዎች ማህበር ምክር ቤት ለከፍተኛ ከነማ ወኪል የተፃፈዉ ደብዳቤ አከራካሪዉ ቤትና ቦታ በሚች ወ/ሮ ለምለም ሞገስ ተመዝግቦ የሚገኝ መሆኑን፣ ከዚህ ቦታና ቤት በስተቀር በስማቸዉ ተመዝግቦ የሚገኝ በእርሱ ዘንድ አለመኖሩን መግለጹን፤ በመቀጠልም በቁጥር ለተቀፍፍ/2/1/78 በ25/04/1978 ዓ.ም የከተማ ልማትና ቤት ሚኒስቴር የሐረርጌ ክ/ሀገር ቅርንጫፍ መስሪያ ቤት በፃፈዉ ደብዳቤ የተጠሪ አዉራሽ ቤቱ እንዲመለስላቸዉ ማመልከታቸዉን ተከትሎ በቦታዉ ላይ በግንባር ተገኝቶ በመመልከት የቤቱ አሰራር ለድርጅት ሆኖ ያገኘዉ መሆኑን እና ከአዋጁ በፊትም በድርጅትነት ተይዞ የነበረ መሆኑን ማረጋገጡን፣ በዚህም ምክንያት ለክርክሩ መነሻ የሆነዉን ቤት ምክር ቤቱ አጠቃላዩን ተረክቦ ምትክ ቤት ለተጠሪ አዉራሽ እንዲሰጣቸዉ ያስታወቀ መሆኑን የሚያሳይ መሆኑን ከስር ፍርድ ቤት መዝገብ መገንዘብ ይቻላል፡፡ ይህም በግልጽ የሚያሳየዉ የተወረሱ ቤቶችን ለመመለስ በወቅቱ ስልጣን የነበረዉ የከተማ ልማትና ቤት ሚኒስቴር ለክርክሩ መነሻ የሆነዉ ቤት ለሚች ለምለም ሞገስ (ለተጠሪ አዉራሽ) እንዲመለስ አለመወሰኑን፣ ይልቁንም ስልጣን ያለዉ የከተማ አስተዳደር ምትክ ቤት እንዲሰጣቸዉ መወሰኑን ነዉ፡፡ ለሚች ምትክ ቤት ይሰጥ ማለት የተወረሰ ቤት ይመለስ ማለት እንዳልሆነ ግልጽ ነዉ፡፡ ይህ ሆኖ እያለ የስር ሁለቱ ፍርድ ቤቶች የተጠሪ አዉራሽ ሌላ ቤት የሌላቸዉ ስለመሆኑ ተረጋግጦ ለክርክሩ መነሻ የሆነዉ ቤት በወቅቱ ስልጣን በነበረዉ አካል ተመልሶላቸዋል በሚል ድምዳሜ ላይ ሲደርሱ ምንን መነሻ አድርገዉ እንደሆነ ግልጽ አይደለም፡፡

ተከሳሽ በከሳሽ የቀረበበትን ክስ ክዶ የተከራከረ እንደሆነ ከሳሽ ክሱን በማስረጃዎቹ የማስረዳት ግዴታ እንዳለበት በፍ/ብ/ሥ/ሥርዓት ህጉ አንቀጽ 258(1) እና 259(1) ስር ከተመለከቱት ድንጋጌዎች የምንገነዘበዉ ነዉ፡፡ ፍርድ ቤቶች በፍሬ ነገር ደረጃ የሚደርሱበት ድምዳሜ የቀረቡትን ማስረጃዎች መሠረት ሊያደርግ እንደሚገባ እሙን ነዉ፡፡ የዳኝነት አሰጣጥ ስርዓት መሰረታዊ መርህም ነዉ፡፡ ከዚህ አንፃር ሲታይ ለክርክሩ መነሻ የሆነዉ ቤት ከተወረሰ በኂላ ለአዉራሻቸዉ የተመለሰ መሆኑን የሚያሳይ ስልጣን ባለዉ አካል የተወሰነ ዉሳኔ መኖሩን የሚያሳይ ማስረጃ ተጠሪ ባላቀረቡበት ሁኔታ እና ፍርድ ቤት በተጨማሪነት ያቀረባቸዉ ማስረጃዎችም ቤቱ ከተወረሰ በኂላ ለአዉራሻቸዉ የተመለሰ መሆኑን የማያስረዳ ሆኖ እያለ አመልካች ለክርክሩ መነሻ የሆነዉን ቤት ለተጠሪ ሊያስረክብ ይገባል በሚል በስር ሁለቱ ፍርድ ቤቶች የተሰጠ ዉሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በመሆኑም ተከታዩ ተወስኗል፡፡

## ዉሳኔ

1. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 59375 በቀን 22/01/2010 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት፣ እንዲሁም የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 13594 በቀን 05/02/2011 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት የሰጡት ዉሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህጉ አንቀጽ 348(1) መሠረት ተሽረዋል፡፡

2. ምትክ ቤት አስመልክቶ ተጠሪ መብቴን ለማስከበር የሚያቀርበው ጥያቄ ካለ በዚህ ውሳኔ ምክንያት አይታገድም፡፡

3. በዚህ ችሎት የተደረገዉ ክርክር ያስከተለዉን ወጪ እና ኪሳራ ግራ ቀኝ የየራሳቸዉን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

ሳ/ፀ                    የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

የሰበር መዝገብ ቁጥር 169648

ሰኔ 21 ቀን 2011 ዓ/ም

**ዳኞች፡-** ብርሃኑ አመነዉ

በዕዉቀት በላይ

እንዳሻዉ አዳነ

ሃይሉ ነጋሽ

እትመት አሰፋ

**አመልካች:-** አቶ ተሻለ ዋቆ

**ተጠሪዎች፡-**1ኛ. አቶ ንጉሴ ቦንቱ

2ኛ. አቶ አብደላ ቦንቱ

3ኛ. አቶ ነገዎ በዳሶ

4ኛ አቶ አቡ ነገዎ

5ኛ. አቶ ገመቹ ካይሞ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለዉ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ለዚህ ሰበር ክርክር መነሻ የሆነው የገጠር መሬት የመጠቀም መብት የተመለከተ ጉዳይ ሆኖ የተጀመረው በኦሮሚያ ብ/ክ/መ/ በአርሲ ነገሌ ወረዳ ፍርድ ቤት ነው፡፡ በዚሁ ፍ/ቤት የአሁን አመልካች ከሳሽ የአሁን ተጠሪዎች ተከሳሾች ሁነው ሲከራከሩ እንደነበረ መዝገቡ ያመለክታል፡፡ አመልካች በስር ተከሳሾች ላይ ያቀረቡት ክስ ይዘት ባጭሩ፡- ተከሳሾች መብት ሳይኖራቸው በነጌሌ አርሲ ወረዳ በመራሮ ሀዊሎ ቀበሌ የሚገኝ አዋሳኙ በክሳቸው ላይ የተጠቀሰውን ሁለት ሄክታር እርሻ መሬት ተከሳሾች ከ2004 ዓ/ም ጀምረው ያለአግባብ የያዙብኝ ስለሆነ እንዲለቁልኝ ይወሰንልኝ በማለት ክስ አቅርበዋል፡፡ ፍርድ ቤቱ ከመሬት ጋር ተያይዞ የሚቀርብ ማንኛውም ክስና ክርክር በኦሮሚያ ክልላዊ መንግስት የገጠር መሬት አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር 130/1990 ዓንቀፅ 16 መሰረት የመጀመሪያው ክርክር መነሳት ያለበት በቀበሌ ሽማግሌዎች በኩል በመሆኑ አመልካች ካቀረበው ክስ ጋር የቀበሌ ሽማግሌዎች የእርቅ

ውጤት እንዲያቀርብ ትእዛዝ ሰጥቷል፡፡ አመልካችም ጎዱሮ ቀበሌ የእርቅ ውጤት ያቀረበ በመሆኑ እና የከሳሽ መሬት የሚገኝበት በመራሮ ሀዊሎ ቀበሌ በመሆኑ የዚሁ ቀበሌ የሽማግሌዎች የእርቅ ውጤት ማቅረብ ያለበት ሆኖ እያለ ያልቀረበ በመሆኑ አመልካች (ከሳሽ) የመራሮ ሀዊሎ ቀበሌ የሽማግሌዎች የእርቅ ውጤት ሲያቀርብ ክስ የማቅረብ መብት አለው በማለት መዝገቡን ዘግቷል፡፡ አመልካች ውሳኔውን በመቃወም ቅሬታቸውን ለምእራብ አርሲ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት እንዲሁም የሰበር አቤቱታቸው ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት እንደቅደም ተከተላቸው ያቀረቡ ቢሆንም የአመልካች አቤቱታ ባለመቀበል ሰርዘውታል፡፡ ይህ የሰበር አቤቱታ የቀረበው አመልካች በዚሁ ውሳኔ ቅር በመሰኘታቸው ለማስለወጥ ነው፡፡

አመልካች በቀን 20/05/2011 ዓ/ም የተፃፈ 2 ገፅ አቤቱታ አቅርበዋል ፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ ይዘት፡- ተጠሪዎች የአመልካች ይዞታ የሆነውን ሁለት ሄክታር መሬት በህገ ወጥ መንገድ የያዙ መሆናቸው በ3/11/2009 ዓ/ም እና 26/2/2010 ዓ/ም የአካባቢው ሽማግሌዎች ያጣሩልን ሆኖ እያለ የወረዳው ፍርድ ቤት ይህ ይዞታ የማን ነው ግራ ቀኙን ማስረጃ አድምጦ ሳይለይ እና ያቀረብኩት ማስረጃ ሳይሰማ መዝገቡን መዝጋቱ መሰረታዊ የህግ ስህተት ስለሆነ ሊሻር ይገባል የሚል ነው፡፡ አመልካች ያቀረቡት አቤቱታ ተመርምሮ በሰበር ችሎት ሊታይ የሚገባው ሆኖ በመገኘቱ ከ2ኛ ተጠሪ በስተቀር ሌሎቹ ተጠሪዎች ቀርበው በፅሁፍ ተከራክረዋል ፡፡ 2ኛ ተጠሪ መልስ እንዲሰጥ መጥሪያ ተልኮለት መልስ ስላላቀረበ መልስ በፅሁፍ የመስጠት መብቱ የታለፈ ስለመሆኑ መዝገቡ ያመለክታል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ በአጭሩ ከላይ የተገለጸው ነው፡፡ እኛም እንዲጣራ የተያዘውን ነጥብ ከግራ ቀኙ ክርክር፤ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸው ሕጎች ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው መርምረነዋል፡፡ ከመዝገቡ ይዘት መገንዘብ እንደሚቻለዉ አመልካች ክስ ያቀረበዉ ይዞታ መሬቱ ያለአግባብ በተጠሪዎች መያዙን መሰረት በማድረግ ተጠሪዎች ይዞታውን እንዲያስረክቡት ይወሰን ዘንድ ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡ ጉዳዩን በመጀመሪያ ስልጣኑ የተመለከተው የወረዳ ፍርድ ቤት አመልካች ባቀረበው ክስ የተጠቀሰው ይዞታ መሬቱ በሽማግሌ እንዲለቁለት ጠይቆ ተጠሪዎች ፍቃደኞች ባለመሆናቸው ፍርድቤቱ ውሳኔ እንዲሰጥ የጠየቀ ሲሆን ፍርድ ቤቱ የግራ ቀኙን ክርክር በክልሉ ገጠር መሬት አስተዳደር አዋጅ ቁ/130/99 አንቀጽ 16 መሰረት የመጀመሪያው ክርክር መነሳት ያለበት በቀበሌ ሽማግሌዎች በኩል በመሆኑ አመልካች ካቀረበው ክስ ጋር የቀበሌ ሽማግሌዎች የእርቅ ውጤት እንዲያቀርብ ትእዛዝ ተሰጥቶት የጎዱሮ ቀበሌ የእርቅ ውጤት ያቀረበ በመሆኑ እና የከሳሽ መሬት የሚገኘው በመራሮ ሀዊሎ ቀበሌ በመሆኑ የዚሁ ቀበሌ የሽማግሌዎች የእርቅ ውጤት ስላላቀረበ ክሱ ውድቅ በማድረግ ወስኗል፡፡ አሁን መታየት ያለበት ጉዳይ የገጠር መሬት ይገባኛል ክስ ፍርድቤት ለማቅረብ የሽማግሌዎች የእርቅ ውጤት መቅረብ ግዴታ ነው ወይስ አይደለም የሚለውን ከህጉ ጋር መመርመሩ አስፈላጊ ነው፡፡

በመሬት የመጠቀም መብት፣መብቱን በዉርስ የማስተላለፍና መሰል መብቶች አስመልክቶ የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገ መንግስት የተደነገገዉን መርህ ተከትሎ የወጣዉ የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር 456/97 ሲሆን ይህንን አዋጅ ለማስፈጸም ዝርዝር ህጎች የሚወጡት በክልል እንደሚሆን በአዋጁ አንቀጽ 17 ላይ ተመልክቷል፡፡ የገጠር መሬት ይዞታ መብትን በሚመለከት የሚነሱ ክርክሮች በሚመለከታቸዉ ተከራካሪ ወገኖች በዉይይትና በስምምነት እንዲፈታ ጥረት የሚደረግ ስለመሆኑ እና በስምምነት ሊፈታ ካልቻለ በተከራካሪ ወገኖች በተመረጠ ሽምግልና ወይንም በክልሉ የገጠር መሬት አስተዳደር ህግ በተደነገገዉ መሰረት እንደሚወሰን በአዋጁ አንቀጽ 12 ላይ ተደንግጓል፡፡

በአዋጁ አንቀጽ 17 መሰረት በኦሮሚያ ክልል መንግስት ወጥቶ በስራ ላይ ያለዉ የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም አዋጅ ቁ/ 130/99 ከመሬት ይዞታ ጋር በተያያዘ ግጭትና አለመግባባት የሚፈታበትን ስርዓት የሚደነግገዉ አንቀጽ 16 ስር እንደተመለከተዉ በመጀመሪያ በቀበሌ መስተዳደር አማካይነት በሽማግሌ እንዲታይ የሚደረግ ስለመሆኑ እና ይህም የግራ ቀኙን ስምምነት መሰረት የሚያደርግ ስለመሆኑ በዚህም የሽማግሌዎች የእርቅ ዉጤት ያልተስማማ ወገን የሽማግሌዎችን ዉሳኔ በማያያዝ ክሱን ለወረዳ ፍርድ ቤት ማቅረብ እንደሚችል ይደነግጋል፡፡ ከዚህ ድንጋጌ ይዘት መገንዘብ የሚቻለዉ ጉዳዩን በስምምነት ለመጨረስ ጥረት የሚደረገዉ የግራ ቀኙን ስምምነት ሲኖር እንጂ በአስገዳጅነት ሁኔታ የገጠር መሬት ክርክር በቀበሌ አስተዳደር ክስ ወይም አቤቱታ ቀርቦ ዉሳኔ እንደሚሰጥ ቀጥሎም ለመደበኛ ፍርድ ቤት በይግባኝ እንደሚቀርብ ተደርጎ አሳሪ ወይም ጥብቅ የሆነ ስነስርዓት የተዘረጋ አይደለም ፡፡

ስለሆነም በተያዘዉ ጉዳይ ጉዳዩ አስቀድሞ በቀበሌ አስተዳደር አማካይነት ወይም በተከራካሪ ወገኖች ምርጫ በስምምነት በሽማግሌዎች ታይቶ እንዲፈታ ማድረግ ለተከራካሪ ወገኖች የተፈቀደ አማራጭ እንጂ አስገዳጅ ባለመሆኑ ጉዳዩ በመጀመሪያ ስልጣኑ የተመለከተው የአርሲ ነገሌ ወረዳ ፍርድ ቤት አመልካች ካቀረበው ክስ ጋር የሽማግሌዎች የእርቅ ውጤት ባለማቅረቡ አመልካች ያቀረበውን ክስ ውድቅ በማድረግ መወሰኑም ሆነ በየእርከኑ ያሉት የክልሉ የበላይ ፍርድ ቤቶች ሳያርሙ ማፅናታቸው መሰረታዊ የህግ ስህተት በመሆኑ ሊታረም የሚገባ ሆኖ አግኝተናል፡፡በዚሁ አግባብ ተከታዩን ዉሳኔ ሰጥተናል፡፡

## ው ሳ ኔ

1ኛ/ የኦሮሚያ ክልል የአርሲ ነገሌ ወረዳ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 34612 ግንቦት 29 ቀን 2010 ዓ/ም ውሳኔ ተሰጥቶ ፣የምእራብ አርሲ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 38111 ሃምሌ 03 ቀን 2010 ዓ/ም በዋለው ችሎት እንዲሁም የክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 299015 ጥቅምት 22 ቀን 2011 ዓ.ም በዋለው ችሎት እንደቀደም ተከተላቸው የወረዳ ፍርድ ቤት ውሳኔ በማፅናት የሰጡት ውሳኔ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህግ ቁ/348/1/መሰረት ተሽሯል፡፡

2ኛ/ የአርሲ ነገሌ ወረዳ ፍርድ ቤት በስር ከሳሽ (አመልካች) በኩል የቀረበውን ክስ ተቀብሎ ሊያስተናግድ ይገባል ብለናል፡፡ስለሆነም የተዘጋውን መዝገብ ቁጥር 34612 በማንቀሳቀስ በጉዳዩ ላይ አከራክሮ ህጋዊ ውሳኔ እንዲሰጥበት በፍ/ስ/ስ/ሕግ ቁጥር 341(1) መሠረት መልሰንለታል፡፡ ይፃፍ፡፡

3ኛ/ በዚህ ፍ/ቤት ለተደረገዉ ክርክር ወጪና ኪሳራ ግራቀኙ የየራሳቸዉን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

**ብ/ግ**

የሰ/መ/ቁጥር164489

ግንቦት 28 ቀን 2011 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ብርሃኑ አመነዉ

በዕዉቀት በላይ

እንዳሻዉ አዳነ

ሃይሉ ነጋሽ

እትመት አሠፋ

**አመልካች:-** አቶ አባዝናብ አባድማ -ቀረቡ፡፡

**ተጠሪ፡-** አቶ አባተማም ሼህ ሽኩር - ቀረቡ፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለዉ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍ ር ድ**

ለዚህ ሰበር ክርክር መነሻ የሆነው የገጠር መሬት አላባ ጉዳይ ሲሆን የተጀመረው በደቡብ ክልል በየም ልዩ ወረዳ ፍርድ ቤት ነው፡፡ በዚህ ፍርድ ቤት ተጠሪ በአመልካች ላይ ያቀረቡት ክስ ይዘት፡- አመልካች ምንም መብት ሳይኖራቸዉና የግል ንብረቴ የሆነዉን ባሕር ዛፍ ለጥቅም የደረሰዉን በጥቅምት ወር 2009 ዓ.ም መንጥሮ ለ3ኛ ወገን በመሸጥ ላይ ሳሉ በሕግ ያስቆምኳቸዉ ሲሆን ቆርጠዉ የወሰዱትና የሸጡብኝ የባሕር ዛፍ ምርት ጠቅላላ ዋጋዉ ብር 17,400 በመሆኑ ግምቱን ይክፈለኝ የሚል ነዉ፡፡

አመልካች በበኩላቸዉ በሰጡት መልስ ክስ የቀረበብኝ የባህር ዛፍ ንብረት ይዞታ የእኔ እንጂ የተጠሪ ባለመሆኑ ክሱ ዉድቅ ተደርጎ ባቀረብኩት ማስረጃ መሠረት ይወሰንልኝ በማለት ተከራክሯል፡፡

ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተዉ የየም ልዩ ወረዳ ፍ/ቤት ግራ ቀኙን አከራክሮና ማስረጃ ሰምቶ እንዲሁም የባህር ዛፉ ይዞታ የማን ነዉ የሚለዉ በወረዳዉ እርሻና ተፈጥሮ ሀብት ጽ/ቤት በኩል ተጣርቶ እንዲቀርብለት ካደረገ በኃላ ይዞታዉ የአመልካች መሆኑ በመረጋገጡ ቆርጦ የወሰደዉንና የሸጠዉን ባህር ዛፍ ግምት ሊከፍል አይገባም በማለት የተጠሪን ክስ ዉድቅ በማድረግ ወስኗል፡፡ በዚህ ዉሳኔ ቅር ተሰኝተዉ ተጠሪ ባቀረቡት ይግባኝ መነሻነት ጉዳዩን የተመለከተዉ የየም ልዩ ወረዳ ከፍተኛ ፍ/ቤት ግራ ቀኙን ካከራከረ በኂላ መርምሮ በ1997/98 ዓ.ም በነበረዉ የመጀመሪያ ደረጃ የመሬት

ልኬት ወቅት ለተጠሪ ይዞታዉ ተለክቶ የይዞታ ማረጋገጫ ደብተር ተሰጥቶት የነበረ ሆኖ እያለ በ2006 ዓ.ም ልኬት ያለአግባብ በአመልካች መመዝገቡ ስለተረጋገጠ፤ ተጠሪ በባህር ዛፉ በጋራ ለመጠቀም ይዞታዉን ለአመልካች ሰጥቶ ባህር ዛፉን የተከሉ መሆኑን ተጠሪ የተናገረዉን መሠረት በማድረግ የተቆረጠዉ ባህር ዛፍ የጋራ ነዉ በማለት ግምቱ በባለሙያ ተገምቶ እኩል ይከፋፈሉ በማለት የስር ፍ/ቤትን ዉሳኔ በመሻር ወስኗል፡፡ በዚህ ዉሳኔ አመልካች ቅር ተሰኝተዉ ይግባኝ ለክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ቢያቀርቡም ተቀባይነት አላገኘም፡፡ በመቀጠል አመልካች ባቀረቡት የሰበር አቤቱታ መነሻነት ጉዳዩን የተመለከተዉ የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ግራ ቀኙን ካከራከረ በኋላ ዉሳኔዉን በማጽናት ወስኗል፡፡ ይህ የሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚሁ ዉሳኔ አመልካች ቅር በመሰኘታቸዉ ነው፡፡

አመልካች ያቀረቡት የሰበር አቤቱታ ይዘት፡- በክልሉ የገጠር መሬት አዋጅ ቁጥር 110/99 አንቀጽ 12(1) መሰረት ጉዳዩ በቅድሚያ በቀበሌ አስተዳደር የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ኮሚቴ በእርቅና ድርድር ሳይታይ መወሰኑ ተገቢ አይደለም፡፡ በዉሳኔዉ ይዞታዉ የተጠሪ ነዉ ብሎ ሲወሰን ለዉሳኔ መሠረት ያደረገዉ የወረዳዉ የእርሻና ተፈጥሮ ሀብት ልማት ጽ/ቤት በ1997/98 ዓ.ም መሬት ሲለካ ተጠሪ በስሙ ተለክቷል ብሏል፡፡ ነገር ግን በ2006 ዓ.ም የወረዳዉ መሬት በጅፒኤስ ዘመናዊ መሳሪያ ሲለካ በስሜ መለካቱን፤ ሲለካም ተጠሪ ተቃዉሞ እንዳላሰማ በጻፈዉ ደብዳቤ አረጋግጧል፡፡ ይዞታዉ የእኔ መሆኑን የሚያረጋግጥ የይዞታ ማረጋገጫ አቅርቤያለሁ፡፡ ተጠሪ የይዞታ ማረጋገጫ ሰነድ አቅርቦ ባላስረዳበት የተሰጠዉ ዉሳኔ ተገቢ ባለመሆኑ ተሽሮ የወረዳዉ ፍ/ቤት ዉሳኔ ይጽናልኝ ሚል ነዉ፡፡

የአመልካች አቤቱታ ተመርምሮ በዚህ ጉዳይ አከራካሪዉ ይዞታ ለአመልካች ከተሰጠዉ የይዞታ ማረጋገጫ አንጻር ሳይሆን የስር ፍ/ቤቶች በገመድ ልኬትና በኮምፒዩተር መመዝገብና አለመመዝገብ ላይ ትኩረት በማድረግ የተሰጡት ዉሳኔ አግባብነት ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ ለሰበር ያስቀርባል የተባለ ሲሆን ግራ ቀኙ መልስና የመልስ መልስ በጽሁፍ በማቅረብ ተከራክረዋል፡፡

ተጠሪ ያቀረቡት መልስ ይዘት በስር ፍ/ቤት አመልካች በማስረጃነት ያቀረበዉ ሀሰተኛ ማስረጃ ነዉ፡፡ በወረዳ ደረጃ እስከ ቦታዉ ድረስ እንዲጣራ ሲደረግ አመልካች ምንም ዓይነት ይዞታ እንደሌላቸዉ ተገልጿል፡፡ አመልካች ያቀረቡት ማስረጃ በድብቅ በሀሰት ተዘጋጅቶ የተሰጠ ነዉ፡፡ የባህር ዛፍ ንብረቱም በአያቴ ዘመን ተተክሎ አባቴ እየተጠቀመበት ቆይቶ ሲሞት በተራዬ መጠቀም ከጀመርኩ 40 ዓመት ያስቆጠረና የገበርኩበትን አመልካች ሳይመለከታቸዉ ያቀረቡት ክርክር ተገቢነት የሌለዉ በመሆኑ ዉሳኔዉ ስህተት የለዉም ተብሎ ይወሰንልኝ የሚል ነዉ፡፡ አመልካች ባቀረቡት የመልስ መልስ የሰበር አቤቱታቸዉን በሚያጠናክር መልኩ ተከራክረዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ከላይ የተመለከተዉን የሚመስል ሲሆን ከስር ፍ/ቤት ዉሳኔ እና ጉዳዩ ለሰበር ያስቀርባል ተብሎ ከተያዘዉ ጭብጥ ጋር በማገናዘብ መርምረናል፡፡

መርምረን እንደተረዳነዉ በስር ፍ/ቤት ተጠሪ አመልካች ባህር ዛፉን ቆርጦ የሸጠበት መሆኑን ገልጾ ግምቱ ብር 17,400 እንዲከፍለዉ የጠየቀ ሲሆን አመልካች ባህር ዛፉ የራሱ መሆኑን በመግለጽ ግምት

ሊከፍል እንደማይገባ በመግለጽ ተከራክሯል፡፡ ጉዳዩን በቅድሚያ የተመለከተዉ የወረዳ ፍ/ቤት በግራ ቀኙ የቀረቡ ማስረጃዎችንና የወረዳዉ እርሻና የተፈጥሮ ሀብት መሬት አስተዳደር ጽ/ቤት የጻፈዉን ደብዳቤ መርምሮ ይዞታዉ የተጠሪ የነበረ ቢሆንም በ1979 ዓ.ም ጀምሮ ለአመልካች ሰጥቶት አመልካች ባህር ዛፉን በእጁ ተክሎ ሲጠቀምና ግብር ሲከፈል መቆየቱ ተረጋግጧል በሚል የተጠሪን የባህር ዛፍ ግምት ጥያቄ ዉድቅ በማድረግ ወስኗል፡፡ የልዩ ወረዳዉ ከፍተኛ ፍ/ቤት በበኩሉ ምንም እንኳ ይዞታዉ በ2006 ዓ.ም በተደረገዉ ልኬት በአመልካች ተመዝግቦ የተገኘ ቢሆንም በ1997/98 ዓ.ም በተደረገዉ ልኬት በተጠሪ ተመዝግቦ የሚታወቅ መሆኑን በመግለጽ ተጠሪ በሕግ አግባብ ይዞታዉ ሳይወሰድበት ለአመልካች ሊተላለፍ የሚችልበት አግባብ አለመኖሩን እንዲሁም ተጠሪ ለእኩል ለመጠቀም ለአመልካች መስጠቱን በቃል መግለጹን በመጥቀስ ይዞታዉ የተጠሪ ሆኖ አመልካች እኩል ለመጠቀም ባህር ዛፉን ያለማዉ ነዉ በሚል የባህር ዛፉ ግምት በባለሙያ ተገምቶ ግማሹን ለተጠሪ ይክፈል ሲል ወስኗል፡፡ አመልካች አጥብቀዉ የሚከራከሩትም ሆነ አቤቱታዉ ለሰበር ያስቀርባል የተባለዉ አመልካች በ2006 ዓ.ም የይዞታ ማረጋገጫ ተሰጥቶት እያለ በ1997/98 ዓ.ም በነበረዉ ልኬት ወቅት በኮምፒዩተር መመዝገብ አለመመዝገቡ ላይ ትኩረት በመስጠት ይዞታዉ የተጠሪ ነዉ ተብሎ መወሰኑ በአግባቡ ነዉ? ወይስ አይደለም? የሚለዉ ነዉ፡፡

በመሠረቱ በኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 40(3) የገጠርም ሆነ የከተማ መሬትና የተፈጥሮ ሀብት ባለቤትነት መብት የመንግስትና የህዝብ እንደሆነና መሬት የማይሸጥ የማይለወጥ የኢትዮጵያ ብሔሮች ብሔረሰቦችና ህዝቦች የጋራ ሀብት መሆኑ የተመለከተ ሲሆን አርሶ አደሮች በነጻ መሬት የማግኘትና ከመሬታቸዉ ያለመነቀል መብት ያላቸዉ መሆኑ በዚሁ አንቀጽ 4 ተደንግጎ ይገኛል፡፡ በአዋጅ ቁጥር 456/97"ም" ቢሆን ባለይዞታ አርሶ አደር የመሬት ይዞታውን በስጦታም ሆነ በዉርስ ለቤተሰቡ አባል ካልሆነ ወይም በሕግ በተፈቀደዉ መሠረት ለተወሰነ ጊዜ በማከራየት ካልሆነ በቀር ለ3ኛ ወገን ማስተላለፍ አይችልም፡፡ በሌላ በኩል የፍ/ብ/ሕ/ቁ 1175 የባለመሬቱን ወይም የባለይዞታዉን ፈቃድ በመጣስ አትክልቶችን የተከለ ሰዉ በአትክልቶቹ ላይ ምንም ዓይነት መብት እንደሌለዉና ካሳ መጠየቅ እንደማይችል የተመለከተ ሲሆን ቁጥር 1176 ደግሞ በባለመሬቱ ወይም በባለይዞታዉ ፈቃድ አትክልቶቹን የተከለ ሰዉ በስምምነታቸዉ መሠረት ተጠቃሚ እንደሆነና ከስምምነቱ ዉጪ እንዲነሱ ሲደረግ ካሳ እንደሚገባዉ ተደንግጓል፡፡

በተያዘዉ ጉዳይ አመልካች ባህር ዛፍ የተተከለበትን ይዞታ በራሱ ስም በመያዝ እና በ2006 ዓ.ም ይዞታዉን በስሙ ከማስመዝገቡ በፊት ይዞታዉ በ1997/98 ዓ.ም በክልሉ በነበረዉ የመሬት ልኬት ወቅት በተጠሪ ስም ተመዝግቦ የነበረ መሆኑንና ይዞታዉ በአመልካች እጅ ሊገባ የቻለዉ በግራ ቀኙ መካከል ባህር ዛፍ አመልካች እንዲያለማና ለእኩል ለመጠቀም በነበረ ስምምነት መሆኑን ማስረጃ ለመመዘንና ፍሬ ነገርን ለማረጋገጥ ስልጣን የተሰጣቸዉ የስር ፍ/ቤቶች አረጋግጠዋል፡፡ አመልካች በዚህ አግባብ በእጁ የገባዉን ይዞታ በስሙ በድብቅ ማስመዝገቡና የይዞታ ማረጋገጫ ማዉጣቱ፣ ይዞታዉ ከተጠሪ በሕግ አግባብ የተላለፈለት መሆኑ እስካልተረጋገጠ ድረስ ያለአግባብ የይዞታ ማረጋገጫ

ስለተሰጠዉ ብቻ የተጠሪን ባለይዞታነት መብት አያስቀርም፡፡ እንዲሁም በሕግ አግባብ ካልሆነ በቀር የአስተዳደር አካሉ ተጠሪን ከመሬት ይዞታዉ ከሕግ ዉጪ አፈናቀሎ ለአመልካች ይዞታ ማረጋገጫ ሊሰጥ አይችልም፡፡ ስለሆነም የዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት ይህንን በማረጋገጥ አመልካች በተጠሪ ይዞታ ላይ ለእኩል ለመጠቀም በነበረ ስምምነት ያለማዉን ባህር ዛፍ ለብቻዉ ቆርጦ መዉሰዱን በማረጋገጥ የባህር ዛፉ ግምት በባለሙያ ተጣርቶ ግማሹ አመልካች ለተጠሪ ይክፈል በማለት የሰጠዉና በየደረጃዉ የጸናዉ ዉሳኔ የሚነቀፍበት በቂ ምክንያት አልተገኘም፡፡

ሲጠቃለል የየም ልዩ ወረዳ ከፍተኛ ፍ/ቤት ይዞታዉ የተጠሪ ሆኖ በአመልካች እጅ ሊገባና በ2006 ዓ.ም በስሙ አስመዝግቦ ባህር ዛፍ አልምቶ ቆርጦ ሊሸጥ የቻለዉ ከተጠሪ ጋር በነበራቸዉ ስምምነት መሆኑን በማረጋገጥ ያለአግባብ በአመልካች ስም መመዝበሩ የተጠሪን ባለይዞታነት ሊያስቀር አይችልም በማለት ባህር ዛፉ ተገምቶ ግማሹን ግምት ለተጠሪ ይክፈል በማለት የሰጠዉ ዉሳኔ የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገመንግስት አንቀጽ 40(3 እና 4)፣ የፍ/ብ/ሕ/ቁ 1175 እና ተከታዮችን ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ ያገናዘበ በመሆኑ መሰረታዊ የህግ ስህተት ተፈጽሞበታል ለማለት አልተቻለም፡፡ በመሆኑም የሚከተለው ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

## ው ሳ ኔ

1ኛ. በየም ልዩ ወረዳ ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 03255 ሚያዚያ 04 ቀን 2010 ዓ.ም ተሰጥቶ በደቡብ ብ/ብ/ሕ/ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁ 10591 ግንቦት 09 ቀን 2010 ዓ.ም በተሰጠ ትዕዛዝ እና በክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁ 10772 ነሐሴ 25 ቀን 2010 ዓ.ም የተሰጠዉ ዉሳኔ የጸናዉ ዉሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348(1) መሠረት ጸንቷል፡፡

2ኛ. በስር ፍ/ቤት የተጀመረዉ አፈጻጸም ለጊዜዉ ታግዶ እንዲቆይ ታሕሳስ 10 ቀን 2010 ዓ.ም የተሰጠዉ የእግድ ትዕዛዝ ተነስቷል፡፡ ይጻፍ፡፡

3ኛ. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ ግራቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡ መዝገቡ ተዘግቷል፣ ወደ መዝገብ ቤት ተመላሽ ብለናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ሳ/ፀ

ሰ/መ/ቁ. 158527

ጥር 27 ቀን 2011ዓ.ም

ዳኞች ፡-ብርሃኑ አመነዉ

በዕዉቀት በላይ

እንደሻዉ አዳነ

ሃይሉ ነጋሽ

እትመት አሰፋ

አመልካች፡-ወ/ሮ ዘይነባ ሀሰን

ተጠሪ፡-1ኛ/የቢሸፍቱ ከተማ የመሬት ልማትና ማኔጅመንት ኤጀንሲ

2ኛ/የኦሮሚያ የመሬት ልማትና ማ/ኤጀንሲ

መዝገቡ ለምርመራ የተቀጠረ በመሆኑ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍር ድ

በዚህ መዝገብ የቀረበዉ ጉዳይ በሊዝ ዉል የተያዘ መሬት ለማስለቀቅ በተጠሪዎች የተሰጠዉ ማስጠንቀቂያ የሑከት ተግባር ነዉ በሚል አመልካች ተጠሪዎች ላይ ያቀረበችዉ ክስ የሚመለከት ነዉ፡፡የጉዳዩ አመጣጥ ሲታይ በስር ፍርድ ቤት ከሳሽ የአሁኗ አመልካች ስትሆን ተጠሪዎች ተከሳሾች ናቸዉ፡፡የአመልካች ክስ ይዘት ባጭሩ በቢሾፍቱ ከተማ ቀበሌ 01 ክልል ዉስጥ 11,000ካ.ሜ ይዞታ ለሪል እስቴት ግንባታ የሚዉል በ27/05/2000ዓ.ም በተደረገ ዉል የተሰጣት ካርታ ቁ/28/29 የተመዘገበዉን በቦታዉ ላይ ሁለት ትልልቅ መጋዝን ተሰርቶበት እና ሌሎች የግንባታ እቃዎች ያሉበትን ተጠሪዎች በ24/05/08 ዓ.ም እና በ26/05/08ዓ.ም በተጻፈ ደብዳቤ በ7 ቀን ዉስጥ ንብረት በማንሳት ቦታዉን እንዲትለቅ ማስጠንቀቂያ መስጠታቸዉ የሁከት ተግባር ነዉ በሚል ሁከት እንዲወገድ ዳኝነት የጠየቀች ሲሆን በተጠሪዎች በኩል የቀረበዉ መልስ ባጭሩ አመልካች በሊዝ ዉሉ መሰረት ግንባታዉን በ6 ወር ጊዜ ዉስጥ ባለመጀመሯ ተደጋጋሚ ማስጠንቀቂያ ተሰጥቶ ባለመፈጸሚ ካርታዉ እንዲሰረዝና መሬቱ ወደ መንግስት እንዲመለስ የተወሰነ ስለመሆኑና የአመልካች ይዞታ መብት የተቋረጠ ስለሆነ ክስ የማቅረብ መብት እንደሌላት እንዲሁም የተጻፈዉ ደብዳቤም በሊዝ አዋጅና ደንብ እንዲሁም ተዛማጅነት

ባላቸዉ መመሪያዎች መሰረት ለተከሳሾች የተሰጠ ስልጣን መሰረት ስለመሆኑ በመግለጽ ድርጊቱ የሁከት ተግባር ሊባል አይችልም በማለት ተከራክረዋል፡፡

ክርክሩን በመጀመሪያ የዳኝነት ስልጣን የተመለከተዉ የአደአ ወረዳ ፍርድ ቤት የግራቀኙን ክርክርና ማስረጃ ከመረመረ በኋላ በቦታዉ ላይ የተሰራዉ ግንባታ መጠን እና ዋጋ ግምት በባለሙያ ተጣርቶ እንዲቀርብ በማድረግ በቦታዉ ላይ ያለዉ ንብረትና ግንባታ ግምት ብር 2,233,875.00 ስለመሆኑና ይህም ካጠቃላይ ግንባታ አንጻር ሲሰላ 2.92% መሆኑን እንደሚያሳይና አመልካች ግንባታ አልጀመረችም በሚል የተሰጠዉ ማስጠንቀቂያ ተገቢ አይደለም በማለት ሁከት እንዲወገድ ዉሳኔ ሰጥቷል፡፡ስር ተከሳሾች ይህንን ዉሳኔ በመቃወም ለምስራቅ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ አቅርበዉ ፍርድ ቤቱ ግራቀኙን ካከራከረ በኋላ ክስ የቀረበበትን ይዞታ አመልካች በሊዝ ዉል መሰረት ያገኙች ስለመሆኑና በሊዝ ዉሉ መሰረት በጊዜዉ ሳታለማ በመቅረቷበ12/07/2006 ዓ.ም በተደረገ ስብሰባ የሊዝ ዉሉ እንዲቋረጥ እና ይዞታ ማረጋገጫ እንደተሰረዘ ተወስኖ በ23/10/06ዓ.ም እንደተገለጸላት የተረጋገጠ ስለመሆኑና መሬቱ እስካሁን በእጇ ላይ የቆየ ቢሆንም የሊዝ ዉሉ ከተቋረጠ ቀን ጀምሮ መብት የላትም በማለት የፍ/ብ/ህግ አንቀጽ 1140 እና 1149 ላይ የተደነገገዉን ምርኩዝ በማድረግ ስር ተከሳሾች መሬቱን ለማስለቀቅ የሰጡት ማስጠንቀቂያ የሁከት ተግባር ነዉ ሊባል አይገባም በማለት የወረዳ ፍርድ ቤት ዉሳኔ ሽሯል፡፡

አመልካች በበኩሏ በዚህ ዉሳኔ ቅር በመሰኘት ለኦሮሚያ ጠ/ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ይግባኝ ቅሬታ በማቅረቧ ፍርድ ቤቱም የግራቀኙን ክርክር ሰምቶ የሊዝ ዉሉ በ2006 ዓ.ም የተሰረዘ ቢሆንም ይዞታዉ እስከ አሁን ድረስ በአመልካች እጅ ይገኛል በሚል ምክንያት የከፍተኛዉን ፍርድ ቤት ዉሳኔ በመሻር የወረዳ ፍርድ ቤት ዉሳኔ አጽንቷል፡፡ተጠሪዎች ጉዳዩን ለኦሮሚያ ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በአቤቱታ አቅርበዉ ሰበር ችሎቱም ጉዳዩ ላይ ግራቀኙን አከራክሮ በሊዝ አዋጅ ቁ/721/04 አንቀጽ 22 እና በደንብ ቁ/182/08 አንቀጽ 39/7 መሰረት በሊዝ ዉሉ መሰረት ግንባታ ካልተጀመረ አስተዳደሩ መሬቱን መልሶ መዉሰድ እንደሚችል ስለመደንገጉ፣የአመልካች ዉል በ2006 ዓ.ም ከተሰረዘ ጊዜ ጀምሮ ንብረቷን ለማንሳት ከሁለት ዓመት በላይ ጊዜ እንደነበራት እንዲሁም የሊዝ ዉሉ መሰረዝ የለበትም በሚል ለክልሉ ኢንቨስትመንት ቦርድ አቤቱታ አቅርባ ከሆነም እግድ ከመጠየቅ ዉጪ የሊዝ ዉል መብት በተቋረጠበት ሁኔታ የአስተዳደር አካል ተግባር በፍ/ህግ አንቀጽ 1149/3/ መሰረት ተገቢ በመሆኑ ሁከት የለም በማለት ዉሳኔ ሰጥቷል፡፡

ለዚህ ሰበር ችሎት አቤቱታ የቀረበዉ በዚህ ላይ ሲሆን የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ አመልካች በቦታዉ ላይ የሰራችዉ ግንባታ መጠን 2.92% መሆኑ በባለሙያ ተረጋግጦ በቀረበበት ሁኔታ የተጠሪዎች ድርጊት ሁከት አይደለም መባሉ ተገቢ መሆን አለመሆኑን ከፍ/ብ/ህግ አንቀጽ 1149 እና አዋጅ ቁ/721/04 እና ደንብ ቁ/182/08 ጋር በማገናዘብ ለመመርመር በሚል ጭብጥ ተይዞ ተጠሪዎች

መልስ እንዲሰጡ ተደርጓል።በተጠሪዎች በኩል የቀረበዉ መልስ ባጭሩ አመልካች በ29/08/2000ዓ.ም በተደረገ የሊዝ ዉል በከተማዉ ዉስጥ ዋና መንገድ ዳር ላይ 11,000ካ/ሜ መሬት ለሪል እስቴት ግንባታ መዉሰዷን ፤በአዋጅ ቁ/272/94 አንቀጽ 15/1 እንዲሁም 721/04 አንቀጽ 25/1/ሀ እና ደንብ ቁ/119/99 አንቀጽ 10/5 እንዲሁም 155/05ና ማሻሻያዉ ደንብ ቁ/182/08 መሰረት በተገቢዉ ጊዜ ዉስጥ ግንባታ ሳይገነቡና ወደ ስራ ሳይገቡ በመቅረታቸዉ መሬቱ ወደ መሬት ባንክ እንዲመለስ መወሰኑና ንብረታቸዉን እንዲያነሱ ማስጠንቀቂያ መሰጠቱ ህጋዊ ተግባር ስለመሆኑ በመዘርዘር የሑከት ተግባር የለም በማለት ተከራክሯል።አመልካችም አቤቱታዋን በማጠናከር በጠበቃ አማካይነት የመልስ መልስ ሰጥተዋል።

የጉዳዩ አመጣጥና የግራቀኙ ክርክር ከላይ ባጭሩ የተገለጸ ሲሆን እኛም አግባብነት ካለዉ ህግ ጋር በማገነዘብ መርመረናል።መዝገቡን መርምረን እንደተገነዘብነዉ አመልካች በ2000 ዓ.ም በተደረገ የሊዝ ዉል 11,000ካ.ሜ ይዞታ ከከተማዉ አስተዳደር መረከባቸዉና የይዞታ ማረጋገጫ ቁ.28/29 የተሰጣቸዉ ስለመሆኑ አላከራከረም።አመልካች በሊዝ ዉሉና በህጉ መሰረት ግንባታ አላከናወኑም ለተገልጋዩ አላማ አልዋለም በሚል ምክንያት የሊዝ ዉሉ እንዲቋረጥና የይዞታ ማረጋጫ ካርታ እንዲሰረዝ በ12/07/2006ዓ.ም በክልሉ የሚመለከተዉ አካል ዉሳኔ መሰጠቱም በስር ፍርድ ቤት የተረጋገጠ ጉዳይ ነዉ።አመልካችም ይህንን ፍሬነገር በግልጽ ሳይክዱ ለክልሉ ኢንቨስትመንት ቦርድ አቤቱታ አቅርበዉ ዉሳኔ በመጠባበቅ ላይ ስለመሆናቸዉ ገልጸዉ ተከራክረዋል።አቤቱታ የቀረበለት የሊዝ ቦርድ የተለየ ዉሳኔ ስለመስጠቱ አመልካች አስረጂ አላቀረቡም።ስለሆነም የሊዝ ዉሉ እንዲሰረዝ ና ይዞታዉ ወደ መሬት ባንክ እንዲገባ የተሰጠ አስተዳደራዊ ዉሳኔ ተከትሎ የከተማዉ አስተዳደር መሬቱን ለመረከብ ሲል በ24/05/08 እና በ26/05/08ዓ.ም የሰጠዉ ማስጠንቀቂያ የሑከት ተግባር ነዉ ሊባል አይችልም በማለት የኦሮሚያ ክልል ሰበር ችሎት የሰጠዉ ዉሳኔ አግባብነት ከህጉ ጋር በማገንዘብ እንመለከታለን።

በመሠረቱ የአንድ ንብረት ባለይዞታ የሆነ ሰው ይዞታው ለመንጠቅ ወይም በይዞታው ላይ ሁከት ለመፍጠር የሚፈፀምን ማንኛውንም ድርጊት እንዲቆም ወይም ተገቢው መብት እንዲመለስለት ህጉ ከዘረጋቸው መንገዶች አንዱ የይዞታ ክስ /Possessory action/ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ.1149/1/ ድንጋጌ ያስገነዝባል። በዚህ ድንጋጌ መሠረት የሁከት ይወገድልኝ ክስ ለማቅረብ የሚቻለው አቤቱታ አቅራቢው ለክርክሩ መነሻ በሆነው ንብረት ላይ በቀጥታ ወይም በጠባቂ ይዞታ ሲኖረውና ይህንኑ ሁኔታ በኃይል ሲነጠቅ ወይም በይዞታዉ ስር ባለንብረት የመጠቀም መብቱ የሚያዉክ ተግባር ሲፈጸም ነው። እንዲሁም የይዞታ ክስ የሚቀርበው ለክርክሩ መነሻ የሆነውን ንብረት በወቅቱ ለመያዝ ምንም ዓይነት መብት የሌለው ሰው ሲይዝ ስለመሆኑም ተጠቃሹ ድንጋጌ ያሣያል። በመሆኑም የሁከት ይወገድልኝ አቤቱታ አቅራቢ ማረጋገጥ ያለበት ንብረቱ በህግ አግባብ በይዞታው የነበረና የሁከት ድርጊት ፈፃሚው የኃይል ተግባር በመጠቀም ወይም በሚስጢር ንብረቱን የወሰደበት መሆኑን ነው። ይህ የድንጋጌው መንፈስ የሚያስረዳው የሁከት ተግባር የሚኖረው ባለይዞታ የሆነው ሰው በይዞታው ሥር በሚገኘው

ንብረት እንዳይገለገልበት ሌላ ሰው ጣልቃ ገብቶበት መሰናክል ሲፈጥርበት ወይም ረብሻ ሲፈጥርበት መሆኑን ነው፡፡ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1140 እና 1149 ድንጋጌዎች ይዘት የሚያሣዩትም ይህንኑ ነው፡፡ እነዚህ ድንጋጌዎች ከላይ ከተገለፀው ነጥብ በተጨማሪ የሚያስገነዝቡት ነጥብ የሁከት ይወገድልኝ ክስ አቅራቢ የተሻለ የይዞታ መብት ያለው ስለመሆኑ ማረጋገጥ ያለበት መሆኑን ነው፡፡

በዚህ መዝገብ በተያዘዉ ጉዳይ አመልካች ክስ የቀረበበትን ይዞታ የመጠቀም መብት ያገኙት በ29/08/2000 ዓ.ም በተደረገ የሊዝ ዉል መነሻ ስለመሆኑና በሊዝ ዉል እና በህጉ አግባብ ተገቢዉን ግንባታ በወቅቱ አለማፈጸማቸዉ በሚመለከተዉ አካል ተረጋግጦ የሊዝ ዉሉ እንዲሰረዝ እና መሬቱ ወደ መንግስት ይዞታ እንዲመለስ በ12/07/06ዓ.ም በሚመለከተዉ አካል ዉሳኔ ተሰጥቶ ያደረ ስለመሆኑ በስር ፍርድ ቤቶች የተረጋገጠ ፍሬነገር ጉዳይ ነዉ፡፡በስራ ላይ ባለዉ የከተማ ቦታን በሊዝ ስለመያዝ የሚደነግገዉ አዋጅ ቁ/721/04 አንቀጽ 25 መሰረት የሊዝ ዉል ስለምቋረጥበትና የሚያስከትለዉ ዉጤት በዝርዝር ተመልክቷል፡፡ይህንን አስተዳደራዊ ዉሳኔ የሚቃወም ወገን ይግባኝ ስለሚያቀርብበት ስርዓትም በአዋጁ ላይ ተደንግጓል፡፡አመልካች የሊዝ ዉሉ መሰረዙን በመቃወም ለሚመለከተዉ አካል አቤቱታ አቅርበዉ ምላሽ በመጠባበቅ ላይ ስለመሆናቸዉ ከመግለጽ ዉጪ የተሰጠ አስተዳደራዊ ዉሳኔ ስለመኖሩ ያቀረቡት ማስረጃ የለም፡፡ስለሆነም የሊዝ ዉሉ እንዲቋረጥ በ12/07/2006 ዓ.ም የተሰጠዉ አስተዳደራዊ ዉሳኔ ባልተሻረበት ሁኔታ ተጠሪዎች መሬቱን ለመረከብ እንዲቻላቸዉ አመልካቿ ንብረታቸዉን እንዲያነሱ ማስጠንቀቂያ መስጠታቸዉ በሊዝ አዋጁና ይህን ተከትሎ የወጡትን ማስፈጸሚያ ደንብና መመሪያ የተከተለ እና ድርጊታቸዉም በህግ የተሰጠ ስልጣን መሰረት ያደረገ ስለመሆኑ የተረጋገጠ ከመሆኑ አኳያ በፍ/ብ ህግ አንቀጽ 1149/3/ ጋር ሲታይ የሁከት ተግባር ነዉ ሊባል የማይቻል መሆኑን ያሥገነዝባል፡፡ ስለሆነም የክልሉ ሰበር ችሎት ዉሳኔ ላይ መሰረታዊ የህግ ስህተት ተፈጽሟል የሚባልበት ህጋዊ ምክንያት አልተገኘም፡፡

**ዉሳኔ**

1ኛ/ የኦሮሚያ ክልል ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ/270624 በ29/08/2010 ዓ.ም የሰተዉ ዉሳኔ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህግ ቁ/348/1/መሰረት ጸንቷል፡፡

2ኛ/ በዚህ መዝገብ ላይ በ06/10/10 ዓ.ም ተሰጥቶ የነበረዉ የእግድ ትእዛዝ ተነስተዋል፡፡ይጻፍ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ም/ቶ

ሰበር መ/ቁ161676

የካቲት 25 ቀን 2011ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ብርሃኑ አመነዉ

በዕዉቀት በላይ

እንደሻዉ አዳነ

ሃይሉ ነጋሽ

እትመት አሰፋ

**አመልካች፡-** አቶ መልካሙ አበራ

**ተጠሪ፡-** ቄስ ዳምጤ በየነ

መዝገቡ ለምርመራ የተቀጠረ በመሆኑ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍ ር ድ**

በዚህ መዝገብ የቀረበዉ ጉዳይ የገጠር መሬት ይዞታ የሚመለከት ነዉ፡፡በስር ፍርድ ቤት ከሳሽ የአሁኑ ተጠሪ ሲሆን የአሁኑ አመልካች ተከሳሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡የተጠሪ ክስ ይዘት ባጭሩ በስሙ የተመዘገበዉን አዋሳኙ እና መጠኑ በክሱ ዝርዝር የተገለጸዉን የእርሻ መሬት በህገወጥ ልዉዉጥ ምክንያት አመልካች ይዞ ስለሚገኝ እንዲለቅ እንዲወሰን የሚል ሲሆን በአመልካች በኩል የቀረበዉ ክርክር ልዉዉጥ የተደረገዉ ግንቦት 25 ቀን 2000ዓ.ም መሆኑንና ክሱ በ10ዓመት ይርጋ መታገድ ያለበት ስለመሆኑ እንዲሁም ተጠሪ በልዉዉጥ ዉል የወሰደዉን መሬት እየተጠቀመ ስለመሆኑ በመግለጽ ክሱ ዉድቅ እንዲደረግ የሚል ነዉ፡፡

የግራቀችን ክርክር በመጀመሪያ ደረጃ የዳኝነት ስልጣን የተመለከተዉ የፎገራ ወረዳ ፍርድ ቤት የግራቀችን ምስክር ሰምቶ እና ከወረዳዉ መሬት አስተዳደር መረጃ አጣርቶ ክስ የቀረበበት መሬት ለተጠሪ የተደለደለ ስለመሆኑ፣በግራቀች መካካል የተደረገዉ የመሬት ልዉዉጥ ዉል በሚመለከተዉ የመሬት አስተዳደር አካል ያልተመዘገበ ስለመሆኑና አመልካች በሃሰተኛ መረጃ በዚህ መሬት ላይ ደብተር የተሰጠዉ ስለመሆኑ በማረጋገጥ የልዉዉጥ ዉል የተደረገዉ በ25/09/2000ዓ.ም በመሆኑና ክስ የቀረበዉ በ22/03/2010ዓ.ም በመሆኑ ዉል ከተደረገበት አንስቶ ክስ እስከቀረበበት ያለዉ ጊዜ 10ዓመት ያልሞላዉ ስለሆነ አመልካች ያቀረበዉ 10ዓመት ይርጋ ዉድቅ በማድረግ የልዉዉጥ ዉል በክልሉ የገጠር መሬት አዋጅ ቁ/252/09 አንቀጽ 20/3/ መሰረት ያልተመዘገበ በመሆኑ ተፈጻሚነት የለዉም

በማለት አመልካች በልዉዉጥ ምክንያት የያዘዉን የተጠሪ መሬት እንዲለቅ ዉሳኔ ሰጥቷል፡፡አመልካች በዚህ ዉሳኔ ቅር ተሰኝቶ ለዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት እና ለክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት እንደቅደም ተከተሉ ይግባኝ እና የሰበር አቤቱታ ያቀረበ ቢሆንም ክርክሩ ተቀባይነት አላገኘም፡፡

ለዚህ ሰበር ችሎት አቤቱታ የቀረበዉ በዚህ ላይ ሲሆን የአመልካች ሰበር አቤቱታ ተመርምሮ ክርክር ያስነሳዉ የይዞታ ቅይይር መደረጉ በተጠሪ ታምኖ ባለበት እንዲሁም ልዉዉጡ ያልተመዘገበ ቢሆንም ይህንን ደረጃ አልፎ የይዞታ ማረጋገጫ በተሰጠበት ሁኔታ ይዞታዉን አመልካች ይልቀቅ ተብሎ መወሰኑ ተገቢ መሆን አለመሆኑን ለመመርመር እንዲቻል ጭብጥ ተይዞ ተጠሪ መልስ እንዲሰጥ ታዟል፡፡በተጠሪ በኩል የቀረበዉ መልስ ባጭሩ ባህላዊ ልዉዉጥ የተደረገ ቢሆንም አመልካች ሁለቱንም መሬት ይዞ አልሰጥም በማለቱ በሽማግሌም ተጠይቆ እምቢተኛ በመሆኑ ልዉዉጡ ያልተመዘገበ በመሆኑ ቀሪ ሆኖ ወደነበሩበት እንዲመለሱ መወሰኑ ተገቢ ስለመሆኑ ተከራክሯል፡፡አመልካችም አቤቱታዉን በማጠናከር የመልስ መልስ ሰጥቷል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ እና የግራቀኙ ክርክር ከላይ ባጭሩ የተገለጸ ሲሆን እኛም በሰበር አጣሪ የተያዘዉን ጭብጥ መሰረት በማድረግ አግባብነት ካለዉ ህግ ጋር በማገናዘብ መርምረናል፡፡ መዝገቡን መርምረን እንደተገነዘብነዉ ለክርክር መነሻ የሆነዉ ጉዳይ በግራቀኙ መካከል የተደረገ የመሬት ልዉዉጥ ዉል ተፈጻሚነት በሚመለከት ነዉ፡፡የስር ፍርድ ቤት ዉሳኔ የተሰጠዉ ክስ የቀረበበት መሬት የተጠሪ ስለመሆኑ፣የመሬት ልዉዉጡ ያልተመዘገበ ስለመሆኑና አመልካች በሀሰተኛ መረጃ በዚሁ መሬት ደብተር ያገኘ መሆኑ በሚመለከተዉ የመሬት አስተዳደር አካል ስለተረጋገጠ አመልካች የተጠሪን መሬት እንዲለቅ ዉሳኔ መስጠቱን ነዉ፡፡

በአማራ ብ/ክ/መንግስት የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም አዋጅ ቁ/252/09 አንቀጽ 20/3/ ላይ እንደተመለከተዉ የገጠር መሬት ባለይዞታዎች መካከል የሚደረግ ማንኛዉም የልዉዉጥ ዉል አግባብ ባለዉ የወረዳ የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ጽ/ቤት ቀርቦ መመዝገብ ያለበት ስለመሆኑ ነዉ፡፡በዚህ መዝገብ በተያዘዉ ክርክር ከጅምሩም ተጠሪ ክስ ያቀረበዉ የልዉዉጥ ዉል መደረጉን ሳይክድ በህገወጥ የልዉዉጥ ዉል ምክንያት አመልካች የያዘዉን የተጠሪ መሬት እንዲለቅ እንዲወሰን ነዉ፡፡ከዚህም ባሻገር አመልካች የራሱን መሬት ለተጠሪ ሳያስረክብ በለዉጥ ምክንያት የያዘዉንና የራሱን መሬት ድርቦ መያዙም በክርክሩ ሂደት የተገለጸ ነዉ፡፡

ስለሆነም ዉሉ ህገወጥ ነዉ ተፈጻሚነት የለዉም የሚለዉ የተጠሪ ክርክር ዉል መኖርን መነሻ ያደረገ ስለሚሆን ተጠሪ ዉሉን አምኗል የሚለዉ የሰበር አጣሪ ችሎት ጭብጥ የክርክር መነሻ ከመሆኑ አኳያ፣ይህም የልዉዉጥ ዉል በህጉ አግባብ ያልተፈጸመ ስለመሆኑ እንዲሁም አመልካች በዚህ ይዞታ ላይ ደብተር ያገኘዉ በሀሰተኛ መረጃ ላይ መሰረት በማድረግ አስተዳደሩን በማሳሳት ስለመሆኑ በስር ፍርድ ቤት ከመሬት አስተዳደር አካል ጭምር በቀረበ ማስረጃ የተረጋገጠ ፍሬጉዳይ በመሆኑ በሀሰተኛ

መረጃ ላይ ተመስርቶ የተመዘገበ ደብተር  መሆኑ እስከተረጋገጠ ድረስ በክልሉ የገጠር መሬት አዋጅ ቁ/252/09 አንቀጽ 34/5/መሰረት በሀሰተኛ መረጃ ላይ ተመስርቶ ፣ የተደረገ ምዝገባ ህጋዊ ውጤት ስለማይኖረው እና በህግ ፊት በማይፀና ውል የያዘውን የተጠሪ መሬት አመልካች እንዲለቅ በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጠዉ ዉሳኔ ላይ መሰረታዊ የህግ ስህተት ተፈጽሟል የሚባልበት ህጋዊ ምክንያት አላገኘንም፡፡በዚሁ አግባብ ተከታዩን ዉሳኔ ሰጥተናል፡፡

## ዉ ሳ ኔ

1ኛ/ በፎገራ ወረዳ ፍ/ቤት በመ/ቁ/29546 ላይ በ12/06/2010 ዓ.ም የተሰጠዉ ፍርድ እና ይህንኑ በማጽናት የደቡብ ጎንደር ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ/65196 ላይ በ01/10/2010ዓ.ም የሰጠዉ ዉሳኔ እና የአማራ ብ/ክ/መ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ/79074 ላይ በ12/11/2010ዓ.ም የሰጠዉ ትእዛዝ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህግ ቁ/348/1 መሰረት ጸንቷል፡፡

2ኛ/በዚህ ፍ/ቤት ለተደረገዉ ክርክር ወጪና ኪሳራ ግራቀኙ የየራሳቸዉን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት ፡፡

ፅ/ወ

የመ/ቁ. 169030

ህዳር 30/2012 ዓ.ም

ዳኞች፡-እትመት አሰፋ

ጳውሎስ ኦርሺሶ

ፀሐይ መንክር

መላኩ ካሳዬ

እስቲበል አንዱዓለም

| | | |
|---|---|---|
| አመልካቾች፡ | 1.አቶ አሰፋ ሰቦቃ<br>2. አቶ ታደሰ ሰቦቃ<br>3. ወ/ሮ ቀነኒ ሰቦቃ<br>4. ወ/ት ኩሜ ሰቦቃ | ጠበቃ አቶ ከበደ ቱፋ ቀርበዋል፡፡ |
| ተጠሪዎች፡ | 1.አቶ ከበደ ሰቦቃ<br>2. አቶ ኩማ ሰቦቃ | ቀርበዋል፡፡ |
| | 3. ወ/ሮ አለሚ ሰቦቃ<br>4. ወ/ሮ ደስታ ሰቦቃ | አልቀረቡም፡፡ |

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የገጠር እርሻ መሬት የውርስ ይገባኛል ክርክርን የሚመለከት ነው፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው የኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት በሰ/መ/ቁ/282886 ላይ ጥቅምት 19/2011 ዓ.ም በዋለው ችሎት የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔን በማሻሻል የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት አለበት በሚል ለማስለወጥ ነው፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ በአጭሩ እንዲህ ነው፡፡ የአሁን 2ኛ እና 3ኛ አመልካቾች ከሳሽ፤ 1ኛ እና 4ኛ አመልካቾች ደግሞ ተከሳሽ በመሆን በደቡብ ምዕራብ ሸዋ ዞን ዳዎ ወረዳ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 27141 ላይ በክርክር ላይ እያሉ ጉዳዩ በእርቅ ስምምነት ጨርሰው ስምምነቱን ለፍርድ ቤቱ አቅርበው በስምምነቱ መሰረት ውሳኔ ተሰጥቶ መዝገቡ ይዘጋል፡፡ ከዚህ በኋላ የአሁን 1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች በእርቅ በተዘጋው መዝገብ ላይ በመቃወም በአመልካችነት ቀርበው መዝገቡ ተከፍቶ ጉዳዩ በክርክር ላይ እያለ የአሁን 3ኛ እና 4ኛ ተጠሪዎች በጣልቃ ገብነት በመቅረባቸው ፍርድ ቤቱ የክርክሩ አካል አድርጓቸው የግራ ቀኙ ክርክር እና ማስረጃ በመስማት እንዲሁም ክርክር ስላልተነሳበት ይዞታ ጉዳይ ከሚመለከተው አስተዳደር ክፍል ተጣርቶ እንዲቀርብለት በማድረግ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

በውሳኔውም ግራ ቀኙ የሚከራከሩበት የውርስ ይዞታ በአጠቃላይ 16(አስራ ስድስት) ቀርጥ መሆኑን፤የአሁን አመልካቾች ወላጆቻቸው በህይወት እያሉ ለእያንዳንዳቸው ሁለት ቀርጥ መሬት ተሰጥቷቸው ይዘው እየተጠቀሙበት ስለመሆኑ እንዲሁም የአሁን 3ኛ እና 4ኛ አመልካቾች ክርክር በቀረበበት ይዞታ ላይ ወላጆቻቸው እስከሞቱበት ድረስ በጥገኝነት ሲኖሩ የነበረ ለመሆኑ ከወረዳው መሬት አስተዳደር የተገለፀለት መሆኑን፤ የግራ ቀኙ የሰው ምስክሮችም የአሁን 1ኛ እና 2ኛ አመልካቾች ወላጆቻቸው በህይወት እያሉ ለእያንዳንዳቸው ሁለት ቀርጥ መሬት ተሰጥቷቸው ይዞታውን በእጃቸው አድርገው እየተጠቀሙበት ያሉ መሆኑን፤ 3ኛ እና 4ኛ አመልካቾች በወረዳው መሬት አስተዳደር በተገለፀው አኳኋን በይዞታው ላይ ከወላጆቻቸው ጋር በጥገኝነት ይኖሩ የነበረ ለመሆኑ ያረጋገጡ መሆኑን በመጥቀስ 3ኛ እና 4ኛ አመልካቾች በይዞታው ላይ ጥገኛ በመሆናቸው፤ 1ኛ እና 2ኛ አመልካቾች ደግሞ ቀድሞ በወላጆቻቸው በተሰጣቸው ሁለት ቀርጥ መሬት ላይ የቀዳሚነት መብት ያላቸው መሆኑን በምክንያትነት በመጥቀስ 3ኛ እና 4ኛ አመልካቾች በክልሉ ገጠር መሬት አስተዳደር እና አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር 130/1999 አንቀፅ 2(16) እና 5(5) እንዲሁም ይህንኑ አዋጅ ለማስፈፀም በወጣው ደንብ ቁጥር 151/2005 አንቀፅ 3(13) መሰረት እያንዳንዳቸው አንድ ሄክታር (አራት ቀርጥ) እንዲወስዱ፤ 1ኛ እና 2ኛ አመልካቾች ቀድሞ ለእያንዳንዳቸው የተሰጣቸው ሁለት ቀርጥ መሬት ከአጠቃላይ የውርስ ይዞታው ውስጥ ከወጣ በኋላ ቀሪውን አራት ቀርጥ ለስምንቱም ወራሾች የሚከፋፈል ቢሆን በክልሉ የገጠር መሬት አዋጅ መሰረት የመሬት መበጣጠስን የሚያስከትል በመሆኑ ግራ ቀኙ በጋራ ሊጠቀሙበት ይግባል ብሏል፡፡

የአሁን ተጠሪዎች በዚሁ ውሳኔ ላይ ይግባኝ ለደቡብ ምዕራብ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ያቀረቡ ቢሆንም ፍርድ ቤቱ የይግባኝ አቤቱታውን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህግ ቁጥር 337 መሰረት ሰርዟል፡፡

በዚሁ ውሳኔ ላይ የሰበር አቤቱታ የቀረበለት የክልሉ ሰበር ችሎት በበኩሉ የግራ ቀኙን የሰበር ክርክር ከሰማ በኋላ ከላይ በተጠቀሰው የመዝገብ ቁጥር እና ቀን በዋለው ችሎት ለአሁን 1ኛ እና 2ኛ አመልካቾች ተሰጥቷል የተባለውን ስጦታ በተመለከተ በክልሉ ገጠር መሬት አስተዳደር እና አጠቃቀም

ህግ መሰረት የሚፀና የስጦታ ውል ባይኖርም ከውርስ ሃብት ስጦታ ከተቀበሉ በኋላ ከቀሪ የውርስ ሃብት ለመካፈል የጠየቁ በመሆኑ በፍ/ብ/ህ/ቁጥር 1066 መሰረት ስጦታውን ወደ ውርስ ሃብት ሊመልሱ ይገባል፤ 3ኛ እና 4ኛ አመልካቾችም የቅድሚያ መብት ያላቸው መሆኑን ቢረጋገጥም በቀዳሚነት መብታቸው ሊደርሳቸው የሚገባው የድርሻ መጠን እንደውርስ ሃብቱ ስፋት እና ወራሾች ብዛት የሚወሰን እንጂ እያንዳንዳቸው አንድ ሄክታር እንዲያገኙ የክልሉ ገጠር መሬት አስተዳደር እና አጠቃቀም ደንብ የማያስገድድ መሆኑን በመጥቀስ እያንዳንዳቸው አንድ ቀርጥ መሬት በቀዳሚነት ሊደርሳቸው ይገባል፤የተቀረውን 14 ቀርጥ መሬት ስምንቱም ወራሾች እኩል ሊካፈሉ ይገባል በማለት የስር ፍርድ ቤት ውሳኔን በማሻሻል ወስኗል፡፡

የአሁን የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ነው፡፡ አመልካቾች ጥር 08/2011 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ በክልሉ ሰበር ችሎት ውሳኔ ላይ ያላቸውን ቅሬታ ዘርዝረው በዚህ ችሎት እንዲታረምላቸው ጠይቀዋል፡፡ የቅሬታው ፍሬ ቃልም በእርቅ ባለቀ እና በተፈፀመ ጉዳይ ላይ የስር ፍርድ ቤቶች የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁጥር 358 እና 41 ቀላቅለው መወሰናቸው ከሥነ ሥርዓት ውጭ ነው፤ተጠሪዎች የራሳቸው የእርሻ መሬት ያላቸው ለመሆኑ እና በአውራሾቻችን መሬት ላይ በጥገኝነት የምንኖረው አመልካቾች ለመሆናችን በፍሬ ነገር ደረጃ ተረጋግጦ እያለ ይዞታውን እኩል እንድንካፈል መወሰኑ ከክልሉ የገጠር መሬት አዋጅ ቁጥር 130/1999 አንቀፅ 9 እና ደንብ ቁጥር 151/2005 አንቀፅ 10 ድንጋጌ ውጭ ከመሆኑም በላይ ይኸው ሰበር ችሎት በሰ/መ/ቁ/109776 ላይ የሰጠውን አስገዳጅ የህግ ትርጉም የተላለፈ በመሆኑ ውሳኔው ተሽሮ በይዞታው ላይ የቅድሚያ መብት አላችሁ ተብለን ለእያዳንዳችን አንድ ሄክታር መሬት ሊወሰንልን ይገባል የሚል ነው፡፡

የቀረበው የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ በክልሉ ሰበር ችሎት በአሁን ተጠሪዎች የቀረበው ቅሬታ የአሁን አመልካቾች የውርስ ይዞታው ላይ ቀድሞ የተሰጣቸው መሬት እያላቸው በድጋሚ ከውርሱ ሊካፈሉ አይገባም የሚል ሆኖ እያለ የክልሉ ሰበር ችሎት ከዚህ ጭብጥ ውጭ በመውጣት ስጦታውን አፍርሶ ሁሉም ወራሾች እኩል ይካፈሉ በማለት የወሰነበት አግባብ ለዚህ ሰበር ችሎት ቀርቦ እንዲታይ በመታዘዙ ግራ ቀኙ የፅሁፍ ክርክር እንዲለዋወጡ ተደርጓል፡፡

ተጠሪዎች መጋቢት 20/2011 ዓ.ም በተፃፈ መልስ አመልካቾች በወረዳው ፍርድ ቤት አቅርበዉ የነበረው ክርክር በእርቅ ስለማለቁ እንጂ በእርቁ መሰረት ለመፈፀሙ የተረጋገጠ ነገር ባለመኖሩ በጉዳዩ ላይ በመቃወም አመልካችነት ቀርበን መስተናገዳችን በአግባቡ ነው፤አመልካቾች ሂደቱ ከሥነ ሥርዓት ውጭ ነው ቢሉም በምን አግባብ ከሥነ ሥርዓት ውጭ እንደሆነ ለይተው የገለፁት ነገር የለም በማለት በተቀረው የክልሉ ሰበር ችሎት በስር ፍርድ ቤቶች የተረጋገጠን ፍሬ ነገር መሰረት አድርጎ የወሰነ በመሆኑ የሚነቀፍበት መሰረታዊ የህግ ስህተት የለም በማለት ሞግተዋል፡፡ አመልካቾችም በመልስ መልሳቸው የሰበር ቅሬታቸውን በማጠናከር ተከራክረዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ ይዘት አጠር ባለ መልኩ ከላይ የተመለከተውን ሲመስል ችሎቱም በማስቀረቢያው ነጥብ ሳይወሰን አጠቃላይ የክርክሩ ይዘት መርምሯል፡፡ በዚሁ መሰረት የክልሉ ሰበር ችሎት የጠቀሰው የፍ/ብ/ህ/ቁጥር 1066 ክርክር ለተነሳበት ጉዳይ ተፈፃሚነት ያለው መሆኑን አለመሆኑ በቅድሚያ ሊታይ የሚገባ ነጥብ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

የክልሉ ሰበር ችሎት የአሁን 1ኛ እና 2ኛ አመልካቾች ከውርስ ሃብቱ ቀድሞ ስጦታ የተቀበሉ ቢሆንም ከተቀረው ውርስ ለመካፈል የጠየቁ በመሆኑ በፍ/ብ/ህ/ቁ/1066 መሰረት ቀድሞ በስጦታ የተቀበሉትን ይዞታ ወደ ውርስ መልሰው ከሌሎች ወራሾች ጋር ሊካፈሉ ይገባል በማለት ወስኗል፡፡

በእርግጥ ከሟች ወደታች የሚቆጠሩ የጋራ ወራሾች ውስጥ መመለስ የለብህም ተብሎ ቀድሞ ከሟቹ ያገኘውን ችሮታ/ስጦታ/ ካልሆነ በቀር ስጦታ ተቀባዩ ውርሱን የሚቀበል ከሆነ ተቀብሎት የነበረውን ንብረት ዋጋ ከውርሱ ውስጥ መልሶ ማግባት ያለበት ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁጥር 1065 ይደነግጋል፡፡ የዚህ ድንጋጌ መሰረታዊ ዓላማ የሟች ወደታች የሚቆጠሩ ወራሾች ሟች በህይወት እያለ ከውርስ ሃብቱ ቀድሞ ስጦታ የተቀበሉ ቢሆንም በሟቹ የውርስ ሃብት ላይ ከሚኖራቸው ተነፃፃሪ መብት አኳያ ወራሾችን በተቻለ መጠን እኩል ማድረግ ስለመሆኑ ከድንጋጌው ይዘት እና መንፈስ መረዳት ይቻላል፡፡

መሰረታዊ ዓላማው ይህ ቢሆንም ሊስተዋል የሚገባው ነጥብ ውርሱን የተቀበለው ወራሽ እንዲመልስ የሚገደደው በስጦታ የተቀበለውን ንብረት በዓይነት ሳይሆን የንብረቱን ግምት ነው፡፡ የንብረቱን ግምት መመለስ ሲባልም ወራሹ ቀድሞ በስጦታ የተቀበለው ንብረት ተገምቶ በውርስ ሀብት ክፍፍል ከተቀረው ንብረት ጋር ተደምሮ ወራሾቹ እኩል ድርሻ እንዲኖራቸው ይደረጋል ለማለት እንጅ ወራሹ የንብረቱን ግምት ይከፍላል ማለት እንዳልሆነ ከፍ/ብ/ህ/ቁ/1066 እስከ 1074 ከተመለከቱት ድንጋጌዎች ይዘት መገንዘብ ይቻላል፡፡ ቀድሞ ከሟች ስጦታ የተቀበለ ወደታች የሚቆጠር ወራሽ ከሌሎች ስጦታ ካልተቀበሉ ወራሾች የሚለየው አብይ ጉዳይ ስጦታ ተቀባዩ ከውርስ ንብረቱ ውስጥ በዓይነት የሚደርሰውን ቀድሞ የሚያውቅ ሲሆን ሌሎች ወራሾች ግን በንፅፅር የሚደርሳቸውን ድርሻ መጠን እንጂ በዓይነት የሚደርሳቸውን ንብረት የማያውቁ መሆኑ ነው፡፡ እናም በዚህ ድንጋጌ መሰረት ከውርስ ንብረት ስጦታ የተቀበለ ወራሽ የንብረቱ ዋጋ ወደ ውርሱ ለመመለስ ንብረቱ ሊገመት የሚችል ሊሆን ይገባል ማለት ነው፡፡

አሁን በቀረበው ጉዳይ ግራ ቀኙ የሚከራከሩበት የውርስ ሀብት የገጠር እርሻ መሬት ሲሆን የአሁን 1ኛ እና 2ኛ አመልካቾች ቀድመው በስጦታ ወስደዋል የተባሉትም ይህንኑ የገጠር መሬት ይዞታን ነው፡፡ እነዚህ አመልካቾች የተቀረውን የአውራሾቻቸውን የይዞታ ውርስ ለመቀበል ከፈለጉ በፍ/ብ/ህ/ቁጥር 1065 መሰረት ወደ ውርሱ ሊመልሱ የሚገደዱት በስጦታ የተቀበሉትን ይዞታ በዓይነት ሳይሆን የይዞታውን ግምት ዋጋን ነው፡፡ ሆኖም በኢ.ፌ.ዴ.ሪ. ህገ መንግስት አንቀፅ 40(3) የገጠርም ሆነ ከተማ መሬትና የተፈጥሮ ሃብት ባለቤትነት መብት የመንግስትና የህዝብ ብቻ መሆኑን እና መሬት የማይሸጥ

የማይለወጥ የኢትዮጵያ ብሔሮች፣ብሔረሰቦችና ሕዝቦች የጋራ ንብረት መሆኑ የተደነገገ በመሆኑ በዋጋ ሊገመት የሚችል አይደለም፡፡

ከዚህ አኳያ የኢ.ፌ.ዴ.ሪ. ህገ መንግስት ከታወጀ በኋላ ባለው የመሬት ስሪት መሰረት የፍ/ብ/ህ/ቁ/1065 እና ተከታዮቹ መሬትን በሚመለከት ተፈፃሚነት የለውም ማለት ይቻላል፡፡ ሆኖም ህገ መንግስቱ ከመታወጁ በፊት የነበሩት የሀገሪቱ ህጎች በህግ አግባብ ተፈፃሚነታቸው እስካልተሻረ ድረስ ከህገ መንግስቱ ጋር በተጣጣመ መልኩ ስራ ላይ ሊውሉ በሚችሉበት አኳኋን ሊተረጎም ይገባል፡፡ በዚሁ አግባብ መሬትን በተመለከተ የፍ/ብ/ህ/ቁጥር 1065 ድንጋጌ ተፈፃሚ ሊሆን የሚችለው ቀድሞ ከሟች ስጦታ የተቀበለ ወደታች የሚቆጠር ወራሽ ውርሱን ለመቀበል ፍቃደኛ ከሆነ ቀድሞ የተቀበለው የመሬት ይዞታ መጠን በአካባቢው የመሬት ልኬት ልማድ መሰረት ተለክቶ ከተቀረው የውርስ ይዞታ ላይ ከሚደርሰው ድርሻ ጋር እንዲጣጣም በማድረግ በሚል ሲተረጎም ነው፡፡ በዚህ ስሌት መሰረት ወራሹ ቀድሞ በስጦታ የተቀበለው ይዞታ ከአጠቃላይ የውርስ ይዞታው ከሚደርሰው ድርሻ መጠን በታች ከሆነ ከተቀረው የውርስ ይዞታ ላይ የሚቀረውን መጠን ያክል እንዲካፈል፤ ስጦታው ከድርሻው በላይ ከሆነ ደግሞ ቀድሞ የተቀበለውን ስጦታ ብቻ ይዞ እንዲቆይ ይደረጋል ማለት ነው፡፡

ጉዳዩ በዚህ መልኩ ሊታኝ ሲገባ የክልሉ ሰበር ችሎት 1ኛ እና 2ኛ አመልካቾች ቀድመው በስጦታ የተቀበሉትን የእርሻ መሬት ወደ ውርሱ መልሰው ከሌሎች ወራሾች ጋር እንዲካፈሉ መወሰኑ ለውሳኔው መሰረት ካደረገውን የፍ/ብ/ህ/ቁር 1065 ድንጋጌ መንፈስ ውጭ ከመሆኑም በላይ የኢ.ፌ.ዴ.ሪ. ህገ መንግስትን የመሬት ስሪት ባህሪን ያላገናዘበ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ከመሬት ጋር በተያያዘ የፍ/ብ/ህ/ቁ/ 1065 ድንጋጌ ተፈፃሚነት በይዞታ መጠን ልኬት ማቻቻል ነው ከተባለ ግራ ቀኙ የሚከራከሩበት የውርስ ይዞታ ክፍፍል በምን መልኩ ሊመራ ይገባል የሚለው ቀጥሎ ሊታይ የሚገባው ነጥብ ነው፡፡ይህንኑ ነጥብ በአግባቡ ለመፍታት በስር ፍርድ ቤት በፍሬ ነገር ደረጃ የተረጋገጡትን መነሻ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ በዚሁ መሰረት ጉዳዩ በመጀመሪያ ደረጃ በተመለከተው የወረዳው ፍርድ ቤት በነበረው ክርክር በሰው እና በሰነድ ማስረጃዎች በፍሬ ነገር ደረጃ የተረጋገጠው ግራ ቀኙ የሚከራከሩበት የውርስ ይዞታ በጠቅላላው 16 ቀርጥ ሲሆን ወራሾች ደግሞ 8 መሆናቸውን፤የአሁን 1ኛ እና 2ኛ አመልካቾች የግራ ቀኙ ወላጆች በህይወት እያሉ ለእያንዳንዳቸው ሁለት ቀርጥ መሬት የሰጧቸው መሆኑን፤ 3ኛ እና 4ኛ አመልካቾች ክርክር በተነሳበት ይዞታ ላይ በጥገኝነት ሲኖሩ የነበረ መሆኑን እና ሌሎች ወራሾች የራሳቸው ይዞታ ያላቸው መሆኑን ነው፡፡

3ኛ እና 4ኛ አመልካቾች ክርክር በተነሳበት ይዞታ ላይ በጥገኝነት ሲኖሩ የነበረ ለመሆኑ በፍሬ ነገር ደረጃ የተረጋገጠ በመሆኑ እና በቀዳሚነት መብት ሊደርሳቸው የሚገባውም የድርሻ መጠን በክልሉ ሰበር ችሎት እንደተገለፀው ከውርስ ይዞታው ስፋት እና ወራሾች ብዛት አኳያ ታይቶ ሊወሰን የሚገባው በመሆኑ በክልሉ ገጠር መሬት አስተዳደር እና አጠቃቀም አዋጁ ቁጥር 130/1999 አንቀፅ 9(2) እና

ደንብ ቁጥር 151/2005 አንቀፅ 10(10) መሰረት እያንዳንዳቸው ሁለት ቀርጥ ሊደርሳቸው እንደሚገባቸው ታምኗል፡፡ የሚቀረው 12 ቀርጥ መሬት ለሁሉም ወራሾች እኩል ሲካፈል ለ1ኛ እና 2ኛ አመልካቾች የሚደርሳቸው የይዞታ መጠን ቀድሞ በስጦታ ከተቀበሉት መጠን በታች በመሆኑ በስጦታ ያገኙትን የይዞታ መጠን ይዘው ሊቀጥሉ ይገባል፡፡ ይኸው ከቀሪ የውርስ ይዞታ ላይ ሲነሳ የሚቀረው 8 ቀርጥ ሲሆን በተቀሩት ስድስት ወራሾች መካከል የሚካፈል ይሆናል፡፡

በመሆኑም በዚሁ ስሌት መሰረት 1ኛ እና 2ኛ አመልካቾች የግራ ቀኙ ወላጆች በህይወት እያሉ እያንዳንዳቸው ያገኙትን ሁለት ቀርጥ መሬት ይዘው እንዲቆዩ፤ ለ3ኛ እና 4ኛ አመልካቾች ለእያንዳንዳቸው ሁለት ቀርጥ መሬት በቀዳሚነት መብት ተነስቶላቸው ቀሪውን ስምንት ቀርጥ 3ኛ እና 4ኛ አመልካቾች ከአሁን ተጠሪዎች ጋር እኩል እንዲካፈሉ ማድረጉ ፍትሐዊ ሆኖ የተገኘ በመሆኑ ተከታዩ ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

**<u>ው ሳ ኔ</u>**

1. የኢ.ፌ.ዴ.ሪ. ህገ መንግስት ከታወጀ በኋላ ባለው የመሬት ስሪት መሰረት የፍ/ብ/ህ/ቁ/1065 መሬትን በሚመለከት ተፈፃሚ የሚሆነው ቀድሞ በስጦታ የተወሰደውን ይዞታ በዓይነት ወደ ውርስ ይዞታ እንዲመለስ በማድረግ ሳይሆን የይዞታውን መጠን በልኬት በመለየት መጠኑ ከአጠቃላይ የውርስ ይዞታው ውስጥ ለስጦታ ተቀባዩ ከሚደርሰው ድርሻ ላይ እንዲቀነስ በማድረግ ነው፡፡

2. በውሳኔ ተራ ቁጥር አንድ ስር ከተገለፀው አኳያ የኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት በሰ/መ/ቁ/282886 ላይ ጥቅምት 19/2011 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህግ ቁጥር 348(1) መሰረት ተሻሽሎ፡-

    2.1. 1ኛ እና 2ኛ አመልካቾች (አቶ አሰፋ ሰቦቃ እና አቶ ታደሰ ሰቦቃ) የግራ ቀኙ ወላጆች በህይወት እያሉ የሰጧቸውን እያንዳንዳቸው ሁለት ቀርጥ መሬት ይዘው እንዲጠቀሙበት፤

    2.2. 3ኛ እና 4ኛ (ቀነኒ ሰቦቃ እና ኩሜ ሰቦቃ) ክርክር በተነሳበት ይዞታ ላይ ጥገኛ የቤተሰብ አባል በመሆናቸው እና የቅድሚያ መብት ያላቸው በመሆኑ እያንዳንዳቸው ከውርስ ይዞታው ሁለት ቀርጥ መሬት እንዲካፈሉ፤እና

    2.3. የተቀረውን ስምንት ቀርጥ መሬት 3ኛ እና 4ኛ አመልካቾች እንዲሁም የአሁን ተጠሪዎች በክልሉ ገጠር መሬት ድልድል መመዘኛ መሰረት የመሬት መበጣጠስን የማያስከትል ከሆነ እኩል እንዲካፈሉ፤ ካልሆነ በስምምነት በጋራ እንዲጠቀሙበት ተወስኗል፡፡

## ት ዕ ዛ ዝ

1. ውሳኔው መሻሻሉን እንዲያውቅ የዚህ ፍርድ ትክክለኛ ግልባጭ ለስር ፍርድ ቤት ይተላለፍ፡፡
2. የዚህን ሰበር ችሎት ክርክር ወጪ ግራ ቀኙ የራሳቸውን ይቻሉ፡፡
3. መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ብ/ታ

የሰ.መ.ቁ 168556

ሰኔ 14 ቀን 2011 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ብርሃኑ አመነዉ

በዕዉቀት በላይ

እንዳሻዉ አዳነ

ሀይሉ ነጋሽ

እትመት አሠፋ

አመልካች:- አቶ ተሾመ ድለንሴ

ተጠሪዎች፡-1.የቀርሳ ማሊማ ወረዳ ገጠር መ/ ባለስልጣን ጽ/ቤት

2. የቀርሳ ወርኮ ቀበሌ ገ/ማ//ጽ/ቤት

መዝገቡን መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ የገጠር መሬት ይዞታ ለህዝብ መንገድ ስራ በሚል ከአመልካች ላይ በመወሰዱ ካሳና ትክ መሬት እንዲሰጠዉ አመልካች ያቀረበዉ የዳኝነት ጥያቄ የስር ወረዳ ፍርድ ቤት በአዋጅ ቁ/455/97 መሰረት የሚታይ እንጂ የፍርድ ቤት ስልጣን አይደለም በማለት የሰጠዉን ብይን የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት እና የኦሮሚያ ክልል ሰበር ሰሚ ችሎት በማጽናቱ ዉሳኔዉ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ በሚል እንዲታረም አቤቱታ የቀረበበት ነዉ፡፡

የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ የአመልካች የዳኝነት ጥያቄ ለመንገድ በተወሰደዉ መሬት ምትክ ቦታ ወይም ካሳ ስላልተሰጠኝ በፍ/ቤት ይወሰንልኝ የሚል ሆኖ አቤቱታ ሰሚ ኮሚቴ ስለመቋቋሙ ባልተረጋገጠበት ሁኔታ ጉዳዩን የማየት ስልጣን የለኝም በማለት የስር ፍርድ ቤት የሰጠዉ ዉሳኔ አግባብነት ከአዋጅ ቁ/ 455/97 አንጻር ለመመርመር በሚል ጭብጥ ተይዞ ተጠሪዎች መልስ እንዲሰጡ ተድርጓል፡፡በ1ኛ ተጠሪ በኩል የቀረበዉ መልስ ባጭሩ በአዋጅ ቁ/455/97 አንቀጽ 11/1/መሰረት ለአስተዳደር አካል ቅሬታ ቀርቦ ዉሳኔ ሳይሰጥ ለፍርድ ቤት መቅረቡ ተገቢ አለመሆኑንና ቅሬታ ሰሚ አስተዳደራዊ አካል አልተቋቋመም ቢባል እንኳን ቅሬታ ማቅረቢያ ጊዜ አልፎበታል በሚል የስር ፍርድ ቤት ዉሳኔ እንዲጸና የተከራከረ ሲሆን 2ኛ ተጠሪ በበኩሉ ከአመልካች ይዞታ ላይ 110ሜ በ12ሜ የሆነ የእርሻ መሬት ለህዝብ መንገድ የተወሰደበት መሆኑን ገልጾ ቀበሌዉ የወል መሬት የሌለዉ በመሆኑ ትክ መሬት ሊሰጠዉ እንዳልቻለ እንዲሁም ለዚህ ተብሎ የተያዘ በጀት ባለመኖሩ ካሳም እንዳልተከፈለ ገልጾ የስር ፍርድ ቤት ዉሳኔ እንዲጸና ጠይቋል፡፡አመልካችም አቤቱታዉን በማጠናከር የመልስ መልስ ሰጥቷል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ በአጭሩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን እኛም እንዲጣራ የተያዘውን ነጥብ ከግራቀኙ ክርክር፤ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸው ሕጎች ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

የአመልካች የዳኝነት ጥያቄ የእርሻ መሬት ይዞታዉ ላይ ለህዝብ መንገድ ተብሎ የተወሰደዉን መሬት ትክ መሬት ወይም ካሳ እንዲከፈለዉ ለአስተዳደር አካላት አቤቱታ አቅርቦ ምላሽ በማጣቱ ፍርድ ቤት ዉሳኔ እንዲሰጠዉ ዳኝነት የጠየቀ ስለመሆኑ መዝገቡ ያስረዳል፡፡ ተጠሪዎችም የአመልካች መሬት በከፊል ለህዝብ መንገድ ስራ መዋሉን አልካዱም፡፡ ነገር ግን በቅድሚያ በአሥተዳደሩ በተቋቋመ ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ ሊታይ ይገባል የሚል መቃወሚያ አቅርበዋል፡፡የስር ፍርድ ቤቶችም ይህንኑ መሰረት አድርገዉ ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን በዳኝነት የማየት ስልጣን የለዉም በማለት ዉሳኔ የሰጡ ስለመሆኑ መገንዘብ ተችሏል፡፡

በመሰረቱ የገጠርም ሆነ የከተማ መሬት እና የተፈጥሮ ሀብት የባለቤትነት መብት የመንግስትና የህዝብ ስለመሆኑ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገመንግስት አንቀጽ 40/3/ ላይ ተደንግጓል፡፡ የኢትዮጵያ አርሶ አደሮች መሬት በነጻ የማግኘትና ከመሬታቸዉ ያለመፈናቀል መብታቸዉ የተከበረ ስለመሆኑና አፈጻጸሙ በዝርዝር ህግ የሚወሰን መሆኑን አንቀጽ 40/4/ ላይ ተደንግጓል፡፡ይህንኑ ህገ መንግስታዊ ድንጋጌ ተከትሎ የወጣዉ የፌዴራል የገጠር መሬት አስተዳደር አዋጅ ቁ456/97 አንቀጽ 5/3/ እንዲሁም በስራ ላይ ያለዉ የኦሮሚያ ክልል የገጠር መሬት አጠቃቀምና አስተዳደር አዋጅ ቁ/130/99 አንቀጽ 5/1 እና 5 ድንጋጌዎች እንደሚያስገነዝቡት በገጠር መሬት የመጠቀም የይዞታ መብት የሚገኘዉ በመንግስት በሚደረግ ድልድል፣በዉርስ ወይም በስጦታ ነዉ፡፡ስለሆነም የገጠር መሬት ላይ የይዞታ መብት አለኝ የሚል ሰዉ ከእነዚህ በአንደኛዉ አግባብ ይዞታዉን ያገኘ እንደሆነ ያለገደብ መሬቱን የመጠቀም ፤በመሬቱ ላይ ያፈራዉን ንብረት የመሸጥ፣የመለወጥና የማስተላለፍ መብት እንዳለዉ እና ይህም መብት ሊቋረጥ የሚችለዉ መሬቱ ለበለጠ የህዝብ ጥቅም ሲፈለግ ስለመሆኑና ለዚህም ካሳ እና ትክ መሬት እንደሚሰጠዉ ትክ መሬት መስጠት ካልተቻለ መልሶ ማቋቋሚያ ካሳ እንደሚከፈለዉ አዋጅ ቁ/ 130/99 አንቀጽ 6/1፣10፣11እና 12 ድንጋጌዎች ይዘት ያሥገነዝባሉ፡

ሕገ-መንግሥቱን መሠረት በማድረግ የወጣው ለሕዝብ ጥቅም ሲባል የመሬት ይዞታ የሚለቀቅበትን እና የንብረት ካሣ የሚከፈልበትን ሁኔታ ለመወሰን የወጣው አዋጅ ቁጥር 455/ 1997 አንቀጽ 2/1 'ካሣ' ማለት የመሬት ይዞታውን እንዲለቅ ለሚወሰንበት ባለይዞታ በመሬቱ ላይ ለሰፈረው ንብረት በዓይነት ወይም በገንዘብ ወይም በሁለቱም የሚከፈል ክፍያ ነው በማለት ይደነግጋል፡፡ የአዋጁ አንቀጽ 11/1/ ተቃራኒ ንባብ የመሬት ነክ አቤቱታ ሠሚ አሥተዳደራዊ አካል በተቋቋመባቸው ከተሞች የካሣ መጠንን አስመልክቶ አቤቱታ የሚቀርበው በከተማው አሥተዳደር ለተቋቋመ የመሬት ነክ አቤቱታ ሰሚ አሥተዳደራዊ አካል መሆኑን ነገር ግን አቤቱታ ሰሚ አካል ባልተቋቋመባቸዉ የከተማ አስተዳደርና የገጠር መሬት አስመልክቶ ቅሬታዉን ለመደበኛ ፍርድ ቤት ማቅረብ እንደሚችል ያስገነዝባል፡፡

በተያዘው ጉዳይ የአመልካች የዳኝነት ጥያቄ አሥተዳደሩ ለሕዝብ ጥቅም ሲባል በወሰደው የእርሻ መሬት ይዞታ ላይ ካሳ ያልተከፈለዉ ወይም ትክ ቦታ ያልተሰጠዉ መሆኑን መሰረት አድርጎ ዳኝነት የጠየቀ ሲሆን ከክርክሩ መገንዘብ እንደሚቻለዉ ከጅምሩም ካሳ ወይም ትክ መሬት ያልተሰጠዉ መሆኑና ለዚህም አስተዳደራዊ መፍትሄ ፍለጋ ያቀረበዉ አቤቱታ ምላሽ ያልተሰጠዉ መሆኑን ነዉ፡፡በመሰረቱ ከአዋጅ ቁ/455/97 አንቀጽ 3/1/ላይ እንደተደነገገዉ የገጠር መሬት ሲሆን የወረዳዉ አስተዳደር መሬቱን ከማስለቀቁ በፊት ተገቢዉ ካሳ ስለመከፈሉ የማረጋገጥ ግዴታ አለበት፡፡ በዚህ ጉዳይ ግን የአመልካች የእርሻ መሬት ለመንገድ ስራ መወሰዱ በተጠሪዎች የታመነ ጉዳይ ሆኖ ካሳም ሆነ ትክ መሬት ለአመልካች ስለመሰጠቱ ክርክር ያልቀረበበት ሆኖ በአስተዳደር አካልም መፍትሄ ካልተሰጠዉ ለፍርድ ቤት አቤቱታ ሲቀርብ የዳኝነት ስልጣን የለዉም የሚለዉ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገመንግሥት አንቀጽ 37 ላይ የተመለከተውን የዜጎች ፍትሕ የማግኘት መብታቸውን የሚጻረር ነው፡፡

በመሆኑም በስር ፍርድ ቤት ዳኝነት የጠየቀበት ጉዳይ የገጠር መሬት ይዞታ ላይ በመሆኑ በህገ መንግስትና በአዋጅ ቁ/455/97 አንቀጽ 11/1/ ድንጋጌዎች ጋር ተገናዝቦ ሲታይ መደበኛዉ ፍርድ ቤት አከራክሮ ዳኝነት ሊሰጥበት የሚገባዉ በመሆኑ የስር ፍርድ ቤት የዳኝነት ስልጣን የለኝም በሚል የሰጠዉ ብይንና ይህንኑ በማጽናት የበላይ ፍርድ ቤቶች የሰጡት ዉሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል ብለናል፡፡በዚህም ምክንያት ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

## <u>ው ሳ ኔ</u>

1. በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ቀርሳ ማሊማ ወረዳ ፍ/ቤት በመ.ቁ 20990 ጥቅምት 27 ቀን 2010 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ፤የደቡብ ም/ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 42674 በ17/07/2010ዓ.ም የሰጠው ዉሳኔ እና የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት በመ.ቁ290177 በ06/12/2010ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 348/1 መሠረት ተሽሯል፡፡
2. የቀርሳ ማሊማ ወረዳ ፍ/ቤት ከላይ በፍርድ ሐተታው ላይ በተገለጸው አግባብ ጉዳዩን አከራክሮ ተገቢውን እንዲወስን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 341/1 መሠረት ጉዳዩ ተመልሶለታል፡፡ይጻፍ፡፡
3. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪ ግራቀኙ የየራሣቸውን ይቻሉ፡፡

-መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ብ/ግ

**የሰ/መ/ቁ** - 169864

**ቀን** - 28/09/2011

**ዳኞች**፡- ተኽሊት ይመሰል

ተፈሪ ገብሩ (ዶ/ር)

ቀነዓ ቂጣታ

ተሾመ ሽፈራዉ

ፀሐይ መንክር

አመልካች፡- ወ/ሮ ብርሃን ማለዶ

ተጠሪ፡- የባህር ዳር ከተማ ጣና ክ/ከተማ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍ ር ድ**

ለዚህ ፍርድ መነሻ የሆነዉ ጉዳይ የተጀመረዉ በባሕር ዳር ከተማ አስተዳደር ከተማ ነክ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ሲሆን፣ አመልካች ከሳሽ ተጠሪ ደግሞ ተከሳሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡

የአመልካች ክስ ይዘትም በአጭሩ፡- በባሕር ዳር ከተማ ጣና ክ/ከተማ ክልል ዉስጥ በ1988 ዓ.ም በስጦታ ተሰጥቶኝ በእጄ አድርጌ ግብር እየከፈልኩ ለረጅም ዓመታት ብሎኬት የማምረት ስራ እየሰራሁና ትንሽ መኖሪያ ቤትም በመስራት ስጠቀምበት የቆየሁ ሲሆን በነባር ይዞታነትም ቀበሌዉ አረጋግጦ ጊዜያዊ የይዞታ ማረጋገጫ ተሰጥቶኛል፤ ከ1996 ዓ.ም ጀምሮ ግብር እየከፈልኩ የንግድ ፍቃድ አዉጥቼ የብሎኬት ስራ ስሰራ የቤ/ቁጥር D-247 በሚል ተሰጥቶኝ የዉሃ እና የቴሌ አገልግሎት ክፍያዎችን እየከፈልኩ እና ቦታዉን ህጋዊ አድርጌ በመያዜ በመመሪያ ቁጥር 8/2007 መሠረት የይዞታ ማረጋገጫ ከተሰጠኝ በኋላ ተከሳሽ ያለበቂ እና ህጋዊ ምክንያት በቀን 22/10/2009 ዓ.ም በፃፈዉ ደብዳቤ ይዞታዬን ማምከኑ መብቴን የሚጥስና ይዞታዬንም የሚያሳጣኝ በመሆኑ ማረጋገጫዉ ሊመክን አይገባም እንዲባልልኝ እንዲሁም ቋሚ የይዞታ ማረጋገጫ ደብተር ተሰርቶ እንዲሰጠኝ ይወሰንልኝ የሚል ነዉ፡፡

ተጠሪ የመጀመሪያ መቃወሚያዎች ናቸዉ የሚላቸዉን ክርክሮች በማስቀደም ለክሱ በሰጠዉ መልስ፡- ከሳሽ መመሪያ ቁጥር 8/2007 ሰነድ አልባና የተሟላ ሰነድ የሌላቸዉን ይዞታዎች በተመለከተ የወጣውን መስፈርት ባለማሟላታቸው አጣሪ ኮሚቴዉ ባለይዞታ አይደሉም በማለት ያቀረበዉን የዉሳኔ

ሃሳብ በመቃወም እስከ ከንቲባ ጽ/ቤት ቀርቦ ታይቶ ባለይዞታ አለመሆናቸዉ በመረጋገጡ የይዞታ ማረጋገጫ አልተሰጣቸዉም፤ አመራሩ አዲስ በመሆኑ በ2009 ዓ.ም የይዞታ ማረጋገጫ ለከሳሽ የሰጣቸዉ ቢሆንም በድጋሚ ማጣራት ተደርጎ ያላግባብ መሆኑ ተረጋግጦ ሰኔ 12 ቀን 2009 ዓ.ም እንዲመክን መደረጉን እና ይህም ተገቢ መሆኑን፤ ከሳሽ ያቀረቡት የስጦታ ዉልም ህጋዊ ባለመሆኑ በማስረጃነት የሚያገለግል አለመሆኑን፤ ባለ ይዞታዎቹ አቶ መለስ ካሴ እና ልጆቹ ትክና ካሳ ተከፍሎአቸዉ ቦታዉን እንዲለቁ መደረጉን፤ ቦታዉ የመንግስትና የህዝብ በመሆኑ በቦታዉ ላይ ተሰራ የተባለዉ ቤትም ህገ ወጥ መሆኑን ጠቅሶ የቀረበበት ክስ ዉድቅ እንዲሆንለት ተከራክሯል፡፡

ጉዳዩን በመጀመሪያ የተመለከተዉ ፍርድ ቤትም ከግራ ቀኝ በዚህ መልኩ የቀረበዉን ክርክር እና ማስረጃ ከሰማ በኋላ ከሳሽ ቦታዉ በስጦታ የተሰጣቸዉ መሆኑን የሚያሳይ ማስረጃ አለማቅረባቸዉን እና ሌሎች ከሳሽ ያቀረቧቸዉ ሰነዶችም ሰነድ የሌላቸዉና ሰነድ አልባ ይዞታዎችን በማጣራት ህጋዊ የይዞታ ማረጋገጫ የሚሰጥበትን ሁኔታ በተመለከተ በመመሪያ ቁጥር 8/2007 አንቀጽ 4(5) ላይ የተመለከተዉን መስፈርት የሚያሟላ ማስረጃ ከሳሽ አለማቅረባቸዉ በመጥቀስ የቀረበዉን ክስ ዉድቅ በማድረግ ወስኗል፡፡ አመልካች ይህን ዉሳኔ ባለመቀበል ለባህር ዳር ከተማ ነክ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ያቀረቡት ይግባኝ ተቀባይነት ባለማግኘቱ ለአብክመ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አቤቱታ ያቀረቡ ቢሆንም፣ ሰበር ሰሚዉ ችሎትም መዝገቡን አስቀርቦ የግራ ቀኝ ክርክር ከሰማ በኋላ በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጠዉን ዉሳኔ በማጽናት በአብላጫ ድምጽ ወስኗል፡፡

ይህ የሰበር አቤቱታ የቀረበዉም ይህኑን ዉሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ሲሆን፣ አመልካች በቀን 23/05/2011 ዓ.ም ተጽፎ በጠበቃቸዉ አማካይነት በቀረበ አምስት ገጽ የሰበር አቤቱታ በስር በክልሉ በየደረጃዉ ባሉት ፍርድ ቤቶች የተሰጠዉ ዉሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ የሚሉባቸዉን ምክንያቶች በመዘርዘር ታርሞ ይወሰንላቸዉ ዘንድ ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡ አቤቱታዉ ተመርምሮም ቀደም ሲል በመ/ቁጥር 2847 ላይ የተሰጠዉ ዉሳኔ አሁን በተያዘዉ ጉዳይ ላይ ያለዉን ተፈፃሚነት እንዲሁም ለሰበር አቤቱታዉ ምክንያት የሆነዉን ዉሳኔ ከመመሪያ ቁጥር 8/2007 አንፃር አገናዝቦ ለመመርመር ሲባል ያስቀርባል በመባሉም ተጠሪ በተደረገለት ጥሪ መሰረት ቀርቦ ግራ ቀኝ ክርክራቸዉን በጽሑፍ ተለዋዉጠዋል፡፡

ከስር ጀምሮ የጉዳዩ አመጣጥ እና የግራ ቀኝ ክርክር ይዘት አጠር አጠር ባለ መልኩ ሲታይ ከላይ የተመለከተዉ ሲሆን፣ ይህ ችሎትም መዝገቡን ለማስቀረብ የተያዘዉን ጭብጥ ከግራ ቀኝ ክርክር እና ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸዉ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መዝገቡን እንደሚከተለዉ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረዉም ለክርክሩ መነሻ የሆነዉ ቦታ ከ1988 ዓ.ም ጀምሮ አመልካች ይዘዉ የሚገኙ ስለመሆኑ ተጠሪ ክዶ አልተከራከረም፡፡ አመልካች በቦታዉ ላይ በሰሩት ቤት ቁጥር ላይ የንግድ ፍቃድ በማዉጣት የብሎኬት ማምረቻ ስራ ሲሰሩበት እንደነበረ ጠቅሰዉ አመልካች ያቀረቡት ክርክርም በተጠሪ

አልተካደም፡፡ አመልካች በይዞታዉ ላይ የሰሩት ቤት ህገ ወጥ መሆኑን ጠቅሶ የሰጠዉ ማስጠንቀቂያ ሁከት ነዉ በሚል አመልካች በተጠሪ ላይ ያቀረቡትን የሁከት ይወገድልኝ ክስ መሠረት በማድረግ የባህር ዳር ከተማ አስተዳደር ከተማ ነክ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 2847 ላይ በቀን 01/03/2010 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት በሰጠዉ ዉሳኔ አመልካች በቦታዉ ላይ ግንባታ ያከናወኑት አግባብ ባለዉ የከተማ አስተዳደር አካል የግንባታ ፍቃድ ተሰጥቶአቸዉ መሆኑን አረጋግጦ ሁከት እንዲወገድ የሚል ዉሳኔ መስጠቱን ከመዝገቡ መረዳት ተችሏል፡፡ ፍርድ ቤቱ በዚህ መልኩ ለሰጠዉ ዉሳኔ መነሻዉ የሁከት ይወገድልኝ ክስ ሆኖ ለተሰጠዉ ዉሳኔ በምክንያትነት የተጠቀሰዉ አመልካች ቤቱን የገነቡት ስልጣን ያለዉ አካል በሰጣቸዉ የግንባታ ፍቃድ መሠረት መሆኑ እንጂ ለክርክሩ መነሻ በሆነዉ ቦታ ላይ ህጋዊ ባለይዞታ መሆናቸዉ ተረጋግጦ ባለመሆኑ ለያዝነዉ ጉዳይ መነሻ የሆነዉ ክስ እንዳይቀርብ የሚከለክለዉ (resjudicata) ባይሆንም፣ ዉሳኔዉ አመልካች በቦታዉ ላይ ቤት የሰሩት በተጠሪ ዕዉቅና እና ፍቃድ ስለመሆኑ አረጋጋጭ ነዉ፡፡ ከዚህም አልፎ አመልካች ቦታዉን የያዙት በ1988 ዓ.ም አጎታቸዉ አቶ መለስ ካሴ ሰጥተዉቸዉ ስለመሆኑ በሰዉ እና በሰነድ ማስረጃ የተረጋገጠ ሲሆን፣ ስጦታዉን አድርገዋል የተባሉት ሰዉም በምስክርነት ቀርበዉ ቦታዉን ለአመልካች እንደሰጡ ማስረዳታቸዉን የስር ፍርድ ቤት ዉሳኔ ግልባጭ ያሳያል፡፡ ቦታዉን ሰጥተዋል የተባሉት አቶ መለስ ካሴ ቦታዉን ለመንግስት አስረክበዉ ትክ ቦታ ለእርሳቸዉ እና ለቤተሰባቸዉ ተሰጥቷል የሚል ክርክር ተጠሪ በስር ፍርድ ቤት አንስቶ የተከራከረ ቢሆንም ይህን የሚያረጋግጥ ማስረጃ አላቀረበም፡፡

ይህ ሁሉ የሚያሳየዉ አመልካች ይዞታዉ ወደ ከተማ ከመጠቃለሉ በፊት ከ1988 ዓ.ም ጀምሮ ይዞታዉን በእጃቸዉ አድርጎ ሲጠቀሙበት እንደነበረ እና ቦታዉ በከተማ ስር ከገባ በኋላም ለረጅም ዓመታት በቤትና ቦታዉ ላይ የንግድ ፍቃድ በማዉጣት እና በከተማዉ ጉዳዩ ከሚመለከታቸዉ አካላት ዕዉቅና ተሰጥቶ የግንባታ ፍቃድ ሁሉ በማዉጣት ቤት ሰርተዉ ሲጠቀሙበት የነበሩ መሆኑን ነዉ፡፡ የሚመለከተዉ አካል በቦታዉ ላይ ጊዜያዊ የይዞታ ማረጋገጫ ለአመልካች ሊሰጥ የቻለዉም ይህኑን እዉነታ ግምት ዉስጥ በማስገባት እንደሆነ ይታመናል፡፡ የይዞታ ማረጋገጫ የተሰጠዉ ሰዉ በይዞታ ማረጋገጫዉ ላይ በተመለከተዉ ንብረት ላይ የባለቤትነት/የባለይዞታነት መብት እንዳለዉ የሚገመት ስለመሆኑ የፍትሐብሔር ህጉ አንቀጽ 1195 ድንጋጌ ያስገነዝባል፡፡ ከዚህ የፍሬ ነገር ግምት ጀርባ ያለዉ መሠረተ ሃሳብም የሚመለከተዉ አካል የይዞታ ማረጋገጫ ማስረጃን ሲሰጥ በህግ የተዘረጋዉን ተገቢዉን ስርዓት ተከትሎ የይዞታ ማረጋገጫዉ ማስረጃ የተሰጠዉ ሰዉ በማስረጃዉ ላይ በተመለከተዉ ንብረት ላይ መብት ያለዉ መሆኑን በማረጋገጥ ነዉ ተብሎ ስለሚታመን ስለመሆኑ መገንዘቡ ተገቢ ነዉ፡፡ የይዞታ ማረጋገጫዉ ማስረጃ የሰጠ አካል በህጉ አንቀጽ ማስረጃዉ የተሰጠዉ ያላግባብ መሆኑን ከተረዳ የባለቤትነት/የይዞታ ማረጋገጫዉን የማምከን ስልጣን ያለዉ ቢሆንም፣ ማስረጃዉን ለማምከን የሚያስችል በቂ እና በህግ ተቀባይነት ያለዉ ምክንያት ሊኖረዉ እንደሚገባ በህጉ አንቀጽ 1196 ላይ ከተመለከተዉ ድንጋጌ መንፈስ የምንገነዘበዉ ነዉ፡፡

የተያዘዉን ጉዳይ በተመለከተ ተጠሪ ለአመልካች ተሰጥቶ የነበረዉን ጊዜያዊ የይዞታ ማረጋገጫ ማምከን የቻለዉ አመልካች መመሪያ ቁጥር 8/2007 ሰነድ አልባና የተሟላ ሰነድ የሌላቸዉን ይዞታዎች በተመለከተ የወጣዉን መስፈርት ባለማሟላታቸዉ እና የይዞታ ማረጋገጫዉን የሰጠዉ አመራርም አዲስ መሆናቸዉን ሲሆን፣ የስር የክልሉ ፍርድ ቤቶች የአመልካችን የዳኝነት ጥያቄ ዉድቅ በማድረግ ለሰጡት ዉሳኔ መሰረት ያደረጉን አመልካች ቦታዉ በስጦታ የተሰጣቸዉ መሆኑን እና በህግ አግባብ የያዙ መሆኑን የሚያሳይ ማስረጃ አለመቅረባቸዉን እና ይዞታዉ ህጋዊ እንዲሆን በመመሪያ ቁጥር 8/2007 አንቀጽ 4(5) ላይ የተመለከተዉን መስፈርት አመልካች አለመሟላታቸዉን ስለመሆኑ ተመልክተናል፡፡ መመሪያ ቁጥር 8/2007 ዓ.ም በክልሉ ከተሞች ዉስጥ የተሟላ ሰነድ የሌላቸዉና ሰነድ አልባ ይዞታዎችን በማጣራት የይዞታ ማረጋገጫ ሰነድ/ካርታ ለመስጠት ተሻሽሎ የወጣ ነዉ፡፡ ይህ መመሪያ በክፍል ሁለት የተሟላ ሰነድ የሌላቸዉና የሰነድ አልባ ይዞታዎች መለያ መስፈርቶችን ይደነግጋል፡፡ ለዚህ ክርክር መነሻ የሆነዉ ይዞታ የገጠር የእርሻ መሬት የነበረ በመሆኑ ተፈፃሚነት ያለዉ ድንጋጌ በአንቀጽ 4(5) ላይ የተመለከተዉ ነዉ፡፡ ይህ ድንጋጌ "በአርሶ አደር የእርሻ መሬት ይዞታ ላይ ያልተሰራ ቤት ሆኖ ነገር ግን ከተማዉ ወይም ቀበሌዉ በምሪት የተያዙ ህጋዊ ይዞታዎች ስለመሆናቸዉ ማረጋገጫ የሚሰጣቸዉ ሆነዉ ለሦስተኛ ወገን የተላለፉና የባህላዊ ግዥ ወይም ስጦታ ዉል ማስረጃ ማቅረብ የሚችሉ እና ቤት የተሰራባቸዉ ይዞታዎች" በማለት ይደነግጋል፡፡ አመልካች ለክርክሩ መነሻ የሆነዉን ይዞታ ያገኙት ከመንግስት በምሪት ሳይሆን በስጦታ መሆኑን በመግለጽ ይከራከራሉ፡፡ መሬቱን በስጦታ ከአጎታቸዉ ስለማግኘታቸዉ ባቀረቡት ማስረጃ አረጋግጠዋል፡፡ የስር የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ይህን ስጦታ ዉድቅ ለማድረግ በምክንያትነት ከጠቀሰዉ ዉስጥ አንዱ የስጦታ ዉሉ በሚመለከተዉ የአስተዳደር አካል ዘንድ አለመመዝገቡን ነዉ፡፡ ይሁንና ከፍ ሲል የተመለከተዉ ድንጋጌ "የባህላዊ ግዥ ወይም ስጦታ" በሚል ሲደነግግ ይዞታዉ የእርሻ መሬት ሲሆን አንድ ሰዉ በስጦታ የሰነድ አልባ ይዞታ መብት ያለዉ መሆኑን ለማስረዳት የገጠር መሬትን በስጦታ ለማስተላለፍ በሚመለከተዉ ህግ የተመለከተዉን ጥብቅ ድንጋጌ መከተል አስፈላጊ አለመሆኑን ለማስገንዘብ እንደሆነ መገንዘቡ ተገቢ ነዉ፡፡ ይህ የሆነበት ምክንያትም አንድ ሰዉ ይዞታዉ በገጠር ቀበሌ ስር በነበረበት ወቅት ለረጅም ጊዜ ይዞ ሲጠቀምበት የነበረዉን መሬት ቦታዉ በከተማ ስር በመግባቱ ምክንያት እንዳይፈናቀል ጥበቃ ለማድረግ ታስቦ እንደሆነ ይታመናል፡፡ ከመመሪያዉ አፈፃፀም ጋር በተያያዘ የሚሰጥ ትርጉምም ይህኑን ግምት ዉስጥ ያስገባ ሊሆን ይገባል የሚል እምነት አለን፡፡

በአጠቃላይ አመልካች ለክርክሩ መነሻ የሆነዉን ይዞታ በስጦታ አግኝተዉ ለረጅም ዓመታት ይዘዉ በሚመለከታቸዉ የመንግስት አካላት ዕዉቅና ሲጠቀሙበት የነበረዉ ይዞታ መሆኑ ተረጋግጦ እያለ በመመሪያ ቁጥር 8/2007 መሰረትም ተጠቃሚ ሊሆኑ አይችሉም በሚል በከተማዉ የከተማ ነክ ፍርድ ቤቶች ተሰጥቶ በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በአብላጫ ድምፅ የፀናው ዉሳኔ

በግራ ቀኝ ክርክር የተረጋገጠዉን ፍሬ ነገር እንዲሁም የመመሪያ ቁጥር 8/2007 አንቀጽ 4(5) ትክክለኛ አፈፃፀም ያላገናዘበ በመሆኑ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ ብለን ተከታዩን ወስነናል፡፡

**ው ሳ ኔ**

1. የብህር ዳር ከተማ ከተማ ነክ የመጀመሪያ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 2945 በቀን 17/08/2010 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠው ውሳኔ፣ የከተማ ነክ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት 1041/2010 ዓ.ም በቀን 15/09/2010 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠው ትዕዛዝ፤ እንዲሁም የአማ/ብ/ክ/መ/ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 78578 በቀን 12/03/2011 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥርዓት ህጉ አንቀጽ 348(1) መሠረት ተሽረዋል፡፡
2. ለክርክሩ መነሻ የሆነውን ቤትና ይዞታ በተመለከተ ለአመልካች ተሰጥቶ የነበረው ጊዜያዊ የይዞታ ማረጋገጫ ማስረጃ ሰኔ 22 ቀን 2009 ዓ.ም ከተጠሪ በተፃፈ ደብዳቤ መምከኑ በአግባቡ አይደለም ብለናል፡፡
3. አመልካች ለክርክሩ መነሻ በሆነው ቤትና ይዞታ ላይ በክልሉ ከተሞች ውስጥ የተሟላ ሰነድ የሌላቸውና ሰነድ አልባ ይዞታዎችን በማጣራት የይዞታ ማረጋገጫ ሰነድ/ካርታ ለመስጠት ተሻሽሎ በወጣ መመሪያ ቁጥር 8/2007 መሠረት የመስተናገድ መብት አላቸው ብለናል፡፡
4. ይህ ችሎት በቀን 11/07/2011 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠው የእግድ ትዕዛዝ ተነስቷል፡፡
5. በዚህ ችሎት የተደረገዉ ክርክር ያስከተለውን ወጪ እና ኪሳራ ግራ ቀኝ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡

**መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ**

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ሠ/ኃ

የሰ.መ.ቁ 179827

ታሕሳስ 20 ቀን 2012 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** እትመት አሠፋ

ጳውሎስ ኦርሾሶ

ፀሐይ መንክር

መላኩ ካሣዬ

እስቲበል አንዱዓለም

አመልካቾች፡- ካሱ ምስጋናው ቀረቡ፡፡

ተጠሪዎች፡- ጥላዬ አስረስ አልቀረቡም፡፡

መዝገቡ ለምርመራ የተቀጠረ ነው፡፡ በመሆኑም መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**<u>ፍርድ</u>**

የሰበር አቤቱታው ሊቀርብ የቻለው አመልካች ሠኔ 25 ቀን 2012 ዓ.ም ጽፈው ባቀረቡት የሰበር አቤቱታ በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የጋዞ ወረዳ ፍ/ቤት በመ.ቁ 0104609 ግንቦት 29 ቀን 2010 ዓ.ም የአመልካች ክስ በይርጋ ይታገዳል በማለት የሰጠው ብይን፤ ይህንኑ ብይን በማጽናት የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 01-07464 ግንቦት 12 ቀን 2011 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ እና የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 0326324 የሰጠው ትዕዛዝ መሠረታዊ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት አቤቱታ በማቅረባቸው ነው፡፡

ጉዳዩ የገጠር ሣር መሬት ክርክርን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የጋዞ ወረዳ ፍ/ቤት ነው፡፡ በሥር ፍ/ቤት በተደረገው ክርክር የአሁን አመልካች ከሳሽ፤ የአሁን ተጠሪ ደግሞ ተከሳሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡ የአሁን አመልካች በሥር ፍ/ቤት ያቀረቡት ክስ ይዘት በአጭሩ፡- በጋዞ ወረዳ 11 ቀበሌ ልዩ ስሙ ግመል ተራራ ከሚባለው ቦታ የሚገኘውን እና አዋሳኙ በምስራቅ የምንሹ አዳነ ሳር፤ በምዕራብ የሞላልኝ ደሳለኝ ሣር፤ በደቡብ የመኮንን ታረቀ እርሻ በሰሜን ወንዝ የሆነውን የሳር መሬት በ1983 ዓ.ም በተመን የተሰጣቸው እና በይዞታ ማረጋገጫ የተመዘገበላቸው ይዞታቸው መሆኑን እና ተጠሪ መሬቱን ከ2006 ዓ.ም ጀምሮ የነጠቃቸው መሆኑን በመግለጽ በፍርድ ሀይል እንዲመለስላቸው ይወሰንላቸው ዘንድ ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ የአሁን ተጠሪ በሰጡት መልስ የአመልካች ክስ በይርጋ የሚታገድ መሆኑን በመግለጽ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ አቅርበዋል፡፡

ጉዳዩ የቀረበለት ፍ/ቤትም የግራቀኙን ምስክሮች ከሰማ እና ስለጉዳዩም ከወረዳው መሬት አስተዳደር እና አጠቃቀም ጽ/ቤት ተጣርቶ እንዲቀርብለት ካደረገ በኋላ ተጠሪ ክስ የቀረበበትን መሬት ከ20 ዓመት በላይ የያዘ መሆኑን በቀረበው ማስረጃ ተረጋግጧል፤ የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 69302 በአርሶ አደሮች መካከል የሚነሱ የገጠር መሬት ክርክሮች በ10 ዓመት ይርጋ ቀሪ እንደሚሆን አስገዳጅ የሕግ ትርጉም ሰጥቶበታል፤ የክልሉ የገጠር መሬት ሕግ አዋጅ ቁጥር 252/09 አንቀጽ 55 ከሕግ ውጪ እና በወረራ የተያዙ መሬቶችን አስመልክቶ የይርጋ መቃወሚያ ተፈጻሚ እንደማይሆን የሚያመለክት ቢሆንም ተጠሪ ይዞታውን የያዘው ባለይዞታዎቹ በሰጡት መሬት በመቀላቀል በመሆኑ በአዋጁ ከተጠቀሱት ሁኔታዎች ውጪ ነው፤ አመልካች መሬቱን በ1983 ዓ.ም የተሰጣቸው ቢሆንም መሬቱን ከ1984 ዓ.ም በኋላ ያልተጠቀሙበት እና ተጠሪ እንዲመልስላቸው ያልጠየቁ በመሆኑ ያቀረቡት ክስ በይርጋ የሚታገድ ነው በማለት ብይን ሰጥቷል፡፡

አመልካች ይህን ውሳኔ በመቃወም ለሰሜን ወሎ ዞን አስተዳደር ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የይግባኝ አቤቱታ አቅርበዋል፡፡ ይግባኙ የቀረበለት ፍ/ቤት ግራቀኙን ካከራከረ በኋለ በስር ፍ/ቤት ከተሰማው ማስረጃ ተጠሪ ይዞታውን የያዘው ሕጋዊ ባልሆነ መንገድ በመሆኑ የይርጋ መቃወሚያው በአዋጅ ቁጥር 252/09 አንቀጽ 55 መሠረት ሕጋዊ ውጤት የለውም፤ አመልካች የአከራካሪው መሬት ባለይዞታ ስለሆነች ተጠሪ መሬቱን ለአመልካች ሊለቅ ይገባል በማለት ወስኗል፡፡

ተጠሪ በበኩላቸው ይህን ውሳኔ በመቃወም ለክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የይግባኝ አቤቱታ አቅርበዋል፡፡ አቤቱታው የቀረበለት ፍ/ቤትም ግራቀኙን ካከራከረ በኋላ አከራካሪው መሬት በ1983 ዓ.ም ለአመልካች የተሰጠ ቢሆንም መሬቱን ትታው በመሄድዋ በሌሎች ግለሰቦች እጅ ከወደቀ በኋላ ከይዞታቸው በማዋጣት በ1984 ጀምሮ ሰጥተውት ከ20 ዓመት በላይ ይዞ የሚጠቀምበት በመሆኑ መሬቱን ይዞ ሲጠቀምበት የነበረው በሕገወጥ መንገድ ነው የሚያስብል ሆኖ አልተገኘም በማለት የስር ይግባኝ ሰሚው ከፍተኛው ፍ/ቤት የሰጠውን ውሳኔ በመሻር የወረዳው ፍ/ቤት የሰጠውን ውሳኔ አጽንቷል፡፡ አመልካች በተራቸው ይህን ውሳኔ በመቃወም ለክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አቤቱታ ያቀረቡ ቢሆንም አቤቱታቸው በትዕዛዝ ውድቅ ተደርጓል፡፡

የሰበር አቤቱታው የቀረበው ይህን ውሳኔ በመቃወም መሠረታዊ የሕግ ስሕተት ተፈጽሞበታል በሚል ሲሆን ይዘቱም፡- አከራካሪው የሳር መሬት በ1983 ዓ.ም ለአመልካች በድልድል የተሰጠኝ ሲሆን የይዞታ ማረጋገጫውም በስሜ ተመዝግቧል፤ ተጠሪ ምንም መብት ሳይኖረው መያዙ በተረጋገጠበት ሁኔታ የወረዳው ፍ/ቤት እና በክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት የአመልካች ክስ በይርጋ ይታገዳል በማለት የሰጡት ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት በመሆኑ በሰበር ታይቶ ሊታረም ይገባል የሚል ነው፡፡

የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ በክሱ የተገለጸው የመሬት አዋሳኝ ለአመልካች ጥቅምት 06 ቀን 2004 ዓ.ም በተሰጣቸው የመሬት ይዞታ ማረጋገጫ ደብተራቸው ተ.ቁ 11 ተመዝግቦ እያለ የወረዳው

መሬት አስተዳደር ጽ/ቤት የመሬቱ አዋሳኝ የተለየ መሆኑን እና መሬቱ በ1983 ዓ.ም ለአመልካች እና ለእናታቸው የተሰጠ ቢሆንም ተጠሪ ከ1984 ዓ.ም ጀምሮ እየተጠቀመበት ቆይቷል በሚል የሰጠውን ምላሽ መሠረት በማድረግ የአመልካች ክስ በይርጋ ይታገዳል በማለት የመወሰኑን አግባብነት ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ በዚህ ችሎት እንዲታይ ተደርጓል፡፡ ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎም ግራቀኙ በጽሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

የተጠሪ መልስ ይዘት በአጭሩ፡- ተጠሪ አከራካሪውን መሬት ከ1983 ዓ.ም ጀምሮ በመያዝ ግብር የምገብርበት እና የምጠቀምበት መሆኑ በማስረጃ ተረጋግጧል፤ የይዞታው አዋሳኝ በአመልካች ደብተር ላይ መመዝገቡ አመልካች መብት እንዳላት የማያሳይ በመሆኑ ክሱ በይርጋ ይታገዳል በማለት የተሰጠው ወሳኔ ተገቢ ስለሆነ ሊጸና ይገባል የሚል ነው፡፡ አመልካችም የሰበር አቤቱታቸውን በማጠናከር የመልስ መልስ ሰጥተዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ በአጭሩ ከላይ የተገለጸው ነው፡፡ ይህ ችሎትም በሰበር አጣሪው ችሎት ሊጣራ ይገባዋል ተብሎ የተያዘውን ነጥብ ከግራቀኙ ክርክር፤ ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸው ሕጎች ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው መርምሮታል፡፡

አከራካሪው የሳር መሬት በ1983 ዓ.ም ለአመልካች እና ለእናታቸው ለወ/ሮ ሙሉ ወርቁ የተሰጠ መሆኑን፤ ተጠሪ አከራካሪውን መሬት ከ1984 ዓ.ም ጀምሮ ይዞ የሚጠቀምበት መሆኑን፤ ተጠሪ መሬቱን ሊይዝ የቻለው ካሳ አበበ ምላሹ አዳነ እና ሞላልኝ ደሳለኝ የተባሉ የአካባቢው ሰዎች ሳራችንን ጠብቅልን በማለት ሁለት ሁለት ዘንግ ሰጥተውት ስለነበር በዚሁ ምክንያት ክስ የተመሰረተበትንም መሬት የያዘ መሆኑን ፍሬነገርን የማጣራት እና ማስረጃን የመመዘን ስልጣን ባላቸው የስር ፍ/ቤቶች ተረጋግጧል፡፡ በመሆኑም በስር ፍ/ቤት ከተረጋገጠው ፍሬነገር አንጻር በየደረጃው ያሉ ፍ/ቤቶች የሰጡት ውሳኔ አግባብነት ከአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የገጠር መሬት አስተዳደር እና አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር 252/2009 አንቀጽ 55 ድንጋጌ እና ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት የገጠር መሬትን አስመልክቶ በሚቀርቡ ክርክሮች ላይ የይርጋ ተፈጻሚነትን አስመልክቶ ከተሰጠው አስገዳጅ የሕግ ትርጉም ጋር በማገናዘብ ምላሽ ሊሰጠው የሚገባ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ.መ.ቁ 69302 እና በሌሎችም በርካታ መዛግብት በሰጠው ውሳኔ የገጠር መሬትን አስተዳደር እና አጠቃቀም በሚመለከት የወጡ ሕጎች የእርሻ መሬት ባለይዞታና የመጠቀም መብቴ በሌላ ሰው ተደፍሮብኛል የሚል አርሶ አደር የመሬት ባለይዞታነትና የመጠቀም መብቱን ለማስከበር ክስ ማቅረብ ያለበት በስንት ጊዜ ውስጥ እንደሆነ የማይደነግጉ ቢሆንም የይርጋ ሕግ ድንጋጌ በሕገ መንግስቱ በተደነገገው የአርሶ አደሮች የመሬት ባለይዞታነት እና የመጠቀም መብት በማያጣብብ ሁኔታ አግባብነት ካላቸው የፍትሐብሔር ሕጉ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ሊተረጎም እንደሚገባው፤ ማንኛውም አርሶ አደር ምክንያታዊ በሆነ የጊዜ ገደብ ውስጥ በእርሻ መሬት

ላይ ያለውን የይዞታና የመጠቀም መብት ለማስከበር ተገቢውን ትጋት የማድረግ ግዴታ ያለበት መሆኑን፤ በፍ/ብ/ሕ/ቁ 1677/1/ እና 1845 የተደነገገው የአሥር ዓመት የይርጋ የጊዜ ገደብ አርሶ አደሮች በሕገ መንግስቱ የተከበረላቸውን የመሬት ባለይዞታነትና በመሬት የመጠቀም መብት በፍርድ ከስሰው ለማስከበር ሰፋ ያለ ዕድል የሚሰጥ መሆኑን እና ይዞታውን በሌላ ሰው የተነጠቀ አርሶ አደር ወይም ወራሾቹ ይዞታው በሌላ ሰው ከህግ ወይም ከውል ውጭ ከተያዘበት ቀን ጀምሮ በአስር ዓመት ውስጥ የእርሻ መሬት የባለይዞታነትና የመጠቀም መብቱን ለማስከበር ክስ ካላቀረበ ክሱ በአሥር ዓመት የይርጋ የጊዜ ገደብ እንደሚታገድ በመግለጽ በአዋጅ ቁጥር 454/97 አንቀጽ 2/1 መሠረት በየትኛውም እርከን ላይ ላሉ ፍ/ቤቶች አስገዳጅ የሆነ የሕግ ትርጉም ሰጥቶበታል፡፡

በሌላ በኩል የተሻሻለው የአማራ ብሔራው ክልላዊ መንግስት የገጠር መሬት አስተዳደር እና አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር 252/2009 አንቀጽ 55 የገጠር መሬትን በወረራ ወይም በሌላ ማናቸውም ሕገወጥ በሆነ መንገድ ይዞ በመገልገል ላይ የሚገኝ ማናቸውም ሰው መሬቱን እንዲለቅ በማንኛውም ሌላ ሰው ወይም ስልጣን ባለው የመንግስት አስተዳደር አካል ሲጠየቅ ወይም በመደበኛ ፍ/ቤ ሲከሰስ የይርጋ ጊዜ ገደብን በስነ-ስርዓት መቃወሚነት ሊያነሳ አይችልም በማለት ይደነግጋል፡፡ የዚሁ ሕግ አንቀጽ 2/39 ሕገወጥ ይዞታ ማለት ሕጋዊ ባልሆነ መንገድ የተያዘ እና አግባብ ባለው አካል እውቅና ያልተሰጠው ማናቸውም የገጠር መሬት ይዞታ ነው በማለት ይደነግጋል፡፡

የተሻሻለው የክልሉ የገጠር መሬት አስተዳደር እና አጠቃቀም አዋጅ ቁ/252/09 ስራ ላይ የዋለዉ ከጥቅምት 20 ቀን 2010ዓ.ም ጀምሮ በመሆኑ እና አመልካች ክስ ያቀረቡት የካቲት 20 ቀን 2010 ዓ.ም በመሆኑ ይርጋን አስመልክቶ በዚህ ሰበር ችሎት በሰ.መ.ቁ 69302 የተሰጠውን አስገዳጅ የሕግ ትርጉም ተሻሽሎ ከወጣው የክልሉ የገጠር መሬት ሕግ ጋር በሚጣጣም መልኩ ተገናዝቦ ውሳኔ ሊሰጥበት የሚገባ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

የወረዳው ፍ/ቤት እና የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የአመልካች ክስ በይርጋ ይታገዳል ከሚል መደምደሚያ ላይ ሊደርሱ የቻሉት አከራካሪው መሬት በ1983 ዓ.ም ለአመልካች የተሰጠ ቢሆንም መሬቱን ትታው በመሄድዋ በሌሎች ግለሰቦች እጅ ከወደቀ በኋላ ከይዞታቸው በማዋጣት በ1984 ዓ.ም ጀምሮ ለተጠሪ ሰጥተውት ከ20 ዓመት በላይ ይዞ የሚጠቀምበት በመሆኑ ተጠሪ ይዞታውን የያዘው በሕገወጥ መንገድ ነው ሊባል አይችልም በሚል ነው፡፡ ሆኖም ተጠሪ አከራካሪውን መሬት በክልሉ የገጠር መሬት ሕግ መሠረት በሚመለከተው የአስተዳደር አካል ተፈቅዶላቸው በሕጋዊ መንገድ የያዙት ስለመሆኑ ወይም አመልካች ፈቅደውላቸው የያዙት ስለመሆኑ የተረጋገጠ ፍሬነገር የለም፡፡ ተጠሪ አከራካሪውን መሬት በሕጋዊ መንገድ የያዙት ስለመሆኑ እስካልተረጋገጠ ጊዜ ድረስ ተጠሪ መሬቱን የያዙት በሕገወጥ መንገድ መሆኑ ግምት የሚወሰድበት በመሆኑ በአዋጅ ቁጥር 252/2009 አንቀጽ 55 እና 2/39 መሠረት የይርጋ መቃወሚያን በስነ-ስርዓት መቃወሚያነት ሊያነሱ

አይችሉም፡፡ በመሆኑም የወረዳው ፍ/ቤት እና የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ተጠሪ አከራካሪውን መሬት የያዘው በሕገወጥ መንገድ ነው ሊባል ስለማይችል የአመልካች ክስ በይርጋ ይታገዳል በማለት ብይን መስጠታቸው የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎትም ይህንኑ ሳያርም መቅረቱ ተሻሽሎ የወጣውን የክልሉን የገጠር መሬት አስተዳደር እና አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር 252/2009 አንቀጽ 55 እና 2/39 ድንጋጌዎች ይዘት ያላገናዘበ እና መሠረታዊ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ ስለሆነም ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

<u>ውሳኔ</u>

1. በአማራ ብሔራው ክልላዊ መንግስት የጋዞ ወረዳ ፍ/ቤት በመ.ቁ 0104609 ግንቦት 29 2010 ዓ.ም በሰጠው ብይን የአመልካች ክስ በይርጋ ይታገዳል በማለት የሰጠው ብይን፤ ይህንኑ ብይን በማጽናት የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 01-07464 ግንቦት 12 ቀን 2011 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ፤ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 0326324 የሰጠው ትዕዛዝ የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 348/1 መሠረት ተሽሯል፡፡
2. በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የሰሜን ወሎ ዞን አስተዳደር ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 24741 በቀን 13/10/2010 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 348/1 መሠረት ጸንቷል፡፡
3. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪ ግራቀኙ የየራሣቸውን ይቻሉ፡፡

- መዝገቡ ውሳኔ ስላገኘ ተዘግቷል፡፡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ፍ

# ንግድና ኢንሹራንስ

የሠ/መ/ቁ161598

የካቲት 13 ቀን 2011 ዓ.ም

ዳኞች፡….ተኽሊት ይመስል

ተፈሪ ገብሩ (ዶ/ር)

ቀነዓ ቂጣታ

ተሾመ ሽፈራዉ

ፀሐይ መንክር

አመልካች፡…… አቶ ሰለሞን በቀለ፦ ጠበቃ አቶ ዜና ደባሱ ቀርበዋል፡፡

ተጠሪ፡………. ኢትዮ ላይፍ ኤንድ ጄኔራል ኢንሹራንስ አ.ማ፦ የቀረበ የለም፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለዉ ፍርድ ተሰጥቷል።

**ፍርድ**

ይህ የሰበር ጉዳይ የተጀመረዉ በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ሲሆን፣የአሁን አመልካች ተከሳሽ፣የአሁን ተጠሪ ደግሞ ከሳሽ ሁኖ ሲከራከሩ ነበር።ይህ ጉዳይ ለዚህ ችሎት ሊቀርብ የቻለዉ የአሁን አመልካች የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ.214848 በ5/11/2010 ዓ.ም የሰጠዉን ትዕዛዝ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ እንዲታረምልኝ በማለት በማመልከታቸዉ ነዉ።

የጉዳዩ አመጣጥ ሲታይ ከሳሽ (የአሁን ተጠሪ) ባቀረቡት ክስ የተከሳሽ ንብረት የሆነዉ የሰሌዳ ቁጥር ኮድ 2-A77230 አ.አ የሆነዉ ተሽከርካሪ ከከሳሽ የ3ኛ ወገን መድን ሽፋን የተሰጠዉ ሲሆን፣ ይህ ተሽከርካሪ በ16/11/2008 ዓ.ም በቂርቆስ ክ/ከተማ መስከረም ማዞሪያ አካባቢ የ3ኛ ወገን ንብረት የሆነዉን የሰሌዳ ቁጥር ኮድ 2-A70206 አ.አ የሆነዉን ተሽከርካሪ ገጭቶ ጉዳት በማድረሱ ከሳሽ ብር 23,573.93 ለተጎጅዉ የከፈለ በመሆኑ፣ ተከሳሽ በመድን ዉሉ መሰረት ጉዳት መድረሱን ለከሳሽ የማሳወቅ ግዴታዉን ያልተወጣ ስለሆነ፣ ይህን ገንዘብ ክሱ ከቀረበበት ቀን ጀምሮ ከሚታሰብ ሕጋዊ ወለድ ጋር ተከሳሽ እንዲከፍለኝ እንዲወሰንልን በማለት ከሷል።

በዚህ ክስ ላይ ተከሳሽ ባቀረበዉ መልስ ከሳሽ የመድን ዉል መኖሩንና አደጋዉ መድረሱን በማመን ለፖሊስ ደብዳቤ የጻፈዉ በተከሳሽ አማካይነት አደጋ መድረሱን በማወቁ ነዉ፣ ተሽከርካሪዉ ወደ ተከሳሽ ስም መዛወሩን የባለቤትነት ማረጋገጫ ሰነድ በከሳሽ እጅ መገኘቱ ነዉ፣ ለደረሰዉ አደጋ ኃላፊነቱ የከሳሽ ነዉ በማለት ተከራክሯል።

ከዚህ በኂላ የሥር የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ጉዳዩን በመመርመር በሰጠዉ ዉሳኔ ከሳሽ ለተከሳሽ ተሽከርካሪ በሰጠዉ የ3ኛ ወገን የመድን ዉል ተከሳሹ ተጠቃሚ በመሆኑ፣ በዉሉ የተጣለበትን ቅድመ ሁኔታ ማለትም የደረሰዉን አደጋ ለከሳሽ የማሳወቅ ግዴታ የመወጣት ኃለፊነት አለበት፤ እንዲሁም በአዋጅ ቁጥር 799/05 አንቀጽ 17 [1] መሰረት የተመለከቱትን ቅድመ ሁኔታዎች መካከል አደጋን የማሳወቅ ግዴታ ነዉ። ተከሳሽ ፖሊስ የአደጋዉን ዝርዝር ሁኔታ ለከሳሽ እንዲገልጽ መጠየቃቸዉ አደጋ መድረሱን ከሳሽ እንዲያዉቅ የማድረግ ግዴታቸዉን ተወጥቷል ለማለት ስለማይቻል፤ ተከሳሽ በመድን

ዉልም ሆነ በአዋጁ አደጋን የማሳወቅ ግዴታዉን ስላልተወጣ፣ ከሳሽ በሕግ የተጣለበትን አደጋ የደረሰበትን 3ኛ ወገን ያለምንም ቅድመ ሁኔታ የመካስ ኃላፊነት ለመወጣት አደጋዉ ለደረሰበት 3ኛ ወገን የከፈለዉን ብር 23,573.93 ክስ ከቀረበበት ከ6/4/2010 ዓ.ም ጀምሮ ክፍያዉ እስኪጠናቀቅ ድረስ ከሚታሰብ 9% ወለድ ጋር ለከሳሽ እንዲከፍል፣ የተለያዩ ወጪዎችንም እንዲከፍል ወስኗል፡፡ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በዚህ ጉዳይ የቀረበለትን ይግባኝ ዉድቅ በማድረግ የሥር ዉሳኔ በማጽናት ወስኗል፡፡ የአሁን የሰበር አቤቱታ ያቀረበዉ ይህን ዉሳኔና ትዕዛዝ በመቃወም ለማሻር ነዉ፡፡

የአሁን አመልካች ሐምሌ 13 ቀን 2010 ዓ.ም በተጻፈ የሰበር አቤቱታ፡ ከተጠሪ የ3ኛ ወገን መድን ሽፋን የተሰጠዉ የአመልካች ንብረት የሆነዉ የሰሌዳ ቁጥር ኮድ 2-A77230 አ.አ የሆነዉ ተሽከርካሪ የ3ኛ ወገን ንብረት በሆነዉ የሰሌዳ ቁጥር ኮድ 2-A70206 አ.አ ተሽካርካሪ ላይ የግጭት አደጋ በማድረስ ጉዳት ያደረሰ መሆኑን በአመልካች ተሽከርካሪ ላይ አሽከርካሪ የነበረዉ አቶ ካሱ ወርዶፋ አማካኝነት የግጭት አደጋ በ16/11/2008 ዓ.ም መድረሱን ወዲያዉኑ በወቅቱ ማሳወቁን ተጠሪ አምነዉ ተከራክሯል፡፡ ተጠሪዉ በዚህ መሰረት አደጋ መድረሱን የአመልካች ተሽከርካሪ ሾፌር በማሳወቃቸዉ አደጋዉ በደረሰ በአራተኛዉ ቀን በ20/11/2008 ዓ.ም በአዲስ አበባ ከተማ ለቂርቆስ ክ/ከተማ ፖሊስ መምሪያ በአመልካች አማካኝነት የግጭት አደጋዉ መመዝገቡን ማሳወቁንና ዝርዝር ሁኔታዉን እንዲያሳዉቀዉ ጥያቄዎችን ጽፏል፡፡ በዚህ መሰረት የፖሊስ መምሪያዉ በ20/11/2008 ዓ.ም የተጻፈ የትራፊክ አደጋ ሪፖርት መስጫ ፎርም ቅጽ ቁጥር 005/02 ለተጠሪ ያሳወቀበት ሰነድ በተጠሪ እንደማስረጃ የቀረበ ጉዳይ ነዉ፡፡ በመሆኑም የአሁን አመልካች በመድን ዉሉም ሆነ በአዋጅ ቁጥር 799/2005 አንቀጽ 17 [1] መሰረት አደጋን የማሳወቅ ግዴታ ተሰጥቶ እያለ የሥር ፍ/ቤቶች አመልካች ይህን ግዴታዉን ስላልተወጣ የአሁን ተጠሪ ለ3ኛ ወገን የከፈለዉን የካሳ ገንዘብ እንዲከፍለዉ በማለት የሰጡት ዉሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ እንዲሻርልን፣ ወጪና ኪሳራ የመጠየቅ መብት እንዲጠበቅልኝ በማለት በዝርዝር አመልክቷል፡፡

የሰበር አጣሪ ችሎት ይህን ጉዳይ በማየት ፣በዚህ ጉዳይ አመልካች ተሽከርካሪዉ ያደረሰዉን የግጭት አደጋ በወቅቱ ለመድን ሰጪ ለሆነዉ ለተጠሪ አላሳወቀዉም ተብሎ ተጠሪ ያወጣዉን ወጪ ሊተካ ይገባል ተብሎ የመወሰኑን አግባብነት፣ ለመመርመር ሲባል የሰበር አቤቱታዉ ያስቀርባል በማለት ተጠሪ መልስ እንዲሰጥ ባዘዘዉ መሰረት መስከረም 30 ቀን 2011 ዓ.ም የተጻፈ መልስ አቅርቧል፡፡ የመልሱም ይዘት በአጭሩ፡ የአሁን አመልካች በመድን ዉሉ እና ህግ የተመለከተዉ አደጋዉን ለመድን ሰጪ ለሆነዉ ለተጠሪ አደጋዉ በደረሰ በአስር ተከታታይ ቀናት የማሳወቅ ግዴታዉን ያልተወጡ መሆኑን የሥር ፍ/ቤቶች ያረጋገጡት ጉዳይ ነዉ፤ ተጠሪ አደጋ መድረሱን ሊያዉቅ የቻለዉ ጉዳት የደረሰበት 3ኛ ወገን የካሳ ክፍያ እንዲፈጸምለት በጠየቀበት ወቅት ነዉ እንጂ አመልካች በተጠሪ ኩባንያ አደጋ ማሳወቂያ ቅፅ በመሙላት ያሳወቀዉ ነገር መኖሩን ያቀረበ ማስረጃ የለም፡፡ ስለዚህ የሥር ፍ/ቤቶች በዚህ ረገድ የሰጡት ዉሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት ተፈጽሞበታል ተብሎ የሚነቀፍ ባለመሆኑ፣

አመልካች ያቀረበዉ አቤቱታ ዉድቅ ሆኖ፣ የሥር ፍ/ቤቶች ዉሳኔዎች እንዲጸናልን በማለት በዝርዝር ተከራክሯል፡፡ የአሁን አመልካች የመልስ መልስ አቅርቧል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ከፍ ሲል የተመለከተዉ ሲሆን ይህ ችሎት የግራ ቀኛቸዉን ክርክር አግባብነት ካላቸዉ የህግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ እንዲሁም የሰበር አቤቱታዉ ያስቀርባል ሲባል ከተያዘዉ ጭብጥ አንጻር እንደሚከተለዉ መርምሮታል፡፡ እንደመረመርነዉ የአሁን ተጠሪ የአመልካች ንብረት የሰሌዳ ቁጥር ኮድ 2-A77230 አ.አ ለሆነዉ ተሽከርካሪ የ3ኛ ወገን መድን ሽፋን መስጠቱ ያልተካደ ፍሬ ነገር ነዉ፡፡ ይህ ተሽከርካሪ የ3ኛ ወገን ንብረት በሆነዉ የሰሌዳ ቁጥር ኮድ 2-A70206 አ.አ ተሽካርካሪ ላይ የግጭት አደጋ በማድረስ ጉዳት ያደረሰ መሆኑን እና በዚህ ምክንያት የአሁን ተጠሪ በመድን ዉሉ መሰረት ጉዳት ለደረሰበት 3ኛ ወገን ካሳ የከፈለ መሆኑ በሥር ፍ/ቤት የተረጋገጠ ፍሬ ነገር ነበር፡፡ ይህን ተከትሎ የአሁን ተጠሪ ባቀረበዉ ክስ አመልካች በመድን ዉሉ መሰረት ለተጠሪ አደጋ የማሳወቅ ግዴታዉን ስላልተወጣ ለ3ኛ ወገን የከፈልኩትን ብር 23,573.93 ከሕጋዊ ወለድ ጋር አመልካች እንዲከፍለኝ በማለት ዳኝነት ጠይቋል፡፡ አመልካች በበኩሉ ባቀረበዉ ክርክር በዉሉ መሰረት አደጋዉን ለተጠሪ የማሳወቅ ግዴታ ስለተወጣሁኝ ይህን ገንዘብ መክፈል የለብኝም በማለት ተከራክሯል፡፡ የሥር ፍ/ቤቶች ጉዳዩን በመመርመር በሰጡት ዉሳኔ አመልካች በዉሉ እና በሕጉ አግባብ አደጋን የማሳወቅ ግዴታዉን ስላልተወጣ ተጠሪ በክሱ የጠቀሰዉን ገንዘብ ከሕጋዊ ወለድ ጋር እንዲከፈለዉ ወስኗል፡፡ እንግዲህ እነዚህ ጉዳዮች በሥር ፍ/ቤቶች የተረጋገጡ ፍሬ ነገሮች ሲሆኑ በሕጉ አግባብ ሲታይ የአሁን አመልካች በመድን ዉሉ እና ስለተሽከርካሪ አደጋ የሦስተኛ ወገን መድን የወጣ አዋጅ ቁጥር 799/2005 አንቀጽ 17 [1] መሰረት አደጋን የማሳውቅ ግዴታዉን አልተወጣም ተብሎ የተጠየቀዉን ገንዘብ ለተጠሪ እንዲከፈል የመወሰኑን አግባብነት መመርመሩ ተገቢ ነዉ፡፡

እንደሚታወቀዉ በአዋጅ ቁጥር 799/2005 አንቀጽ 17 [1] ሥር እንደተመለከተዉ ከአቅም በላይ የሆነ ምክንያት ካልኖረ በስተቀር መድን ተገቢዉ መድን የተገባለት ተሽከርካሪ አደጋ መድረሱን ወዲያዉኑ ወይም ቢዘጋይ በአስር ቀን ዉስጥ ለመድን ሰጭዉ ማስታወቅ አለበት፡፡ ከዚህ ድንጋጌ መገንዘብ እንደሚቻለዉ የ3ኛ ወገን መድን ዉል ገቢዉ መድን የተገባለት ተሽከርካሪ አደጋ ያደረሰ እንደሆነ አደጋ መድረሱን ለመድን ሰጭዉ በሕጉ በተመለከተዉ ጊዜ ዉስጥ የማሳወቅ ግዴታ የተጣለበት መሆኑን ነዉ፡፡ በመሆኑም አንድ የመድን ገቢዉ በዚህ ድንጋጌ መሰረት በሕግ የተጣለበትን ለመድን ሰጭዉ አደጋን የማሳወቅ ግዴታዉን ካልተወጣ በ3ኛ ወገን የመድን ዉል ተጠቃሚ ለመሆን በሕግ የተመለከተዉን ቅድመ ሁኔታ እንዳልተወጣ ስለሚያስቆጥረዉ መብቱን የሚያጣበት ሁኔታ ሊኖር እንደሚችል መገንዘብ ያስፈልጋል፡፡

በዚህ አግባብ አሁን ወደ ተያዘዉ ጉዳይ ስንመለስ በግራ ቀኛቸዉ መካከል በተደረገዉ የ3ኛ ወገን የመድን ዉል መሰረት አመልካች ለተጠሪ አደጋ የማሳወቅ ግዴታ እንደተጣለበት ያልተካደ ጉዳይ ነዉ፡፡ የአሁን አመልካች ባቀረበዉ ክርክር የተሽከርካሪ አደጋ መድረሱን ለክፍሉ ፖሊስም ሆነ ለተጠሪ

ማሳወቁን ገልጾ ተከራክሯል፡፡ ተጠሪ በበኩሉ ባቀረበዉ ክርክር በክሱ የተጠቀሰዉ ተሽከርካሪ አደጋ ማድረሱን ያወቅኩት የሶስተኛ ወገን ካሳ እንዲከፈለዉ ጥያቄ በማቅረቡ ነዉ እንጂ አመልካች አደጋዉን ለተጠሪ የማሳወቅ ግዴታዉን አልተወጣም በማለት ተከራክሯል፡፡

በዚህ ረገድ ከሥር ፍ/ቤት መዝገብ መገንዘብ እንደሚቻለዉ የአመልካች ንብረት የሆነዉ ተሽከርካሪ በሶስተኛ ወገን ተሽከርካሪ ላይ የግጭት አደጋ ያደረሰዉ በ16/11/2008 ዓ.ም ሲሆን፣ የአሁን ተጠሪ ስለተሽከርካሪዉ ግጭት ጉዳይ ፖሊስ ዝርዝር መግለጫ እንዲሰጠዉ በ20/11/2008 ዓ.ም በተጻፈ ደብዳቤ የጠየቀ መሆኑን ነዉ፡፡ በዚህ መሰረት የቂርቆስ ክ/ከተማ ፖሊስ መምሪያ በቂ/ፖመ/11/1002/08 በ20/11/2008 ዓ.ም በጻፈዉ የትራፊክ አደጋ ሪፖርት መግለጫ ፎርም ቅጽ ቁጥር 005/02 የአመልካች ንብረት የሆነዉ ተሽከርካሪ ስላደረሰዉአደጋ ዝርዝር መግለጫ ለተጠሪ ማሳወቁን ማየት ይቻላል፡፡ ይህ ማለት ተጠሪ አደጋዉ እንደደረሰ በአራት ቀን ዉስጥ ስለአደጋዉ እንዲያዉቅ የተደረገ መሆኑን ነዉ፡፡ የአሁን ተጠሪ ባቀረበዉ ክርክር ይህ ተሽከርካሪ አደጋ ማድረሱን ያወቅነዉ ጉዳት የደረሰበት ሶስተኛ ወገን ካሳ እንዲከፈለዉ ጥያቄ በማቅረቡ ነዉ ይባል እንጂ ይህ ሶስተኛ ወገን መቼ እንዳሳወቀዉ፣ አደጋዉን ያሳወቀበት ቅጽ እንደማስረጃ ማቅረቡን የሥር ፍ/ቤት መዝገብ የሚያሳየዉ ነገር የለም፡፡ ተጠሪ ባቀረበዉ ክርክር አደጋ መድረሱን ማሳወቅ የሚቻለዉ በተጠሪ ኩባንያ በተዘጋጀዉ ቅጽ በመሙላት ብቻ ነዉ የሚል እስከሆነ ድረስ ስለአደጋዉ ማድረስ ሌላ ወገን ያሳወቀዉ መሆኑን የሚያስረዳ ማስረጃ ማቅረቡን የሥር ዉሳኔ የሚያሳየዉ ነገር የለም፡፡ ከሥር ፍ/ቤት ዉሳኔ መገንዘብ እንደሚቻለዉ የአሁን አመልካች ተቀጣሪ የሆነዉ አሽከርካሪ የነበረዉ አቶ ካሱ ወርዶፋ ተሽከርካሪዉ ያደረሰዉን አደጋ ወዲያዉኑ ለክፍሉ ፖሊስ ሪፖርት አድርጎ ማሳወቁን እና ፖሊስ ደግሞ ስለአደጋዉ ዝርዝር መግለጫ ለተጠሪ ማሳወቁን በፍሬ ነገር ደረጃ አረጋግጧል፡፡ ከፍ ሲል እንደተጠቀሰዉ የአሁን ተጠሪ በተሽከርካሪ ጉዳት የደረሰበት ሶስተኛ ወገን ስለአደጋዉ ለተጠሪ ያሳወቀዉ መሆኑን የሚያመለክት ማስረጃ በሥር ፍ/ቤት እስካላቀረበ ድረስ፣ ክርክሩን በማስረጃ የማስረዳት ኃላፊነቱን ተወጥቷል ለማለት ያዳግታል፡፡ ስለሆነም የአመልካች ንብረት የሆነዉ ተሽከርካሪ የ3ኛ ወገን ንብረት በሆነዉ ተሽከርካሪ ላይ ባደረሰዉ የግጭት አደጋ ጉዳት ማድረሱን እና ለዚህ ተሽከርካሪ በተጠሪ ዘንድ የ3ኛ ወገን የመድን ዉል የተገባለት መሆኑን ለክፍሉ ፖሊስ ያሳወቁ መሆኑን፣ በዚህ ሂደትም በተሽከርካሪዉ አደጋ ስለመድረሱ ተጠሪ እንዲያዉቅ የተደረገ መሆኑን መገንዘብ ይቻላል፡፡ የአሁን አመልካች በተቀጣሪዉ አሽከርካሪ በኩል ስለአደጋዉ መድረስና ተሽከርካሪ በተጠሪ ዘንድ የሶስተኛ ወገን የመድን ዉል የተገባለት መሆኑን ወዲያዉኑ ለክፍሉ ፖሊስ ባያሳዉቀዉ እና አደጋዉ ስለመድረሱ ለተጠሪ እንዲታወቅ ባይድረግ ኖሮ፣ ይህ ተሽከርካሪ በተጠሪ ዘንድ የሶስተኛ ወገን የመድን ሽፋን ያለዉ መሆኑን ለማወቅ አስቸጋሪ እንደሚሆን መገመት አያዳግትም፡፡

በዚህ መሰረት የአመልካች ንብረት የሆነዉ ተሽከርካሪ በ3ኛ ወገን ተሽከርካሪ ላይ የግጭት አደጋ ያደረሰዉ በ16/11/2008 ዓ.ም ሲሆን፣ የአሁን አመልካች በዚህ ተሽከርካሪ አሽከርካሪ በኩል ወዲያዉኑ ስለአደጋዉ ለክፍሉ ፖሊስም ሆነ ለተጠሪ በማሳወቁ፣ ተጠሪ የክፍሉ ፖሊስ ስለአደጋዉ ዝርዝር

መግለጫ እንዲሰጠዉ ጠይቆ፣ ፖሊስ ደግሞ በ20/11/2008 ዓ.ም በተጻፈ የአደጋ ዝርዝር መግለጫ ለተጠሪ ማሳወቁን ከሥር መዝገብ መገንዘብ ይቻላል፡፡ ይህ ማለት ተጠሪ የአመልካች ንብረት የሆነዉ ተሽከርካሪ አደጋዉ እንደደረሰ በአራት ቀን ዉስጥ እንዲያዉቅና ስለአደጋዉ ዝርዝር መግለጫ ያገኘ መሆኑን ነዉ፡፡ ይህ ከሆነ ደግሞ በመድን ዉሉም ሆነ ከፍ ሲል በተጠቀሰዉ ሕግ መሰረት ስለአደጋዉ መድረስ ወዲያዉኑ ወይም ቢዘጋይ በአስር ቀን ዉስጥ ለተጠሪ እንዲታወቅ መደረግ አለበት የሚለዉ ጉዳይ መሟላቱን የሚያስገነዝብ ነዉ፡፡ የአሁን ተጠሪ አደጋዉ እንደደረሰ በአራት ቀን ዉስጥ ስለአደጋዉ ዝርዝር መግለጫ እስካወቀ ድረስ፣ በመድን ዉሉም ሆነ በሕጉ የተቀመጠዉ የቅድመ ሁኔታ መሟላቱን ያሳያል፡፡ ተጠሪ ስለአደጋዉ መድረስ በዚህ አግባብ እንዲያዉቅ የተደረገና አደጋዉ መድረሱን አዉቆ ተገቢዉን ሁሉ ለመፈጸም ወይም እርምጃ ለመዉሰድ የሚያችለዉ እስከሆነ ድረስ፣ በመድን ዉሉም ሆነ በሕጉ የተቀመጠዉ ቅድመ ሁኔታ አልተሟላም በማለት የሚያቀርበዉ ክርክር የህግ ድጋፍ የለዉም፡፡ ስለሆነም የአሁን ተጠሪ አደጋዉ እንደደረሰ በአራት ቀን ዉስጥ ስለአደጋዉ ዝርዝር መግለጫ እንዲያዉቅ የተደረገ እስከሆነ ድረስ፣ አመልካች በመድን ዉሉም ሆነ በሕጉ የተመለከተዉን አደጋ የማሳወቅ ግዴታዉን አልተወጣም በማለት ያቀረበዉ ክርክር ተቀባይነት የለዉም፡፡ በመሆኑም የሥር ፍ/ቤቶች የአሁን አመልካች በመድን ዉሉም ሆነ በሕግ የተጣለበትን መድን ሰጭ ለሆነዉ ለተጠሪ አደጋን የማሳወቅ ግዴታዉን አልተወጣም በማለት ተጠሪዉ ለ3ኛ ወገን የከፈለዉን ገንዘብ መልሶ እንዲከፍለዉ የሰጡት ዉሳኔ በሕጉ አግባብ ሁኖ አልተገኘም፡፡

ሲጠቃለል የሥር ፍ/ቤቶች የአሁን ተጠሪ የአመልካች ንብረት የሆነዉ ተሽከርካሪ በሶስተኛ ወገን ተሽከርካሪ ላይ የግጭት አደጋ ያደረሰ መሆኑን አደጋዉ እንደደረሰ በአራት ቀን ዉስጥ እንዲያዉቅ መደረጉ በማስረጃ ተረጋግጦ እና በመድን ዉሉም ሆነ በሕጉ የተመለከተዉ አደጋን የማሳወቅ ቅድመ ሁኔታ ተሟልቶ እያለ፣ አመልካች አደጋን የማሳወቅ ግዴታዉን አልተወጣም በማለት ተጠሪዉ ለሶስተኛ ወገን የከፈለዉን ገንዘብ መልሶ እንዲከፍለዉ የሰጡት ዉሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ የሚከተለዉ ተወስኗል፡፡

**<u>ዉሳኔ</u>**

1. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ.ቁ.258901 በ19/7/2010 ዓ.ም የሰጠዉ ዉሳኔ እና የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ.214848 በ5/11/2010 ዓ.ም የሰጠዉ ትዕዛዝ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመባቸዉ ስለሆኑ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.348 [1] መሰረት በአብላጫ ድምጽ ተሽሯል፡፡
2. የአመልካች ንብረት ለሆነዉ ተሽከርካሪ በተገባለት የመድን ዉልም ሆነ በሕጉ የተመለከተዉን ለመድን ሰጭዉ አደጋን የማሰወቅ ቅድመ ሁኔታ በአግባቡ ተሟልቶ እያለ የአሁን ተጠሪ ለ3ኛ ወገን የከፈለዉን ካሳ አመልካች መልሶ ለተጠሪዉ የሚከፍልበት አግባብ የለም ብለናል፡፡
3. የዚህ ዉሳኔ ግልባጭ ለሥር ፍ/ቤቶች ይድረስ፡፡

4. ግራ ቀኛቸዉ በዚህ ችሎት የደረሰባቸዉን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸዉን ይቻሉ፡፡

5. የመ.ቁ.258901 የሆነዉ ለፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ልደታ ምድብ ችሎት ይመለስ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

የማይነበብ የአራት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ሠ/ን

## የልዩነት ሃሣብ

እኔ ስሜ በተራ ቁጥር 5 ስር የተሰየምኩት ዳኛ ከአብላጫው ሀሣብ እና ውሣኔ በሚከተለው ምክንያት ተለይቻለሁ፡፡

ኢንሹራንሶች ለደንበኞቻቸው የሚሰጡትን የመድን ሽፋን ታማኝ በመሆን አደጋ በደረሰባቸው ጊዜ ወይም ሲያደርሱ እንደውሉ ሊሸፍኑላቸው እንደሚገባና በሰበብ በአስባብ ሽፋን አልሰጥም በማለት ቅን ተዋዋዩችን ጉዳት ላይ እንዳይጥሉ መጠንቀቅ ተገቢ መሆኑን አምናለሁ፡፡

ኢንሹራንሶች ኘሪሚየም ከደንበኞቻቸው የሚሰበስቡ ሲሆን ከቅን ልቦና ውጭ በሆነ ሁኔታ አንዳንድ ደንበኞችም ኢንሹራንሱን ላልተገባ ክፍያ እንዳይዳርጉትም በእኩልነት ሊታይ ይገባል ባይ ነኝ፡፡ በዚህ መሠረት አመልካች ከተጠሪ ጋር ውል ሲያደርጉ አደጋን የማሳወቅ ግዴታ እንደ ቅድመ ሁኔታ በሕግም ሆነ በውላቸው የተቀመጠ መሆኑን አላውቅም የሚል ክርክር የላቸውም፡፡ ይልቁንም አመልካች የሚከራከሩት አደጋ መድረሱን ለፖሊስ አሳውቄአለሁ በሚል ነው፡፡

በመድን ሸጪው እና በመድን ገቢው መካከል የሚኖረው ግንኙነት የሚገዛው በግራ ቀኙ ውል ሲሆን ኢንሹንሱ/ መድን ሰጪው/ ላይ መድን ገቢው አደጋ በሚያጋጥምበት ጊዜ ለኢንሹራንሱ/ መድን ሰጪው / በንግድ ሕግ አንቀጽ 670 እና ውሉ የተደገረው የ3ኛ ወገን ሽፋንን የሚመለከት ከሆነ ደግሞ በአዋጅ ቁጥር 799/ አንቀጽ 17/1/ መሠረት አደጋ ከደረሰ እስከ 5 ቀን ከአቅም በላይ የሆነ ነገር መድን ገቢውን ካጋጠመው ቢበዛ እስከ 10 ቀን አደጋን የማሳወቅ ግዴታ እንዳለበት የሚደነግገውን መሠረት በማድረግ የማሳወቅ ግዴታውን መድን ገቢው እንዲወጣ የተዋዋሉ መሆኑን ተመልክተናል፡፡

በግራ ቀኙ ውል የማሳወቅ ግዴታ በመድን ገቢው ላይ የተጣለና በሕግም ይህ ግዴታ የተቀመጠ ከሆነ መድን ገቢው የማሳወቅ ግዴታውን መወጣት ይኖርበታል፡፡

በተያዘው ጉዳይ አመልካች እያሉ ያሉት አደጋ በደረሰ ጊዜ ለፖሊስ አደጋውን በሹፌሬ አማካይነት አሳውቄአለሁ በኢንሹራንሱ ጠያቂነትም ፖሊስ ለኢንሹራንሱ አሳውቋል የሚል ክርክር ያነሱና በውል እና በሕግ የተጣለብኝን ግዴታ ተወጥቻለሁ የሚል ነው፡፡

ነገር ግን ውሉ የተቋቋመው በኢንሹራንስ ሰጭውና እና በመድን ገቢው የአሁን አመልካች መካከል እንጂ ፖሊስ የውሉ አካል አይደለም፡፡ ሕጉ ጥበቃ የሚያደርገውም በኢንሹንራስ ገቢው እና በኢንሹራንስ ሰጪው መካከል ያለውን ውል እና ተዋዋዩችን ነው፡፡

በተለይ በተለይ የቀረበውን ጉዳይ ማሳወቅ ግዴታ መወጣትን ልዩ የሚያደርገው በ3ኛ ወገን መኪና ላይ ተለጣፊ በሆነው የ3ኛ ወገን ቦሎ ላይ ኢንሹራንስ ገቢው አደጋ በደረሰ ጊዜ ለኢንሹንራንስ /መድን ሰጪው የማሳወቅ ግዴታ እንዳለበት በግልጽ ተመልክቷል፡፡ በመድን ገቢውና በመድን ሰጪው መካከል በህግ በአስገዳጅ ሁኔታ የተደነገገውን በውላቸው ላይ ማስቀመጣቸው የማሳወቅ ግዴታን የማይደራደሩበት መሆኑን ለማመልከት እንጂ ውሉም ባይኖር እንኳን በህግ የማሳወቅ ግዴታ የመድን ገቢው ዋነኛ ግዴታ ነው፡፡ እንዲሁም በተዋዋዩች መካከል ያለን ግዴታ ሌላ ወገን ተወጥቶታል የሚለው አተረጓጐም በተለይ በኢንሹራንስ እና በደንበኞቻቸው መካከል የሚደረጉ ውሎችን ዋጋ ችግር ላይ የሚጥል ይሆናል፡፡ የማሳወቅ ግዴታ ይህን ያህል ትኩረት ተሰጥቶት በውል እና በሕግ ጥበቃ የሚደረግለት እስከሆነ ድረስ ይህን ግዴታ መወጣት ያለበት ወገን መወጣት ይኖርበታል፡፡ በመሆኑም ግዴታውን ባልተወጣበት እና በሕግ እና በውል በአስገዳጅ ሁኔታ በተደነገገበት ለፖሊስ አሳውቄአለሁ በመሆኑም ግዴታህን አልተወጣህም ልባል አይገባም በማለት ተጠሪ ያቀረበውን የመዳረግ ጥያቄ ውድቅ እንዲሆን መከራከር ተገቢ ሆኖ አላገኘሁትም፡፡ በመሆኑም አብላጫው ድምጽ ለፖሊስ ካሣወቀ ከአላማው አንፃር እንዳሳወቀ ይቆጠራል በማለት የሰጠውን ውሣኔ ባለመቀበል ከላይ በተጠቀሰው ምክንያት የስር ፍ/ቤት ውሣኔ ሊፀና እንጂ ሊሻር አይገባውም ነበር በሚል የሃሣብ ልዩነት ከአብላጫው ሃሣብ ተለይቻለሁ፡፡

የማይነብብ የአንድ ዳኛ ፊርማ አለበት፡፡

ሠ/ኃ

የሰ/መ/ቁ. 160602

ኅዳር 30 ቀን 2012 ዓ/ም

**ዳኞች፡-** ብርሃኑ አመነዉ

ተሾመ ሽፈራዉ

ሀብታሙ እርቅይሁን

ብርሃኑ መንግስቱ

ነጻነት ተገኘ

**አመልካች ፡-** አቶ ነጋ ባንቲሁን

**ተጠሪ፡-** የኢትዮጵያ መድን ድርጅት

መዝገቡ ተመርምሮ ከዚህ የሚከተለዉ የፍርድ ዉሳኔ ተሰጥቷል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ የኢንሹራንስ ካሳ የሚመለከት ሲሆን ጉዳዩን በመጀመሪያ ዳኝነት ስልጣን የዳኛው የግልግል ጉባኤ ሲሆን በጉባኤው የአሁን አመልካች ከሳሽ ሲሆኑ የአሁን ተጠሪ ደግሞ ተከሳሽ በመሆን ተከራክሯል፡፡ ከክርክሩ እንደተረዳነው አመልካች በስር የግልግል ዳኝነት ጉባኤ በቀን 01/10/2008 ዓ/ም ፅፈው ባቀረቡት ክስ ከተጠሪ ድርጅት በ15/11/2006 ዓም በተደረገ የኢንሹራንስ ውል ከ16/11/2006 ዓ/ም እስከ 7/5/2007 ዓ/ም የሚቆይ በዉሉ በተመለከቱት የአደጋ ምክንያቶች ጉዳት በደረሰ ጊዜ ብር 10,528,000.00 ካሳ ለማግኘት ከተጠሪ የመድን ሽፋን መግኘታቸውን፤ በዚህ የኢንሹራንስ ውል የተሰጠው የሽፋን አይነት እሳት እና መብረቅ፣ ጎርፍ፣ ውርጭ፣ ንፋስ፣ አውሎ ንፋስ፤ እና ከ35 ሚ.ሜ በላይ በሆነ ከባድ ዝናብ ምክንያት በጥጥ አዝዕርት ላይ ጉዳት ወይም ጥፋት ቢደርስ ካሳ የሚከፈላቸው መሆኑን ገልፀው የአመልካች የጥጥ አዝዕርት ከቀን 01/03/2006 ዓ/ም እስከ 03/13/2006 ዓ/ም ድረስ በአካባቢው በዘነበው ከባድ ዝናብና ጎርፍ እንዲሁም በቀን 25/1/2007 ዓም በዘነበው ከባድ ዝናብ ምክንያት የአመልካች የጥጥ ማሳ በጎርፍ በመጥለቅለቁና ሙሉ ለሙሉ በጎርፍ በመውደሙ አመልካች ለተጠሪ ጉዳቱን ወዲያውኑ በማሳወቅ በመድን ውሉ መሰረት የጉዳት መነሻ 25% ተቀንሶ ኢንሹራንስ የተገባለት መጠን 75% ብር 7,896,000.00 በጥጥ አዝርዕት ላይ ጉዳት ከደረሰበት ቀን ጀምሮ በሚታሰብ 9% ወለድ ጋር እንዲከፈላቸው ዳኝነት ጠይቀዋል ፡፡

የአሁን ተጠሪ ድርጅት የአመልካች ክስ ደርሶት በቀን 14/10/2008 ዓ/ም በሰጠው መልስ አመልካች በቀን 15/11/2006 ዓ.ም ተፈርሟል ሲሉ የጠቀሱት የመድን ውል ፖሊሲ ጊዜያዊ ውል መሆኑን፤ ይህ ጊዜያዊ ውል የመጨረሻው ውል እስከሚዘጋጅ ድረስ የሚያገለግል መሆኑን፤ይህ ጊዜያዊ ውል የተሰጠው እርሻው በባለሙያ እስኪታይና እስከሚመረመር ድረስ እንዲያገለግል መሆኑን፤ በዚሁ

መሰረት ጊዜያዊ ውሉ በቀን 08/12/2006 ዓ/ም የባለሙያ ሪፖርት ከተዘጋጀ በኂላ ለጥጥ እርሻው የሚከፈለው የዐረቦን መጠን አመልካች መጀመሪያ ከከፈሉት የዐረቦን መጠን ላይ ተጨማሪ የሚያስከፍል መሆኑን ቢገለፅላቸውም ከሳሽ የሰሊጡን ተጨማሪ ክፍያ ብቻ በመክፈል የጥጡን ተጨማሪ ክፍያ ባለመክፈላቸው በቀን 12/12/2006 ዓ.ም ጊዚያዊ የመድን ውሉ ተሰርዞ በዋናዉ ውል የተተካ መሆኑን፤ጊዜያዊ ውሉ በሌላ ውል ከተተካ በኂላ በጥጥ አዝርዕት ላይ የደረሰውን ጉዳት በሚመለከት ተፈፃሚነት ያለው ጊዜያዊ ውሉ ሳይሆን ዋናው ውል መሆኑን፤ በዚህ ውል መሰረት በውሉ ሰንጠረዥ ሽፋን የተሰጣቸው የአደጋ ምክንያቶች እሳት እና የመብረቅ አደጋ፤ጎርፍ፤በረዶ የቀላቀለ አውሎ ንፋስ እና ቁር/ውርጭ/ ብቻ መሆኑን ጠቅሶ ከ35 ሚ.ሜ. በላይ የሆነ ከባድ ዝናብ መዝነብና መጥለቅለቅ ዝናባማ አውሎ ንፋስ የተሰኙት የአደጋ ምክንያቶች በአመልካች እና በተጠሪ በቀን 12/12/2006ዓ.ም በተፈጸመ ውል በሽፋኑ አለመካተታቸውን፤ በመድን ውሉ በተመለከተው ትርጉም መሰረት ጎርፍ አለመከሰቱን እና የመድን ውል ሽፋን የሚሰጣቸውና የማይሸፍናቸው አደጋዎች፤ቅድመ ሁኔታዎች፣ ማግለያዎችና ትርጓሜዎችን የሚይዘው ዝርዝር የመድን ፖሊሲው የመድን ውሉ ሰንጠረዥ አካል ሆኖ ሳይነጣጠል ሊቀርብ የሚገባው በመሆኑ በቀን 12/12/2006 ዓ.ም ከተፈረመው ዋናው ውል ውጭ የቀረበ ክስ ነዉ ተብሎ ዉድቅ እንዲደረግለት በመጠየቅ ተከራክሯል።

ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ ዳኝነት ሥልጣን ያየው የግልግል ጉባኤ ግራ ቀኙን አከራክሮና ምስክሮች ሰምቶ በሰጠውውሳኔ አመልካች ለክሳቸው መሰረት ያደረጉት የመድን ውል በንግድ ሕጉ አንቀጽ 657/3 በተመለከተዉ መሰረት ዋናው የመድን ውል እስከሚፈጸም ድረስ የተደረገ አስገዳጅነት ያለውውል እንደሆነ እና ይህ ጊዜያዊ ውል አደጋው ከመድረሱ በፊት በዋናውውል መተካቱን እንዳረጋገጠ በመግለጽ ለጉዳዩ ተፈጻሚነት ያለው የመድን ውል በቀን 12/12/2006ዓ.ም የተፈጸመውውል ነዉ በሚል በአብላጫ ድምጽ ወስኗል።እንዲሁም በዚህ ውል መሰረት ተጠሪ ካሳ ለመክፈል የሚገደደው በእሳት፣ በመብረቅ፣ በጎርፍ፣ በበረዶ በቀላቀለ አውሎ ንፋስ እና ቁር(ዉርጭ) ምክንያቶች የደረሰ ጉዳት ቢኖር ብቻ ነው በሚል ከባድ ዝናብና የውሃ መጥለቅለቅ የሚሉ የአደጋ ምክንያቶች በጊዜያዊ ውሉ ሽፋን የተሰጣቸው ቢሆኑም ከዋናውውል የተቀነሱ የሽፋን አይነቶች ስለሆኑ በከባድ ዝናብና በውሃ ማጥለቅለቅ በአመልካች የጥጥ አዝዕርት ላይ ለደረሰ ጉዳት ተጠሪ የመድን ካሳ የመክፈል ኃላፊነት የለበትም በማለት በአብላጫ ድምጽ ወስኗል። እንዲሁም በመድን ውሉ ለጎርፍ በተሰጠ ትርጉም መሰረት ጎርፍ የሚባለዉ ከመደበኛ የውሃ ማፍሰሻ ቦታ ወጥቶ እርሻውን ሲጎዳ በመሆኑ በዚህ አግባብ የጥጥ ማሳው በጎርፍ መጎዳቱን አመልካች በማስረጃ እንዳላስረዱና በውሉ ለ"ጎርፍ" የተሰጠው ትርጉም ግልጽ በመሆኑ መተርጎም አስፈላጊ አይደለም በማለት በውሉ መሰረት በጎርፍ የደረሰ ጉዳት የለም በሚል ከዚህ አኳያ የተጠየቀውን የካሳ ጥያቄ ውድቅ በማድረግ በከፊል በረዶ በቀላቀለ አውሎ ንፋስ ምክንያት በ15 ሄክታር የጥጥ ማሳ ላይ ለደረሰው ጉዳት ብር 180,000.00 ተጠሪ ለአመልካች ካሳ እንዲከፍል በቀን 14/04/2010ዓ.ም በአብላጫ ድምጽ ወስኗል።

ከላይ በተገለጸው መሰረት በግልግል ጉባኤ በተሰጠ ውሳኔ ቅር በመሰኘት አመልካች ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ቢያቀርቡም ፍርድ ቤቱ ግራ ቀኙን በመ/ቁጥር 152280 ላይ አከራክሮ በቀን 29/08/2010ዓ.ም በዋለው ችሎት በሰጠው የፍርድ ውሳኔ የግልግል ጉባኤውን ውሳኔ በማጽናት ወስኗል፡፡አመልካች የሰበር አቤቱታ ያቀረቡትም በዚህ አግባብ በተሰጡ ውሳኔዎች መሰረታዊ የህግ ስህተት ተፈጽሟል በሚል ሲሆን በቀን 25/10/2010ዓ.ም ጽፈዉ ያቀረቡት አቤቱታ ይዘት በአጭሩ የሚከተለውነው፡፡

የጎርፍ ውሃ እና የዝናብ መጥለቅለቅ በሚመለከት በመድን ውሉ በተራ ቁጥር 2.1.2 ላይ ለጎርፍ የተሰጠ ትርጉም እንዲሁም በተራ ቁጥር 2.1.7 ላይ ደግሞ የዝናብ መጠን በየራሳቸው ተለይቶ የመድን ዋስትና ሽፋን ተሰጥቶ ሳለ በእነዚህ ምክንያቶች ለደረሰ ጉዳት የመድን ሽፋን አልተሰጠም ተብሎ በጉባኤውና በጠቅላይ ፍርድ ቤት የተሰጠው ትርጉም ግልጽ የሆነ የሕግ ስህተት እንደሆነ፤ በአመልካች የጥጥ አዝዕርት ላይ ጉዳት ያደረሰው ጎርፍ ከደምቢ ዶሎ እና ከላሬ ወረዳ ከዘነበው ከባድ ዝናብ የመጣ መሆኑን ከጋምቤላ ክልል የአደጋ መከላከል መስሪያ ቤት በቀን 08/07/2007ዓ.ም በተጻፈ ደብዳቤ የተረጋገጠውን ተጠሪ ሳያስተባብል አመልካች በሰነድ ማስረጃ አላስረዳም በሚል እና ውሃው ከቆመበት ፈንቅሎ ካልወጣ ጎርፍ እንደማይባል የተሰጠው ትርጉም የጎርፍ መነሻው ከባድ ዝናብ ብቻ መሆኑን የዘነጋ እና ውሃ በውስጣዊ ንቅናቄ ከቆመበት ፈንቅሎ ሲወጣ ማእበል እንጂ ጎርፍ ሊባል እንደማይችል እየታወቀ ከእውነታው የራቀ ትርጉም መሰጠቱ መሰረታዊ የህግ ስህተት እንደሆነ፤ በጊዜያዊና በዋናውውል መካከል ልዩነት አለመኖሩ እንደተጠበቀ ሆኖ ዋና ውል የተባለውን አመልካች እንደማያውቁና እንዳልፈረሙና ስምምነታቸዉን ያልሰጡበት ውል እንደሆነ በመግለጽ እንደማያስገድዳቸው ላቀረቡት ክርክር ዋጋ ሳይሰጥ መታለፉ እንዲሁም በጎርፍ ተጥለቅልቆ የጥጥ እርሻው መጎዳቱ ከመንግስት ተቋም በመጣ ማስረጃና በተጠሪ ምስክር ጭምር ተመስክሮ የተረጋገጠዉ ታልፎ መወሰኑ መሰረታዊ የህግ ስህተት እንደሆነ፤

እንዲሁም የተጠሪ ምስክሮች የክረምት ጊዜ ካለፈ በኋላ ሄደው ያዩትን በመግለጽ የሰጡትን ምስክርነት ቃል ጎርፍና የውሃ መጥለቅለቅን ለመተርጎም መጠቀማቸው መሰረታዊ የህግ ስህተት መሆኑን፤ አመልካች ሁለተኛውን ውል አለመፈረማቸዉ እንደተጠበቀ ሆኖ ሁለቱም ውሎች ላይ ጎርፍም ሆነ የውሃ መጥለቅለቅ የመድን ሽፋን የተሰጣቸው የአደጋ ምክንያቶች ሆነው እያለና በባለሙያ ምስክርነት ቃል እና ከጋምቤላ ክልል መንግስት ተቋማት ከተሰጡ ማስረጃዎች መካከል የተፈጠረ ልዩነት ካለም በሌላ ገለልተኛ ማስረጃ ማረጋገጥ እየተቻለ በዚህ አግባብ በማስረጃ እንዲረጋገጥ ሳይደረግ የተደረሰበት ድምዳሜ መሰረታዊ የህግ ስህተት ነው ተብሎ የግልግል ጉባኤው በአብላጫ ድምጽ የተሰጠውውሳኔ እና ጠቅላይ ፍርድ ቤት ጉዳዩን በይግባኝ በማየት የሰጠውውሳኔ ተሽረው በጠየቁት መሰረት ተጠሪ ካሳ እንዲከፍላቸዉ እንዲወሰንላቸዉ በመጠየቅ ተከራክረዋል፡፡

የሰበር አጣሪ ችሎት የሰበር አቤቱታውን፣ በግልግል ዳኝነት የተሰጠ ውሳኔ እና በጠቅላይ ፍርድ ቤት ጉዳዩ በይግባኝ ታይቶ የተሰጠ ውሳኔ መርምሮ በአመልካች የጥጥ አዝርዕት ላይ የደረሰ ጉዳት በጎርፍ ምክንያት መሆኑ በተከራካሪ ወገኖች የተካደ ባለመሆኑ ግራ ቀኙ በመድን ውል ላይ ለጎርፍ ከሰጡት ትርጓሜ አንፃር የተሰጡትን ውሳኔዎች አግባብነት ለመመርመር መዝገቡ ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ እና ተጠሪ መልስ እንዲሰጥ ትዕዛዝ በመስጠቱ ተጠሪ በቀን 01/04/2011ዓ.ም የተጻፈ መልስ ያቀረበ ሲሆን የመልሱ ይዘት በአጭሩ የሚከተለውነው፡፡

የሰበር አጣሪ ችሎቱ ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ያስቀርባል ሲል የያዘው ጭብጥ በአመልካች የጥጥ አዝርዕት ላይ በጎርፍ ምክንያት ጉዳት የደረሰ ስለመሆኑ በተከራካሪ ወገኖች የተካደ አይደለም በሚል መነሻ ቢሆንም ተጠሪ ከስር ክርክር ጀምሮ አንድም ጊዜ ጎርፍ ስለመድረሱ ያላመነና በማስረጃ አስደግፎ የተከራከረበት በመሆኑ የሰበር አጣሪው ጎርፍ መከሰቱ የታመነ ነው በማለት መዝገቡ ያስቀርባል ማለቱ ስህተት እንደሆነ፤ሰበር ሰሚ ችሎቱ ተቀብሎ ማስተናገድ የሚገባው መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመባቸውን ጉዳዮች ብቻ ሆኖ እያለ አመልካች በጥጥ እርሻዬ ላይ ጎርፍ ስለመከሰቱ በጋምቤላ ክልል በሚገኙ መስሪያ ቤቶች በተሰጡ ማስረጃዎች ተረጋግጦልኝ እያለ ጎርፍ አልተከሰተም በሚል አለአግባብ ታልፎብኛል በሚል ያቀረቡት ቅሬታ ግን በማስረጃ እና በፍሬ ነገር ክርክር ላይ የተመሰረተ ነው ተብሎ ውድቅ እንዲደረግለት፤ አመልካች ለጎርፍ በፖሊሲዉ ላይ በተራ ቁጥር 2.1.2 ለውሃ መጥለቅለቅ ደግሞ በተራ ቁጥር 2.1.7 ስር የመድን ሽፋን ተሰጥቶታል በሚል የጠቀሱት በቀጥታ ሽፋን ሊሰጣቸው የሚችሉ የአደጋ ስጋቶች (risks coverable) ናቸው እንጂ ሽፋን የተሰጠው ተለይቶ የተቀመጠበት ሰንጠረዥ እንዳልሆነና በቀን 12/12/2006 ዓ.ም በተደረገ ውል ላይ ባለ ሠንጠረዥ ላይ የውሃ መጥለቅለቅ ሽፋን ያልተሰጠው አደጋ እንደሆነ፤ የመጀመሪያውውል በራሱ ጊዜያዊ ውል መሆኑ በግልጽ የተመለከተበት እንደሆነ፤ ሊሰጥ የሚገባው የመድን ሽፋን ዓይነት እና የአመልካች የሚከፈል አቅም ከግምት ገብቶ አመልካች መክፈል ያለባቸዉ አርቦን ተሻሽሎ ዋና ዉል እንደሚፈጸም በጊዜያዊ ዉሉ ላይ በተገለጸዉ መሰረት ዋናውውል የተፈጸመ መሆኑን፤ በዋናውውል ላይ የውሃ መጥለቅለቅ የመድን ሽፋን ያልተሰጠው መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ የውሃ መጥለቅለቅ የመድን ሽፋን ተሰጥቶታል ቢባል እንኳን በውሉ አንቀጽ 2.1.7 ስር እንደተገለጸው መጥለቅለቁ መከሰት ያለበት ከ35ሚ.ሜ በላይ በሆነ ከባድ ዝናብ የተከሰተ መጥለቅለቅ መሆን ይገባዋል፤ ሆኖም ጉዳቱ ደረሰ በተባለባቸው ቀናት በዚህ ልክ ዝናብ አለመዝነቡን ለጉባኤውበቀረበው ማስረጃ ስለተረጋገጠና ከመነሻውም በዋናውውል የውሃ መጥለቅለቅ የመድን ሽፋን ያልተሰጠው በመሆኑ ከዚህ አንጻር የቀረበው ቅሬታ ተቀባይነት እንደሌለው፤ ህዳር 1 ቀን 2007 ዓ.ም የእርሻ ባለሙያ የምርመራ ሪፖርት እንዲሁም በተጠሪ ሶስተኛ የሞያ ምስክር በተሰጠ ምስክርነት በ5 ሄክታር የአመልካች እርሻ ላይ አነስተኛ የውሃ መጥለቅለቅ እና መታቆር እንዲሁም በከፍተኛ ሁኔታ በአረም መወረርን ጠቀሰ እንጂ እርሻው በሙሉ ተጥለቀለቀ አለማለቱን፤ የውሃ ማቆር ደግሞ ከውሃ መጥለቅለቅ የሚለይና ሽፋን ያልተሰጠው መሆኑ፤ጎርፍም ያልተከሰተ

መሆኑን፤አመልካች በደፈናው በውሃ መጥለቅለቅ የጥጥ ሰብሌን አወደመብኝ ከማለት ባሻገር በስር ያቀረቧቸውም ምስክሮች በእርሻው ላይ አደጋ እንደተከሰተ በቀን 03/13/2006 ዓ.ም በስልክ ሪፖርት መደረጉን ከመመስከር ባለፈ ስለ አደጋው አደራረስ፣የአደጋ ምክንያትም ሆነ የጉዳት መጠን ምንም እንዳላስረዱና በአመልካች የሙያ ምስክሮች ተመስክሮ የተረጋገጠዉን የማስተባበል አቅም ያለው ምስክርነት እንዳልሆነ በመግለጽ ቅሬታው የፍሬ ነገር እና የማስረጃ ጉዳይ እንጂ የህግ ስህተትን የተመለከተ አይደለም ተብሎ ውድቅ እንዲደረግለት በመጠየቅ ተከራክሯል፡፡

አመልካችም በቀን 23/04/2011 ዓ.ም የተጻፈ የመልስ መልስ በማቅረብ የሠበር አቤቱታቸውን በማጠናከር ተከራክረዋል፡፡

ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በዚህ ሰበር ችሎት ደረጃ ግራ ቀኝ ያደረጉት ክርክር ከዚህ በላይ የተመዘገበዉ ሲሆን እኛም ጉዳዩን ሰበር አጣሪ ችሎት ጉዳዩ ለሰበር ያስቀርባል ሲል የያዘዉን ጭብጥ መሰረት በማድረግ እና ለጉዳዩ ተፈጻሚነት ያለዉ የኢንሹራንስ ዉል በቀን 15/11/2006 ዓ.ም የተደረገዉ ነዉ ወይስ በቀን 12/12/2006 ዓ.ም የተደረገዉ ነዉ? እንዲሁም በአመልካች የጥጥ ማሳ ላይ ጉዳት የደረሰው በኢንሹራንስ ውሉ ሽፋን በተሰጠው የአደጋ ምክንያት መሆን አለመሆኑንና ከዚህ አንጻር የተፈጸመ መሰረታዊ የሕግ ስህተት መኖር አለመኖሩን መርምረናል፡፡ እንደመረመርነውም የግራ ቀኝ ክርክር መሰረት ያደረገው በግራ ቀኝ መካከል የተደረጉትን የኢንሹራንስ ውሎች ሲሆን አመልካች የኢንሹራንስ ካሳ ለማስከፈል በተጠሪ ላይ በመሰረቱት ክስ መሰረት ያደረጉት በቀን 15/11/2006 ዓ.ም የተደረገ የኢንሹራንስ ውል ሲሆን ተጠሪ ደግሞ ይህ በቀን 15/11/2006 ዓ.ም የተደረገ የኢንሹራንስ ውል ጊዜያዊ የኢንሹራንስ ውል እንደሆነና አገልግሎቱም የአመልካች አረቦን የመክፈል አቅማቸው ከግምት ገብቶ አመልካች መክፈል ያለባቸው አረቦን ተሻሽሎ ዋና ውል እንደሚፈጸም በጊዜያዊ ውሉ ላይ በተገለጸው መሰረት ዋናውውል እስከሚደረግ ድረስ የኢንሹራንስ ሽፋን ለመስጠት የተዘጋጀ ጊዜያዊ ውል እንደሆነና በክሱ የተጠቀሰው አደጋ ከመድረሱ በፊት ይህ ጊዜያዊ ውል በቀን 12/12/2006ዓ.ም በተፈረመ ዋና ውል ስለተተካ አመልካች ለክሳቸዉ ጊዜያዊ ውሉን መጠቀማቸዉ አግባብ አይደለም በሚል ተከራክሯል፡፡አመልካች ከዚህ ጋር ተያይዞ ተጠሪ በቀን 12/12/2006ዓ.ም ተደረገ ያለውን የኢንሹራንስ ውል ስላልፈረምኩ አያስገድደኝም በሚል ተከራክረዋል፡፡

በንግድ ሕግ ቁጥር 657/3 ስር እንደተደነገገው ጊዜያዊ የኢንሹራንስ ሽፋን ማረጋገጫ ማለት የኢንሹራንስ ፖሊሲው ወይም የፖሊሲዉ ተጨማሪ ጽሁፍ ከመፈረሙ በፊት ለጊዜዉ ማረጋገጫ መድን እንዲሆን የሚሰጥ ጽሁፍ(ሰነድ) ሲሆን ዓላማውም ኢንሹራንስ ሰጪውና እንሹራንስ ገቢው አንዱ ለአንዱ ግዴታ እንደገቡ የሚያሳይ ማረጋገጫ ሰነድ፡፡ ይህ ጊዜያዊ የኢንሹራንስ ሽፋን ማረጋገጫ በኢንሹራንስ ስራ ዘርፍ በሰፊው ጊዜያዊ የኢንሹራንስ ማረጋገጫ ሰነድ (Cover Note) ተብሎ የሚታወቅ ሲሆን ዋና (መደበኛ) የኢንሹራንስ ውል እና ፖሊሲ ማዘጋጀት የሚቻለውስለሚከፈለው

አርቦን መጠን፣ስለአደጋ ተጋላጭነት ሁኔታና መንስኤዎች፣ስለማግሊያዎች፣ ስለካሳ መጠን በባሉሙያ ጥናት ከተደረገ እና ተዋዋዮች ከተዳራደሩ በኋላ በሆነ ጊዜ እነዚህ ተግባራት እስከሚጠናቀቁ እና ዋናውውል እስከሚፈጸም ድረስ ኢንሹራንስ የሚገባለት ነገር ያለሽፋን እንዳይቀመጥ በሰነዱ በግልጽ ለተመለከተው የተወሰነ ጊዜ ስለሚከፈል አርቦን መጠን እና በሰነዱ በተገለጹት ምክንያቶች ዋናው የኢንሹራንስ ውል እስከሚፈረም ድረስ አደጋ በደረሰ ጊዜ ስለሚከፈል ካሳ ተገልጾ የሚሰጥ ጊዜያዊ የኢንሹራንስ ሽፋን ነው፡፡

በተያዘው ጉዳይ ላይ ግራ ቀኝ በቀን 15/11/2006 ዓ.ም በውል ቁጥር ጂኤኤም/4/አርኤልሲአር/0001/14 በተዋዋሉት የሰብል መድን ዋስትና ላይ በአመልካች የጥጥና ሰሊጥ ሰብል ላይ በእሳትና መብረቅ፣ በጎርፍ፣ በኃይለኛ ንፋስና ውርጭ፣ በረዶ በቀላቀለ አውሉ ንፋስ፣አቧራ በቀላቀለ አውሎ ንፋስ፣በአውሎ ንፋስ እና መጥለቅለቅ (በቀን ከ35ሚ.ሜ በላይ የሆነ ከፍተኛ ዝናብ) በሆኑ የአደጋ ምክንያቶች ከቀን 16/11/2006 እስከ 07/07/2007 ዓ/ም ድረስ ባለው ጊዜ ጉዳት ሲደርስ በጥጥ አዝእርት ላይ ለሚደርስ ጉዳት እስከ ብር 10,528,000.00 (በውሉ መሰረት 25% የሚቀነስ መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ) ካሳ ለመክፈል ተጠሪ ግዴታ መግባቱን ፣አመልካችም የዚህን 2.5% አርቦን ለመክፍል መስማማታቸውን፤ እንዲሁም ኢንሹራንስ የተገባላቸዉ ሰብሎች በእርሻ ባለሙያ/ሰርቬየር ከተመረመረ (ከታየ) በኋላ ከላይ በዚህ ውል ሰንጠረዥ በተገለጸው መድን የተገባለት ንብረት/ጥቅም ማስተካከል እንደሚቻል ስምምነት ማድረጋቸዉን እና ይህም ውል ጊዜያዊ የመድን ውል እንደሆነና የሚያገለግለውም የመጨረሻው የመድን ውል እስከሚሰጥበት ጊዜ ድረስ ብቻ እንደሆነ በውሉ ላይ በግልጽ ተመልክቶ ስምምነት መደረጉን ከውሉ ሰነድ እና ጉዳዩን በመጀመሪያ ዳኝነት ስልጣን ያየው የግልግል ጉባኤ ከሰጠውውሳኔ ይዘት ተገንዝበናል፡፡

እንዲሁም ተጠሪ አጥብቆ እንደሚከራከረው በቀን 15/11/2006ዓ.ም ውል ከተደረገ በኋላ በባለሙያ እንዲጣራ ተደርጎ ለክሱ መነሻ የሆነው አደጋ ከመድረሱ በፊት ጊዜያዊ ውሉ ሊሻሻል እንደሚገባ እና አመልካች የጥጡን ተጨማሪ የአርቦን ክፍያ እንዲከፍሉ ተጠይቀው ለመክፈል ፈቃደኛ ባለመሆናቸው ጊዜያዊ ውሉ ተሰርዞ በቀን 12/12/2006ዓ/ም በተደረገ ዋና የኢንሹራንስ ውል መሰረት የአርቦን ክፍያውበቀድሞው መጠን እንዲቀጥል በዚህ ዋና ውል የጊዜያዊ ውሉ ሰንጠረዥ ተሻሽሎ ሽፋን የተሰጣቸው የአደጋ ምክያቶች(ምንጮች) ደግሞ እሳት እና መብረቅ፣ጎርፍ፣በረዶ የቀላቀለ አውሉ ንፋስ እና ቁር/ውርጭ እንዲሆን መደረጉን በመግለጽ ለክርክሩ ተፈጻሚነት ያለው ይህ ዋናው የኢንሹራንስ ውል ነዉ በሚል ተከራክሯል፡፡

እንደሚታወቀው በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 1711 ስር በግልጽ እንደተደነገገው ተዋዋይ ወገኖች ሕግ ከወሰናቸውና ከከለከላቸው ነገሮች በቀር የሚዋዋሉበትን ጉዳይ እንደመሰላቸው የመወሰን መብት አላቸው፡፡በሕጉ አግባብ የተቋቋሙ ወሎች ደግሞ ባቋቋሚቸው ሰዎች መብትና ግዴታን ስለሚጥሉ

እንደሕግ ሆነው እንደሚያገለግሉ በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 1731/1 ስር በግልጽ ተደንግጓል፡፡ በተያዘው ጉዳይ ከዚህ በላይ እንደተመለከተው በግራ ቀኝ መካከል በቀን 15/11/2006 ዓ.ም የተደረገው የኢንሹራንስ ውል ጊዜያዊ የኢንሹራንስ ማረጋገጫ ሰነድ (Cover Note) እንደሆነና የሚያገለግለውም ዋናው(በሰነዱ ላይ የመጨረሻ ተብሎ የተገለጸው)የኢንሹራንስ ውል እስከሚደረግ ብቻ እንደሆነ በሰነዱ ላይ በግልጽ የተመለከተና በዚህ አግባብ በቀን 12/12/2006ዓ.ም በተጠሪ በተፈረመ ዋና የኢንሹራንስ ውል መተካቱን መረዳት ችለናል፡፡ ለክርክሩ መነሻ የሆነው አደጋ የደረሰው ደግሞ አመልካች በክሳቸው ላይ እንደገለጹት ከቀን 01/13/2006ዓ.ም እስከ ቀን 03/13/2006ዓ.ም ድረስ እና በቀን 25/01/2007ዓ.ም በእርሻ ቦታ አካባቢና በአጎራባች አገር በዘነበ ከባድ ዝናብ መጥለቅለቅ እና ጎርፍ ምክንያት ስለሆነ ዋናውውል ከተደረገ በኋላ የደረሰ አደጋ መሆኑን የሚያሳይ ነዉ፡፡ እንዲህ አይነት የኢንሹራንስ ውል አደራረግና የመድን ሽፋን አሰጣጥ በንግድ ሕጉ አንቀጽ 657/3 ስር የተፈቀደ ነው፡፡ በዚህ አግባብ ግራ ቀኝ የመጀመሪያዉን ውል ፈቅደው የተስማሙበት በመሆኑ ለግራ ቀኝ ክርክር እንደ ሕግ ሆኖ ሊያገለግል የሚገባው በቀን 15/11/2006 ዓ.ም የተደረገው ጊዜያዊ የኢንሹራንስ ውል ሳይሆን ይህንን ውል የተካው በቀን 12/12/2006ዓ.ም የተደረገውዋናው የኢንሹራንስ ውል እንደሆነ አረጋግጠናል፡፡

እንዲሁም አመልካች ዋናውን ውል ስላልፈረምኩና ስምምነቴን ስላልገለጽኩ ይህ ውል አያስገድደኝም በሚል የተከራከሩ ቢሆንም ይህንን ፍሬ ነገር በግራ ቀኝ ማስረጃ የማረጋገጥ ስልጣን ያለው የግልግል ጉባኤ በማስረጃ እንዳረጋገጠው ተጠሪ የተሻሻለውን ተጨማሪ የአርቦን ክፍያ እንዲከፍሉ አመልካችን ጠይቆ አመልካች ተጨማሪ የአርቦን ክፍያ ለመክፈል ፈቃደኛ ባለመሆናቸው በጊዜያዊ የኢንሹራንስ ሽፋን ሰንጠረዥ ላይ ከተዘረዘሩት የአደጋ ምክንያቶችን መካከል የተወሰኑትን በመቀነስ በጊዜያዊ የኢንሹራንስ ሽፋን ዉሉ ላይ የተገለጸዉ የአርቦን ክፍያ እየተከፈለ የኢንሹራንስ ሽፋኑ እንዲቀጥል ዋናውን ውል በመፈረም ተጠሪ ለአመልካች ማሳወቁን የግልግል ጉባኤው የቀረቡለትን ማስረጃዎች መርምሮና መዝኖ ማረጋገጡን በውሳኔው አስፍሯል፡፡ መድን ሰጭው በሚያዘጋጀውፖሊሲላይ እራሱ መፈረም እንዳለበት በንግድ ሕጉ ቁጥር 657 ላይ ከመመልከቱ በስተቀር መድን ገቢው መፈረም እንደሚገባው ያልተመለከተ በመሆኑ በውል ማቅረቢያ /offer/ ሰነዱ ጊዜያዊ ውሉ ከመደረጉ በፊት በነበረው ላይ አመልካች (ኢንሹራንስ ገቢው)ከፈረሙና በዋናው የኢንሱራንስ ዉልና ፖሊሲው ላይ ደግሞ ተጠሪ (ኢንሹራንሰ ሰጭው) ከፈረመ በሁለቱ መካከል የመድን ውል ስለመደረጉ በቂ አስረጂ በመሆኑ የኢንሹራንሲ ዉልን ልዩ ባህሪ ከግምት ማስገባት የሚገባ በመሆኑ አመልካች በቀን 12/12/2006 ዓ.ም የተደረገውን የኢንሹራንስ ውል ስላልፈረምኩ አያስገድደኝም በማለት ያቀረቡት ክርክር በግልግል ጉባኤ ተቀባይነት ማጣቱ የሚነቀፍ አይደለም፡፡በመሆኑም ለጉዳዩ ተፈጻሚነት ያለውውል በቀን 12/12/2006ዓ.ም የተደረገው የኢንሹራንስ ውል ነው ተብሎ በመወሰኑ የተፈጸመ መሠረታዊ የህግ ስህተት አልተገኘም፡፡

በአመልካች የጥጥ ማሳ ላይ ጉዳት የደረሰው በኢንሹራንስ ውሉ ሽፋን በተሰጠው የአደጋ ምክንያት ነው ወይስ አይደለም? በሚል የያዝነውን ጭብጥ እንደመረመርነው ከዚህ በላይ በተገለጸው መሰረት ለጉዳዩ ተፈጻሚነት ያለው የኢንሹራንስ ውል በቀን 12/12/2006ዓ.ም መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ በዚህ የኢንሹራንስ ውል መሰረት ሽፋን ያገኙት የአደጋ ምክንያቶች ደግሞ እሳት እና መብረቅ፣ጎርፍ፣በረዶ የቀላቀለ አውሎ ንፋስ እና ቁር/ውርጭ ብቻ ናቸው፡፡አመልካች በጥጥ ሰብላቸው ላይ ጉዳት ያደረሱ ምክንያቶች ናቸውብለውበክሳቸው ከለጹት ውስጥ አንዱ በከባድ ዝናብ የጥጥ ማሳው መጥለቅለቅና ሙሉ በሙሉ መውደም የሚለውነው፡፡ በውሃ መጥለቅለቅ የተከሰተ ጉዳት በመጀመሪያው ጊዜያዊ ሽፋን የኢንሹራንስ ውል ሽፋን የተሰጠው ቢሆንም በቀን 12/12/2006ዓ.ም በተደረገ ዋና የኢንሹራንስ ውል ግን ሽፋን የተሰጠው የአደጋ ምክንያት አይደለም፡፡ ስለሆነም ለጉዳዩ ተፈጻሚነት ያለው በቀን 12/12/2006 ዓ.ም የተደረገው የኢንሹራንስ ውል በመሆኑ አመልካች በውሃ መጥለቅለቅ የአደጋ ምክንያት መነሻ በጥጥ ማሳዬ ላይ ጉዳት ስለደረሰብኝ በሚል የጠየቁትን ካሳ ተጠሪ ሊከፍል አይገባም ተብሎ በግልግል ጉባኤው መወሰኑና ይሄዉ በይግባኝ ታይቶ መጽናቱ አግባብነት ያለው በመሆኑ ከዚህም አኳያ አመልካች ያቀረቡት አቤቱታ የመድን ሽፋኑን መሰረት ያላደረገ በመሆኑ አልተቀበልንም፡፡

ሌላዉ የዚህን ችሎት ምላሽ የሚሻ አከራካሪው ነጥብ አመልካች በጥጥ ማሳዉ ላይ ጉዳት አደረሰ ብለው የገለጹት ሁለተኛው የአደጋ ምክንያት ጎርፍ ሲሆን የግልግል ጉባኤውና ጉዳዩን በይግባኝ አይቶ የወሰነው የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ደግሞ የተጠሪን ክርክር ተቀብለው ምንም እንኳን በጥጥ ሰብሉ ላይ በጎርፍ ምክንያት ለሚደርስ ጉዳት ካሳ ለመክፈል በቀን 12/12/2006ዓ.ም በተደረገ ዋናዉ የኢንሹራንስ ዉል ሽፋን የተሰጠ ቢሆንም በዚህ ዉል ላይ ለጎርፍ በተሰጠዉ ትርጉም መሰረት በጎርፍ የደረሰ ጉዳት የለም በሚል አመልካች በዚህ የአደጋ ምክንያት መነሻ የጠየቁትንም ካሳ ተጠሪ ሊከፍል አይገባም በማለት ወስነዋል፡፡ ከዚህም አኳያ የተነሳዉን ክርክር እንደመረመርነው በጎርፍ ምክንያት በአመልካች የጥጥ ማሳ ላይ ለሚደርስ ጉዳት ተጠሪ የመድን ሽፋን መስጠቱ በቀን 12/12/2006ዓ.ም በተደረገ ዋናው የኢንሹራንስ ውል ላይ በግልጽ የተመለከተ ከመሆኑም በተጨማሪ ተጠሪም የካደው ጉዳይ አይደለም፡፡ በዚህ ረገድ ግራ ቀኙን ያከራከረው በኢንሹራንስ ፖሊሲው የትርጉም ክፍል ተራ ቁጥር 1 ስር ለ"ለጎርፍ" የተሰጠው ትርጉም ነው፡፡ የተሰጠው ትርጉም ይዘት የሚከተለውነው፡-

Flood shall mean loss of or damage to the crop insured caused by the overflow of water from the normal confine of any natural or artificial water course(other than water thanks, apparatus or pipes) or lakes. Reservoir, canal or dam whether resulting from storm or tempest (as defined herein) or otherwise. ይህም ጎርፍ ማለት በተፈጥሮ ወይም በሰዉ ሰራሽ መንገድ ውሃ ከተገደበበት ስፍራ(የዉሃ ታንከር፣ ቧንቧ ወይም መሰል ቁስ( apparatus) ሳይጨምር) ከሀይቅ፣ ከማጠራቀሚያ( Reservoir)፣ ከውሃ ማስተላለፊያ (canal ) ወይም ከግድብ(

dam ) በማእበል አማካኝነት( storm or tempest) ወይም በሌላ ምክንያት ውሃ ሞልቶ በመፍሰስ ኢንሹራንስ በተገባለት ሰብል ላይ የሚያደርስ ጥፋት ወይም ጉዳት ነው የሚል የአማርኛ ቋንቋ ትርጉም ያለዉ ነው፡፡ ግራ ቀኝ ይህንን ትርጉም ተስማምተው የተቀበሉት በኢንሹራንስ ፖሊሲው የትርጉም ክፍል ነው፡፡ በንግድ ሕግ ቁጥር 657/1 ስር እንደተደነገገው የኢንሹራንስ ውሉ በኢንሹራንስ ውል ፖለሲ በሚባል ጽሁፍ መደገፍ ይገባዋል፡፡ይህ ከላይ የተጠቀሰው "ጎርፍ" ለሚለው ቃል ትርጉም የሚሰጠውም ግራ ቀኝ በቀን 12/12/2006ዓ.ም ባደረጉት ዋና ውልም ሆነ በመጀመሪያው ጊዜያዊ የኢንሹራንስ ሽፋን ውል አካል አድርገው(የኢንሹራንስ ውሎቹን አስደግፈው) የተስማሙበት የኢንሹራንስ ውል ፖሊሲ ሲሆን ግራ ቀኝም ይህንኑ አልተካካዱም፡፡ በዚህ የኢንሹራንስ ፖሊስ ላይ የተመለከተው ነገር ግራ ቀኝ ተጨማሪ በሆነ ጽሁፍ በሌላ አግባብ ካልተስማሙ በቀር ሊለወጥ እንደማይችል በንግድ ሕጉ አንቀጽ 657/2 ሥር ተደንግጓል፡፡ከላይ በተገለጸው መሰረት በተጠቀሰው አግባብ ለጎርፍ ትርጉም የሚሰጠው የኢንሹራንስ ውል ፖሊስ ተጨማሪ በሆነ ጽሁፍ የተለወጠ ስለመሆኑ በግራ ቀኝ የቀረበ ክርክር የለም፡፡

በተጨማሪም አመልካች ከዚህ ጋር አያይዘው እየተከራከሩ ያሉት ውሃው ከቆመበት ከውስጣዊ ንቅናቄ ፈንቅሎ ካልወጣ ጎርፍ እንደማይባል በዘፈቀደ ትርጉም የሚወጣለት ሳይሆን ጎርፍ በዓለም ደረጃ የሚታወቀው በከባድ ዝናብ መነሻ የሚከሰት ክስተት ሆኖ እያለ ከእውነታው የወጣ ትርጉም መስጠቱ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ነው በሚል ነው፡፡በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 1733 ስር ውለታዎች ግልጽ በሆኑ ጊዜ ግልጽ ሆኖ ከሚሰማው በመራቅ የተዋዋዮቹ ፈቃድ ምን እንደነበር ዳኞች ለመተርጎም እንደማይችሉ በግልጽ ተደንግጓል፡፡ በተያዘውም ጉዳይ በንግድ ሕጉ ቁጥር 657(1 እና 2) መሰረት የኢንሹራንስ ፖለሲው የኢንሹራንስ ውሉ አካል በመሆኑ በኢንሹራንስ ፖሊሲው ላይ የተመለከተው ቃል የኢንሹራንስ ውል ቃል ተደርጎ ሊወሰድ የሚገባ በመሆኑ፣ በፖሊሲው ላይ ግራ ቀኝ ከላይ በተመለከተው መሰረት ጎርፍ ለሚለዉ ቃል ጠባብ ትርጉም በመስጠት እስከተዋዋሉና በዚህ አግባብ ለቃሉ ጠባብ ትርጉም በመስጠት መዋዋልን የሚከለክል ሕግ ባለመኖሩ፣ በፖሊሲው ለጎርፍ የተሰጠው ትርጉም ግልጽ አይደለም በሚል በአመልካች የቀረበ ክርክር ባለመኖሩና የተሰጠውም ትርጉም ግልጽ በመሆኑ ጎርፍ በነባራዊው ዓለም በትርጉሙ በተጠቀሰው ሁኔታ ብቻ የሚከሰት አይደለም የሚል ክርክር በአመልካች በመነሳቱ ብቻ በግራ ቀኝ መካከል እንደ ሕግ የሚያገለግለዉ የውል ቃል በሰፊው እንዲተረጎም የሚያስችል የሕግ መሰረት የለም፡፡

በመሆኑም ምንም እንኳን በጎርፍ አደጋ ኢንሹራንስ በተገባለት የጥጥ አዝእርት ላይ የሚከሰት ጉዳት በቀን 12/12/2006ዓ.ም በተደረገ የኢንሹራንስ ውል የመድን ሽፋን የተሰጠው የአደጋ ምክንያት ቢሆንም ግራ ቀኝ በኢንሹራንስ ፖሊሲው ላይ ለጎርፍ በሰጡት ትርጉም መሰረት በአመልካች የጥጥ አዝእርት ላይ ጉዳት ያደረሰው ጎርፍ በተፈጥሮ ወይም በሰው ሰራሽ መንገድ ውሃ ከተገደበበት ስፍራ(የውሃ ታንከር፣ ቧንቧ ወይም መሰል ቁስ( apparatus) ሳይጨምር) ከሀይቅ፣ ከማጠራቀሚያ(

Reservoir)፣ ከውሃ ማስተላለፊያ (canal ) ወይም ከግድብ( dam ) ላይ በማእበል አማካኝነት( storm or tempest) ወይም በሌላ ምክንያት ውሃ ሞልቶ በመፍሰሱ ምክንያት የተከሰተ ጎርፍ አለመሆኑን ፍሬ ነገርን በማስረጃ አጣርቶና መዝኖ የማረጋገጥ ስልጣን ያለው የግልግል ጉባኤ በአብላጫ ድምጽ ውሳኔ መስጠቱና ይሄውውሳኔ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት መጽናቱ ተገቢ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 80/3 ስልጣን የተሰጠው መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበትን ማናቸውንም የመጨረሻ ውሳኔ እንዲያርም እንጂ ከማስረጃ ምዘና ጋር በተያየዘ የሚቀርቡለትን የፍሬ ነገር ስህተት እንዲያርም ባለመሆኑ አመልካች ጎርፍ ስለመከሰቱ በማስረጃ አስረድቻለሁ ሲሉ ያቀረቡት ክርክር በኢንሹራንስ ፖሊሲው የተቀመጠውን የጎርፍ ትርጉም ያላገናዘበ ከመሆኑም በተጨማሪ ፍሬ ነገርን ከቀረበው ማስረጃ አንጻር መርምሮና መዝኖ የማረጋገጥ የዳኝነት ተግባር በዚህ ችሎት ደረጃ ሊታይ የሚችል አይደለም፡፡እንዲሁም የማስረጃ ምዘና ስርዓትና መርህ ተከትሎ የግራ ቀኝን ማስረጃ ከመመዘን አንጻር የግልግል ጉባኤውም ሆነ ጉዳዩን በይግባኝ ያየው የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በሰጡት ውሳኔዎች መሰረታዊ የሕግ ስህተት አልፈጸሙም፡፡ ስለሆነም ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

**<u>ው ሳ ኔ</u>**

1. የግልግል ዳኝነት ጉባኤ በቀን 14/04/2010 ዓ.ም የሰጠውውሳኔ እና የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 152280 ላይ በቀን 29/08/2010 ዓ.ም በዋለው ችሎት የግልግል ዳኝነት ጉባኤው የሰጠውን ውሳኔ በማፅናት የሰጠውን የፍርድ ውሳኔ በፍ/ብ/ስ/ስ/ሕግ ቁጥር 348/1 መሠረት ጸንቷል፡፡
2. ግራ ቀኝ በዚህ ችሎት ደራጃ ያወጡትን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸዉን እንዲችሉ ተወስኗል፡፡
   - የውሳኔው ግልባጭ ለግራ ቀኝ ይሰጣቸዉ፡፡
   - ውሳኔው ይታተም ዘንድ ግልባጩ ለፍርድ ቤቱ ጉዳዩ ለሚመለከተው ክፍል ይተላለፍ፡፡
   - መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት ፡፡

ፅ/ወ

የሰ/መ/ቁ.158262

ሀምሌ 30 ቀን 2011 ዓ.ም.

**ዳኞች ፡-** መዓዛ አሸናፊ

ተፈሪ ገብሩ (ዶ/ር)

ቀነአ ቂጣታ

ተሾመ ሽፈራው

ኑረዲን ከድር

**አመልካች ፡-** ናይል ኢንሹራንስ ኩባንያ አ.ማ - ጠ/ቴዎድሮስ ተስፋዬ

**ተጠሪ ፡-** ጀነራል ኢንሹራንስ ብሮከርስ - ጠ/ተካልኝ ዓለሙ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

በዚህ መዝገብ የተያዘው ክርክር የተጀመረው በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የአሁኑ ተጠሪና ስራ አስኪያጇ ወ/ሮ ጌጤነሽ ኃ/ማሪያም በአሁን በአመልካች ላይ ባቀረቡት ክስ ነው፡፡

የተጠሪ ክስ ይዘት፡- ኢስት አፍሪካ አትዮጵያ ሊሚትድ የተባለው ኩባንያ በስሩ የሚገኙ ድርጅቶችን የመድህን ሽፋን በተመለከተ የተለያዩ አገልግሎቶች ለማግኘት ሰኔ 23 ቀን 1996 ዓ.ም (ጁን 30/2004) በተፃፈ ከሳሽን መርጦ የወከለ መሆኑን ለተከሳሽ አሳውቋል፤ ይህም ሌሎች በአዋጅ ቁጥር 86/1988 አንቀጽ 11 የተመለከቱትን በመድን ድለላ መስክ የሚከናወኑ ተግባራትን የሚያጠቃልል ሲሆን ከሳሽ ይህን የመድን ገቢውን አደራ በመቀበል ከመስከረም 21 ቀን 1997 ዓ.ም (ኦክቶበር 2004) እስከ ሰኔ 23 ቀን 1997 ዓ.ም (ጁን 30/2005)፣ ከሰኔ 24ቀን 1997 ዓ.ም (ጁላይ 1/2005) እስከ ሰኔ 23/1998 ዓ.ም (ጁን 30/2005) እንዲሁም ከሰኔ 24/1998 ዓ.ም (ጁላይ 1/2006) እስከ ሰኔ 23 ቀን 1999 ዓ.ም (ጁን 30 ቀን 1997) ላሉት ሶስት ዓመታት በደንበኛው ስር የሚገኙ 22 ድርጅቶች የመድን ሽፋናቸውን ከተከሳሽ እንዲያገኙ አድርጌያለሁ፤ ከሳሽ እነዚህን በርካታ የመድን ፖሊሲዎች በተመለከተ የካሳ ክፍያና ሌሎች የውል አስተዳድርን (contract administration) የሚመለከቱ ተግባራትን አከናውኗል፤ ተከሳሽ በከሳሽ አማካኝነት በመጣለት የመድህን ሥራ ብር 7,262,987.79 አረቦን ከደንበኛው ላይ ተቀብሏል፤ ከዚህ የአረቦን ገንዘብ ላይ የመድህን ድለላ ኮሚሽን ለከሳሽ መክፈል ይገባዋል፤ በመድህን ገበያው እንደሚሰራበት አንድ መድህን ሰጪ ደንበኛው ከሚከፍለው የአርቦን መጠን ላይ ለግል ተሽከርካሪዎች መድን 12.5%፣ ለንግድ ተሽከርካሪዎች መድን 10%፣ ለእሳትና መብረቅ 17.5% እንዲሁም ለሌሎች የመድን ፖሊሲዎች 15% የድለላ ኮሚሽን መክፈል አለበት፤ በዚህ መሰረት ተከሳሽ ለቀረበለት የኮሚሽን ክፍያ ጥያቄ በሰጠው ምላሽ በከሳሽ ያገኘውን የድለላ አገልግሎት የሚያምን ቢሆንም መድን ገቢው የተከሳሽ ኩባንያ ባለአክሲዮን በመሆኑ ኮሚሽን ያለመክፈል የውስጥ

መመሪያ አለን በሚል ከሳሽን የማይመለከት ምክንያት አቅርቧል፤ ነገር ግን ተከሳሽ ለከሳሽ የሚከፍለውን ኮሚሽን አስመልክቶ የብሮከር ኮድ ቁጥር 01G00135 ሊከፈለው የሚገባውን የኮሚሽን ገንዘብ የሚያሳይ መረጃ አውጥቷል፤ እንዲሁም ከኮሚሽኑ ገንዘብ ላይ ብር 5,085.00 ለከሳሽ ከፍሏል፤ ቀሪውን ገንዘብ ለመክፈል ፈቃደኛ አይደለም፤ ስለሆነም ተከሳሽ ላገኘው አገልግሎት መክፈል ያለበትን ብር 1,057,908.31 (አንድ ሚሊዮን ሃምሳ ሰባት ሺህ ዘጠኝ መቶ ስምንት ከ31/100) የኮሚሽን ክፍያ ከነወለዱ እንዲከፍል ይወሰንልኝ በማለት ዳኝነት መጠየቁን የሚያሳይ ነው፡፡

አመልካች ለክሱ መቃወሚያ እና የፍሬ ነገር መልስ አቅርቧል፡፡ አመልካች በሰጠው መልስ ኢስት አፍሪካ (ኢትዮ) ሊሚትድ ለመድን ሥራ ከሳሽን ወክሏል በሚል የተገለፀውን በተመለከተ እ.ኤ.አ በ30/06/2004 በመድን ገቢው በተፃፈው ደብዳቤ የመጨረሻ አንቀጽ ስር ጀነራል ኢንሹራንስ ብሮከርና አማካሪዎች የመ/ቤቱን የመድህን ፍላጎት እንዲያጠናና እንዲመረምር በድርጅቱ የተመደበና ኃላፊነት የተሰጠው መሆኑን ከመግለጽ በቀር የተለያዩ የመድን ሽፋኖችን ለማግኘት ከሳሽን የመረጠ ስለመሆኑ አያስረዳም፤ ከዚህ በተቃራኒ ደብዳቤው መድን ገቢው ከተከሳሽ ጋር የኢንሹራንስ ሽፋን ያለው ሲሆን ወደፊትም የሚኖረውን ግንኙነት እራሱ እንደሚያሳውቅ አረጋግጧል፤ በንግድ ህግ ቁጥር 56(1) መሰረት የድለላ ስራ ማለት ውል የሚዋዋሉ ሰዎችን ፈልጎ የሚያገናኝና የሚያዋውል ሲሆን የመድን ስራን ለመቆጣጠር በወጣው አዋጅ መሰረት ደግሞ በመድህን ገቢዎች ወይም የጠለፋ ዋስትና ለማግኘት ጥያቄ በሚያቀርቡ ሰዎች ስም የመድህን ንግድ ስራን ከመድህን ሰጪው ጋር የሚያገናኝ እና የመድን ውል ለመዋዋል ለሚፈልጉ ቅድመ ዝግጅትን የሚያመቻች ነው፤ በተያዘው ጉዳይ ግን ከሳሽ ከፍሲል ከተመለከቱት ድርጊቶች የትኛውንም አልፈፀመም፤ መድን ገቢው የተከሳሽ ኩባንያ መስራች ባለአክሲዮን ሲሆን በስሩ ያሉት ድርጅቶች ንብረት በተከሳሽ በኩል የኢንሹራንስ ሽፋን ሲሰጣቸው የነበረው ያለ መድን ድለላ ነው፤ ተከሳሽ የድለላ ክፍያ የሚፈጽመው በህግ ላይ በተመለከተው መሰረት አዲስ ደንበኛ አምጥተው ለሚያገናኙ ደላሎች ብቻ ነው፤ ተከሳሽ ለከሳሽ የኮሚሽን ጥያቄ የሰጠው ደብዳቤ በየትኛውም መመዘኛ ከሳሽ መድን ገቢውን ከተከሳሽ ጋር የሚያገናኝ ስራ መስራቱን አያረጋግጥም፤ ስለሚከፈለው ገንዘብ መረጃ አውጥቷል የተባለውን በተመለከተም በብሮከር ኮድ ቁጥር 01/J00135 የወጣውን መረጃ ተከሳሽ አያውቀውም፤ ተከፈለ የተባለው ገንዘብም ለከሳሽ ያልተከፈለና ከመድን ገቢው ጋር የተገናኘ አይደለም፤ መድን ገቢው የሚያስተዳድራቸው ንብረቶች የተከሳሽ መድን የነበራቸው ሲሆን ሽፋኑ የተሰጠውም ሆነ የሚታደሰው ካለምንም አገናኝ በመሆኑ ከሳሽ ክስ ባቀረበበት ጉዳይ የድለላ ስራ አልሰራም በመሆኑም ተከሳሽ ለክሱ ኃላፊነት የለበትም፤ ተከሳሽ ለክሱ ኃላፊ ነው ቢባል እንኳ በመድን ስራው አማካኝነት ተከሳሽ ገቢ አግኝቷል የተባለ ቢሆንም ይህንን የሚያስረዳ ማስረጃ አልቀረበም፤ ከሳሽ ያለምንም የሂሳብ ሰነድ እና የሰራውን ስራ የሚገልጽ ማስረጃ ያቀረበው የገንዘብ መጠን ተቀባይነት የለውም፤ ስለሆነም ከሳሽ የጠየቀው የገንዘብ መጠን በማስረጃ ያልተደገፈ በመሆኑ ውድቅ ሊደረግ ይገባል፤ ይህ የሚታለፍ ከሆነም ለከሳሽ ሊከፈል የሚገባው ክፍያ መድን ገቢው የከፈለው የአርቦን ክፍያ እና ከሳሽ በመድን ገቢው በተፃፈው ደብዳቤ ላይ በተመለከቱት ድርጅቶች ስም ያስገባው የኢንሹራንስ

ሽፋንና የተከፈለ የአርቦን ክፍያ በገለልተኛ የሂሳብ ባለሙያ ተለይቶ እንዲቀርብ ትዕዛዝ ተሰጥቶ በሚቀርበው ምላሽ መሰረት እንዲወሰን በማለት ተከራክሯል፡፡

ጉዳዩ በዚህ መልኩ የቀረበለት የከፍተኛው ፍርድ ቤት ተከሳሽ ያቀረበውን መቃወሚያ መርምሮ ሚያዚያ11/2005 ዓ.ም ብይን ተሰጥቶበታል፡፡ ፍሬ ጉዳዩን በተመለከተም ተከሳሽ ለከሳሽ የተጠየቀውን የድለላ ኮሚሽን የመክፈል ኃላፊነት አለበት ወይስ የለበትም? ኃላፊት አለበት ከተባለስ ሊከፍል የሚገባው የገንዘብ መጠን ምን ያህል ሊሆን ይገባል? የሚሉ ጭብጦች በመያዝ ክርክርና ማስረጃውን መርምሮ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ በሰጠው ውሳኔ የመድን ውል ደንበኛው ከመግባቱ በፊት ጨረታ አውጥተው የመድን ውል እንዲፈጸም እና የመድን ውሎች ስለሚታደሱበት አግባብ ከተከሳሽ ጋር በመነጋገር ውሉ እንዲታደስ የማድረግ፤ ደንበኛውን በመድህን ውል ዙሪያ የማማከር እንዲሁም የካሳ ጥያቄዎች ሲኖሩ ተከታትሎ የማስፈፀም ስራዎችን ከደንበኛው ውክልና በመውሰድ ሲሰራ የነበረ መሆኑ በከሳሽ በኩል ከቀረቡት ለተከሳሽ የተፃፉ ደብዳቤዎች፤ ተከሳሽ ለከሳሽ ከፃፈው ደብዳቤ፤ ከመድን ገቢው ለፍርድ ቤቱ ከተሰጠው ምላሽ፤ እንዲሁም ምስክሮች በሰጡት ቃል የተረጋገጠ ሲሆን ተከሳሽ ይህን የሚያስተባብል ማስረጃ አላቀረበም፡፡ በመሆኑም የመድን ስራን ለመደንገግ በወጣው አዋጅ ቁጥር 746/2004 አንቀጽ 2(19) አንፃር ከሳሽ ደንበኛው የሆነውን ኢስት አፍሪካ ሊሚትድ ግሩፕ በመወከል ከ1996 ዓ.ም እስከ 1999 ዓ.ም ድረስ የመድን የደላላነት ሥራዎች የሰራ መሆኑን ፍርድ ቤቱ አረጋግጧል፡፡ በሌላ በኩል ስራው የተሰራው የተከሳሽ ኩባንያ ዋና ባለአክሲዮን ለሆነ ወገን በመሆኑ የድለላ ኮሚሽን ልከፍል አይገባም በማለት ተከሳሽ ቢከራከርም ይህን ይደግፋል የሚለውን የዳይሬክተሮች ቦርድ ውሳኔ አያይዞ ካለማቅረቡም በላይ ውሳኔው አለ ቢባል እንኳ ተከሳሽ በራሱ አስተዳደር አካል የተላለፈንና ሌሎች አካላትን የማይገዛ ውሳኔን መሰረት በማድረግ ከኃላፊነት የሚድንበት አግባብ የለም፤ ስራዎቹ መሰራታቸው እስከተረጋገጠ እና በስራውም አማካኝነት ተከሳሽ ገቢ ማግኘቱ ከተረጋገጠ የኮሚሽን ክፍያ የማይከፍልበት አግባብ አይኖርም፡፡ በመሆኑም በተጠሪ ለተሰሩት የመድህን ደላላነት ስራዎች ወይም አገልግሎቶች አመልካች ኮሚሽን የመክፈል ኃላፊነት አለበት በማለት ወስኗል፡፡ ሊከፈል የሚገባውን የገንዘብ መጠን በተመለከተም ከሳሽ በማስረጃነት የተከሳሽን የዳታ ቤዝ ግልባጭ ያቀረበ ሲሆን ተከሳሽ ማስረጃውን እንደማያውቀውና ከዳታቤዙ የወጣ አለመሆኑን ክዶ ቢከራከርም ብሄራዊ ባንክ ጉዳዩን አጣርቶ እንዲገልጽ ታዞ ማስረጃው ከተከሳሽ ኩባንያ ዳታ ቤዝ የወጣ መሆኑን አረጋግጧል፤ ተከሳሹም ከዳታ ቤዝ የተገኘው ማስረጃ ይዘት ላይ ምንም አይነት ክርክር አላቀረበም፤ በመሆኑም በማስረጃው የተመለከተውን ብር 1,057,908.31 (አንድ ሚሊዮን ሀምሳ ሰባት ሺህ ዘጠኝ መቶ ስምንት ብር ከ31/100) የመጨረሻው የድለላ ስራ ከተሰራበት ህዳር 25/1999 ዓ.ም ጀምሮ ከሚታሰብ ወለድ ጋር አመልካች ለተጠሪ ሊከፍል ይገባል በማለት ወስኗል፡፡

በዚህ ውሳኔ ባለመስማማት አመልካች ይግባኙን ለፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ቢያቀርብም ውሳኔው ጉድለት የለበትም ተብሎ ይግባኙ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 337 መሰረት ተሰርዟል፡፡

የሰበር አቤቱታው የቀረበው ይህን በመቃወም ነው፡፡ አመልካች ሚያዚያ 18/2010 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ የበታች ፍርድ ቤቶች ባሳለፉት ውሳኔና ትዕዛዝ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ተፈፅሟል የሚልበትን ምክንያት በመዘርዘር አቅርቧል፡፡ አቤቱታው በአጣሪ ችሎቱ ተመርምሮ ለጉዳዩ ተፈፃሚነት ያለው ህግ አዋጅ ቁጥር 86/1986 ነው ወይስ ይህን አዋጅ የተካው አዋጅ ቁጥር 746/2004፤ ተጠሪ ለሰጠው አገልግሎት አመልካችን የመጠየቅ መብት አለው ቢባል የአሁን አመልካች ባቀረበው ክርክር እንደገለፀው ለተሰራው ሥራ ሊከፈል የሚገባው ክፍያ በገለልተኛ ባለሙያ ይጣራልኝ በማለት ያቀረበው ክርክር ታልፎ የተሰጠውን ውሳኔ አግባብነት ለማየት ሲባል ጉዳዩ ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ እና ተጠሪ መልስ እንዲሰጥበት ተደርጓል፡፡ ተጠሪ ጥቅምት 9/2011 ዓ.ም በተጻፈ መልስ በኃላፊነትም ሆነ በመጠን ረገድ የተሰጠው ውሳኔ ስህተት የሌለበት በመሆኑ የሰበር ቅሬታው ውድቅ ሊደረግ ይገባል በማለት ተከራክሯል፡፡ አመልካችም ክርክሩን በማጠናከር የመልስ መልስ አቅርቧል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ባጭሩ ከፍሲል የተገለፀው ሲሆን በበኩላችን የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩ ለዚህ ሰበር ችሎት ሲቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አንፃር በሚከተለው መልኩ መርምረናል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ እንደተቻለው ተጠሪ አመልካቹ ካገኘው የአርቦን ክፍያ ገቢ መክፈል ያለበትን የመድን ድለላ አገልግሎት የኮሚሽን ክፍያ ብር 1,057,908.31 (አንድ ሚሊዮን ሃምሳ ሰባት ሺህ ዘጠኝ መቶ ስምንት ከ31/100) ከነወለዱ እንዲከፍል እንዲወሰን ዳኝነት መጠየቁን ሲሆን አመልካች በበኩሉ ተጠሪ ክስ ባቀረበበት ጉዳይ የድለላ ስራ አልሰራም ስለሆነም ለክሱ ኃላፊነት የለብኝም፤ አመልካች ለክሱ ኃላፊ ነው ቢባል እንኳ በመድን ስራው አማካኝነት አመልካች ያገኘውን ገቢ የሚያስረዳ ማስረጃ አልቀረበም፤ ተጠሪ ያለምንም የሂሳብ ሰነድ ያቀረበው የገንዘብ መጠን ተቀባይነት ሊኖረው አይገባም፤ ይህ የሚታለፍ ከሆነም ለተጠሪ ሊከፈል የሚገባው ክፍያ በገለልተኛ የሂሳብ ባለሙያ ተለይቶ እንዲቀርብ ትዕዛዝ ተሰጥቶ በሚቀርበው ምላሽ መሰረት እንዲወሰን በማለት ተከራክሯል፡፡ የስር ፍርድ ቤት ክርክርና ማስረጃውን መርምሮ ከፍሲል የተገለፀውን ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

በመድን ሥራ አዋጅ ቁጥር 746/2004 አንቀጽ 2(19) ስር እንደተደነገገው "የመድን ደላላ" ማለት ኮሚሽን በማስከፈል በመድን ገቢው ሰው ስም የመድን ውል ለመዋዋል የሚያስችሉ ቅድመ ዝግጅቶችን የሚያመቻች፤ የመድን ውል ቀጣይ አስተዳደርና እድሳትን በሚመለከት እገዛ የሚያደርግ፤ እንዲሁም በመድን ውለታና በካሳ ክፍያ ጥያቄ ላይ ለመድን ገቢው የማማከር አገልግሎት የሚሰጥ ነው፡፡ የተሻረው የመድን ስራ ስለመፍቀድና ስለመቆጣጠር የወጣው አዋጅ ቁጥር 86/1986 አንቀጽ 2(11) ለ"መድን ደላላ" የሰጠው ትርጓሜ ይዘትም ከዚህ የተለየ አይደለም፡፡ ከዚህም ሌላ በንግድ ህጉ ስለደላሎች ትርጓሜ በሚሰጠው አንቀጽ 56(1) ስር "ደላላ" ማለት ውል የሚዋዋሉ ሰዎችን ይልቁንም እንደ ሽያጭ፣ ኪራይ፣ ኢንሹራንስ፣ የማመላለሻ ውልንና እንደዚህ ያሉትን ውሎች የሚዋዋሉ ሰዎችን ፈልገው የሚያገናኙና የሚያዋዉሉ ራሱን የቻለ የሞያ ተግባራቸው አድርገው ጥቅም ለማግኘት የሚሰሩ ሰዎች ወይም ይህንኑ የደላልነት ሥራ የሚሰራ የንግድ ማህበር ነው በማለት ትርጉም ተሰጥቶታል፡፡

በተያዘው ጉዳይ የሥር ፍርድ ቤት የግራቀችን ክርክርና ማስረጃ መርምሮ ተጠሪ የመድን ውል እንዲፈጸም እና እንዲታደስ የማድረግ፤ የመድን ውሎች ስለሚታደሱበት አግባብ ከአመልካች ጋር በመነጋገር ውሉ እንዲታደስ የማድረግ፤ ደንበኛውን በመድህን ውል ዙሪያ የማማከር እንዲሁም የካሳ ጥያቄዎች ሲኖሩ ተከታትሎ የማስፈፀም ስራዎችን ከደንበኛው ውክልና በመውሰድ ሲሰራ የነበረ መሆኑ ከተፃፃፏቸው ደብዳቤዎች፤ ፍርድ ቤቱ ካስቀረበው ማስረጃ እንዲሁም ምስክሮች በሰጡት ቃል በማረጋገጥ ተጠሪ ደንበኛው የሆነውን ኢስት አፍሪካ ሊሚትድ ግሩፕ በመወከል ከ1996 ዓ.ም እስከ 1999 ዓ.ም ድረስ የመድን የደላላነት ሥራዎች የሰራ መሆኑንና በስራውም አማካኝነት አመልካች ገቢ ማግኘቱን በማረጋገጥ በተጠሪ ለተሰራው የመድህን ደላላነት ስራ አመልካች ኮሚሽን የመክፈል ኃላፊነት እንዳለበት ወስኗል፡፡ የሥር ፍርድ ቤት እዚህ መደምደሚያ ላይ የደረሰው ፍሬ ነገሩን ለማጣራት እና ማስረጃ ለመመዘን ባለው ስልጣን መሰረት በማጣራትና በማስረጃ በማረጋገጥ ነው፡፡ እንደሚታወቀው ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት በተሰጠው ውሳኔ የተፈፀመ የህግ ስህተት ካለ ከሚመለከት በቀር መሰል የፍሬ ነገር ክርክርን መርምሮ እና ማስረጃ መዝኖ ውሳኔ የሚሰጥ ስላለመሆኑ ከህገ መንግስቱ አንቀፅ 80(3(ሀ) እና አዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 10 ግልፅ ድንጋጌ መገንዘብ ይቻላል፡፡ ተጠሪ የመድን ውል እንዲፈጸም እና እንዲታደስ የማድረግ፤ ደንበኛውን በመድህን ውል ዙሪያ የማማከር እና የካሳ ጥያቄዎች ተከታትሎ የማስፈፀም ስራዎችን ሲሰራ የነበረ መሆኑ ከተረጋገጠ ደግሞ ከፍሲል ከተጠቀሰው የህጉ ትርጉም አንፃር ኮሚሽን የሚያስከፍል የድለላ ሥራ መስራቱን መገንዘብ ይቻላል፡፡ በመሆኑም በተጠሪ ለተሰራው የመድህን ደላላነት ስራ አመልካች ኃላፊነት አለበት ተብሎ በተሰጠው ውሳኔ በዚህ ችሎት የሚታረም የህግ ስህተት የለም ብለናል፡፡

በሌላ በኩል የክፍያውን መጠን በተመለከተ ከፍሲል እንደተጠቀሰው ተጠሪ ብር 1057908.31 (አንድ ሚሊዮን ሃምሳ ሰባት ሺህ ዘጠኝ መቶ ስምንት ከ31/100) ከነወለዱ እንዲከፈለው የጠየቀ ሲሆን አመልካች በበኩሉ በስር ፍርድ ቤት ለክሱ በሰጠው መልስ በመድን ስራው አማካኝነት አመልካች ያገኘውን ገቢ የሚያስረዳ ማስረጃ ስላልቀረበ ተጠሪ ያለምንም የሂሳብ ሰነድ በክሱ ያቀረበው የገንዘብ መጠን ተቀባይነት የለውም እንዲባል፤ ይህ የሚታለፍ ከሆነም ክፍያው በገለልተኛ የሂሳብ ባለሙያ ተለይቶ እንዲቀርብ ትዕዛዝ እንዲሰጥ ጠይቋል፡፡ የከፍተኛው ፍርድ ቤት ባሳለፈው ውሳኔ እንደተመለከተው በአመልካች ዳታ ቤዝ ተገኘ የተባለን ማስረጃ መሰረት በማድረግ ተጠሪ የጠየቀውን ክፍያ ከነወለዱ እንዲከፈል ከመወሰኑ በቀር ኮሚሽን ለተጠየቀበት የድለላ ስራ ክፍያ አወሳሰን በሚረዳ መልኩ ተጠሪ ያስጠው የኢንሹራንስ ሽፋንና በመድን ገቢዎች የተከፈለ የአርቦን ክፍያ እንዲሁም ለጉዳዩ ተግባራዊ የሚሆነው የኮሚሽን መጠን በዝርዝር በገለልተኛ የሂሳብ ባለሙያ ተለይቶ እንዲቀርብ ተደርጎ ከስምምነታቸው እና ከህጉ እንዲሁም ከቀረበው ክርክር አንጻር ተለይቶ ውሳኔ አለመሰጠቱን ተገንዝበናል፡፡

ስለሆነም ጉዳዩ ከዚህ አንጻር ሳይታይና ሳይጣራ እንዲሁም ዝርዝር ምክንያት ሳይሰጥ በዳታ ቤዝ ተገኘ የተባለን ማስረጃ መሰረት በማድረግ ብቻ ተጠሪ የጠየቀውን ብር 1,057,908.31 (አንድ ሚሊዮን

ሃምሳ ሰባት ሺህ ዘጠኝ መቶ ስምንት ከ31/100) ከነወለዱ አመልካች እንዲከፍል የተሰጠው የውሳኔ ክፍል የህግ ስህተት የተፈፀመበት ነው ብለናል፡፡ ተከታዩንም ወስነናል፡፡

**ው ሣ ኔ**

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በኮ/መ/ቁጥር 86785 ሚያዝያ 11/2005 ዓ.ም ያሳለፈው ብይንና ታህሳስ 17 ቀን 2010 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ፤ እንዲሁም በፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በፍ/ይ/መ/ቁ 153508 መጋቢት 12/2010 እና ይህን በማረም ግንቦት 10 ቀን 2010 ዓ.ም ያስተላለፈው ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 348(1) መሰረት ተሻሽሏል፡፡
2. በተጠሪ ለተሰራው የመድህን ደላላነት ስራ አመልካች ኃላፊነት አለበት ተብሎ በተሰጠው ውሳኔ የተፈፀመ የህግ ስህተት የለም ብለናል፡፡
3. በዳታ ቤዝ ተገኘ የተባለን ማስረጃ መሰረት በማድረግ ብቻ ተጠሪ የጠየቀውን ብር 1,057,908.31 (አንድ ሚሊዮን ሃምሳ ሰባት ሺህ ዘጠኝ መቶ ስምንት ከ31/100) ከነወለዱ አመልካች እንዲከፍል የተሰጠው የውሳኔ ተሽሯል፡፡
4. የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የተዘጋውን መዝገብ በማንቀሳቀስ ኮሚሽን ለተጠየቀበት የድለላ ስራ ክፍያ አወሳሰን በሚረዳ መልኩ ተጠሪ ያሰጠው የኢንሹራንስ ሽፋንና በመድን ገቢዎች ለአመልካች የተከፈለ የአርቦን ክፍያ መጠን፤ እንዲሁም ለጉዳዩ ተግባራዊ የሚሆነውን የኮሚሽን መጠንና ለተጠሪ ተከፋይ ስለሚሆነው ገንዘብ በዝርዝር በገለልተኛ የሂሳብ ባለሙያ ተጣርቶ እንዲቀርብ በማድረግ በምክንያት የተደገፈ ውሳኔ እንዲሰጥ ጉዳዩን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 343(1) መሰረት መልሰናል፡፡ የውሳኔው ግልባጭ ይድረሰው፡፡
5. የሥር ፍርድ ቤት መዝገብ በመጣበት መልኩ ይመለስ፡፡
6. የሰበር ክርክሩ ያስከተለውን ወጪና ኪሳራ ይቻቻሉ፡፡

መዝገቡተዘግቷልወደመዝገብቤትይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ፅ/ወ

የሰ/መ/ቁ.103472

ቀን 27/01/2008 ዓ.ም

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

ተሻገር ገ/ሥላሴ

ተፈሪ ገብሩ

ሸምሱ ሲርጋጋ

አብርሃ መሠለ

አመልካች፡- የኢት/ንግድ ባንክ ነ/ፈጅ ኢትዮጵያ ታመነ

ተጠሪዎች፡- 1. አቶ ጌታነህ ምናለ

2. ወ/ሮ የአልጋነሽ አበጀ

3. ዶዶላ ኢንተርናሽናል ትሬዲንግ ኃ/የተ/የግል/ማ

መዝገቡን መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል ፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የዕግድ ትእዛዝ የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የጀመረው የአሁኑ አመልካች በፌ/ከፍ/ፍ/ቤት ተጠሪዎች /1ኛ እና 2ኛ/ ላይ ክስ መስርቶ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ.154/ለ/ መሠረት የእግድ ትእዛዝ ከተሰጠ በኃላ የአሁኑ 3ኛ ተጠሪ የዕግድ ትእዛዝ እንዲነሳ ባቀረበው አቤቱታ ነው፡፡

የአሁኑ 3ኛ ተጠሪ ለፌ/ከፍ/ፍ/ቤት ያቀረበው አቤቱታ ይዘት ባልተከሰስንበት እና በማይመለከተን እዳ ምክንያት በአመልካች ስም ያለው ንብረት /ቤት/ እንዲታገድ የተደረገው በአግቡቡ ስላልሆነ ዕግዱ ይነሳ የሚል ሲሆን የአሁኑ አመልካች በበኩሉ የሰጠው መልስ መጋቢት 24 ቀን 2005 ዓ.ም በተሠጠው የእግድ ትእዛዝ መሠረት በንግድ ማህበሩ ተከሳሽ /1ኛ ተጠሪ/ አባል መሆን አለመሆናቸው ተጣርቶ እግዱ እንዲመዘገብ በታዘዘው መሠረት ለፍርድ ቤቱ ምላሽ ሰጥተናል ባሉት ደብዳቤ በግልፅ ተከሣሾች የንግድ ማህበሩ አባል አለመሆናቸውን የሚያረጋግጥ ማስረጃ አቅርበው ሲሆን ፍ/ቤቱ በወቅቱ ተገቢውን ብይን ይሰጥበት ነበር ፡፡ አመልካች ባቀረቡት ማስረጃ ዝርዝር የንግድ ማህበሩ የካቲት 9/2005 ዓ.ም ባደረገው ስብሰባ በተያዘው ቃለ ጉባኤ በግልፅ እንደተመለከተው 1ኛ ተከሣሽ የነበረው አቶ ጌታነህ ምናሉ በማህበሩ የነበረው የአክሲዮን ድርሻና የማህበሩን የሥራ አስኪያጅነት ሥልጣን ለአቶ

ይታየው ታደሰ ያስረከበ መሆኑ ያሳያል ሆኖም 1ኛ ተከሣሽ የፍ/ቤቱ የዕግድ ትእዛዝ የማህበሩ ሥራ እስኪያጅ ነኝ በማለት ፈርሞ የተቀበለ በመሆኑ በወቅቱም የከሣሽ ባለሙያዎች ወደ ንግድ ማህበሩ ዋና ጽ/ቤት ሲሄዱ 1ኛ ተከሣሽን ያገኙአቸው በመሆኑ የእግድ ትእዛዙ እስከተሰጠበት ጊዜ ድረስ 1ኛ ተከሣሽ የማህበሩ አባል እና ሥራ አስኪያጅ የነበረና የእግድ ትእዛዝ ከተሠጠ በኃላ አመልካች ሆን ብለው የባንኩን ጥቅም ለመጉዳት በመነሣሣት ያቀረቡት አቤቱታ ውድቅ ይደረግልን፡፡ የአባላቱ አክሲዮን ሽያጭ በቃለ ጉባኤ ተይዞ በሠነዶች ማረጋገጫና ምዝገባ ጽ/ቤት እየፀደቀ እንድተላለፈ የተገለፀ ቢሆንም የዕግድ ትእዛዝ የተሰጠበት ፋብሪካ ስመ ሀብቱ ሊተላለፍ የሚችለው ፋብሪካው በሚገኝበት የቡራዩ ከተማ አስተዳደር በማስመዝገብ በመሆኑ አመልካች ከአቤቱታው ጋር በማያያዝ ያቀረበው ቃለ ጉባኤ የፋብሪካው ባለቤት አያደርገውም፡፡ የዕግድ ትእዛዙን ለማስመዝገብ ባደረግነው እንቀስቃሴ የንግድ ማህበሩን በበላይነት የሚያስተዳድረው የኦሮሚያ እንቨስትመንት ኮሚሽን የንግድ ማህበሩ ከፍተኛ የአክሲዩን ድርሻ ያላቸውና የድርጅቱ ባለቤቶች 1ኛ እና 2ኛ ተከሣሾች መሆናቸውን ያረጋገጠልን በመሆኑ አመልካች ያቀረቡት አቤቱታ በባንኩ ላይ ውጤት የለውም ተብሎ ውድቅ ይደረግልን የሚል ነው፡፡

ፍ/ቤቱ የግራ ቀኙን ክርክር መርምሮ አመልካች የተመሠረተው መስከረም 1998 ዓ.ም በወ/ሮ ስርጉት እንግዳወርቅ 900 አክሲዩን እና በወ/ሮ ሀድራት ሲባኒ  100 አክሲዩን በብር 1,000,000 ካፒታል ሲሆን 1ኛ እና 2ኛ ተከሣሾች ንግድ ማህበሩን የተቀላቀሉት መጋቢት 13/2003 ዓ.ም በተያዘ ቃለ ጉባኤ የወ/ሮ ስርጉትን የአክሲዮን ድርሻ 1ኛ ተከሣሽ የወ/ሮ ሀድራት ሲባኒን የአክሲዩን ድርሻ 2ኛ ተከሣሽ በመግዛት የአክሲዩን ሽያጩ መጋቢት 14/2003 ሰነዶች ምዝገባና ማረጋገጫ ጽ/ቤት ተመዝግቧል፡፡

1ኛ ተከሣሽ ይህንን የአክሲዩን ድርሻቸዉን መስከረም 12/2005፣ታህሳስ 22/2005 እና የካቲት 9/2005 በተያዘ ቃለ ጉባኤ በሽያጭ ለሌሎች በሽያጭ አስተላልፈው የካቲት 9/2005 ከማህበሩ የተሰናበቱ ሲሆን 2ኛ ተከሣሽም የነበረችውን  የአክሲዩን ድርሻ ታህሳስ 22/2005 በተደረገ የማህበሩ ስብሰባ ለሌሎች ሰዎች በሽያጭ አስተላልፈው ከማህበሩ የተሰናበቱ መሆኑን እና ቃለ ጉባኤው በሚመለከተው የሰነዶች ምዝገባና ማረጋገጫ ጽ/ቤት ዋና መ/ቤት መመዝገቡን አመልካች ካቀረበው ማስረጃ ፍ/ቤቱ ተገንዝቧል ከሳሽ በአመልካች የንግድ ማህበር ስም በሚንቀሳቀሰው ፋብሪካ/ቤት/ ላይ መጋቢት 24/2005 ዓ.ም በፍ/ቤት የዕግድ ትእዛዝ የሰጠው 1ኛ እና 2ኛ ተከሣሾች በንግድ ማህበሩ የነበራቸውን የአክሲዩን ድርሻ በሽያጭ ለሌሎች ሰዎች አስተላልፈው ከማህበሩ ከተሰናበቱ በኃላ መሆኑን መረዳት ተችሏል፡፡

ከሳሽ አሣግጅያለው ያለው ቤት ይዞታ ያለው ራሱን ችሎ የሕግ ሠውነት ባለው አመልካች ስም እንጂ ክስ በቀረበባቸው 1ኛ እና 2ኛ ተከሣሾች ስም አይደለም ስለሆነም 1ኛ እና 2ኛ ተከሳሾች

የአክሲዮን ድርሻቸውን ሸጠው ከማህበሩ አባልነት በመሠናበታቸው ምክንያት የማህበሩ ንብረት ደግሞ የሚመዘገብበት አግባብ የለም በማለት የዕግድ ትእዛዝ እንዲነሣ ወስኗል፡፡

የአሁኑ አመልካች በዚህ ውሣኔ ላይ ያለውን ቅሬታ በይግባኝ ለማሳረም ለፌ/ጠ/ፍ/ቤት አቅርቦ ይግባኝ የተባለበት ውሣኔ ጉድለት የለበትም በማለት ይግባኙ ተቀባይነት አላገኘም፡፡

አመልካች በስር ፍ/ቤቶች ውሣኔ ላይ የተፈፀመ ያለውን መሠረታዊ የሕግ ስህተት በዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት ለማሳረም አቤቱታ አቅርቧል፡፡

የአመልካች አቤቱታ ይዘት ፡- የአሁኑ ተጠሪ የአክሲዮን ድርሻ ቃለ ጉባኤ መሠረት በውልና ማስረጃ በማፅደቅ የአክሱዮን ድርሻ ማስተላለፋቸውን ገልፀዋል፡፡ ሆኖም የአክሲዮን ድርሻ በውልና ማስረጃ ሊያልፍ የሚችል ቢሆንም በከሳሽ የታገደው ፋብሪካን ማስተላለፍ የሚቻለው ፋብሪካው በሚገኝበት በቡራዮ ከተማ አስተዳዳር ሽያጩን በተመለከተ በማስመዝገብ እንጂ በውልና ማስረጀ በማፅደቅ ብቻ ባለመሆኑ አመልካች ለክርክር መነሻ ለሆነው ንብረት ባለቤት አያደርገውም፡፡ ቤቱን ለማሳገድ በተንቀሳቀስንበት ወቅት በቡራዩ ከተማ አስተዳደር እንኳን ተጠሪ የፋብሪካው ባለቤት መሆናቸውን የሚገልፅ ምንም ዓይነት ማስረጃ አለመኖሩ እንዲሁም ለሰነዶች ምዝገባና ማረጋገጫ ጽ/ቤት የዕግድ ትእዛዙን ባስገባንበት ጊዜ ተጠሪ የንብረቱ ባለቤት ነው ተብሎ ያልተገለፀልን ከመሆኑ በተጨማሪ የንብረቱ ባለቤት 1ኛ እና 2ኛ ተከሳሾች መሆናቸውን በሰነድ ጭምር አረጋግጠናል በመሆኑም አመልካች /የአሁኑ ተጠሪ/ ያቀረበው ሰነድ ሐሰተኛ በመሆኑ በባንኩ ላይ ሕጋዊ ውጤት የለውም እንዲባልልን አቤቱታ ብናቀርብም የስር ፍ/ቤት በዝምታ አልፎታል የአክሲዮን ድርሻ ሲተላለፍ የተላለፈላቸው በአክሲዮኖች የአክሲዮኑ ንብረት በሆኑት የማይንቀሳቀሱ ንብረቶች በሚገኙበት የመንግስት አስተዳደር /የስመ ንብረት ዝውውርን የሚያደርገው አካል/ መገለጽ የለበትም ማለቱ እና በአሁኑ ተጠሪ ውስጥ ያለው የአክሲዮን ድርሻ መተላለፋ ሕጋዊነቱ ይጣራልን ብለን ያቀረብነው መቃወሚያን በማለፍ የተሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት በመሆኑ ውድቅ ይደረግልን የሚል ነው፡፡

የአመልካች አቤቱታ ለዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት ይቅረብ የተባለው 1ኛ ተጠሪ ዕግድ በተሰጠበት ንብረት ላይ መስከረም፣ታህሳስ እና የካቲት 2005 ዓ.ም በተያዘው ቃለ - ጉባኤና ሰነዶች ማረጋገጫና ምዝገባ ጽ/ቤት በተረጋገጠ የሽያጭ ለሌላ 3ኛ ወገን ያስተላለፈ እና የእግድ ትእዛዙም መጋቢት 24/2005 ዓ.ም የተሰጠው ባለሀብትነቱ በሽያጭ ከተላለፈ በኃላ በመሆኑ አስቀድሞ የተሰጠው የዕግድ ትእዛዝ ሊነሳ ይገባል በሚል በስር ፍ/ቤቶች የተሰጠውን ዳኝነት የሽያጭን ስምምነት በሰነዶች ማረጋገጫ ማረጋገጥ የሚያስከትለው ውጤት በተዋዋይ ወገኖች መካከል ነው ወይስ 3ኛ ወገን በሆነው አመልካች ላይም ህጋዊ ውጤት ያስከትላል?ንብረቱ ተላለፈ የሚባለውን ውልን ከማረጋገጥ ባሻገር በሚመለከተው

የመንግስት መ/ቤት ስመ ሀብቱ ከሻጩ ወደ ገዥው የተላላፈ መሆኑ በሚያመለክተው ሁኔታ የምዝገባ ስርዓቱ መከናወኑ ሲታወቅ? ከሚሉ ነጥቦች አንጻር ለማየት ተብሎ ነው፡፡

የ3ኛ ተጠሪ መልስ ይዘት መጋቢት 24/2005 ዓ.ም በስር ፍ/ቤት የተሰጠው የዕግድ ትእዛዝ 1ኛ ተከሳሽ አቶ ጌታነህ ታምሩ በዶዶላ ኢንተርናሽናል ትሬዲንግ ኃላ/የተ/የግ/ማ. ውስጥ ያለው ድርሻ የተከሳሾች ስም ተመዝግበው የሚገኝ መሆኑ ተጣርቶ እንዳይሸጥ እንዳይለወጥ ለ 3ኛ ወገን እንዳይተላለፍ የሚል ነው፡፡ ተጠሪ ራሱን የቻለ የሕግ ሰውነት ያለው ተቋም ሆኖ እንደተፈጥሮ ሰው በራሱ የመክሰስ፣የመከሰስ፣ ንብረት የማንቀሳቀስ መብት ያለው ኃላ/የተ/የግ/ማህበር ሆኖ የተቋቋመ ነው ፡፡ አቶ ጌታሁን ምናለ እና 3ኛ ተጠሪ ሁለት የተለያዩ ራሳቸውን የቻሉ የሕግ ሰውነት ያላቸው ናቸው በአቶ ጌታነህ ምናለ አኪሲዩን ድርሻ ላይ የተሰጠው የዕግድ ትእዛዝ የሚመለከተው አቶ ጌታነህን ብቻ ነው የ3ኛ ተጠሪ አክሲዩንም ሆነ የሚንቀሳቀስና የማይንቀሳቀስ ንብረት እንዲከበር የተሰጠ ትእዛዝ የለም የእግድ ትእዛዝ የተሰጠበት አክሲዩን ከእግዱ በፊት በሌላ ወገን ተላልፋል፡፡ 3ኛ ተጠሪ የስር ተከሣሽ ባለመሆኑ የማገጃ ትእዛዝ አይመለከተውም፡፡ ማንኛውም አኪሲዩን በሰነዶች ማረጋገጫና ምዝገባ ጽ/ቤት ከተመዘገበ ይተላለፋል እንጂ እንደገና በቡራዮ ከተማም ሆነ በሌላ ማዘጋጀ ቤት ቀጣይ ምዝገባ እንደሚፈፀምበት የሚደነግግ ሕግ የለም በተጠሪ ስም የተመሠረተ ግንባታ እንጂ ፋብሪካ የለም፡፡ የባንኩን ጥቅም ለመጉዳት ተጠሪ የፈፀመው ሕገ ወጥ ድርጊት የለም ፡፡ የፋብሪካው ላይ የተሰጠ ምንም አይነት እግድ ስለለሌ በቡራዮ ከተማ ማዘጋጃ ቤት የሚከናወን የምዝገባ ሥርዓት የለም የሚል ነው፡፡

1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች መልስ አላቀረቡም የአመልካች የመልስ መልስ ተያይዟል በግራ ቀኙ መካከል የተደረገው አጠቃላይ ክርክር ከዚህ በላይ በአጭሩ የተመዘገበው ሲሆን እኛም ክርክራቸውን ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው የሥር ፍ/ቤት ውሣኔ የአመልካች አቤቱታ ለዚህ ሰበር ችሎት ይቅረብ ከተባለበት ነጥብ እና አግባብነት ካለው ድንጋጌ ጋር እንደሚከተለው መርምረናል ፡፡

እንደመረመርነውም 3ኛ ተጠሪ በብር 1,000,000/አንድሚሊዩን ብር / በ1998 ዓ.ም የተመሠረተ ሲሆን 1ኛ ተጠሪ 800 አክሲዩኖችን 2ኛ ተጠሪ ደግሞ 100 አክሲዩን ከወ/ሮ ስርጉት እንግዳወርቅ ገዝተው 1ኛ ተጠሪ ማህበሩን በስራ አስኪያጅነት ሲመሩት ቆይተው የአክሲዩን ድርሻቸውን መስከረም 12/2005፣ታህሳስ 22/2005 እና የካቲት 9/2005 ዓ.ም በተደረገ የማህበሩ ስብሰባ ላይ በተያዘ ቃለ ጉባኤ በሽያጭ ለሌሎች ሰዎች አስተላልፈው ከማህበሩ የካቲት 9/2005 ዓ.ም የተሰናበቱ መሆኑ እና ቃለ ጉባኤው በሰነዶች ምዝገባና ማረጋገጫ የተመዘገበ ቢሆንም መጋቢት 24 ቀን 2005 ዓ.ም ከፍ/ቤት የተሰጠውን የዕግድ ትእዛዝ 1ኛ ተጠሪ የተቀበለ መሆኑ፣አመልካች የዕግድ ትእዛዙን ለማስመዝገብ ባደረጉት እንቅስቃሴ የ 3ኛ ተጠሪ ማህበር ከፍተኛ አክሲዮን ድርሻ ያላቸውና የድርጅቱ ባለቤቶች 1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች መሆናቸውን የኦሮሚያ ኢንቨስት መንት ኮሚሽን ለአመልካች ያረጋገጠላቸው መሆኑ፣1ኛ ተጠሪ ከዚህ በላይ እንደተመዘገበው በ 3ኛ ተጠሪ ማህበር የነበራቸውን የአኪሲዩን ድርሻ

በሽያጭ ለሌላ ሰው ማስተላለፋቸው በሰነዶች ምዝገባና ማረጋገጫ ጽ/ቤት የተመዘገበ መሆኑ በማህበሩ ባለአክሲዮኖች መካከል ወይም በማህበሩ እና በባለአክሲዬን መካከል ያለውን ግንኙነት በሚመለከት ካልሆነ በቀር በንግድ ሕጉ አንቀፅ 522 በተመለከተው መሠረት የአክሲዮን መተላለፋ በፅሑፍ ተረጋግጦ በባለ አክሲዬኖች መዝገብ ላይ ካልተፃፈ በ 3ኛ መገኖች ላይ መቃወሚያ ሊሆን የማይችል መሆኑ ጋር ተገናዝቦ ሲታይ የ 1ኛ ተጠሪ የአክሲዬን ድርሻ ለሌሎች ሰዎች በሽያጭ መተላለፍ በሰነዶች ምዝገባና ማረጋገጫ መመዝገቡ ብቻውን በ 3ኛ ወገኖች ላይ መቃወሚያ ሊሆን አይችልም፡፡ ሌላው 3ኛ ተጠሪ በስር ፌ/ከፍ/ፍ/ቤት የዕግድ ትእዛዝ እንዲነሳለት የቀረበው አቤቱታ ይዘት በስሜ ያለው ንብረት /ቤት/ እንዲታገድ የተደረገው በአግባቡ ስላልሆነ ዕግዱ ይነሳልኝ በሚል ሲሆን በዚህ ሰበር ችሎት ባደረገው ክርክር ወይም በሰጠው መልስ ላይ ደግሞ በስር ፍ/ቤት የተሰጠው የዕግድ ትእዛዝ የ1ኛ ተጠሪ የአክሲዮን ድርሻ ላይ ነው፡፡ ተጠሪ እና 3ኛ ተጠሪ ሁለት የተለያዩ ራሳቸውን የቻሉ የሕግ ሰውነት ያላቸው ናቸው፡፡ 1ኛ ተጠሪ ላይ የተሰጠው የዕግድ ትእዛዝ የሚመለከተው 1ኛ ተጠሪን ብቻ ነው፡፡ የ3ኛ ተጠሪ የሚንቀሳቀስም ሆነ የማይንቀሳቀስ ንብረት እንዲታገድ የተሰጠ ትእዛዝ የለም ብሎ የተከራከረው በስር ፍ/ቤት ዕግድ ትእዛዝ እንዲነሳለት ከቀረበው አቤቱታ ጋር የሚጋጭ ሲሆን 3ኛ ተጠሪ በመልሱ እንደገለፀው የእግድ ትእዛዝ የተሰጠው በ1ኛ ተጠሪ የአኪሲዮን ድርሻ ላይ ከሆነ እና የ3ኛ ተጠሪ የሚንቀሳቀስም ሆነ የማይንቀሳቀስ ንብረት በፍ/ቤቱ ትእዛዝ ያልተገደበ ከሆነ 1ኛ ተጠሪ በሚመለከት ጉዳዩ 3ኛ ተጠሪ የሚንቀሳቀስም ሆነ የማይንቀሳቀስ ንብረት በፍ/ቤቱ ትእዛዝ ያልተገደበ ከሆነ 1ኛ ተጠሪን በሚመለከት ጉዳይ 3ኛ ተጠሪ የዕግድ ይነሣልኝ አቤቱታ ለማቅረብ የሚያስችል መብት ወይም ጥቅም የሌለው መሆኑን ተጠሪው ካቀረበው መልስ መረዳት ይቻላል ፡፡

ከዚህ በላይ እንደተመዘገበው የ1ኛ ተጠሪ የአክሲዮን ድርሻ ሽያጭ በባለአኪስዮኖች መዝገብ ላይ ያልተፃፈ በመሆኑ በንግድ ሕግ አንቀፅ 522 መሠረት ሶስተኛ ወገኖች የአክሲዬን ሽያጭ መፈፀሙን ወይም የ1ኛ ተጠሪ አክሲዬን ድርሻ በሽያጭ ወደ ሌላ ሰው መተላለፋን የሚያውቁበት መንገድ ባለመኖሩ መቃወሚያ ሊሆን አይችልም፡፡ የ1ኛ ተጠሪ የአኪሲዬን ድርሻ ለሌላ ሰው በሽያጭ ስለመተላለፋ ማህበርተኞችም የተስማሙበት ውሣኔ በንግድ መዝገብ ላይ መመዝገብ እንዳለበት በንግድ ሕጉ አንቀጽ 523 /3/ የተመለከተ ሲሆን በተያዘው ጉዳይ የ1ኛ ተጠሪ የአክሲዮን ድርሻ ሽያጭ ጉዳይ በሰነዶች ምዝገባና ማረጋገጫ ጽ/ቤት ከመመዝገቡ በቀር በንግድ ሕጉ አንቀጽ 522 እና 523 /3/ በተመለከተው መሠረት ያልተመዘገበ በመሆኑ 3ኛ ወገን በሆነው በኢት/ንግድ ባንክ /አመልካች/ ላይ መቃወሚያ ሊሆነው አይችልም የስር ፍ/ቤቶች የአክሲዩን ሽያጩ በሰነዶች ምዝገባና ማረጋገጫ ጽ/ቤት የተመዘገበ መሆኑን እና ሽያጩ የተደረገው የዕግድ ትእዛዝ ከመስጠቱ በፊት መሆኑን ብቻ በመውሰድ የዕግድ ትእዛዙ እንዲነሳ የሰጡት ትእዛዝ ከ3ኛ ወገን መብት ጋር በአግባቡ ባለማገናዘብ የተሰጠ ስህተት በመሆኑ መሠታዊ የሕግ ስህተት ተፈፅሟል ሊታረም ይገባል ብለናል ፡፡

## ው ሣ ኔ

1. የፌ/ከፍ/ፍ/ቤት በኮ/መ/ቁ.134151 መጋቢት 12 ቀን 2006 ዓ.ም በዋለ ችሎት የሰጠው ትእዛዝ እና የፌ/ጠ/ፍ/ቤት በፍ/ብ/ይ/መ/ቁ.100764 በቀን 25/09/2005 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠውን ትእዛዝ በፍ/ብ/ስ/ስ/ቁ.348/1/ መሠረት ተሽሯል ፡፡
2. በስር ፍ/ቤት መጋቢት 24 ቀን 2005 ዓ.ም በዋለው ችሎት የተሰጠው የዕግድ ትእዛዝ ሊነሳ አይገባም ብለናል ፡፡
3. መዝገቡ ዕልባት ያገኘ በመሆኑ ወደ መ/ቤት ይመለስ ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

መ/ብ

የሰ/መ/ቁጥር---154564

ግንቦት 30 ቀን 2011 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ብርሃኑ አመነዉ

በዕዉቀት በላይ

እንዳሻዉ አዳነ

ሃይሉ ነጋሽ

እትመት አሠፋ

**አመልካቾች፡-** 1. አቶ አብዱሰላም ሰይዱ አብዴ

2. አቶ ጥላሁን አቻምየለህ ይርሳዉ

3. አቶ ሰይዱ አብዴ አድጎ

**ተጠሪ፡-** የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለዉ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍ ር ድ**

ለዚህ ሰበር ክርክር መነሻ የሆነው አፈጻጸምን የሚመለከት ሲሆን የተጀመረዉ በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ነዉ፡፡ በዚሁ ፍ/ቤት የአሁን ተጠሪ የፍርድ ባለመብት፤ አቶ ጌታነህ ምናለ እና ወ/ሮ አልጋነሽ አበጀ የፍርድ ባለዕዳዎች ሲሆኑ የአሁን አመልካቾች ደግሞ የመቃወም አመልካቾች ነበሩ፡፡ አመልካቾች በስር ፍ/ቤት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 418 መሠረት ያቀረቡት የመቃወሚያ አቤቱታ ይዘት፡- የፍርድ ባለዕዳዎች በዶዶላ ኢንተርናሽናል ትሬዲንግ ኃ/የተ/የግ/ማህበር ዉስጥ ያላቸዉ የአክሲዮን ድርሻ ተሽጦ ለተጠሪ እንዲከፈል በሚል የካቲት 15 ቀን 2008 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት የተሰጠዉ የአፈጻጸም ትዕዛዝ የፍርድ ባለዕዳዎች በማህበር ዉስጥ 1ኛ የፍርድ ባለዕዳ ከነበራቸዉ 800 አክሲዮኖች ዉስጥ ለ1ኛ፣ 2ኛ እና 3ኛ አመልካቾች እንደቅደም ተከተላቸዉ 266፣ 100 እና 434 አክሲዮኖችን በሽያጭ አስተላልፈዉ በሰነዶች ማረጋገጫና ምዝገባ ጽ/ቤት በቁጥር ዋ/መ/5533/4ለ/05 የካቲት 18 ቀን 2005 ዓ.ም ያስተላለፉ ሲሆን 2ኛ የፍርድ ባለዕዳ ደግሞ ከነበራቸዉ 100 አክሲዮኖች ዉስጥ ለ1ኛ እና 2ኛ አመልካቾች እንደቅደም ተከተላቸዉ 67 እና 44 አክሲዮኖችን በሽያጭ በሰነዶች ማረጋገጫና ምዝገባ

ጽ/ቤት በቁጥር ዋ/መ/5992/4ለ/05 ጥር 01 ቀን 2005 ዓ.ም ቀርበዉ አስተላልፈዉ ከማህበሩ ተሰናብተዋል፡፡ የአክሲዮን ድርሻቸዉ ስለመተላለፉም በንግድ መዝገብ ላይ ተመዝግቧል፡፡ ስለሆነም የፍርድ ባለዕዳዎች የአክሲዮን ድርሻ የሌላቸዉና ትዕዛዙ የተሰጠዉ በአመልካቾች ሀብትና የአክሲዮን ድርሻ ላይ በመሆኑ የአፈጻጸሙ ትዕዛዝ ይነሳልን የሚል ነዉ፡፡

ተጠሪ ለመቃወሚያዉ በሰጠዉ መልስ ለክርክሩ መነሻ የሆኑት አክሲዮኖች የታገዱት የፍ/ባለመብት ባቀረበዉ ክስ መነሻነት በመ/ቁ 134151 መጋቢት 24 ቀን 2005 ዓ.ም ነዉ፡፡ በወቅቱ የፍ/ቤቱን ትዕዛዝ ባደረስንበት ወቅት 1ኛ የፍርድ ባለዕዳ የዶዶላ ኢንተርናሽናል ትሬዲንግ ማህበር ሥራ አስኪያጅ ነበሩ፡፡ በወቅቱ በእግዱ ምክንያት በማህበሩ ስም የሚገኝ ቤት መታገዱን ገልጾ ማህበሩ እግዱ እንዲነሳለት የጠየቀ ሲሆን በስር ፍ/ቤት ዕግዱ እንዲነሳ ተደርጎ የሰበር አቤቱታ አቅርበንበት በንግድ ሕጉ አንቀጽ 522 መሰረት የአክሲዮን መተላለፉ በጽሁፍ ተረጋግጦ በባለአክሲዮኖች መዝገብ እስካልተመዘገበ ድረስ በ3ኛ ወገኖች ላይ መቃወሚያ አይሆንም ተብሎ እግዱ እንዲነሳ የተባለበት ትዕዛዝ በዉሳኔ ተሽሯል፡፡ በወቅቱ አመልካቾች የማህበሩ አባላት መሆናቸዉን ማህበሩ የገለጸ በመሆኑ ጉዳዩ ፍጻሜ ማግኘቱን እያወቁ ያቀረቡት አቤቱታ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 418(1) መሰረት ዉድቅ ሊደረግ ይገባል፡፡ የአክሲዮኖቹ ሽያጭ በንግድ መዝገብ ላይ ተመዝግቧል የሚል ክርክር ቢያቀርቡም የምዝገባ ቀናት ተብለዉ የተጠቀሱት ቃለ-ጉባኤዎቹ በሰነዶች ማረጋገጫ እና ምዝገባ ጽ/ቤት የተመዘገቡበት ቀን እንጂ በንግድ ሕጉ መሠረት በንግድ መዝገብ መመዝገባቸዉን አያሳይም፤ የቀረበዉ ማስረጃ በቃለ ጉባኤዎቹ ላይ የንግድ ሚኒስቴር ማህተም መደረጉን ከሚያሳይ በቀር የአክሲዮን ማስተላለፉ በንግድ ሕግ ቁጥር 523 መሠረት መመዝገቡን አያሳይም፤ የቀረበ የሰነድ ማስረጃም የለም፡፡ አሁን በማስረጃነት የተያያዘዉ ከንግድ ሚኒስቴር የተሰጠዉ ሰነድም አመልካቾች ይህንን አቤቱታ ከማቅረባቸዉ ጥቂት ቀናት ቀደም ብሎ መሆኑ ሲታይ አስቀድሞ ያስመዝገቡ ለማስመሰል እየጣሩ መሆኑን ነዉ፡፡ ስለሆነም አቤቱታዉ ዉድቅ ይደረግልን በማለት ተከራክሯል፡፡

የስር ፍ/ቤት የአመልካቾችን የመቃወም አቤቱታ እና የተጠሪን መልስ መርምሮ በአክሲዮኖች ላይ ዕግድ በተሰጠበት ወቅት የፍርድ ባለዕዳዎች በማህበሩ የነበራቸዉን የአክሲዮን ድርሻ በሽያጭ ለሌላ ሰዉ ስለማስተላለፋቸዉ በሰነዶች ምዝገባና ማረጋገጫ ጽ/ቤት ከመመዝገቡ በቀር በወቅቱ የአክሲዮን ማስተላለፍ የንግድ ሕግ ቁጥር 523 መሠረት የተመዘገበ አለመሆኑን የሚያስገነዝበን በመሆኑና ካልተመዘገበ ደግሞ የተጠሪን ጨምሮ ባሉ ሌሎች 3ኛ ወገኖች ላይ በመቃወሚያነት ሊቀርብ የማይገባ በመሆኑ ቀደም ሲል የፍርድ ባለዕዳዎች በዶዶላ ኢንተርናሽል ትሬዲንግ ኃ/የተ/የግ/ማህበር ዉስጥ ያላቸዉ የአክሲዮን ድርሻ በሀራጅ ጨረታ ተሽጦ ገንዘቡ ለተጠሪ እንዲከፈል በሚል የካቲት 15 ቀን 2008 ዓ.ም የሰጠዉ ትዕዛዝ እንዲነሳላቸዉ አመልካቾች ያቀረቡት መቃወሚያ ዉድቅ ተደርጓል በማለት አፈጻጸሙን እንዲቀጥልበት ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡ በዚህ የአፈጻጸም ትዕዛዝ ቅር በመሰኘት አመልካቾች ቅሬታ ቢያቀርቡም ፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በትዕዛዝ የስር ፍ/ቤትን ዉሳኔ አጽንቶታል፡፡ አመልካቾች የሰበር አቤቱታ ያቀረቡት ይህን ዉሳኔ በመቃወም ለማስቀየር ነዉ፡፡

አመልካቾች ያቀረቡት የሰበር አቤቱታ ይዘት፡- የፍርድ ባለዕዳዎች በአክሲዮን ማህበሩ ዉስጥ የአክሲዮን ድርሻ መኖሩ ተረጋግጦ ሳይታገድ በሰበር መ/ቁ 103472 በስር ፍ/ቤት የተሰጠዉ የዕግድ ትዕዛዝ አይነሳም መባሉ የፍርድ ባለዕዳዎች በአክሲዮን ማህበሩ ዉስጥ የአክሲዮን ድርሻ አላቸዉ ለማለት የሚያስችል በቂ ምክንያት አይደለም፡፡ አመልካቾች የማህበሩን አክሲዮኖች ከሌሎች ባለአክሲዮኖች በመግዛት በሰነዶች ማረጋገጫና ምዝገባ ጽ/ቤት ቀርበዉ በ29/08/2005 ዓ.ም በተመዘገበ ቃለ ጉባኤ እንዲሁም ሚያዚያ 29 ቀን 2005 በተደረገ ምዝገባ በንግድ መዝገብ አስመዝግበን የያዝን ሲሆን የማህበሩን አክሲዮን አሳድገን የማህበሩን የአክሲዮን ድርሻ ሙሉ በሙሉ ይዘን እንገኛለን፡፡ የፍርድ ባለዕዳዎች በሰነዶች ማረጋገጫና ምዝገባ ጽ/ቤት በቀን 18/06/2005 ዓ.ም እና በ01/05/2005 ዓ.ም ከማህበሩ ያላቸዉን ድርሻ ከእኛ በፊት የአክሲዮን አባላት ለነበሩ ግለሰቦች በሽያጭ አስተላልፈዉ የተሰናበቱ እና የአክሲዮን ድርሻዉም ስለመተላለፉ በንግድ መዝገብ ላይ በ15/01/2005 ዓ.ም፣ በ01/05/2005 ዓ.ም በ19/06/2005 ዓ.ም በሽያጭ ስለመተላለፉ ተመዝግቧል፡፡ በሰ/መ/ቁ 103472 ላይ የተሰጠዉን የዕግድ አይነሳም ትዕዛዝ መኖሩን አመልካቾች ያወቅነዉ የስር ፍ/ቤት የካቲት 15 ቀን 2008 ዓ.ም በሰጠዉ ትዕዛዝ የፍርድ ባለዕዳዎች ድርሻ በሀራጅ ተሽጦ ለፍርድ ባለመብት እንዲከፈል የሚለዉ ትዕዛዝ ከደረሰን በኋላ ስለሆነ አመልካቾች ተከራካሪ ባልሆኑበት ማህበሩ መብትና ጥቅም የለዉም የተባለበት ዉሳኔ መሠረት የባለዕዳዎች አክሲዮን ድርሻ መኖሩ ተረጋግጦ ባልታገደበት ባለዕዳዎች የአክሲዮን ድርሻ አላቸዉ መባሉ ስህተት ነዉ፡፡

የስር ፍ/ቤት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 418 መሠረት ያቀረብነዉን የክስ አቤቱታ መደበኛዉን የክስ መስማት ሂደት ሳይከተልና ያቀረብነዉን ክስና ማስረጃ በተገቢዉ ሳይመዝን የሰጠዉ ዉሳኔ ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁ 86133 እና 87833 ላይ የሰጠዉን አስገዳጅ ትርጉም የጣሰ በመሆኑ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ፡፡ የአክሲዮን መተላለፉ በሚገባ ሁኔታ በሰነዶች ማረጋገጥና ምዝገባ ጽ/ቤት ፀድቆ መተላለፉን 3ኛ ወገኖች በሚያዉቁት ሁኔታ የተመዘገበ ሆኖ እያለ አልተመዘገበም መባሉ ስህተት ነዉ፡፡ እንዲሁም ንግድ ሚኒስቴር መጋቢት 14 ቀን 2009 ዓ.ም በጻፈዉ ማስረጃ የአክሲዮን መተላለፉን 3ኛ ወገኖች እንዲያዉቁ በንግድ ሚኒስቴር የንግድ መዝገብ ላይ ስለመመዝገቡ የስር ፍ/ቤት በፍርድ ሀተታዉ አረጋግጧል፡፡ የአክሲዮን መተላለፍ ለዉጡና ማሻሻያዉ በሕግ እንዲመዘገብ በተቀመጠዉ አስገዳጅ የምዝገባ ጊዜያት የሚመዘገብ ሆኖ እያለ የምዝገባዉ ጊዜዉ አልተጠቀሰም በሚል ሽያጩ በንግድ መዝገብ ላይ አልተመዘገበም መባሉ ስህተት በመሆኑ የስር ፍ/ቤት ዉሳኔ ይሻርልን የሚል ነዉ፡፡

የአመልካቾች አቤቱታ ተመርምሮ ከዚህ ቀደም በአሁኑ ተጠሪ፣ በፍርድ ባለዕዳዎችና በማህበሩ መካከል የነበረዉ ዕግድ ይነሳልን ክርክር አሁን ክርክር ባስነሳዉ የአክሲዮን ድርሻ ላይ ነዉ ወይስ የማህበሩ ንብረት በሆነዉ ቤት ላይ? ይህ ክርክር እስከ ሰበር ሰሚ ችሎት ደርሶ በዉሳኔ በተቋጨ ጊዜ የአሁን አመልካቾች የክርክር ተካፋይ ነበሩ ወይስ አልነበሩም? የአሁን አመልካቾች በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 418 መነሻ የክርክር ተካፋይ የሆነዉ ክርክሩ በሚታይበት ጊዜ የአሁን አመልካቾች የአክሲዮን ድርሻ

ሽያጭ በዉልና ማስረጃ ምዝገባ ጽ/ቤት የተደረገ ከመሆኑም በላይ በንግድ ሕጉ ቁጥር 522 መሠረት የአክሲዮኖቹ መዝገብም ላይ የተመዘገበ ነዉ በሚል አቅርበዉ የሚከራከሩ እንደመሆኑ መጠን አሁን በግራ ቀኙ የተነሳዉ ክርክር አስቀድሞ በሰበር ሰሚዉ ችሎት ቀርቦ ዉሳኔ ያገኘ ጉዳይ ነዉ ማለት ይቻላል? አይቻልም? የአክሲዮን ድርሻ በሽያጭ ለመተላለፉስ ይኸዉ በሽያጭ የማስተላለፍ ተግባር በ3ኛ ወገን ላይ ዉጤት ያስከትል ዘንድ በንግድ ሚኒስቴር አማካኝነት በባለ አክሲዮኖች መዝገብ ላይ ተመዝግቧል ሲል ያቀረበዉ ክርክር በንግድ ሕግ ቁጥር 523 የተመለከተዉን መስፈርት ያሟላ ነዉ ወይስ አይደለም? ከሚሉት ነጥቦች አንጻር ጉዳዩ ይታይ ዘንድ ለሰበር ያስቀርባል የተባለ ሲሆን የግራ ቀኙን መልስ እና የመልስ መልስ በጽሁፍ በማቀባበል እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

ተጠሪ በሰበር መልሱ ያቀረበዉ ክርክር ይዘት፡- ተጠሪ በስር ፍ/ቤት በመ/ቁ 134151 መጋቢት 24 ቀን 2005 ዓ.ም በሰጠዉ የእግድ ትዕዛዝ መሠረት በፍርድ ባለዕዳዎች በእነ አቶ ጌታነህ ምናለ ስም በዶዶላ ኢንተርናሽናል ትሬዲንግ ኃ/የተ/የግ/ማህበር ዉስጥ ተመዝግበዉ የሚገኙ አክሲዮኖቹን በአግባቡ እንዲታገዱ አድርጓል፡፡ የዕግድ ትዕዛዙ ለማህበሩ እንዲደርስ የተደረገ ሲሆን በወቅቱ የዕግድ ትዕዛዙን የማህበሩ ሥራ አስኪያጅ ነኝ በማለት ፈርመዉ የተቀበሉት አቶ ጌታነህ ምናለ ናቸዉ፡፡ ማህበሩ አክሲዮኖቹ በሽያጭ ለሌላ 3ኛ ወገን በመተላለፋቸዉ ምክንያት ለማገድ አልችልም በማለት ለስር ፍ/ቤት የሰጠዉ ምላሽ የዕግድ ትዕዛዙን መቀበሉን ያመለክታል፡፡ በወቅቱ ማህበሩ በንብረቱ ላይ የተላለፈዉ የዕግድ ይነሳልኝ ሲል ጥያቄ ያቀረበ ቢሆንም የዕግድ ትዕዛዙ የተላለፈዉ በማህበሩ ቤት ላይ ሳይሆን በባለዕዳዎቹ የአክሲዮን ድርሻ ላይ ነዉ፡፡ የስር ፍ/ቤትም ሚያዚያ 12 ቀን 2006 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት የሰጠዉ ትዕዛዝ የአክሲዮን ድርሻዎቹ እንዲታገዱ በ24/07/2005 ዓ.ም የተሰጠዉ የዕግድ ትዕዛዝ እንዲነሳ ነዉ፡፡

በሰ/መ/ቁ 103472 ሰበር ሰሚ ችሎት እግዱ ሊነሳ አይገባም በማለት የሰጠዉ ዉሳኔ የአክሲዮኖቹ ሽያጭ በንግድ ሕግ ቁጥር 522 እና 523(3) መሰረት ባለመመዝገቡ በ3ኛ ወገን ላይ በመቃወሚያነት ሊቀርብ እንደማይችል ገልጾ ነዉ፡፡ በመሆኑም የተሰጠዉ ዉሳኔ የፍርድ ባለዕዳዎቹ የማህበሩ ባለአክሲዮኖች መሆናቸዉን በተዘዋዋሪ መንገድ ያመለከተ ነዉ፡፡ በተጠቀሰዉ የመዝገብ ቁጥር ሰበር ሰሚ በሰጠዉ ዉሳኔ ማህበሩ ክስ ለማቅረብ የሚያስችል መብት የለዉም አላለም፡፡ አመልካቾችም በዚህ መዝገብ ተከራካሪ አልነበርንም በማለት ያቀረቡት ክርክር ተገቢነት የለዉም፡፡ ማህበሩ የአክሲዮን መተላለፉ በሰነዶች ማረጋገጫና ምዝገባ ጽ/ቤት መመዝገቡን ብቻ በመግለጽ ሲከራከር ቆይቷል፡፡ ችሎቱም በጽ/ቤቱ ብቻ መመዝገቡ በቂ አለመሆኑን ገልጾ ዉሳኔ ሲሰጥ ደግሞ የማህበሩ ባለአክሲዮኖች ከማህበሩ ጋር ምንም ዓይነት ግንኙነት እንደሌላቸዉ በማስመሰል በቃለ-ጉባኤዉ የሚኒስትሩ መስሪያ ቤት ማህተም እንዲያርፍባቸዉ ጥያቄ ባቀረቡት መሠረት ማህተም ያረፈባቸዉን ቃለ ጉባኤዎች ለስር ፍ/ቤት በማቅረብ ምዝገባ እንደተከናወነ አድርገዉ የሚያቀርቡት ክርክር አግባብነት የለዉም፡፡

አመልካቾች በስር ፍ/ቤት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 418 መሠረት ያቀረቡት አቤቱታ በአግባቡ ታይቶና ተመርምሮ ዉሳኔ የተሰጠበት ነዉ፡፡ የአክሲዮን መተለለፍ የተደረገባቸዉን ቃለ ጉባኤዎች

በሰነዶች ማረጋገጫና ምዝገባ ጽ/ቤት የተመዘገበቡትን ቀን በንግድ መዝገብ የተመዘገቡበት ቀን እንደሆነ በማስመሰል እንዲሁም አቤቱታዉን ለፍ/ቤቱ ከማቅረባቸዉ ከአንድ ቀን በፊት ቃለ ጉባኤዎቹ በማህተም ተረጋግጦ እንዲሰጣቸዉ ጠይቀዉ የንግድ ሚኒስቴር ማህተም ያረፈባቸዉን ቃለ ጉባኤዎች በማስረጃነት አቅርበዋል፡፡ ይሁን እንጂ ማህተም ማረፉ በንግድ ሕጉ ቁጥር 523 መሠረት በንግድ መዝገብ መመዝገብን አያረጋግጥም፡፡ ስለሆነም በስር ፍ/ቤት አክሲዮኖቹ በአግባቡ መታገዳቸዉ እና ማህበሩ ያካሄደዉ የአክሲዮን ማስተላለፍ በሕጉ መሰረት በአግባቡ አለመመዝገቡ ተረጋግጦ በስር ፍ/ቤት የተሰጠዉ ዉሳኔ በአግባቡ ስለሆነ ይጽናልን የሚል ነዉ፡፡

አመልካቾች በበኩላቸዉ የሰበር አቤቱታቸዉን በሚያጠናክር መልኩ የመልስ መልስ አቅርበዋል፡፡

የግራቀኙ ክርክር ባጭሩ ከላይ የተመለከተዉን የሚመስል ሲሆን እኛም አቤቱታ ከቀረበበት ዉሳኔ እና አግባብነት ካለዉ የሕግ ድንጋጌ ጋር በማገናዘብ መዝገቡን መርምረናል፡፡ የሰበር አቤቱታዉ ያስቀርባል ሲባል ከተያዙ ጭብጦች አንጻር መርምረን እንደተረዳነዉ መጋቢት 24 ቀን 2005 ዓ.ም በስር ፍ/ቤት የተሰጠዉ የእግድ ትዕዛዝ የፍርድ ባለዕዳዎች በዶዶላ ኢንተርናሽናል ትሬዲንግ ኃ/የተ/የግል ማህበር ዉስጥ የነበሯቸዉ የአክሲዮን ድርሻዎች የታገዱ መሆኑን፤ የፍርድ ባለዕዳዎች በማህበሩ ዉስጥ የነበሯቸዉን አክሲዮኖች በሽያጭ ለአመልካቾች የ1ኛ የፍርድ ባለዕዳ 750 አክሲዮኖች መስከረም 15 ቀን 2005 ዓ.ም፣ 26 አክሲዮኖች ጥር 01 ቀን 2005 ዓ.ም እና 24 አክሲዮኖች የካቲት 19 ቀን 2005 ዓ.ም እንዲሁም የ2ኛ የፍርድ ባለዕዳ አክሲዮኖች ጥር 01 ቀን 2005 ዓ.ም የተላለፉበት ቃለ-ጉባኤ በሰነዶች ማረጋገጫና ምዝገባ ጽ/ቤት ተመዝግቦ የተላለፈ መሆኑ፤ ማህበሩ በስር ፍ/ቤት በተሰጠ የእግድ ትዕዛዝ ቤቱ መታገዱን ገልጾ የፍርድ ባለዕዳዎች የአክሲዮን ድርሻቸዉን ለሌሎች ሰዎች አስተላልፈዉ ከማህበሩ በመልቀቃቸዉ የዕግድ ትዕዛዝ እንዲነሳለት ጠይቆ ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁ 103472 መስከረም 27 ቀን 2008 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት የአክሲዮን መተላለፉ በንግድ ሚኒስተር በንግድ መዝገብ አልተመዘገበም በማለት በንግድ ሕግ ቁጥር 522 እና 523 መሰረት የአክሲዮን ሽያጩ እስኪመዘገብ ድረስ በ3ኛ ወገኖች ላይ መቃወሚያ ስለማይችል የእግድ ትዕዛዙ ሊነሳ አይገባም በማለት የወሰነ መሆኑ በስር ፍ/ቤት የተረጋገጠ ነዉ፡፡

አመልካቾች የፍርድ ባለዕዳዎች የአክሲዮን ድርሻ በሀራጅ ተሸጦ ለተጠሪ ይከፈል ተብሎ የካቲት 15 ቀን 2008 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት የተሰጠዉን የአፈጻጸም ትዕዛዝ በመቃወም አቤቱታ ያቀረቡት የፍርድ ባለዕዳዎች የነበሩ አክሲዮኖች በሽያጭ አስቀድሞ የተላለፉላቸዉና መተላለፋቸዉም በሰነዶች ማረጋገጥና ምዝገባ ጽ/ቤት እና በንግድ ሚኒስቴር የንግድ መዝገብ የተመዘገበ በመሆኑ የአፈጻጸም ትዕዛዙ እንዲነሳ ሲሆን የስር ፍ/ቤት የአፈጻጸም ትዕዛዙ ሊነሳ አይገባም በማለት ለሰጠዉ ዉሳኔ በዋናነት የሰጠዉ ምክንያት የፍርድ ባለዕዳዎች የአክሲዮን ድርሻቸዉን ለአመልካቾች በሽያጭ ያስተላለፉበት ቃለ-ጉባኤ በሰነዶች ማረጋገጫና ምዝገባ ጽ/ቤት የተመዘገበ ቢሆንም በንግድ ሕግ ቁጥር 522 እና 523 አግባብ የፍርድ ባለዕዳዎች አክሲዮን በሽያጭ እንዳይተላለፍ በስር ፍ/ቤት መጋቢት 24 ቀን 2005 ዓ.ም ከተሰጠዉ የዕግድ ትዕዛዝ በፊት በንግድ ሚኒስቴር የንግድ መዝገብ መመዝገቡን

የሚያረጋግጥ ማስረጃ ካለመቅረቡም በላይ በሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁ 103472 የአክሲዮኖች ማስተላለፍ ሂደት በአክሲዮኖች መዝገብ አለመመዝገቡን ያረጋገጠበት ነዉ በማለት የአመልካቾችን አቤቱታ ዉድቅ ማድረጉን ነዉ፡፡ አመልካቾች አጥብቀዉ የሚከራከሩበትም ሆነ የዚህን ችሎት ምላሽ የሚሻዉ አብይ ጭብጥ የስር ፍ/ቤት ክርክር ያስነሱ የማህበሩ አክሲዮኖች ወደ አመልካቾች በሽያጭ መተላለፋቸዉ የፍርድ ባለዕዳዎች አክሲዮኖች ወደ 3ኛ ወገን እንዳይታለፉ በስር ፍ/ቤት የእግድ ትዕዛዝ ከመሰጠቱ በፊት በንግድ ሚኒስቴር አክሲዮኖች መዝገብ ላይ አልተመዘገበም በማለት የደረሰበት ድምዳሜም ሆነ የአመልካቾችን መቃወሚያ ዉድቅ ማድረጉ በአግባቡ ነዉ ወይስ አይደለም የሚለዉ ሲሆን በተጨማሪም እንደአስፈላጊነቱ ጉዳዩ ለሰበር ያስቀርባል ሲባል የተያዙ ሌሎች ጭብጦችን ጭምር ቀጥለን እንመለከታለን፡፡

በመሠረቱ የንግድ ሕግ ቁጥር 522 የአክሲዮኖች መተላለፍ በጽሁፍ የተረጋገጠ መሆን አለበት፤ መተላለፉም በአክሲዮኖቹ መዝገብ ላይ ካልተጻፈ በቀር ማህበሩና ሦስተኛ ወገኖችን መቃወሚያ ሊሆን አይችልም በማለት ሲደነግግ ቁጥር 523(3) ደግሞ አክሲዮን የተላለፈለት ለማህበሩ ባዕድ ለሆነ ሰዉ ሲሆን ማህበርተኞቹ የተስማሙበት ዉሳኔ በንግድ መዝገብ ላይ እንዲመዘገብ ያስፈልጋል በማለት በግልጽ ደንግጎ ይገኛል፡፡ ከእነዚህ ድንጋጌዎች ይዘት መገንዘብ የሚቻለዉ የአክሲዮን መተላለፍ ገዥና ሻጭን ለማስገደድ በጽሁፍ መደረግ ያለበት ሲሆን ማህበሩን ለማስገደድና የተላለፈለት ሰዉ በባለአክሲዮንነት ሙሉ መብት ለመጠቀም ስለአክሲዮን መተላለፉ ማህበርተኞች የተስማሙበት ዉሳኔ በአክሲዮኖች መዝገብ ሊመዘገብ ይገባል፡፡ እንዲሁም በ3ኛ ወገኖች ላይ እንደመቃወሚያ ሊቀርብ የሚችለዉ የአክሲዮኖቹ መተላለፍ በንግድ ሚኒስቴር የአክሲዮኖች መዝገብ ላይ ሲመዘገብ ነዉ፡፡ ይህን አስመልክቶ ከዚህ ቀደም አሁን ክርክር ባስነሱ አክሲዮኖች መተላለፍ ላይ ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁ 103472 ግልጽ ትርጉም ሰጥቶበታል፡፡ ስለዚህ የአክሲዮኖች መተላለፍ በ3ኛ ወገን ላይ መቃወሚያ ሊሆን የሚችለዉ ስለአክሲዮኖች መተላለፍ ዉል ሲኖር ወይም ማህበርተኞቹ የአክሲዮኖችን መተላለፍ ተቀብለዉ የተስማሙበት ሰነድ በሰነዶች ማረጋገጫና ምዝገባ ጽ/ቤት ተረጋግጦ መመዝገቡ ሳይሆን በአክሲዮኖች መዝገብ መመዝገቡ ነዉ፡፡

በተያዘዉ ጉዳይ አመልካቾች አክሲዮኖቹ የተላለፉላቸዉ መሆኑ በሰነዶች ማረጋገጥና ምዝገባ ጽ/ቤት የተመዘገበዉም ሆነ በንግድ ሚኒስቴር በአክሲዮኖች መዝገብ የተመዘገበዉ የስር ፍ/ቤት መጋቢት 24 ቀን 2005 ዓ.ም የዕግድ ትዕዛዝ ከመስጠቱ በፊት ነዉ የሚለዉን ክርክር ለማረጋገጥ ያቀረቡት ክርክርና ማስረጃዎች ማህበሩ የፍርድ ቤቱ የዕግድ ትዕዛዝ እንደደረሰዉ በቁጥር ARD/316/05 በ05/09/2005 ዓ.ም በጻፈዉ ደብዳቤ የፍርድ ባለዕዳዎቹ የማህበሩ አባል እንዳልሆኑና የአክሲዮን ድርሻ የሌላቸዉ መሆኑን የገለጸበት፤ በሰነዶች ማረጋገጫና ምዝገባ ጽ/ቤት የፍርድ ባለዕዳዎች አክሲዮኖች ወደ አመልካቾች በሽያጭ መተላለፋቸዉን የሚገልጸዉ ቃለ-ጉባኤ በቁጥር ዋ/መ/5992/4ለ/05 ጥር 01 ቀን 2005 ዓ.ም የተመዘገበበት እና የንግድ ሚኒስቴር መጋቢት 14 ቀን 2009 ዓ.ም ለዶዶላ ኢንተርናሽናል ትሬዲንግ ኃ/የተ/የግ/ማህበር በጻፈዉ ደብዳቤ ማህበሩ በ1998 ዓ.ም ሲቋቋም ጀምሮ የንግድ ምዝገባና

ፈቃድ አዉጥቶ በመስራት ላይ መሆኑንና በተለያዩ ጊዜያት ማህበሩ የመመስረቻ ጽሁፍ ለዉጡንና የአክሲዮን ማስተላለፍ የሚያደርግባቸዉን ቃለ-ጉባኤ በማጸደቅ የተመዘገበ መሆኑን ጠቅሶ፤ የቀረቡት ቃለ-ጉባኤ ሰነዶችም ማህተም አርፎና ተረጋግጠዉ የተመዘገቡ መሆኑን የገለጸበት ናቸዉ፡፡ ከእነዚህ ሰነዶች መካከል በንግድ ሕጉ ቁጥር 522 መሠረት የአክሲዮን መተላለፉ በ3ኛ ወገኖች መቃወሚያ በሚሆን መልኩ በአክሲዮኖች መዝገብ ላይ በስር ፍ/ቤት የዕግድ ትዕዛዝ ከተሰጠበት መጋቢት 24 ቀን 2005 ዓ.ም በፊት መፈጸሙን የሚያረጋግጥ ማስረጃ የለም፡፡ ይህን ማስረጃ የማቅረብና የማስረዳት ኃላፊነት የአመልካቾች ሲሆን የአክሲዮን መተላለፉ በሰነዶች ማረጋገጫና ምዝገባ ጽ/ቤት ጥር 01 ቀን 2005 ዓ.ም መመዝገቡ እንደተረጋገጠ ሁሉ በአክሲዮኖች መዝገብ የተመዘገበበትን ግልጽ ቀን የሚያረጋግጥ ማስረጃ ማቅረብ በቻሉ ነበር፡፡ የስር ፍ/ቤት የቀረቡለትን ክርክርና ማስረጃዎች መርምሮና መዝኖ የአክሲዮኖች መተላለፍ ፍ/ቤቱ ዕግድ ከሰጠበት መጋቢት 24 ቀን 2005 ዓ.ም በፊት በአክሲዮኖች መዝገብ መመዝገቡ አልተረጋገጠም ሲል የደረሰበት ድምዳሜ የሚነቀፍበት በቂ ምክንያት ካለመኖሩም በላይ ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት ማስረጃን ለመመዘንና ፍሬ ነገርን ለማረጋገጥ ስልጣን የተሰጣቸዉ የስር ፍ/ቤቶች ከደረሰቡበት የፍሬ ነገር ድምዳሜ ዉጪ ማስረጃ ለመመዘንና ፍሬ ነገርን ወደ ማረጋገጥ የሚገባበት የሕግ አግባብ የለም፡፡

ክርክር ያስነሱ አክሲዮኖች ወደ አመልካቾች በሽያጭ የተላለፉት በስር ፍ/ቤት የዕግድ ትዕዛዝ ከተሰጠበት መጋቢት 24 ቀን 2005 ዓ.ም በፊት ቢሆንም በአክሲዮኖች መዝገብ አለመመዝገቡ በስር ፍ/ቤቶች በፍሬ ነገር ደረጃ ከተረጋገጠዉ አንጻር ሲታይ በንግድ ሕግ ቁጥር 522 እና 523(3) መሠረት የአክሲዮን ሽያጩ በተጠሪ ላይ መቃወሚያ ሆኖ ሊቀርብ አይችልም፡፡ ስለሆነም የስር ፍ/ቤት ምንም እንኳ የአክሲዮን ሽያጩ የተከናወነዉም ሆነ የማህበሩ አባላት ተስማምተዉ በሰነዶች ማረጋገጫና ምዝገባ ጽ/ቤት የተመዘገበዉ ተጠሪ በአክሲዮኖቹ ላይ የዕግድ ትዕዛዝ ካሰጠበት መጋቢት 24 ቀን 2005 ዓ.ም በፊት ቢሆንም ከዚህ ቀን በፊት በአክሲዮኖች መዝገብ ላይ መመዝገቡ አለመረጋገጡን በመግለጽ አመልካቾች አክሲዮኖች በሀራጅ ተሸጠዉ ለተጠሪ እንዲከፈሉ የስር ፍ/ቤት የሰጠዉ የአፈጻጸም ትዕዛዝ እንዲነሳ ያቀረቡትን መቃወሚያ ዉድቅ በማድረግ መወሰኑ የሚነቀፍ አይደለም፡፡

የአመልካቾች አቤቱታ ለሰበር ያስቀርባል ሲባል በተያዙ ሌሎች ጭብጦች ላይ ምላሽ መስጠቱ አስፈላጊ ሆኖ ባለመገኘቱ ታልፏል፡፡

ሲጠቃለል የስር ፍ/ቤት የፍርድ ባለዕዳዎች የነበሩ የዶዶላ ኢንተርናሽናል ትሬዲንግ ኃ/የተ/የግ/ማህበር አክሲዮኖች በስር ፍ/ቤት በተሰጠ ዕግድ ትዕዛዝ ለ3ኛ ወገን እንዳይተላለፉ ከመታገዱ በፊት አክሲዮኖቹ ለአመልካቾች በሽያጭ ስለመተላለፋቸዉ በንግድ ሚኒስቴር የአክሲዮን መዝገብ ላይ ስለመመዝገቡ አልተረጋገጠም በማለት የአመልካቾችን መቃወሚያ ዉድቅ ማድረጉ የንግድ ሕግ ቁጥር 522 እና 523(3) ድንጋጌዎችንና እነዚህን ድንጋጌዎችን አስመልክቶ ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁ 103472 በተመሳሳይ አክሲዮኖች በሽያጭ መተላለፍ ላይ የሰጠዉን አስገዳጅ ትርጉም ያገናዘበ በመሆኑ

ዉሳኔዉ መሰረታዊ የህግ ስህተት ተፈጽሞበታል ለማለት አልተቻለም፡፡ በመሆኑም የሚከተለዉ ዉሳኔ ተሰጥቷል፡፡

**ዉ ሳ ኔ**

1. በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 142286 ጥቅምት 01 ቀን 2010 ዓ.ም ተሰጥቶ፤ በፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት መ/ቁ 149467 ታሕሳስ 10 ቀን 2010 ዓ.ም በተሰጠ ትዕዛዝ የጸናዉ ዉሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 348(1) መሠረት ጸንቷል፡፡

2. የሰበር ክርክሩ ያስከተለዉን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸዉን ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ዉሳኔ ያገኘ ስለሆነ ተዘግቷል፡፡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ብ/ግ

የሰበር መ/ቁ/188419

መስከረም 25 ቀን 2012 ዓ.ም

ዳኞች፡ብርሃኑ አመነው

ተሾመ ሽፈራው

ሀብታሙ እርቅይሁን

ብርሃኑ መንግስቱ

ነፃነት ተገኝ

አመልካች፡- አባይ ባንክ አ.ማ

ተጠሪ፡- አቶ ማርቆስ ጋትሮ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍርድ**

በዚህ መዝገብ የቀረበዉ ጉዳይ በሃዋላ የተላከ ገንዘብ ባንኩ ለማይገባ ሰዉ ከፍሏል በሚል ባንኩ ሃላፊ መደረጉን የሚመለከት ነዉ፡፡ክርክሩ የተጀመረው በደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/መ የወላይታ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ሲሆን የአሁኑ ተጠሪ ከሳሽ ፤የአሁኑ አመልካች ተከሳሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡መዝገቡ እንደሚያሳየዉ የተጠሪ የክስ ምክንያት እ.ኤ.አ በ10/12/2018 ወይም እ.ኤ.አ በ01/04/2011 ዓ.ም ከሊባኖስ ሀገር እህቱ በአሰሪዋ በአቶ ኤልያስ ኢልሀበር አማካይነት በዌስተርን ዩኒየን ገንዘብ መላኪያ አማካኝነት 675 የአሜሪካን ዶላር ወይም በወቅቱ ምንዛሪ ብር 18,839 የላከችለት ገንዘብ አመልካች ለማይገባው ሰው ስለከፈለ ገንዘቡ ለእኔ የተላከ ስለመሆኑ ከኢትዮ ቴሌኮም ማረጋገጫ የተቀበልኩ በመሆኑ በችልተኝነት ለሌላ ሰው የከፈለውን ገንዘብ ከወለድና ወጪ ጋር እንዲከፍለኝ ይወሰንልኝ የሚል ሲሆን አመልካች በበኩሉ የሰጠው መልስ ተጠሪ የሚጠበቅባቸውን ህጋዊነትን በማረጋገጥ የደረሳቸውን ግላዊ ሚስጥር ቁጥር ኮድ ይዘው በማቅረባቸው ባንኩ ባለው አሰራር ክፍያውን ለሚገባው ሰው በ02/04/2011ዓ.ም በአዲስ አበባ ከተማ ገላን ኮንዶሚኒየም ቅርንጫፍ ለተጠሪ ከፍሏል፣ስለዚህ ከውጭ ሀገር ገንዘብ ሲላክ ለተቀባይ ግለሰብ የሚደርሰው ሚስጥር ቁጥርና የሚጠይቅ ልዩ ኮድ ያለ ሲሆን በዚሁ መሰረት ክፍያ የተፈፀመ በመሆኑ ክሱ ተቀባይነት የለውም በማለት መልስ ሰጥቷል፡፡

ክሱን በመጀመሪያ የተመለከተዉ የወላይታ ሶዶ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ጉዳዩን መርምሮ አመልካች ገንዘቡን አድራሻዉና ማንነቱ ላልታወቀ ሰው ያለአግባብ የከፈለ መሆኑን በማስረጃ ስለተረጋገጠ አመልካች

ለተጠሪ የተላከለትን ገንዘብ የመክፈል ሃላፊነት አለበት በማለት ክስ የቀረበበትን ገንዘብ ከህጋዊ ወለድ ጋር እንዲከፍል በማለት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ለክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ አቅርቦ ፍ/ቤቱ የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኂላ የስር ፍ/ቤት ውሳኔ ተገቢ ነዉ በማለት አፅንቷል፡፡

አመልካች በዚህ ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት ተፈፅሟል በማለት ያቀረበው ቅሬታ ይዘት ባጭሩ በኢትዮጵያ ውስጥ ያሉ ባንኮች በየትኛውም ግለሰብ ስም በዌስተርን ዩኒየን አማካኝነት ገንዘብ የተላከለት ሰው የመረጠው ባንክ በአካል ቀርቦ ክፍያ እስኪጠይቅበት ድረስ በግለሰቡ ስም ገንዘብ ስለመላኩ እና ስለተላከለት ገንዘብ መጠን ሊያውቅ የሚችልበት ምንም አይነት መንገድ የለም፡፡በዚሁ መሰረት ባንኮች ክፍያ የሚፈፅሙት ገንዘቡ በስሙ የተላከለት ሰው የገንዘብ መቀበያ የሚስጥር ቁጥር እና ማንነቱን የሚያሳይ መታወቂያ ይዞ ለቀረበ ሰው ነው፡፡ይህ የሚሆነው ገንዘብ የተላከለት ሰው ወይም ገንዘብ የላከው ሰው የሚስጥር ቁጥር ለሌላ ሶስተኛ ሰው አሳልፎ ይሰጣሉ ተብሎ ስለማይገመት እና አሳልፎ ከሰጡም መቆጣጠሪያ ዘዴ ስለማይኖር ነው፡፡ገንዘቡ ከተላከለት ሰው ጋር ትክክለኛ የሚስጥር ቁጥር ለባንኩ በማቅረብ ለተፈፀመ ክፍያ ባንኩ ያለአግባብ ለማይመለከተው ሰው ክፍያ ፈፅሟል የሚያስብል አይደለም፡፡ተጠሪ ማንነታቸውን የሚያሳይ የቀበሌ መታወቂያ እና የሚስጥር ቁጥር ይዘው በመቅረባቸው አመልካች የተላከለት ገንዘብ ክፍያ ፈፅሟል፣ከተጠሪ ውጪ የሚስጥር ቁጥሩ ሊያውቅ የሚችል ሌላ ሰው የሌለ በመሆኑ አመልካች ክፍያውን የፈፀመው የባንክ አሰራር ተከትሎ ስለሆነ ክፍያ የተፈፀመው ላልተገባ ሰው ነው ተብሎ የተሰጠዉ ውሳኔ ስህተት በመሆኑ ተሽሮ አመልካች ገንዘቡን ለመክፈል ሃላፊነት የለበትም በማለት እንዲወሰን ጠይቋል፡፡

የአመልካች አቤቱታ በሰበር አጣሪ ችሎት ተመርምሮ በዌስተርን ዩኒየን አማካኝነት ገንዘብ የተላከለት ሰው በአካል ቀርቦ ክፍያ እስኪጠይቅ ድረስ በግለሰቡ ስም ገንዘብ ስለመላኩና ስለተላከው ገንዘብ መጠን ሊታወቅ የሚችልበት መንገድ እንደሌለ፣ገንዘብ በስሙ የተላከለት ሰው የገንዘብ መቀበያ የሚስጥር ቁጥር እና ማንነቱን የሚያሳይ መታወቂያ ይዞ ቀርቦ መክፈሉ በተረጋገጠበት ሁኔታ ክፍያው የተፈፀመው ለሌላ 3ኛ ወገን ነው ተብሎ አመልካች በድጋሚ ይክፈል የመባሉን አግባብነት ከባንክ አሰራር ሂደት አንፃር ለማጣራት ጉዳዩ ለሰበር ሰሚ ችሎት ያስቀርባል ተብሎ ተጠሪ መልስ እንዲሰጥበት ታዟል፡፡

በተጠሪ በኩል የቀረበው መልስ ባጭሩ በስር ፍ/ቤት ጉዳዩን ለማጣራት የሰውና የሰነድ ማስረጃ በማቅረብ አመልካች ገንዘቡን ከፍሎለታል ለተባለው ግለሰብ በትክክል የወላይታ ዞን ዳሞት ፑላሣ ወረዳ የሴራ ቀበሌ ነዋሪ መሆኑ አለመሆኑን ለማጣራት በወቅቱ ያቀረበው መታወቂያ ወረቀት ላይ የፈረሙትና የታተመው ማህተም ህጋዊ መሆን አለመሆን ለማጣራት የቀበሌው አስተዳደርና የቀበሌዉ ስራ አስኪያጅ በሰጡት ምስክርነት ቃላቸው ግለሰቡ የሴራ ቀበሌ ነዋሪ አለመሆኑ ተገቢ ማጣራት በማድረግ የተሰጠ ውሳኔ በመሆኑ ስህተት አልተፈፀመም፡፡ገንዘቡ ለእኔ እንደተላከ በተጠሪ ስልክ

የተላከውን መልዕክት ከኢትዮ ቴሌኮም ወደ ወረቀት ተቀይሮ በመጣ ማስረጃ ተረጋግጧል፣የሚስጥር ቁጥር በተመለከተ ቀደም ብሎ የሚስጥር ቁጥሩ ለባንኩ ስለሚደርስና ተቋሙ ከፍቶ የማየት እድል ከፍተኛ ስለሆነ ገንዘቡን እንደፈለገ እንዲያደርግ የሚከለክል የለም፡፡ የሚስጥር ቁጥር ይዞ የሚመጣ ሰው ማንነት በሚገባ የማረጋገጥ ሃላፊነት የአመልካች ሆኖ እያለ የክፍያ ሂደት ላይ በተገቢዉ ሳያጣራ መረጃዎችን በአግባቡ መፈተሽ ሲገባ ለእኔ የተላከውን ገንዘብ ባልታወቀ ሁኔታ ለሌላ ሰው ስለከፈለ የስር ፍ/ቤት ውሳኔ የህግ ስህተት የለውም ተብሎ እንዲፀና በማለት ተከራክረዋል፡፡አመልካች አቤቱታውን የሚያጠናክር የመልስ መልስ አቅርበው ከመዝገቡ ጋር ተያይዘዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ እና የግራቀኙ ክርክር አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተመለከትነው ሲሆን ጉዳዩ ለሰበር ያስቀርባል ከተባለበት ጭብጥ አንጻር የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መርምረናል፡፡መዝገቡን መርምረን እንደተገነዘብነዉ ለክሱ ምክንያት የሆነዉ ገንዘብ በአመልካች በኩል ለተጠሪ እንዲከፈል በሃዋላ የተላከ ስለመሆኑ አላከራከረም፡፡የሥር ፍርድ ቤት ገንዘቡ የተከፈለለት ሰዉ ይዞ የቀረበዉ መታወቂያ ከተባለዉ ቀበሌ አስተዳደር የተሰጠ አለመሆኑ ተረጋግጧል በሚል ምክንያት ገንዘቡ ለተገቢዉ ሰዉ አልተከፈለም የሚል ድምዳሜ ላይ መድረሱን የዉሳኔዉ ይዘት ያሣያል፡፡አመልካችም አጥብቆ የሚከራከረዉ ክፍያ የተፈጸመዉ በባንኩ አሰራር መሰረት በተገቢዉ መረጃ ማጣራት ተደርጎ ስለሆነ በሃላፊነት የሚያስጠይቅ ጥፋት የለም በማለት ነዉ፡፡

በመሰረቱ የደንበኞችን ገንዘብ በሀገር ዉስጥም ሆነ ከሀገር ዉጪ ማስተላላፍ ስራ ከባንክ ስራዎች አንዱ ስለመሆኑ አዋጅ ቁጥር 592/2000 አንቀጽ 2/2/መ/ ላይ ተመልክቷል፡፡ባንክ በአደራ የተቀበለውን የደንበኛውን ገንዘብ የመጠበቅ ህጋዊ ግዴታ ያለበት ስለመሆኑ በንግድ ህጉ ከቁጥር 896 እስከ 902 ከተደነገጉት ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ የምንገነዘበው ጉዳይ ነው፡፡የእነዚህ ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ ሲታይ ባንኩና ደንበኛው የአደራ ስምምነት ውል መግባታቸውን በመግለጽ በውሉ ተቃራኒ ስምምነት ከሌለ በቀር ባንኩ በአደራ የተቀበለውን ገንዘብ ለታዘዘለት ሰዉ የማድረስ ወይም ለባለአደራዉ የመመለስ ግዴታ ያለበት መሆኑን ያመለክታል፡፡ባንኩ በሕጉ የተጣለበትን ግዴታ ማለትም የደንበኛውን ገንዘብ የባንክ ስራ የሚጠይቀውን አሰራርና ስርዓት በመከተል መጠበቅና ሲጠይቅም ገንዘቡን መክፈል ነው፡፡ባንክ ተገቢውን ጥንቃቄ ሳያደርግ ቀርቶ በደንበኛው ገንዘብ ላይ ለሚደርስ ጉዳት ተጠያቂነት የሚኖርበት መሆኑንም ከላይ ከተጠቀሱት ድንጋጌዎች መሰረታዊ ይዘትና ዓላማ የምንረዳው ጉዳይ ነው፡፡ባንኩ የደንበኛውን መብትና ጥቅም ማስከበር የሚገባው ተገቢውን ጥንቃቄ ወይም የተለመደ አሠራር በመከተል እንዳለበት በሌላ በኩል ባልተገባ መንገድ በደንበኛው ገንዘብ ላይ ጉዳት እንዳይደርስ መከላከል ጭምር በህግ ግዴታ የተጣለበት ስለመሆኑ እና እዉነታዎችን በማረጋገጥ ረገድ ተገቢዉን ትጋት ማድረግ ያለበት መሆኑን ከአዋጅ ቁጥር 592/2000 አንቀፅ 53 ድንጋጌ ይዘት የምንገነዘበዉ ጉዳይ ነው፡፡

በዚህ መዝገብ በተያዘዉ ጉዳይ አመልካች ክፍያ የፈጸመዉ አስፈላጊዉን መረጃ ከገንዘብ ጠያቂዉ በማጣራት ስለመሆኑ በተለይም የላኪዉን ማንነት፣የተላከዉን ገንዘብ መጠን እና የሚስጥር ቁጥር ገንዘቡን ለመቀበል ከቀረበዉም ሰዉ በማረጋገጥ ክፍያ የፈጸመ ስለመሆኑ አላከራከረም፡፡የስር ፍርድ ቤትም እነዚህ ፍሬ ነገሮች ከማጣራት አንጻር ባንኩ ስህተት ፈጽሟል አላለም፡፡ነገር ግን ፍርድ ቤቱ አመልካችን ሃላፊ ያደረገዉ በዋናነት ተከፋዩ ወይም ገንዘቡን ተቀብሏል የተባለዉ ሰዉ ተጠሪ ሳይሆን በተጠሪ ስም ሀሰተኛ የቀበሌ መታወቂያ ይዞ የቀረበ ሌላ ሰዉ ነዉ በማለት ነዉ፡፡ባንኩ ክፍያ የፈጸመዉ በባንኩ ያለዉ መረጃ ገንዘቡን ለመቀበል ከቀረበዉ ሰዉ መረጃ በማጣራት ስለመሆኑ እና የተላከለት ሰዉ ማንነት መታወቂያዉን በመመልከት በማገናዘብ አረጋግጦ ስለመሆኑ ይህም በባንኩ የተለመደዉ አሰራር መሰረት የተፈጸመ መሆኑን በመግለጽ ሃላፊነት እንደሌለበት አጥብቆ ተከራክሯል፡፡ በመሰረቱ ባንኩ የተከፋዩን ማንነት ለማረጋገጥ መታወቂያዉ የቀበሌዉ ማህተም የተደረገበት እና የሚመለከተዉ ሃላፊ ስምና ፊርማ ያለበት መሆኑን በምልከታ ከማረጋገጥ በስተቀር ማህተሙ የቀበሌዉ ነዉ ወይስ አይደለም፤ፊርማዉ የሚመለከተዉ ሃላፊ ነዉ ወይስ አይደለም በሚል ተጨማሪ ምርመራ እንዲያደረግ የሚያስገድድ የህግ ምክንያት የለም፡፡ የባንክ የስራ ባህርይም ይህንን የሚፈቅድ አለመሆኑ ይታወቃል፡፡ባንኩ ክፍያ ሲፈጽም በዋናነት እንዲያረጋግጥ የሚጠበቀዉ ተከፋዩ ሰዉ ብቻ ያዉቀዋል ተብሎ የሚገመተዉን ፍሬነገር ማለትም ገንዘቡን የላከዉ ሰዉ ማንነት፤የተላከዉ ገንዘብ መጠን፤የሚስጥር ቁጥር እና የተላከለት ሰዉ ስም ነዉ፡፡እነዚህ ፍሬ ነገሮች በባንኩ ካለዉ መረጃ ጋር በማዛመድ ተመሳሳይ መሆናቸዉ ከተረጋገጠ መረጃ ይዞ የቀረበዉ ሰዉ ትክክለኛ ተከፋይ ነዉ ተብሎ እንደሚታሰብ እና ገንዘብ ተቀባዩን ማንነት የሚያሳይ መታወቂያ አቅርቦ እንዲከፈለዉ ከታዘዘለት ሰዉ ስም ጋር አንድ መሆኑ ከታወቀ ባንኩ ተገቢዉን ጥንቃቄ ሳያደርግ ቀርቷል ተብሎ ተጠያቂ ሊሆን የሚችልበት ምክንያት የለም፡፡በዚህ ረገድ ይህ ሰበር ችሎት በሰበር መ/ቁ/ 41535 ላይ የሰጠዉ ዉሳኔ እንደሚያሳዉ ባንኩ የተለመደዉን አሰራርና ተገቢዉን ጥንቃቄ አድርጎ ክፍያ ከፈጸመ የሰነዶቹን ህጋዊነት አላረጋገጠም ተብሎ በድጋሚ እንዲከፍል ሃላፊነት የለበትም ሲል ዉሳኔ መስጠቱን ልብ ይለዋል፡፡

ስለሆነም ተከፋዩ ይዞ የቀረበዉ መታወቂያ ላይ ያለዉ ፊርማ እና ማህተም የቀበሌዉ አይደለም የሚል በሰዉ ምስክር ከመገለጹ ዉጪ ሌሎቹ መረጃዎች ማለትም የተላከዉ ገንዘብ መጠን፣የላኪዉ ስም እና የሚስጥር ቁጥሩ እንዲሁም ተከፋይ ሰዉ ስም ስህተት ነዉ አልተባለም፡፡እነዚህ አስፈላጊና ወሳኝ መረጃዎች ከተከፋዩ ሌላ ሰዉ ሊያዉቅ የሚችልበት ሁኔታ ስለመኖሩ ባልተረጋገጠበት ሁኔታ ባንኩ ለማይገባዉ ሰዉ ክፍያ ፈጽሟል ሊባል አይችልም፡፡በዚህም ሁኔታ ለማይገባ ሰዉ ተከፍሎ ቢሆን እንኳን የተታለለዉ መረጃዉን ያለአግባብ ያባከነዉ ተጠሪ ነዉ ከሚባል በስተቀር ባንኩ ነዉ ሊባል አይችልም፡፡

ሲጠቃለል አመልካች ክፍያ የፈጸመዉ በባንኩ የተያዙት መረጃዎች እና ተከፋዩ ሰዉ የሰጠዉ መረጃ ተዛማጅና ትክክል መሆናቸዉ በተለመደዉ አሰራር መሰረት በማረጋገጥ እስከሆነ ድረስ ክፍያዉን የተቀበለዉ በተጠሪ ስም ሀሰተኛ የቀበሌ መታወቂያ ይዞ የቀረበ ሌላ ሰዉ ነዉ በሚል ምክንያት ባንኩ ድጋሚ ገንዘቡን ለተጠሪ እንዲከፍል በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጠዉ ዉሳኔ ስለባንክ ክፍያ አፈጻጸም የተለመደዉን አሰራር እና የተረጋገጡ መሰረታዊ ፍሬ ነገር ጉዳዮችን እንዲሁም ህጉን ያገናዘበ ባለመሆኑ መሠረታዊ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ ብለናል፡፡በዚሁ አግባብ ተከታዩን ዉሳኔ ሰጥተናል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. የወላይታ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ/ 43492 ላይ በ21/02/1012ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ እና ይህንኑ በማጽናት የደ/ብ/ብ/ህ/ክልል ጠ/ፍ/ቤት በመ/ቁ/32198 ላይ 17/04/2012ዓ.ም የሰጠው ዉሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህግ ቁ/ 348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡
2. አመልካች ለክሱ ምክንያት የሆነውን ገንዘብ ለተጠሪ እንዲከፍል የሚገደድበት የህግ ምክንያት የለም ብለናል፡፡
3. ግራ ቀኝ ወገኖች ወጪና ኪሣራ ይቻቻሉ፡፡

**መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ይመለስ፡፡**

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ሠ/ኃ

# ውል

የሰበር መዝገብ ቁጥር 161153

ሚያዝያ 28 ቀን 2011 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ተኽሊት ይመሰል

ተፈሪ ገብሩ (ዶ/ር)

ቀነዓ ቂጣታ

ተሾመ ሽፈራው

ፀሐይ መንክር

አመልካች፡-ወጋገን ባንክ አ.ማ. ነ/ፈጅ ቢኒያም ትዕግስቴ ቀረቡ፡፡

ተጠሪ፡- የኢትዮጵያ የንግድ እና የዘርፍ ማህበራት ም/ቤት ነ/ፈጅ ሠላም ሠጠኝ አደራ ቀረቡ፡፡

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍርድ

ለዚህ የሰበር አቤቱታው ምክንያት የሆነው ጉዳይ የተጀመረው በግልግል ዳኞች ጉባዔ ሲሆን አመልካች ከሣሽ ተጠሪ ደግሞ ተከሣሽ እና የተከሣሽ ከሣሽ በመሆን የተከራከሩ እና ክርክሩም መሠረት ያደረገው የቤት ኪራይን መነሻ በማድረግ ነው፡፡

አመልካች አቅርቦት የነበረው ክስ የሚያሳየው ከተጠሪ ላይ ለባንክ አገልግሎት የሚውል ቤት በወር በብር 33,890.05 / ሰላሳ ሶስት ሺ ስምንት መቶ ዘጠና ብር ከዜሮ አምስት ሣንቲም / ተከራይቶ የ6 ወር ክፍያ በአንድ ጊዜ መክፈሉን እና ቤቱን ለሥራ አመቺ ለማድረግ ሲሞክር የክ/ከተማ መሬት ማኔጅመንት የግንባታ ፈቃድ የላችሁም በሚል ሥራውን በ16/04/2008 ዓ.ም. አስቁሟል፡፡

ተጠሪ/ተከሣሽ/ የግንባታ ፈቃድ እንዲጠይቅና እንዲያስፈቅድ ብንጠይቀውም ፈቃደኛ ባለመሆኑ የውል መሠረታዊ አላማ እንዳይፈፀም ያደረገ በመሆኑ የግንባታ ፈቃድ እንደማያገኝ ቀድሞ ቢያውቅ ኖሮ የማይዋዋል በመሆኑ፣ የተከራየውንም ቤት እንዳልተጠቀምኩበት እያወቀም ውዝፍ ኪራይ እንደሚጠይቅ ማስጠንቀቂያ ሰጥቶኝ ውሉን አቋርጧል፡፡

በመሆኑም ቅድሚያ ክፍያ የከፈልኩትን ብር 203,343.00 /ሁለት መቶ ሶስት ሺ ሶስት መቶ አርባ ሶስት ብር/ እና ቤቱን ለማስተካከል ያወጣሁትን ወጪ ብር 37,956.02/ ሰላሳ ሰባት ሺ ዘጠኝ መቶ አምሳ ስድስት ብር ከዜሮ ሁለት ሣንቲም/ በድምሩ ብር 241,299.02 /ሁለት መቶ አርባ አንድ ሺ ሁለት መቶ ዘጠና ዘጠኝ ብር ከዜሮ ሁለት ሣንቲም/ ማስጠንቀቂያ ከሰጠሁበት ቀን አንስቶ ከሚታሰብ ህጋዊ ወለድ ጋር እንዲከፍል ይወሰንልኝ ሲል ዳኝነት ጠይቋል፡፡

ተከሣሽ በሰጠው መልስ ቤቱን ማከራየቱ እውነት ነው ከሣሽ የተከራየውን ቤት ተረክቧል ለአገልግሎት የማዋል የራሱ ኃላፊነት ነው፡፡ የተከራየውን ቤት ከጥቅምት 1 ቀን 2008 ዓ.ም.ጀምሮ ለአገልግሎት ማዋል ይገደዳል፡፡ ለክፍሎች ማሻሻያ ያወጣውን ተከሣሽ አይሸፍንም፡፡ በውሉ ላይ ስለማሻሻያ ፍቃድ ስለማስገኘት ቀድሞ አልተደራደረም፡፡ በመሆኑም ለ10 ወራት የተከራየውን ቤት ይዞ የኪራይ ገንዘብ ይመልስልኝ ያለው ተቀባይነት የለውም ፡፡ ቤቱን ሲረከብ ለባንክ አገልግሎት እንደሚያውል ስለማመኑ የውሉ አንቀጽ 3 ያሳያል፣ ለከሣሽ እድሳት እንዲፈቀድ የበኩሌን ጥረት አድርጌያለሁ በመሆኑም ክሱ ውድቅ ሊሆን ይገባል በማለት ጠይቋል፡፡

ተከሣሽ በበኩሉ ባቀረበው የተከሣሽ ከሣሽነት ክስ የተከራየውን ቤት ጣራ እና የአንድ ጐን ግድግዳ ወደ ነበረበት ሊመልስ ስለሚገባ ብር 60,530.00 ወደ ነበረበት ለመመለስ ወጪ ያደረኩ በመሆኑ፣ የጥገናው ሥራ ተጠናቆ ወደ ሥራ ሊገባ የቻለው ጥቅምት 16/2009 ዓ.ም. በመሆኑ ቤቱ በነበረበት ተረክቤ ቢሆን ከሣሽ እንደለቀቀ ወዲያው አከራይቼ አገኝ የነበረ ቢሆንም እስከ ጥቅምት 2009 ሊቆይ የቻለው በከሣሽ ተከሣሹ ባፈረሰው ክፍል ምክንያት በመሆኑ ከሐምሌ 27 ቀን 2008 እስከ ጥቅምት 16 ቀን 2009 ዓ.ም. ድረስ ኪራይ ሊከፍል ስለሚገባ፣ ያልከፈለውን የ4 ወር ኪራይ ብር 135,562.00፣ የፈረሰው ቤት ወደ ነበረበት እስኪመለስ እና እስኪከራይ ያጣሁት ኪራይ ብር 84,726.25፣ ቤቱን ወደነበረበት ለመመለስ ያወጣሁት 60,530.00፣ በአጠቃላይ 280,818.25/ ሁለት መቶ ሰማንያ ሺ ስምንት መቶ አስራ ስምንት ብር ከሃያ አምስት ሣንቲም/ ከግልግል ጉባኤው የዳኝነት ወጪ ጋር ይክፈለኝ ሲል ዳኝነት ጠይቋል፡፡

የከሣሽ ተከሣሽ መልስ ያቀረበ ሲሆን ቤቱን ለባንክ አገልግሎት በሚውል መልኩ በራሱ ወጪ ተገቢውን እድሳት ለማድረግ ግዴታ ገብቷል፡፡ ይህንንም አከራይ የሆነው የተከሣሽ ከሣሽ በውሉ እውቅና በመስጠት በጉዳዩ ላይ በህግ የሚጣሉበትን ሀላፊነቶች ለመወጣት ግዴታ ገብቷል፡፡ ይህ የውል ግዴታ በአግባቡ እንዲፈፀም የተከሣሽ ከሣሽ እንደ ንብረቱ ባለቤት የሚመለከተው የመንግሥት አካል ተገቢውን የግንባታ ፍቃድ የማውጣት በህግ የተጣለበት ግዴታ ያለበት ቢሆንም ግዴታውን አልተወጣም፡፡

ከዚህም የተነሳ በውሉ አፈፃፀም ላይ አይነተኛ እና መሠረታዊ ውል መጣስ ከተከሣሽ ከሣሽ በኩል የተፈፀመ በመሆኑ የኪራይ ውል ፈርሶ ግራ ቀኞችን ወደነበርንበት ሁኔታ መመለስ አለብን፣ ያልተከፈለ

የኪራይ ክፍያ ይከፈለኝ ጥያቄ አግባብነት የለውም፣ የተከሣሽ ከሣሽ የግንባታ ፈቃድ ከሚመለከተው የመንግሥት አካል እንዲያወጣ በማሳሰብ ቤቱን የማስተካከል ሥራው ከቆመበት ከ16/4/2008 ዓ.ም. ጀምሮ ያለው የቤት ኪራይ ክፍያ የከሣሽ ተከሣሽ ያልተጠቀመበት መሆኑን እንዲያውቅ በጽሁፍ ያሳወቀ በመሆኑ ሲታይ የተከሣሽ ከሣሽ ጥያቄ አግባብነት የለውም፣ ወደ ነበርንበት የምንመለስ ከሆነ ደግሞ ለ3ኛ ወገን ቤቱ ባለመከራየቱ ሊከፈል ይገባል በማለት የቀረበው ተገቢ አለመሆኑን፣ ቤቱ ወደ ነበረበት ለመመለስ ወጣ የተባለው ብር 60,530.00 ማን እንደገመተው የማይታወቅ መሆኑ ለቀረበው የተከሣሽ ተከሣሽነት ክስ ከሣሽ ተጠያቂ ሊሆን አይገባም  በማለት መልስ አቅርቧል፡፡

ጉባዔው የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ 4 ጭብጦችን ይዞ ጉዳዩን የመረመረ ሲሆን በዚሁ መሠረት፡-

1. ተከራይ የተከራየውን ቤት ለባንክ ሥራ ሳይጠቀምበት የቀረው በማን ጥፋት ነው? የሚለውንን ጭብጥ አስመልክቶ ፡- በውሉ ላይ ስለ ግንባታ ፈቃድ ማስገኘት አለማስገኘት የተቀመጠ ነገር የሌለ መሆኑን፣ የተከራየው ቤት የግንባታ ፈቃድ ያስፈልገው እንደነበረ የሚያውቅ ሆኖ ነገር ግን ተከሣሽ ፈቃዱን ከሚመለከተው አካል ተከሣሽ ያስገኝልኛል የሚል እምነት የነበረው በመሆኑ መሆኑን በቃል ክርክር ከሣሽ ማስረዳቱን፣ ሆኖም በውሉ አንቀጽ 9/2 በተከሣሽ ላይ አንፃራዊ ግዴታን የሚጥል መሆኑን በልማድም ፣ፍትሕ ቅን ልቦና እና የውሉ አይነት የሚያስከትሉትን ነገሮች ጭምር መሆኑን እንዲሁም በህንፃ አዋጅ ቁጥር 624/2001 አንቀጽ 4/4 መሠረት የግንባታ ፈቃድ የሚጠይቀው ባለንብረቱ ከመሆኑ አንፃር በውሉ ባይገለፅም በፍ/ብ/ሕ/ቁ/ 1713 መሠረት በልማድና በአሰራር የግንባታ ፈቃድ የመጠየቅ ግዴታ የአከራዩ/የተከሣሽ በመሆኑ የግንባታ ፈቃድ የመጠየቅ ግዴታ አከራይ የሚኖርበት መሆኑን፣ ነገር ግን የግዴታው ባህሪን አስመልክቶ የግንባታ ፈቃዱን ለማስገኘት ተገቢ ትጋት ማድረግ ወይስ ፍቃዱን ማግኘት ነው የሚለውን ስንመለከት አከራይ ፍቃድን ለማግኘት ትጋት ማድረግን እንጂ ፈቃድ መስጠቱ በ3ኛ ወገን እጅ ያለ ነገር በመሆኑ ፈቃድ የማስገኘት ግዴታ የሌለበት በመሆኑ ከሣሽ ከተከራየሁ በኋላ ሣልጠቀም የቀረሁት በተከሣሽ ጥፋት ነው በማለት ያቀረበው ጥያቄ ተቀባይነት የለውም በሚል ወስኗል፡፡
2. ተከራይ ቤቱን ከተረከበ በኋላ ለተከራየበት ዓላማ ሳይጠቀም መቅረቱ ውሉ ጸንቶ እስከቆየበት ጊዜ ድረስ ያለውን ኪራይ ላለመክፈል በቂ ምክንያት ሊሆን ይችላል ወይስ አይችልም ? በሚል ለተያዘው ጭብጥ ውሉ በግራ ቀኙ መፈረሙን አለመካካዳቸውን፣ ከሣሽ ውሉ በሁኔታ ላይ የተመሠረተ ነው ቢልም በሁኔታ ላይ ግን የተመሠረተ ውል አለመሆኑን፣ ለዚህም የውሉ አንቀጽ 4.1 ላይ የተገለፀው ኃይለ ቃል የሚያሳይ መሆኑን፣ ከሣሽም ቤቱን ተረክቦ ይዞ እንደነበረ አለመካዱን፣ ቤቱን በመያዜ ብቻ ሳይሆን አድሼ ሥራ ላይ ሳውል ነው በማለት ከሣሽ ያነሳውን በተመለከተ ውሉን ሲዋዋል ገና ቤቱን ማሻሻል እንዳለበት የሚያውቅ መሆኑን፣

እድሳት የጀመረው ተከሣሽን ፈቃድ እንዲያወጣለት ሳይጠይቅ መሆኑ፣ የግንባታ ፈቃድ አለመገኘት የሚያስከትለውን ኃላፊነት አውቆ አመዛዝኖ እና ተቀብሎ ወደ ውል የገባ በመሆኑ የግንባታ ፈቃድ እንደማያገኝ ካወቀበት ጊዜ ጀምሮ ከሣሽ ውሉን አቋርጦ ቤቱን ለአከራዩ መልሶ የሚደርስበትን ኪሣራ መቀነስ ሲገባው አከራይ ውሉን እስኪያቋርጥ ድረስ በዝምታ መቀመጡ ተገቢ እንዳልሆነ ገልጾ አስቀድሞ ተቀብሎ የነበረውን የኪራይ ገንዘብ ብር 203,343.00 ተከሣሽ ሊመልስ አይገባም፡፡ እንዲሁም ውዝፍ የቤት ኪራይ ብር 135,562.00 ከሣሽ የመክፈል ኃላፊነት አለበት ሲል ወስኗል፡፡

3. የቤት ዕድሳትን አስመልክቶ ከሣሽ ያፈረሰውን ወደ ነበረበት የመመለስ ኃላፊነት ያለበት መሆን ያለመሆኑን አስመልክቶ ከውላቸው አንቀጽ 9/2/ አንፃር መርምሮ በአከራይ በኩል ያልተፈፀመ የውል ወይም የህግ ግዴታ የሌለ በመሆኑ የማሻሻያ ሥራው የተቋረጠው በ3ኛ ወገን ምክንያት መሆኑን፣ አከራይም የግንባታ ፈቃድ ለማግኘት የተቻለውን ጥረት ያደረገ በመሆኑ ለማሻሻያ ያወጣሁትን ብር 37,956.00 ተከሣሽ ሊተካልኝ ይገባል በማለት ያቀረበው ጥያቄ ተቀባይነት እንደሌለው፣በአንፃሩ የተከራየውን ቤት ለሥራው ለማዋል በሚል የቤቱን ጣራ፣ ወለል እና ግድግዳ ከሣሽ የማፍረስ ሥራ ጀምሮ የተቋረጠ በመሆኑ ተከራይ አከራይ ቤቱን ወደነበረበት ለመመለስ የሚያወጣውን ወጪ በገንዘብ ተተምኖ ሊካስ የሚችል በመሆኑ እናየመተካት ኃላፊነትም የከሳሽ መሆኑን ፣ በግምቱም መስማማቱን ተከራይ በደብዳቤ ስለገለፀ ብር 60,503.00 ለተከሳሽ ከሣሽ ሊከፍል ይገባል በሚል ወስኗል፡፡

4. ቤቱን ወደ ነበረበት ለመመለስ በፈጀው ጊዜ ውስጥ ሳይከራይ በመቅረቱ ተከራይ ለታጣው ገቢ ኃላፊነት አለበት የለበትም የሚለውን አስመልክቶ፡- የኪራይ ውሉ የፈረሰው በአከራይ ጥፋት ነው በማለት ተከራይ ይከራከር እንጂ ውሉ የተቋረጠው በተከራይ ጥፋት መሆኑ ድምዳሜ ላይ የተደረሰ በመሆኑ፣ እድሳት ሳይደረግለት ሊከራይ ይችላል ለማለት አዳጋች በመሆኑ ቤቱ ሳይከራይ የቀረው በአከራይ ጥፋት ነው ማለት ስለማይቻል እንዲሁም የኪራይ ውሉ የተቋረጠው ተከራይ የኪራይ ገንዘብ ለመክፈል ፈቃደኛ ባለመሆኑ በውሉ አንቀጽ 19.1 እና 3 መሠረት የተከራይ አከራይ ጥፋት በመሆኑ በፍ/ብ/ሕ/ቁ/ 2944 መሠረት አከራይ ቤቱን እንደገና ለማከራየት ለሚወስድበት ጊዜ ሊከፈል የሚገባውን የኪራይ ገንዘብ ተከራዩ እንዲከፍል የሚያስገድድ በመሆኑ የ2 ወር ተኩል ኪራይ ብር 84,726.25 ተከራይ/ከሣሽ ሊከፍል ይገባል በማለት ጉባኤው ወስኗል፡፡

በውሣኔው ቅር ተሰኝቶ አመልካች ይግባኙን ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ያቀረበ ሲሆን ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት የይግባኝ ቅሬታውን አልተቀበለውም፡፡

አመልካች በግልግል ጉባኤው ተፈጽሟል ያላቸውን የህግ ስህተቶች በመዘርዘር በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት ሐምሌ 09 ቀን 2010 ዓ.ም. የተፃፈ 4 ገጽ የሰበር አቤቱታ አቅርቧል፡፡

ይዘቱም በአጭሩ፡- ተከራይ በውል የተሰጠውን የተከራየውን ቤት አድሶ እና አስተካክሎ የመጠቀም መብት እንዲሰራበት የግንባታ ፈቃድ ያላቀረበ አከራይ መሠረታዊ የውል መጣስ የፈፀመ በመሆኑ ውሉ በፍ/ህ/ቁ/ 1884 መሠረት ፈራሽ ሆኖ ተዋዋይ ወገኖች ውሉ ከመፈፀሙ በፊት ወደ ነበሩበት ሁኔታ ሊመለሱ ሲገባ ውዝፍ ኪራይ እንድከፍል መወሰኑ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት በመሆኑ፣ አመልካች በውል ያገኘውን መብት እንዲሰራበት እና የውሉም መሠረታዊ አላማ እንዲሳካ ተጠሪ በህግ የተጣለበትን ግዴታ ባለመወጣቱ መሠረታዊ የውል መጣስ ተፈጽሞ እና አመልካች ቤቱን በማደስ እና በማስተካከል ሂደት ውስጥ ያወጣው ገንዘብ ብር 37,956.02 ለኪሳራ ተዳርጎ እያለ የስር የዳኝነት አካላት ተጠሪን ይህንን ገንዘብ ሊተካ አይገባም በማለት የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት በመሆኑ፣ በተጠሪ በኩል የተፈፀመ የውል መጣስ የለም በሚል መደምደሚያ ላይ ደርሶ የሁለት ወር ኪራይ እንድከፍል መወሰኑ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት በመሆኑ፣ተጠሪ ቤቱን ወደ ነበረበት ለመመለስ ያወጣውን ወጪ አመልካች እንዲተካለበት ያቀረበውን የተከሣሽ ከሣሽነት ክስ አስመልክቶ ተጠሪ ባቀረበው የገንዘብ መጠን ላይ የተጠቀሰውን ገንዘብ ሊያወጣ እንደሚችል ማመኑ ኃላፊነቱን ተቀበለ ማለት ባለመሆኑ የተፈፀመ የውል መጣስ በሌለበት ኃላፊ መባሌ መሠረታዊ የህግ ስህተት በመሆኑ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ ሲል ሰፊ አቤቱታ አቅርቧል፡፡

አቤቱታው ተመርምሮም አመልካች የተከራየውን ቤት ለተከራየበት አላማ ሳይጠቀምበት በመቅረቱ ውሉ ጸንቶ እስከሚቆይበት ጊዜ ተከራይ የቤት ኪራይ የመክፈል ግዴታ አለበት መባሉ የኪራይ ውሉ አፈጻጸም በሁኔታ ላይ የተመሰረተ አይደለም የሚያሰኝ መሆን ያለመሆኑን ግራ ቀኙ ከተዋዋሉት ውል አንፃር አግባብነቱን ለመመርመር ለሰበር ችሎት ይቅረብ በሚል ጭብጥ በመያዙ መዝገቡ ሊቀርብ ችሏል፡፡

በዚሁ መሠረት አቤቱታው እና ማስቀረቢያ ነጥቡ ለተጠሪ እንዲደርስ ተደርጎ መስከረም 25 ቀን 2011 ዓ.ም. የተፃፈ 5 ገጽ መልስ ተጠሪ ያቀረበ ሲሆን ይዘቱም በአጭሩ፡- በውሉ አንቀጽ 9.2 መሠረት ቤቱ በደህና ሁኔታ ላይ መሆኑን ተመልክቶ የተዋዋለ ሆኖ እያለ፣ አገልግሎት መስጠት የማይችል ጅምር ቤት እንዳስረከበው እና ይህንንም ለማጠናቀቅ የሚያስችል ሥራ የግንባታ ፈቃድ ሊወጣለት ባለመቻሉ በውሉ አለመከበር ምክንያት ተጠሪ እንደሆነ ለማስመሰል ጥረት አድርጓል፡፡ አመልካች ለተጠሪ ሳያሳውቅና ስምምነት ሳያገኝ በራሱ ተነሳሽነት እና ዕቅድ ብቻ የተከራየውን ቤት በአንድ ገጽ ያለውን ግድግዳ እና ጣሪያውን አፍርሶበደንብ አስከባሪዎች እንዲቆም ተደርጓል፣ ይህ አፍርሶ የመስራት ተግባር በውል ስምምነታችን ውስጥ ያልተገለፀ ሲሆን አመልካች ማፍረስ ሳያስፈልገው የውስጥ ሥራ ብቻ በመስራት መጠቀም ማደራጀት እየቻለ ያለተጠሪ ፈቃድ በማፍረስ ሕገወጥ እና የውል ጥሰት በመፈፀሙ የሚመለከተውን አካል የግንባታ ፈቃድ ቢጠየቅም ፈቃድ

ለመስጠት ፈቃድ በመከልከሉ ያለአግባብ ያፈረሰውን ወደ ነበረበት ለመመለስ እንጂ በውል የተቀመጠ አይደለም፡፡

አፍርሶ መስራት በተዋዋዮቹ የታሰበ ጉዳይ አለመሆኑን፣ የግንባታ ፈቃዱም ቢገኝ አመልካች ምን ዓይነት ግንባታ ለማከናወን ፈልጎ እንደነበረ ራሱ ለተጠሪ ግልጽ አለመሆኑ፣ በውሉም ላይ እድሳትን በተመለከተ የተጠሪን ፈቃድ ማግኘት ያለበት መሆኑ በቅድመ ሁኔታነት የተቀመጠው ተጠሪ በንብረቱ ላይ ሊደርስ የሚችለውን ጉዳት አስቀድሞ ለመከላከል እድል እንዲያገኝ መሆኑን፣ የተከፈለው የኪራይ ገንዘብ አመልካች ለያዘው ክፍል ሲሆን ክፍሉ በአመልካች ባይያዝ ኖሮ ለሌላ ተከራይ በማስተላለፍ ገቢ ያገኝ የነበረ መሆኑ፣ ተጠሪ በጥፋቱ ምክንያት ክሶ ውሉን አቋርጦ መሄድ ሲገባው ቤቱ እንደፈረሰ ጥሎ ሄዷል፡፡ በዚህ ሁኔታ የ4 ወር ኪራይ እንዲከፍል መወሰኑ ቤቱንም ወደ ነበረበት ለመመለስ የወጣውን ወጪ እንዲተካ መደረጉ የተፈፀመበት ስህተት ስለሌለ አቤቱታው ውድቅ ሆኖ በግልግል ዳኝነቱ የተሰጠው ውሣኔ ሊፀና ይገባል በማለት መልሱን አቅርቧል፡፡ አመልካችም የመልስ መልሱን አቅርቦ ከመዝገብ ተያይዞ የጽሁፍ ክርክሩ በዚህ ተጠናቋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ከላይ የተመለከተውን ሲመስል እኛም የቀረበውን አቤቱታ፣ መልስ እና የመልስ መልስ ከስር የግልግል ጉባዔው ውሣኔ በግራ ቀኙ ከተደረገ የውል ስምምነት እና አጠቃላይ ጉዳዩ ከሚመለከታቸው የሕግ ድንጋጌዎች ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡

እንደመረመርነውም በአመልካች እና በተጠሪ መካከል የተደረገ የቤት ኪራይ መኖሩን፣ ቤቱን አመልካች የተከራየው ለባንክ ሥራ አገልግሎት መሆኑ እና አከራይ የ6 ወር ኪራይ ቀድሞ መቀበሉ እንዲሁም ተከራይ የተከራየውን ቤት መረከቡ በግራ ቀኙ አልተካደም፡፡

በአመልካች እና በተጠሪ መካከል የቤት ኪራይ ውል ጥቅምት 1 ቀን 2008 ዓ.ም. የተፈረመ እና አከራይ የ6 ወር ኪራይ በወር 33,890.50 ተባዝቶ የተከፈለው ሲሆን አመልካች ደግሞ የተከራየውን ቤት ተረክቧል፡፡ በዚህ ውል አንቀጽ 3.1 መሠረት አመልካች ቤቱን የተከራየው ለባንክ ሥራ አገልግሎት መሆኑ ተገልጿል፡፡ አመልካች የተረከበው ቤት ለባንክ ሥራ አገልግሎት በሚሆን መልኩ በቢሮ የተከፋፈለ ሳይሆን የወለል ስፋቱ 84.2 ካሬ ሜትር መሆኑን ውሉ ያሳያል፡፡

አመልካች በውል ስምምነቱ መሠረት ቤቱን ለሥራው አመቺ ለማድረግ ተጠሪን ፈቃድ መጠየቅ የሚያስፈልገው ስለመሆኑ በውሉ አልተገለፀም፡፡ ይልቁንም አመልካች ተጠሪን ፈቃድ ለመጠየቅ የሚገደደው በተከራየው ክፍል ላይ የግንባታ ማሻሻያ የቅርጽ ወይም የይዘት ለውጥ ማድረግ ከፈለገ ስለመሆኑ በውሉ አንቀጽ 11.1 ላይ ከተመለከተው መገንዘብ ይቻላል፡፡

በዚህ መሠረት አመልካች ክፍሎችን ለሥራ አመቺ ለማድረግና ወደ ሥራ ለማስገባት ስንቀሳቀስ በአስተዳደሩ ተከልክያለሁ፣ የተከለከልኩበት ምክንያትም የግንባታ ፈቃድ የለህም በሚል ሲሆን ተጠሪ የቤቱ ባለቤት በመሆኑ የግንባታ ፈቃድ ማውጣት ሲገባው ፈቃድ ሊያስገኝልኝ አልቻለም በመሆኑም የግንባታ ፈቃድ የማያስገኝልኝ መሆኑን ባውቅ ኖሮ ቀድሞውንም ውሉን አልዋዋልም ነበር በማለት የሚከራከሩበት ሲሆን፣ተጠሪ የግንባታ ፈቃዱን ለማስገኘት የራሱን ጥረት ማድረጉን ነገር ግን የግንባታ ፈቃድ የሚሰጠው 3ኛ ወገን በመሆኑ ማስገኘት የግድ ማሰራት አለበት ሊባል የሚችል አለመሆኑን የግልግል ዳኝነት ጉባዔው አረጋግጦ ወስኗል፡፡

እንግዲህ ግራ ቀኝ ያልተካካዱበት እና በግልግል ዳኝነት ጉባዔው የተረጋገጠው ፍሬ ነገር ከፍ ሲል የተመለከተው ሲሆን፣ አመልካች የቤቱን ኪራይ እንዲከፍል በሚል በግልግል ዳኝነት ጉባዔው የተሰጠ ውሣኔ አመልካች በእርግጥም ይህን ለመክፈል ኃላፊነት ያለበት መሆኑን በማረጋገጥ ነው ወይ? የሚለው ነጥብ የዚህ ችሎት ምላሽ የሚያስፈልገው ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ከላይ እንደተገለፀው ለክርክሩ መነሻ የሆነው የኪራይ ውል ዓላማ ለኪራይ ውሉ ምክንያት የሆነው ቤት ለባንክ አገልግሎት ማዋል ነው፡፡ የግንባታ ፈቃድ በመከልከሉ ምክንያት ለቤቱ ክፍፍል/ partition/ ባለመሠራቱ ቤቱን ለባንክ አገልግሎት ማዋል አልተቻለም፡፡ በዚህ ምክንያት ውሉ ለተፈለገው ዓላማ ሳይውል መቅረቱ ከፍ/ብ/ሕጉ አንቀጽ 1788 ለውሉ መሠረዝ ምክንያት ይሆናል፡፡ ለመሠረዙ ምክንያቱ ምንም ይሁን ምን አንድ ውል ከተሰረዘ ተዋዋይ ወገኖች ከውል በፊት ወደ ነበሩበት ሁኔታ እንዲመለሱ የማድረግ ውጤት እንደሚያስከትል በፍ/ብሄር ሕጉ አንቀጽ 1815 ስር ከተመለከቱት ድንጋጌዎች መገንዘብ ይቻላል፡፡

ከዚህ አንፃር የያዝነውን ጉዳይ ስንመለከት የሚመለከተው የአስተዳደር አካል የግንባታ ፍቃድ ለመስጠት ፍቃደኛ አለመሆኑ በግራ ቀኙ መካከል የተደረገ ውል መሠረታዊ ዓላማ የሚነካ መሆኑን ተከትሎ ውሉ መሠረዙ አመልካች በኪራይ የያዘውን ቤት በተረከበበት ሁኔታ ለተጠሪ የመመለስ ግዴታ ያለበት ሲሆን፣ ተጠሪ በበኩሉ በኪራይ ውሉ ምክንያት የተቀበለውን ገንዘብ ለአመልካች መልስ የመክፈል ግዴታ ይኖርበታል፡፡ ይህ በመርህ ደረጃ ሲሆን ውሉ በመሠረዙ ምክንያት የደረሰ ጉዳት ካለ ለደረሰ ጉዳት በካሣ መልክ አንዱ ለሌላው የመክፈል ግዴታ በፍ/ብ/ሕጉ አንቀጽ 1771/2/፣1790 እና 1791 ላይ ከተመለከተው ድንጋጌዎች መገንዘብ ይቻላል፡፡ በዚህ ረገድ አመልካች ውሉ የተሰረዘው ተጠሪ የግንባታ ፈቃዱን የማስገኘት በውሉ የተጣለበትን ግዴታ ባለመወጣቱ ምክንያት መሆኑን በመግለጽ የሚከራከር ሲሆን፣ ተጠሪ በበኩሉ የግንባታ ፍቃዱ የተከለከለው የሚመለከተው የአስተዳደር አካል ፍቃደኛ ባለመሆኑ እንጂ በበኩሉ በውሉ የሚጠበቅበትን ግዴታ ባለመወጣቱ አይደለም በማለት ይከራከራል፡፡ የግንባታ ፈቃድ እንዲሰጥ ተገቢውን ትጋት ከማድረግ በዘለለ ተጠሪ የግንባታ ፈቃዱን የማስገኘት ግዴታ እንደሌለበት

የግልግል ዳኝነት ጉባዔው በፍሬ ነገር ደረጃ አረጋግጦ የወሰነ መሆኑን ስለተገነዘብን ውሉ ሊሰረዝ የቻለዉ በተጠሪ ምክንያት ነው በሚል አመልካች እያቀረበ ያለው ክርክር ተቀባይነት ያለው አይደለም፡፡

አመልካች የቤቱን ኪራይ መክፈል ግዴታ ያለበት መሆን አለመሆኑን በተመለከተ ተጠሪ ባቀረበው የተከሣሽ ከሣሽነት ክስ አመልካች የቤቱን ኪራይ መክፈል ግዴታ አለበት በማለት ለጠየቀው ዳኝነት መሠረት ያደረገው አመልካች የቤቱን ደረጃ በማሳደግ ደንበኛውን ወደሚሰጠው አገልግሎት ለመሳብ ያደረገው ጥረት ያልተሳካለት መሆኑን እያወቀ ቤቱን ወደ ነበረበት ሁኔታ ለመመለስ በውል ስምምነቱ ባለመቀጠል ሊመጣበት የሚችለውን ግዴታ ለመቀነስ ጥረት አለማድረጉን እና ይልቁንም በራሱ ጥናት ላይ ለመመስረት የቤቱን አቀማመጥ ጠቀሜታን ግምት ውስጥ በማስገባት ሌሎች አገልግሎት ሰጪ ተቋማት እንዳይዙበት በውል ስምምነቱ መግፋቱን መርጦ መቆየቱን ነው፡፡ ከላይ እንደተገለፀው አመልካች ቤቱ በእጁ በነበረበት ወቅት ያለውን የቤቱን ኪራይ በካሽ መልክ ለተጠሪ ለመክፈል የሚገደደው ለውሉ መሠረዝ ምክንያት ከሆነ ወይም ውሉ መሰረዙን እያወቀ ቤቱን በተገቢው ጊዜ ለተጠሪ በማስረከብ ሊመጣ የሚችለውን ጉዳት እንደመቀነስ ቤቱን ያለአግባብ በእጁ ያቆየ ስለመሆኑ ተጠሪ ካቀረበው የተከሣሽ ከሣሽነት ክስ አንፃር የተረጋገጠ ሲሆን ነው፡፡

አመልካች ተጠሪ በዚህ መልኩ ላቀረበው የተከሣሽ ከሣሽነት ክስ ቤቱን የማስተካከል ሥራው ከቆመበት ከ16/04/2008 ዓ.ም. ጀምሮ የቤቱን ኪራይ ያልተጠቀመበት መሆኑን በደብዳቤ ተጠሪን ያሳሰበ መሆኑን እና ቤቱን 3ኛ ወገን ለመከራየት ስላለመለፈለጉ ተጠሪ በማስረጃ አስደግፎ ማቅረቡን ገልጾ ተከራክሯል፡፡ የግልግል ዳኝነት ጉባዔው ግራ ቀኝ በዚህ መልኩ ያቀረቡትን ክርክር በጭብጥነት ይዞ በማስረጃ አላረጋገጠም፡፡ ይልቁንም ለግልግል ዳኝነት ጉባዔው አመልካች የቤቱን ኪራይ የመክፈል ኃላፊነት አለበት በሚል ድምዳሜ ላይ የደረሰው የግንባታ ፍቃድ አለመገኘቱ የሚያስከትለውን ኃላፊነት አውቆ እና አመዛዝኖ ወደ ውል መግባቱን እንዲሁም የግንባታ ፍቃድ እንደማይገኝ ካወቀበት ጊዜ ጀምሮ ውሉን አቋርጦ ቤቱን ለአከራይ /ለተጠሪ/ በማስረከብ የሚደርስበትን ኪሳራ እንደመቀነስ ውሉ እስኪቋረጥ ድረስ በዝምታ መቀመጡን ነው፡፡ ከላይ እንደተመለከተው የቤቱ ኪራይ መሠረታዊ አላማ ለባንክ አገልግሎት መሆኑን እና ውሉ በተደረገበት ወቅት ቤቱ ለባንክ አገልግሎት በሚውል መልኩ ክፍፍል ተደርጉበት ያልተዘጋጀ መሆኑን ግምት ውስጥ በማስገባት እና ለባንክ አገልግሎት በሚውል መልኩ ክፍፍል ማድረግ ግዴታ መሆኑን እና ይህን ለማድረግ የግንባታ ፈቃድ አስፈላጊ መሆኑን ግራ ቀኙአምነውበት በውላቸው አንቀጽ 9.2፣9.8፣11.1 እና 11.6 አመልክተዋል፡፡

ይህ በሆነበት ሁኔታ አመልካች የግንባታ ፍቃድ አለመገኘቱ የሚያስከትለውን ህጋዊ ውጤት አውቆ እና አመዛዝኖ የገባበት መሆኑን እንደአንድ ምክንያት በመውሰድ አመልካች ኃላፊነት እንዳለበት በግልግል ጉባዔው የሰጠው ውሣኔ በአግባቡ ሆኖ አልተገኘም፡፡

የግንባታ ፍቃድ የተከለከለው መቼ እንደሆነ እና የግንባታ ፍቃድ ባለመገኘቱ ቤቱ አገልግሎት እየሰጠ እንዳልሆነ አመልካች ለተጠሪ ያሳሰበው መሆን አለመሆኑን እንዲሁም ተጠሪ ደብዳቤው የደረሰው መሆን አለመሆኑን የደረሰው ከሆነ መቼ እንደደረሰው እና ቤቱን በተገቢው ጊዜ ከአመልካች ተረክቦ ለሌላ በማከራየት ሊደርስ የሚችለውን ጉዳት በመቀነስ ረገድ ተጠሪ በኩል ያደረገው ጥረት ስለመኖሩ በፍትሐብሔር ህጉ አንቀጽ 1802 መሠረት ባልተጠራበት ሁኔታ አመልካች ቤቱን በተገቢው ጊዜ አላስረከበም በሚል የግልግል ዳኝነት ጉባዔው የሰጠው ምክንያትም ተገቢነት የሌለው ነው፡፡

በአጠቃላይ ውሉ መሠረዙን ተከትሎ ተጠሪ ከቤቱ ኪራይ ማግኘት ይችል የነበረውን ገቢ በማጣት ለደረሰበት ጉዳት አመልካች የቤቱን ኪራይ በካሣ መልክ ለመክፈል የሚገደደው በበኩሉ የፈፀመው ጥፋት መኖሩ ሲረጋገጥ ሲሆን፣ በዚህም መሠረት ጉዳዩ በመጀመሪያ የቀረበለት የግልግል ዳኝነት ጉባዔው ከግራ ቀኝ ክርክር አኳያ አግባብነት ያላቸውን ጭብጦች በመያዝ አመልካች ኃላፊነት ያለበት መሆን አለመሆኑን አረጋግጦ አመልካች እንዲከፍል የሚገደደዉን የካሳ መጠንም በፍ/ብሄር ሕጉ አንቀጽ 1799 እና ተከታዮቹ ድንጋጌዎች መሠረት አስልቶ መወሰን ነበረበት ፡፡ በመሆኑም የግልግል ዳኝነት ጉባዔው በሌሎች ጭብጦች ላይ የሰጣቸው ውሣኔዎች በአግባቡ በመሆናቸው እኛም የምንቀበለው ሆኖ አመልካች የቤቱን ኪራይ እንዲከፍል በሚል የተሰጠው የውሣኔ ክፍል ግን ከላይ በዝርዝር ከተመለከቱት ምክንያቶች አንፃር ሲታይ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ በመገኘቱ ተከታዩ ተወስኗል፡፡

<u>**ውሣኔ**</u>

1. የግልግል ጉባዔ ጥቅምት 4 ቀን 2010 ዓ.ም. የሰጠው ፍርድ ፣ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ/ 205218 ግንቦት 23 ቀን 2010 ዓ.ም. በዋለው ችሎት የሰጠው ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ/ 348/1/ መሠረት ተሻሽሏል፡፡
2. አመልካች ለተጠሪ ከፍሎ የነበረው የቤት ኪራይ ብር 203343.00/ ሁለት መቶ ሶስት ሺ ሶስት መቶ አርባ ሶስት ብር/ ሊመለስለት አይገባም፣ አመልካች በተጨማሪ ብር 135562.00/ አንድ መቶ ሰላሳ አምስት ሺ አምስት መቶ ስድሳ ሁለት ብር/ ለተጠሪ ሊከፈል ይገባል በሚል የተሰጠው የውሣኔ ክፍል ተሸሯል፡፡

3. ከላይ በፍርድ ሃተታው በተመለከተው መሠረት አመልካች የተከራየው ቤት  የግንባታ ፈቃድ በመከልከሉ ምክንያት ለተገቢው ዓላማ አለማዋሉን ያወቀው መቼ ነው? ለተፈለገው አላማ አለማዋሉን እንዳወቀ ተጠሪ ይህንኑ እንዲያውቅ አድርጓል ወይ?አመልካች ተጠሪ ይህን እንዲያውቅ አድርጐ ከሆነ ተጠሪ ቤቱን በተገቢው ጊዜ ያልተረከበው ለምንድን ነው?  ተጠሪ ቤቱን በተገቢው ጊዜ መረከብ እየቻለ ይህን አለማድረጉ በፍትሐብሄር ሕጉ ምን ውጤት አለው:? የሚሉትን ነጥቦች ግራ ቀኙ ካቀረቡት ማስረጃ አንፃር በመመርመር ተገቢ ነው ያለውን ሕጋዊ ውሣኔ እንዲወስን በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ/ 343/1/ መሠረት ለግልግል ዳኝነት ጉባዔው ጉዳዩን መልሰን ልከንለታል፡፡
4. በዚህ ሰበር ችሎት በግራ ቀኙ የወጣ ወጪ ካለ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡
5. የውሣኔው ትክክል ግልባጭ ለስር ፍ/ቤት እና ለግልግል ዳኝነት ጉባዔው ይድረስ ብለናል፡፡

መዝገቡ ውሣኔ ስላገኘ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ሠ/ኃ

የሰ/መ/ቁ. 169077

ሰኔ 28ቀን 2011 ዓ.ም.

ዳኞች -ተፈሪ ገብሩ (ዶ/ር)

ቀነአ ቂጣታ

ተሾመ ሽፈራው

ፀሐይ መንክር

ኑረዲን ከድር

አመልካች ፡- መይ ሪል ስቴት ዴቨሎፕመንት ኃ/የተ/የግ/ማህበር

ተጠሪ፡- አቶ ያየህ ይራድ ፍቅሬ

መዝገቡን መርምረን ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

በግራ ቀኙ መካከል በተደረገው የህንፃ ክፍል ሰርቶ የማስረከብ ውል መነሻነት ክስ ቀርቦ የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የካቲት 24 ቀን 2008 ዓ.ም በሰጠው ፍርድ የአሁን አመልካች አከራካሪውን ቤት ለተጠሪ እንዲያስረክብ እና በውሉ መሰረት ቤቱን በጊዜው ባለማስረከቡ በተጠሪ ላይ በኪራይ ማጣት የደረሰውን ኪሳራ እንዲከፍል፤ እንዲሁም የኪራዩ መጠን ተጣርቶ እንዲወሰን በማለት ውሳኔ አሳልፏል፡፡

ኪራይን በተመለከተ ተጠሪ የሚገነባው ቤት በወር ብር 30,000.00 (ሰላሳ ሺህ) ይከራይ እንደነበር ጠቅሰው ቤቱን ማስረከብ ከነበረበት የካቲት 2000 ዓ.ም ጀምሮ በዚህ አግባብ ተሰልቶ እንዲከፈላቸው የጠየቁ ሲሆን አመልካች በበኩሉ ኪራይ ሊከፍል የማይገባበትን ምክንያት እና የኪራዩ መጠን በማስረጃ የተደገፈ አለመሆኑን በማንሳት ተከራክሯል፡፡

የስር ፍርድ ቤት ክርክር የተነሳበት ቤት ስፋት እና ሁኔታ ጋር ተመሳሳይነት ያላቸው በአካባቢው የሚገኙ ቤቶች በምን ያህል እንደሚከራዩ ተጣርቶ እንዲቀርብ በቅድሚያ ለቂርቆስ ክ/ከተማ ወረዳ 8 አስተዳደር ፍትህ ጽቤት ትዕዛዝ ሰጥቶ ጽ/ቤቱ በቁጥር ቀ/ክ/ከ/ወ/08/ፍ/ጽ/ቤት 1353/09 በቀን 29/05/2009 ዓ.ም በላከው ምላሽ ከአካባቢው በተገኘው መረጃ ከ2000 ዓ.ም እስከ 2005 ዓ.ም ባለው ጊዜ ባለሁለት መኝታ 83 ካ.ሜ የህንጻ ቤት በአማካይ ከብር 8,000.00 እስከ 10,000.00 እንደሚከራይ እንዲሁም 115 ካ.ሜ ከብር 12,000.00 እስከ 15,000.00 እንደሚከራይ ገልጿል፡፡ ፍርድ ቤቱ የቀረበው ማስረጃ አከራካሪውን ጭብጥ በተፈለገው ሁኔታ እና ደረጃ አጣርቶ ለመወሰን የሚያስችል አይደለም በማለት በድጋሚ ተጣርቶ እንዲቀርብ ለኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ትዕዛዝ ሰጥቶ ባለስልጣኑ በቁጥር ሞዕ/3-20/10/17833 በቀን 14/09/2009 ዓ.ም በፃፈው ምላሽ ስፋቱ 152.2 እና

152.6 የሆኑ ቤቶች በ2007 ዓ.ም ርክክብ ተደርጎ የተከራዩበትን ዋጋ የገለፀ ሲሆን ፍርድ ቤቱ ክርክር የተነሳበት ቤት ስፋት 225 ካ.ሜ በመሆኑ የቀረበው ምላሽ ጉዳዩን ለመወሰን የሚያስችል አይደለም በማለት አልፎታል፡፡

ከዚህ በኋላ ፍርድ ቤቱ የኪራዩን መጠን በተመለከተ ግራ ቀኙ ምስክሮቻቸውን አቅርበው እንዲያስረዱ ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡ በዚህ መሰረት ተጠሪ በአካባቢው በደላላነት እንደሚሰሩ የገለፁ አንድ ምስክር አቅርበው አሰምተዋል፡፡ ምስክሩ በሰጡት ቃል ቤቶቹ ከ2000 እስከ 2005 ዓ.ም ድረስ ከ2,000.00 የአሜሪካ ዶላር ጀምሮ እንደሚከራዩ መስክረዋል፡፡ አመልካች በበኩሉ ያቀረባቸው ሁለት ምስክሮች ከ2000 — 2005 ዓ.ም ድረስ በአካባቢው ቤቶች ተሰርተው ባለመጠናቀቃቸው እንደማይከራዩ መስክረዋል፡፡ በመጨረሻ ፍርድ ቤቱ በሰጠው ፍርድ የአመልካች ምስክሮች የሰጡትን ቃል ውድቅ በማድረግ የተጠሪ ምስክር ከጠቀሱት ዋጋ ላይ መነሻውን 2,000.00 የአሜሪካ ዶላር በመያዝ ኪራዩ ሊሰላ ይገባል ብሏል፡፡ በዚህ መሰረት በወቅቱ በነበረው የምንዛሬ መጠን አስልቶ ከየካቲት 2000 ዓ.ም እስከ ሰኔ 2005 ዓ.ም ላለው ጊዜ ብር 1,768,407.60 (አንድ ሚሊዮን ሰባት መቶ ስድሳ ስምንት ሺህ አራት መቶ ሰባት ብር ከስድሳ ሳንቲም) ኪሳራ በኪራይ መልክ ከነወለዱ አመልካች ለተጠሪ ሊከፍል ይገባል በማለት ወስኗል፡፡

አመልካች ይህን ውሳኔ በመቃወም የይግባኝ ቅሬታውን ለፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ቢያቀርብም ይግባኙ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 337 መሰረት ተሰርዟል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚህ ነው፡፡

ጥር 13/2011 ዓ.ም የቀረበው የሰበር አቤቱታ በአጣሪ ችሎቱ ተመርምሮ አመልካች እንደውላቸው ቤቱን በጊዜው ሰርቶ ባለማስረከቡ በተጠሪ ላይ በደረሰው የገንዘብ ጉዳት ሊከፍል የሚገባውን የካሳ መጠን በኪራይ መልክ አስልቶ ለማስከፈል የፌ/ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ከመንግስታዊ ተቋማት ስለኪራዩ መጠን የሚገልጽ ማስረጃ ካስቀረበ በኃላ ወደጎን በመተው በአንድ ሰው ምስክርነት ቃል ላይ ብቻ ተንተርሶ የሰጠውን ዳኝነት ከማስረጃው አግባብነት አንፃር ተገቢ መሆን አለመሆኑንና ተያያዥ ጉዳዮችን አጣርቶ ለመወሰን ሲባል ጉዳዩ ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ እና ተጠሪ መልስ እንዲሰጡበት ተደርጓል፡፡ ተጠሪ ሚያዚያ 25/2011 ዓ.ም በተፃፈ መልስ በሥር ፍርድ ቤት ውሳኔ የተፈፀመ መሰረታዊ የህግ ስህተት የለም ተብሎ ቅሬታው ውድቅ እንዲደረግ ተከራክረዋል፡፡ አመልካችም ክርክሩን በማጠናከር የመልስ መልስ አቅርቧል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ከላይ ባጭሩ የተጠቀሰው ሲሆን እኛም ጉዳዩን እንደሚከተለው መርምረናል፡፡ ከክርክሩ መረዳት እንደሚቻለው የግራ ቀኙ ግንኙነት ውልን መሰረት ያደረገ ነው፡፡ እንደውሉ ያልተፈፀመለት ወገን እንደውሉ ባለመፈፀሙ ምክንያት ለደረሰበት ጉዳት በጥቅም መቋረጥ መልኩም ሆነ በሌላ ሁኔታ ኪሳራ የመጠየቅ መብት ያለው ስለመሆኑ በፍ/ብ/ህ/ቁ 1771 ሥር በመርህ ደረጃ

ተደንግጓል፡፡ በተያዘው ጉዳይ አመልካች በውሉ መሰረት ቤቱን በጊዜው ለተጠሪ ባለማስረከቡ በተጠሪ ላይ በኪራይ ማጣት መልክ የደረሰውን ኪሳራ እንዲክስ ተጠሪ መጠየቃቸውና የሥር ፍርድ ቤትም በዚሁ መሰረት ውሳኔ ላይ መደረሱ የህጉን ይዘትና መንፈስ የተከተለ አይደለም የሚሰኝ ሆኖ አላገኘነውም፡፡

በአንፃሩ የውል ጥሰት ሲኖር ሊከፈል የሚገባውን ኪሳራ አቆራረጥ በተመለከተ በህጉ የተመለከቱትን ድንጋጌዎች፤ እንዲሁም ኪሳራው የሚቆረጠው በኪራይ ስሌት ተመን ነው ቢባልና ግራቀኙ አስቀድመው የተመኑት ኪራይ ልክ ባይኖር ኪራዩን ለመወሰን አግባብነት የሚኖረው ማስረጃ ምን አይነት ነው የሚሉትን በተመለከተ ከህጉ ጋር አያይዞ በመመልከት የሥር ፍርድ ቤቶች ባሳለፉት ውሳኔ የተፈፀመ የህግ ስህተት መኖር አለመኖሩን በመመርመር ውሳኔ ላይ ሊደረስ እንደሚገባ ተገንዝበናል፡፡

በፍ/ብ/ህ/ቁ 1771 ሥር በመርህ ደረጃ የተደነገገው የውል አለመፈፀም ስለሚያስከትለው የጉዳት ኪሳራ የተመለከተው ቢኖርም የሚከፈለው ኪሳራ የሚታሰበው በፍ/ብ/ህ/ቁ 1799 ሥር እንደተደነገገው አእምሮ ያለው ሰው ውሉ ባለመፈፀሙ ይደርሳል ብሎ በሚገመተው አስተያየት ልክ ነው፡፡ በዚህ አኳኋን የውሉ መሰረቶች ናቸው ተብለው የሚያዙት የውሉን አይነት መመልከት ብቻ ሳይሆን የተዋዋዮችን የሙያ፣ ሥራ፣ ከዚህ በፊት የነበራቸውን ግንኙነት፣ ባለዕዳው የሚያውቃቸውን ሁኔታዎች እና ማናቸውንም አጋጣሚ ሁኔታዎች ሁሉ በመመልከት ስለመሆኑ ይደነግጋል፡፡ ይህም ብቻ ሳይሆን ኪሳራው ባለገንዘቡ በደረሰበት እርግጠኛ ጉዳት ልክ እንዲሆን አድርጎ መወሰን የሚቻል ቢሆንም እንዲህ አይነት ውሳኔ ሊሰጥ የሚችለው ግን ባለገንዘቡ ውል ሲያደርግ ጉዳቱን ይበልጥ የሚያከብዱበትን ልዩ ልዩ ምክንያቶች ለባለዕዳው አስቀድሞ ያስታወቀ ሲሆን መሆኑን ከፍ/ብ/ህ/ቁ 1801 ግልጽ ድንጋጌ መገንዘብ ይቻላል፡፡

በተያዘው ጉዳይ የሥር ፍርድ ቤት በውሉ የተመለከተውን የማስረከቢያ ጊዜ እና በተጠሪ የተጠየቀውን የኪራይ ኪሳራ ብቻ በመመልከት በተጠሪ ላይ ይደርሳል ያለውን እርግጠኛ ጉዳት ልክ ላይ ውሳኔ ከመስጠቱ በቀር እንደ ህጉ ድንጋጌዎች የውሉን አይነት፣ የተዋዋዮችን ሥራና የነበራቸውን ግንኙነት እንዲሁም ከቀረበው የዳኝነት ጥያቄ አንፃር ባለዕዳ የሆነው የአሁን አመልካች የሚያውቃቸውን ሁኔታዎች ሁሉ እንዲሁም ጉዳቱን የሚያከብዱ ሁኔታዎች አስቀድሞ እንዲያውቅ የተደረገበት ሁኔታ መኖር አለመኖሩን ሁሉ በማጣራት ውሳኔ ላይ መደረሱን መዝገቡ አያሳይም፡፡ ክርክሩ ከፍሲል በተጠቀሰው የህግ አግባብ ታይቶ እና ጉዳዩ በአግባቡ ተጣርቶ ኪሳራው ካልተወነ ውሳኔው ህጉን መሰረት ያደረገ ነው ሊባል አይችልም፡፡

በሌላም በኩል ኪሳራው የሚቆረጠው በኪራይ ውል ስሌት ተመን መሰረት ነው ቢባልና ግራቀኙ አስቀድመው የተመኑት የገንዘብ ልክ ባይኖር የኪራዩን ገንዘብ ልክ ለመወሰን አግባብነት የሚኖረው ማስረጃ ምን አይነት እንደሆነ በህጉ ተመልክቷል፡፡ በፍ/ብ/ህ/ቁ 2950(2) የቤት ኪራይ ልክ በሚያጠራጥር ጊዜ የማዘጋጃ ቤት ባለስልጣናት በወሰኑት ታሪፍ መሰረት ወይም የተወሰነ ታሪፍ ከሌለ የቦታዎቹን ልማድ በመከተል ሊወሰን እንደሚገባ ይደነግጋል፡፡ ከዚህ አንፃር ሲታይ አመልካች እንደውሉ ቤቱን በጊዜው ሰርቶ ባለማስረከቡ በተጠሪ ላይ በደረሰው የገንዘብ ጉዳት ሊከፍል የሚገባውን የካሳ መጠን በኪራይ መልክ አስልቶ ማስከፈል ተገቢ መሆኑ ከታመነበትና የኪራዩ መጠን አከራካሪ በሆነበት የፌ/ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ከመንግስታዊ ተቋማት ስለኪራዩ መጠን የሚገልጽ ማስረጃ ካስቀረበ በኃላ ይህን ወደጎን በመተው በደላላነት የተሰማሩ ሰው የሰጡት ምስክርነት ቃል ላይ ተንተርሶ የሰጠው ዳኝነት ከማስረጃው አግባብነት አንፃር ሲታይም ህጉን የተከተለ ሆኖ አላገኘነውም፡፡

በአጠቃላይ የአሁን አመልካች እንደውሉ ባለመፈፀሙ ምክንያት በተጠሪ ላይ ለደረሰው ጉዳት የመካስ ኃላፊነት አለበት በሚል የተሰጠው ውሣኔ በአግባቡ ቢሆንም ሊከፈል የሚገባውን የኪሣራ መጠን በመወሰን ረገድ ግን በግራቀኙ መካከል የተደረገውን የውል አይነት፣ የነበራቸውን ግንኙነት እንዲሁም የአሁን አመልካች አስቀድሞ የሚያውቃቸውን ሁኔታዎች ሁሉ በማጣራት ውሳኔ ላይ አለመደረሱ እንዲሁም ኪሳራው የሚቆረጠው በኪራይ ውል ስሌት ተመን መሰረት ነው ቢባልም የኪራዩን ገንዘብ ልክ ለመወሰን አግባብነት የሚኖረው ማስረጃ የማዘጋጃ ቤት ባለስልጣናት የወሰኑት ታሪፍ ስለመሆኑ ወይም የተወሰነ ታሪፍ ከሌለ የቦታዎቹን ልማድ በመከተል ሊወሰን እንደሚገባ በህጉ ተመልክቶ እያለ በዚህ አግባብ ጉዳዩ ሳይታይ የተሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ስላገኘነው የሚከተለውን ውሣኔ ሰጥተናል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 134470 ግንቦት 24 ቀን 2010 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ እንዲሁም የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በፍ/ይ/መ/ቁ 161698 ጥቅምት 15/2011 ዓ.ም ያሳለፈው ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 348(1) መሰረት ተሽሯል፡፡
2. የአሁን አመልካች እንደውሉ ባለመፈፀሙ በተጠሪ ላይ ለደረሰው ጉዳት ኪሳራ የመክፈል ኃላፊነት አለበት ተብሎ አስቀድሞ የተሰጠው ውሳኔ እንደተጠበቀ ነው ብለናል፡፡
3. የከፍተኛው ፍርድ ቤት የተዘጋውን መዝገብ በማንቀሳቀስ ሊከፈል የሚገባውን የኪሣራ መጠን በመወሰን ረገድ በግራቀኙ መካከል የተደረገውን የውል አይነት፣ የነበራቸውን ግንኙነት እንዲሁም የአሁን አመልካች አስቀድሞ የሚያውቃቸው ሁኔታዎች ሁሉ ኪሳራውን ለመወሰን ግምት ውስጥ ሊገቡ የሚገባቸው ጉዳዮች መሆናቸውን ተገንዝቦ ይህን መነሻ በማድረግ የህጉን

ይዞትና መንፈስ ተከትሎ ውሳኔ እንዲሰጥ፤ ኪሳራው የሚቆረጠው በኪራይ ውል ስሌት ተመን መሰረት ነው ስለተባለም የኪራዩን ገንዘብ ልክ ለመወሰን አግባብነት የሚኖረው ማስረጃ የማዘጋጃ ቤት ባለስልጣናት የወሰኑት ታሪፍ በመሆኑ ለተመሳሳይ ቤት የሚታወቅ ታሪፍ ቢኖር በመጠየቅ እንዲሁም ታሪፍ ከሌለ የቦታዎቹን ልማድ በመከተል በአግባቡ አጣርቶ እንዲወስን ጉዳዩን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 343(1) መሠረት መልሰናል፡፡ ይፃፍ፡፡

4. በዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት ግራ ቀኙ ያደረጉት ክርክር ያስከተለውን ወጭና ኪሣራ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ሠ/ኃ

የሰ.መ.ቁ.168198

ሰኔ 24 ቀን 2011 ዓ.ም

**ዳኞች፡**.... ተፈሪ ገብሩ (ዶ/ር)

ቀነዓ ቂጣታ

ተሾመ ሽፈራዉ

ፀሐይ መንክር

ኑረዲን ከድር

አመልካች፡...... . ..አፍሪካ ክንፋ መረዳጃ እድር፡- ሺፈታ በለጠ ቀርበዋል፡፡

ተጠሪዎች፡......... . .1. አቶ ዮሴፍ ደበበ } የቀረበ የለም፡፡

2. አቶ ኤርሚያስ ጌታቸዉ

ይህ መዝገብ ተመርምሮ የሚከተለዉ ፍርድ ተሰጥቷል።

**ፍርድ**

ይህ ክርክር የተጀመረዉ በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ሲሆን፣የአሁን አመልካች ከሳሽ፣ የአሁን ተጠሪዎች ደግሞ ተከሳሾች ሆኖ ሲከራከሩ ነበር።ጉዳዩ ለዚህ ችሎት ሊቀርብ የቻለዉ የአሁን አመልካች የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ.214403 ታህሳስ 9 ቀን 2011 ዓ.ም የሰጠዉ ትዕዛዝ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ እንዲታረምልን በማለት በማመልከቱ ነዉ።

የጉዳዩ አመጣጥ ሲታይ ከሳሽ (የአሁን አመልካች )ባቀረበዉ ክስ ተከሳሾች ከ1/6/2007 ዓ.ም እስከ 30/11/2009 ዓ.ም ድረስ ያለዉን ዉዝፍ ኪራይ እና ተጨማሪ እሴት ታክስ እና ወለድን ጨምሮ ብር 464,887.50 እንዲከፍሏቸዉ ጠይቋል።

በዚህ ክስ ላይ ተከሳሾች ባቀረቡት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ከሳሽ ያቀረበዉ የኪራይ ይከፈለኝ ጥያቄ በ2 ዓመት ይርጋ የሚታገድ ስለሆነ መዝገቡ እንዲዘጋልን በማለት ተከራክሯል። ከሳሽ በዚህ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ላይ በሰጠዉ ምላሽ ይህ ክስ በፍ/ብ/ሕ/ቁ.2025 (ለ) መሰረት በይርጋ የሚታገድ አይደለም በማለት ተከራክሯል።

ከዚህ በኋላ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በተከሳሾች በተነሳዉ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ላይ በሰጠዉ ብይን ከዚህ ቀደም በግራ ቀኛቸዉ መካከል በተደረገዉ ክርክር ተከሳሽ ቤቱን እንዲለቁ እና ኪራይ እንዲከፍሉ የተጠየቀ ሲሆን ፍ/ቤቱ እስከ 30/11/2007 ዓ.ም ያለዉን ኪራይ የወሰነ ቢሆንም ከ1/12/2007 ዓ.ም ጀምሮ ላለዉ ጊዜ ዉዝፍ ኪራይ ጠይቋል ለማለት

ስለማይቻል፣ ከሳሽ ከ1/6/2007 ዓ.ም እስከ 30/11/2007 ዓ.ም የጠየቀዉን ዉዝፍ የቤት ኪራይ ይከፈለኝ ጥያቄ በ2 አመት ይርጋ የሚታገድ ነዉ በማለት ክሱን ዉድቅ በማድረግ ወስኗል።

የሥር ከሳሽ በዚህ ዉሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ያቀረበ ቢሆንም ፍ/ቤቱ የቀረበዉን ይግባኝ ማመልከቻ በትዕዛዝ ዉድቅ በማድረግ የሥር ዉሳኔ በማጽናት ወስኗል። የአሁን የሰበር አቤቱታ የቀረበዉ በዚህ ትዕዛዝ ቅር በመሰኘት ለማሻር ነዉ።

የአሁን አመልካች በ25/4/2011 ዓ.ም በተጻፈ የሰበር አቤቱታ ከዚህ ቀደም በዚህ ጉዳይ ከፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት እስከ የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት እስከ 26/10/2009 ዓ.ም ድረስ ስንከራከር ስለነበርን በክርክር ላይ የቆየን በመሆኑ፣ በዚህ ምክንያት በ1/6/2007 ዓ.ም እስከ 30/11/2009 ዓ.ም ያለዉ ጊዜ በተመለከተ የ2 ዓመት ይርጋ የማይመለከተዉ ነዉ። የሥር ፍ/ቤቶች ከዚህ ቀደም የተሰጠዉን ዉሳኔ እና የፍ/ብ/ሕ/ቁ.2025(ለ) ያላገናዘበ ስለሆነ ተሽሮ ታርሞ እንዲወሰንልን በማለት አመልክቷል።

የሰበር አጣሪ ችሎት ጉዳዩን በማየት ፣አመልካች ያቀረበዉ ዉዝፍ የቤት ኪራይ ክፍያ ጥያቄ በ2 ዓመት ይርጋ ቀሪ ይሆናል ተብሎ የተሰጠዉ ዉሳኔ ከፍ/ብ/ሕ/ቁ.2024 እና 2025 አንጻር ፣ለመመርመር ሲባል የሰበር አቤቱታዉ ያስቀርባል ተጠሪዎች መልስ እንዲሰጡ ባዘዘዉ መሰረት መጋቢት 4 ቀን 2011 ዓ.ም የተጻፈ መልስ አቅርቧል። የመልሱም ይዘት በአጭሩ፡ የሥር ፍ/ቤቶች አመልካች ያቀረበዉ ዉዝፍ የቤት ኪራይ ይከፈለኝ ጥያቄ በተመለከተ በፍ/ብ/ሕ/ቁ.2024 በ2 ዓመት ጊዜ ዉስጥ ያልተከፈለ የቤት ኪራይ እንደተከፈለ የህግ ግምት ይወሰድበታል በሚለዉ ድንጋጌ ሥር የሚወድቅ ስለሆነ የተሰጠዉ ዉሳኔ ምንም ዓይነት የህግ ስህተት ያልተፈጸመበት ስለሆነ የሥር ዉሳኔ እንዲጸናልን ወጪና ኪሳራ እንዲወሰንልን በማለት በዝርዝር ተከራክሯል። የአሁን አመልካች የመልስ መልስ አቅርቧል።

የጉዳዩ አመጣጥ ከፍ ሲል የተመለከተዉ ይህ ችሎት የግራ ቀኛቸውን ክርክር አግባብነት ካላቸዉ የህግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ እንዲሁም የሰበር አቤቱታዉ ያስቀርባል ሲባል ከተያዘዉ ጭብጥ አንጻር እንደሚከተለዉ መርምሮታል። እንደመረመርነዉ የአሁን አመልካች እና ተጠሪዎች የቤት ኪራይ ክፍያ በተመለከተ ከፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ጀምሮ እስከ የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ሲከራከሩ ቆይተዉ፣ ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ.መ.ቁ.128939 ሰኔ 26 ቀን 2009 ዓ.ም በሰጠዉ ዉሳኔ የሥር ፍ/ቤት ዉሳኔ በማሻሻል ወስኗል። በዚህ ዉሳኔ ተጠሪዎች ከየካቲት 1 ቀን 2007 ዓ.ም እስከ ሐምሌ 30/2007 ዓ.ም ድረስ ያልከፈሉትን የቤት ኪራይ እና በቀጣይም የዉሉ ጊዜ በዉሉ መሰረት ለአመልካች እንዲከፍሉ

ወስኗል። ከዚህ መገንዘብ የሚቻለዉ ግራ ቀኛቸዉ ከሥር ፍ/ቤቶች ጀምሮ እስከዚህ ችሎት ድረስ እስከ ሰኔ 26 ቀን 2009 ዓ.ም ድረስ በቤት ኪራይ ክፍያ ሲከራከሩ እንደነበር የሚያመለክት ነዉ። ከዚህ በኋላ አመልካች ሐምሌ 22 ቀን 2009 ዓ.ም በተጻፈ ክስ ተጠሪዎች ከየካቲት 1 ቀን 2007 ዓ.ም እስከ ሐምሌ 30 ቀን 2009 ዓ.ም ያለዉን ዉዝፍ የቤት ኪራይ እና ተጨማሪ እሴት ታክስ ለማስከፈል ክስ ማቅረቡን ተገንዝበናል። ይህ በሥር ፍ/ቤት የተረጋገጠ ፍሬ ነገር ሲሆን በሕጉ አግባብ መርምረናል።

እንደሚታወቀዉ የፍ/ብ/ሕ/ቁ.2024 (መ) መሰረት ዕዳዉ እንዲከፈል መጠበቅ ከሚገባበት ቀን ጀምሮ እስከ ሁለት ዓመት ሳይከፈል የቀረ ገንዘብ እንደተከፈለ ከሚቆጠሩት ጉዳዮች አንዱ የቤቶች ኪራይ ዕዳ እንደሆነ ያመለክታል። የዚህ ድንጋጌ ዓላማ ሲታይ የቤት ኪራይ ክፍያ ሳይከፈል ሁለት ዓመት ያለፈ እንደሆነ እና ከዚህ አንጻር መቃወሚያ የቀረበ እንደሆነ፣ ይህ የቤት ኪራይ ክፍያ እንደተከፈለ ስለሚቆጠር፣ የዚህ የቤት ኪራይ ክፍያ ይከፈለኝ ጥያቄ ተቀባይነት የሚያጣ ይሆናል ማለት ነዉ። ይህ ደግሞ የይርጋ ጉዳይ ሳይሆን የቤት ኪራይ ክፍያዉ እንደተፈጸመ በሕግ ግምት የሚወሰድበት መሆኑን ነዉ። ነገር ግን በፍ/ብ/ሕ/ቁ.2025 ሥር የተመለከቱትን ሁኔታዎች የሚያስረዳ ማስረጃ በማቅረብ ይህን የሕግ ግምት ቀሪ ማድረግ እንደሚቻል ተመልክቷል። ከእነዚህ ሁኔታዎች ዉስጥ አንዱ በዚህ ድንጋጌ ንዑስ አንቀጽ (ለ) ሥር የተደነገገዉ ፣በሕግ የተደነገገዉ የጊዜ ዉሳኔ ሳይደርስ ባለገንዘቡ ገንዘቡን እንዲከፍለዉ ባለዕዳዉን ከፍርድ ቤት አስጠርቶ እንደሆነ እዳዉ እንደተከፈለ መቆጠሩ ቀሪ ይሆናል፣ በማለት ይደነግጋል። ከዚህ አንጻር አሁን ወደ ተያዘዉ ጉዳይ ስንመለስ የአሁን አመልካች ከዚህ ቀደም ተጠሪዎች ቤቱን እንዲለቁ እና ዉዝፍ የቤት ኪራይ እንዲከፍሉት በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ክስ አቅርቦ እስከዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት ሲከራከሩ ቆይተዉ ሰኔ 26 ቀን 2009 ዓ.ም ዉሳኔ ያገኘ እና እስከ 30/11/2007 ዓ.ም ድረስ ያለዉ የኪራይ ክፍያ እንዲከፍሉ የተወሰነ መሆኑ ሲታይ አመልካች የቤት ኪራይ እንዲከፈለዉ ተጠሪዎችን ከፍ/ቤት አስጠርቶ ሲከራከሩ ቆይቶ በኋላ ዉሳኔ የተሰጠበት መሆኑን የሚያስገነዝብ ነዉ። በመሆኑም በፍ/ብ/ሕ/ቁ.2024 (ለ) መሰረት የቤት ኪራይ እንዲከፈል መጠየቅ ካለበት ጊዜ ጀምሮ እስከ ሁለት ዓመት ድረስ ያልተጠየቀ የቤት ኪራይ ክፍያ እንደተከፈለ ይቆጠራል የሚለዉ የሕግ ግምት፣ በፍ/ብ/ሕ/ቁ.2025 (ለ) ሥር የተመለከተዉ ሁኔታ መኖሩን የሚያስረዳ ማስረጃ የቀረበ እንደሆነ የቤት ኪራይ ክፍያዉ እንደተከፈለ ይቆጠራል የሚለዉ ግምት ቀሪ መሆኑን የሚያስገነዝብ ነዉ። ስለዚህ የአሁን አመልካች የቤት ኪራይ ክፍያ እንዲከፈለዉ ያቀረበዉ ክስ በሁለት ዓመት ይርጋ የሚታገድበት የህግ አግባብ የለም።

ሲጠቃለል የሥር ፍ/ቤቶች የአሁን አመልካች ዉዝፍ የቤት ኪራይ እንዲከፈለዉ በተጠሪዎች ላይ የቀረበዉ ክስ በሁለት ዓመት ይርጋ የሚታገድበት የህግ አግባብ በሌለበት ክሱ በሁለት ዓመት

ይርጋ የሚታገድ ነዉ በማለት ክሱን ዉድቅ በማድረግ የሰጡት ዉሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ የሚከተለዉ ዉሳኔ ተሰጥቷል።

**ዉሳኔ**

1. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ በመ.ቁ.46706 በ10/7/2010 ዓ.ም የሰጠዉ ብይን እና የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ.214403 ታህሳስ 9 ቀን 2011 ዓ.ም የሰጠዉ ትዕዛዝ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያልተፈጸመበት ስለሆነ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.348 (1) መሰረት ተሽሯል።
2. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የተዘጋዉን መዝገብ በማንቀሳቀስ በፍርድ ሐተታዉ በተመለከተዉ አግባብ የአሁን አመልካች ያቀረበዉ ክስ በሁለት ዓመት ይርጋ የሚታገድ ባለመሆኑ፣ በዋናዉ ጉዳይ ላይ ግራ ቀኛቸዉን በማከራከር በማጣራት ተገቢ ነዉ ያለዉን ዉሳኔ እንዲሰጥበት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.341 (1) መሰረት ተመልሶለታል።
3. የዚህ ዉሳኔ ግልባጭ ለሥር ፍ/ቤቶች ይድረስ።
4. ግራ ቀኛቸዉ በዚህ ችሎት የደረሰባቸዉን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸዉን ይቻሉ።

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ሠ/ኃ

# ከውል ውጪ ኃላፊነት

የሰ/መ/ቁጥር 161417

ቀን 12/9/2011 ዓ/ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ሙስጠፋ አህመድ

አብርሃ መሰለ

ፊይሳ ወርቁ

ጳውሎስ ኦርሺሶ

አመልካች ፡- - ፀሀይ ኢንሹራንስ አ/ማ ነ/ፈ ቀሮሚሳ ፍሌ - ቀረቡ፡፡

ተጠሪ፡- - የኢትዮጵያ መድን ድርጅት - የቀረበ የለም ፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ለዚህ ሰበር መዝገብ ክርክር መነሻ የሆነው ጉዳይ የቀረበው አመልካች ሐምሌ 10 ቀን 2010 ዓ.ም በተፃፈ አቤቱታ የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁጥር 205570 ሚያዝያ 17 ቀን 2010 ዓ/ም በዋለው ችሎት የሰጠው ትእዛዝ እና የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁጥር 39741 ጥቅምት 8 ቀን 2011 ዓ/ም በዋለው ችሎት የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት ቅሬታውን በማቅረቡ ነው፡፡ ቅሬታውም አቤት የተባለበትን ውሣኔ፣ አመልካች የሚቃወምባቸውን ምክንያቶች የሚዘረዝርና በሰበር ሰሚው ችሎት በኩል ሊታይልኝ ይገባል የሚለውን ዳኝነት የሚጠይቅ ሲሆን፣ አመልካች ክስ ያቀረበው ከተጠሪ ህንጻ ላይ የወደቀ ፍራሽ የደንበኛዬ መኪና ላይ ወድቆ በመኪናው ላይ ጉዳት አድርሷል በሚል ሲሆን የውል ወይም ከውል ወጪ የሚል ነገር ሊነሳ አይችልም፡፡ በውል ምክንያት ነው ክስ የሚቀርበው ከተባለ እንኳ ወደ ውል ችሎት ወይም መብት ይጠበቅልኛል እንጂ የስር ፍ/ቤቶች በደፈናው ክሴን ውድቅ ማድረጋቸው ተገቢ አይደለም፡፡ የአመልካች ደንበኛ የተከራየው ቤት ለቢሮ የሚሆን ክፍል እንጂ መኪና ማቆሚያ ቦታ አይደለም፡፡ መኪና ማቆሚያ ቦታ ማንኛውም የተጠሪ ተጠቃሚ የሆነው ሰው ሁሉ የሚጠቀምበት በመሆኑ እንደውል የሚቆጠር ባለመሆኑ ክሴ ውድቅ መደረጉ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ይታረምልኝ የሚል ነው፡፡

በስር ፍ/ቤት የነበረው ክርክር የጀመረው ከፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ሲሆን ከሳሽ የአሁን አመልካች ባቀረበው ክስ ንብረትነቱ የተከሳሽ የአሁን ተጠሪ ከሆነው ህንጻ ላይ የህንጻው ፍርስራሽ ወድቆ የከሳሽ ደንበኛ በሆነው መኪና ላይ ወድቆ ጉዳት አድርሶበታል፡፡ ከሳሽ ከደንበኛው ጋር ባለው ውል መሰረት ብር 38853.19 ለማስጠገኛ ከፍሏል፡፡ ተከሳሽ ሊከፍለኝ ፍቃደኛ ባለመሆኑ ከ16/6/2007 ዓ/ም ጀምሮ ከወለድ ጋር እንዲከፍለኝ ሲል ጠይቋል፡፡ ተከሳሽም የከሳሽ ደንበኛ ጉዳት አድርሷል በተባለው ህንጻ ላይ ተከራይ ያለ በመሆኑ በፍ/ብ/ህግ ቁጥር 2088(1) መሰረት ሊጠይቀኝ አይችልም፡፡ በፍ/ብ/ህግ ቁጥር 2089 ጥቅም በሌለው ግንኙነት ህንጻው ለሚያደርሰው ጉዳት የህንጻው ባለቤት ጥፋት ከሌለበት ሃላፊነት የለበትም፡፡ ተከሳሽና የከሳሽ ደንበኛ ውል ያለን በመሆኑ እና በተከሳሽ ጥፋት ምክንያት ጉዳት የደረሰ ባለመሆኑ ተከሳሽ ኃላፊነት የለበትም፡፡ ካለጨረታ የተደረገ ጥገና ተከሳሽን የሚጎዳ በመሆኑ ውድቅ ይደረግልኝ፡፡ ከሳሽ ተተክቶ መጠየቅ የሚችለው ደንበኛው ባለው መብት በመሆኑና ደንበኛው ሊጠይቅ የማይችለውን መዳረግ ስለማይችል ክሱ ውድቅ ይሁንልኝ በሚል መልስ ሰጥተዋል፡፡ የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁጥር 39741 ጥቅምት 8 ቀን 2011 ዓ/ም በዋለው ችሎት በሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ህግ አንቀጽ 2088(1) እና (2) እንዲሁም በፍ/ብ/ህግ ቁጥር 2077 መሰረት የከሳሽ ደንበኛ ከተከሳሽ ጋር የቤት ኪራይ ውል የነበራቸው በመሆኑ ከተከራየው ህንጻ ላይ በወደቀው ፍራሽ ምክንያት በደረሰው ጉዳት የሚጠይቀው ባላቸው ውል መሰረት በማድረግ እንጂ ከውል ውጪ ሃላፊነት ህጎች በመጠቀም አይደለም፡፡ ከሳሽም ደንበኛው በሌለው መብት ሊተካ አይችልም፡፡ በመሆኑም ተከሳሽ ከውል ውጪ የሚመነጭ ሃላፊነት የለበትም ሲል ክሱን ውድቅ አድርጎታል፡፡ ከሳሽ የአሁን አመልካች ለፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት የይግባኝ ቅሬታ አቅርቦ በመ/ቁጥር 205570 ሚያዝያ 17 ቀን 2010 ዓ/ም በዋለው ችሎት የሰጠው ትእዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህግ ቁጥር 337 መሰረት አያስቀርብም ሲል ይግባኙም ሰርዞታል፡፡

የአሁን አመልካችም ይህን ውሳኔ በመቃወም ቀርቧል፡፡ መዝገቡም ተመርምሮ የስር ፍ/ቤት ጉዳት የደረሰበት መኪና ባለቤት ለጉዳቱ መንስኤ ከሆነው የህንጻው ባለቤት ጋር የኪራይ ውል ግንኙነት ያለው መሆኑ ከተረጋገጠ በፍ/ብ/ህግ አንቀጽ 2088(2) ከውል የመነጨ ክስ የማቅረብ መብት ያለው በመሆኑ የአሁን አመልካች በዚህ መብት በመዳረግ ከግራ ቀኙ የኪራይ ውል ስምምነት አድማስ እና ተፈጻሚነት ካላቸው ህጎች አንጻር ክርክሩ ሊመራ ይገባ ነበር ወይስ አልነበረም? ከዚህ አንጻር አመልካች ደንበኛው ባለው ከውል የመነጨ ግዴታ ክስ የማቅረብ መብት ሊዳረግ ይገባል ወይስ አይገባም ከሚለው ነጥብ አንጻር ለመመርመር ሲባል ቀርቧል፡፡ መልስና የመልስ መልስም ተሰጥቶበታል፡፡ ተጠሪ ጥቅምት 14 ቀን 2011 ዓ/ም በተጻፈ መልስ የስር ፍ/ቤት የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት እንዳልተፈጸመበት በማንሳት ይጽናልኝ ሲል ተከራክሯል፡፡ አመልካችም ህዳር 13 ቀን 2011 ዓ/ም በተጻፈ የመልስ መልስ አቤቱታቸውን በማጠናከር ተከራክረዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ከላይ የተመለከተውን ሲሆን፣ እኛም የቀረበውን አቤቱታ፣ መልስ እና የመልስ መልሱን እንዲሁም የስር ፍርድ ቤት ውሣኔዎችን እና ከጉዳዩ ጋር አግባብነት ያላቸውን የሕግ ድንጋጌዎችን መሠረት በማድረግ በጉዳዩ ላይ የተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት መኖር አለመኖሩን መርምረናል፡፡ እንደመረመርነውም በስር ፍ/ቤት በተደረገው ክርክር የአሁን አመልካች ደንበኛ የሆነው በአሁን ተጠሪ ህንጻ ላይ ተከራይቶ የነበረ መሆኑ፣ የአሁን አመልካች ደንበኛ መኪና ቆማ ባለችበት ከተጠሪ ህንጻ ላይ የወደቀው የህንጻው ፍርስራሽ ወድቆባት ጉዳት ያደረሰበት መሆኑ አላከራከረም፡፡ የስር ፍ/ቤቶች በአሁን አመልካች ደንበኛ እና በተጠሪ መሀከል የቤት ኪራይ ውል ያለ በመሆኑ በፍ/ብ/ህግ አንቀጽ 2088(2) ድንጋጌ መሰረት የአመልካች ደንበኛ ተጠሪን ሊጠይቀው የሚችለው በመሀላቸው ባለው የገቡት የውል ግዴታ መሰረት በመሆኑና የአሁን አመልካችም በደንበኛው ተዳርጎ ክስ ማቅረብ የሚችለው ደንበኛው ባለው መብት ልክ በመሆኑ አመልካች በተጠሪ ላይ ያቀረበው ከውል ውጪ ኃላፊነት ተቀባይነት የለም በሚል ክሱን ውድቅ አድርገውታል፡፡ የፍ/ብ/ህግ አንቀጽ 2088(1) ጉዳቱን ካደረሰው አደገኛ ኢንዱስትሪ፣ ወይም እንስሳ፣ ወይም ሕንጻ ወይም ሌላ ነገር ግንኙነት ያለውና በሕግ በኩልም ለነዚሁም ሃላፊ ከተባለው ሰው ጋራ ተዋውያለሁ የሚለው ሰው አሥጊ የሆኑ ነገሮችን በመፍጠር ወይም በእንስሳዎች ወይም በሕንጻዎች ወይም በሌላ ነገሮች ለሚደርሱ ጉዳቶች የኃላፊነትን ደንቦች በመጥቀስ ከኃላፊነት ለመዳን እንደማይቻል ይደነግጋል፡፡ በዚህ ጉዳይ ህንጻን በተመለከተ ከሚደርስ ጉዳት ጋር በተገናኘ ጉዳቱን ያደረሰው ህንጻ ኃላፊ ከሆነው ሰው ጋር የውል ግንኙነት ባለው ሰው ምክንያት ለሚደርሱ ጉዳቶች ይሄው ሰው ከኃላፊነት መዳን እንደማይችል የሚደነግግ ሲሆን በዚህ ጊዜ ጉዳቱን ያደረሰው ሰው ኃላፊነት የሚመራው በፍ/ብ/ህግ አንቀጽ 2088(2) በሚደነግገው መሰረት በመሀላቸው ባለው ውል መሰረት እንደሆነ የሚደነግግ ነው፡፡ የፍ/ብ/ህግ ቁጥር 2077(2) ድንጋጌም ይህንኑ የሚያስገነዝብ ነው፡፡ በመሆኑም የፍ/ብ/ህግ አንቀጽ 2088 ድንጋጌ የሚያመለክተው ከህንጻ ባለቤት ወይም ኃላፊ ከሆነው ሰው ጋር ውል ባደረገው ሰው ምክንያት የሚመጣ የጉዳት ሃላፊነት የሚመራው ባደረገው ውል መሰረት መሆኑን እንጂ ስለ ህንጻው ባለቤት ወይም ኃላፊ የሆነው ሰው የሚያወራ አይደለም፡፡ በፍ/ብ/ህግ ቁጥር 2077(1) ያንድ ሕንጻ ባለሀብት ወይም ባለይዞታ ሕንጻው ሊያደርስ ይችላል ተብሎ ያልታሰበ ድንገተኛ ነገር ቢያደርስም፣ ይህ ሕንጻ በሚያደርሰው ጉዳት ኃላፊ እንደሆነ ደንግጎ ይገኛል፡፡ በዚህ ጉዳይ የአሁን ተጠሪ ጉዳት ያደረሰው ሕንጻ ባለቤት መሆኑን እና ከህንጻው ላይ የወደቀው ፍርስራሽ በአመልካች ደንበኛ መኪና ላይ ጉዳት ያደረሰ መሆኑን አያስተባብልም፡፡ እንዲሁም የጉዳቱን መጠን በተመለከተ አመልካች የጠየቀው የመኪናዋ ማስጠገኛ ዋጋ በጨረታ የተደረገ ጥገና ባለመሆኑ ይጎዳኛል ከማለት ውጪ፣ ጉዳት የደረሰባት መኪና የተጠገነችው ከጨረታ ወጪ ስለመሆኑና ከተጠየቀው የማስጠገኛ ዋጋ አነስተኛ ዋጋ የቀረበ ስለመሆኑም ያቀረበው ክርክርና ማስረጃ የለም፡፡ በፍ/ብ/ህግ አንቀጽ 2077(1) ድንጋጌ መሰረት የአሁን ተጠሪ ሕንጻው ለሚያደርሰው ጉዳት ከውል ወጪ ኃላፊነት ያለበት ሲሆን የአሁን አመልካችም ከደንበኛው ጋር ካለው የኢንሹራንስ ውልና ከንግድ ህጉ አንቀጽ 683 ድንጋጌ የመነጨ ተተክቶ የአሁን

ተጠሪን ለመጠየቅ መብት አለው፡፡ ይህ ሆኖ እያለ የስር ፍ/ቤቶች የፍሬ ነገር ክርክሩን ካለመገንዘብ ከህጉ ድንጋጌ ትርጉም ውጪ የሰጡት ውሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡

**ውሳኔ**

1. የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁጥር 205570 ሚያዝያ 17 ቀን 2010 ዓ/ም በዋለው ችሎት የሰጠው ትእዛዝ እና የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁጥር 39741 ጥቅምት 8 ቀን 2011 ዓ/ም በዋለው ችሎት የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህግ ቁጥር 348(1) መሰረት ተሽሯል፡፡

2. የአሁን ተጠሪ ከህንጻው ላይ የወደቀው ፍርስራሽ በአሁን አመልካች ደንበኛ መኪና ላይ ላደረሰው ጉዳት ከውል ውጪ ኃላፊነት አለበት፡፡ የተጠሪ ህንጻ ላደረሰው ጉዳት የአሁን አመልካች በደንበኛው ተተክቶ የጉዳት ካሳ መጠየቅ ይችላል፡፡ የተጠሪ ህንጻ በአመልካች ድንገተኛ መኪና ላይ ላደረሰው ጉዳት ለመኪና ማስጠገኛ የወጣውን ወጪ ብር 38853.19 ተጠሪ ለአሁን አመልካች ይክፈለው፡፡ ተጠሪ አመልካች እንዲከፍለው ከጠየቀበትና ሊከፍለው ፍቃደኛ ካልሆነበት ከ16/6/2007 ዓ/ም ጀምሮ ከ9 % ወለድ ጋር ክፍያውን እስኪፈጽም ድረስ ታስቦ እንዲከፍለው ብለናል፡፡

3. በዚህ መዝገብ ክርክር ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሣቸውን ይቻሉ፡፡

4. የዚህ ውሳኔ ትክክለኛ ግልባጭ ለስር ፍ/ቤት ይድረሳቸው ብለናል፡፡

5. መዝገቡ ተዘግቶ ወደ መ/ቤት ተመልሷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ፅ/ወ

የሰ/መ/ቁ. 175142

ግንቦት 24 ቀን 2012 ዓ.ም

ዳኞች፡- ብርሃኑ አመነው

ተሾመ ሽፈራው

ሀብታሙ እርቅይሁን

ብርሃኑ መንግስቱ

ነፃነት ተገኝ

አመልካች ፡- የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት ሠሜን ሪጅን ሑመራ ዲስትሪክት

ተጠሪ ፡- አቶ ወሉ ገ/ሔር

መዝገቡ ተምርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሠጠ፡፡

**ፍ ር ድ**

የሰበር አቤቱታው የቀረበው የትግራይ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በሠጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሞበታል በሚል ነው፡፡ የክርክሩን አመጣጥ ከስር ፍርድ ቤት የመዝገብ ግልባጭ እንደተረዳነው አመልካች የስር ተከሳሽ ሲሆን ተጠሪ ከሳሽ ነበሩ፡፡ ተጠሪ ያቀረቡት ክስ በቃፍታ ሑመራ ወረዳ ማይ ከድራ ከተማ ቀጠና 02 በምኖርበት ቤት የካቲት 18 ቀን 2009 ዓ/ም በአመልካች የተዘረጋ የኤሌክትሪክ መሥመር በተነሳ የእሳት ቃጠሎ መኖሪያ ቤቴ ስለወደመ ግምቱ ብር 49,500.00 ካሣ እንዲከፈለኝ በማለት ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡ አመልካች የሠጠው መልስ ተጠሪ ለጉዳቱ ሊጋለጡ የቻሉት ከአመልካች ድርጅት ኤሌክትሪክ ተጠቃሚ ደምበኛ የሆኑ አቶ ማማይ ተገኝ ለግል ቤታቸው ሊጠቀሙበት ከተሠጣቸው ኤሌክትሪክ ሀይል፤ ከሕግ ውጭ ከቆጣሪው ስበው ሲጠቀሙ አደጋው ከወ/ሮ አከዛ ተስፋይ ቤት ውስጥ በራሳቸው ችግር ምክንያት የተፈጠረ ስለሆነ ልንጠየቅ አይገባም፡፡ የተዘረጋው መስመር ደረጃውን የጠበቀ በመሆኑና ጥፋት ስላልፈጸምን ለክሱ ኃላፊነት የለብንም በማለት ተከራክሯል፡፡

የምዕራብ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሑመራ ምድብ ችሎት የግራቀኙን ማስረጃ በመስማትና የፎረንሲክ ምርመራ ውጤቱን በመመልከት የቃጠሎ አደጋው ከወ/ሮ አከዛ ቤት መነሳቱ አልተረጋገጠም፡፡ ቢረጋገጥ እንኳን ተጠሪ ጥፋት የሌለባቸው በመሆኑ በፍ/ሕ/ቁ. 2086 መሠረት አመልካች ለጉዳቱ ኃላፊነት አለበት፡፡ በመኖሪያ ቤታቸው ላይ ለደረሠው ጉዳት ካሣ ብር 42,700.00 ከወጭና ኪሣራ ብር 3,500.00

ጋር አመልካች ለተጠሪ እንዲከፍል ወስኗል፡፡ አመልካች ለትግራይ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ አቅርቦ ፍርድ ቤቱ የአመልካችን ይግባኝ ባለመቀበል ሠርዟል፡፡

ይህ የሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚህ ውሳኔ ነው፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ ይዘትም ከተጠሪ ጋር የውል ግንኙነት የለንም፡፡ በፎረንሲክ ምርመራ አደጋው የተነሳው ከወ/ሮ አከዛ ቤት ስለመሆኑ ተረጋግጧል፡፡ ስለዚህ ለክሱ ኃላፊ ልንባል ስለማይገባ ውሳኔው ይሻርልን፤ አላግባብ የኤሌክትሪክ ሀይል ያከፋፈሉት አቶ ማማይ ተገኘ ጣልቃ እንዲገቡ ጠይቀንም መታለፉ ስህተት ያለበት ነው የሚል ነው፡፡ የሰበር አጣሪ ችሎት ጉዳዩን ተመልክቶ አመልካች ለተጠሪ ቆጣሪ ያልሠጠና በራሳቸው ጊዜ ከሌላ ሠው ስበው ለደረሰው ጉዳት ኃላፊነት የለብኝም በማለት እየተከራከረ ለክሱ ኃላፊ መሆኑ ከፍ/ሕ/ቁ. 2086(2) እና 2098(1)(2) አኳያ ለመመርመር ተጠሪ መልስ እንዲያቀርቡ አዟል፡፡ የተጠሪ መልስ የአመልካች መስመር ተቆርጦ ወደ መኖሪያ ቤት ወድቆ የተነሳ ቃጠሎ ነው፡፡ ጥፋቱ የእኔ የተበዳይ ስለመሆኑ እስካላረጋገጠ ድረስ ለጉዳቱ አመልካች ተጠያቂ ነው፡፡ ያጠፋሁት ጥፋት ደግሞ ስለሌለ ውሳኔው ተገቢ ነው ብለዋል፡፡ አመልካች የመልስ መልስ በማቅረብ የሠበር አቤቱታውን አጠናክሮ ተከራክሯል፡፡

የክርክሩ ሂደት በአጭሩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን እኛም አመልካች ለክሱ ኃላፊ መባሉ ሕጋዊ መሆን አለመሆኑን በጭብጥነት በመያዝ መዝገቡን መርምረናል፡፡

እንደመረመርነው ተጠሪ የጠየቁት ዳኝነት ከውል ውጭ ኃላፊነትን መሠረት ያደረገ ሲሆን በአመልካች የተዘረጋ በኤሌክትሪክ መሥመር ምክንያት በተነሳ የእሳት ቃጠሎ ቤቴ ስለወደመ ካሣ እንዲከፍለኝ የሚል ነው፡፡ አመልካች ያቀረበው መከራከሪያ ተጠሪ ለጉዳቱ ሊጋለጡ የቻሉት የአመልካች ድርጅት አሠራርና ደንብ በመጣስ ሌላ ግለሠብ ቆጣሪ ለተጠሪዎች እና ለሌሎች ግለሠቦች የኤሌክትሪክ ገመድ በመዘርጋት ኤሌክትሪክ ሀይል በመስጠታቸው እና አደጋውም ከወ/ሮ አከዛ ተስፋይ ቤት ውስጥ በራሳቸው ችግር ኤሌክትሪክ ሰርኪዩት ሾርት ምክንያት የተፈጠረ ስለመሆኑ የትግራይ ክልል ፖሊስ ኮሚሽን ባደረገው የፎረንሲክ ቃጠሎ ማጣራት አረጋግጧል፡፡ ተጠሪ የአመልካች ደምበኛ አይደሉም፡፡ ኤሌክትሪክ ሀይል የሚጠቀሙትም በሕገ-ወጥ መንገድ በተቀጠለ ገመድ ስለሆነ ኃላፊነት የለብኝም በማለት ነው፡፡

በፍ/ሕ/ቁ. 2069(1) መሠረት እንደተመለከተው አንድ ሠው ከፍተኛ ጉልበት ያለው የኤሌክትሪክ መስመር በመዘርጋት በሌላ ሠው ላይ ጉዳት ካደረሠ ለጉዳቱ ኃላፊ ነው፡፡ የኤሌክትሪክ መስመሩን የዘረጋው ሰው ጥፋት ባይኖርበትም የንብረቱ ባለቤት በመሆኑ አጥፊ ሳይሆን አላፊ ስለመሆን በተደነገገው ክፍል ስር በተመለከተው አግባብ ለጉዳቱ ኃላፊነት ይወስዳል፡፡ ከኃላፊነት ለመዳን በፍ/ሕ/ቁ 2086(2) እንደተመለከተው ጉዳቱ የደረሠው በተበዳዩ ጥፋት መሆኑን ማስረዳት አለበት፡፡ በሥር ፍርድ ቤቶች የተወሰነውም አመልካች ለዘረጋው የኤሌክትሪክ መስመር ለሚያስከትለው ጉዳት ኃላፊነት አለበት በማለት ነው፡፡

በተያዘው ጉዳይ በሕግ ማስረጃ የመመዘን ሥልጣን ያላቸው የሥር ፍርድ ቤቶች አመልካች ያቀረበውን ፎረንሲክ ምርመራ ውጤቱን ባለመቀበል ማስረጃ መዝነው አመልካች በዘረጋው የአሌክትሪክ መሥመር ጉዳት ደርሷል በማለት ድምዳሜ ላይ ደርሰዋል፡፡ የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በኢፌዲሪ ሕገ-መንግሥቱ አንቀጽ 80(3) ሆነ የፌደራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 10 ላይ በመጨረሻ ውሳኔ ላይ በተፈጸመ መሠረታዊ የሕግ ስህተት እንጂ ማስረጃው ተመዝኖ የተደረሠበትን የፍሬ ነገር ድምዳሜ ላይ እንዲመለከት ሥልጣን አልተሠጠውም፡፡ ነገር ግን ማስረጃ ለመመዘን ሥልጣን የተሠጠው ፍርድ ቤት ማስረጃ ሲቀበል የተከራካሪዎችን እኩል የመደመጥ መብት ካላከበረ፣ የማስረዳት ሸክም የማን ነው የሚለውን ካልለየ፣ የማስረጃ ተቀባይነትና ተገቢነት ላይ መከተል የሚገባውን ሥርዓት ካልተከተለ ወይም በምዘና ጊዜ የሁሉንም ተከራካሪዎች ማስረጃ አብሮ ካልመዘነ፤ በመሠረታዊ ሕግ ሆነ በሥነ-ሥርዓት ሕግ ያሉትን የማስረጃ ሕጎችና መርሆች ካላከበረ ጉዳዩ የማስረጃ ምዘና ሳይሆን የሕግ አተረጓጎም ስህተትና ፍርድ ቤት ያለበትን ኃላፊነት አለመወጣት ስለሚሆን የሰበር ሰሚ ችሎቱ የሚመለከተው ጉዳይ ይሆናል፡፡

ጉዳት ያደረሠው ተጠሪ እና ሌሎች ግለሠቦች ከአመልካች ደምበኛ ሳይፈቀድላቸው ስበው በወሰዱትና ቤታቸው ወስጥ በዘረጉት የኤሌክትሪክ መሥመር ሀይል ስለመሆኑ በትግራይ ክልል ፖሊስ ኮሚሽን በባለሙያ በተደረገ የፎረንሲክ ቃጠሎ ምርመራ ውጤት ተረጋግጧል፡፡ የባለሙያ ማስረጃ በቀረበ ጊዜ በዋናነት የሚመረመረው የባለሙያው ገለልተኛነት እና ሙያዊ ብቃት ሲሆን ሁለቱን መስፈርቶች ካሟላ ማስረጃው የፍሬ ነገሩን መኖር ወይም አለመኖር ለማረጋገጥ ከፍተኛ ግምት የሚሠጠው (high probative value) ማስረጃ እንደሆነ ተቀባይነት ካላቸው የማስረጃ ምዘና መርሆዎች የምንረዳው ነው፡፡ የሥር ፍርድ ቤቶች ከኤሌክትሪክ አደጋ ጋር በተያያዘ የሚደርስ ጉዳት የአደጋውን መንሥዔ ለማወቅ ሙያ የሚጠይቅ ሆኖ እያለ ለባለሙያ ማስረጃው ውጤት ሳይሰጡ የፎረንሲክ ምርመራ ውጤቱን አለመቀበላቸው የማስረጃ ምዘና መርህ ስህተት ነው፡፡ የፎረንሲክ ምርመራ ውጤቱ ቃጠሎ ሊያስነሳ የሚችሉ ሁኔታዎች እንዳልነበሩ፣ የቃጠሎው ምክንያት በኤሌክትሪክ ሰርኪዩት ሾርት ምክንያት አቀጣጣይ ሀይል መሆኑን፣ ቃጠሎው ከወ/ሮ አከዛ ቤት ተነስቶ ወደ ሌሎች ቤት እንደተሸጋገረ እና በአመልካች በዘረጋው ፖል ገመድ ላይ ቃጠሎው ጉዳት አድርሶ የተበጠሰ ስለመሆኑ በተመሳሳይ የቃጠሎ አደጋ ይሕ ፍርድ ቤት በሰበር መዝገብ ቁጥር 175139 ውሳኔ በሠጠበትና በተያዘው መዝገብ የተረጋገጠ ነው፡፡ ይህም ጉዳት ያደረሠው አመልካች የዘረጋው የኤሌክትሪክ መሥመር አለመሆኑን ያሳያል፡፡

አመልካች ራሱ ለዘረጋው የኤሌክትሪክ መሥመር ኃላፊነት ይወስዳል እንጂ ግለሠቦች በቤታቸው ለዘረጉትና ባለቤት ላልሆነበት የኤሌክትሪክ መሥመር አጥፊ ሳይሆኑ ኃላፊ ስለመሆን በተደነገገው የውል ውጭ ኃላፊነት የፍትሐ ብሔር ሕግ ክፍል (ከፍ/ሕ/ቁ 2066 - 2086) ስር ኃላፊ ሊሆን አይችልም፡፡ የፍ/ሕ/ቁ 2069(1) ኃላፊነትን በግልጽ ያቋቋመው የኤሌክትሪክ መሥመሩን የዘረጋው ሠው

ላይ ነው፡፡ ይህም አጥፊ ሳይሆኑ ኃላፊ ስለመሆን ከውል ውጭ የፍትሐ ብሔር ኃላፊነት የሚከተለው የኤሌክትሪክ መሥመሩን ባለቤት እንጂ የኤሌክትሪክ ሀይሉን ባለቤት አለመሆኑን ያሳያል፡፡ የኤሌክትሪክ ሀይሉ ባለቤት ኃላፊነት ሊኖርበት የሚችለው ማድረግ የሚገባውን ጥንቃቄ ካላደረገና ጥፋት ከፈጸመ ብቻ ነው፡፡

አመልካች በዘረጋው ከቆጣሪው በመለስ ባለው መስመር ላይም ላደረሰው ጉዳት ኃላፊነት የሚኖርበት ቆጣሪ ለሠጠው ደምበኛ ላይ ለደረሠ ጉዳት ነው፡፡ ተጠሪ የአመልካች ደምበኛ እና ፈቃድ ወስደው የኤሌክትሪክ መሥመር ያስገቡ አይደሉም፡፡ ከአመልካች ፈቃድ ውጭ ተጠሪ እና ወ/ሮ አከዛ ተስፋይ በራሳቸው በዘረጉት የኤሌክትሪክ መሥመር ምክንያት ለደረሠ ጉዳት አመልካች ኃላፊነት የለበትም፡፡ ስለሆነም አመልካች ለጉዳቱ ከውል ውጭ የፍትሐብሔር ኃላፊነት ሳይኖርበት ኃላፊ እንዲሆን የተሠጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

<u>ው ሳ ኔ</u>

1. የትግራይ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 110766 ጥር 10 ቀን 2011 ዓ.ም እና የምዕራብ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሑመራ ምድብ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 15158 መስከረም 22 ቀን 2011 ዓ.ም የሠጡት ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348(1) መሰረት ተሽሯል፡፡
2. አመልካች ለጉዳት ካሣው ኃላፊነት የለበትም ተብሎ ተወስኗል፡፡
3. በዚህ ችሎት ለወጣ ወጭና ኪሣራ አመልካች የራሱን እንዲችል ብለናል፡፡

<u>ት ዕ ዛ ዝ</u>

- የውሳኔው ግልባጭ ለስር ፍርድ ቤቶች ይተላለፍ፡፡
- መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

# የወንጀል ሕግ

የሰ/መ/ቁ 153016

ጥር 30 ቀን 2011 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ብርሃኑ አመነዉ

በዕዉቀት በላይ

እንዳሻዉ አዳነ

ሃይሉ ነጋሽ

እትመት አሠፋ

**አመልካች:-** ወ/ሮ ከበደች ዘሚካኤል

**ተጠሪ፡-** የአራዳ ክፍለ ከተማ አነስተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት

መዝገቡ የተቀጠረው መርምሮ ፍርድ ለመስጠት ነው፡፡ በመሆኑም መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

ይህ የሰበር አቤቱታ ሊቀርብ የቻለው አመልካች ጥር 21 ቀን 2010 ዓ.ም ጽፈው ባቀረቡት የሰበር አቤቱታ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ 27532 ታሕሳስ 19 ቀን 2010 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለታቸው ነው፡፡

ጉዳዩ ግብርን የሚመለከት ሲሆን የአሁን አመልካች ለአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ በዚህ የሰበር አቤቱታ የተያዘውን ጉዳይ በተመለከተ ያቀረቡት አቤቱታ ይዘት በአጭሩ በአራዳ ክፍለ ከተማ በመኪና ጌጣጌጥ ንግድ ስራ የተሰማሩ መሆኑን፤ ከተጠሪው ሚያዝያ 26 ቀን 2008 ዓ.ም ተወስኖ በደረሳቸው የኦዲት ውሳኔ ላይ ቅሬታ ያቀረቡ ቢሆንም ኮሚቴው ቅሬታቸውን ሳይመረምር ውሳኔውን ያጸናው መሆኑን፤ በድርጅታቸው ውስጥ በአደራ ተቀምጠው በተገኙ የቀድሞ ባለቤታቸው የግል ማስታወሻዎች ላይ በመንተራስ ቀደም ሲል ከ2003 ዓ.ም እስከ 2007 ዓ.ም ያሳወቁትን ዓመታዊ ሽያጭ ገቢ በመቀየር ፈጽሞ ባልሰሩት እና ባላገኙት ገቢ ብር 1,698,297.96 ግብር እና ታክስ ወለድ እና መቀጫ እንዲከፍሉ የተጠየቁ መሆኑን እና የራሳቸው ባልሆነ የግኝት ምንጭ በመንተራስ ተገቢውን የመረጃ ማጣራት ስራ ሳይሰራ የተወሰነባቸው መሆኑን፤ የባለስልጣን መስሪያ ቤቱ አሳሽ ቡድን ከድርጅቱ የሌላ ግለሰብ ማስታወሻዎች ሲወስድ የአመልካች አለመሆኑን

ያስረዱ ቢሆንም በድጋሚ ተጠርተው በድርጅቱ በተገኙት ሰነዶች ላይ የድርጅቱን ማህተም እንዲያሳርፉ የተገደዱ መሆኑን በመግለጽ ሰነዱን መሰረት በማድረግ የተሰጠው የግብር ውሳኔ እንዲሰረዝላቸው ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡

ተጠሪ በሰጠው መልስ አመልካች እና ሌሎች በአካባቢው በተመሳሳይ ስራ ላይ የተሰማሩ ግብር ከፋዮች አየር በአየር ግብይት እንደሚያከናውኑ እና ምንጩ ያልታወቀ ሀብት እንደሚያንቀሳቅሱ በተደረገው ጥናት መሠረት በግብር ከፋይዋ ድርጅት በአካል በመገኘት ባደረገው ድንገተኛ ፍተሻያገኛቸውን ሰነዶች ለጉዳዩ አግባብነት ኦዲት በማድረግ በደረሰበት ውጤት መሠረት እና በቀን ገቢ ግምት መሠረት ለዘጉት የሀገር ውስጥ ችርቻሮ ንግዳቸው ያላሳወቁት ገቢ መኖሩ ተደርሶበት ከ2003 ዓ.ም እስከ 2007 ዓ.ም ድረስ ላሉት የግብር ዘመናት ያቀረቧቸው የሂሳብ መዝገቦችን አስተካክሎ ተጨማሪ ግብር የወሰነ መሆኑን፤ የግብር ሰብሳቢው መስሪያ ቤት በአመልካች ድርጅት በአካል በመገኘት ንግድ ባካሄዱባቸው ወቅት ያዘጋጇቸው ማስታወሻ ደብተሮች ያገኘ መሆኑን፤ አመልካች ሰነዶቹ የባለቤታቸው ለመሆኑ ምንም ዓይነት ማስረጃ ያላቀረቡ መሆኑን፤ በተቃራኒው ደብተሮቹ የተገኙት በድርጅታቸው ውስጥ ከመሆኑም በላይ በውስጣቸው የያዙት መረጃ አመልካች ስለሚሸጡት የመኪና ጌጣጌጥ ዕቃዎች ዓይነት እና ዝርዝር ዋጋ ዕቃዎቹ ለማን እንደተሸጡ በቅድሚያስለተፈጸሙ ክፍያዎች እና ስለቀሪ ክፍያዎች የሚሳዩ መረጃዎች መሆናቸውን፤ በሚስጥር ከተደረገው የብርበራ ቀን በኋላ አመልካችን ጨምሮ በተመሳሳይ ንግድ ላይ የተሰማሩ 15 ግብር ከፋዮች አየር ባየር ንግድ እንደሚያከናውኑ እና ምንጩ ያልታወቀ ሐብት እንደሚያንቀሳቅሱ በጥናት የተደረሰበት መሆኑን እና ማስታወሻዎቹ ለአመልካች ተሰጥተው የራሳቸው የሆኑትን አራት ደብተሮች የለዩ እና ማሕተም ያሳረፉበት መሆኑን በመግለጽ የአመልካች አቤቱታ ውድቅ ሊደረግ ይገባል በማለት ተከራክሯል፡፡

የግብር ይግባኝ ሰሚው ጉባኤ የግራቀኙን ክርክር እና ማስረጃ ከመረመረ በኋላ ተጠሪ አመልካችዋ ገቢ ደብቀዋል በማለት ግብር እና ታክስን ለመወሰን የተጠቀመው እና መነሻ ያደረገው የአመልካች ናቸው የተባሉትን አራት ማስታወሻ ደብተሮች የአመልካች መሆኑን በመጥቀስ ነው፤ በግብር አወሳሰን ስርዓት ውስጥ የታክስ ስወራን ለመከላከል እንደመረጃ የሚወስድበት አግባብ ግብር ከፋዮች በየእለቱ የሚያከናውኑትን የዕለት ከዕለት ሽያጭ በግል ማስታወሻም ሆነ በሌሎች አማራጭ ሂሳባቸውን የሚከታተሉበት እና የሚያውቁበት እንዲሁም ሌሎች የግል ጉዳዮችንም የሚያዝበት ሁኔታ ሊሆን እንደሚችል ታሳቢ ሊደረግ የሚገባ ከመሆን ባለፈ የተደበቀ ገቢ መሆኑን የሚያሳይ ሰነድ የመሆን ብቃት ሊኖረው እና ፍትሐዊ የአወሳሰን ዘዴ መሆኑን በአግባቡ ማረጋገጥን የሚጠይቅ ነው፤ በግል ማስታወሻ ደብተር ከተጠቀሰው ገንዘብ መጠን ውስጥ በሀሰተኛ ደረሰኝ ግብይት የተፈጸመበት ግኝት ወይም ያለደረሰኝ የዱቤ ሽያጭ ወይም የእጅ በእጅ ሽያጭ የተሸጠ መሆኑን ለማረጋገጥ የሚያስችል የሚያሳይ ውጤት በሌለበት የግል ማስታወሻ ላይ የተጻፈውን የተለያየ ይዘት ያላቸውን ሁኔታዎች ብቻ በመውሰድ ግብር እና ታክስ እንዲወሰን መደረጉ አመልካች በየዓመቱ ካሳዩት እና

ካሳወቁት የገቢ ዕድገት አንጻር የሚጣጣም እና ፍትሐዊ ሆኖ አልተገኘም፤ አመልካች በደረሰኝ ግብይት አለማከናወናቸውን የሚያሳይ ተጨባጭ ግኝት ስለመኖሩም አብሮ ሊታይ ይገባል፤ የግል ማስታወሻ መያዝ የተለመደ የግል ጉዳይ ከመሆኑ አንጻር በግብር ከፋዮች ዘንድ የእጅ ማስታወሻ ከተገኘ ግብር ይጣልብኛል የሚል ስጋት ወደ መፍጠር የሚያመዝን ከመሆን በዘለለ በትክክለኛ ግኝት ላይ የተመሰረተ ሕጋዊ ውሳኔ ለመስጠት የሚያረጋግጥ ማስታወሻ አይደለም በማለት ይህንኑ መሠረት ተደርጎ የተሰጠውን የግብር ውሳኔ ሽሮታል፡፡

የአሁን ተጠሪ ይህን ውሳኔ በመቃወም ለአዲአበባ ከተማ ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት የይግባኝ አቤቱታ ያቀረበ ቢሆንም ይግባኙ የቀረበለት ፍ/ቤት ግራቀኙን ካከራከረ በኋላ የግብር ይግባኝ ሰሚው ጉባኤ የሰጠውን ውሳኔ አጽንቷል፡፡

ተጠሪ በመቀጠል ለአዲስአበባ ከተማ ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የሰበር አቤቱታ አቅርቧል፡፡ አቤቱታው የቀረበለት ፍ/ቤት ግራቀኙን ካከራከረ በኋላ የባለስልጣኑ መስሪያ ቤት የኢንተሊጀንስ ዳይሬክቶሬት በአካባቢው ተመሣሣይ የንግድ ስራ ላይ የተሰማሩ ነጋዴዎችን የንግድ ድርጅት ላይ ባደረገው ድንገተኛ ብርበራ ለክርክሩ መነሻ የሆኑትን የግል ሰነዶች ከአመልካች የንግድ ድርጅት ስለመገኘታቸው እና እነዚህም ሰነዶች የአመልካች ስለመሆናቸው የግብር ይግባኝ ሰሚው ጉባኤ ተቀብሎ እነዚህ ሰነዶች የግል ሰነዶች በመሆናቸው ተጠሪ በእነዚህ የግል ሰነዶቸ ብቻ ገቢን ደብቀዋል ለማለት የማይቻል እና የተጠሪን ገቢ በየዓመቱ የ26% ዕድገት ያሳየ በመሆኑ በእጅ ጽሑፍ በግል ማስታወሻ ደብተር ላይ የተጻፈን የቁጥር ጽሑፍ ብቻ እንደገቢ በመውሰድ ተጨማሪ ግብር መወሰኑ አግባብ አይደለም በማለት ነው፤ ይሁን እንጂ የተጠሪ ጽ/ቤት በእነዚህ የተጠሪ የግል ማስታወሻዎች ላይ ተመስርቶ ተጨማሪ ግብሩን የወሰነው በጥናት ላይ ተመስርቶ እና እነዚህ ሰነዶች ተጠሪ ከሚነግዱበት ንግድ ጋር በቀጥታ የተገናኘ እና በሒሳብ አዋቂ ተረጋግጦ እና ማስረጃ ቀርቦ በመሆኑ የግብር ይግባኝ ሰሚው ጉባኤ የሰጠው ውሳኔ የገቢ ግብር አዋጅን አንቀጽ 38/2/ሀ እና 66/5 እንዲሁም የፍ/ብ/ህ/ቁ 1677/1፤2017 እና 2018 ያላገናዘብ እና መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት ነው በማለት የግብር ይግባኝ ሰሚው ጉባኤ እና የስር ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤቱ የሰጠውን ውሳኔ በመሻር የተጠሪ ጽ/ቤት በቁጥር 29-4-1/2685/08 በቀን 26/08/08 ዓ.ም ለአመልካች ወስኖ የሰጣቸው ተጨማሪ የንግድ ትርፍ ግብር ፍሬግብር ወለድ እና መቀጫን ጨምሮ እና የተጨማሪ እሴት ታክሱን ፍሬግብሩን ወለድ እና መቀጫውን ጨምሮ የተሰጣቸውን የግብር ውሳኔ ማስታወቂያ በማጽናት ወስኗል፡፡

የሰበር አቤቱታው የቀረበው ይህን ውሳኔ በመቃወም መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስሕተት ተፈጽሞበታል በሚል ሲሆን ይዘቱም፡- የአዲስአበባ ከተማ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት የተፈጸመን የሕግ ስሕተት ማረም እንጂ ማስረጃን የመመዘን ስልጣን የለውም፤ በብርበራ የተገኙት ሰነዶች የአመልካች አለመሆናቸውን ለጉባኤው ማስረጃ አቅርቤአለሁ፤ ጉባኤውም ደብተሮቹ

የአመልካች ናቸው አላለም፤ ደብተሮቹ የአመልካች ናቸው ባልተባለበት ሁኔታ የአመልካች እንደሆኑ ተደርጎ የተሰጠው ውሳኔ ተገቢ አይደለም፤ አመልካች ያላሳወቅኩት ወይም የደበቅኩት ገቢ የለም፤ የሒሳብ መዝገቤ ተቀባይነት አግኝቶ ግብር እና ታክሱ ስለመወሰኑ ባለስልጣን መስሪያ ቤቱ አልካደም፤ ከ2003 ዓ.ም እስከ 2007 ዓ.ም ድረስ ባለው የግብር ዘመን ዓመታዊ ገቢዬ እየጨመረ የሄደበት ሁኔታ እንጂ አመልካች የቀነስኩት ገቢ እንዳለ በተጨባጭ የሚያረጋግጥ ማስረጃ ባልቀረበበት ሁኔታ የአዲስአበባ ከተማ ሰበር ሰሚ ችሎት ሰነዱ የአመልካች መሆኑ ተረጋግጧል በማለት የግብር ይግባኝ ሰሚው ጉባኤ እና የስር ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት የሰጡትን ውሳኔ በመሻር የሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ሥሕተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል የሚል ነው፡፡

የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ አመልካች ገቢያቸውን አሳውቀው ሳለ ከድርጅታቸው ተገኘ የተባለውን የግል ማስታወሻ ከሚደረገው ግብይት ግንኙነት አለው ተብሎ ግብር እንዲከፍሉ የመደረጉን አግባብነት ከግብር አዋጅ ቁጥር 286/94 አንቀጽ 38 እና 66/5 ጋር በማገናዘብ ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ በዚህ ችሎት እንዲታይ ተደርጓል፡፡ ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎም ግራቀኙ በጽሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

የተጠሪ መልስ ይዘት በአጭሩ ደብተሮቹ የአመልካች መሆናቸውን ጉባኤው ባረጋገጠበት ሁኔታ የንግድ እንቅስቃሴአቸውን በሚያሳዩት በእነዚሁ ደብተሮች ላይ ተመርኩዘን በኦዲት የወሰነው ተጨማሪ ግብር በሕጉ አግባብ በመሆኑ እና ተጠሪ አጥብቆ የሚከራከርበት የግብር ታክስ አሰራር ስርዓት መከበር ጉዳይ በመሆኑ የአዲስአበባ ከተማ አስተዳደር ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የሰጠው ውሳኔ ሊጸና ይገባል የሚል ነው፡፡ አመልካችም የሰበር አቤቱታቸውን በማጠናከር የመልስ መልስ ሰጥተዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ በአጭሩ ከላይ የተገለጸው ነው፡፡ ይህ ችሎትም የግራቀኙን ክርክር ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸው ሕጎች እና በሰበር አጣሪው ችሎት ሊጣራ ይገባል ተብሎ ከተያዘው ነጥብ ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው መርምረነዋል፡፡

ተጠሪው መስሪያ ቤት ከ2003 ዓ.ም እስከ 2007 ዓ.ም ድረስ ላሉት የግብር ዘመናት አመልካች ያቀረቧቸው የሂሳብ መዝገቦችን መርምሮ እና አስተካክሎ ተጨማሪ ግብር ሊወስን የቻለው አመልካች እና ሌሎች በአካባቢው በተመሳሳይ የንግድ ስራ ላይ የተሰማሩ ግብር ከፋዮች አየር በአየር ግብይት እንደሚያከናውኑ በተደረገው ጥናት በግብር ከፋይዋ ድርጅት በአካል በመገኘት ባደረገው ፍተሻ ንግድ ባካሄዱባቸው ወቅት ያዘጋጇቸው ማስታወሻ ደብተሮች አግኝቻለሁ፤ አመልካች ሰነዶቹን ለይተው ማሕተም አሳርፈውበታል፤ ሰነዶቹ አመልካች ስለሚሸጡት የመኪና ጌጣጌጥ ዕቃዎች ዓይነት እና ዝርዝር ዋጋ ዕቃዎቹ ለማን እንደተሸጡ በቅድሚያ ስለተፈጸመ ክፍያዎች እና ስለቀሪ ክፍያዎች የሚሳዩ መረጃዎች ናቸው በሚል መሆኑን፤ አመልካች በበኩላቸውም ባለስልጣን መስሪያ ቤቱ በተጨማሪ ያሳወቃውን የግብር ውሳኔ ልከፍል አይገባም በማለት የሚከራከሩት በብርበራ የተገኙት ሰነዶች

የአመልካች አይደሉም፤ አመልካች የደበቅኩትም ሆኖ ያላሳወቅቱም ገቢ የለም በሚል መሆኑን፤ የግብር ይግባኝ ሰሚው ጉባኤው አመልካች ባለስልጣን መስሪያ ቤቱ በተጨማሪ እንዲከፍሉ ያሳወቃቸውን የግብር ውሳኔ ሊከፍሉ አይገባም ከሚል መደምደሚያ ላይ የደረሰው ሰነዱ የተደበቀ ገቢ መኖሩን የሚያሳይ ሰነድ የመሆን ብቃት የለውም፤ በግል ማስታወሻ ደብተር ከተጠቀሰው ገንዘብ መጠን ውስጥ በሀሰተኛ ደረሰኝ ግብይት የተፈጸመበት ግኝት ወይም ያለደረሰኝ የዱቤ ሽያጭ ወይም የእጅ በእጅ ሽያጭ የተሸጠ መሆኑን ለማረጋገጥ የሚያስችል የሚያሳይ ውጤት በሌለበት የግል ማስታወሻ ላይ የተጻፈውን የተለያየ ይዘት ያላቸውን ሁኔታዎች ብቻ በመውሰድ ግብር እና ታክስ እንዲወሰን መደረጉ አመልካች በየዓመቱ ካሳዩት እና ካሳወቁት የገቢ ዕድገት አንጻር የሚጣጣም እና ፍትሐዊ ሆኖ አልተገኘም በሚል መሆኑን፤ ጉዳዩን በሰበር የተመለከተው የስር ፍ/ቤትም ሰነዶቹ የአመልካች የግል ሰነዶች መሆናቸው ጉባኤው ተቀብሎታል፤ የተጠሪ ጽ/ቤት በእነዚህ የተጠሪ የግል ማስታወሻዎች ላይ ተመስርቶ ተጨማሪ ግብሩን የወሰነው በጥናት ላይ ተመስርቶ እና እነዚህ ሰነዶች ተጠሪ ከሚነግዱበት ንግድ ጋር በቀጥታ የተገናኘ እና በሒሳብ አዋቂ ተረጋግጦ እና ማስረጃ ቀርቦለት በመሆኑ አመልካች የተጠየቁትን ተጨማሪ ግብር ሊከፍሉ ይገባል ከሚል መደምደሚያ ላይ የደረሰ መሆኑን ከክርክሩ ሒደት መገንዘብ ችለናል፡፡

የገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 286/94 አንቀጽ 38/2 ድንጋጌ እንደሚያመለክተው በማንኛውም ሌላ ሕግ ውስጥ ተቃራኒ የሆኑ ድንጋጌዎች ቢኖሩም የግብር አስገቢው ባለስልጣን በማንኛውም ጊዜ በግብር ከፋይ የቀረቡ ማንኛውንም መግለጫዎች ሰነዶች እና የሂሳብ መዝገቦች ለማረጋገጥ ሕጋዊ ሥልጣን የተሰጣቸው ተቆጣጣሪዎችን ወደ ግብር ከፋዩ የንግድ ወይም የሙያ ስራ ቦታ በመላክ ገቢ እና ወጪን የሚያሳዩ ሰነዶችን፤ ለንግድ የተከማቹ ዕቃዎችን፤ ሌሎች ዕቃዎችን፤ ወይም የሒሳብ መዛግብትን እና ሰነዶችን ለማመሳከር እና ለመመርመር እንደሚችል ይደነግጋል፡፡ የዚሁ አዋጅ አንቀጽ 66/5 በገቢ ማስታወቂያው ላይ የተመለከተው እና በዘመኑ መከፈል ያለበት ግብር፤ በግብር አስገቢው ባለስልጣን የተወሰነው ግብር ሆኖ ይቆጠራል፤ ሆኖም የግብር አስገቢው ባለስልጣን ስህተት ወይም ያልተካተተ ገቢ ያለ መሆኑን ያረጋገጠ እንደሆነ ውሳኔውን በዚያው መጠን በማሻሻል የግብር ውሳኔ ማስታወቂያ ይሰጣል በማለት ይደነግጋል፡፡

በያዝነውም ጉዳይ አመልካች ከ2003 እስከ 2007 ዓ.ም ያቀረቡትን የሂሳብ ሰነዶች በመመርመር ከአመልካች ግብይት ጋር በማገናዘብ ያላሳወቁት ገቢ አለ በሚል ግምት በአመልካች ድርጅት በመገኘት ንግድ ባካሄዱበት ወቅት ያዘጋጃቸውን ማስታወሻዎች በንግድ ድርጅቱ ውስጥ ማግኘታቸውን ይኸው አመልካች ስለሚሸጡት የመኪና ጌጣጌጥ ዕቃዎች፤ ለማን እንዴት እንደተሸጠና ክፍያን የተመለከተ መሆኑን እና የተገኙት ማስታወሻዎችም ከአመልካች ስለመሆኑ በድርጅቱ እንዲረጋገጥ ካደረጉ በኋላ ተጨማሪ ግብር የተወሰነ መሆኑን ነው፡፡ ይህ ደግሞ በአዋጅ 286/94 አንቀጽ 38 እና 66/1/ የተመለከተ ነው፡፡በዚህም መሰረት ተጠሪ ይህንኑ በአዋጁ በተመለከተው መሰረት በማድረግ አመልካች ገቢውን በየጊዜው እያሳወቀ ግብሩን እየከፈለ መሆኑ ብቻ በቂ አይደለም ብሎ በማመመኑና እነዚህን

ሠነዶች እና የሂሳብ መዝገብ በማናቸውም ጊዜ ለመመርመርና ለማረጋገጥ የሚችል በመሆኑ በአመልካች የተገኙትን የግብይት ማስታወቀሻዎች በተጠሪ ባለሙያዎች ተመርምረው ተጨማሪ ግብር መወሰኑ የገቢ ግብር አዋጁን መሠረት ያደረገ ነው ከሚባል በቀር መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ነው ለማለት አልተቻለም ፡፡ በዚህ መሠረት ተከታዩን ውሳኔ ሠጥተናል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአዲስ አበባ ከተማ ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ 27532 ታሕሳስ 19 ቀን 2010 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 348/1 መሠረት ጸንቷል፡፡
2. አመልካችና ተጠሪ በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር ያወጡትን ወጪ የየራሣቸውን ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ብ/ግ

የሰ/መ/ቁ 161867
ሚያዚያ 25 ቀን 2011 ዓ.ም.

**ዳኞች፡-**ብርሃኑ አመነው

በዕውቀት በላይ

እንዳሻዉ አዳነ

ሃይሉ ነጋሽ

እትመት አሠፋ

**አመልካች** :-የኢትዮጵያ ገቢዎች ጉምሩክ ባለሥልጣን

**ተጠሪ** ፡-ሱፐር ማክስ ኦብቲካል ሚዲያ ኃላ/የተ/የግ/ማህበር

መዝገቡ የተቀጠረው መርምሮ ፍርድ ለመስጠት ነው፡፡ በመሆኑም መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

ይህ የሰበር አቤቱታ ሊቀርብ የቻለው አመልካች ሐምሌ 24 ቀን 2010 ዓ.ም በተጻፈ አቤቱታ የፌደራል ግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባዔ በመ/ቁ ከሱ-1019 ነሐሴ 17 ቀን 2008 ዓ.ም የሰጠውን ውሳኔ የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 185869 በቀን 04/07/2010 እንዲሁም የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 155956 በቀን 24/08/2010 ዓ.ም በማጽናታቸው መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመ በመሆኑ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለታቸው ነው፡፡

ጉዳዩ የንግድ ትርፍ ግብርን የሚመለከት ነው፡፡ ተጠሪ በ21/02/2007 ዓ.ም የደረሰውን የ2010 ዓ.ም የግብር ዘመን የንግድ ትርፍ ግብር በመቃወም ለአቤቱታ አጣሪ ኮሚቴ ቢያቀርብም ተቀባይነት ባለማግኘቱ ለግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባዔ ያቀረበው ይግባኝ ይዘት ድርጅቱ በኤሌክትሮኒክስ ነክ አታሚነት ዘርፍ ሐምሌ 16/2000 በተሰጠው ፈቃድ ሲዲ እና ዲቪዲ፤ ኦዲዮ ቪዲዮ እና ተያያዥ ምርቶችን የሚያመርት መሆኑን፤ ለዚሁ ተግባር በኢንቨስትመንት ማበረታቻው በመጠቀም የማምረቻ ማሽን ዕቃዎችን ያስገባ መሆኑን፤ በዚህም ለ2000 ዓ.ም በጀት ዓመት ቀሪው 14 ቀን ቢሆንም የ2000 ዓ.ም የሐብትና ዕዳ መግለጫ ለግብር አስገቢው መ/ቤት አሳውቋል፤ ሆኖም በዚህ ዘመን ንግድ ፈቃድ የወሰደበት እንጂ የንግድ ሥራ እንቅስቃሴ ማምረትና መሸጥ ያልተጀመረበት ሆኖ ሳለ የሐብትና ዕዳ መግለጫ ሲዘጋጅ ለምስረታና ማሽነሪ ግዢ የወጡትን ወጪዎች በበጀት ዓመቱ የደረሰ ኪሳራ እንደሆነ የሚያሳይ ሰነድ ቀርቧል፤ ግብይት ባልተደረገበት በጀት ዓመት ሊታይ እና ሊያዝ የሚችል ኪሳራ

አለመኖሩ የሚታወቅ በመሆኑ በ2001 በበጀት ዓመት ላይ ሊያዝ የሚገባ በመሆኑ ማስተካከያ እንዲደረግ ለግብር አስገቢው ባለሥልጣን አሳውቀናል፣ በ2001 እና በ2002 በጀት ዓመት ኪሳራ የታየ እና በ2003 ትርፍ ማስመዝገብ የጀመርን መሆኑ የተረጋገጠ ሆኖ አመልካች በ21/07/07 በተጻፈ የንግድ ትርፍ ግብር ማስታወቂያ በ2002 ዓ.ም ግብር የሚከፍልበት ትርፍ አለ በማለት ግብር ፤ወለድና መቀጫ በማስላት በድምሩ ብር 824317.41 እንድንከፍል በግብር ውሳኔ አሳውቆናል ስለሆነም በ2000 በጀት ዓመት ኪሳራ ተብሎ የቀረበው በ2001 በቀረበው የሂሳብ ሰነድ የተስተካከለ በመሆኑና ኪሳራ ደርሶበታል የሚባለው ማምረት እና ግብይት መፈፀም ከጀመረ ጊዜ ጀምሮ በመሆኑ ኪሳራው የደረሰው በ2001 ዓ.ም ይባልልን፣ በአዋጅ ቁጥር 286/94 አንቀጽ 28/1/ መሠረት ኪሳራው ለሶስት ተከታታይ ዓመት የሚሸጋገር በመሆኑ በ2002 የግብር ዘመን ኪሳራ አለመድረሱ በሒሳብ በባለሙያ ተረጋግጦ ቀርቦ ኪሳራ የለም በ2001፤ የደረሰውም ኪሳራ ወደ 2002 ማሸጋገር አትችሉም ተብሎ አቤቱታው ውድቅ የተደረገው ይሻርልኝ የሚል ነው፡፡

አመልካች በሰጠው መልስም ግብር ከፋዩ የሚያቀርበው መረጃ በግብር ህጉ በደንብ እና በመመሪያ መሠረት መሆን የሚጠበቅበት በ2000 ዓ.ም ግብይት መፈፀም አልጀመርኩም ይበል እንጂ እንደጀመረ አረጋግጠናል፣ ለዘመኑ ኪሳራ ተብሎ የተገለፀው በእርጅና ቅናሽ ላይ መቀነስ የነበረበት ገንዘብ መጠን ነው፣ ማስተካከያ ቀርቧል ይበል እንጂ አልቀረበም፣ በአዋጅ ቁጥር 286/94 አንቀጽ 28/1/ እና /3/ ኪሳራ ሊሸጋገር የሚችልበትንና ሁኔታና ጊዜ የተደነገገ ሲሆን በደንብ ቁጥር 78/94 አንቀጽ 12 ደግሞ ኪሳራው ሊሸጋገር የሚችለው በግብር ባለሥልጣኑ ኦዲት ተደርጐ ተቀባይነት ሲያገኝ ወይም በውጭ ኦዲተር የተመረመረ ሂሳብ ሲቀርብ በመሆኑ ተጠሪ የ2000 ግብር ዘመን የሂሳብ መዝገቡ በባለሥልጣኑ ኦዲተር ስላልተረጋገጠ ያልተያዘላቸው ሲሆን የ2001 ኪሳራ ግን በውጭ ኦዲተር የተረጋገጠ በመሆኑ በባለሥልጣኑ ባይረጋገጥም በውጭ ኦዲተር የተረጋገጠ በመሆኑ ኪሳራው ተይዞለት በ2003 ካገኘው ትርፍ ተካክሶ ግብር የተወሰነ በመሆኑ ተጠሪ እንደሚለው አይደለም፤ ይህም የተጠሪ ጥያቄ እርስ በርሱ የሚጋጭ ነው፤ ኪሳራ የሚሸጋገረው ወደ ተገኘበት የግብር ዘመን ነው፡፡ ስለሆነም ውሳኔው ተገቢ በመሆኑ ይጽናልኝ፣ ተጠሪ በ2000፣ በ2001፣ በ2002 የግብር ዘመን ኪሳራ ያሳወቀ በመሆኑ በተጠቀሰው አንቀጽ መሠረት የ2002 ኪሳራ ሊሸጋገር አይችልም ብሏል፡፡

የግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባዔው የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ ተጠሪ በ2000 ዓ.ም የምስረታ ወጪን በስህተት የኪሳራ ማሳወቂያ ላይ በመሙላት የተፈጠረውን ስህተት ማረሚያ የሚሆን የ2001 ዓ.ም የሐብትና ዕዳ መግለጫ ላይ ማስተካከያ አቅርቤያለው በሚለው ላይ የሂሳብ መግለጫው በድጋሚ ታይተው እንዲቀርቡ ለተከራካሪዎች ታዞ የአሞላል ስህተቱ የማስተካከያ እርምጃ ተጠሪ የወሰደ መሆኑን፣ መቼ የሚለውም የቀረበው ማስተካከያ ላይ ሲታይ በ2001 ዓ.ም የሐብት እና ዕዳ ማሳወቂያ ላይ እንደሆነ ጉባዔው የተገነዘበ መሆኑን ገልጾ የ2000 ዓ.ም ኪሳራን በስህተት ማሳወቁን ከቀረበው ሰነዶች እና ተፈፀመ የተባለው ስህተት ማስተካከያ ማቅረቡም በግራ ቀኙ የተረጋገጠ፤ በ2000 ዓ.ም

ኪሳራ ደርሷል ተብሎ የተያዘው በስህተት እንደሆነ በጉባዔው የተረጋገጠ በመሆኑ ኪሳራው የደረሰው በ2001 እና በ2002 ዓ.ም በመሆኑ በዚሁ አግባብ የግብር ኃላፊነት ተስተካክሎ እንዲሰላ ጉባዔው በማለት ወስኗል፡፡

አመልካች በዚህ ፍርድ ቅር በመሰኘት ያቀረበውን ይግባኝ የተመለከተው የፌደራሉ ከፍተኛ ፍ/ቤት ግራ ቀኙን አስቀርቦ ከሰማና ከመረመረ በኋላ የግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባዔውን ውሳኔ ሲያፀናው የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤትም በይግባኝ ቀርቦ ተጠሪን መጥራት ሳያስፈልገው በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 337 መሠረት ይግባኙን ዘግቷል፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ በመቃወም ነው፡፡

የአመልካች የሰበር አቤቱታ ይዘትም የግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባዔ በ2000 ዓ.ም ኪሳራ በስህተት ለአመልካች ያሳወቀ ስለመሆኑ ከቀረቡት ሰነዶች ጉባዔው የተረዳ መሆኑን የገለፀ ቢሆንም በአንድ የግብር ዘመን የቀረበ ሂሳብ መዝገብ ስህተት ካለበት ማስተካከያ መቅረብ ያለበት በቀጣዩ የግብር ዘመን ሆኖ ተቀባይነት የሚያገኘውም ግብር የሚከፈልበት ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ሲያጸድቀው እና ማስተካከያ ሲሰጥበት ነው ተጠሪ ይህንን አላስረዳም፣ ማስተካከያውም መቅረብ ያለበት በ2001 ማሳወቅ የነበረበት በመሆኑ አያገለግልም፤ የቀረቡትን ማስረጃዎች በሚገባ አልተመዘኑም፤ በይግባኝ የተመለከተው ፍርድ ቤትም በተከራካሪዎች ወገኖች ያልተነሳን የንግድ ፈቃድ መኖርና ማረጋገጥ ጉዳይ ላይ ውሳኔ ሠጥቷል፤ በ2000 ኪሳራ ተደርጐ የቀረበው የሂሳብ መግለጫ የእርጅና ቅናሽ ተብሎ ለአመልካች ያሳወቀ ስለመሆኑ የፍሬ ነገር ክርክሩን በሚያጣራው አካል የተረጋገጠ ነው በማለት ውሳኔ የሰጠ ቢሆንም የምስራቅ ቅርንጫፍ የግብር አወሳሰን አሰባሰብ እና ክትትል የሥራ ሂደት የሂሳብ መዝገቡ ላይ ምንም ማስተካከያ እንዳልቀረበ አረጋግጧል፣ ስለሆነም ለጉባዔው ተጣርቷል የተባለበት ስህተት በመሆኑ ይታረምልኝ የሚል ነው፡፡

የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ በስር ፍ/ቤት የተሰጠውን ውሳኔ ከግብር አዋጁ 286/94 አንቀጽ 28/1/ አንጻር ለመመርመር ተጠሪ ቀርቦ መልስ እንዲሰጥ በታዘዘው መሠረት በሰጠው መልሱ በ2000 ዓ.ም ድርጅቱ ገና የንግድ ሥራውን ለመጀመር ቅድመ ዝግጅት ሂደት ላይ የቆየበት ጊዜ በመሆኑ በሐብትና ዕዳ ማሳያ ላይ ኪሳራ በመገለጹ እና በተግባር ኪሳራ ሳይደርስ አመልካች የወሰደ ቢሆንም በ2001 የሀብትና ዕዳ መግለጫ ላይ ተስተካክሎ እንዲቀርብ ተደርጓል፣ ይህ በጉባዔውም ተረጋግጧል ተወስኗል፤ በሂሳብ አያያዝ ረገድ የተፈፀሙ ስህተቶች ደግሞ የፍሬ ነገር ክርክር እንጂ የህግ ጉዳይ ባለመሆኑ በአዋጅ 286/94 አንቀጽ 112/1/ እና በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 320/1/ መሠረት ይግባኙ የሚፈቀድ አይደለም፡፡ ተጠሪ ስህተቱን በቀጣዩ የግብር ዘመን በ2001 አሳውቀናል፡፡ ስለሆነም በአዋጁ አንቀጽ 28 መሠረት እንድንስተናገድ የሶስት የግብር ዘመን ኪሳራ አልተጠየቀም ፤የክርክሩም ጭብጥ አይደለም፤ ጉባዔው በስህተት የቀረበውም አጣርቶ በሁለቱም ተከራካሪ ወገኖች እና ሰነዶች ጭምር የተረጋገጠ በመሆኑ የተሰጠ ውሳኔ ነው ፤ይግባኝ ሰሚው ፌ/ከ/ፍ/ቤት ይህንኑ ነው ያፀናው ስለሆነም

ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤቱም በጽሁፍና በቃል በነበረው ክርክር ድርጅቱ ኪሳራ ሊደርስበት የሚችለውን የንግድ ሥራ ቁመና የነበረውን በማረጋገጥ የተሰጠ እንጂ አንደ አዲስ ጭብጥ ተይዞ የተወሰነ አይደለም፣ ተጠሪ በ2000 ዓ.ም የተፈጠረውን ስህተት እንደተረዳ በ2001 የሂሳብ መግለጫ ላይ ማስተካከያ አሳውቀናል ማስረጃውም ለሥር ፍ/ቤት የቀረበ እንጂ በ2002 የቀረበ አይደለም ማስተካከያው ዘገየ በሚል ምክንያት የግብር ኃላፊነት መጣል ተቀባይነት ያለው አይደለም፤ የከፍተኛው ፍ/ቤት የሰጠው ውሳኔ የፍሬ ነገርን የማጣራት ሥልጣን የጉባዔው ነው በማለት የሰጠው እንጂ የከፍተኛው ፍ/ቤት ሥልጣን የለውም አላለም፡፡ ስለሆነም የስር ፍ/ቤት ውሳኔ ሊጸና ይገባል ብሏል፡፡ አመልካችም አቤቱታውን በማጠናከር የመልስ መልሱን አቅርቧል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ከላይ የተመለከተው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው ሲቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አንጻር አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩን በሚከተለው መልኩ መርምሯል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የሚቻለው ተጠሪ በኤሌክትሮኒክስ ነክ አታሚነት ዘርፍ ሐምሌ 16 ቀን 2000 ዓ.ም ፈቃድ የወሰደ መሆኑንና በዚሁ ዘመን የንግድ ሥራ እንቅስቃሴ ያልጀመረበት ቢሆንም የ2000 በጀት ዓመት የሀብትና ዕዳ መግለጫ ሲዘጋጅ የካፖታል ዕቃዎች እና የእርጅና ቅናሽ ተቀናናሽ መሞላት ካለበት ፎርም ኪሳራ ማሳወቂያ ላይ የተላለፈና ስህተት በ2001 የድርጅቱ ሂሳብ መግለጫ ማሳወቁን ይህም በግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባዔውም መረጋገጡን በተጨማሪም በሰነዶች እና በግራ ቀኙ መረጋገጡን ስለሆነም የ2001 የደረሰው ኪሳራ ታስቦ ወደ 2002 የግብር ዘመን ሊሸጋገር የሚገባ በመሆኑ ይኸው ተሰልቶ ግብሩ እንዲወሰን የሚጠይቅ መሆኑን ነው፡፡

በመሠረታዊነት በንግድ የግብር ዘመን የደረሰ ኪሳራ ሊሸጋገር የሚችለው በአዋጅ ቁጥር 286/94 አንቀጽ 28/1/ እና /3/ እንደተመለከተው ከሚቀጥሉት ሶስት የግብረ ዘመናት ውስጥ የሚገኝ ግብር የሚከፈልበት ገቢ ላይ መጀመሪያ ያጋጠመው ኪሳራ በኋላ ካጋጠመው አስቀድሞ በማካካስ ሊሸጋገር የሚችል እና ይህም በማናቸውም ሁኔታ ከሁለት ሶስት ዓመታት ከሚቆጠሩ ስድስት ዓመታት በላይ ሊሸጋገርና ሊቀናነስ እንደማይችል እና በደንብ ቁጥር 78/1994 እንደተሻሻለው አንቀጽ 12 መሠረት የግብር ከፋዩ ኪሳራ ሊሸጋገር የሚችለው በግብር ባለሥልጠኑ ኦዲት ተደርጐ ተቀባይነት ሲያገኝ ወይም በውጭ ኦዲተር የተመረመረ የሂሳብ መግለጫ ሲቀርብ ነው፡፡

በያዝነው ጉዳይ ተጠሪ የሂሳብ ሪፖርት በ2000፣ በ2001 እና 2002 የግብር ዘመን የሐብትና ዕዳውን ሲያሳውቅ የ2000 ዓ.ም የሐብትና ዕዳ መግለጫው ሲዘጋጅ ድርጅቱ ሐምሌ 16/2000 ዓ.ም የንግድ ፈቃዱን የወሰደ በመሆኑ የካፒታል ዕቃዎች እና የእርጅና ቅናሽ ተቀናናሽ መሙላት ሲገባው የኪሳራ ማሳወቂያ ፎርም መሙላትና ማስተላለፉን ይህንኑ ስህተት በ2001 ሂሳብ ላይ ያሳዩ መሆኑን፤ የግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባዔ ማስረጃዎችን በመመርመር መገንዘቡን፣ በተጨማሪም በተከራካሪ ወገኖች

የተረጋገጠ በመሆኑ በ2000 ኪሳራ ደርሳል ተብሎ የወሰደው ስህተት መሆኑን ማረጋገጡን ጉባዔው ፍሬ ነገሩንና ማስረጃዎችን በሚመዝን ጊዜ አረጋግጧል፡፡ በአዋጅ ቁጥር 286/1994 አንቀጽ 112/1/ መሠረት ደግሞ በጉባዔው በተሰጠ ውሳኔ ላይ በህግ ረገድ ስህተት ነው በማለት የሚቀርበው ብቻ ይግባኙ ሥልጣን ባለው ፍ/ቤት ቀርቦ የሚታይ በመሆኑና ይኸው ፍሬ ነገር እና ማስረጃ በመመዘን የተደረሰበት ድምዳሜ በፌደራል ከፍተኛ እና ጠቅላይ ፍርድ ቤትም የፀና በመሆኑ ይህ ችሎትም እንዳለ በመቀበል በህገ-መንግስቱ አንቀጽ 80/3/ እና አዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 10 መሠረት መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት የተባለውን ብቻ መርምረናል፡፡

በዚህ መሠረት ተጠሪ ኪሳራውን ያሳወቀው በ2001 ስለሚሆን ይኸው በ2001 በጀት ዓመት በተጠሪ የደረሰው ኪሳራ በአዋጅ ቁጥር 286/1994 አንቀጽ 28/1/ እና /3/ በሚቀጥሉት ሶስት የግብር ዘመናት ውስጥ በሚገኝ ግብር በሚከፈልበት ገቢ ላይ ያጋጠመው ኪሳራ በኂላ ካጋጠመው አስቀድሞ በሚካካስ የሚሸጋገር በመሆኑ በአመልካች ኦዲት ተደርጐ ተቀባይነት ካገኘ ወይም ተጠሪ በውጭ ኦዲተር የሂሳብ መግለጫው ያቀረበ ከሆነ ኪሳራው ሊሸጋገርለት የሚገባ ነው፡፡

በአጠቃላይ ተጠሪ በ2000 በጀት ዓመት ኪሳራ በስህተት ያሳወቀ ስለመሆኑና በ2000 ደርሷል የተባለው ኪሳራ በ2001 ዓ.ም ያሳወቀው መሆኑን በግብር ይግባኝ ሰሚው ጉባዔ በፍሬ ነገር እና ማስረጃ ምዘና ወቅት የተረገገጠ በመሆኑ ኪሳራው በሚቀጥለው ሁለት ሶስት ዓመት በማሸጋገር የንግድ ትርፍ ግብሩ ተሰልቶ እንዲወሰን በማለት በስር ፍቤቶች የሰጡት ውሳኔ አዋጅ ቁጥር 286/1994 አንቀጽ 28/1/ እና /3/ ፣ 112 እና ደንብ ቁጥር 78/1994 እንደተሻሻለው አንቀጽ 12 የተመለከተውን መሠረት ያደረገ በመሆኑ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ አልተገኘም፡፡ በዚህ መሠረት የሚከተለውን ውሳኔ ሠጥተናል፡፡

## <u>ውሳኔ</u>

1. የፌደራል ግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባዔ በመ/ቁ ከሱ-1019 ነሐሴ 17 ቀን 2008 ዓ.ም የሰጠውን እና በፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 185869 በቀን 04/07/2010 እንዲሁም በፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 155956 በቀን 24/08/2010 ዓ.ም የጸናው ውሳኔ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 348/1 መሰረት ጸንቷል፡፡

2. አመልካችና ተጠሪ በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር ያወጡትን ወጪና ኪሳራ ይቻቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት ፡፡

*ፅ/ወ*

የሰ/መ/ቁ.171943

ህዳር 26 ቀን 2012 ዓ.ም

ዳኞች፡- መዓዛ አሽናፊ

ሰለሞን አረዳ

እትመት አሰፋ

ጳውሎስ ኦርሺሶ

ፀሐይ መንክር

አመልካች፡- የፌዴራል ጠቅላይ ዐቃቤ ህግ - ቀረበ፡፡

ተጠሪ፡- ኪዳኔ ቶላ - የቀረበ የለም፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ ቀጥሎ ያለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ ለዚህ ሰበር ችሎት ሊቀርብ የቻለው የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በወንጀል ይግባኝ መዝገብ ቁጥር 161002 በቀን 12/04/2011 ዓ.ም በሰጠው የቅጣት ውሳኔ ላይ መሠረታዊ የህግ ስህተት ተፈጽሟል በማለት አመልካች እንዲታረምለት የካቲት 10 ቀን 2011 ዓ.ም የተጻፈ አቤቱታ በማቅረቡ ነው፡፡

የነገሩ አመጣጥ የወንጀል ጉዳይን የሚመለከት ነው፡፡የአሁን ተጠሪ በሥር ፍርድ ቤት 1ኛ ተከሳሽ የነበረ ሲሆን የአሁን አመልካች በአሁን ተጠሪ እና በሌሎች ሁለት ተከሳሾች ላይ የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የወንጀል ህግ አንቀጽ 32 (1) (ሀ) እና 539 (1)(ሀ) የተመለከተውን በመተላለፍ በሟች ሙሉጌታ ይመር ላይ ከባድ የሰው መግደል ወንጀል ፈጽሟል በማለት ክስ ያቀረበ ሲሆን የአሁን ተጠሪ ክዶ ተከራክሯል፡፡ የግራ ቀኙ ማስረጃዎች ከተሰሙ በኋላ ተጠሪ የዐቃቤ ህግን ክስና ማስረጃ አላስተባበለም ተብሎ በተከሰሰበት የህግ ድንጋጌ ሥር ከግብረ አባሮቹ ጋር የጥፋተኝት ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡ቅጣትን በተመለከተ በአሁን ተጠሪ ላይ የ18 ዓመት ከ6 ወር የጽኑ እስራት ቅጣት ተወስኖበታል፡፡

በዚህ የአሁን ተጠሪ ቅር ተሰኝቶ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ አቅርቧል፡፡የይግባኝ ሰሚው ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኙን ተቀብሎ የግራ ቀኙን ክርክር ካዳመጠ በኋላ ሟች በተጠሪ ላይ ጉዳት ቢያደርስም ተጠሪ ይህን ተከትሎ ብቀላ ከመፈጸም ይልቅ በህግ አግባብ ለህግ ማቅረብና መከታተል

ሲገባው በራሱ እርምጃ መውሰዱ የብቀላ ድርጊት መፈጸሙን የሚያሳይ ነው፡፡ ሆኖም ግን የደረሰበት ጉዳት የወንጀል ድርጊቱን ለመፈጸም ስሜት ቀስቃሽ መሆኑን መገንዘብ ይቻላል፡፡በዚህ ረገድም መልስ ሰጭ /የአሁን አመልካች/ ጉዳቱ በህክምና ከተረጋገጠበ ቅጣት ማቅለያነት ቢያዝ የሚደግፍ መሆኑን የገለጸ ሲሆን የጉዳቱን ደረጃ የህክምና ማስረጃውን ተክቶ  መገመት ባይቻልም ጉዳቱን መገንዘብ እስከተቻለ ድረስ ይኸው ምክንያት በቅጣት ማቅለያነት ሊያዝ የሚገባው ሆኖ አግኝተነዋል በዚህ ረገድም የሥር ፍርድ ቤት የቅጣት ውሳኔ መሻሻልና መቀነስ ያለበት ነው፡፡የቅጣት ማቅለያውን አያያዝ በተመለከተ በቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 2/2006 መሠረት ቢሰላ አንድ እርከን ብቻ የሚያስቀንስ በመሆኑና በዚህ ሁኔታ የሚቀነሰው ቅጣት ደግሞ ከእርከን 36 ላይ አንድ እርከን ተቀንሶ በእርከን 35 ፍቅደ ሥልጣን ከ16 ዓመት ከ6 ወር እስከ 19 ዓመት ከ6 ወር በሚያስቀጣው ሊቀጣ የሚችል በመሆኑና ይህም ከቅጣት ማቅለያው መሠረታዊነት አንጻር ሲታይ ከቅጣት አወሳሰን መመሪያው በመውጣት በቅጣት አወሳሰን መመሪያው አንቀጽ 27 (1) መሠረት ሊወሰን የሚገባው ነው፡፡በመሆኑም የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 0001008 ሚያዚያ 4 ቀን 2010 ዓ.ም ያስተላለፈው የ18 ዓመት ከ6 ወር ጽኑ እስራት የቅጣት ውሳኔ በወንጀለኛ መቅጫ ህግ ሥነ-ሥርዓት ቁጥር 195 (2) (ለ) (2) መሠረት ተሻሽሎና ተቀንሶ ይግባኝ ባይ /የአሁን ተጠሪ/ በዚህ ጉዳይ የታሰረው በሚታሰብ በ12 /አስራ ሁለት/ ዓመት ጽኑ እሥራት ሊቀጣ ይገባል ሲል ወስኗል፡፡

ይህ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም በቅጣት ላይ የተሰጠውን ውሳኔ ለማስቀየር ነው፡፡አመልካች የካቲት 10 ቀን 2011 ዓ.ም በተጻፈ አቤቱታ ዝርዝር የቅሬታ ነጥቦችን አቅርቧል፡፡የአቤቱታው ይዘትም በአጭሩ፡- የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ቅጣቱን ከቅጣት አወሳሰን መመሪያ ውጪ ሲወስን የጠቀሰው የተሻሻለውን የቅጣት አወሳሰን መመሪያውን አንቀጽ 27 (1) ሲሆን ይህ አንቀጽ ደግሞ ፍርድ ቤት ከቅጣት አወሳሰን መመሪያው ውጪ ቅጣት ሊወስን የሚችለው የወንጀሉ አፈጻጸምም ሆነ ባህሪው በመመሪያው መሠረት ቅጣትን መወሰን የወንጀል ህግ ዓላማ እና ግብ የማያሳካ ነው ብሎ ሲያምን እንደሆነ ተመልክቷል፡፡ በዚህ ጉዳይ ተጠሪ የወንጀል ድርጊቱን የፈጸመው በቂም በቀል መሆኑን እና ሟች ጉዳት አድርሶብኝ በዋስ ተለቀቀ በሚል ምክንያት ፍትህ በራሱ ለማስፈጸም ያደረገው መሆኑን እራሱ ይግባኝ ሰሚው ችሎት ያመነበት ስለመሆኑ በውሳኔው ላይ ያካተተው ከመሆኑ አንጻር የአካል ጉዳቱን እንደ አንድ ማቅለያ ከመያዝ ባለፈ ከመመሪያው ወጥቶ ቅጣት እንዲወስን የሚያደርግ አይደለም፡፡ከዚህ በተጨማሪ ቅጣቱን ከመመሪያው ውጪ ወጥቶ የወሰነበትን ምክንያት ፍርድ ቤቱ አላስቀመጠም፡፡ስለሆነም የመመሪያውን አንቀጽ በአግባቡ መተግበር ሲገባው ምክንያቱን በዝርዝር ሳያስቀምጥ በደፈናው ቅጣቱን ከመመሪያው ውጪ በማውጣት መወሰኑ መመሪያውን ያልተከተለ ነው፡፡በዚህም ምክንያት ውሳኔው መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ እንዲታረምልን እንጠይቃለን የሚል ነው፡፡

የሰበር አቤቱታው ተመርምሮ ተጠሪ በሥር ፍርድ ቤት የወንጀል ህግ ቁጥር 539 (1) (ሀ) በመተላለፍ ከባድ የግድያ ወንጀል መፈጸሙ ተረጋግጦ ጥፋተኛ በተባለበት ሁኔታ ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተው የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ተጠሪ ላይ የደረሰበት ጉዳት ወንጀሉን ለመፈጸም ስሜቱን የሚቀሰቅስነው፣በቅጣት ማቅለያ ሊያዝ የሚገባ ነው ካለ በቅጣት ማቅለያነት ተቀብሎ ቅጣት ማሻሻል ሲገባው ከቅጣት መመሪያው በመውጣት ቅጣቱን ከ18 ዓመት ወደ 12 ዓመት በማሻሻል የወሰነበትን አግባብነት ከቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 2/2006 አንቀጽ 27 እና ከወንጀል ህግ ቁጥር 539 (1) (ሀ) ጋር በማገናዘብ ለመመርመር ተብሎ ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ ተደርጓል፡፡

ለተጠሪ ባለበት ማረሚያ ቤት በኩል ጥሪ ተደርጎለት በቀን 22/11/2011 ዓ.ም የተጻፈ 2 ገጽ መልስ ቀርቦ ከመዝገቡ ጋር ተያይዟል፡፡ይዘቱም በአጭሩ፡- ሟች በተጠሪ ላይ ጉዳት ካደረሰ በኋላ በህግ ቁጥጥር ሥር ከሆነ በኃላ በዋስ መለቀቁ ስሜት ቀስቃሽና በፍትህ በደል የደረሰብኝ መስሎ ቢታየኝ እንኳን የሚያስገርም አይደለም፡፡ምክንያቱም በወቅቱ የነበረው የፍትህ ሂደትና ሥርዓት ሚዛናዊነት የሌለው ሲሆን ተጠሪ ከበቀል ስሜት ውጪ የነበርኩኝ ሆኖ በሟች ላይ የከፋ ጉዳት ለማድረስ የሚያስችል አቅም ያልነበረኝ መሆኑ ግምት ውስጥ ገብቶ የሥር ፍርድ ቤት ውሳኔ እንዲፀናልኝ የሚል ነው፡፡አመልካቹም መስከረም 26 ቀን 2012 ዓ.ም የተጻፈ የመልስ መልስ አቅርቧል፡፡

የነገሩ አመጣጥና የክርክሩ ሂደት በአጭሩ ከላይ እንደተመለከተው ሲሆን ጉዳዩን አጣሪው የያዘውን ጭብጥ መሠረት በማድረግ ከሥር ፍርድ ቤት ውሳኔ እንዲሁም አግባብነት ካለው ህግ ጋር በማገናዘብ መርምረናል፡፡ሟች ሙሉጌታ ይመር የአሁን ተጠሪን እጅ በመምታት ጉዳት አድርሷል ተብሎ በፖሊስ ተይዞ በጊዜ ቀጠሮ መቆየቱን፣ከዚያም በዋስትና መለቀቁን፣ሟች ከዚህ በፊት ደብድቦ በቀኝ እጅ ላይ ጉዳት አድርሶብኛል በሚል የአሁን ተጠሪ ቂም በመያዝ ከሥር ፍርድ ቤት 2ኛ እኛ 3ኛ ተከሳሾች ጋር በመሆን ሟችን መንገድ ላይ ጠብቀው ከምሽቱ 4:30 ላይ የአሁን ተጠሪ በፍልጥ እንጨት የሟችን ጭንቅላት መምታቱን፣ሌሎች ሁለቱ ተከሳሾች ሟችን ተባብረው መምታታቸውን፣ሟች ሲወድቅ ወደ ሶስተኛ ተከሳሽ ቤት በመሄድ ቢላዋ ይዘው ሟች ወደ ወደቀበት ቦታ በመመለስ የአሁን ተጠሪ /የሥር 1ኛ ተከሳሽ/ የሟችን የግራ እጁን በቢላዋ ወግቶ ስብራት በማድረስና የተለያየ ሰውነት ክፍሉን በቢላዋ በመውጋት የገደሉት መሆኑ የተረጋገጠ ፍሬ ነገር ነው፡፡ከተረጋገጠው ፍሬ ነገር ተነስተን የሟችን አገዳደል ስንመለከት የአሁን ተጠሪ ሟች ደብድቦ በእጁ ላይ ጉዳት አድርሶብኛል በሚል ቂም በመያዝ፣እንዲሁም ለምን በዋስትና ተለቀቀ በሚል ፍትህ እንደሌለ በመቁጠር የሥር 2ኛ እና 3ኛ ተከሳሾችን በማስተባበር በመንገድ ላይ ጠብቀው ሟችን ጭካኔ በተሞላበት ሁኔታ የገደሉ መሆናቸውን ነው፡፡ሟች ተመቶ ከወደቀ በኋላ ወደ ሶስተኛ ተከሳሽ ቤት በመሄድ ቢላዋ ይዘው በመምጣት ሟችን በወደቀበት የአሁን ተጠሪ ወጋግቶ እንዲሞት ማድረጉ የተፈጸመውን የወንጀል ድርጊቱን ክብደት የሚያሳይ ነው፡፡ይህ የወንጀል አፈጻጸም ታይቶ የአሁን ተጠሪን /የሥር 1ኛ ተከሳሽን/ ጨምሮ ሶስቱም ተከሳሾች በተከሰሱበት የህግ ድንጋጌ ሥር ጥፋተኛ

ተብለዋል፡፡ቅጣትንም በተመለከተ የወንጀል ድርጊት አፈጻጸማቸው ታይቶ ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በአሁን ተጠሪ ላይ የ18 ዓመት ከ6 ወር የጽኑ እሥራት ቅጣት ወስኖበታል፡፡የአሁን ተጠሪ የጥፋተኝነትም ሆነ የቅጣት ውሳኔውን በመቃወም ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ አቅርቧል፡፡የጠቅላይ ፍርድ ቤቱም ይግባኙን ተቀብሎ ክርክራቸውን ካዳመጠ በኋላ ሟች በአሁን ተጠሪ /ይግባኝ ባይ/ ላይ ያደረሰ ጉዳት ካለ በህግ አግባብ ማስከበር እየተቻለ በበደል አድራሹ ላይ እርምጃ መውሰድ እና የብቀላ ድርጊት መፈጸም የተከሰሰበት የወንጀል ድንጋጌን የሚያሟላ ነው በማለት የጥፋተኝነት ውሳኔን አጽንቶታል፡፡ቅጣትን በተመለከተ ግን ሟች በአሁን ተጠሪ ላይ ያደረሰው ጉዳት ስሜትን የሚቀሰቅስ በመሆኑ ቅጣት ሊቀልለት ይገባል በማለት ከቅጣት መመሪያው በመውጣት ተጠሪ በ12 /አስራ ሁለት/ ዓመት ጽኑ እሥራት እንዲቀጣ ሲል ወስኗል፡፡ይህ ውሳኔ ተጠሪ ከፈጸመው የወንጀል አፈጻጸም እንዲሁም ከወንጀል ህግ ዓላማ እና ግብ አንጻር ሲታይ ተገቢ ነው ወይ? የሚለውን በቅድሚያ መመልከት ያስፈልጋል፡፡ሟች የአሁን ተጠሪን በመደብደብ በእጁ ላይ ጉዳት ካደረሰ በኋላ በህግ ቁጥጥር ሥር ውሏል፡፡በጊዜ ቀጠሮ ምርመራ ከተደረገ በኋላ በዋስትና ተለቋል፡፡በጊዜ ቀጠሮ ቆይቶ በዋስትና ከተለቀቀ በኋላ የአሁን ተጠሪ በሟች ላይ የግድያ ወንጀል መፈጸሙ ሲታይ በከፍተኛ ስሜት ቀስቃሽነት ወንጀሉን ፈጽሟል ሊያስብል የሚችል አይሆንም፡፡ምክንያቱም ተጠሪ የዚህን ዓይነት ድርጊት የፈጸመው ወንጀሉ እንደ ተፈጸመ ወዲያውኑ ቢሆን ኖሮ ፍርድ ቤቱ የያዘውን ዓይነት ግንዛቤ ሊወስድ ይችል ነበር፡፡ነገር ግን በሟች ላይ የግድያ ወንጀል የተፈጸመው ሟች በተጠሪ ላይ ጉዳት አድርሶ ከቆየ በኋላ ነው፡፡ይህ ተረጋግጦ ተጠሪ በወንጀል ህግ አንቀጽ 539 (1) (ሀ) ሥር ጥፋተኛ ተደርጎ በቅጣት አወሳሰን መመሪያው መሠረት የግራ ቀኙ የቅጣት አስተያየት ተወስዶ የ18 ዓመት ከ6 ወር ጽኑ እሥራት ቅጣት ሊወሰን ችሏል፡፡የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤቱ ይህን ቅጣት በማሻሻል ተጠሪ በ12 ዓመት ጽኑ እሥራት እንዲቀጣ መወሰኑ ከወንጀል ህግ መሠረታዊ ዓላማ እንዲሁም ከቅጣት መመሪያው ዓላማ አንጻር ሊታይ ይገባል፡፡የወንጀል ህግ ዓላማ እና ግብ በወንጀል ህግ አንቀጽ 1 ተዘርዝሮ ተቀምጧል፡፡የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የወንጀል ህግ ዓላማ ሰላም፣ ደህንነት፣ ሥርዓት፣ መብትና ጥቅም መጠበቅና ማረጋገጥ ነው፡፡ይህን ዓላማ ለማሳካት ከተቀመጡ ስልቶች መካከል አንዱ በአጥፊዎች ላይ ተገቢውን ቅጣት መወሰን ነው፡፡

የወንጀል ሕግ ግብ ደግሞ ወንጀል እንዳይፈፀም መከላከል ነው፡፡ስለዚህ በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የወንጀል ሕግ ውስጥ ቅጣት ግብ ሳይሆን የወንጀል መከላከሉን ግብ ለማሳካት የተቀመጠ አንዱ ስልት ነው፡፡ይህንን የሚያደርገው በመጀመሪያ ስለወንጀሎችና ስለቅጣታቸው በቅድሚያ ማስጠንቀቂያ በመስጠት ነው፡፡ማስጠንቀቂያነቱ በቂ ባልሆነበት ጊዜ ወንጀል አድራጊዎቹ ተቀጥተው ሌላ ወንጀል ከመፈፀም እንዲቆጠቡ፣ ለሌሎች ማስተማሪያ እንዲሆኑ ወይም እንዲታረሙ በማድረግ ወይም ተጨማሪ ወንጀሎች እንዳይፈፅሙ እርምጃዎችን በመውሰድ ነው፡፡ ይህም ጠቅለል ተደርጎ ሲታይ ወንጀል አድራጊው ሌላ ወንጀል እንዳይፈጽም የሚያደርግ (prevention)፣ ሌሎችን ወንጀል ከመፈጸም

እንዲቆጠቡ የሚያደርግ (deterrence)፣ እንዲሁም ወንጀል አድራጊን ማረም (rehabilitaiton )እንደሆነ እንረዳለን። ከዚህ የምንገነዘበው ቅጣት የወንጀል ሕግ ማስፈጸሚያ አንዱ መሰረታዊ መሳሪያ እንደሆነ ነው።

ይህ በእንዲህ እንዳለ የቅጣት አወሳሰን ትክክለኛነትና አንድ ወጥነት ለማረጋገጥ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የቅጣት አወሳሰን መመሪያ / Manual/ እንደሚያወጣ በወንጀል ህጉ አንቀጽ 88 (4) ተደንግጓል።ይህን ድንጋጌ ተከትሎ የቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 1/2002 ወጥቶ በሥራ ላይ ከዋለ በኋላ ይህ መመሪያ ተሽሮ የተሻሻለ የወንጀል ቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 2/2006 ወጥቶ ወይም ተዘጋጅቶ በሥራ ላይ ይገኛል።የዚህ መመሪያ ዓላማና ግብ በአንቀጽ 3 ሥር ተቀምጧል።የመመሪያው ዓላማ የዳኝነት አካሉ ግልጽነትና ተጠያቂነትን ባረጋገጠ መልኩ ውጤታማና ተገማችነት ያለው ቅጣት የሚሰጥበትን ሥርዓት መመሥረት ነው።የመመሪያው ግቦች ደግሞ በተቀራራቢና ተመሳሳይ የወንጀል ጉዳዮች መካከል ተቀራራቢነት ያለው ቅጣት እንዲወሰን ማድረግ፤እንደወንጀሉ ክብደትና አደገኛነት የቅጣት ተመጣጣኝነት ማረጋገጥ ናቸው።ይህን ዓላማ እና ግብ ለማሳካት የቅጣት አወሳሰን መመሪያው ደረጃ ለወጣላቸው የወንጀል ህግ ድንጋጌዎች ዝርዝር መስፈርቶችን አስቀምጧል።የወንጀል ደረጃ ከወጣላቸው የወንጀል ህግ ድንጋጌዎች መካከል አንዱ አንቀጽ 539 ነው።ለወንጀል ህግ አንቀጽ 539 (1) (ሀ) ሁለት የወንጀል ደረጃዎች፣እንዲሁም ለወንጀል ደረጃዎቹ የወንጀሉ ደረጃ መግለጫ ተዘርዝሮ ተቀምጧል። በያዝነው ጉዳይ የአሁን ተጠሪ ተከሶ ጥፋተኛ ለተደረገበት የወንጀል ህግ አንቀጽ 539 (1) (ሀ) በቅጣት መመሪያው መሠረት በደረጃ 1 የተዘረዘረውን የወንጀል ደረጃ መግለጫ መሠረት በማድረግ የእሥራት ቅጣት መነሻ እርከን 38 ላይ እንዲያርፍ ተደርጎ እንደተወሰደ የከፍተኛ ፍርድ ቤት ውሳኔ ያሳያል።ይህ ከሆነ በኋላ ለተጠሪ ሁለት የቅጣት ማቅለያ ተይዞ በእርከን 36 ከተቀመጠው የፍቅድ ሥልጣን በ18 ዓመት ከ6 ወር ጽኑ እስራት ቅጣት ተጠሪ እንዲቀጣ ተወስኗል።

ከዚህ መመሪያ ውጪ ቅጣት ሊወሰን የሚችልበት ሁኔታ በተመለከተ በአንቀጽ 27 (1) ላይ ተደንግጓል።በዚህ ድንጋጌ መሠረት የመጀመሪያው ፍርድ ቤቱ የወንጀል ሕጉን የቅጣት ዓላማ እና ግብ የማያሳካ ነው ብሎ ካመነ ከመመሪያው ውጪ በመውጣት ቅጣት ሊወስን ይችላል።የወንጀል ህጉ ዓላማ እና ግብ ምን እንደሆነ ከፍ ብሎ ለማስቀመጥ ተሞክሯል። በአንቀጽ 27 (1) የተቀመጠው ሁለተኛው መሠረታዊ ነገር መመሪያውን ተግባራዊ ለማድረግ የማይችልበትን ምክንያት ፍርድ ቤቱ በዝርዝር በማስቀመጥ ነው።

በተያዘው ጉዳይ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ከመመሪያው ውጪ በመውጣት ቅጣት የወሰነ ቢሆንም የወንጀል ህጉን ዓላማ እና ግብ ለማሳካት የሚያስችል ነው ብሎ ለመውሰድ የሚቻል እንዳልሆነ ይህ ችሎት ግንዛቤ ወስዶበታል።ይኸውም ከወንጀሉ ከባድነት እና ተጠሪ ከፈጸመው የወንጀል አፈጻጸም አንጻር ሲመዘን ከመመሪያው ውጪ የተወጣው የወንጀል ህጉን ዓላማ እና ግብ የሚያሳካ

አይደለም፡፡ከዚህ በተጨማሪ የጠቅላይ ፍርድ ቤቱ የወንጀል ይግባኝ ሰሚ ችሎት መመሪያውን ተግባራዊ ለማድረግ የማይችልበትን ምክንያት በዝርዝር አላስቀመጥም፡፡ጠቅላይ ፍርድ ቤቱ ሟች በተጠሪ እጅ ላይ ያደረሰው ጉዳት ወንጀል ለመፈጸም ቀስቃሽ ሆኗል የሚል ነው፡፡ይህ ምክንያት አስፈላጊ ከሆነ በቅጣት ማቅለያነት ከሚያዝ በስተቀር ከላይ በተገለጸው መሠረት ተጠሪበሟች ላይ ወንጀሉን የፈጸመው ውሎ አድሮ ከቆይታ በኂላ በመሆኑ ይሁንታ የሚሰጠው አይደለም፡፡

በመጨረሻም ሟች በተጠሪ ላይ ድብደባ በመፈጸም በእጁ ላይ ጉዳት በማድረሱ በህግ ቁጥጥር ሥር ውሎ በዋስ በመፈታቱ ላይ ቅሬታ ቢኖረው በህግ በተቀመጠው ሥነ-ሥርዓት መጠየቅ እንጂ ለምን በዋስ ተፈታ፣እንደገና ጉዳት ያደርስብኛል በሚል ትንበያ፣እንዲሁም ፍትህ ተዳክሟል በሚል በራሱ ፍትህን ለማስፈጸም ግድ ያፈጽማል፡፡ይህ ሆኖ ባለበት ቅጣትን አቅልሎ መወሰን ተጠሪን የማያስተምር እና ፍትህን በራሱ መፈጸሙ ምክንያታዊ እንደሆነ እንዲሰማው የሚያደርግ፣ሌላውን ማኅበረሰብ ፍትህን በራሱ እንዲያስፈጽም የሚገፋፋ ወይም መጥፎ አርአያ የሚሆን፣ዋነኛው የወንጀል ህግ ዓላማ የሆነውን የህዝብን ሠላምና ደኅነት የማስጠበቅ ዓላማ እንዳይሳካ የሚያደርግ በመሆኑ የተጠሪ ድርጊት ሊነቀፍ የሚገባ ነው፡፡የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ከላይየተጠቀሱትን መሠረታዊ ነገሮችን በአግባቡ ሳያጤን ከቅጣት መመሪያው ውጪ በማውጣት የወሰነው የቅጣት ውሳኔ መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነው፡፡

ሲጠቃለልም ተጠሪ የወንጀል ድርጊቱን የፈጸመው ሟች በተጠሪ እጅ ላይ ጉዳት በማድረሱ ስሜቱን ቀስቅሶታል የሚባል ከሆነ አንድ የቅጣት ማቅለያ ቢያዝለት አመልካች እንደማይቃወም በክርክር ሂደት ያስመዘገበ በመሆኑ በሥር ፍርድ ቤት ከተያዙት ሁለት ማቅለያዎች በተጨማሪ ሊያዝለት ይገባል፡፡ይህም ሲቀነስ ከእርከን 36 ወደ እርከን 35 ዝቅ ይላል፡፡በዚህ እርከን የተቀመጠው የፍቅድ ሥልጣን 16 ዓመት ከ6 ወር- 19 ዓመት ከ6 ወር ነው፡፡በመሆኑም የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

<u>ው ሳ ኔ</u>

1. ተጠሪ 16 ዓመት ከ6 ወር የጽኑ እሥራት ቅጣት እንዲቀጣ በወንጀለኛ መቅጫ ህግ ሥነ ሥርዓት ቁጥር 195 (2) (ለ) (2) መሠረት ተሻሽሎ ተወስኗል፡፡
2. በተሻሻለው የቅጣት ውሳኔ መሠረት እንዲያስፈጸም ተጠሪ ለሚገኙበት ማረሚያ

   ቤት ይጻፍ፡፡
3. ቅጣት ተሻሽሎ የተወሰነ መሆኑን ተጠሪ እንዲያውቅ ባለበት ማረሚያ ቤት በኩል ይድረሰው፡፡
4. የውሳኔው ግልባጭ ለሥር ፍርድ ይድረስ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ሰ/ጥ

የሰ/መ/ቁጥር169726

ግንቦት 14 ቀን 2011 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ብርሃኑ አመነዉ

በዕዉቀት በላይ

እንዳሻዉ አዳነ

ሃይሉ ነጋሽ

እትመት አሠፋ

**አመልካች:-** አቶ ፍቅሩ ደሌሳ

**ተጠሪ፡-** የፌዴራል ጠቅላይ ዐ/ሕግ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለዉ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍርድ

ጉዳዩ የተጨማሪ እሴት ታክስ ደረሰኝ አለመስጠት ወንጀልን የሚመለከት ሲሆን የተጀመረዉ በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ተጠሪ ሙሉ አርጋዉ፣ ሰርግነሽ በዛ እና በአሁኑ አመልካች ላይ በመሠረተዉ ክስ መነሻነት ነዉ፡፡ አመልካች ላይ የቀርበዉ 2ኛ ክስ ሲሆን ይዘቱ፡- በፌዴራል የታክስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 983/2008 አንቀጽ 128 እና 131(1/ለ) ስር የተመለከተዉን በመተላለፍ የስር 1ኛ ተከሳሽን የንግድ ሥራ እንዲቆጣጠር፣ እንዲያስተዳድር፣ ሙሉ ዉክልና ወስዶ በንግድ ቤቱ ደረሰኝ መሰጠቱን መቆጣጠር ሲገባዉ ይህንን ሳያደርግ የቀረ በመሆኑ በፈጸመዉ ከሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያ ከታተመ ደረሰኝ ዉጪ ግብይት እንዲከናወን የመርዳት ወንጀል ተከሷል የሚል ነዉ፡፡

በስር ፍ/ቤት አመልካች የእምነት ክህደት ቃል ሲጠየቅ የወንጀል ድርጊቱን መፈጸሙን አምኖ ጥፋተኝነቱ በራሱ በማረጋገጡ ፍርድ ቤቱ አመልካችን በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ 134(1) መሠረት የታክስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 983/08/አንቀጽ 128 እና 131(1/ለ) ስር ጥፋተኛ በማድረግ በአንድ ዓመት ጽኑ እስራት እንዲቀጣ ሲወስን የአመልካችን የገደብ ጥያቄ በዝምታ ሳይቀበለዉ ቀርቷል፡፡ አመልካች የገደብ ጥያቄዉ በስር ፍ/ቤት በመታለፉ ቅር ተሰኝቶ ይግባኝ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ቢያቀርብም ተቀባይነት አላገኘም፡፡ የሰበር አቤቱታ የቀረበዉ ይህንኑ የዉሳኔ ክፍል በመቃወም ለማስቀየር ነዉ፡፡

አመልካች ያቀረቡት የሰበር አቤቱታ ይዘት፡- ድርጊቱ የተፈጸመዉ አመልካች ዕቃ ለመግዛት በወጣሁበት ወቅት በስር 2ኛ ተከሳሽ መሆኑን፤ ነገር ግን በዉክልናዉ መሰረት ስራዉን ስከታተል የነበርኩት እኔ ስለሆንኩ መቆጣጠር ስለነበረብኝ ይህንን ባለማድረጌ ጥፋተኛ ነኝ ብያለሁ፡፡ የቀድሞ ጥፋተኝነት ሪኮርድ የሌለብኝ፤ ድርጊቱን በማመን መጸጸቴን በተግባር ማሳየቴን፤ የቤተሰብ አስተዳዳሪነቴን እንዲሁም በልማት በመሳተፍ መልካም ሰዉ መሆኔን በማስረጃ አረጋግጫለሁ፡፡ ይህ በወ/ሕግ አንቀጽ 192 መሰረት ቅጣቱን በገደብ በማድረግ የአመልካችን ፀባይ ቢፈተን አንድ ጽኑ ማስጠንቀቂያ በቂ ነዉ የሚያስብል በቂ ምክንያት ቢኖርም የስር ፍ/ቤት በምን ምክንያት ሊቀበለዉ እንዳልቻለ እንኳን ሳይገልጽ ማለፉ ተገቢ አይደለም፡፡ ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁ 46382 በሰጠዉ ትርጉም መሠረት ቅጣቱ ቢገደብልኝ እና አንድ ጽኑ ማስጠንቀቂያ ተሰጥቶኝ ጸባዬ ቢፈተን ዳግመኛ ወንጀል እንደማልፈጽም የሚያሳዩ በቂ ምክንያቶች እያሉኝ የገደብ ጥያቄ መታለፉ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ይኸዉ የዉሳኔ ክፍል ተሽሮ ቅጣቱ ይገደብልኝ የሚል ነዉ፡፡

የአመልካች አቤቱታ ተመርምሮ አመልካች በስር ፍ/ቤት የተከሰሱበትን ወንጀል አምነዉ የጥፋተኝነት ዉሳኔ ከተሰጠ በኃላ ቅጣቱ እንዲገደብላቸዉ ያቀረቡትን አቤቱታ የስር ፍ/ቤቶች በዝምታ ያለፉበትን አግባብ ከአዋጅ ቁጥር 983/08 አንቀጽ 128፣ 131(1/ለ)፣ ከወ/ሕግ አንቀጽ 192 እና ተከታይ ድንጋጌዎች አንጻር ለማጣራት ሲባል ጉዳዩ ለሰበር ያስቀርባል የተባለ ሲሆን ግራ ቀኙ መልስና የመልስ መልስ በጽሁፍ በማቅረብ ተከራክረዋል፡፡

ተጠሪ ያቀረበዉ መልስ፡- የስር ፍ/ቤት አመልካች ያቀረባቸዉን የቅጣት ማቅለያዎችን ተቀብሎ ቅጣት በማቅለል የወሰነ ሲሆን ቅጣቱ እንዲገደብ ትዕዛዝ አለመስጠቱ ብቻ መሠረታዊ የህግ ስህተት ፈጽሟል አያስብልም፡፡ የወ/ሕ/አንቀጽ 192 ፍ/ቤቱ የነገሮችን ሁኔታ ዓይቶ ጥፋተኛዉ በጽኑ ማስጠንቀቂያ ቢታለፍ ይሻላል ብሎ ሲያምን የሚወስነዉ እንጂ አመልካች እንዳቀረቡት እንደመብት ሊጠየቅ የሚገባዉ አይደለም፡፡ አመልካች ባጠፋዉ ጥፋት በግሉ መታረሙን ብቻ የሚጠይቅ ሳይሆን ሌሎች የንግዱ ማህበረሰብ አባላት ከተመሳሳይ ድርጊት እንዲቆጠቡ በማስተማር የሕዝብና የመንግስትን ጥቅም ማስጠበቅን ታሳቢ አድርጎ ቅጣት ሊጣል እንደሚገባ የሚታመን በመሆኑ የቅጣት ዉሳኔ አለመገደቡ ከወንጀል ሕጉ አላማ ጋር የተጣጣመ በመሆኑ የሚነቀፍ አይደለም፡፡ በሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁ 46382 የተሰጠዉ ዉሳኔ ከዚህ ጉዳይ ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት የለዉም፡፡ ስለሆነም ዉሳኔዉ ይጽናልን የሚል ነዉ፡፡ አመልካች በሰጠዉ የመልስ መልስ የሰበር አቤቱታዉን በሚያጠናክር መልኩ ተከራክሯል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ ይዘት ከላይ የተገለጸዉን የሚመስል ሲሆን የአመልካችን አቤቱታ ያስቀርባል ሲባል ከተያዘዉ ጭብጥ አንጻር ከስር ፍ/ቤት ዉሳኔን አግባብነት ካላቸዉ የሕግ ድንጋጌዎች አኳያ መርምረናል፡፡ በዚህም መሠረት መርምረን እንደተረዳነዉ አመልካች በፌዴራል የታክስ አስተዳደር

አዋጅ ቁጥር 983/2008 አንቀጽ 128 እና 131(1/ለ) የተመለከተዉን በመተላለፍ የስር 1ኛ ተከሳሽን የንግድ ሥራ እንዲቆጣጠር ሙሉ ዉክልና ወስዶ በንግድ ደርጅቱ ደረሰኝ መሰጠቱን መቆጣጠር ሲገባዉ ይህንን ሳያደርግ በመቅረቱና ግብይቱ ከሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያ ከታተመ ደረሰኝ ዉጪ መከናወኑ በአመልካች የእምነት ቃል ተረጋግጦ በተጠቀሰዉ የሕግ አንቀጽ ስር ጥፋተኛ መባሉም ሆነ በአንድ ዓመት ጽኑ እስራት መቀጣቱ ላይ አመልካች ያቀረበዉ ቅሬታ የለም፡፡ አመልካች አጥብቆ የሚከራከረዉም ሆነ አቤቱታዉ ለሰበር ያስቀርባል ሲባል የተያዘዉ ጭብጥ ከወ/ሕ/አንቀጽ 192 ድንጋጌ አንጻር አመልካች ቅጣት እንዲገደብለት ያቀረበዉን ጥያቄ የስር ፍ/ቤት በዝምታ ሳይቀበለዉ መቅረቱ በአግባቡ ነዉ? ወይስ አይደለም? የሚለዉ ነዉ፡፡

የወንጀል ቅጣት በገደብ ለማቆየት በሕጉ የተዘረዘሩት ቅድመ ሁኔታዎች ሊሟሉ እንደሚገባ በወ/ሕ/አ/197(1) እና(2) ተመልክቷል፡፡ አንድ ተከሳሽ ቅጣቱ ሊገደብለት የሚችለው በመልካም ጠባይ እንደሚመራ ግዴታ የሚቀበል መሆኑ መረጋገጥ እንዳለበት፤ በጥፋቱ ያደረሰውን ጉዳት እና የፍ/ቤት ወጪ ለመክፈል ማረጋገጫ መስጠት ያለበት ስለመሆኑ፤ ጥፋተኛው ለገባበት ግዴታ አፈፃፀም እንደ መተማመኛ መስጠት እንዳለበት ሕጉ አስገደጅ መስፈርት አስቀምጧል፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሠበር ሰሚ ችሎት ከዚህን ቀደም በሰ/መ/ቁ 94404 በሰጠው አስገዳጅ ውሳኔ አንድ ጥፋተኛ በተወሰነ ገደብ ከእስር ለመፍታት በሕጉ የተቀመጡትን ቅድመ ሁኔታዎች ያሟላ መሆኑን ፍርድ ቤቱ አስቀድሞ ማረጋገጥ ያለበት ጉዳይ መሆኑን በመግለጽ ትርጉም ሰጥቷል፡፡ ሆኖም በወ/ሕ/አንቀጽ 197 የተመለከቱ መስፈርቶች ተሟልተዉ መገኘት አንድ አጥፊ የተወሰነበት እስራት የግድ ይገደብለታል ማለት አይደለም፡፡ ይልቁንም ቅጣትን በገደብ ለማቆሞ በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 190 የተመለከተው መሰረታዊ መርህ ከወ/ሕ/አንቀጽ 192 እና 196 ድንጋጌ ጋር ተገናዝቦ ሊታይ ይገባል፡፡

በመርህ ደረጃ የወንጀል ቅጣት የሚገደበው የወንጀለኛው ጠባይ ለማረምና ለማሻሻል ወደ መደበኛ ማህበራዊ ኑሮው ለመመለስ ጠቃሚ ሊሆን የሚችል መሆኑን ፍ/ቤቱ ማረጋገጥና ማመን ሲችል መሆኑን የወ/ሕ/አንቀጽ 190 ድንጋጌ ያስገናዝበናል፡፡ እንዲሁም በአንድ ወንጀል ፈፃሚ ላይ የተወሰነው ቅጣት እንዳይፈጸም የሚታገደው ለሁለተኛ ጊዜ ጥፋት ከማድረግ የሚታገድ መሆኑንና ስለጠበዩም ማሻሻል አንድ ጽኑ ማስጠንቀቂያ ብቻ በቂ መሆኑን ፍርድ ቤቱ ሲያምን መሆኑ በወ/ሕ/አንቀጽ 192 ተመልክቷል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ቅጣትን እንዳይፈጽም ለማገድ በወንጀል ሕጉ አንቀፅ 196 የተዘረዘሩት የወል ድንጋጌዎች በአግባቡ ሊታዩ እንደሚገባ ከድንጋጌው መሠረታዊ ይዘትና መንፈስ መረዳት ይቻላል፡፡ በዚህ ድንጋጌ መሰረት ፍርድ ቤት የዕግድ ትዕዛዝ ሲመረጥ ምክንያቱን በውሳኔው ማካተት እንዳለበት የተከሳሹ የቀደመ ታሪክ፤ የጠበዩና የዓመሉ አካሄድ ሲመዘን ጊዜ መስጠቱ መልካም ውጤት የሚያስገኝ መስሎ ካልታየው የማገጃ ትዕዛዝ እንደማይሰጥ በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 1 ተደንግጓል፡፡ ከዚህ ድንጋጌ ይዘት መገንዘብ የሚቻለዉ ከምንም በላይ ጉዳዩን ያየዉ

ፍ/ቤት የአጥፊዉን ጠባይና የዓመሉን ሁኔታ ሲመዝን ቅጣትን ማገድ መልካም ዉጤት የሚያስገኝ መሆኑን ካላመነ ወይም ካልገመተ በቀር የተወሰኑ መስፈርቶች ስለተሟሉ ብቻ ቅጣት ማገድ ነበረበት ሊባል አይችልም፡፡

በተያዘዉ ጉዳይ አመልካች የቀድሞ የጥፋተኝነት ሪኮርድ ያልቀረበበት፣ ጥፋቱን አምኖ ተፀፀተና የቤተሰብ አስተዳዳሪ መሆኑ ሲታይ በወ/ሕ/አንቀጽ 197 የተመለከቱትን ቅድመ ሁኔታዎች በአብዛኛው ያሟላ ቢሆንም በወ/ሕ/አንቀጽ 190 እና 192 ድንጋጌዎች መሠረት በአመልካች ላይ የተወሰነው ቅጣት ሳይፈጸም ቢገደብ ለሁለተኛ ጊዜ ጥፋት ከማድረግ የሚታገድ መሆኑንና ስለጠበዩም ማሻሻል አንድ ጽኑ ማስጠንቀቂያ ብቻ በቂ መሆኑን የስር ፍ/ቤት ባለማመኑ የአመልካችን የገደብ ጥያቄ በዝምታ ሳይቀበል ቀርቷል፡፡ የስር ፍ/ቤት በዝምታ ማለፉ ወይም ምክንያት አለመስጠቱ ተገቢ ባይሆንም ይህ ችሎት አመልካች ጥፋተኛ የተባለበት የወንጀል ዓይነት የመንግስት ገቢን በመሰብሰብ አቅም ላይ ያለዉን አሉታዊ ተጽእኖ እና በወ/ሕ/አንቀጽ 197 የተመለከቱ መስፈርቶች በአብዛኛዉ ተሟልተዉ ተገኝቷል በሚል ቅጣቱ ሳይፈጸም ቢቀር ለአመልካችም ሆነ በተመሳሳይ ድርጊት ላይ ሌሎች እንዳይሳተፉ ከማድረግ አንጻር ቅጣት ማገዱ መልካም ዉጤት ያመጣል የሚል እምነት ለመጣል አልቻለም፡፡ ከዚህ አንጻር የስር ፍ/ቤት የአመልካችን የገደብ ጥያቄ ዉድቅ ሲያደርግ ምክንያት ስላልሰጠ ብቻ ጉዳዩን ወደ ስር ፍ/ቤት መመለሱ የተለየ ዉጤት የሚያመጣ ባለመሆኑ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ ለማለት አልተቻለም፡፡

ሲጠቃለል የስር ፍ/ቤት አመልካች የወሰነዉን የአንድ ዓመት ጽኑ እስራት ቅጣት ዉሳኔ ሳይገደብ መቅረቱ ከወ/ሕ/አንቀጽ 190፣ 192 እና 197 ድንጋጌዎች አንጻር የሚነቀፍ ባለመሆኑ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ ለማለት አልተቻለም፡፡ በመሆኑም ተከታዩ በአብላጫ ድምፅ ተወስኗል፡፡

<u>ዉሳኔ</u>

1. በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በኮ/መ/ቁ 262072 ጥቅምት 14 እና 15 ቀን 2011 ዓ.ም ተሰጥቶ በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁ 225003 ታሕሳስ 09 ቀን 2011 ዓ.ም በተሰጠ ትዕዛዝ የጸናዉ ዉሳኔ በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ 195(2/ለ) መሠረት ጸንቷል፡፡
2. መዝገቡ ዉሳኔ ያገኘ ስለሆነ ተዘግቷል፡፡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአራት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ሠ/ኃ

## የልዩነት ሐሳብ

ስሜ በተ.ቁ 5 ላይ የተገለጸው ዳኛ የስር ፍ/ቤት የአመልካችን የቅጣት ገደብ ጥያቄ በዝምታ በማለፍ በሰጠው ውሳኔ ላይ አብላጫው ድምጽ በደረሰበት መደምደሚያ በሀሳብ ስለተለየሁ የሀሳብ ልዩነቴን እንደሚከተለው አስፍሬአለሁ፡፡

አመልካች የወንጀል ድርጊቱን መፈጸሙን አምኖ ጥፋተኝነቱ በራሱ በማረጋገጡ ፍርድ ቤቱ አመልካችን በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ 134(1) መሠረት የታክስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 983/08/አንቀጽ 128 እና 131(1/ለ) ስር ጥፋተኛ በማድረግ በአንድ ዓመት ጽኑ እስራት እንዲቀጣ ሲወስን የአመልካችን የገደብ ጥያቄ በዝምታ ሳይቀበለዉ አልፎታል፡፡

አመልካች ድርጊቱን ማመኑ እና በፈጸመው ድርጊት ምክንያት የተጸጸተ መሆኑ፤ የቀድሞ ጥፋተኝነት ሪኮርድ የሌለበት መሆኑ፤ የቤተሰብ አስተዳዳሪ መሆኑ በስር ፍ/ቤት የተረጋገጠ ፍሬነገር ሲሆን አብላጫው ድምጽም አመልካች የቀድሞ የጥፋተኝነት ሪኮርድ ያልቀረበበት፣ ጥፋቱን አምኖ የተፀፀተና የቤተሰብ አስተዳዳሪ መሆኑ ሲታይ በወ/ሕ/አንቀጽ 197 የተመለከቱትን ቅድመ ሁኔታዎች በከፊል ያሟላ መሆኑን በመግለጽ በውሳኔው ላይ አስፍሯል፡፡ አብላጫው ድምጽ የአመልካችን የገደብ ጥያቄ ያልተቀበለው የስር ፍ/ቤት በዝምታ ማለፉ ወይም ምክንያት አለመስጠቱ ተገቢ ባይሆንም ይህ ችሎት አመልካች ጥፋተኛ የተባለበት የወንጀል ዓይነት የመንግስት ገቢን በመሰብሰብ አቅም ላይ ያለዉን አሉታዊ ተጽእኖ እና በወ/ሕ/አንቀጽ 197 የተመለከቱ መስፈርቶች በአብዛኛዉ ተሟልተዉ ተገኝቷል በሚል ቅጣቱ ሳይፈጸም ቢቀር ለአመልካችም ሆነ በተመሳሳይ ድርጊት ላይ ሌሎች እንዳይሳተፉ ከማድረግ አንጻር ቅጣት ማገዱ መልካም ዉጤት ያመጣል የሚል እምነት ለመጣል አልቻለም በሚል ነው፡፡

በመሠረቱ የወንጀል ሕጉ ዓላማ ወንጀል እንዳይፈጸም ማድረግ ሲሆን ይህንንም የሚያደርገው ስለወንጀሎች እና ስለቅጣታቸው በቅድሚያ ማስጠንቀቂያ በመስጠት፤ ማስጠንቀቂያነቱ በቂ ባልሆነ ጊዜ ደግሞ ወንጀል ፈጻሚዎች ተቀጥተው ሌላ ወንጀል ከመፈጸም እንዲቆጠቡ እና ለሌሎች ማስተማሪያ እንዲሆኑ ወይም እንዲታረሙ በማድረግ እንደሆነ ከወንጀል ሕጉ ዓላማ እና ግብ መገንዘብ ይቻላል፡፡ ቅጣት ሲገደብ የፍርዱ ውሳኔ በወንጀለኞች መዝገብ ላይ ተመዝግቦ ከሌላው ውጤት ጋር ነዋሪ የሚሆን በመሆኑ ቅጣትን መገደብ በወንጀለኛው ላይ ቅጣት እንዳይፈጸም የማድረግ ውጤት ብቻ ያለው ሳይሆን ወንጀለኛው ዳግም ጥፋት ከመፈጸም እንዲታቀብ የማድረግ ውጤት ያለው በመሆኑ ቅጣትን መገደብ የወንጀል ሕጉ ዓላማ እና ግብ ከሚሳካባቸው መንገዶች አንዱ ነው፡፡

ቅጣት ሊገደብ የሚችለውም ጥፋተኛ የተባለን ሰው ለጥፋቱ መነሻ የሆኑትን ምክንያቶችን በጠቅላላው በመመልከት በጥፋተኛው ላይ የተወሰነውን ቅጣት ለጊዜው በገደብ እንዲታገድ በማድረግ የወንጀለኛውን ጠባይ ለማረምና ለማሻሻል እንዲሁም ወደ መደበኛ ማህበራዊ ኑሮው ለመመለስ ጠቃሚ መሆኑ

በታመነ ጊዜ ስለመሆኑ የቅጣት ገደብን  አስመልክቶ ከተደነገጉት የወንጀል ሕጉ ድንጋጌዎች መገንዘብ ይቻላል፡፡ ይህንንም ተፈጻሚ ለማድረግ ፍ/ቤቶች ቅጣትን ለመገደብ  የሚያስችሉ የተለያዩ ሁኔታዎች ከግምት ውስጥ ማስባት እንዳለባቸው፤ እነዚህም ሁኔታዎች ወንጀለኛው ቀድሞ ያልተቀጣ ሆኖ ጠባዩም አደገኛነት እንደሌለው የሚታመንበት እንደሆነ፤ጥፋቱ በመቀጮ፤ በግዴታ ስራ ወይም ከሶስት አመት የማይበልጥ ቀላል እስራት የሚያስቀጣ እንደሆነ ፍርድ ቤቱ ጥፋተኝነቱን ካረጋገጠ በኋላ ለወደፊት ጠባዩን ለማረም እንደሚችል እምነት ሊጣልበት የሚችል መሆኑና በዚህ ውሳኔ ብቻእስከ መጨረሻው ሊሻሻል የሚችል መሆኑን 'ያመነበት' እንደሆነ፤ እንዲሁምጥፋተኛው አስቀድሞ የተፈረደበት ቢሆንም ባይሆንም የተፈረደበትን ቅጣት ከመፈፀሙ በፊት ለተወሰነ ጊዜ ቅጣቱ ታግዶለት አመሉ ቢፈተን ሁለተኛ ጥፋት ከማድረግም የሚታገድ መሆኑናስለጠባዩም መሻሻል አንድ ፅኑ ማስጠንቀቂያ ብቻ የሚበቃ መሆኑ ፍርድ ቤቱ ያመነበት እንደሆነ ቅጣቱ ከአፈፃፀም ታግዶ እንዲቆይ ሊያዝ የሚችል ስለመሆኑ ከወንጀል ሕግ አንቀጽ 192 እና ተከታይ ድንጋጌዎች ይዘት መገንዘብ ይቻላል፡፡

በሌላ በኩል በጥፋተኛው ላይ የተወሰነው ቅጣት እንዳይገደብ ሊያደርጉ የሚችሉ በሕጉ የተቀመጡ ሁኔታዎች ያሉ መሆኑን፤እነኚህም ሁኔታዎች ጥፋተኛው ከዚህ በፊት የጽኑ እሥራት ቅጣት ወይም ከሦስት ዓመት የሚበልጥ ቀላል እሥራት ቅጣት ተፈርዶበት እንደሆነ እና እንደገናም በተከሰሰበት ወንጀል ከእነዚህ ቅጣቶች አንዱ የሚወሰንበት እንደሆነ ወይም  ጥፋተኛው ከዚህ ቀደም ያልተቀጣ ሆኖ በተከሰሰበት ወንጀል ከአምስት አመት የበለጠ የጽኑ እሥራት ቅጣት የሚፈረድበት እንደሆነ ነው በማለት የወንጀል ሕጉ አንቀጽ 194 ድንጋጌ ላይ በዝርዝር ተመልክቷል፡፡ በሕጉ ከተመለከቱት ከእነኚህ ሁኔታዎች ውጪ ጥፋተኛው ጥፋተኛ የተባለበት የወንጀል ዓይነት በመንግስት ላይ የሚያመጣው አሉታዊ ተጽእኖ እንዲገደብ ለማድረግ የሚያስችል ምክንያት ነው ተብሎ በሕጉ ላይ አልተገለጸም፡፡ በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 196/2 የወንጀሉ ከባድነት / the gravity of the crime /፤ በወንጀል ድርጊት መደጋገም ሊያደርስ የሚችለውን ጉዳት እና በጥፋተኛው ላይ ሊጣልበት የሚችለው እምነት ከግምት ውስጥ መግባት አለበት የሚባለው ፍ/ቤቱ ቅጣቱ እንዲገደብ አቋም ከያዘ በኋላ ቅጣቱ ተገድቦ የሚቆይበትን የፈተና ጊዜ ለመወሰን / ….. to fix the probation period ….. / እንጂ ቅጣቱን ለመገደብ ሊሟላ ይገባል ተብሎ የተቀመጠ ቅድመ-ሁኔታ አይደለም፡፡

በመሠረቱ ከባድ ወንጀሎች ከፍተኛ ቅጣት የሚያስከትሉ ናቸው፡፡ የወንጀል ሕጉ አንቀጽ 194/1/ለ ድንጋጌም ይህንኑ ታሳቢ በማድረግ ጥፋተኛው አሁን በተከሰሰበት ወንጀል ከአምስት ዓመት የበለጠ የጽኑ እሥራት ቅጣት የሚፈረድበት እንደሆነ ቅጣትን ማገድ አይቻልም በማለት በግልጽ መደንገጉ ከመነሻውም ቢሆን ከባድ ወንጀል የፈጸመ ወንጀለኛ በሚጣልበት ከፍተኛ የቅጣት መጠን ምክንያት ቅጣት ሊገደብለት የማይችል በመሆኑ በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 196/2 ላይ የተገለጸው 'የወንጀሉ ክብደት' የሚለው ቃል ለፈተናው ጊዜ አወሳሰን ታሳቢ የሚደረግ መሆኑን የሚያሳይ እንጂ ቅጣቱን ለመገደብ በመመዘኛነት የተቀመጠ አለመሆኑን የሚያሳይ ነው፡፡

በሌላ በኩል በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 197 የተመለከቱት ቅድመ-ሁኔታዎች ፈተና የሚሰጥባቸውን ሁኔታዎች እንደሆኑ ከድንጋጌው ርዕስ መገንዘብ የሚቻል ሲሆን እነኚህ ሁኔታዎች መሟላት አለመሟላታቸው ሊረጋገጥ የሚችለው ፍ/ቤቱ ከተከሳሹ የቀድሞ ታሪክ፣ የጠባዩ እና የዓመሉ አካሄድ በመነሳት ቅጣቱን መገደብ እንዳለበት ሲያምን እና ጥፋተኛው በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 197 ላይ የተመለከቱትን ቅድመ-ሁኔታዎች እንደሚያሟላ ማረጋገጫ እንዲሰጥ በማድረግ እንደሆነ ከወንጀል ሕጉ አንቀጽ 192፣196/1 እና 197 ድንጋጌዎች ጣምራ ንባብ መገንዘብ ይቻላል፡፡ ጥፋተኛው በድንጋጌው የተመለከቱትን ቅድመ- ሁኔታዎች ማሟላት አለሟሟላቱን ማረጋገጥ የሚቻለውም ጥፋተኛው ራሱ በራሱ ተነሳሽነት በሕጉ የተመለከቱትን ቅድመ-ሁኔታዎች ያሟላ ሆኖ በተገኘ ጊዜ ወይም ፍ/ቤቱ ጥፋተኛው በሕጉ የተቀመጡትን ቅድመ-ሁኔታዎች እንዲያሟላ እድል በሰጠው ጊዜ ነው፡፡

ፍ/ቤቱ በጥፋተኛው ላይ የሚጣለውን ቅጣት ለጊዜው ማገድ ለወደፊቱ ጥፋቱን ለማረም እንደሚችል ሊያምን ወይም ላያምን የሚችለው የጥፋተኛውን የቀድሞ ታሪኩ፣ የጠባዩ እና የዓመሉ አካሄድ አስመልክቶ በችሎቱ የተረጋገጡትን እውነታዎች መነሻ በማድረግ ሲሆን ፍ/ቤቶች በሕግ እና በተገቢ ምክንያት የተደገፈ ውሳኔ መስጠት ያለባቸው በመሆኑ አመልካች ቅጣቱን ለማስገደብ ያቀረባቸው ምክንያቶች ፍ/ቤቱን የሚያሳምኑ ናቸው ወይም አይደለም ለማለት ሕግን መሠረት በማድረግ እና አግባብነት ያለውን ምክንያት በመስጠት ሊሆን ይገባል፡፡

በተያዘዉ ጉዳይ አመልካች ድርጊቱን ማመኑ እና በፈጸመው ድርጊት ምክንያት የተጸጸተ መሆኑ፣ የቀድሞ ጥፋተኝነት ሪኮርድ የሌለበት መሆኑ፣ የቤተሰብ አስተዳዳሪ መሆኑ በስር ፍ/ቤት የተረጋገጠ ፍሬነገር ነው፡፡ እነኚህ ሁኔታዎች የተከሳሹን የቀድሞ ታሪክ፣ የጠባዩን እና የዓመሉን አካሄድ ለመመዘን የሚያስችሉ እና ቅጣቱ ቢገደብ የአመልካችን ጠባይ ለማረምና ለማሻሻል እንዲሁም ወደ መደበኛ ማህበራዊ ኑሮው ለመመለስ የሚያስችሉ አሳማኝ ሁኔታዎች ናቸው፡፡

በያዝነው ጉዳይ የስር ፍ/ቤት የአመልካችን የገደብ ጥያቄ በዝምታ ከማለፉ በቀር የአመልካችን የገደብ ጥያቄ ለማስከልከል የሚያስችል ሕጋዊ ምክንያት ያለ ስለመሆኑ በውሳኔው ላይ አልገለጸም፡፡ አብላጫው ድምጽ አመልካች ጥፋተኛ የተባለበት የወንጀል ዓይነት የመንግስት ገቢን በመሰብሰብ አቅም ላይ ያለዉን አሉታዊ ተጽእኖ እና በወ/ሕ/አንቀጽ 197 የተመለከቱ መስፈርቶች በአብዛኛዉ ተሟልተዉ ተገኝቷል በሚል ቅጣቱ ሳይፈጸም ቢቀር ለአመልካችም ሆነ በተመሳሳይ ድርጊት ላይ ሌሎች እንዳይሳተፉ ከማድረግ አንጻር ቅጣት ማገዱ መልካም ዉጤት ያመጣል የሚል እምነት ለመጣል አልቻለም ከሚል መደምደሚያ ላይ የደረሰ ቢሆንም ይህ ምክንያት በሕጉ ቅጣትን እንዳይገደብ ለማድረግ የሚያስችል ምክንያት ነው ተብሎ ያልተገለጸ ከመሆኑ አኳያ የስር ፍ/ቤት ቅጣቱ እንዳይገደብ የሚያደርጉ ሕጋዊ ምክንያቶች ያሉ መሆን አለመሆኑን አረጋግጦ በምክንያት የተደገፈ ውሳኔ እንዲሰጥ ጉዳዩ ሊመለስለት ይገባ ነበር በማለት በሀሳብ ተለይቻለሁ፡፡

በመሆኑም የእነኚህን ሁኔታዎች የአመልካቹን የቀድሞ ታሪክ፣ የጠባዩን እና የዓመሉን አካሄድ ለመመዘን የሚያስችሉ አሳማኝ እና በአመልካች ላይ የተጣለው ቅጣት ታግዶ ቢቆይ ዳግም ጥፋት ከመፈጸም እንዲቆጠብ ለማድረግ የሚያስችሉ ሁኔታዎች ሆነው ሳለ አመልካች በራሱ ተነሳሽነት በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 197 ላይ የተመለከቱትን ቅድመ ሁኔታዎች አሟልቶ ከሆነ ይህንኑ መሠረት በማድረግ ወይም እንዲያሟላ በማድረግ ቅጣቱን መገደብ ሲገባው በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 194 ቅጣት እንዳይገደብ ለማድረግ የሚያስችሉ ሁኔታዎች ውስጥ ያልተቀመጠውን ሁኔታ መሠረት በማድረግ ከተፈጸመው ወንጀል ጋር ሲታይ ቅጣቱን ለመገደብ አላመንኩበትም  በማለት የአመልካችን የገደብ ጥያቄ ውድቅ በማድረግ የሰጠው ውሳኔ መታረም ይገባው ነበር በማለት በሀሳብ ተለይቻለሁ፡፡

የማይነበብ የአንድ ዳኛ ፊርማ አለበት

ሡ/ኃ

መዝገቡ ከተዘጋ በኃላ ሊቀርብ የቻለው ይህ ችሎት በዚሁ መዝገብ ግንቦት 14 ቀን 2011 ዓ.ም በሰጠው ውሳኔ በልዩነት ድምጽ ላይ በመጨረሻው ፓራግራፍ/ አንቀጽ/ የተካተተው ሀሳብ በአጻጻፍ ስሕተት የገባ በመሆኑ ይህንኑ ለማስተካከል ነው፡፡ በመሆኑም በልዩነት ድምጽ ላይ በመጨረሻው ፓራግርፍ/ አንቀጽ/ የተካተተው ሀሳብ በአጻጻፍ ስሕተት የገባ በመሆኑ ከልዩነት ድምጽ እንዲወጣ በሚል ተስተከክሏል በዚሁ መሠረት ይጻፍ፡፡

ግንቦት 29 ቀን 2011 ዓ.ም.

የሰ/መ/ቁ 168067

**ዳኞች፡-** ብርሃኑ አመነው

በዕውቀት በላይ

እንዳሻዉ አዳነ

ሃይሉ ነጋሽ

እትመት አሠፋ

**አመልካቾች፡-** ሰይድ አሊ አበጋዝ

**ተጠሪ፡-** የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የንግድ እና ሸማቾች ዓቃቤ ሕግ

መዝገቡ የተቀጠረው መርምሮ ፍርድ ለመስጠት ነው፡፡ በመሆኑም መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍርድ**

ይህ የሰበር አቤቱታ ሊቀርብ የቻለው አመልካች ታህሳስ 24 ቀን 2011 ዓ.ም ጽፎ ባቀረበው የሰበር አቤቱታ በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት በኦሮሞ ብሔረሠብ አስተዳደር ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 0202449 ሐምሌ 30 ቀን 2010 ዓ.ም የሰጠው የጥፋተኝነት እና የቅጣት ውሳኔ በማጽናት የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁ 026018 ጥቅምት 05 ቀን 2011 ዓ.ም እና የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ 0323711 ጥቅምት 22 ቀን 2011 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለቱ ነው፡፡

ለሰበር አቤቱታው መነሻ የሆነው ጉዳይ የወንጀል ክርክርን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት በኦሮሞ ብሔረሠብ አስተዳደር ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ነው፡፡የአሁን ተጠሪ በአሁን አመልካች ላይ በስር ፍ/ቤት ያቀረባቸው ክሶች ሁለት ሲሆኑ ይዘታቸውም 1ኛ ክስ አመልካች የንግድ ፈቃድ ምዝገባ አዋጅ ቁጥር 980/2008 አንቀጽ 49/2 ድንጋጌን በመተላለፍ በቀን 01/09/2009 ዓ.ም ከምሽቱ በግምት 1፡30 ሰዓት በባቲ ወረዳ አስተዳደር 015 ሞቱማ ቀበሌ ልዩ ቦታው ኡላኡላ በሚባል ቦታ ግምቱ ብር 58500 የሆነ 9 ጥቅል ጂኦመምብሬን የሰሌዳ ቁጥሩ ኢ.አ-3-30687 በሆነ አይሱዙ መኪና በመጫን ለመሸጥ ኬላ ጥሶ ይዞ ሲሄድ በሕብረተሰቡ እገዛ መኪናውን በማስቆም እጅ ከፍንጅ ያለንግድ ፈቃድ ንግድ መፈጸም ወንጀል ተከሷል የሚል ሲሆን 2ኛ ክስ ደግሞ በአሁን አመልካች እና በስር 2ኛ እና 3ኛ ተከሳሾች በነበሩት ላይ የቀረበ ሲሆን ይዘቱም፡- ተከሳሾች

የወንጀል ሕግ አንቀጽ 32/1/ሀ እና የንግድ ሕግ አንቀጽ 118/1/ እና የነጋዴዎች እና የሸማቾች ጥበቃ አዋጅ ቁጥር 813/2006 አንቀጽ 24/3/ እና 43/4/ ድንጋጌን በመተላለፍ በቀን 13/09/2009 ዓ.ም በባቲ ወረዳ አስተዳደር 015 ሞቱማ ቀበሌ ልዩ ቦታው ኡላኡላ በሚባል ቦታ አመልካች ባለሀብት በመሆን፤ የስር 2ኛ ተከሳሽ የሰሌዳ ቁጥሩ አ.አ 3-30687 የሆነው መኪና አሽከርካሪ በመሆን 3ኛ ተከሳሽ ደግሞ የመኪናው ረዳት በመሆነ ጂኦመምብሬን 9 ጥቅል ግምቱ ብር 58500 የሚያወጣ የማዘዋወር ወይም የመደበቅ ወንጀል ፈጽመዋል የሚል ነው፡፡

ክሱ አመልካቾች እንዲረዱት ከተደረገ በኋላ አመልካች ድርጊቱን የፈጸመ መሆኑን ሆኖም የተያዘው ዕቃ የወንድሙ መሆኑን እና ንግድ ፈቃድ ያለው መሆኑን በመግለጽ ጥፋተኛ አይደለሁም በማለት የተከራከረ ሲሆን ሌሎቹ ተከሳሾችም ድርጊቱን የፈጸሙ መሆኑን ሆኖም አመልካች ንግድ ፈቃድ እንዳለው ስለገለጸላቸው ዕቃውን የጫኑ መሆኑን በመግለጽ ጥፋተኛ አይደለንም በማለት ተከራክረዋል፡፡

ፍ/ቤቱም የዓቃቤ ሕግን ማስረጃዎች ከሰማ በኋላ የዓቃቤ ሕግ ምስክሮች 1ኛ ክስን በተመለከተ መኪናው ጭኖ እየሄደ መያዛቸውን እንጂ እየነገደበት መሆኑን ያላስረዱ በመሆኑ አመልካች ከ1ኛ ክስ መከላከል ሳያስፈልገው በነጻ ተሰናብቷል፤ 2ኛ ክስን በተመለከተ ግን ተከሳሾች ድርጊቱን ስለመፈጸማቸው በዓቃቤ ሕግ ማስረጃ ስለተረጋገጠባቸው እንዲከላከሉ ሲል ብይን ሰጥቷል፡፡ ተከሳሾችም ክሱን ይከላከልልናል ያሉትን ማስረጃ አስቀርበው አሰምተዋል፡፡ ፍ/ቤቱም የግራቀኙን ማስረጃ ከመረመረ በኋላ የአመልካች መከላከያ ምስክሮች የተያዘው ጅኦመምብሬን የአመልካች ወንድም መሆኑን እና አምጣልኝ ተብሎ የተላከ እና ይዞ ሲመለስ የተያዘ መሆኑን፤ ወንድሙ የሚነግድበት እና ንግድ ፈቃድ ይዞ ፍ/ቤት በመሄድ ሲከራከር እንደነበር መመስከራቸው ምስክሮቹ ሀሰተኛ እና ተደራጅተው የቀረቡ መሆኑን መረዳት ይቻላል፤ አመልካች የዕቃው ባለንብረት በመሆን እና ንግድ ፈቃድ ስለሌለው የተያዘውን ዕቃ ወደ ፖሊስ እንደወሰዱት የዓቃቤ ሕግ ምስክሮች የመሰከሩ በመሆኑ ተከሳሾች በአዋጅ ቁጥር 813/2006 አንቀጽ 24/3 እና 43/3 መሠረት ጥፋተኛ ብሏቸዋል፡፡ ቅጣቱንም በቅጣት አወሳሰን መመሪያው መሠረት በማስላት የእስር ቅጣቱን ወደ ገንዘብ ቅጣት በመለወጥ እና ከገንዘብ ቅጣቱ ጋር በመደመር አመልካች በብር 1500 የገንዘብ መቀጮ የስር ተከሳሾች ደግሞ እያንዳንዳቸው በብር 2000 የገንዘብ መቀጮ እንዲቀጡ እና የተያዘው 9 ጥቅል ጂኦመምብሬን ተሸጦ ለመንግስት ገቢ እንዲሆን ሲል ወስኗል፡፡ አመልካች ይህን ውሳኔ በመቃወም በየደረጃው ላሉ የክልሉ ፍ/ቤቶች አቤቱታ ያቀረበ ቢሆንም አቤቱታው ተቀባይነት አላገኘም፡፡

የሰበር አቤቱታው የቀረበው ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈጽሞበታል በሚል ሲሆን ይዘቱም አመልካች የተከሰሰኩባቸው የአዋጅ ቁጥር 813/2006 አንቀጽ 24/3/ እና 43/4/ ድንጋጌዎች ተፈጻሚ የሚሆኑት ነጋዴ በሆነ ሰው ላይ ነው፤ አመልካች ከ1ኛው ክስ

ነጻ የሆነው ነጋዴ አይደለም ወይም የንግድ ስራ አልሰራም ተብሎ ነው፤ በመሆኑም አመልካች ነጋዴ ሳይሆን ጥፋተኛ መባሉ ከሕግ ውጪ ነው፤ በአዋጁ አንቀጽ 24/4/ ድንጋጌ መሠረት ወንጀል የሆነው ተግባር እጥረት ያለበት መሆኑ በንግድ ሚኒስቴር በወጣ የሕዝብ ማስታወቂያ የተገለጸ የንግድ ዕቃን ለግል ወይም ለቤተሰብ ፍጆታ ከሚውል በላይ በሆነ መጠን ከተፈቀደው የስርጭት መስመር ውጪ ሚንንዝ ወይም እንዲንንዝ ማድረግ ነው፤ ዓቃቤ ሕግ ባቀረበው ክስ ጂኦሜምብሬን የተባለው ዕቃ የንግድ ሚኒስቴር ባወጣው ማስታወቂያ እጥረት ያለበት ስለመሆኑ መገለጹን አልጠቀሰም ይህንንም አላስረዳም፤ ዕቃውም የተፈቀደ የስርጭት መስመር ያለው መሆኑ እና ከዚህ ከተፈቀደው መስመር ውጪ ሲንንዝ የነበረ መሆኑን አላረጋገጠም፤ በመሆኑም አመልካች በተገለጸው ድንጋጌ መሠረት ጥፋተኛ ልባል አይገባም፤ የአመልካች መከላከያ ምስክሮች ዕቃው የአመልካች ወንድም ንብረት መሆኑን እና ዕቃውን ወደ ወንድሙ እየወሰድኩ የነበረ መሆኑን በሚገባ አስረድተው ሳለ ፍ/ቤቱ ምስክርነቱ በሀሰት የተሰጠ ነው በማለት ውድቅ ማድረጉ አግባብ አይደለም፤ በመሆኑም የስር ፍ/ቤት አመልካችን ጥፋተኛ በማለት የሰጠው የቅጣት ውሳኔ እና የንብረት ውርስ ውሳኔ በመሠረታዊ የሆነ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል  የሚል ነው፡፡

የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ የስር ፍ/ቤት በአሁን አመልካች ላይ በቀረበው 1ኛ ክስ ጭኖ መሄዱ እንጂ እየነገደበት መሆኑን አልተረጋገጠም ተብሎ ነጻ ከተባለ በኋላ በ2ኛው ክስ ጥፋተኛ የመባሉን አግባብነት ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ በዚህ ችሎት እንዲታይ ተደርጓል፡፡ ለተጠሪዎች ጥሪ ተደርጎም ግራቀኙ በጽሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

የተጠሪ መልስ ይዘት በአጭሩ፦ ጂኦመምብሬን የንግድ ሚኒስቴር በገበያ ላይ እጥረት አለባቸው በሚል በገለጻቸው እና ዋጋ እና የስርጭት ሁኔታቸውን በወሰናቸው የንግድ ዕቃዎች ውስጥ የተካተተ አይደለም፤ ይህ ዕቃ ምንም እንኳን በየደረጃው ያለ የሚመለከተው የአስተዳደር አካል ለታለመለት ዓላማ ብቻ እንዲውል በሚል እንዲሁ ክትትል እና ቁጥጥር የሚያደርግበት ቢሆንም በን/ው/ሽ/ጥ/አ/ቁ 813/2006 አንቀጽ 25 እና 26 መሠረት የንግድ ሚኒስቴር ጥናት አድርጎ ዋጋቸው እና የስርጭት ሁኔታቸው እንዲወሰን ለሚንስትሮች ምክር ቤት አቅርቦ በማስፈቀድ በማስታወቂያ በገለጻቸው የንግድ ዕቃዎች ውስጥ የተካተተ ባለመሆኑ እና የአዋጁን አንቀጽ 24 በመጥቀስ የወንጀል ሀላፊነትን መወሰን የማይቻል በመሆኑ ይህ ችሎት የስር ፍ/ቤት ውሳኔን በመሻር የመሰለውን ቢወስን አንቃወምም የሚል ነው፡፡ አመልካችም የሰበር አቤቱታውን በማጠናከር የመልስ መልስ ሰጥቷል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ በአጭሩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ፤ ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር እና በሰበር አጣሪው ችሎት ሊጣራ ይገባል ተብሎ ከተያዘው ነጥብ ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው መርምሮታል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የሚቻለው የአመልካች አቤቱታ የቀረበው በሁለተኛው ክስ ጥፋተኛ መባሉን አስመልክቶ ሲሆን የክሱ ይዘትም አዋጅ ቁጥር 813/2006 አንቀጽ 24/3/ እና 43/4/ በመተላለፍ በቀን 13/09/2009 ዓ.ም ከባቲ ወረዳ አስተዳደር 015 ሞቱማ ቀበሌ ልዩ ቦታው ኡላኡላ ከሚባል ቦታ አመልካች ባለሀብት በመሆን በሰሌዳ ቁጥሩ አ.አ 3-30687 በሆነ መኪና 9 ጥቅል ጂኦመምብሬን ግምቱ ብር 58500 የሚያወጣ አዘዋውሯል ወይም የመደበቅ ወንጀል ፈጽመዋል የሚል በመሆኑ አመልካች የወንጀል ድርጊቱንን ፈጽመዋል ተብሎ አዋጅ ቁጥር 813/2006 አንቀጽ 24/3/ እና 43/4/ በመተላለፍ ተጠያቂ መደረጋቸው በአግባቡ ነው? ወይስ አይደለም? የሚለው መሆኑን ነው፡፡

በመሰረቱ አንድ ሰው ወንጀል አደረገ የሚባለው ወንጀሉን የሚቋቋሙት ሕጋዊ፣ ግዙፋዊ እና ሞራላዊ ፍሬ ነገሮች በአንድነት ተሟልተው ሲገኙ ብቻ መሆኑ በወንጀል ሕግ አንቀጽ 23 (2) ስር ተደንግጎ የሚገኝ ሲሆን ማንም ሰው በዋና ወንጀል አድራጊነት ወንጀል እንዳደረገ ተቆጥሮ የሚቀጣው በቀጥታ ወይም በእጅ አዙር ወንጀሉን ያደረገ በሆነ ጊዜ ወይም ወንጀሉን እርሱ በቀጥታ ባያደርገውም እንኳን በመላ አሳቡና አድራጎቱ በወንጀሉ ድርጊትና በሚሰጠው ውጤት ሙሉ ተካፋይ በመሆን ድርጊቱን የራሱ ያደረገ በሆነ ጊዜ ስለመሆኑም በወንጀል ሕግ አንቀጽ 32(1) ስር ተደንግጓል፡፡ በወንጀል ጉዳይ የሚቀርብ የክስ ማመልከቻ ተከሳሹ የተከሰሰበትን ወንጀል እንዲሁም የወንጀሉ መሰረታዊ ፍሬ ነገርና ሁኔታዎች የተገለጹበት ሊሆን እንደሚገባ እና ስለ ወንጀሉና ስለሁኔታው የሚሰጠው ዝርዝር መግለጫ ተከሳሹ ፈጸመ የተባለውን ተግባር ወንጀል ከሚያደርገው ሕግ አነጋገር ጋር በጣም የተቀራረበ መሆን እንደሚገባው በወ/መ/ሕ/ስ/ስ/ቁ. 111 እና 112 ድንጋጌዎች ስር ተደንግጎ ይገኛል፡፡ ይህም ከሳሹን ወገን በወ/ሕ/አ. 23 (2) ስር የተመለከቱት የወንጀል ማቋቋሚያ ፍሬ ነገሮች ተሟልተው መገኘታቸውን ለማስረዳት እንዲያስችለው መሆኑን የሚያስገነዝብ ሲሆን ከሳሽ ወገን በክሱ መሰረት የማስረዳት ግዴታ ተወጥቷል ሊባል የሚችለውም በወ/መ/ሕ/ስ/ስ/ቁ. 111 እና 112 ድንጋጌዎች መሰረት አዘጋጅቶ ባቀረበው የክስ ማመልከቻ መሰረት ተከሳሹ ወንጀል መፈጸሙን በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁጥር 141 በተመለተከው የማስረጃ መለኪያ መሰረት ማስረዳት በቻለ ጊዜ ነው፡፡በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 142 ስር የተመለከተው ድንጋጌ ይዘት ሲታይም ክሱ የቀረበለት ፍ/ቤትም ተከሳሹ መከላከያ ማስረጃ አቅርቦ ክሱን እንዲከላከል ትዕዛዝ ሊሰጥ የሚችለው ከሳሽ ወገን ያቀረበው ማስረጃ ተከሳሹን ጥፋተኛ የሚያደርገው መሆኑን በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁጥር 141 በተመለከተው የማስረጃ መለኪያ መርህ መሰረት በበቂና አሳማኝ ሁኔታ አስረድቶ ሲገኝ መሆኑን ያስገነዝባል፡፡

በያዝነው ጉዳይ በመሰረታዊነት በአዋጅ ቁጥር 813/2006 አንቀጽ 24/3/ እና 43/4/ መሰረት ድርጊት ፈጻሚውን ሊያስጠይቅ የሚችለው ማንኛውም የንግድ ዕቃን ከመደበኛውን የግብይት አሰራር ውጭ በማናቸውም ማጓጓዣ ከተፈቀደው የስርጭት መስመር ውጭ ሲጓጓዝ ከተገኘ እንደተከማቸ ወይም እንደተደበቀ የንግድ ዕቃ የሚቆጠር በመሆኑ ይህንን ሲያጓጓዝ የተገኘ ነጋዴ መሆን ይገባዋል፡፡ ከዚህ አንጻር የወንጀሉ ፍሬ ነገር የሆኑትን አመልካች ጂኦሜምብሬን የተባለው ዕቃ የንግድ ዕቃ

መሆኑን አለመሆኑን፤ ከመደበኛው የግብይት አሰራር ውጭ ሲያጓጓዝ የተያዘ ስለመሆኑ በስር ፍርድ ቤት አልተረጋገጠም አመልካችና ተጠሪም በዚሁ ፍርድ ቤት ባደረጉት የጽሁፍ ክርክር የንግድ ሚኒስቴር ባወጣው ማስታወቂያ እጥረት ያለበት ስለመሆኑ አለመገለጹን፤ ዕቃውም የተፈቀደ የስርጭት መስመር ያለው መሆን አለመሆኑንና ከዚህ መስመር ውጪ ሲጓጓዝ የነበረ መሆኑን አለመረጋገጡን ገልጸዋል፡፡ ይህም የሚያመለክተው ወንጀሉን የሚቋቋሙት ሕጋዊ፣ ግዙፋዊ እና ሞራላዊ ፍሬ ነገሮች ተሟልተው አለመገኘታቸውን ነው፡፡

በመሆኑም ተጠሪ አዋጅ ቁጥር 813/2006 አንቀጽ 24/3/ እና 43/4/ ይዘትና መንፈስ መሰረት የማስረዳት ግዴታውን ባልተወጣበት ሁኔታ አመልካች እንዲከላከል መደረጉም ሆነ የመከላከያ ማስረጃዎቻቸው ከተሰሙ በኃላም አልተከላከለም ተብሎ በወንጀሉ ጥፋተኛ ተደርገው እንዲቀጡ መወሰኑ ከወንጀል ሕጉ አንቀጽ 23(2) እና በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁጥር 141 ድንጋጌ ስር ከተመለከተው የማስረጃ ምዘና መርህ ጋር የማይሄድ ሁኖ አግኝተናል፡፡ በዚህም ምክንያት የበታች ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ያለበት በመሆኑ ተከታዩን ወስናል፡፡

**<u>ውሳኔ</u>**

1. በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት በኦሮሞ ብሔረሠብ አስተዳደር ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 0202449 ሐምሌ 30 ቀን 2010 ዓ.ም የሰጠው የጥፋተኝነት እና የቅጣት ውሳኔ በማጽናት የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁ 026018 ጥቅምት 05 ቀን 2011 ዓ.ም እና የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ 0323711 ጥቅምት 22 ቀን 2011 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ በወ/መ/ስ/ስ/ሕ/ቁ 195/2/ለ/2 መሠረት ተሽሯል፡፡
2. አመልካቾች አዋጅ ቁጥር 813/2006 አንቀጽ 24/3/ እና 43/4/ ተላልፏል በማለት በቀረበበት 2ኛ ክስ ጥፋተኛ አይደለም ብለናል፡፡
3. በአመልካቾች ላይ የተሰጠው የጥፋተኝነትና የቅጣት ወሳኔ የተሻረ በመሆኑ የተወሰነበት የገንዘብ መቀጮ ብር 1500 / አንድ ሺህ አምስት መቶ/ ለመንግስት ገቢ ከሆነ ተመላሽ እንዲሆን ብለናል ፡፡ ይጻፍ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

ሳ/ፀ የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

የሰ/መ/ቁ. 163069

ሕዳር 26 ቀን 2012 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** እትመት አሠፋ

ጳውሎስ ኦርሺሶ

ፀሐይ መንክር

መላኩ ካሣዬ

እስቲበል አንዱዓለም

አመልካች፡- የፌዴራል ጠቅላይ ዓቃቤሕግ አልቀረበም

ተጠሪዎች፡- 1.ክኤሳድ ጠቅላላ የንግድ ሥራ ኃላ/የተ/የግ/ማሕበር ⎫ ጠበቃቸው ወርቅነህ በረደድ

2. አቶ ሀይሉ አስገዶም ⎭ ቀረቡ ::

3. አቶ ክብሮም ሀይሉ አስገዶም - ቀረቡ::

መዝገቡ ለምርመራ የተቀጠረ ነው፡፡ በመሆኑም መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

የሰበር አቤቱታው ሊቀርብ የቻለው አመልካች ነሐሴ 23 ቀን 2010 ዓ.ም ጽፎ ባቀረበው የሰበር አቤቱታ የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ.ቁ 247746 ጥቅምት 22 ቀን 2010 ዓ.ም ተጠሪዎችን ከቀረበባቸው ክስ መከላከል ሳያስፈልጋቸው በነጻ በማሰናበት የሰጠው ብይን እና ይህንኑ ብይን በማጽናት የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 209526 ሠኔ 19 ቀን 2010 ዓ.ም የሰጠው ብይን መሠረታዊ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት አቤቱታ በማቅረቡ ነው፡፡

የአሁን አመልካች በአሁን ተጠሪዎች ላይ ያቀረባቸወ ክሶች ሁለት ሲሆኑ ክሳቸውም፡-

<u>በ1ኛ ክስ፡-</u> የአሁን 1ኛ ተጠሪ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 34/1 እና የጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 859/06 አንቀጽ 169/2 እና 173 ድንጋጌን በመተላለፍ ከቻይና ሐገር በዲክላራሲዮን ቁጥር ሲ-2195/2016 በቀን 12/12/2008 ዓ.ም እና በደረሰኝ ቁጥር ኤ.ኤች 16ኤ081 በቀን 20/10/08 ዓ.ም ብዛቱ 6372 ደርዘን ኦ.ኤል ፕላስቲክ ጆግ ወደ ሐገር ውስጥ ለማስገባት አሳውቆ የነበረ ሲሆን በኢትዮጲያ ገቢዎች እና ጉምሩክ ባለስልጣን የአዲስአበባ ቃሊቲ ጉምሩክ ቅርንጫች ጽ/ቤት በቀን 18/12/08 ዓ.ም በአካል ሲፈተሸ

በሰነድ ላይ ያልተገለጸ ብዛቱ 3186 ደርዘን ኩባያ በመገኘቱ ተደብቀው የተገኙት የዕቃዎች ዋጋ 11,182.86 ዶላር ወይም 247,646.67 ብር መሆኑን እና ይህም በሰነዱ ከተገለጸው አጠቃላይ የዕቃው ዋጋ 11,278.44 ዶላር ወይም 333001.43 ብር ጋር ሲነጻጸር የዋጋ ልዩነቱ ከ50% በላይ ወይም 99% ሆኖ በመገኘቱ በፈጸመው የማጭበርበር ወንጀል ተከሷል የሚል ነው፡፡

2ኛ ክስ፡- የአሁን 2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች የወንጀል ሕግ አንቀጽ 34/1 እና የጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 859/2006 አንቀጽ 169/2 ድንጋጌን በመተላለፍ 2ኛ ተጠሪ የ1ኛ ተጠሪ ማሕበር ስራ አስኪያጅ በመሆን፤ 3ኛ ተጠሪ ደግሞ በውክልና ማሕበሩን ሲመሩ ተገቢውን የአሰራር ስርዓት ባለመዘርጋት የድርጅቱን ጥቅም በሕገወጥ መንገድ ለመምራት በማሰብ 1ኛ ተጠሪ በ1ኛ ክስ የተገለጸውን ወንጀል እንዲፈጽም በማድረጋቸው በፈጸሙት የማጭበርበር ወንጀል ተከሰዋል የሚል ነው፡፡

ጉዳዩ የቀረበለት የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ተጠሪዎች ድርጊቱን አልፈጸምንም ብለው ክደው በመከራከራቸው የአመልካችን ማስረጃዎች ከሰማ በኋላ በላኪው በኩል የተጠየቀው ጆግ ብቻ እንጂ ኩባያ የማይጨምር በመሆኑ ላኪው ያልተጠየቀውን ኩባያ በመላኩ በስህተት መሆኑን በመግለጽ የእርማት ደብዳቤ ወደ ሐገር ውስጥ ተልኮ በባለስልጣኑ የወንጀል ምርመራ ክፍል የደረሰ ስለመሆኑ በዓቃቤሕግ ምስክርም ተገልጿል፤ በአካላዊ ፍተሻ የተገኙት ጆጎች መጠን ደረጃ ልዩነት ሳይኖራቸው ግማሽ በሚሆን መጠን ላይ ባሉት ጆጎች ውስጥ አራር አራት ኩባያዎች መገኘታቸው በተከሳሽም ሆን ብለው ኩባያዎቹን ደብቆ ለማስገባት የወንጀል ሐሳብ የነበራቸው መሆኑን አያሳይም፤ ከድርጅት ሀላፊዎች አንጻር በ2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች ላይ የቀረበው ክስ የሚነቀፍ ባይሆንም ልዩነቱ 99% መሆኑ ክስ የቀረበበት ዕቃ በስህተት ምክንያት የተፈጠረ መሆኑን የሚጠቁም እንጂ አስቀድሞ በሰነዶች ያልተጠቀሱትን ኩባያዎች በድብቅ ወደ ሐገር ውስጥ ለማስገባት ሃሳብ የነበረቻው መሆኑ በቂ ማስረጃ ባለመቅረቡ እና ተገውን ቀረጥ እና ታክስ በማስከፈል እና አስፈላጊውን አስተዳደራዊ እርምጃ መውሰድ ተገቢ በመሆኑ እና በተከሳሾች ላይ በወንጀል ተጠያቂነት ረገድ ጠንካራ በቂ እና አሳማኝ ማስረጃ በሌለበት ሁኔታ የወንጀል ተጠያቂ ለማድረግ የሚያስችል ሁኔታ የለም በማለት ተጠሪዎችን በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 141 መሠረት ከቀረበባቸው ክስ በነጻ አሰናብቷቸዋል፡፡ አመልካች ይህን ውሳኔ በመቃወም ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የይግባኝ አቤቱታ ያቀረበ ቢሆንም አቤቱታው ተቀባይነት አላገኘም፡፡

የሰበር አቤቱታው የቀረበው ይህን ውሳኔ በመቃወም መሠረታዊ የሕግ ስሕተት ተፈጽሞበታል በሚል ሲሆን ይዘቱም፡- ወደ ሐገር ሲገባ ተደብቆ የተገኘው የዕቃ ዋጋ በሕጋዊ መንገድ ወደ ሐገር ከገቡት ዕቃዎች ዋጋ ጋር ሲነጻጸር 99% ባላይ መሆኑ ተረጋግጧል፤ ልዩነቱ ሊፈጠር የቻለውም በአካላዊ ፍተሻ በሕጋዊ ዕቃ ውስጥ ተደብቀው ብዛታቸው 3186 ኩባያዎች በጆጎቹ ውስጥ ተደብቆ የተገኘ መሆኑን አስረድተናል፤ ይህም የተጠሪዎችን ወንጀል የመፈጸም ሀሳብ ክፍል የሚያረጋግጥ ነው፤ የስር

ፍ/ቤት 1ኛ የዓቃቤሕግ ምስክር በወቅቱ 3ኛ ተጠሪ ዕቃው በስህተት እንደተላከላቸው በመግለጽ የእርምት ደብዳቤ ወደ ምርመራ ክፍል አስገብተው የነበረ መሆኑን ገልጿል ከማለት ውጪ ማስረጃው ቀርቦ የነበረ መሆን አለመሆኑን አላረጋገጠም፤ ላኪው ድርጅት ለትርፍ የሚሰራ ከመሆኑ አንጻር ይህን ያህል ልዩነት ያለውን ዕቃ ክፍያ ሳይፈጸምለት በስሕተት ይልካል ብሎ ድምዳሜ መውሰድ ተገቢነት የለውም ፤ ስሕተቱ መፈጸሙን በተመለከተም ከላኪው ድርጅት የተገለጸ ነገር የለም፤ ስሕተቱ ተፈጸመ ቢባል እንኳን ተጠሪዎች ወንጀል የመፈጸም ሀሳብ ባይኖራቸው ዕቃው ወደሐገር ውስጥ ገብቶ ከመፈተሹ በፊት ለባለስልጣን መስሪያ ቤቱ ያሳውቁ ነበር እንጂ ድርጊቱ መፈጸሙ ከታወቀባቸው በኋላ መከራከሪያ ሆኖ ሊቀርብ አይገባም የሚል ነው፡፡

የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ ተጠሪ ከውጪ ሐገር ወደ ሐገር ውስጥ ፕላስቲክ ጆግ ለማስገባት አሳውቆ ውስጡ ኩባያ መገኘቱ ባልተካደበት ሁኔታ ተጠሪዎች ክሱን እንዲከላከሉ ብይን ሳይሰጥ በነጻ የመሰናበታቸውን አግባብነት ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ በዚህ ችሎት እንዲታይ ተደርጓል፡፡ ለተጠሪዎች ጥሪ ተደርጎም ግራቀኙ በጽሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

የተጠሪዎች መልስ ይዘት በአጭሩ፡- እሽጉ በምስክሩ ፊት ሲከፈት ጉምሩክ አስተላላፊው በቦታው የነበረ ሲሆን ተጧዎች በቦታው አልነበሩም፤ ተጠሪዎች በቦታው የተገኙት ዕቃው ልዩነት ተገኝቶበታል ከተባለ በኋላ ነው፤ 3ኛ ተጠሪ በ1ኛ ተጠሪ ስም ያዘዙት ጆግ ብቻ እንደሆነ እና ኩባያውን እንደማያውቁት እና በስሕተት እንደተላከ ገልጸው የማስተካከያ ደብዳቤ ለባለስልጣኑ የወንጀል ምርመራ ገልጸዋል፤ 2ኛ ምስክርም በዲክላራሲዮን የተመዘገበው ዕቃ ጆግ ብቻ መሆኑን፤ በአካላዊ ፍተሻ ኩባያ የያዙ መሆናቸውን፤ የተገኘው ዕቃ አስቀድሞ ከተገለጸው ጋር ሲነጻጸር 99% መሆኑን ገልጸዋል፤ ተጠሪዎች በጆጎቹ ከለላነት ኩባያውን ወደ ሐገር ለማስገባት ሀሳብ እንደነበራቸው አልተረጋገጠም፤ ዕቃው ወደ ሐገር የገባው በስሕተት መሆኑን የአመልካች ምስክር አረጋግጧል፤ የተገኘው ጆግ መጠን ከታዘዘው ጋር ምንም የዓይነትም ሆነ የደረጃ ልዩነት ሳይኖራቸው ግማሽ መጠን ባለው ጆግ ውስጥ አራት አራት ኩባያ መገኘቱ በተጠሪዎች በኩል ኩባያ አለመታዘዙ እና በላኪው ስሕተት ምክንያት ችግሩ የተፈጠረ ስለመሆኑ የሚያሳይ ነው፤ አስመጪው የሚያስመጣቸው ዕቃዎች እንዲመጡለት የሚያደርገው ሐገር ውስጥ በመሆን ከባንክ ጋር በሚደረግ ግንኙነት ሲሆን ተጠሪዎች እንዲላክልን የጠየቅነው በግዢ ሰነድ የተመለከቱትን እቃዎች ብቻ ነው፤ ላኪው አገር የሚልከውን ምስክር ወረቀት እና የቅድመ ጭነት ምርመራ ሲቀርብ እና ዕቃው በአካል ሲፈተሽ ምን እንደመጣ ከምናውቅ በቀር አስቀድመን ልናውቅ የምንችልበት ሌላ መንገድ የለም፤ ዕቃው ተጠሪዎች ባለንበት አልታሸገም ፤ ተጠሪዎች የወንጀል ሀሳብ የነበረን ስለመሆኑ በክሱ እና በማስረጃው ባልተረጋገጠበት ሁኔታ ዕቃው በ1ኛ ተጠሪ ስም መምጣቱን መነሻ በማድረግ ተጠያቂ ልንሆን አይገባም የሚል ነው፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ በአጭሩ ከላይ የተገለጸው ነው። ይህ ችሎትም በሰበር አጣሪው ችሎት ሊጣራ ይገባዋል ተብሎ የተያዘውን ነጥብ ከግራቀኙ ክርክር፣ ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸው ሕጎች ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው መርምሮታል።

አመልካች በተጠሪዎች ላይ ክስ ያቀረበው ብዛታቸው 6372 ደርዘን የሆኑ ፕላስቲክ ጆግ ወደ ሐገር ውስጥ ለማስገባት አሳውቀው በባለስልጣን መስሪያ ቤቱ በተደረገው አካላዊ ፍተሻ በሰነድ ላይ ያልተገለጹ ብዛታቸው 3186 ደርዘን ኩባያዎች ተገኝተዋል፣ ተደብቀው የተገኙት የዕቃዎች ዋጋ 11,182.86 ዶላር ወይም 247,646.67 ብር መሆኑን እና ይህም በሰነዱ ከተገለጸው አጠቃላይ የዕቃው ዋጋ 11,278.44 ዶላር ወይም 333001.43 ብር ጋር ሲነጻጸር የዋጋ ልዩነቱ 99% ሆኖ በመገኘቱ በጉምሩክ ማጭበርበር ወንጀል ተጠያቂ ሊሆኑ ይገባል በሚል ሲሆን ዕቃው ከጂቡቲ ወደ ቃሊቲ ጉምሩክ ገብቶ እሸጉ ሲፈታ በተደረገው አካላዊ ፍተሻ በሰነድ ከተገለጸው ውጪ ብዛታቸው 3186 ኩባያዎች በጆጎቹ ውስጥ የተገኙ መሆኑ እና ተደብቀው የተገኙት የዕቃዎች ዋጋ 11,182.86 ዶላር ወይም 247,646.67 ብር መሆኑን እና ይህም በሰነዱ ከተገለጸው አጠቃላይ የዕቃው ዋጋ 11,278.44 ዶላር ወይም 333001.43 ብር ጋር ሲነጻጸር የዋጋ ልዩነቱ 99% በስር ፍ/ቤት የተረጋገጠ ፍሬነገር ነው።

የጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 859/06 አንቀጽ 13/4 ዲክላራሲዮኑ ከተመዘገበ በኋላ ለማጭበርበር በማሰብ ወይም በከባድ ቸልተኝነት የተፈጸመ ግድፈት በአዋጁ መሠረት ያስቀጣል በማለት ይደነግጋል። የአዋጁ አንቀጽ 169/2 ተደብቆ የተገኘው ዕቃ በዲክላራሲዮን ላይ ከተገለጸው ጠቅላላ ዋጋ 50% በላይ ሆኖ ከተገኘ ዕቃዎችን በመደበቅ ሕገወጥ በሆነ መንገድ ወደ ሐገር በማስገባት ወይም ከሐገር ለማስወጣት የሞከረ ማናቸውም ሰው ከአምስት ዓመት በማያንስ እና ከአስር ዓመት በማይበልጥ ጽኑ እሥራት እና ከብር 50,000 በማያንስ እና ከብር 100,000 በማይበልጥ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል በማለት ይደነግጋል።

የስር ፍ/ቤት ተጠሪዎችን መከላከል ሳያስፈልጋቸው በነጻ ያሰናበታቸው በላኪው በኩል የተጠየቀው ጆግ ብቻ እንጂ ኩባያ የማይጨምር በመሆኑ ላኪው ያልተጠየቀውን ኩባያ መላኩ በስህተት መሆኑን በመግለጽ የእርማት ደብዳቤ ወደ ሐገር ውስጥ ተልኮ በባለስልጣኑ የወንጀል ምርመራ ክፍል የደረሰ ስለመሆኑ በዓቃቤሕግ ምስክርም ተገልጿል፣ በአካላዊ ፍተሻ የተገኙት ጆጎች መጠን ደረጃ ልዩነት ሳይኖራቸው ግማሽ በሚሆን መጠን ላይ ባሉት ጆጎች ውስጥ አራር አራት ኩባያዎች መገኘታቸው በተከሳሻም ሆን ብለው ኩባያዎቹን ደብቆ ለማስገባት የወንጀል ሐሳብ የነበራቸው መሆኑን አያሳይም በማለት ነው። በመሠረቱ አንድን ዕቃ ከውጪ የሚያስመጣ ሰው ለጉምሩክ ሥርዓት አፈጻጸም ሲባል ስለሚያስመጣው ዕቃ አስፈላጊ የሆኑ መግለጫዎችን በመስጠት በዲክላራሲዮን ላይ ማስመዝገብ ያለበት ስለመሆኑ እና ወደ ሐገር ውስጥ የሚገባው ዕቃ በዲክላራሲዮን ላይ ከተመዘገበ በኋላ ለማጭበርበር በማሰብ ወይም በከባድ ቸልተኝነት የተፈጸመ ግድፈት የሚያስቀጣ መሆኑን ከጉምሩክ አዋጅ ቁጥር

859/06 አንቀጽ 13/4 መገንዘብ ይቻላል፡፡ በዚህ አግባብ ተመዝግበው ወደ ሐገር ውስጥ የሚገቡ ዕቃዎች በላኪው እና በአስመጪው መካከል በሚደረግ ስምምነት ወደ ሐገር ውስጥ የሚገቡ ከመሆናቸው አኳያ ወደ ሐገር ውስጥ እንዲገባ የተደረገው ዕቃ አስመጪው በዲክላራሲዮን ካስመዘገበው ዕቃ የበለጠ ዋጋ ያለው ሆኖ በተገኘ ጊዜ አስመጪው የተላከውን ዕቃ ሊያውቅ የሚችልበት ሁኔታ የለም ተብሎ ክሱ የቀረበበት ተከሳሽ መከላከል ሳያስፈልገው ከወዲሁ በነጻ ሊሰናበት ይገባል ተብሎ ድምዳሜ የሚወሰድበት አይደለም፡፡

በያዝነው ጉዳይ የስር ፍ/ቤት ተጠሪዎችን መከላከል ሳያስፈልጋቸው በነጻ ያሰናበተው በላኪው በኩል የተጠየቀው ጆግ ብቻ እንጂ ኩባያን አይጨምርም፤ ላኪው ያልተጠየቀውን ኩባያ መላኩ በስህተት መሆኑን በመግለጽ የእርማት ደብዳቤ ወደ ሐገር ውስጥ ተልኮ በባለስልጣኑ የወንጀል ምርመራ ክፍል የደረሰ በመሆኑ በአካላዊ ፍተሻ የተገኙት ጆጎች መጠን ደረጃ ልዩነት ሳይኖራቸው ግማሽ በሚሆን መጠን ላይ ባሉት ጆጎች ውስጥ አራት አራት ኩባያዎች መገኘታቸው ተጠሪዎች ሆን ብለው ኩባያዎቹን ደብቀው ለማስገባት የወንጀል ሐሳብ የነበራቸው ስለመሆኑ አያሳይም በማለት ነው፡፡ የስር ፍ/ቤት ተጠሪዎችን በዚህ አግባብ በነጻ ያሰናበታቸው ቢሆንም ተጠሪዎች በአዋጁ መሠረት በዲክላራሲዮን አስመዝግበው ላስገቡት ዕቃ ትክክለኛነት ሀላፊነት ያለባቸው በመሆኑ፤ ተጠሪዎች በዲክላራሲዮኑ ላይ ወደ ሐገር ውስጥ ለማስገባት በዲክላራሲዮን ካስመዘገቡት ፕላሲቲክ ጆጎች ውጪ ብዛታቸው 3186 ኩባያዎች በጆጎቹ ውስጥ የተገኙ መሆኑ እና ተደብቀው የተገኙት የዕቃዎች ዋጋ 11,182.86 ዶላር ወይም 247,646.67 ብር መሆኑን እና ይህም በሰነዱ ከተገለጸው አጠቃላይ የዕቃው ዋጋ 11,278.44 ዶላር ወይም 333001.43 ብር ጋር ሲነጻጸር የዋጋ ልዩነቱ 99% በመሆኑ፤ ዕቃው ወደ ሐገር ውስጥ የሚገባው በላኪው ድርጅት እና በተጠሪ መካከል በሚደረግ ስምምነት በመሆኑ፤ ላኪው ደርጅት በንግድ ላይ የተሰማራ አትራፊ ድርጅት ከመሆኑ አኳያ ከተጠሪዎች ዕውቅና ውጪ ክፍያ ያልተፈጸመባቸውን እና እንዲላኩ ያልተጠየቁ ዕቃዎችን ይልካል ተብሎ አስቀድሞ ድምዳሜ ላይ መድረስ የማይቻል በመሆኑ፤ ግብይቱ በባንክ መፈጸሙ ተጠሪዎች የተላከው ዕቃ በዲክላራሲዮን ከተመዘገበው ዕቃ የተለየ ዕቃ መሆኑን ሊያውቁ አያስችላቸውም ተብሎ ድምዳሜ ላይ ለመድረስ የማያስችል በመሆኑ፤ ተጠሪዎች በእርግጥም ዕቃው በስሕተት የገባ ነው የሚሉ ከሆነ በአካላዊ ፍተሻ በሰነድ ከተገለጸው ዕቃ ውጪ ሌላ ዕቃ እንደገባ ከመረጋገጡ በፊት አስቀድመው ለባለስልጣን መስሪያ ቤቱ አለማሳወቃቸው በክሱ የተገለጸውን የወንጀል ድርጊት የመፈጸም ሀሳብ እንደነበራቸው አመላካች ነው ከሚባል በቀር ዕቃው በስሕተት የገባ ነው ብሎ ከወዲሁ ለመደምደም እና ተጠሪዎች የቀረበባቸውን ክስ ሳይከላከል ከወዲሁ በነጻ ለማሰናበት የሚያስችል ባለመሆኑ ተጠሪዎች የቀረበባቸውን ክስ ሊከላከሉ ይገባል፡፡ በመሆኑም የስር ፍ/ቤት ዓቃቤሕግ ባቀረበው ማስረጃ ተጠሪዎችን በክሱ የተገለጸውን ወንጀል የፈጸሙ ስለመሆናቸው ያረጋገጠ ሆኖ ሳለ ተጠሪዎችን መከላከል ሳያስፈልጋቸው በነጻ ማሰናበቱ፤

ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተው ፍ/ቤትም ይህንኑ ሳያርም ማለፉ መሠረታዊ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

**<u>ው ሳ ኔ</u>**

4. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ.ቁ 247746 ጥቅምት 22 ቀን 2010 ዓ.ም ተጠሪዎችን ከቀረበባቸው ክስ መከላከል ሳያስፈልጋቸው በነጻ በማሰናበት የሰጠው ብይን እና ይህንኑ ብይን በማጽናት የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 209526 ሠኔ 19 ቀን 2010 ዓ.ም የሰጠው ብይን በወ/መ/ሥ/ስ/ሕ/ቁ 195/2/ለ/2 መሠረት ተሽሯል፡፡
5. ዓቃቤ ሕግ ባቀረበው ማስረጃ ተጠሪዎች በክሱ የተገለጸውን የወንጀል ድርጊት ስለመፈጸማቸው በበቂ ሁኔታ ያረጋገጠባቸው በመሆኑ ተጠሪዎች የቀረበባቸውን ክስ ሊከላከሉ ይገባል በማለት ወስነናል፡፡
6. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ተጠሪዎችን በነጻ በማሰናበት የሰጠው ብይን የተሻረ እና ተጠሪዎች የቀረበባቸውን ክስ እንዲከላከሉ የተወሰነ መሆኑን አውቆ ተጠሪዎች መከላከያ ማስረጃ እንዲያቀርቡ ካደረገ በኋላ የግራቀኙን ማስረጃ መርምሮ ተገቢውን እንዲወስን በማለት ጉዳዩን መልሰንለታል፡፡

**<u>ት ዕ ዛ ዝ</u>**

- የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በብይን የዘጋውን መዝገብ እንደገና በማንቀሳቀስ ተጠሪዎች መከላከያ ማስረጃ ካላቸው አስቀረቦ ሰምቶ ተገቢውን እንዲወስን ታዟል፡፡
- መዝገቡ ውሳኔ ስላገኘ ተዘግቷል፡፡ ይመለስ::

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ብ/ታ

የሰ/መ/ቁ. 181958

ታሕሳስ 20 ቀን 2012 ዓም

ዳኞች፡- እትመት አሰፋ

ጻውሎስኦርሺሶ

ፀሐይ መንክር

መላኩ ካሣዬ

እስቲበል አንዱዓለም

አመልካች፡- አቶ ገበያው ሽቴ ጠበቃቸው፡- አቶ ብናልፈው ነጋ ቀርበዋል::

ተጠሪ፡- የሰሜን ሸዋ ዞን ገቢዎች ዐ/ህግ፡- አልቀረቡም::

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል።

**ፍርድ**

ጉዳዩ ከተገኘ ገቢ የሚከፈል ግብርንና የተሰበሰበን ተጨማሪ እሴት ታክስ ክፍያን ለገቢ ሰብሣቢው ተቋም ገቢ አለማድረግ እንዲሁም ሐሰተኛ ወይም አሣሣች የክፍያ ደረሰኝ ማቅረብን በሚመለከት የቀረበ የወንጀል ክስን የሚመለከት ሲሆን አመልካች ልዩ ልዩ ግብይት መፈፀሜን ያረጋግጡልኛል በሚል ለገቢ ሰብሣቢ መስሪያ ቤቱ ያቀረባቸው ደረሰኞች እንዲታተሙ ፍቃድ ያልተሰጠባቸው፣በቀሪውና ለከፋይ በሚሰጠው ደረሰኝ የተፃፈው የገንዘብ መጠን የተለያዪ መሆኑን እንዲሁም የቀንና የቁጥር ቅደም ተከተል መዛባት ምክንያት በማድረግ መከፈል የነበረበትን ግብር አለመክፈል፣ ሃሰተኛ ወይም አሣሳች ደረሰኝ ለገቢ ሰብሣቢ መስሪያ ቤቱ ማቅረብ እና ከልዩ ልዩ ግብይቶች የሰበሰበውን ተጨማሪ እሴት ክፍያ በወቅቱ አሣውቆ ገቢ አለማድረግ ሶስት የወንልጀ ድርጊቶችን የፈፀመ ጥፋተኛ ነው ተብሎ በስምንት ዓመት ከአምስት ወር ፅኑ እስራትና በአንድ መቶ ሺህ ብር መቀጮ እንዲቀጣ መወሰኑ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ውሣኔ ተብሎ እንዲታረም የቀረበ ክርክርን ይመለከታል።

ክርክሩ የተጀመረው በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ሰሜን ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሲሆን ተጠሪ ግንቦት 29 ቀን 2009 ዓ.ም በተፃፈ ክሱ የአሁን አመልካች ደብረ ብርሃን ከተማ በኮንስትራክሽን መሣሪያዎች ኪራይ የንግድ ስራ የተሰማራ የተጨማሪ እሴት ታክስ ተመዝጋቢ መሆኑን በመዘርዘር፡-

- በ1ኛ ክስ በ2005ዓ.ም የግብር ዘመን 1,409,349.95 ብር ግብር የሚሰበሰብበት ገቢ አግኝቶ 485,322.49 ብር ግብር በወቅቱ መክፈል ሲገባው ባለመክፈሉ የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ

መንግስት የገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 76/94 አንቀፅ 97 የሚደነግገውን ተላልፎ ግብር አለመክፈል፡-

- በ2ኛ ክስ አመልካች በ2005ዓ.ም 1,409,349.95 ብር ዋጋ ያለው ግብይት በመፈፀሙ ከዚህ ውስጥመክፈልየነበረበትን ተጨማሪ እሴት ታክስ አንሶ እንዲከፈል በማቀድ ከአቶ ያለው አበበ፣ከአቶ ታፈረ ሰንደቁ እንዲሁም ከአቶ ተፈሪ ባንቴ ጋር በገባቸው የገልባጭ መኪና ኪራይ ውሎች ገንዘብ የከፈለ እንዲሁም ከአቶ ሁሴን ኢብራሂም የተሸከርካሪ ጎማ ገዝቶ ክፍያ የፈፀመ በማስመሰል በታክስ ማስታወቂያ ወቅት 19 ሀሰተኛና የተጭበረበሩ ደረሰኞች ለገቢ ሰብሣቢ መስሪያ ቤቱ በማቅረቡ የተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ ቁጥር 285/94 አንቀፅ 50(3)(ለ) የተመለከተውን በመተላለፍ ለገቢ ሰብሣቢ መስሪያ ቤቱ ሃሰተኛና የተጭበረበሩ ደረሰኞችን ማቅረብ፡-
- በ3ኛ ክስ የተጨማሪ እሴት ታክስ ተመዝጋቢ የሆነው አመልካች ከልዩ ልዩ ገቢዎች የሰበሰበውን 4517.49 ብር በሐምሌ ወር 2005ዓ.ም ለገቢ ተቋሙ አሣውቆ መክፈል ሲገባው ባለመፈፀሙ የተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ ቁጥር 285/94 አንቀፅ 49 መሰረት የተጨማሪ እሴት ታክስ ገቢ አለማድረግ በጥቅሉ ሶስት ወንጀሎችን ፈፅሟል የሚሉ ክሶችን አቅርቦበታል፡፡

አመልካች ክዶ በመከራከሩ የስር ፍርድ ቤት የሆነው የሰሜን ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ማስረጃ ካዳመጠ በኂላ አመልካች በሁለተኛው ክስ ከተዘረዘሩት 19 ደረሰኞች መካከል ከአቶ ሁሴን ኢብራሂም ተሰጥቶኛል ሲል ያቀረበው አንድ ደረሰኝ እንዲሁም ከአቶ ታፈረ ሰንደቁ ተሰጥቶኛል በሚል ያቀረባቸው ሰባት ደረሰኞች እውነተኛ መሆናቸው ተረጋግጧል፤ ቀሪዎቹ ከአቶ ያለው አበበ የቀረቡት ደረሰኞች በበራሪው ላይ የተፃፈው የገንዘብ መጠን በቀሪው ላይ አለመፃፉን፣ አቶ ያለው አበበ ደረሰኞችን እንዲያሳትም ከሚመለከተው አካል ፈቃድ ያልተሰጠው መሆኑን የቁጥርና የቀን ቅደም ተከተል የተዛባ መሆኑ፤ እንዲሁም ከአቶ ታፈረ ሰንደቁ ተሰጥቶኛል በሚል የቀረቡት አምስት ደረሰኞች በበራሪው ላይ የተፃፈው የገንዘብ መጠን በቀሪው ላይ አለመፃፉን ተፈሪ ሰንደቁ ደረሰኙን እንዲያሣትም ፈቃድ አለማግኘቱን የደረሰኝ ቁጥርና የተሰጡበት የቀን ቅደም ተከተል መዛባቱ ደረሰኞች ላይ የተከናወነው የፎረንሲክ ምርምራ አረጋግጧል፤ አመልካችም ደረሰኞቹን ግለሰቦች ሰጡኝ ከሚል በስተቀር ግለሰቦች እንዲያሣትሙ ፈቃድ የተሰጣቸው መሆኑንና በተሰጡት ደረሰኞች ላይ የተፃፈባቸው ገንዘብ በቀሪዎቹ ላይ ስለመፃፉ ሕጋዊ ስለመሆናቸው አላስረዳም ስለሆነም ሀሰተኛ በሆኑት አስራ አንድ ደረሰኞች መክፈል የነበረበትን 192,534.43 ብር ግብር አለመክፈሉ ሀሰተኛ ደረሰኝ ማቅረቡ እንዲሁም 4517.49 ብር ተጨማሪ እሴት ታክስ ሰብስቦ ገቢ ማድረግ ሲገባው ገቢ አለማድረጉ ተረጋግጧል በሚል በሶስቱም ክሶች ጥፋተኛ ብሎ በስምንት ዓመት ከአምስት ወር ፅኑ እስራትና በአንድ መቶ ሽህ ብር ቅጣት እንዲቀጣ ወስኗል፡፡

በዚህ ውሣኔ ቅር የተሰኘው አመልካች የይግባኝ አቤቱታውን ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ያቀረበ ቢሆንም ተቀባይነት በማጣቱ ይህን የሰበር አቤቱታ አቅርቧል፡፡ የአመልካች ጠበቃ ሐምሌ 30ቀን 2011ዓ.ም ፅፈው ባቀረቡት የሰበር አቤቱታቸው አመልካች ከአቶ ያለው አበበ፣ ከአቶ ተፈሪ በንቲ፤ ከአቶ ታፈረ ሰንደቁ ጋር የመኪና ኪራይ ውል ስለመግባቱ የውል ሰነዶችን በማቅረብ፣ ለተጠቀሱት ሰዎች ክፍያ በመፈፀም ወጪ ያወጣ ስለመሆኑ ደረሰኞችን በማቅረብ፤ ያለው አበበና ተፈሪ በንቲ ከአመልካች ጋር በገቡት የመኪና ኪራይ ውል መሰረት ገንዘብ ተቀብለው ደረሰኝ ስለመስጠታቸው ለገቢ ሰብሣቢው መስሪያቤት አረጋግጠው ሣለ፤ አቶ ተፈሪ ሰንደቁ የኪራይ ዋጋ መቀበሉንና ደረሰኝ መስጠቱን ሣይክድ ገንዘቡን አመልካች እንደፃፈው ቢገልፅም በፎረንሲክ በተደረገው ምርምራ ደረሰኙን ራሱ ፅፎ ያወጣው ስለመሆኑ በተረጋገጠበት፤ አቶ ሁሴን ኢብራሂም የተገዛውን ጎማ በሚመለከት በቀረበው አንድ ደረሰኝ ግብይት አልፈፀምኩም ቢሉም እንዲሁም ከአቶ ተፈረ ሰንደቁ የተሰጡት ሰባት ደረሰኞች በፎረንሲክ ተመርምረው እውነተኛ ደረሰኞች መሆናቸው በተረጋገጠበት ጥፋተኛ መባላቸው፤ አመልካች ጥፋተኛ የተባለበት ድንጋጌ ሐሰተኛ ማስረጃ ማቅረብ ጥፋት የሚባለው ግብር ላለመክፈል የሌለን ፍሬ ነገር እንዳለ አስመስሎ ማቅረብን በሚመለከት ሲሆን አመልካች ደረሰኞችን ያቀረባቸው በወጪ እንዲያዝላቸው ሆኖ ሣለና ደረሰኞች ያለፈቃድ መታተማቸው በቀሪና በበራሪው ላይ የተለያዩ መጠን ያለው ገንዘብ መፃፉ የቀን ቅድም ተከተል መዛነፉ ደረሰኞችን ሃሰተኛ ሊያስብላቸው የማይችል ሆኖ ሣለ፣ በበራሪውና በቀሪው ላይ አስተካክሎ መፃፍ የአመልካች ግዴታ ሣይሆን፤ ይልቁንም አመልካች ባቀረበው ማስረጃ ግብይት በመፈፀም ወጪ ማውጣቱን ባረጋገጠበት፤ አመልካች ከአቶ ሁሴን ኢብራሒም ያቀረበው ደረሰኝ ትክክለኛ በመሆኑ ተጠያቂነት የለበትም ከተባለ በኋላ በ3ኛው ክስ ጥፋኛ መባሉ በቀረቡበት ክሶች ጥፋተኛ ተብሎ ቅጣት መወሰኑ መሰረታዊ የህግ ስህተት መሆኑን በመዘርዘር እንዲታረምለት ጠይቋል፡፡

የአመልካችን የሰበር አቤቱታ የመረመረው አጣሪ ችሎት አመልካች ከተጠቀሱት ሰዎች ጋር ግብይት መፈፀሙ በተረጋገጠበት፤ በአስራ አንዱ ደረሰኞች ላይ ተረጋገጠ የተባለው የቀንና የቁጥር ቅድም ተከተል መዛባት፣ በቀሪዎች ላይ የገንዘብ መጠን አለመፃፍ፣ ከሚመለከተው ተቋም ደረሰኞች እንዲታተሙ ፈቃድ ያልተሰጣቸው መሆን በተለይም ደረሰኞችን ከሰጡት ሰዎች ጋር የወንጀል ተሣትፎ የነበረው ስለመሆኑ ባልተረጋገጠበት አመልካችን በሃላፊነት ሊያስጠይቅ የሚችል ስለመሆን አለመሆኑና የሶስተኛው ክስ መሰረት የሆነው ደረሰኝ በፎፈረንሲክ ምርምራ ትክክለኛ መሆኑ በተረጋጠበት በሶስቱም ክሶች ጥፈተኛ ተብሎ ቅጣት የመወሰኑን ተገቢነት ተመርምሮ እንዲወሰን ተጠሪም የመልስ ክርክር እንዲያቀርብ ትዕዛዝ በመስጠቱ መዝገቡ ለዚህ ችሎት ቀርቧል፡፡

ተጠሪ መስከረም 30ቀን 2011 (ፍርድ ቤቱ የአፃፃፍ ስህተት እንደሆነ ግንዛቤ ወስዶበታል)በተፃፈ መልሱ ለቀረቡበት ክሶች ምክንያት የሆኑት ደረሰኞች መካከል ስምንቱ አጠራጣሪ በሆነ የፎረንሲክ ምርምራ ውጤት ሕጋዊ ናቸው መባሉ ተገቢ አለመሆኑን፤ አመልካች የተጨማሪ እሴት ታክስ ተመዝጋቢ

በመሆኑ ግብይትም ሊፈፅም የሚገባው ከሌሎች ቫት ተመዝጋቢዎች ሆኖ ሣለ ከሕግ ውጪ ከተርን ኦቨር ታክስ ተመዝጋቢዎች ጋር ግብይት ፈፅሞ በወጪ እንዲያዝለት ደረሰኝ ማቅረቡ ከመነሻው ሕገ ወጥ መሆኑን፣ ደረሰኞች እንዲታተሙ ከገቢ ሰብሣቢ መስሪያ ቤቱ ፈቃድ ያልተሰጠባቸው መሆኑ መረጋጡን፤ የአመልካችና ደረሰኙን የሰጡት ሰዎች የወንጀል ተሣትፎ ከጅምሩ የዐ/ሕግ ክስ መሰረት አለመሆኑን፤ የሶሰተኛውን ክስ በሚመለከት አመልካች በወቅቱ ገቢ አሣውቆ ስለመክፍሉ ማረጋገጫ አለማቅረቡን ያቀረበው ደረሰኝም በ2005ዓ.ም ግብይት ስለመፈፀሙ አለመረጋገጡን በጥቅሉ የስር ፍርድ ቤት አመልካችን በሶስቱም ክሶች ጥፋተኛ ብሎ ቅጣት በመወሰኑ የፈፀመው መሰረታዊ የሕግ ስህተት የለም ተብሎ የአመልካች አቤቱታ ውድቅ እንዲደረግለት የመልስ ክርክሩን አቅርቧል፡፡

አመልካች የሰበር አቤቱታውን የሚያጠናክር የመልስ መልስ ክርክሩን አቅርቧል፡፡

ከፍ ሲል የተመለከትነው የጉዳዩን አመጣጥ ሲሆን አጣሪ ችሎቱ ተመርምሮ ውሣኔ እንዲሰጥበት ለለዬው ማስቀረቢያ ነጥብ መልስ ለመስጠት የግራ ቀኙን ክርክር አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው ምርመረናል፡፡

እንደሚታወቀው የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገ መንግስት አንቀፅ 80(3)(ሀ)ና አዋጅ ቁጥር 25/88 አንቀፅ 10 እንደሚደነግጉት የክልልና የፌዴራል ፍርድ ቤቶች እንዲሁም የዳኝነት ስልጣን በሕግ የተሠጣቸው ሌሎች አካላት የቀረበላቸውን ጉዳይ አከራክረው የመጨረሻ ውሣኔ ሲሰጡ መሰረታዊ የሕግ ስህተት መፈፃማቸው በክርክር ሂደት ሲረጋገጥ የማረም ስልጣን ለዚህ ችሎት ተሠጥቶታል፡፡ በዚህ መሰረት በያዝነው ክርክር የዚህ ችሎት ስልጣን አከራካሪ የሆነ ፍሬ ነገርን በማስረጃ ማጣራት ሣይሆን የበታች ፍርድ ቤቶች በጉዳዩ ላይ የቀረበውን ክርክር መርምረው ውሳኔ ሲሰጡ የፈፀሙት መሰረታዊ የሕግ ስህተት ካለ ማረም መሆኑን ከወዲሁ ልብ ሊባል ይገባል፡፡

የወንጀል ሕግ አንድ ሰው በሕግ አድርግ ወይም እንዳታደርግ ብሎ የሚደነግግ መደረግ ያለባቸውንና መደረግ የሌለባቸውን ድርጊቶች በዝርዝር የሚያመለክትና በመደረጋቸውና ባለመደረጋቸው የተነሣ የድርጊቱን ፈፃሚዎች የሚቀጣ የቅጣቱን መጠንና ዓይነት የሚወሰን ሕግ ነው፡፡ ይህም ማለት ወንጀል ድርጊት ተፈፅሟል የሚባለው በወንጀል ሕግ የተከለከሉ ድርጊቶችን መፈፀም ወይም እንዲፈፀሙ የተታዘዙ ድርቶችን አለመፈፀም ነው፡፡

ከዚህ መርህ በመነሣት ወደያዝነው ጉዳይ ስንመለስ ተጠሪ በአመልካች ላይ ያቀረባቸው የሶስቱም ክሶች መነሻቸው ሀሰተኛ ወይም አሣሣች ደረሰኝ ማቅረቡ እንደሆነ የስር ፍርድ ቤቱ የውሣኔ ግልባጭ ያስገነዝባል፡፡ አዋጅ ቁጥር 285/94 አንቀፅ 50(1) ለታክሱ ባለስልጣን ሰራተኛ አንድን ነጥብ በሚመለከት የሐሰት ወይም አሳሳች ማስረጃ ያቀረበ ወይም ማስረጃው አሣሣች እንዳይሆኑ መካተት የሚገባቸውን ነገሮች ቀንሶ ያስቀረ ወንጀል እንፈጸመ የሚቆጠርበት መሆኑና በዚሁ አዋጅ በአንቀፅ50(3)

(ሀ)ና(ለ) ድንጋጌ መሰረት የሐሰት መግለጫው የተሰጠው እንዲካተት የሚገባው ነገር ያልተካተተው ሆነ ተብሎ ወይም በከባድ ቸልተኝነት የሆነ እንደሆነ ወንጀል መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ የቅጣቱ መጠን ከፍ እንደሚል ይደነግጋል። እነዚህን ድንጋጌዎች ተላልፏል በሚል በአመልካች ላይ የቀረቡትን ክሶች የአመልካች ድርጊት ወንጀል መሆን ያለመመሆናቸው ሊወሰን የሚገባው በኢ.ፌ.ዴ.ሪ የወንጀል ሕግ አንቀፅ 23(2) የተደነገጉትን የወንጀል ማቋቋሚያ መመዘኛዎችና በአንቀፅ 58(1)(ሀ) ላይ የተደነገገውን ድርጊቱ ወንጀል ነው ለማለት ታስቦ የተፈፀመ መሆን እንደሚገባው የተደነገገውን መርህ ግምት ውስጥ በማስገባት ሊሆን ይገባል።

ይህ ከሆነ ተጠሪ ዐ/ሕግ ያቀረበውን ክስ ማስረዳት የሚጠበቅበት አመልካች ሃሰተኛ ደረሰኙን ማቅረቡን ብቻ ሣይሆን ሃሰተኛ ደረሰኙን በማዘጋጀት ተሳትፎ ማድረጉን ወይም ራሱ በክሱ ላይ እንደጠቀሰው አመልካች ግብር ቀንሶ እንዲከፍል እና የሰበሰበውን ተጨማሪ እሴት ታክስ ገቢ ላለማድረግ በማሰብ ሃሰተኛ መሆኑን እያወቀ ገቢ ማድረጉን ማስረዳት ይኖርበታል።

ይህ ሆኖ ሣለ የግራቀኙን ክርክር ከስር ፍርድ ቤት ውሣኔ ግልባጭ ጋር በማገናዘብ ስንመረምረው ዐ/ህግ በክሱ ላይ ሃሰተኛ ናቸው የሚላቸውን ደረሰኞች ለአመልካች ቆርጠው የሰጡት ሰዎች በክልሉ ውስጥ ሕጋዊ ነጋዴዎች ከመሆናቸውም በላይ እነዚህ ደረሰኞች ከእነሱ የወጡ ስለመሆኑ ደረሰኙን በሰጡት ሰዎች አልተካደም። ይህም ሆኖ የስር ፍርድ ቤት ደረሰኞቹ ሀሰተኛ ናቸው አመልካችም ጥፋተኛ ነው ለሚለው መደምደሚያ ያበቁት ሶስት ምክንያቶች ናቸው። እነዚህም በተለምዶ ቀሪ እና በራሪ በሚባለው ወይም ለከፋዩ በሚሰጠውና ከጥራዙ ጋር በሚቀረው ደረሰኝ ላይ የተፃፈው ገንዘብ መበላለጥ በአንዳንዶች ላይ ለከፋዩ በተሰጠው ላይ ተፅፎ በቀሪው ላይ ያለመፃፍ፤ የቁጥርና የቀን ቅደም ተከተል መዛነፍ እና ደረሰኙን የሰጡት ሰዎች ከገቢ ሰብሣቢው መስሪያ ቤት ደረሰኞችን እንዲያሣትሙ ፈቃድ ያልተሰጣቸው መሆኑ ናቸው።

በኢ.ፌ.ዴ.ሪ ወንጀል ሕግ አንቀፅ 23(1) ድንጋጌ መሰረት አንድ ሰው በሕግ እንዲያደርግ (እንዲፈፅም) ወይም እንዳያደርግ(እንዳይፈፅም) በሕግ ግዴታ የተጣለበትን ተላልፎ የሚያስቀጣ ድርጊት ፈፅሞ ሲገኝ ወንጀል እንፈጸመ ታምኖበት ቅጣትም እንደሚወሰንበት ይደነግጋል። ስለሆነም ከላይ ለቀረቡት ደረሰኞች ሐሰተኛ መሆናቸው ብቻ አመልካችን ጥፋተኛ ሊያስብለው ስለማይችል የስር ፍርድ ቤት ሐሰተኛ ደረሰኝ ናቸው በተባሉት ደረሰኞች አፈጣጠርና ለገቢ ሰብሣቢው መስሪያቤት አቀራረብ ሂደት ላይ የአመልካችን ድርሻና በሕግ የተጣለበት ግዴታ ከወንጀል ሕግ አንቀፅ 23(1) መርህ አንፃር ሊመረመር ይገባል።

እነዚህ ደረሰኞች ከተጠቀሱት ነጋዴዎች ለአመልካች የተሰጡበት በመካከላቸው በነበረው የአከራይና ተከራይ ግብይት ምክንያትና አመልካች ተከራይ(ገዥ) ደረሰኙን ያወጡት ሰዎች ደግሞ አከራይ(ሻጭ) እንደነበሩ የግራቀኙ ማስረጃና የስር ፍርድ ቤት መዝገብ ግልባጭ ያስገነዝባል። ይህ ከሆነ ለከፋዩ በሚሰጠውና ከጥራዙ ጋር በሚቀረው ደረሰኝ ላይ የተፃፈው ገንዘብ መበላለጥ እንዳይኖር ማድረግ፣

ለከፋዩ በተሰጠው ደረሰኝ የተፃፈውን ገንዘብ መጠን በቀሪው ላይ መፃፍ፣ የቁጥርና የቀን ቅደም ተከተል መዛነፍ እንዳይኖር መጠንቀቅ፣ ደረሰኞች እንዲታተሙ ፈቃድ የወጣባቸው ስለመሆኑ ማረጋገጥ የአመልካች ግዴታ ሊሆን ይገባዋልን የሚለው የግራቀኙ የክርክር ነጥብ በመሆኑ ሊመረመር ይገባዋል፡፡

ከዚህ አንፃር ማንም ምክንያታዊ ሰው በኑሮ ልማድ እንደሚገነዘበውና አዋጅ ቁጥር 285/94 አንቀፅ 22 እንደሚደነግገው ትክክለኛ ደረሰኝ የመስጠት ግዴታ የተጣለው የተጨማሪ እሴት ታክስ ተመዝጋቢ የሆነው ሻጭ ስለመሆኑ ተደንግጓል፡፡ የምክንያታዊ ገዥ ሃላፊነት ለከፈለው ገንዘብ ደረሰኝ እንዲሰጠው ከመጠየቅ በዘለለ ደረሰኞች ፈቃድ ወቶባቸው መታተማቸውን ወይም ለከፋዩ በተሰጠው ደረሰኝ ላይ የተፃፈው ገንዘብ በቀሪው ላይ መፃፍ አለመፃፉን፣ የደረሰኞች ቅድም ተከተል ስለመጠበቁ ወይም አለመጠበቁ የማረጋገጥ ግዴታ የገዥ ስለመሆኑ ዐ/ሕግ በክሱ ላይ የጠቀሣቸው አዋጆች አልደነገጉም፡፡ በሌላ በኩል ለክሱ ምክንያት የሆኑትን ደረሰኞች በማዘጋጀት ረገድ አመልካችና ደረሰኞችን ያወጡት ሰዎች ወንጀል ለመፈፀም ስምምነት ለማድረጋቸውና አመልካችም ተሳትፎ የነበረው ስለመሆኑ ወይም ደረሰኙን በማዘጋጀት ወይም ሐሰተኛ መሆናቸው እያወቀ ግብሩን አሣንሶ ለመክፈል በማሰብ ድርጊቱን ስለመፈፀሙ ዐ/ህግ አላስረዳም፡፡

ተጠሪ ካቀረባቸው ማስረጃዎች መካከል የተጠሪ ምስክር በጥቅሉ ሁሉም ደረሰኞች ሃሰተኞች መሆናቸውን የመሰከረ ሲሆን ሃሰተኛ ናቸው ያለበት ምክንያት ለክሱ ምክንያት ከሆኑት 19 ደረሰኞች ውስጥ አስራ አንዱ የቀን እና የቁጥር ቅደም ተከተል የተዛነፈባቸው እንዲሁም እንዲታተሙ ፈቃድ ያልተሰጠባቸውና ለአመልካች በተሰጠው ድርሻ ገንዘብ ተፅፎ በቀሪው ላይ ባለመፃፉ ቢፃፍም ተበላልጦ መፃፉን ምክንያት በማድረግ ስለመሆኑ መዝገቡ ያስረዳል፡፡ ሆኖም አመልካች ደረሰኞች በእጁ የገቡት ደረሰኞችን ከሰጡት ሕጋዊ ነጋዴዎች ጋር በፈፀመው ግብይት ስለመሆኑ በግራ ቀኙ ማስረጃ በተረጋገጠበት፤ በአንፃሩ ተጠሪ አመልካች ያቀረባቸውን ደረሰኞች ሐሰተኛ ስለመሆናቸው እያወቀ ወይም ሊያውቅ የሚችልበት ሁኔታ መኖሩ ባልተረጋገጠበት የአመልካች ግዴታ ባልሆኑ ከላይ በተጠቀሱት መመዘኛዎች ደረሰኞች ሕጋዊ አይደሉም በሚል ብቻ አመልካችን ጥፋተኛ ሊያደርገው የሚችል ማስረጃና ክርክር ባልቀረበበት በ1ኛ እና በ2ኛ ክሶች ስለመፈፀሙ በበቂ ሁኔታ ተመስክሮበታል በሚል እንዲከላከል ብይን መሰጠቱና በኋላም አልተከላከለም በሚል ጥፋተኛ መባሉ ተገቢ ሆኖ አላገኘነውም፡፡

ሶስተኛውን ክስ በሚመለከት የተጠሪ ክስ መሰረት የሚያደርገው ከልዩ ልዩ ግብይት የተሰበሰበ የተጨማሪ እሴት ታክስ ክፍያ በሐምሌ ወር 2005ዓ.ም ለገቢ ተቋሙ አሣውቆ ገቢ ማድረግ ሲገባው ባለማድረጉ የተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ ቁጥር 285/94 አንቀፅ 49 ድንጋጌን ተላለፏል የሚል ነው፡፡ አመልካች የሰበሰብኩትን የተጨማሪ እሴት ታክስ ገቢ ባለመድረጌ የተፈጠረ ችግር ሣይሆን ልዩነቱ የተከሰተው ከአቶ ሁሴን ኢብራሂም ጎማ ስገዛ የከፈልኩትን ተጨማሪ እሴት ታክስ ደረሰኝ አቅርቤ ተጠሪ ሐሰተኛ ነው በሚል ለመያዝ ፈቃደኛ አለመሆኑ ተከትሎ የመጣ ችግር እንደሆነ ይከራከራል፡፡

በተጠሪ ገቢ ያልሆነው ገንዘብ ምንጭ አመልካች ከአቶ ሁሤን ኢብራሒም ጋር በነበረው የጎማ ግዥ ግብይት ነው በሚለው ክርክር ላይ ግልፅ ተቃውሞ ሣያቀርብ አመልካች ከሁሴን ኢብራሒም ጋር የጎማ ግዥ የፈፀመው በ2005ዓ.ም ሣይሆን በ2006ዓ.ም መሆኑን ራሱ አቶ ሁሴን ኢብራሂም አረጋግጧል ይህ ደግሞ የ2006 ደረሰኝን ለ2005ማቅረቡ ጥፋት እንደሆነ ይከራከራል፡፡ ሆኖም በአመልካች ጠያቂነት ደረሰኙ በፎረንሲክ ሲመረመር እውነተኛ ደረሰኝ ስለመሆኑ ተረጋግጧል፡፡ ምርምራው የተደረገው አንድ ነጠላ ፍሬ ነገርን ለማረጋገጥ ታስቦ ስለመሆኑ በተለየ ሁኔታ ካልተገለፀ በስተቀር የአንድ ደረሰኝ በፎረንሲክ ላቦራቶር ተምርምሮ እውነተኛ ነው ከተባለ የወጣበትን ቀን ጨምሮ በደረሰኙ ላይ የተፃፉትን ፍሬ ነገሮች በሞላ  የሚያጠቃልል ነው፡፡ ስለሆነም የሶስተኛው ክስ መሰረት አመልካች ከአቶ ሁሴን ኢብራሂም የተቀበለው ደረሰኝ መሆኑ ባልተካደበት፣ ይህ ደረሰኝ በተጠሪ በኩል ሃሰተኛ ነው በሚል ተቀባይነት በማጣቱ ክርክር ተደርጎበት እውነተኛ መሆኑ በተረጋጠበት የስር ፍርድ ቤትም የምርመራውን ውጤት ውድቅ ባላደረገበት የደረሰኙ እውነተኛ መሆን የአመልካች ክርክር ተገቢ መሆኑን ባረጋገጠበት በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 149(2) መሰረት አመልካችን በነፃ ማሰናበት ሲገባ ጥፋተኛ ማለቱ ተገቢ ሆኖ አልተገኘም፡፡

ሲጠቃለል ተጠሪ በአመልካች ላይ ያቀረባቸውን 1ኛና 2ኛ ክሶች በሚመለከት አመልካች ከሕጋዊ ነጋዴዎች ጋር ግብይት በመፈፀሙ ለከፈለው ክፍያ ከነጋዴዎች ደረሰኝ መቀበሉን ባስረዳበት የእሱ ግዴታ ባልሆኑ መመዘኛዎች ማለትም ለከፋዩ በሚሰጠውና ከጥራዙ ጋር በሚቀረው ደረሰኝ ላይ የተፃፈው ገንዘብ መበላለጥ፣  ለከፋዩ በተሰጠው ደረሰኝ የተፃፈውን ገንዘብ መጠን በቀሪው አለመፃፍ፣ የቁጥርና የቀን ቅደም ተከተል መዛነፍ መኖር፣ ደረሰኞቹ እንዲታተሙ ፈቃድ የወጣባቸው አለመሆናቸው በሚሉት መመዘኛዎች ተመዝነው ሀሰተኛ ናቸው የተባሉትን ደረሰኞች ለገቢ ሰብሳቢው መስሪያ ቤት አመልካች ስለቀረበ ብቻና ደረሰኞቹ ሃሰተኛ ስለመሆናቸው እውቅና ኖሮት ስለማቅረቡ ግምት የሚያስወስዱ ሁኔታዎች ስለመኖራቸው በተጠሪ ማስረጃ ባልተረጋገጠበት፤ የተጨማሪ እሴት ታክስ ገንዘብ ልዩነቱ የተፈጠረው ገቢ ሰብሣቢ መስሪያ ቤቱ ትክክለኛውን ደረሰኝ ሀሰተኛ ነው በሚል አልይዝም በማለቱ እንደሆነ በተረጋገጠበት የስር ፍርድ ቤት አመልካችን ጥፋተኛ ብሎ ቅጣት መወሰኑ የይግባኝ ክርክሩን የመረመረው የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤትም ይህን አለማረሙ ፍርድ ቤቶች ሊተገብሩት የሚገባውን መሰረታዊ የወንጀል ማስረጃ ምዘና መርህን ያልተከተ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ውሣኔ በመሆኑ ተከታዩ ተወስኗል፡፡

**<u>ውሣኔ</u>**

1. የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ሰሜን ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 0239664 በሆነው ሰኔ 28ቀን 2011ዓ.ም በዋለው ችሎት አመልካችን በቀረቡበት ሶስት ክሶች ጥፋተኛ ብሎ በስምንት ዓመት ከአምስት ወር ፅኑ እስራትና በአንድ መቶ ሺህ ብር እንዲቀጣ

የወሰነው ውሳኔና ይህን ተከትሎ አመልካች ያቀረበውን ይግባኝ ክርክር የመረመረው የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 20465 በሆነው ሐምሌ 18ቀን 2011ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠው ትዕዛዛ በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁጥር 195(2)(ለ)(1) መሰረት ተሽሯል፡፡

2. አመልካች በተጠሪ ከቀረቡበት ክሶች ከላይ በተገለፁት ምክንያቶች በነፃ እንዲሰናበት ተወስኗል፡፡

**ትዕዛዝ**

1. የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ደብረ ብርሀን ማረሚያ ቤት አመልካች በሌላ ወንጀል የማይፈለግ ከሆነ ዛሬውኑ ከእስር እንዲፈታው ታዟል፤ ይፃፍ፡፡
2. መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይለመስ፡፡የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

የሰ/መ/ቁ 164030

ሕዳር 30 ቀን 2012 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** እትመት አሠፋ

ጳውሎስ ኦርሺሶ

ፀሐይ መንክር

መላኩ ካሣዬ

እስቲበል አንዱዓለም

አመልካች፡- የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ፍትሕ ቢሮ ዓቃቤ ሕግ

ተጠሪዎች፡- 1. ሐብታሙ በለጠ

2. ያደለው ቻላቸው

3. ተመስጌን ታደሰ

መዝገቡ የተቀጠረው መርምሮ ፍርድ ለመስጠት ነው፡፡ በመሆኑም መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ይህ የሰበር አቤቱታ ሊቀርብ የቻለው አመልካች ነሐሴ 11 ቀን 2010 ዓ.ም ጽፎ ባቀረበው የሰበር አቤቱታ በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 0218981 መጋቢት 14 ቀን 2010 ዓ.ም በሰጠው ውሳኔ የ2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች ሀሳብ በሟች ላይ መጠነኛ የሆነ የአካል ጉዳት እንዲደርስበት ማድረግ በመሆኑ ጥፋተኛ ሊባሉ የሚገባው በተከሰሱበት የወንጀል ሕግ አንቀጽ 539/1/ሀ ሳይሆን በአንቀጽ 556/2/ሀ ነው፤1ኛ ተጠሪም ጥፋተኛ ሊባል የሚገባው በወንጀል ሕግ አንቀጽ 540 ነው በማለት 1ኛ ተጠሪን በዘጠኝ ዓመት ጽኑ እሥራት፤ 2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎችን እንደቅደም ተከተላቸው ደግሞ በስድስት ወር እና በስምንት ወር እሥራት እንዲቀጡ ሲል የሰጠው ውሳኔ፤ ይህንኑ ውሳኔ በማጽናት የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 78191 ሠኔ 28 ቀን 2010 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለቱ ነው፡፡

ጉዳዩ የወንጀል ክርክርን የሚመለከት ነው፡፡ የአሁን አመልካች ተጠሪዎች የወንጀል ሕጉን አንቀጽ 32/1/ሀ እና 539/1/ሀ ድንጋጌን በመተላለፍ ሰውን ለመግደል አስቀድመው ሀሳብ በመያዝ እና ሟች 2ኛ ተጠሪን በቦክስ በመምታት በተማሪዎች መሀል አዋርዶታል ልንበቀለው ይገባል በሚል ሀሳብ ተነሳስተው የ3ኛ ተጠሪ የእህት ልጅ የሆነውን 1ኛ ተጠሪን በስልክ ደውለው ከጠሩ በኋላ ሟችን እንዲበቀልላቸው በማግባባት የሟችን ፎቶ በማሳየት ሚያዝያ 21 ቀን 2009 ዓ.ም በግምት ከምሽቱ 1፡50 ሠዓት በባሕርዳር ከተማ ቀበሌ 10 ልዩ ቦታው ጌታቸው ግሮሰሪ አካባቢ የ5ኛ ዓመት የኢንጅነሪንግ ተመራቂ ተማሪ የሆነውን ሟች ተመስገን ተሾመን ከጓደኞቹ ጋር እራት በልቶ ሲመለስ 2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች ሟችን ለ1ኛ ተጠሪ ጠቁመው ካሳዩት በኋላ 1ኛ ተጠሪም ተደብቆ ቆይቶ ሟችን በድንጋይ ግንባሩ ላይ በመምታት የገደለው ሲሆን 2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች በመላ ሀሳባቸው እና ድርጊታቸው የወንጀሉን ውጤት በመቀበል ሟች እንዲገደል ያደረጉ በመሆኑ በፈጸሙት በዋና ወንጀል አደራጊነት ከባድ የሰው ግድያ ወንጀል ተከሰዋል በማለት ያቀረበውን ክስ የተመለከተው የባሕርዳር እና አካባቢዋ ከፍተኛ ፍ/ቤት ተጠሪዎችን በተከሰሱበት የወንጀል ሕግ አንቀጽ 32/1/ሀ እና 539/1/ሀ ድንጋጌ መሠረት ጥፋተኛ በማለት 1ኛ ተጠሪ በአሥራ ስምንት ዓመት ጽኑ እሥራት፤ 2ኛ ተጠሪ በአሥራ ስድስት ዓመት ከስድስት ወር ጽኑ እሥራት፤ 3ኛ ተጠሪ ደግሞ በአሥራ ስምንት ዓመት ጽኑ እስራት እንዲቀጡ ሲል ወስኗል፡፡

ተጠሪዎች ይህን ውሳኔ በመቃወም 1ኛ ተጠሪ ለብቻ፤ 2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች ደግሞ አንድ ላይ በመሆን በተለያየ መዝገብ ለክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የይግባኝ አቤቱታ አቅርበዋል፡፡ ይግባኙ የቀረበለት ፍ/ቤት ተጠሪዎች በተለያየ መዝገብ ያቀረቡትን የይግባኝ አቤቱታ አጣምሮ ግራቀኙን ካካራከረ በኋላ በዓቃቤ ሕግ በኩል በማስረጃነት የቀረበው የተጠሪዎች የእምነት ቃል የሚያሳየው ሟች ከ2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች ጋር በሚኖርበት ዩኒቨርሲቲ ግቢ ውስጥ የተጣሉ እና 3ኛ ተጠሪን በመሳደቡ እና ለመደብደብ በመሞከሩ፤ 2ኛ ተጠሪንም በቦክስ ፊቱ ላይ መቶ ምልክት ስላደረገበት ሟች ከዚህ ድርጊቱ እንዲቆጠብ 1ኛ ተጠሪ ቀለል ያለ ጉዳት አድርሶ እንዲያስፈራራው ፈልገው ነው፤ ምንም እንኳን 2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች ከሟች ጋር ቀደም ሲል ተጣልተው የነበረ ቢሆንም 1ኛ ተጠሪ ሟችን በድንጋይ ፈራ ተባ እያለ እና ለመምታት እያወላወለ አንድ ጊዜ መቶት መሮጡ የሚያሳየው 1ኛ ተጠሪ ሟችን ቀላል ጉዳት አድርሶ እንዲያስፈራራላቸው አስበው ለ1ኛ ተጠሪ አሳይተውት ሟች በድንጋይ ተመቶ የሞተ መሆኑን ነው፤ በመሆኑም የ2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎቸ ሀሳብ ሟች ቀለል ያለ ጉዳት እንዲደርስበት ማድረግ እንጂ እንዲሞት ስላልሆነ በወንጀል ሕግ አንቀጽ 32/2 እና 58/3 በተቀመጠው አግባብ ሊቀጡ የሚገባው በሀሳባቸው ልክ በመሆኑ 2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎቸ ጥፋተኛ ሊባሉ የሚገባው በወንጀል ሕግ አንቀጽ 556/2/ሀ መሠረት ነው፤ 1ኛ ተጠሪም ሟችን ለመግደል አስቀድሞ ሀሳብ እንደነበረው ዓቃቤሕግ አላስረዳም፤ የድርጊት አፈጻጸሙም የተለየ ጨካኝነቱን እና ነውረኝነቱን የሚያሳይ ስላልሆነ ጥፋተኛ ሊባል የሚገባው በወንጀል ሕግ አንቀጽ 540 መሠረት ነው በማለት 1ኛ ተጠሪ

በዘጠኝ ዓመት ጽኑ እሥራት፣ 2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች እንደቅደም ተከተላቸው ደግሞ በስድስት ወር እና በስምንት ወር እሥራት እንዲቀጡ ሲል ወስኗል፡፡ አመልካች ይህን ውሳኔ በመቃወም ለክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አቤቱታ ያቀረበ ቢሆንም አቤቱታው ተቀባይነት አላገኘም፡፡

የሰበር አቤቱታው የቀረበው ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም መሠረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሞበታል በሚል ሲሆን ይዘቱም፡- ተጠሪዎች ወንጀሉን የፈጸሙት ሟች 2ኛ ተጠሪን በተማሪ መሐል በቦክስ መቷል በሚል ቂም መሆኑን፣ ለ1ኛ ተጠሪ የሟችን ፎቶ ያሳዩት እና 1ኛ ተጠሪ ለመምታት በዝግጅት ላይ እንዳለ 3ኛ ተጠሪ የሴት ልጅ በለው በማለት ይዞት በነበረው ድንጋይ ግንባሩን የመታው መሆኑን፣ ሟች በደረሰበት ምት ምክንያት ሕይወቱ ያለፈ መሆኑን አስረድተናል፣ ሟች በቀን 26/07/09 ዓ.ም በተጻፈ አቤቱታ 3ኛ ተጠሪ እወጋሃለሁ እያለ ሲዝትበት የነበረ እና ተረጋግቶ መማር እንዳልቻለ ለሚማርበት ዩኒቨርሲቲ በአቤቱታ መግለጹ 2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎቸ ሟችን ለመግደል ቀድመው ሃሳብ የነበራቸው መሆኑን ያሳያል፣ የሀሳብ ክፍል ሊረጋገጥ የሚችለው ከድርጊት አፈጻጸም ሆኖ ሳለ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት እና የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት እነኚህን ሁኔታዎች ሳያገናዝቡ ተጠሪዎች ሟችን አስቀድሞ የመግደል ሀሳብ አልነበራቸውም በማለት የሰጡት ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል የሚል ነው፡፡

የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ 2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች አስቀድሞ የነበረውን ቂም ምክንያት በማድረግ 1ኛ ተጠሪ እንዲበቀልላቸው በመንገራቸው የፈጸሙት መሆኑ በተመሰከረበት ሁኔታ ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ተጠሪዎችን በወንጀል ሕግ አንቀጽ 539/1/ሀ መሠረት ጥፋተኛ ያለማለቱን አግባብነት ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ በዚህ ችሎት እንዲታይ ተደርጓል፡፡ ለተጠሪዎች ጥሪ ተደርጎም 1ኛ ተጠሪ መጥሪያ ለመቀበል ፈቃደኛ አለመሆኑ የተረጋገጠ በመሆኑ 2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች ደግሞ በአዲስ ዘመን ጋዜጣ ጥሪ ተደርጎላቸው ባለመቅረባቸው መልስ የመስጠት መብታቸው ታልፏል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ በአጭሩ ከላይ የተገለጸው ነው፡፡ ይህ ችሎትም በሰበር አጣሪው ችሎት ሊጣራ ይገባል ተብሎ የተያዘውን ነጥብ ከግራቀኙ ክርክር፣ ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸው ሕጎች ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው መርምሮታል፡፡

ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተው የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት 2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች ጥፋተኛ ሊባሉ የሚገባው በወንጀል ሕግ አንቀጽ 556/2/ሀ መሠረት ነው፣ 1ኛ ተጠሪም ጥፋተኛ ሊባል የሚገባው በወንጀል ሕግ አንቀጽ 540 መሠረት ነው ከሚል መደምደሚያ ላይ ሊደርስ የቻለው የ2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች ሀሳብ ሟች ቀለል ያለ ጉዳት እንዲደርስበት ማድረግ እንጂ እንዲሞት አልነበረም፣ 1ኛ ተጠሪም ሟችን ለመግደል አስቀድሞ የነበረው ሀሳበ እንደነበረው ዓቃቤሕግ አላስረዳም፣ የድርጊት አፈጻጸሙም የተለየ ጨካኝነቱን እና ነውረኝነቱን አያሳይም በሚል ነው፡፡ በመሆኑም የስር ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ተጠሪዎች የተከሰሱበትን የሕግ አንቀጽ ለመቀየር የሰጠው ምክንያት ተገቢ ነው ወይስ

አይደለም ለሚለው የክርክሩ መሠረታዊ ነጥብ ምላሽ ለመስጠት በዓቃቤሕግ በኩል በስር ፍ/ቤት የቀረቡትን የሰው ምስክሮች ቃል እና የሰነድ ማስረጃዎች ይዘት መመልከት አስፈላጊ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ በዚሁ መሠረት፡-

1ኛ የዓቃቤሕግ ምስክር ለፍ/ቤቱ የሰጠው የምስክርነት ቃል ይዘት፡- በዕለቱ ሟችን እና ሌሎች ጓደኞቹን እራት ለመብላት ሲጠብቃቸው የነበረ መሆኑን፣ 2ኛ ተጠሪ ስልክ ደውሎ አንጠጣም ወይ ያለው መሆኑን፣ ምስክሩም እራት በልቼያለው መሆኑን፣ ጓደኞቹን እየጠበቀ ሳለ ስልክ የደወሉለት መሆኑን፣ ተነስቶ ሲሄድ 2ኛ ተጠሪ ደውሎ እራት አልበላህም ወይ ያለው መሆኑን፣ ምስክሩም አዎ ሲለው ብላና እንጠጣለን ያለው መሆኑን፣ ምስክሩም ስጨርስ እደውላለሁ ብሎት የሄደ መሆኑን፣ እራት ከሚበሉበት ቦታ ሲደርስ ጓደኞቹ ሲጠብቁት የነበረ መሆኑን፣ ምግቡ እስኪደርስ ድረስ ስልክ የተደወለለት እና የአባቱ ስልክ መሆኑን፣ ምግቡን እየተሻሙ ስለሚበሉ ስልኩን ድምጽ አልባ አድርጎ ኪሱ ውስጥ ያስገባ መሆኑን፣ በልተው ሲወጡ ሟችን ስልክ ሲያወራ የነበረ መሆኑን፣ ሟች እና 2ኛ ተጠሪ የዶርማቸው ልጆች በመሆናቸው እናስታርቃቸው ያሉ መሆኑን እና ሾላ ዛፍ ያለበት ቦታ ሲደርሱ አንድ ሜትር ሟች ወደ ኋላ ቀረት ያለ መሆኑን፣ ከዚያም ኳ የሚል ድምጽ የሰሙ መሆኑን፣ ደንግጠው ዞር ሲሉ ሟች ወደፊት ተንደርድሮ ሲወድቅ ከዚያን ቀን በፊት አይተውት የማያውቁ ልጅ ስላዩ ተከትለውት የሄዱ መሆኑን፣ ሟችን ክሊኒክ የወሰዱት መሆኑን እና ሪፈር ተጽፎላቸው ሆስፒታል ሲደርሱ ሟች ሕይወቱ ያለፈ መሆኑን፣ 1ኛ ተጠሪ ተጠሪዎች ደውለው ሚሽን እንዳሉት እና መጠጥ ቤት ሲጠጡ አምሽተው የሟችን ፎቶ ያሳዩት መሆኑን፣ ሟች  አዋርዶኛል ሰድቦኛል ብመታው ሪከርድ አለብኝ ተመራቂ ስለሆንኩ አካዳሚክ ዲስሚሳል ሊያጋጥመኝ ይችላል፣ ሟችን አስፈራራልኝ ምታልኝ ያሉት መሆኑን፣ ከሾላ ስር ተደብቆ ፈርቶ ሊተወው ሲል ፊት ለፊት ሆኖ ስኳር ሸሚዝ የለበሰው ነው አንተ የሴት ልጅ በለው ሲለው አይኔን ጨፍኖ በድንጋይ እንደመታው ሲናገር የሰማ መሆኑን በመግለጽ መመስከሩን የሚያሳይ ነው፡፡ ሌሎች ምስክሮችም በተመሳሳይ የመሰከሩ መሆኑን የስር ፍ/ቤት ውሳኔ ያሳያል፡፡

የዳግማዊ ምኒሊክ ሆስፒታል የጻፈው የአስከሬን ምርመራ ማስረጃ ሟች በድብደባ ምክንያት ሕይወቱ ያለፈ መሆኑን፣ አስከሬኑ በጋዝ ክምችት ያለ እና መበስበስ ደረጃ ላይ የደረሰ መሆኑን፣ በቀኝ ግንባሩ በኩል ሁለት ቦታ በትንሹ የአጥንት ጉዳት የሚታይ መሆኑን በጭንቅላቱ ቆዳ ውስጥ ደም የፈሰሰ መሆኑን፣ የራስ ቅሉ ያልተሰበረ መሆኑን፣ ጭንቅላቱ ተከፍቶ ሲታይ አንጎሉ ከደም ጋር የተቀላቀለ ወደ ፈሳሽነት የተቀየረ መሆኑን ለሞት ያበቃው የጭንቅላት ጉዳት እና የአንጎል ጉዳት መሆኑን የሚያሳይ ነው፡፡

ሚች ከሚማርበት ዩኒቨርሲቲ ቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት የተላከ ማስረጃ ሚች የ5ኛ ዓመት የመካኒካል ኢንጅነሪንግ ተማሪ መሆኑን፤ በአንድ ዶርም ውስጥ የሚኖረው 2ኛ ተጠሪ የዛቻ ወንጀል ፈጽሞብኛል በማለት መረጃ የሰጣቸው መሆኑን የሚገልጽ ነው፡፡

1ኛ ተጠሪ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 35 መሠረት የሰጠው ቃል ይዘት፡- ተጠሪዎች ስልክ ደውለው ዛሬ ተልዕኮ አለ መምጣት አለብህ ያሉት መሆኑን፤ የምን ተልዕኮ ብሎ ሲጠይቃቸው ስትመጣ ይነገርሃል ያሉት  መሆኑን እና ኮንሰርት ለማየት ስመጣ እደውልልሃለሁ ያላቸው መሆኑን፤ በመቀጠልም 3ኛ ተጠሪ ደውሎለት 10:00 ሰዓት ላይ የተገናኙ መሆኑን እና መጠጥ የገዛለት መሆኑን፤ ከ2ኛ ተጠሪ ጋር እየተደዋወለ ልጁን እየተከታተልከው ነው ወይ ያለው መሆኑን እና ከትንሽ ደቂቃ በኋላ ተገናኝተው የሄዱ መሆኑን፤ 1ኛ ተጠሪም ወደ ኮንሰርት ሄዶ ረብሻ ስለነበር ሳይገባ የቀረ መሆኑን፤ በመቀጠልም መጠጥ ቤት ገብቶ ሲጠጣ የነበረ መሆኑን፤ 3ኛ ተጠሪም ስልክ ደውሎ ሙን ላይት ከሚባለው ቦታ እንድትመጣ ያለው መሆኑን፤ ካሉት ቦታ ላይ ሄዶ መጠጥ የጠጣ መሆኑን፤ ወዲዚህ ለምን መጣን ሲላቸው 3ኛ ተጠሪ እኔ የተጣላሁት ልጅ አለ፤ ከሰው መሃል ክብሬን ገፎኛል በቦክስ መቶ ጥሎኛል ያለው መሆኑን፤ በምን ምክንያት ተጣላችሁ ሲለው በብሔር ምክንያት ነው እናንተ ጉረኞች ናችሁ የተለየ ምን አላችሁ ብሎኛል ያለው መሆኑን፤ አንተም ሰው ነህ እሱም ሰው ነው ሲለው ፈርቼ እንዳይመስልህ ግቢ ፈርመናል በሀምሳ ቀን ሌላ ጥፋት ከተገኘብን ያባርሩናል ያለው መሆኑን፤ 2ኛ ተጠሪ ለሚች ጓደኛ ስልክ ደውሎ ለእራት ትመጣላችሁ ወይ ያለው መሆኑን እና እንመጣለን ሲለው ደስ ያለው መሆኑን፤ ሚች እና ጓደኞቹ እራት ወደሚበላበት ቦታ ሲያልፉ ያሳዩት መሆኑን፤ ብዙ ጠብቆ አልወጣ ሲለው ታክሲ አላገኝም ልሂድ ያላቸው መሆኑን፤ ከዚያም ሚች እና ጓደኞቹ ሲወጡ 2ኛ ተጠሪ ደውሎ ስልክ ደውሎ ስልክ የሚያናግረው ነው መጣልህ ያለው መሆኑን እና ዞር ብሎ በድንጋይ ከኋላው በኪል አንድ ጊዜ የመታው መሆኑን በመግለጽ ቃሉን የሰጠ መሆኑን የሚያሳይ ነው፡፡

2ኛ ተጠሪ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 35 መሠረት የሰጠው ቃል ይዘት፡- በዕለት ግጭት ከሚች ጋር ከአንድ ወር በላይ የተጣሉ መሆኑን፤ የጠቡ ምክንያት ሙዚቃ ከፍቶ ዶርም ውስጥ ስፖርት ሲሰራ ሚች ጠላ ቤት አስመሰላችሁት ያላቸው መሆኑን፤ የሎከር በር ተዘግቶ ስለነበር ዘጋ አድርጎት ሲልፍ አንተ ዕብድ ነህ ወይ ሲለው እብድ አይደለሁም ያለው መሆኑን፤ ሚችም ትረብሻለህ ሲለው ተያይዘው በጥፊ ሲመታው ሚችም በቦክስ የመታው መሆኑን እና ፊቱ ላይ የተሰፋ መሆኑን፤ ሌሎች ጓደኞቹ በድርጊቱ ይናደዱ የነበረ መሆኑን፤ እሱም ዋጋ ከፍለን እንመረቅ ሳንመረቅ እንዳንቀር ያላቸው መሆኑን፤ ከ1ኛ ተጠሪ ጋር ስለጠቡ ያወሩ መሆኑን እና ከፊቱ ላይ የሆነ ምልክት መኖር አለበት በማለት ሚችን እንዲመታው የነገረው መሆኑን የሚያሳይ ነው፡፡

3ኛ ተጠሪ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 27/2 መሠረት የሰጠው ቃል ይዘት፡- ካምፓስ ግቢ ውስጥ 2ኛ ተጠሪ ሙዚቃ ከፍቶ ስፖርት ሲሰራ ሚች ሙዚቃውን ቀንስ በማለት ተጣልተው 2ኛ ተጠሪ ዓይኑ አካባቢ

የተመታ እና ጉዳት የደረሰበት መሆኑን ሲነግረው ተናዶ 1ኛ ተጠሪን ዘንዘልማ ከተባለ ቦታ ወደ ባሕርዳር ከተማ እንዲመጣ ስልክ የደወለለት መሆኑን፣ ሚች ግቢ ውስጥ መቶ እንደዘረረው እና በተማሪዎች ፊት እንዳዋረደው የነገረው መሆኑን፣ ቀለል ያለ ጉዳት እንዲደርስበት የነገው መሆኑን፣ 2ኛ ተጠሪም ከሚች ጋር የተነሳውን ፎቶ ያሳየው መሆኑን እና በጣም እንዲጎዳ ሳይሆን እንዲደነግጥ አድርገህ ቀለል ያለ ጉዳት አድርስበት ያለው መሆኑን፣ ቀይ እስኬር ሸሚዝ የለበሰው ነው በማለት ያሳዩት መሆኑን የሚያሳይ ነው፡፡

በመሠረቱ አንድ ሰው ወንጀል አደረገ የሚባለው ሕገ ወጥነቱና አስቀጪነቱ በሕግ የተደነገገን ድርጊት ፈጽሞ በተገኘ ጊዜ መሆኑ እና አንድ ወንጀል ተደረገ የሚባለውም ወንጀሉን የሚቋቋሙት ሕጋዊ፣ ግዙፋዊ እና ሞራላዊ ፍሬ ነገሮች በአንድነት ተሟልተው ሲገኙ ብቻ መሆኑ በወንጀል ሕግ አንቀጽ 23 (1) እና (2) ስር ተደንግጎ የሚገኝ ሲሆን በወንጀል ጉዳይ የሚቀርብ የክስ ማመልከቻ ደግሞ ተከሳሹ የተከሰሰበትን ወንጀል እንዲሁም የወንጀሉ መሰረታዊ ነገርና ሁኔታዎች የተገለጹበት ሊሆን እንደሚገባ እና ስለ ወንጀሉና ስለሁኔታው የሚሰጠው ዝርዝር መግለጫ ተከሳሹ ፈጸመ የተባለውን ተግባር ወንጀል ከሚያደርገው ሕግ አነጋገር ጋር በጣም የተቀራረበ መሆን እንደሚገባው በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 111 እና 112 ድንጋጌዎች ላይ የተደነገገውም ከሳሹን ወገን በወ/ሕ/አንቀጽ 23(2) ስር የተመለከቱት የወንጀል መማቋቋሚያ ፍሬ ነገሮች ተሟልተው መገኘታቸውን ለማስረዳት እንዲያስችለው መሆኑን ከድንጋጌዎቹ ይዘት መገንዘብ ይቻላል፡፡ ይህም ከሳሽ ወገን በክሱ መሰረት የማስረዳት ግዴታ ተወጥቷል ሊባል የሚችለው ቀደም ሲል በተጠቀሱት የወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 111 እና 112 ድንጋጌዎች መሰረት አዘጋጅቶ ባቀረበው የክስ ማመልከቻ መሠረት ተከሳሹ ወንጀል መፈጸሙን ማስረዳት በቻለ ጊዜ ነው፡፡ ተከሳሽ ባቀረበው መከላከያ ማስረጃ በዓቃቤሕግ ማስረጃ የተረጋገጠበትን ፍሬነገር በቂ እና አሳማኝ ሊባል በሚችል ማስረጃ ካላስተባበለም ጥፋተኛ እንደሚባል ከወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 149/1 ድንጋጌ ይዘት መዘገንዘብ ይቻላል፡፡

በያዝነው ጉዳይ ዓቃቤሕግ ያቀረባቸው የሰው ምስክሮች እና የሰነድ ማስረጃዎች ይዘት የሚያስገነዝቡት በሚች እና በ2ኛ ተጠሪ መካከል አስቀድሞ ጸብ የነበረ መሆኑን፣ በሚች እና በ2ኛ ተጠሪ መካከል ጸብ ከተፈጠረ በኋላ ሚች ለሚማርበት ዩኒቨርሲቲ ቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት በአንድ ዶርም ውስጥ የሚኖረው 2ኛ ተጠሪ የዛቻ ወንጀል ፈጽሞብኛል በማለት ያሳወቀ መሆኑን፣ 2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች ስልክ ደውለው ዛሬ ተልዕኮ አለ መምጣት አለብህ በማለት 1ኛ ተጠሪን የጠሩት መሆኑን፣ የምን ተልዕኮ ብሎ ሲጠይቃቸው ስትመጣ ይነገርሃል ያሉት መሆኑን፣ 2ኛ ተጠሪ ለሚች ጓደኛ ስልክ ደውሎ ለእራት ትመጣላችሁ ወይ ያለው መሆኑን እና እንመጣለን ሲለው ደስ ያለው መሆኑን፣ በ2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች ጥሪ መሠረት 1ኛ ተጠሪ ወደ ተባለው ቦታ ሲሄድ መጠጥ የገዛለት መሆኑን፣ 3ኛ ተጠሪ ከ2ኛ ተጠሪ ጋር እየተደዋወለ ልጁን እየተከታተልከው ነው ወይ ያለው መሆኑን እና ከትንሽ ደቂቃ በኋላ ተገናኝተው የሄዱ መሆኑን፣ 3ኛ ተጠሪም ስልክ ደውሎ ሙን ላይት ከሚባለው ቦታ እንድትመጣ

ያለው መሆኑን፤ ካሉት ቦታ ላይ ሄዶ መጠጥ እየጠጡ ወዲዚህ ለምን መጣን ሲላቸው 3ኛ ተጠሪ እኔ የተጣላሁት ልጅ አለ፤ ከሰው መሃል ክብሬን ገፎኛል በቦክስ መቶ ጥሎኛል ያለው መሆኑን፤ በምን ምክንያት ተጣላችሁ ሲለው በብሔር ምክንያት ነው እናንት ጉረኞች ናችሁ የተለየ ምን አላችሁ ብሎኛል ያለው መሆኑን፤ በመቀጠልም ፈርቼ እንዳይመስልህ ግቢ ፈርመናል በሀምሳ ቀን ሌላ ጥፋት ከተገኘብን ያባርሩናል ያለው መሆኑን፤ ሟች እና ጓደኞቹ እራት ወደሚበላበት ቦታ ሲያልፉ ያሳዩት መሆኑን፤ ከዚያም ሟች እና ጓደኞቹ ሲወጡ 2ኛ ተጠሪ ደውሎ ስልክ የሚያናግረው ነው መጣልህ ያለው መሆኑን እና ዞር ብሎ በድንጋይ ከኋላው የመታው መሆኑን እና ሟች ወደፊት ተንደርድሮ የወደቀ መሆኑን እና በጭንቅላቱ ላይ በደረሰበት ጉዳት ሕይወቱ ያለፈ መሆኑን ነው፡፡

በስር ፍ/ቤት ቀርበው የተሰሙት የዓቃቤሕግ ማስረጃዎች የሚያስገነዝቡት ከላይ የተመለከተውን ነው የምንል ከሆነ 1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 35 መሠረት ለፍ/ቤት በሰጡት ቃል፤ 3ኛ ተጠሪ ደግሞ  በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 27/2 መሠረት ለፖሊስ በሰጠው ቃል ሀሳባችን የነበረው በሟች ላይ ቀላል ጉዳት እንዲደርስ ነበር በማለት ያስመዘገቡት ቃል ብቻውን ተነጥሎ ተጠሪዎች ሊቀጡ የሚገባው በሀሳባቸው ልክ ነው ወደሚል መደምደሚያ የሚያደርስ ነው ወይ? የሚለው የዚህ ችሎት ምላሽ የሚያስፈልገው የክርክሩ መሠረታዊ ጭብጥ ነው፡፡

ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተው የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የ2ኛ እና 3ኛ ተጠሪ ሀሳብ በሟች ላይ ቀለል ያለ ጉዳት እንዲደርስ ነበር ከሚል መደምደሚያ ላይ የደረሰ ቢሆንም ተጠሪዎች ክሱን እንዲከላከሉ ብይን ከተሰጠ በኋላ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 142/3 መሠረት ለፍ/ቤቱ በሰጡት ቃል ድርጊቱን አልፈጸምንም በማለት ከመካዳቸው በቀር ሀሳባችን የነበረው በሟች ላይ ቀላል ጉዳት እንዲደርስበት ነበር በማለት የሰጡት ቃል ካለመኖሩም በላይ ሀሳባቸው በሟች ላይ ቀላል ጉዳት እንዲደርስ ስለመሆኑ በሌላ ደጋፊ ማስረጃ የተረጋገጠ ስለመሆኑ የስር ፍ/ቤት ውሳኔ ይዘት አያሳይም፡፡  በ2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች ጥሪ መሠረት ድርጊቱን የፈጸመው 1ኛ ተጠሪ  በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 35 መሠረት በሰጠው ቃልም ተጠሪዎች በሟች ላይ ቀለል ያለ ጉዳት እንዲያደርስበት የነገሩት ስለመሆኑ በመግለጽ የሰጠው ቃል የለም፡፡ ይልቁንም ሟች እና 2ኛ ተጠሪ በዩኒቨርሲቲው ዶርም ውስጥ ሙዚቃ ከፍታችኋል በሚል ተጣልተው ሟች እና 2ኛ ተጠሪ የተደባደቡ እና በዚህ ምክንያት በመካከላቸው አለመግባባት የተፈጠረ መሆኑ፤ ሟች 2ኛ ተጠሪ ዛቻ ይፈጽምበት እንደነበረ ለዩኒቨርሲቲው ቀደም ብሎ ያሳወቀ መሆኑ፤  2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች ስልክ ደውለው ዛሬ ተልዕኮ አለ መምጣት አለብህ በማለት 1ኛ ተጠሪን የጠሩት መሆኑ፤ 3ኛ ተጠሪ ሟች ከሰው መሃል ክብሬን ገፎኛል በቦክስ መቶ ጥሎኛል የተጣላነው በብሔር ምክንያት ነው እናንተ ጉረኞች ናችሁ የተለየ ምን አላችሁ ብሎኛል ያለው መሆኑ፤ በመቀጠልም ፈርቼ እንዳይመስልህ ግቢ ፈርመናል በሀምሳ ቀን ሌላ ጥፋት ከተገኘብን ያባርሩናል ያለው መሆኑ፤ 3ኛ ተጠሪ ከ2ኛ ተጠሪ ጋር እየተደዋወለ ሟች  እራት ወደሚበላበት ቦታ መምጣት አለምምጣቱን ለማረጋገጥ መከታተላቸው፤ 2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች 1ኛ ተጠሪን መጠጥ በመጋበዝ ሟች ራት በልቶ እስኪወጣ

ድረስ እንዲጠብቅ ማድረጋቸው እና ሚች ከጓደኞቹ ጋር እራት በልቶ ሲመለስ  ስኳር ሸሚዝ የለበሰው እና ስልክ የሚያወራው ነው በማለት ሚችን ለይተው ማሳየታቸው ዓቃቤሕግ ባቀረባቸው ሌሎች ደጋፊ ማስረጃዎች መረጋገጡ ሲታይ ከሳሽ የሆነው ዓቃቤሕግ ባቀረበው የወንጀል ክስ ውስጥ የገለጻቸውን ፍሬ ጉዳዮች ትክክለኛነት ተጠሪዎች ስለመፈጸማቸው ለማሳየት ያቀረባቸው ማስረጃዎች እርስ በርሳቸው የሚደጋገፉና ተያያዥነት ያላቸው እና የተጠሪዎች ሀሳብ በሚች ላይ ቀላል ጉዳት እንዲደርስ ሳይሆን ሚችን የመግደል ሀሳብ እንደነበር የሚያሳይ ነው፡፡ የተጠሪዎች ሀሳብ የመግደል ሀሳብ ከነበረ ቀጥሎ መታየት ያለበት ተጠሪዎች ጥፋተኛ ሊባሉ የሚገባው በየትኛው የወንጀል ሕጉ ድንጋጌ ነው? የሚለው ነው፡፡

አንድ ሰው በወንጀል ሕግ አንቀፅ 539(1(ሀ)) መሠረት ጥፋተኛ ሊባል የሚችለው ሰውን ለመግደል አስቀድሞ የነበረው ሐሳብ ወይም ምክንያት፤ ለመግደል የተጠቀመበት መሣሪያ ወይም ዘዴ፤ ያገዳደሉ ሁኔታ ወይም ግድያው የተፈጸመበት ቅጣትን የሚያከብድ ጠቅላላ ምክንያት አንቀጽ 84 ወይም 86 ስር ሲታይ ወንጀል አድራጊው በተለይ ጨካኝ፣ ነውረኛ ወይም አደገኛ መሆኑን የሚያመለክት ሆኖ ሲገኝ እንደሆነ ነው በማለት ይደነግጋል፡፡ ከድንጋጌው ይዘት መገንዘብ የሚቻለው በድንጋጌው ላይ የተጠቀሱት ነጥቦች እያንዳንዳቸው ራሣቸውን ችለው የሚቆሙ መሆኑን ነው፡፡

በያዝነው ጉዳይ 2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች በሚች እና በ2ኛ ተጠሪ መካከል በተፈጠረው አለመግባባት መነሻነት የያዙትን ቂም መሠረት በማድረግ 1ኛ ተጠሪን ተልዕኮ አለ በማለት በመጥራት እና ሚችን ለይተው በማሳየት ሚች በድንጋይ ተመቶ እንዲሞት ለማድረግ ዋናውን ዕቅድ ያቀነባባሩ እና የወንጀሉ ዋና ጠንሳሽ መሆናቸው የተረጋገጠ በመሆኑ የ1ኛ ተጠሪ የወንጀል ድርጊት በሚች ላይ የሚያመጣውን ውጤት ሙሉ ለሙሉ መቀበላቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ ወንጀሉ ቂምን መሠረት በማድረግ ሶስቱም ግብረአበሮች ተሳታፊ ሆነው የፈጸሙት በመሆኑ እና ሚች ጭንቅላቱን በድንጋይ ተመቶ በጭንቅላቱ ላይ በደረሰው ጉዳት ምክንያት ሕይወቱ ያለፈ መሆኑ በሕክምና ማስረጃ የተረጋገጠ በመሆኑ ተጠሪዎቸ ጥፋተኛ ሊባሉ የሚገባው በወንጀል ሕግ አንቀጽ 32/1/ሀ እና 539/1/ሀ ድንጋጌ መሠረት ነው፡፡ በመሆኑም የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የ2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች ሀሳብ በሚች ላይ መጠነኛ የሆነ የአካል ጉዳት እንዲደርስበት ማድረግ በመሆኑ ጥፋተኛ ሊባሉ የሚገባው በተከሰሱበት የወንጀል ሕግ አንቀጽ 539/1/ሀ ሳይሆን በአንቀጽ 556/2/ሀ ነው፤ 1ኛ ተጠሪም ጥፋተኛ ሊባል የሚገባው በወንጀል ሕግ አንቀጽ 540 ነው በማለት 1ኛ ተጠሪን በዘጠኝ ዓመት ጽኑ እሥራት፤ 2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎችን እንደቅደም ተከተላቸው ደግሞ በስድስት ወር እና በስምንት ወር እሥራት እንዲቀጡ ሲል የሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ ስለሆነም ተከታዩን ውሳኔ በአብላጫ ድምጽ ሰጥተናል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 0218981 መጋቢት 14 ቀን 2010 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ፤ ይህንኑ ውሳኔ በማጽናት የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 78191 ሠኔ 28 ቀን 2010 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ በወ/መ/ስ/ስ/ሕ/ቁ 195/2/ለ/2 መሠረት ተሽሯል፡፡
2. በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የባሕርዳር እና አካባቢዋ ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ 04-04796 ሕዳር 29 ቀን 2010 ዓ.ም የሰጠው የጥፋተኝነት ውሳኔ እና ታሕሳስ 04 ቀን 2010 ዓ.ም የሰጠው የቅጣት ውሳኔ በወ/መ/ስ/ስ/ሕ/ቁ 195/2/ለ/2 መሠረት ጸንቷል፡፡

## ትዕዛዝ

- የፌዴራል፤ የክልሉ እና የአዲስ አበባ ፖሊስ 2ኛ እና 3ኛ ተጠዎችን በተገኙበት ቦታ ይዘው ለሚመለከተው ማረሚያ ቤት እንዲያስረክቡ ታዟል፡፡
- የሚመለከተው ማረሚያ ቤት አስተዳደርም 2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች በፖሊስ ተይዘው ሲቀርቡለት 1ኛ ተጠሪም በማረሚያ ቤት የሚገኝ በመሆኑ ሶስቱም ተጠሪዎች በዚህ ጉዳይ ከዚህ በፊት የታሰሩት ካለ ታሳቢ በማድረግ በዚህ ችሎት በተሰጠው ውሳኔ መሠረት ተከታትሎ ቅጣቱን እንዲያስፈጽም ታዟል፡፡ ይጻፍ
- መዝገቡ ውሳኔ ስለገኘ ተዘግቷል፡፡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የሦስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

## የልዩነት ሀሳብ

በተራ ቁጥር 4 እና 5 ላይ የተመዘገበው ዳኞች በዚህ መዝገብ በቀረበው ጉዳይ አከራካሪ በሆነው ጭብጥ አብላጫ ድምፅ የያዙት የስራ ባልደረቦቻችን በሰጡት ውሣኔ ስላልተስማማን ለልዩነት ያበቁንን ምክንያቶች ከዚህ ቀጥሎ አስፍረናል፡፡

በመዝገቡ ላይ ከቀረቡት ክርክሮች መካከል ዋናውና በመካከላችን አከራካሪ የነበረው ነጥብ ተጠሪዎች ጥፋተኛ ተብለው ቅጣት ሊወሰንባቸው የሚገባው የባህር ዳር እና አካባቢዋ ከፍተኛ ፍርድ ቤት እንደሰጠው ፍርድ በከባድ የሰው ግድያ ወንጀል ነው ወይስ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አሻሽሎ እንደወሰነው 1ኛ ተጠሪ በተራ የሰው ግድያ ወንጀል፤ 2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች ደግሞ ታስቦ በሚፈፀም ቀላል የአካል ጉዳት ወንጀል የሚለው ነው፡፡ የስር ፍርድ ቤት የሆነው የባህር ዳርና አካባቢዋ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የአሁን 2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች ከሟች ጋር  የነበራቸውን ቂም መነሻ በማድረግ ሶስቱም የወንጀል ህግ አንቀጽ 32/1/ /ሀ/ ና አንቀጽ 539/1/ /ሀ/ የተመለከተውን ክልከላ ተላልፈው ከባድ የሰው መግደል ወንጀል ፈፅመው የሚል ውሣኔ ሰጥቷል፡፡የአሁን ተጠሪዎች ባቀረቡት

የይግባኝ አቤቱታ መነሻነት የግራ ቀኙን ክርክር የመረመረው የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በቀረበው የዐ/ህግ ማስረጃ አመልካቾች ድርጊቱ መፈፀማቸው ተረጋግጦባቸው የዐ/ሕግ ማስረጃ ያላስተባበሉ በመሆናቸው የጥፋተኝነት ፍርድ መሰጠቱ ተገቢ ሆኖ ሣለ ጥፋተኛ ሊባሉ የሚገባው ግን 1ኛ ተጠሪ በወንጀል ሕግ አንቀጽ 540 እና 2ኛ እና 3ኛ ተጠሪ ታስቦ በሚፈፀም ቀላል የአካል ጉዳት ማድረስ ወንጀል ነው ሲል የከፍተኛው ፍርድ ቤቱን ውሣኔ አሻሽሏል፡፡ ይህ ውሣኔ በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር በሚ ችሎት ተመርምሮ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ያልተፈፀመበት ስለመሆኑ ትእዛዝ ተሰጥቶበታል፡፡

ከላይ እንደተገለፀው በፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር  ሰሚ ችሎት ተጠሪዎች የወንጀል ድርጊት መፈፀማቸው ስለተረጋገጠባቸው የጥፋተኝነት ፍርድ መወሰኑ ተገቢ ሆኖ ሣለ አከራካሪ የነበረውና ለልዩነታችን ምክንያት የሆነው ተጠሪዎች ወንጀል መፈፀማቸውን ለማስረዳት ዐ/ሕግ ለስር ፍርድ ቤት ያቀረባቸው ማስረጃዎች ካረጋገጡት ፍሬ ነገር አንፃር ጥፋተኛ ሊባሉ የሚገባው በየትኛው ድንጋጌ ነው፡፡ ዐ/ሕግ ባቀረበው ማስረጃ 1ኛ ተጠሪ ይህን ድርጊት የፈፀመውም 2ኛ ና 3ኛ ተጠሪዎች ሟች ሁለተኛ ተጠሪን ደብድቦት ስለነበር በዚህ ድርጊት በሁለተኛ ተጠሪ የደረሰውን የሞራል ጉዳት ለማካካስ በማሰብ 1ኛ ተጠሪ ሟችን እንዲያስፈራራቸውና እንዲያስደነግጥላቸው ስለጠየቁት ለማስፈራራትና ለማስደንገጥ አስቦ ፈራ ተባ እያለ አንድ ጊዜ ድንጋይ ወርውሮ የሟችን ጭንቅላት መምታቱን በዚህ ምት ምክንያት ሟች ለሞት መብቃቱ የስር ፍርድ ቤቶች የመዝገብ ግልባጭ ያስገነዝባል፡፡

በወንጀል ሕግ አንቀጽ 539 ድንጋጌ መሰረት አንድ ሰው የሰው ግድያ ወንጀል ፈፅሟል ተብሎ ጥፋተኛ የሚባለውና የሚቀጣው የሰው መግደል ወንጀል ከመፈፀሙ በፊት አስቀድሞ ሰውን ለመግደል በማሰብ የነበረውን ሃሳብና ሃሳቡን ከፍፃሜ ለማድረስ ያደረገውን ዝግጅት እንዲሁም የተጠቀሰበትን መሣሪያ ለወንጀሉ መፈፀም ያበቃውን ምክንያትና አገዳደሉን ሁኔታ ወይም አድራጊውን ጨካኝነት ወይም ነውረኝነት ግምት ውስጥ በማስገባት ሊሆን እንደሚገባ ተደንግጓል፡፡ በዚህ ድንጋጌ መሰረት አድራጊው ወንጀል ለመፈፀም ማሰብ ብቻ ሣይሆን አስቀድሞ መግደል አለብኝ ብሎ ማቀድን መዘጋጀትን እና ባቀደው መሰረት መፈፀሙ መረጋገጥ ይኖርበታል፡፡ ተከሳሽ በእነዚህ መመዘኛዎች መሰረት ድርጊቱን የፈፀመ ስለመሆኑ በቅድሚያ የማስረዳት ሀላፊነቱ የዐ/ሕግ ስለመሆኑ የታመነ ነው፡፡

በሌላ በኩል ወንጀል ተፈፅሟል ለማለት የድርጊት ፈፃሚውን ወንጀል ለመፈፀም የነበረውን ሐሳብና በተፈፀመው ድርጊት የተገኘውን ውጤት ለማግኘት አስቦ አድራጊው ድርጊቱን ስለመፈፀሙ በታመነ ጊዜ ስለመሆኑ፤ ነገር ግን አድራጊው መፈፀም ካሰበው ድርጊት ለተፈፀመው ድርጊት ባስከተለው ውጤት ተጠያቂ ሊሆን እንደማይገባ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 23፤32/2/፤58 ይደነግጋል፡፡

በተያዘው መዝገብ ቅድሚያ የማስረዳት ሃላፊነቱን ለመወጣት ማስረጃ ያቀረበው ዐ/ሕግ ባቀረበው ማስረጃ 2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች 1ኛ ተጠሪ ሟችን እንዲገልላቸው ፍፁም ሐሳብ ያልነበራቸው መሆኑን፤

1ኛ ተጠሪም ድረጊቱን የፈፀመው ሟችን ለመግደል አስቦ ሣይሆን 2ኛና 3ኛ ተጠሪዎች በነበሩት መሰረት ለማስፈራራትና ለማስደንገጥ ብሎ እንደሆነ ተረጋግጧል፡፡

ይህ ከሆነ 2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች ሟች በ1ኛ ተጠሪ እንዲገደል አስቀድሞ ሐሳብ የነበራቸው ስለመሆኑ ባልተረጋገጠበትና ይልቁንም ዐ/ሕግ ራሱ ባቀረበው ማስረጃ 1ኛ ተጠሪ ሟችን እንዲያስፈራራላቸው አስበው የጠየቁትና በዚሁ መሰረት ማስፈራራት ድረጊቱን ለመፈፀም አስቦ 1ኛ ተጠሪ በፈፀመው ድርጊት ሟች ስለሞተ ብቻ ከባድ የሰው መግደል ወንጀል ፈፅመዋል በሚል 1ኛ ተጠሪም 2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች በለመኑት መሰረት ሟችን ለማስፈራራት አስቦና አቅዶ ይህን ለመፈፀም ሟችን አንድ ጊዜ በድንጋይ ሲመታው ስለሞተ ከላይ የተዘረዘሩት የከባድ የሰው መግደል ወንጀል ማቋቋሚያ ከሆኑት መመዘኛዎች መካከል አንዱም ሣያሟላ በከባድ የሰው መግደል ወንጀል ጥፋተኛ ተብለው ቅጣት የወሰነባቸው የከፍተኛ ፍርድ ቤቱ ውሣኔ እንዲፀና መደረጉ መሰረታዊ የማስረጃ ምዘና መርህን የጣሰ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ውሣኔ ነው በሚል ምክንያት ከባልደረቦቻችን የተለየ ሐሳብ ስለያዝን፤ ይልቁንም የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት 1ኛ ተጠሪን የወንጀል ሕግ አንቀጽ 540 ተላልፎ ተራ የሆነ የሰው ግድያ ወንጀል ፈፅሟል በሚል 2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች 1ኛ ተጠሪ በሟች ላይ እንዲፈፀም የፈለጉትን ድርጊት መጠየቅ አለባቸው በሚል የወንጀል ሕግ አንቀጽ 556/2/ ተላልፈው ቀላል የአካል ጉዳት ወንጀል እንዲፈፀም መስማማታቸውን ድርጊቱ እንዲፈፀም ማድረጋቸው ተረጋግጧል በሚል የከፍተኛው ፍርድ ቤት ውሣኔ በማሻሻል መወሰኑ ተገቢ ነበር በሚል በሀሳብ ተለይተናል፡፡

የማይነበብ የሁለት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ብ/ግ

የሰ/መ/ቁ. 167965

ሕዳር 26 ቀን 2012 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** እትመት አሠፋ

ጻውሎስ ኦርሺሶ

ፀሐይ መንክር

መላኩ ካሣዬ

እስቲበል አንዱዓለም

**አመልካች/ቾች፡-** አሕመድ ኢብራሂም ንጉሴ - አልተጠሩም፡፡

**ተጠሪ/ዎች፡-** የኦሮሚያ ክልል ዓቃቤ ሕግ - ዐ.ህግ ምዕራፍ ወርቁ - ቀረቡ፡፡

መዝገቡ የተቀጠረው መርምሮ ፍርድ ለመስጠት ነው፡፡ በመሆኑም መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## <u>ፍርድ</u>

ይህ የሰበር አቤቱታ ሊቀርብ የቻለው አመልካች ሕዳር 09 ቀን 2011 ዓ.ም ጽፎ ባቀረበው የሰበር አቤቱታ በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 284629 ጥቅምት 12 ቀን 2011 ዓ.ም በሰጠው ውሳኔ አመልካች በሕገወጥ መንገድ ሰዎችን ማዘዋወር ወንጀል በቀረቡበት ስድስት ክሶች ተሳትፎ ውጤቱንም የወሰደ በመሆኑ በወንጀል ሕግ አንቀጽ 60/ሐ እና 184/2 ጥፋተኛ መባሉ ተገቢ ነው ሲል የሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለቱ ነው፡፡

ጉዳዩ የወንጀል ክርክርን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ምዕራብ ወለጋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ነው፡፡የአሁን ተጠሪ በአሁን አመልካች እና በስር 1ኛ ተከሳሽ ላይ በስር ፍ/ቤት ያቀረባቸው ክሶች ስድስት ሲሆኑ ይዘታቸውም፡-

<u>1ኛ ክስ</u>፡- ተከሳሾች የወንጀል ሕግ አንቀጽ 32/1/ሀ እና አዋጅ ቁጥር 909/2007 አንቀጽ 3/2/ሀ ድንጋጌን በመተላለፍ ጉቴ በተባለ ልዩ ቦታ በቀን 30/04/10 ዓ.ም ከቀኑ በግምት 5፡00 ሰዓት ማንነቱ ካልታወቀ እና ለጊዜው በቁጥጥር ስር ያልዋለ ግለሰብ የግል ተበዳይ አሲያ አባጋሮ ሱቅ ሄዳ ስትመለስ አብዱልቃድር አባጋሮ ጥሩ ስራ አግኝቶልሻል አትፈልጊም ወይ? የሚደርስሽ ጥሩ ስራ እና ጥሩ ቦታ

ነው በማለት በማባበል፣ አልፋው ስትገባ በማግስቱም መጥቶ በማባበል ነገ ስለምትሄዱ በማለዳ 1ኛ ተከሳሽ ጋር አደርሳችኋለሁ በማለት፣ በማግስቱም ከቤት በማስወጣት ስሙ ካልታወቀ ግለሰብ ጋር በመሄድ 1ኛ ተከሳሽ ከሌላ ሰው ጋር በመሆን ተቀብሎ አመልካች ቤት በማምጣት በመሸሸግ፣ ለጊዜው በቁጥጥር ስር ያልዋለች የአመልካች ባለቤት ጋር ተበዳይዋን ፎቶ በማንሳት አትፍሪ ችግር የለም ሲቸግርሽ ለእኔ ትነግሪኛለሽ ፎቶሽን ደግሞ ብትጠፊ ትፈለጊበታለሽ ከሁለት ሳምንት በኋላ ወደ ውጪ ሐገር ሄደሽ እንድትሰሪ አደርግሻለሁ በማለት ወደ ሰው ቤት አሳልፈው በመስጠት ከሰዎች ጋር በስልክ እየተግባቡ ፖሊስ ባደረገው ክትትል የተያዘ በመሆኑ በፈጸመው በሕገወጥ መንገድ ሰዎችን ማዘዋወር ወንጀል ተከሷል የሚል ነው፡፡

<u>2ኛ ክስ፡</u>- ተከሳሾች የወንጀል ሕግ አንቀጽ 32/1/ሀ እና አዋጅ ቁጥር 909/2007 አንቀጽ 3/2/ሀ ድንጋጌን በመተላለፍ በ1ኛ ክስ በተገለጸው ሁኔታ ስሙ እና ማንነቱ ያልታወቀ ግለሰብ የግል ተበዳይ ሩሴ አባሲመንን በቀን 03//05/10 ከቤት በማውጣት ስሙ ካልታወቀ ግለሰብ ጋር ሄዳ 1ኛ ተከሳሽ ስሙ ካልታወቀው ግለሰብ ተቀብሎ ነቀምቴ ከተማ በማሳድር በቀን 04/05/10 አመልካች ቤት በማሳደር ሸሽጎ በቁጥጥር ስር ካልዋለች የአመልካች ባለቤት ጋር በ1ኛ ክስ የተገለጸውን ድርጊት በመፈጸም ላይ ሳሉ ፖሊስ ባደረገው ክትትል ስለተያዙ በፈጸመው በሕገወጥ መንገድ ሰዎችን ማዘዋወር ወንጀል ተከሷል የሚል ነው፡፡

<u>3ኛ ክስ፡</u>- ተከሳሾች የወንጀል ሕግ አንቀጽ 32/1/ሀ እና አዋጅ ቁጥር 909/2007 አንቀጽ 3/2/ሀ ድንጋጌን በመተላለፍ ለጊዜው በቁጥጥር ስር ካልዋለች አለውያ ሰዒድ ጋር በመሆን የግል ተበዳይ ነብያት መሐመድን በቀን 03/05/10 ከቀኑ በግምት 8፡00 ሰዓት 1ኛ ተከሳሽ ከበደሌ ከተማ ወደ ነቀምቴ ከተማ እየተጓዘች ሳለ ከጎንዋ በመቀመጥ ጊምቢ ከተማ ጥሩ ስራ አለ ወደዚያው አደርስሻለሁ በማለት በሌሎች ክሶች ላይ የተገለጹትን ተበዳዮች ሲሳያት በደላላ እጅ ወደ ሌላ ሰው ቤት አልገባም እንጂ ስራ እፈልጋለሁ ስትለው የደላላ እጅ አላውቅም በማለት በድጋሚ አባብሏት በነቀምቴ ከተማ አሳድሯት በቀን 04/05/2010 በግምት 3፡00 ሰዓት በአመልካች ቤት በማምጣት ሸሽገው ከአመልካች ባለቤት ጋር በቤታቸው ሸሽገው 1ኛ ተከሳሽ ገንዘብ ተቀብሎባት አመልካች እና ባለቤቱ ደግሞ ፎቶ በማንሳት አትፍሪ ስትጠፊ ትፈለጊበታለሽ ከሁለት ሳምንት በኋላ ወደ ውጪ ሐገር እንድትሰሪ እናደርግሻለን በማለት ወደ ሌላ ሰው ቤት አሳልፈው ለመስጠት በስልክ እየተግባቡ ሳሉ በፖሊስ ክትትል ስለተያዙ በፈጸመው በሕገወጥ መንገድ ሰዎችን ማዘዋወር ወንጀል ተከሷል የሚል ነው፡፡

<u>4ኛ ክስ፡</u>- ተከሳሾች የወንጀል ሕግ አንቀጽ 32/1/ሀ እና አዋጅ ቁጥር 909/2007 አንቀጽ 3/2/ሀ ድንጋጌን በመተላለፍ ለጊዜው በቁጥጥር ስር ካልዋለች አለውያ ሰዒድ ጋር በመሆን ወ/ት ሳቢቃ ካማል የተባለችውን የግል ተበዳይ በቀን 30/04/10 ከምሽቱ 12፡00 ሰዓት ተበዳይ ሱቅ ሄዳ ስትመለስ 1ኛ ተከሳሽ በመንገድ አስቁሟት አዲስአበባ አደርስሻለሁ እዚያ ሄደሽ ጥሩ ስራ ሰርተሽ ገንዘብ ታገኛለሽ

እራስሽንም ቤተሰብሽንም ትረጃለሽ በማለት፤ እማራለሁ አልሄድም ስትለው ሐሙስ ቀን ድረስ ተማሪ ከዚያ በኋላ ትሄጃለሽ በማለት በቀን 03/05/10 ጠዋት እንዲሄዱ በመንገር፤ ተበዳይዋ ቤተሰቦችዋን ደብቃ ከቤት ወጥታ እንድትሄድ በማድረግ በ6ኛ ክስ ላይ ከተገለጸችው የግል ተበዳይ ጋር 1ኛ ተከሳሹ በመኪና አሳፍሮአቸው ነቀምት ከተማ አሳድሯት በማግስቱም በአመልካች ቤት በማምጣት ሸሽገው ለጊዜው በቁጥጥር ስራ ካልዋለች የአመልካች ባለቤት ጋር በመሆን በራሳቸው ቤት ውስጥ በመሸሸግ፤ 1ኛ ተከሳሽ ገንዘብ ተቀብሎ አመልካች እና ባለቤቱ ደግሞ ፎቶ በማንሳት ወደ ውጪ ትሄጃለሽ በማለት በማባበል ወደ ሌላ ሰው ቤት አሳልፎ ለመስጠት ከሌሎች ሰዎች ጋር በስልክ እየተግባቡ ሳሉ በፖሊስ ክትትል የተያዙ በመሆኑ በፈጸመው በሕገወጥ መንገድ ሰዎችን ማዘዋወር ወንጀል ተከሷል የሚል ነው፡፡

<u>5ኛ ክስ፡</u>- ተከሳሾች የወንጀል ሕግ አንቀጽ 32/1/ሀ እና አዋጅ ቁጥር 909/2007 አንቀጽ 3/2/ሀ ድንጋጌን በመተላለፍ ለጊዜው በቁጥጥር ስር ካልዋለች አለውያ ሰዒድ ጋር በመሆን የግል ተበዳይ ወ/ት ለይላ አህመድ የተባለችውን 1ኛ ተከሳሽ ጓደኛዋን ሳቢቃ ከማል በሕገወጥ መንገድ ለማዘዋወር በተደጋጋሚ ሲጠይቃት ቆይቶ በቀን 02/05/10 ከቀኑ በግምት 5፡00 ሰዓት መንገድ ላይ አግኝቷት ጊምቢ ወደ ተባለ ጥሩ ሐገር አደርስሻለሁ እዚያ ገንዘብ አግኝተሽ እራስሽን ችለሽ ቤተሰብሽንም ትረጃለሽ በማለት በማባበል በማግስቱ ጉዞ ስለሆነ ተዘጋጂ በማለዳ ተነስተን እንሄዳለን እኔ ቶባ ከተማ እጠብቅሻለሁ በማለት በቀን 03/05/10 ዓ.ም ጠዋት ከቤት በማውጣት 1ኛ ተከሳሽ መኪና አሳፍሯት ነቀምት ከተማ አሳድሯት በማግስቱ ወደ አመልካች ቤት በማምጣት ሸሽገው ለጊዜው ካልተያዘችው የአመልካች ባለቤት ጋር በመሆን ከላይ ባሉት ክሶች በተገለጸው ሁኔታ የተያዙ በመሆኑ በፈጸመው በሕገወጥ መንገድ ሰዎችን ማዘዋወር ወንጀል ተከሷል የሚል ነው፡፡

<u>6ኛ ክስ፡</u>- ተከሳሾች የወንጀል ሕግ አንቀጽ 32/1/ሀ እና አዋጅ ቁጥር 909/2007 አንቀጽ 3/2/ሀ ድንጋጌን በመተላለፍ ለጊዜው በቁጥጥር ስር ካልዋለች አለውያ ሰዒድ ጋር በመሆን የግል ተበዳይ ወ/ት አይሻ አህመድ የተባለችውን በጓደኛዋ ሳቢቃ ከማል በቀን 02/05/10 ዓ.ም የሐሰት ቃል በመንገር በማታለል በማግስቱ ከቤት በማውጣት በ4ኛ ክስ ተበዳይ ከሆነችው ከሳቢቃ ከማል ጋር በመሆን 1ኛ ተከሳሽ መኪና አሳፍሮ ነቀምት ከተማ አሳድሯት በማግስቱ በአመልካች መኖሪያ ቤት በማምጣት ሸሽገው 1ኛ ተከሳሽ ገንዘብ ተቀብሎባት ካልተያዘቸው የአመልካች ባለቤት ጋር በመሆን ከላይ ባሉት ክሶች በተገለጸው ሁኔታ የተያዙ በመሆኑ በፈጸመው በሕገወጥ መንገድ ሰዎችን ማዘዋወር ወንጀል ተከሷል የሚል ነው፡፡

ተከሳሾች ክሱ ተነቦላቸው እንዲረዱት ከተደረገ በኋላ ተቀብለውታል የተባለው የገንዘብ መጠን በክሱ ውስጥ አልተገለጸም በማለት ክሱን ተቃውመው ክሱ በዚህ አግባብ እንዲሻሻል የተደረገ መሆኑን የውሳኔው ይዘት ያሳያል፡፡ አመልካች የእምነት ክሕደት ቃሉን ሲጠየቅም በዓቃቤሕግ ክስ መሠረት

ድርጊቱ ያልተፈጸመ መሆኑን፤ በቀን 4/5/10 ዓ.ም ፖሊስ ተበዳዮችን በ2ኛ ተከሳሽ ቤት ሄዶ ሲቆጣጠር 1ኛ ተከሳሽ በ2ኛ ተከሳሽ ቤት የሚቀመጥ ልጅ ስላለው ወደ 2ኛ ተከሳሽ ቤት ሄዶ በር ሲያንኳኳ ወደ ራሱ ቤት ያስገባቸው ቀድሞውኑ 1ኛ ተከሳሽን ስለሚያውቅ እንጂ ስለተበዳዮቹ የሚያውቀው ነገር የሌለ መሆኑ እና 1ኛ ተከሳሽም ማዘዋወሩን የሚያውቀው ነገር የሌለ መሆኑን፤ ከ1ኛ ተከሳሽ ጋር የተባለውን ወንጀል ያልፈጸመ መሆኑን፤ በአመልካች ቤት ቆይተው የሄዱት አንድ ሰዓት ለማይበልጥ ጊዜ መሆኑን በመግለጽ የእምነት ክሕደት ቃሉን የሰጠ በመሆኑ ፍ/ቤቱ የዓቃቤሕግን ማስረጃዎች ሰምቷል፡፡

ፍ/ቤቱ የዓቃቤ ሕግን ማስረጃ ከሰማ በኋላ ዓቃቤሕግ ባቀረበው ማስረጃ 1ኛ ተከሳሾች ተበዳዮችን ጥሩ ገንዘብ ታገኛላችሁ በማለት ተስፋ ስጥቶአቸው መልምሎ በማጓጓዝ ወደ ግምቢ ከተማ ማምጣቱን፤ 2ኛ ተከሳሽ ደግሞ ከሰዎች ጋር በስልክ መነጋገሩን እና ተበዳዮችን ከ1ኛ ተከሳሽ ተቀብሎ በድርጊቱ መሳተፉን ስላስረዳ ተከሳሾች የቀረበባቸውን ክስ እንዲከላከሉ በማለት ብይን ሰጥቷል፡፡ በዚሁ መሠረት የስር 1ኛ ተከሳሽ መከላከያ ማስረጃ የለኝም በማለት ያስመዘገበ መሆኑን  እና አመልካች ደግሞ ሁለት መከላከያ ምስክሮችን አቅርቦ ያሰማ መሆኑን መዝገቡ ያመለክታል፡፡

ፍ/ቤቱም በመቀጠል የግራቀኙን ማስረጃ ከመረመረ በኋላ የዓቃቤሕግ ምስክሮች ከጥርጣሬ በላይ በሆነ መልኩ ተከሳሾች የተከሰሱበትን ወንጀል መፈጸማቸውን አስረድተዋል፤ የአመልካች መከላከያ ምስክሮች የሰጡት የምስክርነት ቃል አጠራጣሪ ነው፤ አመልካች ተመልምለው የተስፋ ቃል ተሰጥቶአቸው ተጭነው ወደ ቤቱ የመጡትን ተበዳዮችን ከ1ኛ ተከሳሽ ተቀብሎ በር ከፍቶ መቀበሉ ዋሳችሁ እኔ ነኝ የምትቸገሩት ነገር የለም ከ2-3 ዓመት ከሰራችሁ ወደ ውጪ ሐገር እልካችኋለሁ በማለት የተስፋ ቃል መስጠቱ የተረጋገጠ በመሆኑ አዋጅ ቁጥር 909/2007 አንቀጽ 3/2/ሀ መሠረት በስድስቱም ክሶች ጥፋተኞች ናቸው በማለት የጥፋተኝነት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ ቅጣቱንም በቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 02/2006 መሠረት በማስላት በ 25 ዓመት ጽኑ እስራት እና ብር 10000 መቀጮ እንዲቀጣ ሲል ወስኗል፡፡  አመልካች ይህን ውሳኔ በመቃወም ለክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የይግባኝ አቤቱታ ያቀረበ ቢሆንም አቤቱታው ተቀባይነት አላገኘም፡፡ አመልካች በመቀጠል ለክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት አቤቱታ አቅርቧል፡፡ የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ግራቀኙን ካከራከረ በኋላ የስር ፍ/ቤቶች የሰጡት ውሳኔ ተገቢ ነው ሲል አጽንቷል፡፡

የሰበር አቤቱታው የቀረበው ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም መሠረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሞበታል በሚል ሲሆን ይዘቱም፡- በተጠሪ ምስክሮች እንደተገለጸው የግል ተበዳይ ናቸው የተባሉት ወጣት ሴት ሰራተኞች ወደ ጊምቢ ከተማ የመጡት በቤት ሰራተኝነት አገልገልው የሚገባቸውን ተመጣጣኝ ደመወዝ ለማግኘት ከመሆኑ በቀር ለብዝበዛ ዓላማ አይደለም፤ ደመወዛችን ተመጣጣኝ አይደለም ባሉም ጊዜ ሥራውን አቋርጠው የመሄድ ሙሉ መብት አላቸው፤ ይህም በማናቸውም የቤት ሰራተኛ የቅጥር ግንኙነት የተለመደ ተግባር ነው፤ በመሆኑም የወንጀሉ ማቋቋሚያ ግዙፋዊ ፍሬነገር ባልተሟላበት

ሁኔታ የጥፋተኝነት ውሳኔ መሠጠቱ አግባብ አይደለም፤ አመልካች የግል ተበዳዮችን ያየሁት ከስር 1ኛ ተከሳሽ ጋር ሆነው ወደ ቤቴ በመጡ ጊዜ ነው፤ የሰር 1ኛ ተከሳሽ ልጅ በእኔ ቤት ተቀጥራ ትሰራ የነበረ በመሆኑ ልጁን ለመጠየቅ ነው የሚል ግንዛቤ ነበረኝ፤ የልጁ ቀጣሪ ከመሆኔ ውጪ ከስር 1ኛ ተከሳሽ ጋር ሌላ ምንም ዓይነት ግንኙነት የለኝም፤ አመልካች በቤቴ እንዳለሁ በቁጥጥር ስር በዋልኩበት ጊዜ የሞባይል ስልኬ ወዲያው የተያዘ በመሆኑ ከ1ኛ ተከሳሽ ጋር አስቀድሞ የነበረ ግንኙነት ቢኖረኝ ኖሮ ተጠሪ በቴሌኮም ማስረጃ ከማስረዳት የሚያግደው ነገር አልነበረም፤ ፎቶ አንስተሀል የሚለው እውነት ቢሆን ኖሮ ተጠሪውም የፎቶግራፍ ማስረጃውን እንደማስረጃ ያቀርበው ነበር፤ ፎቶግራፍ ማንሳቴ ተረጋግጦ ቢሆን ኖሮ እንኳን ይህን ማድረጌ ብቻ በሕገወጥ የሰዎች ዝውውር የእድሜየን ግማሽ ማረሚያ ቤት እንዳሳልፍ የሚያደርገኝ አይደለም፤ አመልካች ስለግለሰቦቹ ከተማ መምጣት ምንም እውቀት ያልነበረኝ በመሆኑ ወደ ውጪ አገር ትሄዳለችሁ ልል የምችልበት መነሻ ሁኔታ ስለሌለ የስር ፍ/ቤቶች የሰጡት የጥፋተኝነት እና የቅጣት ውሳኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል የሚል ነው፡፡

የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ አመልካች ሕገወጥ የሰዎች ዝውውር ለመፈጸም ሀሳብ የነበረው ለመሆኑ እና በድርጊቱም ስለመሳተፉ ባልተረጋገጠበት ሁኔታ በአዋጅ ቁጥር 909/07 አንቀጽ 3/2/ሀ መሠረት በቀረቡበት ስድስት ክሶች ጥፋተኛ የመባሉን አግባብነት ከወንጀል ሕግ አንቀጽ 23/2 ጋር በማገናዘብ ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ በዚህ ችሎት እንዲታይ ተደርጓል፡፡ ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎም ግራቀኙ በጽሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

የተጠሪ መልስ ይዘት በአጭሩ፡- አመልካች ከስር 1ኛ ተከሳሽ፤ ለጊዜው ካልተያዘች ባለቤቱ እና ማንነቱ ካልታወቀ ግለሰብ ጋር በመሆን ስራ ሰርታችሁ ትለወጣላችሁ በማለት ስድስት ሴት ልጆችን መልምሎ በመኪና ወደ ነቀምት ከተማ ወስዷቸው ካሳደሯቸው በኋላ በማግስቱ ወደ ጊምቢ ከተማ አስገብቶ በማቆየት ለልጆቹ ምግብ ከሰጡ በኋላ ሥራ ሰርታችሁ ትለወጣላችሁ፤ ከ 2 ወይም 3 ዓመት በኋላ ወደ ውጪ አገር ትሄዳላችሁ በማለት ለማስታወሻ የሚሆን ፎቶ አንስቶአቸው እንደነበር እና ከብር 1000 እስከ 1500 ብር ይዛችሁ ትመጣላችሁ በማለት ስልክ ከሌላ ሰው ጋር እየተደዋወለ ሳለ ድንገት ፖሊስ ደርሶባቸው እጅ ከፍንጅ እንደተያዙ ያስረዳን በመሆኑ ለብዝበዛ ዓላማ ሊያውል እንደነበር አመላካች ነው፤ አመልካች በዓቃቤሕግ ማስረጃ የተረጋገጠበትን ፍሬነገር ባቀረበው ማስረጃ ያላስተባበለ በመሆኑ የስር ፍ/ቤቶቸ አመልካችን ጥፋተኛ በማለት የሰጡት ውሳኔ ውሳኔ ሊጸና ይገባል የሚል ነው፡፡ አመልካችም የሰበር አቤቱታውን በማጠናከር የመልስ መልስ ሰጥቷል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ በአጭሩ ከላይ የተገለጸው ነው፡፡ ይህ ችሎትም በሰበር አጣሪው ችሎት ሊጣራ ይገባል ተብሎ የተያዘውን ነጥብ ከግራቀኙ ክርክር፤ ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸው ሕጎች ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው መርምሮታል፡፡

በሰበር አጣሪው ችሎት ሊጣራ ይገባል በማለት የተያዘው ነጥብ አመልካች ሕገወጥ የሰዎች ዝውውር ለመፈጸም ሀሳብ የነበረው ለመሆኑ እና በድርጊቱም ስለመሳተፉ ባልተረጋገጠበት ሁኔታ በአዋጅ ቁጥር 909/07 አንቀጽ 3/2/ሀ መሠረት በቀረቡበት ስድስት ክሶች ጥፋተኛ የመባሉን አግባብነት ከወንጀል ሕግ አንቀጽ 23/2 ጋር በማገናዘብ ለመመርመር በሚል በመሆኑ የዐቃቤሕግ ምስክሮች አመልካችን በሚመለከት በስር ፍ/ቤት የሰጡትን የምስክርነት ቃል ይዘት መመልከት አስፈላጊ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ የተጠሪ ምስክሮች ለስር ፍ/ቤት የሰጡት የምስክርነት ቃል ይዘት ጠቅለል ብሎ ሲታይ ማንነቱን የማያውቁት ሰው ትሄዳላችሁ ብሎ ያባበላቸው መሆኑን እና ወደ ሌላ ከተማ ጉዞ ሲያደርጉ የጉዞ ወጪ ሲሸፍን የነበረው 1ኛ ተከሰሳሽ መሆኑን፤ ካሉበት ከተማ ወደ ጊንቢ ከተማ የአመልካች ባለቤት ወደ ሆነችው አለውያ ቤት የገቡ መሆኑን እና ስትጠፉ ትፈለጉበታላችሁ ተስተካከሉ ብለው ፎቶ ያነሳቸው መሆኑን፤ሐገሪቱ ጥሩ ናት ሰርታችሁ ትለወጣላችሁ ከ2 እስከ 3 ዓመት ስትሰሩ ደግሞ ወደ ውጪ አገር ትሄዳላችሁ ያላቸው መሆኑን፤ 1ኛ ተከሳሽ ስልክ ሲደወልለት አንተ የምትለውን ልጆች አምጥቼልሀለሁ ያላቸው መሆኑን፤ የአመልካች ባለቤት አሲያ እና ሳቢቃ አስቀራቸዋለሁ ሌሎቹን እንደፈለግክ አድርግ ያለች መሆኑን፤ ስልክ ደውላም ገንዘብ ይዘሽ ነይ ያለች መሆኑን እና አሲያን እና ሳቢቃን አስቀርተው ከቤት እየወጡ ሳሉ ፖሊሰ የመጣባቸው መሆኑን በመግለጽ የምስክርነት ቃላቸውን የሰጡ ሲሆን 6ኛ ምስክር ደግሞ በጊምቢ ከተማ የአመልካች ባለቤት ቤት ሲባል መረጃ ሰምተው ሄደው በቤት ውስጥ ያሉ ልጆች አምጧቸው ሲባል ሰዎቹን ያመጧቸው መሆኑን፤ 1ኛ ተከሳሽን ሲያናግሩ ከጅማ ዞን የአመልካችን ባለቤት ላነጋግራት መጥቻለሁ ያላቸው መሆኑን፤ ፖሊስ ጽ/ቤት ልጆቹን የወሰዷቸው መሆኑን እና ፖሊስ ሲመረምራቸው 1ኛ ተከሳሽ በፈለጋችሁበት ቦታ ገንዘብ ታገኛላችሁ ብሎ አባብሎ አምጥቶናል በማለት ገልጸዋል በማለት የመሰከረ መሆኑን የሚያሳይ ነው፡፡

በመሠረቱ አንድ ሰው ወንጀል አደረገ የሚባለው ሕገወጥነቱና አስቀጪነቱ በሕግ የተደነገገን ድርጊት ፈጽሞ በተገኘ ጊዜ መሆኑ እና አንድ ወንጀል ተደረገ የሚባለውም ወንጀሉን የሚቋቋሙት ሕጋዊ፤ ግዙፋዊ እና ሞራላዊ ፍሬ ነገሮች በአንድነት ተሟልተው ሲገኙ ብቻ መሆኑ በወንጀል ሕግ አንቀጽ 23 (1) እና (2) ስር ተደንግጎ የሚገኝ ሲሆን በወንጀል ጉዳይ የሚቀርብ የክስ ማመልከቻ ደግሞ ተከሳሹ የተከሰሰበትን ወንጀል እንዲሁም የወንጀሉ መሰረታዊ ነገርና ሁኔታዎች የተገለጹበት ሊሆን እንደሚገባ እና ስለ ወንጀሉና ስለሁኔታው የሚሰጠው ዝርዝር መግለጫ ተከሳሹ ፈጸመ የተባለውን ተግባር ወንጀል ከሚያደርገው ሕግ አነጋገር ጋር በጣም የተቀራረበ መሆን እንደሚገባው በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 111 እና 112 ድንጋጌዎች ላይ የተደነገገውም ከሳሹን ወገን በወ/ሕ/አንቀጽ 23(2) ስር የተመለከቱት የወንጀል መማቋቋሚያ ፍሬ ነገሮች ተሟልተው መገኘታቸውን ለማስረዳት እንዲያስችለው መሆኑን ከድንጋጌዎቹ ይዘት መገንዘብ ይቻላል፡፡ ይህም ከሳሽ ወገን በክሱ መሰረት የማስረዳት ግዴታ ተወጥቶአል ሊባል የሚችለው ቀደም ሲል በተጠቀሱት የወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 111 እና 112 ድንጋጌዎች መሰረት አዘጋጅቶ ባቀረበው የክስ ማመልከቻ መሠረት ተከሳሹ ወንጀል

መፈጸሙን ማስረዳት በቻለ ጊዜ ነው፡፡ ክሱ የቀረበለት ፍ/ቤትም ተከሳሹ መከላከያ ማስረጃ አቅርቦ ክሱን እንዲከላከል በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ.142 መሠረት ትዕዛዝ ሊሰጥ የሚችለው ከሳሽ ወገን ያቀረበው ማስረጃ ተከሳሹን ጥፋተኛ የሚያደርገው መሆኑን ሲያረጋግጥ ስለመሆኑ በወ/መ/ሕ/ስ/ስ/ቁ. 141 ስር በግልጽ ተደንግጎ ይገኛል፡፡

አመልካች የተከሰሰበት ሕገወጥ የሰዎች ዝውውርን እና ስደተኞችን በሕገወጥ መንገድ ድንበር ማሻገር ወንጀልን ለመከላከል እና ለመቆጣጠር የወጣው አዋጅ ቁጥር 909/2007 አንቀጽ 3/2/ሀ ማንኛውም ሰው በኢትዮጲያ የግዛት ክልል ውስጥም ሆነ ከኢትዮጲያ የግዛት ክልል ውጪ ለብዝበዛ ዓላማ ሲባል በአገር ውስጥ ስራ እና ሰራተኛን ለማገናኘት ወይም ለስራ ወይም ለስራ ልምምድ ወደ ውጪ አገር ለስራ መላክ በሚል ሽፋን ዛቻን ሀይልን ወይም ሌላ ማናቸውም ዘዴ በመጠቀም፤ በማገት፤ በመጥለፍ ወይም በተንኮል በማለታለል ወይም የተስፋ ቃል በመስጠት ሰዎችን የመለመለ ያጓጓዘ፤ ያዘዋወረ፤ ያስጠለለ፤ ወይም የተቀበለ እንደሆነ እና ይህም ድርጊት በሕጻናት በሴቶች ወይም በአእምሮ ወይም በአካል ጉዳተኞች ላይ የተፈጸመ እንደሆነ ከ 25 ዓመት በማያንስ ጽኑ እሥራት ወይም እድሜልክ ጽኑ እስራት እና ከብር 200000-500000 በሚደርስ መቀጮ ይቀጣል በማለት ይደነግጋል፡፡ በዚህ ድንጋጌ መሠረት የተከሰሰን ሰው ጥፋተኛ ለማለት ተከሳሹ በድንጋጌው በተገለጸው አግባብ ድርጊቱን የፈጸመ ስለመሆኑ በቅድሚያ ሊረጋገጥበት ይገባል፡፡

የብዝበዛ ዓላማ ማለት ደግሞ በሌሎች ሰዎች ዝሙት አዳሪነት መጠቀም ወይም ማናቸውም ዓይነት ወሲባዊ ብዝበዛን፤ የጉልበት ብዝበዛን የግዳጅ ስራን ወይም አገልጋይነት፤ ባርነት ወይም ባርነት መሰል ተግባር፤ የወሲብ አገልጋይነትን ጨምሮ ሰውን የማይገባ አገልጋይ ማድረግ፤ በመያዣነት መያዝ ወይም አሳልፎ ለሌላ መስጠት፤ የሰው ልጅን አካል ማውጣት ወይም መወሰድ፤ አስገድዶ በልመና ተግባር ማሰማራት ወይም ሕጻናትን ለወታደራዊ አገልግሎት ማሰማራት እንደሆነ በአዋጁ አንቀጽ 2/4 ላይ ከተሰጠው ትርጉም መገንዘብ ይቻላል፡፡

በያዝነው ጉዳይ ክሱን ለማስረዳት የቀረቡት የዓቃቤሕግ ምስክሮች ካሉበት ከተማ ወደ ጊንቢ ከተማ የአመልካች ባለቤት ወደ ሆነችው አለውያ ቤት የገቡ መሆኑን እና ስትጠፉ ትፈለጉበታላችሁ ተስተካከሉ ብለው ፎቶ ያነሳቸው መሆኑን፤ ሐገሪቱ ጥሩ ናት ሰርታችሁ ትለወጣላችሁ ከ2 እስከ 3 ዓመት ስትሰሩ ደግሞ ወደ ውጪ አገር ትሄዳላችሁ ያላቸው መሆኑን በመግለጽ ከመመስከራቸው በቀር አመልካች በተከሰሰበት የአዋጅ ቁጥር 909/2007 አንቀጽ 3/2/ሀ ድንጋጌ አግባብ አመልካች ለብዝበዛ ዓላማ ሲል ዛቻን ሀይልን ወይም ሌላ ማናቸውም ዘዴ በመጠቀም፤ በማገት፤ በመጥለፍ ወይም በተንኮል በማታለል ወይም የተስፋ ቃል በመስጠት በሕገወጥ መንገድ ያዘዋወራቸው መሆኑን በመግለጽ የሰጡት የምስክርነት ቃል የለም፡፡ አመልካች በሕጉ በተገለጸው አግባብ የግል ተበዳዮችን በሕገወጥ መንገድ

ስለማዘዋወሩ እስካልተረጋገጠ ድረስ የተከሰሰበትን የሕግ ድንጋጌ ጥሷል በማለት ጥፋተኛ ሊባል የሚችልበት ሕጋዊ ምክንያት ስለሌለ አመልካች ከቀረበበት ክስ በነጻ ሊሰናበት ይገባል፡፡

በአጠቃላይ የስር ፍ/ቤቶች አመልካች በሕጉ አግባብ ድርጊቱን ስለመፈጸሙ ባልተረጋገጠበት ሁኔታ በአመልካች ላይ ያስተላለፉት የጥፋተኝነትም ሆነ የቅጣት ውሳኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ ስለሆነም ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

## <u>ውሳኔ</u>

1. በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የምዕራብ ወለጋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ 35700 መጋቢት 18 ቀን 2010 ዓ.ም አመልካችን በሚመለከት የሰጠው የጥፋተኝነት ውሳኔ እና የቅጣት ውሳኔ፣ ይህን ውሳኔ በማጽናት የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 214895 በቀን 11/08/2010 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ እና የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 284629 ጥቅምት 12 ቀን 2011 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ በወ/መ/ስ/ስ/ሕ/ቁ 195/2/ለ/2 መሠረት ተሽሯል፡፡
2. ከላይ በፍርድ ሐተታው ላይ በተገለጸው ምክንያት አመልካች ከተከሰሰበት ክስ በነጻ እንዲሰናበት ወስነናል፡፡

## <u>ትዕዛዝ</u>

የሚመለከተው ማረሚያ ቤት በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የምዕራብ ወለጋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ 35700 መጋቢት 18 ቀን 2010 ዓ.ም አመልካችን በሚመለከት የሰጠው የጥፋተኝነት ውሳኔ እና የቅጣት ውሳኔ፣ ይህን ውሳኔ በማጽናት የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 214895 በቀን 11/08/2010 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ እና የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 284629 ጥቅምት 12 ቀን 2011 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ ተሽሮ አመልካች በነጻ እንዲሰናበት የተወሰነ መሆኑን አውቆ አመልካችን ከእስር እንዲለቅ ታዟል፡፡ ይጻፍ

- መዝገቡ ውሳኔ ስለገኘ ተዘግቷል፡፡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት ፡፡

**ፀ/ወ**

የሰ/መ/ቁ.167805

ጥቅምት 26/2012 ዓ.ም

ዳኞች፡ እትመት አሰፋ

ኃይሉ ነጋሽ

ፀሐይ መንክር

መላኩ ካሳዬ

እስቲበል አንዱዓለም

አመልካች፡ የትግራይ ክልል ፍትህ ቢሮ - የቀረበ የለም፡፡

ተጠሪዎች፡ 1. አቶ ታደሰ ኪዳነ ማርያም

2. አቶ ዳንኤል ኃይለ

3. አቶ ኪሮስ ፀጋይ

4. አቶ ብርሃነ ፀጋይ

ቀርበዋል፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍርድ

በዚህ መዝገብ ላይ የቀረበው ጉዳይ የአራጣ ወንጀልን የሚመለከት ሲሆን የሰበር አቤቱታው የቀረበው የትግራይ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት በሰ/መ/ቁ/100969 ላይ ጥቅምት 02/2011 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠውን ውሳኔ በመቃወም ነው፡፡

ክርክሩ የተጀመረው የአሁን አመልካች በሽረ እንዳስላሴ ወረዳ ፍርድ ቤት በአሁን ተጠሪዎች ላይ የ1996 ዓ.ም የወንጀለ ህግ 712(1(ሀ)) ጠቅሶ ባቀረበው የአራጣ ወንጀል ክስ ነው፡፡ የክሱም ጭብጥ የአሁን ተጠሪዎች "ወልደ ገብርኤል አሊጋሁን እና ጓደኞቻቸው ዕጣን ለቀማ ሕብረት ሽርክና ማህበር" ለተባለው ተበዳይ በሽረ እንዳስላሴ ከተማ ውስጥ በተለያዩ ቀናት የተለያየ መጠን ያለውን ገንዘብ በአራጣ በማበደር የአራጣ ወንጀል ፈፅመዋል የሚል ነው፡፡

ጉዳዩ የቀረበለት ፍርድ ቤት ተጠሪዎች ክሱን እንዲከላከሉ አድርጎ የመከላከያ ማስረጃቸውን ከሰማ በኋላ ተጠሪዎች የተከሰሱበትን የአራጣ ወንጀል ያልፈፀሙ ለመሆኑ የዐቃቤ ህግ ማስረጃን በሚያስተባብል መልኩ አስረድተዋል በሚል ከተከሰሱበት ወንጀል በወንጀል ህግ ሥነ ሥረዓት ቁጥር 149(2) መሰረት በነፃ አሰናብቷል፡፡ በዚሁ ውሳኔ ላይ ይግባኝ የቀረበለት የሰሜን ምዕራብ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት የአመልካችን አቤቱታው በወንጀል ህግ ሥነ ሥረዓት ቁር 195(1) መሰረት ሰርዟል፡፡

ጉዳዩን በሰበር የተመለከተው የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ከላይ በተጠቀሰው የመዝገብ ቁጥር እና ቀን በዋለው ችሎት የአራጣ ወንጀል የሚፈፀመው የተበዳይን ችግር፣ የበታችነት፣ ወይም የገንዘብ ችግር፣ ወይም መንፈስ ደካማነት ወይም ልማድ ወይም ችሎታ ማጣትን መሰረት ተደርጎ መሆኑን፤ እነዚህ ተግባራት ሊኖሩ የሚችሉት በተፈጥሮ ሰው ላይ መሆኑን፤ በቀረበለት ጉዳይ ላይ የአራጣ ወንጀል ተፈጽሟል የተባለው በህግ የሰውነት መብት በተሰጠው ማህበር ላይ በመሆኑ በወንጀል ህጉ ስለ አራጣ ወንጀል ከአንቀፅ 712-715 ድረስ የተደነገጉት ለተፈጥሮ ሰው እንጂ በህግ የሰውነት መብት ለተሰጠው አካል ተፈፃሚነት የለውም፤ በፍሬ ነገር ደረጃም በግራ ቀኙ መካከል የአራጣ ብድር ግኑኝነት ያልነበረ ለመሆኑ በመከላከያ ማስረጃ በመረጋገጡ ተጠሪዎች ከክሱ በነፃ መሰናበታቸው ተገቢ ነው በማለት በውጤት ደረጃ የስር ፍርድ ቤት ውሳኔን በአብላጫ ድምፅ አፅንቷል፡፡

የአሁን የሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚሁ ውሳኔ ላይ ነው፡፡ አመልካች ታህሳስ 15/2011 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ በክልሉ ሰበር ችሎት ትርጉም ላይ ያለውን ቅሬታ በመጥቀስ በዚህ ችሎት እንዲታረምለት ጠይቋል፡፡ ፍሬ ቃሉም በወንጀል ህግ አንቀፅ 712(1(ሀ)) ስር "ማንኛውም ሰው" ተብሎ የተጠቀሰው የተፈጥሮም ሆነ በህግ የሰውነት መብት የተሰጠውን አካል የሚያጠቃልል ሆኖ እያለ የክልሉ ሰበር ችሎት የድንጋጌው ተፈፃሚነት ለተፈጥሮ ሰው ብቻ ነው ብሎ መተርጎሙ አግባብ ባለመሆኑ በህግ የሰውነት መብት ለተሰጣቸው ድርጅቶችም ተፈፃሚነት አለው በሚል ተተርጉሞ ተጠሪዎች በተከሰሱበት ወንጀል ጥፋተኛ ተብለው ሊቀጡ ይገባል የሚል ነው፡፡

የክልሉ ሰበር ችሎት ውሳኔ ከወንጀል ህግ አንቀፅ 23(2) እና 712(1(ሀ)) ጋር ተገናዝቦ ተመርምሮ በዚህ ችሎት ትርጉም እንዲሰጥበት በዚህ ፍርድ ቤት ሰበር አጣሪ ችሎት በመታዘዙ ተጠሪዎች መልስ እንዲሰጡበት ተደርጎ 1ኛ ተጠሪ ለብቻው፤ ከ2ኛ እስከ 4ኛ ያሉት ተጠሪዎች ደግሞ በጋራ ሰኔ 03/2011 ዓ.ም የተፃፈ መልስ አቅርበዋል፡፡

ተጠሪዎች ያቀረቡት መልስ ዘርዘር ያለ ሲሆን አጠቃላይ ጭብጥ በሁለት ነጥብ ላይ ያተኮረ ነው፡፡ የመጀመሪያው የአራጣ ወንጀልን የሚያቋቁሙት ድንጋጌዎች ስር የተቀመጡት መመዘኛዎች የተፈጥሮ ሰውን ብቻ የሚመለከቱ በመሆናቸው እና የአራጣ ብድር ተሰጥቷል የተባለው ለማህበር በመሆኑ የክልሉ ሰበር ችሎት በአተረጓጎም ረገድ የፈፀመው ስህተት የለም የሚል ነው፡፡ ሁለተኛው በስር ፍርድ ቤቶች በነፃ የተለቀቁት ከተበዳይ ጋር ተራ የብድር ውል ግኑኝነት እንጂ የአራጣ ብድር ያልነበረ ለመሆኑ በሰው እና በሰነድ ማስረጃ ተረጋግጦ በመሆኑ ውሳኔው የሚነቀፍ አይደለም የሚል ነው፡፡

አመልካች ሰኔ 14/2011 ዓ.ም በሰጠው የመልስ መልስ ቀደም ሲል ያቀረበውን የቅሬታ ነጥብ የሚያጠናክርበትን ምክንያት በማከል በቀረበው ቅሬታ መሰረት እንዲወሰንለት ጠይቋል፡፡

በግራ ቀኙ የቀረበው ክርክር አጠር ባለ መልኩ ከላይ የተመለከተውን ሲመስል ችሎቱም ጉዳዩ አግባብነት ካለው ህግ ጋር በማገናዘብ መርምሯል፡፡

በመሰረቱ ተጠሪዎች በተከሰሱበት የወንጀል ህጉ አንቀፅ 712 ስር "ማንም ሰው" ተብሎ የተጠቀሰው የወንጀል ፈፃሚውን ማንነት የሚመለከት እንጂ የተባዳዩን ማንነት የሚገልፅ አይደለም፡፡ ሆኖም ይህ ድንጋጌ ያለበት የወንጀል ህጉ ስድስተኛ መፀሃፍ፣ ምዕራፍ ሶስት፣ ክፍል ሶስት "የኀሊናን ወይም የሰውን ችግር መሰረት በማድረግ የሚፈፀሙ ወንጀሎች" በሚል አርዕስት ስር በመሆኑ ዞሮ ዞሮ የአራጣ ወንጀል የሚፈፀምበት ተበዳይ ሰው መሆኑን መገንዘብ ይቻላል፡፡

በህግ አስተምህሮ ሰው ማለት የተፈጥሮ ሰው እና በህግ የሰውነት መብት የተሰጠው የንግድ ማህበር/ድርጅት/ ስለመሆኑ በችሎቱ ግንዛቤ የሚወሰድበት ነው፡፡ በህግ የሰውነት መብት የተሰጠው ድርጅት በልዩ ዓላማ የመብት እና ግዴታ ባለቤት እንዲሆን የተደረገ ቢሆንም የሚንቀሳቀሰውም ሆነ ስራውን የሚከውነው በተፈጥሮ ሰው አማካኝነት ነው፡፡ ድርጅቱን ለማንቀሳቀስ በህግም ይሁን በውል ስልጣን የተሰጠው የተፈጥሮ ሰው በተሰጠው የስልጣን ክልል ውስጥ ለድርጅቱ ጥቅም እና መብት እስከሰራ ድረስ በተሰራው ስራ ተጠቃሚውም ሆነ ተጎጂው ድርጅቱ ይሆናል፡፡

ይህ በመሆኑም ነው ከድርጅቱ ኃላፊዎች ወይም ሰራተኞች አንዱ ከድርጅቱ ስራ ጋር በተያዘ ሁኔታ የድርጅቱን ጥቅም በህገወጥ መንገድ ለማራመድ በማሰብ ወይም የድርጅቱን ህጋዊ ግዴታ በመጣስ ወይም ድርጅቱን በመሳሪያነት ያለአግባብ በመጠቀም በተለያየ የወንጀል ተሳትፎ ደረጃ ወንጀል አድርገው በተገኙ ጊዜ በእንደራሴዎቹ የተሳትፎ ደረጃ ልክ ድርጅቱ እራሱ ወንጀል እንዳደረገ ተቆጥሮ በወንጀል ጥፋተኛ ተብሎ የሚቀጣ ስለመሆኑ በወንጀል ህግ አንቀፅ 23(3) እና 34 ስር የተደነገገው፡፡ እናም በህግ የሰውነት መብት የተሰጠው ድርጅት የመብት እና ግዴታ ባለቤት በመሆኑ በህግ በግልፅ በተደነገገ ጊዜ በወንጀል ተከስሶ ሊቀጣ እንዲሁም እንደማንኛውም የተፈጥሮ ሰው የወንጀል ድርጊት ተጎጂ ሊሆን ይችላል ማለት ነው፡፡

አሁን በቀረበው ጉዳይ በትግራይ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት የተሰጠው ትርጉም የአራጣ ወንጀልን የሚያቋቁሙት ፍሬ ነገሮች በባህሪያቸው የተፈጥሮ ሰውን ብቻ የሚመለከቱ በመሆኑ ድንጋጌው በህግ የሰውነት መብት ለተሰጠው ድርጅት ተፈፃሚነት የለውም የሚል ነው፡፡ በእርግጥ የአራጣ ወንጀል የሚፈፀመው የተበዳዩን ችግርተኝነት፣ የበታችነት፣ ወይም የገንዘብ ችግሩን ወይም መንፈሰ ደካማነቱን ወይም ልምድ ወይም ችሎታ የሌለው መሆኑን መሰረት በማድረግ ስለመሆኑ የወንጀል ህግ አንቀፅ 712(1(ሀ)) ድንጋጌ ያስገነዝባል፡፡ በዚህ አንቀፅ ስር የወንጀሉ ማቋቋሚያ ፍሬ ነገሮች ተብለው የተጠቀሱት በአማራጭ መስፈርትነት የተቀመጡ ሲሆን አንዳንዶቹ በትክክልም የተፈጥሮ ሰውን ብቻ የሚመለከቱ ሲሆን ሌሎቹ ደግሞ እንደ አግባብነታቸው በህግ የሰውነት መብት ለተሰጠው አካልም የሚሰሩ ናቸው፡፡ ለአብነት ያክል

“መንፈሰ ደካማነት” እና “የበታችነት” የሚለው የተፈጥሮ ሰውን ብቻ የሚመለከት ሲሆን “ችግርተኝነት ወይም የገንዘብ ችግር” የተባለው ደግሞ ለተፈጥሮም ሆነ በህግ የሰውነት መብት ለተሰጠው አካል ሊፈፀም የሚችል ነው፡፡

እናም የወንጀል ማቋቋሚያ ፍሬ ነገሮቹ በአማራጭነት የተቀመጡ በመሆናቸው እንደ ነገሩ ሁኔታ እና አግባብነት መመዘኛው ለተፈጥሮም ሆነ በህግ የሰውነት መብት ለተሰጠው ድርጅት/ማህበር/ ተግባራዊ ከሚደረግ በቀር ድንጋጌው ተፈፃሚነቱ ለተፈጥሮ ሰው ብቻ ነው የሚባል አይደለም፡፡

በተያዘው ጉዳይ በተጠሪዎች ላይ የቀረበው የወንጀል ክስ በቀረበበት አግባብ ተረጋግጧል አልተረጋገጠም የሚለው ቀጥሎ የሚታይ ሆኖ በድርጊቱ ተበዳይ ተብሎ የተጠቀሰው የንግድ ማህበር እንደራሴዎች በክሱ ውስጥ የተጠቀሰውን ገንዘብ ከተጠሪዎች ሲበደሩ የነበረው ድርጅቱ አጋጥሞት በነበረው ከፍተኛ የገንዘብ ችግር ምክንያት መሆኑን ከክርክሩ አጠቃላይ አመጣጥ መገንዘብ ተችሏል፡፡ የአንድ ድርጅት እንደራሴዎች ድርጅቱ ባጋጠመው የገንዘብ ችግር ምክንያት በአራጣ ገንዘብ ከተበደሩ እና ይህ ለመሆኑ በፍሬ ነገር ደረጃ ማረጋገጥ ከተቻለ የንግድ ድርጅቱ በአራጣ ወንጀል ድርጊት ተበዳይነት የማይጠቀስበት ምክንያት የለም፡፡

በመሆኑም የትግራይ ሰበር ችሎት የወንጀል ህጉን አንቀፅ 712 የተረጎመበት መንገድ የድንጋጌውን አጠቃላይ ይዘት እና መንፈስ ያላገናዘበ መሰረታዊ የህግ አተረጓጎም ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡

በሌላ በኩል የወንጀሉን ድርጊት በተመለከተ ማስረጃና ፍሬ ነገርን የመመርመር እና የመመዘን ስልጣን ያላቸው በየደረጃው ያሉ ፍርድ ቤቶች የቀረበላቸውን ማስረጃዎች መርምረውና መዝነው በተጠሪዎች እና በተበዳይ ድርጅት መካከል የነበረው ግንኙነት የተራ ብድር እንጂ የአራጣ ብድር አለመሆኑን ያረጋገጡ ለመሆኑ ከቀረበው የመዝገብ ግልባጭ ለመገንዘብ ተችሏል፡፡ አመልካች ተጠሪዎች በተከሰሱበት ወንጀል ጥፋተኛ ሊባሉ ይገባል ከማለት ባለፈ የስር ፍርድ ቤቶች የአራጣ ወንጀል አልተፈፀመም ለማለት በተጓዙበት መንገድ እና በደረሱበት ድምዳሜ ውስጥ የፈፀሙት መሰረታዊ የህግ ስህተት ምን እንደሆነ ለይቶ ያላመለከተ በመሆኑ ተጠሪዎችን ነፃ በመልቀቅ በተሰጠው ውሳኔ ላይ መሰረታዊ የህግ ስህተት ተፈፅሟል ለማለት አልተቻለም፡፡

ሲጠቃለል ይህንን ጉዳይ በተመለከተ ተከታዩ ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

## <u>ውሳኔ</u>

1. የትግራይ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት በሰ/መ/ቁ/100969 ላይ ጥቅምት 02/2011 ዓ.ም በዋለው ችሎት በወንጀል ህግ አንቀፅ 712(1(ሀ)) ስር

የተመለከተው የአራጣ ወንጀል ተፈፃሚነት የተፈጥሮ ሰው በሆነ ተበዳይ ላይ ብቻ ነው በማለት የሰጠው የውሳኔ ክፍል ብቻ ተሽሮ የተቀረው በወንጀል ህግ ሥነ ሥረዓት ቁጥር 195(2) መሰረት ፀንቷል፡፡

2. በወንጀል ህግ አንቀፅ 712 ስር የተመለከተው የአራጣ ወንጀል በህግ የሰውነት መብት በተሰጠው ድርጅት/ማህበር/ ላይ ሊፈፀም ይችላል፡፡

## ትዕዛዝ

1. ውሳኔው መሻሻሉን እንዲያውቅ የዚህ ፍርድ ትክክለኛ ግልባጭ ለስር ፍርድ ቤት ይተላለፍ፡፡
2. መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ዮ/መ

የሰ/መ/ቁጥር---161791

ቀን- የካቲት 25 ቀን 2011 ዓ.ም

ዳኞች፡- ብርሃኑ አመነዉ

በዕዉቀት በላይ

እንዳሻዉ አዳነ

ኃይሉ ነጋሽ

እትመት አሰፋ

**አመልካች:-** ታምሬ አበራ ረጋሳ

**ተጠሪ፡-** የፌዴራል ጠቅላይ ዐ/ሕግ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለዉ ፍርድ ተሰጥቷል።

**ፍርድ**

ለዚህ ሰበር ክርክር መነሻ የሆነው የወንጀል ጉዳይ ሲሆን የተጀመረው በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ተጠሪ አመልካችን ጨምሮ በ10 ተከሳሾች ላይ በመሠረተዉ ክስ መነሻነት ነው። በስር ፍ/ቤት አመልካች 8ኛ ተከሳሽ የነበረ ሲሆን አመልካችን የሚመለከተዉ 3ኛ ክስ ሆኖ ይዘቱ፡- የስር 1ኛ፣ 4ኛ፣ 7ኛ፣ 8ኛ(ተጠሪ)፣ 9ኛ እና 10ኛ ተከሳሾች የወ/ሕ/አንቀጽ 32(1/ሀ) እና 669(3/ለ) የተመለከተዉን በመተላለፍ በዋና ወንጀል አድራጊነት ተካፋይ በመሆን ሐምሌ 17 ቀን 2006 ዓ.ም ለሐምሌ 18 ቀን 2006 ዓ.ም አጥቢያ ሌሊት ባልታወቀ ሰዓት በቦሌ ክ/ከተማ ገርጂ ተብሎ በሚጠራዉ አካባቢ ከሚገኘዉ ሙለጌ ኃ/የተ/የግል ማህበር ዉስጥ ተጠሪና 10ኛ ተከሳሽ ያላቸዉን የስራ ኃላፊነት ተጠቅመዉ 1ኛ እና 9ኛ ተከሳሾች የግል ተበዳይ በሆነዉ ድርጅት ዉስጥ ተመድበዉ የጥበቃ ሥራቸዉን እንዲሰሩ በማድረግ ሁኔታዎችን ካመቻቹ በኃላ እኚሁ ተከሳሾች አይሱዙ ይዘዉ በመምጣት ከድርጅቱ መጋዝን ዉስጥ የተለያዩ ብዛትና ዓይነት ያላቸዉ የሕጻናት ወተቶች እና የሕጻናት ንጽህና መጠበቂያ ዳይፐር አጠቃላይ ግምታቸዉ ብር 1,092,950 የሚሆን በመኪና ጭነዉ ከወሰዱ እና ጥበቃዎቹም ለትብብራቸዉ እያንዳንዳቸዉ ብር 30,000 ከተቀበሉ እንዲሁም 7ኛ እና 4ኛ ተከሳሾች የተጫነዉን ዕቃ በሌላ ሰዉ መጋዝን አራግፈዉ ከሄዱ በኃላ የተያዙ ስለሆነ በግብርአበርነት በፈጸሙት የከባድ ስርቆት ወንጀል ተከሰዋል የሚል ነዉ።

በስር ፍ/ቤት አመልካችም ሆነ የስር ተከሳሾቹ የእምነት ክህደት ቃል ሲጠየቁ ወንጀሉን አለመፈጸማቸዉን ገልጸዉ ክደዉ ተከራክረዋል። የተጠሪ ምስክሮችና ማስረጃዎች ከተሰሙ በኃላ አመልካችና የስር ተከሳሾች እንዲከላከሉ ብይን የተሰጠ ሲሆን የስር ፍ/ቤት የአመልካችንና የሌሎች ተከሳሾችን ማስረጃዎች ከሰማ በኃላ መርምሮ በተከሰሱበት አንቀጽ ስር ጥፋተኛ በማድረግ አመልካች በ11 ዓመት ጽኑ እስራት እንዲቀጣ ወስኗል። አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሠኘት ያቀረበዉን ይግባኝ የተመለከተዉ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ግራ ቀኙን ካከራከረ በኃላ መርምሮ መነሻ ቅጣቱን ከእርከን

29 ወደ እርከን 26 ዝቅ በማድረግ በአንድ የቅጣት ማክበጃ ምክንያትና አንድ የቅጣት ማቅለያ ምክንያት በመያዝ እርከን 26 ስር በ8 ዓመት ጽኑ እስራት እንዲቀጣ አሻሽሎ ወስኗል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው ይህን ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡

የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሠረታዊ ይዘት፡- በስር ፍ/ቤቶች የተሰጠዉ የጥፋተኝነት ዉሳኔ መሠረት ያደረገዉ አመልካች ታስሮ በነበረበት ወቅት በፖሊስ የሰጠዉን የተከሳሽነት ቃል ሲሆን ሕገ-መንግስቱንና ሕግን ባልተከተለ መንገድ በግዳጅ የተገኘ ማስረጃ በመሆኑ የጥፋተኝነት ዉሳኔዉ ሊሻር ይገባል፡፡ ቅጣትን በተመለከተ በአመልካች ላይ ሰዉ በመግደል ወንጀል የተጣለዉ ቅጣት የ5 ዓመት ጊዜ ያለፈዉና የቅጣት ዉሳኔዉ የተሰረዘ በመሆኑ የአመልካች የቀድሞ ሕይወቱ መልካም እንደነበረ ስለሚገመት የተፈጸመዉም የወንጀል ድርጊት በሀሳብ ደረጃ የተለያዬ ስለሆነ እንደ አንድ የቅጣት ማቅለያ ተደርጎ እንዲያዝልኝ፡፡ ለሌሎች የስር ተከሳሾች በወንጀሉ በዋና አድራጊነት ተሳታፊ የነበሩ ቢሆንም ከወንጀሉ ያገኙት ጥቅም አነስተኛ መሆንና በትምህርት ያልገፉ መሆናቸዉ ታይቶ አንድ የቅጣት ማቅለያ ምክንያት ተይዞላቸዉ ቅጣት የተቀነሰላቸዉ ስለሆነ ይኸዉ የቅጣት ማቅለያ ምክንያት ለአመልካች የማይያዝበት ምክንያት ባለመኖሩ ማቅለያ ምክንያቱ ተይዞልኝ ቅጣት ይቅለልልኝ የሚል ነዉ፡፡

የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ አመልካች ቀደም ሲል በ2001 ዓ.ም ጥፋተኛ ተብሎ የተቀጣዉ በግድያ ወንጀል ሲሆን በዚህ መዝገብ ደግሞ ከባድ ስርቆት ሆኖ ሳለ የስር ፍ/ቤት ወንጀል መፈጸም ልማድ በማድረጉ በማለት ማክበጃ የያዘበት አግባብ ከወ/ሕ/አንቀጽ 84 አንጻር እንዲሁም ቅጣቱን ጨርሶ ከተፈታ 5 ዓመት ያለፈዉ በመሆኑ ፍ/ቤቱ ተገንዝቦ እያለ ሪከርድ አለበት በማለት በወ/ሕ/አንቀጽ 82(1/ሀ) ማቅለያ ሳይዝ ያለፈበትን አግባብነት ለማጣራት ሲባል ጉዳዩ ለሰበር ያስቀርባል የተባለ ሲሆን ግራ ቀኙ መልስና የመልስ መልስ በጽሁፍ በማቅረብ ተከራክረዋል፡፡

ተጠሪ የሰጠዉ መልስ ይዘት፡- አመልካች በሰዉ መግደል ወንጀል ጥፋተኛ የተባለዉ እና የተቀጣዉ በ16/03/2001 ዓ.ም ሲሆን የተፈታበት ጊዜ በተመለከተ ሁለት ሦስተኛ ቅጣቱን ፈጽሞ በአመክሮ ተፈታ እንኳ ቢባል የሚፈታዉ በ2004 ዓ.ም በመሆኑ ከተፈታ በኃላ 5 ዓመት ስንቆጥር እስሩ የሚጠናቀቀዉ በ2008 ዓ.ም ነዉ፡፡ አመልካች የወ/ሕ/አንቀጽ 669(3/ለ) የተመለከተዉን ተላልፎ ወንጀል ፈጽሟል የተባለዉ ሀምሌ 1 ቀን 2006 ዓ.ም በአመክሮ ተፈትቶ በአንድ ዓመቱ በመሆኑ ፍርዱ ተሠርዞልኛል የሚለዉ ተገቢ አይደለም፡፡ ስለሆነም የስር ፍ/ቤት በወ/ሕ/አንቀጽ 67 መሠረት ደጋጋሚ ነዉ በሚል ቅጣቱን በመሰለዉ ማክበድ ሲችል ማለፉ አመልካችን የሚጠቅም እንጂ የሚጎዳዉ ባለመሆኑ የተፈጸመ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ባለመኖሩ ዉሳኔዉ ይጽናልን የሚል ነዉ፡፡ አመልካች በሰጠዉ የመልስ መልስ የሰበር አቤቱታቸዉን በሚያጠናክር መልኩ ተከራክሯል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥና ክርክር ከላይ የተመለከተዉን የሚመስል ሲሆን የአመልካቾችን አቤቱታ ከስር ፍ/ቤት ዉሳኔ እና አግባብነት ካላቸዉ የሕግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መርምረናል፡፡ አቤቱታዉ ለሰበር ያስቀርባል ሲባል ከተያዘዉ ጭብጥ አንጻር መርምረን እንደተረዳነዉ ይግባኝ ሰሚዉ የፌዴራል

ከፍተኛ ፍ/ቤት አመልካች ለፈጸመዉ የከባድ ስርቆት ወንጀል መነሻ ቅጣቱን በስር ፍ/ቤት ተይዞ ከነበረዉ መነሻ እርከን ከሆነዉ እርከን 28 ዝቅ በማድረግ እርከን 26 ላይ መነሻ እርከን ከያዘ በኃላ አመልካች አስቀድሞ በሰዉ ግድያ ወንጀል ጥፋተኛ ተብሎ 5 ዓመት መቀጣቱን በመጥቀስ በወ/መ/ሕ/ቁ 84(1/ሐ) መሰረት ወንጀል መፈጸምን ሙያዉ አድርጎ ይዞታል በማለት አንድ የቅጣት ማክበጃ ምክንያት የያዘበት ከመሆኑም በላይ በወ/ሕ/አንቀጽ 232 እና ተከታዮቹ ድንጋጌዎች መሰረት ስለመሰየሙ የቀረበ ማስረጃ ባለመኖሩ በወ/ሕ/አንቀጽ 82(1/ሀ) መሠረት የዘዉትር ባህሪው መልካም ነዉ ለማለት ባለመቻሉ በቅጣት ማቅለያነት ሊይዝለት አለመቻሉን በመግለጽ፤ የቤተሰብ አስተዳዳሪ መሆኑን ብቻ በወ/ሕ/አንቀጽ 86 መሰረት አንድ ልዩ የቅጣት ማቅለያ ምክንያት በመያዝ እርከን 26 ስር በ8(ስምንት) ዓመት ጽኑ እስራት እንዲቀጣ ወስኗል፡፡ አመልካች አጥብቆ የሚከራከረዉም ሆነ አቤቱታዉ ለሰበር ያስቀርባል ሲባል የተያዘዉ ጭብጥ አመልካች አስቀድሞ ጥፋተኛ የተባለበትና የተቀጣበት የግድያ ወንጀል በወ/ሕ/አንቀጽ 84(1/ሐ) መሰረት በማክበጃነት መያዙ በአግባቡ ነዉ? ወይስ አይደለም? በአግባቡ አይደለም የሚባል ቢሆን በወ/ሕ/አንቀጽ 82(1/ሀ) መሰረት ተጨማሪ አንድ የቅጣት ማቅለያ ያለመያዙ በአግባቡ ነዉ? ወይስ አይደለም? የሚሉት ናቸዉ፡፡

በመሠረቱ የወ/ሕ/አንቀጽ 84(1/ሐ) ወንጀለኛዉ በቀድሞ ጥፋተኛነቱ፣ ወንጀልን ማድረግ ሙያ ወይም ልማድ አድርጎ መያዙ፣ ወይም የወንጀሉ አፈጻጸም ዘዴ፣ ጊዜ፣ ቦታና አፈጻጸሙ አኳኋን፣ በተለይም በሌሊት ወይም በሽብር ወይም በሁከት ለአደጋ ሽፋን ወይም በጦር መሳሪያ ወይም በሌላ አደገኛ መሣሪያ ወንጀሉን በማድረግ የተለየ አደገኝነቱን አሳይቶ እንደሆነ ይላል፡፡ ከዚህ ድንጋጌ ይዘት መገንዘብ የሚቻለዉ በድንጋጌዉ መሠረት በቅጣት ማክበጃነት ሊያዙ ከሚችሉት ምክንያቶች ዉስጥ አንዱ ወንጀለኛዉ አስቀድሞ ጥፋተኛ የተባለበት ሪከርድ መኖሩ አደገኝነቱን የሚያሳይ ሲሆን ማክበጃ ምክንያት ሊያዝበት የሚችል መሆኑን ነዉ፡፡ በሌላ በኩል አስቀድሞ የነበረዉ የጥፋተኝነት ሪከርድ ከፍርድ መዝገብ እንዲሰረዝና ወደፊትም እንዳልተፈረደበት ለመቆጠር በወ/ሕ/አንቀጽ 232 እና ተከታዮቹ ድንጋጌዎች መሠረት መሰየም የሚኖርበት ሲሆን ቅጣቱ ጽኑ እስራት ሲሆን በአመክሮ ከተፈታበት ጊዜ አንስቶ የ5 ዓመት ጊዜ ያለፈዉ እንደሆነና የመሰየም ጥያቄ ቀርቦ ተቀባይነት ሲያገኝ ነዉ፡፡ መሠየም የሚገኘዉ በመልካም ሥራ ነዉ እንጂ በይገባኛል አለመሆኑም በተጠቀሠዉ አንቀጽ ሥር ተመልክቷል፡፡

በተያዘዉ ጉዳይ አመልካች በግድያ ወንጀል ጥፋተኛ የተባለዉ ሕዳር 03 ቀን 2001 ዓ.ም ሲሆን በአመክሮ የተፈታዉ መጋቢት 23 ቀን 2001 ዓ.ም ነዉ፡፡ አመልካች በካባድ ስርቆት ተሳትፎ የተገኘዉ ደግሞ ሐምሌ 17 ቀን 2006 ዓ.ም በመጀመሪያዉ ወንጀል በአመክሮ ከተፈታ 5 ዓመት እንዳለፈዉ ነዉ፡፡ ሆኖም አመልካቹ ለመሰየም የሚያበቃዉ የ5 ዓመት ጊዜ ያለፈዉ ቢሆንም ለፍ/ቤቱ የመሰየም ጥያቄ ካለማቅረቡም በላይ በወ/ሕ/አንቀጽ 233 መሰረት ሌሎች ለመሰየም የሚያበቁ ቅድመ ሁኔታዎች መሟላታቸዉ አልተረጋገጠም፡፡ መሰየምም የሚገኘዉ በመልካም ሥራ ነዉ እንጂ ጊዜዉ በማለፉ ብቻ አይደለም፡፡ ስለሆነም አመልካች አስቀድሞ ጥፋተኛ በተባለበት ወንጀል ባልተሰየመበትና ቅጣቱም ከፍርድ መዝገብ ተሰርዞ እንዳልተሰጠ ባልተቆጠረበት ሁኔታ በሪከርድነት ተይዞ በቅጣት ማክበጃነት

በወ/ሕ/አንቀጽ 84(1/ሐ) መሠረት መያዙ ተገቢ አይደለም ሲል ያቀረበዉ መከራከሪያ ተገቢነት የሌለዉ በመሆኑ ክርክሩን አልተቀበልንም፡፡

በሌላ በኩል አመልካች አስቀድሞ በፈጸመዉ ወንጀል ጥፋተኛ ተብሎ በአመክሮ ከተፈታ 5 ዓመት ያለፈዉ ቢሆንም ባለመሰየሙ ምክንያት የጥፋተኝነቱ ሪኮርዱ ያልተሰረዘና በማክበጃነት የተያዘበት በመሆኑ በወ/ሕ/አንቀጽ 82(1/ሀ) መሰረት የአመልካች የቀድሞ ባህሪዉ መልካም ነዉ ሊባል የማይችል ነዉ፡፡ ይህ ከሆነ ደግሞ በወ/ሕ/አንቀጽ 82(1/ሀ) መሰረት የቅጣት ማቅለያ ምክንያት የሚያዝበት አግባብ የለም፡፡

ሲጠቃለል የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በስር ፍ/ቤት በአመልካች ላይ የተወሰነዉን የጥፋተኝነት ዉሳኔ በማጽናት በወ/ሕ/አንቀጽ 84(1/ሐ) መሰረት አንድ የቅጣት ማክበጃ ምክንያት መያዙም ሆነ በወ/ሕ/አንቀጽ 82(1/ሀ) መሰረት የቅጣት ማቅለያ ምክንያት አለመያዙ የሚነቀፍበት የሕግ ምክንያት ባለመኖሩ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል ለማለት አልተቻለም፡፡ በመሆኑም የሚከተለዉ ተወስኗል፡፡

<u>**ውሳኔ**</u>

1. በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁጥር 002643 ግንቦት 01 ቀን 2010 ዓ.ም የተሰጠዉ ዉሳኔ በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ 195/2/ለ/2/ መሠረት ጸንቷል፡፡
2. መዝገቡ ተዘግቷል፤ ተመላሽ ይደረግ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ፋ/ዘ

**የሰ/መ/ቁ/** - 137908

**ቀን** - 21/05/2010

**ዳኞች፡-ዳኜ መላኩ**

ተኽሊት ይመሰል

ቀነዓ ቂጣታ

ተሾመ ሽፈራዉ

ፀሐይ መንክር

**አመልካች፡-** የጋሞ አካባቢ ከፍተኛ ዐቃቤ ሕግ አልቀረበም፡፡

**ተጠሪ፡-** ወ/ሮ ፀሐይ አሰፋ ከጠበቃ ደመነ ቱንኤ ጋር ቀረቡ፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍርድ**

ጉዳዩ ተጠሪ በሕፃናት ማሳደጊያ ሰበብ ከተለያዩ በጎ አድራጎት ድርጅት በተገኘዉ ገንዘብ ያፈሩት ሀብት እና ንብረት እንዲመልሱ እንዲሁም በሕፃናት ላይ ለደረሰዉ የሞራል ካሳ ገንዘብ እንዲከፍሉ የቀረበዉን ክስ መሠረት በማድረግ የተሰጠዉን ፍርድ በመቃወም የቀረበ የሰበር አቤቱታን የሚመለከት ነዉ፡፡

ክርክሩ የተጀመረዉ በጋሞ አካባቢ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሲሆን፣ አመልካች ከሳሽ ተጠሪ ደግሞ ተከሳሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡ የአመልካች ክስ ይዘትም በአጭሩ፤ ተጠሪ የሕፃናት ማሳደጊያ ድርጅት ፈቃድ ሳይኖራቸዉ ያላቸዉ በማስመሰል ፀሐይ አሰፋ የሕፃናት ማሳደጊያ ማዕከል በሚል ስያሜ ከ1983 ዓ.ም እስከ 2002 ዓ.ም ድረስ ቁጥራቸዉ 282 የሚሆኑ ወላጅ አልባ ሕፃናትን ለሌላ ድርጅት አሳልፈዉ የሰጡ መሆናቸዉን፣ በዚህ ምክንያት ከአርባ ምንጭ ከተማ 1000 ካ/ሜትር ቦታ ወስደዉ 800,000.00 ብር የሚገመት ቤት መገንባታቸዉን፣ ከተለያዩ በጎ አድራጎት ድርጅቶች ገንዘብ በማግኘት የተለያዩ ንብረቶችን በህገ ወጥ መንገድ ማፍራታቸዉን፣ በዚህም ምክንያት በወንጀል ተከስሰዉ ጥፋተኛ ተብለዉ የተቀጡ በመሆኑ በወንጀል ህጉ አንቀጽ 100(1) መሠረት በህገ ወጥ መንገድ ያፈሩትን ንብረት ለመንግስት ገቢ ማድረግ ያለባቸዉ በመሆኑ የተለያዩ ንብረቶች ዋጋ ብር 1,916,300.00፣ በ282

ሕፃናት ላይ ለደረሰ የሞራል ጉዳት ካሳ ብር 282,000.00 እንዲከፍሉ እና በአርባ ምንጭ ከተማ በ1000 ካ/ሜትር ላይ ያረፈዉን ቤት እና ቦታዉን ለመንግስት እንዲያስረክቡ ይወሰንለት ዘንድ ዳኝነት መጠየቁን የሚያሳይ ነዉ፡፡

ተጠሪ ለቀረበባቸዉ ክስ በሰጡት መልስ፤ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያዎች ናቸዉ የሚሏቸዉን ነጥቦች ካነሱ በኋላ፣ ፍሬ ነገሩን በተመለከተ በወንጀል ድርጊት የተገኘን ገንዘብ/ንብረት ለመንግስት ገቢ ማድረግ የሚቻለዉ በወንጀሉ ማቋቋሚያ ድንጋጌ ላይ በግልጽ የተመለከተ ሲሆን በመሆኑ እና ተጠሪ ጥፋተኛ የተባሉበት የወንጀል ህጉ አንቀጽ 433 ድንጋጌ ንብረት የሚወረስ ስለመሆኑ የማይደነግግ መሆኑን፣ ተጠሪ ካላቸዉ የሰብአዊነት እና የእናትነት ፍቅር በመነሳሳት ወላጆቻቸዉን በሞት ያጡ እና በችግር ላይ ያሉትን ሕፃናት በሚመለከታቸዉ የመንግስት አካላት ተጣርቶ በሚቀርብላቸዉ መሠረት ተቀብለዉ ወደ ሕፃናት ማሳደጊያ ድርጅት ከማስተላለፍ በስተቀር በስማቸዉ የሚታወቅ የሕፃናት ማሳደጊያ ድርጅት የሌላቸዉ መሆኑን፣ ተጠሪ እ.ኤ.አ ጥር 10/2007 እስከ እ.ኤ.አ ነሐሴ 05/2011 ዓ.ም ድረስ ከኤስ ኦ ኤስ አንፋንትስ ኢትዮጵያ ጋር የስራ ዉል በመፈጸም የድርጅቱ የአርባ ምንጭ ቅርንጫፍ ኃላፊና ተጠሪ በመሆን ሲሰሩ መቆየታቸዉን፣ ድርጅቱ የተጠሪን የመኖሪያ ቤት ተከራይቶ ሲሰራ መቆየቱን እና አመልካች በክሱ የጠቀሳቸዉ 282 ሕፃናትም ድርጅቱ በስሙ የተረከባቸዉ እንጂ በግል ያልተረከቡ መሆኑን፣ ችግረኛ ሕፃናትን ተቀብለዉ በግል ገንዘባቸዉ በራሳቸዉ መኖሪያ ቤት የሚያሳድጉ መሆኑን ተገንዝቦ የአርባ ምንጭ ከተማ ማዘጋጃ ቤት 1000 ካ/ሜ ቦታ የሰጣቸዉ ሲሆን በቦታዉ ላይ የተሰራ ቤት በግላቸዉ የሰሩት መኖሪያ ቤት እንጂ የሕፃናት ማሳደጊያ ቤት አለመሆኑን፣ በ25 ሕፃናት ስም በየወሩ ሲላክ የነበረዉ 120.00 ብር በኢ/ንግድ ባንክ አ/ምንጭ ቅርንጫፍ ሂሳብ ቁጥር 1033 ገቢ ሲደረግ የነበረዉም በድርጅቱ ባለሙያ ህጋዊነቱ ተጣርቶ ሂሳቡ የተዘጋ መሆኑን፣ ተጠሪ ለስራ ሲጠቀሙበት የነበረዉ እና አመልካች በክሱ የጠቀሰዉ መኪናም የልጃቸዉ መሆኑን፣ አመልካች በክሱ የዘረዘራቸዉ ሌሎች የተለያዩ ቁሳቁሶችም የተጠሪ የግል ንብረቶች መሆናቸዉን፣ ለ282 ሕፃናት የተጠየቀ የሞራል ካሳም የህግ መሠረት የሌለዉ መሆኑን በመጥቀስ የቀረበባቸዉ ክስ ዉድቅ ሆኖ ይወሰንላቸዉ ዘንድ ተከራክረዋል፡፡

ጉዳዩ በመጀመሪያ የቀረበለት የጋሞ አካባቢ ከፍተኛ ፍርድ ቤትም በዚህ መልኩ ግራ ቀኝ ያቀረቡትን ክርክር እና የተለያዩ የሰነድ ማስረጃዎችን እንዲሁም የሰዉ ምስክሮችን አቅርቦ ከሰማ እና ከመረመረ በኋላ፤ በአርባ ምንጭ ከተማ 1000 ካ/ሜትር ቦታ ለተጠሪ ሊሰጥ የቻለዉ ለወላጅ አልባ ሕፃናት ማሳደጊያነት መሆኑ ስለተረጋገጠ ተጠሪ ይህን ቦታ ሊመልሱ እንደሚገባ፣ በቦታዉ ላይ የተገነባ ቤት በህገ ወጥ መንገድ በተገኘ ገንዘብ ስለመሆኑ አመልካች በማስረጃዎቹ ያላስረዳ መሆኑን እና ተጠሪ ቤቱን የሠራዉ ያለማንም ተቃዉሞ መሆኑ ስለተረጋገጠ የግንባታዉ ወጪ ተገምቶ ሲቀርብ አመልካች እንዲከፍል በማለት የወሰነ ሲሆን፤ ሌሎች የተለያዩ ንብረቶችን ተጠሪ በህገ ወጥ መንገድ ያፈሩ መሆኑን አመልካች ያላስረዳ መሆኑን በመግለጽ በዚህ ረገድ የቀረበዉን ዳኝነት ዉድቅ በማድረግ

ወስኗል፡፡ አመልካች ይህን ዉሳኔ ባለመቀበል ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ እና ሰበር ሰሚ ችሎት ያቀረበዉ አቤቱታም ተቀባይነት አላገኘም፡፡

ይህ የሰበር አቤቱታ የቀረበዉም ይህኑን ዉሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ሲሆን አመልካች በቀን 10/06/09 ዓ.ም አዘጋጅቶ ባቀረበዉ የሰበር አቤቱታ፤ ተጠሪ በሕፃናት ማሳደጊያ ስም በአርባ ምንጭ ከተማ በተሰጣቸዉ ቦታ ላይ የሰሩት በሕፃናት ስም ከተለያዩ ድርጅቶች በተገኘ ገንዘብ መሆኑ እየታወቀ ቤቱን በተመለከተ መንግስት ካሳ ከፍሎ መሬቱን እንዲወስድ መወሰኑ፣ መኪናዉን እና ለሕፃናት ማሳደጊያ የሚሆኑ የተለያዩ ቁሳቁሶች ከተለያዩ የመንግስት ተቋማት በተቋቋመ ኮሚቴ ታሽጎ እያለ ተጠሪ ገንጥለዉ መዉሰዳቸዉ ተረጋግጦ እያለ አመልካች እንደ ክሱ አላስረዳም በሚል ምክንያት ዉድቅ መደረጉ እንዲሁም ተጠሪ በወንጀል ተከሶ ጥፋተኛ መሆናቸዉ እና በወንጀል ፍሬ የተገኘ ሀብት ደግሞ ሊወረስ እንደሚገባ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አስገዳጅ ዉሳኔ ሰጥቶ እያለ ተጠሪ ኃላፊነት የለባቸዉም ሲል በከፍተኛ ፍርድ ቤት ተወስኖ እስከ ክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ፀንቶ የተወሰነ ዉሳኔ መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት መሆኑን ጠቅሶ ታርሞ ይወሰንለት ዘንድ ዳኝነት ጠይቋል፡፡

አቤቱታዉ ተመርምሮም በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጡ ዉሳኔዎች ከወንጀል ዉሳኔዉ ጋር ተገናዝበዉ የታዩ መሆን አለመሆናቸዉን ግራ ቀኝ በተገኙበት አጣርቶ ለመወሰን ሲባል ያስቀርባል በመባሉ ተጠሪ ቀርበዉ እንዲከራከሩ ጥሪ የተደረገላቸዉ ሲሆን፣ በዚህም መሠረት በቀን 24/09/2010 ዓ.ም ተዘጋጅቶ በጠበቃቸዉ አማካይነት በጽሑፍ በቀረበ መልስ፤ በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጠዉ ዉሳኔ መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት አይደለም የሚሉባቸዉን ምክንያቶች በመዘርዘር ፀንቶ እንዲወሰንላቸዉ ጠይቀዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ እና የግራ ቀኝ ክርክር ይዘት አጠር አጠር ባለ መልኩ ሲታይ ከፍ ሲል የተመለከተዉን የሚመስል ሲሆን ይህ ችሎትም ለአቤቱታዉ ምክንያት የሆነዉን ዉሳኔ ከግራ ቀኝ ክርክር እና ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸዉ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መዝገቡን እንደሚከተለዉ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረዉም ተጠሪ በወንጀል ጥፋተኛ ሆኖ በመገኘታቸዉ ብቻ ከ1000 ካ/ሜትሩ የከተማ መሬት ዉጪ ያሉትን እና አመልካች በክሱ ያመለከታቸዉ ንብረቶችን ወይም የንብረቶቹን ዋጋ ለመንግስት ገቢ እንዲያደርጉ ለመጠየቅ የሚያስችለዉ መብት አለዉ ወይስ የለዉም? መብት አለዉ የሚባል ከሆነ በክሱ የተዘረዘሩትን ንብረቶች ተጠሪ በሕፃናት ማሳደጊያ ድርጅት ስም በህገ ወጥ መንገድ ያፈሩ መሆን አለመሆኑ ከግራ ቀኝ ክርክር አንፃር በስር ፍርድ ቤት በአግባቡ ተጣርቷል ወይ? የሚሉ ጭብጦች የዚህን ችሎት ምላሽ የሚሹ ሆነዉ ተገኝተዋል፡፡

በመግቢያዉ እንደተመለከተዉ አመልካች በስር ፍርድ ቤት ላቀረበዉ ክስ መሠረት ያደረገዉ 1ኛ ተጠሪ ፈቃድ ሳይኖራቸዉ ፈቃድ ያላቸዉ በማስመሰል የሕፃናት ማሳደጊያ ድርጅት በስማቸዉ በማድረግ

ሕፃናትን በመዉሰድ ለሌላ ድርጅት ሲሰጡ የነበረ በመሆኑ በወንጀል ተከሰዉ ጥፋተኛ መባላቸዉን፣ ይህን ህገ ወጥ ድርጊት በመፈጸም ከተለያዩ በጎ አድራጎት ድርጅቶች ባገኙት ገንዘብ የተለያዩ ንብረቶችን በማፍራታቸዉ እና የከተማ ቦታ በመዉሰዳቸዉ በወንጀል ህጉ አንቀጽ 100(1) መሠረት ንብረቱ ለመንግስት ገቢ መደረግ የሚገባዉ መሆኑን በመጥቀስ ነዉ፡፡ ይህንን መሠረት በማድረግም ተጠሪ ለመንግስት ገቢ ሊያደርጉ ይገባል የሚላቸዉን ንብረቶች ዝርዝር በማቅረብ ግምቱን እንዲከፍል፤ በሕፃናት ማሳደጊያ ድርጅት ስም የተሰጣቸዉን 1000 ካ/ሜትር ይዞታም እንዲመልሱ የጠየቀ መሆኑን መዝገቡ ያሳያል፡፡

በመሠረቱ በወንጀል ጉዳይ ንብረት ወይም ሀብት ሊወረስ ወይም ለመንግስት ገቢ እንዲሆን ማድረግ በወንጀል ህጉ ከተመለከቱት የቅጣት እና የጥንቃቄ እርምጃዎች አንዱ ስለመሆኑ ንብረት ስለሚወረስበት ሁኔታን የሚመለከቱ የወንጀል ህጉ ድንጋጌዎች ከሚገኙበት የህጉ ሁለተኛ መጽሐፍ ምዕራፍ ሁለት ድንጋጌዎች አጠቃላይ አወቃቀር እና ይዘት መረዳት ይቻላል፡፡ በወንጀል ጉዳይ ንብረት ወይም ሀብት ሊወረስ ወይም ለመንግስት ገቢ እንዲሆን ማድረግ የሚቻልባቸዉ ሁኔታዎች፤ ቅጣቱ ንብረት መዉረስን እንደሚያካትት በወንጀል ህጉ ልዩ ክፍል በግልጽ የተደነገገ ሲሆን፣ የጥፋተኛነት ዉሳኔ በተሰጠበት የወንጀል ስራ ወንጀለኛዉ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ ያገኘዉ ንብረት ሲኖር፣ አንድ ሰዉ ለወንጀል ስራ እንዲነሳሳ ወይም ወንጀሉን ለመስራት እንዲረዳዉ ወይም ወንጀሉን ለፈጸመበት ዋጋ እንዲሆነዉ የተሰጠዉ ወይም ሊሰጠዉ የታቀደዉ ንብረት ሲኖር፣ ወንጀልን ለመፈጸም ሊያገለግሉ የሚችሉ ወይም ለወንጀል ተግባር ያገለገሉ ወይም የወንጀል ተግባር ፍሬ የሆኑ አደገኛ የሆኑ ነገሮች ሲሆኑ ስለመሆኑ በወንጀል ህጉ አንቀጽ 98፣ 100(1) እና 140 ስር ከተመለከቱት ድንጋጌዎች መረዳት ይቻላል፡፡ ንብረት እንዲወረስ ወይም ለመንግስት ገቢ እንዲሆን ማድረግ በወንጀለኛዉ ላይ ሊጣሉ ከሚችሉ ቅጣቶች አንዱ በመሆኑም፣ ፍርድ ቤቶች የጥፋተኝነት እና የቅጣት ዉሳኔን ተከትሎ ንብረት ወይም ሀብት እንዲወረስ ወይም ለመንግስት ገቢ እንዲሆን መወሰን የሚችሉት እነዚህን ድንጋጌዎች መሠረት በማድረግ አቃቤ ህግ ሊወረሱ የሚገባቸዉን ንብረቶች ዝርዝር በወንጀል ክሱ ካመለከተ፣ ንብረቶቹም ከፍ ሲል በተመለከቱት ድንጋጌዎች አግባብ የተገኙ ስለመሆኑ በወንጀል ፍርድ ሂደት ከተረጋገጠ እና በወንጀል መዝገቡ ላይ አቃቤ ህግ ንብረቶቹ እንዲወረሱ ካመለከተ ስለመሆኑ ከላይ ከተጠቀሱት ድንጋጌዎች እንዲሁም በወንጀል ሥ/ሥ/ሥርዓት ህጉ አንቀጽ 211 ስር ከተመለከቱት ድንጋጌዎች ይዘት እና መንፈስ መረዳት ይቻላል፡፡

ከዚህ አንፃር የተያዘዉን ጉዳይ ስንመለከት፣ ከፍ ሲል እንደተመለከተዉ፣ አመልካች በተጠሪ ላይ ላቀረበዉ ክስ መሠረት ያደረገዉ 1ኛ ተጠሪ ፈቃድ ሳይኖራቸዉ ፈቃድ ያላቸዉ በማስመሰል የሕፃናት ማሳደጊያ ድርጅት በስማቸዉ በማድረግ ሕፃናትን በመዉሰድ ለሌላ ድርጅት ሲሰጡ የነበረ በመሆኑ በወንጀል ተከሰዉ ጥፋተኛ መሆናቸዉን ነዉ፡፡ በርግጥ ተጠሪ ከዚሁ ጉዳይ ጋር በተያያዘ በወንጀል ህጉ አንቀጽ 433 ስር ጥፋተኛ ተብለዉ የተወሰነባቸዉ ስለመሆኑ ግራ ቀኝ አልተካካዱም፡፡ ይሁንና በወንጀል

ህጉ አንቀጽ 433 መሠረት ጥፋተኛ በሆነ ሰዉ ላይ የሚጣል ቅጣት ንብረት መዉረስን ወይም ለመንግስት ገቢ ማድረግን እንደሚያካትት በድንጋጌዉ አልተመለከተም፡፡ ተጠሪ ፍቃድ ሳይኖራቸዉ ሕጻናትን በማሳደግ ስራ ላይ በመሰማራት በፈጸሙት የወንጀል ተግባር በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ መንገድ ያገኙት ንብረት ካለ በወንጀል ህጉ አንቀጽ 98(2) መሠረት ሊወረስ የሚችልበት ሁኔታ ቢኖርም፣ ይህ የሚሆነዉ፣ ከላይ በተገለጸዉ ምክንያት፣ አቃቤ ህግ የወንጀል ክሱን ሲያቀርብ ተጠሪ ጥፋተኛ በተባሉበት ድርጊት ምክንያት በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ ያፈሩት ንብረት ስለመኖሩ ገልፆ በዚህ መልኩ ተጠሪ ያፈሩት ንብረትም በወንጀል መዝገቡ ላይ ተረጋግጦ ንብረቱ እንዲወረስም በወንጀል መዝገቡ ላይ አቃቤ ህጉ በሚያቀርበዉ የቅጣት አስተያየት መሰረት ፍርድ ቤቱ ትዕዛዝ ሲሰጥ ነዉ፡፡ ከዚህ ዉጪ፣ በወንጀል መዝገብ ላይ ቀርቦ ክርክር ተደርጎበት ተረጋግጦ በቅጣት መልክ ንብረት እንዲወረስ የወንጀል መዝገቡን በያዘዉ ፍርድ ቤት ባልታዘዘበት ሁኔታ፣ ቀደም ሲል በወንጀል መዝገብ ላይ የተሰጠዉን የጥፋተኝነት እና የቅጣት ዉሳኔ መሠረት በማድረግ በክሱ የተመለከቱትን ንብረቶችን ተጠሪ ለመንግስት ገቢ እንዲያደርጉ በፍትሐብሔር መዝገብ ዳኝነት የጠየቀበት አግባብ የወንጀል ድርጊትን መነሻ በማድረግ ንብረት ሊወረስ የሚችልበትን ዓላማ መሰረት ያደረገ ሆኖ አልተገኘም፡፡

ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ ተጠሪ በፈጸሙት የወንጀል ድርጊት ምክንያት በመንግስት ላይ ያደረሱት ፍትሐብሔራዊ ጉዳት ካለ በፍትሐብሔር ሕጉ አንቀጽ 2035 እና 2162 መሠረት ኃላፊነት የሚኖርባቸዉ በመሆኑ አመልካች የደረሰዉን ጉዳት ጠቅሶ በተጠሪ ላይ ክስ እንዳያቀርብ የሚከለክለዉ የለም፡፡ ይሁንና ይህ ሂደት የሚመራዉ በመደበኛዉ የፍትሐብሔር የሙግት ስርዓት በመሆኑ፣ ክርክሩ በፍትሐብሔር ሥ/ሥርዓት ህጉ የተመለከቱትን ደንቦች እና መርሆዎች የተከተለ ሊሆን ይገባል፡፡ በህጉ ከተመለከቱት ደንቦች ዉስጥም ከሳሽ ለክሱ መነሻ በሆነዉ ነገር ወይም ክሱ በተመሰረተበት ሀብት ላይ መብት ወይም ጥቅም ያለዉ መሆኑን የማሳየት ግዴታ አንዱ እና ዋነኛዉ ነዉ፡፡ የዚህ መርህ ጠቀሜታ ጉዳት ከደረሰበት ሰዉ በቀር አንድ ሌላ ሰዉ ስለ እርሱ ሆኖ ወይም እርሱን ተክቶ ክስ እንዳይመሰርት ለማድረግ በመሆኑ ክሱ የሚቀርብለት ፍርድ ቤትም ከሳሽ ክሱን ለማቅረብ መብት ወይም ጥቅም ያለዉ መሆን አለመሆኑን የማረጋገጥ ግዴታ አለበት (የፍ/ሥ/ሥ/ህጉ አንቀጽ 33/2/ እና 231/1-ሀ/ ድንጋጌዎች ይመለከቷል)፡፡ በዚህ ረገድ አመልካች በስር ፍርድ ቤት ባቀረበዉ ክስ ለመንግስት ገቢ እንዲደረግ በክሱ ከጠቀሳቸዉ ንብረቶች ዉስጥ አንዱ በአርባ ምንጭ ከተማ በሕፃናት ማሳደጊያ ድርጅት ስም ለተጠሪ ያላግባብ የተሰጠ 1000 ካ/ሜትር ቦታ ሲሆን፣ ተጠሪ በፈጸሙት ህገ ወጥ ድርጊት መሬቱ በእጃቸዉ የገባ መሆኑን አረጋግጦ አመልካች መንግስትን ወክሎ መሬቱ እንዲመለስ ለማስወሰን ክስ ለማቅረብ በደቡብ ብ/ብ/ሕ/ክልላዊ መንግስት የአስፈፃሚ አካላትን ስልጣን ለመወሰን በወጣዉ አዋጅ ቁጥር 106/99 መሠረት ስልጣን ያለዉ ከመሆኑም በላይ ከዚህ ጋር በተያያዘ የተሰጠዉን ዉሳኔ በመቃወም ተጠሪ ያቀረቡት አቤቱታ ባለመኖሩ ይህን በተመለከተ የተሰጠዉን ዉሳኔ ማየቱ አስፈላጊ ሆኖ አልተገኘም፡፡

ይሁንና ከመሬቱ ዉጪ ያሉትን ሌሎች ንብረቶችን በተመለከተ አመልካች ለክሱ መሠረት ያደረገዉ ተጠሪ በሕፃናት ማሳደጊያ ድርጅት ስም ከተለያዩ የበጎ አድራጎት ድርጅቶች ባገኙት ገንዘብ ተጠሪ በክሱ የተመለከቱትን ንብረቶች ማፍራታቸዉን ነዉ፡፡ አመልካች ይህን ክስ ሲያቀርብ ተጠሪ ከሌሎች በጎ አድራጎት ድርጅቶች ባገኙት ገንዘብ ንብረቶቹን ማፍራታቸዉ የአመልካችን መብት እንዴት ሊጎዳ እንደሚችል ያልገለጸ ከመሆኑም በላይ፣ ተጠሪ ሕፃናትን የማሳደግ ህጋዊ ፈቃድ ሳይኖራቸዉ ፈቃድ ያላቸዉ በማስመሰል የፈጸሙት ድርጊት እዉነት መስሎአቸዉ እርዳታዉን ሲያደርጉ የነበሩ የበጎ አድራጎት ድርጅቶችን ስም በክሱ አላመለከተም፡፡ አመልካች እነዚህን በጎ አድራጎት ድርጅቶችን ጭምር ወክሎ መከራከር የሚችል ስለመሆኑም አልገለጸም፡፡ ክሱ የቀረበለት ፍርድ ቤትም ወደ ዋናዉ ክርክር ከመግባቱ በፊት አመልካች በክሱ ካመለከታቸዉ ንብረቶች ጋር በተያያዘ መብት ወይም ጥቅም ያለዉ መሆን አለመሆኑን በቅድሚያ ማረጋገጥ ነበረበት፡፡

የፍሬ ነገር ክርክሩን በተመለከተ አመልካች በክሱ ባመለከተዉ እና ለመንግስት እንዲመለስ በተወሰነዉ 1000 ካ/ሜ ቦታ ላይ ለሕፃናት ማሳደጊያ የሚሆኑ የተለያዩ ክፍሎች ያሉት ቤት መሰራቱን፣ ለዚሁ ዓላማ የሚዉሉ የተለያዩ ቁሳቁሶች መኖራቸዉ፣ የሰሌዳ ቁጥሩ ኮድ 3-20744 የሆነ መኪና በተጠሪ ስም ተገዝቶ በእጃቸዉ የሚገኝ እና ለስራዉ የሚጠቀሙበት ስለመሆኑ ተረጋግጧል፡፡ ይህ ከተረጋገጠ ተጠሪ እነዚህን ንብረቶች ሊያፈሩ የሚችሉበት ሌላ የተለየ ገቢ ያላቸዉ መሆን አለመሆኑ በተጨማሪ ማስረጃ ተጣርቶ ሊወሰን የሚገባዉ ነዉ፡፡

ሲጠቃለል ከወንጀል ድርጊት ጋር በተያያዘ ንብረት የሚወረሰዉ ወይም ለመንግስት ገቢ የሚደረገዉ በወንጀል ህጉ እና በወንጀል ስ/ስ/ህጉ መሠረት በቅጣት መልክ ከመሆኑ አንፃር ሲታይ ንብረቱ የሚወረስ መሆን አለመሆኑ ዉሳኔ ማግኘት ያለበት በወንጀል መዝገብ እንጂ በወንጀል መዝገብ ላይ የተሰጠውን ውሳኔ ብቻ መነሻ በማድረግ በአዲስ መልክ በሚቀርብ የፍትሐብሔር ክርክር ሊሆን አይችልም፡፡ ይህ ከሆነ ተጠሪ በፈጸሙት የወንጀል ድርጊት ምክንያት ያፈሯቸዉ ንብረቶች የአመልካችን ጥቅም ወይም መብት የሚነካ ከሆነ ክሱ የሚቀርበዉ እና ሙግቱም የሚመራዉ መደበኛዉን የፍትሐብሔር ስነ ስርዓት በተከተለ መንገድ በመሆኑ፣ አመልካች መብት ወይም ጥቅም ያለዉ መሆኑን በክሱ በግልጽ ሳያሳይ እና ፍርድ ቤቱም ይህን በቅድሚያ ማረጋገጥ ሲገባዉ ይህን ሳያደርግ ከከተማ ቦታ ዉጪ ያሉትን ንብረቶች በተመለከተ ወደ ፍሬ ነገር ክርክር ገብቶ አከራክሮ ያዉም በክሱ የተመለከቱትን ንብረቶች ለማፍራት የሚያስችላቸዉ ተጠሪ የተለየ ገቢ ያላቸዉ መሆን አለመሆኑ በአግባቡ ሳይረጋገጥ በጋሞ አካባቢ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ተሰጥቶ እስከ ክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ፀንቶ የተወሰነዉ ዉሳኔ መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በመሆኑም ተከታዩ ተወስኗል፡፡

**ዉሳኔ**

1. የደቡብ ብ/ብ/ሕዝቦች ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 11871 በቀን 21/04/08 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት፣ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይ/ሰሚ ችሎት በመ/ቁ/11000 ላይ እንዲሁም የጋሞ አካባቢ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ/26888 የሰጧቸዉን ዉሳኔዎች በማጽናት፣ የሰጠዉ ዉሳኔ በፍ/ሥ/ሥ/ ህጉ አንቀጽ 348(1) መሠረት ተሻሽሏል፡፡
2. በአርባ ምንጭ ከተማ የተሰጣቸዉን 1000 ካ/ሜትር ቦታ ተጠሪ እንዲመል በሚል የተሰጠዉን የዉሳኔ ክፍል በማጽናት፤ ቀሪዉን የዉሳኔ ክፍል በመሻር ወስነናል፡፡
3. የጋሞ አካባቢ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አመልካች በጎ አድራጎት ድርጅቶች በሚል የገለፃቸዉ ድርጅቶች እነ ማን ናቸዉ? አመልካች ከ1000 ካ/ሜትር ቦታ ዉጪ ቀሪዎቹን ንብረቶችን በተመለከተ ክስ ለማቅረብ የሚያስችለዉ ከህግ የመነጨ መብት አለዉ ወይስ የለዉም? አመልካች ክሱን ለማቅረብ መብት ያለዉ መሆኑ ተረጋግጦ ወደ ፍሬ ነገር ክርክር የሚገባ ከሆነ በ1000 ካ/ሜትር ቦታ ላይ የተገነቡትን ቤቶች ጨምሮ ሌሎች በክሱ የተመለከቱትን ንብረቶች ለማፍራት የሚያስችላቸዉ ተጠሪ የተለየ የገቢ ምንጭ አላቸዉ ወይስ የላቸዉም? በሚሉት ጭብጦች ላይ የግራ ቀኝ ክርክር እና ተጨማሪ ማስረጃዎችን በመስማት እንዲሁም የፍ/ሥ/ሥርዓት ሕጉ በሚፈቅደዉ መሠረት ጭብጦቹን በአግባቡ አጣርቶ በጉዳዩ ላይ ፍትሐዊ ዉሳኔ ለመስጠት የሚያስችለዉን ተገቢዉን ሁሉ በማድረግ ጉዳዩን አጣርቶ ዉሳኔ እንዲሰጥበት መዝገቡ በፍ/ሥ/ሥርዓት ሕጉ አንቀጽ 343(1) መሠረት ተመልሶለታል፡፡
4. በዚህ ችሎት የተደረገዉ ክርክር ያስከተለዉን ወጪ እና ኪሳራ ግራ ቀኝ የየራሳቸዉን ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ም/ቶ

የሰበር መዝገብ ቁጥር 168166

ግንቦት 28 ቀን 2011 ዓ.ም.

**ዳኞች፡-** ብርሃኑ አመነው

በዕውቀት በላይ

እንዳሻው አዳነ

ሃይሉ ነጋሽ

እትመት አሠፋ

**አመልካቾች፡-** አቶ ይገዙ ቡርዜ

**ተጠሪ፡-** የደቡብ ብ/ብ/ሕ/ክ/መ/ ፍትህ ቢሮ ዓቃቤ ህግ

መዝገቡን መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ ወንጀልን ይመለከታል፡፡ አከራካሪው ጉዳይ የተጀመረው በደቡብ ብ/ብ/ሕ/ክ/መ/ የአርባ ምንጭ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የአሁኑ ተጠሪ በአመልካች ላይ በቀረበው ክስ መነሻነት ነው፡፡ የክሱ ይዘትም፡- አመልካች የኢ.ፌ.ዴ.ሪ. የወንጀል ሕግ አንቀፅ 555(1) የተመለከተውን በመተላለፍ መስከረም 17 ቀን 2009 ዓ.ም ከምሽቱ 4፡00 ሰዓት በሚሆንበት ጊዜ በውሃ ምንጭ ቀበሌ እባያ ግሮሰሪ ውስጥ የግል ተበዳይ ፀጋ ወይሾ የተባለውን በቦክስና በቴስታ ግራ በኩል አገጩን በመምታት የግራ መንጋጋ አጥንት እንዲሰበር በማድረጉ ከባድ የአካል ጉዳት ማድረስ ወንጀል ፈፅመዋል በማለት ክስ ቀርቦበታል፡፡

አመልካች የእምነት ክህደት ቃሉ ሲጠየቅ ድርጊቱ አለመፈፀሙ ክዶ ጥፋተኛ አይደለሁም በማለት ተከራክሯል፡፡ የስር ፍርድ ቤትም የዐቃቤ ሕግ ክርክር እና ማስረጃ መርምሮ አመልካች የተከሰሰበት የህግ ዓንቀፅ በመቀየር የወንጀል ሕግ አንቀፅ 556(1) እንዲከላከሉ ብይን ሰጥቷል፡፡ ተከሳሾች መከላከያ ማስረጃ አቅርበው ያሰሙ ሲሆን ፍርድ ቤቱ ጉዳዩ ከመረመረ በኋላ የቀረበው የሰውና የሰነድ ማስረጃ በመመዘን ተከሳሽ የቀረበበት ክስ ተከላክሏል በማለት በነፃ እንዲሰናበት ወስኗል፡፡

የአሁኑ ተጠሪ በተሰጠው ውሳኔ ቅር በመሰኘት ለጋሞ አካባቢ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አቤቱታ አቅርቦ ፍርድ ቤቱ ቅሬታው ባለመቀበል ሰርዞታል፡፡ በመቀጠል ተጠሪ የተሰጠውን

ውሳኔ በመቃወም ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የሰበር አቤቱታ አቅርቦ ፍርድ ቤቱ ግራ ቀኙን አስቀርቦ ካከራከረ በኋላ የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ በመሻር አመልካች በዓ/ህግ የቀረበበት ወንጀል የፈፀመ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ተከሳሽ ባቀረበው የመከላከያ ምስክሮችም አልተከላከለም በማለት ክስ በቀረበበት የህግ ዓንቀፅ ወንጀል ህግ ዓንቀፅ 555(ሐ) ስር የጥፋተኛነት ውሳኔ ሰጥቷል ፡፡ ፍርድ ቤቱ የግራ ቀኙን የቅጣት አስተያየት ከተቀበለ በኋላ ቅጣቱን በቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 2/2006 መሰረት በማስላት አመልካችን በሁለት አመት ከሶስት ወር ፅኑ እስራት እንዲቀጣ ወስኗል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም የስር ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሳኔ በመቃወም ለማሳረም ነው፡፡

አመልካች በስር ፍርድ ቤት ተፈፀመ ያለውን ስህተት በመዘርዘር ያቀረበ ሲሆን የቅሬታው መሰረታዊ ነጥቦች ሲጠቃለሉ፡- የክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ወንጀል መፈፀሜ ባልተረጋገጠበት ሁኔታ የሰጠው የጥፋተኝነት ውሳኔ እንዲሁም የግራ ቀኙ ማስረጃ የመዘነበት አግባብ እና የስር ሁለቱም ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሳኔ ለመሻር የሰጠው ምክንያት መሰረታዊ የማስረጃ ምዘና መርህ ያልተከተለ በመሆኑ ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት መሆኑ ገልፀው ሊታረም እንደሚገባ መጠየቃቸው የሚያሳይ ነው፡፡ ጉዳዩ ተመርምሮ ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ በመወሰኑ ተጠሪ ቀርቦ በፅሁፍ ተከራክረዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ይዘት ያለው ሲሆን ይህ ችሎትም አመልካች ያቀረበው የሰበር አቤቱታ፣ ለሰበር አቤቱታ መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ያስቀርባል በማለት የተያዘው ጭብጥ ብቻ መርምሮታል፡፡ እንደመረመርነው መዝገቡ ለሰበር ያስቀርባል ሲባል በተያዘው ጭብጥ በአሁኑ አመልካች ተፈፀመ የተባለው ድርጊት አፈፃፀም እና ከተጠቀሙት መሳሪያ አንፃር ጥፋተኛ መባል ያለበት በወንጀል ህግ አንቀጽ 555(ሐ) ነው ?ወይስ የወንጀል ህግ አንቀጽ 556 (1) መሰረት ነው ? በሚል አግባብ ሲታይ አመልካች በቦክስ እና በቴስታ በመምታት በግል ተበዳዩ አካል ላይ ጉዳት ስለማድረሱ በሥር ፍርድ ቤቶች በተደረገው ክርክር በማስረጃዎች የተረጋገጠ ሲሆን ዋናው ምላሽ የሚያስፈለገው ጉዳይ ግን በማስረጃዎች ከተረጋገጠው ፍሬ ነገር አንጻር አግባብነት ያለውን የወንጀል ህግ አንቀጽ የመለየቱ ጉዳይ ነው፡፡

በተያዘው ጉዳይ ላይ በስር ፍርድ ቤት የተሰሙት የዓ/ህግ ምስክሮች የሰጡት የምስክርነት ቃል ሲታይ አመልካች በክሱ በተገለጸው ቦታና ጊዜ በተከሳሽ ግሮሰሪ እየተዝናኑ እያለ ሽንት ቤት ደርሶ ሲመለስ ባጃጅ ውስጥ ታሞ የተኛውን ጓደኛቸውን ተከሳሽ ውጣ ሲል ባጃጁ የኛ ነው ብሎ የግል ተበዳይ ሲናገረው ተከሳሹ አንድ ጊዜ በግራ ጉንጩ ላይ በቦክስ እና በቴስታ የመታው መሆኑ መስክረዋል፡፡ በአንፃሩ የተከሳሽ መከላከያ ምስክሮች የላሜራ ብረት መትቶት ጉዳት የደረሰበት መሆኑ ገልፀው የምስክርነት ቃል ሰጥተዋል፣ ጉዳቱን የሚያመለክት የሃኪም ማስረጃም ቀርቦ ከመዝገቡ ጋር የተያያዘ መሆኑ ተገንዝበናል፡፡ ስለሆነም ከተረጋገጠው ፍሬ ነገር አመልካች በክሱ በተገለጸው የቦታ፣የጊዜ እና የወንጀል አፈጻጸም ዝርዝር መሰረት የግል ተበዳይ የሆነውን ፀጋ ወይሶ በቦክስ እና በቴስታ የመታው

መሆኑ በዐቃቤ ሕግ ማስረጃ መረጋገጡን፣በአመልካቹ በኩል ቀርበው የተሰሙት የመከላከያ ምስክሮችም በዐቃቤ ሕግ የሰው እና የሰነድ ማስረጃ የተመሰከረውን የወንጀል ፍሬ ነገር ለማስተባበል ያልቻሉ ስለመሆኑ በስር ፍርድ ቤት የተረጋገጠ ጉዳይ ነው፡፡

አሁን ከዚህ ችሎት ምላሽ የሚያስፈልገው ጉዳይ በአመልካች መፈጸሙ የተረጋገጠው የወንጀል ተግባር የሚሸፈነው በወንጀል ህግ አንቀፅ 555 ስር ነው? ወይስ በወንጀል ህግ አንቀፅ 556(1) ስር ነው? የሚለው ነጥብ ነው:: በተያዘው ጉዳይ ድርጊቱ የተፈፀመው እና አመልካች ጉዳት ለማድረስ የተጠቀመበት መሳሪያ በተመለከተ በእርግጥም የከባድ የአካል ጉዳት ወንጀል ነው? ወይስ የቀላል የአካል ጉዳት የሚያቋቋም ነው? የሚለውን መለየት እንዲቻል ለድርጊቱ አፈፃፀምና አመልካች የተጠቀሙበት መሳሪያ ድርጊቱ የተፈፀመበት የተበዳይ የሰውነት ክፍል እንዲሁም የወንጀሉ አፈፃፀም ሁኔታ መታየት ያለበት ነው፡፡

በመሠረቱ አንድ ወንጀል ተደረገ የሚባለው ወንጀሉን የሚያቋቁሙት ህጋዊ ግዙፋዊ እና ሞራላዊ ፍሬ ነገሮች በአንድነት ተሟልተው ሲገኙ ብቻ መሆኑን በአዋጅ ቁጥር 414/1996 የወንጀል ህጉ አንቀፅ 23(2) በግልፅ ተደንግጓል፡፡ እንግዲህ አንድን ድርጊት ወንጀል ነው ብሎ ለመወሰን ህጋዊ፣ ግዙፋዊ እና ሞራላዊ ፍሬ ነገሮች ተጣምረው መገኘት የግድ ይላል፡፡ ህጋዊ ፍሬ ነገሮች የሚባሉት ደግሞ ለጉዳዩ አግባብነት አለው ተብሎ የተጠቀሰውን ድንጋጌ ለማቋቋም ሙሉ በሙሉ መሟላት ያለባቸውን ነጥቦች ሲሆን ግዙፋዊና ሞራላዊ ፍሬ ነገሮች የሚባሉት ደግሞ እንደየቅደም ተከተላቸው ከድርጊት ማድረግ ወይም አለማድረግና ከሀሳብ ክፍል ጋር በህጉ የተመለከቱትን ሁኔታዎች የሚመለከቱ መሆናቸው የሚታወቅ ነው፡፡ ሌላው ወንጀል ክርክር አንድ ሰው ክሱን እንዲከላከል ወይም ጥፋተኛ ሊባል የሚችለው ዐቃቤ ህግ በህጉ የተጣለበትን የማስረዳት ግዴታውን የተወጣ መሆኑን ሲረጋገጥ መሆኑም የሚታወቅ ነው፡፡ የወ/መ/ህ/ስ/ስ/ህ/ቁ 141 ድንጋጌ አቀራረፅና ይዘት ከወ/መሥ/ሥ/ህ/ቁጥር 111 እና 112 ድንጋጌዎች ተጣምሮ ሲታይም በወንጀል ጉዳይ ዐቃቤ ህግ እንደክሱ በበቂ ሁኔታ የማስረዳት ግዴታ ያለበት መሆኑን የሚያስገነዝብ ነው፡፡ ይህን በህጉ የተመለከተውን የማስረጃ መለኪያ መስፈርት መሰረት በማድረግ የወንጀል ድርጊቱ መፈፀሙን የፈፀመውን ሰው ማንነት እና በአፈፃፀሙ ላይ የነበረውን የተሳትፎ ደረጃ ማረጋገጥ የግድ ይላል፡፡ ዐቃቤ ህግ የተከሳሽን የአእምሮ ክፍል ሊያስረዳ የሚችለው የድርጊቱን አፈፃፀም በማረጋጥ ሲሆን ከድርጊቱ አፈፃፀም ድርጊት ፈፃሚው ወንጀሉን ሲፈፅም የነበረውን የአእምሮ ሁኔታ ፍርድ ሰጪው አካል ሊረዳ የሚችል መሆኑም የሚታመን ነው፡፡

ይህንኑ የህጉን ይዘትና መንፈስ ይዘን ወደዚህ ጉዳይ ስንመለስም ከመዝገቡ ይዘት ለመረዳት እንደተቻለው ተፈፀመ የተባለው ድርጊት አመልካች ስለመፈፀሙ የተረጋገጠ ጉዳይ ሲሆን አመልካች ወንጀሉን ለመፈፀም የተጠቀመበት መሳሪያ የሴለና በቦክስና በቴስታ የመታ በመሆኑ ከቀረቡት የዓ/ህግ ማስረጃዎች የተረጋገጠ መሆኑ በፍሬ ነገር ደረጃ በስር ፍርድ ቤቶች የተረጋገጠ ጉዳይ ነው፡፡

ታስቦ የሚፈፀም ከባድ የአካል ጉዳት  በወንጀል ሕግ አንቀፅ 555(ሐ) መሰረት ድርጊት ፈጻሚውን ሊያስጠይቅ የሚችለው ድርጊቱ ሆነ ተብሎ በማንኛውም ሌላ መንገድ ከባድ የሆነ ጉዳትን ወይም በሽታን በሌላ ሰው ላይ ያደረሰ እንደሆነ የሚያመለክት ነው። አንድ ሰው ይህንን ከላይ የተጠቀሰውን ሃሳብና የድርጊት አፈጻጸም መሰረት ወንጀል  ፈጽሞ ቢገኝ እና ይህም ሁኔታ በማስረጃ ሲረጋገጥ  ተከሣሽ በዚህ አንቀጽ ስር ጥፋተኛ ሊባል የሚችል መሆኑን የሕጉ ይዘት ያሳያል ፡፡

በያዝነው ጉዳይ አመልካች የግል ተበዳይ ለሆነውን  ፀጋ ወይሾ ላይ አስቦ በተበዳይ አካል ላይ ጉዳት ያደረሰ ቢሆን ጉዳት ያደረሰው በቦክስ እና በቴስታ መሆኑ እና ከባድ የሆነ ጉዳትን ወይም በሽታን በተበዳይ ላይ ያደረሰ መሆኑ ያልተረጋገጠ በመሆኑ፣ይህ ተግባር ከወንጀል ሕግ አንቀፅ 555 ከተመለከተው ውጪ ስለሆነ አመልካች የፈፀመው ተግባር ወንጀል ሕግ አንቀፅ 556(1) የተመለከተውን የህግ ድንጋጌ በመጣስ መሆኑ የሚያሳይ ነው፡፡

ስለሆነም የአመልካች የወንጀል ድርጊት በስር ፍርድ ቤት የጥፋተኝነት ውሳኔ የተሰጠበት የወንጀል ህግ ድንጋጌ የማይሸፈን በመሆኑ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አመልካችን በወንጀል ህግ ዓንቀፅ 555(ሐ) ጥፋተኛ በማለት ቅጣት መወሰኑ አግባብ ስላልሆነ፣ በተረጋገጠው የአመልካች የወንጀል አድራጎት የወንጀል ህግ አንቀጽ 556(1) የተመለከተውን በመተላለፍ ጥፋተኛ ነው ብለናል፡፡

በአመልካች ላይ ተጥሎ የነበረው የጥፋተኛነት ውሳኔ የተለወጠ ስለሆነ የቅጣት ውሳኔውም ሊስተካከል ይገባል፡፡ ቅጣትን በተመለከተ አመልካች ጥፋተኛ የተባለበት ድንጋጌ በተሻሻለው የቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 2/2006  የወንጀል ደረጃና እርከን የወጣለት በመሆኑ በመመሪያው ዓንቀፅ 26 መሰረት የቅጣት አሰላል ስነ ስርአት ቅደም ተከተል ሲታይ የጥፋተኝነት ውሳኔ ከተሰጠ በኋላ የወንጀሉ ደረጃ ሊወሰን ስለሚገባው አመልካች ጥፋተኛ የተባለበት የህግ ድንጋጌ የወንጀል ህግ አንቀጽ 556(1) አንድ አመት በማይበልጥ ቀላል እስራት ወይም በመቀጮ የሚያስቀጣ በመሆኑ በቀላል እስራት እንዲቀጣ ወስነናል፡፡

ስለሆነም አመልካች በሰው አካል ወይም ጤና ላይ አስቦ ቀላል ጉዳት ያደረሰ ስለሆነ የወንጀሉን ደረጃ 1 እርከን 2 የሚያርፍ ነው፡፡ በስር ፍ/ቤት የቀረበና ተቀባይነት ያገኘ የቅጣት ማክበጃም ማቅለያም ስላልነበረ የቅጣት እርከኑ አልጨመረም አልቀነሰም ስለሆነም የወንጀሉን አፈጻጸም እና የደረሰውን ጉዳት ግምት ውስጥ በማስገባት በዚህ ጉዳይ የታሰረበት ካለ የሚታሰብለት ሆኖ አመልካች ለፈፀመው ወንጀል በሶስት ወር ቀላል እስራት ሊቀጣ የሚገባው ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በዚሁ መሠረት የስር ፍ/ቤት የሰጠው የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመት በመሆኑ በማሻሻል ተከታዩን ውሳኔ ሠጥተናል፡፡

## ውሳኔ

1 . በደቡብ ብ/ብ/ሕ/ክ/መ/ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 27905 ታህሳስ 05 ቀን 2011 ዓ.ም. የሰጠውን የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሳኔ በወ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ 195/ለ/2/ መሰረት ተሻሽሏል፡፡

2 .አመልካች የወንጀል ህግ አንቀጽ 556(1) የተመለከተውን በመተላለፍ ጥፋተኛ ነው በማለት በዚህ ጉዳይ የታሰሩበት ካለ ታሳቢ ሆኖ በሶስት ወር ቀላል እስራት እንዲቀጡ ተወስኗል፡፡

3 .በተሻሻለው የቅጣት ውሳኔ መሠረት እንዲፈፀም አመልካች ለሚገኙበት ማረሚያ ቤት ይጻፍ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

የሠበር መዝገብ ቁጥር 171403

ሕዳር 22 ቀን 2012 ዓ.ም

ዳኞች፡- እትመት አሠፋ

ጳውሎስ ኦርሺሶ

ፀሐይ መንክር

መላኩ ካሣዬ

እስቲበል አንዱዓለም

አመልካች/ቾች፡- መላኩ ያዕቆብ፡- አልቀረቡም፡፡

ተጠሪ/ዎች፡- የፌዴራል ጠቅላይ ዓቃቤሕግ፡- ዐ/ህግ ኤፍሬም ደመቀ ቀረቡ፡፡

መዝገቡ የተቀጠረው መርምሮ ፍርድ ለመስጠት ነው፡፡ በመሆኑም መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍርድ

ይህ የሰበር አቤቱታ ሊቀርብ የቻለው አመልካች በጠበቃው አማካኝነት የካቲት 14 ቀን 2011 ዓ.ም ጽፎባቀረበው የሰበርአቤቱታየስር ፍ/ቤቶች የአመልካችን የቅጣት ገደብ ጥያቄ ውድቅ በማድረግ የሰጡት ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለቱ ነው፡፡

የአሁን ተጠሪ በአመልካች ላይ በስር ፍ/ቤት ያቀረበው ክስ ይዘት በአጭሩ፡- አመልካች የወንጀል ሕግ አንቀጽ 543/2 ድንጋጌን በመተላለፍ በቀን 08/2010 ከጠዋቱ 4፡00 ሰዓት በንፋስስልክ ላፍቶ ክፍለከተማ ወረዳ 01 ልዩ ቦታው ሲፈን ተብሎ በሚጠራው አካባቢ የሰ.ቁ ኮድ 2-7769 አ.አ የሆነ ሞተር ሳይክል እያሽከረከረ ከቀኝ ወደ ግራ በማቋረጥ ላይ የነበሩትን ሟች ሸዋ ቀና ጥላሁን ቅድሚያ ሰጥቶ ማለፍ ሲገባው ሟችን ቅድሚያ በመከልከል በሞተር ሳይክሉ የፊት ለፊት አካል የግራ ጎናቸውን በመግጨት በሞተሩ አካል ሟችን ወደፊት ጎትተቶ በመውሰድ አስፓልት ላይ እንዲወድቁ በማድረግ ሟች ስለታማ በሆነ ግዑዝ ቁስ አካል በራሳቸው፣ በደረታቸው እና በሆዳቸው ላይ በደረሰባቸው ጉዳት ምክንያት በቀን 09/08/2010 ዓ.ም ሕይወታቸው እንዲያልፍ ያደረገ በመሆኑ በፈጸመው በቸልተኝነት ሰው መግደል ወንጀል ተከሷል የሚል ነው፡፡

አመልካች ክሱ ተነበለት ክሱን ሳይቃወም ወንጀሉን የፈጸመ እና ጥፋተኛ መሆኑን እና ቅድሚያ በመከልከል ሟችን የገጫቸው መሆኑን በመግለጽ የእምነት ክሕደት ቃሉን ሰጥቷል፡፡ ዓቃቤሕግ ባመነው መሠረት ጥፋተኛ ይባልልን በማለት በገለጸው መሠረትም ፍ/ቤቱ አመልካች ድርጊቱን የፈጸመ ስለመሆኑ ሙሉ በሙሉ  አምኗል በማለት በወንጀል ሕግ አንቀጽ 543/2/ ጥፋተኛ ብሎታል፡፡ ቅጣቱንም በቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 2/2006 መሠረት በማስላት በዓቃቤሕግ በኩል የቀረበ የቅጣት ማክበጃ ምክንያት የለም በማለት፤  አመልካች የዘወትር ባሕርይው መልካም መሆኑ፤ ክሱን ያመነ መሆኑ ፤ ከሟች ቤተሰቦች ጋር በመታረቅ ካሳ የከፈለ መሆኑን የሚያሳይ የእርቅ ስምምነት የቀረበ በመሆኑ፤ የቤተሰብ አስተዳዳሪ መሆኑ፤ በማሕበረሰቡ በጎ ተግባራት እና ልማት ተሳታፊ መሆኑ፤ አደጋው ከደረሰ በኋላ ሟችን ወደ ሕክምና ቦታ መውሰዱን እና ለመርማሪ ፖሊስ እጁን መስጠቱ በድምሩ ስድስት የቅጣት ማቅለያ ምክንያቶችን በመያዝ በአንድ ዓመት ከሁለት ወር ቀላል እስራት እና በብር 500 መቀጮ እንዲቀጣ የወሰነ ሲሆን የገደብ ጥያቄውን በሚመለከት ግን ከአደጋው አሳሳቢነት አንጻር ተቀባይነት የለውም በማለት ወድቅ አደርጎታል፡፡ አመልካች ይህን ውሳኔ በመቃወም ለፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አቤቱታ ያቀረበ ቢሆንም አቤቱታው ተቀባይነት አላገኘም፡፡

የሰበር አቤቱታው የቀረበው ይህን ውሳኔ በመቃወም መሠረታዊ የሕግ ስሕተት ተፈጽሞበታል በሚል ሲሆን ይዘቱም፡- አመልካች ፖሊስ ጣቢያም ሆነ ፍርድ ቤት በመቅረብ ቃሌን በማመን ሰጥቻለሁ፤ መጸጸቴንም አሳይቻለሁ፤ የሟችን ሕይወት ለማትረፍ ኮንትራት ታክሲ ይዤ ወደ ሕክምና ቦታ ወስጃለሁ፤ አደጋው ከደረሰ በኋላም ሞተር ሳይክሉን በመሸጥ የሟችን ቤተሰብ ክሻለሁ፤ አመልካች ባለትዳር ስሆን ቅጣቱ በተላለፈበት ወቅትም ባለቤቴ የ 9 ወር እርጉዝ ነበረች፤  የሶስት ልጆች አባት እና የቤተሰብ አስተዳዳሪም ነኝ፤ የወንጀል ሪከርድ የለኝም፤ ከሟች ቤተሰቦች ጋርም የታረቅኩ ሲሆን በገደብ ብለቀቅ የገደቡን ሁኔታ በሚገባ እንደሚሟላ አረጋግጫለሁ፡፡ በመሆኑም የስር ፍ/ቤቶች አመልካች ቅጣቱ እንዲገደብ ያቀረብኩትን ጥያቄ ውድቅ በማድረግ የሰጡት ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል የሚል ነው፡፡
የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ አመልካች የተከሰሰበትን ወንጀል አምኖ የጥፋተኝነት ውሳኔ በተሰጠበት፤ ከሟች ቤተሰብ ጋር እርቅ ፈጽሞ በካሰበት ሁኔታ የስር ፍ/ቤት የቅጣት ገደብ ጥያቄውን አሁን ካለው የአደጋው አሳሳቢነት አንጻር ተቀባይነት የለውም በሚል ያለፈበትን አግባብነት በወንጀል ሕግ ቁጥር 192 እና ተከታይ ድንጋጌዎች እና ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ..መ.ቁ 94404፤85596 እና 34280 ከሰጠው አስገዳጅ የሕግ ትርጉም ጋር በማገናዘብለመመርመር ሲባል ጉዳዩ በዚህ ችሎት እንዲታይ ተደርጓል፡፡ ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎም ግራቀኙ በጽሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

የተጠሪ መልስ ይዘት በአጭሩ፡- የስር ፍ/ቤት ከወንጀሉ አፈጻጸም እና እየደረሰ ካለው የትራፊክ አደጋ አንጻር የአመልካች ቅጣት መታገድ የጥፋተኛውን ጸባይ ለማረም በቂ አይደለም፤ ሌሎችንም አያስተምርም የሚል መደምደሚያ ላይ ደርሷል፤ አመልካቾ ከፈጸመው የወንጀል ድርጊት ጋር በተመሳሳይ ሁኔታ ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ.መ.ቁ 153597 የቅጣት መገደብ እና አለመገደብ ነባራዊ ሁኔዎች ታይተው የወንጀል ሕግ ግብን ከማስፈጸም አንጻር ሲሆን እንዲሚገባ አስገዳጅ የሕግ ትርጉም የሰጠበት በመሆኑ የስር ፍ/ቤት አሁን ካለው የአደጋው አሳሳቢነት አንጻር ቅጣቱ ሊገደብ አይደገባም በማለት የሰጠው ውሳኔ በአግባቡ ስለሆነ ሊጸና ይገባል የሚል ነው፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ በአጭሩ ከላይ የተገለጸዉ ነው፡፡ ይህ ችሎትም በሰበር አጣሪው ችሎት ያስቀርባል ተብሎ የተያዘውን ጭብጥ ከግራቀኙ ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸው ሕጎች ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው መርምሮታል፡፡

አመልካች የቀረበበትን ክስ ሙሉ በሙሉ ያመነ እና በድርጊቱም መጸጸቱን እና ጥፋተኛ ሊባል የሚገባ መሆኑን በመግለጽ የእምነት ክሕደት ቃሉን የሰጠ መሆኑን፤ ፍ/ቤቱም አመልካች ባመነው መሠረት በወንጀል ሕግ አንቀጽ 543/2 ጥፋተኛ ያለው መሆኑን፤ አመልካች አደጋው ከደረሰ በኂላ ሟችን ወደ ሕክምና ቦታ የወሰደ እና ለመርማሪ ፖሊስ እጁን የሰጠ መሆኑ፤ የዘወትር ባሕርይው መልካም መሆኑ፤ የቤተሰብ አስተዳዳሪ መሆኑ፤ በማሕበረሰቡ በጎ ተግባራት እና ልማት ተሳታፊ መሆኑ፤ ከሟች ቤተሰቦች ጋር በመታረቅ ካሳ የከፈለ መሆኑን የሚያሳይ የእርቅ ስምምነት የቀረበ በመሆኑ፤ የሟች ባለቤትም በችሎት ቀርበው ከአመልካች ጋር የታረቁ መሆኑን፤ አመልካች ሁሉንም እርዳታ ያደረገላቸው እና አሁንም እያገዛቸው ያለ መሆኑን በመግለጽ ቃላቸውን የሰጡ መሆኑን በስር ፍ/ቤት ከተረጋገጠው ፍሬነገር መገንዘብ ይቻላል፡፡

የስር ፍ/ቤት የአመልካችን የገደብ ጥያቄ ውድቅ ያደረገው አመልካች ቅጣቱ እንዲገደብ ያቀረበው ምክንያት ቅጣት ስለሚገደብባቸው ሁኔታዎች በሕጉ የተቀመጡትን መስፈርቶች የሚያሟሉ መሆን አለመሆኑን መዝኖ ሳይሆን የአመልካች የቅጣት ገደብ ጥያቄ ከአደጋው አሳሳቢነት አንጻር ተቀባይነት የለውም በማለት መሆኑን ከውሳኔ ይዘት መገንዘብ ችለናል፡፡

በመሠረቱ የወንጀል ሕጉ ዓላማ ወንጀል እንዳይፈጸም ማድረግ ሲሆን ይህንንም የሚያደርገው ስለወንጀሎች እና ስለቅጣታቸው በቅድሚያ ማስጠንቀቂያ በመስጠት፤ ማስጠንቀቂያነቱ በቂ ባልሆነ ጊዜ ደግሞ ወንጀል ፈጻሚዎች ተቀጥተው ሌላ ወንጀል ከመፈጸም እንዲቆጠቡ እና ለሌሎች ማስተማሪያ እንዲሆኑ ወይም እንዲታረሙ በማድረግ እንደሆነ ከወንጀል ሕጉ ዓላማ እና ግብ መገንዘብ ይቻላል፡፡ ቅጣት ሲገደብ የፍርዱ ውሳኔ በወንጀለኞች መዝገብ ላይ ተመዝግቦ ከሌላው ውጤት ጋር ነዋሪ የሚሆን በመሆኑ ቅጣትን መገደብ በወንጀለኛው ላይ ቅጣት እንዳይፈጸም የማድረግ ውጤት ብቻ ያለው ሳይሆን

ወንጀለኛው ዳግም ጥፋት ከመፈጸም እንዲታቀብ የማድረግ ውጤት ስላለው ቅጣትን መገደብ የወንጀል ሕጉ ዓላማ እና ግብ ከሚሳካባቸው መንገዶች አንዱ ነው፡፡

ቅጣት ሊገደብ የሚችለውም ጥፋተኛ የተባለን ሰው ለጥፋቱ መነሻ የሆኑትን ምክንያቶችን በጠቅላላው በመመልከት በጥፋተኛው ላይ የተወሰነውን ቅጣት ለጊዜው በገደብ እንዲታገድ በማድረግ የወንጀለኛውን ጠባይ ለማረምና ለማሻሻል እንዲሁም ወደ መደበኛ ማህበራዊ ኑሮው ለመመለስ ጠቃሚ መሆኑ በታመነ ጊዜ ስለመሆኑ የቅጣት ገደብን አስመልክቶ ከተደነገጉት የወንጀል ሕጉ ድንጋጌዎች መገንዘብ ይቻላል፡፡ ይህንንም ተፈጻሚ ለማድረግ ፍ/ቤቶች ቅጣትን ለመገደብ የሚያስችሉ የተለያዩ ሁኔታዎችን ከግምት ውስጥ ማስገባት እንዳለባቸው፤ እነዚህም ሁኔታዎች ወንጀለኛው ቀድሞ ያልተቀጣ ሆኖ ጠባዩም አደገኛነት እንደሌለው የሚታመንበት እንደሆነ፤ጥፋቱ በመቀጮ፤ በግዴታ ስራ ወይም ከሶስት አመት የማይበልጥ ቀላል እስራት የሚያስቀጣ እንደሆነ ፍርድ ቤቱ ጥፋተኝነቱን ካረጋገጠ በኋላ ለወደፊት ጠባዩን ለማረም እንደሚችል እምነት ሊጣልበት የሚችል መሆኑና በዚህ ውሳኔ ብቻእስከ መጨረሻው ሊሻሻል የሚችል መሆኑን ‘ያመነበት’ እንደሆነ፤ እንዲሁምጥፋተኛው አስቀድሞ የተፈረደበት ቢሆንም ባይሆንም የተፈረደበትን ቅጣት ከመፈፀሙ በፊት ለተወሰነ ጊዜ ቅጣቱ ታግዶለት አመሉ ቢፈተን ሁለተኛ ጥፋት ከማድረግም የሚታገድ መሆኑናስለጠባዩም መሻሻል አንድ ዕኑ ማስጠንቀቂያ ብቻ የሚበቃ መሆኑ ፍርድ ቤቱ ያመነበት እንደሆነ ቅጣቱ ከአፈፃፀም ታግዶ እንዲቆይ ሊያዝ የሚችል ስለመሆኑ ከወንጀል ሕግ አንቀጽ 192 እና ተከታይ ድንጋጌዎች ይዘት መገንዘብ ይቻላል፡፡

በሌላ በኩል በጥፋተኛው ላይ የተወሰነው ቅጣት እንዳይገደብ ሊያደርጉ የሚችሉ በሕጉ የተቀመጡ ሁኔታዎች ያሉ መሆኑን፤እነኚህም ሁኔታዎች ጥፋተኛው ከዚህ በፊት የጽኑ እሥራት ቅጣት ወይም ከሦስት ዓመት የሚበልጥ ቀላል እሥራት ቅጣት ተፈርዶበት እንደሆነ እና እንደገናም በተከሰሰበት ወንጀል ከእነዚህ ቅጣቶች አንዱ የሚወሰንበት እንደሆነ ወይም ጥፋተኛው ከዚህ ቀደም ያልተቀጣ ሆኖ በተከሰሰበት ወንጀል ከአምስት አመት የበለጠ የጽኑ እሥራት ቅጣት የሚፈረድበት እንደሆነ ነው በማለት የወንጀል ሕጉ አንቀጽ 194 ድንጋጌ ላይ በዝርዝር ተመልክቷል፡፡ በሕጉ ከተመለከቱት ከእነኚህ ሁኔታዎች ውጪ የወንጀሉ ከባድነት ወይም ጥፋተኛው ያደረሰው አደጋ አሳሳቢነት ቅጣት እንዲገደብ ለማድረግ የሚያስችል ምክንያት ነው ተብሎ በሕጉ ላይ አልተገለጸም፡፡ በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 196/2 የወንጀሉ ከባድነት / the gravity of the crime /፤ በወንጀል ድርጊት መደጋገም ሊያደርስ የሚችለውን ጉዳት እና በጥፋተኛው ላይ ሊጣልበት የሚችለው እምነት ከግምት ውስጥ መግባት አለበት የሚባለው ፍ/ቤቱ ቅጣቱ እንዲገደብ አቋም ከያዘ በኋላ ቅጣቱ ተገድቦ የሚቆይበትን የፈተና ጊዜ ለመወሰን / ….. to fix the probation period ….. / እንጂ ጥፋተኛው ፈጽሞታል ከተባለው ወንጀል ወይም አድርሶታል ከተባለው አደጋ ጋር እየተገናዘበ ቅጣትን ለመገደብ ሊመዘን ይገባል ተብሎ እንደመስፈርት የተቀመጠ አይደለም፡፡

በመሠረቱ ከባድ ወንጀሎች ከፍተኛ ቅጣት የሚያስከትሉ ናቸው፡፡ የወንጀል ሕጉ አንቀጽ 194/1/ለ ድንጋጌም ይህንኑ ታሳቢ በማድረግ ጥፋተኛው አሁን በተከሰሰበት ወንጀል ከአምስት ዓመት የበለጠ የጽኑ እሥራት ቅጣት የሚፈረድበት እንደሆነ ቅጣትን ማገድ አይቻልም በማለት በግልጽ መደንገጉ ከመነሻውም ቢሆን ከባድ ወንጀል የፈጸመ ወንጀለኛ በሚጣልበት ከፍተኛ የቅጣት መጠን ምክንያት ቅጣት ሊገደብለት የማይችል በመሆኑ በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 196/2 ላይ የተገለጸው 'የወንጀሉ ክብደት' የሚለው ቃል ለፈተናው ጊዜ አወሳሰን ታሳቢ የሚደረግ መሆኑን የሚያሳይ እንጂ ጥፋተኛው የፈጸመው ወንጀል አሳሳቢነትን የሚመለከት አለመሆኑን እና ቅጣቱን ለመገደብበመመዘኛነት የተቀመጠ አለመሆኑን የሚያሳይ ነው፡፡

በሌላ በኩል በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 197 የተመለከቱት ቅድመ-ሁኔታዎች ፈተና የሚሰጥባቸውን ሁኔታዎች እንደሆኑ ከድንጋጌው ርዕስ መገንዘብ የሚቻል ሲሆን እነኚህ ሁኔታዎች መሟላት አለመሟላታቸው ሊረጋገጥ የሚችለው ፍ/ቤቱ ከተከሳሹ የቀድሞ ታሪክ፣ የጠባዩ እና የዓመሉ አካሄድ በመነሳት ቅጣቱን መገደብ እንዳለበት ሲያምን እና ጥፋተኛው በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 197 ላይ የተመለከቱትን ቅድመ-ሁኔታዎች እንደሚያሟላ ማረጋገጫ እንዲሰጥ በማድረግ እንደሆነ ከወንጀል ሕጉ አንቀጽ 192፣196/1 እና 197 ድንጋጌዎች ጣምራ ንባብ መገንዘብ ይቻላል፡፡ ጥፋተኛው በድንጋጌው የተመለከቱትን ቅድመ- ሁኔታዎች ማሟላት አለሟሟላቱን ማረጋገጥ የሚቻለውም ጥፋተኛው ራሱ በራሱ ተነሳሽነት በሕጉ የተመለከቱትን ቅድመሁኔታዎች ያሟላ ሆኖ በተገኘ ጊዜ ወይም ፍ/ቤቱ ጥፋተኛው በሕጉ የተቀመጡትን ቅድመሁኔታዎች እንዲያሟላ እድል በሰጠው ጊዜ ነው፡፡

ፍ/ቤቱ በጥፋተኛው ላይ የሚጣለውን ቅጣት ለጊዜው ማገድ ለወደፊቱ ጥፋቱን ለማረም እንደሚችል ሊያምን ወይም ላያምን የሚችለው የጥፋተኛውን የቀድሞ ታሪኩ፣ የጠባዩ እና የዓመሉ አካሄድ አስመልክቶ በችሎቱ የተረጋገጡትን እውነታዎች መነሻ በማድረግ ሲሆን ፍ/ቤቶች በሕግ እና በተገቢ ምክንያት የተደገፈ ውሳኔ መስጠት ያለባቸው ከመሆኑ አመልካች ቅጣቱን ለማስገደብ ያቀረባቸው ምክንያቶች ፍ/ቤቱን የሚያሳምኑ ናቸው ወይም አይደለም ለማለት ሕግን መሠረት በማድረግ እና አግባብነት ያለውን ምክንያት በመስጠት ሊሆን ይገባል፡፡

በተያዘዉ ጉዳይ አመልካች የቀረበበትን ክስ ሙሉ በሙሉ ያመነ እና በድርጊቱም መጸጸቱን እና ጥፋተኛ ሊባል የሚገባ መሆኑን በመግለጽ የእምነት ክሕደት ቃሉን የሰጠ መሆኑን፣ ፍ/ቤቱም አመልካች ባመነው መሠረት በወንጀል ሕግ አንቀጽ 543/2 ጥፋተኛ ያለው መሆኑን፣ አመልካች አደጋው ከደረሰ በኂላ ሟችን ወደ ሕክምና ቦታ የወሰደ እና ለመርማሪ ፖሊስ እጁን የሰጠ መሆኑ፣ የዘወትር ባሕርይው መልካም መሆኑ፣ የቤተሰብ አስተዳዳሪ መሆኑ፣ በማሕበረሰቡ በጎ ተግባራት እና ልማት ተሳታፊ መሆኑ፣ ከሟች ቤተሰቦች ጋር በመታረቅ ካሳ የከፈለ መሆኑን የሚያሳይ የእርቅ ስምምነት የቀረበ በመሆኑ፣ የሟች ባለቤትም በችሎት ቀርበው ከአመልካች ጋር የታረቁ መሆኑን፣

አመልካች ሁሉንም እርዳታ ያደረገላቸው እና አሁንም እያገዛቸው ያለ መሆኑን በመግለጽ አረጋግጠዋል፡፡ እነኚህ ሁኔታዎች የተከሳሹን የቀድሞ ታሪክ፤ የጠባዩን እና የዓመሉን አካሄድ ለመመዘን የሚያስችሉ እና ቅጣቱ ቢገደብ የአመልካችን ጠባይ ለማረምና ለማሻሻል እንዲሁም ወደ መደበኛ ማህበራዊ ኑሮው ለመመለስ የሚያስችሉ አሳማኝ ሁኔታዎች ናቸው፡፡

አመልካች ቅጣቱ እንዲገደብለት ያቀረባቸው ምክንያቶች የአመልካቹን የቀድሞ ታሪክ፤ የጠባዩን እና የዓመሉን አካሄድ ለመመዘን የሚያስችሉ አሳማኝ እና በአመልካች ላይ የተጣለው ቅጣት ታግዶ ቢቆይ ዳግም ጥፋት ከመፈጸም እንዲቆጠብ ለማድረግ የሚያስችሉ ሁኔታዎች ሆነው ሳለ ቅጣቱን መገደብ ሲገባው በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 194 ቅጣት እንዳይገደብ ለማድረግ የሚያስችሉ ሁኔታዎች ውስጥ ያልተቀመጠውን መስፈርት መሠረት በማድረግ የአመልካች የቅጣት ገደብ ጥያቄ ከአደጋው አሳሳቢነት አንጻር ተቀባይነት የለውም በማለት የአመልካችን የገደብ ጥያቄ ውድቅ በማድረግ የሰጠው ውሳኔ በወንጀል ሕጉ ቅጣት ስለሚገደብባቸው የተቀመጡትን ቅድመሁኔታዎች ያላገናዘበ እና መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ ስለሆነም የስር ፍቤቶች በአመልካች ላይ ያስተላለፉት የአንድ ዓመት ከሁለት ወር ቀላል እስራት ቅጣት በሁለት ዓመት ገደብ ይቆይ በማለት በወንጀል ሕግ አንቀጽ 192 እና 197/1 መሠረት ወስነናል፡፡

**ውሳኔ**

የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ 221242 ታሕሳስ 04 ቀን 2011 ዓ.ም በአመልካች ላይ ያስተላለፉትን የቅጣት ውሳኔ በማጽናት አፈጻጸሙን በሚመለከት ግን ከላይ በፍርድ ሐተታው ላይ በተገለጸው ምክንያት ቀሪ እስራት ሳይፈጸም ለሁለት ዓመት እንዲገደብ በማለት ወስነናል፡፡

**ትዕዛዝ**

አመልካች በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 197 መሠት የብር 1500 / አንድ ሺህ አምስት መቶ ብር /መተማመኛ ዋስትና እንዲያሲዝ ታዟል፡፡ይኸው ሲፈጸም የሚመለከተው ማረሚያ ቤት አመልካችን ከእሥር እንዲለቅ ታዟል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ይመለስ

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ሠ/ኃ

የሰ/መ/ቁ. 177216

ሕዳር 30 ቀን 2012 ዓ.ም

ዳኞች፡- መዓዛ አሸናፊ

ሰለሞን አረዳ

እትመት አሠፋ

ጳውሎስ ኦርሺሶ

ፀሐይ መንክር

አመልካች፡- አቶ ገብርኤል ፓራቶሪ አንቶንዮ

ተጠሪ፡- የፌዴራል ጠቅላይ ዐቃቤ ህግ

መዝገቡ ለምርመራ ለ23/4/2012 ዓ.ም የተቀጠረ ሲሆን ከቀጠሮ በፊት ቀርቦ ሊመረመር የቻለው የአመልካች ጠበቃ ህዳር 09 ቀን 2012 ዓ.ም ጽፎ ባቀረበው አቤቱታ አመልካች በከፍተኛ የደም ግፊት ህመም በመሰቃየት ላይ የሚገኝ እና ባለቤቱም የካንሰር ህመም ታማሚ በመሆኗ ምክንያት ህጻናት ልጆቻቸው በችግር ውስጥ የሚገኙ መሆኑን በመግለጽ ጉዳዩ ታይቶ ውሳኔ እስኪያገኝ ድረስ በዋስ እንዲቆዩ እንዲፈቀድለት በመጠየቁ ነው፡፡ በዚህ ምክንያት ለምርመራ የተያዘው ቀነ ቀጠሮ ተሰብሮ ጉዳዩ ተመርምሮ ቀጥሎ ያለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍርድ

ጉዳዩ ለዚህ ሰበርችሎት ሊቀርብ የቻለው የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በወንጀል መዝገብ ቁጥር 003364 በቀን 20/02/2011 ዓ.ም በሰጠው የጥፋተኝነት ውሳኔ፣እንዲሁም በ 10/03/2011 ዓ.ም በሰጠው የቅጣት ውሳኔ እና የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በወንጀል መዝገብ ቁጥር166293 ሚያዚያ 25 ቀን 2011 በቀን 5/10/2010 ዓ.ም በሰጠው ውሳኔ ላይ መሠረታዊ የህግ ስህተት ተፈጽሟል በማለት አመልካች እንዲታረምላቸው ግንቦት 12 ቀን 2011 ዓ.ም የተጻፈ አቤቱታ በማቅረባቸው ነው፡፡

የነገሩ አመጣጥ የወንጀል ጉዳይን የሚመለከት ነው፡፡የአሁን ተጠሪ ግንቦት 28 ቀን 2009 ዓ.ም ያቀረበው የክስ ይዘትም፡-የሥር ተከሳሽ/የአሁን አመልካች/ ኢትዮጵያዊያን ዜጎችን ወደ ውጭ ሀገር ለመላክ የሚያስችል ህጋዊ የሥራ ፈቃድ ሳይኖረው ወ/ሮ እመቤት ይልማ ገ/የሱስ የተባለችውን የግል ተበዳይ ወደውጭ ሀገር ዱባይ እንደሚልካት በመግለጽ ከምትኖርበት አዲስ አበባ ከተማ ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክፍለ ከተማ ወረዳ 12 ነዋሪ የሆነችውን ፓስፖርት፣ሁለት ጉርድ ፎቶግራፍ እና የህክምና የምርመራ ውጤት እንደሚያስፈልጋት በመግለጽ ስምንት ሺህ ብር እንደሚያስፈልግ በመነጋገር ሂደቱን

ካስጨረሰ በኃላ ህዳርወር 2008 ዓ.ም ስልክ በመደወል ቪዛሽ መጥቷል ታህሳስ 3 ቀን 2008 ዓ.ም ከንጋቱ 12፡.00 ሰዓት ወደ ዱባይ በራራ ስለምታደርግ አየር መንገድ መገኘት እንዳለባት ከገለጸላት በኃላ የግል ተበዳይም አሁን አልተዘጋጀሁም፣ለአንድ ሳምንት አራዝምልኝ በማለት በጠየቀችው መሠረት አራዝሞላት የበረራው ቀን ሳይደርስ ቀደም ብላ የግል ተበዳይ ከ2ኛ እና ከ3ኛ የዐቃቤ ህግ ምስክሮችጋር በመሆን ወደተከሳሽ የባለቤቱ እህት ሜሮን ኃይሉ መኖሪያ ቤት ቀኑን በትክክል በማያስታውሱበት ታህሳስ ወር 2008 ዓ.ም በመሄድ የመላኪያውን ገንዘብ በመስጠት የአየር ቲኬትና ቪዛ ተቀብ ለው ከተመለሱ በኃላ በታህሳስ 10 ቀን 2008 ዓ.ም ከንጋቱ 12፡00 ሰዓት ቦሌ ዓለም አቀፍ አየር መንገድ በኩል ወደ ዱባይ ሀገር እንድት ሄድ ካደረገ በኃላ ዱባይ ሀገር አሠሪዋ የግል ተበዳይ ጭንቅላቷ ላይ በብረትድስት በመምታት የፈነከተቻት ና ያቆሰለቻት፣ሁለት እጆዋን በቢላዋ የወጋቻት ና እንዲቆስል ያደረገች በመሆኑ፣እንዲሁም የሠራችበትን የአራት ወር ደሞዝዋንም ያልከፈለቻት ና ከፍተኛ ስቃይ እና ጉዳት እንዲ ደርስባት ያደረገው በመሆኑ በፈጸመው በህገወጥ መንገድ ኢትዮጵያዊን ለሥራ ወደ ውጭ ሀገር መላክ ወንጀል ተከሷል የሚልነው፡፡

የአሁን አመልካች ፍርድ ቤት ቀርቦ የእምነት ክህደት ሲጠየቅ የወንጅል ድርጊቱን አልፈጸምኩም፣ ጥፋተኛ አይደለሁም በማለት አስመዝግቧል፡፡ ዐቃቤ ህግ የሰው ምስክሮች አቅርቦ አሰምቷል፡፡ ፍርድ ቤቱም ተከሳሽን እንዲከላከል ብይን ሰጥቶ መከላከያ ምስክሮችን አቅርቦ አሰምቷል፡፡

ጉዳዩን የተመለከተው የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የግራቀኙን ክርክር ና ማስረጃዎችን መርምሮ ተከሳሽ በበኩሉ በጣቢያ የሰጠሁትን የእምነት ቃል ተገድጄ የሰጡት በመሆኑ ፍርድቤቱ እንዲያይልኝ ያለውን በሚመለከት ቃሉን ተገዶ የሰጠው ለመሆኑ በማስረጃ አስደግፎ ያላቀረበ በመሆኑ ና በእለቱ በቦታው አልነበረም የሚለው መከራከሪያ ዐቃቤ ህግ ካቀረቡት ማስረጃዎች ጋር ሲመዘን ተከሳሽ በዐቃቤ ህግ የቀረበበትን ክስ በመከላከያ ማስረጃ ተከላክሏል የሚያስብል በቂ ምክንያት ያላገኘን በመሆኑ አልተከላከለም ብለን ፈርደናል፡፡ ስለዚህ ተከሳሽ በ1996 ዓ.ም የወጣውን የወንጀል ህግ ቁጥር 598 (2) ሥር የተመለከተውን ድንጋጌ በመተላለፍ በህገ ወጥ መንገድ ኢትዮጵያዊያንን ለሥራ ወደ ውጭ አገር መላክ ወንጀል በመፈጸሙ በወንጀለኛ መቅጫ ህግ ሥነ ሥርዓት ቁጥር 149(1) መሰረት ጥፋተኛ ነው ሲል ወስኗል፡፡ ቅጣትን በተመለከተ ፍርድ ቤቱ የግራቀኙን የቅጣት አስተያየት ተቀብሏል፡፡ ዐቃቤ ህግ ያቀረበ የቅጣት ማቅለያ የለም፡፡ ተከሳሽ የወንጀል ሪከርድ የሌለ መሆኑን፣የቤተሰብ አስተዳዳሪ መሆኑን፣በተለያዩ የበጎ አድራጎት ተግባራት እና ማሕበራዊ ተሳትፎ ያበረከተውን፣እንዲሁም በቤተክርስቲያን ያገለገለበትን አራት የቅጣት ማቅለያዎችን ፍርድ ቤቱ ተቀብሏል፡፡ፍርድ ቤቱ የእሥራት መነሻ እርከን 22 ይዟል፡፡ከዚህ ላይ አራት የቅጣት ማቅለያን በመቀነስ እርከን 18 ላይ እንዲያርፍ ካደረገ በኃላ ተከሳሽ በ3 ዓመት ከ7 ወር /ሶስት ዓመት ከሰባት ወር/ ጽኑ እሥራት እናብር 500. 00 /አምስት መቶብር/ ሊቀጣ ይገባል በማለት በወንጀለኛ መቅጫ ህግ ሥነ-ሥርዓት ቁጥር 149 (5) መሠረት የቅጣት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

የአሁን አመልካች በጥፋተኝነትም ሆነ በቅጣት ውሳኔ ላይ ቅር በመሰኘት ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ አቅርቧል፡፡የይግባኝ ሰሚው ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኙን ተቀብሎ ግራቀኙን ካከራከራቸው በኃላ የሥር ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሳኔ የሚያስለውጥ በቂ ና አሳማኝ የሆነ የፍሬነገርም ሆነ የህግ ስህተት የሌለ ሆኖ ስላገኘነው በወንጀለኛ መቅጫ ህግ ሥነሥርዓት ቁጥር 195 (2) (ለ) (2) መሠረት አጽንተናል በማለት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

ይህ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም የጥፋተኝነት እንዲሁም የቅጣት ውሳኔውን በመቃወም ነው፡፡የአመልካች ጠበቃ ግንቦት 12 ቀን 2011 ዓ.ም የተጻፈ ዝርዝር የቅሬታ ነጥቦችን አቅርቧል፡፡ይዘቱም በአጭሩ የተጠሪ ምስክሮች ቃል እርስ በእርሱ የሚጋጭ ነው፣አመልካች ባቀረባቸው ማስረጃ በሚገባ ተከላክሏል፡በተጠሪ በኩል ተጠቅሶ የቀረበው ክስ የወንጀል ህግ ቁጥር 598 (2) ድንጋጌን በመተላለፍ የወንጀል ድርጊት ፈጽሟል የሚል ሆኖ በግል ተበዳይ ላይ የደረሰው የአካል ጉዳት ስለመድረሱ የቀረበ የህክምና ማስረጃ የለም፣ክስ በቀረበበት ፍርድ ቤትም በግል ተበዳይ ላይ የደረሰው ጉዳት ተመርምሮ እንዲቀርብ አመልካች ቢጠይቅም ፍርድ ቤቱም ያለአግባብ ሳይቀበል ቀርቷል፡፡በግል ተበዳይ ላይ የደረሰው ጉዳት በማስረጃ ባልተጠራበት ይህ ድንጋጌ ተጠቅሶ ክስ መቅረቡ የፍትህ መጓደል አምጥቷል፡፡በግል ተበዳይ ላይ የአካል ጉዳት አለመድረሱ ቢረጋገጥ በአመልካች ላይ የሚጠቀሰው የአንቀጹ ንዑስ አንቀጽ 2 መሆኑ ቀርቶ ንዑስ አንቀጽ 1 ይሆን ነበር፡፡በዚህ ምክንያት በአመልካች ላይ የተጣለው ቅጣት ይቀንስ ነበር ማለት ነው፡፡ስለሆነም የግል ተበዳይ የአካል ጉዳት ደርሶባታል የሚያስብል የማያጠራጥር ማስረጃ በዐቃቤ ህግ በኩል ስላልቀረበ በአመልካች ላይ ተፈጻሚ መሆን የሚገባው ድንጋጌ አንቀጽ 598 (1) ሆኖ፣ቅጣቱ በዚህ አንቀጽ መሠረት ታሳቢ ሊደረግ ይገበዋል ካለ በኃላ የሚጠይቀው ዳኝነት በማለት 1ኛ/ የሥር ችሎቶች የሰጡት የጥፋተኝነት ውሳኔ ውድቅ ተደርጎ አመልካች በነፃ ይሰናበትልን ዘንድ እና እናመለክታለን፡፡ 2ኛ/ የሰበር ሰሚ ችሎቱ የጥፋተኝነት ውሳኔውን የሚያፀናው ከሆነ ተፈጻሚ የሚሆነው አንቀጽ ግን 598 (1) ነው ካለ በኂላ፣በሥር ፍርድ ቤት ታሳቢ የተደረጉትን 4 (አራት) የቅጣት ማቅለያዎች ግምት ውስጥ አስገብቶ ውሳኔውን ይቀንስልን ዘንድ እናመልክታለን የሚል ነው፡፡

የሰበር አቤቱታው ተመርምሮ የሥር ፍርድ ቤት የግል ተበዳይ የደረሰባት ጉዳት ስለመኖሩ ባልተረጋገጠበት ሁኔታ የአሁኑ አመልካችን በወንጀል ህግ ቁጥር 598 (2) ሥር ጥፋተኛ በማለት የወሰነበት አግባብነት ከወንጀል ህግ ቁጥር 598 (1) አንጻር መጣራት ያለበት መሆኑ ስለታመነበት ጉዳዩ ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ ተደርጓል፡፡

ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎለት ቀርቦ በቀን 3/2/2012 ዓ.ም የተጻፈ ዝርዝር መልስ ሰጥቷል፡፡የመልሱ ይዘትም በአጭሩ ዐቃቤ ህግ ባቀረባቸው ማስረጃዎች የግል ተበዳይ በአመልካች ወደ ውጭ አገር የተላከች መሆኑን፣ከተላከች በኃላም የሰብአዊ መብት ጥሰት እና የአካል ጉዳት እንደደረሰባት አስረድቷል፡፡

በአመልካች በኩል የቀረቡት የመከላከያ ማስረጃዎች ይህን ያስተባበሉ አይደሉም፡፡ አመልካች ከቀረቡት ማስረጃዎች አንጻር በወንጀል ህግ አንቀጽ 598 (2) ጥፋተኛ መባሉ አግባብ ነው፡፡ ስለሆነም ሰበር ሰሚ ችሎቱ የሥር ፍርድ ቤቶችን ውሳኔ አግባብ ነው በማለት እንዲያፀናልን የሚል ነው፡፡

የአመልካች ጠበቃም ጥቅምት 12 ቀን 2012 ዓ.ም በሰጠው የመልስ መልስ በግል ተበዳይዋ ላይ ደረሰ የተባለው የአካል ጉዳት ምሆነ ሌላ የሰብአዊ መብት ጥሰት የግል ተበዳይዋ ከሰጠችው ምስክርነት ቃል በስተቀር በሌላ በምንም ዓይነት ማስረጃ አልተረጋገጠም፡፡የግል ተበዳይዋ የምትሰጠው ቃል ደግሞ ብቻውን ተወስዶ አመልካችን በ ንዑስ ቁጥር 2 ሥርተጠያቂ ሊያደርገው አይችልም፡፡ሌላው ቢቀር በግል ተበዳይዋ ላይ የአካል ጉዳት የደረሰ መሆን አለመሆኑ በህክምና ማስረጃ ሊረጋገጥ እየቻለ የሥር ፍርድ ቤት የህክምና ምርመራ ሊደረግ አይገባም በማለት የዐቃቤ ህግ ምስክሮች የሰጡትን የምስክርነት ቃል ብቻ መሰረት በማድረግ ውሳኔ መስጠቱ አግባብነት የለውም፡፡በመሆኑም የዐቃቤ ህግ ምስክሮች የሰጡት ቃል ዐቃቤ ህግ የወንጀል ህግ ቁጥር 598 (2) 'ን' መሰረት በማድረግ የመሠረተውን ክስ የሚደግፍ ባለመሆኑ አመልካች ልጠየቅ የሚገባው በወንጀል ህግ ቁጥር 598 (1) ሥር ነው፡፡ ስለዚህ ችሎቱ ይህንን ተገንዝቦልን አመልካችን ጥፋተኛ ሊባል የሚገባው በአንቀጽ 598(1) ሥር ነው እንዲባልልን እናመለክታለን በማለት ተከራክሯል፡፡

የነገሩ አመጣጥና የክርክሩ ሂደት ከላይ እንደ ተገለጸው ሲሆን ጉዳዩን የሰበር አጣሪው ከያዘው ጭብጥ አንጻር መርምረናል፡፡ የፍሬ ነገር ክርክርን መሠረት በማድረግ ከማስረጃ ጋር ተያይዞ የጥፋተኝነት ውሳኔው ተገቢ አይደለም ተብሎ የቀረበውን የአመልካችን ቅሬታ የሰበር አጣሪው በጭብጥነት አልያዘውም፡፡ ይህ ችሎትም ይህ ተገቢ እንደሆነ ያምናል፡፡ ነገር ግን የሰበር አጣሪው የያዘውን የህግ መከራከሪያ ነጥብን በተመለከተ በሥር ፍርድ ቤት እና በዚህ ችሎት የተነሳውን ክርክር እንዲሁም ተያይዞ የቀረበውን ውሳኔ እና አግባብነት ያለውን ህግ መሠረት በማድረግ ተመልክተናል፡፡ የወንጀል ህግ አንቀጽ 598 (1) ማንም ሰው ፈቃድ ሳይኖረው ወይም በማናቸውም ሌላ ህገ ወጥ መንገድ ኢትዮጵያዊ ዜጋን ለሥራ ወደ ውጭ አገር የላከ እንደሆነ፣ከአምስት ዓመት እስከ አሥር ዓመት ሊደርስ በሚችል ጽኑ እሥራት ና ከሃያ አምስት ሺህ ብር በማይበልጥ መቀጮ ይቀጣል ሲል ይደነግጋል፡፡በዚህ ድንጋጌ መሠረት ፈቃድ ሳይኖር ወይም በህገወጥ መንገድ ኢትዮጵያዊ ዜጋን ለሥራ ወደ ውጭ ሀገር መላክ ወንጀል ሆኖ ተደንግጓል፡፡ በወንጀል ህግ አንቀጽ 598 (2) በዚህ ድርጊት ምክንያት የተላከችው ኢትዮጵያዊት በሰብአዊ መብቷ፣በህይወትዋ ወይም በአካልዋ ላይ ጉዳት የደረሰባት እንደሆ ነቅጣቱ ከአምስት ዓመት እስከ ሃያ ዓመት የሚደርስ ጽኑ እስራት ና ከሃምሳ ሺህ ብር የማይበልጥ መቀጮ ይሆናል በሚል ተደንግጓል፡፡ ይህ ድንጋጌ ወደ ውጭ አገር የተላከችው ኢትዮጵያዊት በሰብአዊ መብቷ፣በአካል ደኅንነትዋ ወይም በህይወትዋ ላይ የሚደርሰውን ጉዳት ታሳቢ በማድረግ ቅጣቱን ከፍ አድርጎ አስቀምጧል፡፡ የወንጀል ህግ ቁጥር 598 ንዑስ ቁጥር 1 እና 2

የሚለየው በተላከችው ኢትዮጵያዊት ላይ በደረሰው የሰብዓዊ መብት ጥሰት፣በህይወት ወይም በአካል ላይ የደረሰውን ጉዳት መሠረት በማድረግ ነው፡፡

በያዝነው ጉዳይ የአሁን አመልካች የግል ተበዳይ ወ/ሮ እመቤት ይልማ ገ/የሱስ የተባለችውን ወደ ዱባይ ከላካት በኃላ የግል ተበዳይ አሠሪዋ ጭንቅላቷ ላይ በብረትድስት በመምታት የፈነከተቻትና ያቆሰለቻት ስለመሆኑ የዐቃቤ ህግ ክስ ያስረዳል፡፡ ይህን በተመለከተ የግል ተበዳይ የመሰከረች ቢሆንም በህክምና ማስረጃ መረጋገጥ ሲገባው ያለመረጋገጡ የሚያጠራጥር እንደሆነ አመልካች አጥብቀው ይከራከራሉ፡፡ በክርክር ሂደትም በግል ተበዳይ ላይ የአካል ጉዳት መድረስ ያለመድረሱ የህክምና ምርመራ እንዲደረግ ጠይቀው በፍርድ ቤት በኩል የተከለከለ መሆኑ የፍትህ መጓደልን ያስከተለ መሆኑን አመልካች በቅሬታነት አንስተዋል፡፡በግል ተበዳይ ላይ የደረሰው የአካል ጉዳት ካለ የህክምና ምርመራ እንዲ ደርግ አመልከች መጠየቁን ተጠሪ ሳይክድ ቁስሉ ከዳነ በኃላ የህክምና ምርመራ ሊደረግ ስለማይችል የሥር ፍርድ ቤት ጥያቄውን ውደቅ ማድረጉ ተገቢ ነው በማለት ተጠሪ ተከራክሯል፡፡ በመሠረቱ ከሳሽ በክሱ የጠቀሳቸውን ፍሬ ነገሮችን አግባብነት ባለው ማስረጃ የማስረዳት ሸክም ያለበት መሆኑ የማስረጃ ህግ መሠረታዊ መርህ ነው፡፡ ዐቃቤ ህግ በክሱ ላይ ያቀረበውን ፍሬ ነገር በአግባቡ ካላስረዳና ጥርጣሬን የሚፈጥር ከሆነ ተጠቃሚው ተከሳሽ ይሆናል ማለት ነው፡፡ ስለሆነም በተያዘው ጉዳይ አመልካች ፈቃድ ሳይኖራው የግል ተበዳይን ወደ ውጭ ሀገር መላኩ በማስረጃ የተረጋገጠ ፍሬ ነገር በመሆኑ አመልካች ጥፋተኛ ሊደረግ የሚገባውም በወንጀል ህግ ቁጥር 598 (1) እንጂ በንዑስ አንቀጽ 2 መሠረት አይደለም፡፡በመሆኑም አመልካች በወንጀል ህግ ቁጥር 598 (2) መሠረት ጥፋተኛ መደረጉ መሠረታዊ የሆነ ህግ ስህተት ነው ብለናል፡፡ ስለዚህ በወንጀለኛ መቅጫ ህግ ቁጥር 113 (2) መሠረት አመልካች የተከሰሰበትን የህግ አንቀጽ ቀይረን በወንጀል ህግ ቁጥር 598 (1) ሥር ጥፋተኛነው ብለን በወንጀል ህግ ቁጥር 195 (2) (ለ) (2) መሠረት ወስነናል፡፡

ቅጣትን በተመለከተ የወንጀል ህግ ቁጥር 598 በቅጣት መመሪያ ቁጥር 2/2006 መሠረት ደረጃ የወጣለት ነው፡፡አመልካች ጥፋተኛ የተደረገበት የወንጀል ህግ ቁጥር 598 (1) ደረጃ 1፣እርከን 21 ሥር ያርፋል፡፡ለአመልካች በሥር ፍርድ ቤት የተያዘው አራት የቅጣት ማቅለያ ተቀንሶ እርከን 17 ላይያርፋል፡፡በዚህ እርከን ላይ ያለው ፍቅድሥልጣን 3 ዓመት ከ3 ወር - 3 ዓመት ከ11 ወር ነው፡፡ በዚህ ፍቅድ ሥልጣን መሠረት በአመልካች ላይ 3 ዓመት ከ3 ወር /ሶስት ዓመት ከሶስት ወር/ ጽኑ እስራት ቅጣት ተወስኗል፡፡

በሌላ በኩል ክርክሩ አሁን ባለበት ደረጃ አመልካች ከማረሚያ ቤት ከላከው አቤቱታ እና የአመልካችም ባለቤት በችሎት በአካል ቀርባ ችሎቱ አይቶ ካረጋገጠው አመልካች በከፍተኛ የደም ግፊት ሕመም ታማሚ መሆኑን፤ ባለቤቱም የካንሰር ታማሚ መሆንዋ እና ጡትዋ በካንሰር ሕመም ምክንያት የተቆረጠ እና የኬሞትራፒ መደሃኒት በመውሰድ ላይ የምትገኝ መሆኑን እና ሕጻናት ልጆቻቸውም

በችግር ውስጥ የሚገኙ መሆኑን ተገንዝበናል፡፡ በመሆኑም በአመልካች ላይ የተላለፈውን ቅጣት አፈጻጸም በተመለከተ በዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት ታይቶ እልባት ሊሰጠው የሚገባ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

በመሠረታዊነት ቅጣት ሊገደብ የሚችለውም ጥፋተኛ የተባለን ሰው ለጥፋቱ መነሻ የሆኑትን ምክንያቶችን በጠቅላላው በመመልከት በጥፋተኛው ላይ የተወሰነውን ቅጣት ለጊዜው በገደብ እንዲታገድ በማድረግ የወንጀለኛውን ጠባይ ለማረምና ለማሻሻል እንዲሁም ወደ መደበኛ ማህበራዊ ኑሮው ለመመለስ ጠቃሚ መሆኑ በታመነ ጊዜ ስለመሆኑ የቅጣት ገደብን አስመልክቶ ከተደነገጉት የወንጀል ሕጉ ድንጋጌዎች መገንዘብ ይቻላል፡፡ ይህንንም ተፈጻሚ ለማድረግ ፍ/ቤቶች ቅጣትን ለመገደብ የሚያስችሉ የተለያዩ ሁኔታዎችን ከግምት ውስጥ ማስገባት እንዳለባቸው፤ እነዚህም ሁኔታዎች ወንጀለኛው ቀድሞ ያልተቀጣ ሆኖ ጠባዩም አደገኛነት እንደሌለው የሚታመንበት እንደሆነ፤ጥፋቱ በመቀጮ፤ በግዴታ ስራ ወይም ከሶስት አመት የማይበልጥ ቀላል እስራት የሚያስቀጣ እንደሆነ ፍርድ ቤቱ ጥፋተኝነቱን ካረጋገጠ በኋላ ለወደፊት ጠባዩን ለማረም እንደሚችል እምነት ሊጣልበት የሚችል ሆኖ ሲገኝ ነው፡፡

የአመልካች የዘወትር ባሕርይ መልካም መሆኑ፤ በተለያዩ የበጎ አድራጎት ተግባራት ማሕበራዊ ተሳትፎ የሚያደርግ መሆኑ እና የቤተሰብ አስተዳዳሪ መሆኑ በስር ፍ/ቤት የተረጋገጠ ከመሆኑ አኳያ እነኚህ የአመልካቹ ግላዊ ሁኔታዎች በወንጀል ሕጉ ቅጣትን ለመገደብ ከተቀመጡት ቅድመሁኔታዎች ውስጥ አመልካች ከፊሉን የሚያሟላ መሆኑን የሚያሳዩ ናቸው፡፡ በሌላ በኩል አመልካች በከፍተኛ የደም ግፊት ሕመም በመሰቃየት ላይ የሚገኝ እና ባለቤቱም በካንሰር ህመም ምክንያት ጡትዋ ተቆርጦ የኬሞትራፒ ሕክምና በመውሰድ ላይ የምትገኝ በመሆኑ እና ሕጻናት ልጆቻቸውም በችግር ውስጥ የሚገኙ በመሆናቸው በወንጀል ሕጉ ቅጣት ስለሚገደብበት ሁኔታዎች አስመልክቶ በተደነገጉት ድንጋጌዎች ብቻ ሳንገደብ ጉዳዩን እንደሚከተለው አይተናል፡፡

አመልካች በተጠቀሰው ህመም ምክንያት ህክምና የሚከታተል ስለመሆኑም ከአቤቱታው ጋር ተያይዘው የቀረቡት የህክምና ማስረጃዎች ያረጋግጣሉ፡፡ አመልካች በፈጸመው የወንጀል ድርጊት ጥፋተኛ ተብሎ ቅጣት ተወስኖበት በማረሚያ ቤት የሚገኝ ሲሆን የባለቤቱ መታመም ተጨምሮ በልጆቻቸው አስተዳደግና እንክብካቤ ላይ የሚያደርሰው ተጽዕኖ ከኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ህገ መንግሥት እንዲሁም ከዓለም አቀፍ የህጻናት መብቶች ኮንቬንሽን አንጻር እንዴት ይታያል? የሚለውን እንመልከት፡፡

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲዊ ሪፐብሊክ ህገ መንግሥት አንቀጽ 36 (1) (ሐ) ሕፃናት ወላጆቻቸውን ወይም አሳዳጊዎቻቸውን የማወቅና የእነሱንም እንክብካቤ የማግኘት መብት አላቸው በማለት ይደነግጋል፡፡ በዚህ ድንጋጌ ከተቀመጡት ፍሬ ነገሮች ውስጥ አንዱ ህፃናት የወላጆቻቸውን እንክብካቤ የማግኘት መብት ነው፡፡ የዚህ ድንጋጌ ዓላማ ህፃናት በአእምሯቸውና በአካላቸው ያልበሰሉ

ለጋ በመሆናቸው የወላጆች ጥበቃ የሚያስፈልጋቸው መሆኑን ታሳቢ ያደረገ እንደሆነ መገመት አያዳግትም። ሌላኛው መሠረታዊ ነገር ህፃናት ለአንድ አገር እድገትና ልማት የወደፊት ተስፋ እንዲሁም አገር ተረካቢዎች በመሆናቸው በመልካም አስተዳደግ ማደግ የሚገባቸው በመሆኑ ወላጆች በቅርበት ሆነው መከታተል፣ መቆጣጠርና ማሳደግ የሚገባቸው በመሆኑ ነው።

ከሕገ መንግሥቱ ድንጋጌ በተጨማሪ ኢትዮጲያ በአዋጅ ቁጥር 10/1984 ያጸደቀችው ዓለምአቀፍ የሕጻናት መብት የቃልኪዳን ሰነድ ስምምነት ወላጆች በህፃናት አስተዳደግ እና እንክብካቤ ላይ ያላቸውን ሚና በግልጽ ያስቀምጣል። የዓለም አቀፉ የህፃናት መብቶች ስምምነት የጠቅላላ ጉባኤ ውሳኔ ቁጥር 44/25 እንደ ኤሮፓውያን አቆጣጠር 1989 የወጣው አንቀጽ 7 (1) ማንኛውም ህፃን ወላጆቹን የማወቅና ከወላጆቹ እንክብካቤ የማግኘት መብት እንዳለው ይደነግጋል። ለህፃናት አስተዳደርና አያያዝ ሁለቱም ወላጆች የጋራ ሃላፊነት ያለባቸው መሆኑን የህፃናት መብቶች ኮንቬንሽን አንቀጽ 18 (1/) ይደነግጋል። ይህ ድንጋጌም ለህፃናት አስተዳደግና አያያዝ ወላጆች ያላቸውን ኃላፊነት ያስቀምጣል። የኮንቬንሽኑ አንቀጽ 18 (2) በዚህ ስምምነት የተመለከቱትን የህፃናት መብቶች ተፈጻሚነትን ለማረጋገጥ ህጻናትን የማሳደግ ሃላፊነታቸውን እንዲወጡ ለማድረግና ለማበረታታት ተዋዋይ አገሮች ለወላጆችና ለህጋዊ አሳዳሪዎች ተገቢውን እርዳታ ያደርጋሉ ሲል ያስቀምጣል። ከእነዚህ ድንጋጌዎች የምንገነዘበው ለህፃናት መልካም አስተዳደግ መሠረቱ ወላጆች መሆናቸውን ነው።

በሌላ በኩል የሕጻናት መብት የቃልኪዳን ሰነድ ስምምነትቱ አንቀጽ 3 ድንጋጌ እና የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገመንግሥት አንቀጽ 36/2 ድንጋጌ ሕጻናትን የሚመለከቱ እርምጃዎች በሚወሰዱበት ጊዜ በመንግሥታዊ ወይም በግል የበጎ አድራጎት ተቋሞች፤ በፍርድ ቤቶች፤ በአስተዳደር ባለስልጣኖች ወይም በሕግ አውጪ አካላት የሕጻናት ደሕንነት በቀደምትነት መታሰብ ያለበት መሆኑን ይደነግጋል።

በያዝነው ጉዳይ ከላይ እንደተገለጸው አመልካች በፈጸመው ወንጀል ምክንያት የቅጣት ውሳኔ ተላልፎበት ቅጣቱን በማረሚያ ቤት በመሆን በመፈጸም ላይ የሚገኝ ሲሆን ባለቤቱ ደግሞ በካንሰር ሕመም ምክንያት ጡትዋ ተቆርጦ የኬሞቴራፒ መድሃኒት በመውሰድ ላይ የምትገኝ በመሆኑ በሕፃናት ልጆቻቸው ላይ የሚደርስባቸውን ቁሳዊም ሆነ ኅሊናዊ ጫና መገመት አያዳግትም።

የአመልካች ልጆች አንድም አባታቸው በማረሚያ ቤት የሚገኝ በመሆኑ እናታቸውም በሕመም ምክንያት በሕክምና ላይ የምትገኝ በመሆኑ ምክንያት በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገመንግስት እና አገሪቱ በተቀበለቻቸው ዓለም አቀፍ እና አሕጉራዊ የሕፃናት መብቶች ስምምነቶች ሕጻናቱ የተጠበቀላቸውን የወላጆቻቸውን እንክብካቤ የማግኘት መብት የሚያሳጣቸው ነው። በመሆኑም በአመልካች እና በባለቤቱ ላይ በተከሰተው ከአቅም በላይ በሆነ ችግር ምክንያት ከአብራካቸው በተወለዱ ህፃናት ላይ የሚደርስባቸውን ችግር ወይም የሕይወትና የኑሮ ጫና፣ እንዲሁም የኅሊና ጉዳት ታሳቢ በማድረግ ሕጋዊ መፍትሔ መስጠት የሚያስፈልግ ሆኖ ተገኝቷል።

አመልካች በፈጸመው ወንጀል ምክንያት በማረሚያ ቤት በመሆኑ እና ባለቤቱም በካንሰር ሕመም ምክንያት ጡትዋ ተቆርጦ የኬሞቴራፒ መድሃኒት በመውሰድ ላይ የምትገኝ በመሆኑ በሕፃናት ልጆቻቸው ላይ የሚደርሰውን ቁሳዊም ሆነ ኅሊናዊ ጫና ለማስቀረት ሲባል እንዲሁም ሕጻናቱ የወላጆቻቸውን እንክብካቤ እና ድጋፍ አግኝተው እንዲያድጉ ለማድረግ ሲባል፤ ፍ/ቤቶችም የሕጻናት ደሕንነት በቅድሚያ የማረጋገጥ ሕገመንግስታዊ ግዴታ ያለባቸው በመሆኑ በአመልካች ላይ የተወሰነውን ቅጣት በመገደብ ህፃናቱ ተገቢውን የወላጅ እንክብካቤ እንዲያገኙ ለማድረግ ያስችል ዘንድ የተወሰነውን ቅጣት እንዳይፈጸም ለማገድ በወንጀል ህግ ቁጥር 194 መሠረት የሚከለክል ህጋዊ ምክንያት ያለመኖሩን ተመልክተናል፡፡ ፍርድ ቤት በአንድ ሰው ላይ የቅጣት ውሳኔ ከሰጠ በኋላ የቅጣት ውሳኔውን ለመገደብ እንደሚችልና የቅጣት ውሳኔው ሊገደብ የሚገባው ምን መሰረታዊ ሁኔታዎች ሲሟሉ እንደሆነ በወንጀል ህጉ አንቀጽ 192 ላይ መሰረታዊ መርሁ ተቀምጧል፡፡ ስለሆነም በአመልካች ላይ የተወሰነውን ቅጣት ለመገደብ የሚከለክል ሕጋዊ ምክንያት ባለመኖሩ ቅጣትን መገደብን የተመለከቱ ድንጋጌዎችን ግምት ውስጥ በማስገባት ይህ ውሣኔ ከተሰጠበት ጊዜ ጀምሮ አመልካች ያልፈፀመው ቀሪው የእስራት ቅጣት በሶስት ዓመት የጊዜ ገደብ ሊገደብለት ይገባል በማለት ፍርድ ሰጥተናል፡፡ ስለሆነም ተከታዩ ተወስኗል፡፡

## ውሳኔ

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ 003364 ጥቅምት 20 ቀን 2011 ዓ.ም እና ሕዳር 10 ቀን 2011 ዓ.ም የሰጠው የጥፋተኝነት እና የቅጣት ውሳኔ፤ ይህንኑ ውሳኔ በማጽናት የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 166293 በቀን 25/08/11 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 195/2/ለ/2 መሠረት ተሻሽሏል፡፡
2. ከላይ በፍርድ ሐተታው ላይ በተገለጸው ምክንያት አመልካች ጥፋተኛ ሊባል የሚገባው በወንጀልሕግቁጥር 598 (1) ነው በማለት ወስነናል፡፡ በዚሁ መሠረት በአመልካች ላይ የተላለፈው የቅጣት ውሳኔ ተሻሽሎ በሶስት ዓመት ከሶስት ወር ጽኑ እስራት እንዲቀጣ እና ቀሪው የእስራት ቅጣት አፈጻጸም በሶስት ዓመት የጊዜ ገደብ እንዲገደብ በማለት ወስነናል፡፡
3. የስር ፍ/ቤቶች የሰጡት የገንዘብ መቀጮ ቅጣት በዚህ ውሳኔ አልተነካም፡፡

## ትዕዛዝ

1. አመልካች በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 197 መሠት የብር 3000 / ሶስት ሺህ ብር /መተማመኛ ዋስትና እንዲያስይዝ ታዟል፡፡ይኸው ሲፈጸም የሚመለከተው ማረሚያ ቤት አመልካችን ከእሥር እንዲለቅ ታዟል፡፡
2. የውሳኔው ግልባጭ አመልካች ለሚገኝበት ማረሚያ ቤት እና ለሥር ፍርድ ቤቶች ይድረሳቸው፡፡

3. አመልካች በማረሚያ ቤት የሚገኝ በመሆኑ የዚህ ውሳኔ ግልባጭ በፍ/ቤቱ መልእክት ክፍል በኩል ለአመልካች ይድረሰው፡፡

- መዝገቡ ውሳኔ ስላገኘ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ፋ/ዘ

የሰ.መ.ቁ 165440

ጥር 27 ቀን 2012 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** እትመት አሠፋ

ጳውሎስ ኦርሺሶ

ፀሐይ መንክር

መላኩ ካሣዬ

እስቲበል አንዱዓለም

**አመልካች፡-** አየለ ሀሬቦ

**ተጠሪዎች፡-** የደቡብ ክልል ፍትሕ ቢሮ ዓቃቤ ሕግ

መዝገቡ የተቀጠረው መርምሮ ፍርድ ለመስጠት ነው፡፡ በመሆኑም መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ይህ የሰበር አቤቱታ ሊቀርብ የቻለው አመልካች ሕዳር 06 ቀን 2011 ዓ.ም ጽፎ ባቀረበው የሰበር አቤቱታ በደቡብ ብሔሮች ብሔረሠቦች እና ሕዝቦች ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የዱና ወረዳ ፍ/ቤት በመ.ቁ 09609 ግንቦት 06 ቀን 2010 ዓ.ም የሰጠው የጥፋተኝነት ውሳኔ እና ግንቦት 07 ቀን 2010 ዓ.ም የሰጠው የቅጣት ውሳኔ፤ የሀድያ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ 18276 ጥር 05 ቀን 2010 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ፤ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ.መ.ቁ 11028 ጥቅምት 28 ቀን 2011 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለቱ ነው፡፡

ጉዳዩ ወንጀል ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው በደቡብ ብሔሮች ብሔረሰቦች እና ሕዝቦች ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ዱና ወረዳ ፍ/ቤት ነው፡፡ በስር ፍ/ቤት በተደረገው ክርክር የአሁን አመልካች 1ኛ ተከሳሽ፤ ሌሎች አራት ግለሰቦች ደግሞ ከ2ኛ እስከ 4ኛ ተከሳሾች ነበሩ፡፡ የአሁን ተጠሪ በአሁን አመልካች እና በሌሎች ተከሳሾች ላይ በስር ፍ/ቤት ካቀረባቸው ክሶች ውስጥ አመልካችን የሚመለከተው 1ኛ እና 3ኛ ክስ ሲሆን ይዘታቸውም፡-

1ኛ ክስ፡- ተከሳሾች የወንጀል ሕጉን አንቀጽ 32/1/ሀ፤60/ለ እና 462/2/ሀ በመተላለፍ ጥር 17 ቀን 2010 ዓ.ም ጌምቤራ ቀበሌ ተብሎ በሚጠራው ቦታ ደሪሎ ኒሪም የተባለ ግለሰብ በፍ/ቤት መያዣ ትዕዛዝ ለመያዝ የሄዱት የፖሊስ አባላት ተጠርጣሪውን በቁጥጥር ስር ካዋሉት በኋላ አመልካች እነዚህ ፖሊሶች ያለእኔ ዕውቅና የመጡ ስለሆነ ተጠርጣሪውን መያዝ እና መውሰድ አይችሉም በማለት ፖሊሶቹን ተባብረው በመያዝ እና በመምታት እስረኛውን አስመልጠዋል የሚል ሲሆን፡-

3ኛ ክስ፡- ተከሳሾች የወንጀል ሕጉን አንቀጽ 32/1/ሀ፤ 60/ለ እና 441 ድንጋጌን በመተላለፍ በ1ኛ ክስ ለፈጸመው ድርጊት የክፍሉን ፖሊሶች በሀይል እና በማስገደድ ስራቸውን እንዳይሰሩ በማድረጋቸው በፈጸሙት የመንግስት ስራ በሀይል ድርጊት ማሰናከል ወንጀል ተከሰዋል የሚል ነው፡፡

ጉዳዩ የቀረበለት የዱና ወረዳ ፍ/ቤት አመልካችን እና የስር ተከሳሾችን ጥፋተኛ ሆነው ስላገኛቸው በተከሰሱበት የሕግ አንቀጽ ጥፋተኛ ብሏቸዋል፡፡ ቅጣቱንም በቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 02/2006 መሠረት በማስላት ለ1ኛ ክስ ድርጊቱ የተፈጸመው በቡድን እና በጸጥታ አስከባሪ አካላት ላይ በመሆኑ የጽኑ እሥራት አማራጭ ተወስዷል በማለት፤ የወንጀል ደረጃውን መካከለኛ በማለት በእርከን 15 ላይ በማሳረፍ፤ ምንም እንኳን አመልካች ያነሳሳ ቢሆንም በቀጥታ የፖሊሱን አካል ያልያዘ በመሆኑ መነሻ ቅጣት ሁለት ዓመት ከአስር ወር በመያዝ፤ ለ3ኛ ክስ የወንጀሉን ደረጃ መካከለኛ በማለት በእርከን 6 ላይ በማሳረፍ አንድ ዓመት እስራት የተወሰደ ቢሆንም በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 184/ለ መሠረት አንድ ጽኑ እስራት እና አንድ ቀላል እሥራት ተደራርበው በተፈጸሙ ጊዜ ቀላል እስራት ታጥፎ መደመር ያለበት በመሆኑ ቀላል እስራቱን ወደ ስድስት ወር ጽኑ እስራት በመቀየር በድምሩ ሶስት ዓመት ከአራት ወር በመያዝ በእርከን 17 ላይ በማሳረፍ፤ በዓቃቤ ሕግ በኩል የቀረበውን የቅጣት ማክበጃ ምክንያት ባለመቀበል እና ለአመልካች ሁለት የቅጣት ማቅለያ ምክንያቶችን በመያዝ ቅጣቱን አቅሎ በእርከን 15 ላይ በማሳረፍ አመልካች በሁለት ዓመት ከአስራ አንድ ወር ጽኑ እስራት እንዲቀጣ ሲል ወስኗል፡፡

አመልካች ይህን ውሳኔ በመቃወም ለሀዲያ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የይግባኝ አቤቱታ ያቀረበ ቢሆንም አቤቱታው ተቀባይነት አላገኘም፡፡ አመልካች በመቀጠል ለክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አቤቱታ አቅርቧል፡፡ የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ግራቀኙን ካከራከረ በኋላ አመልካች ክሱን አላስተባበለም በማለት በወንጀል ሕግ አንቀጽ 462/2 እና 441/2 ድንጋጌ ጥፋተኛ ብሎታል፡፡ ቅጣትን በተመለከተ ደግሞ አመልካች ጥፋተኛ የተባለበት የወንጀል ሕግ አንቀጽ 462/2/ሀ የአመልካች ድርጊት አፈጻጸም በጠለፋ የተጠረጠረን ግለሰብ ለማስመለጥ በሕግ አስከባሪ አካላት ላይ በቡድን የተፈጸመ ወንጀል በመሆኑ በከባድ ሊቀጣ ይገባል በማለት የወንጀሉን ደረጃ መካከለኛ በማለት መነሻ ቅጣት ሁለት ዓመት ከስድስት ወር በመያዝ፤ አመልካች ጥፋተኛ የተባለበት የወንጀል ሕግ አንቀጽ 441/2 የወንጀል ደረጃውን መካከለኛ በማለት መነሻ ቅጣት ሁለት ዓመት በመያዝ፤ አመልካች ጥፋተኛ ለተባለበት ሕግ የተያዙትን መነሻ ቅጣቶች በመደመር አራት ዓመት ከስድስት ወር መነሻ ቅጣት በመያዝ እና በእርከን

19 ላይ በማሳረፍ፤ አመልካች የተያዘለት ሁለት የቅጣት ማቅለያ ምክንያት በመያዝ ቅጣቱን አቅሎ በእርከን 17 ላይ በማሳረፍ በሶስት ዓመት ከሶስት ወር ጽኑ እስራት እንዲቀጣ ሲል ወስኗል፡፡

የሰበር አቤቱታው የቀረበው ይህን ውሳኔ በመቃወም መሠረታዊ የሕግ ስሕተት ተፈጽሞበታል በሚል ሲሆን ይዘቱም፡- ዓቃቤሕግ ባቀረባቸው ምስክሮች አመልካች ወንጀል የፈጸምኩ ስለመሆኔ አላስረዳም፤ የወረዳው ፍ/ቤት አመልካች የቀረበብኝን ክስ እንድከላከል ብይን የሰጠ ቢሆንም ባቀረብኩት መከላከያ ማስረጃ የአቃቤሕግን ክስ አስተባብዬ ሳለ ጥፋተኛ መባሌ አግባብ አይደለም፤ የስር ፍ/ቤት የአመልካችን መከላከያ ማስረጃ ውድቅ ያደረገበትን ምክንያት በውሳኔው ላይ አልገለጸም፤ አመልካች ለክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ያቀረብኩት አቤቱታ የጥፋተኝነት እና የቅጣት ውሳኔው አግባብ አይደለም የሚል ሆኖ ሳለ የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት በስር ፍ/ቤቶች የተሰጠውን የጥፋተኝነት ውሳኔ ካጸና በኋላ ባልታወቀ ምክንያት ባልተጠየቀ ዳኝነት የቅጣት ውሳኔውን አምስት ዓመት ከሁለት ወር ብሎ በመያዝ ከፍ በማድረግ ቀንሶ እንዳሻሻለ በማድረግ የሶስት ዓመት ከሶስት ወር እሥራት እንድቀጣ የሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል የሚል ነው፡፡

የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ የስር ፍ/ቤት አመልካች በሁለት ዓመት ከአስራ አንድ ወር እስራት እንዲቀጣ በሰጠው ውሳኔ አመልካች ለክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ባቀረበው አቤቱታ መነሻነት የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት አመልካች በስር ፍ/ቤት ከተወሰነበት ቅጣት በላይ በሦስት ዓመት ከሦስት ወር እንዲቀጣ በማለት የመወሰኑን አግባብነት ከወ/መ/ስ/ስ/ሕ/ቁ 195 ጋር በማገናዘብ ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ በዚህ ችሎት እንዲታይ ተደርጓል፡፡ ተጠሪ መጥሪያ ተልኮለት ስላልቀረበ በጽሑፍ መልስ የመስጠት መብቱ ታልፏል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ በአጭሩ ከላይ የተገለጸው ነው፡፡ ይህ ችሎትም የአመልካችን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ምክንያት ከሆነው ውሳኔ፤ እና ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸው ሕጎች ጋር በማገናዘብ፡-

1. የአሁን ተጠሪ በአመልካች ላይ በስር ፍ/ቤት አቅርቦት የነበረው 3ኛ ክስ አቀራረብ በወንጀል ስነስርዓት ሕጉ ስለክስ አቀራረብ በተቀመጡት ድንጋጌዎች አግባብ የቀረበ ነው? ወይስ አይደለም?
2. በየደረጃው ያሉት የክልሉ ፍ/ቤቶች በአመልካች ላይ ቀርቦ የነበረውን 3ኛ ክስን አስመልክቶ የሰጡት ውሳኔ ተገቢ ነው? ወይስ አይደለም? የሚሉትን ጭብጦች በመያዝ ጉዳዩን እንደሚከተለው መርምረነዋል፡፡

የአሁን ተጠሪ በአሁን አመልካች እና በስር ተከሳሾች ላይ አቅርቦት የነበረው 3ኛ ክስ ይዘት ተከሳሾች የወንጀል ሕጉን አንቀጽ 32/1/ሀ፤ 60/ለ እና 441 ድንጋጌን በመተላለፍ በ1ኛ ክስ ለፈጸመው ድርጊት የክፍሉን ፖሊሶች በሀይል እና በማስገደድ ስራቸውን እንዳይሰሩ በማድረጋቸው በፈጸሙት የመንግስት ስራ በሀይል ድርጊት ማሰናከል ወንጀል ፈጽመዋል የሚል ነው፡፡

የወንጀል ሕግ አንቀጽ 441፡- ማንም ሰው፡-

ሀ/ አንድ የመንግስት ሰራተኛ የስራ ግዴታው የሆነውን ተግባር እንዳያከናውን በዛቻ፣ በማስገደድ ወይም በሀይል ድርጊት ያሰናከለ ወይም ይህን ግዴታውን እንዲያከናውን ወይም ማድረግ የሌለበትን እንዲያደርግ ያስገደደ እንደሆነ፣ ወይም

ለ/ የመንግስት ሰራተኛን ወይም በስራው የሚረዳውን ሰው የደበደበ ወይም የሀይል ወይም የማስገደድ ድርጊት ወይም ማናቸውንም ሌላ የማስገደድ ድርጊት የፈጸመ እንደሆነ፣

ከሶስት ዓመት በማይበልጥ ቀላል እስራት ወይም ከአምስት ሺህ ብር በማይበልጥ መቀጮ ይቀጣል በማለት ይደነግጋል፡፡

ከድንጋጌዎቹ ይዘት መገንዘብ የሚቻለው በድንጋጌው ንዑስ (ሀ) እና (ለ) ላይ የተቀመጡት የወንጀል ማቋቋሚያ መስፈርቶች ራሳቸውን ችለው የተቀመጡ መስፈርቶች መሆናቸውን ነው፡፡

የአሁን ተጠሪ በስር ፍ/ቤት ባቀረበው 3ኛ ክስ ተከሳሾች የወንጀል ሕጉን አንቀጽ 441 በመተላለፍ የመንግስት ስራ በሀይል ድርጊት ማሰናከል ወንጀል ፈጽመዋል ከማለት በቀር ተከሳሾች በወንጀል ሕግ አንቀጽ 441 ላይ በተለያየ ንዑስ ቁጥር ላይ ከተቀመጡት ድንጋጌዎች ውስጥ የትኛውን የንዑስ ቁጥር ድንጋጌ እንደተላለፉ በክሱ ላይ ለይቶ አላመለከተም፡፡

ጉዳዩ የቀረበለት የወረዳው ፍ/ቤትም አመልካችን በ3ኛ ክስ በወንጀል ሕግ አንቀጽ 441 መሠረት ጥፋተኛ ከማለት በቀር አመልካች ጥፋተኛ የተባለበትን የድንጋጌውን ንዑስ ቁጥር ለይቶ አላመለከተም፣ በአመልካች አቤቱታ አቅራቢነት ጉዳዩን በሰበር የተመለከተው የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎትም 3ኛን ክስ በሚመለከት አመልካችን በወንጀል ሕግ አንቀጽ 441/2 ጥፋተኛ ሲለው ይህን ያደረገበትን ምክንያት አልገለጸም፡፡

በመሠረቱ ከሳሽ የሆነው ዓቃቤሕግ የሚቀርበው የወንጀል ክስ ማመልከቻ በምን አኳኃን መቅረብ እንዳለበት በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 111 እና 112 ላይ በዝርዝር ተመልክቷል፡፡ ከድንጋጌዎቹ ይዘት መገንዘብ የሚቻለው ዓቃቤሕግ በሚያቀርበው ክስ ላይ በዝርዝር እንዲገልጽ ከሚጠበቅበት መሰረታዊ ፍሬነገሮች ዉስጥ ተከሳሹ ተላልፎታል የተባለው የወንጀል ሕግ ድንጋጌ እና ተከሳሹ የፈጸመዉ የወንጀል ተግባር በመሠረታዊነት ሊጠቀሱ የሚገባቸው ናቸው፡፡ ክሱ በዚህ አግባብ ተዘጋጅቶ እስካልቀረበ ጊዜ ድረስ ተከሳሽ የሆነው ወገን ክሱን በአግባቡ ሊረዳ እና ክሱን ሊከላከል አይችልም፡፡ ይህም በወንጀል የተከሰሱ ሰዎች በሕገመንግስቱ የተጠበቀላቸውን የቀረበባቸውን ክስ የመረዳት እና የመከላከል መሠረታዊ መብት የሚጻረር ነው፡፡

ፍ/ቤቱም ዓቃቤሕጉ ያቀረበው የክስ አቤቱታ በሥነ-ሥርዓት ሕጉ መሠረት ያልቀረበ ሆኖ ባገኘው ጊዜ በራሱ አነሳሽነት በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ ቁጥር 118 እና 119/1 ላይ በተገለጸው አግባብ ክሱ ተሻሽሎ እንዲቀርብ ማድረግ ይኖርበታል፡፡ ዓቃቤሕግ ክሱን አሻሽሎ እንዲቀርብ እስካልተደረገ ጊዜ ድረስ በሕጉ አግባብ ተዘጋጅቶ ያልቀረበው ክስ የተከሳሹን የመከላከል መብት የሚያጣብብ በመሆኑ ተከሳሹ በሕግ አግባብ ተዘጋጅቶ ባልቀረበው ክስ ጥፋተኛ ሊባል አይገባም፡፡

በያዝነው ጉዳይ ተጠሪ በስር ፍ/ቤት ባቀረበው ክስ 3ኛውን ክስ በተመለከተ ተከሳሾች የወንጀል ሕጉን አንቀጽ 441 በመተላለፍ የመንግስት ስራ በሀይል ድርጊት ማሰናከል ወንጀል ፈጽመዋል ከማለት በቀር ተከሳሾች በወንጀል ሕግ አንቀጽ 441 ላይ በተለያየ ንዑስ ቁጥር ላይ ከተቀመጡት ድንጋጌዎች ውስጥ የትኛውን የንዑስ ቁጥር ድንጋጌ እንደተላለፉ በክሱ ላይ ለይቶ አላመለከተም፡፡ ተጠሪ በአመልካች ላይ ያቀረበው 3ኛ ክስ የተለያዩ ንዑስ አንቀጾች ያሉት እና በንዑስ አንቀጾቹ ላይ የተቀመጡት የወንጀል ማቋቋሚያ መስፈርቶች ራሳቸውን ችለው የተቀመጡ መስፈርቶች በመሆናቸው አመልካች ተላልፎታል የተባለው ንዑስ አንቀጽ ተለይቶ በክስ አቤቱታው ላይ እስካልተገለጸ ጊዜ ድረስ አመልካች የቀረበበትን ክስ በአግባቡ ሊረዳ አይችልም፡፡ ዓቃቤሕግ ክሱን አሻሽሎ እንዲቀርብ እስካልተደረገ ጊዜ ድረስ በሕጉ አግባብ ተዘጋጅቶ ያልቀረበው ክስ የተከሳሹን የመከላከል መብት የሚያጣብብ በመሆኑ ተከሳሹ በሕግ አግባብ ተዘጋጅቶ ባልቀረበው ክስ መነሻነት ጥፋተኛ ሊባል አይገባም፡፡

በመሆኑም ጉዳዩ የቀረበለት ፍ/ቤት ተጠሪ ያቀረበው ክስ በሕጉ መሠረት የቀረበ አለመሆኑን ሲረዳው ክሱ እንዲሻሻል ትዕዛዝ መስጠት ሲገባው አመልካች በተከሰሰበት ሕግ ከተቀመጡት ንዑስ አንቀጾች ውስጥ አመልካች የተላለፈውን የሕግ ድንጋጌ ሳይለይ በደፈናው አመልካችን በወንጀል ሕግ አንቀጽ 441 መሠረት ጥፋተኛ ማለቱ፤ ጉዳዩን በሰበር የተመለከተው የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎትም ይሕንኑ ሳያርም እና ምንም ዓይነት ምክንያት ሳይሰጥ አመልካችን በ3ኛው ክስ በወንጀል ሕግ አንቀጽ 441/2 ጥፋተኛ በማለት የሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

በሌላ በኩል ዓቃቤሕግ በአመልካች ላይ ያቀረበው 1ኛ ክስ በሕጉ አግባብ የቀረበ እና አመልካች በክሱ ላይ የተመለከተውን ድርጊት ስለመፈጸሙ ተረጋግጦበት ክሱን ያልተከላከለ በመሆኑ አመልካች 1ኛውን ክስ በሚመለከት ያቀረበውን ቅሬታ አልተቀበልነውም፡፡ በመሆኑም የስር ፍ/ቤቶች በአመልካች ላይ 3ኛ ክስን በተመለከተ ያስተላለፉትን የጥፋተኝነት እና የቅጣት ውሳኔ በመሻር 1ኛ ክስን በሚመለከት ብቻ ቅጣቱን እንደሚከተለው አስልተናል፡፡

በክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አመልካች በ1ኛ ክስ ጥፋተኛ የተባለበት የወንጀል ሕግ አንቀጽ 462/2/ሀ አመልካች ጥፋተኛ የተባለበት የወንጀል ሕግ አንቀጽ 462/2/ሀ የወንጀሉ ደረጃ መካከለኛ በማለት መነሻ ቅጣት ሁለት ዓመት ከስድስት ወር የተያዘለት በመሆኑ ይህ መነሻ በእርከን 12 ላይ የሚያርፍ ነው፤ በአመልካች ላይ ተቀባይነት ያገኘ የቅጣት ማክበጃ ምክንያት የለም፤ አመልካች

በስር ፍ/ቤት ሁለት የቅጣት ማቅለያ ምክንያት የተያዘለት በመሆኑ ቅጣቱ ሲቀል በእርከን 10 ላይ ያርፋል፤ በእርከን 10 ያለው ፍቅደ ስልጣን ከአንድ ዓመት ከስድስት ወር እስከ ሁለት ዓመት ነው፡፡ በዚህ እርከን ስር አመልካችን ያርማል ሌሎቹንም ያስጠነቅቃል ብለን ያመንበትን አመልካች በአንድ ዓመት ከዘጠኝ ወር ጽኑ እስራት እንዲቀጣ በማለት ወስነናል፡፡ ስለሆነም ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. በደቡብ ብሔሮች ብሔረሠቦች እና ሕዝቦች ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የዱና ወረዳ ፍ/ቤት በመ.ቁ 09609 ግንቦት 06 ቀን 2010 ዓ.ም የሰጠው የጥፋተኝነት ውሳኔ እና ግንቦት 07 ቀን 2010 ዓ.ም የሰጠው የቅጣት ውሳኔ፤ የሀድያ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ 18276 ጥር 05 ቀን 2010 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ፤ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ.መ.ቁ 11028 ጥቅምት 28 ቀን 2011 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 195/2/ለ/2 መሠረት ተሻሽሏል ፡፡
2. ከላይ በፍርድ ሐተታው ላይ በተገለጸው ምክንያት አመልካች ከ3ኛ ክስ በነጻ ተሰናብቷል፡፡
3. አመልካች ከ3ኛ ክስ በነጻ የተሰናበተ በመሆኑ የስር ፍ/ቤቶች የሰጡት የቅጣት ውሳኔ ተሻሽሎ በአንድ ዓመት ከዘጠኝ ወር ጽኑ እስራት እንዲቀጣ በማለት ወስነናል፡፡

## ትዕዛዝ

- የሚመለከተው ማረሚያ ቤት በአመልካች ላይ በስር ፍ/ቤቶች ተላልፎ የነበረው የጥፋተኝነት እና የቅጣት ውሳኔ ተሻሽሎ አመልካች በአንድ ዓመት ከዘጠኝ ወር ጽኑ እስራት እንዲቀጣ የተወሰነ መሆኑን አውቆ በተሻሻለው ውሳኔ መሠረት እንዲያስፈጽም ታዟል፡፡
- በደቡብ ብሔሮች ብሔረሰቦች እና ሕዝቦች ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የሀዲያ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት የመ.ቁ 18276 የሆነው መዝገብ በመጣበት አኳሃን ወደ መጣበት ይመለስ፡፡
- መዝገቡ ውሳኔ ስላገኘ ተዘግቷል፡፡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት ፡፡

ፅ/ወ

የሰ/መ/ቁ 162738

መጋቢት 30 ቀን 2012 ዓ.ም

ዳኞች፡- እትመት አሠፋ

ጳውሎስ ኦርሺሶ

ፀሐይ መንክር

መላኩ ካሣዬ

እስቲበል አንዱዓለም

አመልካች፡- 1. አቶ መሐመድ ያዕቆብ ከድር አልይዘአ

2. አቶ ዘውዴ ጂዳ

3. አቶ እሸቱ አበበ

4. አቶ ኡመር መሐመድ

5. አቶ ዳምጠው ለማ

6. አቶ መሐመድ አወል ጀማል ከድር

7. አቶ ሀይሌ ተሰማ አያኔ

8. አቶ ዳምጠው ጀግና

9. ወ/ሮ ገነት ሁስማን ሼካ

10. ወ/ሮ ሀዋ አደም

11. አቶ ዘውዴ ሽመልስ ለገሰ

12. አቶ መሐመድ ቃሲም ገርቢ

13. አቶ አብዱልቃድር ከድር አሎ

14. አቶ አበራ ቶሎሳ ጋሹ

15. ወ/ሮ ቀመሪያ ገሮ ሐቤቤ

ተጠሪ፡- የኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጸረ ሙስና ኮሚሽን ዓቃቤ ሕግ

መዝገቡ ለምርመራ የተቀጠረ ነው። በመሆኑም መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል።

## ፍርድ

ይህ የሰበር አቤቱታ ሊቀርብ የቻለው አመልካቾች በጠበቆቻቸው አማካኝነት ነሐሴ 17 ቀን 2010 ዓ.ም ተጽፎ በቀረበ የሰበር አቤቱታ በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የባሌ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ 22898 አመልካቾች ያቀረብነውን መቃወሚያ በማለፍ የሰጠው ብይን፤ በዚሁ መዝገብ በቀን 10/01/2010 ዓ.ም የሰጠው የጥፋተኝነት ውሳኔ እና በቀን 11/01/2010 ዓ.ም የሰጠው የቅጣት ውሳኔ፤ ይህን ውሳኔ በማጽናት የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት እና የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 278007 በቀን 21/09/2010 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት በመሆኑ በሰበር ታይቶ ይታረምልን በማለት በመጠየቃቸው ነው።

ጉዳዩ የሙስና ወንጀልን በሚመለከት የቀረበ ክርክር ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የባሌ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ነው። የአሁን ተጠሪ በስር ፍ/ቤት አመልካቾችን ጨምሮ በ38 ተከሳሾች ላይ ክስ ያቀረበ ሲሆን የአሁን አመልካቾች እንደ ቅደም ተከተላቸው 1ኛ፤ 2ኛ፤ 3ኛ፤ 4ኛ፤ 5ኛ፤ 6ኛ፤ 7ኛ፤ 8ኛ፤ 9ኛ፤ 12ኛ፤13ኛ፤14ኛ፤16ኛ፤19ኛ እና 21ኛ ተከሳሾች ነበሩ። የአሁን ተጠሪ በአሁን አመልካቾች እና ለዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት አቤቱታ ባላቀረቡ ቀሪ ተከሳሾች ላይ በስር ተከሳሾች ላይ በስር ፍ/ቤት ያቀረባቸው ክሶቸ 11 ሲሆኑ የመጀመሪያዎቹ ስድስቱ ክሶች አመልካቾችን የሚመለከቱ ናቸው። ይዘታቸውም፦

<u>1ኛ ክስ፦</u> አመልካቾች እና የስር 10ኛ፤11ኛ፤15ኛ እና 20ኛ ተከሳሾች የሙስና ወንጀሎች አዋጅ ቁጥር 881/2007 አንቀጽ 9/3 ድንጋጌን በመተላለፍ የሮቤ ከተማ ማኔጅመንት፤ የሮቤ ከተማ መሬት አስተዳደር እና ማኔጅመንት ሆነው ሲሰሩ የማይገባቸውን ጥቅም ለማግኘት ወይም ለሌላ ሰው ለማስገኘት ወይም በመንግስት እና በሕዝብ ጥቅም ላይ ጉዳት ለማድረስ አስበው አመልካቾች እና የስር 10ኛ፤11ኛ፤15ኛ ተከሳሾች በቀን 01/10/2007 ዓ.ም ቃለጉባኤ በመያዝ፤ የስር 10ኛ፤ 11ኛ እና 20ኛ ተከሳሾች እንዲሁም የአሁን 14ኛ እና 15ኛ አመልካቾች በያዙት ቃለጉባኤ መሬት የመንግስት እና የኢትዮጵያ ሕዝቦች ሐብት እና የማይሸጥ የማይለወጥ መሆኑን እያወቁ፤ የገጠር መሬት ወደ ከተማ መሬት ሲካለል በፌዴራል አዋጅ 455/97 ፤ 721/2004፤ በኦሮሚያ የመሬት አዋጅ ቁጥር 130/99፤ ደንብ ቁጥር 155/2005 እና መመሪያ ቁጥር 9/2005 መሠረት መፈጸም እንዳለበት እያወቁ ሕግ የሚፈቅድላቸው በማስመሰል በከተማ ስር የገባውን የገጠር መሬት 45% መሬት የገበሬ ነው፤ 55% መሬት ደግሞ የመንግስት ነው ተብሎ ተከፋፍሎ የቆየ እና ይህን መሬት ገበሬው በሽያጭ ሲያስተላልፍ የቆየ መሆኑን በያዙት ቃለጉባኤ ገልጸው እያለ ሕገወጥ ግንባታ እና የድሮ ይዞታ በማስመሰል ስልጣንን አላግባብ በመጠቀም ስፋቱ 247,161 እና 997 ፕሎት መሬት 76 ለሆኑ ገበሬዎች በመስጠት ለእነዚህ ገበሬዎች በሕጉ አግባብ ለእያንዳንዳቸው 500 ካ.ሜ መሬት ተስጥቷቸው ቢሆን ኖሮ ስፋቱ 894,970

እንዲሰጥ በማድረግ መንግስት ሊያገኝ የሚችለው ገቢ 199,277.70 ስላሳጡት ስልጣንን አላግባብ በመጠቀም የሙስና ወንጀል ተከሰዋል የሚል ነው፡፡

2ኛ ክስ፡- አመልካቾች እና የስር 10ኛ፣11ኛ፣15ኛ ተከሳሾች አዋጅ ቁጥር 881/2007 አንቀጽ 13/3 በመተላለፍ በ1ኛው ክስ ውስጥ በተወሰነው ውሳኔ መሠረት ቁጥራቸው 308 ለሆኑ ሰዎች በድምሩ ስፋቱ 120,000 የሆነ መሬት እንዲሰጥ በመወሰን፣ 1ኛ እና 11ኛ ተከሳሾች፣ 14ኛ አመልካች እና የስር 36ኛ ተከሳሽ ደግሞ መሬት በወሰዱ እና በከተማው አስተዳደር መካከል የተደረገውን ሕገወጥ ውል በማጽደቅ፣ 27ኛ፣ 28ኛ እና 29ኛ ተከሳሾች በሕገወጥ በተላለፈው በዚህ መሬት ላይ ካርታ በማዘጋጀት፣ የስር 10ኛ፣ 11ኛ፣ 23ኛ እና 36ኛ ተከሳሾች እና 13ኛ እና 14ኛ አመልካቾች ደግሞ በሕገወጥ መንገድ በተሰጠ መሬት ላይ የተዘጋጀን ካርታ በማጽደቅ፣16ኛ አመልካች እና 20ኛ፣ 24ኛ፣ 26ኛ፣ 28ኛ፣ 30ኛ፣ 31ኛ፣ 38ኛ ተከሳሾች ሕገወጥ የሆነን ቅጽ በመሙላት፣ በአጠቃለይ ተከሳሾች በጋራ በመሆን ሕዝብና መንግስት እኩል ሊጠቀሙበት የሚገባውን ይዞታ ሕግ እና መመሪያ በመተላለፍ ስፋቱ 65,755 የሆነ መሬት ለግለሰቦች እንዲሰጥ በማድረግ መንግስት ሊያገኝ የሚገባውን ገቢ 14,624,569.75 አሳጥተዋል የሚል ነው፡፡

3ኛ ክስ፡- 17ኛ እና 18ኛ ተከሳሾች የአዋጁን አንቀጽ 9/1/ለ ድንጋጌ በመተላለፍ በ1ኛው ክስ በቀን 01/07/07 እና 03/09/07 በያዙት ቃለጉባኤ ሕገወጥ የመሬት አሰጣጡን ስራ ላይ የማዋል ድርጊት በመገምገም ሕገወጥ ስራው እንዲቀጥል አድርገዋል የሚል ነው፡፡

4ኛው ክስ፡- 1ኛ እና 8ኛ አመልካቾች እንዲሁም 10ኛ፣17ኛ እና 18ኛ ተከሳሾች የኦሮሚያ ከተማ መሬቶችን በሊዝ ለማስተዳደር የወጣውን ደንብ ቁጥር 155/2005 አንቀጽ 59/1 ድንጋጌን በመተላለፍ በ3ኛ ክስ የተገለጸውን ቃለጉባኤ በመያዝ ሕገወጥ የሆነውን 45/55 ተብሎ የሚታወቀውን አሰራር በስራ ላይ እንዲውል አድርገዋል የሚል ነው፡፡

5ኛ ክስ፡- 10ኛ፣ 11ኛ፣ ፣20ኛ ተከሳሾች፣ 14ኛ እና 15ኛ አመልካቾች አዋጅ ቁጥር 881/2007 አንቀጽ 9/3 ድንጋጌን በመተላለፍ የሮቤ ከተማ አስተዳደር እና ማኔጅመንት ኮሚቴዎች በመሆን እና 17ኛው ተከሳሽ የገቢዎች የባለስልጣን ሀላፊ በመሆን የሙስና ወንጀሎችን አዋጅ ቁጥር 881/2007 አንቀጽ 9/3 በመተላለፍ 10ኛ፣11ኛ፣20ኛ ተከሳሾች እና 14ኛ እና 15ኛ አመልካቾች በቀን 14/09/2007 በያዙት ቃለጉባኤ ገበሬዎች ከድርሻቸው መሬት ላይ የሸጡትን ይዞታ የድሮ ይዞታ በማስመሰል ክፍያ እንዲፈጸምበት በመወሰን ለገቢዎች ባለስልጣን በመላክ፣ 17ኛው ተከሳሽ በተለያዩ ጊዜዎች ሲይዟቸው በነበሩት ቃለ ጉባኤዎች በመስሪያ ቤቱ ውስጥ የሚገኙ መሆናቸውን እያወቀና እያየ ይህ ክፍያ እንዲፈጸም አድርጓል የሚል ነው፡፡

6ኛ ክስ፡- 1ኛ እና 15ኛ አመልካቾች 10ኛ፤ 11ኛ እና ከ22ኛ እስከ 25ኛ ያሉ ተከሳሾች የወንጀል ሕጉን አንቀጽ 32/1/ሀ እና የሙስና ወንጀሎችን አዋጅ ቁጥር 881/2007 አንቀጽ 13/1/ሐን በመተላለፍ 15ኛ አመልካች እና ከ22ኛ እስክ 25ኛ ያሉት ተከሳሾች ሕገወጥ በሆነ መንገድ የአጣሪ ኮሚቴ ሆነው በመመረጥ መመሪያው እንደሚከለክላቸው እያወቁ እንደ ሕጋዊ ኮሚቴ እራሳቸውን በመቁጠር በሮቤ ከተማ መሬት ማኔጅመንት ኤጀንሲ በሚጣራ የመኖሪያ ቤት ክምችት በቀን 11/01/07 ቁጥሩ 1076/k13/2007 በሆነ እና ለባሌ ዞን መሬት ማኔጅመንት እና ልማት ኤጀንሲ በተጻፈ ደብዳቤ 530 ሰዎች ብቻ ተጣርተው የተላከ ሆኖ ሳለ 56 ሰዎችን በመጨመር እና ሌሎች ሰዎችን በመቀነስ አጣርተው ልከዋል የሚል ነው፡፡

የአሁን 4ኛ፤5ኛ፤8ኛ፤10ኛ አመልካቾች በአዲስ ዘመን ጋዜጣ ጥሪ ተደርጎላቸው ስላልቀረቡ ጉዳያቸው በሌሉበት የታየ መሆኑን መዝገቡ ያመለክታል፤ 1ኛ፤ 2ኛ፤ 3ኛ፤ 6ኛ፤7ኛ ፤9ኛ ፤11ኛ ፤12ኛ፤13ኛ ፤14ኛ እና 15ኛ አመልካቾች ችሎት ቀርበው ክሱ ተነቦላቸው እንዲረዱት ከተደረገ በኂላ መቃወሚያ አቅርበው በብይን ውድቅ ተደርጓል፡፡ የእምነት ክህደት ቃላቸውን ሲጠየቁም ድርጊቱን አልፈጸምንም በማለት ክደው በመከራከራቸው ፍ/ቤቱ የዓቃቤ ሕግን ማስረጃዎች ሰምቷል፡፡

ፍ/ቤቱ የዓቃቤሕግ ምስክሮች የሰጡትን የምስክርነት ቃል እና ዓቃቤሕግ ከክሱ ጋር አያይዞ ያቀረባቸውን የሰነድ ማስረጃዎች ከመረመረ በኂላ ከ1ኛ እስከ 5ኛ ድረስ ያሉት ክሶች ተከሳሾች 45/55 የተባለን አሰራር በስራ ላይ እንዲውል መወሰናቸውን እና በስራ ላይ ከማዋላቸው ጋር የሚያያዝ ነው፡፡ በዚህ አሰራር መሬት ተሰጥቷቸዋል የተባሉት ሰዎች በተለያዩ ክሶች የተገለጹ ቢሆንም በተያዘው ቃለ ጉባኤ የተጣሩ ሰዎች እራሳቸው ናቸው፤ ይህም በአንድ በሕግ በተጠበቀ መብት ላይ የተፈጸመን ወንጀል ከግብ ለማድረስ ተቀላቅለው የተፈጸሙ የወንጀል ድርጊቶች መሆናቸውን የሚሳይ ነው፤ በሌላ በኩል ድርጊቶቹ ሲያይዋቸው የነበሩትን ችግሮቸ ለመቅረፍ የተደረጉ በመሆኑ ከሙስና ወንጀሎችን አዋጅ ስልጣንን አላግባብ ከመጠቀም ድንጋጌ ጋር የሚያያዝ ሳይሆን የመንግስት ስራን በማያመች መንገድ ከመስራት ጋር የሚያያዙ ናቸው፤ ስለዚህ ከ1ኛ እስከ 5ኛ ባሉት ክሶች በተደራራቢ ወንጀል ተከላከሉ ሊባሉ አይገባም፤ በዚሁ መሠረት ከ1ኛ እስከ 5ኛ ያሉት ክሶች እንደ አንድ ክስ ታይተው አመልካቾች እና 10ኛ፤11ኛ እና 20ኛ ተከሳሾች የወንጀሉ ድርጊት በስራ ላይ እንዲውል የተወሰነውን ቃለ ጉባኤ በመያዛቸው እና በማጽደቅ እንዲሁም 10ኛ፤ 11ኛ፤20ኛ ተከሳሾች እና 13ኛ እና 14ኛ አመልካቾች በስራ ላይ በማዋል ውሎችን እና የተለያዩ ሰነዶችን በማዘጋጀት እና በማጽደቅ መሳተፋቸው የተረጋገጠባቸው በመሆኑ በአዋጁ 881/2007 አንቀጽ 13/3 ስር እንዲከላከሉ በማለት ብይን የሰጠ ሲሆን፤ 6ኛ ክስን በተመለከተ ደግሞ የቀረበው ማስረጃ 15ኛ አመልካች እና ከ22ኛ እስከ 24ኛ ያሉት ተከሳሾች የቴክኒክ ኮሚቴ በመሆን ሁለት ጊዜ የማጣራት ስራ ሰርተው ለከፍተኛው ኮሚቴ ያቀረቡ መሆናቸውን የሚያሳይ ነው፤ ይህ ኮሚቴ የመሬት ክምችትን ለማስመለስ በወጣው መመሪያ ቁጥር 12/2007 አንቀጽ 8/1 መሠረት መቋቋም ካለበት መስሪያ ቤቶች በሙሉ አልተቋቋመም፤ ይህም ይህን

ኮሚቴ ያቋቋመው የቤቱ ከፍተኛ ኮሚቴ የመንግስትን ስራ አመቺ ባልሆነ መንገድ መምራቱን የሚያሳይ ስለሆነ 1ኛ አመልካች እና 10ኛ እና 11ኛ ተከሳሾች በአዋጅ ቁጥር 881/2007 አንቀጽ 13/1/ሐ ስር እንዲከላከሉ፤ ከ15ኛ አመልካች እና ከ22ኛ እስከ 24ኛ ያሉት ተከሳሾችን ደግሞ አጣርተው ለበላይ ኮሚቴ ማቅረባቸው ብቻውን እራሱን ችሎ እንደ ወንጀል ድርጊት የሚወሰድ አይደለም በማለት ዓቃቤሕግ ያቀረበባቸውን ክስ እና ማስረጃ መካላከል ሳያስፈልጋቸው በነጻ እንዲሰናበቱ ሲል ብይን ሰጥቷል፡፡

በዚሁ መሠረት 1ኛ አመልካች በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 142/3 መሠረት ቃላቸውን የሰጡ ሲሆን ክሱን ለመከላከል ያስችለናል ያሉትን የመከላከያ ምስክሮችን አቅርበዋል አሰምተዋል የሰነድ ማስረጃም አቅርበዋል፡፡ ፍ/ቤቱም የግራቀኙን ማስረጃ ከመረመረ በኋላ ከ1ኛ እስከ 13ኛ ያሉት አመልካቾች እና 15ኛ ተከሳሽ ከ1998 እስከ 2001 ዓ.ም በስራ ላይ የነበረውን እና ፍጻሜ ሳያገኝ የቀረውን 45/55 የተባለ ሕገወጥ አሰራር በ21/09/2007 በሮቤ ከተማ አስተዳደር ከንቲባ ጽ/ቤት በያዙት ቃለ ጉባኤ በሕገወጥ መንገድ ለሰዎች ተላልፎ የነበረን መሬት ማስረጃ እንዲሰጥበት ማስደረጋቸው በቀረበው የሰነድ ማስረጃ በግልጽ ተረጋግጧል፤ 10ኛ፤ 11ኛ፤ 20 ተከሳሾች እና 14ኛ እና 15ኛ አመልካቾች በተመሳሳይ ቀን በ21/09/2007 በሮቤ ከተማ መሬት ልማት እና ማኔጅመንት ጽ/ቤት በተያያዘ ቃለ ጉባኤ ይህ በሕገወጥ መንገድ የተሰጠ የመሬት ይዞታ በከንቲባው ጽ/ቤት በተያዘ ቃለ ጉባኤ አቅጣጫ በተመሳሳይ መንገድ መፍትሄ እንዲያገኝ ማድረጋቸው ተረጋግጧል፤ ተከሳሾች ቀርበው የተከራከሩት ድርጊታችን ሕጋዊ ነው በማለት እንጂ ድርጊቱን አልፈጸምንም በማለት አልተከላከሉም፤ ድርጊቱ የተፈጸመበት ዓላማ 45/55 የተባለው ሙሉ በሙሉ በሕገመንግስቱ እና በሕጉ መሠረት ወደ ኋላ ተመልሶ መፍትሄ የሚሰጠው ከሆነ በተለይም በመንግስት ላይ የፖለቲካል ኢኮኖሚ ፈተና ሊሆን እንደሚችል መገንዘብ ይቻላል፤ በከተማ አስተዳደሩ ስሕተት ምክንያት ከገበሬው መሬት የገዙ ሰዎች እና አብዛኛው ገበሬ በዚህ መሬት ላይ ከ2005 ዓ.ም በፊት ግንባታ የገነባበት እና መሬቱን ያለማው በመሆኑ ይህንን ማሕበረሰብ የመንግስት መዋቅር በፈጠረው ስሕተት ምክንያት ማፈናቀል እና የሚገባቸውን የካሳ ክፍያ መክፈል ከፍተኛ ፈተና ነው፤ በመሆኑም የአመልካቾች ድርጊት ወንጀል ቢሆንም አመልካቾች ይህን ወንጀል የፈጸሙበት ዓላማ ከፍተኛ ሊያስብለው የሚችል አይደለም፤ ከአመልካቾች ስልጣን ጋር በተያያዘም ሁሉም አመልካቾች የከተማ አስተዳደሩ አመራሮች ቢሆኑም ከተማዋ የዞን ከተማ ያልሆነች እና ተጠሪነቷም ለዞን የነበረ ስለሆነ ስልጣናቸው በሙስና ወንጀሎች አዋጅ ቁጥር 433/97 አንቀጽ 2/5 ድንጋጌ መሠረት ከፍተኛ ነው ሊባል የሚችል አይደለም፤ በመሆኑም ወንጀሉን ከሚያከብዱት ምክንያቶች መካከል የደረሰው ጉዳት ከፍተኛ መሆኑ ብቻ ነው በማለት አመልካቾችን እና 10ኛ፤ 11ኛ፤ 15ኛ 20ኛ ተከሳሾችን የተከሰሱበትን የሕግ አንቀጽ በመለወጥ በአዋጅ ቁጥር 881/2007 አንቀጽ 13/2 መሠረት የጥፋተኝነት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

6ኛን ክስን በሚመለከት የቴክኒክ ኮሚቴው በመመሪያ ቁጥር 12/2007 መሠረት መቋቋም ካለባቸው ተቋሚት ተወካይ ተሚልቶ ያልተቋቋም መሆኑን የሚያሳይ በመሆኑ የቴክኒክ ኮሚቴውን ያቋቋመው አካል የመንግስትን ስራ አመቺ ባልሆነ መንገድ በመምራት የሚጠየቅ ይሆናል፤ የቴክኒክ ኮሚቴው አባላት መመረጣቸውን በቀን 10/06/2007 ዓ.ም የጻፈው 2ኛ አመልካች አልተከሰሰም፤ 1ኛ አመልካች በሕጉ አግባብ ባልተመረጠ በዚህ ኮሚቴ የቀረበውን ቃለጉባኤ በማጽደቅ በ30/07/07 በበላይ ኮሚቴው የተያዘን ቃለ ጉባኤ የመራው እና በሸኚ ደብዳቤ ለዞን የላከው 1ኛ አመልካች መሆኑ ተረጋግጧል፤ 10ኛ እና 11ኛ ተከሳሾች ይህንን ቃለ ጉባኤ መያዛቸው እና ይህ በሕገወጥ መንገድ የተመረጠው ኮሚቴ ያቀረበው ውጤት እንዲጸድቅ ማድረጋቸው ተረጋግጧል፤ የ1ኛ አመልካች መከላከያ ማስረጃዎች ይህ ኮሚቴ በሕጉ አግባብ ባለመመረጡ የተፈጠረ ችግር ስለሌለ ድርጊቱ ሕገወጥ አይደለም በማለት የመሰከሩ ቢሆንም በዚህ ማጣራት ውስጥ የአጣሪ ኮሚቴው ስላልተከሰሰ እንጂ ፕሎትን የመዝለል ችግሮች የተፈጠሩ መሆናቸው በዓቃቤሕግ 7ኛ ክስ እና ከቀረበው የሰነድ ማስረጃ መረዳት የሚቻል በመሆኑ በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 32/1/ሀ እና በአዋጅ ቁጥር 881/2007 አንቀጽ 13/1/ሐ ስር ጥፋተኞች ናቸው በማለት የጥፋተኝነት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡፡

በመቀጠልም ቅጣቱን በቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 2/2006 መሠረት በማስላት 1ኛ አመልካች በስምንት ዓመት ጽኑ እስራት እና በብር 20,000፤ 2ኛ፤3ኛ፤6ኛ፤7ኛ፤9ኛ እና ከ11ኛ-15ኛ ያሉት አመልካቾች በስድስት ዓመት ጽኑ እስራት እና በብር 15,000 ፤ 4ኛ፤5ኛ፤8ኛ፤10ኛ በሰባት ዓመት ጽኑ እስራት እና በብር 16,000 የገንዘብ መቀጮ እንዲቀጡ ሲል ወስኗል፡፡

አመልካቾች ይህን ውሳኔ በመቃወም ለክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የይግባኝ አቤቱታ ያቀረቡ ቢሆንም አቤቱታቸው ተቀባይነት አላገኘም፡፡ አመልካቾች በመቀጠል ለክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አቤቱታ አቅርበዋል፡፡ የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ግራቀኙን ካከራከረ በኋላ የስር ፍ/ቤቶች የሰጡትን የጥፋተኝነት ውሳኔ ተገቢ ነው በማለት ያጸና ሲሆን በቅጣት ረገድ ግን ቅጣቱን አሻሽሎ 1ኛ አመልካች በአምስት ዓመት ከስድስት ወር ጽኑ እሥራት እና በብር 7,000 የገንዘብ መቀጮ ከ2ኛ እስከ 15ኛ ያሉት አመልካቾች ደግሞ በአምስት ዓመት ጽኑ እሥራት እና በብር 5,000 የገንዘብ መቀጮ እንዲቀጡ ሲል ወስኗል፡፡

የሰበር አቤቱታው የቀረበው ይህን ውሳኔ በመቃወም መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስሕተት ተፈጽሞበታል በሚል ሲሆን ይዘቱም፡- የአመልካቾች ድርጊት ወንጀል ነው ተብሎ በሕግ አልተደነገገም፤ አከራካሪው መሬት በመንግስት ፈቃድ በከተማ ነዋሪዎች እጅ የገባው በ1998 ዓ.ም ሲሆን ከ1998 ዓ.ም ጀምሮ እስከ 2001 ዓ.ም ድረስ ግንባታ ገንብተውበታል፤ አመልካቾች በ2007 ዓ.ም በሃላፊነት ስንመደብ ይዞታው ባዶ ቦታ አልነበረም፤ መንግስት ከከተማው ነዋሪዎች ጋር በገባው ውል መሠረት ነዋሪዎቹ ክፍያ ከፍለው ደረሰኝ ይዘው ነበር፤ አመልካቾች በያዝነው ቃለጉባኤ የወሰነው ከ1998 ዓ.ም እስከ 2001

ዓ.ም ድረስ ለክሱ መነሻ የሆነው መሬት ባለይዞታ የሆኑ ነዋሪዎች የሊዝ አዋጅ ከመታወጁ በፊት በመሬቱ ላይ ግንባታ ፈጽመው አልምተው እየተገለገሉበት ለሚገኙት ነዋሪዎች ብቻ መንግስት በውል በገባው ግዴታ መሠረት በሕጉ አግባብ የይዞታ ማረጋገጫ ሰነድ እንዲሰጣቸው ነው፤ የጠቅላይ ሚንስትር ጽ/ቤት ስራው በአስቸኳይ እንዲሰራ ያዘዘ በመሆኑ ድርጊቱ እንደ ወንጀል ሊቆጠር አይገባም፤ አመልካቾች ባዶ መሬት ሰጥተዋል የሚል ክስ አልቀረበብንም፤ አመልካቾች ከ2004 ዓ.ም በኋላ በተያዘ ይዞታ ላይ የባለቤትነት ማረጋገጫ ካርታ እንዲሰጥ ያስተላለፍነው ውሳኔ ሳይኖር የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የጠቅላይ ሚንስትር ጽ/ቤት መመሪያ አመልካቾችን አይመለከትም ማለቱ አግባብ አይደለም፤ የስር ፍ/ቤት 3ኛ፤ 4ኛ፤ 5ኛ እና 16ኛ ተከሳሾች በሕዝባዊ ድርጅት ስር የሚመደበው የኦህዴድ ተሿሚዎች በመሆናቸው አዋጁም በእነሱም ላይ ተፈጻሚነት አለው ማለቱ አግባብ አይደለም፤ አመልካቾች ክሱን እንድትከላከሉ በማለት የተሰጠው ብይንም ሆነ ክሱን ተከላክለን ሳለ አልተከላከላችሁም በማለት የተሰጠው የጥፋተኝነት እና የቅጣት ውሳኔ አግባብ አይደለም፤ በ21/09/2007 በተፈረመ ቃለ ጉባኤ የፈጸምነው ድርጊት ወንጀል ተብሎ ባልተከሰስንበት ይህን ቃለጉባኤ መነሻ በማድረግ ጥፋተኛ መባላችን አግባብ አይደለም፤ ወንጀሉን ለማቋቋም የሚያስችሉ ፍሬነገሮች አልተሟሉም፤ በቅጣትም ረገድም የዓቃቤሕግን ማክበጃ በመቀበል እና አመልካቾች ያቀረብነውን ማቅለያዎችን ውድቅ በማድረግ የተሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል የሚል ነው፡፡

የአመልካቾች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ 45/55 በሚል ይዞታቸው ለልማት ለተወሰደባቸው ሰዎች ማካካሻነት በ1998 ዓ.ም የተሰጠ እና ሕጋዊ እንዲሆንላቸው ገበሬዎቹ መንግስትን ጠይቀው በዚህ መነሻነት መስመር ለማስያዝ አመልካቾች በስራ በሃላፊነት በቃለ-ጉባኤ የወሰኑት ውሳኔ ሕገወጥ ነው በሚል ጥፋተኛ የመባላቸውን አግባብነት ከተከሰሱበት የሕግ ድንጋጌ አንጻር ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ በዚህ ችሎት እንዲታይ ተደርጓል፡፡

የተጠሪ መልስ ይዘት በአጭሩ፡- አመልካቾች መሬት ከአርሶ አደር ሲነጠቅ አግባብ ባለው ሕግ መሠረት ካሳ መክፈል እና በሕግ አግባብ የተፈቀደለትን መሬት መስጠት ሲገባቸው ይህን አለማድረጋቸው፤ ከአርሶ አደሩ በሕገወጥ መንገድ 3ኛ ወገኖች ከገበሬው የገዙትን መሬት ለመንግስት ገቢ ሳያደርግ ሽያጭ ማካሄዳቸው፤ ከአርሶ አደሩ መሬት የገዙትን ሰዎች ነባር ይዞታ ወይም የድሮ ይዞታ በማለት ማስተናገዳቸው፤ የክልሉን የመሬት ሕግ መመሪያ በመጣስ በክሱ የተመለከተውን ድርጊት መፈጸማቸው የመንግስትን ስራ በማያመች አኳሃን መምራት ስለሆነ በአዋጅ ቁጥር 881/2007 መከሰሳቸው እና ጥፋተኛ መባላቸው ተገቢ ነው፤ በ45/55 መሬት በእጃቸው የገባው አርሶ አደሮች በድሮ ይዞታ ስር መውሰድ ሲገባቸው በሊዝ ስር እንዲገባ መደረጉ፤ ከአርሶአደሮች በፊት መሬት በሕገወጥ መንገድ የገዙና በከተማው አስተዳደር እውቅና ተሰጥቶአቸው ማስረጃ የተሰጣቸው በሕገወጥ ይዞታ እና ውዝፍ ስር የሚካተቱ አይደሉም፤ ከጠቅላይ ሚኒስቴር መ/ቤት የተላለፈው መመሪያ የሚመለከተው ከ2004 ዓ.ም

በፊት የነበረውን ሕገወጥ ይዞታና ውዝፍ እንዲ አመልካቾች የፈጸሙትን ድርጊት የማይመለከት በመሆኑ የስር ፍ/ቤት በአመልካቾች ላይ ያስተላለፈው የጥፋተኝነት እና የቅጣት ውሳኔ ሊጸና ይገባል የሚለው ነው፡፡ አመልካቾችም የሰበር አቤቱታቸውን በማጠናከር የመልስ መልስ ሰጥተዋል፡፡

በአመልካቾች ላይ የቀረቡት ክሶች የመንግስትን ስራ በማያመች አኳሃን መምራትን የሚመለከቱ ናቸው፡፡ የመንግስትን ስራ በማያመች አኳሃን መምራት ደግሞ የሙስና ወንጀል ነው፡፡ የሙስና ወንጀል በልዩ ሕግ የተደነገገ ሲሆን ሕጉ ከወጣለት ዓላማ አንጻር በአዋጁ ወንጀል ናቸው ተብለው የተደነገጉት ድንጋጌዎች ወንጀል መሆናቸውን ለማሳየት የራሱ የሆነ መስፈርት በልዩ ሕጉ የተቀመጠለት ከመሆኑ አኳያ የስር ፍ/ቤቶች አመልካቾች ክሱን እንዲከላከሉ ብይን መስጠታቸው፤ አመልካቾች መካላከያ ማስረጃ ካሰሙ በኂላም በዓቃቤሕግ ማስረጃ የተረጋገጠባቸውን ፍሬነገሮች አላስረዱም በማለት በአመልካቾች ላይ የጥፋተኝነት ውሳኔ እና የቅጣት ውሳኔ ማስተላለፋቸው ከሙስና ወንጀሎች አዋጅ፤ ከመደበኛው የወንጀል ሕግ እና ከወንጀለኛ መቅጫ ስነስርዓት ሕጉ እንዲሁም የተከሰሱ ሰዎች በሕገመንግስቱ ከተጠበቁላቸው መሠረታዊ መብቶች ጋር በማገናዘብ በጥንቃቄ ሊታይ የሚገባው ነው፡፡ በመሆኑም በዚህ ችሎት ምላሽ ሊሰጠው የሚገባው የክርክሩ መሠረታዊ ጭብጥ፡-

1. የስር ፍ/ቤት አመልካቾች የቀረበባቸውን ክስ እንዲከላከሉ ብይን መስጠቱ ተገቢ ነው? ወይስ አይደለም?
2. የስር ፍ/ቤት አመልካቾች የቀረበባቸውን ክስ እንዲከላከሉ ብይን መስጠቱ ተገቢ ነው ከተባለ አመልካቾች ባቀረቡት መከላከያ የቀረበባቸውን ክስ ተከላክለዋል? ወይስ አልተከላከሉም? የሚሉት ናቸው፡፡

<u>የመጀመሪያውን ጭብጥ በተመለከተ</u>፡-

በአመልካቾች ላይ የቀረቡት ክሶች የመንግስት ስራን በማያመች አኳሃን መምራትን የሚመለከቱ ናቸው፡፡ ዓቃቤሕግ አመልካቾች በክሱ የተገለጸውን ድርጊት ስለመፈጸማቸው ለማስረዳት የሰው ምስክሮችን እና የተለያዩ የሰነድ ማስረጃዎችን አቅርቧል፡፡ የስር ፍ/ቤት አመልካቾች የቀረበባቸውን ክስ እንዲከላከሉ ብይን መስጠቱ ተገቢ ነው? ወይስ አይደለም? ለሚለው ነጥብ ምላሽ ከመስጠታችን በፊት ከመነሻውም ቢሆን ዓቃቤሕግ አመልካቾች በክሱ የተመለከተውን ድርጊት ፈጽመዋል ለማለት ማስረዳት የሚጠበቅበት ምንድነው? የሚለው መሠረታዊ ነጥብ ምላሽ ማግኘት አለበት፡፡

የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 23/2 አንድ ወንጀል ተደረገ የሚባለው ወንጀሉን የሚያቋቁሙለት ሕጋዊ፤ ግዙፋዊ እና ሞራላዊ ፍሬነገሮች በአንድነት ተሟልተው ሲገኙ ብቻ ነው በማለት ይደነግጋል፡፡ ከዚህ ድንጋጌ ይዘት መገንዘብ የሚቻለው ዓቃቤሕግ መደበኛውን የወንጀል ሕግ ወይም ወንጀል መፈጸሙን ለማስረዳት ልዩ መስፈርትን የማያስቀምጡ ልዩ ሕጎችን መሠረት በማድረግ ክስ ሲያቀርብ

ተከሳሹ ወንጀል ለመስራት የነበረውን የሀሳብ ክፍል የማስረዳት ሸክም ያለበት መሆኑን እና ይህን ካላስረዳ በቀር ተከሳሹ የቀረበበትን ክስ እንዲከላከል ብይን መስጠት የማይቻል መሆኑን ነው፡፡

በሌላ በኩል የሙስና ወንጀሎች በፈጣን ሁኔታ የመቀያየር ባሕርይ ስላላቸው አጠቃላይ ወንጀሎችን በሚደነግገው የወንጀል ሕግ ውስጥ እንዲካተቱ ከማድረግ ይልቅ ራሱን በቻለ አዋጅ እንዲደነገጉ ተመራጭ ሆኖ በመገኘቱ በሐገራችን የሙስና ወንጀሎች አዋጅ በልዩ ሕግ ወጥቶ የተለያየ ማሻሻያ ሲደረግበት ቆይቷል፡፡ ይህንኑ መሠረት በማድረግም የሙስና ወንጀሎች አዋጅ ቁጥር 881/2007 ወጥቶ ስራ ላይ ውሏል፡፡

የሙስና ወንጀሎች አዋጅ ቁጥር 881/2007 አንቀጽ 3 ተቃራኒ ማስረጃ ካልቀረበ በቀር የሙስና ወንጀሎቹ የተፈጸሙት የማይገባ ጥቅም ለማግኘት ወይም ለማስገኘት ወይም ሌላውን ሰው ለመጉዳት መሆኑ በተደነገገ ጊዜ በድንጋጌው የተመለከተው ግዙፋዊ ፍሬነገር መፈጸሙ ከተረጋገጠ ድርጊቱ የተፈጸመው ተገቢ ያልሆነ ጥቅም ለራስ ለማግኘት ወይም ለሌላ ሰው ለማስገኘት ወይም የሶስተኛ ወገንን መብት ወይም ጥቅም ለራስ ለማግኘት ወይም ለሌላ ሰው ለማስገኘት ወይም የሶስተኛ ወገንን መብት ወይም ጥቅም ለመጉዳት እንደሆነ ይገመታል በማለት ይደነግጋል፡፡ ይህም የሙስና ወንጀል በሙስና ወንጀል አድራጊው እና በወንጀሉ በሚጠቀመው ሰው መካከል ስምምነት የሚፈጸም በመሆኑ ዓቃቤሕግ ወንጀሉ መፈጸሙን በበቂ ሁኔታ የማስረዳት ሸክም ከባድ የሚያደርግበት በመሆኑ ክሱ የቀረበው ያለአግባብ ነው የሚለው ወገን የዓቃቤሕግ ክስ ትክክል አለመሆኑን ያስረዳ ዘንድ የማስረዳት ሸክሙ ይዛወርበታል፡፡ ይህም ዓቃቤሕግ ክስ ሲመሰርት በሌሎች ወንጀሎች ላይ ከተጣለበት በመደበኛነት ከሚታወቀው የማስረዳት ሸክም ወጣ ያለ ልዩ ሁኔታ መሆኑን የሚያሳይ ነው፡፡

ከላይ ከተመለከቱት የወንጀል ሕጉ አንቀጽ 23/2 ድንጋጌ እና የሙስና ወንጀሎች አዋጅ ቁጥር 881/2007 አንቀጽ 3 ድንጋጌ ጣምራ ንባብ መገንዘብ የሚቻለው ዓቃቤ ሕግ መደበኛውን የወንጀል ሕግ ወይም ወንጀል መፈጸሙን ለማስረዳት ልዩ መስፈርትን የማያስቀምጡ ልዩ ሕጎችን መሠረት በማድረግ ክስ ሲያቀርብ በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 23/2 መሠረት የተከሳሹን የሀሳብ ክፍል እንዲያረጋግጥ የተጣለበት የማስረዳት ሸክም ለሙስና ወንጀሎች በተመሳሳይ ተፈጻሚ የማይሆን መሆኑን፤ ይልቁንም በሙስና ወንጀሎች አዋጅ ቁጥር 881/2007 አንቀጽ 3 በተደነገገው መሠረት በድንጋጌው የተመለከተው ግዙፋዊ ፍሬነገር መፈጸሙ ከተረጋገጠ ተከሳሹ በድንጋጌው የተመለከተውን ግዙፋዊ ፍሬነገር ለመፈጸም የነበረውን የሀሳብ ክፍል ተቃራኒ ማስረጃ በማቅረብ እንዲያስተባብለው የማስረዳት ሸክሙ ወደ ተከሳሹ የሚዛወር መሆኑን ነው፡፡ ስለሆነም ዓቃቤሕግ ማስረዳት የሚጠበቅበት በድንጋጌው የተመለከተው ግዙፋዊ ፍሬነገር መፈጸሙን ብቻ እንጂ ተከሳሹ ወንጀል ለመፈጸም የነበረውን የሃሳብ ክፍል አለመሆኑን እና የተከሳሹን የሀሳብ ክፍል አላስረዳህም ተብሎ ተከሳሹን መከላከል ሳያስፈልገው በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 141 መሠረት ነጻ ሊያወጣው የሚችል አይደለም፡፡

ከላይ የተመለከቱትን ድንጋጌዎች መሠረት በማድረግ ዓቃቤሕግ በሕጉ አግባብ የተጣለበትን አመልካቾች በተከሰሱበት ድንጋጌ ላይ የተመለከተውን ግዙፋዊ ፍሬነገር መፈጸሙን አስረድቷል? ወይስ አላስረዳም? ለሚለው ነጥብ ምላሽ ለመስጠት በስር ፍ/ቤት የተሰሙትን የዓቃቤሕግ ማስረጃዎች ይዘት መመልከት አስፈላጊ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

1ኛ የዓቃቤሕግ ምስክር ለፍ/ቤቱ የሰጡት የምስክርነት ቃል ይዘት ፡-

ከሌሎች ሰዎች ጋር በመሆን ጉዳዩን ያጣሩ መሆኑን፤ የሮቤ ከተማ ማስተር ፕላን የሮቤ ዙሪያ ቀበሌ እና ሆራ ቦቃን የሚያቅፍ መሆኑን፤ በከተማው ማስተር ፕላን ስር ያለ ቢሆንም በሲናና ወረዳ እና በሮቤ ከተማ መካከል ርክክብ ያልተፈጸመ በመሆኑ የከተማው አስተዳደር በመሬቱ ላይ ማዘዝ አይችልም በማለት የመለሱ መሆኑን፤ ባክሎግ ለማስመለስ የተቋቋሙ ኮሚቴዎችን እና ቃለጉባኤ ያዩ ቢሆንም ሰው ሲፈርም ያላዩ መሆኑን፤ በቴክኒክ ኮሚቴ ውስጥ የተቋቋሙት አዋጁ የማይፈቅድላቸው መሆናቸውን፤ በአንድ ኮሚቴ የተደረገው ማጣራት 530 ሰዎች ሲሆኑ ሁለተኛው ኮሚቴ ደግሞ 56 ሰዎችን ጨምሮ ያቀረበ መሆኑን፤ 45/55 የሚለው አሰራር ገበሬው ካለው መሬት 45% የሚወስድ ሲሆን 55% ለመንግስት የሚገባ መሆኑን፤ በ21/09/2007 ዓ.ም የተጻፈን ቃለጉባኤ መነሻ በማድረግ የከተማ አስተዳደር በገንዘብ ሊከፈል የሚችል ክፍያ ስለሌለው እንዲፈቀድልን በማለት የኦሮሚያ መሬት ልማት እና ማኔጅመንትን እና ዞኑን በደብዳቤ የጠየቁ መሆኑን፤ ለደብዳቤዎቹ የተሰጠ ምላሽ ማግኘት ያልቻሉ መሆኑን፤ 45/55 የሚባል አሰራር በሕግ የሌለ መሆኑን፤ ካሳ የሚከፈልበት መንገድ በሕጉ የተቀመጠ ቢሆንም በሕጉ መሠረት ያልተከፈለ መሆኑን፤ በገበሬው መሬት ላይ በከተማው አስተዳደር እና በሲናና ወረዳ መካከል ርክክብ ያልተደረገ መሆኑን፤ 45/55 የተባለው አሰራር በሮቤ ከተማ እና በሲናና ወረዳ መካከል ሲስፋፋ የነበረው ከ1998ዓ.ም እስከ 2001 ዓ.ም መሆኑን፤ ከሲናና ወረዳ ወደ ሮቤ ከተማ በገባ መሬት የተለያዩ መንግስታዊ ተቋማት የተሰሩ መሆኑን፤ ገበሬው በ45/55 ከተሰጠው መሬት ለግለሰብ አስተላልፎ አብዛኛው እጅ ከ2007 ዓ.ም በፊት ግንባታ የተገነባበት መሆኑን፤ መንግስት በወሰደው 55% መሬት ላይ ማስረጃ አለመመርመራቸውን፤ በ2004 ዓ.ም እና በ2005 ዓ.ም በገበሬው እና በከተማው አስተዳደሩ መካከል ክርክር ተነስቶ የነበረ መሆኑን፤ 45/55 የተባለው አሰራር የሕዝብን ጥያቄ እንመልሳለን በሚል የተሰራ ቢሆንም መንግስት የሕዝብን ጥያቄ የሚመልስበት መመሪያ ያለው መሆኑን፤ 45/55 የተባለው አሰራር ሲጀመር አመልካቾች በከተማው አስተዳደር በሀላፊነት ላይ ያልነበሩ መሆኑን በመግለጽ መመስከራቸውን የሚያሳይ ነው፡፡

2ኛ የዓቃቤ ሕግ ምስክር ለፍ/ቤቱ የሰጠው የምስክርነት ቃል ይዘት ፡-

በአብዛኛው 1ኛ ምስክር ከሰጡት የምስክርነት ቃል ጋር ተመሳሳይ ይዘት ያለውን ምስክርነት የሰጡ ሲሆን በከንቲባው የሚመራው ኮሚቴ 530 ሰዎች በባክሎግ መሬት ማግኘት የሚገባቸው መሆኑን ያጣራ መሆኑን፤ 2ኛው ኮሚቴ 56 ሰዎችን ጨምሮ ያጣራ መሆኑን፤ 32 ሰዎች መሬት ተሰጥቷቸዋል

የተባለውን በሚመለከት ማስረጃ የሌላቸው መሆኑን፤ በቃለ ጉባኤ ላይ 45/55 የተባለው አሰራር በተመለከተ ገበሬው የ45% ድርሻውን ለግለሰቦች ማስተላለፍ ይችላል በማለት የተገለጸ ቢሆንም በምን አግባብ እንዲሚያስተላልፍ የማያውቁ መሆኑን፤ አመልካቾች 45/55 በስራ ላይ እንዲውል እንዲፈቀድላቸው ላቀረቡት ጥያቄ የተሰጠ መልስ ያላዩ መሆኑን፤ 79 ለሆኑ ገበሬዎች በ45/55 መሬታቸው የተሰጣቸው መሆኑን በመግለጽ መመስከራቸውን የሚያሳይ ነው፡፡

3ኛ የዓቃቤ ሕግ ምስክር ለፍ/ቤቱ የሰጠው የምስክርነት ቃል ይዘት ፡-

ከ76 ገበሬዎች ጋር በተያያዘ የቀረበው ማስረጃ በከተማው ድንበር ያሉ ገበሬዎች ቤተሰቦች ስፋት፣ መሬቱ አገልግሎቱ እና ደረጃው ምን እንደሆነ የሚገልጽ ነገር የሌለው መሆኑን፤ ገላጭ ነገር ባለማግኘታቸው ምክንያት በደንብ 155/2005 መሠረት ከ200 ካ.ሜትር በላይ ያለው ገበሬ በኪራይ ስርዓት፤ ከዚህ በላይ ከሆነ 500 ካ.ሜ ለባለይዞታው ተሰጥቶ ከዚህ የቀረው ደግሞ የመንግስት መሬት ስለሚሆን መንግስት ከዚህ መሬት ሊያገኝ የሚገባው ገቢ ነው በማለት ያሰሉ መሆኑን፤ የሮቤ ከተማ የከተማው ኤጀንሲ ከተዘጋጀ በኋላ 3ኛ ደረጃ የነበረች መሆኑን ከሐምሌ ወር 2007 ዓ.ም ጀምሮ ወደ 2ኛ ለደረጃ ያደገች መሆኑን፤ መሬቱ በመመሪያው መሠረት ቢተላለፍ ኖሮ 1ኛ ደረጃ ወይም 2ኛ ደረጃ በማለት ለይተው በዞኑ ኮሚቴ በተያዘው ቃለ ጉባኤ ላይ ተንተርሰው የሰሩ መሆኑን፤ የሮቤን ከተማ ስታንዳርድ ትልቁን በ 200 ካ.ሜ ወስደን በደንብ ቁጥር 155/2005 መሠረት የመሬቱ ይዞታ ባለቤት ለሆነው ገበሬው 500 ካ.ሜ ይጸድቅለታል፤ ከ500 ካ.ሜ በላይ የሆነው ይወሰድበታል፤ 105 ካ.ሜ ከሆነ ተመዝግቦ ይቀመጣል፤ በዚህ መሠረት መንግስት ማግኘት ይገባው የነበረውን ገንዘብ አስልተው ያስቀመጡ መሆኑን በመግለጽ መመስከራቸውን የሚያሳይ ነው፡፡

4ኛ የዓቃቤ ሕግ ምስክር ለፍ/ቤቱ የሰጠው የምስክርነት ቃል ይዘት ፡-

የሮቤ ከተማ መሬት ማኔጅመንት የመዝገብ ቤት አገልግሎት አቀናጅ መሆናቸውን፤ በኦሮሚያ ጸረ ሙስና ኮሚሽን 311 ሰዎችን በሚመለከት እንዲያጣሩ ተጠይቀው 47 ሰዎችን ማግኘት ያልቻሉ መሆኑን፤ 47ቱ ሰዎች ስራ በነበረበት ጊዜ ደረሰኝ ቆርጠው መዝገብ ያስከፈቱ መሆኑን፤ ውል ሳይሞሉ የቀሩ ብዙ ሰዎች የነበሩ መሆኑን፤ ውል ተሞልቶላቸው ባለስልጣኑ ሳይፈርምበት የቀረባቸው ሰዎችም የነበሩ መሆኑን፤ 47ቱ ሰዎች መሬት አላቸው ተብሎ የመጣላቸው ቢሆንም በመዝገብ ውስጥ ግን የሌለ መሆኑን፤ የተለያዩ ሰዎች እየመጡ ለመስተናገድ ይጠይቁ የነበረ እና ስራው ይቁም ስለተባለ ልናስተናግዳችሁ አንችልም እያሉ ይመልስዋቸው የነበረ መሆኑን፤ ፍቃድ ያላቸው ሰዎች ብቻ ደረሰኝ የቆረጡ መሆኑን፤ 47ቱ ሰዎች ደረሰኝ ያላቸው ከመሆን ውጪ ለይተው የማያውቋቸው መሆኑን በመግለጽ መመስከራቸውን የሚያሳይ ነው፡፡

ዓቃቤ ሕግ ያቀረባቸው የሰነድ ማስረጃዎች ይዘት፡-

ዓቃቤ ሕግ ክሱን ለማስረዳት በርካታ የሰነድ ማስረጃዎችን ያቀረበ ሲሆን ዋነኞቹ አመልካቾች 45/55 የተባለ አሰራር እንዲፈቀድላቸው የያዟቸው ቃለጉባኤዎች እና ቃለ ጉባኤዎችን መሠረት በማድረግ ለበላይ አካል የጻፏቸው ደብዳቤዎች፣ በ45/55 ከገበሬዎች ተወስዷል የተባለው መሬት የገበሬው ድርሻ ነው የተባለው 45% በውሉ መሠረት ያልተላለፈ መሆኑን፣ በሰነድ ማስረጃ መሠረት የ76ቱ ገበሬዎች መሬት ይዞታ 919100 እንደሆነ የባክሎግ አጣሪ ኮሚቴው ከሚመለከታቸው መስሪያ ቤት በሙሉ ያልተቋቋመ መሆኑን፣ በቴክኒክ ኮሚቴው ሁለት ጊዜ የተጣራው ልዩነት ያለው መሆኑን የሚያሳይ ሪፖርት፣ ከከተማው መስፋፋት ጋር ተያይዞ በሮቤ ከተማ ስር የታቀፉት የገጠር ቀበሌዎች ላይ በሲናና ወረዳ እና በሮቤ ከተማ አስተዳደር መካከል ርክክብ አለመከናወኑን የሚያሳይ ደብዳቤ ለመሬት ክምችት ከተመዘገቡት 642 ሰዎች መሃከል 530 ሰዎች መሬት እንዲያገኙ መደረጉን፣ 98 ሰዎች ማግኘት የሌለባቸው መሆኑን መረጋገጡን እና በዚህ ረገድ እየተሰራ ያለው ስራ ያልተጠናቀቀ መሆኑን የሚያሳይ ቃለጉባኤ፣ ከተለያዩ ሰዎች ጋር የተደረጉ ውሎች ናቸው፡፡

ከላይ በዝርዝር እንደተመለከተው የዓቃቤ ሕግ የሰው ምስክሮች ለፍ/ቤቱ ከሰጡት የምስክርነት ቃል እና ዓቃቤሕግ ካቀረባቸው የሰነድ ማስረጃዎች ይዘት መገንዘብ የሚቻለው ዓቃቤሕግ ባቀረበው ማስረጃ አመልካቾች በተከሰሱበት የሙስና ሕግ ድንጋጌ ላይ የተመለከተው ግዙፋዊ ፍሬነገር መፈጸሙን ያረጋገጠ መሆኑን ነው፡፡ ዓቃቤ ሕግ መደበኛውን የወንጀል ሕግ ወይም ወንጀል መፈጸሙን ለማስረዳት ልዩ መስፈርትን የማያስቀምጡ ልዩ ሕጎችን መሠረት በማድረግ ክስ ሲያቀርብ በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 23/2 መሠረት የተከሳሹን የሀሳብ ክፍል እንዲያረጋግጥ የተጣለበት የማስረዳት ሸክም ለሙስና ወንጀሎች በተመሳሳይ ተፈጻሚ የማይሆን እና በሙስና ወንጀሎች አዋጅ ቁጥር 881/2007 አንቀጽ 3 በተደነገገው መሠረት በድንጋጌው የተመለከተው ግዙፋዊ ፍሬነገር መፈጸሙ ከተረጋገጠ ተከሳሹ በድንጋጌው የተመለከተውን ግዙፋዊ ፍሬነገር ለመፈጸም የነበረውን የሀሳብ ክፍል ተቃራኒ ማስረጃ በማቅረብ እንዲያስተባብለው የማስረዳት ሸክሙ ወደ ተከሳሹ የሚዛወር በመሆኑ የስር ፍ/ቤት ከ1ኛ እስከ 5ኛ ያሉት ክሶች እንደ አንድ ክስ ታይተው አመልካቾች የወንጀሉ ድርጊት በስራ ላይ እንዲውል የተወሰነውን ቃለ ጉባኤ በመያዛቸው እና በማጽደቃቸው በአዋጅ ቁጥር 881/2007 አንቀጽ 13/3 ስር እንዲከላከሉ፣ 1ኛ አመልካች ደግሞ ስድስተኛውንም ክስ በተጨማሪ እንዲከላከል በማለት ብይን መስጠቱ የሚነቀፍ ሆኖ አላገኘነውም፡፡

<u>ሁለተኛውን ጭብጥ በተመለከተ፡-</u>

የስር ፍ/ቤት አመልካቾች የቀረበባቸውን ክስ እንዲከላከሉ ብይን መስጠቱ በአግባቡ ነው ከተባለ አመልካቾች ባቀረቡት የመከላከያ ማስረጃ የቀረበባቸውን ክስ ተከላክለዋል? ወይስ አልተከላከሉም? የሚለው ሁለተኛው መሠረታዊ ጭብጥ አመልካቾች በስር ፍ/ቤት ካቀረቡት የመከላከያ ማስረጃ አንጻር

በአግባቡ ታይቶ ምላሽ ሊያገኝ የሚገባው ነው። ስለሆነም አመልካቾች በስር ፍ/ቤት ያቀረቡት የመከላከያ ማስረጃ ይዘት በቅድሚያ መመልከት አስፈላጊ ሆኖ አግኝተነዋል።

1ኛ አመልካች በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 142/3 መሠረት ለፍ/ቤቱ የሰጠው ቃል ይዘት፡-

አመልካቾች የመጡት በ2007 ዓ.ም መሆኑን፤ የከተማው አስተዳደር ለገበሬው ይዞታ ካሳ ለመክፈል የገንዘብ ችግር ስለነበረበት 45/55 የተባለው አሰራር ከ1998 እስከ 2000 ዓ.ም ባለው ጊዜ ውስጥ የተጀመረ መሆኑን፤፤ 55% የገበሬውን መሬት መንግስት ወስዶ ያለማው መሆኑን፤ 45% ደግሞ ለ3ኛ ወገን የተላለፈ መሆኑን፤ ወደኗላ ያለው 10 ዓመት ግንባታ ተገንብቶበት የለማ በመሆኑ፤ የሰብልን ካሳ ለመክፈል መሬቱ 10 ዓመት እዳሪ የነበረ በመሆኑ፤ የንብረት ካሳ ለመክፈል ንብረቱ በከተማ አስተዳደር ተወስዶ የራሱ መሆን የነበረበት በመሆኑን ምክንያት በአዋጅ 455/97 መሠረት ተፈጻሚ ያልተደረገ መሆኑን፤ የከተማ አስተዳደሩ እስከ ክልል መንግስት ድረስ ጥያቄ ሲያቀርብ የነበረ መሆኑን፤ ከክልሉ እና ከከተማው አስተዳደር ኮሚቴ ተቋቁሞ ጉዳዩ ሲታይ የነበረ መሆኑን ፤ መንግስት ባክሎግ የነበረበት በመሆኑ አዋጅ ቁጥር 721/2007 በስራ ላይ ለማዋል የጠቅላይ ሚንስትሩን ቢሮ በመጠየቅ የጠቅላይ ሚንስትሩ ቢሮም ጉዳዩ ለመጨረሻ ጊዜ መልስ እንዲያገኝ በጻፈው ደብዳቤ ፍቃድ የተሰጠ መሆኑን፤ በቀን 18/05/2007 ከጠቅላይ ሚንስትሩ ቢሮ ለክልሉ ፕሬዝደንት ጽ/ቤት በቀጥታ በተጻፈ ደብዳቤ ላይ ሁለት መሠረታዊ ነጥቦችን የያዘ ሲሆን እነኚህም 1ኛ ደረሰኝ ያላቸው ባክሎግ ደረሰኝ ቆርጠው መሬት ሳይገኙ የቀሩ ተስተናግደው ምላሽ እንዲሰጣቸው፤ 2ኛ መሬት ይዘው ቤት የሰሩት ሰዎች ሙሉ ሰነድ ሳይኖራቸው የቀሩት ለመጨረሻ ጊዜ እንዲስተናገዱ የሚል መሆኑን፤ በዚህ ደብዳቤ ላይ በመመስረት የፕሬዝደንት ጽ/ቤት ለክልሉ ኢንደስትሪ እና ከተማ ልማት ቢሮ እና ለክልሉ መሬት ኤጀንሲ በቀን 05/06/2007 ዓ.ም በጻፈው ደብዳቤ የተጠቀሱትን ጉዳዮች ለማስተናገድ እንዲችሉ በማለት የጻፈ መሆኑን፤ ይህን ለማስፈጸምም ሁለቱ ቢሮዎች እቅድ በማውጣት በየደረጃው ላሉ ኦረንቴሽን በመስጠት ወደ ስራ እንዲገባ አቅጣጫ የተቀመጠ መሆኑን፤ የክልሉን ሕግ እና መመሪያ መሠረት በማድረግ በባክሎግ በሕገወጥ ግንባታ እና ነባር ይዞታ ላይ መልስ እንዲሰጡ የተደረገ መሆኑን፤ ለገበሬው በካሳ የተሰጠው 45% ከከተማ መስተዳድሩ ጋር የፈጸሙት ውል በእጃቸው የነበረ በመሆኑ በመግለጽ ቃሉን መስጠቱን የሚያሳይ ነው።

1ኛ መካላከያ ምስክር የሰጡት የምስክርነት ቃል ይዘት፡-

በ1998 ዓ.ም በሮቤ ከተማ አባገዳ አዳራሽ ሰብስበው ከተማዋ ዞን ስለሆነች ልትለቁ ይገባል ያሏቸው መሆኑን፤ መሬቱን አንለቅም ሲሉ ልማትን ማደናቀፍ አትችሉም መንግስት እንዲሁም ሊወስድባችሁ ስለሚችል ካሳችሁን 45/55 እናደርግላችኋለን ያሏቸው መሆኑን፤ ካርኒ ሳይቆረጥላቸው በመቅረቱ ከ2005 እስከ 2006 አቤቱታ ሲያቀርቡ የነበረ መሆኑን፤ መፍትሄ እንዲሰጣቸው በየጊዜው ለነበሩ የክልሉ ፕሬዝደንቶች በተለያየ ጊዜ አቤቱታ ሲያቀርቡ የነበረ መሆኑን፤ ሀላፊዎቹም እናንተ ጥፋት

አልፈጸማችሁም ጥፋት የፈጸሙት እራሳችን እዛ ያስቀመጥናቸው ሰራተኞቸ ናቸው ከባክሎግ ጋር አንድ ላይ ተደምሮ እንዲስተካከልላችሁ እናደርጋለን ያሏቸው መሆኑን፤ በ1998 ዓ.ም ተሸንሽኖ የነበረን መሬት እና ቤት የተሰራበትን ዞረው እያሳዩ አጣርተው ለይተው ካርኒ ይቆረጥላቸው የሚል ድምጽ የተሰማ መሆኑን፤ ከዚህ በኂላ በአዳራሽ ሰብስበው ሊዝ የቆረጡባቸው መሆኑን ፤ አመልካቾችም በ1998 ዓ.ም የተመሩትን ሰዎች ወደ ኂላ ተመልሰው በ2007 ዓ.ም ሊዝ ያስከፈሏቸው መሆኑን ፤ ወደ ሊዝ በመለሷቸው ጊዜ 45/55 የተባለው ይዞታ ሁሉም ቤት የነበረበት መሆኑን፤ ለመንግስት የሰጡት መሬት የተለያየ ተቋማት ተሰርቶበት ሙሉ ለሙሉ ለመንግስት ጥቅም የዋለ መሆኑን በመግለጽ መመስከራቸውን የሚያሳይ ነው፡፡

2ኛ መከላከያ ምስክር የሰጡት የምስክርነት ቃል ይዘት

45/55 የተባለውን አሰራር በተመለከተ ከ1ኛ ምስክር ጋር ተመሳሳይ ይዘት ያለው ምስክርነት የሰጡ ሲሆን በተጨማሪም አብዛኛው ሰው በወቅቱ የግብርና ስራ አቁሞ ስለነበረ ቀለብ ያልነበረው መሆኑን፤ ሕዝቡ ለሰባት ስምንት ዓመታት እርሻ አቁሞ የራሱን መሬት እየገዛ የነበረ መሆኑን፤ የራሳችንን መሬት ሰጥተናችሁ መልሰን እንገዛለን ሲል የነበረ መሆኑን፤ አመልካቾች ወደ ሊዝ ስርዓት ይገባል 45/55 በሚለው ስርዓት አይፈጸምም ብለዋቸው የነበረ መሆኑን፤ በአመልካቾች የተሸነሸነ መሬት የሌለ መሆኑን፤ አመልካቾች በሊዝ ክፍያ ያስከፈሉበት ዓላማ የሕዝብን ችግር ለመፍታት መሆኑን፤ መሬት ወደ ከተማ ሲመለስ የመሬት ንጥቂያ በዝቶ የነበረ እና ግለሰቦች የተለያየ ማስረጃዎች አሰርተው በሰዎች ላይ ክርክር እያቀረቡ የነበረ መሆኑን፤ ዋስትናችን ምንድነው? በምን እንከላከላለን? በከተማ ድንበር ውስጥ አስገብታችሁ እንዳናገዝ ከልክላችሁናል ውል ሞልተናል ይህንን ውል ማፍረስ አንችልም የሚሉ ነጥቦችን አንስተው በእጃቸው ላይ ያለው ይዞታ እንዲጸድቅላቸው የጠየቁ መሆኑን፤ 45/55 ን እንደዳታ ተጠቅመው ውል የፈጸሙላቸው መሆኑን በመግለጽ መመስከራቸውን የሚያሳይ ነው፡፡

3ኛ መከላከያ ምስክር የሰጡት የምስክርነት ቃል ይዘት በአጭሩ፡-

45/55 የተባለውን አሰራር በተመለከተ ከ1ኛ እና 2ኛ ምስክር ከሰጡት ቃል ጋር ተመሳሳይ ይዘት ያለው ምስክርነት የሰጡ ሲሆን በተጨማሪም ከላይ ካሉት ጋር ተመሳሳይ በሆነ 45/55 ውል በፈረሙበት እለት ለሌላ ሰው ያስተላለፉ መሆኑን፤ በይዞታው ላይ .ቤት የተገነባበት መሆኑን፤ ከ2001 ዓ.ም ጀምሮ ካርኒ መቁረጥ ቆሟል በማለት የከለከሏቸው መሆኑን፤ መሬቱ በተወሰደባቸው ጊዜ አመልካቾች ያልነበሩ መሆኑን፤ አመልካቾች ከመምጣታቸው በፊት የፈጸሙት ውል እያለ አንፈጽምም በማለት በሊዝ ያስከፈሏቸው መሆኑን፤ በበፊቱ ውል እንዲፈጸምላቸው ሲጠየቁ መመሪያ ይከለክለናል ያሏቸው መሆኑን በመግለጽ መመስከራቸውን የሚያሳይ ነው፡፡

4ኛ መከላከያ ምስክር የሰጡት የምስክርነት ቃል ይዘት፡-

በወቅቱ የከተማው አስተዳደር ለገበሬው ካሳ ለመክፈል ገቢ ያልነበረው መሆኑን፤ ገበሬው የራሱን ግንባታ ሲገነባበት ሌላውን ደግሞ አሳልፎ ለሰው ሲሰጥ የነበረ መሆኑን፤ መሬት የመስጠት ጉዳይ ከቀን 16/09/2001 ዓ.ም ጀምሮ በወቅቱ በነበሩት የክልሉ ፕሬዝደንት በነበሩት የቆመ መሆኑን፤ ምስክሩ መሬት መስጠት ከቆመ ከአንድ ወር በኋላ ከንቲባ የሆኑ መሆኑን፤ ገበሬው በተለያየ ጊዜ እየቀረበ በመሬታቸው ላይ ማሕተም ተመቶበት ከንቲባ እና የማዘጋጃ ቤቱ ባለሙያ የፈረመበትን ውል ይዞ በመምጣት ካርኒ ቆርጣችሁ ባለይዞታችንን አረጋግጡልን በማለት ጥያቄ ሲያቀርብ የነበረ መሆኑን፤ ከገበሬው ላይ መሬትን በስጦታም ሆነ በሽያጭ የወሰዱትም ተመሳሳይ ጥያቄ ሲያቀርቡ የነበረ መሆኑን፤ ገበሬው መልስ ሊያገኝ ስላልቻለ እስከ ክልል አስተዳደር ድረስ በመሄድ ሲጠይቅ የነበረ መሆኑን፤ በ2007 ዓ.ም ምርጫ ሲቃረብ ጥያቄውን ለመመለስ መንግስት ባስተላለፈው መመሪያ በመንተራስ አመልካቾች የገበሬዎቹን ጥያቄ የመለሱ መሆኑን፤  አመልካቾች ከ1998 ዓ.ም ጀምሮ እስከ 2001 ዓ.ም በተሰራው ስራ ውስጥ ድርሻ የሌላቸው መሆኑን፤ የነባር ይዞታው ባለቤት ከ2001 ዓ.ም ጀምሮ የድሮ ይዞታ የመንግስት ክፍያን ከፍሎ ባለይዞታነቱ እንዲረጋገጥ የተደረገ መሆኑን፤ ከገበሬው ላይ ተላልፎለት መሬት ያገኘ ሰው ደግሞ የሊዝ መነሻ ዋጋ ክፍያን ከፍሎ ባለይዞታነቱ እንዲረጋገጥ የተደረገ መሆኑን በመግለጽ መመስከራቸውን የሚያሳይ ነው፡፡

5ኛ ምስክር የሰጡት የምስክርነት ቃል ይዘት፦

ምስክሩ የማዘጋጃ ቤቱ ስራ አስኪያጅ የነበሩ መሆኑን፤ ተንጠልጥለው የቆዩ ጉዳዮችን በሚመለከት የሚፈጸሙበትን ሁኔታ ስልጠና የወሰዱ መሆኑን፤ በጠቅላይ ሚንስቴር እና በክልል ደረጃ የተጻፉ ደብዳቤዎች ስለነበሩ 45/55 በዚህ ሊስተናገድ የሚችል መሆኑን፤ በ1997 እና በ1998 አካባቢ የከተማዋ ገቢ ከ 4,000,000 የማይበልጥ የነበረ በመሆኑ ለ10 ዓመት ወደ ኋላ ተመልሰው ካሳ መክፈል የማይቻል መሆኑ፤ መንግስት መሬት መስጠትን አግዶ ገበሬዎች የራሳቸውን ድርሻ መሬት ሲወስዱ የነበረ መሆኑን፤ መንግስትም የራሱን ድርሻ ወስዶ ሲያለማበት የቆየ መሆኑን፤ እስከ 500 ካ.ሜ ካርኒ ሲቆረጥበት የቆየ መሆኑን ፤ በወቅቱ የእገሌ ቤተሰብ ነኝ በማለት ደረሰኝ ይቆረጥልኝ በማለት አቤቱታ ሲያቀርቡ ካርኒ በመቁረጥ ይስተናገዱ የነበረ መሆኑን፤ ከሚፈቀደው ስታንዳርድ በላይ የጸደቀ የሌለ መሆኑን፤ ገበሬው ወደ ከተማ አስተዳደሩ እንዲሁም ወደ ክልሉ አስተዳደር በመሄድ ሃላፊዎች ያነጋገረ መሆኑን፤ የሕዝቡ ቅሬታ በመብዛቱ በአባገዳ አዳራሽ ሰብስበው አናግረዋቸው የደንብ ስለወጣ በአጭር ጊዜ ውስጥ መፍትሄ ይሰጣችኋል ያሏቸው መሆኑን፤ ለአመራሩም ኦረንቴሽን የተሰጠ መሆኑን፤ አመልካቾች ሳይጠናቀቅ ተንጠልጥሎ የቆየን ነገር ሕጋዊ መስመር አስይዘው ከማጠናቀቅ ውጪ 45/55ን በአዲስ መልክ የሰሩት ነገር የሌለ መሆኑን፤ 45/55 የተባለው አሰራር በዞንም በክልልም እንደጥሩ ምሳሌ ተወስዶ የነበረ መሆኑን፤ ገበሬው በራሱ ድርሻ ላይ ማስረጃ ያለው መሆኑን፤  ገበሬው ወደ ኋላ ተመልሶ በሊዝ እንዲከፍል ስለተደረገ የተጎዳው ገበሬው እንጂ በመንግስት ላይ የደረሰ ጉዳት የሌለ መሆኑን፤ ከከተማ አስተዳደር ጋር ውል የሌላቸው ሰዎች ሕጋዊ ያልተደረጉ መሆኑን፤ ግንባታ

የፈጸሙ እና ከገበሬው ውጪ ያሉ ሰዎች ደግሞ በሊዝ ስርዓት ባለቤትነታቸው የተረጋገጠ መሆኑን፣ ከገበሬው ጋር የተለያዩ ውሎች ሲደረጉ የነበረ መሆኑን፣ መንግስት 55% መብት እንዳለው ሁሉ ገበሬውም በ45% ላይ ሊያዝበት መብት ያለው መሆኑን በመግለጽ መመስከራቸውን የሚያሳይ ነው፡፡

6ኛ መከላከያ ምስክር የሰጡት የምስክርነት ቃል ይዘት፡-

.45/55 የተባለውን አሰራር በተመለከተ ሌሎች ምስክሮች ከሰጡት የምስክርነት ቃል ጋር በተመሳሳይ የመሰከሩ ሲሆን በተጨማሪም መንግስት በ2007 ዓ.ም በሊዝ መሸጋገሪያ ጊዜ ተይዘው የነበሩ መሬቶች በሊዝ መመሪያ ተጠቃለው እንዲስተናገዱ፣ በድሮ ይዞታ እና በሕገወጥ ግንባታ መካከል ተንጠልጥሎ የነበረ ይዞታ መፍትሔ እንዲያገኝ አቅጣጫ ያስቀመጠ መሆኑን፣ አስቀድሞ መሬቱ የገበሬው የራሱ የእርሻ መሬት ስለሆነ ገበሬው መሬቱን መኖሪያ ቤት ለማድረግ፣ በስጦታ ለማስተላለፍ መብት አለው፣ አመልካቾች በ2007 ዓ.ም 45/55 ን በማስቀጠል ለገበሬው ካሳ ሳይከፍሉ የወሰዱት መሬት የሌለ መሆኑን፣ አመልካቾች በ2007 ዓ.ም የሰሩት ነገር መሬቱ አስቀድሞ ስለተሰጠ ማስረጃ ብቻ መስጠት እንጂ መሬት ያልሰጡ መሆኑን፣ መጀመሪያ ከከተማ አስተዳደሩ ጋር በተደረገ ውል በተሰጠ መሬት ላይ መሟላት ያለበት መስፈርት በሙሉ መሟላቱን አረጋግጠው ሳይት ፕላን እና ማስረጃ የሰጡ መሆኑን በመግለጽ መመስከራቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ አመልካቾች በተጨማሪም በምስክሮቻቸው የተገለጸውን የምስክርነት ቃል የሚደግፍ የሰነድ ማስረጃ አቅርበዋል፡፡

እንግዲህ ከላይ በተገለጸው መሠረት አመልካቾች ደርጊቱን ለመፈጸም የቻሉበትን ምክንያት ካስረዱ አመልካቾች ባቀረቡት መከላከያ ማስረጃ የመንግስትን ስራ በማያመች አኳኃን መርታችኋል በማለት እንዲከላከሉ በተሰጠው ብይን መሠረት ተከላክለዋል ወይስ አልተከላከሉም ለማለት አመልካቾች በመከላከያ ማስረጃዎቻቸው እንዲያስተባብሉት የሚጠበቀው ምንድነው? የሚለው ለጉዳዩ አወሳሰን መሠረታዊ ነጥብ ነው፡፡ በተያዘው መሠረታዊ ጭብጥ ላይ ምላሽ ለመስጠት ከላይ በመጀመሪያው ጭብጥ ላይ የገለጽነውን የማስረዳት ሸክም ወደ አመልካቾች የተላለፈበትን ምክንያት በድጋሚ መመልከት አስፈላጊ ነው፡፡

አመልካቾች እንዲከላከሉ በማለት ብይን የተሰጠባቸው የአዋጅ ቁጥር 881/2007 አንቀጽ 13/3 እና 13/1/ሐ ድንጋጌ የማይገባ ጥቅም ለማግኘት ወይም ለማስገኘት ስልጣንን ወይም ሀላፊነትን ተጠቅሞ የመንግስትን ስራ በማያመች አኳኃን መምራት ወንጀል ነው፡፡ ዓቃቤሕግ በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 23/2 መሠረት የተከሳሹን የሀሳብ ክፍል እንዲያረጋግጥ የተጣለበት የማስረዳት ሸክም ለሙስና ወንጀሎች በተመሳሳይ ተፈጻሚ የማይሆን እና በሙስና ወንጀሎች አዋጅ ቁጥር 881/2007 አንቀጽ 3 በተደነገገው መሠረት በድንጋጌው የተመለከተው ግዙፋዊ ፍሬነገር መፈጸሙ በተረጋገጠ ጊዜ ተከሳሹ በድንጋጌው የተመለከተውን ግዙፋዊ ፍሬነገር ለመፈጸም የነበረውን የሀሳብ ክፍል ተቃራኒ ማስረጃ በማቅረብ እንዲያስተባብለው የማስረዳት ሸክሙ ወደ ተከሳሹ ይዞራል፡፡ ይህም ማለት አመልካቾች ድርጊቱን

የፈጸሙት የማይገባ ጥቅም ለማግኘት ወይም ለማስገኘት ወይም ሌላውን ሰው ለመጉዳት ነው በማለት አስቀድሞ ተይዞባቸው የነበረውን የሕግ ግምት ስራውን የመሩት የማይገባ ጥቅም ለማግኘት ወይም ለማስገኘት ወይም ሌላውን ሰው ለመጉዳት አለመሆኑን እና ስራውን በሚያመች አኳኋን የመሩ መሆኑን ሊያሳይ የሚችል ተቃራኒ ማስረጃ በማቅረብ ማስተባበል ይጠበቅባቸዋል ማለት ነው፡፡

ከላይ እንደተገለጸው በሙስና ወንጀሎች ግዙፋዊ ፍሬነገሩ መፈጸሙ በተረጋገጠ ጊዜ ተከሳሹ በድንጋጌው የተመለከተውን ግዙፋዊ ፍሬነገር መፈጸሙን የሕግ ግምት የሚያዝበት መሆኑ፤ ተከሳሹም ይህን አስቀድሞ የተያዘበትን የሕግ ግምት ተቃራኒ ማስረጃ በማቅረብ ሊያስተባብለው የሚችል በመሆኑ ፍ/ቤቶች ይህንኑ መሠረት በማድረግ ውሳኔ በሚሰጡበት ጊዜ ተገቢውን ሚዛን የጠበቀ ውሳኔ መስጠት ይጠበቅባቸዋል፡፡ ይህም በአንድ በኩል የሙስና ወንጀሎች አዋጅ የሕዝብ እና የመንግስትን ጥቅም ለማስጠበቅ የወጣ በመሆኑ ወንጀሉን ፈጽመዋል ተብለው ክስ የቀረበባቸው ሰዎች ወንጀሉን የፈጸሙ መሆኑ በተረጋገጠባቸው ጊዜ ተገቢውን ቅጣት ማግኘት ያለባቸው በመሆኑ፤ በሌላ በኩል ደግሞ የተከሰሱ ሰዎች የመሰማት መብታቸው ተጠብቆ በቀረበባቸው ክስ ጥፋተኛ መሆናቸው በማስረጃ እስካልተረጋገጠ ድረስ ጥፋተኛ ሆኖ ያለመቆጠር መብት ያላቸው መሆኑ ነው፡፡

ይህንኑ መሠረት በማድረግ ጉዳዩን እንደተመለከትነው አንድ ሰው የማይገባ ጥቅም ለማግኘት ወይም ለማስገኘት ወይም ሌላውን ሰው ለመጉዳት ሲል ስራን በማያመች አኳኋን መርቷል ለማለት ስራውን በሚያመቸ አኳሃን ለመምራት የሚያስችል ሕግ እና የተዘረጋ ስርዓት መኖሩ እና ተከሳሹ ይህንኑ ሕግ እና ስርዓት ተላልፎ ስራውን በማያመች አኳኋን የመራ መሆኑ ሊረጋገጥበት ይገባል፡፡

በያዝነው ጉዳይ 45/55 የተባለው አሰራር ከ1998 እስከ 2001 ዓ.ም ባለው ጊዜ ውስጥ የተጀመረ መሆኑን፤ አመልካቾች ወደ ሀላፊነት የመጡት በ2007 ዓ.ም መሆኑ፤ የከተማው አስተዳደር ለገበሬው ይዞታ ካሳ ለመክፈል የገንዘብ ችግር ስለነበረበት 45/55 የተባለው አሰራር የተጀመረ መሆኑን፤ በዚሁ መሠረት 45% ገበሬው በካሳ መልክ እንዲወስደው 55% የገበሬውን መሬት ደግሞ መንግስት እንዲወስድ የተደረገ መሆኑን፤ መንግስት በወሰደው 55% ድርሻው ላይ የተለያዩ ተቋማትን በመገንባት ያለማው መሆኑን፤ ገበሬው ደግሞ ድርሻው በሆነው 45% ከፊሉን ራሱ የወሰደ ከፊሉን ደግሞ ለ3ኛ ወገን ያስተላለፈ መሆኑን፤ ገበሬው ከከተማው አስተዳደር ጋር ውል ፈጽሞ የነበረ መሆኑን፤ ወደኋላ ያለው 10 ዓመት በመሬቱ ላይ ግንባታ ተገንብቶበት የለማ በመሆኑ፤ የሰብልን ካሳ ለመክፈል መሬቱ 10 ዓመት እዳሪ የነበረ በመሆኑ ምክንያት በአዋጅ 455/97 መሠረት ተፈጻሚ ያልተደረገ መሆኑን፤ የከተማ አስተዳደሩ እስከ ክልል መንግሰት ድረስ ጥያቄ ሲያቀርብ የነበረ መሆኑን፤ ከክልሉ እና ከከተማው አስተዳደር ኮሚቴ ተቋቁሞ ጉዳዩ ሲታይ የነበረ መሆኑን ፤ መንግስት ምላሽ ያልሰጠበት ባክሎግ የነበረበት መሆኑ፤ ገበሬው ተደራጅቶ በተለያየ ጊዜ ለነበሩ የክልሉ ፕሬዝደንቶች ጥያቄ ሲያቀርብ የነበረ መሆኑን፤ ሀላፊዎቹም እናንተ ጥፋት አልፈጸማችሁም ጥፋት የፈጸሙት እራሳችን እዛ

ያስቀመጥናቸው ሰራተኞች ናቸው ከባክ ሎግ ጋር አንድ ላይ ተደምሮ እንዲስተካከልላችሁ እናደርጋለን ያሏቸው መሆኑን፤ ገበሬው አስቀድሞ በነበረው አሰራር መሠረት ካርኒ እንዲቀረጥለት ሲጠይቅ አመልካቾች ይህንኑ ለመፈጸም ፈቃደኛ ያልነበሩ መሆኑን፤ የገበሬው ጥያቄ ገፍቶ እስከ ጠቅላይ ሚንስትር ጽ/ቤት ድረስ የደረሰ መሆኑን፤ የጠቅላይ ሚንስትሩ ቢሮም ጉዳዩ ለመጨረሻ ጊዜ መልስ እንዲያገኝ በጻፈው ደብዳቤ ደረሰኝ ያላቸው ባክሎግ ደረሰኝ ቆርጠው መሬት ሳያገኙ የቀሩ ተስተናግደው ምላሽ እንዲሰጣቸው፤ መሬት ይዘው ቤት የሰሩት ሰዎች ሙሉ ሰነድ ሳይኖራቸው የቀሩት ለመጨረሻ ጊዜ እንዲስተናገዱ የሚል መሆኑን፤ ይህንኑ መሠረት በማድረግ የክልሉ ፕሬዝደንት በጻፈው ደብዳቤ የተጠቀሱትን ጉዳዮች ለማስተናገድ እንዲችሉ በማለት የጻፈ መሆኑን፤ አመልካቾች ሳይጠናቀቅ ተንጠልጥሎ የቆየን ነገር ሕጋዊ መስመር አስይዘው ከማጠናቀቅ ውጪ 45/55 የተባለውን አሰራር በአዲስ መልክ ያልሰሩ መሆኑን፤ ገበሬው በራሱ ድርሻ ላይ ማስረጃ ያለው መሆኑን፤ ከከተማ አስተዳደር ጋር ውል የሌላቸው ሰዎች ሕጋዊ ያልተደረጉ መሆኑን፤ ግንባታ የፈጸሙ እና ከገበሬው ውጪ ያሉ ሰዎች ደግሞ በሊዝ ስርዓት ባለቤትነታቸው የተረጋገጠ መሆኑን፤ አመልካቾች በ2007 ዓ.ም የሰሩት ስራ መሬቱ አስቀድሞ ስለተሰጠ ማስረጃ ብቻ መስጠት እንጂ መሬት ያልሰጡ መሆኑን፤ መጀመሪያ ከከተማ አስተዳደሩ ጋር በተደረገ ውል በተሰጠ መሬት ላይ መሟላት ያለበት መስፈርት በሙሉ መሟላቱን ተረጋግጦ ማስረጃ የተሰጠ መሆኑን አመልካቾች ካቀረቡት መከላከያ ማስረጃ ይዘት መገንዘብ ይቻላል፡፡

ገበሬው ተገቢ የሆነ ካሳ ሳይከፈለው ከእርሻ መሬቱ ያለመፈናቀል መብት እንዳለው በሕገ-መንግስቱም ሆነ በክልሉ የመሬት ሕግ የተደነገገ ቢሆንም ገበሬው ከይዞታው ላይ እንዲነሳ በተደረገ ጊዜ ከተማዋ ካሳ ለመክፈል የሚያስችል የገንዘብ አቅም ያልነበራት መሆኑ፤ 45/55 የተባለው አሰራር በሕግ ያልተደነገገ ቢሆንም በወቅቱ የተፈጠረውን ችግር ለመቅረፍ ሲባል በወቅቱ በነበሩ ሀላፊዎች ሲተገበር የነበረ መሆኑ፤ ይህንኑ ተከትሎ መሬቱ ከፊሉ በገበሬው እጅ ከፊሉ ደግሞ ለተለያዩ ግለሰቦች የተላለፈ መሆኑን፤ በከተማው አስተዳደር ስሕተት ምክንያት ከገበሬው መሬት የገዙ ሰዎች እና አብዛኛው ገበሬ በዚህ መሬት ላይ ከ2005 ዓ.ም በፊት ግንባታ የገነባበት እና መሬቱን ያለማው በመሆኑ ሕብረተሰቡን ለማፈናቀል እና የሚገባውን የካሳ ክፍያ ለመክፈል ከፍተኛ ማሕበራዊ ቀውስ የሚፈጥር እና መንግስታዊ ኢኮኖሚውም ላይ ከፍተኛ ጫና የሚያመጣ መሆኑን፤ ከጠቅላይ ሚንስትር ጽ/ቤትም ሆነ ከክልሉ ፕሬዝደንት ለጉዳዩ መፍትሔ እንዲሰጥ በደብዳቤ የተገለጸ በመሆኑ፤ አመልካቾች ውሳኔ ሳይሰጥባቸው ተከማችተው ያሉ ጉዳዮችን ለመፍታት የነደፉትና የተገበሯቸው አሰራሮች መሆናቸውን በግራ ቀኙ የቀረቡት ማስረጃዎች የተረጋገጠ ሲሆን ይህ ደግሞ ሆነ ብለው ወይም በቸልተኝነት አንዱን አካል ለመጥቀም ወይም ለመጉዳት ከመነጨ ሀሳብ የተፈጸመ ተግባር ስለመሆኑ አስቀድሞ ተወስዶ የነበረውን የህግ ግምት ጥያቄ ላይ የሚጥል ነው፡፡ አመልካቾች በወቅቱ የነበረውን ሁኔታ መሠረት አድርገው የሠጧቸው ውሳኔያቸው ምንም ይሁን ምን የነበረውን ክፍተት በተገቢው አግባብ ለመድፈን

የተፈጸመ መሆኑን የሚያስገነዝብ በመሆኑ ስራውን የሰሩት የማይገባ ጥቅም ለማግኘት ወይም ለማስገኘት ወይም ሌላውን ሰው ለመጉዳት ነው የሚያስብል ሆኖ አላገኘነውም፡፡ በመሆኑም የስር ፍ/ቤቶች በአመልካቾች ላይ ያስተላለፉት የጥፋተኝነትም ሆነ የቅጣት ውሳኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት ነው በማለት በአብላጫ ድምጽ ወስነናል፡፡ ስለሆነም ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

## ውሳኔ

1. በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የባሌ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት አመልካቾችን በሚመለከት በመ.ቁ 22898 በቀን 10/01/2010 ዓ.ም የሰጠው የጥፋተኝት ውሳኔ እና በቀን 11/01/2010 ዓ.ም የሰጠው የቅጣት ውሳኔ፤ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 260202 በቀን 04/04/2010 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ፤ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 278007 በቀን 21/09/2010 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 195/2/ለ/2 መሠረት ተሽሯል፡፡
2. ከላይ በፍርድ ሐተታው ላይ በተገለጸው ምክንያት አመልካቾች ከቀረበባቸው ክስ በነጻ እንዲሰናበቱ ተወስኗል፡፡

## ትዕዛዝ

የሚመለከተው ማረሚያ ቤት የስር ፍ/ቤቶቸ በአመልካቾች ላይ አስተላልፈውት የነበረው የጥፋተኝነት እና የቅጣት ውሳኔ ተሽሮ አመልካቾች በነጻ እንዲሰናበቱ የተወሰነ መሆኑን አውቆ አመልካቾችን በዛሬው እለት ከእስር እንዲፈጹ ታዟል፡፡ ይጻፍ፡፡

የፍ/ቤቱ ሬጅስትራር የዚህን ውሳኔ ግልባጭ ለሚመለከተው ማረሚያ ቤት በአስቸኳይ እንዲልክ ታዟል፡፡

መዝገቡ ውሳኔ ስላገኘ ተዘግቷል፡፡

የማይነበብ የሶስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ፋ/ዘ

## የልዩነት ሃሳብ

ስማችን በአራተኛ እና አምስተኛ መስመር ላይ የተጠቀሰው ዳኞች አብላጫው ድምጽ አመልካቾችን ከወንጀል ተጠያቂነት ነፃ ለማለት በጠቀሰው ምክንያት እና በደረሰበት ድምዳሜ ያልተስማማን በመሆኑ የልዩነት ሀሳባችንን በሚከተለው መልኩ አስፍረናል፡፡

ከቀረበው ክስ መረዳት እንደሚቻለው አመልካቾች መጀመሪያ የተከሰሱት በተሰጣቸው የመንግስት የስራ ኃላፊነት ላይ ሆነው የቀረበላቸውን ጥያቄ በተመለከተ በክሱ ዝርዝር የተጠቀሱን የፌዴራል እና የክልል አዋጅ ደንብ እና መመሪያን መሰረት አድርገው ምላሽ መስጠት ሲገባቸው ይህንን ወደ ጎን በማለት የማይገባቸውን ጥቅም ለራሳቸው ለማግኘት ወይም በሌላ ሰው ለማስገኘት  በማሰብ የተሰጣቸውን

ስልጣን ያለአግባብ በመጠቀም በህግ ያልተመለከተን እና 45% 55% የሚባል አሰራርን በመዘርጋት በህዝብ እና መንግስት ጥቅም ላይ ጉዳት አድርሰዋል በሚል ነው፡፡

ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤትም አመልካቾች ቃለ ጉባኤ ይዘው ስራ ላይ ያዋሉት 45% 55% የተባለው አሰራር የህግ መሰረት የሌለው መሆኑን ማረጋገጡን ሆኖም ድርጊታቸው ስልጣንን ያለአግባብ መጠቀም ሳይሆን የህግ መሰረት የሌለውን አሰራር በመዘርጋት የመንግስት ስራ በማያመች‹ መንገድ መምራት ወንጀልን ነው በሚል ክስ የቀረበበትን አንቀጽ ቀይሮ እንዲከላከሉ አዟል፡፡

አመልካቾች በመከላከያ ማስረጃቸው 45% 55% የተባለው አሰራር እነርሱ ወደ ኃላፊነት ከመምጣታቸው በፊት የነበረ መሆኑን ከመግለጽ ባለፈ አሰራሩ የህግ ማዕቀፍ ያለው ስለመሆኑ ያቀረቡት ክርክርም ሆነ ከዚህ አኳያ ያረጋገጡት ነገር የለም፡፡ ቀድሞ የነበረ ብልሹ አሰራር በቃለ ጉባኤ እውቅና ሰጥቶ ማስቀጠል ደግሞ የወንጀል ክስ መከላከያ ሊሆን የሚችልበት የህግ አግባብ የለም፡፡

አብላጫው ድምፅ አመልካቾችን ጥፋተኛ ከተባሉበት ወንጀል በነፃ ለመልቀቅ በምክንያትነት የጠቀሰው አመልካቾች የመንግስትን ስራ በማያመች መንገድ መርተዋል በሚል ጥፋተኛ ለማለት ቀድሞ ‹‹የሚያመች አሰራር ሊኖር ይገባል›› የሚል ነው፡፡ ሆኖም የቀረበው ክስ በራሱ አመልካቾች የሰሩት ስራ ሊመራ እና ምላሽ ሊያገኝ ይገባ የነበረው በክሱ ዝርዝር ውስጥ የተጠቀሱትን የፌዴራል እና የክልል ህግጋት መሰረት በማድረግ ስለመሆኑ ተገልጿል፡፡ ከዚህ በላይ ምን አይነት አሰራር እንደተፈለገ ግልጽ አይደለም፡፡ አመልካቾችም ቢሆኑ በቃለ ጉባኤ ያስቀጠሉት ብልሹ አሰራር ከእነርሱ በፊትም የነበረ መሆኑን ከመግለጽ ባለፈ ለጉዳዩ አግባብነት አላቸው የተባሉት የህግ ማዕቀፎች መፍትሄ ለመስጠት አላስቻሉንም የሚል መከራከሪያ አላቀረቡም፡፡ ከዚህ አንፃር መከራከሪያ ቀርቦ ቢሆን እንኳን ህግ ክፍተት በህግ አግባብ ስልጣን ባለው አካል ስራን በሚያሳልጥ መልኩ እንዲታረም ከሚደረግ በቀር ‹‹ህጉ አላሰራኝም›› በሚል ሽፋን ህግ በቃለ ጉባኤ ተተክቶ የሚሰራበት አግባብ የለም፡፡

በመሆኑም የስር ፍርድ ቤቶች አመልካቾች ለጉዳዩ አግባብነት ያለውን ህግ ወደ ጎን ትተው የህግ መሰረት የሌለውን አሰራር ስራ ላይ በማዋል የመንግስትን ስራ በማያመች መንገድ መርተዋል በማለት የሰጡት የጥፋተኝነት እና የቅጣት ውሳኔ በማስረጃ የተረጋገጠን ፍሬ ነገር መሰረት ያደረገ ነው ከሚባል በቀር የሚነቀፍበት መሰረታዊ የህግ ስህተት ባለመኖሩ ሊሻር አይገባውም በሚል ከስራ ባልደረቦቻችን በሀሳብ ተለይተናል፡፡

የማይነበብ የሁለት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ፋ/ዘ

የሰ.መ.ቁ 173967

መጋቢት 28 ቀን 2012 ዓ.ም

ዳኞች፡- እትመት አሠፋ

ጻውሎስ ኦርሾሶ

ፀሐይ መንክር

መላኩ ካሣዬ

እስቲበል አንዱዓለም

አመልካቾች፡- አቶ አማኑኤል ገ/ጊዮርግስ

ተጠሪዎች፡- የትግራይ ክልል ፍትሕ ቢሮ ዓቃቤ ሕግ

መዝገቡ ለምርመራ የተቀጠረ ነው፡፡ በመሆኑም መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍርድ

የሰበር አቤቱታው ሊቀርብ የቻለው አመልካች መጋቢት 07 ቀን 2011 ዓ.ም ጽፎ ባቀረበው የሰበር አቤቱታ በትግራይ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የሰሜን ምዕራባዊ ዞን የሽሬ እንዳስላሴ ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ 22620 መጋቢት 05 ቀን 2011 ዓ.ም አመልካች በሌለበት ታይቶ የተሰጠው ውሳኔ ሊነሳ አይገባም በማለት የሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት አቤቱታ በማቅረቡ ነው፡፡

ጉዳዩ በወንጀል ጉዳይ በሌለሁበት ታይቶ የተሰጠ ውሳኔ ይነሳልኝ በሚል የቀረበን ክርክርን የሚመለከት ነው፡፡ የአሁን ተጠሪ አመልካች የአዋጅ ቁጥር 909/2007 አንቀጽ 4/5 ድንጋጌን በመተላለፍ ሕገወጥ ማንቀሳቀሻ በተጭበረበረ ሰነድ መስራት ወንጀል ፈጽሟል በማለት ያቀረባቸውን ስድስት ክሶች የተመለከተው በትግራይ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የሰሜን ምዕራባዊ ዞን የሽሬ እንዳስላሴ ከፍተኛ ፍ/ቤት አመልካች ተፈልጎ በአድራሻው ሊገኝ ስላልቻለ በመቃልህ ጋዜጣ ጥሪ ተደርጎለት ስላልቀረበ በሌለበት ጉዳዩን በማየት በተከሰሰበት የሕግ አንቀጽ ጥፋተኛ በማለት በ18 ዓመት ጽኑ እሥራት እንዲቀጣ ሲል ወስኗል፡፡

አመልካች ውሳኔውን ለሰጠው ፍ/ቤት ባቀረበው አቤቱታ በሌለበት ታይቶ የተሰጠውን ውሳኔ ያወቀው በቀን 23/05/11 ዓ/ም በሕመም ምክንያት አዲስ አበባ በነበሩበት ጊዜ መሆኑን፤ በጊዜ ቀጠሮ ጊዜ ዋስ የሆኗቸው ግለሰብ በሽሬ ከተማ የሚገኙ ቢሆንም አመልካችን እንዲያቀርቡ ያልተጠየቁ መሆኑን፤ በሌሉበት ጉዳያቸው እንዲታይ የተደረገው ከትግራይ ክልል ውጪ ሽፋን በሌለው በመቃልሕ ጋዜጣ

መሆኑን በመግለጽ በሌሉበት ታይቶ የተሰጠው ፍርድ ተሰርዞ ጉዳያቸው ባሉበት እንዲታይ አቤቱታ አቅርበዋል፡፡

ፍ/ቤቱም ተጠሪ በጉዳዩ ላይ አስተያየት እንዲሰጥበት ካደረገ እና የአመልካችን ምስክሮች ከሰማ በኋላ ምስክሮቹ አመልካች በሐምሌ ወር 2008 ዓ.ም ወደ አዲስ አበባ ሄዶ የታከመ እና ኒሞኒያ የተገኘበት መሆኑን፤ በኋላም እስከ 2009 ዓ/ም ድረስ ቆይቶ ለስራ ወደ ዱባይ የሄደ እና በ2010 ዓ.ም ወደ መቀሌ ተመልሶ እስከ ሚያዝያ ወር ድረስ ይኖር እንደነበር አስረድተዋል፤ ይህንኑ የሚያሳይ የሕክምና ማስረጃም ቀርቧል፤ አመልካች መጀመሪያ ክስ ቀርቦበት በመደበኛ መጥሪያ እንዲቀርብ ፖሊስ በቀጠሮ እንዲቀርብ ያዘዘው መሆኑን ለፍ/ቤቱ በጻፈው ምላሽ አሳውቋል፤ አመልካች የክስ ቻርጅ ደርሶት በመጥሪያ ሳይቀርብ በመቅረቱ ፖሊስ በእስር እንዲያቀርበው ከታዘዘ ጠፍቶ እንደተሸሸገ መረዳት ይቻላል፤ የክፍሉ አስተዳደር ጽ/ቤት አመልካች በአድራሻው እንደሌለ የገለጸ በመሆኑ አመልካች በመቃልህ ጋዜጣ ጥሪ ተደርጎለታል፤ አመልካች ባስመዘገበው ቀበሌ እንደሌለ ተረጋግጦ ፍ/ቤቱ በምትክ መጥሪያ አጠራር ስርዓት አመልካችን በሚጠቅም መንገድ የጋዜጣ ጥሪ ያደረገለት እና ያልቀረበ በመሆኑ ፍ/ቤቱ የፈጸመው የስነ ስርዓት ስሕተት የለም በማለት የአመልካች አቤቱታው ውድቅ በማድረግ ወስኗል፡፡

የሰበር አቤቱታው የቀረበው ይህን ውሳኔ በመቃወም መሠረታዊ የሕግ ስሕተት ተፈጽሞበታል በሚል ሲሆን ይዘቱም፡- የስር ከፍተኛው ፍ/ቤት ፖሊስ መጥሪያ ሰጥቸዋለሁ ብሎ ወረቀት ስለጻፈ መጥሪያ ደርሶሃል ቢልም ፖሊስ አልነገረኝም፤ አመልካች የፈረምኩበትንም ማስረጃ አላቀረበም፤ ፖሊስ ነግሬዋለሁ ብቻ ማለቱ እንደነገረኝ ማረጋገጫ አይደለም፤ በወ/መ/ስ/ስ/ሕ/ቁ 125 በግልጽ እንደተደነገገው ተከሳሽ በእስር እንዲቀርብ ትዕዛዝ የሚሰጠው ተከሳሹ ፍርድ ቤት እንዲቀርብ መጥሪያ እንደደረሰው ማረጋገጫ ከቀረበ በኋላ ነው፤ ፖሊስ በእስር እንዲያቀርበኝ በፍ/ቤት ሲታዘዝ በእስር እያቀረብኩት ነው ብሎ በቀን 3/01/2009 ምላሽ የሰጠ ቢሆንም ይህን ምላሽ የሰጠው አመልካችን ሳይዝ ነው፤ ፖሊስ የፍ/ቤቱን ትዕዛዝ ለአመልካች ነግሬአለሁ ባለበት ሰዓት አመልካች በሽሬም ከተማ ሆነ በትግራይ ክልል አልነበርኩም፤ አመልካች በወቅቱ አዲስ አበባ ውስጥ እንደነበርኩ ባቀረብኳቸው ማስረጃዎች ያስረዳሁ ቢሆንም የስር ከፍተኛው ፍ/ቤት ይህን ማስረጃ ሳይመዝን አልፎታል፤ በመሆኑም የስር ፍ/ቤት የአመልካች ማስረጃዎች በአግባቡ ሳይመዝን የአመልካችን አቤቱታ ውድቅ በማድረግ የሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት በመሆኑ በሰበር ታይቶ ሊታረም ይገባል የሚል ነው፡፡

የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ የስር ፍ/ቤት መጥሪያ ለአሁን አመልካች በቀጥታ መድረሱ ባልተረጋገጠበት ሁኔታ ፖሊስ አመልካች ወደ ፍ/ቤት እንዲቀርብ ነግሬዋለሁ በማለት ሪፖርት ማድረጉን መሠረት በማድረግ እና በጋዜጣ መጥሪያ መውጣቱን በቂ አድርጎ በሌለበት የተሰጠው ውሳኔ ሊነሳ አይገባም በማለት የመወሰኑን አግባብነት ከወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 125 ጋር በማገናዘብ ለመመርመር

ሲባል ጉዳዩ በዚህ ችሎት እንዲታይ ተደርጓል፡፡ ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎም ግራቀኙ በጽሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

የተጠሪ መልስ ይዘት በአጭሩ፡- ፖሊስ ለፍ/ቤቱ በሰጠው ምላሽ አመልካች በቀጠሮው ቀን እንዲቀርብ የተነገረው መሆኑን ምላሽ ገልጿል፤ ፍ/ቤቱም አመልካች እንዲቀርብ መጥሪያ ደርሶት ስላልቀረበ ታስሮ እንዲቀርብ ትዕዛዝ ከሰጠ በኋላ የክፍሉ አስተዳደር ጽ/ቤት አመልካች ባስመዘገበው አድራሻ እንደሌለ በመግለጽ ምላሽ ልኳል፤ አመልካች በመቃልህ ጋዜጣ ጥሪ ተደርጎለት ሊቀርብ ስላልቻለ ጉዳዩ በሌለበት ታይቶ የጥፋተኝነት እና የቅጣት ውሳኔ ተላልፎበታል፤ ፖሊስ የፍ/ቤቱን ትዕዛዝ ለአመልካች እንደነገረው ምላሽ የሰጠ በመሆኑ መልስ የላከ በመሆኑ አመልካች ከፍትሕ ራሱን ደብቆ ተሸሽጎ እንደነበር የሚያመለክት ነው፤ አመልካች በሕክምና ላይ እንደቆየ ለማሳየት ያቀረባቸው ማስረጃዎች ጉንፋን እና ኒሞንያ በሽታ እንዳለበት ከሚያሳዩ በቀር በጤና ጣቢያው ተኝቶ ታካሚ እንደነበር አያሳዩም፤ አመልካች በትግራይ ክልል ባሉ ሆስፒታሎች ሕክምና ማግኘት ይችል ነበር፤ የአመልካች ምስክሮች ዘመዶቹ በመሆናቸው ገለልተኛ ምስክሮች አይደሉም፤ የስር ፍ/ቤት መጥሪያ አደራረስን አስመልክቶ የፈጸመው የስነ ስርዓት ስሕተት ስለሌለ የአመልካችን አቤቱታ ውድቅ በማድረግ የሰጠው ውሳኔ ሊጸና ይገባል የሚል ነው፡፡ አመልካችም የሰበር አቤቱታውን በማጠናከር የመልስ መልስ ሰጥቷል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ በአጭሩ ከላይ የተገለጸው ነው፡፡ ይህ ችሎትም በሰበር አጣሪው ችሎት ሊጣራ ይገባዋል ተብሎ የተያዘውን ነጥብ ከግራቀኙ ክርክር፤ ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸው ሕጎች ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው መርምሮታል፡፡

አመልካች ካቀረበው አቤቱታ እና የስር ፍ/ቤት ለውሳኔው መሠረት ካደረጋቸው ነጥቦች አንጻር የዚህን ችሎት ምላሽ የሚፈልገው የክርክሩ መሠረታዊ ጭብጥ የስር ፍ/ቤት አመልካች በሌለበት ታይቶ የተሰጠው ውሳኔ እንዲነሳለት እና ጉዳዩ ባለበት እንዲታይ ያቀረበውን አቤቱታ ፖሊስ የፍ/ቤቱን ትዕዛዝ ለአመልካች የነገረው መሆኑን አሳውቋል፤ የክፍሉ አስተዳደር አመልካች ባስመዘገበው አድራሻ የሌለ መሆኑን በመግለጽ ምላሽ ሰጥቷል፤ ፍ/ቤቱ አመልካችን በሚጠቅም መልኩ በምትክ መጥሪያ አደራረስ በመቃልህ ጋዜጣ እንዲጠራ አድርጎ አመልካች ባለመቅረቡ በሌለበት እንዲታይ ማድረጉ የፈጸመው የስነስርዓት ስሕተት የለም በማለት የአመልካችን አቤቱታ ዉድቅ ማድረጉ በአግባቡ ነዉ? ወይስ አይደለም? የሚለው ነው፡፡

በመሠረቱ በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ 161 የተቀመጡት ቅድመ ሁኔታዎች ተሟልተው አንድ ክስ ተከሳሽ በሌለበት ነገሩ እንዲሰማ ፍ/ቤቱ ትዕዛዝ የሰጠ እንደሆነ የፍ/ቤቱ ትዕዛዝ ተከሳሹ የተከሰሰበት ወንጀል ዝርዝር፤ ነገሩ እንዲሰማ በተቀጠረበት ቀን ተከሳሹ ሳይቀርብ ቢቀር በሌለበት የሚፈረድ መሆኑን የሚገልጽ የመጥሪያ ማስታወቂያ በጋዜጣ እንዲወጣ ወይም ለተከሳሹ የሚደርስ መስሎ ከታየዉ

መጥሪያዉ የሚደርስበትን ሌላ መንገድ ፍርድ ቤቱ ሊያዝ እንደሚችል በዚሁ ሕግ ቁጥር 162 ላይ በግልጽ ተመልክቷል፡፡ በዚህ ድንጋጌ መሠረት የሚደረግ የጋዜጣ ጥሪም ጉዳዩን አመልካች በሌለበት ለማየት የሚያስችል ቅድመ ሁኔታ ነው፡፡ ይህን ሥርዓት ተከትሎና በዚሁ ሕግ ቁጥር 163(3) መሠረት እንደ ማንኛዉም ደንበኛ ክስ ታይቶ ፍርድ የተሰጠ እንደሆነ በሕጉ ቁጥር 197 እስከ 202 በተመለከቱት ምክንያቶች ፍርዱ ዉድቅ እንዲደረግ ተከሳሹ ማመልከቻ ማቅረብ እንደሚችል በቁጥር 164 ተመልክቷል፡፡ ተከሳሹ በሌለበት የተሰጠው ፍርድ ውድቅ ተደርጎ ጉዳዩ እንደገና እንዲታይ ያቀረበው ማመልከቻ የሚፈቀደው እንዲቀርብ መጥሪያ ያልደረሰዉ እንደ ሆነ ወይም ራሱ ወይም ጠበቃዉ ከዐቅም በላይ በሆነ ኃይል ምክንያት መቅረብ አለመቻሉን ያስረዳ እንደ ሆነ ነዉ በማለት በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 199 ላይ ተደንግጓል፡፡

በያዝነው ጉዳይ የስር ፍ/ቤት ፖሊስ የፍ/ቤቱን ትዕዛዝ ለአመልካች የነገረው መሆኑን ለፍ/ቤቱ ያሳወቀ መሆኑን እና የክፍሉ አስተዳደር አመልካች ባስመዘገበው አድራሻ የሌለ መሆኑን በመግለጽ ምላሽ የሰጠ መሆኑን በስር ፍ/ቤት ውሳኔ ላይ በግልጽ ሰፍሯል፡፡ በአመልካች ላይ የቀረበው ክስ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 161 ላይ በተመለከቱት ሁኔታዎች በሌለበት የሚታይ ከመሆኑ አኳያ ፍ/ቤቱ በቀጣይነት አመልካች በጋዜጣ ጥሪ እንዲደረግለት ትዕዛዝ መስጠቱ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 162 አግባብ የተሰጠ በመሆኑ በዚህ ረገድ ፍ/ቤቱ የፈጸመው ስሕተት የለም፡፡ ሆኖም ፍ/ቤቱ ለተከሳሽ የጋዜጣ ጥሪ ያስተላለፈው በመቃልህ ጋዜጣ ከመሆኑ አኳያ ተከሳሹ በሌለበት ታይቶ የተሰጠው ፍርድ እንዲነሳለት የሚያቀርበው ማመልከቻ ስለሚፈቀድባቸው ምክንያቶች አስመልክቶ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 199 (ሀ) ላይ "መጥሪያዉ ያልደረሰዉ እንደሆነ" በማለት ከተቀመጠው መስፈርት እና የተከሰሱ ሰዎች በሕገመንግስቱ ከተጠበቁላቸው መሠረታዊ መብቶች ገር በማገናዘብ ምላሽ ሊሰጠው የሚገባ የክርክሩ መሠረታዊ ጭብጥ ነው፡፡

የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 20/4 የተከሰሱ ሰዎች ጉዳያቸው በፍርድ ቤት ሲታይ በችሎት ተገኝተው የቀረበባቸውን ማስረጃ የመመልከት፣ የቀረበባቸውን ምስክሮችን የመጠየቅ፣ ለመከላከል የሚያስችላቸውን ማስረጃ የማቅረብ ወይም የማስቀረብ እንዲሁም ምስክሮቹ ቀርበዉ እንዲሰሙላቸው የመጠየቅ መብት አላቸው፡፡ ከዚህ ሕገ-መንግስታዊ ድንጋጌ ይዘት መገንዘብ የሚቻለዉ የወንጀል ጉዳዮች ተከሳሽ በተገኘበትና የመከላከል መብቱ በተጠበቀበት ሁኔታ ማካሄድ መርሁ ሲሆን ልዩ ሁኔታው ደግሞ በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ 161 እና ተከታዮቹ ድንጋጌዎች መሠረት አንድ ጉዳይ ተከሳሽ በሌለበት ታይቶ በተወሰነ ጊዜ በመርሁ የተቀመጠዉን የተከሳሽን የመከራከር መብት ለማረጋገጥ ሲባል ፍርዱ እንደገና ተነስቶ ጉዳዩ እንደገና የሚታይበት ስርዓት በቁጥር 197 እና ተከታዮቹ ድንጋጌዎች የተቀመጠ በመሆኑ በተቻለ መጠን ተከሳሹ በእርግጠኝነት መጥሪያ ደርሶት በችሎት የመገኘትና የመከራከር መብቱን አዉቆ መተዉ እስካልተረጋገጠ ድረስ ይህ መብቱ ሊነፈግ አይገባም፡፡ በመሆኑም በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 199 (ሀ) ላይ "መጥሪያዉ ያልደረሰዉ እንደሆነ" በሚል የተቀመጠውን መስፈርት መሠረት በማድረግ ተከሳሹ በሌለበት ታይቶ የተሰጠው ፍርድ እንዲነሳ ባመለከተ ጊዜ ከሳሽ የሆነው ዓቃቤሕግ ተከሳሹ የፍ/ቤቱን

መጥሪያ ሰምቶ ያልቀረበ መሆኑን የማስረዳት ግዴታ ያለበት ሲሆን ፍ/ቤቱም ይህንን የማረጋገጥ ሀላፊነት አለበት፡፡

ስለሆነም ከላይ ከተገለጹት ድንጋጌዎች እና ምክንያቶች አንጻር የወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ 199(ሀ) ተከሳሹ በትክክል መጥሪያ ደርሶት የመከራከር መብቱን አዉቆ በመተዉ መቅረቱ አሻሚ ባልሆነ መልኩ ዐ/ሕግ በሚያቀርበዉ በቂ ማስረጃ ካልተረጋገጠ በቀር ማወቅ ነበረበት ወይም ሊያዉቅ ይችላል የሚል ግምት በመዉሰድ ተከሳሹ በሌለበት ታይቶ የተሰጠው ውሳኔ ተነስቶ ጉዳዩ ባለበት እንዲታይ ያቀረበዉ ማመልከቻ ዉድቅ ሊደረግ አይገባም፡፡

በተያዘዉ ጉዳይ የስር ፍ/ቤት የአመልካችን አቤቱታ ውድቅ ያደረገዉ አመልካች በአገር ዉስጥ አለመኖሩ ተረጋግጦ በምትክ መጥሪያ አጠራር ስርዓት በመቃልህ ጋዜጣ ጥሪ ተደርጎለት ያልቀረበ በመሆኑ ፍ/ቤቱ ተከሳሽ በሌለበት ጉዳዩን አይቶ መወሰኑ የፈጸመው የስነስርዓት ስሕተት የለም በሚል ነዉ፡፡ ሆኖም አመልካች ጥሪ የተደረገለት በክልሉ ብቻ ተደራሽ በሆነው መቃልህ ጋዜጣ እንጂ ሐገር አቀፍ ስርጭት ባለው ጋዜጣ አይደለም፤ ዓቃቤሕግ ባቀረበው ክርክርም ለአመልካች ጥሪ የተላለፈበት መቃልህ ጋዜጣ ሐገር ዓቀፍ ስርጭት ያለው ስለመሆኑ አላረጋገጠም፤ ይልቁንስ አመልካች ባቀረባቸው ማስረጃዎች በጤና ችግር ምክንያት ከክልሉ ውጪ እንደነበር በኋላም በስራ ምክንያት ከኢትዮጲያ ውጪ እንደነበር አስረድቷል፡፡ አንድ ተከሳሽ በጋዜጣ ጥሪ ተደርጎለት ክስ የቀረበበት ስለመሆኑ አውቋል የሚል ግምት ሊወሰድ የሚገባው ሐገር አቀፍ ስርጭት ባለው ጋዜጣ ጥሪ የተደነገለት መሆኑ በተረጋገጠ ጊዜ እንጂ በክልሉ ብቻ ተደራሽ በሆነው ጋዜጣ ብቻ ጥሪ መደረጉ ተከሳሹ ክስ እንደቀረበበት አውቋል የሚል ግምት የሚያስወስድ አይደለም፡፡

በመሆኑም የስር ፍ/ቤት በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ 162 ተከሳሹ በሌለበት ነገሩ እንዲሰማ ፍ/ቤቱ ትዕዛዝ ለመስጠት የሚችልበትን ቅድመ ሁኔታ መነሻ በማድረግ ሐገራዊ ስርጭት በሌለው መቃልህ ጋዜጣ ለአመልካች ጥሪ ማስተላለፉን ለአመልካች መጥሪያ እንደደረሰው ማረጋገጫ አድርጎ በመውሰድ እና መጥሪያ ደርሶታል የሚል ግምት በመውሰድ አመልካች በሌለበት ታይቶ የተሰጠው ውሳኔ ተነስቶ ጉዳዩ ባለበት እንዲታይ ያቀረበውን ማመልከቻ ውድቅ በማድረግ የሰጠው ውሳኔ የወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ 199(ሀ) ድንጋጌ ይዘትና በሕገመንግስቱ ለተከሰሱ ሰዎች የተጠበቁላቸውን መሠረታዊ መብቶች ያላገናዘበ እና መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ ስለሆነም ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

ውሳኔ

1. በትግራይ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ሰሜን ምዕራብ ዞን የሽሬ እንዳስላሴ ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ 22620 መጋቢት 15 ቀን 2009 ዓ.ም የሰጠው የጥፋተኝነት ውሳኔ እና መጋቢት 19 ቀን 2009 ዓ.ም የሰጠው የቅጣት ውሳኔ እንዲሁም መጋቢት 05 ቀን 2011 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 195/2/ለ/2 መሠረት ተሽሯል፡፡

2. ከላይ በፍርድ ሐተታው ላይ በተገለጸው ምክንያት የስር ፍ/ቤት አመልካች በሌለበት ታይቶ የተሰጠው ውሳኔ ተነስቶ ጉዳዩ ባለበት እንዲታይ ያቀረበውን ማመልከቻ ውድቅ በማድረግ የሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት ነው በማለት ክርክሩ አመልካች ባለበት ታይቶ ውሳኔ እንዲያገኝ በማለት ወስነናል፡፡
3. የሸሬ እንዳስላሴ ከፍተኛ አመልካች ባለበት ክርክሩን ቀጥሎ ተገቢውን እንዲወስን በማለት ጉዳዩ ተመልሶለታል፡፡

- መዝገቡ ውሳኔ ስላገኘ ተዘግቷል፡፡ ይመለስ፡፡

# የወንጀል ሥነ-ሥርዓት ሕግ

የሰ/መ/ቁ. 182266

ጥቅምት 19 ቀን 2012 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** እትመት አሠፋ

ሃይሉ ነጋሽ

ፀሐይ መንክር

መላኩ ካሣዬ

እስቲበል አንዷለም

አመልካች፡- የደቡብ ብሔሮች ብሔረሠቦች እና ሕዝቦች ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ዓ/ሕግ የቀረበ የለም፡፡

ተጠሪዎች፡- አሸብር ዳጌታ ሄሎ(42 ሰዎች)

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**<u>ፍ ር ድ</u>**

ይህ የሰበር አቤቱታ ሊቀርብ የቻለው አመልካች ነሐሴ 06 ቀን 2012 ዓ.ም ጽፎ ባቀረበው የሰበር አቤቱታ የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ/ቁ 178178 ሐምሌ 30 ቀን 2011 ዓ.ም በሰጠው ፍርድ ተጠሪዎች በዋስ ሆነው ጉዳያቸውን እንዲከታተሉ በማለት የሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለቱ ነው፡፡

ጉዳዩ በወንጀል ጉዳይ የተከሰሰን ሰው ዋስትና በሚመለከት የቀረበ ክርክር ነው፡፡ የአሁን አመልካች በተጠሪዎች ላይ በስር ፍ/ቤት ያቀረበው ክስ ይዘት በአጭሩ ተጠሪዎች የወንጀል ሕጉን አንቀጽ 32/1/ሀ፣ 35 እና 239 ድንጋጌን በመተላለፍ ሕዳር 20 ቀን 2011 ዓ.ም በግምት ከጠዋቱ 3፡30 እስከ ቀኑ 9፡00 ሰዓት በደቡብ ክልል በቀድሞ ጋሞ ጎፋ ዞን በሳውላ ከተማ አዲሱን የዞን ምስረታ ማብሰሪያ እና ቀደም ሲል ከተለያዩ አመራር እና ከአካባቢ ማሕበረሰብ ጋር የተፈጠረውን ቅሬታ ለመፍታት እንዲሁም በአካባቢው ሰላም እና ቀጣይ ልማት ዙሪያ ውይይት ለማድረግ የክልሉ ዴ.ኢ.ህ.ዴን ጽ/ቤት ባስቀመጠው አቅጣጫ እና በተያዘው ፕሮግራም መሠረት በሳውሎ ከተማ ሚልንየም አዳራሽ በተዘጋጀው ስብሰባ የተለያዩ የፌዴራል መንግስት ከፍተኛ ባለስልጣናት፣ የፓርላማ አባላት፣ የክልል ቢሮ ሀላፊዎች የዞን አመራሮች እንዲሁም የተለያዩ ምሁራን እና ግለሰቦች ተጋብዘው በተጠቀሰው ቀን በስብሰባ ቦታ ሁሉም ተሰብሳቢዎች በተገኙበት፣ እኛ ባልተገኘንበት ስብሰባ አይደረግም፤

ከተሳታፊ ባለስልጣናት የምንፈልጋቸው ሰዎች አሉ በማለት ከጸጥታ ሀይል ቁጥጥር ውጪ በመሆን ወደ ስብሰባ አዳራሽ በመግባት ስብሰባውን በመበተን ተሳታፊዎችን ከስብሰባ አዳራሽ እንዲወጡ አድርገዋል፤ የተሽከርካሪ እንቅስቃሴ እንዳይደረግ መንገድ ዘግተዋል፤ በጸጥታ ሀይሎች ላይ ድንጋይ በመወርወር መከላከል እንዳያደርጉ በማድረግ መኪኖችን ሰበረዋል፣ ሱቆችን ሰብረው ዘርፈዋል፤ ንግድ ቤቶች እና የመንግስት መስሪያቤቶች እንዲዘጉ አድርገዋል፤የተፈጠረው ሁከት እና ብጥብጥ የከፋ ውጤት እንዳያስከትል ሲባል በጸጥታ ሀይሎች በተወሰደው እርምጃ የሁለት ሰዎች ሕይወት እንዲያልፍ በአምስት ሰዎች ላይ ደግሞ የአካል ጉዳት እንዲደርስ ምክንያት ስለሆኑ በሕብረት በፈጸሙት ሕገመንግስታዊ ስልጣንን ማሰናከል ወንጀል ተከሰዋል የሚል ነው፡፡

ተከሳሾች ክሱ ከተነበበላቸው በኂላ የተከሰሱበት የሕግ አንቀጽ ከአስራ አምስት አመት በማይበልጥ እስራት የሚያስቀጣ በመሆኑ እና የሰው ሕይወት ያለፈው በጸጥታ ሀይሎች በተወሰደው እርምጃ በመሆኑ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 63(1)መሠረት የዋስትና መብታቸውን የሚያስከለክል ምክንያት የሌለ መሆኑን፤ ምናልባት ፤ ቋሚ አድራሻ ያላቸው እና የቤተሰብ ሀላፊዎች በመሆናቸው ጥቂቶቹ ደግሞ ተማሪዎች በመሆናቸው፤ ምስክሮች ታባብላላችሁ እንዳይባሉ ምስክሮች የፖሊስ አባላት በመሆናቸው እና ከመካከላቸው በዋስትና የተለቀቁ ሰዎች መኖራቸው የተከሰሱበት ሕግ ዋስትና የማያስከልከል መሆኑ አመላካች መሆኑን በመግለጽ በዋስ ሆነው እንዲከራሩ ጠይቀዋል፡፡

የአሁን አመልካች ተጠሪዎች ባቀረቡት የዋስትና ጥያቄ ላይ በሰጠው አስተያየት ተጠሪዎች የተከሰሱበት የህግ አንቀጽ እስከ አስራ አምስት አመት በሚደርስ ጽኑ እስራት የሚያስቀጣ በመሆኑ እና በተከሳሾች ቀጥታ ድርጊት ባይሆንም የሁለት ሰዎች ሕይወት ያለፈበት ጉዳይ ስለሆነ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 63(1) መሠረት ሊከለከሉ ይገባል፤ ፍ/ቤቱ ይህንን በበቂ ምክንያት የሚያልፈው ቢሆን ተከሳሾች ቢለቀቀሉ ቀጠሮ አክብረው ሊቀርቡ የማይችሉ በመሆኑ፤ በማረሚያ ቤት ቆይታቸው ተቋሙን ሲረብሹ የነበሩ እና በጊዜ ቀጠሮም ፍ/ቤት ሲመላለሱ የሳውላ ከተማ ፖሊሶች ላይ ሲዝቱ ስለነበር በዋስትና ቢለቀቁ ሌላ ወንጀል ሊፈጽሙ ስለሚችሉ እና ምስክሮች ላይ ተጽእኖ ሊያደርሱ ስለሚችሉ የተከሳሾች የዋስትና መብት በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 67 (ሀ)(ለ)እና(ሐ) መሠረት ሊከለከል ይገባል በማለት መልስ ሰጥተዋል፡፡

ጉዳዩ የቀረበለት ፍ/ቤት የተጠሪዎችን የዋስትና ጥያቄ እና አመልካች በጉዳዩ ላይ የሰጠውን አስተያየት ከመረመረ በኂላ ተጠሪዎች በወንጀል ሕግ አንቀጽ 239 ድንጋጌ የተከሰሱ ሲሆን የፈጠሩት ሁከት እና ብጥብጥ የከፋ ውጤት እንዳያስከትል በጸጥታ ሀይሎች በተወሰደው እርምጃ የሁለት ሰዎች ሕይወት ማለፍ መንስኤ መሆኑን የሚያሳይ እና ድንጋጌው እስከ 15 ዓመት በሚደርስ ጽኑ እስራት ሊያስቀጣ የሚችል በመሆኑ ያቀረቡት የዋስትና መብት ጥያቄ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 63(1 )መሠረት ተቀባይነት የለውም በማለት ውድቅ አድርጎታል፡፡

ተጠሪዎች ይህንን ብይን በመቃወም ለፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የይግባኝ አቤቱታ አቅርበዋል፡፡ ይግባኙ የቀረበለት ፍ/ቤት ግራቀኙን ካከራከረ በኂላ ተጠሪዎች የተከሰሱበት የወንጀል ሕግ አንቀጽ 239 እስከ 15 ዓመት በሚደርስ እስራት የሚያስቀጣ በመሆኑ 15 ዓመት ሊቀጡ እንደሚችሉ መገንዘብ ይቻላል፤ ወንጀል የተፈጸመበት ሰው የሞተ እንደሆነ ከሚለው የወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 63/1 መመዘኛ ሲታይ በተጠሪዎች በተፈጸመው ሁከት እና ብጥብጥ የከፋ ውጤት እንዳይመጣ ለማስቆም በጸጥታ ሀይሎች በተወሰደ እርምጃ የሁለት ሰዎች ሕይወት ያለፈ በመሆኑ ተጠሪዎች በሕይወት ማለፍ ቀጥተኛ በሆነ የግድያ ወንጀል ተጠያቂ አይደሉም፤ በሞቱት ሰዎች ላይ ሀላፊነት የሌለባቸው እና ተጠያቂነታቸው የሕገመንግስታዊ ስልጣንን ተግባራዊነት ማሰናካል ከሆነ የወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 63/1 በተጠሪዎች ላይ ተፈጻሚነት የሚኖረው አይደለም፤ ከወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 67 አኳያ በተጠሪዎች ላይ ሌላ የዋስትና መከላከያ ምክንያት በዓ/ሀግ እስካልቀረበ ድረስ የተከሰሱበት ክስ የዋስትና መብት ይከለክላል መባሉ አግባብ አይደለም በማለት ተጠሪዎች እያንዳንዳቸው ለብር 20,000 የዋስትና ግዴታ በመግባት ጉዳያቸውን በውጪ ሆነው እንዲከታተሉ ሲል ወስኗል፡፡

የሰበር አቤቱታው የቀረበው ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈጽሞበታል በሚል ሲሆን ይዘቱም ተጠሪዎች በፈጸሙት የሕገመንግስታዊ ስርዓት ተግባራዊነት ማሰናከል ወንጀል ለማስቆም ሲባል በጸጥታ ሀይሎች በተወሰደው እርምጃ የሁለት ሰዎች ሕይወት አልፏል፤ ተጠሪዎች ራሳቸው በቀጥታ ሟቾችን ባይገድሉም ተጠሪዎች ሁከት እና ብጥብጥ ባይፈጥሩ ኖሮ የሰው ሕይወት አያልፍም ነበር፤ ተጠሪዎች በፈጸሙት ድርጊት ምክንያት የሰው ሕይወት ያለፈ በመሆኑ በወ/ሕ/ቁ 24/1 መሠረት በምክንያት እና ውጤት መካከል ግንኙነት አለ፤ ተጠሪዎች አስከ 15 ዓመት በሚደርስ እስራት ሊያስቀጣ በሚችል ወንጀል የተከሰሱ በመሆናቸው በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 63/1 መሠረት የዋስትና መብታቸው ሊከለከል ይገባል፤ ይህ ቢታለፍ እንኳን አመልካች በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 67/(ሀ)(ለ)(ሐ) መሠረት ተገቢ ምክንያት በመስጠት የተከሳሾች የዋስትና መብት ሊነፈግ ይገባል በማለት መቃወሚያ አቅርቦ ሳለ የስር ፍ/ቤት አይቶ መወሰን ሲገባው ማለፉ አግባብ አይደለም፤ ተጠሪዎች በዋስትና ቢለቀቁ በአካባቢያቸው በከፍተኛ ሁኔታ ሰላም እና መረጋጋትን ወደ ማይመለስ ቀውስ ውሥጥ ሊያስገቡ የሚችሉ የተደረጃ ቡድን በመሆናቸው የስር ፍ/ቤት ወሳኔ ተሽሮ ማረሚያ ሆነው ጉዳያቸውን ሊከታተሉ ይገባል የሚል ነው፡፡ አመልካች ያቀረበው የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ በሰበር ችሎት ሊታይ እንደሚገባው ስለታመነበት ጉዳዩ በዚህ ችሎት እንዲታይ ተደርጓል፡፡ ለተጠሪዎች ጥሪ ተደርጎም ግራቀኙ በጽሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ፣ ለዚህ ሰበር ችሎት ያስቀርባል ሲባል ከተያዘው ጭብጥ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩን በሚከተለው መልኩ መርምረነዋል፡፡ እንደመረመርነው በሰበር አጣሪው ችሎት ሊጣራ ይገባዋል ተብሎ የተያዘው ነጥብ፤አመልካች በስር ከፍተኛ ፍ/ቤት በተጠሪዎች

የቀረበውን የዋስትና ጥያቄ በመቃወም የተከራከረው በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 67 እና 63 መሠረት በማድረግ ሲሆን ፍ/ቤቱ አንቀጽ 63ን መሠረት በማድረግ የተጠሪዎችን አቤቱታ ውድቅ ያደረገ ሲሆን ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተው ፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት የወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 63 በተከሳሾች ላይ ተፈጻሚነት የለውም በተጠቃሹ ሕግ አንቀጽ 67 መሠረት ምክንያት እስካልቀረበ ድረስ የተከሰሱበት ድንጋጌ የዋስትና መብት አያስከለክልም በማለት የስር ፍ/ቤትን ውሳኔ በመሻር የወሰነበትን አግባብነት ከተጠቀሱት የስነ-ስርዓት ድንጋጌዎች እና ከመሠረታዊ የክርክር አመራር ሥነ-ሥርዓት ጋር በማገናዘብ ለመጣራት በሚል ነው፡፡

በመሠረቱ የዋስትና መብት በሕገ መንግስት ጥበቃ ከተደረገት የተያዙ ሰዎች መሠረታዊ መብቶች አንዱ ነው፡፡ የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግሥት በአንቀጽ 19/6/ ስር የተያዙ ሰዎች በዋስትና የመፈታት መብት ያላቸው መሆኑን በመርህ ደረጃ ያስቀመጠ ሲሆን ይህ በሕገ መንግሥቱ የተከበረው መሠረታዊ መብት ሊነፈግ፣ ሊገደብ ወይም በቂ የሆነ የዋሰትና መረጋገጫ እንዲቀርብ የሚደረገውም አግባብነት ባላቸው ሌሎች ዝርዝር ሕጎች መሠረት በልዩ ሁኔታ ስለመሆኑ ይኸው የሕገ መንግስቱ ድንጋጌ በግልጽ ያሳያል፡፡ በመሆኑም የዋስትና መብት መሠረታዊ የሆነ ሕገ መንግስትዊ መብት ቢሆንም ፍጹም መብት ሳይሆን በሕጉ አግባብ ሊነፈግ የሚችል ነው፡፡ ስለሆነም የዋስትናው ጥያቄ ተቀባይነት አለው ወይም የለውም የሚለው ላይ ውሳኔ የሚሰጠው ፍርድ ቤት እንደመሆኑ መጠን በዚህ ረገድ አግባብነት ያለውን ልዩ ሕግ መሠረት አድርጎ ጉዳዩን ሊመዝነውና ተገቢውን ውሳኔ ሊልሰጥ እንደሚገባ ግልጽ ነው፡፡

በያዝነው ጉዳይ በስር ከፍተኛ ፍ/ቤት በተጠሪዎች የቀረበውን የዋስትና ጥያቄ ውድቅ የተደረገው በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 63 “ን” መሠረት በማድረግ የተጠሪዎችን አቤቱታ ውድቅ ያደረገ ሲሆን ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተው የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት የወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 63 በተከሳሾች ላይ ተፈጻሚነት የለውም በተጠቃሹ ሕግ አንቀጽ 67 መሠረት ምክንያት እስካልቀረበ ድረስ የተከሰሱበት ድንጋጌ የዋስትና መብት አያስከለክልም በማለት የስር ፍ/ቤትን ውሳኔ በመሻር ውሳኔ ሰጥቷል፡፡በስር ፍርድ ቤት የአሁኑ ተጠሪዎች ፈጽመውታል የተባለው የወንጀል ሕግ አንቀጽ 239 ድንጋጌን በመተላለፍ የሕገመንግስታዊ ሥልጣንን ተግባራዊነት ማሰናከል ወንጀል ምክንያት በተፈጠረው ሁከት እና ብጥብጥ የከፋ ውጤት እንዳይመጣ ለማስቆም ሲባል በጸጥታ ሀይሎች በተወሰደው እርምጃ የሁለት ሰዎች ሕይወት ማለፉ የሚመለከት ነው፡፡

የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የአመልካች አቤቱታ ውድቅ በማድረግ ተጠሪዎች ዋስትና መብት እንዲከበርላቸው ውሳኔ የሰጠው የቀረበው ክስ የዋስትና መብት የማያስከለክል በመሆኑና በተፈጠረው ሁከት እና ብጥብጥ የከፋ ውጤት እንዳይመጣ ለማስቆም ሲባል በጸጥታ ሀይሎች በተወሰደው እርምጃ የሁለት ሰዎች ሕይወት ማለፉ ተጠሪዎችን ቀጥተኛ በሆነ የግድያ ወንጀል

የማያስጠይቃቸው በመሆኑ የወ/መ//ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 63/1 በተጠሪዎች ላይ ተፈጻሚነት የለውም በማለት ነው፡፡

በመሰረቱ ከወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 63/1 ይዘት ለመረዳት እንደሚቻለው  ማንኛውም የተያዘ ሰው የተከሰሰበት ወንጀል የሞት ቅጣትን ወይም አሥራ አምሥት ዓመት ወይም በላይ በሆነ ጽኑ እስራት የማያስቀጣው ከሆነና ወንጀል የተፈጸመበት ሰው በደረሰበት ጉዳት የማይሞት የሆነ እንደሆነ ፍ/ቤቱ የዋስትና ወረቀት አስፈርሞ ለመልቀቅ ይችላል በማለት ይደነግጋል ፡፡ ከድንጋጌው ይዘት መገንዘብ የሚቻለው ተከሳሹ የተከሰሰበት የሕግ አንቀጽ በሞት ወይም ከ15 ዓመት በላይ የሚያስቀጣ ከሆነ እና ጉዳት የደረሰበት ሰው የሞተ እንደሆነ በዋስትና መልቀቅ የማይቻል መሆኑን ፤ሆኖም ተከሳሹ የተከሰሰበት የሕግ አንቀጽ በሞት ወይም ከ15 ዓመት እና በላይ የማያስቀጣ እና ጉዳት የደረሰበት ሰው ያልሞተ እንደሆነ ተከሳሹን በዋስትና መልቀቅ የሚቻል መሆኑን ነው፡፡

በያዝነው ጉዳይ ተጠሪዎች የተከሰሰበት የወንጀል ሕግ አንቀጽ 239 ድንጋጌን በመተላለፍ ሆኖ ድንጋጌው  እስከ 15 ዓመት በሚደርስ ጽኑ እሥራት የሚያስቀጣ ቢሆንም በተጠሪዎች ተግባር የሞተ ሰው ስሌለ እና ሞቱ የተባሉት ሁለት ሰዎች በሌላ አካል በተወሰደ እርምጃ መሞታቸው የተረጋገጠ መሆኑ በዚሁ ጉዳይም በተጠሪዎች ላይ ክስ ያልቀረበና በዓ/ህግ በኩል ያልተገለፀ በመሆኑ፣ በወንጀል ሕግ አንቀጽ 63/1 የተመለከቱት ተከሳሹ የተከሰሰበት የሕግ አንቀጽ በሞት ወይም ከ15 ዓመት በላይ የሚያስቀጣ ከሆነ እና ጉዳት የደረሰበት ሰው የሞተ እንደሆነ የሚሉት ቅድመ ሁኔታዎች አልተሟሉም፡፡ በመሆኑም የስር ፍ/ቤት በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 63/1 ላይ የተመለከቱት ቅድመ ሁኔታዎች አልተሟሉም በማለት ከድምዳሜ ላይ መድረሱ በአግባቡ ነው ብለናል፡፡ በተመሳሳይ ጉዳዮች ላይ ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁጥር 171880  በአዋጅ ቁጥር 454/97 አንቀፅ 2 መሠረት በየትኛውም እርከን የሚገኝ ፍርድ ቤትን የሚያስገድድ የሰጠው የህግ ትርጉም ለዚህ ጉዳይ ተፈፃሚነት እንዳለው ተመልክተናል፡፡

አመልካች የተከሳሾች የዋስትና መብት በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 67 (ሀ)(ለ)እና(ሐ) መሠረት ሊከለከል ይገባል በማለት ያቀረበው ክርክር በተመለከተ ጉዳዩ በይግባኝ የተመለከተው የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ላይ ክርክር ያልቀረበበት መሆኑ የይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ዋና መዝገብ በማስቀረብ ያረጋገጥን በመሆኑ ፍርድቤቱ “በወ/መ/ሥ/ሥ/ግ/ቁ 67 መሠረት የዋስትና መከልከያ ምክንያት እስካልቀረበ ድረስ“ በማለት የገለፀው ሲታይ አመልካች በስር ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት ባልተከራከረበት ጉዳይ የተጠሪዎች የዋስትና መብት ለመከልከል የቀረበ አዲስ ክርክር በመሆኑ ተቀባይነት ያለው አይደለም ስለሆነም የስር ፍ/ቤቱ የተጠሪዎችን የዋስትና መብት እንዲከበርላቸው እና ተጠሪዎች በዋስ ሆነው ጉዳያቸውን እንዲከታተሉ በማለት የሰጠው ውሳኔ በአግባቡ ነው ብለናል፡፡

በመሆኑም የበታች ፍርድ ቤት በህገ መንግስቱ አንቀጽ 19/6/ እና በወ/መ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ 63 እና 67 መሠረት በማድረግ የሰጠው ብይን ሕጉ የሰጠውን ሥልጣን መሠረት ያደረገ ነው ከሚባል በቀር በህግ አተረጓጉምና አተገባበር ረገድ መሠረታዊ ሕግ ስህተት የተፈፀመበት ነው ለማለት አልተቻለም፡፡ በዚህም መሠረት በአብላጫ ድምፅ ተከታዩን ውሳኔ ሠጥተናል፡፡

## ው ሳ ኔ

1/ በፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 178178 በቀን 30/11/2011 ዓ.ም በዋለው ችሎት የተሰጠው ውሳኔ በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ 75/2/ መሠረት ፀንቷል፡፡

2 / ነሃሴ 10 ቀን 2011 ዓ.ም በዋለው ችሎት በተሰጠ የእግድ ትእዛዝ ተጠሪዎች በነበሩበት ማረምያ ቤትሆነው ጉዳያቸው እንዲከታተሉ ተሰጥቶ የነበረው እግድ ተነስቷል፡፡ለሚመለከተው አካል ይፃፍ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ወደመዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡

ቤ/ፍ የማይነበብ የአራት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

## የልዩነት ሀሳብ

ስሜ በተ.ቁ 1 ላይ የተገለጸው ዳኛ አብላጫው ድምጽ የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት አመልካቾች የተከሰሱበት ወንጀል በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 63/1 መሠረት ዋስትናን አያስከለክልም በማለት የሰጠው ውሳኔ ተገቢ ነው ሲል የደረሰበት መደምደሚያ እኔም የምስማማበት ነው፡፡ ሆኖም የተጠሪዎች መብት በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ሕ/ቁ 67 (ሀ)(ለ)(ሐ) መሠረት ሊከለከል ይገባል በማለት ክርክር ያልቀረበበት መሆኑ የጠቅላይ ፍ/ቤቱን መዝገብ በማስቀረብ ያረጋገጥን ስለሆነ አመልካች በስር ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ባልተከራከረበት ጉዳይ የዋስትና መብትን ለመከልከል የቀረበ አዲስ ክርክር በመሆኑ ተቀባይነት የለውም ሲል በደረሰበት መደሚደሚያ በሐሳብ ስለተለየሁ የሀሳብ ልዩነቴን እንደሚከተለው አስፍሬአለሁ፡፡

ዓቃቤ ሕግ በአሁን ተጠሪዎች ላይ ክስ ያቀረበው ተጠሪዎች የወንጀል ሕጉን አንቀጽ ጉ 32/1/ሀ፣ 35 እና 239 ድንጋጌን በመተላለፍ ሁከት እና ብጥብጥ በመፍጠር የሕገ መንግስታዊ ስልጣንን ተግባራዊነት ማሰናከል ወንጀል ፈጽመዋል፣ ተከሳሾች የፈጠሩት ሁከት እና ብጥብጥ የከፋ ውጤት እንዳያስከትል ሲባል በጸጥታ ሀይሎች በተወሰደው እርምጃ የሁለት ሰዎች ሕይወት አልፏል በሚል ነው፡፡

ተጠሪዎች ለስር ፍ/ቤት ባቀረቡት አቤቱታ የተከሰሱበት የሕግ አንቀጽ ከአስራ አምስት አመት በማይበልጥ እስራት የማያስቀጣ በመሆኑ እና የሰው ሕይወት ያለፈው በጸጥታ ሀይሎች በተወሰደው

እርምጃ በመሆኑ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 63/1 መሠረት የዋስትና መብታቸውን የሚያስከለክል ምክንያት የሌለ መሆኑን፤ ቋሚ አድራሻ ያላቸው እና የቤተሰብ ሀላፊዎች መሆናቸው፤ ጥቂቶቹ ደግሞ ተማሪዎች መሆናቸው፤ ምስክሮች ታባብላላችሁ እንዳይባሉ ምስክሮች የፖሊስ አባላት በመሆናቸው እና ከመካከላቸውም በዋስትና የተለቀቁ ሰዎች መኖራቸውን በመግለጽ በዋስ ሆነው እንዲከራከሩ እንዲፈቀድላቸው ጠይቀዋል፡፡

የአሁን አመልካች ተጠሪዎች ባቀረቡት የዋስትና ጥያቄ ላይ በሰጠው አስተያየት ተጠሪዎች የተከሰሱበት የህግ አንቀጽ እስከ አስራ አምስት አመት በሚደርስ ጽኑ እስራት የሚያስቀጣ በመሆኑ እና በተከሳሾች ቀጥታ ድርጊት ባይሆንም የሁለት ሰዎች ሕይወት ያለፈ በመሆኑ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 63/1 መሠረት ሊከለከሉ ይገባል በማለት አስተያየት የሰጠ ሲሆን ፍ/ቤቱ ይህን በበቂ ምክንያት የሚያልፈው ቢሆን ተከሳሾች ቢለቀቁ ቀጠሮ አክብረው ሊቀርቡ የማይችሉ በመሆኑ፤ በማረሚያ ቆይታቸው ተቋሙን ሲረብሹ የነበሩ እና በጊዜ ቀጠሮም ፖሊሶች ላይ ሲዝቱ ስለነበር በዋስትና ቢለቀቁ ሌላ ወንጀል ሊፈጽሙ ስለሚችሉ እና ምስክሮች ላይ ተጽእኖ ሊያደርሱ ስለሚችሉ የተከሳሾች የዋስትና መብት በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 67 (ሀ)(ለ)እና(ሐ) መሠረት ሊከለከል ይገባል በማለት አስተያየት  የሰጠ መሆኑን የስር ውሳኔ በግልጽ ያሳያል፡፡

ጉዳዩ የቀረበለት የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ተከሳሾች በፈጸሙት የሕገ መንግስታዊ ስልጣን ተግባራዊነት ማሰናከል ወንጀል ምክንያት የተፈጠረው ሁከት እና ብጥብጥ የከፋ ውጤት እንዳያመጣ ሲባል በጸጥታ ሀይሎች በተወሰደው እርምጃ ምክንያት የሁለት ሰዎች ሕይወት ያለፈ በመሆኑ የተከሳሾች የዋስትና መብት በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 63/1 መሠረት ተቀባይነት የለውም በማለት ውድቅ ያደረገው በመሆኑ ዓቃቤ ሕግ ዋስትናውን ለማስከልከል የሚያስችሉ በቂ ሁኔታዎች አሉ በማለት በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ 67 (ሀ)(ለ)እና(ሐ) መሠረት ያቀረባቸውን ምክንያቶች አልመረመረም፡፡

ይግባኙ የቀረበለት የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤትም ተጠሪዎች በፈጸሙት ሁከት እና ብጥብጥ ምክንያት የሁለት ሰዎች ሕይወት ያለፈ ቢሆንም ተጠሪዎችን ቀጥተኛ በሆነ የግድያ ወንጀል ተጠያቂ የማያደርጋቸው በመሆኑ የወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 63/1 በተጠሪዎች ላይ ተፈጻሚነት የለውም ካለ በኋላ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 67 መሠረት የዋስትና መከልከያ ምክንያት እስካልቀረበ ድረስ የተጠሪዎች የዋስትና መብት ሊነፈግ አይገባም ከሚል መደምደሚያ ላይ የደረሰ መሆኑ የውሳኔው ይዘት ያሳያል፡፡

ከሳሽ የሆነው ዓቃቤሕግ የተጠሪዎችን  የዋስትና መብት የተቃወመው በአንድ በኩል የተጠሪዎች የዋስትና መብት በሕግ የተከለከለ ነው በማለት ሲሆን ይህ የሚታለፍ ከሆነም በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 67 (ሀ)(ለ)እና(ሐ) መሠረት የተጠሪዎችን የዋስትና መብት ሊያስከለክል የሚችል ሁኔታ አለ በማለት እንደሆነ የስር ውሳኔ ይዘት የሚያመለክት በመሆኑ ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተው የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ከወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 67 አኳያ የዋስትና መከልከያ ምክንያት እስካልቀረበ ድረስ የተከሰሱበት ክስ

የዋስትና መብት ይከለክላል መባሉ አግባብ አይደለም በማለት የሰጠው ወሳኔ ተገቢ መሆን አለመሆኑ ዋስትናን አስመልክቶ አግባብነት ካላቸው ሕጎች እና ፍ/ቤቶች ክርክርን በመምራት ረገድ ሊኖራቸው ከሚገባው ተግባር እና ሀላፊነት ጋር ተገናዝቦ ሊታይ ይገባዋል፡፡

በመሠረቱ የተያዙ ሰዎች በሕገ-መንግስቱ ጥበቃ ከተደረጉላቸው መብቶች አንዱ የዋስትና መብት ነው፡፡ የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግሥት በአንቀጽ 19/6 የተያዙ ሰዎች በዋስትና የመፈታት መብት ያላቸው መሆኑን በመርህ ደረጃ ያስቀመጠ ሲሆን ይህ በሕገ መንግሥቱ የተከበረው መሠረታዊ መብት ሊነፈግ፣ ሊገደብ ወይም በቂ የሆነ የዋሰትና ማረጋገጫ እንዲቀርብ የሚደረገውም አግባብነት ባላቸው ሌሎች ዝርዝር ሕጎች መሠረት በልዩ ሁኔታ ስለመሆኑ ከድንጋጌው ይዘት መገንዘብ ይቻላል፡፡ በሕገ-መንግስቱ ልዩ ጥበቃ የተሰጠው ይህ መብት መሠረታዊ ዓላማውም ተከሳሹ በተከሰሰበት ወንጀል ጥፋተኝነቱ ሳይረጋገጥበት በእስር እንዳይቆይ ማድረግ ነው፡፡ በመሆኑም የዋስትና መብት መርህ መፍቀድ ሲሆን ልዩ ሁኔታው ደግሞ መከልከል ነው፡፡

ይህን መሠረታዊ መብት አስመልክቶ የመወሰን ስልጣን እና ሃለፊነት የተሰጣቸው ፍ/ቤቶችም በወንጀል ጉዳይ ተጠርጥሮ ክስ የቀረበበት ሰው የሚያቀርበውን የዋስትና መብት ጥያቄ እና ከሣሽ የሆነው ዓቃቤ ሕግም በጉዳዩ ላይ የሚሰጠውን አስተያየት ከሕገ መንግስቱ መሠረታዊ ዓላማ እና ዋስትናን አስመልክቶ በልዩ ሕጎች ከተደነገጉት ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በጥንቃቄ መርምረው ውሳኔ መስጠት ይጠበቅባቸዋል፡፡ ይህንኑ ተግባራዊ ሲያደርጉም በመርህ ደረጃ የዋስትናን መብት መፍቀድ ያለባቸው ሲሆን በሁለት መሠረታዊ ምክንያቶች ግን የዋስትናን መብት በልዩ ሁኔታ ሊነፍጉ ይችላሉ፡፡ እነዚህም ምክንያቶች አንደኛው ተከሳሽ ፈጽሞታል የተባለው ወንጀል በዋስትና ለመለቀቅ የሚከለክል ሲሆን በወ/መ//ሥ/ሥ/ሕቁ 63 የሕግ ክልከላን መሠረት በማድረግ ሲሆን ሁለተኛው ምክንያት ደግሞ ተከሳሹ ፈጽሞታል የተባለው ወንጀል በዋስ መለቀቅን የማይከለክል ቢሆንም ተጠርጣሪው ቢለቀቅ በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ 67 የተገለፁትን ተግባራት ይፈጽማል ተብሎ ሲታመን ነው፡፡

ፍ/ቤቶች ተከሳሹ ፈጽሞታል የተባለው ወንጀል የዋስትናን መብት የሚያስከለክል ሆኖ ባገኙት ጊዜ የወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 63/1ን መሠረት በማድረግ የተከሳሹን የዋስትና መብት ከከለከሉ / ከነፈጉ / ከመነሻውም ቢሆን የተከሳሹ የዋስትና መብት የተከለከለው በሕግ በመሆኑ ዋስትናን ሊያስከለክሉ ይችላሉ ተብለው በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 67 ላይ የተመለከቱትን ሁኔታዎች መመርምር እና መመዘን አይጠበቅባቸውም፡፡ ሆኖም ተከሳሽ ፈጽሞታል የተባለው ወንጀል ዋስትናን የማያስከለክል ከሆነ እና ከሳሽ የሆነው ዓቃቤሕግ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 67 ላይ የተመለከተቱትን ሁኔታዎቸ መሠረት በማድረግ የተከሳሹን የዋስትና መብት ጥያቄ ተቃውሞት ከሆነ ግን ፍ/ቤቱ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 67 መሠረት የተከሳሽን የዋስትና መብት ለማስከልከል የቀረቡት ምክንያቶች ዋስትናውን ለማስከልከል የሚያስችሉ በቂ እና ሕጋዊ ምክንያቶች መሆን አለመሆናቸውን መርምሮ እና መዝኖ ውሳኔ ሊያሳርፍበት ይገባል፡፡

እንግዲህ የዋስትናን መብት ለመፍቀድ ወይም ለመንፈግ / ለመከልከል / የሚያስችሉ መሠረታዊ ድንጋጌዎች ከላይ የተመለከቱት ሲሆኑ እነዚህን ድንጋጌዎች መሠረት በማድረግ ጥያቄው መቅረብ ያለበት ለየትኛው ፍ/ቤት ነው? ዋስትናው ሊፈቀድ ይገባል ወይም አይገባም የሚለውን ውሳኔ መስጠት የሚችለውስ የትኛው ፍ/ቤት ነው? ዋስትናውን በመፍቀድ ወይም በመከልከል የተሰጠውን ውሳኔ ተከትሎ የሚቀርበውን ይግባኝ የሚመረምረው ፍ/ቤት ስልጣን እና ተግባሩ ምንድነው? የሚሉት ነጥቦች በዚህ መዝገብ ለተያዘው ጉዳይ ምላሽ ማግኘት ያለባቸው መሠረታዊ ነጥቦች ነው፡፡

የተያዘው ሰው በዋስትና ወረቀት እንዲለቀቅ በማናቸውም ጊዜ መጠየቅ የሚችል መሆኑን፤ የሚቀርበውንም ማመልከቻ ማናቸውም ፍ/ቤት መፍቀድ የሚችል መሆኑን የወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 64 እና 65 ድንጋጌዎች ያስገነዝቡናል፡፡ የዋስትና መብት በማናቸውም ፍ/ቤት ሊጠየቅ እስከቻለ ድረስ እና ዋስትናን ሊፈቀድ ወይም ሊነፈግ ስለሚችልባቸው ሁኔታዎች አስመልክቶ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 63 እና 67 ላይ የተደነገጉት ድንጋጌዎችም የሕግ ክርክሮች በመሆናቸው ጉዳዩን በቀጥታ በሚያየው ፍ/ቤት የቀረቡ መሆናቸው እስከተረጋገጠ ጊዜ ድረስ በይግባኝ ደረጃ ክርክር አልቀረበባቸውም ተብሎ የሚታለፉ ሳይሆኑ በይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤትም በአግባቡ ተመርምረው ውሳኔ ሊሰጥባቸው የሚገባ ስለመሆኑ ከድንጋጌዎቹ ይዘት መገንዘብ ይቻላል፡፡

በተያዘው ጉዳይ ተከሳሾች ላቀረቡት የዋስትና መብት ጥያቄ ዓቃቤሕግ በሰጠው አስተያየት ተጠሪዎች የተከሰሱበት የህግ አንቀጽ እስከ አስራ አምስት አመት በሚደርስ ጽኑ እስራት የሚያስቀጣ በመሆኑ እና በተከሳሾች ቀጥታ ድርጊት ባይሆንም የሁለት ሰዎች ሕይወት ያለፈ በመሆኑ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 63/1 መሠረት ሊከለከሉ ይገባል በማለት አስተያየት የሰጠ ሲሆን ፍ/ቤቱ ይህን በበቂ ምክንያት የሚያልፈው ቢሆን ተከሳሾች ቢለቀቁ ቀጠሮ አክብረው ሊቀርቡ የማይችሉ በመሆኑ፤ በማረሚያ ቆይታቸው ተቋሙን ሲረብሹ የነበሩ እና በጊዜ ቀጠሮም ፍ/ቤት ፖሊሶች ላይ ሲዝቱ ስለነበር በዋስትና ቢለቀቁ ሌላ ወንጀል ሊፈጽሙ ስለሚችሉ እና ምስክሮች ላይ ተጽእኖ ሊያደርሱ ስለሚችሉ የተከሳሾች የዋስትና መብት በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 67 (ሀ)(ለ)እና(ሐ) መሠረት ሊከለከል ይገባል በማለት በግልጽ ተቃውሞታል፡፡

ጉዳዩ የቀረበለት የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ተከሳሾች በፈጸሙት የሕገ መንግስታዊ ስልጣን ተግባራዊነት ማሰናከል ወንጀል ምክንያት የተፈጠረው ሁከት እና ብጥብጥ የከፋ ውጤት እንዳያመጣ ሲባል በጸጥታ ሀይሎች በተወሰደው እርምጃ ምክንያት የሁለት ሰዎች ሕይወት ያለፈ በመሆኑ የተከሳሾች የዋስትና መብት በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 63 መሠረት ሊፈቀድ አይገባም በማለት ውድቅ ያደረገው በመሆኑ ዓቃቤ ሕግ ዋስትናውን ለማስከልከል የሚያስችሉ በቂ ሁኔታዎች አሉ በማለት በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ 67 (ሀ)(ለ)እና(ሐ) መሠረት ያቀረባቸውን ምክንያቶቸ አልመረመረም፡፡ ከሣሽ የሆነው ዓቃቤ ሕግም የተጠሪዎች የዋስትና መብት በሕግ የተከለከለ ነው በማለት የተወሰነ በመሆኑ እና በውሳኔው ውጤትም ተጠቃሚ በመሆኑ በተሰጠው ውሳኔ ላይ ይግባኝ አልጠየቀበትም፡፡

ተጠሪዎች የስር ከፍተኛው ፍ/ቤት በዋስትናው ላይ የሰጠውን ውሳኔ በመቃወም ለፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ይግባኝ ያቀረቡትም የስር ከፍተኛ ፍ/ቤቱ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 63 መሠረት የዋስትና መብታችንን መከልከሉ አግባብ አይደለም በሚል ሲሆን ዓቃቤ ሕጉ ምላሽ የሰጠውም ይህንኑ ድንጋጌ መሠረት በማድረግ ነው፡፡

ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተው የስር ይግባኝ ሰሚው ጠቅላይ ፍ/ቤት የወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 63/1 በተከሳሾች ላይ ተፈጻሚ አይደለም ከሚል መደምደሚያ ላይ የደረሰ ሲሆን በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 67 መሠረት የዋስትና መከልከያ ምክንያት እስካልቀረበ ድረስ የተጠሪዎች የዋስትና መብት ሊነፈግ አይገባም በማለት የተጠሪዎች የዋስትና መብት ሊነፈግ አይገባም በሚል ወስኗል፡፡ የስር ይግባኝ ሰሚው ጠቅላይ ፍ/ቤት ይህንኑ መሠረት በማድረግ ውሳኔ የሰጠ ቢሆንም ዓቃቤ ሕግ በስር ከፍተኛው ፍ/ቤት ተከሳሾች ቢለቀቁ ቀጠሮ አክብረው ሊቀርቡ የማይችሉ በመሆኑ፤ በማረሚያ ቆይታቸው ተቋሙን ሲረብሹ የነበሩ እና በጊዜ ቀጠሮም ፖሊሶች ላይ ሲዝቱ ስለነበር በዋስትና ቢለቀቁ ሌላ ወንጀል ሊፈጽሙ ስለሚችሉ እና ምስክሮች ላይ ተጽእኖ ሊያደርሱ ስለሚችሉ የተከሳሾች የዋስትና መብት በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 67 (ሀ)(ለ)እና(ሐ) መሠረት ሊከለከል ይገባል በማለት የጠየቀ መሆኑ የስር ከፍተኛው ፍ/ቤት ወሳኔ በግልጽ የሚያሳይ ሆኖ ሳለ ይህንኑ ምክንያት መርምሮ ራሱ ውሳኔ ሊሰጥበት ወይም ጉዳዩን ለስር ከፍተኛው ፍ/ቤት በመመለስ የስር ከፍተኛው ፍ/ቤት ምክንያቶቹ ዋስትናን ለማስከልከል የሚያስችሉ በቂ እና አሳማኝ ምክንያቶች መሆናቸውን መርምሮ እና መዝኖ ውሳኔ እንዲሰጥበት ማድረግ ሲገባው ዓቃቤ ሕግ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 67 (ሀ)(ለ)እና(ሐ) መሠረት ለስር ከፍተኛው ፍ/ቤቱ ያቀረባቸው ምክንያቶች ከመነሻውም እንዳልቀረቡ በመቁጠር በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 67 መሠረት የዋስትና መከልከያ ምክንያት እስካልቀረበ ድረስ የተጠሪዎች የዋስትና መብት ሊነፈግ አይገባም በማለት የተጠሪዎችን የዋስትና መብት በመንፈግ የሰጠው ውሳኔ ዋስትናን አስመልክቶ አግባብነት ባላቸው ሕጎች የተደነገጉትን ድንጋጌዎች ያላገናዘበ እና ፍ/ቤቶች ክርክርን በመምራት ረገድ ሊከተሉት የሚገባውን የክርክር አመራር ስርዓት ያላገናዘበ በመሆኑ አብላጫው ድምጽ በዚህ ረገድ የስር ይግባኝ ሰሚው ጠቅላይ ፍ/ቤት የሰጠው ውሳኔ ተገቢ ነው ሲል በደረሰበት መደምደሚያ በሃሳብ ተለይቻለሁ፡፡

ቤ/ፍ የማይነበብ የአንድ ዳኛ ፊርማ አለበት፡፡

የሰ/መ/ቁ.163947

ሐምሌ 15 ቀን 2011 ዓ.ም.

**ዳኞች፡-**ብርሃኑ አመነው

በዕውቀት በላይ

እንዳሻዉ አዳነ

ሃይሉ ነጋሽ

እስቲበል አንዱዓለም

**አመልካች፡-** የፌዴራል ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ

**ተጠሪዎች፡-** 1. አቶ ጌታቸው ዋለልኝ

2. አቶ ብሩክ አስፋው ወሰን

3. አቶ ፍስሐ ጸጋዬ

መዝገቡ የተቀጠረው መርምሮ ፍርድ ለመስጠት ነው፡፡ በመሆኑም መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ይህ የሰበር አቤቱታ ሊቀርብ የቻለው አመልካች መስከረም 22 ቀን 2011 ዓ.ም ጽፎ ባቀረበው የሰበር አቤቱታ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 209610 መጋቢት 18 ቀን 2010 ዓ.ም የሰጠው ብይን በማጽናት የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁ 156419 ሐምሌ 12 ቀን 2010 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለቱ ነው፡፡

ጉዳዩ በሙስና ወንጀል ተከሶ የነበረን ሰው ምስክር ስለማድረግ በሚመለከት የቀረበ የማስረጃን ተቀባይነት ( Admissibility ) ክርክርን የሚመለከት ነው፡፡ የአሁን አመልካች በአሁን ተጠሪዎች ላይ በስር ፍ/ቤት አቅርቦባቸው የነበሩት ክሶች ሶስት ሲሆኑ ይዘታቸውም፡- 1ኛ ክስ፡- ተጠሪዎች የአዋጅ ቁጥር 881/2007 አንቀጽ 32/2 ድንጋጌን በመተላለፍ 1ኛ ተጠሪ የብሔራዊ መረጃ እና ደህንነት አገልግሎት ሠራተኛነቱን በመጠቀም ለሀገራዊ ስራ ነው በሚል ሙሉጌታ ተመስገን እና ኑርሁሴን ጠይብ የተባሉ ሰዎችን በመመልመል በ2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች አማካኝነት ሀሰተኛ የሆኑ የኢምባሲ

መታወቂያዎች እና ሌሎች ሰነዶችን በማዘጋጀት የማይገባ ብልጽግና ለማግኘት ከባድ የአታላይነት ወንጀል ፈጽመዋል፡፡ በ2ኛ ክስ የአዋጅ ቁጥር 881/2007 አንቀጽ 23/2/ ድንጋጌን በመተላለፍ በ1ኛ ክስ በተገለጸው ሁኔታ ሀሰተኛ ሰነድ እንዲዘጋጅ ካደረጉ በኋላ በሀሰተኛ ስም ከየመን እና ከአንጎላ ኤምባሲ ዕቃዎች ፍተሻ ሳይከናወንባቸው እና ቀረጥ እና ታክስ ሳይከፈልባቸው ወደ አገር እንዲገቡ እና ለነጋዴ እንዲከፋፈሉ በማድረግ በወንጀል ድርጊት እና በተገኘው ውጤት ሙሉ ተካፋይ በመሆን ያልተገባ የገንዘብ ጥቅም በማግኘት በግብረአበርነት በፈጸሙት ሀሰተኛ ሰነድ መገልገል የሙስና ወንጀል ተከሰዋል የሚል ነው፡፡ 3ኛ ክስ 1ኛ ተጠሪ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 32/1/ሀ/ እና የጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 859/2007 አንቀጽ 166/1 ድንጋጌን በመተላለፍ በጉምሩክ ወንጀል የተጠረጠረን ዕቃ በማጓጓዝ ላይ የነበረን ተሽከርካሪ ፍተሻ እንዳይደረግበት እና እንዲያመልጥ በማድረግ ሀሰተኛ መረጃ ለጉምሩክ ኢንተልጀንስ ሠራተኞች በመስጠት የጉምሩክ ቁጥጥርን የማሰናከል ወንጀል ፈጽሟል የሚል ነው፡፡

ክሱ ለተጠሪዎች ተነቦላቸው ተጠሪዎች መቃወሚያ በማቅረባቸው ዐቃቤ ሕግ መልስ እንዲሰጥበት በማድረግ ብይን ለመስጠት በተያዘው ቀነ-ቀጠሮ ዓቃቤ ሕግ ለፍ/ቤቱ ባቀረበው አቤቱታ 1ኛ እና 2ኛ የዓቃቤ ሕግ ምስክሮችን ተከሳሽ አድርጎ ለማቅረብ በ2ኛ ተጠሪ ላይ የቀረበውን ክስ ደግሞ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 122/1 መሠረት በማንሳት ምስክር ለማድረግ እንዲፈቀድለት ጠይቋል፡፡

ጉዳዩ የቀረበለት የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ዓቃቤ ሕግ ባቀረበው አቤቱታ ላይ 1ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች አስተያየት እንዲሰጡበት ካደረገ በኋላ ዓቃቤ ሕግ በክሱ ማስረጃ ዝርዝር በተ.ቁ 1 እና 2 ላይ የተመለከቱትን ምስክሮች በተከሳሽነት አካቶ ለማቅረብ ያቀረበው ጥያቄ ተገቢ በመሆኑ በዚህ ረገድ ክሱ ተሻሽሎ እንዲቀርብ ተፈቅዶለታል፤ ሆኖም 2ኛ ተጠሪን ከተከሳሽነት ሰርዞ ምስክር አድርጎ ለማቅረብ የጠየቀውን በተመለከተ በአዋጅ ቁጥር 881/2007 አንቀጽ 8 እና የአዋጅ ቁጥር 882/2007 እና 434/97 አንቀጽ 43 ድንጋጌ በአዋጅ ቁጥር 882/2007 እንደተሻሻለው መሠረት ግብረአበርን ከክሱ ነጻ በማድረግ በምስክርነት አካቶ የመቅረብ መብት ተግባራዊ ሊሆን የሚችለው ጉዳዩ ፍ/ቤት ከመቅረቡ በፊት ስለተፈጸመው ድርጊት እና ስለተባባሪዎቹ ሚና ግለሰብ ጠቃሚ ማስረጃ ከሰጠ ሲሆን ከዚህ ድንጋጌ ግለሰብ የሚጠቀመው ለክርክሩ አመራር ጠቃሚ ማስረጃ ከሰጠ እና የምርመራውን መንገድ መምራቱ ከተረጋገጠ ሲሆን በዚህ ደረጃ የሚሰጠው መረጃም ምስክሩ በገለልተኝነት ፍትሕን የመረዳቱን ሚና እንዲጫወት የሚረዳው ሲሆን ግለሰቡ በተከሳሽነት ከተካተተ በኋላ ያውም ክሱ ተሰምቶ አጠቃላይ የክርክሩን ሂደት በተረዳ እና ተከሳሽ ከሌሎች ተከሳሾች ጋር በመታሰሩ ምክንያት የሚያገኘውን መረጃ እና የቀሪ ተከሳሾችን የክርክር አመራር ከተረዳ በኋላ ወደ ምስክርነት እንዲቀየር መፍቀዱ የክርክሩን ሚዛናው አሰራር የሚጎዳ የተከሳሾችን የመከላከል ሕገ መንግስታዊ መብት የሚሸረሽር በመሆኑ የዓቃቤ ሕግ ጥያቄ በቀጥታ የሙስና አዋጁን ልዩ የስነ-ስርዓት የማስረጃ ሕጉን መሠረት ያላደረገ ቢሆንም ጥያቄው ሊመዘን የሚገባው ችሎቱ በዋነኝነት ከሚመራበት ለጉዳዩ የበለጠ አግባብነት ካለው ከአዋጅ

ቁጥር 882/2007 አንጻር ሲሆን ስለሚገባ ዓቃቤ ሕግ 2ኛ ተጠሪን ምስክር አድርጎ ለማቅረብ ያቀረበው ጥያቄ አግባብነት የለውም በማለት በአብላጫ ድምጽ ውድቅ አድርጎታል፡፡

አመልካች ይህን ትዕዛዝ በመቃወም ለፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የይግባኝ አቤቱታ አቅርበዋል፡፡ ይግባኙ የቀረበለት ፍ/ቤት ግራቀኙን ካከራከረ በኋላ ግብረአበር ከክስ ነጻ ተደርጎ ማስረጃ የሚሆነው ጉዳዩ ፍ/ቤት ከመቅረቡ በፊት ጠቃሚ ማስረጃ ከሰጠ ስለመሆኑ በሕጉ ከማረጋገጣችንም በላይ ሕጉም ይህን ያደረገው በዓላማ በመሆኑ እና አሁን ክስ ይነሳለት የተባለው ግለሰብ ግን ከግብረአበሮቹ ጋር አብሮ በፍ/ቤት ክስ ቀርቦበት የግብረአበሮቹን የክርክር አመራር ከተረዳ በኋላ ስለሆነ የስር ፍ/ቤት የሰጠው ብይን ሊነቀፍ አይገባም በማለት አጽንቶታል፡፡

የሰበር አቤቱታው የቀረበው ይህን ውሳኔ በመቃወም መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስሕተት ተፈጽሞበታል በሚል ሲሆን ይዘቱም በአዋጅ ቁጥር 881/2007 አንቀጽ 8 እና አዋጅ ቁጥር 434/97 አንቀጽ 43 … ጉዳዩ ፍ/ቤት ከመቅረቡ በፊት … የሚለው መስፈርት የተቀመጠው በምርመራ ወቅት በወንጀል ተሳታፊ የሆኑ ሰዎችን ማስረጃ የሆኑ ሰነዶችን በማምጣት ሆነ ምስክር በመሆን ምርመራውን እንዲያግዙ እና ለፍትሕ ተባባሪ እንዲሆኑ በማድረግ በምርመራው የተጠናከረ ማስረጃ ለማግኘት ሲባል የተቀመጠ ማበረታቻ ነው፤ በሌላ አገላለጽ አንድ ጠቋሚ ወይም በወንጀሉ ውስጥ ተሳትፎ የነበረው ሰው ወደ ምስክር ሊዞር ይገባል የሚል ጥያቄ ቢያቀርብ ጥያቄው ተቀባይነት የሚያገኝበት መስፈርት ብቻ እንጂ ዓቃቤ ሕግ አንድ ጊዜ ክሱን ፍ/ቤት ካቀረበ በኋላ ክሱን በመሰረዝ ወደ ምስክር ማዞር አይችልም የሚል ክልከላ ያስቀመጠ ድንጋጌ አይደለም፤ ዓቃቤ ሕግ በራሱ ውሳኔ በየትኛውም ደረጃ ላይ የሚገኝን ጉዳይ አስመልክቶ ተከሳሽን ከክስ ነጻ በማውጣት ወደ ምስክር ለማዞር ይህ መስፈርት በየትኛውም ሕግ በአስገዳጅነት አልተቀመጠም፤ የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎትም በሰ.መ.ቁ 57988 ክስ የቀረበ ቢሆንም ዓቃቤ ሕግ ተከሳሽ የነበረን ሰው ወደ ምስክርነት ማዞር እንደሚችል በመግለጽ ትርጉም ሰጥቶበታል፤ ዓቃቤ ሕግ 2ኛ ተጠሪን ከተከሳሽነት አውጥቶ ወደ ምስክር ያዞረበት አግባብ ግለሰቡ ተከሶ ፍ/ቤት ከቀረበ እና በኋላም በመታሰሩ ምክንያት ያገኘውን ዕውቀት ለማስመስከር እና የተከሳሾችን የመከላከል መብት በመሸርሸር የክርክሩን ሚዛናዊ አሰራር ለመጉዳት ሳይሆን ግለሰቡ ቀድሞውንም በወንጀሉ አብሮ የተሳተፈ እና ይህንኑም ክስ ከመመስረቱ በፊት ተጠርጣሪ በሆነበት ጊዜ በምርመራ ክፍል ስለተፈጸመው የወንጀል ድርጊት እና ስለተባባሪዎቹ ሚና የራሱንም ተሳትፎ በመጨመር የሰጠውን የተከሳሽነት ቃል በሙሉ ቃል በቃል የምስክርነት ቃሉንም ሲሰጥ ከመድገም ውጪ ከሌሎች ተከሳሾች ጋር በመታሰሩ ምክንያት የቀየረው ወይም የጨመረው ቃል በሌለበት የወንጀሉ ዋና ፈጻሚ በሆኑ ሰዎች ላይ ውሳኔ ለማሰጠት እና ይህንንም በሌላ መንገድ በተሰበሰቡት ማስረጃዎች ብቻ ለማሳካት በቂ ባለመሆኑ ምክንያት ነው፤ ዓቃቤሕግ የ2ኛ ተጠሪ ክስ እንዲነሳ የጠየቀው በተናጠል ሳይሆን ምስክር መሆኑን እንደ ቅድመ-ሁኔታ በማስቀመጥ የነበረ ሲሆን 2ኛ ተጠሪን ወደ ምስክር ለማዞር ክስ መነሳቱ አስፈላጊ በመሆኑ ወደ ምስክር መዞሩን ፍ/ቤቱ ከፈቀደ ክስ እንዲነሳለት በሚል እሳቤ እንጂ ተከሳሹ

ወንጀል አልፈጸመም በሚል እሳቤ ክሱ እንዲነሳለት ብቻ ተፈልጎ አይደለም፤ በመሆኑም የስር ፍ/ቤቶች እነኚህን ሁኔታዎች ሳያገናዝቡ የሰጡት ውሳኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል የሚል ነው፡፡

የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ አመልካች በስር ፍ/ቤት የሰው ማስረጃ ከመስማቱ በፊት በወ/መ/ስ/ስ/ሕ/ቁ 122/1 መሠረት በቀን 04/07/2010 ዓ.ም በተጻፈ አቤቱታ መሠረት በ2ኛ ተከሳሽ ላይ ያቀረብነው ክስ እንዲነሳ እና በቀሪ ተጠርጣሪዎች ላይ ማስረጃ ለማድረግ የስር ፍ/ቤት የአሁን አመልካችን ጥያቄ ውድቅ የማድረጉን አግባብነት በሰ/መ/ቁ 57988 ከተሰጠው አስገዳጅ የሕግ ትርጉም ጋር በማገናዘብ ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ በዚህ ችሎት እንዲታይ ተደርጓል፡፡ ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎም ግራቀኙ በጽሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡ 2ኛ ተጠሪ በጋዜጣ ጥሪ ተደርጎለት ስላልቀረበ መልስ በጽሑፍ የመስጠት መብቱ ታልፏል፡፡

1ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች የሰጡት መልስ ይዘት በሙስና ወንጀሎች አዋጅ ላይ በግልጽ እንደተመለከተው ተከሳሹ ከሌሎች ተከሳሾች ጋር ክስ ቀርቦበት አብሮ ታስሮ ወደ ምስክርነት ሊቀየር የሚችልበት የሕግ መሠረት የለም፤ 2ኛ ተጠሪ አብሮን ክስ ቀርቦበት የነበረ እና ስለተከሰስንበት ወንጀል አብሮን ተከሳሽ መሆኑን ታሳቢ በማድረግ ከእኛ የሰማውን መረጃ ወደ ምስክርነት ቀይሮ እኛን በሚጎዳ መልኩ እንዲመሰክር መፍቀድ በራሳችን ጉዳይ እኛን የሚጎዳ የምስክርነት ቃል እንዲሰጥ የማስገደድ ያህል ነው፤ አመልካች የጠቀሰው የሰበር መዝገብም ለጉዳዩ ተፈጻሚ ሊሆን አይገባም፤ አመልካች 2ኛ ተጠሪን በምስክርነት ማቅረብ የፈለገበት ምክንያት በአቤቱታው ላይ እንደገለጸው ሳይሆን ሆን ብሎ ከተጠሪዎች ጋር እንዲታሰር በማድረግ ተከሳሾች ነን በሚል ግለሰቡ ነገ በምስክርነት ይቀርብብናል የሚል ጥርጣሬ በሌለበት ከእኛ ያገኘውን መረጃ እና እውቀት ተጠቅሞ እኛን ለመጉዳት ታስቦ የተደረገ በመሆኑ የስር ፍ/ቤቶች 2ኛ ተጠሪ በምስክርነት ሊቀርብ አይገባም በማለት የሰጡት ውሳኔ ተገቢ ስለሆነ ሊጸና ይገባል የሚል ነው፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ በአጭሩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራቀኙን ክርክር፤ ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ፤ ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች እና በሰበር አጣሪው ችሎት ሊጣራ ይገባል ተብሎ ከተያዘው ነጥብ ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው መርምሮታል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የሚቻለው አመልካች በስር ፍ/ቤት 2ኛ ተከሳሽ በነበረው 2ኛ ተጠሪ ላይ አቅርቦት የነበረውን ክስ በማንሳት /በማቋረጥ/ ፤ ሌሎችን በተከሳሽነት በማካተት እና በሌሎች ምክንያት ጭምር ክሱን በማሻሻል 2ኛ ተጠሪን ምስክር አድርጐ ለማቅረብ ያቀረበውን አቤቱታ ፍርድ ቤቱ በ2ኛ ተጠሪ ላይ የቀረበውን ክስ መነሳት ተቀብሎ 2ኛ ተጠሪ ከሌሎች አመልካቾች ጋር ተከሶ የነበረ በመሆኑ ምስክር ሆኖ ሊቀርብ አይችልም በማለት መወሰኑን እና ይኸው በይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት መጽናቱን የሚመለከት በመሆኑ በወንጀል ክስ ክርክር ምክንያት የዐቃቤ ሕግ ምስክር ተቀባይነት የሌለው ምስክር

(Inadmissible evidence) ነው የሚለውን ለዚህ ችሎት ያስቀርባል ሲባል ከተያዘው ነጥብ አንጻር መርምረናል፡፡

የአገራችን የፍትሕ ስርዓት በአንድ መጽሐፍ ስር የተጠቃለለ ዝርዝር የማስረጃ ሕግ የሌለው ቢሆንም በተለያየ ሁኔታ የማስረጃን ተቀባይነት፣ የማስረጃን አግባብነት፤ አመራመርና ምዘና መርሆችን የሚደነግጉ የማስረጃ ሕግ ድንጋጌዎች በሕገ መንግስቱና በሌሎች የይዘትና የስነ-ስርዓት ሕግ ውስጥ በተበታተነ ሁኔታ ተደንግገው ይገኛሉ፡፡ ከነዚህም ውስጥ የወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ እና የተሻሻለው የጸረ ሙስና ልዩ የሥነ ሥርዓትና የማስረጃ ሕግ አዋጅ ቁጥር 434/1997 ተጠቃሽ ነው፡፡

በመሰረታዊነት የአንድን ጉዳይ ዓይነት መሠረት በማድረግ የክርክሩን ጭብጥ ለማስረዳት ሊቀርብ የሚገባዉ የማስረጃ ዓይነት (Admissibility) በልዩ ሁኔታ በህግ እስካልተወሰነ ድረስ በተከራካሪ ወገኖች ክሱን ወይም ክርክሩን ያስረዱልኛል ወይም ይከላከሉልኛል የሚሏቸዉን ማንኛዉንም ዓይነት ማስረጃ ማቅረብ የሚችሉ ስለመሆኑ፣ በዚህ መልኩ በተከራካሪ ወገኖች የሚቀርብ ማስረጃ ደግሞ የተያዘዉን የክስ (ክርክር) ጭብጥ ለማስረዳት አግባብነት ያለው መሆኑ (Relevancy) እስከተረጋገጠ ድረስ የክርክሩን ጭብጥ ለማስረዳት ብቃት አለዉ ተብሎ እንደሚገመት፣ ጉዳዩን የያዘዉ ፍርድ ቤትም ግራ ቀኝ ያቀረቧቸዉን ማስረጃዎች ለእያንዳንዱ ማስረጃ ተገቢዉን ዋጋ በመስጠት ማስረጃዎችን ከነሙሉ ይዘታቸዉ መመዘን እንደሚገባዉ የማስረጃ አቀባበል እና ምዘና መርህ ያስገነዝባል፡፡ ስለሆነም አንድ ማስረጃ ተቀባይነት የሌለው ለፍርድ ሥራ በግብዓትነት መቅረብ የሌለበት ነው ወይም ማስረጃው ቀርቦ ከመዝገቡ ጋር ቢያያዝ እንኳን ዳኞች የማስረጃውን ይዘት፣ ተዓማኒነትና ክብደት ለመወሰንና በፍርድ ሥራ በግብዓትነት መጠቀም የሌለባቸው መሆኑን የሚገልጽ፤ማስረጃው በማስረጃነት ቀርቦ ከመመርመርና ከመመዘን የሚከለክለው ግልጽ ከልካይ የሆነ የሕግ ድንጋጌ ሊኖር ይገባል፡፡

ወደያዝነው ጉዳይም በዋነኛነት በወንጀል ክስ ጉዳይ ምክንያት በምስክርነት የሚጠሩ ሰዎች መመስከር የሚጠበቅባቸው ውሳኔ ስለሚሰጥበት ፍሬ ነገር ተገቢ የሆኑትን በቀጥታም ሆነ ቀጥታ ባልሆነ መንገድ ስለሚያውቃቸው ፍሬ ነገሮች (የወ/መ/ሕ/ስ/ስ/ቁ.137(1)) በመሆኑ በወንጀል ጉዳይ የቀረበን አንድ ማስረጃን ውድቅ ሊደረግ የሚችለው በማስረጃነት እንዳይቀርብ ሕግ የከለከለው (Inadmissible ) ሲሆን እና በፍርድ ቤት ተመዝኖ ተቀባይነት ሲያጣ ነው፡፡ ከዚህ ውጪ የወንጀልም ሆነ የሥነሥርዓት ሕጉ የወንጀል ክስን ለማስረዳት ወይም ለመከላከል መቅረብ የሚገባቸውን የማስረጃ ዓይነቶች ለይተው አልደነገጉም፡፡ ከዚህ አንጻር አመልካች ከሌሎች ተጠሪዎች ጋር በ2ኛ ተጠሪ ላይ አቅርቦት የነበረውን ክስ ማንሳቱን ፍርድ ቤቱ ተቀብሎ አመልካች አሻሽሎ በሚያቀርበው በዚሁ ክስ 2ኛ ተጠሪን ምስክር አድርጎ ለማቅረብ ያቀረበውን አቤቱታ ግን ያልተቀበለው ስለመሆኑ የሰጠው ምክንያት ደግሞ አመልካች ግብረአበርን ከክስ ነጻ በማውጣት በምስክርነት ተግባራዊ ሊሆን የሚችለው ጉዳዩ ፍርድ ቤት ከመቅረቡ በፊት ነው እንጂ ክስ ቀርቦ ከተሰማና ከሌሎች ተከሳሾች አጠቃላይ የክርክሩን

አካሄድ ከተረዳ በኋላ ሊቀርብ የሚገባ አይደለም፤ አዋጅ ቁጥር 881/2007 አንቀጽ 8 ፤ አዋጅ ቁጥር 882/2007 ና 434/97 አንቀጽ 43 ድንጋጌዎች መሰረት ያላደረገ ነው የሚል ነው፡፡ ይህም የሚመለክተው 2ኛ ተጠሪ ምስክር ሆኖ እንዳይቀርብ የህግ ክልከላ አለ ወይም በህጉ ምስክር አድርጎ ለማቅረብ አልተመለከተም በማለት ውድቅ ማድረጉን የሚያመለክት ነው፡፡

የሙስና ወንጀሎችን የሚደነግገው አዋጅ ቁጥር 881/2007 አንቀጽ 8 ሆነ የተሻሻለው የጸረ ሙስና ልዩ የሥነ ሥርዓትና የማስረጃ ሕግ አዋጅ ቁጥር 434/1997 እንደተሻሻለው አዋጅ ቁጥር 882/2007 አንቀጽ 41 የሚደነግጉት ከወንጀሉ ልዩ ባህሪ አንጻር በምርመራ ወቅት ፤ጉዳዩ ፍርድ ቤት ከመቅረቡ በፊት ባሉት ጊዜያት፤ በወንጀል ድርጊቱ ተካፋይ የሆነ ሰው በአዋጁ የተመለከቱት ሁኔታዎች ተሟልተው ሲገኙ ሊቀርብበት ከነበረበት ክስ ነጻ ስለሚወጣበት ሁኔታ ነው፡፡ ስለሆነም ስለወንጀሉ በሰጠው ጠቃሚ መረጃ መሰረት ምርመራውን በማገዙ ምክንያት ፍርድ ቤት ክሱ ከመቅረቡ በፊት የሚያገኘው ነው፡፡ በፍርድ ቤት ምስክር አድርጎ የማቅረብ ጉዳይ አመልካች ምርመራው ተጠናቅቋል ብሎ ሲያምን በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ 108-122 እንደተመለከተው የክስ ማመልከቻውን አዘጋጅቶ ሲያቀርብ የሚገልጸው ነው፡፡ የአመልካች አቤቱታም ለስር ፍርድ ቤት የቀረበው በዚሁ የክርክር ደረጃ ላይ ሲሆን የስር ፍርድ ቤት ከክስ በፊት ያለውን የሙስና ወንጀሎችን የሚደነግገው አዋጅ ቁጥር 881/2007 አንቀጽ 8 እና የተሻሻለው የጸረ ሙስና ልዩ የሥነ ሥርዓትና የማስረጃ ሕግ አዋጅ ቁጥር 434/1997 እንደተሻሻለው አዋጅ ቁጥር 882/2007 አንቀጽ 41 መሰረት በማድረግ የደረሱበት ድምዳሜ ህጉን ያላገናዘበ ከመሆኑም ባሻገር  ድንጋጌዎቹ በዋናነት ግብረአበርን ከክስ ነጻ ማድረግን እንጂ በፍርድ ቤት የሚቀርብ ክስ ላይ ምስክር ማድረግን የሚመለከቱ አይደሉም፡፡ በሰ/መ/ቁ 57988 የተሰጠው ፍርድም የሚስገነዝበው ተካሰሽ የነበረን ሰው ዐቃቤ ሕግ ክሱን በማንሳት ምስክር አድርጎ ማቅረቡንና ይህም የሚጥሰው ህግ አለመኖሩን በመግለጽ ክርክሩን አይቶ ማስረጃውን በመመዘን መወሰኑን ነው፡፡

በአጠቃላይ አንድ ድርጊት ከመፈፀሙ በፊት፣ ሲፈፀም ወይም ድርጊቱ ከተፈፀመ በኋላ ዐቃቤ ህግ ስላቀረበው ክስ ማስረጃ ይሆነኛል በማለት በሕጉ አግባብ ያቀረበውን ማስረጃ በማስረጃነት ሊቀርብ የማይችልና ተቀባይነት የሌለው (Inadmissible evidence) ነው የሚል ግልፅ ክልከላ የሚያደርግ የሕግ ድንጋጌ ከሌለ ማስረጃው ቀርቦ፣ በሕጉ አግባብ ተመዝኖ፣ የማስረጃው ትክክለኛነትና ህጋዊነት ተጣርቶ የሚወሰን እንጂ የማስረጃው አስረጂነት ዋጋ ሳይታይና ሳይመዘን በደፈናው ማስረጃው ከተከሳሾች ጋር አብሮ ተከሳሽ የነበረ ነው፤ የተከሳሾችን የመከላከል መብት ይጎዳል በሚል ምክንያት ተቀባይነት የሌለው ነው በማለት ውድቅ ማድረጉ የማስረጃ ተቀባይነት፤አግባብነትና ምዘና መርህን፤ የክርክር አመራርና የዳኝነት አሰጣጥ ስርዓትን ያልተከተለ በመሆኑን መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነው፡፡ በዚህም መሰረት ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

<u>ው ሳ ኔ</u>

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 209610 መጋቢት 18 ቀን 2010 ዓ.ም የሰጠውን ብይን በማጽናት የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁ 156419 ሐምሌ 12 ቀን 2010 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ በወ/መ/ስ/ስ/ሕ/ቁ 195/2/ለ/2 መሰረት ተሽሯል፡፡
2. አመልካች 2ኛ ተጠሪን ምስክር አድርጎ ለማቅረብ ያቀረበው አቤቱታ በልዩ ሁኔታ በህግ ያልተከለከለ በመሆኑ ተቀባይነት ያለው (Admissible) ማስረጃ ነው፡፡
3. የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 209610 የጀመረውን ክርክር ቀጥሎ ማስረጃዎቹን ሰምቶ ለእያንዳንዱ ማስረጃ ተገቢዉን ዋጋ በመስጠት ማስረጃዎችን በመመዘን ተገቢውን ዳኝነት እንዲሰጥበት በማለት መልሰን ልከንለታል፡፡ይጻፍ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ሰ/ጥ

የሰ/መ/ቁጥር 182050

ታሕሳስ 24 ቀን 2012 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** እትመት አሠፋ

ጳውሎስ ኦርሺሶ

ፀሐይ መንክር

መላኩ ካሣዬ

እስቲበል አንዱዓለም

**አመልካች፡-** የፌዴራል ጠቅላይ ዐ/ህግ

**ተጠሪ፡-** ብርጋዴር ጀነራል ሐድጉ ገ/ጊዮርጊስ

መዝገቡ የተቀጠረው መርምሮ ፍርድ ለመስጠት ነው፡፡ በመሆኑም መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍርድ**

ጉዳዩ የዋስትና ክርክርን የሚመለከት ሲሆን የሰበር አቤቱታው የቀረበው የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በወ/ይ/መ/ቁ 180500 ላይ ሐምሌ 30/2011 ዓ.ም በዋለው ችሎት ተጠሪ እንዲከላከሉ ብይን የተሰጠባቸው ሁለቱም ድንጋጌዎች የዋስትና መብት የማያስከለክሉ በመሆኑ በዋስ ሆነው ጉዳያቸውን እንዲከታተሉ ሲል የሰጠውን ውሳኔ በመቃወም ነው፡፡

ጉዳዩ የተጀመረው የአሁን አመልካች በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የአሁን ተጠሪን ጨምሮ በአራት ግለሰቦች ላይ አዋጅ ቁጥር 881/2007 በመጥቀስ ባቀረበው የሙስና ወንጀል ክስ ነው፡፡ ጉዳዩ የቀረበለት ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክር እና የዐቃቤ ሕግ ማስረጃን ከሰማ በኋላ ሰኔ 07 ቀን 2011 ዓ.ም በዋለው ችሎት የአሁን ተጠሪን በተመለከተ ክስ የቀረበበትን የአዋጁን አንቀፅ 9/1/ሀ/ለ/2/ ድንጋጌን በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 113/2/ መሠረት ወደ አንቀፅ 9/1/ሀ/ለ በመቀየር እንዲከላከሉ ብይን ሰጥቷል፡፡ ይህንኑ ብይን ተከትሎ ተጠሪ ባቀረቡት የዋስትና ጥያቄ ላይ የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ ተጠሪ በሁለት ክሶች እንዲከላከሉ የተባለ መሆኑን እና የሁለቱ ክሶች ቅጣት ሲደመር ከ10 ዓመት በላይ መሆኑን በመግለፅ የዋስትና ጥያቄውን በአዋጅ ቁጥር 434/1997 አንቀፅ 4 መሠረት ውድቅ አድርጓል፡፡

ተጠሪ የዋስትና ጥያቄውን በሚመለከት በስር ፍ/ቤት የተሰጠውን ብይን በመቃወም ለፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የይግባኝ አቤቱታ አቅርበዋል፡፡ ከዋስትና አንፃር የተሰጠውን ብይን በይግባኝ የተመለከተው የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎትም ግራቀኙን ካከራከረ በኂላ በአዋጅ ቁጥር 882/2007 አንቀጽ 3/1 ከአራት ዓመት በላይ እና ከአስር ዓመት በታች የሚያስቀጡ ተደራራቢ ወንጀሎች ሲኖሩ እየተደመሩ ከ10 ዓመት በላይ የሚያስቀጣ ከሆነ ዋስትና ይከለክላል የሚለው የሕግ አገላለጽ በግልጽ እንደሚያሳየው ከአራት ዓመት በላይ የሚለው አገላለጽ መነሻ ቅጣቱ አራት ዓመት እና በላይ የሆነ ድንጋጌን የሚመለከት እንደሆነ የሚያሻማ አይደለም፤ ተደራራቢ ወንጀሎች እየተደመሩ ከ10 ዓመት በላይ በሆነ ጊዜ ዋስትና ሊያስከለክል እንደሚገባ የድንጋጌው ሀሳብ ቢሆን ኖሮ ከአራት ዓመት በላይ የሚለው አገላለጽ ባላስፈለገ ነበር፤ ይህ ከሆነ ደግሞ የዚህ ድንጋጌ ዓላማ ከአራት ዓመት በላይ የሚያስቀጣ ተደራራቢ ወንጀልን የሚመለከት እንጂ ተጠሪ እንዲከላከል ብይን የተሰጠበት አንቀጽ 9/1/ሀ/ለ መነሻ ቅጣቱ አንድ ዓመት ቀላል እሥራት ወይም አንድ ዓመት ጽኑ እሥራት የሚለውን የሚጨምር ነው በሚል የሚተረጎም አይደለም፤ በይግባኝ ባይ ላይ የተለየ ከወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 67 አኳያ የዋስትና መብቱን የሚያስከለክል ምክንያት ባልቀረበበት ሁኔታ ተደራራቢ ወንጀሎች ተደምረው ከ10 ዓመት በላይ ሊያስቀጣ የሚችል ነው በማለት የዋስትና መብት መከልከሉ የአዋጅ ቁጥር 882/2007 አንቀጽ 2 ንኡስ ቁጥር 3/1 ድንጋጌን የሚቃረን ነው በማለት ተጠሪ ለብር 100,000 የሚበቃ ዋስ ሲያቀርቡ ከእስር እንዲፈቱ ሲል ወስኗል፡፡

የሰበር አቤቱታው የቀረበው ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም መሠረታዊ የሕግ ስሕተት ተፈጽሞበታል በሚል ሲሆን ይዘቱም፡- የተሻሻለው የፀረ-ሙስና ልዩ የሥነ ሥርዓትና ማስረጃ አዋጅ ቁጥር 434/1997 አንቀፅ 4/1 / በአዋጅ ቁጥር 882/2007 እንደተሻሻለው / የድንጋጌው ይዘት ሊተረጎም የሚገባው ከ4 ዓመት በላይ እና ከ10 ዓመት በታች የሚያስቀጡ ተደራራቢ ወንጀሎች የእያንዳንዱ ተደራራቢ ወንጀል የቅጣት ጣሪያው ከ4 ዓመት በላይ እና ከ10 ዓመት በታች የሚያስቀጡ ሲሆን እንደሆነ እና መደመር ያለባቸው ተደራራቢ ወንጀሎች የቅጣት ጣሪያቸውን እና የወንጀሎችን ክብደት መሠረት በማድረግ እንደሚደመሩ ሕጉ ሲረቀቅ መነሻ ከተደረጉት ምክንያቶች እና ከወንጀሎቹ ክብደት አኳያ መረዳት እየተቻለ ይግባኝ ሰሚ ጠቅላይ ፍርድ ቤት 4 ዓመት የተባለውን እንደመነሻ ቅጣት ወስዶ ተጠሪን በዋስትና መልቀቁ ከህጉ መንፈስ ውጭ ከመሆኑም በላይ የአዋጁን ተፈፃሚነት ከጥያቄ የሚያስገባ ነው፤ በዚህ አዋጅ እና በሌሎችም የሙስና ወንጀሎች ድንጋጌዎች መነሻቸው አራት ዓመት እና ከዚያ በላይ የሆኑ የሙስና ወንጀሎች የሉም፤ በሙስና ወንጀል የዋስትና ክርክር ጊዜ ክስ የቀረበበት ድንጋጌ ጣሪያ ቅጣት ሊታይ እንደሚገባ የፌ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ችሎት በሰ.መ.ቁ 63344 ላይ ትርጉም የሰጠ በመሆኑ 4 ዓመት የተባለው የቅጣቱ ጣሪያ በሚለው ሊወሰድ ሲገባው በሕጉ ባልተደነገገበት ሁኔታ 4 ዓመትን እንደመነሻ ቅጣት መወሰዱ አግባብ አይደለም፤ ከዋስትና አሰጣጥ አንፃር የቀረበው የክስ ብዛት ከግንዛቤ ሊገባ እንደሚገባ ይኸው ሰበር ችሎት በሰ.መ.ቁ 59302 ላይ ትርጉም የሰጠ በመሆኑ እና ተጠሪ እንዲከላከሉ

ብይን የተሰጠው እስከ 10 ዓመት በሚደርስ ፅኑ እስራት ሊያስቀጡ በሚችሉ ሁለት ወንጀሎች በመሆኑ ተደራራቢ ክሱ ከሚያስከትለው ቅጣት አንፃር የዋስትና ጥያቄው በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 67/ሀ መሠረት ሊታይ ሲገባው መታለፉ አግባብ ስላልሆነ የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ ተሽሮ ተጠሪ በማረሚያ ቤት ሆነው ጉዳያቸውን እንዲከታተሉ ሊወሰን ይገባል የሚል ነው፡፡

የአመልካቹ የሰበር አቤቱታ በሰበር አጣሪው ችሎት ተመርምሮ የአሁን ተጠሪ በአዋጅ ቁጥር 881/2007 አንቀፅ 9/1/ ስር በሁለት ወንጀሎች እንዲከላከሉ ብይን ተሰጥቶ እያለ የስር ፍርድ ቤት በዋስትና እንዲለቀቁ የመወሰኑን አግባብነት ከአዋጅ ቁጥር 881/2007 አንቀፅ 9/1፤ አዋጅ ቁጥር 882/2007 አንቀፅ 2 እና በሰ.መ.ቁ 63344 እና 124750 ላይ ከተሰጠው አስገዳጅ ትርጉም አኳያ ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ በዚህ ችሎት እንዲታይ ተደርጓል፡፡ ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎም ግራቀኙ በጽሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

የተጠሪ መልስ ይዘት በአጭሩ፡- በተጠቀሰው ድንጋጌ ውስጥ 4 ዓመት የተባለው መነሻ ቅጣት ለመሆኑ ህጉ በግልፅ ያስቀመጠ በመሆኑ የይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት ውሳኔ የሚነቀፍ አይደለም፤ ዋስትና ሊከለከል የሚችለው ከ4 ዓመት በላይ በሆነ ተደራራቢ ወንጀል ለመሆኑ ሕጉ በግልጽ አስቀምጧል፤ አራት ዓመት እንደቅጣት ጣሪያ ሊወሰድ አይገባም፤ አመልካች ተከላከል የተባልኩበት የሕግ አንቀጽ የቅጣት መነሻ የአንድ ዓመት ቀላል እስራት ነው፤ አመልካች የጠቀሳቸው የሰበር ሰሚ ችሎት ውሳኔዎች ከጉዳዩ ጋር ተያያዥነት የሌላቸው ሲሆን በ2007 ዓ.ም በወጣ አዋጅ ላይም ተፈጻሚ አይሆኑም፤ የይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት አተረጓጎም አዋጅ ቁጥር 881/2007 አፈፃፀምን የሚከለክል አይደለም፤ በአዋጅ ቁጥር 434/1997 እና በተሻሻለው አዋጅ መካከል ልዩነት ካለ አዲሱ ሕግ ተፈፃሚ ሊሆን ይገባል፤ በሰበር ችሎት ማስቀረቢያ ነጥብ ላይ የተጠቀሱት የሰበር ውሳኔዎች አሁን ከቀረበው ጉዳይ ጋር ተመሳሳይ በሆነ ጉዳይ ላይ የተሰጠ ትርጉም ሳይሆን መነሻ እና መድረሻ ቅጣቱ በግልፅ ተለይቶ ባልተጠቀሰ ድንጋጌ ከመሆኑም በላይ በተሻሻለ ሕግ ላይ የተሰጡ በመሆናቸው አሁን ለቀረበው ጉዳይ ተፈፃሚነት የላቸውም፤ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 67/ሀ ድንጋጌ መሠረት የቀረበው ክርክር በስር ፍርድ ቤት ያልተነሳ በመሆኑ ተቀባይነት የለውም፤ በመሆኑም የቀረበው ቅሬታ ውድቅ ተደርጎ የይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት ውሳኔ ሊፀና ይገባል የሚል ነው፡፡

አመልካች ነሐሴ 15/2011 ዓ.ም በተፃፈ የመልስ መልስ ክስ በቀረበበት አዋጅም ሆነ በወንጀል ህጉ መነሻ ቅጣቱ 4 ዓመት የሆነ ድንጋጌ የሌለ በመሆኑ ሕግ አውጪው የማይፈፀም ሕግን ያወጣል ብሎ መውሰድ የሕጉን መንፈስ እና ዓላማ የተከተለ አይደለም፤ ክስ የቀረበበት አዋጅ የሰበር ችሎቱ በሰ.መ.ቁ 63344 ላይ የሰጠውን ትርጉም የሚያጠናክር በመሆኑ ለቀረበው ጉዳይ አግባብነት የለውም ሊባል አይገባም፤ ተጠሪ እንዲከላከሉ ብይን የተሰጠባቸው ሁለቱም አንቀፆች የቅጣት ጣሪያ ሰበር ችሎቱ በተጠቀሰው መዝገብ ላይ የሰጠው ትርጉም ለአዋጅ ቁጥር 881/2007 ተፈፃሚ ሊደረግ ይገባል፤

የወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 67/ሀ/ ድንጋጌን አስመልክቶ የተሰጠው ውሳኔ የሕግ ትርጉም በመሆኑ እና የሰበር ክርክር የሕግ አተረጓጎምን የሚመለከት በመሆኑ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ሊመለከተው ሲገባው ያለፈውን ጉዳይ ማቅረቡ ተገቢ ነው በማለት የሰበር አቤቱታው በማጠናከር ተከራክሯል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ በአጭሩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን ይህ ችሎትም በሰበር አጣሪው ችሎት ሊጣራ ይገባዋል ተብሎ የተያዘውን ነጥብ ከግራቀኙ ክርክር፤ ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸው ሕጎች ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው መርምሮታል፡፡

ከክርክሩ ሒደት መገንዘብ የተቻለው የስር ከፍተኛው ፍ/ቤት ተጠሪ በአዋጅ ቁጥር 882/2007 አንቀፅ 9/1/ሀ/ለ/1/ ድንጋጌ በሁለት ክሶች እንዲከላከሉ ብይን የተሰጠ እና የሁለቱም ክሶች ቅጣት ሲደመር ከ10 ዓመት በላይ በመሆኑ በአዋጅ ቁጥር 434/1997 አንቀፅ 4 መሠረት የዋስትና ጥያቄው ተቀባይነት የለውም በማለት ውድቅ ያደረገው መሆኑን፤ ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተው የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ደግሞ በአዋጅ ቁጥር 882/2007 አንቀጽ 3/1 ከአራት ዓመት በላይ የሚለው አገላለጽ ከአራት ዓመት በላይ የሚያስቀጣ ተደራራቢ ወንጀልን የሚመለከት እንጂ ተጠሪ እንዲከላከል ብይን የተሰጠበትን አንቀጽ 9/1/ሀ/ለ መነሻ ቅጣቱ አንድ ዓመት ቀላል እሥራት ወይም አንድ ዓመት ጽኑ እሥራት የሚለውን የሚጨምር ነው በሚል የሚተረጎም አይደለም በማለት የተጠሪን የዋስ መብት የጠበቀ መሆኑን ነው፡፡ በመሆኑም የዚህን ችሎት ምላሽ የሚፈልገው የክርክሩ መሠረታዊ ጭብጥ፡-

1. በአዋጅ ቁጥር 882/2007 አንቀጽ 3/1 ላይ ከአራት ዓመት በላይ እና ከ10 ዓመት በታች የሚያስቀጡ ተደራራቢ ወንጀሎች ሲኖሩም እየተደመሩ ከ10 ዓመት በላይ የሚያስቀጣ ከሆነ ዋስትናን ይከለክላል በማለት የተቀመጠው ሀሳብ መነሻ ቅጣትን የሚመለከት ነው? አይደለም?
2. ተከሳሹ እንዲከላከል ብይን የተሰጠበት የሕግ አንቀጽ አማራጭ ቅጣትን ባስቀመጠ ጊዜ የዋስትናን መብት ጥያቄን ለመወሰን ሲባል ተፈጻሚ የሚሆነው የትኛው የቅጣት አማራጭ ነው?
3. የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ከወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 67 አኳያ የዋስትና መብቱን የሚያስከለክል መከራከሪያ ባልቀረበበት ሁኔታ የተጠሪ የዋስትና መብት ሊከለከል አይገባም ማለቱ ተገቢ ነው? ወይስ አይደለም? የሚሉት ናቸው፡፡

በመሆኑም ከላይ ለተያዙት መሠረታዊ የክርክሩ ጭብጦች ምላሽ መስጠት ያስችለን ዘንድ የሙስና ወንጀሎችን አስመልክቶ በሐገራችን የወጡትን ሕጎች እና በየጊዜው የወጡትን የማሻሻያ አዋጆች ሕግ አውጪው ሊያሳካው ከፈለገው ግብ እና ከዋስትና መብት መሠረታዊ መርሆዎች እና ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መመርመር አስፈላጊ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

በመሠረቱ የጸረ ሙስና ልዩ የሥነ-ሥርዓት እና የማስረጃ ሕግ አዋጅ ቁጥር 236/93 እንደተሻሻለ / አዋጅ ቁጥር 239/93 አንቀጽ 51/2 / በሙስና ወንጀል ተጠርጥሮ የተያዘ ሰው የዋስትና መብት አይኖረውም በማለት ግልጽ ክልከላ ያደረገ አዋጅ የነበረ ሲሆን ሕግ አውጪው አስቀድሞ ባወጣው

የሙስና ወንጀሎች ሕግ ዋስትናን በግልጽ ክልከላ / ገደብ / ያደረገ መሆኑን፤ በሂደት በወጣው የተሻሻለው የጸረ ሙስና ልዩ የሥነ-ሥርዓት እና የማስረጃ ሕግ አዋጅ ቁጥር 434/97 አንቀጽ 4/1/ በሙስና ወንጀል የተያዘ ሰው በዋስ እንዲለቀቅ ማመልከት ይችላል፤ ሆኖም የተከሰሰበት ወንጀል ከ10 ዓመት በላይ ሊያስቀጣ የሚችል ከሆነ በዋስትና መልቀቅ አይቻልም በማለት የሙስናን ወንጀል ቅጣት መጠንን መሠረት በማድረግ ዋስትናን ለመፍቀድ ወይም ለመንፈግ እንደመስፈርት በማስቀመጥ በዋስ የመለቀቅ መብት በመርህ ደረጃ ሕገ-መንግስታዊ መብት መሆኑን ያመላከተ ነው፡፡

በቀጣይነት የወጣው የተሻሻለው የጸረ ሙስና ልዩ የሥነ-ሥርዓት እና የማስረጃ ሕግ ማሻሻያ አዋጅ ቁጥር 882/2007 አንቀጽ 3/1 ይህንኑ ሕገመንግስታዊ መብት የበለጠ በማስፋት በሙስና ወንጀል የተያዘ ሰው በዋስ እንዲለቀቅ ለፍ/ቤት ማመልከት እንደሚችል ሆኖም የተከሰሰበት ወይም የተጠረጠረበት ወንጀል ከ10 ዓመት በላይ በሆነ ጽኑ እሥራት ሊያስቀጣ የሚችል ከሆነ በቀደሙት አዋጆች እንደተመለከተው በዋስትና መለቀቅ የማይችል መሆኑን፤ ከአራት ዓመት በላይ እና ከ10 ዓመት በታች የሚያስቀጡ ተደራራቢ ወንጀሎች ሲኖሩም እየተደመሩ ከ10 ዓመት በላይ የሚያስቀጣ ከሆነ ግን ዋስትና የሚከለክሉ መሆኑን ይደነግጋል፡፡

በሙስና ወንጀል የተያዘን ሰው የዋስትና መብትን አስመልክቶ በተለያየ ጊዜ የወጡት ሕጎች ከላይ በዝርዝር የተገለጹት ሲሆኑ እነዚህ ሕጎች ሊያሳኩት የፈለጉት መሠረታዊ ዓላማ ከኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገመንግስት እና በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ-ሥርዓት ሕጉ ላይ ዋስትናን አስመልክቶ ከተደነገጉት ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው መርምረነዋል፡፡

በመሠረቱ የተያዙ ሰዎች በሕገ-መንግስቱ ጥበቃ ከተደረጉላቸው መብቶች አንዱ የዋስትና መብት ነው፡፡ የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግሥት በአንቀጽ 19/6 የተያዙ ሰዎች በዋስትና የመፈታት መብት ያላቸው መሆኑን በመርህ ደረጃ ያስቀመጠ ሲሆን ይህ በሕገ መንግሥቱ የተከበረው መሠረታዊ መብት ሊነፈግ፣ ሊገደብ ወይም በቂ የሆነ የዋስትና ማረጋገጫ እንዲቀርብ የሚደረገውም አግባብነት ባላቸው ሌሎች ዝርዝር ሕጎች መሠረት በልዩ ሁኔታ ስለመሆኑ ከድንጋጌው ይዘት መገንዘብ ይቻላል፡፡ በዘመናዊው የሕግ አስተሳሰብም በዋስ ለመለቀቅ ከሚያበቁ ምክንያቶች መካከል ጎልቶ የሚታየው ማንኛውም በወንጀል የተከሰሰ ሰው በፍ/ቤት የጥፋተኝነት ውሳኔ ሳይሰጥበት ሊቀጣ አይገባውም የሚለው ነው፡፡ በሕገ-መንግስቱ ልዩ ጥበቃ የተሰጠው ይህ መብት መሠረታዊ ዓላማውም ተከሳሹ በተከሰሰበት ወንጀል ጥፋተኝነቱ ሳይረጋገጥበት በእስር እንዳይቆይ ማድረግ ነው፡፡ በመሆኑም የዋስትና መብት መርሁ መፍቀድ ሲሆን ልዩ ሁኔታው ደግሞ መከልከል ነው፡፡

ይህን መሠረታዊ መብት አስመልክቶ የመወሰን ስልጣን እና ኃላፊነት የተሰጣቸው ፍ/ቤቶችም በወንጀል ጉዳይ ተጠርጥሮ ክስ የቀረበበት ሰው የሚያቀርበውን የዋስትና መብት ጥያቄ እና ከሣሽ የሆነው ዓቃቤሕግም በጉዳዩ ላይ የሚሰጠውን አስተያየት በሕገመንግስቱ ዋስትናን አስመልክቶ ከደነገገው መሠረታዊ ዓላማ እና በሌሎች ልዩ ሕጎች ከተደነገጉት ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በጥንቃቄ

መርምረው ውሳኔ መስጠት ይጠበቅባቸዋል። ይህንኑ ተግባራዊ ሲያደርጉም በመርህ ደረጃ የዋስትናን መብት መፍቀድ ያለባቸው ሲሆን በሕጉ ተለይተው በተቀመጡ ምክንያቶች ግን የዋስትናን መብት በልዩ ሁኔታ ሊነፍጉ ይችላሉ። እነዚህም ምክንያቶች መርማሪው ፖሊስ ምርመራውን ገና ያላጠናቀቀ ሲሆን በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 59፤ ተከሳሽ ፈጽሞታል የተባለው ወንጀል በዋስትና ለመለቀቅ የሚከለክል ሲሆን በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 63 የሕግ ክልከላን መሠረት በማድረግ እና በሌሎች ልዩ ሕጎች፤ ወይም ተከሳሹ ፈጽሞታል የተባለው ወንጀል በዋስ መለቀቅን የማይከለክል ቢሆንም ተጠርጣሪው ቢለቀቅ በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ 67 የተገለፁትን ተግባራት ይፈጽማል ተብሎ ሲታመን ነው። የዋስትና መብትን አስመልክቶ በሕገመንግስቱ እና በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ-ሥርዓት ሕጉ ላይ የተቀመጡት መሠረታዊ መርሆዎች በዝርዝር የተገለጹት ሲሆኑ በሙስና ወንጀል የተጠረጠረን ወይም የተከሰሰን ሰው አስመልክቶ በየጊዜው ተሻሽለው የወጡት ሕጎች ከዋስትና መብት መሠረታዊ መርሆዎች ጋር ተገናዝበው ሲታዩ ሊያሳኩ የፈለጉት መሠረታዊ ዓላማ ምንድነው የሚለውን ቀጥለን እንመልከት።

የጸረ ሙስና ልዩ የስነስርዓት እና የማስረጃ ሕግ አዋጅ ቁጥር 236/93 እንደተሻሻለ / አዋጅ ቁጥር 239/93 አንቀጽ 51/2 / በሙስና ወንጀል ተጠርጥሮ የተያዘ ሰው የዋስትና መብት አይኖረውም በማለት ግልጽ ክልከላ አድርጎ የነበረ አዋጅ ቢሆንም የዋስትና መብት በሕገመንግስቱ እና ኢትዮጵያ በተቀበለቻቸው ዓለምዓቀፍ ስምምነቶች ጥበቃ የተደረገለት መሠረታዊ መብት መሆኑ ታምኖበት በሂደት በወጣው የተሻሻለው የጸረ ሙስና ልዩ የስነስርዓት እና የማስረጃ ሕግ አዋጅ ቁጥር 434/97 አንቀጽ 4/1 በሙስና ወንጀል የተያዘ ሰው በዋስ እንዲለቀቅ ማመልከት ይችላል፤ ሆኖም የተከሰሰበት ወንጀል ከ10 ዓመት በላይ ሊያስቀጣ የሚችል ከሆነ በዋስትና መለቀቅ እንደማይችል በመግለጽ በሙስና ወንጀል የተከሰሰ ሰው በተከሰሰበት ሕግ ላይ ያለውን የቅጣት መጠን መሠረት በማድረግ የዋስትና መብትን በከፊል የፈቀደ መሆኑን ከድንጋጌው ይዘት መገንዘብ ይቻላል። የአዋጅ ቁጥር 434/97 አንቀጽ 4/1 ድንጋጌ ከፍተኛ ቅጣት ሊያስቀጣ በሚችል የሙስና ወንጀል የተከሰሰ ሰው በዋስ ከመልቀቅ ይልቅ በእስር ሆኖ ጉዳዩን እንዲከታተል ማድረግ፤ በሌላ በኩል ከ10 ዓመት በታች ሊያስቀጣ በሚችል የሙስና ወንጀል የተከሰሰ ሰው በእስር ከማቆየት ይልቅ በዋስ ሆኖ ጉዳዩን እንዲከታተል ማድረግ የዋስትና መብት ሕገመንግስታዊ ሽፋን የተሰጠው መሠረታዊ መብት መሆኑ ታምኖበት ሕግ አውጪው የዋስትና መብትን አስመልክቶ አስቀድሞ በነበረው አዋጅ ላይ አስቀምጦት የነበረውን ፍጹም ክልከላ በተወሰነ ደረጃ በመተው የዋስትና መብትን በተወሰኑ የሙስና ወንጀሎች ላይ የፈቀደ መሆኑን አመላካች ነው።

በተሻሻለው የጸረ ሙስና ልዩ የስነስርዓት እና የማስረጃ ሕግ ማሻሻያ አዋጅ ቁጥር 882/2007 አንቀጽ 3/1 በሙስና ወንጀል የተያዘ ሰው በዋስ እንዲለቀቅ ለፍ/ቤት ማመልከት ይችላል፤ ሆኖም የተከሰሰበት ወይም የተጠረጠረበት ወንጀል ከ10 ዓመት በላይ በሆነ ጽኑ እሥራት ሊያስቀጣ የሚችል ከሆነ በዋስትና መለቀቅ አይችልም። ከአራት ዓመት በላይ እና ከ10 ዓመት በታች የሚያስቀጡ ተደራራቢ ወንጀሎች ሲኖሩም እየተደመሩ ከ10 ዓመት በላይ የሚያስቀጣ ከሆነ ዋስትና ይከለከላል በማለት

ይደነግጋል፡፡ በድንጋጌው የመጀመሪያ ሐሳብ ላይ የተቀመጠው እና የተከሰሰበት ወይም የተጠረጠረበት ወንጀል ከ10 ዓመት በላይ በሆነ ጽኑ እሥራት ሊያስቀጣ የሚችል ከሆነ በዋስትና መለቀቅ አይችልም የሚለው ሐሳብ በአዋጅ ቁጥር 434/97 አንቀጽ 4/1 የተከሰሰበት ወንጀል ከ10 ዓመት በላይ ሊያስቀጣ የሚችል ከሆነ በዋስትና መለቀቅ አይችልም በማለት ከተገለጸው ሀሳብ ጋር ተመሳሳይ በመሆኑ በዚህ ረገድ የአዋጅ ቁጥር 882/2007 አንቀጽ 3/1 የመጀመሪያ ሀሳብ የተለየ ነገር የለውም፡፡ በአዋጅ ቁጥር 882/2007 አንቀጽ 3/1 ላይ የተቀመጠው ሁለተኛው ሀሳብ በዚህ መዝገብ ለተያዘው ጉዳይ አግባብነት ያለው የክርክሩ ጭብጥ በመሆኑ በድንጋጌው ላይ የተቀመጠው ሁለተኛ ሀሳብ መሠረታዊ ዓላማ ከድንጋጌው ይዘት፣ አግባብነት ካላቸው የሙስና ወንጀል ድንጋጌዎች እና ከመደበኛው የወንጀል ሕጉ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መመርመር አስፈላጊ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

ተጠሪ እንዲከላከሉ ብይን የተሰጠው በአዋጅ ቁጥር 881/2007 አንቀጽ 9/1/ሀ/ለ ሲሆን ይህ ደግሞ ከአንድ ዓመት በማያንስ ቀላል እሥራት እና ከሶስት ሺህ ብር በማይበልጥ መቀጮ ወይም ከአሥር ዓመት በማይበልጥ ጽኑ እሥራት እና ከአሥር ሺህ ብር በማይበልጥ መቀጮ የሚያስቀጣ ነው፡፡

በኢ.ፌ.ዲ.ሪ የወንጀል ሕግ የቀላል እሥራት እና የጽኑ እሥራት ቅጣት መጠን በሚገባ ተለይቶ ተቀምጧል፡፡ የወንጀል ሕጉ አንቀጽ 106/1 ቀላል እስራት ከ10 ቀን እስከ ሶስት ዓመት የሚያስቀጣ መሆኑን፣ የዚሁ ሕግ አንቀጽ 108/1 ድንጋጌ ደግሞ ጽኑ እሥራት ከአንድ ዓመት እስከ 25 ዓመት የሚደርስ እና በሕጉ ተገልጾ የተደነገገ ሲሆንም በዕድሜ ልክ የሚያስቀጣ እንደሆነ ይደነግጋል፡፡

የአዋጅ ቁጥር 882/2007 አንቀጽ 3/1 ድንጋጌ የመጀመሪያ ሀሳብ ላይ የተከሰሰበት ወይም የተጠረጠረበት ወንጀል ከ10 ዓመት በላይ በሆነ ጽኑ እሥራት ሊያስቀጣ የሚችል ከሆነ በዋስትና መለቀቅ አይችልም በማለት የተገለጸ በመሆኑ ይህ ሀሳብ የሚመለከተው በጽኑ እሥራት የሚያስቀጡ ወንጀሎችን ነው፡፡ በዚሁ ድንጋጌ ላይ የተቀመጠው ሁለተኛ ሀሳብ የድንጋጌው የመጀመሪያ ሀሳብ በአራት ነጥብ ከተቋጨ በኋላ ይህንኑ ሀሳብ ተከትሎ ከአራት ዓመት በላይ እና ከ10 ዓመት በታች የሚያስቀጡ ተደራራቢ ወንጀሎች ሲኖሩም እየተደመሩ ከ10 ዓመት በላይ የሚያስቀጣ ከሆነ ዋስትና ይከለከላል በማለት የተገለጸ በመሆኑ እና በልዩ ሁኔታ ከወንጀሉ ከባድነት የተነሳ በሕጉ ልዩ ክፍል ተደንግጎ ሲገኝ ወይም በቀላል እስራት የሚያስቀጡ ተደራራቢ ወንጀሎች ሲኖሩ ወይም ወንጀለኛው በተደጋጋሚ ሲቀጣ እስከ አምስት ዓመት ሊደርስ እንደሚችል እንደተጠበቀ ሆኖ ቀላል እሥራት የሚያስቀጣው ከ10 ቀን እስከ ሶስት ዓመት በመሆኑ በአዋጅ ቁጥር 882/2007 አንቀጽ 3/1 ሁለተኛ ሀሳብ ላይ ከአራት ዓመት በላይ እና ከ10 ዓመት በታች የሚያስቀጡ ተደራራቢ ወንጀሎች በማለት የተገለጸው ሀሳብ ከአራት ዓመት በላይ በጽኑ እሥራት ሊያስቀጡ የሚችሉ ወንጀሎችን የሚመለከት እንጂ የቅጣት መነሻቸው አራት ዓመት የሆነ በጽኑ እሥራት የሚያስቀጡ ወንጀሎችን የሚመለከት እንዳልሆነ ከድንጋጌው አቀራረጽ እና ይዘት መገንዘብ ይቻላል፡፡

በአዋጅ ቁጥር 882/2007 አንቀጽ 3/1 ከአራት ዓመት በላይ የሚያስቀጡ ተደራራቢ ወንጀሎች ተፈጽመው በተገኙ ጊዜ በሚል የተገለጸው ሁለተኛ ሀሳብ መነሻ ቅጣትን የሚመለከት አይደለም ካልን

በቀላል እሥራት የሚያስቀጡ ወንጀሎች የፈለገውን ያህል ተደራርበው ቢገኙ ሌላ ሕጋዊ ምክንያት እስካልቀረበ ጊዜ ድረስ ተደራራቢ ወንጀሎች ናቸው በሚል ምክንያት የተከሰሰውን የዋስትና መብት መከልከል የማይቻል መሆኑ፤ ሆኖም ከአራት ዓመት በላይ እና ከ10 ዓመት በታች በሆነ ጽኑ እሥራት የሚያስቀጡ ተደራራቢ ወንጀሎች ሲኖሩ እና እየተደመሩ ከ10 ዓመት በላይ የሚያስቀጣ ከሆነ ግን የተከሰሰውን ሰው የዋስትና መብት የሚከለከል መሆኑን የሚያሳይ ነው፡፡

ከላይ የተመለከተውን የሕጉን ትንታኔ መነሻ በማድረግ በሙስና ወንጀል ሕግ አዋጅ ቁጥር 881/2007 ላይ ከአራት ዓመት በላይ እና ከ10 ዓመት በታች የሚያስቀጡ ወንጀሎች መኖር አለመኖራቸውን በተመለከተ አዋጁን እንደተመለከትነው በአዋጁ አንቀጽ 13/4/ለ የተመለከተው ወንጀል ተፈጽሞ ሲገኝ እንደነገሩ ሁኔታ በቀላል እስራት እና በመቀጮ ወይም ከአምስት ዓመት በማይበልጥ ጽኑ እስራት፤ በአዋጁ አንቀጽ 13/7 የተመለከተው ወንጀል ተፈጽሞ ሲገኝ ከሶስት ዓመት እስከ 7 ዓመት እና ከብር 10,000 እስከ 50,000 መቀጮ፤ በአዋጁ አንቀጽ 17/2 የተመለከተው ወንጀል ተፈጽሞ ሲገኝ ከአንድ ዓመት በማያንስ ቀላል እስራት እና ከሶስት ሺህ ብር በማይበልጥ መቀጮ ወይም ከ7 ዓመት በማይበልጥ ጽኑ እስራት እና ከ 20,000 በማይበልጥ መቀጮ፤ በአዋጁ አንቀጽ 16/1 ላይ የተመለከተው ወንጀል ተፈጽሞ ሲገኝ ከአንድ ዓመት እስከ 10 ዓመት በሚደርስ ጽኑ እስራት እንደሚያስቀጣ ይደነግጋል፡፡ ከእነኚህ ድንጋጌዎች ይዘት መገንዘብ የሚቻለው ድንጋጌዎቹን በመተላለፍ የተከሰሰ ሰው ከአራት ዓመት በላይ እና ከ10 ዓመት በታች በሆነ ጽኑ እሥራት ሊቀጣ እንደሚችል አመላካች ድንጋጌዎች መሆናቸውን ነው፡፡

ይህንኑ መሠረት በማድረግ በእጃችን ያለውን ጉዳይ እንደመረመርነው አመልካች ለዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት ባቀረበው ክርክር መነሻቸው አራት ዓመት እና ከዚያ በላይ የሆኑ የሙስና ወንጀሎች የሉም በማለት የሚከራከር ቢሆንም ከላይ በዝርዝር በተገለጹት ድንጋጌዎች የተከሰሰ ሰው ከአራት አመት በላይ እና ከ10 ዓመት በታች በሆነ ጽኑ እሥራት ሊቀጣ እንደሚችል አመላካች ድንጋጌዎች በመሆናቸው እና በአዋጅ ቁጥር 882/2007 አንቀጽ 3/1 ሁለተኛ ሀሳብ ላይ ከአራት ዓመት በላይ እና ከ10 ዓመት በታች የሚያስቀጡ ተደራራቢ ወንጀሎች በማለት የተገለጸው ሀሳብ ከአራት ዓመት በላይ በጽኑ እሥራት ሊያስቀጡ የሚችሉ ወንጀሎችን የሚመለከት እንጂ መነሻ ቅጣትን የሚመለከት ባለመሆኑ አመልካቸ በዚህ ረገድ ያቀረበው መከራከሪያም ሆነ ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተው የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በድንጋጌው ከአራት ዓመት በላይ እና ከ10 ዓመት በታች የሚያስቀጡ ተደራራቢ ወንጀሎች በሚል የተገለጸው የሕጉ አገላለጽ መነሻ ቅጣቱ አራት ዓመት እና በላይ የሆነን ድንጋጌን የሚመለከት ነው በማለት የደረሰበት መደምደሚያ ተቀባይነት ያለው አይደለም፡፡

በሌላ በኩል አመልካች ለዚህ ችሎት ባቀረበው ክርክር የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ.መ.ቁ 63344 በሙስና ወንጀል የዋስትና ክርክር ጊዜ ክስ የቀረበበት ድንጋጌ ጣሪያ ቅጣት ሊታይ እንደሚገባ አስገዳጅ የሕግ ትርጉም የተሰጠበት በመሆኑ 4 ዓመት የተባለው የቅጣቱ ጣሪያ ሊወሰድ

ይገባል በማለት የሚከራከር ከመሆኑ አኳያ ተጠቃሹ የሰበር ሰሚ ችሎት ወሳኔ ከጉዳዩ ጋር ተያያዥ መሆን አለመሆኑን እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ.መ.ቁ 63344 ሐምሌ 28 ቀን 2003 ዓ.ም በሰጠው ውሳኔ ዋስትናን በሚመለከት የሰጠው አስገዳጅ የሕግ ትርጉም የወንጀል ሕግ አንቀጽ 676/1 በመተላለፍ ከባድ የእምነት ማጉደል የሙስና ወንጀል ፈጽሟል በማለት የተከሰሰን ሰው በሚመለከት የተሰጠ ውሳኔ ሲሆን ድንጋጌው የሚመለከተው ተፈጸመ የተባለውን የወንጀል ድርጊት እና ቅጣቱን የሚመለከት እንጂ አማራጭ ቅጣት አልተቀመጠበትም፤ በድንጋጌው ጥፋተኛ የተባለም ሰው ከአምስት ዓመት እስከ 25 ዓመት በሚደርስ ጽኑ እሥራት እና ከብር 100,000 በማይበልጥ መቀጮ የሚያስቀጣ መሆኑን ይገልጻል፤ ይህንኑ ድንጋጌ እና የአዋጅ 434/97 አንቀጽ 4 ድንጋጌን መሠረት በማድረግ በመዝገቡ የተሰጠው አስገዳጅ የሕግ ትርጉምም ተከሳሹ የተከሰሰበትን ዝቅተኛ የቅጣት መነሻ መውሰድ የአዋጅ ቁጥር 434/97 አንቀጽ 4 ድንጋጌን ውጤታማ በሆነ ሁኔታ ተፈጻሚ የማያደርግ እና ሕግ አውጭው የፀረሙስና ልዩ የሥነ ሥርዓትና የማስረጃ ሕግን በማውጣት ለማሳካት የሚፈልገውን ግብ የማያሳካ ነው የሚል ነው፡፡ ይህ አስገዳጅ ትርጉም አንድ ቅጣት ብቻ ተለይቶ የተቀመጠበትን የወንጀል ሕግ አንቀጽ 676/1 በሚመለከት የተሰጠ አስገዳጅ የሕግ ትርጉም እንጂ ተከሳሹ የተከሰሰበት የሕግ አንቀጽ አማራጭ ቅጣትን ያስቀመጠ በሆነ ጊዜ ለዋስትና ጉዳይ ሲባል ፍ/ቤቱ የትኛውን የቅጣት አማራጭ መውሰድ እንዳለበት በመግለጽ የሰጠው የሕግ ትርጉም የለም፡፡ በመሆኑም አመልካች በዚህ ውሳኔ ላይ የተሰጠው የሕግ ትርጉም ለጉዳዩ አግባብነት አለው በማለት ያቀረበው ክርክር ተቀባይነት ያለው አይደለም፡፡ በሰ.መ.ቁ 124750 የተሰጠው ውሳኔም አስቀድሞ በሰ.መ.ቁ 63344 የተሰጠውን ውሳኔ መሠረት በማድረግ የተሰጠ ውሳኔ በመሆኑ፤ አዋጅ ቁጥር 882/2007 አንቀጽ 58 አዋጁ በስራ ላይ ከመፈጸሙ በፊት የተፈጸሙ ወንጀሎች በነባሩ የስነምግባር እና የጸረ ሙስና ልዩ የስነስርዓት እና የማስረጃ ሕግ አዋጅ ቁጥር 434/97 መሠረት ፍጻሜ ያገኛሉ የሚል በመሆኑ እና አመልካች ፈጸሙት የተባለው የሙስና ወንጀል አዋጅ ቁጥር 882/2007 ከወጣ በኋላ በመሆኑ ተጠቃሾች የሰበር ሰሚ ችሎት ውሳኔዎች ለጉዳዩ አግባብነት ያላቸው አይደሉም፡፡

ተጠሪ እንዲከላከሉ ብይን የተሰጠበት የአዋጅ ቁጥር 881/2007 አንቀፅ 9/1/ሀ/ለ/1/ እንደነገሩ ሁኔታ ከአንድ ዓመት በማያንስ ቀላል እስራት እና ከሶስት ሺህ ብር በማይበልጥ መቀጮ ወይም ከ10 ዓመት በማይበልጥ ጽኑ እሥራት እና ከአሥር ሺህ ብር በማይበልጥ መቀጮ ያስቀጣል በሚል አማራጭ ቅጣትን ያስቀመጠ በመሆኑ፤ የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰመ.ቁ 63344 ም ሆነ በሰ.መ.ቁ 124750 በሰጠው ውሳኔ ተከሳሽ የተከሰሰበት የሕግ አንቀጽ አማራጭ ቅጣትን ባስቀመጠ ጊዜ ለዋስትና ጉዳይ ሲባል ሊያዝ የሚገባው ቅጣት የትኛው እንደሆነ ገዢ ትርጉም ያልሰጠበት በመሆኑ ለዋስትና ጉዳይ ሲባል ሊወሰድ የሚገባው የቅጣት አማራጭ የትኛው ነው የሚለው በጥንቃቄ ሊታይ ይገባዋል፡፡

ተጠሪ እንዲከላከሉ ብይን የተሰጠው በአዋጅ ቁጥር 881/2007 አንቀጽ 9/1/ሀ/ለ ሲሆን ይህ ደግሞ ከአንድ ዓመት በማያንስ ቀላል እሥራት እና ከሶስት ሺህ ብር በማይበልጥ መቀጮ ወይም ከአሥር ዓመት በማይበልጥ ጽኑ እሥራት እና ከአሥር ሺህ ብር በማይበልጥ መቀጮ የሚያስቀጣ ነው፡፡ ከላይ በዝርዝር ካስቀመጥናቸው የሕጉ ትንታኔዎች አኳያ ፍ/ቤቱ ቀላል የእስራት ቅጣት አማራጩን የሚወስድ ከሆነ የተጠሪ የዋስትና መብት የሚፈቀድ ሲሆን ፍ/ቤቱ የጽኑ እሥራት አማራጭን የሚወስድ ከሆነ ደግሞ የተጠሪ የዋስትና መብት የሚከለከል ይሆናል፡፡ በመሆኑም ፍ/ቤቱ ለዋስትና ጉዳይ ሲባል በድንጋጌው ከተቀመጡት ሁለት የቅጣት አማራጮች ውስጥ የትኛውን አማራጭ ተግባራዊ ማድረግ እንዳለበት ተከሳሹ ፈጽሞታል ከተባለው ድርጊት፤ ከሙስና ወንጀል አዋጆች ልዩ ባሕርይ እና ከዋስትና መብት መሠረታዊ ዓላማ ጋር በማገናዘብ መለየት ይኖርበታል፡፡

በያዝነው ጉዳይ የሥር ከፍተኛው ፍ/ቤት ተጠሪ አስቀድሞ ክስ የቀረበባቸውን የአዋጁን አንቀፅ 9/1/ሀ/ለ/2/ ድንጋጌን በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 113 በመለወጥ በአንቀፅ 9/1/ሀ/ለ እንዲከላከሉ ብይን ሲሰጥ እንደምክንያት ያስቀመጠው በተጠሪ አድራጎት ደረሰ የተባለው የጉዳት መጠን ተጠሪ በተከሰሱበት የሕግ አንቀጽ የተቀመጠ አይደለም በሚል ነው፡፡ ተጠሪ ፈጽመውታል በተባለው የወንጀል ድርጊት ምክንያት ደረሰ የተባለው የጉዳት መጠን በዓቃቤሕግ ክስ ላይ የተገለጸው አይደለም የሚባል ከሆነ ተጠሪ ይከላከሉ ከተባለበት የአዋጅ ቁጥር 882/2007 አንቀጽ 9/1/ሀ/ለ ላይ ከተቀመጡት የቀላል እሥራት እና የጽኑ እሥራት የቅጣት አማራጮች ውስጥ የዋስትና መብት ሕገመንግስታዊ ሽፋን የተሰጠው መሠረታዊ መብት ከመሆኑ አኳያ ለዋስትናው ጉዳይ ሲባል የቀላል እሥራት አማራጭን መውሰድ ተመራጭ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ ተጠሪ ይከላከሉ ከተባለበት የአዋጅ ቁጥር 882/2007 አንቀጽ 9/1/ሀ/ለ ላይ ከተቀመጡት የቀላል እሥራት እና የጽኑ እሥራት የቅጣት አማራጮች ውስጥ ለዋስትናው ጉዳይ ሲባል የቀላል እሥራት አማራጭ የተወሰደ በመሆኑ እና በአዋጅ ቁጥር 882/2007 አንቀጽ 3/1 በቀላል እሥራት የሚያስቀጡ ወንጀሎች የፈለገውን ያህል ተደራርበው ቢገኙ ዋስትናን ለማስከልከል የሚያስችል ሌላ ሕጋዊ ምክንያት እስካልቀረበ ጊዜ ድረስ ተደራራቢ ወንጀሎች ናቸው በሚል ምክንያት የተከሰሰውን ሰው የዋስትና መብት መከልከል አይቻልም፡፡

በሌላ በኩል አመልካች ለዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት ባቀረበው ክርክር ተጠሪ እንዲከላከሉ ብይን የተሰጠው እስከ 10 ዓመት በሚደርስ ፅኑ እስራት ሊያስቀጡ በሚችሉ ሁለት ወንጀሎች በመሆኑ ተደራራቢ ክሱ ከሚያስከትለው ቅጣት አንፃር የዋስትና ጥያቄው በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 67/ሀ መሠረት ሊታይ ሲገባው መታለፉ አግባብ አይደለም በማለት የሚከራከር ከመሆኑ አኳያ የስር ይግባኝ ሰሚው የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ከወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 67 መሠረት የዋስትና መብቱን የሚያስከለክል መከራከሪያ ባልቀረበበት ሁኔታ የተጠሪን የዋስትና መብት መከልከል አግባብ አይደለም በማለት የሰጠው ውሳኔ አግባብ መሆን አለመሆኑን ቀጥለን እንመልከት፡፡

ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የዳኝነት ስልጣኑ የተመለከተው የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ተጠሪ የተከሰሱበትን የሕግ አንቀጽ በብይን ሲቀይር ተጠሪ በጠበቃቸው አማካኝነት የዋስትና መብት

እንዲፈቀድላቸው ጠይቀዋል፡፡ ከሳሽ የሆነው ዓቃቤሕግ በዋስትና ጥያቄው ላይ በሰጠው አስተያየት ተጠሪ እንዲከላከሉ ብይን የተሰጠው በሁለት ክሶች በመሆኑ እና የዋስትና መብት ቢጠበቅላቸው ቅጣቱን በመሸሽ የዋስትና ግዴታቸውን አክብረው ስለማይቀርቡ የዋስትና ጥያቄው ተቀባይነት ሊያገኝ አይገባም በማለት የተቃወመ ስለመሆኑ የከፍተኛው ፍ/ቤት የሰጠው ብይን በግልጽ የሚያሳይ በመሆኑ አመልካች የተጠሪ የዋስትና መብት በሕግ ባይከለከልም ዋስትናን ሊያስከለክሉ በሚችሉ ሁኔታዎች ሊነፈግ ይገባል በማለት የተከራከረ መሆኑን መገንዘብ ይቻላል፡፡ የስር ከፍተኛው ፍ/ቤት የተጠሪን የዋስትና ጥያቄ ውድቅ ያደረገው በአዋጅ ቁጥር 434/97 አንቀጽ 4 መሠረት በመሆኑ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 67 በተገለጸው አግባብ የተጠሪን የዋስትና መብት ለማስከልከል የሚያስችሉ ሁኔታዎች መኖር አለመኖራቸውን መመርመር አላስፈለገውም ነበር፡፡ ተጠሪ የስር ከፍተኛው ፍ/ቤት የዋስትና መብታቸውን በመከልከል በሰጠው ብይን ቅር በመሰኘት ለፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የይግባኝ አቤቱታ አቅርበው በተደረገው የቃል ክርክር አመልካች ባቀረበው ክርክር ተጠሪ ጥፋተኛ ሆነው ቢገኙ ሊወሰድ የሚችለው ቅጣት ከባድ ሊሆን እንደሚችል ግምት ከተወሰደ የክሶችን ብዛት እና ከባድነት መነሻ በማድረግ የዋስትና መብት ሊከለከሉ ይገባል በማለት የተከራከረ ስለመሆኑ የስር ይግባኝ ሰሚው ጠቅላይ ፍ/ቤት መዝገብ አስቀርበን ተመልክተናል፡፡ በመሆኑም የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 67 መሠረት ዋስትናን ለማስከልከል የሚያስችል መከራከሪያ አልቀረበም ማለቱ አመልካች በስር ከፍተኛው ፍ/ቤትም ሆነ በይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ዋስትናን በሚመለከት ያቀረበውን ክርክር ያላገናዘበ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ ስለሆነም አመልካች በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 67 መሠረት የተጠሪ የዋስትና መብት ሊከለከል ይገባል የሚል ክርክር ያቀረበ በመሆኑ የተጠሪ የዋስትና መብት በሁኔታ ሊከለከል ይገባል? ወይስ አይገባም? የሚለውን እንደሚከተለው መርምረነዋል፡፡

የወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁጥር 67 ድንጋጌ ተከሳሹ በዋስትና ወረቀት የተመለከቱትን ግዴታዎች የማይፈጽም የማይመስል እንደሆነ የዋስትና ጥያቄው ውድቅ ሊደረግ እንደሚችል ይደነግጋል፡፡ ሆኖም ይህ ድንጋጌ ፍ/ቤቱ ግምቱን መነሻ የሚያደርግባቸው ሁኔታዎች ምን እንደሆኑ በግልጽ አላመላከተም፡፡ በመሆኑም አንድ ተከሣሽ የዋስትና መብት ቢከበርለት ግዴታውን የሚፈጽም እንደማይመስል ግምት የሚወሰደው በቂ እና ሕጋዊ ሊባል በሚችል ምክንያት ሊሆን ይገባል፡፡ እነዚህም ምክንያቶች ከተለያዩ ከባቢያዊ ሁኔታዎችና ከጉዳዩ ልዩ ባሕርይ አንፃር ፍርድ ቤቱ ሊገነዘበው የሚችለው ነጥብ ነው ተብሎ የሚታሰብ ነው፡፡

በያዝነው ጉዳይ የስር ከፍተኛው ፍ/ቤት ተጠሪ አስቀድሞ ክስ የቀረበባቸውን የአዋጁን አንቀፅ 9/1/ሀ/ለ/2/ ድንጋጌን በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 113 በመለወጥ በአንቀፅ 9/1/ሀ/ለ በሁለት ክሶች እንዲከላከሉ ብይን ሲሰጥ እንደምክንያት ያስቀመጠው በተጠሪ አድራጎት ደረሰ የተባለው የጉዳት መጠን ተጠሪ በተከሰሱበት የሕግ አንቀጽ የተቀመጠ አይደለም በሚል ነው፡፡ በተጠሪ የወንጀል ድርጊት ምክንያት ደረሰ የተባለው የጉዳት መጠን በዓቃቤሕግ ክስ ላይ የተገለጸው አይደለም የሚባል ከሆነ ተጠሪ በዋስትና

ቢለቀቁ ዋስትናውን አክብረው ሊቀርቡ አይችሉም የሚል ግምት የሚያሲዝ ሆኖ አላገኘነውም፡፡ በመሆኑም ተጠሪ የዋስትና መብታቸው በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 67 መሠረት ሊከለከል አይገባም፡፡ ሲጠቃለል የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ፍ/ቤት የተጠሪን የዋስትና መብት በመፍቀድ የሰጠው ውሳኔ ተገቢ ነው በማለት በውጤት ደረጃ ተቀብለነዋል፡፡ ስለሆነም ተከታዩን ውሳኔ በአብላጫ ድምጽ ሰጥተናል፡፡

## ውሳኔ

1. የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 180500 ሐምሌ 30 ቀን 2011 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ ከላይ በፍርድ ሐተታው ላይ በተገለጸው ምክንያት በውጤት ደረጃ ጸንቷል፡፡
2. በዚህ መዝገብ ከተሰየምን ዳኞች ውስጥ ሶስት ዳኞች የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት የተጠሪ የዋስትና መብት በአዋጅ ቁጥር 882/2007 አንቀጽ 3/1 መሠረት ሊከለከል አይገባም በማለት የሰጠው ውሳኔ ተገቢ ነው ከሚል መደምደሚያ ላይ የደረስን በመሆኑ፤ ከችሎቱ ዳኞች ውስጥ አራት ዳኞች አመልካች በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 67 መሠረት የተጠሪ የዋስትና መብት በሁኔታ ሊከለከል ይገባል በማለት መከራከሪያ ያቀረበ ቢሆንም የተጠሪ የዋስትና መብት በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 67 መሠረት ሊከለከል አይገባም ከሚል መደምደሚያ ላይ የደረስን በመሆኑ ተጠሪ በሌላ ወንጀል የሚፈለጉ ካልሆነ በቀር በዋስ ሆነው ጉዳያቸውን ሊከታተሉ ይገባል በማለት ወስነናል፡፡

## ትዕዛዝ

የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 180500 ሐምሌ 30 ቀን 2011 ዓ.ም ተጠሪ እንዲያስይዙ ካዘዘው የዋስትና መጠን በተጨማሪ ተጠሪ ከሐገር እንዳይወጡ ታዟል፡፡ ይጻፍ፤ ትዕዛዙ ለሚመለከታቸው አካላት ይድረሳቸው፡፡

- መዝገቡ ውሳኔ ስላገኘ ተዘግቷል፡፡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የሁለት ዳኛ ፊርማ አለበት፡፡

ሠ/ኃ

## የሀሳብ ልዩነት

እኔ ስሜ በተራ ቁጥር 3 ሥር የተሰየምኩት የችሎቱ ዳኛ ከሌሎቹ የችሎቱ ዳኞች በሃሣብ የሚለየኝ በፍሬ ጉዳዩ በአመልካች ተከላከል የተባሉበት የህግ ድንጋጌዎች ዋስትና መብትን የሚያስነፍግ አይደለም በሚል በአብላጫው ድምጽ የተሰጠውን የውሣኔ ክፍል የምደግፍ በመሆኑ በዚህ ላይ ልዩነት የለኝም፡፡

ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ ያየው ፍ/ቤት በእርግጥ በሕግ ጉዳይ ዋስትና የሚያስነፍግ አይደለም በማለት ውሣኔ መስጠቱ እንደተጠበቀ ሆኖ ሕግ ዋስትና በሚያስፈቅድ ጉዳይ ዋስትና መፍቀድ የሚችል ቢሆንም

ዋስትና ሊፈቀድ አይገባም በማለት የወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ 67 ተጠቅሶ ክርክር ካለ ይህንንም መመልከት ይጠበቅበታል፡፡

ነገር ግን የወ/መ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ 67 በሥር ፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ተነስቶ የነበረ እና ፍ/ቤቱ በዚህ ላይ ግራ ቀኙን ሳያከራክር እና ዓቃቤ ሕግ አለኝ የሚለውን የሕግ ግምት የሚያስጥሉ ማስረጃዎችን እንዲያቀርብ፤ተከሣሽም በዐቃቤሕግ የተነሳበትን የሕግ ግምትን እና የቀረበበትን ማስረጃ የሚያስተባብሉ መከላከያ እንዲያቀርብ ሳይደረግ ሕጉ ዋስትና መብትን አያስከለክልም በሚል ዋስትና መፈቀዱ ተገቢ ሆኖ ስላላገኘሁት፤እንዲሁም የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሥር ፍ/ቤት ውሣኔን በመሻር ዋስትና ሊፈቀድ አይገባም ብሎ ሲወስን በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ 67 የተነሳውን መከራከሪያ በሥር ፍ/ቤት የተነሳ በመሆኑ የሥር ፍ/ቤት አከራክሮ ውሣኔ ያላሳረፈበት መሆኑን ከጉዳዩ ከተረዳ ወደ ሥር ፍ/ቤት ተመልሶ በዚህ ድንጋጌ መሠረት ክርክር ተደርጎበት ውሣኔ እንዲሰጥ መመለስ ሲገባው በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ 67 መሠረት የቀረበ ጥያቄ የለም በማለት ወደ ፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ጉዳዩ በተጠቀሰው ድንጋጌ መሠረት ተገቢ ክርክር ተደርጎበት ከቀረበው ክርክር እና ማስረጃ አንፃር ተጣርቶ ዋስትና የመፍቀድ ወይም የመከልከል ውሣኔ ሊሰጥ የሚገባው የነበረ ሆኖ ይህ ሳያደረግ የሥር ፍ/ቤትን ውሣኔ በማጽናት መወሰኑ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመ ሆኖ ስላገኘሁት ከወዲሁ በሥር ፍ/ቤት የወ/መ/ሥ/ሥ/ቁ.67 ላይ የተሰጠ ውሣኔ ሳይኖር በዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት ጉዳዩ ባለበት ደረጃ የወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ 67 ድንጋጌን በማንሳት ዋስትና ሊፈቀድ ይገባል በሚል በአብላጫው ድምጽ ሲወሰን አይገባም ነበር በማለት ከባልደረቦቼ በሃሣብ ተለይቻለሁ፡፡

የማይነበብ የአንድ ዳኛ ፊርማ አለበት

ሠ/ኃ

## የልዩነት ሀሳብ

- ስማችን በሁለተኛ እና በአራተኛ መስመር ላይ የተጠቀሰው ዳኞች ከወንጀል ህግ ሥነ-ሥርዓት ቁጥር 67 አንፃር በተሰጠው የውሳኔ ክፍል የምንስማማ ሲሆን አብላጫው ድምፅ የአዋጅ ቁጥር 882/2007 አንቀፅ 3(1) ድንጋጌ አተረጓጎምን አስመልክቶ በጠቀሰው ምክንያት እና በደረሰበት ድምዳሜ ያልተስማማን በመሆኑ የልዩነት ሀሳባችንን በሚከተለው መልኩ አስፍረናል፡፡
- በመሰረቱ በአብላጫ ድምፅም እንደተገለፀው በዋስ የመለቀቅ መብት ህገ መንግስታዊ መርህ ሲሆን በህግ በተደነገጉ ልዩ ሁኔታዎች ፍርድ ቤት ዋስትና ላለመቀበል የሚችል ለመሆኑ የኢ.ፌ.ዴ.ሪ. ህገ መንግስት አንቀፅ 19(6) ድንጋጌ ያስገነዝባል፡፡ የዋስትና መብትን

በተመለከተ በህግ በልዩ ሁኔታ ገደብ ከተጣለባቸው ሁኔታዎች ውስጥ አንዱ ከሙስና ወንጀል ጋር በተያያዘ የተጠረጠሩ ወይም የተከሰሱ ሰዎችን የሚመለከት ነው፡፡ ከሙስና ወንጀል ጋር በተያያዘ የተሻሻለው የፀረ ሙስና ልዩ የስነ ስርዓትና የማስረጃ ህግ አዋጅ ቁጥር 434/1997 አንቀፅ 4(1) ከአስር ዓመት በላይ ሊያስቀጣ በሚችል የሙስና ወንጀል የተከሰሰ ሰው በዋስትና ሊለቀቅ እንደማይችል ይደነግጋል፡፡

- ይህንኑ አዋጅ ለማሻሻል የወጣው የተሻሻለው ልዩ የፀረ ሙስና የሥነ ሥርዓትና የማስረጃ ህግ /ማሻሻያ/ አዋጅ ቁጥር 882/2007 በአንቀፅ 3(1) ስር ከአስር ዓመት በላይ በሆነ ፅኑ እስራት በሚያስቀጡ ወንጀሎች የተከሰሰን ሰው ጉዳይ በተመለከተ ከላይ የሰፈረውን ድንጋጌ ቃል በቃል ከደገመ በኋላ ቀጥሎ ባለው ዓረፍተ ነገር ከአስር ዓመት በታች በሆነ እስራት የሚያስቀጡ ወንጀሎችን አስመልክቶ አዲስ ሀሳብ አስፍሯል፡፡ ይህም ከአራት ዓመት በላይ እና ከአስር ዓመት በታች የሚያስቀጡ ተደራራቢ ወንጀሎች ሲኖሩ እየተደመሩ ከአስር ዓመት በላይ የሚያስቀጣ ከሆነ ዋስትና ይከለከላል የሚል ነው፡፡
- ግራ ቀኙን ለዚህ ሰበር ችሎት ክርክር ያበቃውም ይኸው በማሻሻያ አዋጁ ውስጥ የተጨመረው አዲስ ሀሳብ አተረጓጎምን የሚመለከት እንጂ ክስ በቀረበበት ወይም ተከላከል በተባለበት አንቀፅ ስር አማራጭ ቅጣት በተቀመጠ ጊዜ ለዋስትና ሲባል የትኛው ቅጣት መታየት አለበት የሚል ባለመሆኑ ለቀረበው ጉዳይ እንደ ዋና ጭብጥ ተደርጎ በአብላጫው ድምፅ መያዙ አግባብ አይመስለንም፡፡ ያም ሆኖ ከሙስና ወንጀል ጋር በተያያዘ ተከሳሹ ለሚያቀርበው የዋስትና ጥያቄ ፍርድ ቤቶች ተከሳሹ በቀረበበት የሙስና ወንጀል ክስ ጥፋተኛ ሆኖ ቢገኝ ሊጣልበት የሚችለውን የቅጣት ጣሪያ መነሻ በማድረግ ውሳኔ ሊሰጡ እንደሚገባ ይኸው ችሎት በሰ/መ/ቁ/63344 ላይ አስገዳጅ የህግ ትርጉም የሰጠ በመሆኑ ዝቅተኛው ቅጣት የሚያዝበት አግባብ የለም፡፡ በእርግጥ አብላጫው ድምፅ ይህ የሰበር ችሎቱ ትርጉም አሁን ለቀረበው ጉዳይ ተፈፃሚነት የለውም ብሏል፡፡ ሆኖም ትርጉሙ የተሰጠው የሙስና ወንጀልን ልዩ ባህሪ መሰረት በማድረግ ከዋስትና ጋር በተያያዘ መነሻ ሊደረግ የሚገባን ነጥብ ያመለከተ እንጂ የቅጣት ዓይነትን ለይቶ የተሰጠ ባለመሆኑ አሁን ለቀረበው ጉዳት ተፈፃሚነት የለውም ሊባል አይገባም፡፡ እናም እነዚህ ነጥቦች ታሳቢ ተደርገው የቀረበውን ጉዳይ በሚከተለው መልኩ ተመልክተናል፡፡
- በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አተረጓጎም መሰረት በድንጋጌው ውስጥ የተጠቀሰው አራት ዓመት መነሻ ቅጣታቸው አራት ዓመት እና በላይ የሆኑ ወንጀሎችን የሚመለከት ነው የሚል ሲሆን በተጠሪ ጠበቃ በኩል ተመሳሳይ አረዳድ መኖሩን ከቀረበው ክርክር መረዳት ይቻላል፡፡ አመልካች በበኩሉ ከአራት ዓመት በላይ ተብሎ የተጠቀሰው መነሻ ቅጣትን ሳይሆን የእያንዳንዱን ተደራራቢ ወንጀሎችን ጣሪያ ቅጣት የሚመለከት ነው የሚል ነው፡፡

- የድንጋጌውን አተረጓጎም ልዩነት በአግባቡ ለመፍታት ይረዳ ዘንድ ጉዳዩን ከሶስት አበይት ነጥቦች አኳያ ማየቱ ተገቢ ይሆናል፡፡ የመጀመሪያው ከሙስና ወንጀል ጋር በተያያዘ የዋስትና መብትን የሚመለከቱ ድንጋጌዎች እድገታዊ አመጣጥን የሚመለከት ነው፡፡ በኢ.ፌ.ዴ.ሪ. መንግስት የሙስና ወንጀልን በተመለከተ ልዩ የሥነ ሥርዓትና የማስረጃ ህግ መጀመሪያ የታወጀው በአዋጅ ቁጥር 236/1993 ነው፡፡ ይህ አዋጅ በታወጀ በ20 ቀኑ በአዋጅ ቁጥር 239/1993 የተሻሻለ ሲሆን ማሻሻያ አዋጁ በአንቀፅ 2 ስር በሙስና ወንጀል ተጠርጥሮ የተያዘ ሰው የዋስትና መብት የሌለው መሆኑን ደንግጓል፡፡ ይህንኑ አዋጅ ለማሻሻል የወጣው አዋጅ ቁጥር 434/1997 ደግሞ ከሙስና ወንጀል ጋር በተያያዘ የዋስትና መብት የከለከለው ከአስር ዓመት በላይ በሆነ እስር ሊያስቀጣ በሚችል የሙስና ወንጀል የተጠረጠረ ወይም የተከሰሰን ሰው መሆኑን በአንቀፅ 4 ስር ደንግጓል፡፡ በመጨረሻም ይህንን አዋጅ ለማሻሻል የወጣው አዋጅ ቁጥር 882/2007 ደግሞ ከአስር ዓመት በታች በሆነ እስራት የሚያስቀጡ ሆነው ነገር ግን ከአራት ዓመት በላይ እና ከአስር ዓመት በታች በሆነ እስራት በሚያስቀጡ ተደራራቢ ወንጀሎች የተከሰሰ ሰው የተደራራቢ ወንጀሎቹ ድምር ቅጣት ከአስር ዓመት በላይ የሚያስቀጣ በሆነ ጊዜ ዋስትና የሚከለከል መሆኑን ደንግጓል፡፡
- የድንጋጌዎቹ የእድገት አመጣጥ የሚያሳየው መጀመሪያ በሙስና ወንጀል የተጠረጠረ ወይም የተከሰሰ ሰው ሙሉ በሙሉ ዋስትና ተከለከለ፤ ቀጥሎ ከአስር ዓመት በላይ በሆነ እስራት ሊያስቀጣ በሚችል ወንጀል የተጠረጠረ ወይም የተከሰሰ ሰው ብቻ ተከለከለ፤ በመጨረሻም ከአስር ዓመት በታች በሆነ እስራት የሚያስቀጡ ተደራራቢ ወንጀሎች የተከሰሰ እና የተደራራቢ ወንጀሎቹ ድምር ቅጣት ከአስር ዓመት በላይ የሆነ ተከሳሽ ብቻ እንዲከለከል መደረጉን ያስገነዝባል፡፡ ከዚህ የእድገቱ አመጣጥ አንፃር አዋጅ ቁጥር 882/2007 በተሻሻለው አዋጅ ቁጥር 434/1997 ከአስር ዓመት በታች በሆነ እስራት የሚያስቀጡን ወንጀሎችን በተመለከተ በተቃራኒ ንባብ እውቅና ተሰጥቶት የነበረውን የዋስትና መብትን በልዩ ሁኔታ የሚገድብ እንጂ አብላጫው ድምፅ በገለፀው አኳኋን የዋስትና መብትን በተሻለ የሚያሰፋ ድንጋጌ አይደለም፡፡ ከልዩ ህጎች የሚጠበቀው ዋስትና መፍቀጃ ምክንያቶችን መዘርዘር ሳይሆን በህገ መንግስቱ የተረጋገጠው መብት ሊገደብ የሚችልበትን ልዩ ሁኔታን ብቻ ለይቶ ማስቀመጥ ነው፡፡ ከተጠቀሱ አዋጆች የእድገት ሂደትም መገንዘብ የሚቻለው ከጊዜ ወደ ጊዜ ዋስትና የሚያስከለክሉ ልዩ ሁኔታዎች ብቻ እየተለዩ መምጣቸውን ነው፡፡
- አዋጅ ቁጥር 434/1997 ከአስር ዓመት በላይ በሆነ እስራት ሊያስቀጣ በሚችል የሙስና ወንጀል የተከሰሰ ሰው በዋስትና ሊለቀቅ እንደማይችል ከመደንገጉ ውጭ ከአስር ዓመት በታች በሆነ እስራት በሚያስቀጣ ወንጀል ስለ ተከሰሰ ሰው ያለው ነገር የለም፡፡ እናም ከፍርድ በፊት ያለመታሰር መብት ህገ መንግስታዊ መርህ በመሆኑ የድንጋጌውን ተቃራኒ ንባብ በመውሰድ ከአስር ዓመት በታች በሆነ እስራት በሚያስቀጣ ወንጀል የተጠረጠረ

ወይም የተከሰሰ ሰው በመደበኛው የወንጀል ህግ ሥነ-ሥርዓት ሊቀርቡ የሚችሉ የዋስትና መቃወሚያዎች እንደተጠበቁ ሆነው ያለ አንዳች ቅድመ ሁኔታ በዋስትና የመለቀቅ መብት ይኖረዋል ማለት ይቻላል፡፡

- ሆኖም ከአስር ዓመት በታች በሆነ እስራት የሚያስቀጡም ሆነው በርካታ ተደራራቢ ወንጀሎች ሊፈፀሙ የሚችሉበት እድል መኖሩ በመዘንጋቱ በአዋጁ ሽፋን አልተሰጠውም፡፡ እናም ከድንጋጌው ይዘት መረዳት የሚቻለው ከዋስትና አንፃር የአዋጅ ቁጥር 882/2007 ዋነኛ ትኩረት ይህንኑ ከአስር ዓመት በታች በሆነ እስራት በሚያስቀጡ ተደራራቢ ወንጀሎች የተከሰሱ ሰዎችን ጉዳይ መልክ ማስያዝ ነው ብሎ መውሰድ ይቻላል፡፡
- የድንጋጌዎቹ የእድገት አመጣጥ ይህን የሚመስል ከሆነ ቀጥሎ ሊታይ የሚገባው ሁለተኛው አበይት ነጥብ የድንጋጌው የቃላት አጠቃቀም ዘዬ ነው፡፡ ከላይ እንደተመለከተው የድንጋጌው ዋና ዓላማ ከአስር ዓመት በታች በሆነ እስራት ሊያስቀጡ በሚችሉ ተደራራቢ ወንጀሎች የተከሰሱ ሰዎችን የዋስትና ሁኔታ መምራት ነው፡፡ ይህ ከሆነ በድንጋጌው ውስጥ "ከአራት ዓመት በላይ እና ከአስር ዓመት በታች የሚያስቀጡ ተደራራቢ ወንጀሎች" የሚለው አገላለፅ ለምን አስፈለገ የሚለው በአግባቡ ሊጤን የሚገባው ነጥብ ይሆናል፡፡ ከድንጋጌው የቃላት አጠቃቀም በጥቅሉ መገንዘብ የሚቻለው የህግ አውጭው ዓላማ ከአስር ዓመት በታች በሆነ እስራት በሚያስቀጡ ተደራራቢ ወንጀሎች የተከሰሱትን ሁሉንም ተከሳሾች ዋስትና መከልከል አለመሆኑን ነው፡፡ ይልቁንም ዋስትና መከልከል የተፈለገው እያንዳንዱ ተደራራቢ ወንጀል ከአራት ዓመት በላይ እና ከአስር ዓመት በታች በሆነ እስራት የሚያስቀጣ ሆኖ የተደራራቢ ወንጀሎቹ ድምር ቅጣት ከአስር ዓመት በላይ በሆነ ወንጀል የተከሰሱትን ሰዎችን ብቻ ነው፡፡
- የድንጋጌው መልዕክት ይህ ከሆነ ከአራት ዓመት በላይ የተባለው የሚያመለክተው የተደራቢ ወንጀሉን መነሻ ቅጣት ነው ወይስ ጣሪያ ቅጣት የሚለው ቀጥሎ የሚታይ ሶስተኛው አበይት ነጥብ ይሆናል፡፡ የዚህን ሀረግ ትክክለኛ ትርጉም ለመረዳት የሙስና ወንጀልን በሚደነግገው መደበኛ የወንጀል ህጉ እና በአዋጅ ቁጥር 881/2007 ስር ለእያንዳንዱ የሙስና ወንጀል የተቀመጠውን ቅጣት መጠን በጥንቃቄ በመፈተሽ ከላይ ከሰፈረው ድንጋጌ ተግባራዊ አፈፃፀም ጋር አዛምዶ ማየትን ይጠይቃል፡፡
- በዚሁ መሰረት በወንጀል ህጉም ሆነ በአዋጅ ቁጥር 881/2007 ውስጥ መነሻ ቅጣቱ አራት ዓመት እስራት የሆነ የሙስና ወንጀል የለም፡፡ መነሻ ቅጣታቸው ከአራት ዓመት በላይ እና ከአስር አመት በታች የሆኑት ሁለት ብቻ ናቸው፡፡ አንዱ መነሻው አምስት አመት ሲሆን ሌላኛው ደግሞ መነሻ ቅጣቱ ሰባት ዓመት የሆነ ነው፡፡ የእነዚህ ሁለቱ ቅጣቶች ጣሪያ ቅጣት እንደ ወንጀሉ ዓይነት የሚለያይ ቢሆንም መዳረሻው ግን ከአስራ አምስት እስከ ሃያ አምስት ዓመት የሚደርስ ፅኑ እስራት ነው፡፡

- በዚሁ አግባብ በድንጋጌው ውስጥ "ከአራት ዓመት በላይ" የሚለው ሀረግ የሚያሳየው የእያንዳንዱን ተደራራቢ ወንጀል መነሻ ቅጣት ነው የሚባል ከሆነ ጣሪያ ቅጣቱ ቢያንስ አስራ አምስት ዓመት ፅኑ እስራት ይሆናል፡፡ ጉዳዩ ይህ ከሆነ በአዋጅ ቁጥር 434/1997 አንቀፅ 4(1) እና ይህ ሰበር ችሎት በሰ/መ/ቁ/63344 ላይ ከሰጠው አስገዳጅ ትርጉም አኳያ የድንጋጌው ጣሪያ ቅጣት ከአስር ዓመት በላይ በመሆኑ እና በራሱ ከመነሻው ዋስትናን የሚያስከለክል በመሆኑ ስለ ተደራራቢ ወንጀል ማንሳት አያስፈልግም፡፡ በመሆኑም "ከአራት ዓመት በላይ" የሚለው ሀረግ መነሻ ቅጣትን የሚያሳይ ነው የሚለው አተረጓጎም የድንጋጌውን ተግባራዊ አፈፃፀም ትርጉም የሚያሳጣ በመሆኑ የሚያስኬድ አይደለም፡፡
- በአንፃሩ መነሻ ቅጣታቸው ምንም ይሁን ምን ጣሪያ ቅጣታቸው ግን ከአራት ዓመት በላይ እና ከአስር ዓመት በታች የሆኑ በአዋጁ ብቻ ከሃያ አንድ በላይ ድንጋጌዎች እንዲሁም ከአራት ዓመት በታች ጣሪያ ቅጣት ያላቸው ወደ አራት ድንጋጌዎች መኖራቸውን ለመገንዘብ ተችሏል፡፡ በተለያየ ምክንያት አንድን የህግ ድንጋጌን መተርጎም ቢያስፈልግ ከመተርጎሚያ ስልቶች ውስጥ አንዱ ህጉን ማወጂ ካስፈለገበት መሰረታዊ ዓላማ አንፃር ድንጋጌው ተግባራዊ ሊሆን በሚችልበት አግባብ መተርጎም(Purposive Interpretation) ስለመሆኑ የህግ አተረጓጎም መሰረተ ሀሳብ ያስገነዝባል፡፡
- ከዚህ አኳያ የህግ አውጭው ዓላማ ነው ተብሎ ከላይ የተመለከተው ተግባራዊ ሊሆን እና በአግባቡ ከግብ ሊደርስ የሚችለው በድንጋጌው ውስጥ "ከአራት ዓመት በላይ" ተብሎ የተጠቀሰው ሀረግ የእያንዳንዱን ተደራራቢ ወንጀሎች ጣሪያ ቅጣት የሚመለከት ነው በሚል ሲተረጎም ስለመሆኑ መረዳት ይቻላል፡፡
- የድንጋጌው ትርጉም ይህ ከሆነ የአሁን ተጠሪ እንዲከላከሉ ብይን በተሰጠባቸው እያንዳንዱ ድንጋጌ ስር ያለው ጣሪያ ቅጣት ከአስር ዓመት የማይበልጥ ፅኑ እስራት ሲሆን የሁለቱ ተደራራቢ ወንጀል ጠቅላላ ቅጣት ከአስር ዓመት በላይ በመሆኑ በፀረ ሙስና ልዩ የሥነ ሥርዓትና የማስረጃ ህግ(ማሻሻያ) አዋጅ ቁጥር 882/2007 አንቀፅ 3(1) መሰረት ዋስትና የሚያስከለክል ነው፡፡ እናም የከፍተኛ ፍርድ ቤቱ አረዳድ የህጉን መንፈስ የተከተለ በመሆኑ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የተከተለው አተረጓጎም ከዚህ አኳያ ሊቃና ይገባ ነበር በማለት ከስራ ባልደረቦቻችን የተለየ አቋም ይዘናል፡፡

የማይነበብ የሁለት ዳኛ ፊርማ አለበት፡፡

ሠ/ኃ

የሰ.መ.ቁ 179416

ሰኔ 23 ቀን 2012 ዓ.ም

ዳኞች፡- እትመት አሡፋ

ፀሐይ መንክር

ኑረዲን ከድር

መላኩ ካሣዬ

እስቲበል አንዱዓለም

አመልካች፡- ሀለቃ ንጉሴ አብርሃ

ተጠሪ፡- የትግራይ ክልል ፍትሕ ቢሮ

መዝገቡ ለምርመራ የተቀጠረ ነው፡፡ በመሆኑም መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍርድ

የሰበር አቤቱታው ሊቀርብ የቻለው አመልካች ሰኔ 07 ቀን 2011 ዓ.ም ጽፈው ባቀረቡት የሰበር አቤቱታ በትግራይ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የቃፍታ ሁመራ ወረዳ ፍ/ቤት በመ.ቁ 1800/11 በቀን 16/07/2011 ዓ.ም አመልካች በሕግ እንደሚፈለግ አውቆ ሆነ ብሎ ሲደበቅ የነበረ እና ሕግን በተከተለ የመጥሪያ ስነ ስርዓት መጥሪያ የተላከለት መሆኑ ስለተረጋገጠ ጉዳዩ ዳግም እንዲታይለት ያቀረበው አቤቱታ ተገቢ አይደለም ሲል የሰጠው ውሳኔ፤ ይህንኑ ውሳኔ በማጽናት የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 115243 ሚያዝያ 28 ቀን 2011 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ መሠረታዊ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት አቤቱታ በማቅረባቸው ነው፡፡

ጉዳዩ በሌለሁበት ታይቶ የተሰጠ ውሳኔ ይነሳልኝ በሚል የቀረበን አቤቱታ የሚመለከት ነው፡፡ አመልካች በስር ፍ/ቤት ባቀረቡት አቤቱታ በቃፍታ ሁመራ ቀበሌ ዓዲሹሁ ነዋሪና ባለትዳር እና ገበሬ መሆናቸውን፤ ወንጀል ፈጽመዋል ተብለው ወደ ሕግ አካል ቀርበው የማያውቁ መሆኑን፤ የመጥሪያ ትዕዛዝ ሳይሰጣቸው በስርቆት ወንጀል የአራት ዓመት ፍርደኛ ነህ ተብለው በቀን 25/06/2011 ዓ.ም ከመኖሪያ ቤታቸው በፖሊስ የተያዙ መሆኑን በመግለጽ ከሕግ ውጪ በሌለሁበት ታይቶ የተሰጠው ውሳኔ ተነስቶ ጉዳያቸው ባሉበት እንዲታይ ይወሰንላቸው ዘንድ ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡

ተጠሪ በሰጠው መልስ አመልካች የተከሰሱበት የወንጀል ሕግ አንቀጽ 669/3/ለ ድንጋጌ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 162 መሠረት በሌሉበት መታየት የሚችል መሆኑን፤ በፖሊስ መጥሪያ እንዲቀርቡ ታዞ ሊቀርቡ ያልቻሉ መሆኑን፤ በአድራሻቸው እንደሌሉ የሚገልጽ ማስረጃ አመልካች ከሚገኙበት አድራሻ የቀረበ መሆኑን፤ በጋዜጣ ጥሪ ተደርጎላቸውም ስላልቀረቡ ጉዳያቸው በሌሉበት ታይቶ ውሳኔ ያገኘ መሆኑን በመግለጽ አቤቱታው ውድቅ ሊደረግ ይገባል በማለት ተከራክሯል፡፡

ፍ/ቤቱም ጉዳዩን መርምሮ አመልካች በተደጋጋሚ እንዲያቀርቡ ታዞ በአድራሻቸው እንደሌሉ ማስረጃ ቀርቧል፤ በመቀጠልም በመቃልህ ጋዜጣ ጥሪ ተደርጎላቸው ሊቀርቡ አልቻሉም፤ አመልካች በክሱ ላይ በተገለጸው እና መደባይ ዛና ወረዳ ቀበሌ ዓዲ ጸጉራ ቀጠና ወይና አምባ በሚባለው አድራሻ እንዳሉ እና ለግዜው ተሰውረው እንደነበር የሚገልጽ ማስረጃ ከቀበሌው ጸጥታ አስተዳደር ቀርቧል፤ ይህ ማረጋገጫም አመልካች በሕግ የሚፈለጉ መሆኑን እያወቁ ሆን ብለው ሲደበቁ እንደነበረ የሚያሳይ ነው፤ ዓዲ ጎሹ በሚባል ቦታ ነው የነበርኩት በማለት የሚከራከሩ ቢሆንም ማስረጃ አላቀረቡም፤ ለአመልካች የደረሰው መጥሪያ ሕግን የተከተለ የመጥሪያ ስነ ስርዓት በመሆኑ አቤቱታቸው ተቀባይነት የለውም በማለት ውድቅ አድርጎታል፡፡ አመልካች ይህን ውሳኔ በመቃወም ለክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አቤቱታ ያቀረቡ ቢሆንም አቤቱታቸው በትዕዛዝ ውድቅ ተደርጓል፡፡

የሰበር አቤቱታው የቀረበው ይህን ውሳኔ በመቃወም መሠረታዊ የሕግ ስሕተት ተፈጽሞበታል በሚል ሲሆን ይዘቱም፡- አመልካች ገበሬ ባለትዳር እና የልጆች አባት መሆኔ በስር ፍ/ቤት ተረጋግጧል፤ አመልካች በወንጀል ጥፋተኛ መባሌን ያወቅኩት በቀን 25/06/2011 ዓ.ም በፖሊስ ከተያዝኩ በኋላ ነው፤ ከዚህ ቀን በፊት ለመርማሪ ፖሊሰ የሰጠሁት ቃል የለም ክስ እንደቀረበብኝ አልተነገረኝም፤ በምኖርበት አካባቢም የተለጠፈ መጥሪያ የለም፤ አመልካች በመርማሪ ፖሊስ ፊት ቀርቤ ትክክለኛ ስሜን እና አድራሻዬን ባልሰጠሁበት ሁኔታ እና ትክክለኛ ስሜም አለቃ ንጉሰ አብርሃ ተክለ አብዝጊ ሆኖ ሳለ አቶ ንጉሰ  አብርሃ ተክሉ ተብሎ በመቃልህ ጋዜጣ መታወጁ አግባብ አይደለም፤ በስር ፍ/ቤት የተሰጠው ፍርድ አመልካችን የሚመለከት መሆኑ ሳይረጋገጥ በሌለሁበት የተሰጠው ፍርድ ተነስቶ ጉዳዩ ባለሁበት እንዲታይ ያቀረብኩትን አቤቱታ ውድቅ በማድረግ የተሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት በመሆኑ በሰበር ታይቶ ሊታረም ይገባል የሚል ነው፡፡

የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ አመልካች በተጠቀሰው አድራሻ የሚገኝ ስለመሆኑ ፖሊስ ቃል ከሰጠ ያስመዘገበው አድራሻ ስለመኖሩ እንዲሁም በአድራሻው የማይገኝ ከሆነም ማረጋገጫ እንዲቀርብ ሳይደረግ፤ የጋዜጣ ጥሪውም በአመልካች ማመልከቻ በተጠቀሰው አግባብ ስለመደረጉ ሳይረጋገጥ ጉዳዩ በሌለበት እንዲታይ መደረጉ የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 942277 ከሰጠው ውሳኔ ጋር በማገናዘብ ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ በዚህ ችሎት እንዲታይ ተደርጓል፡፡ ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎም ግራቀኙ በጽሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

የተጠሪ መልስ ይዘት በአጭሩ፡- ስነ ስርዓቱ በሚያዘው መሠረት መጥሪያ ለአመልካች እንዲደርሰው ተደጋጋሚ ትዕዛዝ ለፖሊስ ተልኳል፤ ፖሊስ ለፍ/ቤቱ በሰጠው ምላሽ አመልካች በአድራሻው እንደሌለ እና ሊያቀርቡት እንደማይችሉ በመግለጽ ምላሽ በመስጠቱ በጋዜጣ እንዲጠራ ተደርጓል፤ አመልካች በጋዜጣ ተጠርቶ ስላልቀረበ ጉዳዩ በሌለበት ታይቷል፤ አመልካች በአድራሻው የነበረ መሆኑን በማስረጃ አላረጋገጠም፤ አመልካች በሌለበት ጉዳዩ ታይቶ የተሰጠው ውሳኔ የመጥሪያ አሰጣጥ ስርዓትን የተከተለ በመሆኑ የስር ፍ/ቤቶች የአመልካችን አቤቱታ ውድቅ በማድረግ የሰጡት ውሳኔ ሊጸና ይገባል የሚል ነው፡፡ አመልካችም የሰበር አቤቱታቸውን በማጠናከር የመልስ መልስ ሰጥተዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ በአጭሩ ከላይ የተገለጸው ነው፡፡ ይህ ችሎትም በሰበር አጣሪ ችሎት ለተያዘው ጭብጥ ምላሽ ከመስጠቱ በፊት ከመነሻውም ቢሆን አመልካች የተከሰሱበት የወንጀል ሕግ አንቀጽ 669/3/ለ በሌሉበት የሚታይ ነው ወይስ አይደለም የሚለውን ጭብጥ በመያዝ ጉዳዩን እንደሚከተለው መርምሮታል፡፡

በመሠረቱ የተከሰሱ ሰዎች በሕግ ከተጠበቁላቸው መብቶች መካከል አንዱ የተከሰሱበት ጉዳይ በፍርድ ቤት ሲታይ በችሎት ተገኝቶ የቀረበባቸውን ማስረጃ የመመልከት፣ የቀረበባቸው ምስክሮችን የመጠየቅ፣ ለመከላከል የሚያስችላቸውን ማስረጃ የማቅረብ ወይም የማስቀረብ እንዲሁም ምስክሮቹ ቀርበዉ እንዲሰሙላቸው የመጠየቅ መብት ነዉ፡፡ ኢትዮጲያ የተቀበለችው ዓለም አቀፍ የሲቪል እና የፖለቲካ መብቶች ስምምነት አንቀጽ 14 ድንጋጌም የተከሰሱ ሰዎች ፍትህ የማግኘት እና በገለልተኛ ፍ/ቤት የመዳኘት እና በአካል ተገኝቶ የመከራከር መብት እንዳላቸው ይደነግጋል፡፡

ከላይ የተመለከቱት ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው በልዩ ሁኔታ በግልጽ በሕግ ከተመለከቱትና ከተፈቀዱት በስተቀር በመርህ ደረጃ የወንጀል ክስ የሚታየዉም ሆነ ክርክር ተደርጎ ዉሳኔ የሚሰጠዉ ተከሳሽ በችሎት በተገኘበት ነዉ፡፡ በልዩ ሁኔታ ሕግ ፈቅዶ ጉዳዩ ተከሳሽ በሌለበት የሚታየዉም ከአሥራ ሁለት ዓመት በማያንስ ጽኑ እሥራት የሚያስቀጡ ወይም በመንግስት ኢኮኖሚ ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎች ሆነዉ በጽኑ እስራት ወይም ከብር 5,000 በላይ የሚያስቀጡ ከባድ ወንጀሎችን የሚመለከቱ ወንጀሎችን ብቻ ስለመሆኑ ከወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ 162(2) ድንጋጌ ይዘት መገንዘብ ይቻላል፡፡ ሕጉ እነዚህን ወንጀሎች አስመልክቶ በልዩ ሁኔታ ተከሳሽ በሌለበት እንዲታዩ የፈቀደበትና አብዛኛዎችን ወንጀሎች ተከሳሽ እስካልተገኘ ድረስ ወይም በአግባቡ መጥሪያ ደርሶት በችሎት ቀርቦ የመከራከር መብቱን እስካልተወ ድረስ ጉዳዩ እንዳይታይ የደነገገበት ዓላማ በአንድ በኩል ተከሳሽ ከባድ ወንጀል ፈጽሞ ከፍትሕ በመሠወሩ የወንጀሉ ተጎጂዎችን ፍትሕ የማግኘት መብት ለማረጋገጥ ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ ሕጉ ለይቶ ባስቀመጣቸው ከባድ ወንጀሎች ውጪ ባሉት ጉዳዮች የተከሳሽ በችሎት ተገኝቶ የመከራከር መብት ከሚጣስ ይልቅ ተከሳሽ እስኪገኝ ድረስ የፍርድ ሂደቱ እንዳይካሄድ ስለመሆኑ ከላይ በዝርዝር ከተደነገጉት ድንጋጌዎች ይዘት መገንዘብ ይቻላል፡፡

በያዝነው ጉዳይ አመልካች የተከሰሱበት የወንጀል ሕግ አንቀጽ 669/3/ለ ድንጋጌ ከአንድ ዓመት በማያንስ ቀላል እሥራት ወይም ከአሥራ አምስት ዓመት የማይበልጥ ጽኑ እሥራት የሚያስቀጣ ነው፡፡ ይህ ድንጋጌ አማራጭ ቅጣቶችን የያዘ ሲሆን በዚህ ድንጋጌ መሠረት ክስ የቀረበበት ተከሳሽ አንድም በቀላል እሥራት አልያም በአማራጭ ከተቀመጠው የጽኑ እሥራት ቅጣት ከ12 ዓመት በታች ወይም ከአሥራ ሁለት ዓመት በላይ በሆነ ጽኑ እሥራት ሊቀጣ እንደሚችል እንገነዘባለን፡፡ በመሆኑም በዚህ ድንጋጌ መሠረት የተከሰሰ ተከሳሽ አስመልክቶ ተመራጭ የሚሆነው የፍርድ ሂደት የወንጀሉ ተጎጂዎችን ፍትሕ የማግኘት መብት ለማረጋገጥ ሲባል ከአሥራ ሁለት ዓመት በላይ በሆነ ጽኑ እሥራት ሊቀጣ እንደሚችል ከወዲሁ ግምት በመውሰድ ጉዳዩን በሌለበት ማየት ነው? ወይስ የተከሳሽ በችሎት ተገኝቶ የመከራከር መብት ከሚጣስ ይልቅ ተከሳሽ እስኪገኝ ድረስ የፍርድ ሂደቱ እንዳይካሄድ ማድረግ? የሚለው በጥንቃቄ ታይቶ ምላሽ ሊሰጠው ይገባል፡፡

በአካል ፍ/ቤት ተገኝቶ የመከራከር መብት ለተከሰሱ ሰዎች በሕገመንግስቱ አንቀጽ 20/4 እና ኢትዮጲያ በተቀበለችው ዓለም ዓቀፍ የሲቪል እና የፖለቲካ መብቶች ስምምነት አንቀጽ 14 ላይ የተጠበቀላቸው መሠረታዊ መብት በመሆኑ፤ አመልካች የተከሰሱበት የወንጀል ሕግ አንቀጽ 669/3/ለ ከባድ የስርቆት ወንጀል ሕግ አውጪው ሊያሳካው ያሰበው ልዩ ዓላማ ኖሮት ለብቻው የሕግ ማዕቀፍ የወጣለት ሳይሆን በመደበኛው የወንጀል ሕግ የተደነገገ በመሆኑ፤ ይህ ድንጋጌም አማራጭ ቅጣቶችን የየዘ በመሆኑ፤ በዚህ ድንጋጌ መሠረት አመልካች ጥፋተኛ ቢባሉ በቀላል እሥራት፤ ከ12 ዓመት በታች በሆነ ጽኑ እሥራት ወይም ከአሥራ ሁለት ዓመት በላይ በሆነ ጽኑ እሥራት ሊቀጡ የሚችሉ በመሆኑ ተመራጭ የሚሆነው የፍርድ ሂደት አመልካች በድንጋጌው የተቀመጠው ከፍተኛ ቅጣት ሊቀጡ ይችላሉ ብሎ ከወዲሁ በማሰብ ጉዳዩን በሌሉበት እንዲታይ ማድረግ ሳይሆን የተከሳሽ በችሎት ተገኝቶ የመከራከር መብት ከሚጣስ ይልቅ ተከሳሽ እስኪገኝ ድረስ የፍርድ ሂደቱ እንዳይካሄድ ማድረግ ነው፡፡ በመሆኑም አመልካች የተከሰሱበት የወንጀል ሕግ አንቀጽ 669/3/ለ ተከሳሹ በሌለበት ሊታይ የሚችል አይደለም፡፡ የስር ፍ/ቤት ጉዳዩን በዚህ አግባብ በማየት አመልካች የተከሰሱበት የሕግ ድንጋጌ በሌሉበት የሚታይ አይደለም በማለት አመልካች እስኪገኙ ድረስ የፍርድ ሒደቱ እንዳይካሄድ ማድረግ ሲገባው አመልካች የተከሰሱበት ድንጋጌ በሌሉበት የሚታይ እንደሆነ ግምት በመውሰድ የሰጠው የጥፋተኝነትም ሆነ የቅጣት ውሳኔ እና አመልካች ጉዳያቸው ባሉበት ያቀረቡትን አቤቱታ ውድቅ በማድረግ የሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ ስለሆነም ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

## ውሳኔ

1. በትግራይ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የቃፍታ ሁመራ ወረዳ ፍ/ቤት በመ.ቁ 1800/11 አመልካች በሌሉበት ጉዳያቸውን በማየት የሰጠው የጥፋተኝነት እና የቅጣት ውሳኔ እንዲሁም በቀን 16/07/2011 ዓ.ም አመልካች በሌሉበት ታይቶ የተሰጠው ውሳኔ ተነስቶ ጉዳያቸው ባሉበት እንዲታይ ያቀረቡትን ማመልከቻ ውድቅ በማድረግ የሰጠው ውሳኔ፤ ይህንኑ ውሳኔ በማጽናት የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 115243 ሚያዝያ 28 ቀን 2011 ዓ.ም በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 195/2/ለ/2 መሠረት ተሽሯል፡፡

2. ከላይ በፍርድ ሐተታው ላይ በተገለጸው ምክንያት አመልካች የተከሰሱበት የወንጀል ሕግ አንቀጽ 669/3/ለ ድንጋጌ ተከሳሽ በሌለበት ሊታይ የሚችል አይደለም በማለት ወስነናል፡፡
3. ስልጣን ያለው ሌላ ችሎት አመልካች ባሉበት ክርክሩን እንዲያይ እና ዓቃቤሕጉም ክሱን ስልጣን ላለው ፍ/ቤት እንዲያቀርብ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 202 መሠረት ተወስኗል፡፡

## ትዕዛዝ

- አመልካች በስር ፍ/ቤት ቀርበው በዋስትና ላይ እስኪከራከሩ ድረስ ለብር 10,000 / አሥር ሺህ/ የሚበቃ ዋስ ሲያቀርቡ ወይም ገንዘቡን በሞዴል 85 ሲያስይዙ ከእስር እንዲለቀቁ በአብላጫ ድምጽ ታዟል፡፡

-የሚመለከተው ማረሚያ ቤት አመልካች በሌሉበት ታይቶ በስር ፍ/ቤቶች የተሰጠው የጥፋተኝነት እና የቅጣት ውሳኔ ተሽሮ አመልካች ባሉበት ጉዳያቸው እንዲታይ የተወሰነ መሆኑን አውቆ በዚህ ችሎት እንዲያስይዙ የተወሰነውን የዋስትና ገንዘብ ማስያዛቸው ሲረጋገጥ በሌላ ጉዳይ የማይፈለጉ መሆኑን አረጋግጦ ከእሥር እንዲለቅ ታዟል፡፡

-መዝገቡ ውሳኔ ስላገኘ ተዘግቷል፡፡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

የሰ/መ/ቁ. 171521

ታህሳስ 23 ቀን 2012 ዓ/ም

**ዳኞች** ፡- እትመት አሰፋ

ጻውሎስ ኦርሺሶ

ፀሐይ መንክር

መላኩ ካሳዬ

እስቲበል አንዱዓለም

**አመልካች** ፡- የፌዴራል ጠቅላይ ዓቃቤህግ - አቶ ብርሃኑ ታደለ ቀረቡ፡፡

**ተጠሪ** ፡- ወ/ሮ ትርሃስ መስፍን ገ/እግዚአብሔር - የቀረበ የለም፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ ቀጥሎ ያለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍርድ**

ለዚህ የሰበር ክርክር መነሻው አመልካች በቁጥር 3-3367/1862/07 በ18/06/2011 ዓ.ም በተጻፈ አቤቱታ የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የልደታ ምድብ ችሎት በኮ/መ/ቁ225717 በቀን 24/02/2009 ዓ.ም የሰጠው ብይን እና የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይህንኑ በማጽናት በኮ/መ/ቁ. 218556 ህዳር 13 ቀን 2011 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነው በማለት በመጠየቁ ነው፡፡

የነገሩ አመጣጥ የወንጀል ክስን የሚመለከት ነው፡፡የአሁን አመልካች /የሥር ከሳሽ/ በቁጥር 2/515/1868/07 በ23/07/07 ዓ.ም ጽፎ ያቀረበው ክስ በ1996 የወጣውን የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲዊ ሪፐብሊክ የወንጀል ህግ አንቀጽ 385 (1) (ለ) ሥር የተመለከተውን በመተላለፍ ተከሳሽ ተከሳለች የሚል ነው፡፡የክሱ ዝርዝር፡- ተከሳሽ /የአሁን ተጠሪ/ ጥቅምን ወይም መሻሻልን ለማግኘት በማሰብ በልደታ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 12/45 ክልል ልዩ ቦታው የኢሚግሬሽን የዜግነት ጉዳይ ዋና መመሪያ ውስጥ በቀን 19/06/07 በግምት ከቀኑ 8.00 ሰዓት ሲሆን ተከሳሽ ዜግነቷ ኤርትራዊ ሆኖ እያለ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክፍለ ከተማ የወረዳ 12 የነዋሪዎች መታወቂያ በማውጣት ቁጥሩ EP 2378734 የሆነ የኢትዮጵያ ፓስፖርት በማውጣቷ ተከሳሽ የማይመለከታትን ትክክለኛ ሰነድ በመገልገል ወንጀል ተከሳለች የሚል ነው፡፡

ተከሳሽ ቀርባ የእምነት ክህደት ቃል ከሰጠች በኋላ የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የልደታ ምድብ ችሎት በኮ/መ/ቁ.225717 በሆነው በቀን 24/02/2009 ዓ.ም በዋለው ችሎት በሰጠው ብይን በቀን

4/11/2008 ዓ.ም በዋለው ችሎት አቃቤ ህግ ያቀረበው ክስና ክርክር እና የተጠቀሰው ድንጋጌ የማይጣጣም በመሆኑ ክሱን አሻሽሎ እንዲያቀርብ ትዕዛዝ እንደተሰጠ፣ይሁን እንጂ ዐቃቤህግ በቀን 10/02/2009 ዓ.ም በተጻፈ መልስ ክሱ በአግባቡ የቀረበ፣የተከሳሽ ድርጊትም ሊወድቅበት በሚችል የወንጀል ህግ ድንጋጌ መሠረት የቀረበበ መሆኑ ክስ የሚሻሻልበት አግባብ የለም ማለቱን ገልጾ ዐቃቤህግ በፍርድ ቤቱ የተሰጠውን ትዕዛዝ ተገቢነት የለውም የሚል ከሆነ በይግባኝ የሚያስተካክል ከመሆን ባለፈ ትዕዛዝ አልፈጽምም መባሉ ተገቢ ሆኖ አልተገኘም፡፡ይህ ችሎትም ቀደም ሲል በዚህ ፍርድ ቤት የተሰጠን የክስ ይሻሻል ትዕዛዝ የማንሳት ሥልጣን የሌለው በመሆኑ እንደትዕዛዙ ዐቃቤህግ ክሱን ባለማሻሻሉ መዝገቡ ሊዘጋ ይገባል ሲል ደምድሞታል፡፡

በዚህ ብይን የአሁን አመልካች ቅር ተሰኝቶ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ያቀረበ ሲሆን ከፍተኛ ፍርድ ቤቱም የሥር ፍርድ ቤት ክስ እንዲሻሻል ያስተላለፈው ትዕዛዝ የወንጀለኛ መቅጫ ሥነሥርዓት ህግ ቁጥር 119 (1) ክስ እንዲለወጥ ወይም እንዲጨመር ወይም አዲስ ክስ እንዲዘጋጅ ፍርድ ቤት ማዘዝ የሚችል መሆኑን ህጉ የሚፈቅድ በመሆኑ የሥር ፍርድ ቤት ይህን ትዕዛዝ ማዘዙ የሚነቀፍ ስላልሆነ የይግባኝ ቅሬታው መልስ ሰጪን አያስቀርብም ሲል ወስኗል፡፡

አመልካች የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ልደታ ምድብ ችሎት የሰጠው ብይን እንዲሁም የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነው በማለት በቁጥር 3-3367/1862/07 በቀን 18/06/2011 ዓ.ም የተጻፈ አቤቱታ አቅርቧል፡፡የአቤቱታው ይዘትም በአጭሩ፡- የሥር ፍርድቤቶች ተጠሪዋ የውጭ ዜጋ ወይም ኤርትራዊ ሆና እያለ እና ለኢትዮጵያዊያን ብቻ የሚያገለግል የነዋሪዎች መታወቂያ ተጠቅማ ፓስፖርት አውጥተው ባሉበት ሁኔታ አመልካች ይህን በሚያሳይ እንዲሁም የወንጀል ድንጋጌውን በሚገልጽ መልኩ ተጠሪ ለእርሷ አገልግሎት የማይውል ነው ሊባል አይገባም ወይም የክሱ ፍሬ ነገርና የወንጀል ድንጋጌው አይጣጣምም ተብሎ የተሰጠው ውሳኔ የወንጀል ህጉን አንቀጽ 385(1) (ለ) ሲተረጉሙ መሠረታዊ የህግ ስህተት መፈፀማቸውን ስለሚያሳይ እንዲታረምልን የሚል ነው፡፡

የሰበር አቤቱታውን አጣሪው መርምሮ አመልካች በሥር ፍርድ ቤት በተጠሪ ላይ በመሠረተው የወንጀል ክስ ላይ የተመለከተው የወንጀል ህግ አንቀጽ እና ዝርዝሩ የማይመጣጠን በመሆኑ አመልካች ክሱን አሻሽሎ እንዲያቀርብ በሥር ፍርድ ቤት በሰጠው ትዕዛዝ መሠረት አመልካች ለማሻሻል ፈቃደኛ አልሆነም፤ቀደም ሲል ክስ እንዲሻሻል የተሰጠውን ትዕዛዝ ማንሳት አይቻልም በሚል የተዘጋበትን አግባብነት ከመሠረታዊ ክርክር አመራር ሥነ-ሥርዓት እና ከወንጀለኛ መቅጫ ሥነ-ሥርዓት ህግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ለመመርመር ለሰበር ያስቀርባል ሲል ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡

ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎላት ቀርባ ሐምሌ 9 ቀን 2011 ዓ.ም በሰጠችው መልስ የሥር ፍርድ ቤት የቀረበው ክስ ስህተት ያለበት ነው ብሎ ያመነ በመሆኑ ክስ እንዲሻሻል በሰጠው ትዕዛዝ ላይ የተፈጸመ

መሠረታዊ የህግ ስህተት የለም በማለት ተከራክራለች፡፡አመልካቹም በ24/11/2011 ዓ.ም የተጻፈ የመልስ መልስ አቅርቧል፡፡

የነገሩ አመጣጥና የክርክሩ ሂደት ከላይ እንደተመለከተው ሲሆን በሥር ፍርድ ቤቶች ብይንም ሆነ ውሳኔ ላይ መሠረታዊ የህግ ስህተት ተፈጽሞበታል? ወይስ አልተፈጸመበትም? የሚል ጭብጥ ተይዞ ጉዳዩ እንደሚከተለው ተመርምሯል፡፡የሥር ፍርድ ቤት የቀረበውን ክስ አመልካች እንዲያሻሽል በ4/11/2008 ዓ.ም ትዕዛዝ መስጠቱ፣ዐቃቤ ህግም በ10/02/2009 ዓ/ም በተጻፈ መልስ ክሱ የተከሳሽ /የተጠሪ/ ድርጊት ሊወድቅበት በሚችል የወንጀል ህግ ድንጋጌ መሠረት የቀረበበ መሆኑ ክስ የሚሻሻልበት አግባብ የለም ሲል መከራከሩ የተረጋገጡ ፍሬ ነገሮች ናቸው፡፡የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ልዳታ ምድብ ችሎት መዝገብ ለመዝጋት መሰረት ያደረገው ዐቃቤ ህግ ክስ እንዲያሻሽል የተሰጠውን ትዕዛዝ የሚቃወም ከሆነ በይግባኝ ከሚያሳርም ውጪ ፍርድ ቤቱ የሰጠውን ትዕዛዝ ሊያነሳ ስለማይችል መዝገቡ ተዘግቷል የሚል ነው፡፡የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የሰጠውን ብይን በተመለከተ ለሁለት ከፍሎ ማየት ተገቢ ነው፡፡የመጀመሪያው ፍርድ ቤቱ ክስ እንዲሻሻል የሰጠውን ትዕዛዝ እራሱ ማንሳት ይችላል? ወይስ አይችልም? የሚለው ነው፡፡የወንጀል ክርክር የሚመራበት ሥርዓት በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ-ሥርዓት ህግ በዝርዝር ተደንግጎ እንመለከታለን፡፡የወንጀልን ጉዳይ የሚመለከት ችሎትም በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ-ሥርዓት ህግ ላይ የተደነገጉትን ድንጋጌዎች ተከትሎ የቀረበለትን ጉዳይ ይመለከታል ክርክሩንም ይመራል፣ችሎቱንም ይቆጣጠራል፣ክርክሩ ሲጠናቀቅ ወይም ጉዳዩ ሲበስል ፍርድ ይሰጣል፡፡ክርክሩን ከሚመራባቸው ሥልቶች መካካል አንዱ ጉዳዩን በሚያይበት ጊዜ አስፈላጊ ነው ብሎ ያመነውን ትዕዛዝ መስጠት ነው፡፡በተያዘው ጉዳይ የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ልደታ ምድብ ችሎት አመልካች ባቀረበው ክስ ላይ የተገለጸው ፍሬ ነገር ከተጠቀሰው የህግ ድንጋጌ ጋር የማይጣጣም ነው በማለት ክሱ እንዲሻሻል በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ-ሥርዓት ህግ ቁጥር 119(1) መሠረት ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡አመልካች ክስ እንዲያሻሽል ትዕዛዝ ሲሰጥ የቀረበው ክስ የሚሻሻልበት ምክንያት አይኖርም በማለት ክስ ለማሻሻል ፈቃደኛ ባለመሆኑ ፍርድ ቤቱ አስቀድሞ የሰጠውን ትዕዛዝ አላነሳም ማለቱ ስህተት አይደለም፡፡በያዝነው ጉዳይ ትዕዛዝ የሰጠው ፍርድ ቤት እራሱ ትዕዛዙን ለማንሳት የማይችልበት አንደኛው ምክንያት ክስ እንዲሻሻል በራሱ በኩል አምኖ ትዕዛዝ የሰጠ በመሆኑ የሰጠውን ትዕዛዝ ማንሳት ተገቢ ሆኖ ስለማይታይ ነው፡፡ ሁለተኛው ምክንያት ትዕዛዝ የሰጠው ፍርድ ቤት እራሱ ተመልሶ ትዕዛዙን የሚያነሳ ከሆነ የክርክር አመራር ሥርዓትን ያልተከተለ ስለሚሆንና ተገልጋዩም በፍርድ ቤቱ ላይ ያለውን አመኔታ የሚቀንስ ወይም የሚሸረሽር በመሆኑ ነው፡፡ሶስተኛው ምክንያት በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ-ሥርዓት ህግ ቁጥር 184 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ፍርድ ቤቱ ክስ እንዲሻሻል የሰጠው ትዕዛዝ ይግባኝ ሊባል የሚችል በመሆኑ ነው፡፡ይግባኝ ሊባል የሚችልበትም ፍርድ ቤቱ የቀረበው ክስ መሻሻል አለበት ብሎ ያመነ በመሆኑ ባዘዘው ትዕዛዝ መሠረት ካልተሻሻለ

በስተቀር ክርክሩን ስለማያካሂድ ነው፡፡ከእነዚህ ምክንያቶች ተነስተን ስናይ የሥር ፍርድ ቤት የሰጠውን ትዕዛዝ አላነሳም ማለቱ የሚነቀፍ ሆኖ አልተገኘም፡፡

በሌላ በኩል ሁለተኛው መሠረታዊ ነገር ፍርድ ቤቱ የቀረበው ክስ ላይ ያለው ፍሬ ነገር እና የተጠቀሰው የህግ ድንጋጌ አይጣጣምም በማለት አመልካች ክስ እንዲያሻሽል ትዕዛዝ መስጠቱ በክስ ላይ የተገለጸውን እና የተጠቀሰውን የህግ ድንጋጌንያገናዘበ ነው ወይ? የሚለው ሊታይ የሚገባው ነው፡፡

በመሠረቱ ፍርድ ቤት ክስ እንዲሻሻል ትእዛዝ የሚሰጠዉ በምን አግባብ ነዉ? ህጋዊ ውጤቱስ ምንድነዉ? የሚለው መታየት ያለበት ነው፡፡የወንጀል ክስ ማመልከቻ አዘጋጃጀት አስመልክቶ ይዘቱና ዓይነቱ በምን አኳኋን እና ዝርዝር ሊኖረዉ እንደሚገባ በወንጀለኛ መቅጫ ስነ ስርዓት ህግ አንቀጽ 111 እና 112 ላይ ተመልክቷል፡፡ከነዚህ ድንጋጌዎች ይዘት መገንዘብ የሚቻለዉ ክሱ በዝርዝር እንዲገለጽ ከሚጠበቅባቸዉ መሰረታዊ ፍሬ ነገሮች ዉስጥ በክሱ የተጠቀሰዉ የወንጀል ህግ ድንጋጌ እና ተከሳሹ የፈጸመው የወንጀል ተግባር የክሱ ፍሬ ነገር ከህጉ አነጋገር ጋር በጣም የተቀራረበ መሆን እንዳለበት ነዉ፡፡የክሱ አዘገጃጀትና ዝርዝር ይዘት ላይ መገለጽ የሚገባው መሰረታዊ ነገር ባለመገለጹ ተከሳሹን ያሳሳተው እንደሆነ ወይም ትክክለኛ ፍርድ ለመስጠት የማይቻል ከሆነ ደግሞ ፍርድ ቤቱ በራሱ አስተያየት ወይም ማመልከቻ በቀረቡለት ጊዜ እንደነገሩ ሁኔታ ክሱ እንዲለወጥ፣እንዲጨመር ወይም አዲስ ክስ እንዲዘጋጅ ትእዛዝ መስጠት እንደሚችል በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርዓት ህግ አንቀጽ 118 እና 119/1/ ድንጋጌዎች ይዘት ያስገነዝባሉ፡፡ስለሆነም ክስ እንዲሻሻል ትእዛዝ የሚሰጠው በክስ ማመልከቻ ፎርም ወይም በክሱ ማመልከቻ ላይ ስለወንጀሉ አስፈላጊ ዝርዝር ውስጥ ስህተት ሲገኝ ወይም ሳይጠቀስ ሲቀርና ይህም መሰረታዊ ነገር ሆኖ ሲገኝ እንደሆነ እንገነዘባለን፡፡በዚህ ምክንያት ፍርድ ቤቱ ክስ እንዲሻሻል ትእዛዝ ሰጥቶ ዐቃቤ ህግ የተሻሻለ ክስ አዘጋጅቶ ያላቀረበ እንደሆነ ተከሳሽ ለጊዜዉ እንደሚለቀቅ የወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርዓት ህግ ቁጥር 122/3/ ድንጋጌ ይገልጻል፡፡ስለሆነም በፍርድ ቤቱ ትእዛዝ መሰረት ክሱ ተሻሽሎ ያልቀረበ እንደሆነ ውጤቱ መዝገቡን ለጊዜው በመዝጋት ተከሳሹን መልቀቅ እንደሆነ ህጉ በግልጽ ደንግጓል፡፡

የክስ ማመልከቻ እንዲሻሻል የሚደረገው ከላይ በተገለጸው አግባብ በክሱ ዝርዝር ላይ መገለጽ የሚገባው መሰረታዊ ጉዳይ ሳይገለጽ የቀረ እንደሆነ ወይም ደግሞ ያለአግባብ የተገለጸው ነገር ተከሳሹን የሚያሳስት ነው ተብሎ ሲታሰብ ነው፡፡

በእጃችን ያለውን ጉዳይ ስንመለከት የዐቃቤ ህግ ክስ ተከሳሽ /የአሁን ተጠሪ/ ጥቅምን ወይም መሻሻልን ለማግኘት በማሰብ በልደታ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 12/45 ክልል ልዩ ቦታው የኢሚግሬሽን የዜግነት ጉዳይ ዋና መምሪያ ውስጥ በቀን 19/06/07 በግምት ከቀኑ 8.00 ሰዓት ሲሆን ተከሳሽ ዜግነቷ ኤርትራዊ ሆኖ እያለ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክፍለ ከተማ የወረዳ 12 የነዋሪዎች መታወቂያ በማውጣት ቁጥሩ EP 2378734 የሆነ የኢትዮጵያ ፓስፖርት በማውጣቷ ተከሳሽ የማይመለከታትን

ትክክለኛ ሰነድ በመገልገል ወንጀል ህግ አንቀጽ 385(1) (ለ) ሥር የተደነገገውን በመተላለፍ ተከሳለች የሚል ነው፡፡በዚህ ክስ ላይ የተገለጹት ፍሬ ነገሮች በወንጀል ህግ አንቀጽ 385(1) (ለ) ሥር ከተቀመጠው ጋር ይጣጣማሉ? ወይስ አይጣጣሙም? የሚለውን መመልከት ተገቢ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡የወንጀል ህግ አንቀጽ 385 (1) (ለ) ወደ ሀሰት የተለወጠውን ወይም መስሎ የተሰራውን ሰነድ ወይም ለእርሱ አገልግሎት ያልታሰበውን ወይም እርሱን የማይመለከተውን ትክክለኛ ሰነድ እያወቀ የተገለገለበት እንደሆነ በቀላል እሥራት ወይም በመቀጮ ይቀጣል ሲል ይደነግጋል፡፡ቀጥሎ ያለው ፓራግራፍም /አንቀጽ/ ተጨማሪ ዝርዝር ነጥቦችንና ቅጣታቸውን ያስቀምጣል፡፡በያዝነው ጉዳይ የአቃቤ ህግ ክስ ተጠሪ ኤርትራዊ ሆና እያለች በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክፍለ ከተማ የወረዳ 12 የነዋሪዎች መታወቂያ በማውጣት ቁጥሩ EP 2378734 የሆነ የኢትዮጵያ ፓስፖርት በማውጣቷ የማይመለከታትን ትክክለኛ ሰነድ በመገልገል ተከሳለች የሚል ነው፡፡ተጠሪ የኢትዮጵያን ፓስፖርት ለማውጣት የተጠቀመችው ከላይ የተጠቀሰው ክፍለ ከተማ የወረዳ 12 ነዋሪ እንደሆነች በማድረግ ያወጣችውን መታወቂያ ደብተር በመጠቀም ነው፡፡ይህ ደግሞ በወንጀል ህግ አንቀጽ 385 (1) (ለ) ሥር ከተቀመጡት ነጥቦች መካከል "እርሱን የማይመለከተውን ትክክለኛ ሰነድ እያወቀ የተገለገለበት እንደሆነ" የሚለው ከአቃቤ ክስ ጋር የሚጣጣም ነው፡፡ በመሆኑም የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት አመልካች /ዐቃቤ ህግ/ ባቀረበው ክስ ላይ የተገለጸው ፍሬ ነገር ከተጠቀሰው የህግ ድንጋጌ ጋር አይጣጣምም ሲል የደረሰው ድምዳሜ የተሳሳተ ነው፡፡ጉዳዩ በይግባኝ የቀረበለት የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤትም ይህንን ሳያርም ማለፉ ሲታይ የሚነቀፍ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ሲጠቃለልም የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ልደታ ምድብ ችሎት ክስ እንዲሻሻል ሲል የሰጠው ትዕዛዝ በክሱ ላይ የተመለከቱትን ፍሬ ነገሮች እና የተጠቀሰውን የህግ ድንጋጌን በአግባቡ ያላጤነ ሆኖ በመገኘቱ እንዲሁም የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤትም ይህንን ሳያርም ማለፉ ሲታይ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡በመሆኑም ቀጥሎ ያለው ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

<u>**ው ሳ ኔ**</u>

1. ፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የልደታ ምድብ ችሎት በኮ/መ/ቁ. 225717 በቀን 24/02/2009 ዓ.ም አመልካች ክስ አላሻሽልም ብሏል በማለት መዝገቡ እንዲዘጋ ሲል የሰጠው ብይን እና የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤትይህንኑ በማጽናት በኮ/መ/ቁ. 218556 ህዳር 13 ቀን 2011 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርዓት ህግ ቁጥር 195 (2 )(ሀ) መሠረት ተሰርዟል፡፡

2. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ልደታ ምድብ ችሎት ክስ እንዲሻሻል ሲል የሰጠው ትዕዛዝ በክሱ ላይ የተመለከቱትን ፍሬ ነገሮች እና የተጠቀሰውን የህግ ድንጋጌን በአግባቡ ያላጤነ ሆኖ በመገኘቱ እና ጉዳዩ በይግባኝ የቀረበለትም የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤትም ይህንን ሳያርም ማለፉ ሲታይ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነው ተብሎ ተወስኗል፡፡

3. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ልደታ ምድብ ችሎት ክስ እንዲሻሻል በ4/11/2008 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠሁትን ትዕዛዝ በራሴ አላነሳም ሲል የደረሰው ድምዳሜ ተገቢ ነው ብለናል፡፡

4. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ልደታ ምድብ ችሎት የዘጋውን መዝገብ በማንቀሳቀስ ክርክሩን ሰምቶ ተገቢውን ውሳኔ እንዲሰጥበት በማለት በወንጀለኛመ ቅጫ ሥነ ሥርዓት ህግ ቁጥር 195 (2) (ሀ) መሰረት ጉዳዩን መልሰንለታል፡፡ይጻፍ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ይመለስ ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

መ/አ

# ልዩ ልዩ

የሰበር መዝገብ ቁጥር 159062

ጥር 30ቀን 2011 ዓ.ም

ዳኞች፡- ተኽሊት ይመሰል

ተፈሪ ገብሩ (ዶ/ር)

ቀነዓ ቂጣታ

ተሾመ ሽፈራው

ፀሐይ መንክር

አመልካች፡- አቶ መረሳ ወ/ማርያም ቀረቡ:: ወ/ሮ አብረኸት ገ/ፃድቃን ወኪል ቀረቡ::

ተጠሪ፡- ቄስ ወ/ጊዩርጊስ ኪዳኔ ጠ/መኮንን አምቦ ::

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍርድ

ይህ የሰበር አቤቱታ ሊቀርብ የቻለው አመልካቾች የአሁን ተጠሪ ላይ በትግራይ ክልል ማዕከላዊ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት አክሱም ምድብ ችሎት የሽያጭ ውልን መነሻ በማድረግ የቀ ረበው ክስ ወፍጮውን እና መሬቱ ከነግንብ አጥሩ ለተከሣሽ የሸጡ በመሆኑ መሬቱን ተከሣሽ ሊለቅ አይገባም ተብሎ መወሰኑና እስከ ክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት መጽናቱ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት በመሆኑ ነው በሚል በሰበር ለማሳረም አቤቱታ በመቅረቡ ነው፡፡

በስር ፍ/ቤት ቀርቦ የነበረው ክስ በአጭሩ የሚያሳየው በወረዳ ታች ማይጨው ማይበራዝዬ ቀበሌ ዓዲ ንፋስ ጎጥ ልዩ ቦታ ዓውደ ኲሐ በተባለ የኢንቨስትመንት ቦታ አዋሣኙ በክሱ የተገለፀውን ቦታ የእህል ወፍጮ ከነሙሉ መሳሪያው በብር 20,000.00/ሃያ ሺ / ከሣሾች ለተከሣሽ የሸጡላቸውና ገንዘቡንም መቀበላቸውን ሆኖም ግን የተሸጠውን ወፍጮ ከኢንቨስትመንት ቦታው ላይ ሊያነሱ በተደጋጋሚ ተከሣሽን ቢጠይቋቸው ፈቃደኛ ባለመሆናቸው የጽሁፍ ማስጠንቀቂያ ቢሰጡም ሊያነሱ ስላልቻሉ አንስተው ቦታውን እንዲለቁልን ይወሰንልን በማለት አመልካቾች ክስ አቅርበዋል፡፡

ተከሣሽ/ተጠሪ / በሰጡት መልስ ወፍጮውን የገዛሁት ከነመሬቱ ነው ለአስተዳደሩም ይህንኑ ገልፀው በቀን 12/1/2007 ዓ.ም. በቁጥር 51/11 በክስ የተገለፀ 40 በ30 ካ/ሜ የመጠቀም መብት የይዞታ ማረጋገጫ ተሰጥቶኛል፡፡ ስለዚህ ህጋዊ ይዞታዬ ነው፡፡ መሬቱንም በብር 20,000.00 ተብሎ ተገምቶ መቅረቡ መሬቱ በገንዘብ አይገመትም ህጋዊነትም የለውም የሚል መልስ በማቅረብ ክሱ ውድቅ እንዲሆንላቸው ጠይቀዋል፡፡

ፍ/ቤቱም ግራ ቀኙን ካከራከረ በኂላ ምስክሮችን በመስማት ጉዳዩን መርምሮ ቤትና ቦታውን ከነወፍጮው የሸጡ መሆኑን ስለተረጋገጠ መሬቱን ተከሣሽ የሚለቁበት ምክንያት የለም በማለት መወሰኑን የውሣኔው ግልባጭ ያሳያል፡፡

አመልካች ይግባኝ ብለው ለክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ያቀረቡ ቢሆንም ይግባኝ ቅሬታቸው ተቀባይነት ሳያገኝ መቅረቱን ተመልክተናል፡፡

አመልካቾች  በስር ፍ/ቤቶች ውሣኔ ላይ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመ በመሆኑ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ ሲሉ ግንቦት 27 ቀን 2010 ዓ.ም. የተፃፈ 5 ገጽ አቤቱታ አቅርበዋል፡፡ ይዘቱም በአጭሩ፡- ክርክር ያስነሳውን ይዞታ ስፋቱ 40በ30 የሆነውን ቦታ በሄክታር 125 ተለክቶ በብር 187.5 ሂሣብ በመክፈል ከ2002 — 2052 ዓ.ም. ድረስ የሚፈለገውን ፎርማሊቲ በማሟላት በቦታው ላይ 4 ክፍል ቤት ያረፈበትን በሊዝ አዋጅ መሠረት በኢንቨስትመንት ተረክበን በቁጥጥር ስር አድርገን እየተጠቀምንበት ነበር፡፡

በይዞታው ላይ ብዙ መዋለ ንዋይ አፍሰን 6 ወፍጮ ተክለን በውክልና ለአሁን ተጠሪ እንዲያስተዳድሩ ጥቅማጥቅም እየሰጡን የሚፈለግ የመንግሥት ክፍያ እየከፈሉ ለ2 ዓመት ቆይተዋል፡፡ ቦታውን እና በላዩ ላይ ያሉ ንብረቶችን ተጠሪ እንድንሸጥላቸው ስለጠየቁን በብር 270,000.00 የሸጥንላቸው መሆኑ በመግለጽ የጣቢያው ጽ/ቤት ለወረዳው ጽ/ቤት ድጋፍ እንዲሰጠን በማለት ጠይቀን የወረዳው አስተዳደር የገጠር የሊዝ መሬት አይሸጥም አይለወጥም በማለት ያገዱት በመሆኑ በላዩ ላይ የሰፈረውን ወፍጮ ድንጋዩና ዕቃዎችን ከነመለዋወጫው በብር 20,000.00/ሃያ ሺ. ብር/ ሸጠንላቸው እያለ ከ2 ዓመት በኂላ የወረዳውን አስተዳደር በማሳሳት በሊዝ የተረከብንበትን ቦታ ከግለሰቦች ጋር በመመሳጠር ይህን ቦታ ያለአግባብ ሊቀሙን ችለዋል፡፡

የስር ፍ/ቤት በሽያጩ ውል ላይ የተመለከተው የወፍጮ ቤትና ዕቃዎች በብር 20,000.00/ሃያ ሺ. ብር/ መሸጡን እየተመለከተና በሁለቱ ወገኖች ፊርማ የተፈረመ የሰነድ ማስረጃ አቅርበን እያለ የሰጠው ውሣኔ ስህተት ስለሆነ እንዲሻርልን እና የተፈፀመው የህግ ስህተት እንዲታረምልን የሚል ሰፊ አቤቱታ አቅርበዋል፡፡

አቤቱታውን የመረመረው የሰበር አጣሪ ችሎትም በግራ ቀኙ የተደረገው የወፍጮ ሽያጭ ውል የአመልካችን አጠቃላይ ይዞታ ስለማጠቃለል አለማጠቃለሉ ግራ ቀኙ በተገኙበት ለማጣራት በሚል ጭብጥ በመያዙ መዝገቡ ለዚህ ችሎት ሊቀርብ ችሏል፡፡

አቤቱታው ከማስቀረቢያ ነጥቡ ጋር ለተጠሪ እንዲደርሳቸውና መልሳቸውን እንዲያቀርቡ በተሰጠው ትዕዛዝ መሠረት ሰኔ 29 ቀን 2010 ዓ.ም. የተፃፈ 5 ገጽ መልስ አቅርበዋል፡፡ ይዘቱም በስር ፍ/ቤት ውሣኔ ላይ የተፈፀመ መሠረታዊ የህግ ስህተት የሌለ በመሆኑ ውሣኔው እንዲፀናላቸው ጠይቀዋል፡፡ አመልካችም የመልስ መልስ አቅርበው የጽሁፍ ክርክሩ በዚህ ተጠናቋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ከላይ የተመለከተውን ሲመስል እኛም አቤቱታውን መልሱን እና የመልስ መልሱን ከስር ፍ/ቤት ውሣኔ እና አግባብነት ካላቸው የህግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መርምረናል፡፡

እንደመረመርነውም አመልካች በስር ፍ/ቤት አቅርበውት የነበረው ክስ ወፍጮ ሸጨለት ወፍጮውን ሊያነሳልኝ አልቻለም በመሆኑም እንዲያነሳልኝ ይወሰንልኝ የሚል ነው፡፡ ተጠሪ በበኩላቸው ወፍጮውን የገዛሁት ከኢንቨስትመንት መሬቱ ጋር በመሆኑ ወፍጮውን ላነሳ አይገባኝም በማለት ተከራክረዋል፡፡

ክርክር ያስነሳው ወፍጮ ያረፈበት መሬት አመልካች ለወፍጮ ሥራ አገልግሎት በኢንቨስትመንት የመሬት ኪራይ ውል መሆኑም በግራ ቀኙን አላከራከረም፡፡ እያከራከረ ያለው ወፍጮው የተሸጠው መሬቱን ጨምሮ ነው ወይስ ወፍጮው ብቻ ነው የሚለው ሲሆን በግራ ቀኙ መካከል ሐምሌ 18 ቀን 2005 ዓ.ም. የተፈረመው የሽያጭ ውል የእህል ወፍጮ ሽያጭ ውል መሆኑን ያሳያል፡፡

ከዚህ የሽያጭ ውል መረዳት የሚቻለው አመልካች 5 ቋት የሚሰራ 1 ቋት የተበላሸ ወፍጮዎችን ለተጠሪ በብር 20,000.00/ሃያ ሺ ብር/ የሸጡ መሆኑን ነው፡፡ አመልካችም በዚህ ውል መሠረት ገንዘቡን መቀበላቸውን ገልፀው ተጠሪ ግን በሽያጭ ውሉ መሠረት ወፍጮውን ከኢንቨስትመንት መሬቱ ላይ አላነሳልኝም የሚል ነው፡፡ ውሉ በግልጽ የወፍጮ ቋት ሽያጭ የተፈፀመ መሆኑን የሚያሳይ ከሆነ ተጠሪ እንደሚሉት ወፍጮው በመሸጡ የኢንቨስትመንት የኪራይ መሬቱን የተጠሪ ሊያደርግ ይችላል አይችልም የሚለውን መመልከት ተገቢ ነው፡፡

በቅድሚያ ለወፍጮ ሥራ መሬት መከራየት በተሻሻለው ትግራይ ክልል የኢንቨስትመንት የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር 239/2006 ውስጥ የሚካተት ነው ወይንስ አይደለም የሚለውን መመልከት ተገቢ ነው፡፡ በዚሁ መሠረት ከላይ በተገለፀው አዋጅ አንቀጽ 2 "ትርጓሜ" በሚለው ስር ንዑስ አንቀጽ 9 "የእርሻ ኢንቨስትመንት" ማለት በአዝርዕት መስኖ፣በእንስሳት ሃብት ልማት፣ በተፈጥሮ ሀብት ልማት፣ በአግሮ ኢንዱስትሪና በሌሎች ተዛማጅ የልማት ሥራዎች የሚካሄድ ኢንቨስትመንት ነው በማለት የደነገገ በመሆኑ ከአስተዳደሩ ጋር በገጠር ይዞታ መሬት ላይ በውል የተደረገው የወፍጮ ሥራ ኢንቨስትመንት በአዋጁ የሚፈቀድ መሆኑን መረዳት ችለናል፡፡

በመሆኑም አመልካች የክልሉ የኢንቨስትመንት አዋጅ በሚፈቅደው ሥራ ተሰማርተው እንዲሰሩ ክርክር ያስነሳውን መሬት ለ5 ዓመት የተከራዩ በመሆኑ ይህን የተከራዩትን የኢንቨስትመነት መሬት ማስተላለፍ ይችላሉ? ወይስ አይችሉም? የሚለውን በተመለከተ በአዋጅ አንቀጽ 24 ስር በተመለከተው መልኩ የገጠር መሬት የእርሻ ኢንቨስትመንትን መብት ከሚተላለፍበት ስርአት ውጭ ለ3ኛ ወገን ማስተላለፍ የተከለከለ ስለመሆኑ በአንቀጽ 22/5 ስር በግልጽ የተመለከተ ከመሆኑም ሌላ በአንቀጽ 26/4 ስር ከሚመለከተው አካል እውቅና ውጭ የተከራየውን መሬት ወደ 3ኛ ወገን አስተላልፎ ሲገኝ የኪራይ

ውሉ የሚያቋርጥ ድርጊት መሆኑን ይደነግጋል፡፡ በመሆኑም ከላይ ከተመለከቱት ድንጋጌዎች የምንረዳው የእርሻ የኢንቨስትመንት መሬትን በሚመለከተው አካል እውቅና በሕግ አግባብ መብት ከሚተላለፍበት ስርአት ውጭ በሽያጭ ለ3ኛ ወገን ማስተላለፍ የማይቻል መሆኑን ነው፡፡

ግራ ቀኙ በክርክራቸው እያነሱ ያሉትም መጀመሪያ ከነመሬቱ ወፍጮውን አመልካች ሊሸጡ ተጠሪ ሊገዙ የተስማሙ ቢሆንም አስተዳደሩ መሬት መሸጥ እንደማይቻል የገለፀላቸው በመሆኑ የወፍጮ ቋት ሽያጭ ውል የፈፀሙ ስለ መሆኑን አንስተዋል፡፡ ከዚህም መረዳት የምንችለው በኪራይ ለኢንቨስትመንት ሥራ የተገኘ መሬት መሸጥ የማይቻል መሆኑን ነው፡፡

በመሆኑም በግራ ቀኙ መካከል የተፈረመው የወፍጮ ቋት ሽያጭ ሆኖ እያለ በውሉ ያልተመለከተ እና በሕግም የእርሻ የኢንቨስትመንት መሬትን በሽያጭ ለ3ኛ ወገን ማስተላለፍ በግልጽ ክልከላ የተደረገበት መሆኑ ተደንግጎ እያለ  እንዲሁም በግራ ቀኙ መካከል የተፈረመው የሽያጭ ውል የወፍጮ ቋት የሽያጭ ውል ስምምነት መሆኑን በግልጽ እያመለከተ የኢንቨስትመንት የኪራይ ውል የተደረገበትን መሬት  ተጠሪ እንደገዙ በማድረግ የኪራዩን መሬት አይለቅም ተብሎ በስር ፍ/ቤት መወሰኑ እና በይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት መጽናቱ ውሉን እና የክልሉን የመሬት አስተዳደር አጠቃቀም አዋጅን ያላገናዘበ  እንዲሁም አንድ የማይንቀሳቀስ ንብረት ወደ 3ኛ ወገን የሚተላለፍበትን የህግ አግባብ ያልተከተለ ሆኖ በመገኘቱ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ በመገኘቱ ሊሻር ይገባል ብለን ተከታዩን ውሣኔ ሰጥተናል፡፡

<u>**ውሣኔ**</u>

1. የትግራይ ክልል የማዕከላዊ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት አክሱም ምድብ ችሎት በመ/ቁ/ 23586 ጥር 23 ቀን 2010 ዓ.ም. በዋለው ችሎት የሰጠው ውሣኔ ፣ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ/ቁ/ 103245 ሚያዝያ 05 ቀን 2010 ዓ.ም. በዋለው ችሎት የሰጠው ትዕዛዝ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ በመገኘቱ በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ/ 348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡
2. ሐምሌ 18 ቀን 2005 ዓ.ም. በተደረገ ውል አመልካች ለተጠሪ የሸጡት የእህል ወፍጮ እንጂ የኢንቨስትመንት መሬቱን አይደለም ብለናል፡፡
3. በመሆኑም ተጠሪ በእህል ወፍጮ ሽያጭ ውሉ መሠረት የገዙትን ወፍጮዎች አመልካች በኪራይ ውል ከያዙት ኢንቨስትመንት መሬት ላይ እንዲያነሱና መሬቱን ለአመልካች እንዲያስረክቡ ተወስኗል፡፡
4. በዚህ ሰበር ችሎት ግራ ቀኙ ላወጡት ወጪ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡

5. የውሣኔው ትክክል ግልባጭ ለስር ፍ/ቤቶች ይድረስ፡፡

መዝገቡ ውሣኔ ስላገኘ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

<u>ትዕዛዝ</u>

ውሣኔው ሲፃፍ ቆይቶ ዛሬ የካቲት 13 ቀን 2011 ዓ.ም. ተነቧል፡፡

*ሠ/ኃ* የማይነበብ የ5 ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

የሰ/መ/ቁ 169729

ግንቦት 30 ቀን 2011 ዓ.ም.

ዳኞች - ተኽሊት ይመስል

ተፈሪ ገብሩ (ዶ/ር)

ቀነአ ቂጣታ

ተሾመ ሽፈራው

ፀሐይ መንክር

አመልካች - የገቢዎች ሚኒስቴር

ተጠሪ - አቶ አስራት አሰግድ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የፌዴራሉ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት እና ይግባኙ የቀረበለት የፌ/ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጡት ውሳኔና ብይን የህግ ስህተት የተፈፀመበት በመሆኑ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት አቤቱታ ስላቀረበ ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው አመልካች በተጠሪ ላይ ባቀረቡት ክስ ነው፡፡

የክሱ ይዘት፡- በኢትዮጵያ የባህር ትራንስፖርት እና ሎጀስቲክስ አገልግሎት ድርጅት በቃሊቲ ወደብ ተርሚናል የመጋዘን ሰራተኛ ሆኜ ስሰራ በወ/ሮ ኤደን ወንዲፍራው ስም ከዱባይ ወደ ኢትዮጵያ ገብተው በቃሊቲ ጉምሩክ የጉምሩክ ሥነ ሥርዓት እንዲፈፀምባቸው ካስገቧቸው ዕቃዎች ውስጥ የኮንትሮባንድ ዕቃዎች በመያዛቸው ለገቢዎችና ጉሙሩክ ቃሊቲ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት በ30/12/2008 ዓ.ም ጥቆማ ሰጥቼ ብር 382,241.60 የሚያወጡ የኮንትሮባንድ ዕቃዎች በቁጥጥር ስር እንዲውሉ አድርጌያለሁ፤ የተከሳሽ መ/ቤት ሥራ አስኪያጅ ሽልማት የሚገባኝ መሆኑን ገልጾ ፎርም እንድሞላ የተደረገ ሲሆን በዚሁ አግባብ በ29/03/2009 ዓ.ም ፎርም ሞልቼ የጠቋሚ መለያ ቁጥር AAKc/230/03/09 ተሰጥቶኛል፤ የምስጋና ደብዳቤም አግኝቻለሁ፤ ነገር ግን የጠቋሚውን ፎርም ከሞላሁ በኃላ በመመሪያ ቁጥር 78/2004 መሰረት 40% ወሮታ ክፍያ ብር 152,896.61 ተጠሪ እንዲከፍለኝ በተደጋጋሚ ጠይቄ ሊከፍለኝ ፈቃደኛ ስላልሆነ ይህን ገንዘብ እንዲከፍል ይወሰንልኝ በማለት ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡

ተጠሪ ለክሱ በሰጠው መልስ በጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 859/2006 አንቀጽ 53 እና 132 መሰረት ራሱ በሚጠብቀው መጋዘን ውስጥ ዕቃ እንዳይወጣ መያዙ የሥራ ግዴታውን ተወጥቷል የሚያስብል እንጂ በመመሪያው መሰረት ወሮታ የሚያስከፍል ጥቆማ ሰጥቷል ስለማይባል ክሱ ውደቅ ይደረግልን፤ የጥቆማ ፎርሙ በ10 ቀን መሞላት ነበረበት ወይም ከአቅም በላይ ያልሞላ መሆኑን ቀርቦ ማስረዳት አለበት፤ የጥቆማ ክፍያ አያሰጥም እንጂ ይሰጣል ቢባል እንኳ የጥቆማ ፎርሙን በ10 ቀን ውስጥ

ስላልሞላ እንዲሁም ከሳሽ ጥቆማ ባያደርግ ኖሮ ኃላፊነት አልተወጣም ተብሎ ተጠያቂ ይሆን ስለነበር ክፍያ ሊጠይቅ አይገባም በማለት ተከራክሯል፡፡

ክሱ በሚሰማበት ጊዜ አመልካች ባይቀርብም ተጠሪ ቀርበው የአመልካች ሰራተኛና የመጋዘን ኃላፊ አለመሆናቸውን፤ አይደለም የመጋዘን ሰራተኛ የፀጥታ አስከባሪዎችም ወሮታ የሚከፈላቸው መሆኑን፤ እቃው ይለቀቅ ተብሎ የመልቀቂያ ቅጽ (release form) የተሞላለት ስለሆነ ጠቋመው ባያስይዙት ኖሮ ምንም ኃላፊነት እንደማይመጣባቸው፤ ጥቆማ የሰጡት በግንባር ቀርበው በመሆኑ በ10 ቀን ውስጥ ፎርም አልሞላም የሚለው ክርክር እንደማይመለከታቸው፤ ይመለከታቸዋል ቢባል እንኳ ዕቃው የተያዘባት ግለሰብ ጠፍታ እርሷ ባለችበት ዕቃውን ለማስፈተሽ ተብሎ በመጠባበቅ የቆየ በመሆኑ እንደ በቂ ምክንያት ሊወሰድ እንደሚገባ ተከራክረዋል፡፡

ጉዳዩ በዚህ መልኩ የቀረበለት የሥር ፍርድ ቤት የአሁን አመልካች ለተጠሪ የወሮታ ክፍያ ለመክፈል ይገደዳል? ወይስ አይገደድም? የሚል ጭብጥ በመያዝ ክርክርና ማስረጃውን መርምሮ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ በሰጠው ውሳኔ ተጠሪ የአመልካች ሰራተኛ ወይም፣ የህግ አስከባሪ አባል ባለመሆናቸው የሥራ ግዴታቸውን ተወጥተዋል ተብሎ የወሮታ ክፍያ አያገኙም የሚባልበት የህግ ምክንያት አልተገኘም፤ አመልካች ጠቅሶ የሚከራከረው የጉሙሩክ አዋጅ ቁጥር 859/2006 አንቀጽ 56 እና 132 ድንጋጌዎችም ተጠሪ ግዴታቸውን ስለተወጡ ክፍያ አያገኙም የሚያስብሉ አይደሉም፤ በተለይም ተጠሪ ለግለሰቧ ዕቃዎቹ እንዲለቀቁላት የመልቀቂያ ፎርም (release form) ተሰጥቶ እንደነበር ተከራክረው በማስረጃም ያረጋገጡ ሲሆን አመልካች ይህን ክዶ ስላልተከራከረም፤ በዚህ መልኩ እንዲለቀቅ የተፈቀደ ዕቃ ላይ ደግሞ በተጠሪ ላይ ኃላፊነት ያስከትል ነበር ማለት ስለማይቻል አመልካች የሚያቀርበው ክርክር ተቀባይነት የለውም፤ በ 10 ቀን ውስጥ የጥቆማ ፎርም አልሞሉም የተባለውን በተመለከተም የቀረቡት ማስረጃዎች ተጠሪ በግንባር ጥቆማ ያቀረቡ መሆኑን የሚያስረዱ በመሆኑ ተቀባይነት የሌለው ሲሆን መሙላት ነበረባቸው ቢባል እንኳ ተጠሪ የጠቋሚ ቅፅ እንዲሞሉ መደረጉና ቅጹ በአመልካች ኢንስፔክሽን ኦፊሰር ተረጋግጦ መፈረሙ ስለተረጋገጠ ተጠሪ እንደሚሉት ቅፁን ሳይሞሉ የቆዩት ዕቃዎቹ ሳይፈተሹ በመቆየታቸው በበቂ ምክንያት መሆኑን ያስረዳል ስለሆነም በዚህም ረገድ የቀረበው ክርክር ተቀባይነት የለውም፡፡ በአጠቃላይ ዳኝነት የተጠየቀበትን 40% የወሮታ ክፍያ ብር 152,896.65 አመልካች ለተጠሪ ሊከፍል ይገባል በማለት ወስኗል፡፡

ይህን ውሳኔ በመቃወም አመልካች ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የይግባኝ ቅሬታውን ቢያቀርብም ውሳኔውን ሊያስነቅፍ የሚችል ምክንያት አልተገኘም ተብሎ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 337 መሰረት ይግባኙ ተሰርዟል፡፡

የሰበር አቤቱታው ለዚህ ፍርድ ቤት የቀረበው በዚህ ነው፡፡ አመልካች ጥር 22 ቀን 2011 ዓ.ም ያቀረበው ማመልከቻ በአጣሪ ችሎቱ ተመርምሮ ተጠሪ የወሮታ ክፍያ ተጠቃሚ ነው? ወይስ አይደለም? የሚለውን አከራካሪ ነጥብ ለይቶ ለመወሰን የሥር ፍርድ ቤት የሰጠውን ትርጉም አግባብነት ለማየት ሲባል መዝገቡ ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ እና ተጠሪ መልስ እንዲሰጡበት ተደርጓል፡፡ ተጠሪ

በሰጡት መልስ የሥር ፍርድ ቤቶች ያሳለፉት ውሳኔ የህግ ስህተት አልተፈፀመበትም ተብሎ እንዲፀና የጠየቁ ሲሆን አመልካችም ክርክሩን በማጠናከር የመልስ መልስ አቅርቧል፡፡

ከፍሲል ባጭሩ የገለጽነው የጉዳዩን አመጣጥ ነው፡፡ በበኩላችን የግራ ቀኙን ክርክር ከተገቢው የህጉ ድንጋጌ ጋር በማያያዝ በሥር ፍርድ ቤቶች በተሰጠው ውሳኔ የተፈፀመ መሰረታዊ የህግ ስህተት መኖር አለመኖሩን መርምረናል፡፡

እንደመረመርነው ተጠሪ የወሮታ ክፍያ ተጠቃሚ ሊሆኑ ይገባል? ወይስ አይገባም? የሚለውን ጭብጥ ለመወሰን ይቻል ዘንድ የህገ ወጥ ዕቃዎች መረጃ አሰጣጥ፣ አያያዝ እና ወሮታ ክፍያን ለመወሰን ተሻሽሎ የወጣውን መመሪያ ቁጥር 78/2004 ይዘት መመርመሩ ተገቢ ነው፡፡ በመመሪያው አንቀጽ 2(7) መሰረት "የወሮታ ክፍያ" ማለት ለጠቆሙ ወይም ለያዙ ወይም ለተባበሩና ድጋፍ ለሰጡ ሰዎች የሚሰጥ ክፍያ ሲሆን የባለሥልጣኑን ሰራተኛ እና የህግ አስከባሪ አካል አባልን/ሰራተኛን እንደማይጨምር ተደንግጓል፡፡ ከዚህ ድንጋጌ መገንዘብ የሚቻለው ክፍያው የማይመለከታቸው የባለሥልጣኑን ሰራተኛ እና የህግ አስከባሪ አካል አባልን/ሰራተኛን መሆኑን መረዳት ይቻላል፡፡

በተያዘው ጉዳይ ተጠሪ በኢትዮጵያ የባህር ትራንስፖርት እና ሎጂስቲክስ አገልግሎት ድርጅት በቃሊቲ ወደብ ተርሚናል የመጋዘን ሰራተኛ መሆናቸውን ገልፀው የኮንትሮባንድ ዕቃዎች መኖራቸውን ተጠራጥረው ለገቢዎችና ጉሙሩክ በማሳወቅ ብር 382,241.60 የሚያወጡ የኮንትሮባንድ ዕቃዎች ስላስያዙ 40% ወሮታ ክፍያ ብር 152,896.61 እንዲከፈላቸው እንዲወሰን የጠየቁ ሲሆን አመልካች በበኩሉ ተጠሪ ራሳቸው በሚጠብቁት መጋዘን የሚጠበቅባቸውን ኃላፊነት ተወጥተዋል ከሚባል በቀር በመመሪያው መሰረት ወሮታ የሚያስከፍል ሥራ ሰርተዋል ስለማይባል ክሱ ውደቅ እንዲደረግ ተከራክሯል፡፡

የስር ፍርድ ቤት ጉዳዩን መርምሮ ተጠሪ የአመልካች ሰራተኛ ወይም፣ የህግ አስከባሪ አባል ባለመሆናቸው የሥራ ግዴታቸውን ተወጥተዋል ተብሎ የወሮታ ክፍያ አያገኙም የሚባልበት ምክንያት አለመኖሩን፤ አመልካች የሚከራከርበት የጉሙሩክ አዋጅ ቁጥር 859/2006 አንቀጽ 56 እና 132 ድንጋጌዎችም ተጠሪ ግዴታቸውን ስለተወጡ ክፍያ አያገኙም የሚያስብሉ አለመሆናቸውን፤ ዕቃዎቹ እንዲለቀቁም የመልቀቂያ ፎርም (release form) ተሰጥቶ እንደነበር በማረጋገጥ ዳኝነት የተጠየቀበትን 40% የወሮታ ክፍያ አመልካች እንዲከፍል ወስኗል፡፡ ይኸው መደምደሚያ በይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤትም ተቀባይነት አግኝቷል፡፡

የፌዴራሉ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት እና ይግባኝ ሰሚው የከፍተኛ ፍርድ ቤት ከፍሲል የተጠቀሰው መደምደሚያ እና ውሳኔ ላይ የደረሱት ፍሬ ነገር ለማጣራት እና ማስረጃ ለመመዘን በህግ በተሰጣቸው ሥልጣን መሰረት ነው፡፡በኢፌዴሪ ህገ መንግስት አንቀፅ 80(3)(ሀ) እና በፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀፅ 10 ስር እንደተደነገገው የዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት ስልጣን በመጨረሻ በተላለፈው ውሳኔ ላይ መሰረታዊ የህግ ስህተት ተፈፅሞ ሲገኝ ማረም እንጅ ፍሬ ነገርን መመርመር አይደለም፡፡ ፍሬ ነገሩን ለማጣራት እና ማስረጃ ለመመዘን በህግ ስልጣኑ የተሰጣቸው የሥር ፍርድ ቤቶች በህጉ

አግባብ ክርክሩን በመምራትና ማስረጃውን በመመዘን ከፍ ሲል የተመለከተው መደምደሚያ ላይ ደርሰዋል፡፡ የህገ ወጥ ዕቃዎች መረጃ አሰጣጥ፣ አያያዝ እና ወሮታ ክፍያን ለመወሰን ተሻሽሎ የወጣውን መመሪያ ቁጥር 78/2004 አንቀጽ 2(7) ለ"የወሮታ ክፍያ" ከሰጠው ትርጉም አንጻርም ተጠሪ ክፍያ ሊጠይቁ አይገባም የሚባል አይደለም፡፡ ስለሆነም በዚህ መልኩ ጉዳዩ ታይቶ አመልካች ለተጠሪው ወሮታ የመክፈል ኃላፊነት አለበት ተብሎ መወሰኑ ህጉን የተከተለ ነው ከሚባል በቀር የሚነቀፍ ሆኖ አላገኘነውም፡፡

ነገር ግን የኃላፊነቱን መጠን በተመለከተ ተጠሪ የኮንትሮባንድ ዕቃውን ይዘው ለገቢዎችና ጉሙሩክ ቃሊቲ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ሪፖርት ማድረጋቸውን ክርክሩ ስለሚያሳይ የወሮታ አበል ሊከፈላቸው የሚገባው የህገ ወጥ ዕቃዎች መረጃ አሰጣጥ፣ አያያዝ እና ወሮታ ክፍያን ለመወሰን ተሻሽሎ በወጣው መመሪያ ቁጥር 78/2004 አንቀፅ 19(ለ) መሰረት 10% ነው፡፡ ከዚህ አንፃር ውሳኔው ሊቃና የሚገባ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ ተከታዩንም ወስነናል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. በፌዴራሉ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 6886 ግንቦት 6/2010 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ እና የፌ/ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁ 215263 በ02/05/2011 ዓ.ም ያሳለፈው ብይን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁጥር 348(1) መሰረት በአብላጫ ድምፅ ተሻሽሏል፡፡
2. አመልካች በተጠሪ ለተያዙት ብር 382,241.60 የሚያወጡ የኮንትሮባንድ ዕቃዎች የወሮታ ክፍያ በመመሪያ ቁጥር 78/2004 አንቀፅ 19(ለ) መሰረት የዕቃውን ዋጋ 10% ብር 38,224.16 (ሰላሳ ስምንት ሺህ ሁለት መቶ ሃያ አራት ብር ከ16/100) ከወጪና ኪሳራ ጋር አመልካች ለተጠሪ እንዲከፍል ወስነናል፡፡
3. በአጣሪ ችሎቱ ጥር 23/2011 ዓ.ም አፈጻፀም እንዲታገድ የተሰጠው ትዕዛዝ ተነስቷል፡፡ ይህ ፍርድ ቤት በሰጠው ውሳኔ መሰረት ይፈፀም ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የሶስት ዳኞች ፊርማ አለበት ፡፡

## <u>የልዩነት ሀሳብ</u>

እኛ ስማችን በተራ ቁጥር ሶስት እና አምስት ላይ የተጠቀስን ዳኞች በዚህ ጉዳይ የአብላጫዉ ድምጽ ከሰጠዉ ዉሳኔ በሚከተለዉ ምክንያት ተለይተን የልዩነት ሀሳብ እናስቀምጣለን፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ሲታይ የአሁን ተጠሪ በጉምሩክ አዋጅ እና መመሪያ መሰረት ለጠቋሚ የሚከፈለዉ የወሮታ ክፍያ እንዲከፈለዉ የጠየቀዉን ዳኝነት የሚመለከት ነዉ፡፡ የአሁን ተጠሪ ባቀረበዉ ክስ በኢትዮጵያ የባህር ትራንስፖርትና ሎጂስቲክስ አገልግሎት ድርጅት በቃሊቲ ወደብ ተርሚናል የመጋዘን ሰራተኛ ሆኜ ስሰራ በወ/ሮ ኤደን ወንዲፍራዉ ስም ከዱባይ ወደ ኢትዮጵያ ገብተዉ በቃሊቲ ጉምሩክ

የጉምሩክ ስነሥርዓት እንዲፈጸምላቸዉ ካስገቧቸዉ ዕቃዎች ዉስጥ የኮንትሮባንድ ዕቃዎች በመያዛቸዉ ለገቢዎችና ጉምሩክ ቃሊቲ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ጥቆማ አቅርቤ አስፈላጊዉን ፎርም የሞላሁኝ ቢሆንም የሕገወጥ ዕቃዎች መረጃ አሰጣጥ፣ አያያዝ፣ አመዘጋገብ እና የወሮታ ክፍያዎችን ለመወሰን ተሻሽሎ የወጣ መመሪያ ቁጥር 78/2004 መሰረት 40% የወሮታ ክፍያ እንዲከፈለዉ ዳኝነት ጠይቋል፡፡ የአሁን አመልካች ባቀረበዉ ክርክር ተጠሪ ራሱ በሚጠብቀዉ መጋዘን ዉስጥ የተጠቀሰዉ ዕቃ እንዳይወጣ ቁጥጥር ሥር እንዲዉል እና እንዲያዝ ማድረጉ የሥራ ግዴታዉን ተወጥቷል የሚያስብል እንጂ በመመሪያዉ መሰረት ለጠቋሚ የሚከፈለዉ ክፍያ የሚገባዉ አይደለም በማለት በዝርዝር ተከራክሯል፡፡ የሥር ፍ/ቤቶች ግራ ቀኛቸዉን በማከራከር በሰጡት ዉሳኔ የአሁን ተጠሪ ያቀረበዉን የዳኝነት ጥያቄ በመቀበል በመመሪያዉ መሰረት 40% የወሮታ ክፍያ እንዲከፈለዉ ወስኗል፡፡ ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት የአብላጫዉ ድምጽ ደግሞ የሥር ዉሳኔ በማሻሻል 10% የወሮታ ክፍያ ለተጠሪ እንዲከፈለዉ ወስኗል፡፡ በዚህ ምክንያት እኛ ስማችን ከፍ ሲል የተጠቀሰዉ ዳኞች ከአብላጫዉ ድምጽ በመለየት የሚከተለዉን የልዩነት ሀሳብ አስቀምጠናል፡፡

በዚህ መሰረት መታየት ያለበት ጉዳይ ተጠሪ በኢትዮጵያ የባህር ትራንስፖርትና ሎጂስቲክስ አገልግሎት ድርጅት በቃሊቲ ወደብ ተርሚናል የመጋዘን ሰራተኛ ሆኖ እያለ ከዚህ መጋዘን ገብቶ ሊወጣ ያለዉን ዕቃዎች ዉስጥ የኮንትሮባንድ ዕቃ መኖሩን ጠቁሞ በማስያዙ ምክንያት በመመሪያ ቁጥር 78/2004 አንቀጽ 19 መሰረት ለጠቋሚ የሚከፈለዉ ክፍያ ይገባዋል ወይስ አይገባዉም? የሚለዉ ነጥብ ነዉ፡፡

እንደሚታወቀዉ በጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 859/2006 አንቀጽ 50 ዕቃዎችን ወደ ጉምሩክ ስለማስገባትን አስመልክቶ መደንገጉን መገንዘብ ይቻላል፡፡ በዚህ ድንጋጌ ንዑስ አንቀጽ 1 ሥር ‹‹የጉምሩክ ወደብ የደረሰ ማናቸዉም ዕቃ ወደ ጊዜያዊ የጉምሩክ ዕቃ ማከማቻ ወይም ቦንድድ የጉምሩክ መጋዘን መግባት አለበት›› በማለት ይደነግጋል፡፡ እንዲሁም የዚህ ድንጋጌ ንዑስ አንቀጽ 2 እንደሚደነግገዉ ‹‹ማናቸዉም ወደ ጊዜያዊ የጉምሩክ ዕቃ ማከማቻ የገባ ዕቃ ዝርዝር ሁኔታዉ እየተገለጸ በመጋዘኑ መዝገብ ላይ ይመዘገባል›› በማለት ተደንግጓል፡፡ ማናቸዉም ወደ ቦንድድ ጉምሩክ መጋዘን የሚገባ ዕቃ በመጋዘን ዲክሊራሲዮን ተመዝግቦ ለባለስልጣኑ መቅረብና መፈቀድ እንዳለበት በዚህ ድንጋጌ ንዑስ አንቀጽ 3 ሥር ተመልክቷል፡፡ በዚህ አግባብ ወደ ጉምሩክ መጋዘን የገባዉ ዕቃ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 51 ሥር በተመለከተዉ የጊዜ ገደብ ዉስጥ አስፈላጊዉ የጉምሩክ ሥነሥርዓት ተከናዉኖበት ከማከማቻዉ መዉጣት እንዳለበት ተገልጾዋል፡፡ በዚህ አግባብ ወደ ጉምሩክ መጋዘን የገቡት ዕቃዎች ከመጋዘኑ የሚወጡበት ሁኔታ በአዋጁ አንቀጽ 52 መሰረት በጉምሩክ ሕጉ እና በዚህ ድንጋጌ ሥር ለተመለከቱት ዓላማዎች ሲባል ብቻ ተመዝግበዉ ከማከማቻዉ ወይም ከመጋዘኑ መዉጣት እንዳለባቸዉ ተጠቅሷል፡፡ ከእነዚህ ሁኔታዎች መካከል አንዱ ‹‹ዕቃዎቹ የሚፈለግባቸዉ ቀረጥና ታክስ ተከፍሎባቸዉ ለአገር ዉስጥ ፍጆታ እንዲዉሉ ሲለቀቁ›› መሆኑ ተመልክቷል፡፡ በዚህ መሰረት ወደ መጋዘን የገቡት ዕቃዎች በዲክላራሲዮኑ፤ በጭነት ማኒፌስት ወይም በትራንዚት ሰነድ ከተገለጸዉ መጠን በላይ በትርፍነት የተገኘ ዕቃ ዲክላራሲዮኑ ለቀረበለበት የባለስልጣኑ ቅርንጫፍ ወዲያዉኑ ሪፖርት መደረግ እንዳለበት እና

በትርፍ ዕቃዉ ላይ ተገቢ ቀረጥና ታክስ እንዲከፈል መደረግ እንዳለበት በአዋጁ አንቀጽ 53 ሥር ተደንግጎ እናገኛለን፡፡ ወደ ጉምሩክ መጋዘን በገቡት ዕቃዎች ላይ ደግሞ የጉምሩክ ቁጥጥር መከናወን እንደሚገባ እና አስፈላጊዉ የጉምሩክ ሥነሥርዓት ተፈጽሞበት ከመጋዘኑ ሲለቀቅም መደረግ የሚገባቸዉን ተግባራት በዚህ አዋጅ አንቀጽ 56 ሥር ተጠቅሷል፡፡ ወደ ጉምሩክ መጋዘን የሚገባዉንና የሚወጣዉን ዕቃ በተመለከተ የጉምሩክ መጋዘን ሰራተኞች ዕቃዎቹን ባለስልጣኑ በሚያወጣዉ መመሪያ መሰረት የመመዝገብና በየጊዜ ሪፖርት ማድረግ ከተጣለባቸዉ የሥራ ግዴታዎች መካከል አንዱ እንደሆነ በአዋጁ አንቀጽ 132 (2) ሥር ተመልክቷል፡፡

በዚህ መሰረት አሁን ወደ ተያዘዉ ጉዳይ ስንመለስ በወ/ሮ ኤደን ወንድፍራዉ ስም ከዱባይ አገር ወደ ኢትዮጵያ የገባዉ ዕቃ የአሁን ተጠሪ በሚሰራዉ የጉምሩክ መጋዘን ሲገባ እና ሲወጣ በአዋጁ አንቀጽ 50፣52፣ 53፣ 56 እና 132 (2) ሥር የተመለከተዉን አስፈላጊዉን የጉምሩክ ስነስርዓት እንደአስፈላጊነቱ መፈጸም ይገባዉ ነበር፡፡ በወ/ሮ ኤደን ስም የተመዘገበዉ ዕቃ ወደ መጋዘን ሲገባ በሕጉ በተመለከተዉ አግባብ ያልተመዘገበ እና ከመጋዘኑ ሲወጣም ደግሞ በትርፍነት የተገኙት ዕቃዎች ተገቢዉ ቀረጥና ታክስ ሳይከፈልባቸዉ ሊወጣ እንደነበር መገንዘብ ተችሏል፡፡ ይህ ማለት የአሁን ተጠሪ የሚሰራበት መጋዘን በሕጉ የተጣለበትን የሥራ ግዴታ ሳይወጣ መቅረቱን የሚያስገነዝብ ጉዳይ ነዉ፡፡ ይህ ከሆነ ጉዳዩ የሚመለከታቸዉ የመጋዘኑ ሰራተኞች በሕግ የተጣለባቸዉን የሥራ ግዴታቸዉን ባለመወጣታቸዉ ተጠያቂነትን ሊያስከትልባቸዉ የሚገባዉ ጉዳይ ነበር፡፡ በዚህ አንጻር ሲታይ የአሁን ተጠሪ የሚሰራበት የጉምሩክ መጋዘን በሕግ የተጣለበትን ግዴታ ሳይወጣ በመቅረቱ ተጠሪ ደግሞ ይህን ሁኔታ በማወቁ ለሚመለከተዉ የገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ቃሊቲ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት በመጠቆም ማሳወቁ በመጋዘኑ በራሱ እና በሌሎች የመጋዘኑ ሰራተኞች ላይ የተጣለዉን የሥራ ግዴታን ተወጥቷል የሚያስብል ነዉ፡፡

በዚህ መመሪያ አንቀጽ 4 መሰረት ‹‹በአገሪቱ የጉምሩክ ክልል በየትኛዉም ሥፍራ ሕገወጥ ዕቃ መኖሩን የሚያዉቅ ማንኛዉም ሰዉ ወዲያዉኑ በአቅራቢያዉ ለሚገኝ የባለስልጣኑ መስሪያ ቤት ወይም ሕግ አስከባሪ አካል ማሳወቅ አለበት›› በማለት ይደነግጋል፡፡ በዚህ አግባብ ጥቆማ ያደረገ ማንኛዉም ሰዉ ደግሞ በመመሪያ አንቀጽ 16 እና ተከታዮቹ ድንጋጌዎች መሰረት የወሮታ ክፍያ እንደሚፈጸምለት ተመልክቷል፡፡ በዚህ አግባብ አሁን የተያዘዉ ጉዳይ ሲታይ የአሁን ተጠሪን ጨምሮ ሌሎች የጉምሩክ መጋዘን ሰራተኞች የሚሰሩት ሰራተኞች በሕግ የተጣለባቸዉን የሥራ ግዴታ ባለመወጣታቸዉ በወ/ሮ ኤደን ስም ተመዝግቦ የገባዉ ዕቃ ዉስጥ በትርፍነት የተገኘዉ ተገቢዉን ቀረጥና ታክስ ሳይከፈልበት ሊወጣ ሲል ተጠሪ ደርሶበት ለሚመለከተዉ የጉምሩክ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት በመጠቆም ማሳወቁ ተጠሪ በእሱ እና በሌሎች የመጋዘኑ ሰራተኞች ላይ የተጣለዉን የሥራ ግዴታ ተወጥቷል ከሚባል በስተቀር በመመሪያ ቁጥር 78/2004 መሰረት ሕገወጥ ዕቃ በተመለከተ መረጃ በመስጠት በመጠቆም አስይዟል ተብሎ የወሮታ ክፍያ ይገባዋል የሚያስብል የህግ መሰረት የለም፡፡ በመሆኑም የአሁን ተጠሪ ያቀረበዉ የወሮታ ክፍያ ጥያቄ የህግ ድጋፍ የለዉም ብለናል፡፡

ሲጠቃለል የሥር ፍ/ቤቶች በዚህ ጉዳይ በመመሪያ ቁጥር 78/2004 አንቀጽ 19 መሰረት ለተጠሪ የወሮታ ክፍያ ሊከፈለዉ ይገባል በማለት የሰጡት ዉሳኔ ከፍ ሲል በተጠቀሰዉ መሰረት የአዋጁንና የመመሪያዉን ዓላማና መንፈስ ያላገናዘበ በመሆኑ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመባቸዉ ስለሆኑ መሻር ይገባቸዉ ነበር ብለን የአብላጫዉ ድምጽ ከሰጠዉ ዉሳኔ በመለየት የልዩነት ሀሳባችን አስቀምጠናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

የማይነበብ የሁለት ዳኞች ፊርማ አለበት ፡፡

ፅ/ወ

የሰ/መ/ቁ.171530

ግንቦት 29 ቀን 2011 ዓ.ም

ዳኞች፡- ተኽሊት ይመስል

ተፈሪ ገብሩ (ዶ/ር)

ቀነአ ቂጣታ

ተሾመ ሽፈራው

ፀሐይ መንክር

አመልካች - የኢፌዴሪ ሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር -

ነ/ፈጅ ሽዋቀረው አስፋው - ቀረቡ

ተጠሪ - አቶ ሱልጣን ጃቢር መሀመድ - ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

የሰበር አቤቱታው የቀረበው የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ያሳለፈውን ውሳኔ በመቃወም ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁን ተጠሪ በአመልካች ላይ በፌዴራሉ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ባቀረቡት ክስ ነው፡፡

ተጠሪ ያቀረቡት ክስ ይዘት፡- በሥሜ የተመዘገበ ሱልጣን ጃቢር በውጭ ሀገር ሥራና ሰራተኛ አገናኝ ኤጀንሲ በአመልካች ፍቃድ ተሰጥቶኝ በዚሁ መሰረት የንግድ ፈቃድ አውጥቼ እና ለሥራውም ዋስትና የሚሆን በብሎክ አካውንት በባንክ ብር 281,200.00 አስቀምጬ ሥሰራ ቆይቼ መንግስት በ2007 ዓ.ም ሥራው ለጊዜው እንዲቆም መመሪያ ሲያስተላልፍ ሥራው ቆሞ የነበረ ቢሆንም ፈቃዱን ግን እያሳደስኩ ቆይቻለሁ፤ ሥራው በአዲስ መልክ ሲፈቀድ 100,000.00 ዶላር (መቶ ሺህ ዶላር) ያሥያዝኩ ሲሆን አስቀድሞ ያስያዝኩትን ገንዘብ አመልካች እንዲለቅልኝ የጠየቅሁ ቢሆንም ከድርጅቱ ጋር ግንኙነት የሌለው አቶ በድሩ ከማል የተባለ ግለሰብ አቤቱታ ስላቀረበ አንለቅልህም ብሏል፤ ስለሆነም አመልካች የያዘብኝን ብር 281,200.00 (ሁለት መቶ ሰማንያ አንድ ሺህ ሁለት መቶ ብር) እንዲለቅ ይወሰንልኝ በማለት ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡

አመልካች ለክሱ በሰጠው መልስ ተጠሪ ክስ ያቀረቡት በ 3 ግለሰቦች በተቋቋመ የግል ማህበር በመሆኑ በግላቸው ክሥ ማቅረብ አይችሉም፤ ተጠሪ ቀደም ሲል ሱልጣን ጃቢር በውጭ ሀገር የግል ሥራና ሠራተኛ አገናኝ ኤጀንሲ ሥም ዜጎችን ለሥራ ሲልክ የቆየ ሲሆን ከ2005 ዓ.ም ጀምሮ የዚህን ኤጀንሲ ሥም በመለወጥ ተጠሪን ጨምሮ 3 ግለሰቦች ሆነው የአክሲዮን ድርሻ በመያዝ በሰነዶች ማረጋገጫና ምዝገባ የተመዘገበ ሱልጣን ጃቢር በውጭ ሀገር ሥራና ሰራተኛ አገናኝ ኤጀንሲ ኃ/የተ/የግል ማህበር አቋቁመው መተዳደሪያ ደንብና መመስረቻ ፅሁፍ ለአመልካች ያቀረቡ በመሆኑ ይህ ማህበር እያለ ተጠሪ በግላቸው በቀድሞው ኤጀንሲ ስም ያቀረቡት ክስ ተቀባይነት የለውም፤ ተጠሪ ለአመልካች

መስሪያ ቤት ገንዘቡ እንዲመለስ ጥያቄ ሲያቀርቡ አስተዳደራዊ ውሳኔ ለመስጠት እንዲቻል ማብራሪያ እንዲሰጡ የተፈለጉ ቢሆንም ባለመቅረባቸው የሚወሰደው አስተዳደራዊ ውሳኔ ሳይነገራቸው ያቀረቡት ክስ አግባብነት የለውም፤ በአጠቃላይ የዋስትና ገንዘቡን በተመለከተ ህጋዊ ሰውነት ያለው ኃ/የተ/የግ/ማህበር ሥለሆነ ተጠሪ ያቀረቡት ክስ ውድቅ ሊሆን ይገባል በማለት ተከራክሯል፡፡

ጉዳዩ በዚህ መልኩ የቀረበለት የሥር ፍርድ ቤት ክርክር የተነሳበት የዋስትና ገንዘብ በሱልጣን ጃቢር ሥራና ሰራተኛ አገናኝ ኤጀንሲ ኃ/የተ/የግ/ማህበር ሥም ገቢ የተደረገ ነው? ወይስ አይደለም? ሊመለስ ይገባል? ወይስ አይገባም? የሚል ጭብጥ ይዞ ጉዳዩን በመመርመር ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ በሰጠው ውሳኔ ተጠሪ ክፍያውን በግላቸው ገቢ ያደረጉት መሆኑን ስላስረዱ በባንክ ገቢ ያደረጉትን ብር 281.200.00 (ሁለት መቶ ሰማንያ አንድ ሽህ ሁለት መቶ) አመልካች ከወጪና ኪሳራ ጋር እንዲለቅ (እንዲመልስ) በማለት ወስኗል፡፡ በዚህ ውሳኔ ላይ በአመልካች በኩል ይግባኙ የቀረበለት የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የግራቀኙን ክርክር ሰምቶ ውሳኔው ስህተት የለበትም በማለት አፅንቶታል፡፡

የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚህ ነው፡፡ አመልካች የካቲት 18/2011 ዓ.ም ያቀረበው ማመልከቻ በአጣሪ ችሎቱ ተመርምሮ ጉዳዩን ከኢትዮጵያ የውጪ ሀገር ስራ ስምሪት አዋጅ ቁጥር 923/2008 እና የውጪ ሀገር ስራ ሥምሪት አፈፃፀም መመሪያ አንጻር ለማጣራት ሲባል ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ እና ተጠሪም መልስ እንዲሰጡበት ተደርጓል፡፡ ተጠሪ በ26/07/2011 ዓ.ም በተፃፈ መልስ ውሳኔው ስህተት አልተፈፀመበትም ተብሎ እንዲፀና ጠይቋል፡፡ አመልካቹም የመልስ መልስ አቅርቧል፡፡ መዝገቡ ለምርመራ የተቀጠረውም በዚህ ሁኔታ ነው፡፡

ከፍሲል ባጭሩ የገለጽነው የጉዳዩን አመጣጥ ሲሆን በበኩላችን ለሰበር ችሎቱ የተያዘውን ጭብጥ ከግራ ቀኙ ክርክር፣ ቅሬታ ከቀረበበት ውሳኔና ተገቢነት ካላቸው የህጉ ድንጋጌዎች ጋር በማያያዝ መርምረናል፡፡

እንደመረመርነው የውጪ ሀገር ስራ ስምሪት አዋጅ ቁጥር 923/2008 እና ይህን አዋጅ ለማስፈፀም የወጣው የውጪ ሀገር ስራ ሥምሪት አፈፃፀም መመሪያ ፈቃድ ስለመመለስና የዋስትና ገንዘብ ስለመልቀቅ ዝርዝር ድንጋጌዎችን ይዘዋል፡፡ በአዋጁ አንቀጽ 60(5) ሥር እንደተደነገገው ኤጀንሲው በማናቸውም ሁኔታ ሥራውን ሲያቆም ሚኒስቴሩ የዋስትናውን ገንዘብ የሚለቀው ከሠራተኛ መብትና ጥቅም ጋር የተያያዘ ጥያቄ ስልጣን በተሰጠው አካል በመታየት ላይ ካልሆነ እና በኤጀንሲው አማካኝነት ለስራ ወደ ውጪ አገር የተላኩ ሠራተኞች በሙሉ የሥራ ውላቸው ከተቋረጠ ከ6 ወር በኃላ ነው፡፡ የመመሪያው አንቀጽ 23 የዋስትና ገንዘብ እንዲለቀቅ ጥያቄ ሲቀርብ መሟላት ስለሚኖርባቸው ሁኔታዎች ይዘረዝራል፡፡

ከዚህም ሌላ የአዋጁ አንቀጽ 78 የመሸጋገሪያ ድንጋጌዎችን የያዘ ሲሆን አስቀድሞ ሥራ ላይ በነበረው አዋጅ ቁጥር 632/2001 መሰረት ፈቃድ ተሰጥቷቸው የነበሩ ኤጀንሲዎች ስለሚኖርባቸው ኃላፊነት እና ፈቃዱ ተሰርዞ ቢሆን እንኳ ኤጀንሲው ለሥራ ወደውጪ አገር የላካቸው ሰራተኞች ከሚያነሱት ማናቸውም የመብት ጥያቄ ነጻ እንደማይሆን ተመልክቷል፡፡

ከፍሲል ከተጠቀሱት የህጉ ድንጋጌዎች መገንዘብ እንደሚቻለው የዋስትና ገንዘብ የሚያዘው በዋናነት ለሰራተኛው መብትና ደህንነት ዋስትና ማስከበሪያ እንዲውል ሲሆን ኤጀንሲው በሚኒስቴሩ የተሰጠውን ፈቃድ በመመለስ ለሥራ ወደ ውጪ አገር ለላካቸው ዜጎች መብትና ደህንነት ማስከበሪያ በባንክ ያስያዘው የዋስትና ገንዘብ እንዲለቀቅለት ጥያቄ ሲያቀርብ አሟልቶ ሊያቀርብ የሚገባቸው ሁኔታዎች በህጉ ተለይተው የተደነገጉ መሆናቸውን ነው፡፡

በተያዘው ጉዳይ የሥር ፍርድ ቤት ክርክር የተነሳበት የዋስትና ገንዘብ አስቀድሞ በሱልጣን ጃቢር ሥራና ሰራተኛ አገናኝ ኤጀንሲ ሥም ገቢ የተደረገ መሆን አለመሆኑን የሚመለከት ጭብጥ በመያዝ የወሰነ ቢሆንም በህጉ ከተቀመጡት ሁኔታዎች አንጻር ተገቢው ጭብጥ ተይዞ በዚሁ አንጻር ክርክርና ማስረጃው ታይቶ በአግባቡ ተገናዝቦ የተሰጠ ውሳኔ ባለመሆኑ ተቀባይነት የሚኖረው አይደለም፡፡

ይልቁንም በህጉ አግባብ ዋስትና ያስያዘው ኤጀንሲ ፈቃዱን መመለስ አለመመለሱ፤ አስቀድሞ የተሰጠ ፈቃድ ካልተመለሰ ፈቃድ ሳይመለስ የዋስትና ገንዘበ ሊመለስ የሚገባ ስለመሆን አለመሆኑ፤ እንዲሁም ኤጀንሲው ለሥራ ወደ ውጪ አገር ለላካቸው ዜጎች መብትና ደህንነት ማስከበሪያ በባንክ ያስያዘው የዋስትና ገንዘብ እንዲለቀቅለት ሊያሟላ የሚገባቸው ሁኔታዎች የተሟሉ መሆን አለመሆኑ ሁሉ ከክርክርና ማስረጃው አንጻር ታይቶና በአግባቡ ተገናዝቦ ውሳኔ ሊሰጥበት ይገባ ነበር፡፡

በአጠቃላይ ለጉዳዩ አወሳሰን ጠቃሚ የሆኑ ፍሬ ነገሮች ከህጉና ከማስረጃው አንፃር በአግባቡ እንዲጣሩ ሳይደረግ ተጠሪ ክፍያውን በግላቸው ገቢ ያደረጉት መሆኑን አስረድተዋል በሚል ምክንያት ብቻ ገቢ ያደረጉትን ብር 281.200.00 (ሁለት መቶ ሰማንያ አንድ ሽህ ሁለት መቶ) አመልካች ሊለቅ ይገባል በማለት በሥር ፍርድ ቤት የተሰጠው ውሳኔ ስህተት የተፈጸመበት ነው ብለናል፡፡ ይግባኝ ሰሚው ችሎትም ይህን ሳያርም ማለፉ የሚነቀፍ ነው፡፡ ስለሆነም ተከታዩን ወስነናል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. በፌዴራሉ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በኮ/መ/ቁ 50815 ሰኔ 29 ቀን 2010 ዓ.ም ተሰጥቶ በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 219600 በ04/06/2011 ዓ.ም የፀናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 348(1) መሰረት ተሽሯል፡፡
2. የፌዴራሉ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የተዘጋውን መዝገብ በማንቀሳቀስ ዋስትና ያስያዘው ኤጀንሲ ፈቃዱን መመለስ አለመመለሱን፤ አስቀድሞ የተሰጠው ፈቃድ ካልተመለሰ ፈቃድ ሳይመለስ የዋስትና ገንዘበ ሊመለስ የሚገባ ስለመሆን አለመሆኑ፤ እንዲሁም ኤጀንሲው ለሥራ ወደ ውጪ አገር ለላካቸው ዜጎች መብትና ደህንነት ማስከበሪያ በባንክ ያስያዘው የዋስትና ገንዘብ እንዲለቀቅለት ሊያሟላ የሚገባቸው ሁኔታዎች የተሟሉ መሆን አለመሆኑን ሁሉ በመመርመር ጉዳዩን በአግባቡ አጣርቶ ተገቢውን ውሳኔ እንዲሰጥ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 343(1) መሰረት መልሰናል፡፡ የውሳኔው ግልባጭ ለሥር ፍርድ ቤቶች ይተላለፍ፡፡

3. የሰበር ክርክሩ ያስከተለውን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ሰ/ጥ

የሰበር መዝገብ ቁጥር 167560

ግንቦት 30 ቀን 2011 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ብርሃኑ አመነው

በእውቀት በላይ

እንዳሻው አዳነ

ሃይሉ ነጋሽ

እትመት አሰፋ

**አመልካች፡-** አቶ ቢቂላ አያኖ

**ተጠሪ፡-** አቶ አሊቢ ቂላ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ ሊቀርብ የቻለው የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 219841 ታህሳስ 11 ቀን 2011 ዓ.ም በዋለው ችሎት የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ በማፅናት የሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ሊታረምልኝ ይገባል በማለት አመልካች ታህሳስ 15 ቀን 2011 ዓ.ም የተፃፈ 02 ገጽ የሰበር አቤቱታ በማቅረባቸው ነው፡፡

ጉዳዩ በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የተጀመረ ሲሆን አመልካች ከዚህ በፊት ፍርድ ቤቱ ችሎታ የላቸውም በማለት የሰጠው ውሳኔ ስህተት መሆኑ በመግለፅ የተደረገላቸው የህግ ክልከላ እንዲነሳ ወሳኔ ለሰጠው ፍርድ ቤት አቤቱታ አቅርበው፣ አቤቱታ ለማቅረብ ችሎታ የላቸውም በሚል ምክንያት ተቀባይነት ማጣታቸው መነሻ በማድረግ አቤቱታ በማቅረባቸው ነው፡፡ ለክርክሩ መነሻ የሆነው ተጠሪ ለፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ባቀረበው አቤቱታ ወላጅ አባቴ አቶ ቢቂላ አያኖ (የአሁኑ አመልካች) በጣም ያረጁ እና ጆሮአቸው የማይሰማ በመሆኑ ነገሮችን ማስተዋልና ማስታወስ ስለማይችሉ የፍርድ ክልከላ ይሰጥልኝ በማለት ባቀረበው አቤቱታ መሰረት ፍርድ ቤቱ በመዝገብ ቁጥር 2600/07 ታህሳስ 28 ቀን 2007 ዓ/ም በዋለው ችሎት የአሁኑ አመልካች በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 351 መሰረት የፍርድ ክልከላ ሰጥቷል፡፡ ይህንን ክልከላ ተከትሎ ተጠሪ በመዝገብ ቁጥር 2600/07 የአመልካች ሞግዚት እንዲሆን ሾሞታል፡፡

አሁን የቀረበው አቤቱታ አመልካች የተደረገባቸው ፍርድ ክልከላ እንዲነሳ ፣ክልከላውን ለሰጠው ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 43358 አቤቱታ አቅርበው ጉዳዩ የቀረበለት ፍርድ ቤትም አመልካች የፍርድ ክልከላ ከተሰጠባቸው በኋላ ክስ ለማቅረብ ችሎታ የላቸውም በማለት በፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 33(1) እና ፍ/ብ/ሕ/ቁ 377 መሰረት ያቀረቡት አቤቱታ ውድቅ አድርጎታል፡፡ አመልካች በተሰጠው ውሳኔ ቅር በመሰኘት ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ይግባኝ አቤቱታ ያቀረቡ ቢሆንም የአመልካች አቤቱታ ባለመቀበል ሰርዞታል፡፡ ይህ የሰበር አቤቱታ የቀረበው በሥር ፍርድ ቤቶች የተሰጠ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡

አመልካች በቀን 15/04/2011 ዓ/ም የተፃፈ 2 ገፅ አቤቱታ አቅርበዋል ፡፡ የአቤቱታው ይዘት ባጭሩ ፡-አመልካች የህግ ክልከላ የተሰጠብኝ መሆኑን መሰረት በማድረግ ክልከላው ይነሳልኝ በማለት ያቀረብኩት አቤቱታ ሆኖ እያለ ፍርድ ቤቱ ክልከላ ይነሳ በማለት አቤቱታ ማቅረብ የሚችሉት በፍ/ሕግ ቁጥር 377 ላይ የተገለፁት ግለሰቦች ናቸው በማለት አቤቱታዬን ወድቅ አድርጎታል፡፡ ይሁን እንጂ ክልከላ የተደረገበት ሰው ክልከላው በመቃወም አቤቱታ ማቅረብ እንደሚችል በፍ/ሕግ ቁጥር 355 ላይ ተገልፆ እያለ የስር ፍርድ ቤቶች ግንኙነት በሌለው የህግ ድንጋጌ መሰረት አቤቱታዬን ውድቅ በማድረግ መወሰናቸው መሰረታዊ የህግ ስህተት ስለሆነ ሊሻር ይገባል የሚል ነው፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ በሰበር ችሎት ሊታይ ይገባዋል በመባሉ ተጠሪ ቀርበው የጽሁፍ ክርክራቸው ተለዋውጠዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙ ፅሑፍ ክርክር የሰበር አቤቱታ ከቀረበበት ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ ለክርክሩ መነሻ የሆነው የአሁኑ ተጠሪ አባት የሆኑት የአሁኑ አመልካች በጣም ያረጁ እና ጆሮአቸው የማይሰማ በመሆኑ ነገሮችን ማስተዋልና ማስታወስ ስለማይችሉ የፍርድ ክልከላ ይሰጥልኝ በማለት ባቀረበው አቤቱታ መነሻነት ፍርድ ቤቱ በመዝገብ ቁጥር 43358 በቀን 28/04/2007 ዓ/ም በዋለው ችሎት በአቶ ቢቂላ አያኖ ንብረት ላይ በፍ/ህግ ቁጥር 351(1) የፍርድ ክልከላ የሰጠ መሆኑ በውሳኔው ላይ አስፍሯል፡፡ ከዚህ በኋላ አመልካች የህግ ክልከላ የተሰጠብኝ ያለአግባብ ነው ችሎታ አለኝ በማለት ክልከላው ይነሳልኝ አቤቱታ አቅርበው ፍርድ ቤቱ ክልከላ ይነሳ በማለት አቤቱታ ማቅረብ የሚችሉት በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 377 ላይ የተገለፁት ግለሰቦች ናቸው በማለት ውሳኔ ሰጥቶ በይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤትም ተቀባይነት አግኝቷል፡፡

በመሰረቱ በህግ ችሎታ ያለው ማንኛውም ሰው ክስ ማቅረብ እንደሚችል በፍ/ሥ/ስ/ሕግ ቁጥር 33(1) ተመልክቷል፡፡ የፍ/ህግ ዓንቀፅ 377 ስር እንደተመለከተው አእምሮው ከጎደለው ሰው በቀር ስለክልከላው ፍርድ እንዲሰጥ ለመጠየቅ የሚችሉት ሰዎች በማንኛውም ጊዜ የክልከላው ውሳኔ እንዲቀር ለዳኞች ጥያቄ ለማቅረብ ይችላሉ በማለት ተመልክቷል፡፡ ከዚሁ ድንጋጌ በመቀጠል ክልከላ እንዲወሰን

ያደረጉት ምክንያቶች በቀኑ ጊዜና የተከለከለ ሰው ንብረቱን ለመምራትና ለማስተዳደር የሚችል የሆነ እንደሆነ ዳኞች የክልከላው ውሳኔ ማስቀረት (ማንሳት) እንዳለባቸው በፍ/ህግ ዓንቀፅ 378 ተደንግጓል ፡፡በሌላ በኩል በፍ/ሕግ ቁጥር 355 እንደተመለከተው አእምሮው ጎደሎ ወይም ድውይ የሆነው ሰው እራሱ ፣ከባልና ሚስት ደህነኛው ከስጋ ወይም ከጋብቻ ዘመዶች አንዱ ወይም ዓቃቤ ህግ ዳኞች ስለክልከላው በሰጡት ፍርድ ላይ አቤቱታ ማቅረብ እንደሚችሉ ተመልክቷል፡፡

ስለሆነም ከላይ ከተጠቀሱት የህግ ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ መረዳት የሚቻለው በፍርድ ክልከላ የተደረገለት ሰው ንብረቱን ለመምራትና ለማስተዳደር የሚችል የሆነ እንደሆነ ክልከላው ቀሪ እንዲሆን መጠየቅ እንደሚችል ፍርድ ቤቶችም ይህንን ተከትለው ውሳኔ መስጠት እንዳለባቸው የተደነገገ በመሆኑ አመልካች በተደረገለት ክልከላ ምክንያት ሌላ አዲስ ክስ ማቅረብ የማይችል ቢሆንም የተደረገለት ክልከላ እንዲነሳለት ግን ከላይ በተጠቀሰው ህግ መሰረት የሚፈቀድለት በመሆኑ የተደረገለት ክልከላ እንዲነሳለት ላቀረበው አቤቱታ ፍርድቤቱ አመልካች የክስ አቤቱታ ለማቅረብ ችሎታ የላቸውም በማለት መዝገቡን መዘጋቱ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ውሳኔ በመሆኑ ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

## <u>ውሳኔ</u>

1. በጉዳዩ ላይ የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትበመ/ቁጥር 43358 ሰኔ 06 ቀን 2010 ዓ/ም ተወስኖ ፣ በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 219841 ታህሳስ 11 ቀን 2011 ዓ/ም በዋለው ችሎት በትእዛዝ የፀናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 348/1/ መሰረት ተሽሯል፡፡
2. በአመልካች ክልከላ እንዲነሳላቸው አቤቱታ ማቅረብ የሚችሉ በመሆናቸው የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የተዘጋውን መዝገብ በማንቀሳቀስ በጉዳዩ ላይ ግራ ቀኙን አከራክሮ ውሳኔ እንዲሰጥበት ተመልሶለታል ፡፡ይፃፍ፡፡
3. በዚህ ችሎት ክርክር ለወጣው ወጭና ኪሳራ ግራ ቀኙ የራሳቸውን ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

ሳ/ፀ የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡